# ፍቅር እስከ መቃብር

(ልቦለድ ታሪክ)

፱ኛ እትም

ከሀዲስ ዓለማየሁ

ሜጋ አሳታሚ ድርጅት

፲፱፻፺፯

© ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1996

☎ 57 17 15

57 17 16

50 44 96

🖂 413 ኮድ 1110

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ



**ደራሲው ሀዲስ አለማየሁ**

ይህ ፡ መጽሀፍ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በቃተመበት ፡ ጊዜ ፡ ተቀማ ጭንቴ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ስለነበረ ፡ አብሮ ፡ አደጌና ፡ ወዳጄ ፡ አቶ ፡ መሀሪ ፡ ካሳ ፡ የሰረፍት ፡ ጊዜያቸውን ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ ሰጥተው ፡ በቅርብ ፡ ባይከታተሉልኝ ፡ ኖሮ ፡ በፈለግሁት ፡ ሁኔታና ፡ ጊዜ ፡ ታትሞ ፡ ለመውጣት ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ አቶ ፡ መሀሪ ፡ ላደረጉልኝ ፡ ውለታ ፡ ምስጋናየ ፡ ወሰን ፡ የለውም ።

እንዲሁም ፡ ከብዙ ፡ ስርዝና ፡ ድልዝ ፡ ጋር ፡ የጻፍሁትን ፡ የመጀመሪያውን ፡ ረቂቅ ፡ እህቴ ፡ ውድነሽ ፡ አምሳሉ ፡ በብዙ ፡ ትጋትና ፡ ጥንቃቄ ፡ እንደገና ፡ ደህና ፡ አድርጋ ፡ ባትጽፍልኝ ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ይገጥመኝ ፡ ስለነበረ ፡ ውለታዋን ፡ አልረሳውም ።

ሀዲስ ፡ አለማየሁ ፡

# ማውጫ


መቅድም ... ፯
ቦጋለ፡ መብራቱና፡ ውድነሽ፡ በጣሙ ... ፲፩
በዛብህ ... ፲፱
የሰእሰት፡ ልጅ ... ፴
የሚታይ፡ እንጂ፡ የማይበሰ፡ ፍሬ ... ፴፱
የወላድ፡ መካኖች ... ፵፯
ነጻነት ... ፶፱
የመጨረሻ፡ ኑዛዜ ... ፷፫
የቅኔ፡ ማእበል ... ፷፩
ተከለ፡ እልፋአ ... ፸፯
ሰብለ፡ ወንጌል ... ፹፫
የፈታውራሪ፡ አሰጌና፡ የሰብለ፡ ወንጌል፡ ጋብቻ፡
መቅረት ... ፺፱
ጉዱ፡ ካሳ ... ፻፳፩
ፍልሚያ ... ፻፵፫
ሀዲር፡ ጊዮርጊስ ... ፻፵፯
የጋሎ፡ ድል ... ፻፷፪
የሰብለ፡ ወንጌል፡ ትምህርት ... ፻፹፬
ቀዳሮ ... ፻፺፯
የባላባቶች፡ መላከቶች ... ፪፻፱
የወቅሳ፡ ዋጤማ ... ፪፻፴፯
የባላገሮች፡ እድማ ... ፪፻፶፩
ዘመቻ ... ፪፻፷፯
አዲስ፡ አለም ... ፫፻፬
አፍ፡ ዝም፡ ቢል፡ ሌላው፡ ይናገራል ... ፫፻፳፫
በዛብህና፡ ቀለሙ ... ፫፻፵፩
መሰናዶ ... ፫፻፶፱
የብራ፡ መብረቅ ... ፫፻፸፫
ሰብለ፡ እንዴት፡ እንደታሰረች ... ፫፻፹፱
ከሰማይ፡ የወረደ፡ መስቀል ... ፬፻፲፩
አዲስ፡ አበባ ... ፬፻፳፫
መርዶ ... ፬፻፵፯

ሰርግና፡ ተዝካር ... ፬፻፷፯
አባ፡ አለም፡ ለምኔ ... ፬፻፹፱
ስርቅታ ... ፭፻፲፩
ፍቅር፡ እስከ፡ መቃብር ... ፭፻፳፩
ማረሚያ ... ፭፻፴፪

# ፍቅር ፡ እስከ ፡ መቃብር ፡

## መቅድም ፡

በልማዱ ፡ የልብ ፡ ወለድ ፡ ድርሰት ፡ ደራሲዎች ፡ ከፍ ፡ ወይም ፡ ዝቅ ፡ ብለው ፡ የሚገመቱት ፡ ለድርሰታቸው ፡ የሚፈጥሩት ፡ ታሪክ ፡ ላንባቢዎች ፡ በሚሰጠው ፡ ትምህርትና ፡ ታሪኩን ፡ በጥሩ ፡ አጻጻፍ ፡ አስጊጦ ፡ ለማቅረብ ፡ ባላቸው ፡ ችሎታ ፡ ነው ። ላንባቢዎች ፡ አእምሮ ፡ ትምርትን ፡ ለልባቸው ፡ ደስታን ፡ የሚሰጥ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ድርሰት ፡ ጥሩ ፡ ድርሰት ፡ ይባላል ። እንዲህ ፡ ላሉ ፡ ድርሰቶች ፡ ደራሲዎችም ፡ ትልቅ ፡ ደራሲዎች ፡ ይባላሉ ።

እኔ ፡ እዚህ ፡ " ፍቅር ፡ እስከ ፡ መቃብር ፡ " ብዬ ፡ ሰይሜ ፡ ላንባቢዎች ፡ የማበረክታት ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ድርሰት ፡ በታሪክዋም ፡ ሆነ ፡ ባጻጻፍዋ ፡ ጥሩ ፡ ድርሰቶች ፡ የሚባሉት ፡ በያዙት ፡ ደረጃ ፡ እንኩዋንስ ፡ ልትደርስ ፡ እንደማትቀርብ ፡ አውቃለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ጥሩ ፡ ድርሰቶች ፡ ያልያዙት ፡ መልክት ፡ ላንባቢዎች ፡ ለማድረስ ፡ የተሰናዳች ፡ ስለሆነችና ፡ በተለይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ አንባቢዎች ፡ ለሚያሳስቡ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ መልስ ፡ ላላገኙ ፡ አንዳንድ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉ ፡ አሳቦች ፡ ይዛ ፡ ስለምትቀርብ ፡ አንባቢዎች ፡ ሳይሰለቹ ፡ በማስተዋል ፡ እንዲመለከቱልኝ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

እስከ ፡ ዛሬ ፡ መልስ ፡ ያላገኙ ፡ ጥያቄዎች ፡ ከዋላቸው ፡ አንዱ ፡ የፊደሎቻችን ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

ዛሬ ፡ ለማነኛውም ፡ ነገር ፡ አቁዋራጭ ፡ መንገድና ፡ ቅልጥፍና ፡ በሚፈለግበት ፡ ጊዜ ፡ የፊደሎቻችን ፡ ያለመጠን ፡ መብዛት ፡ ትምርታችንንም ፡ ሆነ ፡ ስራችነን ፡ ሳያስፈልግ ፡ አስቸጋሪ ፡ አድርጎብናል ። ይህም ፡ ታውቆ ፡ የፊደል ፡ አሻሻይ ፡ ኮሚቴዎች ፡ በዩጊዜው ፡ እዬተሾሙ ፡ አሳብ ፡ መለዋወጣቸውንና ፡ ፊደሎቻችን ፡ የሚሻሻሉበትን ፡ ዘዴ ፡ ማጥናታቸውን ፡ እናውቃለን ። ነገር ፡ ግን ፡ የነዚህ ፡ ኮሚቴዎች ፡ ጥናት ፡ ውጤቱ ፡ ገና ፡ አልታወቀም ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላላው ፡ ስለ ፡ ቁዋንቁዋ ፡ ማስፋፋትም ፡

ሆነ ፡ ሰለ ፡ ፊደል ፡ ማሻሻል ፡ መንግስት ፡ ለሚደክመው ፡ ድካም ፡ ደራሲዎች ፡ የሚሰጡት ፡ ርዳታ ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። አንድ ፡ ደራሲ ፡ የተሻለ ፡ በሚመስለው ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ፊደል ፡ ሲጽፍ ፡ ሌሎች ፡ ደራሲዎች ፡ ተከታትለው ፡ እሱ ፡ በጻፈበት ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ፊደል ፡ ከጻፉና ፡ አንባቢዎችም ፡ ከለመዱት ፡መንግስት ፡ የቁዋንቁዋም ፡ ሆነ ፡ የፊደል ፡ መለወጫ ፡ አዋጅ ፡ ማወጅ ፡ ሳያስፈልገው ፡ ወደሚፈለገው ፡ ግብ ፡ በደራሲዎች ፡ አማካይነት ፡ ይደርሳል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ እኔ ፡ በዚች ፡ መጽሀፍ ፡ የጻፍሁበት ፡ ዘዴ ፡ ከኔ ፡ በሁዋላ ፡ ለሚጽፉ ፡ ደራሲዎች ፡ የሚስማማ ፡ መስሎ ፡ ቢታያቸውና ፡ ቢከተሉት ፡ የፊደሎቻችን ፡ ብዛት ፡ ያስከተለውን ፡ ችግር ፡ በመጠኑ ፡ ያቃልለዋል ፡ ብዬ ፡ በማመን ፡ አሳቤን ፡ ከዚህ፡ ቀጥዬ ፡ አቀርባለሁ ።

አንደኛ ፦ ሶስት ፡ "ሀ" ዎች ፡ ሁለት ፡ "ሰ" ዎች ፡ ሁለት ፡ "አ" ዎች ፡ ሁለት ፡ "ጸ" ዎች ፡ ስላሉን ፡ ከነሱ ፡ አንዳንድ ፡ ብቻ ፡ ይገፎ ፡ የቀሩትን ፡ ጥያቸዋለሁ ። ስለዚህ ፡ የተጣሉት ፡ አምስት ፡ ግእዝ ፡ ፊደሎች ፡ ከነርባታቸው ፡ ሰላሳ ፡ አምስት ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፦ ከፊደላችን ፡ መጨረሻ ፡ " ኰ " ፡ " ጐ " ፡ "ቈ" ፡ ኈ" ፡ የሚባሉትን ፡ ጎደሎ ፡ ፊደሎች ፡ ከነርባታቸው ፡ ጥያቸዋለሁ ። ድምራቸው ፡ ሀያ ፡ ነው ።

ሶስተኛ ፦ " ኸ " እና ፡ " ኧ " ን ፡ ግእዛቸውን ፡ ብቻ ፡ ይገፎ ፡ ርባታቸውን ፡ ጥያለሁ ፡ ከነሱ ፡ የወደቁት ፡ ፊደሎች ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ ናቸው ። እንግዲህ ፡ በጠቅላላው ፡ የተጣሉት ፡ ፊደሎች ፡ ስድሳ ፡ ሰባት ፡ ሲሆኑ ፡ እነሱ ፡ በመሐላቸው ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ የንባብ ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ የምስጢር ፡ መሰወር ፡ ይገጥማል ፡ የሚያሰኝ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርዱን ፡ ይህችን ፡ መጽሀፍ ፡ ለሚያነቡ ፡ እተውዋለሁ ።

አራተኛ ፦ ከፊደል ፡ ወደ ፡ ቃል ፡ ስናልፍ ፡ ሁለት ፡ ተቃራኒ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትርጉም ፡ ያላቸው ፡ አንዳንድ ፡ ቃሎች ፡ እናገኛለን ። ከነዚህ ፡ ቃሎች ፡ ተቃራኒ ፡ ትርጉም ፡

እላቸው ፡ ያልናቸው ፡ ግድረግንና ፡ መደረግን ፡ ገላጮች ፡ ሲሆኑ ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ እንጋገር ፡ ላይ ፡ አድራጊው ፡ ሳልቶ ፡ ተደራጊው ፡ ጠብቆ ፡ ስለሚነገር ፡ ለማስተዋል ፡ ባያስቸግሩ ፡ አጻጻፍ ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ አይነት ፡ ስለሚጻፉ ፡ ያሳስታሉ ። ምክናያቱም ፡ ባነጋገር ፡ የምናጠብቀውን ፡ ቀለም ፡ ባጻጻፍ ፡ የምናጠብቅበት ፡ የማጥበቅያ ፡ ምልክት ፡ ስለሌለን ፡ ነው ። በላቲን ፡ አጻጻፍ ፡ ለማጥበቅ ፡ የሚፈለገው ፡ ቀለም ፡ ሁለት ፡ ሆኖ ፡ ይጻፋል ። በኛ ፡ አጻጻፍ ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ሆኖ ፡ የተጻፈ ፡ አንድ ፡ ቀለም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ለዩብቻ ፡ ይነበባል ፡ እንጂ ፡ አይጠብቅም ። ለምሳሌ ፡- "አረረ ፡ መረረ ፡ አበበ ፡ ከበበ ፡-" ስንል ፡ " ረ " እና ፡ " በ " ፡ በያንዳንዱ ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ መጻፋቸው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንዲነበቡ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲጠብቁ ፡ አይደለም ። -

እስቲ ፡ አሁን ፡ አድራጊና ፡ ተደራጊን ፡ የሚገልጹ ፡ ቃሎች ፡ ባነጋገር ፡ ሲለዩ ፡ ባጻጻፍ ፡ አንድ ፡ ስለሆኑ ፡ ያሳስታሉ ፡ ካልናቸው ፡ ቃሎች ፡ ለምሳሌ ፡ ያክል ፡ ጥቂቶችን ፡ እንመልከት ።

" ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፡ ሲለዩ ፡ ሲሰሩ ። "

"ሲበላ" ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ ላድራጊው ፡ ወይም ፡ ለበዩ ፡ ሰውና ፡ ለተደራጊው ፡ ወይም ፡ ለተበዩ ፡ እንጀራ ፡ አጻጻፉ ፡ አንድ ፡ ነው ። ሰውዩው ፡ " ሲበላ " ፡ አዩሁ ፤ እንጀራው ፡ "ሲበላ" ፡ አዩሁ ፤ ይባላል ። ባነጋገር ፡ ግን ፡ ሰውዩው ፡ ሲበላ ፡ አዩሁ ፡ ሲባል ፡ " በ " እና ፡ " ላ " በመላላታቸው ፡ እንጀራው ፡ ሲበላ ፡ አዩሁ ፡ ሲባል ፡ " በ " እና ፡ " ላ " ፡ በመጥበቃቸው ፡ ትርጉማቸውን ፡ ለማወቅ ፡ አያስቸግርም ። ስለዚህ ፡ እንዳነጋገራችን ፡ ባጻጻፋችንም ፡ አድራጊውን ፡ ከተደራጊው ፡ ለመለዩት ፡ የማጥበቅያ ፡ ምልክት ፡ ስለሚያስፈልግ ፤ ይህ ፡ የማጥበቅያ ፡ ምልክት ፡ በሚጠብቀው ፡ ቀለም ፡ ራስጌ ፡ ነጥብ ፡ እንዲሆን ፡ አሳስቤያለሁ ። ለምሳሌ ፡ ሰውዩው ፡ "ሲበላ" ፡ እንጀራው ፡ " ሲበ፟ላ፟ " ። ሌሎችም ፡ " ሲበላ " ከተባለው ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ የቆጠርናቸውና ፡ እነሱን ፡ የመሳሰሉት ፡ ማጥበቅ ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ቃሎች ፡ ሁሉ ፡ ይህኑ ፡ መንገድ ፡ ይከተላሉ ።

ለ ፡ " የ" ፊደል ፡ ማጥበቅያ ፡ ሀምሱን ፡ አድርጌያለሁ ።

እምስተኛ ፡- ይህች ፡ መጽሀፍ ፡ የቆዩ ፡ ልማዶቻችትነን ፡ ላንባቢዎች ፡ ታስታውሳለች ።

ኢትዮጵያ ፡ እንደሌሎች ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ በጎም ፡ ከፉም ፡ ልማዶች ፡ ነበሩዋት ። ዛሬም ፡ የቀሩት ፡ ቀርተው ፡ ያሉት ፡ አሉ ።

የቆዩ ፡ ልማድ ፡ የቆዩ ፡ በመሆኑ ፡ ሁሉ ፡ አይወድቅም ፤ ወይም ፡ ሁሉ ፡ አይያዝም ። መልካሙና ፡ ጠቃሚው ፡ ይያዛል ፡ የሚሻሻለው ፡ ይሻሻላል ፡ ሊሻሻል ፡ የማይችለው ፡ ይወድቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚወድቀውም ፡ ከፉ ፡ ልማድ ፡ ከስራ ፡ ይወገዳል ፡ እንጂ ፡ ከታሪክ ፡ ጸሀፊዎች ፡ መጽሀፍና ፡ ከደራሲዎች ፡ ድርሰት ፡ ሊወገድ ፡ አይገባውም ። ያለዚያ ፡ በዩጊዜው ፡ የሚደረገው ፡ የፖለቲካም ፡ ሆነ ፡ የኢኮኖሚክ ፡ ወይም ፡ ያስተዳደርና ፡ የማህበራዊ ፡ ኑሮ ፡ መሻሻል ፡ ከምን ፡ ተነስቶ ፡ እምን ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ሊታወቅ ፡ አይቻልም ።

እንግዲህ ፡ ያቀረብሁዋቸውን ፡ አዳዲስ ፡ አሳቦች ፡ ለመግለጽ ፡ ያክል ፡ አንባቢዎቼን ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ካደከምሁዋችሁ ፡ በሁዋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ታሪክ ፡ " ፍቅር ፡ እስከ ፡ መቃብር" ፡ እንድታወሩችሁ ፡ ከስዋ ፡ ጋር ፡ እተዋችሁዋለሁ ።

ሀዲስ አለማየሁ ።

# ምእራፍ ፡ ፩ ፡

## ቦጋለ ፡ መብራቱና ፡ ውድነሽ ፡ በጣሙ፡

ጎጃም ፡ ዳሞት ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ ማንኩሳ ፡ በምትባል ፡
አገር ፡ ቦጋለ ፡ መብራቱ ፡ የሚባሉ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በብቸኛ
ነት ፡ የሚኖሩ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ። ቦጋለ ፡ መብራቱ ፡ ከድሀ ፡ ቤተ ፡
ሰብ ፡ የተወለዱ ፡ በዚያውም ፡ ላይ ፡ ድሆች ፡ ወላጆቻቸው ፡
ገና ፡ በህጻንነታቸው ፡ ሞተውባቸው ፡ ድህነት ፡ ሲያንገላታ
ቸው ፡ ያደጉ ፡ ነበሩ ። ትንሽ ፡ ከፍ ፡ እንዳሉ ፡ መጀመሪያ ፡ የፍ
ዬልና ፡ የጥጃ ፡ እረኛነት ፡ እዬተቀጠሩ ፡ በሁዋላም ፡ እጃቸው ፡
እርፍ ፡ ለመጨበጥ ፡ ያክል ፡ መበርታት ፡ ሲጀምር ፡ ግብርና ፡
እዬተቀጠሩ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ እኩል ፡ እድሜያ
ቸውን ፡ ካሳለፉና ፡ የምሽት ፡ ማግባት ፡ ፍላጎታቸው ፡ እየተ
ቀነሰ ፡ ከሄደ ፡ በሁዋላ ፡- በጉልማሳነታቸው ፡ ጉልበታም ፡ ወዲ
ያው ፡ ጤናማ ፡ በመሆናቸው ፡ ረዳት ፡ ሳይፈልጉ ፡ ራሳቸውን ፡
ረድተው ፡ ለመኖር ፡ ቢችሉም ፡ ምሽት ፡ ካላገቡ ፡ እድሜያቸው ፡
እየገፋ ፡ አቅማቸው ፡ እየተቀነሰ ፡ ሲሄዱ ፡ ረዳት ፡ የሚያጡ ፡
መሆናቸውን ፡ ወዳጆቻቸው ፡ አጥብቀው ፡ ስለመከሩዋቸው ፡
ከዚያው ፡ ከማንኩሳ ፡ ውድነሽ ፡ በጣሙ ፡ የሚባሉትን ፡ ሴት ፡
አገቡ ።

ወይዘሮ ፡ ውድነሽ ፡ ሶስት ፡ ባሎች ፡ በተራ ፡ አግብተው ፡
ሶስቱም ፡ ስለሞቱባቸው ፡ ባል ፡ ፈርቶዋቸው ፡ እሳቸውም ፡
እድላቸውን ፡ ፈርተው ፡ ባል ፡ እንዳይመጣላቸው ፡ ተስፋ ፡
ቆርጠው ፡ ቢመጣም ፡ እንዳያገቡ ፡ ወስነው ፡ ተቀምጠው ፡
ነበር ። በሁዋላ ፡ ቦጋሊ ፡ መብራቱ ፡ የወይዘሮ ፡ ውድነሽን ፡
የንስሀ ፡ አባት ፡ ቄስ ፡ ታምሩን ፡ አማላጅ ፡ ልከው ፡ በብዙ ፡ ደጅ
ጥናት ፡ አገቡዋቸው ።

“ ስሙ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ” አሉ ፡ ቄስ ፡ ታምሩ ፡
አንድ ፡ ቀን ። “ ከዛሬ ፡ በፊት ፡ ባሎችዎን ፡ ሲያገቡ ፡ ላንዳቸ
ውም ፡ አማላጅ ፡ ሆኜ ፡ እንዳልመጣሁ ፡ እስዎ ፡ ያውቃሉ ።
አሁን ፡ ግን ፡ በግድ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ስለመሰለኝ ፡ ነው ፡ አማ
ላጅ ፡ ሆኜ ፡ የመጣሁ ። በውጭ ፡ የሚወራውን ፡ የርስዎ ፡ ጀሮ ፡
አይሰማውም ። ሴት ፡ ብቻዋን ፡ ከተቀመጠች ፡ ትደፈራለች ፡

ባትደፈርም ፡ አልተደፈረችም ፡ አትባልም” ።

“ እንኩዋን ፡ ከወንድ ፡ ከዘመድ ፡ ርቄ ፡ ባዘን ፡ ተጨንቄ ፡ እንጀራ ፡ በንባዩ ፡ እያራስሁ ፡ እዬበላሁ ፡ መቀመጤ ፡ እንዶኝ ፡ ያገሬ ፡ ሰው ፡ ለክፉ ፡ እድሌ ፡ ተባባሪ ፡ ሆኖ ፡ አላስቀምጠኝ ፡ ሲል ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ላድርግ ? እግዚአብሄር ፡ ይየው ፡ እንጂ ! ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ራሳቸውን ፡ እግዚአብሄር ፡ ወዳለበት ፡ ወደላይ ፡ ቀና ፡ አድርገው ።

“ልብዎ ፡ የተጫነውን ፡ ከባድ ፡ አዘን ፡ በትእግስትና ፡ በንጽህና ፡ ተሸክመው ፡ መኖርዎን ፡ ክርስዎና ፡ ከእግዚአብሄር ፡ በቀር ፡ ማን ፡ ያውቅልዎታል ? ሰው ፡ ለብሰውና ፡ መልክዎ ፡ አምሮ ፡ ሲወጡ ፡ ሲያይ ፡ ደስ ፡ ብሎዎ ፡ የስጋ ፡ ፈቃድዎን ፡ ፈጽመው ፡ የሚኖሩ ፡ ይመስለዋል ፤ ሰው ፡ እግዚአብሄር ፡ አይ ደለምና ፡ የውጩን ፡ እንጂ ፡ የውስጡን ፡ አያይም ።!”

“ እኔና ፡ እግዚአብሄር ፡ የምናውቀው ፡ እርስዎ ፡ የማያ ውቁት ፡ አለ ፡ አባቴ ? ”

እኔማ ..... እኔስ ፡ እዚህ .... እዚሁ ፡ በባዶ ፡ ቤት ፡ የገዛ ፡ ጉል በትዎን ፡ እያቀፉ ፡ እዬተኙ ፡ በንጽህና ፡ እንደሚኖሩ ፡ ..... አው ቃለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የኔ ፡ ብቻ ፡ ማወቅ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ? ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ መድሀኒቱ ፡ የሀሜተኛውን ፡ አፍ ፡ የሚዘጋ ፡ የተ ሰበረ ፡ ልብዎን ፡ የሚጠግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የሚያደርግ ፡ አሁን ፡ እንደነገርሁዎ ፡ ያው ፡ ትዳር ፡ መያዙ ፡ ነው ። አዩ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ የባልን ፡ አዘን ፡ ማሸነፍ ፡ የሚቻል ፡ ባል ፡ በማግ ባት ፡ ነው ። ግዴለዎትም ፡ እኔ ፡ ለስዎ ፡ የሚጠቅምንጂ ፡ የሚ ጐዳ ፡ ምክር ፡ አልመክርዎትም ። ”

እመት ፡ ውድነሽ ፡ አይናቸቸውን ፡ ከባ ፡ ታምሩ ፡ ላይ ፡ አንስተው ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ትኩር ፡ ሲያደርጉ ፡ እንባቸው ፡ በቅጽ በት ፡ አይናቸውን ፡ ሞልቶ ፡ ወዲያው ፡ ይፈስ ፡ ጀመረ ።

“ ኧረ ፡ ባዛኝቱ ! ምነው ፡ እመት ፡ ውድነሽ ? ልጅ ፡ አይ ባሉ ፡ ትልቅ ፡ ሴት ፡ ነዎ ፤ ታዲያ ፡ ሰው ፡ ችግር ፡ ሲገጥመው ፡ ከዘመድ ፡ ከወዳጁ ፡ ተመካክሮ ፡ የሚበጀውን ፡ ያደርጋልንጂ ፡ እንደ ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ ችግሩን ፡ እያሰበ ፡ ሲያለቅስ ፡ ይኖራል ፡ እንዴ ? እንደዚህ ፡ ከሆኑማ ፡ እንኩዋን ፡ ለምክር ፡ ለሰላምታም ፡

እደጅዎ ፡ መድረሱን ፡ እተወዋለሁ ! ” አሉ ፡ አባ ፡ ታምሩ ።

“ይቅር ፡ ይበሉኝ ፡ አባቴ ፤ ይቅር ፡ ይበሉኝ ፡ ሆድ ፡ ብሶኝ ፡ ነው ። በኀዳሎ ፡ ሌሊት ፡ የተፈጠርሁ ፡ እድለ ፡ ክፉ ፡ በመሆኔ ፡ ነውንጂ ፡ እሰዎ ፡ እንዲርቁኝ ፡ እሰዎ ፡ እንዳይመክሩኝ ፡ አይ ደለም ፡ የማለቅስ ። እንኳዋን ፡ ለስጋዩ ፡ ለነፍሴስ ፡ ባላደራው ፡ እሰዎ ፡ አይደሉም ፡ አባቴ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ አለኝ ! ” አሉ ፡ እንባ ቸውን ፡ በጅጌያቸው ፡ እየጠረጉ ።

“ይህ ፡ እላፊነቴ ፡ ከብዶኝማ ፡ ነው ፡ በየቀኑ ፡ እዬመጣሁ ፡ የምጨቀጭቅዎ ! ወዲያውም ፡ እድልዎን ፡ ማማረር ፡ አይገ ባም ። ሰው ፡ ገና ፡ ሲወለድ ፡ እድሜው ፡ ከእግዚአብሄር ፡ ተሰ ፍሮ ፡ የሚሰጠው ፡ ስለሆነ ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ እሰዎን ፡ ቢያገ ቡም ፡ ባያገቡም ፡ ከእግዚአብሄር ፡ የተወሰነላቸው ፡ እድሜ ፡ ሲያልቅ ፡ መሞታቸው ፡ አይቀርም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የሰው ፡ አፍ ፡ እዬሰሙ ፡ እግዚአብሄርንም ፡ እድልዎንም ፡ ማማረር ፡ አይገባዎትም” ።

“ እሱስ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ ብቻ ፡ የሰው ፡ መላስ ፡ ከሳት ፡ የበለጠ ፡ ያቃጥላል ። በቀደም ፡ እዚያ ፡ እሰንበቴው ፡ ከብላታ ፡ በዬነ ፡ ባለቤት ፡ ጋር ፡ ባንዳንድ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ተከራክረን ፡ የምትረታ ፡ ስትሆን ፡ ጊዜ ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ እኔን ፡ ስትነካኝ ፡ የሚያሳምመኝና ፡ የሚያሳፍረኝ ፡ ቁስል ፡ ፈልጋ ፡ “ እንቺ ፡ ባሎችሽን ፡ የፈጀሽ ፡ የባል ፡ በሽታ ፡ ” ብላ ፡ በተሰበሰበው ፡ ህዝብ ፡ ፊት ፡ ሰደበችኝ ።” አሉና ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ያነ ለት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እሳቸውን ፡ እያዩ ፡ የሳቀውና ፡ ያሽሙዋጠ ጠው ፡ ታያቸውና ፡ እንደገና ፡ እንባቸው ፡ ባይናቸው ፡ ቸር ፈፍ ፡ አለ ።

“ እንግዲህ ፡ እገዝትዎታለሁ ፡ አዛኝቱን ! እንዲህ ፡ ያለ ውን ፡ ነገር ፡ እግዚአብሄር ፡ አይወደውም ። ” አሉ ፡ አባ ፡ ታምሩ ፡ የመት ፡ ውድነሽ ፡ አይን ፡ እንደገና ፡ እንባ ፡ ሲሞላ ፡ ስላዩ ፡ እንደመቆጣት ፡ ብለው ፡ ጭራቸውን ፡ ከቀኝ ፡ ወደግራ ፡ ሽው ፡ እደረጉና ።

“ ያይን ፡ ጅማቴን ፡ መከፋት ፡ እላልቶት ፡ እንባ ፡ እላ ቆም ፡ ብሎ ፡ ነውንጂ ፡ ለማልቀስ ፡ ፈልጌ ፡ አይምሰልዎ ። እባ

ክዎ ፡ ይቅር ፡ ይበሉኝ ፡ አባቴ ። ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ እንደገና ፡ አይናቸውን ፡ እየጠረጉ ።-

“ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ መድሀኒቱ ፡ ይህ ፡ ስነግርዎ ፡ የሰነበትሁት ፡ ነው ። እኒህን ፡ ሰው ፡ ያግቡ ፤ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ምክር ፡ አልመከርዎትም ። ”

“የሞተ ፡ እንደሆንስ ? እኔስ ፡ መቼም ፡ ሳፍር ፡ ስሰቃይ ፡ ኖሬ ፡ እንዳልፍ ፡ ፈርዶብኛል ! በሱ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ላስፈርድበት ? ”

“ ወይ ፡ የማንኩሳው ፡ አባቴ ! እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ልንገርዎ ? ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ የወሰነለት ፡ እድሜ ፡ ካላለቀ ፡ አይሞትም ፤ መጽሀፉ ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አልነገርሁዎትም ? ”

“ መጽሀፉ ፡ ባል ፡ የሚሞትባት ፡ ሴት ፡ እስከ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ እንድታገባ ፡ ይፈቅዳል ?” ይህን ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ታምሩ ፡ ሰምተውት ፡ የማያውቁት ፡ ጥያቄ ፡ ስለመጣባቸው ፡ እሳባቸው ፡ እንደመሸበር ፡ ግንባራቸው ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መውዛት ፡ አለና ፡ ወዲያው ፡ ጭራቸውን ፡ ዘቅዝቀው ፡ አገጫቸውን ፡ በጭራው ፡ ቀንድ፡ ደገፍ ፡ አድርገው ፡ አይኖቻቸውን ፡ ወደጣራው ፡ ትኩር ፡ አደረጉ፡ መልሱ ፡ እጣራው ፡ ላይ ፡ እንደተጻፈ ፡ ሁሉ ። እንዲህ ፡ አንጋጠው፡ ትንሽ ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ፡ ቀስ ፡ አድርገው ፡ የጭራውን ፡ ቀንድ ፡ ከገጫቸው ፡ ስር ፡ አስወገዱና ፡ አይኖቻቸውን ፡ ወደ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ መለስ ፡ አድርገው ።-

“መጸሀፉ ፡ . . . .አይወስንም ፤ እንግዲህ ፡ ካልወሰነ ፡ ካራተኛ ፡ በላይንኩዋ ፡ አስረኛንኩዋ ፡ ለማግባት ፡ ትችላለች ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ” አሉ ፡ አባ ፡ ታምሩ ፡ አፋቸው ፡ እየፈራ ።

“አስረኛ ? ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ አይናቸውን ፡ በጥፍ ፡ ከፎቱ ፡ አውጥተው ።

“አይ ፡ አስር ፡ ስልኮ ፡ አለመወሰኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የተናገርሁት ፡ ያነጋገር ፡ ዘዴ ፡ ነውንጂ ፡ መጽሀፉ ፡ በተጻፈበት ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ዘጠኝ ፡ ባሎች ፡ ሞተውባት ፡ አስረኛ ፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ ኖራ ፡ አይደለም ፤ ወደፊትም ፡

እንዲህ ፡ ያለ ፡ እንደማይደርስ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ቢደርስ ፡ መጽሀፉ ፡ አይከለክልም ፡ ለማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሚነገር ፡ አይደለም ፡ አደራዎ ፡ በስዎና ፡ በኔ ፡ መሀከል ፡ የሚቀር ፡ ነው ።" አሉ ፡ አባ ፡ ታምሩ ፡ ፊታቸውን ፡ ከስተር ፡ አድርገው ፡ ለወይዘሮ ፡ ውድነሽ ፡ የተናገሩት ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ ራሳቸውም ፡ እርግጠኛ ፡ ስላልነበሩ ፡ ሰግተው ።

"ምነው ፡ አባቴ ፡ በኔና ፡ በስዎ ፡ መሀከል ፡ የሚነገር ፡ ሁሉ ፡ ቁርባን ፡ መሆኑ ፡ ቀረ ?"

" አይ ፡ እንዲያው ፡ ማስጠንቀቅ ፡ አይከፋም ፡ ብዬ ፡ ነው ።"

" እሉስ ፡ ይሁን ፡ ግዴለም ፡ እስቲ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅዎ ፡ አባቴ ፡ መቼም ፡ ከተነጋገርነው ፡ ሁሉ ፡ አይበልጥም ። መጀመሪያ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሲያነሱልኝ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አሳቤን ፡ የሚከነክነውና ፡ ልረዳው ፡ ያልቻልሁ ፡ ............ .........እሉና ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ትንሽ ፡ እንደማፈር ፡ ብለው ፡ አፋቸው ፡ ሲፈራ ፡ አዩና ፡ አባ ፡ ታምሩ ፡ -

" አሳብዎን ፡ የከነከነው ፡ ምንድነው ? " አሉ ።

" እያ ፡ ቢጋስ ፡ የደረሰብኝንና ፡ .......ሰው ፡ ..... የሚለውን ፡ ሁሉ ፡ እዚህ ፡ ተቀምጦ ፡ እያወቀ ፡ ላግባ ፡ ብሎ ፡ መጠየቁ ፡ ማዘኔን ፡ ስለተረዳ ፡ ደስ ፡ ላሰኛት ፡ ልጽደቅባት ፡ ብሎ ፡ ነው ? ወይስ ...........ምንድነው ? "

"አይደለም ፡ ደስ ፡ አሰኝቻት ፡ ደስ ፡ ታሰኘኛለች ፡ ብለው ፡ ነውንጂ ፡ ልጽደቅባት ፡ ብለው ፡ አይደለም ። " አሉ ፡ አባ ፡ ታምሩ ።

" እንዴት ? "

"እስዎ ፡ ባሎችዎ ፡ በመሞታቸው ፡ ምክንያት ፡ እሳቸው ፡ በሌላ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ ብቸኛነት ፡ የሚያስከትለውን ፡ መከፋት ፡ ደኅና ፡ አድርጋችሁ ፡ ያወቃችሁ ፡ ስለሆናችሁ ፡ ሁለታችሁ ፡ ብትገናኙ ፡ ተስማምታችሁ ፡ እንደምትኖሩ ፡ በማመን ፡ ነው ። እያ ፡ ቢጋስ ፡ ቆዳቸው ፡ ጥኝ ፡ ቢመስል ፡ የዋዛ ፡ ሰው ፡ አይምሰሉም ፡ ውስጠ ፡ መሰሪ ፡ ናቸው ፡ " አሉ ፡ አባ ፡ ታምሩ ።

" እመት ፡ ውድነሽ ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ካሳባቸው ፡ ጋር ፡ መጫወት ፡ ስለጀመሩ ፡ -

" ይበሉኮ ፡ እሺ ፡ ይበሉኝና ፡ አሳርጌ ፡ ልሂድ ፡ " አሉ ፡ አባ ፡ ታምሩ ። ከዚያ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ሳምባቸው ፡ እስኪ ሞላ ፡ ጠለቅ ፡ አድርገው ፡ አዬር ፡ ስበው ፡ በረዥሙ ፡ ተነፈሱና ፡-

"እሺ ፡ አባቴ ፡ እስዎ ፡ የመከሩኝን ፡ አልቀበልም ፡ ብዬ ፡ ወዴት ፡ እደርሳለሁ ? እሺ ። "

" እግዚአብሄር ፡ እሺ ፡ ይበልዎ ፤ ጋብቻውንም ፡ የደስታ ፡ ጋብቻ ፡ ያድርገው ። አይዞዎ ፤ ያለፈውን ፡ ሁሉ ፡ ይርሱ ፤ እም ነትዎን ፡ በእግዚአብሄር ያድርጉ ። ግዴለዎትም ፡ ወደፊት ፡ ምንም ፡ አይደርስብዎትም ፤ እኔም ፡ እጸልያለሁ ።"

" በጸሎትዎ ፡ አይርሱኝ ፡ አባቴ ፡ " አሉ ፡ እመት ፡ ውድ ነሽ ፡ በተሰበረ ፡ ድምጽ ፡ ከንባ ፡ ጋር ፡ እዬተናነቁ ። ከዚያ ፡ ቄስ ፡ ታምሩ ፡ የወይዘሮ ፡ ውድነሽን ፡ እንባ ፡ እንዳያዩ ፡ ወዲያ ፡ ለማባረር ፡ እንደፈለጉ ፡ ጭራቸውን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ሽው ፡ ሽው ፡ አድርገው ፡ ቶሎ ፡ ብድግ ፡ አሉና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መሬት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጣራ ፡ እያዩ ፡ አሳርገው ፡ እጃቸውን ፡ ለመት ፡ ውድነሽ ፡ አሳልመው ወጡ ። እመት ፡ ውድነሽም ፡ እንባቸውን ፡ በቀ ሚሳቸው ፡ እጅጌ ፡ እያደረቁ ፡ እስከ ፡ በሩ ፡ የንስሀ ፡ አባታቸ ውን ፡ ተከትለው ፡ ሸኝተዋቸው ፡ ተመለሱ ።

እመት ፡ ውድነሽ ፡ ቄስ ፡ ታምሩን ፡ ተሰናብተው ፡ ተመ ልሰው ፡ እቤታቸው ፡ ቁጭ ፡ ሲሉ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ የብቸኛነት ፡ ኑሮ ፡ በሁዋላ ፡ ባል ፡ የማግባቱ ፡ አሳብ ፡ የፈጠረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስሜት ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ተደበላልቆ ፡ በራሳቸው ፡ ውስጥ ፡ ይንጫ ጫባቸው ፡ ጀመር ። የብላታ ፡ በዬነ ፡ ባለቤትና ፡ እንደሳቸው ፡ በመት ፡ ውድነሽ ፡ የሚቀኑት ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ የሚሉት ፡ የገ ላው ፡ ጸሀይ ፡ ምሽትና ፡ ሌሎች ፡ የመት ፡ ውድነሽ ፡ ወዳጆች ፡ የሚሰማቸው ፡ ደስታ ፡ በጋለ ፡ መብራቱ ፡ እመት ፡ ውድነሽን ፡ ያገቡ ፡ ሁሉ ፡ ሲሞቱ ፡ እያዩና ፡ የሞት ፡ መድሀኒት ፡ እንደሌ ላቸው ፡ እያወቁ ፡ ላግባ ፡ ማለታቸው ፡ ፍቅራቸው ፡ እመት ፡ ውድነሽን ፡ ከሌሎች ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ አብልጦ ፡ ሞትን ፡ እስ ንቆ ፡ ስላሳያቸው ፡ መሆኑ ፡ የበጋለ ፡ መብራቱ ፡ መልክ ፡ ማማ

ርና ፡ ድህነታቸው ፡ የሞቱት ፡ ባሎቻቸው ፡ መልክና ፡ ሀብት ፡ የሳቸው ፡ የራሳቸው ፡ መልክ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ተደ በላልቆ ፡ ይታያቸው ፡ ጀመር ። በሁዋላ ፡ የራሳቸው ፡ መልክ ፡ ማግር ፡ ሁሉንም ፡ አሸንፈና ፡ ባይነህሊናቸው ፡ ፊት ፡ ጐልቶ ፡ ታያቸው ። ወዲያው ፡ አባ ፡ ታምሩ ፡ " ደህና ፡ ለብሰው ፡ መል ክዎ ፡ አሞሮ ፡ ሲታዩ ፡ ደስ ፡ ያለዎና ፡ የስጋ ፡ ፈቃድዎን ፡ ፈጽ መው ፡ የሚኖሩ ፡ ይመስላሉ ። " ያሉት ፡ ትዝ ፡ አላቸው ።

" የስጋ ፡ ፈቃድዎን ፡ ፈጽመው ፡ የሚኖሩ ! ቄስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ሲናገር ፡ ገና ፡ ዛሬ ፡ ሰማሁ ! " አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ብቻቸውን ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብለው ፡ መልካቸውን ፡ ሰማየት ፡ መስታወት ፡ ፍለጋ ፡ ሲነሱ ።

እመት ፡ ውድነሽ ፡ ሙዳያቸውን ፡ ከጉሽጉሽ ፡ ላይ ፡ አው ርደው ፡ ይዘው ፡ ተቀመጡና ፡ የመጨረሻ ፡ ባላቸውን ፡ ብላታ ፡ ብዙነህን ፡ ሲያገቡ ፡ የገዙዋትን ፡ ክብ ፡ መስታወት ፡ አውጥተው ፡ በግ ፡ አድርገው ፡ ሲከፍቱ ፡ አንዲት ፡ እንደመስተዋቱ ፡ ክብብ ፡ ያለች ፡ ፊት ፡ ከመስታወቱ ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ አለች ። ትኩር ፡ ብለው ፡ ሲያዩዋት ፡ እስዋም ፡ ትኩር ፡ ብላ ፡ አየቻቸው ። አንገ ታቸውን ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ዘንበል ፡ አድርገው ፡ ወደመስታዋቱ ፡ ቀረብ ፡ ሲሉ ፡ እስዋም ፡ አንገትዋን ፡ ዘንበል ፡ አድርጋ ፡ ወደሳ ቸው ፡ ቀረብ ፡ አለች ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ያችን ፡ የምታምር ፡ ክብ ፡ ፊት ፡ እየተመለከቱ ፡-

" አንዲት ፡ ፍሬ ፡ ልጅ ! " አሉ ። " አንዲት ፡ ፍሬ ፡ ልጅ ! ሞት ፡ የምታስንቂ ፡ የምታምሪ ፡ አንዲት ፡ ፍሬ ፡ ልጅ ! " አሉ ፡ እመስታዋቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለችውን ፡ ፊት ፡ እንደሚስሙ ፡ ሁሉ ፡ ከንፈራቸውን ፡ ወደፊት ፡ ሙጥሙጥ ፡ አድርገው ። እስ ዋም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገች ። ከዚያ ፡ እዩሳቁ ፡ ወደሁዋላ ፡ ራቅ ፡ ሲሉ ፡ እስዋም ፡ እዩሳቀች ፡ ወደሁዋላ ፡ ራቅ ፡ አለች ።

" ወዬው ፡ ጉድ ! አሁን ፡ የማደርገውን ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ የሚያይ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ይለኝ ፡ ነበር ? አብዳለች ፡ ትታሰር ፡ እባል ፡ ነበር ! የብቻ ፡ መኖር ፡ አንድ ፡ ጥቅሙ ፡ የሰሩትን ፡ ሰርቶ ፡ ያልሰሩ ፡ መስሎ ፡ ለመታዩት ፡ ማስቻሉ ፡ ነው ! ለካ ፡ ሰውን ፡ እብድ ፡ የሚያሰኘው ፡ እብድ ፡ የሚያደርገውን ፡ ማድ

ረግ ፡ አይደለም ፤ እብድ ፡ የሚያደርገውን ፡ ሲያደርጉ ፤ መታ ገቱ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ፊታቸው ፡ ትንሽ ፡ እን ደማዘን ፡ ብሎ ። እመስታዋቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለችው ፡ ከብ ፡ ፊትም ፡ እሳቸው ፡ ሲያዝኑ ፡ አይታ ፡ እንደማዘን ፡ አለች ። ግንባራቸ ውን ቁጥር ፡ አይናቸውን ፡ ትኩር ፡ አድርገው ፡ በተመለከ ቱዋት ፡ መጠን ፡ አዝና ፤ ግንባርዋ ፡ ከቅንድቦችዋ ፡ መሀከል ፡ ታጥፎ ፤ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ስድብ ፡ በጉልህ ፡ ተጽፎ ፡

አዩ ፤ አነበቡት ፡ “እንቺ ፡ ባሎችሽን ፡ የፈጀሽ ፡ የባል ፡ በሽታ ፡” ይላል ፡ ስድቡ ። “የማንኩሳው ፡ አባቱ ፤ የማንኩሳው ፡ አባቴ ፡ ምነው ፡ ምን ፡ አልሁህና ፡ ስድብ ፡ ላማረው ፡ ሁሉ ፡ መስደ ቢያ አደረግኸኝ ፡ እባክህ ፡ በቃሽ ፡ በለኝ !” አሉና ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ መስታዋቱን ፡ ጥለው ፤ አይናቸውን ፡ በሁለት ፡ እጃ ቸው ፡ ሸፍነው ፡ ያለቅሱ ፡ ጀመር ።

# ምዕራፍ ፡ ፪ ፡

## በዛብህ፡-

አቶ ፡ ቦጋለ ፡ መብራቱ ፡ ወይዘሮ ፡ ውድነሽ ፡ በጣሙን ፡ ጥገቡ ፡ በሁለተኛው ፡ አመት ፡ መጨረሻ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወለደላቸው ። ብቻ ፡ ሁለቱ ፡ የሁለት ፡ አለም ፡ ሰዎች ፡ ስለነበሩ ፡ ይልቁንም ፡ ገና ፡ የጋብቻ ፡ ኑሮዋቸውን ፡ እንደጀመሩ ፡ በመሀከላቸው ፡ ግጭቱም ፡ ኩርፊያውም ፡ ይበዛ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እድሜ ፡ ከሰጠ ፡ ለልማድ ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ ከተሰጠው ፡ እንኩዋን ፡ ሰውን ፡ ጅብና ፡ አህያን ፡ ነብርና ፡ ፍዬልን ፡ አብረው ፡ እንዲኖሩ ፡ ለማድረግ ፡ ስለሚቻል ፡ ጊዜ ፡ ባለፈ ፡ መጠን ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ እስበሳቸው ፡ እዬተዋወቁ ፡ እዬተለማመዱ ፡ እዬተዋደዱ ፡ የመተሳሰብ ፡ ማሰሪያቸው ፡ እዬጠበቀ ፡ ሄደ ።

ወይዘሮ ፡ ውድነሽ ፡ ከባለጸጎች ፡ ወገን ፡ ተወልደው ፡ በደህና ፡ ያደጉ ፡ ከዚያ ፡ ባል ፡ ለማግባት ፡ ሲደርሱ ፡ ሶስት ፡ ባለጸጎች ፡ ባሎች ፡ በተራ ፡ አግብተው ፡ በጌትነት ፡ የኖሩ ፡ ሶስት ፡ ባሎቻቸውን ፡ በተራ ፡ ከቀበሩ ፡ በሁዋላም ፡ ያገሩ ፡ ሰው ፡ ስድብና ፡ ሽሙጥ ፡ ከሳቸው ፡ አልፎ ፡ ተርፎ ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ሲነካና ፡ ሲያሳፍር ፡ በማየታቸው ፡ ከዘመድ ፡ ከወዳጅ ፡ ርቀው ፡ ነፍሳቸውን ፡ ይግርና ፡ አባታቸው ፡ ያወረስዋቸው ፡ ሀብት ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ አንዲት ፡ ሙያተኛ ፡ እዬረዳቻቸው ፡ ለብቻቸው ፡ በመቤት ፡ ወግ ፡ የሚኖሩ ፡ ነበሩ ። መቸም ፡ ብቻቸውን ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ ለቤታቸውና ፡ ለዚያች ፡ ላንዲት ፡ ሙያተኛ ፡ ንግስቲትዋ ፡ ይግባኝ ፡ የሌለባቸው ፡ ቆራጭ ፡ ፈላጭዋ ፡ እሳቸው ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ከዚያ ፡ በፊትም ፡ ቢሆን ፡ ልጅ ፡ ሳሉ ፡ ወላጆቻቸው ፡ በሁዋላ ፡ ባሎቻቸው ፡ የበላይ ፡ አዛዦች ፡ ተቆጭዎች ፡ አሸናፊዎች ፡ ቢሆኑም ፡ እሳቸው ፡ በፊንታቸው ፡ የሚያዝዙት ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ አርገው ፡ ገላምጠው ፡ የሚቆጡት ፡ የሚያሸንፉት ፡ ከበታቻቸው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ የሚጠሩ ፡ ብዙ ፡ ነበራቸው ። ወደታች ፡ እያዩ ፡ የሚያዙት ፡ ካለ ፡ ከላይ ፡ የሚያዝ ፡ ቢኖር ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ አይከብድም ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ አርጎ ፡ አይቶ ፡ የማቆጡትና ፡ የሚመቱት ፡ በታች ፡ ካለ ፡ ከላይ ፡ የሚቆጣና ፡ የሚመታ ፡ ቢኖር ፡

እያምም ፡ የሚያሸንፉት ፡ በታች ፡ ካለ ፡ ከላይ ፡ የሚያሸንፍ ፡ ቢኖር ፡ ግድ ፡ የለም ። እቦጋለ ፡ መብራቱ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ የሚያዝ ፡ እንጂ ፡ የሚያዙት ፡ የሚቀጣ ፡ እንጂ ፡ የሚቀጡት ፡ የሚያሸንፍ ፡ እንጂ ፡ የሚያሸንፉት ፡ አለመኖሩ ፡ አስቀድሞ ፡ የወይዘሮ ፡ ውድነሽን ፡ አመል ፡ አከፋው ። አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ሲፈሩ ፡ ሲቸሩ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲደረግ ፡ ያሳሰቡ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲፈልጉ ፡ ባልዮው ፡ ትንሽ ፡ እንኩዋ ፡ የመቃወም ፡ ምልክት ፡ ያሳዩ ፡ እንደሆነ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ይበሳጩና ፡ ወዲያው ፡ እንዳይቶአጣዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ሆድ ፡ ብሶዋቸው ፡ ማልቀስ ፡ ይጀምራሉ ። ያልተለመደ ፡ እንግዳ ፡ ችግር ፡ ቆዳ ፡ ያሳሳል ፡ ሆደ ፡ ባሻ ፡ ያደርጋል ። ደግነቱ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ከተቀጡና ፡ ካለቀሱ ፡ በሁዋላ ፡ ትንሽ ፡ ቆይተው ፡ ሁሉንም ፡ መርሳታቸው ፡ ነው ።

አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ከድሆች ፡ ወገን ፡ ተወልደው ፡ በድህነት ፡ ያደጉ ፡ ከህጻንነት ፡ እስከ ፡ እኩል ፡ እድሜ ፡ ችግር ፡ ያልተለያቸው ፡ ከችግር ፡ ጋር ፡ ሲታገሉ ፡ ሲጥሉት ፡ ሲጥላቸው ፡ አብረው ፡ የኖሩ ፡ ቆዳቸው ፡ ጠንክሮ ፡ ስድብ ፡ ይሁን ፡ ቁጣ ፡ የማይዘልቀው ፡ ነበሩ ። እንኩዋን ፡ ትንሽ ፡ ትልቅ ፡ ቢሆን ፡ የሚገጥማቸውን ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ በጸጥታና ፡ በትግስት ፡ የሚቀበሉና ፡ ለማሸነፍ ፡ የሚሞክሩ ፡ እንጂ ፡ ቶሎ ፡ ሆድ ፡ የሚብሳቸውና ፡ ተስፋ ፡ የሚቆርጡ ፡ አልነበሩም ። ችግር ፡ ሲለምዱት ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ችግር ፡ ሲለምዱት ፡ ጉዋደኛ ፡ ሲያደርጉት ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ እዬታገሉ ፡ እዬወደቁ ፡ እዬተነሱ ፡ ሲኖሩ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ከችግር ፡ ጋር ፡ ሲታገል ፡ የኖረ ፡ ቆዳው ፡ ይወፍራል ፤ ጅማቱ ፡ ይጠነክራል ፤ ጡንቻው ፡ ይደነድናል ፤ የተጣለበትን ፡ ሁሉ ፡ ሸክም ፡ መሸከም ፡ ይችላል ፤ የገጠመውን ፡ ሁሉ ፡ ያሸንፋል ። ስለዚህ ፡ እድሜ ፡ ላሳዳጊያቸው ፡ እድሜ ፡ ላስተማሪያቸው ፡ እድሜ ፡ ለችግር ፡ ቦጋለ ፡ መብራቱን ፡ ቆዳቸውን ፡ አወፍሮ ፡ ጅማታቸውን ፡ አጠንክሮ ፡ ትግል ፡ እያስተማረ ፡ የስድብና ፡ የቁጣ ፡ የንቀትና ፡ የግልምጫ ፡ ውሽንፍር ፡ እንዳይገባቸው ፡ አድርጐ ፡ ሁሉን ፡ እንዳመሉ ፡ እንዲችሉ ፡ አድርጐ ፡ ላነጸቸው ፡ ለቀረጻቸው ፡ እድሜ ፡ ለችግር ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፡

ሁሉንም ፡ ቻይ ፡ ነበሩ ።

ይህ ፡ ያቶ ፡ ቦጋለ ፡ መቻል ፡ ትእግስታቸውና ፡ መሸነ
ፍን ፡ እንደ ፡ ውርደት ፡ አለመቁጠራቸው ፡ ከእመት ፡ ውድነሽ ፡
ይቅርባይነት ፡ ጋር ፡ የተቆጡበትንና ፡ ምርር ፡ ብለው ፡ ያለ
ቀሰበትን ፡ ቶሎ ፡ የሚረሱ ፡ ከመሆናቸው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡
ላይ ፡ ሆኖ ፡ ጊዜ ፡ ባለፈ ፡ መጠን ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ እንዲቻ
ቻሉ ፡ ባህሪ ፡ ለባህሪ ፡ እንዲተዋወቁ ፡ ለፍሬ ፡ እንዲበቁ ፡
ማን ፡ አለው ? ማን ፡ አላት ? እዩተባባሉ ፡ እንዲተሳሰቡ ፡
አደረጋቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ በሁዋላም ፡ ቢሆን ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡
አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲጋጩ ፡ አቶ ፡ ቦጋለና ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡
የተጋቡበትን ፡ ቀን ፡ መርገማቸውና ፡ ትንሽ ፡ ተኮራርፈው ፡
መቆዩታቸው ፡ አልቀረም ። ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ግጭ
ትና ፡ ኩርፊያ ፡ የባልና ፡ ምሽት ፡ ፍቅር ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መደ
ነዝ ፡ ሲል ፡ ለመሞረድና ፡ ለመሳል ፡ የሚያስፈልግ ፡ በሚዋ
ደዱ ፡ ባልና ፡ ምሽቶች ፡ ሁሉ ፡ የሚደርስ ፡ ግጭት ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ባላቸው ፡ ከስራ ፡ ገብ
ተው ፡ የሚበላ ፡ ነገር ፡ አለ ፡ እንደሆነ ፡ እንዲሰጡዋቸው ፡
ቢጠይቁዋቸው ፡ ልጁ ፡ ስለታመመባቸው ፡ የሚጠብቅላቸው ፡
አጥተው ፡ በጊዜ ፡ ምግብ ፡ ሊያሰናዱ ፡ አለመቻላቸውን ፡ ከተ
ናገሩ ፡ በሁዋላ ፡ ነገሩን ፡ ሳያስፈልግ ፡ አራዘሙና ፡ ማማረር ፡
ጀመሩ ። ከዚያ ፡ " እየ ፡ ቁስ ፡ ታምሩ ፡ እግዚአብሄር ፡ ይይ
ልዎ ፤ ብድሩን ፡ እግዚአብሄር ፡ በሴት ፡ ልጅዎ ፡ ይከፈልዎ ፡
ሳልሞት ፡ ገሀነም ፡ ያገቡኝ ፡" አሉና ፡ ምርር ፡ ብለው ፡ አለ
ቀሱ ። አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ለጊዜው ፡ ልባቸው ፡ ወደ ፡ ቁጣ ፡ ተለ
ውጦ ፡ ሊማቱ ፡ ከተነሱ ፡ በሁዋላ ፡ እንደገና ፡ በረድ ፡ አሉና ፡
አንድ ፡ ቃል ፡ ሳይናገሩ ፡ ሽመላቸውን ፡ ይዘው ፡ ወጥተው ፡
ከቤታቸው ፡ ጀርባ ፡ እጉብታዋ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ አሉ ።

" ገሀነም ፡ ያገቡኝ ! " አሉ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ምሽታቸው ፡
ያሉትን ፡ ደግመው ፡ አይናቸውን ፡ እፊታቸው ፡ በተዘረጋው ፡
ባዶ ፡ ላይ ፡ ትኩር ፡ አደረጉና ፡

" ምን ፡ አልሁዋት ? እስቲ ፡ ምን ፡ አልሁዋትና ፡ እን
ዲህ ፡ ያለ ፡ ከኮሶ ፡ የመረረ ፡ ነገር ፡ ተናገረችኝ ? " አሉ ፡ ራሳ

ቸውን ፡ እዩወዘወዙ ፡ አይናቸውን ፡ በባዶው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተከሉ ።

“ ሰው ፡ ከጥዋት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ በስራ ፡ ተጠምዶ ፡ ውሎ ፡ አቢቱ ፡ ሲገባ ፡ እንኳዋን ፡ ምሽቱን ፡ ሌላስ ፡ ቢሆን ፡ ርቦኛልና ፡ እህል ፡ አቅምሱኝ ፡ ማለት ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ያበሳጫል ? ከፉ ፡ ያናግራል ? ያስለቅሳል ? ”አሉ ፡ አይናቸውን ፡ በባደው ፡ ላይ ፡ እንዳፈጠጡ ፡ ከዚያ ፡ አፈታቸው ፡ ከተዘረጋ ፡ ባዶ ፡ ፍርድ ፡ እንደሚጠይቁ ፡ ሁሉ ፡ አይናቸውን ፡ አፍጠው ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ።

“ ለምን ፡ ምሽት ፡ አገባሁ ? ” አሉ ፡ አቶ ፡ በጋለ ፡ ራሳቸውን ፡ ትንሽ ፡ ወደቀኝ ፡ ዘንበል ፡ አድርገው ። “ ለምን ፡ ምሽት ፡ አገባሁ ? ለምን ፡ ቤት ፡ ሰራሁ ? ለምን ፡ ልጅ ፡ ወለድሁ ? ከድሮ ፡ ችግሬ ፡ ምን ፡ ቀለለኝ? ከድሮ ፡ ኑሮየ ፡ ምን ፡ ተሻለኝ ? ምንም ፡ አልተሻለኝ ፡ ምንም ፡ አልቀለለኝ ! ባሰብኝ ፡ እንጂ ፡ ባሰብኝ ። ድሮ ፡ ለምሽት ፡ አላስብ ፡ ለልጅ ፡ ለወር ፡ ጨው ፡ አላስብ ፡ ለህል ፡ ጌቶች ፡ የሰጡኝን ፡ በልቼ ፡ ጠጥቼ ፡ ለቤተሰቤ ፡ ምን ፡ እበላ ፡ ምን ፡ እለብስ ፡ ሳልል ፡ በሰላም ፡ እኖር ፡ ነበር ። የነበረኝ ፡ አሳብ ፡ ምራሁ ፡ ከቀንበሩ ፡ እርፉ ፡ ከሞፈሩ ፡ ማረሻው ፡ ከወገሉ ፡ መስማማቱን ፡ በሮች ፡ እንዳይጎዱ ፡ ወደደህና ፡ ሳር ፡ መሰማራታቸውን ፡ መመልከት ፡ ብቻ ፡ ነበር ። እየ ፡ ምንኛ ፡ መልካም ፡ ኑሮ ፡ እኖር ፡ ኖሬያለሁ ! የሰላም ፡ ኑሮ ! ” አሉና ፡ በጋለ ፡ መብራቱ ፡ ራሳቸውን ፡ በዝግታ ፡ አወዛውዘው ፡ ሁለት ፡ እጆቻቸውን ፡ አመሳቅለው ፡ እጉልበታቸው ፡ ላይ ፡ አድርገው ፡ ማንባራቸውን ፡ እከንዳቸው ፡ ላይ ፡ ደፍተው ፡ አይኖቻቸውን ፡ ሰበስ ፡ አድርገው ፡ ባሳብ ፡ ባህር ፡ ጠለቁ ። መነሻው ፡ መድረሻው ፡ የማይታወቅ ፡ ያሳብ ፡ ባህር ! የህይወት ፡ ታሪካቸው ፡ ያለፉት ፡ ያሉበት ፡ የሚመጣው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተጠራቅሞ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተደባልቆ ፡ የፈጠረው ፡ ጥልቅና ፡ ያሳብ ፡ ማእበል ፡ ያወከው ፡ ባህር ፡ አጠለቃቸው ፡ ይዋኙ ፡ ጀመር ። ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ ፍግም ፡ ቀና ! ፈፉ ፡ መውጣት ፡ ፈለጉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልቻሉም ፡ ስለዚህ ፡ ዋናቸውን ፡ ቀጠሉ ። በዚህ ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡ ድምጽ ፡

አንድ ፡ ትንሽ ፡ ድምጽ ፡ አንድ ፡ በሌሊት ፡ ከሩቅ ፡ እንደሚ ሰሙት ፡ ለስላሳ ፡ ቪዮሊን ፡ ልብ ፡ የሚነካ ፡ ድምጽ ፡ "እባ ፡- አ - አ - እባ ፡ አ" አለ ። ወዲያው ፡ ባህሩ ፡ ጸጥ ፡ አለ ። አቶ ፡ በጋሰን ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ ፍግም ፡ ቀና ፡ ሲያደርጋቸው ፡ ሲያን ገላታቸው ፡ የነበረው ፡ ማእበል ፡ ያ ፡ መላካዊ ፡ ድምጽ ፡ እን ደገሰጸው ፡ ቀም ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀጥ ፡ አለ ። " አባ - አ - አ - ባአአ ፡ ናአ - አ - አ ! " አለ ፡ ደገመና ፡ ድምጹ ። " ዝም ፡ በል ፡ የኔ ፡ ጌታ ! አይዞህ ፡ ዝም ፡ በል ! አባባ ፡ አሁን ፡ ይመጣል ፡ አባብዬ ፡ አሁን ፡ ይመጣልናል ! " አለ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ድምጽ ፡ አንድ ፡ የሴት ፡ ድምጽ ። የፊተ ኛው ፡ የልጃቸው ፡ የሁዋለኛው ፡ የምሽታቸው ፡ ድምጾች ፡ ነበሩ ። አቶ ፡ በጋለ ፡ ራሳቸውን ፡ ከኽንዳቸው ፡ ላይ ፡ ቀስ ፡ ለድርገው ፡ እንሰና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደግራ ፡ በቀስታ ፡ ዘወር ፡ ዘወር ፡ እያሉ ፡ ዙሪያ ፡ ገባውን ፡ ተመለከቱ ፡ እኒያ ፡ ድምጾች ፡ የመጡበትን ፡ እንደሚፈልጉ ፡ ሁሉ ። በዙሪያ ፡ ገባው ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አልነበረም ፡ ከቤታ ቸው ፡ በቀር ፡ ስለዚህ ፡ እኒያ ፡ ድምጾች ፡ ከየትም ፡ ሊመጡ ፡ አይችሉም ፡ ከዚያ ፡ ቤት ፡ በቀር ። በጋለ ፡ መብራቱ ፡ አይኖ ቻቸውን ፡ ትኩር ፡ አድርገው ፡ ይመለከቱ ፡ ጀመር ፡ አሁን ፡ ወደባዶው ፡ አይደለም ፡ ወደቤታቸው ፡ ከሰባት ፡ አመት ፡ በፊት ፡ ወደሰሩት ፡ ቤታቸው ። ከዚያ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ለበስ ፡ ሲያደርጉ ፡ ግርግዳውን ፡ ዘልቀው ፡ ምሽታቸውን ፡ ልጃቸ ውን ፡ ሁኔታቸውንም ፡ ሁሉ ፡ አዩ ። ቤታቸው ፡ ምሽታቸው ፡ ልጃቸው ፡ ሁኔታቸው ፡ ሁሉ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ለበስ ፡ ሲያ ደርጉ ፡ ወለል ፡ ብለው ፡ ታዩዋቸው ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አካላዊ ፡ አይኖች ፡ ሲዘጉ ፡ የማይታዩው ፡ ይታያል ። ለሰው ፡ ሁለት ፡ አይነት ፡ አይኖች ፡ አሉት ። አንዱ ፡ አይነት ፡ አካላዊ ፡ ሁለ ተኛው ፡ አይነ ፡ ሀሊና ፡ ናቸው ። ሁለቱ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አያ ዩም ፡ ቢያዩም ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ አያዩም ። አካላዊ ፡ አይ ኖች ፡ ማየት ፡ የማይችሉትን ፡ ለማየት ፡ አይነ ፡ ሀሊናን ፡ መክፈት ፡ ያስፈልጋል ። በጋለ ፡ መብራቱ ፡ እኒያን ፡ ከህልም ፡ አለም ፡ ወደ ፡ ውን ፡ አለም ፡ የመለሱዋቸውን ፡ ድምጾች ፡ ለመ

ፈለግ ፡ አካላዊ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ፍጥጥ ፡ አድርገው ፡ ተመለከቱ ፤ ማየት ፡ የሚቻለውንም ፡ አዩ ፤ አካላዊ ፡ አይኖች ፡ ማየት ፡ የማይችሉትን ፡ ለማየት ፡ ግን ፡ እነሱን ፡ ዘግተው ፡ አይነ ፡ ህሊናቸውን ፡ ከፈቱ ። ወዲያው ፡ ምሽታቸውን ፡ ልጃቸውን ፡ ድምጾችንም ፡ አዩ ። ቤታቸው ፡ ምሽታቸው ፡ ልጃቸው ፡ ጸጥታቸውንና ፡ ሰላማቸውን ፡ የለወጡባቸው ፤ የሰላም ፡ ዋጋ ! የጸጥታ ፡ ዋጋ !

" አልተጎዳሁም ! " አሉ ፡ አቶ ፡ በጋለ ፡ የማያዩ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ወደ ፡ ፊታቸው ፡ ፍጥጥ ፡ አድርገው ፡ በእሳባቸው ፡ ትንሽ ፡ ሲያስላስሉ ፡ ቆይተው ። " አልተጎዳሁም ፡ ጥሩ ፡ ዋጋ ፡ ነው ፤ ተሳስቻለሁ ፡ አልተጎዳሁም ! ራብ ፡ ከፋው ፡ እንዲህ ፡ ሊያልፍ ፡ ሽማግሌነቴን ፡ አስረሰቶ ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ አቅበጥብጦኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አልተጎዳሁም ! አየ ፡ - ለምን ፡ ሆድን ፡ ፈጠርህ ፡ ጌታዬ ? " አሉ ፡ አቶ ፡ በጋለ ፡ ቤት ፡ ማእርግ ፤ ልጅ ፡ ፍቅር ፡ የሰጡዋቸውን ፡ ምሽታቸውን ፡ ስለራባቸው ፡ ማስቀየማቸው ፡ በጣም ፡ አስጸጽቶዋቸው ። ወዲያው ፡ ባለፈው ፡ እሁድ ፡ አለቃ ፡ በላይ ፡ የሚባሉት ፡ ሊቅ ፡ ስለ ጾም ፡ ራስን ፡ ስለመግዛትና ፡ ስለጋብቻ ፡ በረዥሙ ፡ ከሰበኩት ፡ አንዳንዱ ፡ ትዝ ፡ አላቸው ።

" ሰው ፡ ከንስሳ ፡ የሚለይበት ፡ በሁለት ፡ እግሩ ፡ ቆሞ ፡ በመሄዱ ፡ አይደለም ፤ ዶሮም ፡ በሁለት ፡ እግር ፡ ነው ፡ የሚሄድ ። እንግዲያ ፡ ቋንቋ ፡ ስላለው ፡ ነው ? አይደለም ፤ እንስሳትም ፡ እስበሳቸው ፡ የሚግባቡበት ፡ ቋንቋ ፡ አላቸው ። ሰው ፡ ከንስሳ ፡ የሚለይበት ፡ አይነተኛ ፡ መለዮው ፡ ራሱን ፡ መግዛት ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ሰው ፡ ከንስሳ ፡ የሚለይበት ፡ ራብን ፡ ስስትን ፡ ሴሰኝነትንና ፡ እነሱን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ከእንስሳ ፡ ጋር ፡ የሚጋራቸውን ፡ ባህሪዎች ፡ ለመግታት ፡ በመቻሉ ፡ ነው ። በራብ ፡ ተገፋቶ ፡ የተመኘውን ፡ ሁሉ ፡ ልብላ ፡ ካለ ፡ በስስት ፡ ተገፋቶ ፡ ያዬውን ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ይሁን ፡ ካለ ፡ በሴሰኝነት ፡ ተገፋቶ ፡ ከሚመኛት ፡ ጋር ፡ ግብረ ፡ ዝሙት ፡ የሚፈጽም ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በሁለት ፡ እግሩ ፡ የሚሄድ ፡ እንስሳ ፡ ይሆናል ። ሰው ፡ ከስጋና ፡

ከመንፈስ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተዋህዶ ፡ እንደመፈጠሩ ፡ መጠን ፡ አለማዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ስሜቶች ፡ ያለማቋረጥ ፡ የሚፈራረቁበት ፡ የሚታገሉበት ፤ የሚዋጉበት ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ነው ። በንዲህ ፡ ያለው ፡ ጦርነት ፡ መንፈስ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ስጋንና ፡ የስጋን ፡ ፈቃዶች ፡ ሁሉ ፡ ይገታል ፤ ይገዛል ፡ ማለት ፡ ነው ። የሰውም ፡ መንፈስ ፡ በርትቶ ፡ ስጋውን ፡ ካሸነፈና ፡ የስጋውን ፡ ፈቃዶች ፡ መግታት ፡ ከቻለም ፡ ሰው ፡ ከስጋዊ ፡ አድፍና ፡ ጉስቁልና ፡ ነጽቶ ፡ ጠርቶ ፡ ወደሰማያዊ ፡ አምላኩ ፡ መቅረብና ፡ በጸሎት ፡ መነጋገር ፡ የጻድቃን ፡ ማህበርተኛ ፡ መሆን ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ለዚህ ፡ ነው ፡ ስራተ ፡ ጾም ፡ የተሰራበት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ። ጾም ፡ የተሰራ ፡ መንፈስን ፡ ለማበርታት ፡ ስጋን ፡ ለማድከም ፡ ሰውን ፡ ወደእንስሳት ፡ የሚለውጡትን ፡ ስጋዊ ፡ ምኞቶችና ፡ ፈቃዶች ፡ ለመግታት ፡ ወይም ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ መግዛት ፡ እንዲችል ፡ ነው ። ከመብልና ፡ ከመጠጥ ፡ መጾም ፡ ስጋን ፡ አድክሞ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከማሰብና ፡ ከመፈጸም ፡ ወደ ፡ መጾም ፡ ያደርሳል ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከማሰብና ፡ ከመፈጸም ፡ ከተጾመም ፡ የጻድቃን ፡ ማህበርተኛ ፡ የመላእክት ፡ ጉዋደኛ ፡ ወደመሆን ፡ ይደረሳል ።

“ ዝሙት ፡ ማለትስ ፡ ካላገቡዋት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ግብረ ፡ ዝማዌ ፡ መስራት ፡ ብቻ ፡ ነው ? አይደለም ። ሲያገቡ ፡ ሲፈቱ ፡ መኖርም ፡ ከዝሙት ፡ ይቆጠራል ። በተቀደሰው ፡ በተባረከው ፡ ጋብቻ ፡ ስም ፡ ሴት ፡ እየለዋወጡ ፡ ሲያገቡና ፡ ሲፈቱ ፡ መኖር ፡ ከዝሙት ፡ የተለዩ ፡ አይደለም ።

“ እግዚአብሄር ፡ ሰውን ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮ ፡ ስራተ ፡ ጋብቻን ፡ ሰርቶ ፡ መሬትን ፡ ሙሉዋት ፡ ብሎ ፡ ሲያዝ ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በዩቀኑ ፡ ሰው ፡ ስፈጥር ፡ ሀግና ፡ ስራት ፡ ስሰራ ፡ አልኖርምና ፡ የአለምን ፡ መጨረሻ ፡ እስከ መጣ ፡ ድረስ ፡ የቀደሙት ፡ ፈንታቸውን ፡ ኖረው ፡ ሲያልፉ ፡ የሴትን ፡ ግብር ፡ የምትፈጽም ፡ ሴት ፡ የወንድን ፡ ግብር ፡ የሚፈጽም ፡ ወንድ ፡ በቦታቸው ፡ እዩተኩ ፡ እንዲያልፉ ፡ አዲስ ፡ ተተኪዎችም ፡ በዚሁ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በተሰራው ፡

ሀግና ፡ ስራት ፡ ኖረው ፡ ሲያልፉ ፡ በበኩላቸው ፡ እንዲሁ ፡ እን ዲያደርጉና ፡ ይህ ፡ ሀግና ፡ ስራት ፡ የማይለወጥ ፡ ዘለአለማዊ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ አዝግለሁ ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ራስን ፡ ገዝቶ ፡ የስጋ ፡ ፍላጎቶቹን ፡ ገትቶ ፡ ጋብቻን ፡ አክብሮ ፡ በሁ ሞላም ፡ የእግዚአብሄርን ፡ ሀግና ፡ ስራት ፡ ለሁዋለኛ ፡ ትው ልድ ፡ የሚያስተላልፍ ፡ ዘር ፡ በቦታው ፡ ተክቶ ፡ ማለፍ ፡ የእግ ዚአብሄር ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ። ”

አቶ ፡ ቦጋለ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ገርበብ ፡ አድርገው ፡ ከድ ነው ፡ እጉብታዋ ፡ ላይ ፡ እንደተቀመጡ ፡ ይህን ፡ አለቃ ፡ በላይ ፡ ባለፈው ፡ እሁድ ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሰበኩትን ፡ ሲሰሙ ፡ ራሳቸውን ፡ አለቃ ፡ በላይን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በግር ፡ ጥፍራቸው ፡ እዩቆሙ ፡ እዩረዘሙ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ጉል በታቸውን ፡ ሽብረክ ፡ እያደረጉ ፡ እያጠፉ ፡ ክንዳቸውን ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ ላይና ፡ ታች ፡ እያወናጨፉ ፡ ፊታቸውን ፡ ፈገግ ፡ ኮስተር ፡ እያደረጉ ፡ ሲናገሩ ፡ ባይነ ፡ ህሊናቸው ፡ ሲያዩ ፡ ቆዩና ፡-

“ አሁሁሁሁ....... ” ብለው ፡ በረዥሙ ፡ ተነፈሱ ።

“ ከዚህ ፡ ከተናገሩት ፡ ሁሉ ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ሴሰኝነቱንና ፡ ስስቱን ፡ መግታት ፡ ካልቻለ ፡ ከከብት ፡ አይሻልም ፡ ያሉት ፡ ነው ። ይህ ፡ እውነታቸው ፡ ነው ፤ ራሱን ፡ የማይገዛ ፡ ሰው ፡ ሰው ፡ አይባልም ። ሌላው ፡ ሁሉ ፡ እንዲ ያው ፡ ለንግግር ፡ ማበርከቻ ፡ ነው ። ሰው ፡ እንኩዋን ፡ እስኪደ ክም ፡ እስኪሞት ፡ ቢጾም ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ ይሞታል ፡ እንጂ ፡ የመላእከት ፡ ጉዋደኛ ፡ ሲሆን ፡ የሚችል ፡ አይመስ ለኝም ። ብቻ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ሲናገር ፡ ምንም ፡ ሊቅ ፡ ቢሆን ፡ የተናገረው ፡ ሁሉ ፡ ፍሬ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ እንደህል ፡ ማለት ፡ ነው ። ካንድ ፡ ክምር ፡ እህል ፡ የሚገኘው ፡ ፍሬ ፡ ቢበዛ ፡ ካንድ ፡ ጎታ ፡ አይበልጥም ፤ የቀረው ፡ ገለባ ፡ ነው ። ይህም ፡ እንደዚያው ፡ ማለት ፡ ነው ፡” አሉ ፡ ቦጋለ ፡ መብ ራቱ ፡ እንደመንጠራራት ፡ አሉና ። ከዚያ ፡ ምሽታቸው ፡ የተ ናገሩትና ፡ ልቅሶዋቸው ፡ እንደገና ፡ መጣባቸውና ፡ አይናቸ ውን ፡ ሳያረግቡ ፡ ወደቤቱ ፡ አፍጥጠው ፡ ሲያስቡ ፡ ቆዩ ።

አይናቸው ፡ ቢፈጥም ፡ የምሽታቸውን ፡ ልቅሶ ፡ እንጂ ፡ ቤቱን ፡ አያዩም ፡ ነበር ።

" አዎን ፡ ልትበሳጭ ፡ ልታለቅስ ፡ ይገባታል ! " አሉ ፤ እንዲህ ፡ ሲያስቡ ፡ ቆይተው ። እሷዋ ፡ አትበሳጭ ? ማን ፡ ይበሳጭ ? እሷዋ ፡ አታለቅስ ፡ ማን ፡ ያልቅስ ? በሰፊው ፡ የለመደች ፡ ትልቅነው ፡ አሽከር ፡ ትጭነው ፡ ሰጋር ፡ የነበራት ፡ ወይዘሮ ፡ አይቶ ፡ አጣ ፡ እሷዋን ፡ ሆድ ፡ ያልባሰ ፡ ማንን ፡ ሆድ ፡ ይባሰው ? ቀን ፡ ቢጥላት ፡ ቀን ፡ ቢከፋባት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የጌቶች ፡ ልጅ ፡ እመቤቴ ፡ አልነበረችም ? ቢርበኝም ፡ የእሷዋን ፡ ችግር ፡ አይቼ ፡ ዝም ፡ አለማለቴ ፡ ጥፋተኛው ፡ እኔ ፡ ነኝ ። ልሂድና ፡ ማሪኝ ፡ ልበላት ! " አሉ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ባሳባቸው ። መቼም ፡ የሚወዱት ፡ ሲበድል ፡ ለበደሉ ፡ ምክንያት ፡ ማግኘት ፡ ቀላል ፡ ነው ። ከዚያ ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ ሽመላቸውን ፡ በሁዋላቸው ፡ እየጎተቱ ፡ ወደቤታቸው ፡ ገቡ ።

አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ሲገቡ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ እላይ ፡ ምድጃ ፡ ድስት ፡ እታች ፡ ምድጃ ፡ ምጣድ ፡ ጥደው ፡ ልጃቸውን ፡ በግራ ፡ ጎናቸው ፡ ይዘው ፡ ራት ፡ ቶሎ ፡ ለማድረስ ፡ ከላይ ፡ ታች ፡ ይጣደፉ ፡ ነበር ።

" እያ ፡ ቦጋለ ፡ መጣህ ? ራት ፡ እስኪደርስ ፡ ቶሎ ፡ ስት ቆረጥም ፡ እንድትቆይ ፡ ከጉዋዳ ፡ ይገፔ ፡ እስከመጣ ፡ ጠፋህ ብኝ ፤ ልጁ ፡ ሲያመው ፡ ጊዜ ፡ እየተቅበጠበጠ ፡ ሲያስቸግረኝ ፡ ውሎ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ አንተ ፡ መጥተህ ፡ ለኔ ፡ አስበሽልኝ ፡ አታውቂም ፡ ስትለኝ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የተቆጣሁ ። በል ፡ አሁንም ፡ ተቀመጥና ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ " አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ። ፍትግ ፡ የገብስ ፡ ቆሎ ፡ ከተወቀጠ ፡ ኑግ ፡ ጋር ፡ በዝርግ ፡ ሰፌድ ፡ ሆኖ ፡ እሳቱ ፡ ዳር ፡ እመደቡ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ። አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ሄደው ፡ እመደብ ፡ ሲቀመጡ ፡ ምሽታቸው ፡ ልጁን ፡ እባቱ ፡ አጠገብ ፡ አስቀምጠው ፡ ወደ ፡ ማጀት ፡ ገቡ ።

" ያን ፡ ምርር ፡ ብላ ፡ ያለቀሰችውን ፡ ሁሉ ፡ ረስተዋለች ፤ ይቅር ፡ ብላለች ። አየ ፡ ምነው ፡ የኔን ፡ ልብ ፡ እንደሷዋ ፡ ባደረው ! " አሉ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ባሳባቸው ። ወዲያው ፡ እመት ፡

ውድነሽ ፡ ከማጀት ፡ በሰፌ ፡ ቆንጬ ፡ ጠላ ፡ ይዘው ፡ መጡና ፡ አባላቸው ፡ ፊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፉት ፡ ብለው ፡ — “ እንካ ፡ ባይጥምም ፡ ጥም ፡ ይቆርጣል ።” አሉ ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ፡ ብለው ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ፡ ሲሉ ፡ የሚያስደነግጥ ፡ ልዩ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ነበራቸው ። አቶ ፡ በጋሻ ፡ ተቀብለው ፡ አንድ ፡ ጉንጭ ፡ ቀጡና ፡ ምሽታቸው ፡ ወደምጣዳቸው ፡ መሄድ ፡ ሲጀምሩ ፡-

“ውዴ ፡” አሉ ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ዘወር ፡ ቢሉ ፡ ያቶ ፡ በጋሻ ፡ ከንፈሮች ፡ ዘርዘር ፡ ያሉ ፡ ውብ ፡ ጥርሶቻቸውን ፡ ትተው ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሸሽ ፡ ብለው ፡ ፊታቸውና ፡ አይኖቻቸው ፡ ነውሩ ፡ እንደተገለጸበት ፡ ሰው ፡ ትንሽ ፡ የፍረት ፡ ቀለም ፡ ተባ ፡ አድርጎዋቸው ፡ አዩ ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ይህ ፡ አይነት ፡ አጠራርና ፡ ይህ ፡ አይነት ፡ አስተያየት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ ስለሚያውቁ ፡ ተመልሰው ፡ ወደባላቸው ፡ እዬሄዱ ፡ “ ምነው ! ” አሉ ። የሳቸውም ፡ ፊት ፡ ለልባቸው ፡ የተሰማውን ፡ የፍቅርና ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ እንደ ፡ ንጹህ ፡ መስተዋት ፡ አጥርቶ ፡ እያሳዩ ። የሳቸውም ፡ አይኖች ፡ እንደ ፡ ነውረኛ ፡ አይን ፡ የሚያርቁበት ፡ ጠፍቶዋቸው ፡ ይንከራተቱ ፡ ነበር ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ሀብታቸው ፡ ሲጠፉ ፡ በድህነታቸውና ፡ በችግራቸው ፡ ጊዜ ፡ እንከዋ ፡ በሁዋላ ፡ እድሜ ፡ እስኪወስድባቸው ፡ ድረስ ፡ ውበታቸውና ፡ ደም ፡ ግባታቸው ፡ አልተለዩዋቸውም ። አቶ ፡ በጋሻ ፡ የምሽታቸውን ፡ ቀኝ ፡ እጅ ፡ ይዘው ፡ ትንሽ ፡ ሳብ ፡ ሲያደርጉዋቸው ፡ እቅፋቸው ፡ ላይ ፡ ወደቁ ፤ ወዲያው ፡ ከንፈሮቻቸው ፡ ተገናኙ ።

“ እምጣዱ ፡ ላይ ፡ እንጀራ ፡ አለ ፤ ያራል ፡ ! ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ራሳቸውን ፡ አባላቸው ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ዛል ፡ አድርገው ፡ እንደጣሉ ፡ ሽቅብ ፡ አይናቸውን ፡ እያዩ ።

“ ይረር ፡ ምናባቱ ! ” አሉ ፡ ባልዬው ፤ እኒያ ፡ እደረታቸው ፡ ላይ ፡ የወደቁት ፡ ውብ ፡ ወይዘሮ ፡ የሳቸው ፡ እንዳልሆኑና ፡ የሄዱ ፡ እንደሆነ ፡ አይመለሱም ፡ ብለው ፡ እንደፈሩ ፡ ሁሉ ፡ እቅፋታቸውን ፡ ጠበቅ ፡ እያደረጉ ። በሁዋላ ፡ እመት ፡

ውድነሽ ፡ ተነስተው ፡ ወደምጣዱ ፡ ሲሄዱ ፡-

"አባባ ፡ እምዬ !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ከንፈሩን ፡ እሠቅሮ ። እኔንም ፡ እንደማማ ፡ ሳመኝ ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ አቶ ፡ በጋሻ ፡ እዩሳቁ ፡ ከተቀመጠበት ፡ እንስተው ፡ ታቅፈው ፡ እናቱን ፡ በሳሙበት ፡ አፋቸው ፡ ደጋግመው ፡ ሳሙት ።

"እየ ፡ እያ ፡ በጋለ ! እየ ፡ እያ ፡ በጋለ ! የምትሰራው ፡ ስራ !" አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ሙጣዱን ፡ ከምጣዱ ፡ ላይ ፡ ሲያነሱ ፤ እንጀራው ፡ ያረረ ፡ እያ ፡ በጋለ ፡ ብቻቸውን ፡ በሰሩት ፡ ስራ ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉ ።

"አረረ ?" አሉ ፡ ባልዮው ።

"አረረ ፡ ትላለህ ? ከሰል ፡ ሆነ ፡ እንጂ !"

"ተዪው ፡ ይረር ፡ ምናባቱ !"

"እሱስ ፡ ግድየለም ፡ ምጣዱ ፡ እንዳይበላሽ ፡ ነው ፡ እንጂ !"

"ለምን ፡ ይበላሻል ?"

"ምጣድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በላዩ ፡ እንጀራ ፡ ካረረ ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ እንጀራ ፡ ተበላሽቶ ፡ ነው ፡ ደህና ፡ ማውጣት ፡ የሚቻል ።"

"ታዲያ ፡ ይሁና !"

"እንዲያውስ ፡ ወደን ፡ ነው ?"

እመት ፡ ውድነሽና ፡ አቶ ፡ በጋለ ፡ በጣም ፡ የሚዋደዱ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ ነበሩ ። ብቻ ፡ የተወለዱበት ፤ ያደጉበትና ፡ የኖሩበት ፡ ሁኔታ ፡ የተለያዩ ፡ ስለነበረ ፡ ይልቁንም ፡ መጀመሪያ ፡ እንደተጋቡ ፡ በመሀከላቸው ፡ የነበረው ፡ ግጭትና ፡ ኩርፊያ ፡ ይበዛ ፡ ነበር ። ደግነቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ኩርፊያውን ፡ ተከትሎ ፡ የሚመጣው ፡ አዲስ ፡ ፍቅር ፡ ስለነበረ ፡ ግጭቱና ፡ ኩርፊያው ፡ የቂም ፡ መታሰቢያ ፡ ሳይተው ፡ ያልፍ ፡ ነበር ። በሚዋደዱ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ መሀከል ፡ የሚነሳ ፡ ግጭት ፡ አዲስ ፡ ፍቅር ፡ ፈጥሮ ፡ ባልና ፡ ምሽቱን ፡ የበለጠ ፡ እንደሚያዋድድ ፡ በማይዋደዱ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ መሀከል ፡ የሚነሳ ፡ ግጭት ፡ ግን ፡ በቂም ፡ ላይ ፡ ቂም ፡ ጨምሮ ፡ ወደመለያዩት ፡ እንደሚያደርስ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

## ምእራፍ ፡ ፫ ፡

## የስእለት ፡ ልጅ ፡

በዛብህ ፡ ከተወለደ ፡ ጀምሮ ፡ አምስት ፡ አመት ፡ እስኪ ሞላው ፡ ድረስ ፡ ሙሉ ፡ ጤና ፡ አልነበረውም ። በተወለደ ፡ በሶስት ፡ ወሩ ፡ መጨረሻ ፡ እንክሊስ ፡ የሚባለው ፡ የልጆች ፡ በሽታ ፡ አመመው ፤ በስድስተኛው ፡ ወሩ ፡ ቁዋቁዋት ፡ የሚ ባለው ፡ የልጆች ፡ የሳል ፡ በሽታ ፡ አመመው ፡ ባመቱ ፡ መጨ ረሻ ፡ ላይ ፡ ኩፍኝ ፡ መጣበትና ፡ ሞተ ፡ ከተባለ ፡ በሁዋላ ፡ ተረፈ ። አቅሙ ፡ ገና ፡ በሽታን ፡ ለመቃወም ፡ ሳይበቃ ፡ ከመ ወለዱ ፡ እነዚህ ፡ በሽታዎች ፡ ስለተፈራረቁበት ፡ በጣም ፡ ደካ ማና ፡ ጤናውን ፡ ለማበናከል ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ የሚበቃው ፡ አካሉም ፡ መንማና ፡ ሆኖ ፡ በዛብህም ፡ ተብሎ ፡ የተሰዬመበት ፡ በሽታ ፡ ስለበዛበት ፡ ነው ። በዛብህ ፡ በሽታ ፡ ያለመጠን ፡ ይጠነክርበት ፡ ነበር ። በታመመ ፡ ቁጥር ፡ ወላጆቹ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ከቆረጡ ፡ በሁዋላ ፡ ነበር ፡ የሚተርፍ ። መጀ መሪያ ፡ እንክሊስ ፡ ታሞ ፡ ሳለ ፡ ትኩሳቱ ፡ እንደሳት ፡ እየለ ገጠ ፡ ትንፋሹ ፡ ቦጭር ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ እያለ ፡ ጥቃቅን ፡ እግሮቹና ፡ እጆቹ ፡ እዬተወራጩ ፡ አይኖቹ ፡ ከናቱ ፡ ወዳባቱ ፡ ካባቱ ፡ ወደጣራው ፡ ወደጎታው ፡ ወደማጀቱ ፡ ሲንከራተቱ ፡ ከሞት ፡ መሸሻ ፡ መሸሸግያ ፡ የሚፈልጉ ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ። “ ምነው ፡ እናቴ ፡ ኪዳነምረት ፡ ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ የናት ፡ እንጀታቸው ፡ ከህጻኑ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ እዬተሰቀዬ ፡ ከህጻኑ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ከሞት ፡ እዬታገለ ፡ ከህጻኑ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ጣር ፡ እያንገላታው ። “ ለምን ፡ በጥተሺኝ ፡ ለምን ፡ ትወስጅዋለሽ ? ምን ፡ አጠፋሁ ፡ አሳይተሽ ፡ የምትነሺኝ ! ” ሲሉ ፡ እንባቸውን ፡ እያጎረፉ ። “እባክሽ ፡ ምረትሽን ፡ ላኪ ፡ እናቴ ፡ ወላላዋ ፤ ያዳንሺው ፡ እንደሆን ፡ እድሜውን ፡ ሙሉ ፡ ላንቺ ፡ አገልጋይ ፡ ይሆናል ፡ ቤተከስያንሺን ፡ አጥኖ ፡ ሳታት ሽን ፡ ቆሞ ፡ ያገለግልሻል ፤ ያንቺ ፡ ባርያ ፡ ያንቺ ፡ አገልጋይ ፡ እንዲሆን ፡ በተማሪ ፡ ቤት ፡ አሳድገዋለሁ ፤ ስእለት ፡ ይሁን

ብኝ ።" አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ግን ፡ ደስታቸውን ፡ የሰሩበት ፡ መስ
ረት ፡ ስለተናወጸባቸው ፡ ግር ፡ ብሎዋቸው ፡ ግራ ፡ ገብቶዋ
ቸው ፡ የጋቢያቸውን ፡ ጫፍ ፡ ዘለግ ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡
እንደጭራ ፡ እያወዛወዙ ፡ ዝንቦችን ፡ ከህጻኑ ፡ ፊት ፡ ከመከ
ልከል ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አይናገሩም ፡ ነበር ። እሙት ፡ ውድ
ነሽ ፡ እንባቸውን ፡ በደረታቸው ፡ እያዘነቡ ፡ ኪዳነ ፡ ምህረ
ትን ፡ ሲያማጥኑ ፡ አሳባቸውን ፡ እንደመጠቅለል ፡ አደረጉና ፡-
" እውነት ፡ ነው " ፡ አሉ ። " ስጦቶ ፡ መውሰድ ፡ አሳይቶ ፡
መንሳት ፡ ልክ ፡ አይደለም ፤ እውነትዋ ፡ ነው ፤ ብቻ ፡ ካለ
ችው ፡ ሁሉ ፡ የማልስማማበት ፡ የማልቀበለው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡
ነው ። ልጁን ፡ ደጋፊዬን ፡ ጉልበቴ ፡ ሲደክም ፡ አይኔ ፡ ሲጨ
ልም ፡ የሚጦረኝን ፡ የሚረዳኝን ፡ በስእለት ፡ ለታቦት ፡ መስ
ጠት ፡ የማይሆን ፡ የማይታሰብ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይዳን ፡ ብቻ ፤
ቀድሞ ፡ ይዳን ። እስዋም ፡ ስለጨነቃት ፡ ነው ፡ " እያሉ ፡
በውስጣቸው ፡ ሲተቹ ፡ የበዛብህ ፡ እጅና ፡ እግሮቹ ፡ ከመወ
ራጩቱ ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ጸጥ ፡ እያሉ ፡ ትንፋሹ ፡ ዘለግ ፡
እያለ ፡ አይኖቹም ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ መባከኑን ፡ ትተው ፡ ስል
ምልም ፡ ከፍት ፡ ከድን ፡ ሲሉ ፡ አዩና ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡
ከግር ፡ እስከራሳቸው ፡ በቀዝቃዛ ፡ ላብ ፡ ተነከሩ ። አሁንም ፡
እንደገና ፡ እጅና ፡ እግሮቹ ፡ ትንሽ ፡ እንደመንቀሳቀስ ፡ አሉና ፡
ጸጥ ፡ አሉ ፤ አይኖቹም ፡ ከፍት ፡ ከድን ፡ ስልምልም ፡ አሉና ፡
ገርበብ ፡ ብለው ፡ ዝም ፡ አሉ ። " እያ ፡ ቦጋለ ፡ መጨረሻው ፡
ነው ? መደምደሚያው ፡ ነው ? መሞቱ ፡ ነው ? " አሉ ፡ እሙት ፡
ውድነሽ ፡ ፊታቸው ፡ ከመቅጽበት ፡ ልውጥውጥ ፡ ብሎ ።
አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ጆሮዋቸውን ፡ ወደበሽተኛው ፡ አፍንጫ ፡ ጠጋ ፡
አድርገው ፡ ትንሽ ፡ እንደቆዩ ፡ ዘርዘር ፡ ያሉ ፡ ጥርሶቻቸውን ፡
ብልጭ ፡ አድርገው ፡ ቀና ፡ አሉና ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ " እንቅ
ልፍ ፡ ነው ፡ ይተነፍሳል " ፡ አሉ ። የዚህን ፡ ጊዜ ፡ እሙት ፡
ውድነሽ ፡ ቆሞ ፡ የነበረ ፡ ልባቸው ፡ መስራት ፡ ጀመረ ፤
ቆሞ ፡ የነበረ ፡ ደማቸው ፡ መዘዋወር ፡ ጀመረ ፤ ተዘግቶ ፡ የነ
በረ ፡ ሳንባቸው ፡ ተከፈተና ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ትንፋሽ ፡ ተነ
ፈሱ ። አቶ ፡ ቦጋለ ፡ " ተመስገን ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ "

አሉና ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ ተነስተው ፡ ወደውጭ ፡ ወጡ ፤ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ግን ፡ እኒያን ፡ ገርበብ ፡ ያሉ ፡ አይኖች ፡ እየተመለ ከቱ ፡ እዚያው ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ይጠብቁ ፡ ጀመር ። በሽተ ኛውም ፡ ሁለት ፡ ሰአት ፡ ያክል ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ ከተኛ ፡ በሁዋላ ፡ ሲነቃ ፡ ባዶ ፡ አፉን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ዳርቻው ፡ ከፍቶ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የተደረገው ፡ ለቀልድ ፡ እንደ ተደረገ ፡ ሁሉ ፡ ይስቅ ፡ ጀመር ።

"ተመስገኝ ፡ እናቴ ፡ ወላላዋ ፡ ተመስገኝ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ ይሰጥሻል ? ምን ፡ ይመለስልሻል ? ከምስጋና ፡ በቀር ፡ ምን ፡ ይደረግልሻል ? እንዲያው ፡ ተመስገኝ ፡ ተመስገኝ ።" አሉ ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ወደጣራው ፡ አንስተው ።

እንዲሁም ፡ በዛብህ ፡ በየጊዜው ፡ ሲታመም ፡ ከበሽ ታው ፡ መበርታት ፡ የተነሳ ፡ ወላጆቹ ፡ ተስፋ ፡ እንደቆረጡ ፡ በተለዩ ፡ እናቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለማርያም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለጊዮርጊስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለዮሀንስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለሚካ ኤል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለገብርኤል ፡ እንደተሳሉ ፡ በታቦቶቹ ፡ አደራ ፡ አውጭነትም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ የተሰራበት ፡ ከር ፡ በመበርታቱ ፡ ሞትን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ለማደግ ፡ በቃ ። አቶ ፡ በጋሹ ፡ ምራንና ፡ ቀምበር ፡ እርፍና ፡ ሞፈር ፡ መሬትና ፡ ዘር ፡ የሚስማሙበትን ፡ ዘዴ ፡ አስተምረው ፡ ልጃቸውን ፡ በቦታ ቸው ፡ ለመተካት ፡ ነበር ፡ አሳባቸው ። እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ግን ፡ ልጃቸው ፡ ያደገ ፡ ለታቦቶቹ ፡ በመሳላቸው ፡ መሆኑን ፡ ስላመኑ ፡ በዩጊዜው ፡ በሰጡት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መሰረት ፡ አገ ልግሎቱን ፡ በሙሉ ፡ ለተሳሉላቸው ፡ ታቦቶች ፡ እንዲሰጥ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በዛብህ ፡ አምስት ፡ አመቱን ፡ ጨርሶ ፡ ስድ ስተኛውን ፡ ሲይዝ ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እንዲገባ ፡ አያ ፡ በጋሹ ፡ ግን ፡ ለጥጃ ፡ ወይም ፡ ለፍዬል ፡ እረኝነት ፡ እንዲቀጠር ፡ በማለት ፡ በመሀከላቸው ፡ ጥል ፡ ተነሳ ።

"እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ያንችን ፡ አሳብ ፡ የምቀበል ፡ ብሆን ፡" አሉ ፡ አቶ ፡ በጋሹ ፡ " አንች ፡ በትንሹ ፡ የሰባት ፡ ታቦት ፡ ቤተክርስቲያን ፡ አጥና ፡ ሳታት ፡ ቆሞ ፡ እንዲያገለግል ፡ ተስ

ለሻል ፤ ስለዚህ ፡ መቼም ፡ ለበዛብህ ፡ ሲሉ ፡ ታቦቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸውን ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አይሰሩምና ፡ በዛብህ ፡ በአስራ ፡ ዘጠኝ ፡ ሌሊት ፡ የገብርኤልን ፡ ሳታት ፡ ለመቆምና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማጠን ፡ ባከል ፡ ገብርኤል ፡ እንዲሁም ፡ በሀያ ፡ አንድ ፡ ዛባ ፡ ጽዮን ፡ በሀያ ፡ ሶስት ፡ ጣሚ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በሀያ ፡ አራት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲሁም ፡ የተሳልሻቸውን ፡ ታቦቶች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እዩፈለገ ፡ ሲዞር ፡ ሊኖር ፡ ነው ! ያለዚያ ፡ እንዱን ፡ ታቦት ፡ አገልግሎ ፡ የሌላው ፡ የጎደለበት ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ባንችና ፡ በኔ ፡ መሀከል ፡ የተነሳው ፡ ጥል ፡ በታቦቶች ፡ መሀከል ፡ ይነሳል ፡ ብዬ ፡ እፈራለሁ ። ”

“ የደንቆር ፡ ድንቁርና ፡ ብልህ ፡ ለመሆን ፡ ሲሞክር ፡ ይገለጻል ፡ ይላሉ ፡ ቄስ ፡ ታምሩ ። ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ እዩሳቁ ።

“ ድንቁርናዩን ፡ ሳትነግሪኝ ፡ አውቀዋለሁ ፤ ብቻ ፡ ለጠዩቅሁሽ ፡ መልስ ፡ ስጭኝ ። ”

“ ለሰባት ፡ ቀርቶ ፡ ለመቶ ፡ ታቦቶች ፡ ብሳል ፡ በዛብህ ፡ እዩዞረ ፡ መቶ ፡ ቤተክርስቲያናች ፡ ማጠንና ፡ ሳታት ፡ መቆም ፡ እያስፈልገውም ፤ ከዚሁ ፡ ከገሩ ፡ ሳይወጣ ፡ ሁሉንም ፡ ሊያገለግል ፡ ይችላል ። ”

“ ከማንኩሳ ፡ ሳይወጣ ፡ ? ”

“ ከማንኩሳ ፡ ሳይወጣ ። ”

“ እንዴት ፡ አድርጎ ? ”

“ የተሳልሁዋቸው ፡ ታቦቶች ፡ በሚውሉበት ፡ ቀን ፡ በዩስማቸው ፡ እዚሁ ፡ ማንኩሳ ፡ ሳታት ፡ ቢቆምና ፡ ቢያጥን ፡ በቂ ፡ ነው ። ”

“እህ ፤ እስቲ ፡ ቆይ ! ማንኩሳ ፡ ታቦቱ ፡ ሚካኤል ፡ አይደለም ? ”

“ አዎን ፡ ሚካኤል ፡ ነው ። ”

“ ታዲያ ፡ የሚካኤል ፡ ታቦት ፡ ሲታጠንና ፡ በሚካኤል ፡ ቤተክቢያን ፡ ሳታት ፡ ሲቆም ፡ ለሌሎች ፡ በየት ፡ በኩል ፡ አልፎ ፡ ይደርሳቸዋል ? ”

“ይደርሳቸዋል ፤ ይደርሳቸዋል ፤ ነው ፡ የምልህ ፤ አንተ ፡

አይገባህምና ፡ ዝም ፡ በል ፤ ሁልጊዜ ፡ የሚደረገው ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ? ” አሉ ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ እንደመቆጣት ፡ ብለው ።

“ እዴው ፡ እንግዲህ ፡ ማስረዳት ፡ ሲያቅትሽ ፡ ዋና ፡ መከላከያሽ ፡ መቆጣት ፡ ነው ፤ እስቲ ፡ ሳትቆጭ ፡ ረጋ ፡ ብለን ፡ እንነጋገርማ ! ”

“ ተወልደህ ፡ እስከታረጅ ፡ ሲደረግና ፡ ስታየው ፡ የኖ ረውን ፡ አሁን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አድርገህ ፡ ስታመጣው ፡ ምን ፡ ላድርግ ? ከሁሉም ፡ የሚያናድደኝከ ፡ ልብህ ፡ እያወቀ ፡ አንተ ፡ የፈለግኸው ፡ ስላልሆነ ፡ ብቻ ፡ መከራከርህ ፡ ነው ። ”

“ የምናገረውን ፡ የምናገር ፡ አምኜበት ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ለክርክር ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ የምናውቀው ፡ እግዚአ ብሄርና ፡ እኔ ፡ ነን ፤ አንቺ ፡ አይደለሽም ። ስለዚህ ፡ እሱን ፡ እንተውና ፡ ተወልጄ ፡ እስካረጅ ፡ ሳየው ፡ የኖርሁ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ”

“ እዚሁ ፡ በሚካኤል ፡ ቤተክሲያን ፡ ለማርያም ፡ ለጊ ዮርጊስ ፡ ለባለእግዚአብሄር ፡ ለሌሎችም ፡ እንዲሁ ፡ ሲቀ ደስ ፡ ሲታጠን ፡ ሳታት ፡ ሲቆም ፡ አይተህ ፡ አታውቅም ? ”

“ እሱስ ፡ አዎ ፤ ብቻ ፡ ..........ብቻ ፡ ልክ ፡ አይደ ለም ። ”

“ እሰይ ፡ የኔ ፡ ሊቅ ! በላ ፡ እንግዲህ ፡ ሊቆች ፡ ያወጡ ትን ፡ እግዜር ፡ ያወጣውን ፡ ደንብ ፡ አንተ ፡ ለውጠው ! ”

“ ማንም ፡ ያውጣው ፤ ብቻ ፡ በኔ ፡ አስተያየት ፡ በሚ ካኤል ፡ ቤተክሲያን ፡ ለጊዮርጊስ ፡ ሳታት ፡ መቆም ፡ ወይም ፡ መቀደስ ፡ በገብረ ፡ ማርያም ፡ ሰርግ ፡ ወልደ ፡ ማርያምን ፡ እንደማወደስ ፡ ነው ። ” አሉ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ትንሽ ፡ እንደ መሳቅ ፡ ብለው ።

“ እኮ ፡ አንተ ፡ ሊቁ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የኖረውን ፡ ደንብ ፡ ነገ ፡ ተነስተህ ፡ ለውጫለሁ ፡ ብለህ ፡ አዋጅ ፡ አስነግርና ፡ ሲለወጥ ፡ ሁሉም ፡ ይቀራል ፤ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ያልሁት ፡ ይሆናል ። ”

“ በሚካኤል ፡ ቤተክሲያን ፡ ለጊዮርጊስም ፡ ይሁን ፡ ለማርያም ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ቢቀደስና ፡ ሳታት ፡ ቢቆምምኮ ፡ አገልጋዮቹ ፡ አንቺ ፡ እንደምትይው ፡ ድንግላይ ፡ መሆን ፡ የለባቸውም ። ”

“ እየው ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አመጣህ ! ቅኔን ፡ ማስረዳት ፡ አቃተኝ ፡ ትላለህ ፤ ሳስረዳህ ፡ የያዝኸውን ፡ ትተህ ፡ ወደሌላ ፡ ትሄዳለህ ! ”

“ ምናባቴን ፡ ላድርግ ? ጨንቆኝኮ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ አቶ ፡ በጋሻ ፡ ያዘንና ፡ የጭንቅ ፡ ምልክት ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ ጉልቶ ፡ እዩታዩ ።

“ ለምን ፡ ይጨንቅሀል ? ” አሉ ፡ ምሽታቸው ።

“እግዚአብሄር ፡ አልሀ ፡ እይበለኝና ፡ ይህን ፡ ልጅ ፡ ብዙ ፡ አደጋ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ እንዳይገጥመው ፡ እፈራለሁ ። ”

“ እንዴት ፡ ያለ ፡ መከራ ? ለታቦት ፡ አገልጋይ ፡ ስለ ሆነ ፡ ነው ፡ መከራ ፡ የሚገጥመው ?”

“ አይደለም ! ለታቦት ፡ ስላገለገለ ፡ አይደለም ። ታቦት ፡ ድንግላይ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ የሚያገለግል ። ምሽት ፡ ያገባ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ያበጀም ፡ ቄስ ፡ ደብተራ ፡ ሆኖ ፡ ያገለግላል ። አንቺ ፡ ግን ፡ የምትዪው ፡ ድንግል ፡ ሆኖ ፡ ይቅር ፡ ነው ፤ እኔም ፡ በጣም ፡ የፈራሁት ፡ ይህን ፡ ነው ። እዩኝ ፡ ካደገ ፡ በሁዋላ ፡ እንደሌላው ፡ ሁሉ ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ አበጅቶ ፡ ልጅ ፡ ወልዶ ፡ መኖር ፡ የፈለገ ፡ እንደ ሆነና ፡ ድንግልናውን ፡ ያፈረሰ ፡ እንደሆነ ፡ ይቀሰፍብናል ። ታቦቶች ፡ ቢምሩት ፡ እንኳዋ ፡ ድንግልናውን ፡ ያፈረሰ ፡ እዩተባለ ፡ የሰው ፡ መሳቂያና ፡ መሳለቂያ ፡ ይሆናል ። ያገራችን ፡ ሰው ፡ መላስ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ታውቂያለሽ ። እንኳዋን ፡ ድንግልና ፡ ቅስና ፡ ያፈረሰ ፡ ባገራችን ፡ ከሌባ ፡ የበለጠ ፡ ብርቱ ፡ ነውረኛ ፡ ነው ። ቄስ ፡ ፍሬው ፡ ምሽታቸውን ፡ ስለ ፈቱ ፡ ብቻ ፡ ለምስክርነት ፡ አይበቁም ፤ ላስታራቂነት ፡ ሽምግልና ፡ አይመረጡም ፡ እዩተባሉ ፡ ውሻ ፡ ውሻ ፡ ስለተባሉ ፡ ነው ፡ አገራቸውን ፡ ለመልቀቅና ፡ በሰው ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ ወድቀው ፡ ለመቅረት ፡ የበቁ ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ እንዳ

ይደርስብን ፡ ነው ፡ የምፈራ፡፡"

" በድንግልና ፡ ታቦት ፡ እያገለገለ ፡ በሚኖረው ፡ ሁሉ፡ እንዲህ ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ እንዳልኸው ፡ ያሰ ፡ ችግር ፡ ይደር ስበታል ? ወይስ ፡ የኛ ፡ ልጅ ፡ ስለሆነ ፡ ብቻ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ፡ ነው ፡ የምትል ? አሁን ፡ በቄስ ፡ ፍሬው ፡ የደረሰ ውን ፡ ያነሳኸው ፡ ቄስ ፡ ፍሬው ፡ ድንግላይ ፡ አልነበሩም፡፡ "

" በቄስ ፡ ፍሬው ፡ የደረሰውን ፡ ማንሳቴ ፡ ድንግላይ ፡ ነበሩ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ፤ ሲያድግ ፡ ድንግላይነቱን ፡ ሰማፍ ረስ ፡ የፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ የሚደርስበትን ፡ አደጋ ፡ ሰማስረ ዳት ፡ ነው፡፡"

" ድንግላይነቱን ፡ ያፈረሰ ፡ እንደሆነ ፡ ብሎ ፡ ነገር ፡ አሰ ፡ አባካችሁ ? ለምን ፡ ያፈርሳል ? አያፈርስም ፡፡ " አሉ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ እንደገና ፡ ተቆጥተው፡፡

" ምሽት ፡ ማግባት ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ማበጀት ፡ ፈልጎ! ለምን ፡ እኔ ፡ ምሽት ፡ አገባሁ ? ለምን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ምሽት ፡ ያገባል ? ስለሚፈልግ ፡ አይደለም ? እሱም ፡ እንደሌላው ፡ ሁሉ ፡ ይፈልግ ፡ ይሆናል ፡፡ እግዚአብሄር ፡ እንደሌላው ፡ ሰው፡ ሁሉ ፡ አድርጎ ፡ አይደለም ፡ የፈጠረው ?"

" አይፈልግም፡ " አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ እንደተ ቆጡ ፡፡

" ግዴለሽም ፡ አትቆጪ ፡ ውዴ ፤ እኒህን ፡ ሁለት ፡ ደካ ሞች ፡ በሬዎቻችነን ፡ ሽጠን ፡ ለተሳልሽቸው ፡ ታቦቶች ፡ እን ስጥና ፡ ስእለቱ ፡ ይፈታ ፡፡ ባይሆን ፡ እኔ ፡ እንዳልሁት ፡ አረ ኛና ፡ አራሽ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ይግባና ፡ በሁ ዋላ ፡ ቢፈለግ ፡ ባለህግ ፡ ቄስ ፡ ያለዚያም ፡ ደብተራ ፡ ይሁን ፤ በሁዋላ ፡ ራሱ ፡ የመረጠውን ፡ ይሁን ፡" አሉ ፡ አቶ በጋሰ ፡፡

" ይህማ ፡ የውነቱ ፡ ታዬ ፡ ተረት ፡ ነው፡፡" አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ቁጣቸውን ፡ ትተው ፡ ትንሽ ፡ እንደመ ሳቅ ፡ አሉና፡፡ ባላቸውም ፡ የውነቱ ፡ ታዬን ፡ ታሪክ ፡ ስለሚ ያውቁ ፡ ምንም ፡ ቢያዝኑ ፡ ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ አሉ፡፡

እውነቱ ፡ ታዬ ፡ በሬው ፡ ጠፍቶበት ፡ ከሚካኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብቶ ፡ እንዲያስገኝለት ፡ ተስሎ ፡ ሲወጣ፡

በሬውን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቅጽር ፡ ውጭ ፡ ስር ፡ ሲግጥ ፡ ስላገኘው ፡ መሰሉ ፡ ቁረቁረውና ፡ እንደገና ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ተመልሶ ፡ ገብቶ ፡ “ ሚካኤል ፡ በሬዬን ፡ አግኝቸዋለሁና ፡ በከንቱ ፡ እንዳትደክም ፡ ” ብሎ ፡ ወደበሬው ፡ ቢመለስ ፡ ጅቦች ፡ ከበው ፡ ሲቀራመቱት ፡ አገኘ ። ከዚያ ፡ እያለቀሰ ፡ “ ሚካኤል ፡ ያሞሌ ፡ እጣንህን ፡ እንደሆነ ፡ እሰጥሃለሁ ፤ በሬየን ፡ ብቻ ፡ በሬየን ፡ ” ሲል ፡ ጊዜ ፡ ሚካኤልም ፡ ” እውነቱ ፡ ታዬ ፡ በከንቱ ፡ አትድከም ፤ እኔ ፡ እንዳንተ ፡ የሰጠሁትን ፡ መልሽ ፡ መውሰድ ፡ አላውቅም ፤ አሁን ፡ በሬህን ፡ ለጅቦች ፡ ሰጥቸዋለሁ ። ” አለ ፡ ይባላል ።

“ የውነቱ ፡ ታዬ ፡ ታሪክ ፡ መጨረሻው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ታውቃለህ ፡ እሱን ፡ እንድገም ፡ ነው ፡ የምትለኝ ?” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ።

“ አይደለም ፤ የስእለቱን ፡ ለውጥ ፡ እንስጥ ፡ ነው ፡ የምል ። ”

“ ልጁ ፡ የሞተ ፡ እንደሆንሳ ? ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ወደባላቸው ፡ ዘወር ፡ ብለው ። ባላቸው ፡ የተናገሩት ፡ ልባቸውን ፡ ስለመታውና ፡ ትንሽ ፡ አመንትተው ፡ ስለነበረ ፡ ይህ ፡ ማመንታት ፡ ታቦቶችን ፡ አስቆጥቶ ፡ በልጃቸው ፡ ላይ ፡ የማያውቁት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳይደርስ ፡ ፈርተው ፡ አይናቻቸው ፡ እንባ ፡ ሞልተው ፡ ነበር ። አቶ ፡ ቦጋለ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ አሉ ። በምሽታቸው ፡ አሳብ ፡ ተስማምተው ፡ ሳይሆን ፡ የራሳቸውን ፡ ስሜት ፡ ለምሽታቸው ፡ ማስረዳት ፡ ስላልቻሉ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፤ አዝነው ፡ ዝም ፡ አሉ ።

“ የለም ! ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ እሳቸውም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ትንሽ ፡ ሲያስቡ ፡ ቆይተው ።

“ የለም ፡ ለታቦቶች ፡ ቃል ፡ ገብተናል ፤ ለሱ ፡ የሚበጀውን ፡ እነሱ ፡ ያስቡለት ! በቀናው ፡ መንገድ ፡ እነሱ ፡ ይምሩት ። ”

“ ይሁና ፡ ይሁን ፡ ብቻ ፡ የወላድ ፡ መካኖች ፡ ሆነን ፡ እንዳንቀር ፡ እንጂ ፡ ይሁን ። የኔን ፡ ስሜት ፡ ላስረዳሽ ፡ ሞከ

ርሁ ፤ ብቻ ፡ ከኔ ፡ እንደበት ፡ መጎልደፍ ፡ ይሁን ፡ ካንቺ ፡ የመረዳት ፡ ጉድለት ፡ አልተግባባንም ። እንግዲህ ፡ አንቺ ፡ እንዳልሺው ፡ ይሁን ። እግዚአብሔርን ፡ የምለምነው ፡ የኔን ፡ ስሜት ፡ ከንቱ ፣ ያንቺን ፡ እምነት ፡ እውነት ፡ እንዲያደርገው ፡ ነው ። ” ብለው ፡ ወጡ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ።

# ምእራፍ ፬ ፡

## የሚታይ ፡ እንጂ ፡ የማይበላ ፡ ፍሬ ፡

እመት ፡ ውድነሽ ፡ ባላቸውን ፡ ድል ፡ ከነሱ ፡ በሁዋላ ፡ በዛብህ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ገባ ። ወዲያው ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ በገባ ፡ በሁለት ፡ አመቱ ፡ በተወለደ ፡ በስምንት ፡ አመቱ ፡ ዳዊት ፡ ደገሞ ፡ ባስራ ፡ ሶስት ፡ አመቱ ፡ ጾመድጉዋ ፡ አወቀና ፡ ክህነት ፡ ተቀበለ ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ በዲቁና ፡ እዩቀደሰ ፡ የፍታትና ፡ ያትርሱኝ ፡ ገንዘብ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሲገባ ፡ ድርሻውን ፡ እዩተካፈለ ፡ የወላጆቹን ፡ ቤት ፡ ባሞሌ ፡ ጨው ፡ ሞላው። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ያትርሱኝ ፡ ገንዘብ ፡. በርክት ፡ ሲል ፡ ባሞሌ ፡ ጨው ፡ ፈንታ ፡ አንድም ፡ ሁለትም ፡ እስከ ፡ ሶስት ፡ ብር ፡ ድረስ ፡ እዩያዘ ፡ ይገባ ፡ ነበር ። እናቱ ፡ በተሳሉባቸውና ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በሆኑት ፡ ታቦቶች ፡ ቀን ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ በነጻ ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ስለነበረ ፡ በንደዚያ ፡ ያለ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ከሚገባ ፡ ገንዘብ ፡ አይካፈልም ።

አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ልጃቸው ፡ እዩቀደሰ ፡ በሚያመጣው ፡ ገንዘብ ፡ እጠራቅመው ፡ መጀመሪያ ፡ ምሽታቸው ፡ እዩፈተሉ ፡ ከሚያሰሩላቸው ፡ የዘወትር ፡ ሱሪ ፡ ሌላ ፡ ለክት ፡ የሚሆን ፡ አቡጀዲድ ፡ ሱሪ ፡ ገዙ ። ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ጥሩ ፡ ጃኖ ፡ ሸማ ፡ ተሰራላቸው ። በሁዋላ ፡ በባህር ፡ አረብ ፡ የተከፈፈች ፡ ዝምዝምዋ ፡ ያማረ ፡ ማለፊያ ፡ በርኖስ ፡ ገዙ ። በርኖስዋ ፡ አስራምስት ፡ ብር ፡ ያወጣች ፡ በውነት ፡ የጭዋ ፡ ልብስ ፡ ነበረች ።

እመት ፡ ውድነሽ ፡ ልጃቸው ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እንዲገባ ፡ አጥብቀው ፡ የታገሉ ፡ እሳቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ከባላቸው ፡ አሳብ ፡ የሳቸው ፡ አሳብ ፡ የሚበልጥ ፡ መሆኑን ፡ ባላቸው ፡ የሚረዱት ፡ ድሮ ፡ እዩተመኙ ፡ ገንዘብ ፡ ስላልነበራቸው ፡ ሊያገኙት ፡ ያልቻሉትን ፡ ልጃቸው ፡ እዩቀደሰ ፡ በሚያገባው ፡ ገንዘብ ፡ ያገኙ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በማመን ፡ ለወር ፡ ጨውና ፡ ለቅመማቅመም ፡ ከሚያውሉት ፡ ሌላ ፡ በቀረው ፡

ለራሳቸው ፡ ድሪና ፡ መስቀሉ ፡ እንኩዋ ፡ ሳይገዙ ፡ ያቶ ፡ ቦጋለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልብስ ፡ እንዲገዛበት ፡ ወይም ፡ እንዲሰራበት ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

" እኔ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ልብስ ፡ ስገዛ ፡ አንቺ ፡ አንድ ፡ ነጠላ ፡ እንኩዋ ፡ የማትገዢ ፡ ለምነው ፡ ውዴ ? " ይላሉ ፡ ባልዮው ።

" ጥጥ ፡ ገዝቼ ፡ ፈትሎ ፡ ማሰራቱ ፡ ይሻላል ፡ ብዬ ፡ ለቀሚስም ፡ ለኩታም ፡ የፈተልሁት ፡ አገልግል ፡ እዩዋላ ፡ ተቀምጠዋል ፡ ወደሸማኔ ፡ መሄዱን ፡ ሰንፌ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፈትሉም ፡ ማሰሪያ ፡ ዋጋውም ፡ ተቀምጠዋል ፤ አታስብ ። " ይላሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ውሽታቸውን ።

አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ልጃቸው ፡ ቀድሶ ፡ ባመጣው ፡ ገንዘብ ፡ የገዙትን ፡ ልብስ ፡ ይልቁንም ፡ በርኖሰዋን ፡ በለበሱ ፡ ቁጥር ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እንዲገባ ፡ ምሽታቸው ፡ ሲፈልጉ ፡ እረኛ ፡ ካል ሆን ፡ ብለው ፡ የምሽታቸውን ፡ አሳብ ፡ መቃወማቸው ፡ ትዝ ፡ ይላቸውና ፡–

" ተሳስቼ ፡ ኖሮዋል ፡ ልበል ? "ይላሉ ። " ተማሪ ፡ ከሚሆን ፡ እረኛ ፡ እንዲሆን ፡ መምረጤ ፡ ያለጥርጥር ፡ ተሳስቼ ፡ ኖሮዋል ። እስቲ ፡ የቱ ፡ እረኛ ፡ ነው ፡ አባት ፡ እናቱን ፡ እንዲህ ፡ ቀጥ ፡ አድርጎ ፡ የያዘ ? ለወር ፡ ጨው ፡ ሆን ፡ ለቅመም ፡ አናስብ ፡ እንዲያውም ፡ ከዚያ ፡ አልፎ ፡ ልብሳችንን ፡ የቻለ ፡ እሱ ፡ ነው ! እስቲ ፡ የጥጃ ፡ እረኛ ፡ ሆኖ ፡ ቢሆን ፡ በዬሳምንቱ ፡ የሚያገኘው ፡ ወተት ፡ ተጠራቅሞ ፡ ግፋ ፡ ቢል ፡ ከወር ፡ ጨውና ፡ ከቅመም ፡ ያልፍ ፡ ኖሮዋል ? የፍዬል ፡ ወይም ፡ የላም ፡ እረኛ ፡ ቢሆንም ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ በወር ፡ ያው ፡ አንድ ፡ አሞሌ ፡ ጨው ፡ ቢያገኝ ፡ ነው ። ርግጥ ፡ በዚህስ ፡ ተሳስቼ ፡ ኖርዋል ። ብቻ ፡ እንደሌሎች ፡ ተማሮች ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ዲያቆኖች ፡ በሁዋላ ፡ እንደሌሎች ፡ ቄሶች ፡ ወይም ፡ ደብተሮች ፡ ቢሆን ፡ እኔ ፡ እንዳሰብሁት ፡ እረኛና ፡ አራሽ ፡ ከመሆኑ ፡ ያለጥርጥር ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ አሁን ፡ ተረዳሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ልረዳው ፡ የማልችል ፡ ሌላውን ፡ ነው ! " ይላሉ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያደረገላቸው ፡ ልጃቸው ፡ ብድር ፡ መላሽ ፡ ባይ

ተካ ፡ ልጅ ፡ እንጂ ፡ አባት ፡ ሳይሆን ፡ አላፊ ፡ መሆኑን ፡ ሲያስቡ ፡ በደስታቸው ፡ መሀከል ፡ እዘን ፡ በልባቸው ፡ ይሰነቀርና ። ልጃቸው ፡ ለዚህ ፡ አለም ፡ ደስታ ፡ ተመልካች ፡ ለመከራው ፡ ብቻ ፡ ተካፋይ ፡ መሆኑ ፡ ሲታሰባቸው ፡ እንኩዋን ፡ በበርናስ ፡ ከግር ፡ እስከ ፡ ራሳቸው ፡ በወርቅ ፡ የሚያጅላቸው ፡ ቢሆን ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ሙሉ ፡ ደስታ ፡ እንደማይሰማቸው ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ደስታቸው ፡ ከቅርታ ፡ ጋር ፡ የተደባለቀ ፡ እንደሚሆን ፡ ርግጠኛ ፡ ነበሩ ።

“ እኔስ ፡ ጉልበቴ ፡ ሲደክም ፡ ይረዳኛል ፡ ብዬ ፡ የማስበው ፡ እሱ ፡ አለኝ ፤ እሱ ፡ እንደኔ ፡ ሲደክም ፡ ማነን ፡ ያስባል ? እየ....የወለዱት ፡ ሲወልድ ፡ የተከሉት ፡ ሲያፈራ ፡ በማየት ፡ የሚገኘውን ፡ ደስታ ፡ በምን ፡ ይለውጡታል ? ገበሬ ፡ ይዘራል ፤ የዘራውም ፡ ዘር ፡ አበቃቀሉን ፡ አሳምሮ ፡ ይወጣል ፤ ያድጋል ፤ ይለመልማል ፤ ያብባል ፤ ያምራል ፤ ዘሪውም ፡ ከቡቃያው ፡ እስካበባው ፡ ድረስ ፡ ደስታው ፡ ካዝመራው ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ያድጋል ። ከዚያ ፡ ፍሬውን ፡ ለማየት ፡ በናፍቆት ፡ ሲጠባበቅ ፡ በመሀከሉ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ የመርዶ ፡ ነቢይ ፡ ይመጣና ፡ የዘራኸው ፡ ዘር ፡ ፍሬ ፡ አያፈራም ፡ ባበባው ፡ ደርቆ ፡ ገለባ ፡ ትቢያ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ፤ ያንተም ፡ ደስታ ፡ ከቡቃያው ፡ እስካበባው ፡ በማየት ፡ ብቻ ፡ ይወሰናል ፡ ” ብሎ ፡ ቢያረዳው ፡ ያ ፡ ገበሬ ፡ ምን ፡ ያክል ፡ ይሰቀቅ ? ምን ፡ ያክል ፡ አንጀቱ ፡ ይቆረጥ ፡ ይሆን ? እኔም ፡ እንደሱ ፡ ነኝ ። ወለድሁ ፤ ደስ ፡ አለኝ ፤ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ ልጅ ፡ ወልዶ ፡ ስሜን ፡ ያስጠራል ፡ ብዬ ፡ ተስፋየን ፡ የመሰረትሁበትን ፡ ልጄን ፡ ይህች ፡ እናቱ ፡ ይህች ፡ የመርዶ ፡ ነቢይ ፡ ተስፋህ ፡ ደስታህ ፡ ፍጻሜ ፡ አያገኝም ፤ የወለድኸው ፡ ሳንተ ፡ አይሆንም ፡ ብላ ፡ ልጄን ፡ አንጀቴን ፡ ለብዙ ፡ ታቦት ፡ አከፋፈለችው ! ኧረ ፡ እንኩዋን ፡ እረኛ ፡ ሌላም ፡ በሆነና ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ በቀረብኝ ! ” ይሉና ፡ ባዘንና ፡ በብስጭት ፡ በርኖሳቸውን ፡ አውልቀው ፡ ይጥላሉ ።

አቶ ፡ በጋለ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አልፎ ፡ ሂያጅ ፡ ደስታ ፡ ሲነካቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መሪር ፡ እዘን ፡ ሲሰቃያቸው ፡ በዛብህ ፡ በአካልም ፡ በአእምሮም ፡ እዬጎለመሰ ፡ ሄደ ። ግብረ ፡

ዲቁና ፡ ጠንቅቆ ፡ በማወቅና ፡ በድምጽ ፡ ማማር ፡ በማንኩላኝ ፡ በሎሪያ ፡ ገባው ፡ በዛብህን ፡ የሚተካከል ፡ ዲያቆን ፡ አልነበረም ። ስለዚህ ፡ ባመት ፡ በአል ፡ ቀን ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ገባሬ ፡ ሰናይ ፡ እየሆነ ፡ የሚቀድስ ፡ በዛብህ ፡ ነበር ። በየሳምንቱ ፡ እሁድና ፡ ባመት ፡ ባሉ ፡ ቀን ፡ ጽድቅ ፡ ፍለጋ ፡ ሳይሆን ፡ በዛብህ ፡ ሲቀድስ ፡ ድምጹን ፡ ለመስማትና ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የገዛ ፡ ድምጹን ፡ ተከትሎ ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ወደላይ ፡ ሲያርግ ፡ ለማየት ፡ የሚሰበሰቡት ፡ ከወንድም ፡ ከሴትም ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ።

የነበረበት ፡ ሁኔታ ፡ በሚሰጠው ፡ ስሜትም ፡ ይሁን ፡ በሌላ ፡ በማይታወቅ ፡ ምክንያት ፡ በዛብህ ፡ ዜማ ፡ ሲያዜም ፡ ሙሉ ፡ አካሉ ፡ የዜማውን ፡ ስብር ፡ ተከትሎ ፡ ላይና ፡ ታች ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ሲሄድ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሲያዜም ፡ እንባው ፡ ሲወርድ ፡ አየን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እሁድ ፡ ከቁርባን ፡ በሁዋላ ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ ጽናና ፡ መስቀል ፡ ይዘው ፡ በፊቱ ፡ አንድ ፡ ሳእከ ፡ ዲያቆን ፡ በሁዋላው ፡ ሆነው ፡ በመሀከል ፡ አብደላካኔ ፡ ቀሚስና ፡ ከብ ፡ ወርቅ ፡ ካባ ፡ ለብሶ ፡ ጽዋውን ፡ ይዞ ፡ እሱ ፡ “ ነአኩቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅድሳቶ ፡ ነሲአነ ፡ ከመ ፡ ለህይወተ ፡ ነፍስ ፡ ይኩነነ ፡ ፈውስ ፡......... ” እያለ ፡ በዜማ ፡ መቅደሱን ፡ ኡደት ፡ ሲዞር ፡ እዚያ ፡ የቆሙት ፡ ሁሉ ፡ ልባቸው ፡ አብሮት ፡ ኡደት ፡ ይዞር ፡ ነበር ። እሱ ፡ ኡደቱን ፡ ዞሮ ፡ እመቅደስ ፡ ከገባ ፡ በሁዋላ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የምትባለው ፡ በቅርቡ ፡ ባልዋን ፡ ፈታ ፡ የተመለሰች ፡ ወጣት ፡ ወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ ወደምትባል ፡ ጉዋደኛዋ ፡ ጠጋ ፡ አለችና ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡

“ ታውቂያለሽ ? እኔን ፡ የሚገርመኝ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ድምጽ ፡ ሲወጣው ፡ አፉን ፡ እንደሌሎች ፡ አለመክፈቱ ፡ ነው ! ” አለች ።

“ ማን ? ” አለች ፡ በላይነሽ ፡ እንዳላወቀች ።

“ በዛብህ ፡ ነዋ ! እንግዲያ ፡ ሌሎችንማ ፡ ታያቸው ! ቄስ ፡ ውቤን ፡ ቄስ ፡ ፈለቀን ፡ ያን ፡ ተድላንም ፡ ልብ ፡ አድርገሽ ፡ ተመልከተሽልኝ ፡ እንደሆነ ፡ እረ ፡ ምን ፡ እነሱ ፡ ብቻ ! እንዲያው ፡ ሁሉንም ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ብትመለከች ፡ አፉቸውን ፡

እስከመጨረሻ ፡ ዳርቻው ፡ ይከፍቱና ፡ እንደሚያስቅሱ ፡ ሁሉ ፡ ፊታቸውን ፡ ጭምድድ ፡ አድርገው ፡ እዩቃስቱ ፡ የሚያወጡት ፡ ድምጽ ፡ እንደሱ ፡ አያምርም ። እሱ ፡ ግን ፡ ፊቱን ፡ ፈገግ ፡ አድርጎ ፡ አፉን ፡ እንደነገሱ ፡ ሳይከፍት ፡ የሚያወጣው ፡ ድምጽ ፡ ልብ ፡ ይነካል ! አይመስልሽም ? ”

“ እሱም ፡ እውነትሽ ፡ ነው ! ብቻ ፡ እኔን ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ታውቂያለሽ ? ”

ምንድር ፡ ነው ? ”

“ ትከሻው ፡ ነው ። ትከሻው ፡ ከድምጹ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ ሲል ፡ እንዲያው ፡ እንጃ ! እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ልንገርሽ ! ድምጹ ፡ ጠፈሩን ፡ ሰንጥቆ ፡ ሲሄድ ፡ ትከሻውም ፡ ድምጹን ፡ እንደሚከተል ፡ ሁሉ ፡ ወደላይ ፡ ከ......ፍ ፡ ይላል ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ሲለኝ ፡ ብታይ ! ወዬው ፡ ወንድሜ ፡ ወይም.... እንጃ !.. በሆነ ፡ እላለሁ ። ” አለች ፡ በላይነሽ ።

“አይኖቹስ ፡ ደስ ፡ አይሉሽም ? ” አለች ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እንደቆዩ ። “አይኖቹ ፡ በጣም ፡ አፋራሞች ፡ ናቸው ! አይንሽ ፡ ሲከተላቸው ፡ እዩሸሹ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ከርተት ፡ ከርተት ፡ ሲሉ ፡ ደስ ፡ ማለታቸው ! ቅድም ፡ እዚያ ፡ እመታጠፊያው ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ስርቅ ፡ አድርጎ ፡ ሊያየኝ ፡ ሲል ፡ አይን ፡ ላይን ፡ ግጥም ፡ ስንል ፡ ጊዜ ፡ እደነጋገጡን ፡ ብታይልኝ ! የሱን ፡ ድንጋጤ ፡ ሳይ ፡ እኔም ፡ ለጊዜው ፡ ልቤ ፡ እንደመሸበር ፡ አለ ! ይገርምሻል ! ”

“ የትኛው ፡ መታጠፊያ ? ” አለች ፡ በላይነሽ ።

“ እዚያ ፡ እመታጠፊያው ! ” አለች ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አገጭዋን ፡ ወደምስራቅ ፡ መታጠፊያ ፡ አሹላ ።

“ አ አ....እኔን ፡ አይቶ ፡ ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ነው ? ” አለች ፡ በላይነሽ ።

“ አንቺን ፡ አይቶ ፡ ፈገግ ፡ አለ ፡ [illegible]ዬ ? እሱን ፡ አላዩሁም ። ” አለች ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ።

“ ታዲያ ፡ አንቺን ፡ ስርቅ ፡ አ[illegible] አዩ ፡ እንዴ ? ” እሱን ፡ አላዩሁም ።

ከዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ወጣት ፡ ወይዛዝር ፡ ተኮራርፈው ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እንደቆዩ ፡ ደብሪቱ ፡ የምትባለዋ ፡ ጉዋደኛቸው ፡ ባጠገባቸው ፡ ቆማ ፡ ትሰማ ፡ ነበርና ፡ ቀረብ ፡ ብላ ፦

" እቶቼ ፡ በከንቱ ፡ አትጣሉ ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የስእለት ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ የሚታይ ፡ እንጂ ፡ የማይበላ ፡ ፍሬ ! " አለች ፡ እጅዋን ፡ አፍዋ ፡ ፊት ፡ ደቅና ፡ እዩሳቀች ።

" ዝም ፡ በይ ፡ አባክሽ ፡ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ እኛ ፡ የተናገርነው ፡ ሌላ ፡ ነው ፤ ስለሚበላና ፡ ስለማይበላ ፡ ፍሬ ፡ አይደለም ፡ " አለች ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ።

" የተናገራችሁትን ፡ እንደኔ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ይሰማችሁዋል ! ያላችሁበት ፡ ቦታም ፡ ቤተክሲያን ፡ መሆኑን ፡ አትርሱ ፤ ለናንተ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ግዴለኝም ። " አለች ፡ ደብሪቱ ፤ አሁንም ፡ እጅዋን ፡ አፍዋ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ደቀነች ፡ ራስዋን ፡ ወደ ፡ ጉዋደኞችዋ ፡ ዘንበል ፡ አድርጋ ።

በዛብህ ፡ በልጅነቱ ፡ ጉዋደኞቹ ፡ " የስእለት ፡ ልጅ ፡" እያሉ ፡ ሲቀልዱበት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እያለቀሰ ፡ ወደናቱ ፡ ይሄድና ፡ " ለምን ፡ እናት ፡ አባት ፡ እንደሌለኝ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ የስእለት ፡ ልጅ ፡ ይሉኛል ? " ብሎ ፡ ይጠይቃቸዋል ።

" ቢሉህ ፡ ምንቸገረህ ? የስእለት ፡ ልጅ ፡ መሆን ፡ ያኮራል ፡ እንጂ ፡ አያሳፍርምኮ ። " ይላሉ ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ።

" የስእለት ፡ ልጅ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ? "

" የታቦት ፡ ልጅ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የማርያም ፡ የሚካኤል ፡ የባለ ፡ እግዚአብሄር ፡ ልጅ ፡ ማለት ፡ ነው ። "

" ያንቺና ፡ ያባባ ፡ ልጅ ፡ አይደለሁም ? " አለ ፡ በዛብህ ፡ እንደማዘን ፡ ብሎ ፡ አይቶዋቸው ፡ የማያውቅ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ እንዳሉት ፡ መጀመሪያ ፡ እናቱ ፡ የነገሩት ፡ እለት ።

" ነህ ፡ እንጂ ፤ የኔና ፡ ያባትህ ፡ ልጅ ፡ ነህ ። እኛ ፡ ወለድንህ ፤ እነሱ ፡ አሳደጉህ ። ስትታመም ፡ ጊዜ ፡ እንዲያድኑህና ፡ እዩጠበቁ ፡ እንዲያሳድጉህ ፡ አደራ ፡ አልናቸው ፤ ተሳልናቸውና ፡ አዳኑህ ፡ አሁንም ፡ ይጠብቁሃል ። "

"ሌሎችን ፡ ልጆችሳ ፡ እነበቀለን ፡ እነታዩን ፡ ማን ፡ እዩጠበቀ ፡ ያሳድጋቸዋል ? "

" እንሱን ፡ ማንም ፡ አይጠብቃቸውም ። "

" ሲታመሙስ ፡ ማን ፡ ያድናቸዋል ? "

" ማንም ፡ አያድናቸውም ። " ሲሉት ፡ ከጉዋደኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ለሱ ፡ ብቻ፡የታበት ፡ ምግዚቶች ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፡ ደስ ፡ ብሎትና ፡ ኮርቶ ፡ ይመለስና ፡ ከናቱ ፡ በተቀበለው ፡ መሳሪያ ፡ ጉዋደኞቹን ፡ እፋኝቸውን ፡ ብሎ ፡ ያሸንፋቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የልጅነት ፡ ዘመኑ ፡ እያለፈ ፡ ወደጉልማሳነት ፡ በገባ ፡ መጠን ፡ የስእለት ፡ ልጅነቱ ፡ ከጉዋደኞቹ ፡ ቀልድና ፡ ስድብ ፡ የከበደ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ መሆኑ ፡ ይሰማው ፡ ጀመር ።

በዛብህ ፡ በልጅነቱ ፡ ጨዋታ ፡ ዘፈን ፡ ደስታ ፡ በጣም ፡ ወዳጅ ፡ ነበር ። ሰርግ ፡ ወይም ፡ የሚዘፈንበት ፡ እመትባል ፡ ሲኖር ፡ እሱ ፡ ከሌለበት ፡ የልጆች ፡ ጨዋታ ፡ አይደምቅም ። ስለዚህ ፡ ወደጨዋታው ፡ቦታ ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ ሁሉም ፡ ተሰብስበው ፡ እሱን ፡ ፍለጋ ፡ ወደቤቱ ፡ ይመጡና ፡ ይዘውት ፡ ይሄዳሉ ። ትንሽ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ሲሄድ ፡ የሚያደንቁትና ፡ በልዩ ፡ አስተያየት ፡ የሚያዩትም ፡ ልጃገረዶች ፡ ይበዙ ፡ ጀመር ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ በዛብህ ፡ ድንገት ፡ የተለወጠ ። አስራ ፡ አራት ፡ እመት ፡ ያክል ፡ ሲሆነው ፡ በዩሰርጉና ፡ በያመትባሉ ፡ ትንንሽ ፡ ልጃገረዶች ፡ ስርቅ ፡ አድርገው ፡ አይተው ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ሲሉለት ፡ ባጠገቡ ፡ ሲያልፉ ፡ እንዳላዩ ፡ እግሩን ፡ ረገጥ ፡ ወይም ፡ ቆንጠጥ ፡ አድርገውት ፡ ሲያልፉ ፡ ከሩቅ ፡ ይዘውት ፡ የመጡትን ፡ ሎሚ ፡ ወይም ፡ አበባ ፡ እሱ ፡ ፊት ፡ ሲደርሱ ፡ ያመለጣቸው ፡ አስመስለው ፡ ሲጥሉና ፡ እኒህን ፡ የመሳሰሉ ፡ የምርጫ ፡ መግለጫዎች ፡ የሆኑ ፡ ምልክቶች ፡ ሲያሳዩት ፡ ያንጊዜ ፡ በዛብህ ፡ ድንገት ፡ ተለወጠ ። ዘፈን ፡ ጨዋታ ፡ ደስታ ፡ ይወድ ፡ የነበረው ፡ በዛብህ ፡ ከዘፈን ፡ የራቀ ፡ ዝምተኛ ፡ አዘንተኛ ፡ ሆነ ። ጉዋደኝነታቸውን ፡ ለሱ ፡ ብቻ ፡ መስጠት ፡ የሚመርጡት ፡ ልጃገረዶች ፡ መብዛታቸውንና ፡ እሱ ፡ ለዚህ ፡ ክብር ፡ ያልታደለ ፡ የሴት ፡ ጉዋደኝነት ፡ የማይፈቅድለት ፡ ባይበድል ፡ የተፈረደበት ፡ ሳይጎድል ፡ ጎደሎ ፡ ነህ ፡ ተብሎ ፡ የተመሰከረበት ፡ መሆኑን ፡ ስላወቀ ፡- ካደገበት ፡ የጨዋታ ፡ የደስታ ፡ ማህበር ፡

ይሸሽ ፡ ጀመር ። የሚወደውን ፡ እንዳያደርግ ፡ ለሚወደው ፡ ጉዋደኛ ፡ እንዳይሆን ፡ ብቻውን ፡ እንዲኖር ፡ አስቀድሞ ፡ የተፈረደበት ፡ መሆኑን ፡ ስላወቀ ፦ ከሚወደው ፡ መሸሽ ፡ ዝም ተኛ ፡ አዘንተኛ ፡ መሆን ፡ ጀመረ ። ብቻ ፡ ይህ ፡ አይነት ፡ ኑሮ ፡ ይህ ፡ አይነት ፡ ህይወት ፡ መውጫው ፡ መዝለቂያው ፡ የማይታይ ፡ ከጉግማ ፡ የጨለመ ፡ ከመቃብር ፡ የከበደ ፡ ሆኖ ፡ ታዩውና ፡ ፈራው ፤ ጠላው ።

" ሰው ፡ እስከመቼ ፡ በዚህ ፡ አሆሁዋን ፡ ይኖራል ? እግዚአብሄር ፡ እንደሰው ፡ ከፈጠረኝ ፡ በሁዋላ ፡ እንደሰው ፡ እንዳልኖር ፡ የሚፈልግበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ? የለም ፡ እግዚአብሄር ፡ ይህን ፡ አልፈለገም ፤ እናቴ ፡ ናት ። " ይላል ፡ በዛብህ ፡ ብቻውን ፡ ቁጭ ፡ ይልና ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በዛብህ ፡ ጥንት ፡ የነበሩትን ፡ በዘመ ኑም ፡ የሚኖሩትን ፡ ምሽት ፡ ሳያገቡ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ሳይ ፈልጉ ፡ ህይወታቸውን ፡ በሙሉ ፡ ለእግዚአብሄር ፡ አገልግ ሎት ፡ የሰጡ ፡ ደናግል ፡ ሲያስብ ፡ የተናገረውም ፡ ያሰበውም ፡ ታላቅ ፡ ድፍረትና ፡ ክህደት ፡ ይመስለውና ፡ ፍራት ፡ ይይዘ ዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ፍራት ፡ የጉልማስነት ፡ ደሙ ፡ ሲፈላ ፡ ወዲያውኑ ፡ በኖ ፡ ይጠፋል ።

" አሁን ፡ እኔ ፡ እንድኖረው ፡ የተመደበልኝን ፡ ህይወት ፡ የኖሩ ፡ የሚኖሩም ፡ ብዙዎች ፡ እንደሆኑ ፡ አውቃለሁ ። ቢሆ ንም ፡ መርጠውት ፡ ወደውት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የመ ረጠላቸው ፡ አይመስለኝም ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ የመረጠላቸው ፡ ቢኖሩም ፡ ይህ ፡ ልክ ፡ አይደለም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እኔ ፡ እን ዲህ ፡ ያለውን ፡ ህይወት ፡ አልወደውም ፤ አልመርጠውም ፤ አልፈልገውም ፤ እግዚአብሄር ፡ ይቅር ፡ ይበለኝ ፡ እንጂ ፡ ህይ ወት ፡ አይደለም ። " ይላል ።

ይህም ፡ ሆኖ ፡ በዛብህ ፡ ስራ ፡ አልፈታም ። ህይወትን ፡ በመውደድና ፡ በፍራት ፡ መሀከል ፡ በሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ እን ዲህ ፡ እዩተሰቀዩ ፡ ሀያ ፡ አመቱን ፡ ጨርሶ ፡ ሀያ ፡ አንደኛ ውን ፡ ሲይዝ ፡ የዜማ ፡ መምህርነት ፡ ተመርቆ ፡ ወጣ ።

## ምእራፍ ፡ ፭ ፡
## የወላድ ፡ መከኖች ፡

አንድ ፡ ቀን ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ከዋሉበት ፡ ሲመለሱ ፡ ባለ ቤታቸው ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ እቤቱ ፡ በራፍ ፡ እጠገብ ፡ በተ ጋደመው ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ እንባቸው ፡ መንታ ፡ መንታ ፡ ሆኖ ፡ እየወረደ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ደረሱና ፡

" ምነው ፡ ውዴ ? ምን ፡ ሰማሽ ? " አሉ ፡ ጉልበታቸው ፡ እየተንቀጠቀጠ ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እንባ ቸውን ፡ ከማፍሰስ ፡ በቀር ፡ መልስ ፡ አልሰጡዋቸውም ።

" እባክሽ ፡ ንገሪኝ ፡ ውዴ ! ሞተ ፡ አሉሺ ? አረዱሺ ? "

" የለም ፤ ምንም ፡ አልሰማሁ ። እንዲያው ፡ ነው ። እን ዲያው ፡ በድሌ ፡ እንዲያው ፡ በጎደሉ ፡ ሌሊት ፡ በፈጠረኝ ፡ በእግዚአብሄር ፡ ነው ፡ የማለቅስ ። "

"እሁሁ. . . . . .እንኩዋን ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አልሆነ ! እንኩዋን ፡ ሞቱን ፡ አልሰማሽ ፡ እንጂ ፡ እሱስ ፡ ይሁን ! " አሉ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፤ እድሜ ፡ ያዛለው ፡ ገላቸውን ፡ የተሸከመ ፡ ጉልበታቸው ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ እምሽታቸው ፡ እጠገብ ፡ በግንዱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጡ ።

" ስማሽ ፡ ውዴ !" አሉ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፡ የሽማግሌ ፡ ጠጉ ባቸውን ፡ እግንዱ ፡ ላይ ፡ ለማሳረፍ ፡ ሲታገሉ ፡ የደከማቸው ፡ ድካም ፡ ትንሽ ፡ እንደማለፍ ፡ ካለላቸው ፡ በሁዋላ ። " ስማሽ ፡ ውዴ ! ምንም ፡ ታሌን ፡ ባትቀበይ ፡ ምንም ፡ እኔ ፡ የምናገ ረው ፡ ሁሉ ፡ ባይጥምሽ ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ የነገርሁሽን ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሬ ፡ ስለፈልፈው ፡ የኖርሁትን ፡ አሁንም ፡ መልሼ ፡ እነግርሻለሁ ። ይህ ፡ እግዚአብሄርን ፡ ማማረር ፡ ይህ ፡ እግዚ አብሄርን ፡ መውቀስ ፡ የባሰ ፡ ነገር ፡ ያመጣብሻል ፡ ተዪ ፡ ነው ፡ የምልሽ ። እኔ ፡ ውርድ ፡ ከራሴ ፡ ነው ፤ ተዪ ፡ ብዬሻ ለሁ ! "

" ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ምን ፡ ይመጣብኛል ? ወልጀ ፡ እሳድጌ ፡

በመጠርያየ ፡ ጊዜ ፡ ልጄን ፡ እስኪበላለው ፤ እኔ ፡ አገር ፡ ጥዬ ፡ ስሄድ ፡ ለደካማ ፡ እናቴ ፡ ማን ፡ እሳት ፡ እንዳይል ፡ ልቡን ፡ አደንድኖ ፡ እእምሮውን ፡ ሸፍኖ ፡ ልጄን ፡ እንዲኮበልል ፡ አደረገው ፤ ይህም ፡ አልበቃው ፡ ብሎ ፡ አይኔን ፡ አወረኝ ። ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ምን ፡ ያመጣብኛል ? ሞት ፡ ነው ፤ ባንድ ፡ ፈቱ ፡ ሞት ፡ አይሻልም ? ”

“ እየ ፡ ውዴ ! ሰውን ፡ ሞኝ ፡ ትያለሽ ፡ እንጂ ፡ ሞኝስ ፡ አንቺ ፡ ነሽ ! ለእግዚአብሄር ፡ ያሉት ፡ ክፉ ፡ ነገሮች ፡ ምንቺን ፡ ልጅ ፡ ማኮብለልና ፡ አይንሽን ፡ ማወር ፡ ብቻ ፡ ናቸው ? አይ ምሰልሽ ፤ ብዙ ፡ ክፉ ፡ ነገሮች ፡ ሞልተውታል ፤ ብዙ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አስሮ ፡ ጠፍሮ ፡ ሊያሸክምሽ ፡ ይችላል ! ይልቅ ተዪ ፡ ተጽናኚ ፡ ግዴለሽም ፡ ተጽናኚ ። “ደግሞም ፡” አሉ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፤ ትንሽ ፡ ትንፋሻቸውን ፡ እንደማስተጋባት ፡ አድርገው ፡ ቆዩና ፡- “ ደግሞም ፡ እንደውነቱ ፡ ከሆነ.... ይህን ፡ ሁሉ ፡ በራስሽ ፡ ላይ ፡ ያመጣሽ ፡ አንቺ ፡ ነሽ ። ”

“ እንዴት ? ምን ፡ አድርጌ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በራሴ ፡ ላይ ፡ ያመጣሁ ? ልጄ ፡ እንዳይረዳኝ ፡ እንዳይጦረኝ ፡ እግሬ ፡ እመቃብር ፡ አፍ ፡ በቆመበት ፡ ጊዜ ፡ እንዳይቀብረኝ ፡ አፈር ፡ እንዳይመልስብኝ ፡ አገር ፡ አስለቅቄ ፡ የሰደድሁት ፡ እኔ ፡ ነኝ ! ለምን ፡ ብዬ ፡ ይሆን ? ምን ፡ ትርፍ ፡ አገኝበት ፡ ብዬ ? ” አሉ ፡ ትንሽ ፡ ቆጣ ፡ ብለው ።

“እዎን ፡ አንቺ ፡ ነሽ ፤ ቆይማ ፡ አትቆጪ ፡ ውዴ ። ልጅሽን ፡ አገር ፡ ያስለቀቅሽ ፡ አንቺ ፡ አይንሽን ፡ ያሳወርሽ ፡ አንቺ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሆን ፡ ያደረግሽ ፡ አንቺ ፡ ነሽ ፤ በከንቱ ፡ እግዚአብሄርን ፡ አትውቀሺ ። ”

“ እኮ ፡ ለምን ፡ ብዬ ? እንዴት ፡ አድርጌ ? አትናገርም ? ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ከፊቱ ፡ የበለጠ ፡ ተቆጥተው ።

“ እኮ ፡ አትቆጪ ! እባክሽ ፡ አትቆጪ ። ያው ፡ ሁል ጊዜ ፡ የምነግርሽ ፡ ነው ፤ አዲስ ፡ ነገር ፡ አላመጣም ። እይው ፡ ልጅሽ ፡ ገና ፡ ከመወለዱ ፡ ቢታመም ፡ መታመም ፡ በሉ ፡ የተጀመረ ፡ ይመስል ፡ በስእለት ፡ ለታቦት ፡ ሰጠሽው ፤ ምሽት ፡ ላያገባ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ላያበጅ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡

ገባሽ ። ከደገ ፡ በሁዋላ ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ እንደ ፡ ጉዋደኞቹ ፡ ለመኖር ፡ መፈለጉን ፡ አይቼ ፡ ከብቶቻችንን ፡ ሸጠን ፡ ለተሳልሻቸው ፡ ታቦቶች ፡ እንስጥና ፡ ቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ይፈታ ፤ እሱም ፡ እንደፈለገው ፡ ምሽቱን ፡ አግብቶ ፡ ይቀመጥ ፡ ብልሽ ፡ አይቃማም ፡ አልሽኝ ። ስለዚህ ፡ ታስሮ ፡ መኖር ፡ ስላልፈለገ ፡ በማይታወቅበት ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ በፈለገው ፡ አሆሁዋን ፡ ለመኖር ፡ ያውና ፡ ጠጥሎን ፡ ሄደ ። ” አሉ ፡ በተሰበረ ፡ ድምጽ ፡ እሳቸውም ፡ ልቅሶ ፡ መጣባቸውና ፡ ለማገድ ፡ እዬታገሉ ፡ “ ሳይቀብረን ፡ ጠጥሎን ፡ ሄደ ። ከሄደ ፡ ወዲያ ፡ ወዬ ፡ ወዬ ፡ ስትይ ፡ ምንልሽ ፡ ነበር ? እንቺ ፡ ብትረሺው ፡ እኔ ፡ አልረሳውም ። ተዬ ፡ አታልቅሺ ፤ ልቡን ፡ ወደኛ ፡ እንዲመልሰው ፡ እግዚአብሄርን ፡ መለመን ፡ ነውንጂ ፡ እሱን ፡ መውቀስ ፡ አይገባም ፡ እልሽ ፡ አልነበረም ? ነገር ፡ ግን ፡ አልሰማሽኝም ። በመጨረሻ ፡ ይሄው ፡ አይንሽን ፡ አጥፍተሽ ፡ ቁጭ ፡ አልሽ ! አሁንም ፡ እባክሽ ፡ ተጽናኚ ፤ እግዚአብሄርን ፡ በመውቀስ ፡ ፈንታ ፡ ባይሆን ፡ ይብስ ፡ እታምጣ ፡ እያልሽ ፡ ለምኚው ፤ ይብስ ፡ እንዳያመጣ ። ”

«በል ፡ ዝም ፡ በል ፡ በማሁህ ፡ አንተ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የኔን ፡ ጥፋት ፡ በመብራት ፡ እዬፈለግህ ፡ ስትሰበስብ ፡ ነው ፡ የምትኖር ! እኔ ፡ እንዳንተ ፡ የሰው ፡ ጥፋት ፡ ስቆጥር ፡ አልኖርም ።ለታቦት ፡ ብሳል ፤ ቃል ፡ ኪዳኑ ፡ እንዳይፈታ ፡ ብቃወም ፡ እንዳይሞትብኝ ፡ እድሜ ፡ እንዲያገኝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ እሱም ፡ አንተም ፡ የማትጋሩት ፡ የተለዬ ፡ ጥቅም ፡ በመፈለግ ፡ አልነበረም ። ይሀን ፡ አንተም ፡ እሱም ፡ እግዚአብሄርም ፡ ታውቃላችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ጥፋተኛዋ ፡ ተቀጭዋ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ሆኜ ፡ ተገኘሁ ። » አሉና ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ልቅሶዋቸውን ፡ ቀጠሉ ። እቶ ፡ ቦጋለም ፡ ምሽታቸውን ፡ ለማጽናናት ፡ የሞከሩት ፡ እንዳልተሳካላቸው ፡ ሲያዩ ፡ ምርኩዛቸውን ፡ ይዘው ፡ እንደምንም ፡ ተጣጥረው ፡ ተነሱና ፡ ከቤታቸው ፡ ጀርባ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሚቀመጡበት ፡ ጉብታ ፡ ሄደው ፡ ተቀምጠው ፡ በስተርጅና ፡ የመጣባቸውን ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ያነሱ ፡ ይጥሉ ፡ ጀመር።

እቶ ፡ ቦጋለ ፡ ውለው ፡ ሲገቡ ፡ ምሽታቸው ፡ አሰናድተው ፡

የሚቆዩዋቸው ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ማግረርና ፡ እንባ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ከዋሉበት ፡ ፊታቸውን ፡ ወደቤታቸው ፡ ሲያዞሩ ፡ የሙት ፡ ውድነሽ ፡ ሁኔታ ፡ ይታያቸውና ፡ ተገናኝተው ፡ እስኪ ነጋገሩ ፡ ድረስ ፡ እንደጥፋተኛ ፡ ልጅ ፡ እዬፈሩና ፡ እያመነቱ ፡ ነበር ፡ የሚገቡ ። የሚወዱዋቸውን ፡ ምሽታቸውን ፡ ሁልጊዜ ፡ ከንባ ፡ ጋር ፡ ማየቱ ፡ በጣም ፡ እያሰቀቃቸው ፡ ቤታቸውን ፡ ይጠሉት ፡ ጀመር ፡ በዚህ ፡ አሆሁዋንም ፡ የሚጉዋዙበት ፡ የህይወት ፡ ጎዳና ፡ ምንም ፡ መጨረሻው ፡ ቅርብ ፡ ቢሆን ፡ ረዝሞ ፡ ታያቸው ።

"እንዲህ ፡ ያለች ፡ የሰው ፡ ምክር ፡ የማትቀበል ፡ አለማወቅዋን ፡ የማታውቅ ፡ በደካምነትዋ ፡ የምታሸንፍ ፡ ሴት ፡ አይቼ ፡ አላውቅም ! ሲመክሩዋት ፡ ትበሳጫለች ፤ ጥፋትዋን ፡ ሲነግሩዋት ፡ ተገንዝባ ፡ ለማረም ፡ በመሞከር ፡ ፈንታ ፡ ትቆጣለች ፤ ተስፋ ፡ ቆርጦ ፡ ዝም ፡ ሲሉዋት ፡ ይሄው ፡ ልቅሶዋ ፡ የማይቻል ፡ ሆነ ! ከቶ ፡ ምን ፡ ቢያደርጉዋት ፡ ይሻላል ? በዚህ ፡ ሁኔታዋ ፡ ከቆዩች ፡ መቸም ፡ ሰው ፡ አትሆንም ፤ ትሞታለች ! ምነው፡ ጌታዬ ፡ ልቡዋን ፡ ትንሽ ፡ ብታጠነክረው ? ከቶ ፡ አይደለች ! ደግ ፡ ናት ! ለምን ፡ እንዲህ ፡ ጨከንህባት ?" እያሉ ፡ እሳቸውም ፡ በመጠኑ ፡ እግዚአብሄርን ፡ ሲወቅሱና ፡ በምሽታቸው ፡ ሁኔታ ፡ ሲያዝኑ ፡ ቆይተው ፡ ድንገት ፡ ከንቅልፉ ፡ እንደነቃ ፡ ብንን ፡ ብለው ፡ ዙሪያ ፡ ገባውን ፡ ቢመለከቱ ፡ ጨልሞ ፡ አገኙት ። ከዚያ ፡ በዳበሳ ፡ ምርኩዛቸውን ፡ ፈላልገው ፡ አግኝተው ፡ እንሳለሁ ፡ ቢሉ ፡ ብርድ ፡ ሳይታወቃቸው ፡ ጎድቶዋቸው ፡ ኖሮ ፡ ውጋት ፡ ጥስቅ ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ አላንቀሳቅሳቸው ፡ አለ ። ሆኖም፡ በምርኩዛቸው ፡ ርዳታ ፡ እንደምንም ፡ ተጎትተው ፡ ተነስተው ፡ እቤታቸው ፡ ለመግባት ፡ ቻሉ ።

እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ባለቤታቸው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ገብተው ፡ እሳቱ ፡ ዳር ፡ ባለችው ፡ ትንሽ ፡ መደብ ፡ ሲጋደሙ ፡ እንዲጽናኑና ፡ ልቅሶዋቸውን ፡ እንዲተው ፡ ቢመክሩዋቸው ፡ አልሰማ ፡ ስላሉ ፡ ያኮረፉ ፡ መስሉዋቸው ፡ ነበር ። በሁዋላ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ተነስቶ ፡ እንደተለመደው ፡ ሙያተኛዋ ፡ እሰናድታ ፡ የተወችውን ፡ ራት ፡ አቅርቦ ፡ እንብላ ፡ ይለኛል ፡ ብለው ፡ ቢጠ

ባበቁ ፡ ዝም ፡ ስላሉዋቸው ፡ ስልችቶኝ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሆድ ፡ ባሳቸውና ፡ እንደገና ፡ ያለቅሱ ፡ ጀመር ። አቶ ፡ በጋለም ፡ በሽታዋን ፡ የነገርሁዋት ፡ እንደሆነ ፡ ኅዘንዋ ፡ ተጨማሪ ፡ ይሆንና ፡ የባሰውን ፡ ግራ ፡ ይገባታል ፡ ብለው ፡ ፈርተው ፡ ዝም ፡ አሉ ። በዚህ ፡ አሆሁዋን ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ባላቸው ፡ ድምጻቸውን ፡ አጥፍተው ፡ ከውጋት ፡ ጋር ፡ ሲታገሉ ፡ አደሩ ።

በነጋው ፡ አቶ ፡ በጋለ ፡ እንደልማዳቸው ፡ በጥዋት ፡ ስላልተነሱ ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ተጠራጠሩና ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ እጃቸውን ፡ ሰደው ፡ ባላቸውን ፡ ቢዳብሱ ፡ በላብ ፡ ተነክረው ፡ አገኙዋቸው ። ቢጠይቁዋቸውም ፡ የሚሰጡትን ፡ መልስ ፡ ውጋት ፡ እያቋዋረጠው ፡ በጣም ፡ ሊያስተውሉት ፡ ካለመቻላቸውም ፡ ሌላ ጠይቆ ፡ ለመረዳት ፡ የተረፋቸው ፡ ትንሽ ፡ ትእግስት ፡ አለቀ ። ከዚያ ፡ እዬወደቁ ፡ እዬተነሱ ፡ በሩን ፡ ፈልገው ፡ አገኙና ፡ ወጥተው ፡ ይጮሁ ፡ ጀመር ። ጩኸት ፡ የሰሙ ፡ ጎረቤቶች ፡ ደርሰው ፡ ምንድነው ፡ እያሉ ፡ ቢገቡ ፡ አቶ ፡ በጋለ ፡ ባፍ ፡ ባፍንጫቸው ፡ ደም ፡ እዬወረደ ፡ ሲጣጣሩ ፡ አገኙዋቸው ። እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ይህን ፡ ሲሰሙ ፡ ጭራሽ ፡ ራሳቸውን ፡ መግዛት ፡ አቃታቸው ።

“እግዚአብሄር ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ የዘመተበት ፤ እኔን ፡ ለመውጋት ፡ እኔን ፡ ለመዝረፍ ፡ ታጥቆ ፡ የተነሳበት ፡ ምክንያቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ? እባካችሁ ፡ ንገሩኝ ፡ እናንተ ፡ ሰዎች ፤ ንገሩኝ ። ልጄን ፡ አስኮብልሎ ፡ አይኔን ፡ አውሮ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ልጅም ፡ አባትም ፡ እናትም ፡ አይንም ፡ የሆነኝን ፡ ይህን ፡ አንዱን ፡ ሊቀማኝ ፡ የተነሳ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ? እንዲህ ፡ ያለ ፡ ግፍ ፡ አይታችሁ ፡ ሰምታችሁ ፡ ታውቃላችሁ ? እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ጭካኔ ፡ እነኩዋን ፡ እግዚአብሄር ፡ የገወቻ ፡ ሽፍታስ ፡ ይሰራዋል ? ምን ፡ ባደርግ ፡ ይታረቀኛል ? ምን ፡ ላድርግ ? ንገሩኝ ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ ትላላችሁ ?” እያሉ ፡ ድሮ ፡ አይናቸው ፡ በነበሩበት ፡ የንባ ፡ ጎርፍ ፡ እዬጎረፈ ፡ ወድቀው ፡ ሲንከባለሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ተነስተው ፡ ሲምቦራቹ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ጎረቤቶች ፡ ሁሉ ፡ የማይወዱዋቸው ፡ እንኩዋ ፡ ያለቅሱ ፡ ጀመር ። አቶ ፡ በጋለም ፡ የምሽታቸውን ፡ ሁኔታ ፡ ሲያዩ ፡ ከው

ጋት ፡ ጋር ፡ እዩ-ታገሉ ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር ።

በመጀመሪያዎቹ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ቀኖች ፡ ጎረቤቶች ፡ አልተለዩዋቸውም ፡ ለበሽተኛ ፡ የሚስማማ ፡ ምግብም ፡ እያ ማረጡ ፡ እዩሰሩ ፡ ያመጡላቸው ፡ ነበር ። በሁዋላ ፡ አቶ ፡ በጋሻ፡ የታመሙት ፡ ተስቦ ፡ በሽታ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ስለተወራ ፡ ጎረ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ሸሹ ። ሙያተኛቸው ፡ እንኩዋ ፡ መምጣቱን ተወች ። ስለዚህ ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ በሽተኛ ፡ ባላቸውን ፡ ታቅ ፈው ፡ ብቻቸውን ፡ ቀሩ ። ደግነቱ ፡ የበይ ፡ ውሀ ፡ በቤታቸው ፡ አጠገብ ፡ ያልፍ ፡ ስለነበረ ፡ እዩዳበሱ ፡ ከዚያ ፡ ውሀ ፡ እዩቀዱ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ራብ ፡ ሲሰማቸው ፡ አተርና ፡ ባቄላ ፡ ንፍሮ ፡ እዩቀቀሉ ፡ እዩበሉ ፡ የባላቸውን ፡ ትንፋሽ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።

አቶ ፡ በጋሻ ፡ እንደበታቸው ፡ ተይዞ ፡ ሳይናገሩ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቆዩ ። ምሽታቸው ፡ መኖራቸውን ፡ የሚያውቁት ፡ በሰ ውነታቸው ፡ ሙቀትና ፡ ትንፋሻቸውን ፡ በማዳመጥ ፡ ነበር ። በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ እግራቸው ፡ መቀዝቀዝና ፡ ትንፋሻቸው ፡ ማጠር ፡ ስለጀመረ ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ግራ ፡ ገብቶዋቸው ፡ የሚያደርጉትን ፡ አጥተው ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲደነጋገሩ ፡ ድን ገት ፡ ድምጽ ፡ ሰሙ ። ነገር ፡ ግን ፡ የሰሙት ፡ ድምጽ ፡ ከቤት ፡ ወይም ፡ ከውጭ ፡ መሆኑን ፡ ለይተው ፡ ማወቅ ፡ ስላልቻሉ ፡ በጆሮዋቸው ፡ እንደሚያዩ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የቀኝ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የግራ ፡ ጆሮዋቸውን ፡ ወደበሩ ፡ ሲደቅኑ ፡ "ውዴ" አለ ፡ ያው ፡ ደካማ ፡ ድምጽ ። ያ ፡ ድምጽ ፡ ጣእር ፡ የሚያንገላታው ፡ የባላቸው ፡ ድምጽ ፡ ነበር ።

"አንተ ፡ ነህ ፡ የተጣራህ ፡ የኔ ፡ ጌታ ? ስትናገር ፡ ሰማ ሁህ ፡ የኔ ፡ አባት ? ህልም ፡ ይሆን ፡ ወይስ ፡ እውነት ? እግዚአ ብሄር ፡ ታርቆኝ ፡ ይሆን ፡ ወይስ ፡ ሊቀልድብኝ ፡ ነው ? " እያሉ ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ከደስታቸው ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ባላ ቸው ፡ የተኙበትን ፡ መደብ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ባላቸውን ፡ ሲስሙ፡-

"ውዴ ፡ ጠላ ፡ አማረኝ ፤ወፍራም ፡ ጠላ ፡ አማረኝ!" አሉ ፡ አቶ ፡ በጋሻ ።

"ከጠላው ፡ በፊት ፡ ትንሽ ፡ እህል ፡ ቅመስ ፡ የኔ ፡ አባት ፤ ጠላው ፡ ልብህን ፡ እንዳይመታው ፡ ቀድመህ ፡ እህል ፡ ብትቀ

ምስ ፡ ይሻላል ።” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ከንፍሮ ፡ በቀር ፡ በቤታቸው ፡ ሌላ ፡ የበሰለ ፡ እህል ፡ ከዞረ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ መሆኑን፡ ረስተው ።

“የለም ፡ ጠላ ፡ ነው ፡ ያማረኝ ፡ ውሀ ፡ ያልገባበት ፡ የድፍድፍ ፡ ጠለላ ፡ ” አሉ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ።

ከዚያ ፡ እመት ውድነሽ ፡ አየሩን ፡ በጃቸው ፡ ምድሩን ፡ በግራቸው ፡ እዬዳበሱ ፡ ወጥተው ፡ እደጅ ፡ ቆመው ፡ በጎረቤት ፡ ጠላ ፡ እንዳስቀመጡ ፡ ሁሉ ፡ “ብሩቱ ፡ ሻሼ ፡ ደብሪቱ ፡ በላይነሽ ፡ ቶሎ ፡ ጠላ ፡ አምጡልኝ ፤ የሞት ፡ መድሀኒት ፡ የሚሆን ፡ ጠላ!” እያሉ ፡ ጎረቤቶቻቸውን ፡ አንድባንድ ፡ እዬጠሩ ፡ ብጮሁ ፡ ሁሉም ፡ ቤታቸውን ፡ ዘግተው ፡ ሸሽተው ፡ ስለነበረ ፡ ወይ ፡ የሚላቸው ፡ አጡ ። ከዚያ ፡ መንገዱን ፡ በግራቸው ፡ እዬዳበሱ፡-“እያ ፡ ቦጋለ ፡ በስምንት ፡ ቀኑ ፡ ዛሬ ፡ ተናግሮ ፡ ጠላ፡ አማረኝ ፡ ቢል ፡ የሚሰጠኝ ፡ አጣሁ ፤ እንዴት ፡ አንድ ፡ ዋንጫ፡ ጠላ ፡ አጥቶ ፡ ይሙት ? እንዴት ፡ ተወልዶ ፡ ባደገበት ፡ ያያት ፡ የቅድመአያቱ ፡ እትብት ፡ በተቀበረበት ፡ አንድ ፡ ዋንጫ ፡ ጠላ፡ ለምኖ ፡ ይጣ ? እንዴት ፡ በጋን ፡ ሸሚ ፡ ባጠጣሁበት ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ዋንጫ ፡ ጠላ ፡ ለምኜ ፡ ልጣ ?” እያሉ ፡ እንደብድ ፡ ብቻቸውን ፡ እዬጮሁ ፡ ግማሽ ፡ ምእራፍ ፡ ያክል ፡ ሄደው ፡ እያለቀሱ ፡ ባዶዋቸውን ፡ ተመለሱ ።

“አገር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አድሞ ፡ ጉሮሮየ ፡ እስኪነቃ ፡ ብጠራ ፡ ትንፋሼ ፡ እስኪያልቅ ፡ ብጮህ ፡ የሚሰማኝ ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡ የሚለኝ ፡ አጣሁ ፤ የሞት ፡ መድሀኒት ፡ የሚሆን ፡አንድ፡ ዋንጫ ፡ ጠላ ፡ ለምኜ ፡ አጣሁ ። ግዴለም ፡ እንኩዋን ፡ እግዚአብሄር ፡ ለዚህ ፡ አበቃህ ፡ እንጂ ፡ እንኩዋን ፡ እግዚአብሄር ፡ አፍህን ፡ ለመክፈት ፡ አበቃህ ፡ እንጂ ፡ የጠላ ፡ አምሮት ፡ አይገድልህም ! ” እያሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ እባላቸው ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ያን ፡ የማያልቅ ፡ የማይደርቅ ፡ እንባቸውን ፡ ያፈሱ ፡ ጀመር ። ከዚያ ፡ ጠጋ ፡ አሉና ፡ “ትሰማኛለህ ፡ የኔ ፡ አባት ? እንቅልፍ ፡ ወሰደህ ? ጠላ ፡ አላገኘሁም ፤ አምሮትህን ፡ ቁረጠው ፤ ወዲያውም ፡ ጦምህን ፡ ስንብተህ ፡ በባዶ ፡ ሆድህ ፡ ጠላ ፡ ብትጠጣ ፡ ይጎዳሃል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አያደርግልህ ፤

ይቅርብህ ።" አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ለለፈለፉት ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አላገኙም ። "ተኛህ ? " "እንቅልፍ ፡ ወሰደህ ? የኔ አባት ፡ እንጀቴ! " አሉ ፡ እጃቸውን ፡ ቀስ ፡ አድርገው ፡ ባላቸውን ፡ ለመዳበስ ፡ ሰደው ። ነገር ፡ ግን ፡ እመደቡ ፡ ላይ ፡ በባላቸው ፡ ፈንታ ፡ የነበረው ፡ የበረዶ ፡ ክምር ፡ ነበር ። እጃቸው ፡ እንደተመታ ፡ ቶሎ ፡ ሮጦ ፡ ተመለሰ ። እላቸው ፡ ግን ፡ ደርቀው ፡ በድን ፡ ሆነው ፡ ቀሩ ። ትንሽ ፡ [illegible] ፡ ብለው ፡ ቆይተው ፡ ነፍሳቸውን ፡ ትንሽ ፡ ማወቅ ፡ ሲጀምሩ ፡ እንደምንም ፡ ተደፋፍረው ፡ እንደገና ፡ እጃቸውን ፡ ሰደው ፡ ከላይ ፡ እስከታች ፡ ቢዳብሱ ፡ እመደቡ ፡ ላይ ፡ የተከመረው ፡ በረዶ ፡ እንደሰው ፡ እጅና ፡ እግር ፡ አፍንጫና ፡ ከንፈር ፡ አይንና ፡ ግንባር ፡ ራስም ፡ ጆሮም ፡ ያለው ፡ ነው ። ያ ፡ እመደቡ ፡ ላይ ፡ የተከመረ ፡ በረዶ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እሜት ፡ ውድነሽ ፡ ጠላ ፡ ፍለጋ ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ ሙቀትና ፡ ህይወት ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ነበር ። ያ ፡ የበረዶ ፡ ክምር ፡ ሙቀቱ ፡ ከራሱ ፡ አልፎ ፡ ለሜት ፡ ውድነሽ ፡ ይተርፍ ፡ ነበር ። አሁን ፡ እንኳዋን ፡ ሙቀት ፡ ሊሰጥ ፡ ሙቀት ፡ ሊቀበል ፡ የማይችል ፡ በረዶ ፡ ሆነ !

እሜት ፡ ውድነሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተቀምጠው ፡ ብዙ ፡ ቆዩ ። ለማልቀስምኮ ፡ የሰው ፡ ህዋሳት ፡ በመጠኑ ፡ እንዲሰሩ ፡ ልብ ፡ ደኅና ፡ ሆኖ ፡ እዘን ፡ እንዲሰማው ፡ ያስፈልጋል ! የሜት ፡ ውድነሽ ፡ ህዋሳት ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በደንብ ፡ መስራታቸውን ፡ ስለተዉ ፡ ማልቀስ ፡ እንኳዋ ፡ አልቻሉም ፡ ስለዚህ ፡ ዝም ፡ ብለው ቆዩ ።

በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ብዙ ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ፡ የባላቸው ፡ መሞት፡ የሳቸው ፡ ብቻቸውን ፡ መቅረት ፡ መጀመሪያ ፡ እንደትዝታ ፡ ቀጥሎ ፡ በሙሉ ፡ ሀይሉ ፡ በሙሉ ፡ ክብደቱ ፡ መጥቶ ፡ ተጫናቸውና ፡ እዬተነሱ ፡ እዬወደቁ ፡ ያለቅሱ ፡ ጀመር ። ከዚያ ፡ በሩም ፡ ምድራኩም ፡ እዬገጫቸው ፡ ወጥተው ፡ [illegible] ሯረ ፡ የሰው ፡ ያለህ ፡ የጎረቤት ፡ ያለህ ፡ ተዘረፍሁላችሁ ፡ [illegible] ሁላችሁ ፡" እያሉ ፡ በ[illegible] በ ወድቁ ፡ በ ነሱ ፡ እያ[illegible] ረስሁልሽ ፡ የሚል ፡ [illegible] ሚከተል ፡ ቀማኛ ፡ የሚያ[illegible] ፡ ዘመድ ፡ ጠፋ ። እ[illegible] ድነሽ ፡ እንዲሁ ፡ ከቀት[illegible] ረው ፡ ብቻ

ቸውን ፡ እዬወደቁ ፡ እዬተነሱ ፡ ሲጮሁ ፡ ውለው ፡ ሲደክማ
ቸው ፡ ገብተው ፡ ሬሳቸው ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጡ ።

እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ቀኑን ፡ እንዲህ ፡ እዬወጡም ፡ እዬገ
ቡም ፡ ሲያለቅሱ ፡ ውለው ፡ ሌሊት ፡ ልቅሶዋቸውን ፡ ተውና ፡
በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ በሰው ፡ ደርሶ ፡ የማያ
ውቅ ፡ መከራ ፡ እንደደረሰባቸው ፡ ሲያሰላስሉ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
ባላቸው ፡ ሳይታመሙ ፡ “እግዚአብሄር ፡ የመከራ ፡ ደሀ ፡ አይደም
ሰልሽ ፡ ብዙ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ እስሮ ፡
ጠፍሮ ፡ ሊያሸክምሽ ፡ ይችላልና ፡ ባታማርሪው ፡ ይሻላል ።”
ያሉዋቸው ፡ ትዝ ፡ ሲላቸው ፡ ጊዜ ፡ ፍራት ፡ ያዛቸው ። “ እው
ነትም ፡ እግዚአብሄር ፡ የመከራ ፡ ደሀ ፡ አይደለም ! ከዚህ ፡ የከ
በደም ፡ መከራ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ጠፍሮ ፡ ያሸከመኝ ፡ ይሆናል !
ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ መከራ ፡ ቀረው ? ያለውን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡
አንድ ፡ ላይ ፡ ጠፍሮ ፡ አሸክሞኛል ፡ ምን ፡ መከራ ፡ ቀረው ?
አንዱን ፡ ልጄን ፡ አስኮብልሎ ፡ አይኔን ፡ አውሮ ፡ ባሌን ፡ ገድሎ፡
ሰው ፡ እንዲፈራኝ ፡ እንዲሸሽኝ ፡ አድርጎ ፡ ቀባሪ ፡ አጥቼ ፡ በሀ
ይወቴ ፡ ከሙት ፡ ጋር ፡ እንድቀመጥ ፡ አድርጎኛል ፡ ከዚህ ፡
የከበደ ፡ መከራ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ! ቢኖርስ ፡ እንኳዋን ፡ እኔ ፡
ደካማዋ ፡ ብርቱ ፡ ይችለዋል ? ነገር ፡ ግን ፡ እሱቴ ፡ አላማረው !
መቸም ፡ መከራ ፡ ከሸክሙ ፡ ይልቅ ፡ ወሬው ፡ ይከብዳል !አሁን፡
የተሸከምሁት ፡ መከራ ፡ የሚደርስብኝ ፡ መሆኑን ፡ አስቀድሜ ፡
ብሰማ ፡ ኖሮ ፡ ከብዶት ፡ ይገድለኝ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ይሄው፡
ተሸክሜው ፡ ቁጭ ፡ ብያለሁ ! መከራ ፡ እየምጣ ፡ እንጂ ፡
ከመጣ ፡ ጉልበት ፡ ጨምሮ ፡ ይሰጣል ። እይ ፡ ቢገለ ፡ ምኝ ፡ ሲመ
ስል ፡ ለካ ፡ በጣም ፡ ብልህ ፡ በጣም ፡ አዋቂ ፡ ኖሮዋል ! እኔ ፡ አል
ሰማው ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ አውቆ፡
ነግሮኛል ። እይ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ የሚኖር ፡ ቢሆን ፡ የሚ
መከረኝን ፡ ሁሉ ፡ እንደእግዚአብሄር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ገብ
ርኤል ፡ ቃል ፡ አክብሬ ፡ ፈርቼ ፡ እቀበለው ፡ ነበር !” አሉና ፡-

“ጌታዬ ፡ አባቴ ፡ አንጀቴ ፡ ማረኝ ፡ በድዬሀለሁ ፡ ማረኝ ፡
ምከረኝ ፡ እንግዲህ ፡ እሰማሃለሁ ፡ ምከረኝ ፡ አስከትለኝ ፡ ሁለ
ተኛ ፡ አላስቀድምህም ፡ አስከትለኝ ”፡- እያሉ ፡ ሲያለቅሱ ፡

አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ አማረርሺኝ ፡ ብሎ ፡ በተሸከሙት ፡ መከራ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ መከራ ፡ ጨምሮ ፡ እንዳያሸክማቸው ፡ እየፈሩ ፡ ዝም ፡ ሲሉ ፡ ሌሊቱ ፡ ነጋ ፤ ተከታዩ ፡ ቀንም ፡ እንዲሁ ፡ አለፈ ። በሁለተኛው ፡ ሌሊት ፡ እዶሮ ፡ ጩኸት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንጉዋር ፡ ሆኖ ፡ ተጣራ ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ድምጹን ፡ ቢሰሙ ፡ ተነስተው ፡ በሩን ፡ ፍለጋ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲዳብሱ ፡ ምሰሶውም ፡ ወጋግራውም ፡ እየገጯቸው ፡ ወጥተው ፡- "ማነህ ?" አሉ ።

" እኔ ፡ ቄስ ፡ ምህረቱ ፡ ነኝ ፤ እንዴት ፡ አደሩ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ? "

" እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ አደሩ ፡ አባቴ ።" አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ። አባ ፡ ምህረቱ ፡ ያቶ ፡ በጋሻ ፡ የንስሀ ፡ አባት ፡ ነበሩ ።

" እሰው ፡ አገር ፡ ሰንብቼ ፡ ሳልጠይቃችሁ ፡ ሰነበትሁ ፤ በሽተኛው ፡ እንደምን ፡ ናቸው ?"

"በሽተኛው ? በሽተኛውማ ፡. . . . አረፈ ። " አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ወዳባ ፡ ምህረቱ ፡ ለመሄድ ፡ መንገዳቸውን ፡ እየፈለጉ ።

" አረፉ ? እየ ፡ ሰው ! እየ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ! እዚያው ፡ ይሁኑ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፤ የተከተለዎ ፡ አይታወቅምና ፡ አይ ምኩ ፡ መቼ ፡ አረፉ ?" አሉ ፡ አባ ፡ ምህረቱ ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ወደሳቸው ፡ ለመሄድ ፡ መሞከራቸውን ፡ ሲያዩ ፡ ወደሁዋላ ፡ እየሸሹ ።

"ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ እቀትር ፡ ላይ ፡ አረፈ ። "

" ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ እቀትር ፡ ላይ ! እየ ፡ ጉድ ! ታዲያ ፡ . . . ምን . . . . . ምን ፡ ተናዘዙ ? "

" አልተናዘዘም ። "

" እንዴት ፡ ሳይናዘዙ ፡ ሞቱ ? "

" ለሁሉስ ፡ ዘመድ ፡ ባጠገብ ፡ ቢገኝ ፡ አልነበር ? እኔ ፡ እንኩዋ ፡ ጠላ ፡ አማረኝ ፡ ሲል ፡ ጊዜ ፡ ላላገኝ ፡ ፍለጋ ፡ ሄጄ ፡ ብመለስ ፡ ሞቶ ፡ ቆየኝ ። "

" እየ ፡ የሴት ፡ ነገር ! የደከመ ፡ ሰው ፡ ትተው ፡ ጠላ ፡

ፍለጋ ፡ ይሄዳሉ ? ደግም ፡ አላደረጉ ። ”

“ ጠላ ፡ አማረኝ ፡ ሲል ፡ ጊዜ ፡ የተሻለው ፡ መሰለኝ ፡ እንጂ፡ መቼ ፡ የሚሞት ፡ መሰለኝ ? ”

“ ትልቅ ፡ ሴት ፡ ሆነው ፡ የደከመ ፡ በሽተኛ ፡ ጠላ ፡ አማረኝ ፡ ሲል ፡ ሞቱ ፡ የቀረበ ፡ መሆኑን ፡ አያውቁም ? ”

“ የታባቴ ፡ አውቄ ፡ እባክዎ ! አሁን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እንተወው ፤ አልፎዋል ፤ ይልቅ ፡ የመቃብሩ ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ የሚሆን ? ”

“ የመቃብሩ ፡ ነገርማ ..... አሁን ፡ መቸስ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንችላለን ? ሲነጋ ፡ ለሰዎች ፡ ነግሬ ፡ መቃብሩ ፡ ይቆፈርና ፡ ነገ ፡ ሌሊት ፡ ይቀበራሉ ። ”

“ ነገም ፡ እዚህ ፡ ውሎ ? ” አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ እያለቀሱ ።

“ በሌሊት ፡ ካልሆነ ፡ ማን ፡ ደፍሮ ፡ እበሽታ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ሬሳ ፡ ያወጣል ? እስዎ ፡ ብቻዎን ፡ ሬሳ ፡ ከፍነው ፡ ማውጣት ፡ አይችሉ ! ”

“ ብቻየንማ ፡ እንዴት ፡ እችላለሁ ? ”

“ ይህኮ ፡ ነው ፡ ችግሩ ! መቸስ ..... ምን ፡ ይደረግ ? አሁን ፡ ከብርዱ ፡ ይግቡ ፤ ሲነጋ ፡ መቃብሩ ፡ ተቆፍሮ ፡ ነገ ፡ ሌሊት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የ ..... የኔ ፡ አገልጋይ ፡ ገብሬ ፡ ከፈን ፡ ይዞ ፡ ይመጣልዎታል ፡ የከፈኑን ፡ ዋጋ ፡ በሁዋላ ፡ ይሰጡኛል ፡ ግዴለም ። ” ብለው ፡ አባ ፡ ምህረቱ ፡ ወደቤታቸው ፡ ተመለሱ ። እመት ፡ ውድነሽም ፡ እያለቀሱ ፡ ገቡ ።

ሲነጋ ፡ አባ ፡ ምህረቱ ፡ በዬሰዉ ፡ እዬላኩ ፡ ያቶ ፡ ቦጋለን ፡ አረፍት ፡ ነግረው ፡ መቃብሩን ፡ ካስቆፈሩ ፡ በሁዋላ ፤ አይናቸው ፡ እያዩ ፡ ገብሬን ፡ ወደ ፡ በሽታ ፡ ቤት ፡ መላኩ ፡ አስቸግሮዋቸው ፡ ከገዛ ፡ አሳባቸው ፡ ጋር ፡ ሲሙዋገቱ ፡ ቆዩና ፡-

“ ይሂድ ፡ ግዴለም ፤ እግዚአብሄር ፡ ለኔ ፡ ካለው ፡ ምንም ፡ አይሆን ፤ ያለዚያም ....... መቸስ ፡ የሰው ፡ መፈረጃ ፡ ከመሆን ፡ የማይሻል ፡ የለም ። ” ብለው ፡ እዶሮ ፡ ጩኸት ፡ ላይ ፡ ገብሬን ፡ ከፈን ፡ አስይዘው ፡ ወደእመት ፡ ውድነሽ ፡ ላኩት ።

ከዚያ ፡ እመት ፡ ውድነሽና ፡ ገብሬ ፡ ያን ፡ የሰነበተ ፡ ሬሳ ፡

በብዙ ፡ ችግር ፡ ከፍነው ፡ እሱ ፡ ከራስጌ ፡ እሳቸው ፡ ከግርጌ ፡ ተሸክመው ፡ ትንሽ ፡ እንደሄዱ ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ደከማቸውና ፡ እንረፍ ፡ አሉ ። እንዲህ ፡ እዬተቀመጡ ፡ እዬተነሱ ፡ ግማሽ ፡ ምእራፍ ፡ ያህል ፡ እንደተጉዋዙ ፡ ሬሳውን ፡ ተቀብሎ ፡ ለመቅበር ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ አጠገብ ፡ ደረሱ ። የተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ እሙት ፡ ውድነሽንና ፡ ገብሬን ፡ ሲያዩ ፡ ተጣርተው ፡ " ሬሳውን ፡ እሱ ፡ ላይ ፡ አስቀምጡና ፡ ተመለሱ!" አሉዋቸው ። በሽታ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከገደለ ፡ በሁዋላ ፡ ህያዋንን ፡ እንጂ ፡ ሙታንን ፡ አይከተልም ፡ ስለሚባል ፡ አቶ ፡ በጋለን ፡ የገደለ ፡ በሽታ ፡ እነሙት ፡ ውድነሽን ፡ ተከትሎ ፡ እንዲመለስ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እሙት ፡ ውድነሽና ፡ ገብሬ ፡ እንደታዘዙት ፡ ሬሳውን ፡ አስቀምጠው ፡ በሽታውን ፡ አስከትለው ፡ ወደ መጡበት ፡ ሲመለሱ ፡ ቀባሪዎቹ ፡ እንስተው ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ሳይነጋ ፡ ቀብረው ፡ ወደየቤታቸው ፡ ተበታተኑ ።

አቶ ፡ በጋለ ፡ የተቀበሩ ፡ እለት ፡ እሙት ፡ ውድነሽ ፡ ታመው ፡ አደሩ ። ባላቸው ፡ በታመሙ ፡ ጊዜ ፡ እሳቸው ፡ እንስተው ፡ አስተኝተው ፡ ደካማ ፡ አይኑ ፡ ስውር ፡ ሊያደርገው ፡ የሚችለውን ፡ ሁሉ ፡ አድርገው ፡ በራስጌ ፡ በግርጌ ፡ ሆነው ፡ አስታመው ፡ አልቅሰው ፡ ባይቀብሩ ፡ አስቀበሩዋቸው ። እሳቸው ፡ ሲታመሙ ፡ ግን ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ይቅርና ፡ በር ፡ እንኩዋ ፡ የሚከፍትና ፡ የሚዘጋላቸው ፡ ባጠገባቸው ፡ ማንም ፡ ሳይኖር ፡ በባዶ ፡ ቤት ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ታመው ፡ ሞቱ ። በሽታቸው ፡ ምን ፡ እንደነበረና ፡ እንዴት ፡ እንደሞቱ ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። አስከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በማንኩሳ ፡ ሲመረቅ ፡ "እንደበጋለ ፡ መብራቱና ፡ እንደውድነሽ ፡ በጣሙ ፡ የወላድ ፡ መካኖች ፡ ከመሆን ፡ ያድናችሁ ። " ይባል ፡ ነበር ።

# ምእራፍ ፡ ፯ ፡

## ነጻነት ፡

በዛብህ ፡ ወላጆቹን ፡ ከድቶ ፡ ማንኩሳን ፡ እንደለቀቀ ፡ ዋሸራ ፡ ወደምትባል ፡ አገር ፡ ሄደ ፤ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ገባ ። በዋሸራም ፡ አንድ ፡ አመት ፡ እንደቆየ ፡ ቅኔ ፤ ተቀኝቶ ፡ ዝማሬ ፡ መዋሲት ፡ ለማሄድ ፡ ወደዙር ፡ አምባ ፡ ሄደ ። ዙር ፡ አምባ ፡ ሁለት ፡ አመት ፡ ያክል ፡ ቆይቶ ፡ ዝማሬ ፡ መዋሲትና ፡ ጽህፈት ፡ ካወቀ ፡ በሁዋላ ፡ ደብረወርቅ ፡ እምትባል ፡ አገር ፡ አዲስ ፡ የመጽሀፍ ፡ መምህር ፡ ከጎንደር ፡ መምጣታቸውን ፡ ስለሰማ ፡ ወደዚያ ፡ ሄዶ ፡ መጽሀፍ ፡ ለመቀጸል ፡ ወሰነ ።

ደብረወርቅ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ለአስተርዮ ፡ ማርያም ፡ ዋዜማ ፡ ደርሶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲያገለግል ፡ አደረና ፡ ካህናቱ ፡ የድምጹን ፡ ማማር ፡ አይተው ፡ በበነጋው ፡ ጥዋት ፡ እጣነሞገር ፡ እንዲመራ ፡ ለምነውት ፡ ሲመራ ፡ የሰማው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በድምጹ ፡ ማማር ፡ ተገረመ ።

የአገልግሎቱ ፡ ስነስራት ፡ ተፈጽሞ ፡ ለበአሉ ፡ ከሩቅም ፡ ሆነ ፡ ከቅርብ ፡ የመጡት ፡ ካህናትና ፡ ተማሮች ፡ በየቤቱ ፡ በሚመሩበት ፡ ጊዜ ፡ እመት ፡ ጠጅቱ ፡ ወደበዛብህ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ።

“ ወንድሜ ፡ ደፈርሽኝ ፡ አትበለኝና ፡ ላመት ፡ በአሉ ፡ የመጣህ ፡ ነህ ፡ ወይስ ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ትማራለህ ? ” ብለው ፡ ጠየቁት ።

“ ለጊዜው ፡ እንግዳ ፡ ነኝ ፤ ለወደፊቱ ፡ ግን ፡ እዚሁ ፡ ለመማር ፡ እስቤያለሁ ፡ እመቤቴ ፡ ” አለ ፡ በዛብህ ።

“ በደብረወርቅ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የምታውቀው ፡ ሰው ፡ አለህ ? ”

“ በወሬ ፡ ካልሆነ ፡ ደብረወርቅን ፡ በጭራሽ ፡ አላውቀውም ። ”

“እሁንስ ፡ ወዴት ፡ አርፈሀል ? ”

“ ትናንት ፡ መጥቼ ፡ እዚሁ ፡ እቤተክርስቲያን ፡ ነው ፡ ያደርሁ ። ”

“ የምታውቀው ፡ ሰው ፡ ከሌለህ ፡ በእሉን ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ እንድታርፍ ፡ ትፈቅዳለህ ? ”

“ እመአምላክ ፡ አረፍተ ፡ ነፍስ ፡ ትስጥዎ ፡ የኔ ፡ እመ ቤት ፡ መስተንግዶዎን ፡ እቀበላለሁ ። ”

እሙት ፡ ጠጅቱ ፡ በዛብህንና ፡ ለበአሉ ፡ የተጠሩ ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ እቤት ፡ ሲደርሱ ፡ መብል ፡ መጠጡ ፡ ተሰናድቶ ፡ በየቦታው ፡ ቀርቦ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ነበር ። ከምሳ ፡ በሁዋላ ፡ እበዛብህ ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ አሉና ፡ -

“ ቅድም ፡ ሳታስበው ፡ መጥቼ ፡ እንደንስህ ፡ አባት ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ስመረምርህ ፡ ምን ፡ መሰለህ ፡ እባክህ ? ” አሉ ።

“ ደብረወርቅ ፡ እንዴት ፡ የተባረከ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አደነቅሁ ፡ ”

“ አደለም ፡ ደብረወርቅስ ፡ እንደሌላው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ነው ። ”

“ እንግዲያስ ፡ እርስዎ ፡ የተባረኩ ፡ ቢሆኑ ፡ ነው ፡ እግዚ አብሄር ፡ የወለዱትን ፡ ይባርክልዎ ፡ ”

“ የሰም ፡ እኔ ፡ ምክናያቱን ፡ ልንገርህ ። በመልኩም ፡ በድምጹም ፡ በሁለመናው ፡ ልክ ፡ አንተን ፡ የሚመስል ፡ ልጅ ፡ ነበረኝ ፡ ጥሎኝ ፡ ወደቅኔ ፡ ቤት ፡ ከሄደ ፡ አራት ፡ አመት ፡ ሆነ ፡ እስከዛሬ ፡ ወሬውን ፡ ሰምቸ ፡ አላውቅም ። ቅድም ፡ እካህናቱ ፡ መሀከል ፡ ቀለም ፡ ስትናገር ፡ ስሰማና ፡ ሳይህ ፡ ሰው ፡ እብድ ፡ ባይለኝ ፡ መጥቼ ፡ ባነጋግርህ ፡ እወድ ፡ ነበር ፡ ያፈሰስሁትም ፡ እንባ ፡ ላንድ ፡ የሞተ ፡ ዘመድ ፡ ይበቃ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ልጄን ፡ መስለኸኝ ፡ ነው ፡ ያን ፡ ያክል ፡ አቁሜ ፡ እንደወንጀለኛ ፡ ስመረምርህ ፡ የዋልሁና ፡ በሁዋላም ፡ ወደኔ ፡ ቤት ፡ እንድትመጣ ፡ የለመንሁህ ። አሁንም ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ እስከምትሄድበት ፡ ጊዜ ፡ የኔን ፡ ቤት ፡ እንደናትህ ፡ ቤት ፡ ቆጥረህ ፡ ምግብህን ፡ እዚሁ ፡ እንድትመገብ ፡ ፈቃድህ ፡ ቢሆንልኝ ፡ ደስታውን ፡ ባልቻልሁትም ። ” አሉ ፡ እሙት ፡ ጠጅቱ ።

በዛብህ ፡ አመስግኖ ፡ እሙት ፡ ጠጅቱን ፡ እንደናቱ ፡ ቤታቸውን ፡ እንደናቱ ፡ ቤት ፡ የሚያይ ፡ መሆኑን ፡ ቃል ፡ ሰጠ ።

ስለዚህ ፡ እመት ፡ ጠጅቱ ፡ ምግቡንና ፡ ልብሱን ፡ ችለው ፡ እን ደከፉ ፡ ቀን ፡ እህል ፡ እየተንገበገቡለት ፡ እሱም ፡ በደብር ፡ሬማ ቸው ፡ ባመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ የሚደርስባቸውን ፡ ቅኔ ፡ እየተቀ ኘላቸው ፡ ሁለት ፡ አመት ፡ መጽሀፉን ፡ እየቀጸለ ፡ ተቀመጠ ።

በሶስተኛው ፡ አመት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ምሳውን ፡ በልቶ ፡ ወደ ፡ ተማሪቤቱ ፡ ሲመለስ ፡ እጎጀው ፡ በራፍ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተቀምጦ ፡ አዩ ። እንግዳውም ፡ በዛብህን ፡ ገና ፡ በሩቅ ፡ ሲያይ ፡ ተነስቶ ፡ ወደሱ ፡ ሄደና፡- " እንዴት ፡ ነህ ፡ በዛብህ ፡ እረ ሳኸኝ ፡ ይሆን ? እኔኮ ፡ ደብተራ ፡ በዩን ፡ ነኝ ። " አለ ። በዛብ ህም ፡ " ስረሳ ፡ ብውል ፡ አንተን ፡ እረሳለሁ ? ደብተራ ፡ በዩን " አለና ፡ ተሳሳሙ ። ደብተራ ፡ በዩን ፡ በማንኩሳ ፡ እሉ ፡ ከሚባ ሉት ፡ ደብተሮች ፡ አንዱ ፡ ነበር ። በተለይ ፡ በቅኔ ፡ የሚተካከ ለው ፡ አልነበረም ። በዛብህ ፡ አገሩን ፡ ሳይለቅ ፡ ይመኛቸው ፡ ከነበሩ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ እንደ ፡ ደብተራ ፡ በዩን ፡ ቅኔ ፡ ማወቅ ፡ ነበር ።

" ደብረወርቅ ፡ ምን ፡ እግር ፡ ጣለህ ? ደብተራ ፡ በዩን " አለ ፡ በዛብህ ።

" ሞጣ ፡ አቀቁዋም ፡ ለመማር ፡ ሄጀ ፡ ነበር ፡ ስመለስ ፡ እግረመንገዴን ፡ ደብረወርቅን ፡ አይቼ ፡ ልለፍ ፡ ብዬ ፡ መጣሁ ፡"

" የያዝኸው ፡ ሙያ ፡ መቸ ፡ አነሰህ ፡ ነበር ፡ አቀቁዋም ፡ ልትማር ፡ የመጣህ ? "

" ዛሬ ፡ አቀቁዋም ፡ የማያውቅ ፡ ደብተራ ፡ እንደ ፡ ድምጽ ፡ ከፉ ፡ አዝማሪ ፡ ፈላጊ ፡ የለውም ፡ " አለ ፡ ደብተራ ፡ በየን ፡ እዬ ሳቀ ። ከዚህ ፡ በሁዋላ ፡ እዬተሳሳቁ ፡ ወደበዛብህ ፡ጎጆ ፡ ገብ ተው ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጫወቱ ፡ አመሹ ።

በጨዋታቸው ፡ መሀከል ፡ በዛብህ ፡ የዘመዶቹን ፡ ወሬ ፡ ለመጠዬቅ ፡ እየወደደ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በቀጥታ ፡ ለመጠዬቅ ፡ ፈርቶ ፡ ዳርዳር ፡ እያለ ፡ በዙሪያ ፡ መንገድ ፡ እንዲነግረው ፡ ቢሞ ከር ፡ ደብተራ ፡ በየን ፡ እንዳልገባው ፡ ሁሉ ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ እዬ ሰጠ ፡ አስቸገረው ። በዛብህ ፡ ስለማንኩሳ ፡ በመነጋገር ፡ ከጨ ዋታ ፡ ብዛት ፡ የዘመዶቹ ፡ ነገር ፡ ይነሳል ፡ በማለት ፡ የማንኩ

ሳን ፡ ነገር ፡ ሲያነሳ ፡ ደብተራ ፡ በየነ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ቃል፡ ከመለሰ ፡ በሁዋላ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ጨዋታውን ፡ ወደ ፡ ሞጣ፥ ወደ ፡ ዋሸራ ፥ ወደ ፡ ደብረወርቅ ፡ ይለውጠዋል ። በዚህ ፡ አሆ ሁዋን ፡ ሁለቱ ፡ ደብተሮች ፡ እዩተዋወቁ ፡ ያልተዋወቁ ፡ መስ ለው ፥ አንዱ ፡ ሲሸሽ ፥ ሌላው ፡ ሲያባርር ፡ አምሽተው ፡ በመ ጨረሻ ፡ በዛብህ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጦ ፥ ነገር ፡ ግን አንድ ፡ ከፋ ወሬ ፡ እንዳለ ፡ አረጋግጦ ፡ ዝም ፡ አለ። ጥቂት ፡ ዝም፡ ብለው፡ እንደቆዩ ፡ በዛብህ ፡ እንግዳውን ፡ አስከትሎ ፡ ለራት፡ ወደ መት ፡ ጠጅቱ ፡ ቤት ፡ ሄደ።

እዚያ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ "እመይቴ ፡ ደብተራ ፡ በዬነ ፡ በቅ ርቡ ፡ ካገሬ ፡ ከማንኩሳ ፡ የመጣ ፡ ወንድሜ፡ ነው ፤ ይወቁ ልኝ ።" አለ ፡ በዛብህ።

"እንዲህ ፡ ነው? እንኩዋን ፡ ደህና ፡ መጡ ፤ የበዛብህ ፡ ዘመዶች ፡ ሁሉ ፡ ደህና ፡ ናቸው? ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ወሬያ ቸው ፡ ጠፋኝ ፡ እያለ ፡ ተቸግሮ ፡ ነበር።" አሉ፡ እመት ፡ ጠጅቱ።

"ደህና ፡ ናቸው ፤ ሁሉም ፡ ደህና ፡ ናቸው ፤ በዛብህ ፡ እር ስዎን ፡ የመሰለ ፡ እናት ፡ አግኝቶ ፡ አገሩን ፡ በጭራሽ ፡ ረስቶ ዋል ፤ ደብረወርቅ ፡ ጥሩ ፡ አገር ፡ ነው ፤ እኔማ ፡ በወሬው ፡ ካል ሆነ ፡ አላሁን ፡ መጥቼበት ፡ አላውቅም።" አለና ፡ ደብተራ ፡ በዬነ ፡ ሲያደርገው ፡ እንዳመሸው ፡ ወሬውን ፡ ቶሎ፡ ብሎ ፡ ወደሌላ ፡ መራው ።

በመብል ፡ ጊዜ ፡ በዛብህ ፡ በራስ ፡ ምታት ፡ አመካኝቶ፡ ምንም ፡ ሳይበላ ፡ ተነሳ። ከዚያ ፡ እሱና ፡ እንግዳው ፡ ወደ፡ በዛ ብህም ፡ ጎጆ ፡ ተመልሰው ፡ በመፈራራት ፡ ብዙ ፡ ሳይጫወቱ፡ ወደዬምኝታቸው ፡ ሄዱ።

በዛብህ ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ሳይተኛ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ኮሽ ፡ ባለ ፡ ቁጥር ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ሲያረዳኝ ፡ መጣ ፡ እያለ፡ ተነስቶ ፡ ሲቀመጥ ፡ እንደገናም ፡ ሲጋደም ፡ አድሮ ፡ እንጋቱ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ሸልብ ፡ አደረገው ፤ እሱም ፡ ቅዠት ፡ የሞላበትና፡ የሚያስጨንቅ ፡ እንጂ ፡ የሚያሳርፍ ፡ እንቅልፍ ፡ አልነበ ረም።

በሀልሙ ፡ በገመድ ፡ ሁለት ፡ እግሮቹን ፡ የሁዋሊት ፡ ከግ ንድ ፡ ጋር ፡ ታስሮ ፡ ቆርጦ ፡ ለመሄድ ፡ ባለው ፡ አቅሙ ፡ ሁሉ ታግሎ ፡ ተሸንፎ ፡ ሊወድቅ ፡ ሲል ፡ አንዲት ፡ ርግብ ፡ ከግን ኩሳ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ከእእዋፉ ፡ ላይ ፡ ትንሳና ፡ በትዞር ፡ ቆይታ እታስረበት ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ታርፋለች ፤ ከዚያም ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ ትወ ርድና ፡ የታሰረበትን ፡ ገመድ ፡ ቆርጣ ፡ እፊቱ ፡ ላይ ፡ ጉርጉ ዋድ ፡ ቆፍራ ፡ ትቀብርና ፡- " የታሰርህበት ፡ ገመድ ፡ ያው ፡ ተቆ ርጦ ፡ ተቀበረልህ ፤ እንግዲህ ፡ ወደፈለግህበት ፡ ሂድ ። " ስት ለው ፡ ወዲያው ፡ ብንን ፡ ብሎ ፡ " በስመአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ። " አለና ፡ ያለመው ፡ ህልም ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ትርጉሙን ፡ ሲፈልግ ።

" በዛብህ ፡ ነቅተሀል ? " አለ ፡ ደብተራ ፡ በዩነ ፡

" እምን " አለ ፡ በዛብህ ።

" ከነቃህማ ፡ ተነስ ፡ ታጠቅ ። "

" ብታጠቅ ፡ ሞትን ፡ ድል ፡ መትቼ ፡ የወሰደውን ፡ እስ መልስ ፡ ይመስል ፡ ምን ፡ ያደርጋል ? ይልቅ ፡ አታበጨንቀኝ ፡ ቶሎ ፡ ንገረኝ ፤ እናቴ ፡ ናት ፡ የሞተች ፡ ወይስ ፡ አባቴ ? "

" እናትህም ፡ አባትህም ፡ አርፈዋል ፡ " አለ ፡ ደብተራ ፡ በየነ ።

" ሁለቱም ፡ ሞቱ ? እንግዲህ ፡ በቃ ! " አለና ፡ በዛብህ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆዬ ። በሁዋላ ፡ ተነስቶ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር ።

ደብተራ ፡ በዩነ ፡ በዛብህ ፡ የወላጆቹን ፡ ሞት ፡ ሲሰማ ፡ ባዘን ፡ ብዛት ፡ አንድ ፡ አደጋ ፡ ይደርስበታል ፡ ብሎ ፡ ሰግቶ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንዳለቃቀሰ ፡ ልቅሶ ውን ፡ ትቶ ፡ በምን ፡ አሆሁዋን ፡ እንደሞቱ ፡ ይጠይቀው ፡ ጀመር በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ደብተራ ፡ በዩነ ፡ ወደሀገሩ ፡ ተመለሰ ።-

በዛብህ ፡ የናት ፡ አባቱን ፡ ሞት ፡ ለመስማት ፡ የፈራውን ፡ ያክል ፡ ከሰማ ፡ በሁዋላ ፡ ቀለለው ፤ እንዲያውም ፡ ደስ ፡ አለው። ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ወደሁዋላ ፡ የሚጎትተው ፡ ነገር ፡ ሳይኖር ፡ ወደፈለገው ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ የፈለገውን ፡ አይነት ፡ ሀይወት ፡ ለመኖር ፡ ይችላል ፤ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በማይታወቅበት ፡ አገር፡

ሄዶ ፡ ወቃሽ ፡ ከሳሽ ፡ ሳይፈራ ፡ ምሽቱን ፡ አግብቶ ፡ ቤቱን፡ ሰርቶ ፡ ለመኖር ፡ ይችላል ። ወደፊት ፡ የሚኖረው ፡ የደስታ፡ ኑሮ ፡ ስእሉን ፡ ስሎ ፡ ምስሉን ፡ መስሎ ፡ ታዬው ፤ ስለዚህም፡ ደስ ፡ አለው ። ወላጆቹ ፡ ያቀዱለትን ፡ የሞት ፡ ህይወት ፡ ለመ ኖር ፡ የማይችል ፡ ስለመሰለው ፡ ጥሎዋቸው ፡ ሄዶ ፡ ነበር ። የነሱን ፡ ህይወት ፡ እንደፈለጋቸው ፡ ኖረው ፡ እሱም ፡ ህይወ ቱን ፡ እንደፈለገው ፡ እንዳይኖር ፡ አስቀድመው ፡ ከብዙ ፡ ታቦቶች ፡ ጋር ፡ ስለተዋዋሉበት ፡ ሲቀጣቸው ፡ ጥሎዋቸው፡ ሄዶ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሄደ ፡ በሁዋላ ፡ ቢያስበው ፡ እነ ዚያ ፡ በእድሜ ፡ ጎዳና ፡ የደከሙ ፡ አእሩግ ፡ ወላጆቹ ፡ አሳዘ ኑት ፤ ያደረጉትም ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ስተት ፡ ቢሆን ፡ ለጥቅሙ፡ እንጂ ፡ ለጉዳቱ ፡ አስበው ፡ ያላደረጉት ፡ መሆኑ ፡ ታሰበው ። ከዚ ህም ፡ ሌላ ፡ እግራቸው ፡ እመቃብር ፡ አፍ ፡ ቆሞ ፡ አፈር ፡ ሳይ መልስባቸው ፡ ቢሄድ ፡ የሰው ፡ መፈረጃ ፡ መሆኑ ፡ አስፈ ራው ። ስለዚህ ፡ በመሄድና ፡ በመመለስ ፡ አውታር ፡ ተወ ጥሮ ፣ ሰራሉ ፡ ከመኖርና ፡ ስለ ፡ ወላጆቹ ፡ ካለመኖር ፡ አንዱን፡ መምረጥ ፡ አቅቶት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዋሽራ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዙራ ምባ ፣ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደብረወርቅ ፡ እያለ ፡ ያላሰበውንና ፡ ያልፈ ለገውን ፡ ትምህርት ፡ ሲማር ፡ ቆዩ ፣ በመሄድና ፡ በመመለስ፡ መሀከል ፡ መቁረጥ ፡ አቅቶት ፡ ቆሞ ፡ ሲያመነታ ፡ ጊዜ አይቆ ምም ፤ ጊዜ ፡ ይሄዳል ፤ ጊዜ ፡ ደረሰበት ፤ ጊዜ ፡ ቀደመው ። እና ትና ፡ አባቱ ፡ ሞቱ ። እንዳልወለዱ ፣ እንዳላሳደጉ ፡ አስታ ማሚ ፡ አጥተው ፡ ሞቱ! እንዳልወለዱ ፡ እንዳላሳደጉ ፡ ቀባሪ፡ አጥተው ፡ በሹም ፡ ትእዛዝ ፡ አፈር ፡ ለበሱ! እነሱ ፡ ምን ፡ ከፉ፡ ውለው ፡ ኖሮዋል? ተባሉ ! እሱም ፡ የሰው ፡ መፈረጃ ፡ ሆነ! ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ወደማንኩሳ ፡ መመለስ ፡ በጉዳት ፡ ላይ ፡ ተፈ ርዶ ፡ ከመጨመር ፡ በቀር ፡ ጥቅም ፡ የለውም ። አንደኛውን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፣ ተራራ ፡ ዞሮ ፡ ወደማይታይበት ፣ ወሬው ፡ ወደ ማይሰማበት ፡ አገር ፡ መሄድ ፡ ይሻላል! አሁን ፡ የሁዋሊት አስሮ ፡ አምስት ፡ አመት ፡ ሙሉ ፡ በዋሽራ ፣ በዙራምባ ፣ በደብ ረወርቅ ፡ ዙሪያ ፡ ሲያዞረው ፡ የነበረው ፡ ብርቱ ፡ ማሰሪያ ፡ ተቆ ርጡዋል ፤ አሁን ፡ ነጻነቱን ፡ አግኝቶዋል ፡ ስለዚህ ፡ ወደሚፈ

ልግበት ፡ ሄዶ ፡ እንደሚፈልገው ፡ ይኖራል ። እግዚአብሔርስ ? ታቦቶችስ ? " አሀሀ . . . እስቲ ፡ እሱ ፡ ያውቃል !" አለ ።

በዛብህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ካሰበና ፡ ካሰላሰለ ፡ በሁዋላ ፡ በጠቅላላው ፡ የናት ፡ ያባቱ ፡ ሞት ፡ ያገሩም ፡ መቅረት ፡ አሳዘነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ነጻ ፡ አደረገው ፤ ስለዚህ ፡ ማንኩሳን ፡ ሁለተኛ ፡ አገር ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ላያስበው ፡ ማንኩሳ ፡ ለሌሎች ፡ ይኑር እንጂ ፡ ለሱ ፡ ከናት ፡ አባቱ ፡ ጋር ፡ ሞቶ ፡ እንደተቀበረ ፡ ሊቆጥረው ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ ወደአዲስ ፡ አበባ ፡ ለመሄድ ፡ ወሰነ ። መልስ፡ ያላገኘለትና ፡ መቸም ፡ ቢሆን ፡ የማያገኝለት ፡ ከታቦቶች ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ቃልኪዳን ፡ ነው ፤ እሱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተው !

# ምእራፍ : ፯ :

## የመጨረሻ : ኑዛዜ:

በዛብህ : ደብረወርቅ : በቆዬበት : ጊዜ : ሀዲስና : ብሉይ: አሂዶ : መጽሀፌ : መነከሳት : ጀምሮ : ሰሰነበረ : የጀመረውን: እስኪጨርስ : ደብረወርቅ : ቆይቶ : ዘመን : ሲሰወጥ : እንዲሄድ : አሰበ:: ወዲያውም : ምንም : እንኩዋ : ቅኔ : ቢቀኝ: ምኞቱ : የቅኔ : መምህር : ሰመሆን : ሰሰነበረ : አዲስ : አበባ: ከመሄዱ : በፊት : ዲማ : በሚባሰው : አገር : ትንሽ : ጊዜ: ቆይቶ : ሰቅኔ : መምህርነት : እንዲመረቅ : ወሰነ :: ነገር : ግን: ከደብረ : ወርቅ : ሰመሄድ : መወሰኑን : ጊዜው : እስኪደርስ: ከሙት : ጠጅቱ : መሸሸግ : አስፈላጊ : መሰሎ : ታዬው:: ምክንያቱም : እሙት : ጠጅቱ : በዛብህ : ልጃቸውን : እየመሰላቸው : አጅግ : ይወዱት : ሰሰበረ : መሄዱን : የነገራቸው: እንደሆነ : በጣም : እንደሚያዝኑና : እንደሚያሰቅሱ : አውቆ አዘናቸውንና : ልቅሶዋቸውን : የሚያይበት : ጊዜ : የተቻሰ: ያክል : እንዲያጥርሰት : ነው::

በዛብህ : ከመት : ጠጅቱ : ጋር : ምግቡን : እየመገቡት: ልብሱን : እያሰበሱት : እሱም : ልጅ : ሰናቱ : የሚረዳውን: ያክል : እዬረዳቸው : ከሁሰት : እመት : በላይ : ሲቀመጥ: አንድ : ቀን : ፊት : ሳይዘዙዋሩ ፥ ፍቅራቸው : በዬቀኑ : የመጨመር : እንጂ : የመቀነስ : ምልክት : ሳይታይበት : ኖሩ:: ጊዜ : አጋጠማቸው፤ ተዋደዱ፤ ሰጊዜው : እናትና : ልጅ : ሆኑ፤ እነሆ : ጊዜው : አሰቀ፤ እናትና : ልጅነታቸውም : አብሮ: አሰቀ:: የባእድ : ፍቅር ፥ ይልቁንም : የመንገደኛ : እንደህልም : እዣት : ነው :: የህልም: እዣት : ቀሪ : ፍርፊሪ : የሴሰው ፥ አውሎ: አሳድሮ : የማይበሉት : በህልም : ውስጥ : እስካሉ : የሚያልቅ : የሚደርቅ : አይመስልም:: ብንን : ሲሉ : ግን ፥ አይንን : ሲገልጡ : ምንም : የሰም:: የባእድ : ፍቅርም: እንዲሁ : ነው :: አብሮ : እስካሉ : እንዳንድ : ጊዜ : ሲያጋጥም: ከዘመድ : ፍቅር : ሲበልጥ : ይችላል ፤ የሚያልፍ : አይመስ

ልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሲለያዩ ፡ እንደገና ፡ የሚያገናኝ ፡ መሳቢያ ፡ መታሰቢያ ፡ የለውም ፤ ያልቃል ። ምናልባት ፡ መታሰቢያ ፡ ቢኖር ፡ በያሉበት ፡ ሆነው ፡ ደግ ፡ ሴት ፡ ነበሩ ፤ ደግ ፡ ሰው ነበር ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በቃ ።

መስከረም ፡ ጠባ ፤ ዘመን ፡ ተለወጠ ፤ አዲስ ፡ አመት ፡ ተጀመረ ፤ እንዦ ፡ በዛብህም ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ አገር ፡ ሲለውጥ ፤ አዲስ ፡ ህይወት ፡ ሊጀምር ፡ ነው ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እሁድ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሳሽ ፡ ከቁርስ ፡ በሁዋላ ፡ በዛብህ ፡ ሲፈር ፡ ሲቸር ፡ “ እመይቴ ፤ ትሁኔ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደውጭ ፡ ብትቀይ ፡ የምነግርዎ ፡ ጉዳይ ፡ ነበረኝ ፡ ” አለ ፡- እመት ፡ ጠጅቱም ፡ ትሁኔን ፡ ማድቤት ፡ ሄዳ ፡ እንድትቀይ ፡ አዘው ፡- “ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አገኘህ ? ” አሉት ። በዛብህ ፡ እንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ግንባሩን ፡ ሲያሽ ፡ ቆይና ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ “ እመይቴ ፤ ላደረጉልኝ ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ለመክፈል ፡ አልችልምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋጋዎን ፡ ይክፈልዎ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሚወዱት ፡ ልጅዎ ፡ በአይነ ፡ ሥጋ ፡ ለመገናኘት ፡ ያብቃዎ ፤ አሁን ፡ የመማሁበትን ፡ ትምህርቴን ፡ ስለጨረስሁ ፡ መርቀው ፡ እንዲያሰናብቱኝ ፡ እለምንዎታለሁ ። ” አለ ።

የዚህን ፡ ጊዜ ፡ እመት ፡ ጠጅቱ ፡ አይናቸውን ፡ ለበስ ፡ አድርገው ፡ መልስ ፡ ሳይሰጡት ፡ ትንሽ ፡ ቆይተው ፡ “ ለካ ፡ ይሄም ፡ አለና ” ” አሉ ።

“ ምኑ ? ” አለ ፡ በዛብህ ።

“ ያንተና ፡ የኔ ፡ መለያየት ፡ ”

“ ፊትም ፡ ሳናስበው ፡ ያገናኘን ፡ እግዚአብሄር ፡ ነው ፤ አሁንም ፡ ደህና ፡ ከሆን ፡ ያገናኘን ፡ ይሆናል ። ” አለ ፡ በዛብህ ፡ እንባቸው ፡ እንደቀረበ ፡ ሲያይ ፡ ልቡ ፡ እንደመሸበር ፡ እለና ።

“ ባላገናኘን ፡ ባልተዋወቅን ፡ ይሻለኝ ፡ ነበር ፡ ” አሉ ፡ እመት ፡ ጠጅቱ ፡

“እኔ ፡ ደግሞ ፡ ለሁልጊዜ ፡ የማይረሳ ፡ የደግነትና ፡ የታላቅነት ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ መታሰቢያ ፡ ስላገኘሁ ፡ ያገናኘንን ፡ አምላክ ፡ አመሰግነዋለሁ ። ”

" ስማህ ፡ በዛብህ ፡ የሚወዱት ፡ ሁሉ ፡ ራሱ ፡ እንጂ ፡ መታ ሰቢያው ፡ አያስፈልግም ፡ " አሉ ፡ እመት ፡ ጠጅቱ ።

" እንዴት ? "

" የሚወዱት ፡ ሁሉ ፡ ራሱ ፡ አብሮ ፡ ሲኖር ፡ ደስታ ፡ ይሰ ጣል ፤ ለሁልጊዜ ፡ ሲለይ ፡ ግን ፡ መታሰቢያው ፡ ያው ፡ የሚወ ዱት ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ የሚሰጠውን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባለመኖሩ ፡ የቀረውን ፡ ደስታ ፡ ስለሚያስታውስ ፡ ለልብ ፡ ስቃይ ፡ ከመሆን ፡ በቀር ፡ ጥቅም ፡ የለውም ፡ " ።

" እውነትዎ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ አልተመለከትሁትም ። "

" ለወደፊቱ ፡ ልምከርህ ፤ የምትወደው ፡ ለሁልጊዜ ፡ ሲለ ይህ ፡ የሚያስረሳህ ፡ እንጂ ፡ የሚያስታውስህ ፡ ነገር ፡ አትፈ ልግ ፤ ያለዚያ ፡ ህይወትህ ፡ የስቃይ ፡ ህይወት ፡ ይሆናል ። " አሉ፡ እመት ፡ ጠጅቱ ። በዛብህ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

" ግሩም ፡ ነው ። " አሉ ፡ እመት ፡ ጠጅቱ ፡ ትንሽ ፡ ሳቅ ፡ አሉና ፡ ፊታቸው ፡ በትካዜ ፡ እንደተሞላ ፡-" አባትና ፡ እናት ህን ፡ ተረድተህ ፡ ስታለቅስ ፡ አይኔ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ እያለቀሰ ፡ ልቤ ፡ በምስጢር ፡ የነበረው ፡ ደስታ ፡ ሊነገር ፡ አይቻልም ፡ ነበር ። "

" እንዴት ?" አለ ፡ በዛብህ ።

" በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ልነግርህ ፡ አልችልም ፤ እኔም ፡ ለጊዜው ፡ ራሴን ፡ ታዘብኩት ። ብቻ ፡ በሁዋላ ፡ የሰጠ ሁት ፡ ትርጉም ፡ አባት ፡ እናትህ ፡ ከሞቱ ፡ አገርህን ፡ አታስ ብም ፤ እዚሁ ፡ ለኔ ፡ ሆነህ ፡ ትቀራለህ ፡ ብዬ ፡ በማመን ፡ መሰ ለኝ ። " በዛብህ ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ቆዩ ። ከዚያ ፡ እመት ፡ ጠጅቱ ፡ ቀጠሉና ፡-

" አሁን ፡ ወደ ፡ ሀገርህ ፡ ለመመለስ ፡ ነው ፡ ያሰብኸው?"

"የለም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሄጄ ፡ አቋቋም ፡ ለመቀጸል ፡ ነው ያሰብሁት" ፡ አለ ፡

" ከሸዋ ፡ ለትምህርት ፡ ወደዚህ ፡ ሲመጡ ፡ አንተ ፡ ወደ ዚያ ፡ የምትሄድበት ፡ ምክናያት ፡ ምንድር ፡ ነው ?"

" እብድ ፡ ተክሌ ፡ የሚሉት ፡ አቋቋም ፡ አለና ፡ እሱን ፡

ለመቀጸል ፡ ነው ፡ የምሄድ ፡ ”

እሙት ፡ ጠጅቱ ፡ እንደመሳቅ ፡ አሉና ፡ “ በላ ፡ እግዚአብ ሄር ፡ ይርዳህ ፡ ” አሉ ። ወዲያው ፡ ቀጠሉና ፡- “ ከተገናኘን ፡ እስ ከዛሬ ፡ ድረስ ፡ በህልም ፡ ውስጥ ፡ ነበር ፡ የምኖረው ። በመጀመ ርያ ፡ ህልሜ ፡ ልጄን ፡ አስመስሎ ፡ አሳዬኝና ፡ ወደድሁህ ፤ በሁ ዋላ ፡ ከልጄም ፡ የተሰዬህ ፡ አስመስሎ ፡ እድሜህን ፡ ከፍ ፡ አድ ርጎ ፡ የኔን ፡ እድሜ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ አሳየኝ ፤ ይህም ፡ ከፊተ ኛው ፡ የበለጠ ፡ ልቤን ፡ በደስታ ፡ ሞላው ። አሁን ፡ ዛሬ ፡ ድን ገት ፡ ከእንቅልፌ ፡ ብነቃ ፡ አድረህ ፡ ሂያጅ ፡ ባለብዙ ፡ ተስፋ ፡ ጐልማሳ ፡ መሆንህን ፡ እኔም ፡ ጊዜ ፡ ያለፈብኝ ፡ አሮጊት ፡ መሆ ኔን ፡ አወቅሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ግዴለም ፡ ህልም ፡ ነው ፤ የሁለት ፡ አመት ፡ ተከል ፡ ህልም ! ግዴለም ፡ እንርሳው ። ” አሉና ፡ እን ባቸው ፡ ጣምራ ፡ ጣምራ ፡ እየሆነ ፡ እዬወረደ ፡ ተነስተው ፡ ወደ ፡ ጉዋዳ ፡ ገቡ ።

በዛብህ ፡ የሚያደርገውን ፡ አጥቶ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲን ቆራጠጥ ፡ እሙት ፡ ጠጅቱ ፡ አይናቸውን ፡ አደራርቀው ፡ እንደ ገና ፡ ወጡና፡-

“ መቸ ፡ ለመሄድ ፡ ታስባለህ ?” አሉት ።

“ ዛሬ ፡ ” አለ ፡ በዛብህ ፡

“ ስንቅ ፡ እንኳ ፡ ሳይሰናዳልህ ! ”

“ ግዴለም ፡ ዲማ ፡ ዘመድ ፡ አለኝ ፡ እዚያ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ አድሬ ፡ ይሰናዳልኛል ። ”

“ እዚያ ፡ የምትቆዩውን ፡ እዚህ ፡ ለመቆዬት ፡ አትች ልም ? ”

“ አብሬያቸው ፡ ወደሸዋ ፡ ለመሻገር ፡ የተቃጠርሁዋ ቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዳያመልጡኝ ፡ ብሄድ ፡ ይሻላል ፡ እሙይቴ ። ”

“በል ፡ እንግዲህ ፡ እግዚአብሄር ፡ካንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን፡” አሉ ፡ እሙት ፡ ጠጅቱ ።

በዛብህ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የመሄዱን ፡ ነገር ፡ ለሙት ፡ ጠጅቱ ፡ ሲገልጽ ፡ የመጀመርያ ፡ አሳቡ ፡ አስቀድመው ፡ እው ቀውት ፡ እንዲቆዩ ፡ እንጂ ፡ ያነለት ፡ ለመሄድ ፡ ባይሆን ፡ ሁኔ ታቸውን ፡ ካዩና ፡ የተናገሩትንም ፡ ሁሉ ፡ ከሰማ ፡ በሁዋላ ፡

እንድ ፡ ስእት ፡ እንኳዋ ፡ አብሮዋቸው ፡ ለመቆዩት ፡ ፈራ ። ስለ ዚህ ፡ ያኑለት ፡ ተሰናብቶ ፡ ወደ ፡ ዲማ ፡ ተጉዋዘ ።

# ምእራፍ ፡ ፫ ፡

## የቅኔ ፡ ማእበል ፡

በዛብህ ፡ ዲማን ፡ ከወረው ፡ በቀር ፡ ረግጦት ፡ አያውቅም፡ ነበር ። ዲማ ፡ በጎጃም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ካላቸው ፡ አድባራት ፡ አንዱ ፡ በመሆኑ ፡ እንደስሙ ፡ መልኩ ፡ ያማረ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ተሰርቶ ፡ በዙሪያ ፡ ገባው ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ ዘቅዝቆ ፡ የሚያይ ፡ ከተማው ፡ የሞቀ ፡ የደመቀ ፡ ህዝቡ ፡ የሰለጠነ ፡ መስሎ ፡ ይታየው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ገናና ፡ ደብር ፡ መቼ ፡ ደርሼ ፡ አይቼው ፡ እያለ ፡ ሲሄድ ፡ ወደአንድ ፡ ትንሽ ፡ ኮረብታ ፡ ደረሰና ፡ እሱዋን ፡ እንደ ፡ ዞረ ፡ እደልዳላ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ መንደር ፡ አዬ ። ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እማህል ፡ በዙሪያው ፡ የመንደሩ ፡ ቤቶች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ችፍግ ፡ ብለው ፡ ጫጩቶችዋ ፡ የከበቡዋት ፡ ዶሮ ፡ ይመስላል ። ከመንደሩ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ዙርያ ፡ ገባው ፡ በገብስ ፡ ሰብል ፡ በስንዴና ፡ በሽንብራ ፡ በጤፍም ፡ ቡቃያ ፡ ተዠጎርጉሮ ፡ አጊጦዋል ። መንደሩ ፡ ብቻ ፡ እንደተቃጠለ ፡ ሁሉ ፡ ከአመድ ፡ ከምር ፡ በቀር ፡ እርጥብ ፡ ነገር ፡ አይታይበትም ።

በዛብህ ፡ ገና ፡ እመንደሩ ፡ ሳይደርስ ፡ አንድ ፡ ከመንደሩ ፡ የሚመጣ ፡ ሰው ፡ አገኘና ፡ “ እንዴት ፡ ዋሉ ፡ ጌታ ? ” አለ ።

“እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንደምን ፡ ዋሉ ? ” አለ ፡ መንደረኛው ።

“እባክዎ ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ ዲማ ፡ ከዚህ ፡ ብዙ ፡ ያስኬዳል! ”

“ ደርሰዋል ፡ ”

“ ከዚህ ፡ ከመንደሩ ፡ ወዴት ፡ ነው ? ”

“ ከየትኛው ፡ መንደር ? ”

“ እዚህ ፡ እፊቴ ፡ ከማየው ፡ ” አለ ፡ በዛብህ ፡ አገጩን ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ አሹሎ ፡

“ ሙሉ ፡ ጦቢያ ፡ የሚያከብረውን ፡ ደብር ፡ እርስዎ ፡ መን

ደር ፡ ቢሉት ፡ ክብሩ ፡ አይቀነስም።" አለ ፡ ሰውዬው ፡ ያገር፡ ፍቅር ፡ በተሞላ ፡ መንፈስ።

"ይማሩኝ ፡ ጌታዬ ፡ ባለማወቅ ፡ ነው። " አለ ፡ በዛብህ፡ እንደመደንገጥ ፡ ብሎ ። ሰውዬውም ፡ ገልመጥ ፡ ብሎ ፡ አይቶት ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ።

"ወይ ፡ ዲማ ፡ ለጆሮ ፡ ከባድ ፡ ለአይን ፡ ቀላል ፡ ማለት፡ አንተ ፡ ነህ! ወሬህን ፡ እንደሰማሁ ፡ ሳላይህ ፡ በቀረሁ ፡ ሳከብ ርህ ፡ እኖር ፡ ነበር።" አለና ፡ በዛብህ ፡ እርምጃውን ፡ ቀንሶ፡ ዝግ ፡ እያለ ፡ ባላገሮች ፡ ከተማ ፡ በሚሉት ፡ መንደር ፡ ገባ። መጀመሪያ ፡ ወደቤተክርስቲያን ፡ ሄዶ ፡ ተሳለመና ፡ ቅኔ ፡ መአ ልቱንም፥ ቅድስቱንም ፡ እዬዞረ ፡ ካዬ ፡ በሁዋላ ፡ እዚያ ፡ አንድ፡ ተማሪ ፡ አግኝቶ ፡ ቅኔ ፡ ቤቱን ፡ እንዲያሳዬው ፡ ለመነው።

ቅኔ ፡ ቤቱ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሰሜን ፡ ምእራብ ፡ በአንድ፡ ሰፊ ፡ የሾህ ፡ አጥር ፡ የተከበበ ፡ ነው። ካጥሩ ፡ መሀከል ፡ ዙርያ ውን ፡ ተጠምጥመው ፡ ወገቡን ፡ ካቀፉት ፡ ባላምች ፡ ጋር ፡ ለመ ውደቅ ፡ የሚታገል ፡ አንድ ፡ ረዥም ፡ የእንጨት ፡ ፎቅ ፡ ቤት ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ቁሞዋል ። በፎቁ ፡ ዙሪያ ፡ አንዱን ፡ ከሌ ላው ፡ ለመለዬት ፡ የሚያስቸግሩ፥ ቁጥራቸው ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ በሳር ፡ የተጠደቡ ፡ ትናንሽ ፡ ጎጆዎች ፡ አጥሩን ፡ ሞልተው ታል። ነገር ፡ ግን ፡ ባለፈው ፡ ክረምት ፡ በሽታ ፡ ገብቶ ፡ ጥቂት፡ ተማሪዎች ፡ ስለገደለ ፡ ግማሹ ፡ ተማሪ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደቢቸና ፡ ስለሄደ ፡ ከጎጆዎቹ ፡ ሲሶ ፡ የሚሆኑት ፡ ባዶ ፡ ነበሩ። ቢሆንም፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በትንሹ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ተማሪዎች፡ ነበሩ።

በዛብህ ፡ አጥሩ፡ በሩፍ ፡ ቆሞ ፡ የሚወጡና ፡ የሚገቡትን፡ ተማሪዎች፡ ትንሽ ፡ ሲመለከት ፡ እንደቆዬ ፡ ሰፈር ፡ ሲቸር፡ አጥሩን ፡ ገብቶ ፡ በመጀመሪያ ፡ ወደምትገኘው፡ ጎጆ ፡ ሄዶ፡ እደጅ ፡ ተቀምጠው ፡ ባለፈው ፡ ማታ ፡ በተዘረፈው ፡ ቅኔ፡ ለሚከራከሩ ፡ አራት ፡ ተማሪዎች ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠ። እነሱም፡ ተነስተው ፡ ለሰላምታው ፡ ከመለሱ ፡ በሁዋላ ፡ ማንን ፡ እንደሚ ፈልግ ፡ ጠየቁት።

" በተለይ ፡ የምፈልገው ፡ የለኝም ፤ ለትምህርት ፡ የመ

ማሁ ፡ እንግዳ ፡ ነኝ ፡ ” አለ ፡ በዛብህ ።

ከዚያ ፡ አንደኛው ፡ ተማሪ ፡ ወደ ፡ ጎጆዋ ፡ እዩርጠ ፡ ገብቶ ፡ ካንደኛው ፡ የንጨት ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አጉዋዛ ፡ አምጥቶ ፡ እበሩ ፡ አጠገብ ፡ እተጋደመው ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ አነጠፈና ፡ በዛብህን ፡ እንዲቀመጥ ፡ ለመነው ። ወዲያው ፡ ሁለተኛው ፡ ተማሪ ፡ ውሀ ፡ በቅምጫና ፡ አቅርቦ ፡ እግሩን ፡ አጠበው ። እግሩን ፡ ታጥቦ ፡ እስኪጨርስ ፡ ሶስተኛው ፡ ተማሪ ፡ በፉጋ ፡ ወፍራም ፡ ተልባ ፡ መቶ ፡ እንጀራውን ፡ እስከ ፡ ኮፋዳው ፡ አቅርቦ ፡ “ እኛ ፡ የዘረፋ ፡ ጊዜ ፡ እንዳይደርስብን ፡ ብለን ፡ ከልመና ፡ እንደ ፡ ተመለስን ፡ እራት ፡ በልተናልና ፡ ይብሉ ። ” እያለ ፡ ኮረዳውን ፡ እበዛብህ ፡ ፊት ፡ አጋድሞ ፡ ባፉ ፡ በኩል ፡ እጁን ፡ አግብቶ ፡ ከአምስት ፡ ስድስት ፡ ቤት ፡ የተለመነ ፡ አምስት ፡ ስድስት ፡ አይነት ፡ ቁራሽ ፡ አውጥቶ ፡ አላዩ ፡ አደረገለት ። እሱም ፡ አመስግኖ ፡ ይበላ ፡ ጀመር ። ሊጨርስ ፡ ሲል ፡ እንደገና ፡ ከተጋደመው ፡ ኮረዳ ፡ እያወጣ ፡ ይጨምርለታል ፤ በዚህ ፡ አሆሁዋን ፡ በዛብህ ፡ ራቱን ፡ በላ ። ኮፋዳው ፡ ውስጡ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ላዩ ፡ እንደ ፡ ሞሰብ ፡ መብያ ፡ ነው ።

በዛብህ ፡ ራቱን ፡ ሲበላ ፡ አጠገቡ ፡ ተቀምጦ ፡ ይጋብዘው ፡ የነበረው ፡ ተማሪ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥያቄ ፡ ይጠይቀው ፡ ነበር ።

“ መጽሀፍ ፡ ለመቀጸል ፡ ነው ? ወይስ ፡ ለቅኔ ፡ ትምህርት ፡ ነው ፡ የመጡ ? ”

“ ቅኔ ፡ ለመማር ፡ ነው ። ” አለ ፡ በዛብህ ።

“ እሀ ፡ ለማስዘብ ፡ ነው ? ወይስ ፡ ለመጀመር ? ”

“ ለማስዘብ ፡ ”

“ወዴት ፡ ነው ፡ መጀመሪያ ፡ የተቀኙ ?”

“ዋሸራ ። ”

“ መቼ ? ”

“ ከአራት ፡ አመት ፡ በፊት ። ”

“ ከዚያ ፡ ወዲህስ ? ”

“ ሁለት ፡ አመት ፡ ያክል ፡ ዙራምባ ፡ ዝማሬ ፡ መዋሲት ፡ አሄድሁ ፤ ሁለት ፡ አመት ፡ ተኩል ፡ ያክል ፡ ደብረ ፡ ወርቅ ፡ መጽሀፍ ፡ አቀጸል ፡ ነበር ። ”

ጋባዡ ፡ ተማሪ ፡ ይህን ፡ ሲሰማ ፡ ለመጠዬቅ ፡ እንደመፍ ራት ፡ አለና ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ጉዋደኞቹን ተመለከተ ። እነሱም ፡ ክርክራቸውን ፡ አቋርጠው ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ። ሁሉም ፡ ገና ፡ ያልተቀኙ ፡ ጀማሪዎች ፡ ስለነበሩ ፡ በበዛብህ ፡ ፊት ፡ መከራከ ሩን ፡ ፈሩ ። በመሀከሉ ፡ አንድ ፡ የደንጋይ ፡ ደወል ፡ ተደጋግሞ ፡ ተደወለ ።

"የምን ፡ ደወል ፡ ነው ?" አለ ፡ በዛብህ ፡

"ለዘረፋ ፡ ተሰብሰቡ ፡ ነው ፡" አለ ፡ አንደኛው ፡ ተማሪ ፡

"ማነው ፡ የሚዘርፍ ?"

"ይህን ፡ ሳምንት ፡ የኔታ ፡ ናቸው ፡"

"ሌሎች ፡ ዘራፊዎች ፡ አሉ ?"

"አዎን ፡ ሁለት ፡ አሉ ፡ የሚያስነግሩትማ ፡ ብዙ ፡ ናቸው። እስቲ ፡ . . . . ሰባት ፡ ናቸው ፡ መሰለኝ ፡ አዎን ፡ ሰባት ፡ ናቸው ።"

"ስለዚህ ፡ ከመምህሩ ፡ ሌላ ፡ በውስጣቸው ፡ ዘጠኝ ፡ የቅኔ ፡ መምህራን ፡ አሉ ፡ ማለት ፡ ነው?" አለ ፡ በዛብህ ።

"አዎን ፤ ሰባቱ ፡ ገና ፡ ለመዝረፍ ፡ አልደረሱም ፤ ማስነ ገር ፡ ብቻ ፡ ነው ።" አለና ፡ ተነሳ ። ጉዋደኞቹ ፡ ቀደም ፡ ብለው፡ ወደዘረፋው ፡ ሄደዋል ።

"እኔስ ፡ ብመጣ ፡ ምናለ ?" አለ ፡ በዛብህ ።

"ምናለ ፡ የደብሩ ፡ ዲያቆንና ፡ ደብተራው ፡ እንኩዋ ፡ ሳይ ቀሩ ፡ እዚሁ ፡ ሲሰማ ፡ ነው ፡ የሚያመሽ ፡" አለ ፡ ተማሪው ። ከዚሁ ፡ በሁዋላ ፡ ተያይዘው ፡ የቅኔ ፡ ዝናም ፡ ወደሚዘንምበት ፡ ፎቅ ፡ ሄዱ ።

እዚያ ፡ ሲደርሱ ፡ ከፎቁ ፡ ስር ፡ አደባባዩ ፡ በሰው ፡ ግጥም ፡ ብሎ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ አይንቀሳ ቀስ ፤ አይተነፍስ ፤ አስማት ፡ እንደዞረበት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፎቁ ፡ አንጋጦ ፡ ሲመለከት ፡ እያንዳንዱ ፡ ህይወት ፡ የሌለው ፡ ምስል ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

በመሀከሉ ፡ ከፎቁ ፡ ላይ ፡ የእጅ ፡ ጭብጨባ ፡ ተሰማ ። የዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከዳር ፡ እስከዳር ፡ መንቀሳቀስ ፡ ሆነ ፤ ሹክሹክታ ውም ፡ አደባባዩን ፡ ሞላው ። እንደገና ፡ ሲጨበጨብ ፡ እንደገና ፡ ሁሉም ፡ ጸጥ ፡ አለ ።

" አእመረ ፡ " አለ ፡ አንድ ፡ ድምጽ ፡ ከፎቅ ፡ ላይ ። አለቃ ፡ ክንፉ ፡ ናቸው ።

" አእመረ ፡ " አለ ፡ ተቀባዩ ፡ ተማሪ ፡ ከመሬት ።

" የእምር ፡ ያእምር ፡ ያእምር ፡ አእማሪ ፡ አእማሪት ፡ አእማርያን ፡ አእማርያት ፡ አእምሮ ፡ " አሉ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡- ተማሪውም ፡ ተቀበለ ። ከዚህ ፡ በሁዋላ ፡ ለምሳሌ ፡ ያክል ፡ ከዩቤቱ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ግስ ፡ ነስው ፡ ዘረፉ ፡ ጀመሩ ።

ከጉባየ ፡ ቃና ፡ ጀምረው ፡ እመወድስ ፡ ሲደርሱ ፡ እንደሁል ጊዜው ፡ ሞቅ ፡ አላቸውና ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ እንደፎካሪ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እዩተንጎራደዱ ፡ ማእበሉን ፡ ያወርዱት ፡ ጀመር ። መወድሱን ፡ ሲጨርሱ ፡ እንደገና ፡ "ተቀበል ፡ " አሉና ፡- ከጉባየ ፡ ቃና ፡ አንድ ፡ ብለው ፡ ጀመሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ተቀባዩ ፡ ስለደከመው ፡ እሱ ፡ ተቀምጠ ፡ ሌላው ፡ እስኪተካ ፡ ጉባየ ፡ ቃናውንና ፡ ዘእምላኪየውን ፡ አለተቀባይ ፡ እንጎደጎዱት ፤ እስላሴ ፡ ላይ ፡ ተቀባይ ፡ ደረሰና ፡ እስከ ፡ መወድስ ፡ ተቀበለ ። አለቃ ፡ ክንፉ ፡ ላባቸው ፡ እየተንጠፈጠፈ ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ " ተቀበል ፡ " ብለው ፡ ጉባየ ፡ ቃና ፡ ሲጀምሩ ፡ መምህራት ፡ ወደፎቅ ወጡና ፡ ለምነው ፡ ወደምኝታቸው ፡ ወስደው ፡ አስተኙዋቸው ። ገላጋይ ፡ ባይደርስ ፡ ደከሞዋቸው ፡ እስኪወድቁ ፡ ድረስ ፡ ይዘርፉ ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ እንደዚሁ ፡ ከጉባየ ፡ ቃና ፡ እስከ ፡ መወድስ ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ ዘርፈው ፡ ደከሞዋቸው ፡ ወድቀው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ታመው ፡ ዳኑ ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ቢበዛ ፡ ከዕስት ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ በላይ ፡ ዘርፈው ፡ አያውቁም ። ምክንያቱም ፡ ሰዎች ፡ በመፍራት ፡ እየከለከሉዋቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተቸግረው ፡ አይደለም ። አለቃ ፡ ክንፉ ፡ አእምሮአቸው ፡ ከቅኔ ፡ድርና ፡ ማግ ፡ እንደተሰራ ፡ ራሱ ፡ ካላለቀ ፤ ቅኔው፡ ያልቃል ፡ ተብሎ ፡አይታሰብም ። ከሁሉም ፡ የሚያስገርመው ፡ ብዙ ፡ በዘረፉ ፡ መጠን ፡ እንደሌሎቹ ፡ መምህራን ፡ ቅኔያቸው ፡ እዩቀለለ ፡ በመሄድ ፡ ፈንታ ፡ ምስጢሩ ፡ እዩረቀቀና ፡ ንባቡ ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ መርጠው ፡ እንዳጋጠሙት ፡ ሁሉ ፡ እያማረ ፡ ነው ፡ የሚሄድ ። አለቃ ፡ ክንፉ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹቆጥረው ፡ ከሚቀኙት ፡ እንደሌሎች ፡ መምህራን ፡ አስበው ፡ ተጨንቀው ፡

ከሚዘርፉት ፡ ቅኔ ፡ ሲያስከራቸው ፡ በዚህ ፡ አለም ፡ መኖራቸውን ፡ ሲረሱት ፡ ከጻድቃን ፡ ከሰማእታት ፡ ከምእመናን ፡ ከመላእክት ፡ ጋር ፡ በሌላ ፡ አለም ፡ የሚጫወቱ ፡ ሲመስላቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሳያውቁት ፡ ሳይሰሙቸው ፡ የሚያወርዱት ፡ የቅኔ ፡ ማእበል ፡ የእውነተኛ ፡ የተዋነዩ ፡ ደቀመዝሙር ፡ አሰኚቶዋቸው ፡ ቀረ ። በቅኔ ፡ ቤት ፡ የማይሞት ፡ የማይረሳ ፡ ስም ፡ ሰጣቸው ።

አለቃ ፡ ክንፉ ፡ በመጽሀፍና ፡ በዜማ ፡ በዝማሬ ፡ መዋሲትና ፡ ባቆቋዋም ፡ ቁጥራቸው ፡ ከታላላቁ ፡ መምህራን ፡ ጋር ፡ ነው ፤ በቅኔ ፡ ግን ፡ ቁጥራቸው ፡ ከቅኔው ፡ ፈጣሪ ፡ ከተዋነይ ፡ ጋር ፡ ነው ።

በዛብህ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ የዘረፉትን ፡ ሁለት ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ ቅኔ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ ብሎ ፡ ጀማሪ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ በሶስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለመዝረፍ ፡ የሚችል ፡ መስሎት ፡ የነበረው ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ ዘንድ ፡ ለመቀኘት ፡ ብቻ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ አምኖ ፡ ዋሸራ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ያጠፋውን ፡ ጊዜ ፡ በከንቱ ፡ እንደጠፋ ፡ ቆጥሮ ፡ እያዘነ ፡ ከአስተናጋጆቹ ፡ ጋር ፡ ወደጎጆዋቸው ፡ ተመለሰ ። ያስተናገዱት ፡ ተማሪዎች ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ ሁሉም ፡ ጀማሪዎች ፡ ቢሆኑ ፡ ያንለት ፡ የተዘረፉትን ፡ ቅኔዎች ፡ በመፍታት ፡ እንደሚበልጡት ፡ አምኖ ፡ ባፈታቱ ፡ ወይም ፡ በታሪኩ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ መነጋገር ፡ ወይም ፡ መከራከር ፡ አልፈቀደም ። እንደ ፡ ተመለሰ ፡ ደከሞኛል ፡ ብሎ ፡ ተኛ ። ነገር ፡ ግን ፡ እውቆ ፡ የተኛ ፡ መስሎ ፡ ሌሎቹ ፡ የተዘረፈላቸውን ፡ ቅኔ ፡ አንድባንድ ፡ እያነበቡ ፡ ሲፈቱና ፡ ታሪኩንም ፡ ሲተርኩ ፡ ሲሰማ ፡ አመሸ ። አስተናጋጆቹ ፡ ከተኙ ፡ እንኳዋ ፡ በሁዋላ ፡ ቅኔ ፡ አውቃለሁ ፡ መስሎት ፡ ተቀኝቻለሁ ፡ ብሎ ፡ ያወራውን ፡ የሚያርምበት ፡ መንገድ ፡ ሲፈልግ ፡ እንቅልፍ ፡ እጥቶ ፡ ብዙ ፡ ቆዬ ።

## ምእራፍ ፡ ፱ ፡

# ተክለ ፡ አልፍአ ፡

በበነጋው ፡ በዛብሀ ፡ ከአለቃ ፡ ከንፉ ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ ቢሞከር ፡ ጊዜያቸውን ፡ በሙሉ ፡ ቅኔ ፡ ለሚነግሩትና ፡ መጽ ሀፍ ፡ ለሚቀጽሉት ፡ ዝማሬ ፡ መዋሲትም ፡ ለሚያሄዱት ፡ መድበው ፡ ሰጥተው ፡ ስለነበረና ፡ እንዲሁም ፡ ሜታ ፡ ዘረ ፋው ፡ የሳቸው ፡ ስለነበረ ፡ ሳይመች ፡ ቀርቶ ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ እንዲገናኝ ፡ ተቀጠረ ። በቀጠሮው ፡ ከመምህራት ፡ እንዱ፡ እዩመራው ፡ አለቃ ፡ ከንፉ ፡ ወዳሉበት ፡ ፎቅ ፡ ፊትና ፡ ሁዋላ፡ ሆነው ፡ በዚያ ፡ የተሰራበት ፡ ዘመን ፡ በተረሳ ፡ አሮጌ ፡ መሰ ላል ፡ ሲወጡ ፡ የጨኸቱ ፡ ብዛት ፡ እንኩዋን ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ካጥር ፡ ውጭ ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ ከእንቅልፍ ፡ ያነቃ ፡ ነበር ። መሰ ላሉን ፡ ወጥተው ፡ እንዷት ፡ ትንሽ ፡ ጉዋዳ ፡ በር ፡ ሲደርሱ ፡ መሪው ፡ ወደሁዋላ ፡ ቀረና ፡ በዛብሀን ፡ ወደውስጥ ፡ ገፍቶት ፡ ተመለሰ ። ጉዋዳዋ ፡ ከዳር ፡ እዳር ፡ የፍዬል ፡ ቆዳዎች ፡ ግትም ፡ ብለው ፡ ተነጥፈውባታል ። በእንደኛው ፡ ማእዘን ፡ አለቃ ፡ ከንፉ ፡ ወፍራም ፡ ነጭ ፡ ጋቢ ፡ ለብሰው ፡ ነጭ ፡ ጭራቸውን ፡ ይዘው ፡ እፊታቸው ፡ በአትሮንስ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ መጽ ሀፍ ፡ ዘርግተው ፡ ተቀምጠው ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ።

በዛብህ ፡ ገብቶ ፡ ቆሞ ፡ አለቃ ፡ ከንፉ ፡ ሳያዩት ፡ መጽ ሀፋቸውን ፡ እየተመለከቱ ፡ ግንባራቸውን ፡ ቁጥር ፡ ፊታ ፡ እያ ደረጉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳቅ ፡ ሲሉ ፡ አዩና ፡ እሱም ፡ ሳቅ ፡ መጣበት ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደምንም ፡ ሳቁን ፡ አግዶ ፡ ምን ፡ አይነት ፡ጉድ ፡ ናቸው ፡ እያለ ፡ ሲያስብ ፡ ብራና ፡ በሚገለብ ጡበት ፡ ጊዜ ፡ ቀና ፡ ቢሉ ፡ እፊታቸው ፡ ቆሞ ፡ አዩትና፡-

"ምን ፡ ትሻለህ ፡ ወንድም ?" አሉት ።

"ለትምህርት ፡ የመጣሁ ፡ እንግዳ ፡ ነኝ ፤ ለመገናኘት ፡ ዛሬ ፡ ቀጥረውሀል ፡ ብለውኝ ፡ ለዚሁ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ የመጣሁ"

"እየ ፡ የኔ ፡ ነገር ፡ እረስቼውኮ ፡ እለሁ ፡ ከዚህ ፡ መጽ

ሀና ፡ ጋር ፡ እዩ ተጫወትሁ ፡ ብዙ ፡ አቆምሁህ ? " አሉ ፡ አለቃ ፡ ከንፋ ።

" የለም ፡ የኔታ ፤ ብዙ ፡ አልቆምሁም ፡ "

" ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ከወዴትሳ ፡ መጣህ ?"

" አገሬ ፡ ማንኩሳ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ግን ፡ የመጣሁ ፡ ከደ ብረወርቅ ፡ ነው ። "

" ደብረወርቅሳ ፡ ለምን ፡ ሄድህ ?"

" መጽሀፍ ፡ ለመቀጸል ። "

" ቀናህሳ ?"

" እምን ፤ ህዲስና ፡ ብሉይ ፡ መጽሀፈ ፡ መነከሳት ፡ ቀጸ ልሁ ። "

"ማለፊያ ፤ ማለፊያ ፡ ቅኔሳ ፡ ወዴት ፡ ተቀኘህ ?"

" ዋሸራ ፡ "

"ከእቡይ ፡ ኑሬ ?"

" ከአለቃ ፡ ኑሬ ። "

"እምን ፡ እኛ ፡ እቡይ ፡ ኑሬ ፡ እንለዋለን ። "

" ለምን ?"

" የራሱን ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ የሌሎችን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ የሚገምት ፡ በመሆኑ ፡ ገና ፡ በተማሪ ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ የወጣለት ፡ ስም ፡ ነው ። "

"ኧረ ፡ ዛሬ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጠባይ ፡ የላቸውም ፡ "አለ ፡ በዛብህ ።

" ችግር ፡ ከመከረው ፡ በሁዋላ ፡ እይተኸውንጂ ፡ነው ።"

" እንዴት ፡ ያለ ፡ ችግር ?"

" ድሮ ፡ ከሌላ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ተቀኝተው ፡ የወጡት ፡ተማ ሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ወደሱ ፡ ሲሄዱ ፡ እንደገና ፡ ከጉባየቃና ፡ ጀምሩ ፡ እያለ ፡ ስላስቸገረ፡ መምህራኑ ፡ ሁሉ ፡ ተባብረን ፡ ከሱም ፡ የተ ቀኙት ፡ ተማሪዎች ፡ ወደኛ ፡ ሲመጡ ፡ ከጉባየቃና ፡ እንዲጀ ምሩ ፡ አደረግነ ፡ ስለዚህ ፡ ወደሱ ፡ የሚሄድ ፡ ተማሪ ፡ ጠፍቶ ፡ ብቻውን ፡ ቀረ ። አዩህ ? የሌሎችን ፡ ስም ፡ ለማበላሸት ፡ ያበ ከው ፡ ጭቃ ፡ ለራሱ ፡ ሆነ ። አሁን ፡ ግን ፡ እንደማያዛልቀው ፡ አውቆ ፡ ተመለሰ ፡ እኛም ፡ ማርነው ። "

“ ታዲያኮ ፡ ከሁለታችሁም ፡ ወገን ፡ ክብራችሁን ፡ ለመ ጠበቅ ፡ ባደረጋችሁት ፡ ውድድር ፡ መሀከል ፡ የተጎዱት ፡ ተማ ሪዎች ፡ ናቸው ። ” አለ ፡ በዛብህ ፡ እዬሳቀ ።

“ የተለመደ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ልጄ ፤ ሁለት ፡ ሀያላን ፡ ነገ ስታት ፡ የግል ፡ ክብራቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ የሚጎዳው ፡ ማን ፡ ነው ? ተከታዮቻቸው ፡ አይደሉም ?”

“ አዎን ። ”

“ ይሄም ፡ እንጂ ፡ እንደሱ ፡ ነው ። ”

በዛብህ ፡ እንደመሳቅ ፡ አለና ፡ ዝም ፡ አለ ። አለቃ ፡ ክንፉ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እንደቆዩ ፡

“ ምንሳ ፡ ለመማር ፡ ትሻለህ ?” አሉ ።

“ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ለመሆን ፡ ነው ፡ የምሻ ። ” አለ ፡ በዛብህ ።

“ መልካም ፡ መልካም ፤ እንግዲያስ ፡ በበኩልህ ፡ መጽ ሀፍ ፡ እንድታስቀጽል ፡ ወንበር ፡ ይሰጥሃል ፤ አንተም ፡ ተማ ተህ ፡ ቅኔህን ፡ ተማር ፤ ለመዝረፍ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደማይወ ስድብህ ፡ አምናለሁ ። ” አሉ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ። በዛብህ ፡ እጅ ነስቶ ፡ ወጣ ።

ከዚህ ፡ በሁዋላ ፡ መጽሀፉን ፡ እያስቀጸለ ፡ እሱም ፡ በበ ኩሉ ፡ ቅኔውን ፡ እየተማረ ፡ ተቀመጠ ። ተማሮቹ ፡ ማታ ፡ ማታ፡ ቁራሽ ፡ ለምነው ፡ ሲመለሱ ፡ እዋጥተው ፡ ቢያንስ ፡ የኩፌዳ ፡ ግማሽ ፡ ቁራሽ ፡ ይሰጡታል ፤ ይህም ፡ ንፍሮውና ፡ ቆሎው ፡ ሳይቆጠር ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ አንዱ ፡ ተማሪ ፡ የሰራለት ፡ የሰ ሌን ፡ ምንጣፍ ፡ አንድ ፡ አዋሌ ፡ ጨው ፡ ሁለተኛው ፡ ተማሪ ፡ የሰራለት ፡ የሰሌን ፡ ጥላ ፡ አዋሌ ፡ ከግማሽ ፡ ስለተሸጡ ፡ በሁ ለት ፡ አዋሌ ፡ ከግማሽ ፡ ተልባውን ፡ አሸምቶ ፡ እንጀራ ፡ በተ ልባውን ፡ እየተመገበ ፡ ልብሱን ፡ ተማሮቹ ፡ እያጠቡለት ፡ እግ ሩንም ፡ በየተራ ፡ ተማሮቹ ፡ እያጠቡት ፡ እንደ ፡ ጎጀ ፡ ለብ ቻው ፡ ይዞ ፡ በተማሪ ፡ ደረጃ ፡ ሲገመት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኑሮ ፡ ይኖር ፡ ጀመር ። በሶስት ፡ ወሩ ፡ ቅኔ ፡ መዝረፍ ፡ ቻለ ። ነገር ፡ ግን ፡ በመጀመርያ ፡ እንዳሰበው ፡ ቅኔ ፡ መዝረፍ ፡ እንደቻለ ፡ ወደአዲስ ፡ አበባ ፡ በመሄድ ፡ ፈንታ ፡ ጊማ ፡ እንደገና ፡ አንድ ፡

አመት ፡ ጨምር ፡ ቅኔውን ፡ ለማበርታት ፡ አሰበ ። በመሀከ
ሉም ፡ ተክለ ፡ አልፍአ ፡ ደረሰ ።

ተክለ ፡ አልፍአ ፡ በታህሳስ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ የሚውል ፡ የዲማ፡
አመትባል ፡ ነው ። ክብረበአሉን ፡ ለማየት ፡ ከቅርብና ፡ ከሩቅ ፡
የሚመጣው ፡ ህዝብ ፡ ቁጥሩ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ አይባልም።
የዋዜማው ፡ እለት ፡ ጥዋት ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ አስጠርተው ፡-

" ዛሬ ፡ ማታ ፡ ዋዜማ ፡ ነገ ፡ እጣነ ፡ ሞገር ፡ የምትቀኝ ፡
አንተ ፡ ነህና ፡ እንድታስብበት ፡ " አሉት ።

" ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ የቆዩ ፡ መምህራን ፡ እያሉ ፡ ይህን ፡
ክብር ፡ ትናንት ፡ መጥቼ ፡ ለኔ ፡ ሲሰጡኝ ፡ እንዳይቀየሙ ፡
ቀደም ፡ ብለው ፡ ከመጡት ፡ ላንዱ ፡ ቢሰጥ ፡ ይሻላል ፡ የኔታ ።"
አለ ፡ በዛብህ ።

"ተባረክ ፡ ልጄ ፡ ባለትህትና ፡ ነህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እዚህ ፡
ያሉት ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ በሁዋላ ፡ የመጡ ፡ ናቸው ፡ እንጂ፡
ሁሉም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አልመጡም ፤ ስለዚህ ፡ ላንዱ ፡ ብሰጠው፡
ሌሎቹ ፡ መቀየማቸው ፡ አይቀርም " አሉ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ እዬ
ሳቁ ።

"ሁሉንም ፡ የማያስቀይም ፡ መድሀኒት ፡ አለ ፡" አለ ፡ በዛብህ።

" ምን ? "

" እርስዎ ፡ ቢቀኙ ፡ "

" መልካም ፡ መድሀኒት ፡ እንጂ ፡ አገኘህ ! ግለፍያ ፡ መድ
ሀኒት ፤ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ከተቀኘሁ ፡ አንተ ፡ ትመራለህ ፡ "

" እሺ ፡ የኔታ ፡ " አለ ፡ በዛብህ ።

ማታ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ እንደልማዳቸው ፡ ዋዜማውን ፡ ዘር
ፈው ፡ ሲቀኙ ፡ በዛብህም ፡ ሲመራ ፡ ከቅኔው ፡ ይልቅ ፡ በበዛ
ብህ ፡ ድምጽ ፡ ማማር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተገረመ ። ካህን ፡ በካህን፡
አፍ ፡ ተመስገና ፡ የማያውቀውን ፡ ያንለት ፡ ካህናቱ ፡ ሳይቀሩ፡
በዛብህን ፡ አመሰገኑት ።

አገልግሎቱ ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደተለመደው ፡ ከውጭ ፡ የመ
ጡት ፡ ካህናትና ፡ በዲማም ፡ የሚኖሩ ፡ የሰው ፡ አገር ፡ ተማሮች፡
በዩቤቱ ፡ ሲመሩ ፡ በዛብህና ፡ ሌሎች ፡ ስድስት ፡ ካህናት ፡ ተማ
ሮችም ፡ ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ከሚባሉ ፡ ትልቅ ፡ መኳንን ፡

ቤት ፡ ተመሩ ።

እፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ የተጠራው ፡ ዘመድኖ ፡ አመት በአል ፡ የሰበሰበው ፡ እንግዳ ፡ በሰፊ ፡ አዳራሽ ፡ ግቶም ፡ ብሉ፡ ሞልቶ ፡ መብል ፡ መጠጡ ፡ በታላቅ ፡ ልግስና ፡ ሲሰጥ ፡ አመሸ። ከግብር ፡ በሁዋላ ፡ እንደገና ፡ መጠጥ ፡ እየተጠጣ ፡ ጎበዛዝት ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ዘፈን ፡ ጀመሩ ፡ ካህናቱም ፡ በበኩላቸው ፡ ሿሁሌተ ፡ ገንቦዎቻቸውን ፡ ይወርቡ ፡ ጀመር ። በመጀመርያ ፡ ሌሎች፡ ካህናት ፡ በዮተራ ፡ አውራጆች ፡ ሆነው ፡ በዛብህ ፡ ከተቀባዮቹ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ሲቀበል ፡ ቆዩ ። በሁዋላ ፡ እሱ ፡ ማውረድ ፡ ሲጀምር ፡ በአዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ጫጫታ ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ጸጥ ፡ እያለ ፡ ሄደ ፤ ይዘፍኑ ፡ የነበሩትም ፡ ጎበዛዝት ፡ ዝም፡ አሉና ፡ ሁሉም ፡ የካህናቱን ፡ ወረብ ፡ ይሰሙ ፡ ጀመር ።

“ ከድምጹ ፡ ግጥሙ ፡ ከግጥሙ ፡ ድምጹ ፡ እንዴት ፡ እግዚአብሄር ፡ አሙዋልቶ ፡ የሰጠው ፡ ነው ፡ አባካችሁ ? ” አሉ ፡ ወይዘር ፡ ጥሩአይነት ፡-የቤቱ ፡ እመቤት ። አንዱን ፡ ግጥም ፡ ጨርሶ ፡ ተቀባዮቹ ፡ በሚቀበሉበት ፡ ጊዜ ፡ አዳራሹን ፡ የሞላው፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ያጨበጭብ ፡ ነበር ።-

“ ዝ ፡ ጠላ ፡ ከመ ፡ ወይን ፡ ጣእሙ ፡
እስኩ ፡ ድግሙ ፡ ድግሙ ፤ እስኩ ፡ ድግሙ ፡
እምይቴ ፡ ጥሩአይነት ፡ እጅሽን ፡ ይባርከው ፡ መልሰ ፡
መልሰ ፡ ያደረግሽው ፡ ጠላ ፡ በማር ፡ ተለውሶ ።
ቁርጥማት ፡ አይንካው ፡ ጥሩየ ፡ እጅሽን ፡-
ይህን ፡ ጠላና ፡ ጠጅ ፡ ያደረገውን ፡
ይህን ፡ ጠላና ፡ ጠጅ ፡ የጠጣችሁ ፡ ሁሉ ፡
ጥሩአይነት ፡ ጥሩአይነት ፡ እጡብ ፡ ድንቅ ፡ በሉ።”

እያለ ፡ ሲያወርድ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ከባላቸው ፡ በስተግራ ፡ ቁጭ ፡ እንዳሉ ፡ ደስታቸው ፡ በዚያ ፡ ውበት ፡ በተሞላ ፡ ፊታቸው ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ ይነበብ ፡ ነበር ። ፊታውራሪ ፡ መሸሻም ፡ የምሽታቸውን ፡ ሁኔታ ፡ አዩና ፡ አጋፋሪውን ፡ ጠርተው፡ “ ካህናቱን ፡ እንዳይደክማችሁ ፡ አርፋችሁ ፡ ስትጠጡ ፡ ቆዩ ፡ በላቸው ፡ ” ብለው ፡ ነገሩት ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ሰው ፡ እብድ ፡ ይለኛል ፡ ብለው ፡ እንደምንም ፡ ምላሳቸ

ውን ፡ ባይጎርሱ ፡ " እኔን ፡ ብቻ ፡ ስላሞገሰ ፡ ቀንተው ፡ ነው ፡" ለማለት ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ አልቀራቸውም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደምንም ፡ ብለው ፡ ለጊዜው ፡ የፈላ ፡ ደማቸውን ፡ ለማብረድ ፡ ቻሉ ።

ካህናቱ ፡ በወረብ ፡ ብዛት ፡ የደረቀ ፡ ጉሮሮዋቸውን ፡ በጣፋጭ ፡ ጠጅ ፡ እስኪያለዝቡ ፡ ጎበዛዝት ፡ ይዘፍኑ ፡ ጀመር ። ከዚያም ፡ ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አሽከሮች ፡ መሀከል ፡ አቅራሪዎችና ፡ ፎካሪዎች ፡ እዩተነሱ ፡ ጌታቸው ፡ ያደረጉትንም ፡ ያላደረጉትንም ፡ የጀብዱ ፡ ስራ ፡ እየደረደሩ ፡ የራሳቸውንም ፡ እስከ መቃብር ፡ ድረስ ፡ ታማኝነት ፡ እያረጋገጡ ፡ ሲያቅራሩና ፡ ሲፎክሩ ፡ ቆይተው ፡ የሽልማት ፡ ተስፋ ፡ እየተቀበሉ ፡ ተቀመጡ ።

ከዚህ ፡ በሁዋላ ፡ ካህናቱ ፡ እንደገና ፡ ማህሌት ፡ ገንቦአቸውን ፡ ይወርቡ ፡ ጀመር ። በመጀመርያ ፡ ሁለት ፡ ተማሮች ፡ በተራ ፡ እንዳወረዱ ፡ በዛብህ ፡ ተቀበለና ፦

" በሜዳ ፡ በዳሞት ፡ በነማይ ፡ ስንሻ ፦
ዲማ ፡ ላይ ፡ ተገኘ ፡ ለድሆች ፡ መሸሻ ፡
ለራበው ፡ ለጠማው ፡ ለተቸገረው ፡
መሸሻ ፡ አንተን ፡ ሰጠው ፡ እግዚአብሄር ፡ ቸር ፡ ነው" ፡

ብሎ ፡ ገና ፡ ግጥሙን ፡ የሚቀጥል ፡ መሆኑ ፡ ወይም ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ማቆሙ ፡ ሳይታወቅ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ደስታው ፡ አላስችላቸው ፡ ብሎ ፡ ራሳቸው ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ ግምጃ ፡ ቤታቸውን ፡ ጠርተው ፡ " ንሳ ፡ ንሳ ፡ ይህን ፡ ደማም ፡ ተማሪ ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ሸልመህ ፡ አምጣልኝ ፡ " አሉ ። ወዲያው ፡ በዛብህ ፡ መርዱፋ ፡ ስሪ ፡ ባለዛፍ ፡ እጀጠባብና ፡ ቀጭን ፡ ጥበብ ፡ ኩታ ፡ ለብሶ ፡ መጣና ፡ የጌቶችንና ፡ የመይቴን ፡ ጉልበት ፡ ስሞ ፡ ወደ ቦታው ፡ ሲመለስ ፡ በዚያ ፡ ከነበሩት ፡ ብዙዎቹ "ይገባሃል ፡ ይገባሃል ፡ ለቀሚስና ፡ ለካባ ፡ ለጥንግ ፡ ድርብ ፡ ያብቃህ ፡ " እያሉ ፡ መረቁ ፤ ጉዋደኞቹ ፡ ብቻ ፡ ጠሉት ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ አፋቸውን ፡ እንኩዋን ፡ ለወረብ ፡ ለመጠጥም ፡ መክፈት ፡ አቃታቸው ፡ ወዲያውም ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ ስለነበረ ፡ ጌቶችና ፡ እመይቴ ፡ ተነስተው ፡ ወደልፍኛቸው ፡ ገቡ ።

# ምዕራፍ ፡ ፲ ፡

## ሰብለ ፡ ወንጌል ፡

በዛብህ ፡ በበአሉ ፡ ሳምንት ፡ ለፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ እጅግ ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ ሳይለይ ፡ ሰነበተ ። ከበአሉ ፡ ውጭ ፡ ወደተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ለመመለስ ፡ ሲሰናበት ፦

“ ግርግር ፡ ሆነና ፡ ለብቻ ፡ ተገናኝተን ፡ አላነጋገርሁህም ፡ አገርህ ፡ ወዴት ፡ ነው ? ” አሉት ፡ ፊታውራሪ ።

“ አገሬ ፡ ማንኩሳ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ” አለ ፡ በዛብህ ።

“ እዚህ ፡ አያሌ ፡ ለመቆየት ፡ ታስባለህ ? ”

“ እኔ ፡ አንድ ፡ አመት ፡ ለመቆየት ፡ አስባለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፈጻሚው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። ”

“ እዚህ ፡ በምትቆይበት ፡ ጊዜ ፡ ቤታችን ፡ ቤትህ ፡ ነው ፡ አትለየን ፡ እንዳትሰቀቅ ፡ እንኩዋን ፡ ላንተ ፡ ላንዱ ፡ ለብዙ ፡ እንሆናለን ። ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ረዥም ፡ ጢማቸውን ፡ በግራ ፡ እጃቸው ፡ ወደታች ፡ እየሳቡ ። በዛብህ ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ ስለሽልማቱና ፡ ስለመስተንግዶውም ፡ አመስግኖ ፡ ወደ ተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ለፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ ለወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ለቤተሰቡም ፡ በሙሉ ፡ ቤተኛ ፡ ሆነ ። ለምሳ ፡ ባይሆን ፡ ለራት ፡ ለራት ፡ ባይሆን ፡ ለምሳ ፡ ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ አይጠፋም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳይመጣ ፡ ውሎ ፡ ያደረ ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡ ወለዱት ፡ ልጅ ፡ ተጨንቀው ፡ እተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ድረስ ፡ ጠያቂ ፡ ይልኩ ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በባላባትነታቸው ፡ እጅግ ፡ የሚኩሩ ፡ መኮንን ፡ ነበሩ ። ከትግሬ ፡ ከሸዋ ፡ ከጎንደር ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ያላቸውን ፡ ዝምድና ፡ ቁጥር ፡ ብለው ፡ እንደውዳሴ ፡ ማርያም ፡ መድገም ፡ የጀመሩ ፡ እንደሆነ ፡ ሰሚ ፡ የሚሰለቸው ፡ አይመስላቸውም ። እሳቸው ፡ እንደሚተርኩት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በትግሬም ፡ ይሁን ፡ በሸዋ ፡ ወይም ፡ በጎንደር ፡ መንገስ ፡ ቢቀርባቸው ፡ እንኩዋ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቦታ ፡ ለሌላ ፡ መስጠቱን ፡

እንደ ፡ የግፍ ፡ ግፍ ፡ ይቆጥሩት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ በድል ፡ እንጂ ፡ በትግል ፡ የማይገኝ ፡ ነገር ! “ እኔ ፡ መሸሻ ፡ እኔ ፡ የደፋር ፡ ጌታ ፡ በዘር ፡ ይሁን ፡ በሙያ ፡ እንኩዋን፡ የሚበልጠኝ ፡ የሚተካከለኝ ፡ እንደሌለ ፡ ማንም ፡ ያውቃል ። ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ! ሰው ፡ በዘሩና ፡ በጋሻው ፡ የሚመረጥበት፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ እንሆ ፡ እንደኛ ፡ ያለን ፡ ሰዎች ፡ እዚህ ፡ በባላገር፡ ከገበሮችና ፡ ከበሮች ፡ ጋር ፡ ተሰማርተናል ! ” ብለው ፡ እንደ መቆጣት ፡ ሲሉ ፡ አሽቃባጮቻቸው ፡ “ ግዲለም ፡ ጌቶች ፡ ጊዜ ፡ ያልፋል ፡ እንዲሁ ፡ እንደሆን ፡ አንቀርም ። ” ይሉዋቸውና ፡ ወዲያው ፡ ይጽናናሉ ።

ዘር ፡ በመቁጠር ፡ ምሽታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነትም ፡ ከባላቸው ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ አይሰንፉም ፡ ነበር ። ፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ሰብለወንጌል ፡ የምትባል ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ነበረቻቸው ።

ሰብለወንጌል ፡ ሳትረዝም ፡ ሳታጥር ፡ ሳትቀጥን ፡ ሳትወፍር ፡ በመጠኑ ፡ የተሰራች ፡ ውበት ፡ ከደምግባት ፡ ተባብረው ፡ ያስጌጡዋት ፡ እጅግ ፡ ያማረባት ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ጠባይና ፡ ትሀትና ፡ በሰፊው ፡ የታደለች ፡ ስለነበረችና ፡ በባህርይ ፡ ትምክህት ፡ የምትጠላ ፡ ከወላጆቹዋ ፡ ፈጽማ ፡ የተለዩች ፡ ነበረች ።

ሰብለወንጌል ፡ በአስራ ፡ አራት ፡ አመትዋ ፡ በመኩዋንንት ፡ ልጆች ፡ ወግ ፡ ዳዊት ፡ ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ መልክ ፡ ማርያም ፡ መልክ ፡ ኢየሱስና ፡ መልክ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አወቀች ። ከወይዘሮ ፡ ጥሩአይነትም ፡ ኩራታቸውንና ፡ ግብዝነታቸውን ፡ ብቻ ፡ ለሳቸው ፡ ትታ ፡ የቤት ፡ ባልትናቸውንና ፡ ሌላ ፡ መልካም ፡ ሙያቸውን ፡ ሁሉ ፡ ጠንቅቃ ፡ ስለተማረች ፡ ይህ ፡ ይቀራታል ፡ የማትባል ፡ ሙሉ ፡ ነበረች ። ስለዚህ ፡ በዲማና ፡ ባካባቢው ፡ የሚያውቁዋት ፡ ወይም ፡ ወሬዋን ፡ የሰሙ ፡ መኩዋንንት ፡ ሁሉ ፡ ገና ፡ አስራ ፡ አንድ ፡ አመት ፡ ሲሆናት ፡ ጀምረው ፡ ልጆች ፡ የነበሩዋቸው ፡ ለልጆቻቸው ፡ ልጆች ፡ ያልነበሩዋቸው፡ ለዘመዶቻቸው ፡ ደጅ ፡ ይጠኑ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ወላጆቹዋ ፡ እንደሾህ ፡ አጥር ፡ ዙሪያዋን ፡ ከበው ፡ እየተከላከሉ ፡ ውበትዋ፡

የጠራቸው ፡ ጎበዛዝት ፡ ሁሉ ፡ ጎምዥተው ፡ ዳርዳር ፡ ሲዞሩ ፡ ያች ፡ ያማረች ፡ የጋመረች ፡ የገነት ፡ ፍሬ ፡ የመበያዋ ፡ ወራት ፡ አለፈ ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ ምሽታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ በዘር ፡ ያከለናል ፡ ይመስለናል ፡ የማይሉት ፡ ሰው ፡ ልጃቸውን ፡ ለጋብቻ ፡ ሲጠይቅ ፡ እንኳዋንስ ፡ ሊሰጡ ፡ መጠየቃቸውን ፡ እንደ ፡ ብርቱ ፡ ውርደት ፡ እዩቆጠሩት ፡ እጅግ ፡ ያዝኑ ፡ ነበር ።

" ወዩው ፡ ጉድ ! ጆሮ ፡ አልሰማም ፡ አይልምኮ ፡ እናንተ ? " ይላሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ከውጭ ፡ ሲገቡ ።

" ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ሰሙ ፡ ጌታየ ? " ይላሉ ፡ ባለቤታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ።

" ቀኛዝማች ፡ እገሌ ፡ ሰብለወንጌልን ፡ ለልጄ ፡ ለመነኝ ፡ "

" ቀኛዝማች ፡ እገሌ ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ ነው ? "

" አባቱን ፡ እንኳዋን ፡ እኔ ፡ እሱም ፡ አያውቀው ።"

" ትልቅ ፡ ድፍረት ! " ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ።

" ግራዝማች ፡ እገሌ ፡ ልጅህን ፡ ስጠኝ ፡ አለኝኮ ፡ ጥሩ ፡"

" የማን ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ጌታየ ?"

" አባቱ ፡ ሰው ፡ አይደለም ፡ ገበሬ ፡ ነው ። "

" ይህን ፡ ሳልሰማ ፡ በሞትሁ ! "

" ፊታውራሪ ፡ እገሌ ፡ ልጇን ፡ ለልጄ ፡ ለመነኝ ፡ "

" የማን ፡ ልጅ ፡ ነው ? "

" አባቱ ፡ መጫኛ ፡ ነካሽ ፡ ነጋዴ ፡ ነበር ። "

" ምነው ፡ ከምታሰድበን ፡ ባልተወለደች ። "

" ባላምባራስ ፡ እገሌ ፡ ልጅህን ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ አማላጅ ፡ ላከብኝኮ ፡ ሀ . . ሀ . . ሀ . ወይ ፡ ጊዜ ! "

" የማን ፡ ልጅ ፡ ነው ? "

" አባቱ ፡ ብዙ ፡ ላም ፡ የነበረው ፡ ባለጌ ፡ ባላገር ፡ ነበር ። እሱ ፡ ሲሞት ፡ ላሙን ፡ ሁሉ ፡ አውርሶት ፡ ሞተ ። አሁን ፡ እጉዋቱን ፡ በፋጋ ፡ እዩጠጣ ፡ ሆዱ ፡ ሲነፋ ፡ ጊዜ ፡ ከሰው ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ መስሎት ፡ ይሄዋ ፡ የኛን ፡ ልጅ ፡ ይለምን ፡ ጀመር ! "

"ይበለን ፤ እረ ፡ ይበለን ፡ ሲያንሰን ፡ ነው ፤ ሲያንሰን ፡

ነው ፤ ለቀን ፡ ሰው ፡ ወዳለበት ፡ እንዳንሄድ ፡ እንደታሰርን ፡ ሁሉ ፡ ይሁን ፡ አገር ፡ መልቀቅ ፡ አቅቶን ፡ የባላገር ፡ መጫወቻ ፡ ሆን ። " ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ እንባ ፡ እየተናነቃቸው ፡

" አይ ፡ ያንቺ ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ ወዳለበት ፡ የምትይ ፡ ዛሬ ፡ የሰው ፡ ምርት ፡ አልቆ ፡ ገርዱ ፡ በቀረበት ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ሰው ፡ አለ ? የትም ፡ ብትሄጂ ፡ ቢበዛ ፡ አባት ፡ እንጂ ፡ አያት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ይገኝ ፡ መሰለሽ ? "

" እንዴት ? "

" እንዴትማ ፡ እንደምታውቂው ፡ አንዱ ፡ እህሉን ፡ አንዱ ፡ ጥጡን ፡ አንዱ ፡ ቅቤውን ፡ አንዱ ፡ ቆዳውን ፡ ሸጦ ፡ ጉቦ ፡ እየ ሰጠ ፡ ባላምባራስ ፡ ግራዝማች ፡ ቀኛዝማች ፡ ፊታውራሪ ፡ ይባ ልና ፡ ልጁ ፡ የባላምባራስ ፡ እገሌ ፡ የግራዝማች ፡ እገሌ ፡ የቀኛ ዝማች ፡ እገሌ ፡ የፊታውራሪ ፡ እገሌ ፡ ልጅ ፡ ይባላል ። የሳውቅ ዮሽ ፡ የጨዋታ ፡ ቀኛዝማች ፡ ግራዝማች ! እዚህ ፡ እኛ ፡ ግቢ ፡ የነሰጠኝና ፡ የነአረሩ ፡ ልጆች ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀኛዝማች ፡ ግራ ዝማች ፡ እየተባባልን ፡ እንጫወት ፡ እንደሚሉት ፡ ያለ ፡ ነው ! ከአጥንትና ፡ ከደም ፡ ያልተወረሰ ፡ በጥጥና ፡ በቆዳ ፡ የተገዛ ፡ ፊታውራሪነት ፡ ቀኛዝማችነት ። ሆሆ ! ኧረ ፡ ምን ፡ ዘመን ፡ መጣብን ? ይሄውልሽ ፡ የነዚህ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ የኛን ፡ ልጅ ፡ ለማግባት ፡ የሚጠይቁ ! እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ልጆች ፡ እድሜ ፡ ለቆዳ ፡ እድሜ ፡ ለጥጥ ፡ አባቶቻቸው ፡ ግራዝማች ፡ ቀኛዝማች ፡ አንዳንዶችም ፡ እንደኛ ፡ ፊታውራሪ ፡ ተብለውላቸዋል ፤ አያት ፡ ግን ፡ የላቸውም ። ታዲያ ፡ ለነዚህ ፡ ልጅን ፡ ልስጥ ? የእሌኒን ፡ የገላውዴዎስን ፡ የሱስንዮስን ፡ ልጅ ፡ ለገበሬ ፡ ለነጋዴ ፡ ልስጥ ? እነሱ ፡ ቢያዩ ፡ ባይሰሙ ፡ አጥንታቸው ፡ አይከሰኝም ? አይወቅ ሰኝም ? " ይላሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በቁጣ ፡ ደማቸው ፡ ፈልቶ ፡ ራሳቸውን ፡ እየነቀነቁ ።

" እርስዎም ፡ ልስጥ ፡ ቢሉ ፡ እኔን ፡ መቃብር ፡ ሳይጫነኝ ፡ ልጄ ፡ አጥንተ ፡ ሰባራ ፡ አታገባም ! እንዲያውም ፡ እሳቸዋ ፡ አግብታ ፡ ዘር ፡ ከምታበላሽ ፡ የሚያከላት ፡ የሚመስላት ፡ አጥታ ፡ ሳታገባ ፡ ቀረች ፡ ብትባል ፡ ክብርዋን ፡ ይጨምረዋል ፡

እንጂ ፡ አይቀንሰውም ፡፡"

"እውነትሽ ፡ " ይላሉ ፡ ፊታውራሪ፡፡

ፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ እንደዚህ ፡ እዬተወያዩ ፡ "እውነትሽ ፡ እውነትህ ፡" ሲባባሉ ፡ ልጃቸው ፡ ሰብለወንጌል ፡ ሳታገባ ፡ ሀያ ፡ አራት ፡ አመት ፡ አለፋት፡፡ አስራ፡ ስድስት ፡ አመት ፡ እስኪሆናት ፡ ድረስ ፡ ጠያቂዋ ፡ አባት ፡ እና ትዋን ፡ እረፍት ፡ ከልክሎዋቸው ፡ ነበር፡፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ግን፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ እዬተረሳች ፡ ሄደች፡፡ አንዳንድ ፡ ጠያቂዎች፡ እንኩዋ ፡ አልፈው ፡ አልፈው ፡ ቢመጡ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እን ደሚደረገው ፡ ቆሞ ፡ ቀር ፡ ከሚባሉት ፡ ተቆጥራ ፡ በፈትነት፡ እንጂ ፡ በልጃገረድ ፡ ስራት ፡ ለማግባት ፡ የሚጠይቅ ፡ ጠፋ፡፡

ሰብለወንጌል ፡ ባል ፡ ሳታገባ ፡ ጊዜዋ ፡ በማለፉ ፡ የመን ደሩ ፡ ሰው ፡ ሽሙጥና ፡ ሀሜት ፡ በሄደችበት ፡ ሁሉ ፡ አንገት ዋን ፡ ቀና ፡ አድርጋ ፡ ሰው ፡ ለማየት ፡ ያስቅቃት ፡ ነበር፡፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከናትዋ ፡ ጋር ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቆማ ፡ ስታስቀድስ፡-

"እባክሽ + እባክሽ ፡ እይልኝ ፡ የጌቶችን ፡ ልጅ ፡ እናትዋ ንኮ ፡ አከለች፡፡" አለች ፡ ደብሪቱ ፡ የምትባለዋ ፡ ከመንደሩ፡ አሽሙዋጣጮች ፡ አንድዋ፡፡"

"ምን፡ እናትዋን ፡ አከለች ፡ ትያለሽ? ከናትዋ ፡ በለጠች ፡ በይ ፡ እንጂ! ዳሌዋንና ፡ ደረትዋን ፡ አታይም ፡ አስር ፡ የወለ ደች ፡ መሰላ ፡፡" አለች ፡ ጉዋደኛዋ ፡ ስንዱ፡፡

"እኒህ ፡ አባትዋ ፡ ምን ፡ ሊያደርጉዋት ፡ ነው ፡ አስረው፡ የሚያወፍሩዋት ፡ አርደው ፡ ይበሉዋት ፡ ይመስል ? ወዲያ፡ ላንዱ ፡ አይሰጡዋትም ፡ እንዴ?"

"አሁንማ ፡ ለማን ፡ ይሰጡዋት ፡ ጠያቂ ፡ ሲጠፋ? የጠየ ቂዋቻውን ፡ ሁሉ ፡ አታክሉንም ፤ አትመስሉንም ፤ እያሉ ፡ ሲያ ባርሩ ፡ ኖረው ፡ አሁን ፡ ጠያቂ ፡ አጡ፡፡"

"ኧረ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ጠይቀዋል ፡ አሉ?" አለች ፡ ደብሪቱ ፡ የሽሙጥ ፡ ሳቅ ፡ እየሳቀች፡፡

"የትኛው ፡ አሰጌ?"

"እኒህ ፡ የቢቸናው ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ፡፡"

"ምን ፡ ልጅ ፡ አላቸው?"

" ለራሳቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ልጅ ፡ አላቸው ። "

" ለራሳቸው ? ኧረ ፡ የዲግው ፡ አባቴ ! የልጅ ፡ ልጃቸው፡ አትሆንም ? "

" እንዲያውም ፡ ይገረምሽ ! በልጃገረድ ፡ ስም ፡ አላገባም ፡ ብለው ፡ ሳይፋረሱ ፡ አይቀርም ፡ ይባላል ! "

" ኧረ ፡ በተፋረሱ ፤ ምን ፡ በወጣት ፡ አንዲት ፡ ፍሬ ፡ ልጅ፡ ሞት ፡ የረሳቸውን ፡ አርጌ ፡ ሰብሳቢ ፡ መሆንዋ ፤ አባትዋ ፡ ቤት፡ ብትቀመጥ ፡ ምን ፡ ይጎድልባታል ? "

"የምትኖርበትስ ፡ እያስመኘም ፤ ስቃይ ፡ ነው ፤ አሉ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ መቃብር ፡ ይመስል ፡ የሞተ ፡ ሽማግሌ ፡ ከመሸከም ፡ ያው ፡ የምትኖርበቱ ፡ ስቃይ ፡ ይሻላል ። "

" ኧረ ፡ እባክሽ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ ናት ፤ ምን ፡ ስቃይ ፡ ይኖርባታል ? "

" ስቃዩስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አይባልም ፡ አሉ ፤ ያች ፡ ያመቴ ፡ ልጅ ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ የትሁኔ ፡ ጉዋደኛ ፡ ናት ፤ እቤታችን ፡ በመጣች ፡ ቍጥር ፡ ስትነግረን ፡ ይገርመናል ! እኔማ ፡ የስዋን ፡ ታሪክ ፡ ስሰማ ፡ ደሀ ፡ አድርጎ ፡ የፈጠረኝን ፡ አምላክ ፡ አመሰግናለሁ ። "

" እንዴትኮ ? "

"እንዴትማ ---- እይውልሽ ፤ ካሽከሮች ፡ እንኩዋ ፡ ከሴቶች ፡ በቀር ፡ ወንዶች ፡ እስዋ ፡ በምትኖርበት ፡ ቤት ፡ አቅራቢያ ፡ የታዩ ፡ እንደሆነ ፡ እነሱም ፡ እስዋም ፡ ወዮላቸው ። አሁን ፡ እንደምታያት ፡ እንዲሁ ፡ እቤተክርስቲያንና ፡ እዘመዶችዋ ፡ ቤት ፡ ካልሆነ ፡ ወደሌላ ፡ ወጥታ ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ ለማየት፡ አይፈቀድላትም ፤ ለዚያውም ፡ ቢሆን ፡ እንደስረኛ ፡ ዘወትር ፡ በዘበኛ ፡ ተከባ ፡ ነው ። ከቤትዋ ፡ ወጥታ ፡ ባጥር ፡ ውስጥ ፡ እንኩዋ ፡ ስትዘዋወር ፡ አባትዋ ፡ ወይም ፡ እናትዋ ፡ ያዩዋት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማን ፡ ጠራሽ ? ማንን ፡ ትጠብቂያለሽ ? እያሉ ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ሳይቀር ፡ ያዋርዱዋታል ። ታዲያ ፡ እስዋ ፡ የእድሜ ፡ ጉዋደኞችዋ ፡ እንደልባቸው ፡ ሲሆኑ ፡ እያዩች ፡ አትበላ ፡ አትጠጣ፡ ዘወትር ፡ ማልቀስ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ኧረ ፡ ስንቱን ፡ ልንገርሽ ? ያቺን ፡ ያመቴን ፡ ልጅ ፡ አግኝተሻት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባወራችሽ!

እረ—እረ—እረ—እረ—ድህነት ፡ በስንት ፡ ጣሙ ፡ እቴ ! ” አለች ፡ ደብሪቱ ፡ እንደተቁረቆረች ፡ ሁሉ ፡ ራስዋን ፡ እያወዛወዘች ፡ የምታወራው ፡ ወሬ ፡ በሩቅ ፡ እንዳይሰማ ፡ ግራ ፡ እጅዋን፡ አፍዋ ፡ ፊት ፡ ገድባ ።

“ ለምን ፡ ብለው ፡ ነው ፡ እንዲት ፡ ልጃቸውን ፡ እንዲህ ፡ የሚያስቸግሩዋት ? ” አለች ፡ ሰንዱ ።

“ ክብራቸውን ፡ ለመጠበቅ ፤ የነገሌ ፡ ልጅ ፡ እንዲህ ፡ ሆነች ፡ እንዳይባል ፤ እንግዲያ ፡ ለስዋ ፡ አዝነው ፡ መሰለሽ ? ለስዋስ ፡ ቢያዝኑ ፡ የውብት ፡ አበባዋ ፡ ሳይረግፍ ፡ ላንዱ ፡ ጎበዝ ፡ በሰጡዋት ! ”

“ ለነሱ ፡ ክብር ፡ እስዋ ፡ ዋጋ ፡ ከፋይ ፡ ሆነች ፡ ማለት ፡ ነው ! ”

“ ታዲያስ ! ”

“ ግሩም ፡ ነው ! ለካ ፡ ከጌታ ፡ መወለድ ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ ሲመለከቱት ፡ የክብር ፡ ባርነት ፡ ነው ! ታውቂያለሽ ? እኔ ፡ የምፈራው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነው ። ” አለች ፡ ሰንዱ ።

“ ምን ? ”

“ በፈታውራሪ ፡ ፍላቴ ፡ የደረሰ ፡ በጌቶች ፡ እንዳይደርስባቸው ። ”

“ ማናቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ ፍላቴ ? ”

“ ፊታውራሪ ፡ ፍላቴማ ፡ የደብረ ፡ ወርቅ ፡ አንድ ፡ ታላቅ፡ መኩዋንንት ፡ ናቸው ። የመጀመርያ ፡ ባሌን ፡ አግብቼ ፡ ሁለት፡ አመት ፡ ደብረ ፡ ወርቅ ፡ በተቀመጥሁበት ፡ ጊዜ ፡ ቤታችን ፡ አግቢያቸው ፡ አጠገብ ፡ ስለነበረ ፡ እንኩዋን ፡ አልፎ ፡ ተርፎ ፡ ከተማው ፡ የሚሰማውን ፡ ጥዋት ፡ ማታ ፡ የሚላስ ፡ የሚቀመሰውን ፡ እናውቅ ፡ ነበር ። ሰራየቤት ፡ ያለበት ፡ ቤት ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ታውቂ ፡ የለም ? ለሰራየቤቶችኮ ፡ ጌቶቻቸው ፡ ያሉትንና ፡ ያደረጉትን ፡ ከሌሎች ፡ ቀድሞ ፡ ማውራት ፡ የባለሙዋልነትና ፡ የታላቅነት ፡ ምልክት ፡ ነው ! ታዲያ ፡ ይሄውልሽ ፡ ወደአይነተኛው ፡ ነገር ፡ እንመለስ ። እኒህ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፍላቴ፡ መልኩዋ ፡ ያማረ ፡ የደረሰች ፡ ልጅ ፡ ነበረቻቸው ። እንዲህ ፡

እንደጌቶች ፡ ያችን ፡ ልጅ ፡ እልፍኝ ፡ ዘግተው ፡ ማነን ፡ አዩሽ ፡ ማነን ፡ አነጋገርሽ ፡ እያሉ ፡ ሲያስጨንቁዋትና ፡ ሲያስለቅሱ ዋት ፡ በመጨረሻ ፡ ካገልጋያቸው ፡ አርግዛ ፡ ስለተገኘች ፡ እሱን፡ ገርፈው ፡ አስረው ፡ እሷን ፡ በስውር ፡ ሚጫ ፡ ዘመዶች ፡ እሱ ዋቸው ፡ ወደዚያ ፡ ሰደዷት ። ነገር ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ስራ ፡ በርቶ ፡ ከመሸሸግ ፡ አለመስራቱ ፡ ይቀላል ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ ነገሩ ፡ ወዲያው ፡ ተገለጸና ፡ የደብረ ፡ ወርቅ ፡ ህዝብ ፡ አመት ፡ ሙሉ ፡ ዘፈነበት ። ”

“ው ው ው ፡ ---- ወይ ፡ ውርደት ፡ ወይ ፡ ውርደት ፡ አባት ፡ እናትዋ ፡ እንዴት ፡ ያፍሩ ፡ አባክሽ ? እኔ ፡ በልጅትዋ ፡ አልፈርድም ፤ ራባት ፤ እንጀራ ፡ በወጥ ፡ ለመብላት ፡ ብትፈልግ፡ አጣች ፤ ስለዚህ ፡ በቅርብዋ ፡ ያገኘችውን ፡ ቆሎ ፡ ሰረቀች ፤ ሀሀ ሀሀ ” ብላ ፡ ደብሪቱ ፡ ስትስቅ ፡ ሰብለወንጌል ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ ሁለቱን ፡ አሽሙያጣጭ ፡ ሴቶች ፡ አይታ ፡ ተመለሰች ።

ደብሪቱና ፡ ስንዱ ፡ ደንግጠው ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እንደቆዩ ፡- “ ሰምታን ፡ ይሆን ፡ አባክሽ ? ” አለች ፡ ስንዱ ።

“ እንጃ ፡ ካልተያየትዋ ፡ ሳትሰማን ፡ የቀረች ፡ አይመስለ ኝም ፡ ” አለች ፡ ደብሪቱ ።

እውነትም ፡ ሰብለወንጌል ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ቅጻሴውን ፡ ለማዳመጥ ፡ ብትሞክር ፡ ጆሮዋችዋ ፡ አሽንፈው ፡ ስንዱና ፡ ደብ ሪቱ ፡ የሚያወሩትን ፡ ያዳምጡ ፡ ስለነበረ ፡ ሁለቱ ፡ ሴቶች ፡ ከተናገሩት ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ እንኩዋ ፡ አላመለጣትም ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚያሳፍር ፡ ነገርም ፡ እንደሌላው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከተደጋ ገመና ፡ ከተለመደ ፡ በሁዋላ ፡ ማሳፈሩ ፡ ስለሚቀር ፡ ይሆን ፤ የመሰለ ፡ ሽሙጥ ፡ በሰማች ፡ ቁጥር ፡ እንደመጀመርያው ፡ ጊዜ ፡ በማፈርና ፡ በሀሜተኞች ፡ ላይ ፡ ቂም ፡ በመያዝ ፡ ፈንታ ፡ የምታ ማርረው ፡ ወላጆችዋንና ፡ እድሉዋን ፡ ነበር ።

ያንለት ፡ ከቤተክርስቲያን ፡ ምልስ ፡ እንደተለመደው ፡ ሴት ፡ እልፍኝ ፡ ቁርስ ፡ ሲበላ ፡ ሰብለወንጌል ፡ ምንም ፡ እንኩዋ፡ የመብል ፡ ፍላጎት ፡ ባይኖራት ፡ አባት ፡ እናትዋ ፡ ምክናያት ፡ አግኝተው ፡ እንዳይሰድቡዋት ፡ ብቻ ፡ የበላች ፡ ለመምሰል ፡ እን ጀራውን ፡ እየቆረሰች ፡ ወደአፍዋ ፡ እያደረሰች ፡ ስትመልስ ፡

ቀይታ ፡ ማእዱ ፡ ከተነሳና ፡ አባትዋ ፡ ሊጠይቁዋቸው ፡ የመጡትን ፡ ሰዎች ፡ ለመቀበል ፡ ወደ ፡ ወንድ ፡ እልፍኝ ፡ ከሄዱ ፡ በሁዋላ ፡ እሰዋም ፡ ወደ ፡ እልፍኝዋ ፡ ሄዳ ፡ ልብሰዋን ፡ ለወጠችና ፡ ከልፍኝዋ ፡ ደጅ ፡ በባርጩማ ፡ ተቀምጣ ፡ ጸሀይ ፡ እዬሞቀች ፡ በአካባቢው ፡ የነበረውን ፡ ጸደይ ፡ ያሳመረውን ፡ ግቢ ፡ ትመለከት ፡ ጀመር ። ወራቱ ፡ ጸደይ ፡ ገና ፡ ጥቅምት ፡ መግባቱ ፡ ነበር ።

ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ግቢ ፡ በሚሉት ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ ለድር ቆሽ ፡ የሚያስጠብቁት ፡ ከሰርዶ ፡ ካከርማ ፡ ከጉድይና ፡ ከዋራት ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተደባልቆ ፡ ያደገው ፡ ሳር ፡ - ቀደም ፡ ብሎ ፡ የበቀለው ፡ አፍርቶ ፡ ዘግየት ፡ ብሎ ፡ የበቀለው ፡ ቢጫ ፡ ሰማያዊ ፡ ነጭና ፡ ቀይ ፡ አበባ ፡ አብቦ ፡ ሰብለወንጌል ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ዘቅዝቆ ፡ ሲመለከቱት ፡ ያን ፡ ሰፊ ፡ ግቢ ፡ ለማስጌጥ ፡ ከዳር ፡ እስከዳር ፡ የተዘረጋ ፡ አምሮ ፡ የተሰራ ፡ ዝጉርጉር ፡ ምንጣፍ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ጸሀይ ፡ እየሞቀ ፡ በሄደ ፡ መጠን ፡ በዚያ ፡ ሰፊ ፡ ግቢ ፡ የተነጠፈው ፡ ሳርና ፡ በቤቶች ፡ አካባቢ ፡ የተተከሉ ፡ የፍሬ ፡ አትክልት ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ባየር ፡ ይነዙት ፡ የነበረ ፡ ገንታዊ ፡ መአዛ ፡ ሽቱ ፡ በብዙው ፡ እንደተረፈረፈበት ፡ መዋኛ ፡ ከውስጡ ፡ መውጣት ፡ አያስመኝም ፡ ነበር ። በወፍራምና ፡ በቀጭን ፡ እስማምተው ፡ እዬዘመሩ ፡ ካበባ ፡ ወዳበባ ፡ ይዘዋወሩ ፡ የነበሩ ፡ ንቦችና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በፍሬ ፡ ተክሎች ፡ ዙሪያ ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ በሜዳው ፡ በተነጠፈው ፡ ያበባ ፡ ምንጣፍ ፡ ላይ ፡ በየጉዋዳቸው ፡ እዬዞሩ ፡ ይጨፍሩ ፡ የነበሩ ፡ በጸደይ ፡ ብቻ ፡ የሚመጡ ፡ ጌጠኛ ፡ ብራብሮዎች ፡ ሲታዩ ፡ ያ ፡ ከልምላሜና ፡ ከመአዛ ፡ ከውበትና ፡ ከለዛ ፡ ድርና ፡ ማግ ፡ የተሰራ ፡ ጸደይ ፡ ያ ፡ የክረምትን ፡ ቁርና ፡ የበጋን ፡ ሀሩር ፡ የማያሰማ ፡ ጸደይ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ የሚያልፍ ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ሳያልፍ ፡ እና ጊጥበት ፡ ሳያልፍ ፡ እንደሰትበት ፡ ሳያልፍ ፡ እንስራበት ፡ ብለው የሚጣደፉ ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ።

“ ወይ ፡ አንተ ፡ ግቢ ! ምነው ፡ እንዲህ ፡ እንዳበብህ ፡ እንደተዋብህ ፡ የምትኖር ፡ በሆንህ ! ምነው ፡ ይህ ፡ ውበትህ ፡ የበጋ ፡ ጸሀይ ፡ የማያደርቀው ፡ የክረምት ፡ ጭቃ ፡ የማያጨማልቀው ፡

በሆነ ! ብቻ ፡ ይህ ፡ ውበትህ ፡ አሁን ፡ ያልፋል ! ይህ ፡ አበባህ ፡
አሁን ፡ ይረግፋል ! ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በሁዋላ ፡ እነሆ ፡ መአዛህና ፡
ለዛህ ፡ ጠርቶዋቸው ፡ የሚጨፍሩት ፡ ብራብሮዎችና ፡ የሚዘም
ሩት ፡ ንቦች ፡ እዚህ ፡ አይኖሩም ! ሌላ ፡ ያበባና ፡ የተዋበ ፡ ቦታ ፡
ፍለጋ ፡ ይሄዳሉ ። ” አለች ፡ ሰብለወንጌል ፡ በዙሪያዋ ፡ የተዘረጋ
ውን ፡ በአበባና ፡ በፍሬ ፡ ያጌጠ ፡ ግቢና ፡ በሱ ፡ የሚደበቁትን ፡
ፍጥረት ፣ ዝም ፡ ብላ ፡ ስታስተውል ፡ ቆይታ ። ወዲያው ፡ በሰው
ህይወትና ፡ ከጊዜ ፡ ጋር ፡ በሚለዋወጡት ፡ ቡቃዮች ፡ መሀከል ፡
ያለው ፡ ተመሳሳይነት ፡ ታሰባት ፦ ቡቃያ ፡ አበባ ፡ ፍሬ ፡ ከዚያ ፡
መድረቅ ! ከዚያ ፡ መታጨድ ! ከዚያ ፡ ፍሬ ፡ የሌለው ፡ ገለባ ፡
ትቢያ ፡ ሆኖ ፡ መቅረት ! ፍሬ ፡ ያለው ፡ ብቻ ፡ በዘሩ ፡ ዘለአለም ፡
ህያው ፡ ሆኖ ፡ መኖር !

“ የሰው ፡ ህይወትም ፡ በእድሜው ፡ ደረጃ ፡ እንዲሁ ፡
መሆኑ ፡ ነው ! ህጻንነት ፡ ውርዝውና ፡ ሙሉ ፡ ሰውነት ፡ እር
ጅና ፡ ከዚያ ፡ ሞት ! ዘር ፡ ያለው ፡ ብቻ ፡ በዘሩ ፡ ህያው ፡ ሆኖ !
መኖር ! ዘር ፡ የሌለው ፡ ግን ፡ ልክ ፡ እንደማያፈራው ፡ ባርና ፡
ቡቃያ ፡ ትቢያ ፡ ወይም ፡ ጭቃ ፡ ሆኖ ፡ መቅረት ! ወይ ፡ ግሩም !
ሰውና ፡ ተክል ፡ እንዴት ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ! ” አለች ፡ ሰብለ
ወንጌል ፡ በአሳብዋ ። ከዚያ ፡ በተክል ፡ ህይወት ፡ ያበባው ፡
በሰው ፡ ህይወት ፡ የውርዝውናው ፡ ጊዜ ፡ ተመሳሳይነት ፡ ታሰ
ባት ። “ ተክል ፡ በልምላሜውና ፡ ባበባው ፡ ወራት ፡ እነዚህ ፡
እንዲህ ፡ በዙሪያው ፡ የሚጨፍሩት ፡ ብራብሮችና ፡ የሚዘምሩት
ንቦት ፡ ልምላሜው ፡ ሲጠወልግና ፡ አበባው ፡ ሲረግፍ ፡ ጥለ
ውት ፡ እንደሚጠፉ ፡ እንዲሁም ፡ ሰው ፡ የውርዝውናው ፡ ጊዜ ፡
ሲያልፍ ፡ ይከቡትና ፡ ያደንቁት ፡ የነበሩ ፡ ሁሉ ፡ ጥለውት ፡
ይጠፋሉ ! ” አለችና ፡ በተለይ ፡ እሰዋ ፡ ካስራ ፡ አራት ፡ እስከ ፡
አስራ ፡ ስድስት ፡ አመትዋ ፡ የነበረው ፡ አለሙዋ ፡ ትዝ ፡ አላት።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ታጅባ ፡ በወጣች ፡ ቁጥር ፡ ከከበባት ፡ የዘበኛ ፡
አጥር ፡ ውጭ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለማየትና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመታየት፡
ይጋፉና ፡ ይሽቀዳደሙ ፡ የነበሩ ፡ ወጣቶች ፡ ብዛት ፡ ትዝ ፡ አላት ።
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወጥታ ፡ ስትመለስ ፡ የነበራት ፡ ደስታና ፡ ኩራት ፡
ዛሬ ፡ ወጥታ ፡ ስትመለስ ፡ ከሚገጥማት ፡ አዘንና ፡ እፍረት ፡ ጋር ፡

እብረው ፡ ቆመው ፡ ታዩዋት፡፡ ከዚያ፡ ደብሪቱና፡ስንዱ፡ጥዋት፡ እቤተ፡ ክርስቲያን ፡ የተናገሩት ፡ ሁሉ ፡ እንድ ፡ባንድ ፡ መጣባት፡፡

" እኒህ ፡ እባትዋ፡ምን ፡ ሊያደርጉዋት ፡ ነው፡ እስረው፡ የሚያወፍሩዋት ፡ እርደው ፡ ይበሉዋት ፡ ይመስል ?"

"እሁንማ ፡ ለማን ፡ ይስጡዋት ፡ ጠያቂ ፡ ሲጠፉ ?"

" ፊታውራሪ ፡ እስጌ ፡ ጠይቀዋል ፡ እሉ :"

" የዲማው ፡ እባቴ ፡ የልጅ ፡ ልጃቸውን ? "

" ኧረ ፡ ለዚያውም ፡ በፊትነት ፡ ካልሆነ ፡ እላገባም ፡ ብለዋል፡ እሉ:"

" መቃብር ፡ ይመስል ፡ የሞቱ ፡ ሽማግሌ ፡ ከመሸከም፡ የምትኖርበት ፡ ስቃይ ፡ ይሻላታል፡፡ " የተባባሉትና ፡ የሽሙጥ፡ ሳቃቸው ፡ እንደገና ፡ ጎልቶ ፡ ተሰማት ፡ እሽሙዋጣጮቹም፡ እንደገና ፡ ባካል ፡ እፊትዋ ፡ ቆመው ፡ የሚላገዱባት ፡ መስለው፡ ታዩዋት ፡፡

ወዲያው ፡ ይህ ፡ ሽሙጥ ፡ ይህ ፡ ሳቅና ፡ ስላቅ ፡ ድንገት፡ ሳታስበው ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እዬተጠራቀመ ፡ በልብዋ፡ ታፍኖ ፡ ተደፍኖ ፡ የኖረውን ፡ ሽሙጥ ፡ ሳቅና ፡ ስላቅ ፡ እፍረ ትና ፡ ውርደት ፡ እቀጣጥሎ ፡ በውስጥዋ ፡ የቁዋያ ፡ እሳት ፡ እስ ነሳና ፡ እቃጠላት ፡ እነደዳት ፡፡ ሙሉ ፡ እካሉዋ ፡ እየቀለጠ፡ እንደ ፡ ገሀነም ፡ ባህር ፡ በውስጡዋ ፡ የሚፈላ ፡ መስላት ፡ ታፈ ነች ፡ ተጨነቀች ፡፡ በሁዋላ ፡ በውስጥዋ ፡ የፈላው ፡ ፍላት፡ እንደብርቱ ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ ማገጃውን ፡ እሽንፎ ፡ ሊፈነዳ፡ እንፋሎት ፡ ባፍና ፡ ባፍንጫዋ ፡ እየተትጎለጎለ ፡ የፈላ ፡ እንባ፡ ባይንዋ ፡ እየገነፈለ ፡ መገረፍና ፡ ያን ፡ ውበት ፡ ከደም ፡ ግባት፡ ያስጌጠውን ፡ ፊትዋን ፡ ማበላሸት ፡ ጀመረ፡፡ እንፋሎት ፡ የገረ ፋቸው ፡ እፍንጫዋና ፡ ከንፈሮችዋ ፡ እጎረቡ ፡ የፈላ እንባ፡ የገነፈለባቸው ፡ እይኖችዋ፡ እጎበጎቡ ፡ ጉንጮችዋ ፡ ከለዛና፡ ከደም ፡ ግባታቸው ፡ ታጠቡ፡፡ በውስጥዋ ፡ የሚፈላው፡ የገሀነም ባህር፡ ባናወጣትና፡ ባንቀጠቀጣት ፡ መጠን ፡ ከፍላቱ ፡ የሚነ ሳው፡ እንፋሎት፡ ባነቃትና ፡ ባስጨነቃት ፡ መጠን ፡ ከተሰቀ ለበት ፡ ገመድ ፡እንገቱን ፡ ነጻ ፡ ለማድረግ ፡ እንደሚጣጣር፡

ሰው ፡ አፍዋ ፡ ተበልጥጦ ፡ ጥርስዋ ፡ ገጦ ፡ አይንዋ ፡ ፈጦ ፡ ትን
ፋሽ ፡ አጥርዋት ፡ ከማእር ፡ ስትታገል ፡ ለተመለከታት ፡ ራብዋ ፡
ጣእር ፡ ትመስል ፡ ነበር ። ያች ፡ የውበት ፡ አራያ ፡ የሚሉዋት ፡
ሰብለወንጌል ፡ ለማስፈራሪያና ፡ ለማስጸየፊያ ፡ ያስቀመጡዋት ፡
ትመስል ፡ ነበር ። ይገርማል ! ለካስ ፡ ደም ፡ ግባትና ፡ ለዛ ፡ ስሜ
ትን ፡ የሚከተሉ ፡ የስሜት ፡ ጥላዎች ፡ ናቸው ! ደግነቱ ፡ የፍ
ጥረት ፡ ህግ ፡ በመፈራረቅ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።
ጨለማን ፡ ብርሃን ፡ ስቃይን ፡ እረፍት ፡ ሁከትን ፡ ጸጥታ ፡ አዘ
ንን ፡ ደስታ ፡ የማይከተሉ ፡ ቢሆኑ ፡ መኖር ፡ ባልተቻለ ። ክፉና ፡
በጎ ፡ ተፈራራቂዎች ፡ በመሆናቸውና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የከፋ ፡ ነገር፡
እድሜው ፡ አጭር ፡ በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ መኖር ፡ ይቻላል ። ሰብለ ፡
ወንጌል ፡ በውስጥዋ ፡ በተነሳው ፡ የቁዋያ ፡ እሳት ፡ ስትቃጠል ፡
ውስጠ ፡ አካሉዋ ፡ እየቀለጠ ፡ በፈጠረው ፡ የገሀነም ፡ ባህር ፡
ስትቀቀል ፡ በውስጥዋ ፡ በፈነዳው ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ ስትንቀጠ
ቀጥ ፡ ስትናወጥ ፡ ከቆየችው ፡ በላይ ፡ የምትቆይ ፡ ብትሆን ፡
ኖሮ ፡ ምናልባት ፡ የህይወትዋ ፡ መጨረሻ ፡ ሳይሆን ፡ ባልቀረ ፡
ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ህግ ፡ የሚያቃጥላት ፡
እሳት ፡ መብረድ ፡ የሚያንቃትና ፡ የሚያስጨንቃት ፡ ፍላት ፡
መቀዝቀዝ ፡ እስዋም ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ጸጥ ፡ ማለት ፡ ጀመረች።
ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በሁዋላ ፡ አሳብዋን ፡ መግዛትና ፡ ሰውነ
ትዋን ፡ ማወቅ ፡ ስትጀምር ፡ ባይኖችዋ ፡ የጎረፈው ፡ እንባ ፡
ባፍንጫዋ ፡ የወረደው ፡ ንፍጥና ፡ ባፍዋ ፡ የተዝረበረበው ፡ ለሀ
ጭ ፡ ደርቆ ፡ ስለጨመደዳት ፡ ከቤት ፡ መስታዋት ፡ አምጥታ ፡
ብትመለከት ፡ ፊትዋ ፡ የቡኮ ፡ እቃ ፡ እንደደፋ ፡ ውሻ ፡ ሊጥ ፡
የተበከለ ፡ መስሎ ፡ አገኘችው ። ከዚያ ፡ እንዲያ ፡ እንዳይሆነች ፡
እናትዋ ፡ ወይም ፡ አባትዋ ፡ ደርሰው ፡ ቢያዩዋት ፡ የሚመጣባት፡
መአት ፡ ታሰባትና ፡ ቶሎ ፡ ውሃ ፡ አምጥታ ፡ ነጠላዋን ፡ እየነከ
ረች ፡ ፊትዋን ፡ ደህና ፡ አድርጋ ፡ ጠራረገች ። የአይንዋና ፡ የከ
ንፈርዋ ፡ እብጠት ፡ ብቻ ፡ ለጊዜው ፡ ሊጠረግ ፡ አልተቻለም ።
ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ጸጥ ፡ አለች ፤ ከጥቂት ፡ ጊዜ በፊት ፡ በውስጥዋ፡
ይፈላ ፡ የነበረው ፡ የገሀነም ፡ ባህር ፡ ባይንዋ ፡ እዩገነፈለ፡ ሲጎ
ርፍ ፡ የፍረትና ፡ የውርደት ፡ ስሜትዋን ፡ የልብ ፡ ስቃይዋን ፡

እያጠበ ፡ እየጠረገ ፡ እንደወሰደላት ፡ ሁሉ ፡ ለጊዜው ፡ ሙሉ ፡ ሰላም ፡ ሙሉ ፡ ጸጥታ ፡ ሙሉ ፡ እረፍት ፡ አገኘች ። እንባ ፡ የን ደዴት ፡ የብስጭት ፡ ያዘን ፡ ማጠብያ ፡ በመሆኑ ፡ ለጊዜው ፡ ንዴ ትዋን ፡ ብስጭትዋን ፡ መታወኩዋን ፡ አስታገሰላት ፡ ለጊዜው ፡ ሰላም ፡ አገኘች ።

ትንሽ ፡ ጸጥ ፡ ብላ ፡ እንደቆዩች፡ አንድ ፡ ድምጽ ፡ በሩቅ ፡ እንደሚሰሙት ፡ የብዙ ፡ ንብ ፡ መዝሙር ፡ የሚዝገመገም ፡ ድምጽ ፡ የሰማች ፡ መሰላትና ፡ አንገትዋን ፡ ወደላይ ፡ ሳብ ፡ አድርጋ ፡ አንድ ፡ ጆሮዋን ፡ ድምጹን ፡ ወደሰማችበት ፡ ወገን ፡ ደቅና ፡ ብታዳምጥ ፡ ጠፋ ። የሰም ፡ ብላ ፡ አንገትዋን ፡ ስትሰበ ስብና ፡ ጆሮዋን ፡ ከደቀነችበት ፡ ስትመልስ ፡ ደሞ ፡ መጣና ፡ ልትይዘው ፡ ስትል ፡ ደሞ ፡ ጠፋ ። እንዲሁ ፡ እየሄደ ፡ ከሚመለ ሰው ፡ የአየር ፡ ማእበል ፡ ጋር ፡ ድምጹም ፡ እየሄደ ፡ ሲመጣ ፡ እየሄደ ፡ ሲመጣ ፡ እስዋም ፡ ጨብጣ ፡ ለማስቀረት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀኝ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ግራ ፡ ጆሮዋን ፡ እየደቀነች ፡ ሲያመል ጣት ፡ ቆዩና ፡ በሁዋላ ፡ መሄዱን ፡ ትቶ ፡ መምጣቱን ፡ ቀጠለ ። ሰብለወንጌል ፡ ያን ፡ ተንኮለኛ ፡ ድምጽ ፡ ከሚሸሽበት ፡ በጆ ሮዋ ፡ አባሯ ፡ ይዛ ፡ እንዳመጣችው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላት ። ያ ፡ ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ጠልሞ ፡ ከሰሎ ፡ የነበረ ፡ ፊትዋ ፡ እንደንጋት ፡ ሰማይ ፡ ወገግ ፡ አለ ። ያዘችው ፡ ማረከ ችው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ እስከታውቅ ፡ ቸኮለች ፡ እሱም ፡ ትንሽ፡ በትንሽ ፡ እየቀረበ ፡ እየጎላ ፡ መጣና ፡ በመጨረሻ ፡ እንዲር ፡ መሆ ኑን ፡ አወቀች ፡ የገብሬ ፡ እንዲር !

ገብሬ ፡ ከብቶችን ፡ ካፋፍ ፡ በታች ፡ ወደሳር ፡ አሰማርቶ ፡ እንዲሩን ፡ እየተጫወተ ፡ መመለሱ ፡ ነበር ። ገብሬ ፡ ዱላውን ፡ በግራ ፡ ብብቱ ፡ ሸጉጦ ፡ የሚቆምበት ፡ እንቅፋት ፡ ይሁን ፡ ጉድባ ፡ ሾህ ፡ ይሁን ፡ ጋሬጣ ፡ ሳይመለከት ፡ እንዲሩ ፡ ብቻ ፡ እየመራው ፡ እንዲሩን ፡ ተከትሎ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ። እጥ ሩን ፡ እንደገባ ፡ ወደ ፡ ማድ ፡ ቤት ፡ ሄደና ፡ እደጅ ፡ በተጋደ መው ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ጨዋታውን ፡ ቀጠለ ። ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ የገብሬን ፡ እንዲር ፡ እንዲህ ፡ በሩቁ ፡ በሰማች ፡ መጠን፡ ያፍዋ ፡ ምሬት ፡ እየጣፈጠ ፡ ጠቅላላ ፡ ስሜትዋ ፡ ካዘን ፡ ወደ ፡

ደስታ ፡ እየተለወጠ ፡ ሄደች ። የገባ ፡ ጎርፍ ፡ ያበላሸው ፡ ፊትዋ፡ እንደገና ፡ ውብትና ፡ ደም ፡ ግባት ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ መቀባት ፡ ጀመረ ፡ ደስ ፡ አላት ። ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የተቃጠለው ፡ የቆሰለው ፡ ልብዋ ፡ መለዘብ ፡ ጀመረ ፤ ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ያንገላታትን ፡ ውሽንፍር ፡ መርሳትና ፡ ላጭር ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የጉብሌ ፡ አንዷር ፡ በፈጠረላት ፡ ሰላማዊ ፡ አለም ፡ መኖር ፡ ጀመረች ።

የጉብሌ ፡ አንዷር ፡ ከአንዷሮቹ ፡ ሁሉ ፡ የተለዩ ፡ የሰዎችን ፡ ልብ ፡ ለመግዛት ፡ ለማዘዝ ፡ ለመናዘዝ ፡ ከፈጣሪ ፡ ሀይል ፡ የተሰጠው ፡ ይመስል ፡ ነበር ! የጉብሌ ፡ ትንፋሽ ፡ ከዚያች ፡ ሰበት አጥቅ ፡ ሸንበቆ ፡ በሰባቱ ፡ ቀዳዳዎቹዋ ፡ እየባረከ ፡ ሲያወጣው ፡ አለምን ፡ መጀመርያ ፡ እግዚአብሄር ፡ እንደፈጠራት ፡ ከጣር ፡ ከጋር ፡ ከረሀብ ፡ ከጥም ፡ ከእመም ፤ ከድካም ፡ ነጻ ፡ አስመስሎ ፡ ለማሳዬት ፡ አለምን ፡ የሰላም ፡ የደስታ ፡ የፍቅር ፡ የትዝታ ፡ ቦታ ፡ አስመስሎ ፡ ለማሳዬት ፡ ከፈጣሪ ፡ ሀይል ፡ የተሰጠው ፡ ይመስል ፡ ነበር ! የጉብሌ ፡ አንዷር ፡ ለደካሞች ፡ ብርታትን ፡ ለፈሪዎች ፡ ድፍረትን ፡ ለሀዘናን ፡ መጽናናትን ፡ ለሀሙማን ፡ መድሀኒትን ፡ ለመስጠት ፡ የሰዎችን ፡ ልብ ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ከከፋት ፡ ከተንኮል ፡ ነጻ ፡ አድርጎ ፡ ሰውን ፡ የመላእክት ፡ ጉዋደኛ ፡ ማህበርተኛ ፡ አስመስሎ ፡ ለማሳዬት ፡ ሀይል ፡ የተሰጠው፡ ይመስል ፡ ነበር ! ምነው ፡ የጉብሌ ፡ አንዷር ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ በሰዎች ፡ ልብ ፡ ይገዛው ፡ የነበረ ፡ ግዛት ፡ ለሁልጊዜ ፡ በሆነ ! ምነው ፡ የጉብሌ ፡ አንዷር ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ይፈጥረው ፡ የነበረ ፡ አለም ፡ ለሁልጊዜ ፡ በሆነ !

ጉብሌ ፡ ሲመጣ ፡ ይጫወት ፡ የነበረውን ፡ ዜማ ፡ ቀጥሎ ፡ ሲጫወት ፡ ሰብለወንጌል ፡ በሩቁ ፡ እየሰማች ፡ በደስታ ፡ ባህር ፡ ስትዋኝ ፡ ያመቴ ፡ ልጅ ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ ከማድ ፡ ቤት ፡ ወጥታ ፡ እጉብሌ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አንድ ፡ ደንጋይ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠችና ፡ መናገር ፡ ጀመረች ። ድምጽዋ ፡ ይሰማል ፡ የምትናገረው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ማድ ፡ ቤቱ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ከነበረችበት ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ስለነበረ ፡ ለይታ ፡ ለማወቅ ፡ አልቻለችም ። ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ጉብሌ ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ የምትናገረ

ውን ፡ እንዳልሰማ ፡ ዜማውን ፡ ሳይለውጥ ፡ ጨዋታውን ፡ ቀጠለ ። በሁዋላ ፡ አቋርጦና ፡ የተቀመጠበትን ፡ ግንድ ፡ በግራ ፡ ጎኑ ፡ በክርኑ ፡ በጥፊ ፡ እየመታ ፡ እሱም ፡ ይናገር ፡ ጀመር ። ጥቂት ፡ ክርክር ፡ የሚመስል ፡ ንግግር ፡ ከተለዋወጡ ፡ በሁዋላ ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ ከደንጋዩ ፡ ተነስታ ፡ በገብሬ ፡ ግራ ፡ ጎን ፡ እግንዱ ፡ ላይ ፡ ስትቀመጥ ፡ ከርክሩ ፡ “ እጠገቤ ፡ ተቀመጭ ፡- አልቀመጥም ፡ ” በማለት ፡ እንደነበረ ፡ ሰብለወን ጌል ፡ ገመተች ።

ሀብትሽ ፡ ይሥር ፡ በግራ ፡ ጎኑ ፡ ተቀምጣ ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ እንደወደቀባት ፡ ሀጻን ፡ ራስዋን ፡ እትከሻው ፡ ላይ ፡ ዘን በል ፡ ስታደርግ ፡ ገብሬ ፡ የጨዋታውን ፡ ዜማ ፡ ከንጉርጉር ፡ ወደዘፈን ፡ ለውጦ ፡

“ ሌሊቱ ፡ እያጠረ ፡ እንዲህ ፡ ካስቸገረ ፡”
“ እንቺናኔ ፡ እንተናኔ ፡”-

“ ሳንሞት ፡ እንቀበር ፡ ተኝተን ፡ እንድኖር ፡ ” <u>የሚባለ</u>

ውን ፡ በወራቱ ፡ ባላፍላ ፡ የነበረውን ፡ አዲስ ፡ ዘፈን ፡ እየተጫወተ ፡ ሁለቱም ፡ እንደተቀመጡ ፡ ይወዛወዙ ፡ ጀመር ። በሁዋላ፡ ገብሬ ፡ ጨዋታውን ፡ አቋርጦና ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲናገራት ፡ ሀብትሽ ፡ ራስዋን ፡ ከትከሻው ፡ አንስታ ፡ እንዳያመው ፡ ተጠን ቅቃ ፡ ጆሮባውን ፡ በጥፊ ፡ መታው ፡ ተነስታ ፡ ቆማ ፡ ትናገር ፡ ጀመር ። ገብሬ ፡ እንዲሩን ፡ አስቀምጦ ፡ ሊይዛት ፡ ሲነሳ ፡ ሮጠች ፡ እሱም ፡ ተከተላት ። ከዚያ ፡ እንደምትታይን ፡ ሚዳቋ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየዘለለች ፡ በሳሩ ፡ ውስጥ ፡ ስትሮጥ ፡ ሲከተላት ፡ ሳቁዋ ፡ እንደቤተክርስቲያን ፡ ቃጭል ፡ እየተንከለከለ ፡ ስትሮጥ ፡ ሲከተላች ፡ ደርሶ ፡ ያዘሁዋት ፡ ሲል ፡ ስታመልጠው፡- ወዳንዲት ፡ ቅርንጫፎዋን ፡ ሰፋ ፡ አድርጋ ፡ የተንዘረፈፈች ፡ የፍሬ ፡ ዛፍ ፡ ሲደርሱ ፡ የተወታተበ ፡ ሳር ፡ ጠልፎዋት ፡ ይሁን፡ ወይም ፡ ሆን ፡ ብላ ፡- ወደቀች ፤ እሱም ፡ ተከትሎዋት ፡ ወደቀ ፤ አልተነሱም ። ከላይ ፡ ዛፉ ፡ ከታች ፡ ሳሩ ፡ ከለሉዋቸው ።

ሰብለወንጌል ፡ ሀብትሽና ፡ ገብሬ ፡ እዩተሳሳቁ ፡ ሲሮጡ ፡ የሩጫቸውን ፡ ሁኔታ ፡ እያዩች ፡ ስትስቅ ፡ ነበር ። በሁዋላ ፡ ወድ

ቀው ፡ ሳይነሱ ፡ ሲቀሩ ፡ ያን ፡ የወደቁበትን ፡ ቦታ ፡ ገዘም ፡ ብላ ፡ ስትመለከት ፡ ቆየችና ፦ " እንደ ፡ ብራብሮዎች ፡ እንደንቦች ፡ ሁሉ ! ከብራችንን ፡ እስነካችሁ ፡ ብሎ ፡ የሚቆጣ ፡ የሚቀጣ ፡ የለባችሁ ! " አለች ። ያገልጋዮች ፡ ነጻነት ፡ የሰዋን ፡ የክብር ፡ ባርነት ፡ ሰላሳሰባት ፡ ሳቅዋ ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ወደቅርታ ፡ እየተለወጠ ፡ ሄደና ፡ ትካዙ ፡ ገባት ።

# ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡

## የፊታውራሪ ፡ አሰጌና ፡ የሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ጋብቻ ፡ መቅረት ፡

የፊታውራሪ ፡ አሰጌና ፡ የሰብለወንጌል ፡ ጋብቻ ፡ በመቅረቱ ፡ ዘመድ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ወላጆችዋና ፡ የቤተሰቡ ፡ የንስሀ ፡ አባት ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ፡ ብቻ ፡ አዘኑ ። ወላጆችዋ ፡ ከሀብቱ ፡ ጉዱ ፡ ጀምሮ ፡ ይፈልጉት ፡ የነበረ ፡ አይነት ፡ ጋብቻ ፡ በመቅረቱ፡ አዘኑ ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ፡ የሰብለወንጌል ፡ ወላጆች ፡ ስላዘኑ ፡ አዘኑ ። ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ የቢቸናን ፡ ክፍል ፡ ጠቅልለው ፡ የሚገዙ ፡ አባታቸው ፡ እንደሳቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ አያታቸውና ፡ ቅድመ ፡ አያታቸው ፡ ቀኛዝማቾች ፡ ስለነበሩ ፡ - በፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቁጥንቁጥ ፡ አባት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አያትና ፡ ቅድመ ፡ አያት ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ጭምር ፡ የነበሩዋቸው ፡ በቀዳና ፡ በቅቤ ፡ የተገዛ ፡ ሳይሆን ፡ ካጥንትና ፡ ከደም ፡ የተወረሰ ፡ ጉትንት ፡ የነበራቸው ፡ አጥንታቸውም ፡ ሆነ ፡ ደማቸው ፡ ሚዛን ፡ የሚደፋ ፡ ነበሩ ። ይህን ፡ አይነት ፡ ጋብቻ ፡ ነበር ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ለልጃቸው ፡ የተመኙት ! ይህ ፡ አይነት ፡ ጋብቻ ፡ ነበር ፡ ያለፉት ፡ አባቶቻቸውና ፡ እናቶቻቸው ፡ ነገስታት ፡ ከየመቃብራቸው ፡ ይባርኩት ፡ የነበረ ! ይህ ፡ አይነት ፡ ጋብቻ ፡ ነበር ፡ ባለፉት ፡ አባቶቻቸውና ፡ እናቶቻቸው ፡ በነገስታት ፡ አጥንት ፡ የማይወቀሱበት ፡ የማይከሰሱበት ፡ ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ቀረ ። ስለዚህ ፡ አዘኑ ።

ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ወጣት ፡ ሳሉ ፡ ሁለት ፡ ልጃገረዶች ፡ በተራ ፡ እየተሰረቁ ፡ አግብተው ፡ ፈትዋል ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ እያገቡ ፡ የፈቱዋቸውን ፡ ምሽቶች ፡ ሁሉ ፡ በፈትነት ፡ ሲያገቡ ፡ ቆይተው ፡ አሁን ፡ አምሳ ፡ አመት ፡ ሲያልፋቸው ፡ እንደገና ፡ በልጃገረድ ፡ ወግ ፡ ተሰርገው ፡ ማግባት ፡ ያገር ፡ መሳቂያ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ሰርጉን ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ የህዝቡን ፡ ገንዘብ ፡ ሊዘርፉ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ እንዲተወራ ፡ አድርገው ፡ ሀሜት ፡ ጠባቂና ፡ ባለቅርጥ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆች ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ስለመከሩዋቸው ፡ የሰብለ ፡ ወን

ጌሌ ፡ ዘመዶች ፡ ተለምነው ፡ እሺ ፡ ካሉና ፡ ነገር ፡ ካለቀ ፡ በሁዋላ ፡ በፈትነት ፡ ካልሆነ ፡ በልጃገረድ ፡ ወግ ፡ አላገባም ፡ አሉ ። ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በበኩላቸው ፡ ለጊዜው ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከታታይ ፡ የሌላት ፡ አንድዋ ፡ ልጃቸው ፡ አዱኛዋንና ፡ አበባዋን ፡ ሳታይ ፡ ለሳቸውም ፡ የወለደ ፡ አባት ፡ ወግ ፡ ማእርግ ፡ ሳይደርሳቸው ፡ በዲግና ፡ ባካባቢው ፡ ልጁን ፡ ለዳረ ፡ ሁሉ ፡ አድሜያቸውን ፡ ሙሉ ፡ ሲያፈሱት ፡ ከኖሩት ፡ ብር ፡ በከፊል ፡ እንኩዋ ፡ ሳታስመልስላቸው ፡ እንደሙት ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ እናት ፡ እንደሌላት ፡ እንዲሁ ፡ እጅዋን ፡ ተጎትታ ፡ ትሂድ ፡ መባሉን ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ አድርገው ፡ ቆጥረውት ፡ ሁለተኛ ፡ አታንሱብኝ ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ ተፋጋዮች ፡ ከሁለቱ ፡ አንዳቸውን ፡ ማሸነፍ ፡ ወይም ፡ መሀከለኛ ፡ መንገድ ፡ ማግኘት ፡ አቅቶዋቸው ፡ ስምምነቱ ፡ ፈረሰ ።

" እኔን ፡ ያናደደኝኮ ፡ " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የሳቸውና ፡ የባለቤታቸው ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ዘመዶች ፡ እቤታቸው ፡ ተሰብስበው ፡ ጠጅ ፡ እዬጠጡ ፡ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ሲነጋገሩ ፡ "እኔን ፡ ያናደደኝ ፡ ባማላጅ ፡ መላወሻ ፡ መተንፈሻ ፡ አሳጥቶ ፡ እኛን ፡ እሺ ፡ ካስኘ ፡ በሁዋላ ፡ አልፈልግም ፡ ባይ ፡ እሱ ፡ ሆኖ ፡ መታዬቱ ፡ ነውንጂ ፡ - ባልነቱ ፡ ለልጂ ፡ ቀረባት ፡ ወይም ፡ ዝምድናው ፡ ለኛ ፡ ቀረብን ፡ ብዬ ፡ አይደለም ። ዝምድናችንነንና ፡ ዘራችንን ፡ ሌሎች ፡ ይፈልጉታልንጂ ፡ እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ የሰው ፡ ዝምድናና ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ፍለጋ ፡ የምንሄድ ፡ ሰዎች ፡ አይደለንም ። ዘራችን ፡ ዝምድናችን ፡ በመብራት ፡ የሚፈለግ ፡ ነው ፡ አይደለም ፡ ይሆን ? ተሳስቼ ፡ ይሆን ? ኧ ሀ ሀ ሀ ሀ" ብለው ፡ የውሸት ፡ ሳቅ ፡ ለመሳቅ ፡ ሞከሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ የውሸት ፡ ሳቃቸው ፡ በንዴት ፡ ከተቁዋጠረ ፡ ፊታቸው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የታነቀ ፡ እንጂ ፡ የሳቁ ፡ አያስመስላቸውም ፡ ነበር ። " ሰው ፡ ከትልቅ ፡ መወለዱ ፡ የሚታወቀው ፡ የትልቅን ፡ ሰው ፡ ክብር ፡ ሲጠብቅ ፡ አይደለም ፡ እንዴ ? " አሉ ፡ ቀጠሉና ። " የዛሬውን ፡ ማየት ፡ አያስፈልግምኮ ! ዛሬ ፡ እኛን ፡ ጊዜ ፡ ቢጥለን ፡ የብዙ ነገስታት ፡ ደም ፡ በደም ፡ ስርዋ ፡ የሚፈስ ፡ የትልቅ ፡

ዘር ፡ ናትኮ ። ግዛታችን ፡ ከኛ ፡ ተወስዶ ፡ ለገበሬና ፡ ለነጋዴ ፡ በጥጥና ፡ በቆዳ ፡ ሲሸጥ ፡ ይችላል ፤ ካባቶቻችን ፡ ከነገስታቱ ፡ የወረስነው ፡ አጥንትና ፡ ደም ፡ ግን ፡ መሰረቱን ፡ የማይለቅ ፡ ከነፍስና ፡ ከስጋችን ፡ ጋር ፡ ጠብቆ ፡ የተሰራ ፡ ከግዛታችን ፡ ጋር ፡ ለገበሬና ፡ ለነጋዴ ፡ ሊሰጥ ፡ የማይችል ፡ ነው ። እንዴት ፡ የኛን ፡ ልጅ ፡ በልጃገረድ ፡ ስም ፡ አላገባም ፡ ብሎ ፡ ክብራችንን ፡ ያዋርድ? ” አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ ያለቁት ፡ አባቶቻቸውና ፡ እናቶቻቸው ፡ ነገስታቱ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ግፍ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ጥቃት ፡ ከየመቃብራቸው ፡ የሚያዩ ፡ የሚሰሙ ፡ ቢሆኑ ፡ ኖሮ ፡ ምን ፡ ይሉ ፡ ምን ፡ ያደርጉ ፡ እንደነበረ ፡ ትውስ ፡ ስላላቸው ፡ አንገታቸውን ፡ ትንሽ ፡ ቀልበስ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ለበስ ፡ አድርገው ፡ ራሳቸውን ፡ በቀስታ ፡ እየወዘወዙ ፡- “ ሙት ፡ አያይ ፡ ሙት ፡ አይሰማ ! ” አሉ ፡ - የፊታውራሪን ፡ አዘንና ፡ ትካዜ ፡ እዚያ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ዘመዶቻቸውና ፡ የምሽታቸው ፡ ዘመዶች ፡ ሲመለከቱ ፡ ሁሉም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆዩ ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ብቻ ፡ በመገረም ፡ ይመለከታቸው ፡ ነበር ።

“ መቸም ፡ ” አሉ ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንዳይቆጡዋቸው ፡ ሲፈሩ ፡ ሲቸሩ ፡ - በሁዋላ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ መስማታቸውን ፡ ሲያዩ ፡ ልባቸው ፡ እየሞላ ፡ እንደዘታቸው እየረታ ፡ “ መቸም ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ የሰሩት ፡ ባለጌዎች ፡ ካልሆኑ ፡ የጨዋ ፡ ልጆች ፡ የማይሰሩት ፡ የብልግና ፡ ስራ ፡ መሆኑን ፡ አገር ፡ አውቆት ፡ ጨርሶታል ። ስለዚህ ፡ የባለጌዎችን ፡ ርካሽና ፡ ጎስቁዋላ ፡ ስራ ፡ ንቆና ፡ ተጸይፎ ፡ መተው ፡ ነውንጂ ፡ መቆርቆርና ፡ ማዘን ፡ ለንዲህ ፡ ያሉት ፡ ባለጌ ፡ ሰው ፡ ዋጋ ፡ መስጠት ፡ ነው ። ይህንም ፡ ስል ፡ በብዙ ፡ አማላጅ ፡ አቢታችን ፡ ገብተው ፡ ሰድበውን ፡ አዋርደውን ፡ ለክብራችን ፡ የሚገባ ፡ ካሳ ፡ ሳይከሱን ፡ ይሂዱ ፡ ማለቴ ፡ አይደለም ፤ አፍንጫቸውን ፡ ይዘን ፡ አስጨንቀን ፡ እንዲከሱን ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። ማን ፡ እንደሆን ፡ እንዲያውቁት ፡ ማድረግ ፡ - - - ” ብለው ፡ ሊናገሩ ፡ ያሰቡትን ፡ ሳይጨርሱ ፡ “ አባክዎ ፡ ዝም ፡ ይበሉ ፡ ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደ፡፡ ሁልጊዜው ፡ የንስሀ ፡ አባታቸውን ፡

አሳብ ፡ በመናቅና ፡ በማጎጠጥ ፡ - “ በማያውቁት ፡ ነገር ፡ ገብ ተው ፡ አይዘባርቁ ፡ ዝም ፡ ይበሉ ። እኔ ፡ መሸሻ ፡ ልጄን፡ አላገባህልኝ ፡ ብዬ ፡ ካሰኔ ፡ ካሳ ፡ እንድብላ ፡ ነው ? የልጄን ፡ ክብር ፡ የኔንና ፡ ያባቶቼን ፡ የነገስታቱን ፡ ክብር ፡ በገንዘብ ፡ እንድሸጥ ፡ ነው ? ምነው ፡ እንደ ፡ ድሆች ፡ ምንተ ፡ ማርያም ፡ ብዬ ፡ ለምኜ ፡ አልበላም ? ደግሞ ፡ መቀርቀርና ፡ ማዘን ፡ አያስ ፈልግም ፡ ይሉኛል ! ባዝንስ ፡ በጊዜው ፡ በዘመኑ ፡ አዝን ፡ እን ደሆን ፡ እንጂ ፡ አሰኔ ፡ ልጄን ፡ አላገባልኝ ፡ ብዬ ፡ የማዝን ፡ ይመ ስልዎታል ? ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሰው ፡ ልክ ፡ አለማወቅ ፡ ነው ! ” አሉና ፡ ሁልጊዜ ፡ ሲቆጡ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ሲቃ ፡ እንደያ ዘው ፡ ፈረስ ፡ ሲያንከራፉ ፡ ከፍንጫቸው ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ያደም ፡ ስራቸው ፡ ከመቅጽበት ፡ ተነስቶ ፡ በግንባራቸው ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እንደፍዬል ፡ ቀንድ ፡ መንታ ፡ ሆኖ ፡ ተገተረ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ መሬት ፡ አፍዋን ፡ ከፍታ ፡ ብትውጣቸው ፡ በወ ደዱ ።

“ ምናልባት ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ አልሰሙኞቸው ፡ እንደ ሆንንጂ ፡ አባ ፡ ቁስ ፡ ሞገሴ ፡ የተናገሩትኮ ፡ ክፉ ፡ አልነበረም፡ ፊታውራሪ ! ለኔ ፡ እንደመሰለኝ ፡ - - - ” አሉና ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ እኅት ፡ ነገራቸውን ፡ ሲቀ ጥሉ ፡ ሲሉ ፡-

“ አዎ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ የልጅዎን ፡ ክብር ፡ ያንተንና ፡ ያባቶ ችህን ፡ የነገስታቱን ፡ ክብር ፡ በገንዘብ ፡ ሽጥ ፡ ሲሉኝ ፡ ክፉ ፡ አልተናገሩም ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የባላምባራስን ፡ ንግግር ፡ በቁጣ ፡ አቋርጠው ።

“ ታዲያ ፡ - - - እንዴት ፡ ብለው ፡ በመጠየቅ ፡ ፈንታ ፡ የሚቆጡ ፡ ከሆነ ፡ ሁላችንም ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ ወደዬቤታችን ፡ እንሂድ ፡ መናገርስ ፡ ምን ፡ ያስፈልጋል ! ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ በፈንታቸው ፡ ፊታውራሪን ፡ አቋርጠው ።

“ በልስቲ ፡ ተናገር ! በል ፡ ተናገር ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ ቁጣቸውን ፡ እንደመግታት ፡ ብለው ፡-

“ እዚህ ፡ ያለነው ፡ ሁላትንም ፡ ሽማግሌች ፡ ነን ፡ እንጂ ፡

ሀጳናት ፡ አይደለን ፡ ታዲያ ፡ በማያስቀጣው ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሀጳ ናት ፡ ተቆጥተን ፡ የጀመርነውን ፡ ነገር ፡ ዳር ፡ ስናወጣ ፡ ብንተ ወው ፡ ምን ፡ ያደርጋል ! ” አሉ ፡ ባላንባራስ ፡ ምትኩ ።

“ ተናገር ፡ አልሁህ ! እኔን ፡ መውቀስህን ፡ ተውና ፡ ተናገር ! ”አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የፊታውራሪ ፡ አስጌና ፡ የሰብለወንጌል ፡ ጋብቻ ፡ መቅረቱ ፡ ካስቆጫቸው ፡ ይልቅ ፡ መቆጨታቸው ፡ መታወቁ ፡ የበለጠ ፡ አስቆጭቶዋቸው ፡ ቁጭ ታቸውን ፡ ለመቆጣ ፡ ምራቃቸው ፡ አልበቃቸው ፡ ብሎ ፡ ጉንጫ ቸውን ፡ እየመጠጡ ። -

“ አባቴ ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ክብራችንን ፡ ስለነኩ ፡ ስለደፈሩን ፡ ይካሱን ፤ ይቅርታ ፡ ይለምኑን ፡ አሉ ፡ እንጂ ፡ እርስዎን ፡ ካሳ ፡ ይብሉ ፡ አላሉዎትም ። ካሳ ፡ መካስ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የተካሱትን ፡ ካሳ ፡ መብላት ፡ ሌላ ፡ ነው ። ክብሩ ፡ የተነካና ፡ የተደፈረ ፡ ወይም ፡ የተሰደበ ፡ ሰው ፡ ካልተ ካሰና ፡ ይቅርታ ፡ ካልተለመነ ፡ ስድቡና ፡ መደፈሩ ፡ ልብሱ ፡ ሆኖ ፡ ለሁልጊዜ ፡ መሰደቢያውና ፡ መደፈሪያው ፡ ሆኖ ፡ ይኖ ራል ፤ ስለዚህ ፡ ካሳና ፡ ይቅርታ ፡ ልመና ፡ የክብር ፡ መጠበቂያ ዎች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የክብር ፡ መሸጫዎች ፡ ወይም ፡ የክብር ዋጋዎች ፡ አይደሉም ፡ ይህንም ፡ እዚህ ፡ ካለነው ፡ ሁሉ ፡ የበ ለጠ ፡ እርስዎ ፡ ያውቁታል ። ” ሲሉ ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ግንባር ፡ ትንሽ ፡ ፈታ ፡ አለ ። “ እንደርስዎ ፡ ያለውን ፡ ታላቅ ፡ መኮንን ፡ ”አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ወዲያው ፡ ቀጠሉና ፡ እንደርስዎ፡ ያለውን ፡ ታላቅ ፤ የታላቅ ፡ ዘር ፡ በዚህ ፡ አሆሁዋን ፡ መድፈር ፡ ተደርጎ ፡ የማያውቅ ፤ የማይሆን ፡ ነው ፤ ደፍሮ ፡ ይቅርታ ፡ ሳይ ለምኑና ፡ ሳይክሱ ፡ መቅረት ፡ ግን ፡ ሊደረግ ፡ ሊሆን ፡ የማይታ ሰብ ፡ ነው ።”

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ታላቅ ፡ የታላቅ ፡ ዘር ፡ በመሆና ቸው ፡ እንደማያምኑና ፡ እንደ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ሰርክ፡ እንደ ማይደግሙት ፡ ሁሉ ፡ ከባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ አፍ ፡ ተደጋግሞ ፡ ሲሰሙት ፡ እንደ ፡ ግብዞች ፡ ሁሉ ፡ ብስጭታቸውን ፡ ረስተው ፡ ልባቸው ፡ በደስታ ፡ ተማረከና ፡ አይኖቻቸውን ፡ እንባ ፡ ሞላ ቸው ።

"ይህ ፡ ሁሉ ፡ መቸ ፡ ጠፋኝ ! ብቻ ፡ ልጄን ፡ አላገባም ፡ ስላለ ፡ ካሳ ፡ ቁረጡልኝ ፡ ብሎ ፡ ወደዳኛ ፡ መሄዱ ፡ ነውር ፡ ስለ መሰለኝ ፡ ነውንጂ ።" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ራሳቸውን ፡ እንደ ደፉ ።

"ታዲያ ፡ እንደተደፈሩ ፡ እንደተሰደቡ ፡ መቅረት ፡ ይሻላል ? በብዙ ፡ እማላጅ ፡ እንደርስዎ ፡ ባለ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ እንደርስዎ ፡ ያለ ፡ የትልቅ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ለምኖ ፡ እሺ ፡ ካሰኙ ፡ በሁዋላ ፡ መልሶ ፡ በማይበቃ ፡ ምክንያት ፡ አልፈልግም ፡ ማለትና ፡ መሸሽ ፡ ስድብ ፡ ነውኮ ፡" አሉ ፡ ባላምባራስ ። -

"ስድብነቱማ ፡ ድፍረት ፡ መሆኑ ፡ ምን ፡ አንድና ፡ ሁለት ፡ አለው ? አዋረደን ፤ ሰደበን ። ጊዜ ፡ ሰጥቶት ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ፊቱን ፡ ያዞረ ፡ ጊዜ ፡ እሱን ፡ አቅፎት ፡ በዘራ ፡ ያእቆብ ፡ በልብነ ፡ ድንግል ፡ በፋሲል ፡ ልጅ ፡ ፊቱን ፡ ያዞረ ፡ ጊዜ ፡ ስሉ ፡ ስቆለት ፡ እኛ ፡ አርሰን ፡ በላተኞች ፡ እሱ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ሆኖ ፡ ሰደበን ፡ አጠቃን ፡" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባዘነ ፡ ድምጽ ።

"ታዲያ ፡ ለዚህ ፡ መድሀኒቱ ፡ እዚህ ፡ ተቀምጦ ፡ ማዘን ፡ አይደለምኮ ! እንዳዋረዱን ፡ ተዋርደው ፡ ራሳቸውን ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ ይማሩኝ ፡ እንዲሉና ፡ እርስዎም ፡ ዘቅዝቀው ፡ እያዩ ፡ ምሬሀለሁ ፡ እንዲሉ ፡ ማድረግ ፡ ካሳ ፡ ተከሶ ፡ የተካሱትን ፡ ካሳ ፡ በመማር ፡ ታላቅ ፡ የታላቅ ፡ ዘር ፡ መሆንዎን ፡ ማሳየት ፡ ነው ፡ ለዚህ ፡ መድሀኒቱ ።" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡

"እሱንማ ፡ እሺ ፡ አልሁኮ ! ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ስለኔ ፡ ሆኖ ፡ ይነጋገር ፤ የዘመድ ፡ ዳኞችን ፡ ለመምረጥም ፡ ለማናቸውም ፡ ሁሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ስለኔ ፡ ይሁን ፡" አሉ ፡ ፊታውራሪ ። ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቅርብ ፡ ዘመድና ፡ ነገረ ፡ ፈጃቸው ፡ ናቸው ።

"በቃ ፡ እንግዲህ ፤ በዚህ ፡ አለቀ ፡" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ፊታውራሪን ፡ በማሸነፋቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ብስጭታቸውን ፡ በማስረሳታቸው ፡ ጭምር ፡ ቀኑ ፡ የሳቸው ፡ ስለሆነ ፡ ደስታቸው ፡ በፊታቸው ፡ ጎልቶ ፡ እየታየ ።

"ነገሩስ ፡ እንኩዋን ፡ አለቀ ፤ ብቻ ፡ ለኛ ፡ ሳታካፍሉን ፡ ሁለታችሁ ፡ መጨረሳችሁ ፡ ነውንጂ ፡" አሉ ፡ እዛዥ ፡ ደስታ ፡

ከፊታውራሪ ፡ ዘመዶች ፡ አንዱ ፡ እየሳቁ ።

"አትናገርም ፡ ኖረሃል ? ማን ፡ አፍህን ፡ ያዘው !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በበኩላቸው ፡ እየሳቁ ።

"እረ ፡ ለመሆኑ ፡" አለ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ፡ ሲስቁ ፡ ቆይተው ፡ ፊታቸው ፡ ፈገግ ፡ እንዳለ ።"መቸም ፡ ነገሩ ፡ አልቆሟል ፡ በሱ ፡ አሁን ፡ እንመለስበትም ፤ ብቻ ፡ እስቲ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ ፡ ባላምባራስ ፤ መቸ ፡ ከረመኔነት ፡ ወጥተህ ፤ ዲያቆነህ ፤ ቀስህ ፡ ጳጳስ ፡ ሆንህና ፡ ቄስ ፡ ለማሳመን ፡ በቃህ ፡ እባክህ ?"

"ምን ፡ ማለትዎ ፡ ነው ?" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ። የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ፡ ቀጥለው ፡ የሚናገሩት ፡ ሳያስቅ ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ በመገመት ፡ ለመሳቅ ፡ አፋቸውን ፡ ከፈት ፡ አድርገው ፡ ይመለከቷቸው ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ጋብቻ ፡ ዋና ፡ ሰባኪው ፡ ቄሱ ፡ ፊታውራሪ ፡ ነበረ ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ ጋብቻ ፡ የማታምን ፡ ዋና ፡ ተቃዋሚ ፡ አረመኔ ፡ ነበርህ ። አሁን ፡ ያ ፡ አንተ ፡ ትቃወመው ፡ የነበረ ፡ ጋብቻ ፡ ይቅር ፡ ሲባል ፡ ለምን ፡ ይቀራል ፡ ብለህ ፡ ፊታውራሪ ፡ እሱኑ ፡ በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ እንዲከሰስና ፡ ይቅርታ ፡ እንዲለምን ፡ ካሳ ፡ እንዲከስ ፡ ዋና ፡ ሰባኪ ፡ የነበረውን ፡ ፊታውራሪን ፡ አሳመንህ ፤ ስለዚህ ፡ ምንጊዜ ፡ ካለማመን ፡ ወደማመን ፡ ከዚያ ፡ ዋናውን ፡ ሰባኪ ፡ ወደማሳመን ፡ እንደደረስህ ፡ አልገባኝ ፡ ብሎ ፡ ነው ።" አሉ ፡ አዛዥ ።

"ምሳሌም ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ የሚሆን ፡ አልነበረም ፡ አይገጥምም ፡ አዛዥ ። ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ የማይሆነዎን ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ አባከኑት ።" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ እዬሳቁ ። የተሰበሰበውም ፡ አብረው ፡ ሳቀ ። "ጋብቻውን ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ እቃወማለሁ ። እኛ ፡ አፍርሰነው ፡ ካሳ ፡ እንኪዋ ፡ የሚቆረጥብን ፡ ቢሆን ፡ ብንከፍል ፡ እመርጣለሁ ። ብቻ ፡ አሁን ፡ የጋብቻው ፡ ጉዳይ ፡ ቀርቶ ፡ የምንነጋገርበት ፡ የክብር ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ፊታውራሪ ፡ እሱኑ ፡ ክብራችንን ፡ ስለነኩ ፡ ስለደፈሩን ፡ ስለሰደቡን ፤ እንዲሁ ፡ እንደደፈሩን ፡ ራሳቸውን ፡ ከኛ ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ እንዳደረጉ ፡ ይሄዱ ፡ ወይስ ፡ ጎትተን ፡ ራሳቸውን ፡ ከጉልበታችን ፡ በታች ፡

ዝቅ ፡ አድርገነው ፡ እንዳዋረዱን ፡ ተዋርደው ፡ ማሩኝ ፡ እንዲሉ ፡ እናድርጋቸው ? ይህ ፡ ነው ፡ ጉዳዩ ፤ ጋብቻው ፡ አይደለም ። ጋብቻቸውን ፡ አልፈቅደውም ፤ ድፍረታቸውንና ፡ ስድባቸውን ፡ ግን ፡ የበለጠ ፡ እጠላዋለሁ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ካሳ ፡ ክሰው ፡ ይቅርታ ፡ ይለምኑን ፡ የምለው ፤ ጋብቻቸውን ፡ ስለ ፡ ወደድሁ ፡ አይደለም ። ”

“ ቆዩኝ ፡ እባክህ ! ” አሉ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ። “ እስቲ ፡ ቆየኝ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ ። ደፍሮናል ፤ ሰድቦናልና ፡ ይቅርታ ፡ ይለምነን ፤ ይካሰን ፡ የምትለው ፡ ልጃችንን ፡ ለምኖ ፡ እኛን ፡ አሽ ፡ ካሰኘ ፡ በሁዋላ ፡ መልሶ ፡ አላገባም ፡ ስላለ ፡ አይደለም ? ”

“ ልክ ፡ ነው ። ”

“ መልካም ! እንግዲህ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ራስህን ፡ ከጉልበታችን ፡ በታች ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ ተዋርደህ ፡ ማሩኝ ፡ በለን ፤ ካሳ ፡ ክሰን ፡ ስንለው ፡ ይህን ፡ ከማድረግስ ፡ ልጃችሁን ፡ ማግባት ፡ ይሻለኛል ፡ ያለ ፡ እንደሆነሳ ፡ ያን ፡ የጠላኸውን ፡ ጋብቻ ፡ በካሳና ፡ በይቅርታ ፡ ልመና ፡ አስፈራርተህ ፡ አመጣኸው ፡ ማለት ፡ አይደለም ? ”

“ እኛ ፡ በፈለግነው ፡ መንገድ ፡ የሚያገባ ፡ ከሆነ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ እንፈልጋለን ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አቋርጠው ።

“ የለም ፡ እንደሉ ፡ አይደለም ፤ ይቅር ፡ ይበሉኝ ፡ ፊታውራሪ ፡ ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ፊታውራሪን ፡ በማስተባበላቸው ፡ ከፈገግታ ፡ ጋር ፡ ራሳቸውን ፡ ትንሽ ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፡ የይቅርታ ፡ ልመና ፡ ምልክት ፡ አሳይተው ፡ “ ይቅርታ ፡ ከምለምንና ፡ ከምክስ ፡ ልጃችሁን ፡ አገባለሁ ፡ እንደማይሉ ፡ ስለማውቅ ፡ ነው ። ”

“ እንዴት ፡ ታውቃለህ ? ”

“ እኒህ ፡ ጆሮዎቼ ፡ እንዲህ ፡ ታናናሾች ፡ ሆነው ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማሉ ! ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ሁለት ፡ ጆሮዎቻቸውን ፡ ይዘው እየሳቁ ።

" ምንኮ ፡ ነው ፡ የሰማሽው ? ጉራህን ፡ አቆይና ፡ የሰማሽውን ፡ ንገረን ።"

" ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ እንደ ፡ ፈለጉት ፡ ልጃችነን ፡ በፈትነት ፡ የማንሰጣቸው ፡ ከሆነ ፡ ካሳ ፡ ከሰው ፡ ይቅርታ ፡ ለምነው ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ የወሰኑ ፡ መሆናቸውን ፡ ከታመነ ፡ ሰው ፡ ሰምቻለሁ ።"

" ልጃችነን ፡ በፈትነት ፡ ካልሰጠነው ፡ ውሉን ፡ ማፍረሱን ፡ ሳንተ ፡ የነገረህን ፡ የታመነ ፡ ሰው ፡ ፍለጋ ፡ ሳንሄድ ፡ መላከተኞቹ ፡ ነግረውናል ፤ ይቅርታ ፡ የሚለምንና ፡ ካሳ ፡ የሚከስ ፡ መሆኑን ፡ ግን ፡ አልነገሩንም ።አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ካሳ ፡ እከሳለሁ ፡ ይቅርታ ፡ እለምናለሁ ፡ የሚል ፡ ከሆነ ፡ መላከተኞቹ ፡ ለምን ፡ አልነገሩን ?"

" ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ የወሰኑት ፡ ይህ ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ ፡ አልሁ ፡ እንጂ ፡ መላከተኞች ፡ ለምን ፡ እንዳልነገሩን ፡ አውቃለሁ ፡ አላልሁም ። ወዲያውም ፡ መላከተኞች ፡ የይቅርታ ፡ ልመናና ፡ የካሳ ፡ ነገር ፡ አለማንሳታቸው ፡ ለኛ ፡ የሚበጅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚከፋ ፡ አይደለም ።"

" እዩት ፡ እንግዲህ ፡ የሚሸሽበት ፡ ቀዳዳ ፡ ሲቆፍር ! " አሉ ፡ አዛዥ ፡ ባላምበራስ ፡ ምትኩ ፡ መንገዳቸውን ፡ ለመለወጥ ፡ ሲሞክሩ ፡ ስላዩ ፡ እንዳሸነፉ ፡ ቆጥረውት ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ።

" የምሸሽ ፡ አይምሰልዎ ፡ አዛዥ ! አልሸሽም ። የተወሰነው ፡ ውሳኔ ፡ አሁን ፡ ያልሁት ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ ። መላከተኞቹ ፡ ከተላኩት ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ተናግረው ፡ ሌላውን ፡ ያልተናገሩበትን ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ አላውቅም ። ብቻ ፡ የካሳውንና ፡ የይቅርታ ፡ ልመናውን ፡ ክፍል ፡ ምንም ፡ ቢላኩ ፡ አለመንገራቸው ፡ ለኛ ፡ በጀ ፡ ያልሁበትን ፡ ምክንያት ፡ ላስረዳ ።"

" ደግሞ ፡ ስትያዝ ፡ ይህን ፡ ጥለህ ፡ ሌላ ፡ መሸሻ ፡ ፍለጋ ፡ ሳትሄድ ፡ ውል ፡ እናድርግና ፡ ተናገር ! " አሉ ፡ አዛዥ ፡ እዩሳቄ ።

" ቀልዱን ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ እናቆየው ፡ አዛዥ ! አሁን ፡ የጀመርነውን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ እንጨርስ ። ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ካሳ ፡ ለመካሰና ፡ ይቅርታ ፡ ለመለመን ፡ የወሰኑትን ፡ መላክ

ተኞች ፡ እንደተሳከሩት ፡ ቢነግሩን ፡ ኖሮ ፡ ምንም ፡ በደለኛ ፡ ከመባል ፡ ጨርሰው ፡ ነጻ ፡ ሊወጡ ፡ ባይችሉ ፡ ባይሆን ፡ በደለ ኛነታቸውን ፡ ራሳቸው ፡ ተረድተው ፡ ሳይገደዱ ፡ እከሳለሁ ፤ ይቅርታ ፡ እለምናለሁ ፤ ማለታቸው ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ለመሆና ቸውና ፡ ባለጌ ፡ ላለመሆናቸው ፡ ምስክር ፡ ሆኖ ፡ ያስመሰግና ቸው ፡ ነበር ። ለኛም ፡ እንደ ፡ ተደፈሩ ፡ አልቀሩም ፡ አስገድ ደው ፡ ካሳ ፡ ተካሱ ፤ ይቅርታ ፡ ተለመኑ ፡ መባሉ ፡ ይቀርብን ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ሊያደርጉት ፡ አስቀድ መው ፡ የወሰኑትን ፡ በመላከተኞቻቸው ፡ ጉድለት ፡ አስገድደን ፡ አፍንጫቸውን ፡ ይዘን ፡ ያስደረግናቸው ፡ መስሎ ፡ ሊታይ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ነገሩ ፡ ጥሩ ፡ መንገድ ፡ ይዞዋል ።

"መቸም ፡ ለኛ ፡ አስገድደው ፡ ካሳ ፡ ተካሱ ፤ ይቅርታ ፡ ተለ መኑ ፡ መባሉ ፡ እንደሚሻል ፡ አይጠረጠርም ፡ ብቻ ፡ - - - " ብለው ፡ ቀኛዝማች ፡ እካሉ ፡ ሲናገሩ ፡ ያሰቡትን ፡ ሳይጨርሱ ፡

"እእ - - - - ንደሱ ፡ ማለቴ ፡ ነው !" አሉ ፡ ባላምባራስ ። ቀኛዝማች ፡ እካሉ ፡ በቃል ፡ ሌሎቹ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ከሳቸው ፡ ጋር ፡ መስማማታቸውን ፡ ሲገልጹ ፡ ስላዩ ፡ ጥርሳ ቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ፊታቸው ፡ ሁሉ ፡ በደስታ ፡ ስቆ ። "የም ለውን ፡ አሁን ፡ አስተዋሉ ፡ አዛዥ ?" አሉ ፡ ቀጠሉና ። "ለስም፡ እንደመሰለዎ ፡ ፊት ፡ እጠላው ፡ የነበረው ፡ ጋብቻ ፡ እንዳይፈ ርስ ፡ አይደለም ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌን ፡ በዳኛ ፡ አስገድደን ፡ ካሳ ፡ እንዲከሱንና ፡ ይቅርታ ፡ እንዲለምኑን ፡ እናድርጋቸው ፡ የምለው ። የምንጠላው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ፈርሶ ፡ ወዲያው ፡ ካሳ ፡ ተክሰንና ፡ ይቅርታ ፡ ተለምነን ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የምንለመነው ፡ ይቅርታና ፡ የምንካሰው ፡ ካሳ ፡ በውድ ፡ ሳይ ሆን ፡ በግድ ፡ ያስደረግነው ፡ ሆኖ ፡ እንዲታይ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ የፈ ለግሁት ። የጋብቻው ፡ ውል ፡ እንዲታደስ ፡ አይደለም ። ስለ ፡ ጋብቻው ፡ ያለኝ ፡ አስተያየትስ ፡ ቅድም ፡ እንዳልሁት ፡ ውሉን ፡ እኛ ፡ እፍርሰነው ፡ ከብቶችን ፡ ሁሉ ፡ ሽጠው ፡ ካሳ ፡ ብከፍል ፡ እመርጣለሁ ።"

" ለመሆኑ ፡ አንተ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌን ፡ ለምን ፡ እን ዲህ ፡ ጠላኸው ፡ እባክህ ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እዬሳቁ ።

“ ለሰብለ ፡ ባልነታቸውን ፡ እማችንታቸውን ፡ አልወድም ፡ እንጂ ፡ በሌላው ፡ ሁሉ ፡ አልጠላቸውም ! ”

“ እማችንቱስ ፡ ቢሆን ፡ ከጨዋ ፡ ልጅነቱ ፡ ሌላ ፡ መልካም ፡ ባለጋሻ ፡ ነው ! ለምን ፡ ይጠላል ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በትካዜ ፡ መልክ ።

“ ለመሆኑ ፡ የርሳቸውንና ፡ የሰብለን ፡ ጋብቻ ፡ ከርስምና ፡ ከጥሩየ ፡ በቀር ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ የተቀበለው ፡ ሰው ፡ ኖርዋል ? በናንተ ፡ ይቅርና ፡ በኛ ፡ በዘመዶች ፡ ያልፈረደ ፡ ሰው ፡ ባገር ፡ ይገኛል ? መቅረቱ ፡ በጀ ፡ ብቻ ። ” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፤ የፊታውራሪ ፡ ዘመድና ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ መልሱን ፡ ከባላምባራስ ፡ አፍ ፡ ነጥቀው ።

“ ለምን ? እባክህ ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

“ ስንቱን ፡ ልቁጠርልዎ ! ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በድሜ ፡ የሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አቻዋ ፡ አይደሉም ፤ መቸም ፡ አገር ፡ ጉድ ፡ ያለ ፡ በዚህ ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ - - - - - ” ብለው ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ የፊታውራሪ ፡ አሰኬ ፡ አምቻነት ፡ የማይወደድበትን ፡ ምክናያት ፡ ለመዘርዘር ፡ ሲቃጡ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ዘወር ፡ አደረጉ ። በርሳቸውና ፡ በወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ መሀከል ፡ የነበረው ፡ የእድሜ ፡ ልዩነት ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ስለነበረ ፡ የእድሜ ፡ ነገር ፡ ሲነሳ ፡ ወደሳቸውና ፡ ወደ ፡ ምሽታቸው ፡ የድሜ ፡ ልዩነት ፡ እንዳይመራ ፡ እዬፈሩ ፡ ሁልጊዜ ፡ መሸሽ ፡ ይወዳሉ ።

“ እባክዎ ፡ የድሜ ፡ ልዩነት ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ቁምነገር ፡ የለውም ።” አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ አቁዋርጠው ፡ የባላቸውን ፡ ሁኔታ ፡ ሳይመለከቱ ። “ የድሜ ፡ ልዩነት ፡ ቁምነገር ፡ ያለው ፡ አይመስልዎ ፡ በጌታዬና ፡ በኔ ፡ መሀከል ፡ የሀያ ፡ ሰባት ፡ አመት ፡ ልዩነት ፡ አለ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ልጅ ፡ እንዳንወልድና ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ዘመን ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ አብረን ፡ እንዳንኖር ፡ አልከለከለንም ። ”

“ አዎ ፤ የሀያ ፡ ሰባት ፡ አመት ፡ ልዩነት ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የፍዬል ፡ ቀንዶቻቸው ፡ ከመቅጽበት ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በግንባራቸው ፡ ተገትረው ፡ ሲቃ ፡ እንደያዘው ፤ ፈረስ ፡ እንኮ

ራቱና ። ምሽታቸው ፡ የፈሩትን ፡ ቁስላቸውን ፡ ስለነኩባቸው ፡ በጣም ፡ አሙዋቸው ፡ ተቆጡ ። " ቀድመሽ ፡ ያንችን ፡ እድሜ ፡ እወቂ ! የሰው ፡ እድሜ ፡ አውቃለሁ ፡ ብሎ ፡ የማያውቁትን ፡ ነገር ፡ ለማዋለድ ፡ ከመቸኮል ፡ የራስን ፡ እድሜ ፡ ማወቅ ፡ ነው ! እንዲያውከ ፡ የዲማውን ! በዚህ ፡ ብቻ ፡ አይምሰላችሁ ፤ በሌ ላውም ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ነገር ፡ ማዋላድ ፡ ነገር ፡ ማባዛት ፡ ትወዳለች ፤ ስራ ፡ ብላ ፡ ይዛዋለች ። ታዲያኮ ፡ ሀያ ፡ ሰባት ፡ አመት ፡ ትላለች ፡ እንጂ ፡ በመሀከላችን ፡ የሀያ ፡ አም ስት ፡ አመት ፡ ልዩነት ፡ መኖሩን ፡ እንኩዋ ፡ እንጃ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እድሜዎ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ያሉዋቸው ፡ እነቀኛዝ ማች ፡ አካሉ ፡ እንደሆኑ ፡ ሁሉ ፡ አይናቸውን ፡ ከምሽታቸው ፡ ወደነሱ ፡ አዞረው ፡ እየተመለከቱና ፡ ቁጣቸውን ፡ በውሸት ፡ ፈገግታ ፡ ለመጋረድ ፡ እየሞከሩ ። ከፊታውራሪ ፡ የታወቁ ፡ የቁጣ ፡ ምልክቶች ፡ አንዱ ፡ ያስቆጣቸውን ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ አለማ የት ፡ ነበር ።

" እሺ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፤ ሀያ ፡ አራትም ፡ ይሁን ፤ እኔኮ ፡ የድሜ ፡ ልዩነት ፡ ቁምነገር ፡ የለውም ፡ አልሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ---"

" እኮ ፤ ቀድሞ ፡ የራስን ፡ እድሜ ፡ ማወቅ ፡ ነው ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እየደጋገሙ ፡ የምሽታቸው ፡ እድሜያቸውን ፡ አለማወቅ ፡ ከርሳቸው ፡ እድሜ ፡ እንደሚቀንስላቸው ፡ ሁሉ ።

ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ የጨዋታ ፡ ሙቀት ፡ ስቦዋቸውና ፡ መላሳቸውን ፡ አድጠት ፡ የባላቸውን ፡ ቁስል ፡ ነክተው ፡ በማ ሳመማቸው ፡ አዝነው ፡ በለስላሳ ፡ ቃልም ፡ በለስላሳ ፡ ፈትና ፡ አስተያየትም ፡ የሻከረ ፡ ልባቸውን ፡ ለማለዘብና ፡ ቁጣቸውን ፡ ለማብረድ ፡ ሞክረው ፡ ነበር ። ብቻ ፡ የፊታውራሪ ፡ ፊት ፡ ወደ ርሳቸው ፡ አልዞር ፡ ስላለ ፡ አልሆንላቸውም ። ላጭር ፡ ጊዜ ፡ መናገር ፡ የሚደፍርም ፡ የሚባል ፡ ነገርም ፡ ጠፍቶ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ አዘነተኞች ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆዩ ።

በሁዋላ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ፡ የሞላ ፡ ብርሌያቸውን ፡ አንስ ተው ፡ እስኪጋመስ ፡ እንደቅድቀው ፡ ሲያስቀምጡ ፡ ተደርጎ ፡ የማያውቅ ፡ ነገር ፡ ያደረጉ ፡ ይመስል ፡ ሁሉም ፡ ተመለከቱዋ

ቸው ። ወዲያው ፡ የጠጡት ፡ ጠጅ ፡ የሚሉትን ፡ እንደገለጸላቸው ፡ ሁሉ ፡ "እእሺ ------ ቀኛዝማች ፤ የፊታውራሪ ፡ እሰጌ፡ አምቻነት ፡ የሚጠላበትን ፡ ምክንያት ፡ ልትነግረን ፡ ጀምረህ ፡ ነበር ፤ እንዱን ፡ ነግረኸናል ፤ በል ፡ ሌላውን ፡ ቀጥል ። " አሉ ፡ አዛዥ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉን ፡ ፈገግ ፡ ብለው ፡ እያዩ ። ያዛዥ ፡ ደስታ ፡ አላማ ፡ ያን ፡ በቤት ፡ ዘመድ ፡ ላይ ፡ ያንዣበበውን ፡ ከባድ ፡ የቅርታ ፡ ዝምታ ፡ ለማስወገድና ፡ የድሜ ፡ ልዩነት ፡ ሳይነሳ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አምጥቶ ፡ ቶሎ ፡ እንዲረሳ ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ያዛዥ ፡ አሳብ ፡ ሳይገባቸውና፡ እዚያ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ሁሉ ፡ መላስ ፡ በያፉ ፡ ውስጥ ፡ ዘግቶ ፡ የቆዩ ፡ የድሜ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ረስተው ፡ እንደገና ፡ ወደሱ ፡ ተመለሱ ።

አባ ፡ ሞገሴ ፡- ሰውን ፡ እውቀው ፡ የማያስቀይሙ ፡ ቂም ፡ የማይዙ ፡ ቅን ፡ ሳገልግሎታቸውና ፡ ለበጎ ፡ ስራቸው ፡ ዋር ፡ ድንበር ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ አክባሪ ፡ ከሰው ፡ መጣላት ፡ አጥብቀው ፡ ፈሪ ፡ ሳሉ ፡- ችኩልና ፡ ዘዴ ፡ በጭራሽ ፡ የማያውቁ ፡ ነበሩ ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ባህሪ ፡ እንዳላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ነገራቸውና ፡ መልካም ፡ ስራቸው ፡ የሚገባውን ፡ ዋጋ ፡ ሳያገኝ ፤ እሳቸው ፡ ከመከበርና ፡ ከመወደድ ፡ ይልቅ ፡ በዩሄዱበት ፡ እንደሸክም ፡ ተቆጥረው ፡ የሚኖሩ ፡ ነበሩ ።

" ቅድም ፡ ቀኛዝማች ፡ የፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ አምቻነት ፡ የሚጠላበት ፡ ምክናያት ፡ የድሜያቸው ፡ ትልቅነት ፡ ነው ፡ ስላሉት ። " ብለው ፡ ሲጀምሩ ፡ ሁሉም ፡ አይናቸውን ፡ አፈጠጡባቸው ። ፊታውራሪ ፡ ራሳቸውን ፡ ወደላይ ፡ አንጋጠው ፡ መውጫ ፡ ቀዳዳ ፡ እንደሚፈልጉ ፡ ሁሉ ፡ አይናቸው ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እያለ ፡ ጣራ ፡ ጣራውን ፡ ይመለከቱ ፡ ጀመር ፤ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ብቻ ፡ የሰዎቹን ፡ ሁኔታ ፡ እያዩ ፡ ድምጹን ፡ ሳያሰማ ፡ ይስቅ፡ ነበር ። " አምችነታቸው ፡ የሚጠላበት ፡ የድሜያቸው ፡ ትልቅ ፡ ነት ፡ ነው ፡ ስላሉት ፡- ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ወንድ ፡ ከድሜው ፡ ገፋ ፡ ብሎ ፡ ምራቁን ፡ የዋጠ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ ለቤቱ ፡ ለትዳሩ ፡ አሳቢ ፡ የሚሆነው ። ስለዚህ ፡ እድሜያቸው ፡ ገፋ ፡ ማለቱ ፡ መልካም ፡ እንጂ ፡ ከፉ ፡ አልነበረም ። ብቻ ፡ --- ብቻ ፡ ምን ፡

ይሆናል ፡ ቀረ ።” አሉ ፡ አባ ፡ ሰዎቹ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንዳፈጠጡባቸው ፡ ለማወቅ ፡ እንኩዋ ፡ ሳይቸገሩ ። ይህን ፡ አሉና ፡ መልስ ፡ የሚያገኙ ፡ መስሎዋቸው ፡ ቢጠብቁ ፡ ሁሉም ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ስላሉ ፡ ፈሩ ። ከዚያ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ያባ ፡ ሞገሴ ፡ ሁኔታ ፡ አሳዘናትም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ነገራቸው ፡ ለመልስ ፡ የተመቸ ፡ በመሆኑ ፦ “ ከድሜ ፡ ገፋ ፡ ብሎ ፡ ምራቅን ፡ የዋጡ ፡ መሆን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነው ። አባ ፡ ከድሜ ፡ ገፋ ፡ ብሎ ፡ ምራቅን ፡ መሰብሰብ ፡ የማይችሉ ፡ መሆን ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ነው ። ” አለ ፡ እዬሳቀ ። እዚያ ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ከፊታውራሪ ፡ በቀር ፡ ሳቁ ።

“ ነገር ፡ ማዋለድ ! አሉ ፡ ጌቶች ፡ እውነታቸው ፡ ነው ! ነገር ፡ ማዋለድ ፡ ነገር ፡ ማባዛት ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ እንዲህ ፡ የሚባሉ ፡ ናቸው ፡ ባዛኙቱ ? ” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፦ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ምሽታቸውን ፡ ለማሳዘን ፡ መርጠው ፡ የተናገሩዋቸውን ፡ የስድብ ፡ ቃሎች ፡ ማስታወስ ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ ሳይገነዘቡ ። እዚያ ፡ የነበሩ ፡ ሁሉ ፡ በቁጣ ፡ መልክ ፡ ሲመለከቱዋቸው ፡ ብቻ ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ ተናግሬ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ደነገጡና ፡ ግንባራቸው ፡ ወዛ ።

“ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፦ ላባ ፡ ሞገሴ ፡ መዘባረቅ ፡ መንገድ ፡ የሰጠው ፡ የነሱ ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ እንዳይናገሩ ፡ ለማድረግ ። “የፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ አንዱ ፡ ዋና ፡ በሽታ ፡ ያዩዋትን ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ ሁሉ ፡ ላግባሽ ፡ ማለታቸው ፡ ነው ። ምሽት ፡ ለማግባት ፡ እንጂ ፡ ለማኖር ፡ አያስቡም ። ለብሳ ፡ ተኩዋኩላ ፡ ያዩዋትን ፡ ሁሉ ፡ ላግባሽ ፡ ሲሉ ፤ ሲያገቡ ፡ ሲፈቱ ። ዛሬ ፡ በቢቸና ፡ በማእርግ ፡ ስማቸው ፡ መጠራታቸው ፡ ቀርቶ ፡ ላግባሽ - አሰጌ ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ወጥቶላቸዋል ። ይህን ፡ አልሰሙም ፡ ጌቶች ። ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ፊታውራሪን ፡ እዬተመለከቱ ።

“ አልሰማሁም ፡ ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንዳኮረፈ ፡ ህጻን ፡ ሲናገሩ ፡ አፋቸውን ፡ እንደሚበቃ ፡ ሳይከፍቱ ።

“ እንግዲህ ፡ ልንገርዎ ፦ በቢቸና ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ቢሉ ፡ እሳቸው ፡ መሆናቸውን ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ አያገኙም ፤

የሰቻቸው ፡ ስም ፡ ሳግባሽ - እሰኔ ሆንዋል ። መቸስ ፡ እያገቡ ፡ የፈቱዋቸውን ፡ ምሽቶች ፡ ቁጥር ፡ እግዜር ፡ ያውቀው ፡ እንደ ሆነ ፡ እንጂ ፡ እንኳዋን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እርሳቸው ፡ የሚያውቁት ፡ አይመስለኝም ። ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ እዩሳቁ ። “ በዚህ ፡ ላይ ” አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ “ በሰፈ ፡ ግዛታቸው ፡ ካንድ ፡ ቤታቸው ፡ ተነስቶ ፡ ወደ ፡ ምስራቅ ፡ ወደ ፡ ምእራብ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በያራት ፡ በያምስት ፡ ሰአት ፡ጉዞ ፡ አንዳንድ ፡ ቤትና ፡ አንዳንድ ፡ ቁባት ፡ አላቸው ። እንዚሀ ፡ ቁባቶች ፡ ሁሉ ፡ አሽከር ፡ ቀለብ ፡ ልብስና ፡ የወር ፡ ጨው ፡ ፈላጊዎች ፡ ናቸው ። ስለዚሀ ፡ ምሽቶች ፡ የተባሉት ፡ የሚቀመጡበት ፡ ዋና ፡ ቤታቸው ፡ ከከብራቸውና ፡ ከግርጋቸው ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ ሆኖ ፡ እያውቅም ። ወጥተው ፡ ሲገቡ ፡ ያጀባቸውን ፡ ሁሉ ፡ እስከትለው ፡ ገብተው ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ አምጡ ፡ ሲሉ ፡ ምሽቶቻቸውና ፡ የቤት ፡ ሹሞቻቸው ፡ ያልተቀበሉትን ፡ ከወዴት ፡ ያምጡ ! ታዲያ ፡ እቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ጠባያቸው ፡ መከፋት ! ”

“ ጉድኮ ፡ ነው ፡ እናንተ ! እንዲያው ፡ ለመሆኑ ፡ ነውር ፡ ላድርግሀ ፡ ካሉት ፡ ነውር ፡ የማይሆን ፡ የለም ! ቤት ፡ በየቦታው ፡ መስራት ፡ የጌትነት ፡ ወግ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ከነውር ፡ ተቆጠረ ፤ ቁባት ፡ በዩቤቱ ፡ ማስቀመጥ ፡ የመኳዋንንት ፡ ወግ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ከነውር ፡ ተቆጠረና ፡ ያስወቅስ ፡ ጀመረ ፤ እንግዲሀ ፡ ነውር ፡ ያልሆነው ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ይሆን ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ምሽታቸው ፡ በተናገሩት ፡ ከተቆጡ ፡ ጀምሮ ፡ አፋቸውን ፡ ሞልተው ፡ ሳይናገሩ ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ። ቢሆንም ፡ ምሽታቸው ፡ የተናገሩት ፡ የተወው ፡ ምሬት ፡ ካፋቸው ፡ ጨርሶ ፡ ስላልጠፋ ፡ የሰው ፡ ነገር ፡ ገና ፡ አይጥማቸውም ፡ ነበር ።

“ አይደለምኮ ፡ ጌቶች ፤ ቤት ፡ በዩቦታው ፡ መስራትና ፡ ቁባት ፡ በዩቤቱ ፡ ማስቀመጥ ፡ የመኳዋንንት ፡ ወግ ፡ አይደለም፡ አላልሁም ፤ መኳዋንንቱ ፡ ሁሉ ፡ የሚያደርጉት ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ ፤ ብቻ ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ በትዳሩና ፡ ባቅሙ ፡ መጠን ፡ ካላደረገው ፡ ክብሩ ፡ መዋረዱና ፡ ስሙ ፡ መጥፋቱ ፡ አይቀርም ፡ ማለቴ ፡ ነው ፡ በሳቸው ፡ የደረሰ ፡ ይሀ ፡ ነው ። ደግሞ ፡- - - ” አሉና ፡ ባላምባራስ ፡ ሊቀጥሉ ፡ ሲሉ ፡-

"አባክህ ፡ ድሮውንም ፡ ስም ፡ የሌለው ፡ የሰው ፤ ስም ፡ ማጥፋቱ፥ ክብር ፡ የሌለው ፡ የሰው ፡ ክብር ፡ ማዋረዱ ፡ አዲስ ፡ አይደለም፤ የተለመደ፡ ነው።" ሲሉ ፡ ፊታውራሪ፡-ምሽታቸው ፡ ክት ፡ ብለው ፡ ሳቁ ። ወዲያው ፡ ዘወር ፡ ቢሉ ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩ፡ አይነት ፡ ልብ ፡ ምህረት ፡ ልመና ፡ ከቅድም ፡ ጀምሮ ፡ ደጅ ፡ እንደ ሚጠናና ፡ እንደሚጨነቅ ፡ ካይኖቻቸው ፡ ተመለከቱና ፡ ከመቅጽ በት ፡ የሽማግሌ ፡ ፊታቸው ፡ ሲለሰልስ ፡ ስሜታቸው ፡ ሁሉ ፡ ሲለ ወጥ ፡ ይቅር ፡ ሲሉ ፡ ጎልቶ ፡ ታዩ። ድሮውንም ፡ ወይዘሮ ጥሩ፡ አይነት ፡ እንዲያ ፡ ክት ፡ ብለው ፡ የሳቁት ፡ ባላቸው ፡ ወገባቸውን፡ ጠምዝዘው ፡ ፊታቸውን ፡ አዙረው ፡ አሳያቸው ፡ ስላሉ ፡ አሳባቸ ውን ፡ ለመማረክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፊታውራሪ ፡ የተናገሩት ፡ የሚያ ስቅ ፡ ሆኖ ፡ አልነበረም። አሁን ፡ አሸነፉ ፤ የባላቸውን ፡ አሳብ፡ ልባቸውንም ፡ ማረኩ ፤ ስለዚህ ፡ ደስ ፡ አላቸው።

ፊታውራሪ ፡ በበኩላቸው ፡ ቁጣቸው ፡ ማለፍና ፡ ስሜታቸው፡ መለወጥ ፡ ሲጀምር ፡ የተቆጡበት ፡ ነገር ፡ ከጤፍ ፡ ቅንጣት ፡ ያነሰ፡ እንግዶች ፡ እቤታቸው ፡ ጠርተው፡ ማኩረፍ ፡ እንደሳቸው ፡ ያለ ፡ የታላቅ ፡ ዘር ፡ ታላቅ ፡ የማያደርገው ፡ መሆኑ ፡ ተሰማቸ ውና ፡ ጸጸት ፡ ገባቸው። ስለዚህ ፡ ለጨዋታው ፡ ሙሉ ፡ ተካ ፋይ፡ መሆን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከዚያም ፡ አልፈው ፡ ጨዋታ ውን ፡ ለመምራት ፡ ወስነው ፡ የሚመሩበት ፡ መንገድ ፡ ይፈ ልጉ ፡ ጀመር። ብቻ ፡ ያንሰት ፡ አሳባቸው ፡ የተቃኘ ፡ በልጃ ቸው ፡ ጋብቻ ፡ ስለነበረ ፡ ከሱ ፡ ወጥተው ፡ ጨዋታውን፡ በሌላ፡ መንገድ ፡ ሊመሩ ፡ አልቻሉም ፤ እሱም፡ ተጀምሮ ፡ እስኪጨ ርስ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ የሌለበት ፡ ስለሆነ ፡ አዙሮ ፡ አዙሮ ፡ እቅርታ ፡ ላይ ፡ ይጥላቸው ፡ ነበር።

" እንዲያው ፡ ለመሆኑ፡" አሉ ፡ ፊታውራሪ፡ መጀመ ርያ ፡ ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ ብለው ፡ "እኔማ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳስብ፡ ከቶ ፡ ይች፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ አይነ ፡ ጥላ ፡ አንድ፡ አይነት ፡ ገርጋሪ ፡ ቁራኛ ፡ ይኖርባት ፡ ይሆን ? አላስሁ፡ ደህና ፡ ደህና ፡ የባላባት ፡ ልጆች ፡ ይቀርቡና ፡ ተመልሰው

ይሸሻሉ ። ያንጊዜ ፡ የቆለላው ፡ የደጃች ፡ በዛብህ ፡ ልጅ ፡ ለምኖን ፡ እኛም ፡ እሺ ፡ ብለን ፡ ድግስ ፡ መደገስ ፡ ስንጀምር ፡ ያው ፡ እንደምታውቁት ፡ ቀረ ። ቀጥሎ ፡ የሚመጣው ፡ የፊታውራሪ ፡ ጀምበሬ ፡ ልጅ ፡ ለምኖን ፡ እኛም ፡ እሺ ፡ ብለን ፡ ያው ፡ እንደምታውቁት ፡ ባምባጉዋሮ ፡ ሞተ ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ይሄ ፡ ተሰምቶ፡ የማይታወቅ ፡ ነገር ፡ አሳፍሬ ፡ አስከብሬ ፡ ከልፍኝ ፡ ሳላስወጣ ፡ ያሳደግሁዋትን ፡ ልጃገረዲቱን ፡ ልጄን ፡ በልጃገረድ ፡ ወግ ፡ አላገባም ፡ ብሎ ፡ ይኸው ፡ ውል ፡ አፈረሰ ። እንዲያው ፡ ድንገት ፡ ገርጋሪ ፡ ቁራኛ ፡ ይኖርባት ፡ እንደሆን ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ በደሀና ፡ የገበሮች ፡ ልጆች ፡ ያላጡትን ፡ የኔ ፡ ልጅ ፤ የብዙ ፡ መሳፍንትና ፡ የብዙ ፡ ነገስታት ፡ ልጅ ፡ ባል ፡ ትጣ ? ”

“ ጆሮ ፡ ለባለቤቱ ፡ሩቅ ፡ ነው ፡ የሚባለውን ፡ ተረት ፡ ያውቁታል ፡ ፊታውራሪ ? ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ፡ ብሎ ፡

“ እንዴት ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

“ ጆሮ ፡ ስለባለቤቱና ፡ በዙሪያው ፡ ስላሉት ፡ ማለት ፡ ስለ ቤተሰቡ ፡ የሚባለውን ፡ የሚሰማ ፡ በሩቅ ፡ ያሉት ፡ ሰምተው ፡ ከጨረሱ ፡ በሁዋላ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ታዲያ ፡ እሱት ፡ አይምሰላችሁ ፡ እውነት ፡ ነው ። ” አለ ፡ የተቀመጡትን ፡ ሁሉ ፡ ባይኑ ፡ አዞሮ ፡ ገረፈና ።

“ እንዴትስ ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ።

“ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ባል ፡ እንዳታገባ ፡ ብርቱ ፡ ገርጋሪ ፡ የተቆራኛት ፡ መሆኑን ፡ አገር ፡ በሙሉ ፡ ብዙ ፡ አመት ፡ አውግቶ ፡ ከጨረሰውና ፡ ከተረሳ ፡ በሁዋላ ፡ አሁን ፡ እርስዎ ፡ አዲስ፡ ጥያቄ ፡ አድርገው ፡ ማምጣትዎ ፡ ጆሮ ፡ ለባለቤቱና ፡ ለቤተሰቡ ፡ ሩቅ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ ብሂል ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ። ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ እዬሳቀ ።

“ እና ፡ ትስቃለሀ ! ” አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ የሀታቸውን ፡ ልጅ ።

“ ብዙ ፡ አመት ፡ አዝኜ ፡ አልቅሼ ፡ ወጥቶልኛል ፡ ” አለ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ደንግጠው ፡ ማሰብም ፡ መናገርም ፡ አቃታቸው ፤ በድን ፡ ሆኑ ። ሌሎችም ፡ ሁሉ ፡ ደነገጡ ። ከዚያ ፡ እአምሮዋቸውን ፡ ጋርዶት ፡ የነበረው ፡ ጉም ፡ ትንሽ ፡ ገለጥ ፡ ማለት ፡ ሲጀምር ፦ "ልጂን ፡ ቁራኛ ፡ የተቆራኛት ፡ መሆኑን ፡ ነው ፡ አገር ፡ አውግቶ ፡ የጨረሰው ? " አሉ ፡ በተሰበረ ፡ ድምጽ ።

" እንዴታ ! ብርቱ ፡ ገርጋሪ ፡ የተቆራኛት ፡ መሆኑን ፡" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

" በሞትሁት ፤ በሞትሁት ፤ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለነው ? ጉዳችንን ፡ የማንሰማ ? በዘመድ ፡ በወዳጅ ፡ መሀከል ፡ ያለን ፡ ሲመስለን ፡ ለካ ፡ በባእድ ፡ ባራዊት ፡ መሀከል ፡ ነው ፡ የምንኖር ፡ " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ።

" አዎ ፤ አትሞችም ፡ እንጂ ፡ በሞትሽስ ፡ ሁለታችሁም ፡ ብትሞቱስ ፡ ደህና ፡ ነበር ! ወዴት ፡ ነው ፡ የምንኖረው ፡ ያልሽው ፡ ጥሩ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። እናንተ ፡ ሁለታችሁ ፡ ወዴት ፡ እንደምትኖሩ ፡ እኔ ፡ ልንገርሽ ። " አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እሁንም ፡ እዬሳቀ ። "እናንት ፡ ሁለታችሁ ፡ ፊታውራሪና ፡ እንቺ ፦ ከዛሬ ፡ ሺህ ፡ አመት ፡ በፊት ፡ ባለፈ ፡ አለም ፡ የምትኖሩ ፡ ጉዶች ፡ ናችሁ ። " ካለ ፡ በሁዋላ ፡ ጉድ ፡ ለሱ ፡ የሰጡት ፡ ስም ፡ መሆኑ፡ ትዝ ፡ ስላለው ፡ ፈገግ ፡ አለና ፡ ተቀማጮች ፡ መሳቃቸውን ፡ ለማዬት ፡ አይኑን ፡ ዘወርወር ፡ አድርጎ ፦ ግድየለም ፡ ስለዚህ፡" አለ ። " ስለዚህ ፡ መቸም ፡ ለጉድ ፦ ጉዱን ፡ በዘወርታ ፡ ካልሆነ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ገልጾ ፡ የሚነግረው ፡ የለም ፡ ዘወር ፡ አድርጎ ፡ ቢነግሩዋችሁም ፡ የምትሰሙ ፡ አይደላችሁም ፡ ይሄውልሽ ፡ እንግዲህ ፡ ነገሩ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ " ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የተናገረው፡ ለማንም ፡ አልገባው ።

" ይሁንና ! እንዴት ፡ ያለ ፡ ገርጋሪ ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ ልጂን ፡ የተቆራኛት ? ሰይጣን ፡ ነው ? ወይስ ፡ . . . . . " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አይናቸውን ፡ እንባ ፡ ሞልተው ። ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ያለቅሱ ፡ ጀመር ።

" ሰይጣን ፡ ነው ፡ እንጂ ! ያውም ፡ የረቀቀ ፡ የተደበቀ ፡ ሰይጣን ፡ አይደለም ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ግዙፍ ፡ ጋኔን ፡ ነው ፡ ያ ፡

ቀንዳሙ ፡ ጢማሙ ፡ ጋኔን ፡ ከነጭፍሮቹ ፡ ነው ፡ እህቴን ፡ የተቆራኛት ። ይህ ፡ ከነጭፍሮቹ ፡ የተቆራኛት ፡ ጋኔን ፡ ነው ፡ በፍቅርና ፡ በደስታ ፡ እንድታሳልፈው ፡ ከፈጣሪ ፡ የተሰጣትን ፡ የልጅነት ፡ እድሜ ፡ ባዘንና ፡ በትካዜ ፡ እንድታሳልፍ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ከሌሎች ፡ አልቆ ፡ ሌሎችን ፡ እንድትቀድም ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሄር ፡ የፈጠራትን ፡ እህቴን ፡ ከሁዋለኞች ፡ ወደ ሁዋላ ፡ እንድትሆንና ፡ በፍረት ፡ መጋረጃ ፡ ተሸፍና ፡ እንድትኖር ፡ ያደረጋት ፡ ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፤ በተናገረ ፡ መጠን ፡ ሳቁ ፡ ወደምሬትና ፡ ወደብስጭት ፡ እየተለወጠ ።

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ መጀመርያ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ባል ፡ እንዳታገባ ፡ ገርጋሪ ፡ ጋኔን ፡ ተቆራኝቶዋታል ፡ ሲል ፡ እዚያ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ መስሎዋቸው ፡ ደንግጠው ፡ ነበር ። በሁዋላ ፡ ግን ፡ ከወላጆችዋ ፡ በቀር ፡ ሌሎቹ ፡ እንደልማዱ ፡ ለሰው ፡ የማይገባ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ሊያመጣ ፡ አስቦ ፡ ነውንጂ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ አመት ፡ አገር ፡ ያወጋውን ፡ ነገር ፡ ሳንሰማው ፡ አንቀርም ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ እያንዳንዱ ፡ ካፉ ፡ የሚወጣው ፡ ቃል ፡ ፊታውራሪንና ፡ ምሽታቸውን፡ የሚያስደነግጠውን ፡ ግማሽ ፡ እያስደነግጣቸውም ፡ ነበር ። ፊታውራሪና ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ብቻ ፡ ወላጆች ፡ በመሆናቸው ፡ መችም ፡ ወላጅ ፡ እንኩዋንስ ፡ በወለደው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ደረሰበት ፡ ብለው ፡ ነግረውት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በወለድኸው ፡ ይደርሳል ፡ እንዳይሉት ፡ የሚፈራ ፡ ስለሆነ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ፡ የሚናገረው ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አምነው ፡ እንቅጥቅጥ ፡ ይዞዋቸው ፡ ነበር ።

“ ይህ ፡ ግዙፍ ፡ ቀንዳም ፡ ጢማም ፡ ጋኔን ፡ ከነጭፍሮቹ ፡ ወዴት ፡ እንዳለ ፡ ላሳያችሁ ? ” ሲል ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፦

“ እእ ? ” አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ እውነት ፡ ልጃቸውን ፡ የተቆራኘው ፡ ጋኔን ፡ ከነጭፍሮቹ ፡ እዚያ ፡ የመጣ ፡ መስሎዋቸው፡ ተነስተው ፡ ጉሮሮውን ፡ ለማነቅና ፡ ለመበቀል ፡ እንደፈለጉ ፡ ሁሉ ፡ እልጋቸውን ፡ ተደግፈው ፡ ከተቀመጡበት ፡ አይናቸውን፡ አፍጥጠው ፡ ቀና ፡ አሉ ።

“ ያውላችሁ ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የፊት ፡ ጣቱን ፡ ወደ ፡

ፊታውራሪ ፡ ቀስሮ ። “ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ባል ፡ እንዳታገባ ፡ ገቢጋሪ ፡ ሆኖ ፡ የተቆራኛት ፡ ቀንዳም ፡ ጋኔን ፡ ያውላችሁ ! ጭፍሮቹ ፡ ለመጥፎ ፡ ትምህርቱ ፡ ሀዋርያት ፡ ሆነው ፡ የሚሰብ ኩለት ፡ አጋንንት ፡ እኒያውላችሁ ! ” አለ ፡ አክስቱንና ፡ አባ ፡ ሞገሴን ፡ እያመለከተ ። ፊታውራሪ ፡ አይናቸውን ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ላይ ፡ ሳያነሱ ፡ እንደገና ፡ ቀኝ ፡ ብለው ፡ ወዳሏጋ ፡ ድጋፋ ቸው ፡ መለስ ፡ አሉ ። በዚያን ፡ ... ፡ የሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ እልም፡ ቅዠት ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ አልመሰላቸውም ።

“ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ባል ፡ እንዳታገባ ፡ ያባትና ፡ የናት ፡ ምቀኞች ፡ ሆናችሁ ፡ ከንስሀ ፡ አባታችሁ ፡ ጋር ፡ የጋኔን ፡ ቁራኛ ፡ ገቢጋሪና ፡ አይነ ፡ ጥላ ፡ ሆናችሁ ፡ አቁማችሁ ፡ ያስቀራ ችሁዋት ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ። ” ሲል ፡- ተጭኖዋቸው ፡ የነበረ ፡ ከመርግ ፡ የከበደ ፡ ሸክም ፡ ከትክሻቸው ፡ ገለል ፡ ሲል ፡ ተሰማ ቸውና ፡- አፍፍፍፍፍፍ . . . , . ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ነፋስ ፡ ሞልቶ ፡ ቆይቶ ፡ እንደሚተነፍስ ፡ ማናፊያ ።

“ በል ፡ ዝም ፡ በል ፡ በቃህ ! ያልሰማነው ፡ መርዶ ፡ አረ ዳኸን ፡ መስሎን ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ የተጨነቅንና ፡ ያለቀስን ፡ የእ ኛን ፡ እምነትና ፡ የኛን ፡ አስተያየት ፡ ከሆነ ፡ በጋኔን ፡ ቁራኛና፡ ባይነ ፡ ጥላ ፡ የመሰለኸው ፡ እሱን ፡ የጠዬቀህ ፡ የለም ። ” አሉ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ የታላቅ ፡ እህታቸውን ፡ ልጅ ።

“ እትዬ ፡ ጥሩ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ረሳሽኮ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ መሆ ኔን ፡ ረሳሽ ። የናንተ ፡ ጉድ ፡ የናንተ ፡ እብድ ፡ አይደለሁም ፡ እንዴ ! እብድን ፡ ፍርድ ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚጠይቀውም ፡ ፍርድ ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚከለክለውም ፡ የለምኮ ! የምናገረውን ፡ እትስ ሙት ፤ ስናገር ፡ እንደልማዳችሁ ፡ ጆሮዋችሁን ፡ ድፈኑ ፡ መና ገር ፡ ግን ፡ የጉድነት ፡ የእብድነት ፡ መብቴ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እንደብዮቹ ፡ እናገራለሁ ፤ አታቋርጡኝ ። አንችም ፡ ብትሆኚ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ እኔ ፡ ስናገር ፡ የተናገራችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ከጉድ ፡ ጋር ፡ የተናገረ ፡ ጉድ ፡ ከብድ ፡ ጋር ፡ የተናገረ ፡ እብድ ፡ መባሉን ፡ አትርሱ ፡ ” አለና ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ነገሩን ፡ ቀጠለ ።-

“ ቅድም ፡ እንዳልሁት ፡ ያባትና ፡ የናት ፡ ምቀኞች ፡ ሆና ችሁ ፡ ሰብለን ፡ አቁማችሁ ፡ ያስቀራችሁዋት ፡ እናንተ ፡ ወላ

ጀምዋ ፡ ናችሁ ። ከመኩዋንንት ፡ ልጅ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ ለማ
ግባት ፡ ደጅ ፡ ያልጠናና ፡ ተንበርክኮ ፡ ያልሄደ ፡ ማነው ? እን
ኩዋን ፡ ያያት ፡ ከሩቅ ፡ ወሬዋን ፡ የሰማ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ተጉዞ ፡
እዚህ ፡ ያልተንገላታ ፡ ማነው ? ነገር ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ እንደውሻ ፡
አጥንትና ፡ ደም ፡ ስታሽትቱ ፡ ይሄው ፡ አቁማችሁ ፡ አስቀራች
ሁዋት ። ኧረ ፡ ለመሆኑ ፡ እንደኔ ፡ እብድ ፡ ያልሆነ ፡ ጭምት ፡
ቢጠይቃችሁ ፡ የናንተ ፡ አጥንትና ፡ ደም ፡ ከሌሎቹ ፡ ልዩ ፡ የሆ
ነበት ፡ በምን ፡ ነው ? የናንተ ፡ ደም ፡ ስትሞቱ ፡ አይቆምም ?
አያልቅም ? አይቀርም ? የናንተ ፡ ስጋ ፡ አይፈርስም ? አይበሰብ
ስም ? አይተሎም ? አይገማም ? የናንተ ፡ አጥንት ፡ አይነቅዝም ?
አይሰበርም ፡ አፈር ፡ አይሆንም ? በናንተ ፡ ዘንድ ፡ ድህነትን
ታግሎ ፡ ኖሮ ፡ በላቡ ፡ በድካሙ ፡ በደሙ ፡ ጌትነትን ፡ የሚግ
ርክ ፡ ገዦነትን ፡ ፈጥሮ ፡ ለራሱ ፡ የሚያደርግ ፡ ብርቱ ፡ ጎበዝ ፡
ጀግና ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፤ ካፈር ፡ እንደፈላ ፡ አባት ፡ የለሽ ፡ ይባ
ላል ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ጎበዝ ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ የሚንቁት ፡
የሚጸየፉት ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ጀግና ፡ ልጃችሁን ፡ ላግባ
ሎ ፡ የለመነ ፡ እንደሆነ ፡ ለናንተ ፡ እንደትልቅ ፡ ውርደት ፡
እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሞት ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። በናንተ ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡
የሚሰጠው ፡ ተሰምኖ ፡ ልጅ ፡ ሊዳርለት ፡ የሚገባው ፡ ሳይወጣ ፡
ሳይወርድ ፡ ሳይነድ ፡ ሳይበርድ ፡ የወላጆቹን ፡ ሞት ፡ ጠብቆ ፤
ለወላጆቹ ፡ ሞት ፡ ተስሎ ፡ ሀብታቸውን ፡ የሚወርስ ፡ ቢያጣ ፡
ተቀምጦ ፡ የሚያለቅስና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚወቅስ ፡ ሰነፍ ፡
ነው ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰነፍ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ላባት ፡ ለናቱ ፡
ሞት ፡ ለማኝና ፡ በሰው ፡ ሀብት ፡ የሚኖር ፡ ካልተገኘ ፡ በራሱ ፡
ሀብት ፡ ለሚኖር ፡ ልጃችንን ፡ አንሰጥም ፡ ብላችሁ ፡ ይሄው ፡
አቁማችሁ ፡ አስቀራችሁዋት ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ሰብለ ፡ ወን
ጌል ፡ እድሉዋ ፡ የሚቀና ፡ አንድም ፡ እናንተ ፡ የተጸጸታችሁና ፡
ይህን ፡ ከንቱ ፡ አሳባችሁን ፡ የለወጣችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ያለዚ
ያም ፡ ተዩይዛችሁ ፡ ያለቃችሁላት ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ”
ብሎ ፡ ከሙቀትና ፡ ከስሜት ፡ ጋር ፡ ተናግሮ ፡ ጨረሰ ፡- እዚያ ፡
ከነበሩት ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንደሁልጊዜው ፡ ለነገሩ ፡ ዋጋ ፡ ሳይ
ሰጡ ፡ ስቀው ፡ ዝም ፡ አሉ ። ሌሎቹ ፡ የታላቆች ፡ ዘር ፡ ሆኖ ፡

ከዘር ፡ የሚወረሰን ፡ ታላቅነት ፡ እንዲህ ፡ እድርጎ ፡ ማኮሰሱ ፡ የእእምሮውን ፡ ጎደሎነት ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ስለሆነ ፡ እዝነው ፡ ከንፈራቸውን ፡ ሲመጡ ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ። ፊታውራሪ ፡ በበኩላቸው ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ የምሽታቸው ፡ የታላቅ ፡ እት ፡ ልጅ ፡ ያወረደባቸው ፡ ዘለፋና ፡ ስድብ ፡ በቅርብ ፡ የሚገኝ ፡ ቁጣቸውንና ፡ ኩርፊያቸውን ፡ ለማምጣት ፡ ከሚበቃ ፡ በላይ ፡ ቢሆን ፡ ልጃቸውን ፡ ተቆራኝቶዋታል ፡ የተባለው ፡ የውነተኛ፡ ጋኔን ፡ መስሎዋቸው ፡ በድን ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ በመጨረሻ ፡ ጋኔኑ ፡ ራሳቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ስላወቁ ፡ ዘለፋውን ፡ ደስታቸው ፡ አሸንፎ ፡ ከሚስቁት ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ።

“ ወይ ፡ ግሩም ! የዲማውን ፡ የለውምኮ ! ጋኔን ፡ ተቆራኝቶዋታል ፡ ሲል ፡ እውነት ፡ መሰሎኝ ፡ ጭራሽ ፡ በድን ፡ ሆንሁ። እረ ፡ ለመሆኑ ፡ እኔንና ፡ ጥሩየን ፡ ጉዶች ፡ ያልሽን ፡ አንተ ፡ ምን ፡ ልትባል ፡ ነው ? ጉዱም ፡ ቀንዳሙ ፡ ጋኔንም ፡ አንተ ፡ነህ፡ የዲማውን ፡ ” አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ ከልባቸው ፡ ሲስቁ ፡ ከወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ በቀር ፡ ሁሉም ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ። ጉዱ ፡ ካሳ ነገሩን ፡ አቃለውና ፡ እንዲሁ ፡ ስቀው ፡ ከሚያልፉት ፡ ስድቡም ፡ ዘለፋውም ፡ አምዋቸው ፡ ከንክኗቸው ፡ መልሰው ፡ ቢሰድቡት ፡ ቢመቱት ፡ እንኩዋ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንደሁልጊዜው ፡ የተናገረው ፡ አልጣማቸው ፡ ወይ ፡ አልመረራቸው ፡ እንዲያው ፡ እንዲሁ ፡ ስቀውና ፡ ከንፈራቸውን ፡ መጠው ፡ ዝም ፡ አሉ ። እሱም ፡ እንደ ፡ ዘወትሩ ፡ ለጊዜው ፡ ተቆጥቶ ፡ ሄደ ።

# ምእራፍ ፡ ፲፪ ፡

## ጉዳ ፡ ካሳ ፡

ካሳ ፡ ዳምጪ ፡ ከነግይ ፡ ባላባት ፡ ከፊታውራሪ ፡ ዳምጪ ፡ ብሩና ፡ ከወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ታላቅ ፡ እህት ፡ ከወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ተሰማ ፡ የተወለደ ፡ በሁለት ፡ እጅ ፡ የማይነሳ ፡ ከባድ ፡ የጌታ ፡ ዘር ፡ ነበር ። በመኩዋንንት ፡ ልጆች ፡ ወግ ፡ የቤተ ፡ መንግስት ፡ ስራት ፡ እያጠናና ፡ ደጅ ፡ እየጠና ፡ ቢያድግ ፡ ኖሮ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ያባቱን ፡ ግዛት ፡ ባላማ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አባቱ ፡ በህጻንነቱ ፡ ስለሞቱና ፡ ምቀኞች ፡ ዘመዶቹ ፡ እንኩዋን ፡ ይህን ፡ እድል ፡ እንዲያገኝ ፡ ሊያደፋፍሩትና ፡ ወደፊት ፡ ሊገፉት ፡ ቀድሞ ፡ እሬት ፡ ቢያገኙትም ፡ ወደሁዋላ ፡ ለመኀተት ፡ የማይመለሱ ፡ ስለነበሩ ፡ ከቤተ ፡ መንግስት ፡ ርቆ ፡ ከናቱ ፡ ዘንድ ፡ አደገ ። ከቤት ፡ እዬተመላለሰ ፡ እዚያው ፡ አገሩ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ዳዊት ፡ ከደገመ ፡ በሁዋላ ፡ አሳቡ ፡ ወደትምህርት ፡ ተሳበና ፡ ካንዱ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ወደሌላው ፡ እዬተዘዋወረ ፡ ዜማም ፡ ቅኔም ፡ ተምሮ ፡ ሲጨርስ ፡ ብዙ ፡ አመታት ፡ መጣፍ ፡ ተማረ ። በተለይ ፡ ሀዲስ ፡ አዋቂነቱን ፡ የሚያደንቁ ፡ ብዞች ፡ ነበሩ ። ባገሩ ፡ ትምህርት ፡ እውቀቱ ፡ የጠለቀ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የባላባት ፡ ልጅ ፡ በመሆኑ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሹመት ፡ ፈላጊ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከታላላቁ ፡ አድባራት ፡ ያንዱን ፡ አለቅነት ፡ ቢያንስ ፡ ሊቀጠበብትነት ፡ ሊያገኝ ፡ እንደሚችል ፡ የማይጠረጠር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አስተያየቱ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሪዎችና ፡ ከካህናቱ ፡ በጣም ፡ የተለዩ ፡ ስለነበረና ፡ ስራቸውን ፡ አጥብቆ ፡ ይጠላ ፡ ስለነበረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በነሱ ፡ አይን ፡ እያዬ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይርቅ ፡ ጀመር ። በሁዋላ ፡ እንዲያውም ፡ የሚኖርበት ፡ ማህበር ፡ የተመሰረተበት ፡ ስራት ፡ ልማዱ ፡ ደንቡ ፡ ወጉ ፡ ህጉ ፡ የማይረባ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የሚጎዳ ፡ መሆኑን ፡ ይሰብክና ፡ ይህ ፡ አሮጌ ፡ ስራት ፡ ሳይሻሻል ፡ እንደ ፡ እግዚአብሄር ፡ ቃል ፡ ተከብሮ ፡ እንዲኖር ፡ የሚ

ማጣሩትን ፡ የልማድ ፡ ባሮች ፡ ከብቶች ፡ ደንጋዮች ፡ እያለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ እዬሰጠ ፡ ይዘልፍ ፡ ነበር ።

" የማህበራችን ፡ አቋዋም ፡ የተሰራበት ፡ ስራት ፡ ልማዱ፡ ወጉ ፡ ህጉ ፡ እንደህይወታዊ ፡ ስራተ ፡ ማህበር ፡ ሳይሆን ፡ ህይ ወት ፡ እንደሌለው ፡ የደንጋይ ፡ ካብ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ተደ ራርቦ ፡ የላይኛው ፡ የታችኛውን ፡ ተጭኖ ፡ የታችኛው ፡ የላይ ኛውን ፡ ተሸክሞ ፡ እንዲኖር ፡ ሆኖ ፡ የተሰራ ፡ በመሆኑ ፡ ከጊዜ፡ ብዛት ፡ የታችኛው ፡ ማፈንገጡ ፡ ስለማይቀርና ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ ህንጻው ፡ በሙሉ ፡ እንዳይፈርስ ፡ እንደገና ፡ ተሻሽሎ ፡ ሰውን ፡ ከደንጋይ ፡ በተሻለ ፡ መልክ ፡ የሚያሳይ ፡ የህያዋን ፡ አቋዋመ ፡ ማህበር ፡ እንዲሰራ ፡ ያስፈልጋል ። የዛሬው ፡ ስራተ ፡ ማህበራ ችን ፡ ሲሰራ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለነበረው ፡ ማህበር ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ መሰራቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ኖሮ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለዛ ሬው ፡ ማህበር ፡ ጠቃሚ ፡ አለመሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ማናቸውም ፡ ስራት ፡ ማህበሩ ፡ ለዚያው ፡ ለማህበራዊ ፡ ኑሮው ፡ እንዲያገለግለው ፡ ሰው ፡ የሰራው ፡ ሲሆን ፡- ማህበ ሩን ፡ ባሪያ ፡ አድርጎ ፡ እንዲገዛው ፡ መሆኑ ፡ ጣኦት ፡ ሰርቶ ፡ የሰሩትን ፡ ጣኦት ፡ በፈጣሪ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ማስቀመጥና ፡ እንደ ማምለክ ፡ ነው ። " እያለ ፡ ሲሰብክ ፡ እነዚህ ፡ የልማድ ፡ ባሮች፡ በመሆናቸው ፡ የሚንቃቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ የሚያዝንላ ቸው ፡ ሰዎች ፡ እነዚህ ፡ በደንጋይ ፡ ክምር ፡ የሚመስላቸው ፡ ይልቁንም ፡ የላይኛውን ፡ ክፍል ፡ ተሸክመው ፡ የላይኛው ፡ ክፍል ፡ ተጭኖዋቸው ፡ የሚኖሩት ፡ እነዚህ ፡ ከሚጎዳ ፡ አሮጌ ፡ ስራት ፡ ነጻ ፡ ወጥተው ፡ አዲስ ፡ የሚጠቅም ፡ ስራት ፡ ለመስ ራት ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸውን ፡ እንዲያውቁ ፡ እንዲማሩ ፡ የሚፈልጋቸው ፡ ሰዎች ፡ እነሱ ፡ ደግሞ ፡ በበኩላ ቸው ፡ ከታላቅ ፡ እንዳልተወለደ ፡ እንዳልተማረ ፡ ሁሉ ፡- እእ ምሮው ፡ ጤና ፡ ባለመሆኑ ፡ እንዲህ ፡ ተበላሽቶ ፡ እንዲህ ፡ ውሀ፡ በልቶት ፡ ቀረ ፡- እያሉ ፡ ሲያዝኑለትና ፡ ከንፈራቸውን ፡ ሲመ ጡ ፡ ሲሰማ ፡ የነሱን ፡ ስህተትነትና ፡ የሱን ፡ ትክክለኛነት ፡ የነሱን ፡ ጎደሎነትና ፡ የሱን ፡ ሙሉ ፡ ጤናማነት ፡ ለማሳዬት ፡ ከመናገር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እቅም ፡ የሌለው ፡ በመሆኑ ፡ ያዝንና ፡

ይበሳጭ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ የማህበሩን ፡ እሮጌ ፡ ስራት ፡ ጠል ቶና ፡ ንቅፎ ፡ ላሮጌ ፡ ስራት ፡ ባርያ ፡ የሆኑትን ፡ የማህበሩ ፡ አባ ሎች ፡ ንቆና ፡ ተጸይፎ ፡ በመንፈሳዊውም ፡ ሆነ ፡ በአለማዊው፡ ስራትና ፡ ህግ ፡ ላይ ፡ መንፈሱ ፡ ሸፍቶ ፡ የራሱን ፡ አሳብ ፡ ለራሱ ፡ ካልሆነ ፡ የሚያካፍለው ፡ ጉዋደኛ ፡ የለው ፡ የሚናገ ረው ፡ ለሌሎች ፡ አይጥም ፡ ሌሎች ፡ የሚናገሩት ፡ ለሱ ፡ አይጥ መው ፡ በከበበው ፡ አለም ፡ ውስጥ ፡ የማሉን ፡ አለም ፡ ፈጥሮ ፡ በሰው ፡ መሀከል ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ነበር ። ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሁኔታ ፡ እንደሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡- ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ብቻውን ፡ ይናገር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ብቻውን ፡ ይስቅ ፡ ስለነበር ፡ ይህን ፡ ያዩ ፡ ሰዎች ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ አወጡለት ፡-

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በበኩሉ ፡ የሚኖርበት ፡ ማህበር ፡ አይን ፡ እያ ለው ፡ ፍሬውን ፡ ከገለባ ፡ ለይቶ ፡ ማየት ፡ የማይችል ፡ አእምሮ፡ እያለው ፡ የሚጠቅመውን ፡ ከሚጎዳው ፡ ለይቶ ፡ ማስተዋል ፡ የማይችል ፡ እንደ ፡ በግ ፡ መንጋ ፡ በፊቱ ፡ የሚሄደውን ፡ ተከ ትሎ ፡ የሚንጋጋ ፡ እንደጭነት ፡ ከብት ፡ የጫኑትን ፡ ተሸክሞ፡ የሚንትት ፡ የጉድ ፡ ማህበር ፡ ይለው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ " ብዙሃን ፡ ይመውኡ ፡ " ነውና ፡ ማህበሩ ፡ አሸንፎ ፡ " ጉድ ፡ " የካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ስም ፡ ሆነ ። እሱም ፡ ራሱ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሲሉት ፡ እቤት ፡ ባይል ፡ ስሙ ፡ መሆኑን ፡ አውቆ ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ ሲጠሩት ፡ ዘወር ፡ ይል ፡ ነበር።

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከዘመድም ፡ ሆነ ፡ ከባእድ ፡ መሀከል ፡ ሲና ገር ፡ ደስ ፡ ብሎዋት ፡ ሰምታ ፡ ቢያጠግበውም ፡ ባያጠግበውም፡ ከንፈርዋን ፡ ሳትመጥ ፡ ሳታሽሙዋጥጥ ፡ ለሚጠይቃት ፡ ጥያቄ፡ በስዋ ፡ እድሜ ፡ ያለች ፡ ያስተዋይ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አእምሮ ፡ ሊሰ ጠው ፡ የሚችለውን ፡ መልስ ፡ የምትመልስለት ፡ ሰብለ ፡ ወን ጌል ፡ ብቻ ፡ ነበረች ።

እንኩዋን ፡ እንደሱ ፡ በሚኖርበት ፡ ማህበር ፡ ውስጥ ፡ ቦታ ፡ ያጣ ፡ የማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ልቡ ፡ የሚማረክና ፡ የውነተኛ፡ ፍቅሩ ፡ የሚሳብ ፡ ለአሳቡ ፡ ዋጋ ፡ ወደሚሰጡለትና ፡ አሳቡን ፡

ወደሚያከብሩለት ፡ ሰዎች ፡ ስለሆነ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሰብለ ፡ ወን ጌልን ፡ በጣም ፡ ይወዳት ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አሳቡን ፡ ለራሱ፡ መንገር ፡ ሲሰለቸው ፡ ካቅምዋ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ የሃይማኖት ፡ የፍልስፍና ፡ የአስተዳደር ፡ የማህበር ፡ ስራትና ፡ እነሱን ፡ የመ ሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ ይነግራትና ፡ አሳብዋን ፡ እንድትሰጠው ፡ ሲጠይቃት ፡ ልክም ፡ ቢሆን ፡ ስህተት ፡ በቅንነት ፡ በደስታ ፡ በፈገግታ ፡ ትመልስለታለች ፤ እሱም ፡ ከመልሱ ፡ ይልቅ ፡ መል ሱን ፡ በምትሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በፊትዋ ፡ ጎልቶ ፡ የሚያየው ፡ መል ካም ፡ የልብ ፡ ስሜትዋ ፡ ቅንነትዋ ፡ ደስታዋ ፡ ፈገግታዋ ፡ እጥ ግቦት ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ለጊዜው ፡ በራሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ የራሱ ፡ ግዞተኛ ፡ መሆኑን ፡ ይረሳዋል ፤ የስዋን ፡ ቅንነት ፡ የስ ዋን ፡ መልካም ፡ ስሜት ፤ የስዋን ፡ የተዋበ ፡ ፊት ፡ ሲያይ ፡ ማህ በሩ ፡ ልክ ፡ እንደስዋ ፡ ልቡን ፡ ከፍቶ ፡ ፊቱን ፡ አብርቶ ፡ እጁን፡ ዘርግቶ ፡ የተቀበለው ፡ ይመስለዋል ። ስለዚህ ፡ ጤና ፡ ከሆነ ፡ በሳምንት ፡ እሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ዘንድ ፡ ሳይደርስ ፡ የሚያሳልፋ ቸው ፡ ቀኖች ፡ ጥቂት ፡ነበሩ ።

ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ በበኩልዋ ፡ ከዘመዶችዋ ፡ ሁሉ ፡ ካባት፡ ከናትዋ ፡ ሳይቀር ፡ አብልጣ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ትወድ ፡ ነበር ። የመ ንደሩ ፡ ሽሙጥ ፡ ያቆሰለውን ፡ የልብዋን ፡ ቁስል ፡ ማየት ፡ የሚ ችል ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ስለነበረ ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ እንዳ ታይ ፡ አንገትዋን ፡ የሰበረውን ፡ የፍረት ፡ መዶሻ ፡ የሚያይና ፡ ስቃዩዋን ፡ የሚካፈል ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ስለነበረ ፡ የነጻነትና ፡ የደ ስታ ፡ መብትዋን ፡ ያላግባብ ፡ የተቀማች ፡ መሆንዋን ፡ አውቆ ፡ የሚያዝን ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ስለነበረ ፡ የወጣትነት ፡ ስሜትዋን ፡ የሚያውቅና ፡ የሚያከብር ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ስለነበረ ፡ የልብዋን ፡ ምኞት ፡ ስትነግረው ፡ በቁጣ ፡ ፈንታ ፡ ምክር ፡ የሚሰጣት ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ስለነበረ ፡ ከዘመዶችዋ ፡ ሁሉ ፡ ካባት ፡ ከናትዋ ፡ ሳይቀር ፡ አብልጣ ፡ እሱን ፡ ትወድ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የጠላትዋ ፡ ጠላት ፡ ስለነበረ ፤ ጉዱ ፡ ካሳ ፡- የውበት ፡ አበባዋ ፡ ሳታጌጥበት ፡ እንዲደበዝዝ ፡ የሞቀ ፡ የወ ጣትነት ፡ ልብዋ ፡ ሳትወድበት ፡ እንዲቀዘቅዝ ፡ ለፈረደባት ፡ እርጌ ፡ ስራት ፡ ለተባለ ፡ ጠላትዋ ፡ ጠላት ፡ ስለነበረ ፡ በጣም ፡

ትወደው ፡ ነበር ። የጋራ ፡ ጠላት ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ መዋደዳ ቸው ፡ መተሳሰባቸው ፡ መተጋገዛቸው ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ስለ ዚህ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ እቁም ፡ ያስቀረ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ከሚ ኖርበት ፡ ማህበር ፡ መንፈሱ ፡ እንዲሸፍት ፡ አድርጎ ፡ ያባረረ ፡ እርጌ ፡ ስራት ፡ የሚባል ፡ የጋራ ፡ ጠላት ፡ ስለነበራቸው ፡ ሁለቱ ፡ ይዋደዱ ፡ ይተሳሰቡ ፡ ይተጋገዙ ፡ ነበር ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የወጣቶችን ፡ አለም ፡ ከአዋቆች ፡ አለም ፡ በሚለዩው ፡ ድንበር፡ በአርባ ፡ ዘመኑ ፡ ላይ ፡ ስለነበረ ፡- የወጣቶችን ፡ ስሜት ፡ ገና ፡ ያልረሳ ፡ ገና ፡ ያልሳተ ፡ የአዋቆችን ፡ አስተዋይነት ፡ የተመለ ከተ ፡ በመሆኑ ፡ ለወጣትነት ፡ ስሜት ፡ ተካፋይዋ ፡ ወዳያው ፡ መካርዋና ፡ አስተማሪዋ ፡ ነበር ። ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ ዳዊት ፡ ያስደገሙ ፡ ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ መልከ ፡ ማርያም ፡ መልከየሱ ስና ፡ መልከ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ያስተማሩ ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ የንስሀ ፡ አባት ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ፡ ይሁኑ ፡ እንጂ ፡ አእምሮዋን ፡ ደህና ፡ አድ ርጎ ፡ ያነጸው ፡ አስተያየትዋን ፡ ሰፋ ፡ ባለ ፡ መንገድ ፡ እንዲ መራ ፡ ያደረገው ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ነበር ።

ጉዱ ፡ ካሳን ፡ በሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ፊት ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን፡ በጉዱ ፡ ካሳ ፡ ፊት ፡ በክፉ ፡ እንስቶ ፡ በሰላም ፡ የሚሄድ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ስም ፡ በክፉ ፡ ሲነሳ ፡ የሰማ ፡ እንደሆነ ፡ ተጣልቶ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተደባድቦ ፡ ሰው ፡ ፈንክቶ ፡ ወይም ፡ ተፈንክቶ ፡ ይገባ ፡ ነበር ። እንዲሁም፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ የጉዱ ፡ ካሳ ፡ ስም ፡ በክፉ ፡ ሲነሳ ፡ የሰማች ፡ እንደሆነ ፡ ተጣልታ ፡ ሀሜተኛውን ፡ ለመምታት ፡ ወይም ፡ ለመስደብ ፡ የምትችል ፡ እንኳዋ ፡ ባትሆን ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እልቅሳ ፡ ትሄድ ፡ ነበር ።

እንድ ፡ ቀን ፡ እፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሆኖ ፡ ፊታውራሪንና ፡ ምሽታቸውን ፡ ለመጠዩቅና ፡ በመጠየቅ ፡ ስም ፡ የምሳ ፡ ሰአት ፡ አይተው ፡ ለቅልውጥ ፡ የመ ጡት ፡ እንዲሁም ፡ ከፊታውራሪ ፡ እንዳንድ ፡ ጉልቶች ፡ ለአቤ ቱታ ፡ የመጡት ፡ ሰዎች ፡ ምሳቸውን ፡ በልተው ፡ እንዳንድ ፡ ብርሌ ፡ ጠላ ፡ ጠጥተው ፡ ክወጡ ፡ በሁዋላ ፡ - ባዘቦት ፡ ቀን ፡

ዘወትር ፡ እንደሚደረገው ፡ ዘመዶች ፡ የሆኑና ፡ ልዩ ፡ አስተያ የት ፡ የሚደረግላቸው ፡ ብቻ ፡ ተመርጠው ፡ እንዲቆዩ ፡ ተደረ ገና ፡ ለቆዩት ፡ ሁሉ ፡ ጠጅ ፡ መጣላቸው ። በዛብህ ፡ ቦጋለም ፡ ከቤተ ፡ ዘመድ ፡ ተቆጥሮ ፡ ከቆዩት ፡ መሀከል ፡ ነበር ። መጀመ ርያ ፡ የመጣለትን ፡ ጠጅ ፡ ቶሎ ፡ ጠጥቶ ፡ ወደተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ለመሄድ ፡ ሲነሳ ፡ "ቆይ ፡ ድገም ፡ በሎ ፡" አሉት ፡ ፊታውራሪ።

"የምቸኩልበት ፡ ጉዳይ ፡ አለኝ ፡ ጌታዬ ፡" አለ ፡ በዛብህ፡ ምስጋናውን ፡ ትንሽ ፡ እጅ ፡ በመንሳት ፡ ገልጾ ።

"እንግዲያስ ፡ ለራት ፡ እንዳትቀር !" አሉ ፡ ፊታውራሪ።

በዛብህ ፡ ስንብቱንም ፡ ምስጋናውንም ፡ አጣምሮ ፡ ለመግ ለጽ ፡ ራሱ ፡ መሬት ፡ እስኪነካ ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ ሲወጣ ፦

" ሁልጊዜ ፡ እንገቱን ፡ የደፋ ፡ የማይለወጥ ፡ ልጅ ፡ አሱን ፡ እዩሁ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

"በዛብህ ፤ ምን ፡ መሰል ፡ አለው ! ብቻ ፡ ትምክህቱን ፡ ከኔ ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የለም ፡ ማለቱን ፡ ቢተወ ፡ ጥሩ ፡ ነበር፣ በተረፈ ፡ መሰሉ ፡ የለውም ።" አሉ ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ።

"እርስዎ ፡ ደግሞ ፡ ዘሆን ፡ ዘሆን ፡ የሚያከክለው ፡ የራ ስዎ ፡ጉድለት ፡ ሳይታይዎ ፡ በሌሎች ፡ ላይ ፤ የሌለው ፡ ጉድለት፣ ይታይዎታል ! እንዲህ ፡ ያለው ፡ ደግ ፡ አይደለም ፤ የዲማውን !" ሲሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ትንሽ ፡ እንደማፈር ፡ አሉና ፡ ዝም ፡ አሉ ።

"በዛብህ ፡" አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ "በዛብህ ፡ አንገቱን ፡ የደፋ ፡ የጌታውን ፡ ምንጣፍ ፡ የማይረግጥ ፡ ማለት ፡ ወሰኑን ፡ የሚያውቅ ፡ ቦታውን ፡ የሚያውቅ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ የተ ማረ ፡ ማስፈያ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ታዲያ ፡ መሰንበቻውን ፡ ሳስብ ፦ ሰብለን ፡ ውዳሴ ፡ ማርያምና ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ትርጉም ፡ ጽሀ ፈት ፡ ጭምር ፡ ቢያስተምራት ፡ ምን ፡ አለ ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ መጣብኝ ። እናትዋ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ከንግስትነታቸው ፡ ይልቅ ፡ ስማቸው ፡ የተጠራ ፡ በትምህርታቸው ፡ በእውቀታ ቸው ፡ ነው ።"

"አይ ፡ ጽህፈት ፡ እንኳዋ ፡ ምን ፡ ያደርግላታል ! ውዳሴ፡ ማርያምና ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ትርጉም ፡ ብትማር ፡ ጥሩ ፡ ነው ፤

መቼም ፡ የትምህርት ፡ ክፉ ፡ የለውም ፤ ለማስተማሩ ፡ ግን ፡ ከበ ዛብህ ፡ ይልቅ ፡ ካሳ ፡ዳምጤን ፡ አስተምራት ፡ ብንለው ፡ ደስ ታውን ፡ አይችለውም ፤ በዛብህ ፡ ስራህን ፡ ጥለህ ፡ ልጃችነን ፡ አስተምር ፡ ስንለው ፡ እንዳይከፋው ! ” አሉ ፡ ምሽታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ።

“ ጉዱ ፡ ካሳ ? ” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ እንደመሳቅ ፡ ብለው ። ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ፊትዋ ፡ ከመቅጽበት ፡ ሲለወጥ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

“ አይ ፡ እሱ ፡ እንኳዋ ፡ አይሆንም ። ” አሉ ፡ ልጅ ፡ ተፈራ ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ወንድም ፤ የጉዱ ፡ ካሳ ፡ እኅት።

“ እንዲያው ፡ እሱዋ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ትላ ለች ፡ ሰው ፡ አገኘሁ ፡ ብላ ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፊታቸውን ፡ ከምሽታቸው ፡ አዙረው ።

“ አሳቡ ፡ ከሰው ፡ አሳብ ፡ አለመግጠሙ ፡ ካልሆነ ፡ በት ምህርት ፡ መቸም ፡ እሱን ፡ የሚያክል ፡ የለም ፡ ሲሉ ፡ እሰማ ለሁ ፡ ምን ፡ ላድርግ ? ” አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ የሀታቸው ፡ ልጅ ፡ ከባእድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከቤተ ፡ ዘመድ ፡ ማህበር ፡ ጭምር ፡ እንዲወጣ ፡ የተፈረደበት ፡ በመሆኑ፡ ሲያዝኑ ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የባላቸውን ፡ የቁጣ ፡ ምልክት፡ ስላዩ ፡ ፍራት ፡ ገብቶዋቸው ።

“ እሱ ፡ ነውና ፡ ዋናው ፡ ነገር ! አሳቡ ፡ ከሰው ፡ አሳብ ፡ አለመግጠሙ ፡ ነውኮ ፡ ዋናው ፡ ነገር ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የምሽታቸውን ፡ ትንሽ ፡ ወደሁዋላ ፡ ማፈግፈግ ፡ ስላዩ ፡ ፊታ ቸውን ፡ እንደገና ፡ ወደሳቸው ፡ መልሰው ።

“ አዩሽ ? ” አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ፊታውራሪ ። ” ሰው ፡ ለማ በተግር ፡ ሚዛኑ ፡ ያልተቃወሰ ፡ የተካከለና ፡ ጤናማ ፡ የሆነ ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያስፈልጋል ። ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ . . . . ” ብለው ፡ ሊናገሩ ፡ ያሰቡትን ፡ ሳይቀጥሉ ፡

“ አእምሮው ፡ የተቃወሰ ፡ አእምሮው ፡ ትክክል ፡ ያል ሆነ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ አያ ፡ ካሳን ፡ አእምሮው ፡ ያልተካከለ ፡ የሚ ለው ! ” አለች ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አቋዋረጠችና፡ አባትና ፡ እና ትዋ ፡ መብረቅ ፡ እንደመታቸው ፡ ደርቀው ፡ ቀሩ ። “ አዎ ፡

የሱ ፡ አእምሮ ፡ በሚደርስበት ፡ ሊደርስ ፡ የማይችል ፡ ጎደሎ ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እያ ፡ ካሳን ፡ ጎደሎ ፡ የሚል ! እዚህ ፡ ያላችሁት ፡ ሁሉ ፡ አእምሮ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተሰብስቦ ፡ ቢጨመቅ ፡ የሱን ፡ አእምሮ ፡ ሩብ ፡ አይመዝንም ፡ ሁላችሁም፡ ጎደሎዎች ፡ ና- አ-አ-አ-አ-ችሁ ! ” አለችና ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ እዩተንቀጠቀጠች ፡ ጡዋ ፡ ብላ ፡ አልቅሳ ፡ ተነስታ ፡ ወደልፍኘዋ ፡ ስትሮጥ ፡ እዚያ ፡ ከነበሩት ፡ አንዳንዶቹ ፡ የታመመች ፡ መስሎዋቸው ፡ ሊይዙዋት ፡ ሞከሩ ፤ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የጉዱ ፡ ካሳ ፡ ስም ፡ በክፉ ፡ ሲነሳ ፡ መቆጣትዋን ፡ የሚያውቁት ፡ ግን ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ የፊትዋን ፡ መለዋወጥ ፡ ሲመለከቱ ፡ ቆይተው፡ ስለነበር ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ አሉ ።-

ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አባትና ፡ እናትዋን ፡ ፈሪና ፡ አክባሪ ፡ ነበረች ። እንኳዋን ፡ ሀይለ ፡ ቃል ፡ ልትናገራቸው ፡ እንኳዋን ፡ ልትሰድባቸው ፡ በነሱ ፡ ፊት ፡ ሌሎችን ፡ ሀይለ ፡ ቃል ፡ ተናግራ ፡ በነሱ ፡ ፊት ፡ ሌሎችን ፡ ሰድባ ፡ አታውቅም ። በሚረባውም ፡ በማይረባውም ፡ ሲሰድቡዋት ፡ ሲያዋርዱዋት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሲመትዋት ፡ እንኳዋ ፡ ለብቻዋ ፡ እልፍኝዋ ፡ ገብታ ፡ ታለቅሳለች ፡ እንጂ ፡ እፊታቸው ፥ የቁጣ ፡ መልክ ፡ አሳይታ ፡ ወይም ፡ አልቅሳ ፡ አታውቅም ፡ ነበር ።

አባት ፡ እናትዋ ፡ በበኩላቸው ፡ ካሳ ፡ ዳምጤን ፡ በጣም ፡ እንደምትወድና ፡ ሰው ፡ በክፉ ፡ ሲነሳ ፡ እንደማትወድ ፡ ቢያውቁም ፡ የሱ ፡ መታማት ፡ የወባ ፡ በሽታ ፡ እንደያዛት ፡ እንዲያ ፡ ያንቀጠቅጣታል ፤ እንደ ፡ እብድ ፡ ብቻዋን ፡ ያለች ፡ እስመስሎ፡ እንዲያ ፡ ያጋልጣታል ፤ ፈሪና ፡ አፋራምነትዋን ፡ አስወግዶ ፡ አባትዋን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ እንድትሰድብ ፡ ያደርጋታል ፡ ብለው፡ እንኳዋን ፡ ሊያምኑ ፡ አይጠረጥሩም ፡ ነበር ። በተለይ ፡ አባትዋ፡ ለሷ ፡ የነበራቸው ፡ ፍቅር ፡ ከማንም ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ስለነበረና ፡ እሷዋም ፡ ለሳቸው ፡ የነበራት ፡ ፍቅር ፡ የዚያኑ ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ስለነበረ ፡- ጉዱ ፡ ካሳን ፡ እንኳዋን ፡ ማግት ፡ገድለው ፡ ሲቀብሩት ፡ ብታይ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ታለቅሳለች ፤ ያን ፡ ያክል ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ድምጥዋን ፡ ከፍ ፡ አድርጋ ፡ ታዋርደኛለች ፡ ብለው ፡ የማያምኑ ፡ ስለነበሩ ፡- እንዲያ ፡ ለማ

ልቀስ ፡ እንዲያ ፡ ለመንቀጥቀጥ ፡ እንዲያ ፡ እፍዋን ፡ ሞልታ ፡ አባትዋን ፡ ለመስደብ ፡ ያደረሳት ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ፍቅር ፡ የበለጠ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ መኖር ፡ አለበት ፡ ብለው ፡ አሳባቸው ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ምክናያት ፡ ፍለጋ ፡ ሄደ ።

ራሳቸውን ፡ ወደላይ ፡ እንጋጠው ፡ ጣራ ፡ ጣራውን ፡ ሲመለከቱ ፡ ዘለግ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ቆይተው ፡ "አዎ ፤ ምክንያቱ ፡ ሌላ ፡ ነው ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አይኖቻቸውን ፡ እጣራው ፡ ላይ ፡ ከሰቀሉበት ፡ አውርደው ፡ እፊታቸው ፡ የተቀመጡትን ፡ ሰዎች ፡ እያዩ ፡ " ልጂ ፡ እንዲህ ፡ ያለቀሰች ፡ ሆድ ፡ ብሰዋት ፡ ነው ። አሁን ፡ በሀያ ፡ አምስት ፡ አመትዋ ፡ ቤት ፡ ሰርታ ፡ ንብረት ፡ አበጅታ ፡ ልጅ ፡ መባልዋ ፡ ቀርቶ ፡ እናት ፡ የምትባልበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ባለመሆኑ ፡ ሆድ ፡ ብስዋት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ብላ ፡ እንዳልሰደበችኝ ፡ አውቃለሁ ፡" አሉና ፡ እንደገና ፡ አይኖቻቸውን ፡ ወደጣራው ፡ ትኩር ፡ አድርገው ፡ ቆይተው ፡ ሲመልሰዋቸው ፡ እንባ ፡ ሞልተው ፡ ተመለሱ ። " እውነትዋ ፡ ነው ፡ ትስደበኝ ፡ " አሉ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ እየወዘወዙ ። " ራሱ ፡ ተከብሮ ፡ ልጁን ፡ ለማስከበር ፡ የማይችል ፡ አባት ፡ እንኩዋን ፡ ሲሰድቡት ፡ ሲመቱትም፡ አመመኝ ፡ ሊል ፡ አይገባውም ! እስቲ ፡ እና-እናንተ ፡ ፍ-ረዱ፡" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ንዴትና ፡ ልቅሶ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተደባልቆ ፡ እየተናነቃቸው ፡ በተሰበረ ፡ ድምጽ ፡ " እስቲ ፡ ፍረዱ ፡ ክብርዋን ፡ ጠብቃ ፡ ተጠንቅቃ ፡ ከልፍኝ ፡ ሳትወጣ ፡ ያደገች ፡ ልጁ ገረድ ፡ እንደ ፡ ጋለሞታ ፡ በፈትንነት ፡ ላግባሽ ፡ ተብላ ፡ ስትሰደብ ፡ ስትዋረድ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ የሚመለከት ፡ አባት ፡ ሊደፈር ፡ ሊሰደብ ፡ አይገባውም ? " አሉና ፡ እንደገና ፡ አይኖቻቸውን ፡ ወደጣራው ፡ ልከው ፡ ከጣራው ፡ መልስ ፡ እንደሚጠባበቁ ፡ ሁሉ ፡ እንጋጠው ፡ ትንሽ ፡ እንደቆዩ ፡ ፊታቸው ፡ ካዘን ፡ ወደቁጣ ፡ ተለወጠ ። ወዲያው ፡ አይኖቻቸውን ፡ ከጣራው ፡ ወደሰዎች ፡ መልሰው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ መላልሰው ፡ እንኮራፉና ፡ " እፋለመዋለሁ ፡ " አሉ ። " ፊታውራሪ ፡ እሰኬን ፡ በመረጠው ፡ መሳርያ ፡ እፋለመዋለሁ ! በጦር ፡ ቢል ፡ በጦር ፡ በጎራዴ ፡ ቢል ፡ በጎራዴ ፡ ያለዚያም ፡ በጥይት ፡ በመረጠው ፡ መሳርያ ፡ እፋለመ

ዋለሁ ። እኔ ፡ መሸሻ ፡ እኔ ፡ የደፋር ፡ ጌታ ! ” አሉ ፡ የማንባራቸው ፡ መንታ ፡ ኋንድ ፡ ከማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ረዝሞ ፡ እድሜ ፡ ባሳሳው ፡ የራስ ፡ ጠጉራቸው ፡ ውስጥ ፡ ተገትሮ ፡ እዩታዩ ።

“ ምነው ፡ ጌታዩ ! ” አሉ ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ፡ ተነስተው ። “ ምነው ፡ ጌታዩ ፡ ያለቀ ፡ ነገር ፡ እንደገና ፡ ይጀምራሉ ! የስብለ ፡ ልቅሶ ፡ ለርስዎ ፡ አዲስ ፡ ሆነብዎ ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ ላለነው ፡ ሁሉ ፡ የተለመደ ፡ ነው ። የካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ስም ፡ በክፉ ፡ ሲነሳ ፡ ሰምታ ፡ ሳትጣላ ፡ ወይም ፡ ሳታለቅስ ፡ ገዞ ፡ ብላ ፡ ስታሳልፍ ፡ አይቻለሁ ፡ የሚል ፡ እዚህ ፡ ካሉት ፡ ሁሉ ፡ ይገኝ ፡ እንደሆነ ፡ እስቲ ፡ እንድባንድ ፡ ይጠይቁ ! ስለዚህ ፡ እባክዎ ፡ በሚወዱት ፡ በጻማው ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሰዋ ፡ ልቅሶ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ የሰዋ ፡ ልቅሶ ፡ የሰይጣን ፡ መላክተኛ ፡ ሆኖ ፡ ትናንት ፡ በደሀና ፡ የተፈጸመው ፡ ነገር ፡ አይፍረስ ። ሰይጣን ፡ የዋዛ ፡ አይደለም ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ለማበላሸት ፡ የሚገባበት ፡ አይታይምና ፡ እንወቅበት ! ”

“ ይበሉ ፡ ለማሁዎ ፡ ይቀመጡ ! ልጄን ፡ ከማንም ፡ የበለጠ ፡ እኔ ፡ ስለማውቃት ፡ የሰዋን ፡ ባህሪ ፡ እንዲነግረኝ ፡ የምጠይቀው ፡ ሰው ፡ እዚህ ፡ የለም ። ፊታውራሪ ፡ እስኬን ፡ እፋለማለሁ ፡ ብዬ ፡ ካፌ ፡ ወጥቶዋል ፡ የተፋሁትን ፡ መልሼ ፡ መዋጥ ፡ ልማዶ ፡ አይደለምና ፡ ይልቅ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ሂድና፡ሸማ፡ ጥለህለት ፡ ወዲያውም ፡ መሳርያ ፡ አስመርጠህ ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፡ አስወስነህ ፡ ና ፡ ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

“ አይደለም ፡ ጌታዩ ! እስቲ ፡ አስቀድመን ፡ ሸማ ፡ ከመጣልና ፡ መሳርያ ፡ ከማስመረጥ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ እንነጋገር ! በመገደል ፡ ወይም ፡ በመሞት ፡ ብ[illegible] ፡ አይደለምኮ ፡ የሰው ፡ ክብር ፡ የሚጠበቀው ! የሚፋለሙት ፡ ሰው ፡ መሳርያውን ፡ እፊትዎ ፡ ጥሎ ፡ ይማሩኝ ፡ ፈራሁ ፡ ቢሉም ፡ ያሸናፊነትን፡ ክብር ፡ ተቀብለው ፡ ይምሩታል ፡ እንጂ [illegible] ሁ ፡ ክብሬ ፡ አይጠበቅም ፡ [illegible] መሳርያውን ፡ እንደ[illegible] ንገድሉትም። እንግዲያስ ፡ [illegible] መለመን ፡ ከሆነ ፡ [illegible] ልገው ፡ ፊታውራሪ ፡ [illegible] ድጋን ፡ ምህረት [illegible] ን ፡ ለማ[illegible]

ረግ ፡ ከጨረስን ፡ በሁዋላ ፡ ሳልፋለም ፡ የሚያቀርበውን ፡ ምህ
ረት ፡ ልመና ፡ አልቀበልም ፡ ቢሉ ፡ በተመልካችና ፡ በሰሚ ፡
ፊት ፡ ያስፈርድብዎታል ፡ እንጂ ፡ አያስፈርድልዎትም ። ከዚ
ህም ፡ ሌላ ፡ ዛሬ ፡ እርስዎ ፡ የሚፋለሙትን ፡ የሚገላገሉበት ፡
ነውንጂ ፡ የሚፋለሙበት ፡ ጊዜ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ በርስ
ዎም ፡ በኛም ፡ ሰው ፡ እንዳይፈርድብን ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ እንዲተ
ውትና ፡ ነገሩ ፡ ትናንት ፡ በወሰነው ፡ እንዲያልቅ ፡ ሁላችንም፡
እንለምንዎታለን ፡ " አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ተነስተው ።
" የሱን ፡ ኀልማሳነት ፡ የኔን ፡ መሽምገል ፡ አውቃለሁ ፤
እድሜ ፡ ቢሸሽግ ፡ አቅም ፡ አይሸሽግም ። እሱ ፡ ኀልማሳ ፡ ነው ፤
ጀግና ፡ ነው ። እኔ ፡ በሱ ፡ አይን ፡ ደከሚያለሁ ፤ ሬሳ ፡ ሆኛለሁ ፤
ቢሆንም ፡ እፋለመዋለሁ ። ብገድለው ፡ የመሸሻ ፡ ሬሳው ፡ እን
ኩዋ ፡ ጀግና ፡ ገደለ ፡ እባላለሁ ፤ ቢገድለኝ ፡ ጀግናው ፡ ሬሳ ፡ ገደለ ፡
ነው ፡ የሚባለው ። በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ክብሩ ፡ የኔ ፡ ነው ። በቃ፡
እንግዲህ ፡ ዝም ፡ በሉ ፡ እንዳንጣላ ! የተፋሁትን ፡ መልሸ ፡ አል
ውጥም ፡ ብዬ ፡ ነግሬያችሁዋለሁ ። ሲሆን ፡ እገድለዋለሁ ፤ ቢገ
ድለኝም ፡ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ሞት ፡ አላገኝምና ፡ አሁን ፡ ድንገት ፡
ያጋጠመኝን ፡ ማለፊያ ፡ ሞት ፡ አታስቀሩብኝ ! " አሉ ፡ ፊታው
ራሪ ፡ በቁጣ ። የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ ቁጣቸውን ፡ ሲያዩ ፡ የሚያ
ደርጉትን ፡ አጥተው ፡ ዝም ፡ አሉ ። ምሽታቸው ፡ ብቻ ፡ " ሁላ
ችሁም ፡ እንደኔ ፡ ደካማ ፡ አድርጎ ፡ ያልፈጠራችሁ ፡ ብርቱዎች፡
ናችሁ ፤ አታስሩዋቸውም ? እኔን ፡ ከነልጂ ፡ እንዲሁ ፡ አፍስሰ
ውን ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ እንዲሄዱ ፡ ሲያማክሩዋችሁ ፡ ዝም ፡ ብላ
ችሁ ፡ ትሰዱዋቸዋላችሁ ? ምነው ፡ እርስዎስ ፡ የነፍስ ፡ አባት ፡
የተባሉት ፡ አይገዝቱዋቸውም ? "እያሉ ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር። ነገር፡
ግን ፡ የፊታውራሪ ፡ ቁጣ ፡ ሁሉንም ፡ ዝም ፡ አሰኛቸው ።
ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ሳይሽመግሉ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ተጣል
ተው ፡ ካልተከሰሱ ፡ እሳቸው ፡ ከሰው ፡ በዘመድ ፡ ይሁን ፡ በአ
ካል ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ አዩሁዋቸው ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ አልነ
በረም ። ብዙ ጊዜ ፡ ከሰው ፡ አይጣሉም ፤ ከተጣሉ ፡ ግን ፡ እከሳ
ለሁ ፡ ከማለት ፡ እፋለማለሁ ፡ ማለት ፡ ይቀናቸዋል ፡ ይባላል ።
" ለዳኛ ፡ አቤት ፡ ማለት ፡ ደካማነትን ፡ ወይም ፡ ፈሪነትን ፡

አምኖ ፡ ርዳታ ፡ መሰመን ፡ ነው ፡፡ " ይሉ ፡ ነበር፡፡

ተመትቶ ፥ ወይም ፡ ተሰድቦ ፡ ካሉኝ ፡ ከሚል ፡ መትቶ ፡ ወይም ፡ ሰድቦ ፡ ካሳ ፡ የሚከሰውን ፡ የሚያከብሩ ፡ መሆናቸው ፡ በማንም ፡ ዘንድ ፡ የታወቀላቸው ፡ ነበሩ ፡፡ አገር ፡ ገገር ፡ ሆነው ፡ በዳኝነት ፡ ወንበር ፡ ይቀመጡ ፡ በነበር ፡ ጊዜ ፡ እንኩዋ ፡ ተመ ትቶ ፡ ላቤቱታ ፡ የመጣባቸውን ፡ "እጅ ፡ የለህም ፡ ወይ ? "፥ ተሰድቦ ፡ የመጣባቸውን ፡ " አፍ ፡ የለህም ፡ ወይ ? " ይላሉ ፡ እዩተባለ ፡፡ በሰፊው ፡ ይነገር ፡ ስለነበረና ፡ ራሳቸው ፡ ሀይለኛ ፡ ሆነው ፡ ሀይለኞችን ፡ የሚደግፉ ፡ መሆናቸው ፡ የታወቀ ፡ ስለ ሆነ ፥ ከተነቀፉባቸውና ፡ ግዛታቸው ፡ እንዲወሰድባቸው ፡ ካደረ ጉት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይባላል ፡፡ ብቻ ፡ ከዚህ ፡ የጉልማስነት ፡ በሽታ ፡ እድሜ ፡ አድኖዋቸዋል ፡ ተብሎ ፡ ሲታ መን ፡ በሰባ ፡ አመታቸው ፡ እንደገና ፡ አገረሸባቸው ፡፡

# ምእራፍ ፡ ፲፫ ፡

## ፍልሚያ ፡

ፊታውራሪ ፡ አሰጋኸኝ ፡ በሰው ፡ የቢቸናና ፡ የአካባቢው ፡ ገዢ ፡ የባላባት ፡ ልጅ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ መልካቸው ፡ የተዋበ ፣ ቁመታቸው ፡ ዘለግ ፡ ብሉ ፡ አካላቸውን ፡ ስጋ ፡ ያልከበደው ፣ ልብስና ፡ ትጥቅ ፡ አሳማሪ ፣ ወዲያው ፡ ጥሩ ፡ ባለሙያ ፡ ነበሩ ። በሰንጠረዥና ፡ በስሉስ ፣ በበገናና ፡ በተኩስ ፣ በፈረስና ፡ በጉግስ ፡ እንኳዋን ፡ የሚበልጣቸው ፡ የሚተካከላቸው ፡ አልነበረም ። በዋሉበት ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ሁሉ ፡ ከመመስገን ፡ በቀር ፡ ታምተው ፡ የማያውቁ ፣ ከሴት ፡ በቀር ፡ ጀግና ፡ ያሸንፋቸዋል ፡ የማይባሉ ፣ ሳያውቁ ፡ ካልሆነ ፡ አውቀው ፡ ፍርድ ፡ የማያጉዋድሉ ፣ የሌሎችን ፡ መብላት ፡ የራሳቸውን ፡ ማብላት ፡ የሚወዱ ፣ የሰጡትንም ፡ ሆነ ፡ የተቀበሉትን ፡ መልሰው ፡ የማያስታውሱ ፣ የበደሉትንም ፡ ሆነ ፡ የተበደሉትን ፡ ወዲያው ፡ የሚረሱ ፣ እንደ ፡ ጀግኖች ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ይጎዳኛል ፡ ብለው ፡ ጥርጣሬ ፡ ያልነበራቸው ፣ እንደቅኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ የማነግራቸው ፡ በሙሉ ፡ እውነት ፡ የሚመስላቸው ፣ የጀግኖችን ፣ የቅኖችንና ፡ የጌቶችን ፡ ባህሪ ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበው ፡ የያዙ ፣ የውነተኛ ፡ ጀግና ፣ የውነተኛ ፡ ቅንና ፡ የውነተኛ ፡ ጌታ ፡ ነበሩ ።

ከመንፈሳቸው ፡ ታላቅነትና ፡ ከልባቸው ፡ ለጋስነት ፡ የተነሳ ፡- አንዳንድ ፡ ሰባዊ ፡ ድካሞች ፡ ነበርዋቸው ። ለምሳሌ ፡- ከማናቸውም ፡ የበለጠ ፡ ሴትና ፡ ዘፈን ፡ አጥብቀው ፡ ይወዱ ፡ ነበር ። ከጀግና ፡ ወይም ፡ ከሽማግሌ ፡ አዝማሪ ፡ የሚያከብሩ ፣ ከንጉስ ፡ ቀጠሮ ፡ ለሴት ፡ ቀጠሮ ፡ ቅድሚያ ፡ የሚሰጡ ፡ ነበሩ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከጉንቻ ፡ ገዢ ፡ ከደጃዝማች ፡ ይማም ፡ ጋር ፡ የነበረ ፡ ጠባቸው ፡ እዬከረረ ፡ ሄዶ ፡ መዋጋታቸው ፡ የማይቀር ፡ ስለመሰለ ፡ ደጃዝማች ፡ ይማም ፡ ጠመንጃና ፡ ጥይት ፡ በብዛት ፡ ሲገዙ ፡ ያዩ ፡ ሰው ፡ “ማን ፡ በጠመንጃና ፡ በጥይት ፡ ብዛት ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌን ፡ ሲያሸንፍ ፡ አይተው ፡ ነው ፡ ደጃዝማች ፡

ይህን ፡ ያክል ፡ ጠመንጃና ፡ ጥይት ፦ በመግዛት ፡ ገንዘባቸውን ፡ የሚያባክኑ ? ይልቅ ፡ መካሪ ፡ አጥተው ፥ ነውንጂ ፡ አስር ፡ ቆነጃጅት ፡ ፈልገው ፡ መሰንቆ ፡ አስይዘው ፡ እጠሩ ፡ ሜዳ ፡ ቢያዘፍኑ ፡ ፊታውራሪ ፡ እስጌን ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ እንኳ ፡ ሳይተኩሱ ፡ ከነስራዊታቸው ፡ እንደ ፡ በግ ፡ መንጋ ፡ ነድተው ፡ እንረንቶዋቸው ፡ አግብተው ፡ ሊያስርዋቸው ፡ ይችሉ ፡ ነበር ! ” አለ ፡ ይባላል ።

ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ቆንጆ ፡ ሴት ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ከመውደዳቸው ፡ የተነሳ ፡ ቆንጆ ፡ ሴት ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አእምሮ ፡ የሚሰውር ፡ በሽታ ፡ እንዳለባቸው ፡ ሰዎች ፡ ራሳቸውን ፡ መግዛት ፡ ያቅታቸው ፡ ነበር ። በጦርነትም ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ ከተተኮሰ ፡ በሁዋላ ፡ ከጣላት ፡ ጋር ፡ ተደባልቀው ፡ በጎራዴና ፡ በጦር ፡ የጨበጣን ፡ የሚሰሩትን ፡ የጀግንነት ፡ ሙያ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከድል ፡ በሁዋላ ፡ ሰዎቻቸው ፡ ሲተርኩላቸው ፡ ትዝታው ፡ ይመጣላቸዋል ፡ እንጂ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ አስበውና ፡ አውቀው ፡ ያልሰሩት ፡ መሆናቸውን ፡ ራሳቸው ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ የሚያስገርመው ፡ የጦር ፡ እቅዳቸውን ፡ በጥንቃቄ ፡ አሰናድተውና ፡ የሚያደርጉትን ፡ አውቀው ፡ በሚገጥምዋቸው ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ሁልጊዜም ፡ ድል ፡ የሚያገኙ ፡ እሳቸው ፡ ነበሩ ። ስለዚህ ፡ “የፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ የቢችና ፡ ጊዮርጊስ ፡ ነው ፡ ” እየተባለ ፡ ይነገር ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ሴት ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ መውደዳቸውን ፡ የሚያውቁ ፡ ሰዎቻቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጥቅም ፡ ሲፈልጉ ፡ ሴት ፡ ይዘው ፡ በመቅረብ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ለማቅረብ ፡ ተስፋ ፡ በመስጠት ፡ የሳቸውን ፡ ክብርና ፡ ጥቅም ፡ የሚጎዳ ፡ ወይም ፡ አስተዳደርና ፡ ፍርድ ፡ የሚያጎድል ፡ ብዙ ፡ መጥፎ ፡ ስራ ፡ ያሰርዋቸው ፡ ነበር ። እሳቸውም ፡ የሚሰሩት ፡ መጥፎ ፡ ስራ ፡ ክብራቸውንም ፡ ሆነ ፡ ጥቅማቸውን ፡ ወይም ፡ ባገረ ፡ ገዥነታቸው ፡ ስላስተዳደርና ፡ ስለፍርድ ፡ የነበረባቸውን ፡ አላፊነት ፡ የሚጎዳ ፡ መሆኑን ፡ ለጊዜው ፡ ማየት ፡ አይችሉም ፡ ነበር ። ካለፈ ፡ በሁዋላ ፡ ብዙ ፡ የሰሩት ፡ ስራ ፡ ያስከተለውን ፡ ጉዳት ፡ ሲመለከቱ ፡ ይጸጸታሉ ። ለግል ፡ ጥቅማቸው ፡ ገፋፍተው ፡ እስተት ፡ ላይ ፡ የጣሉዋቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ሳጣሩ ፡ ጊዜ ፡ ይቀየሙዋቸውና ፡ ወዲ

ያው ፡ መልሰው ፡ ሁሉንም ፡ ይረሱታል ።

ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ ባጩ ፡ ጊዜ ፡ የደረሰው ፡ ይህኑ ፡ የመሰለ ፡ ነው ። ለዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አመት ፡ በአል ፡ ታቦት ፡ ለማክበር ፡ በሄዱበት ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ ሲያዩ ፡ ልባቸውም ፡ አእምሮዋቸውም ፡ ተማርኮ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሁሉ ፡ የሚያጋልጥ ፡ ስራ ፡ በዙሪያቸው ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ እንጂ ፡ እሳቸው ፡ አያውቁትም ፡ ነበር ። ምንም ፡ የቆሙበት ፡ የተለያዩና ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፡ ወደሳቸው ፡ ዘወር ፡ ያለች ፡ በመሰላቸው ፡ ቁጥር ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተው ፡ ባይናቸውም ፡ በጃቸውም ፡ ሲጠቅሱ ፡ ባጠገብ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እዩተያዩ ፡ ይስቅባቸው ፡ ነበር ። ጥቅሻቸውን ፡ አላይ ፡ ስትል ፡ በዚያ ፡ ሁሉ ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ እሳቸውና ፡ እሷ ፡ ብቻቸውን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እንደቆሙ ፡ ሁሉ ፡ “ ምን ፡ ክፉ ፡ ነሽ ፡ እባክሽ ፡ ሰው ፡ ሲጨነቅ ፡ ከጉዳይ ፡ የማትጽፊ ! ኧረ ፡ እባክሽ ፡ ባይሆን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደኔ ፡ ዘወር ፡ በይና ፡ ሳቂልኝ ! ነይ ፡ ወዲህ ፡ ቀረብ ፡ በይ ፡ እባክሽ ፡ ነይ ፡ ቢቸና ፡ ቢሆን ፡ እንዲህ ፡ አትጫወችብኝ ፡ ነበርኮ ! ” ይላሉ ፡ በጃቸውም ፡ በራሳቸውም ፡ እዩጠቀሱ ። “ሰውኮ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ያያል ፡ የሚሉትንም ፡ ይሰማል ! ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ አሰግድ ፡ የሚባሉ ፡ አጠገባቸው ፡ የቆሙ ፡ አሽከራቸው ።ከዚያ፡ ከንቅልፋቸው ፡ እንደባነኑ ፡ ሁሉ ፡ ደንግጠው ፡ “እ እ እ ? ” አሉና ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ዘወርወር ፡ ብለው ፡ ከተመለከቱ ፡ በሁዋላ ፡ ሁኔታቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ህልም ፡ ትዝ፡ አላቸውና ፡ “ወዬው ፡ ጉዴ ! ምን ፡ አልሁ ፡ እባክህ ? በሞቴ ፡ ንገረኝ ፡ የሚያጋልጠኝ ፡ ነገር ፡ አደረግሁ ፡ ይሆን ? እግዜር ፡ ያይላትና ፡ ራሴን ፡ አዞረችውኮ ! ምን ፡ አልሁ ፡ ንገረኝ ፡ እባክህ ! ” አሉ ፡ የፍርሀት ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብለው ።

“ እዚህ ፡ አይደለም ፡ እቤት ፡ ስንመለስ ፡ ነው ፡ የምነግርዎ ፡ ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ አሰግድ ፡ እዩሳቁ ።

ወደቤትና ፡ ሲመለሱ ፡ መንገድ ፡ ለመንገድ ፡ ባላምባራስ፡ አሰግድ ፡ የፊታውራሪ ፡ አስጌን ፡ የበቅሎ ፡ ደሀራ ፡ ይዘው ፡ እጃቸው ፡ ሁሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሲያደርጉትና ፡ ሲሉት ፡ የቆዩትን ፡

ከሳቸው ፡ የበለጠ ፡ እንደማያውቅ ፡ ሁሉ ፡ ፊትና ፡ ሁዋላ ፡ ራቅ፡ እንዲል ፡ ተደርጎ ፡ ያሉትንም ፡ ያደረጉትንም ፡ ባላምባራስ ፡እዩ ነገርዋቸው ፡ ሁለቱ ፡ እንደሳቁ ፡ ቢቸና ፡ ገቡ ።

ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ እስኪያጩ ፡ ድረስ ፡ ባላምባራስ ፡ አሰግድና ፡ በዚህ፡ጉዳይ፡ ለመነገድ ፡ የተነሱ ፡ ሰዎቻቸው ፡ ለጉዳዩ ፡ ከሳቸው ፡ የበለጠ ፡ አሳቢዎች ፡ ሆነው ፡ በዲማና ፡ በቢቸና ፡ መሀከል ፡ ተርዋሩጠው ፡ የመተጫጨቱ ፡ ስነ ፡ ስራት ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዲፈጸም ፡ አደረጉ ። ባላምባራስ ፡ አሰግድ ፡ ዋጋቸውን ፡ በግዛታቸው ፡ ላይ ፡ እነከርከር ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ደብር ፡ አገር ፡ እንዲጨመርላቸው ፡ ተስፋ ፡ አገኙ ፡ አዛዡ ፡ ግራዝማች ፡ እጅጉ፡ የወረገና ፡ ጥብቅ ፡ ስለነበሩ ፡ እንዲጸድቅላቸው ፡ ብላታ ፡ ሁል ጊዜ ፡ ፋሲካ ፡ የቢቸናን ፡ ጭቃ ፡ ሹምነት ፡ እንዲያገኙ ፡ ተስፋ፡ ተሰጣቸው ፡ አጭታውም ፡ አስተጫጭዎቹም ፡ ሁሉም ፡ ደስ ፡ ተሰኙ ። ፊታውራሪ ፡ አሰጌን ፡ በመልክ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በጠባይ ፡ በሙያና ፡ በቤት ፡ አስተዳደር ፡ ስትምህርት ፡ ሙሉ ፡ ውበት ፡ ያላት ፡ ምሽት ፡ የማግኘቱ ፡ አሳብ ፡ እድሜያቸውን ፡ ሙሉ ፡ ወግ ፡ ማእርግ ፡ አጥቶ ፡ የኖረው ፡ ቢታቸው ፡ አሁን ፡ በመጨረሻ ፡ ወግ ፡ ማእርግ ፡ የማግኘቱ ፡ አሳብ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ። ባላምባራስ ፡ አሰግድንና ፡ የተንኮል ፡ ጉዋደኞቻቸውን ፡ አገር ፡ ግዛትና ፡ ሹመት ፡ የማግኘቱ ፡ ተስፋ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ። ከዚህ ፡ የዲማው ፡ ጊዮርጊስ ፡ ካወረደው ፡ በረከት ፡ ተካፋይ ፡ ያልሆኑ ፡ የፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ለጊዜው ፡ ተከፉ ። ስለዚህ ፡ በረከቱ ፡ ለነሱም ፡ የሚደርስበትን ፡ ያለዚያ ፡ ለማንም ፡ የማይደርስበትን ፡ ተንኮል ፡ መፍጠር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በሁዋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ፡ የታጨደ ፡ ድርቆሽ ፡ ሲያስከምሩ ፡ ቆይተው ፡ ሲመለሱ ፡ እንደተለመደው ፡ የተከተልዋቸውን ፡ ሁሉ ፡ አዳራሽ ፡ መጠጥ ፡ ጋብዘው ፡ ካሰናበቱ ፡ በሁዋላ ፡ አሜት ፡ ጠባቂዎችና ፡ ወዳጆች፡ነን፡ የሚሉ ፡ ሶስት ፡ መኩዋንንቶቻቸው ፡ ከጌቶች ፡ ጋር ፡ በቆይታ ፡ የሚነጋገሩት ፡ ብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ላጋፋ

ሪው ፡ ነገሩ ።

"ምን ፡ ብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ ይዛችሁልኝ ፡ ወይም ፡ ይዛችሁ ብኝ ፡ መጣችሁ ፡ ልጅ ፡ ስዩም ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደመ ሳቅ ፡ ብለው ።

"የጌታ ፡ ጀሮዎቹ ፡ አሚት ፡ ጠባቂዎች ፡ ወዳጆቹ ፡ ናቸው ፡ እንደሚባለው ፡ በከተማው ፡ ሲወራ ፡ የሰነበተውን ፡ እኛ ፡ ካልነገርነዎ ፡ ለጌታችን ፡ የሚደርስበት ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ የለውም ፡ ብለን ፡ አሁን ፡ እንድንነግርዎና ፡ እንድንመካከር በት ፡ ነው ፡ ምንም ፡ በድካም ፡ ላይ ፡ ቢሆኑ ፡ እንዲቀበሉን ፡ የጠዩቅን ፡ " አሉ ፡ ልጅ ፡ ስዩም ፡ የሚባሉት ፡ ከሶስቱ ፡ መኳ ንንት ፡ አንዱ ።

"ምንድነው ፡ የሚወራው ? ክፉ ፡ እንዳይሆን ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ! "

"ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ስለተደረገው ፡ መተ ጫጨት ፡ ነው ። "

" እኮ ፡ ምንድነው ፡ መተጫጨቱ ፡ ነውር ፡ ነው ? ወይስ ፡ ምንድር ፡ ነው ? "

" ነገሩማ ፡ ምን ፡ ነውር ፡ ነበረበት ፡ ብቻ ፡ ባገራችን ። የሰው ፡ ስም ፡ ለማጥፋት ፡ መሸቀዳደም ፡ የተለመደ ፡ ሆኖ ፡ነው ንጂ ። "

"ባይሆን ፡ ሌላ ፡ ነውንጂ ፡ ምሽት ፡ ማጨት ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ያከፋል ፡ እንዴ ? "

" ግልጽ ፡ አድርገህ ፡ ንገራቸው ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ያሰኝሀል ፡ ልጅ ፡ ስዩም ! በከተማው ፡ የተነሣው ፡ አሁን ፡ ጌቶች ፡ ስስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ተስርገው ፡ ልጃገረድ ፡ ለማግባት ፡ የሚፈልጉ ፡ ይሆን ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ ከድሀው ፡ ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ነው ፡ የሚባል ፡ ወሬ ፡ ነው ። የጌታችን ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ አለመሆ ኑን ፡ ከማንም ፡ የበለጠ ፡ እኛ ፡ እናውቃለን ፡ ብቻ ፡ ይህ ፡ ወሬኛ ፡ ህዝብ ፡ ስተቱን ፡ በቃል ፡ ላስረዳህ ፡ ቢሉት ፡ በጅ ፡ አይልም ፡ ለማስረዳት ፡ በስራ ፡ ማሳዩት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ ያስፈ ልጋል ፡ " አሉ ፡ የሻቃ ፡ ታመነ ።

ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ እንደቆመ ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡

ብለው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ ሲመለከቱ ፡ ቆይተው ፡ “ ጭራሽ ፡ ያላሰብሁት ፡ ነገር ፡ ነውኮ ! ብቻ ፡ . . . . አሳባችን ፡ ይህ ፡ አለ መሆኑንና ፡ ከማንም ፡ አንድ ፡ ገንቦ ፡ ጠላ ፡ እንኳዋ ፡ የማንፈልግ ፡ መሆናችንን ፡ በምን ፡ መንገድ ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ? ”

“ መቼስ ፡ አዋጅ ፡ አይነገር ፤ ሌላም ፡ የምናሳምንበት ፡ መንገድ ፡ የለ ፤ ብቻ ፡ ከዚህ ፡ ችግር ፡ የሚያወጣን ፡ አንድ ፡ነገር፡ ያለ ፡ ይመስለኛል ! ” አሉ ፡ የሻቃ ፡ ታመነ ።

“ ምን ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ያዘን ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብለው ።

“ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቢፈቅዱ ፡ ጋብቻው ፡ በልጃገረድ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በፊት ፡ ወግ ፡ እንዲሆን ፡ ማድረግ ። ልጅቱ ፡ ከሀያ ፡ አምስት ፡ አመት ፡ በላይ ፡ ሆንዋታል ፡ አሉ ፤ ጊዜያቸው ፡ ያለፈ ፡ ልጃገረዶች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አዲስ ፡ አይደለም ። ”

“ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በጣም ፡ ኩሩ ፡ ሰው ፡ መሆናቸውን፤ አውቃለሁና ፡ ይህን ፡ እሺ ፡ የሚሉ ፡ አይመስለኝም ። ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

“ በፈትነት ፡ ካልሆነ ፡ በልጃገረድ ፡ ወግ ፡ አላገባም ፡ ብለው ፡ ጌታችን ፡ ከበረቱ ፡ በመጨረሻ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ እንደሚፈቅዱ ፡ አይጠረጠርም ፤ ወዲያውስ ፡ ዋና ፡ ቁምነገሩ ፡ ጋብቻው ፡ ነውንጂ ፡ የጋብቻው ፡ ስነስራት ፡ ምን ፡ ፍሬ፡አለው ? አሉ ፡ ግራዝማች ፡ ሽፈራው ።

“ ፊታውራሪ ፡ ያልፈቀዱ ፡ እንደሆንስ ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ትንሽ ፡ ሲያስቡ ፡ ቆይተው ።

“ አሁን ፡ እንደተባለው ፡ ጌታችን ፡ የሚጠነክሩ ፡ ከሆነ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ እንደሚፈቅዱ ፡ እኔ ፡ በበኩሌ ፡ ርግጠኛ ፡ ነኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ የሚያስበውን ፡ እንጂ ፡ ሌሎች ፡ የሚያስቡትን ፡ ለማወቅ ፡ አይችልምና ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አሳብ ፡ አሁን ፡ እኛ ፡ ከምንገምተው ፡ የተለዩ ፡ ሆኖ ፡ በልጃገረድ ፡ ወግ ፡ ካልሆነ ፡ ልጄን ፡ አልደርም ፡ የሚሉ ፡ የሆነ ፡ እንደ ሆነ ፡ ለወቃሽና ፡ ለከሳሽ ፡ ጠላት ፡ ከመመቸት ፡ ያኑ ፡ የማይበላ ፡ ከሳ ፡ ከሶ ፡ ውሉን ፡ ማፍረስ ፡ የተሻለ ፡ ይመስለኛል ። የጋብ

ቻም ፡ ሆነ ፡ የሌላ ፡ ደስታ ፡ በክብርና ፡ በማእርግ ፡ እስካሉ ፡ ድረስ ፡ ነው ። በሹመትና ፡ በክብር ፡ ካሉ ፡ ብዙ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ብዙ ፡ ባለሙያ ፡ ሴቶች ፡ ተለምነው ፡ ሳይሆን ፡ ለምነው ፡ ይመጣሉ ፡ ” አሉ ፡ ልጅ ፡ ስዩም ።

ለጊዜው ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ ሲመለከቱ ፡ ቆይተው ፡ በሁዋላ ፡ እፊታቸው ፡ ወደቆሙት ፡ መኳዋንንት ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ “ይሁና ፡ አሁን ፡ ያላችሁት ፡ የሚሻል ፡ ከመሰላችሁ ፡ ይሁን ፤ እናንተ ፡ እንዳላችሁት ፡ ይሁን ፤ ” አሉ ። ወዲያው ፡ እነዚሁ ፡ ሶስት ፡ መኳዋንንት፡መልክቱን ፡ ለፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አደረሱ ።

መጀመርያ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ ሲያጩ ፡ በመሀከላቸው ፡ የነበረው ፡ የእድሜ ፡ ልዩነትና፡ከዚያ ፡ በፊት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ተሰርገው ፡ ልጃገረድ ፡ ማግባታቸው፡ከራሳቸው ፡ አልፎ ፡ ሌላ ፡ ያሳስባል ፡ ብለው ፡ በጭራሽ ፡ ያልጠረጠሩት ፡ ነገር ፡ ነው ። እውነትም ፡ ሶስቱ ፡ ምቀኞች ፡ መኳዋንንት፡ ባቀረቡበት ፡ መልክ ፡ ለጊዜው ፡ ያማ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። እነዚህ ፡ በወዳጅ ፡ ስም ፡ የከበብዋቸው ፡ አጋንንት ፡ የሰሙትን ፡ የማይጎዳ ፡ ወዳልሰሙት ፡ የሚጎዳ ፡ ለውጠው ፡ የሰሙትን ፡ ትንሽ ፡ ካልሰሙት ፡ ብዙ ፡ ጋር ፡ ጨምረው ፡ የሌለ ፡ መሰናክል፡ ፈጥረው ፡ እንድ ፡ ላይ ፡ ክበው ፡ የራስ ፡ ዳሽንን ፡ ተራራ ፡ አሳክለው ፡ ፊታውራሪ ፡ መንገዳቸውን ፡ ካልለወጡ ፡ ያን ፡ መሰናክል፡ ሊያልፉት ፡ እንደማይችሉ ፡ አድርገው ፡ አሳዩዋቸው ። ብቻ ፡ እነሱ ፡ ያሳሰቡት ፡ መንገድ ፡ ወደባሰ ፡ መሰናክል ፡ ወደሁዋላ ፡ ለመመለስ ፡ እንኳዋ ፡ ወደማይቻልበት ፡ ማጥ ፡ የሚመራ፡መሆኑን ፡ እነሱም ፡ ሆነ ፡ ፊታውራሪ ፡ ለጊዜው ፡ አላዩትም ። የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ደብዳቤ ፡ ሲደርሳቸውና ፡ የፍልሚያ ፡ ሸማ ፡ እፊታቸው ፡ ሲወድቅ ፡ ብቻ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ በህይወታቸው ፡ ሙሉ ፡ ደርሶባቸው ፡ የማያውቅ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንደደረሰባቸው ፡ አወቁ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ በወዳጅና ፡ ባሜት ፡ ጠባቂ ፡ ስም ፡ የከበቡዋቸው ፡ ሰዎች ፡ መርተው ፡ ሊወጡበት ፡ ወደማይችሉ ፡ አዘቅት ፡ እንዳገቡዋቸው ፡ ተረዱ ።

ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ እድሜያቸውን ፡ ሙሉ ፡ ከስተት ፡

ተለይተው ፡ አያውቁም ፤ ይህን ፡ ያክል ፡ ስተት ፡ ግን ፡ ተሳስ ተው ፡ አያውቁም ። የሰባ ፡ አመት ፡ ሽማግሌ ፡ መግደል ፡ ወይም በሰባ ፡ አመት ፡ ሽማግሌ ፡ እጅ ፡ መሞት ፡ ሁለቱም ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ ነው ። የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ደብዳቤ ፡ ሲነበብ ፡ በቅ ዝት ፡ እንጂ ፡ በውን ፡ የነበሩ ፡ አልመሰላቸውም ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ የሚያስፈራ ፡ ቅዠት ፡ ይቃዣሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የጎጃም ፡ ህዝብ ፡ በሙሉ ፡ በተሰበሰበበት ፡ ከጠላታቸው ፡ ከደጃዝማች ፡ ይግም ፡ ጋር ፡ ይፋለሙና ፡ እሰ ልፍ ፡ ላይ ፡ ድንገት ፡ እጃቸው ፡ ሲዝል ፡ ወይም ፡ እግራቸው ፡ ሲደነዝዝ ፡ ጎራዴ ፡ መዘው ፡ መከላከል ፡ ጋሻ ፡ መመከት ፡ መሸሽ ፡ እንኳ ፡ አቅትዋቸው ፡ በፍራትና ፡ በፍረት ፡ መሀከል ፡ ቁመው ፡ ሲንቀጠቀጡ ፡ ደዝማች ፡ ይግም ፡ ደስ ፡ ብልዋቸው ፡ እዬሳቁ ፡ በጎራዴያቸው ፡ እየነካኩ ፡ ልክ ፡ ድመት ፡ በአይጥ ፡ እን ደምትጫወት ፡ ሲጫወቱባቸው ፡ ወይም ፡ እንገታቸውን ፡ እጃቸ ውን ፡ እግራቸውን ፡ ቆርጠው ፡ ሲጥልዋቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜው ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ ጠላቶቻቸው ፡ እጅና ፡ እግራቸውን ፡ አስረው ከረዥም ፡ ገደል ፡ ወርውረው ፡ ይጥልዋቸውና ፡ አዛፍ ፡ ላይ ወድቀው ፡ ከዚያ ፡ ሆዳቸው ፡ ተቀዶ ፡ እንጀታቸው ፡ እዬተጎለ ጎለ ፡ ሲወጣ ፡ እያዩ ፡ ሲጨነቁ ፡ ሲሰቃዩ ፡ በመሀከሉ ፡ ይነቁና ፡ ቅዠት ፡ መሆኑን ፡ ሲያውቁ ፡ " በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸእ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ " ይላሉ ። በጣም ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። ይሄም ፡ እንዲህ ፡ ካሉት ፡ ቅዥቶች ፡ አንዱ ፡ ይሆን ? እየየ . . . ምነው ፡ ቅዠት ፡ በሆን ! ኢያሉ ፡ በውስጣቸው ፡ ሲመኙ ፡ ጸሀፊያቸው ፡ ደብዳቤውን ፡ አንብቦ ፡ ጨረሰ ። የሰሙ ትን ፡ ማመንም ፡ አለማመንም ፡ አቃታቸውና ፡ " እስቲ፡ወዲህ፡ በል ፡ " ብለው ፡ ተቀብለው ፡ ድምጻቸውን ፡ ሳያሰሙ ፡ ደብዳቤ ውን ፡ ራሳቸው ፡ ማንበብ ፡ ጀመሩ ።

" የተላከ ፡ ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በሪሁን፤
ይድረስ ፡ ለፊታውራሪ ፡ አሰጋኸኝ ፡ በለው ፡-

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኔ ፡ እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ። ልጄን ፡ እንድድርልህ ፡ በመኩዋንንት ፡ በሽማግሌ፡ በቄስ ፡ በመነኩሴ ፡ አማላጅነት ፡ ለምነህ ፡ እኔን ፡ እሺ ፡ ካሰኘ

ሆና ፡ አገር ፡ ስምምነታችነን ፡ ካወቀው ፡ በሁዋላ ፡ ልጃገረድ
ዋን ፡ ልጇን ፡ በልጃገረድ ፡ ወግ ፡ አላገባም ፡ ብለህ ፡ ስምምነ
ቱን ፡ ለማፍረስ ፡ የላከሀቸው ፡ መለክተኞች ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡
ለጨዋ ፡ ሲልከው ፡ የማይገባ ፡ የስድብ ፡ መልክትህን ፡ አድርሰ
ውልኛል ። ክብርዋን ፡ ጠብቃ ፡ ከሚያሳፍርና ፡ ከሚያስነውር ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ርቃ ፡ ያደገችውን ፡ ልጇን ፡ እግዚአብሄር ፡ ከሰጣት ፡
የመልክ ፡ ውበት ፡ በላይ ፡ የጠባይ ፡ የበጎ ፡ ምግባር ፡ የሙያና ፡
የቀለም ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጡት ፡ ውበት ፡ እንዳይጎድልባት ፡
ተጠንቅቄ ፡ ተጨንቄ ፡ ያሳደግሁዋትን ፡ ልጇን ፡ እንጨት ፡
ሲለቅሙ ፡ ውሀ ፡ ሲቀዱና ፡ ከብት ፡ ሲያግዱ ፡ ክብራቸውን ፡
በዱዱሩና ፡ በየመንገዱ ፡ ጥለው ፡ እንደሚገቡ ፡ የባላገር ፡ ልጆች ፡
ወይም ፡ ወንድ ፡ ለመገብየት ፡ ብቻ ፡ ገባያ ፡ እንደሚወጡ ፡ ጋለ
ሞቶች ፡ እጅዋን ፡ ጎትቼ ፡ ካልወሰድሁ ፡ ውሉን ፡ አፍርሻለሁ ፡
ብለህ ፡ የላከኸው ፡ የስድብ ፡ መልእክት ፡ ደርሶኛል ።

እንዲህ ፡ ያለው ፡ ስድብ ፡ እኔንና ፡ ልጇን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡
ከኔ ፡ በላይ ፡ አባቴን ፡ እያት ፡ ቅድምአያቴን ፡ ስር ፡ መሰረቴን ፡
ከልጇ ፡ በሁዋላ ፡ የሚከተል ፡ ዘር ፡ አዝርእቴን ፡ ሁሉ ፡ የሚያዋ
ርድ ፡ የሚያሳድፍ ፡ መሆኑን ፡ እንኩዋን ፡ አንተ ፡ ማንም ፡ ያው
ቀዋል ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ከመሰረት ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ትው
ልድ ፡ የሚያጎሳቁልና ፡ የሚያሳድፍ ፡ ስድብ ፡ ከደም ፡ በቀር ፡
የሚያጠራው ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ የአባይና ፡ የጣና ፡ ውሀ ፡ አንድ
ላይ ፡ ሆኖ ፡ እንኩዋ ፡ ሊያጠራው ፡ እንደማይችል ፡ አጥተኸው ፡
አይደለም ። እኔን ፡ ጊዜ ፡ የጣለኝ ፡ አንተን ፡ ጊዜ ፡ ያነሳህ ፡ መሆ
ናችንንና ፡ ከሱም ፡ ይልቅ ፡ ጉልበቴ ፡ መድከሙን ፡ ክንዴ ፡ መላ
ሙን ፡ አይተህ ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፡ ብለህ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡
ምንስ ፡ ያክል ፡ ብደክም ፡ ሌላ ፡ ማድረግ ፡ ያቅተኝ ፡ እንጂ ፡
መሞት ፡ የሚያቅተኝ ፡ መሰለህ ? ወይስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የሚያ
ሳፍርና ፡ ዘር ፡ መሰረቴን ፡ የሚያሳድፍ ፡ ውርደት ፡ ተሸክሜ ፡
ከምኖር ፡ ሞቴን ፡ የማልመርጥ ፡ መሰለህ ? እንኩዋንስ ፡ እኔ ፡
ሀይወትን ፡ ለማለፍና ፡ ወደሞት ፡ ድንበር ፡ ለመድረስ ፡ የቀረ
ብሁ ፡ ሽማግሌ ፡ ወደሀይወት ፡ ለመግባት ፡ ገና ፡ የመጀመርያ
ውን ፡ በር ፡ የረገጡ ፡ የጨዋ ፡ ልጆችም ፡ ቢሆኑ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡

እድፍ ፡ ከሚነካቸው ፡ ሞትን ፡ እንደሚመርጡ ፡ አይጠረጠርም። ምናልባት ፡ ይህ ፡ አሳሳች ፡ ጊዜ ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አስረሰቶህ ፡ ይሆናል ! እኔ ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ስላልሆንሁ ፡ የዚያ ፡ ያለፈው ፡ የመልካሙ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ስለሆንሁ ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ አልረሳሁትም። የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ለክብሩ ፡ ይኖራል ፤ ለክብሩ ፡ ይሞታል ። የጨዋ፡ ልጅ ፡ ህይወቱና ፡ ክብሩ ፡ አንድ ፡ ናቸው ። የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ክብሩ ፡ ከጠፋ ፡ ህይወት ፡ አለኝ ፡ ሊልና ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። የጨዋን ፡ ልጅ ፡ ክብር ፡ የገፈፈ ፡ ህይወቱን ፡ ጭምር ፡ መውሰድ ፡ አለበት ። አንተም ፡ ክብሬን ፡ ስለቀማኸኝ ፡ ህይወቴን ፡ ጭምር ፡ መውሰድ ፡ አለብህ ። ስለዚህ ፡ የፍልሚያ ፡ ሽማ፡ስለኔ ፡ እንዲዋልልህ ፡ ወንድሜን ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉን ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ ጭምር ፡ አስይዤ ፡ ሰድጀዋለሁና ፡ ተቀብለህ ፡ መሳርያ ፡ መርጠህ ፡ ቀን ፡ ቆርጠህ ፡ እንድትልከብኝ ፡ ይሁን ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በሪሁን ። "

እንብበው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወረቀቱ ፡ ከጃቸው ፡ ወደቀ።ከዚያ ፡ አንገታቸውን ፡ ታቦት ፡ እንደተሸከሙ ፡ ሁሉ ፡ ቀስስ ፡ ብለው፡ ቀና ፡ አድርገው ፡ አይናቻቸውን ፡ አፊታቸው ፡ በቆሙት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ተከለው ፡ ሳያረግቡ ፡ ብዙ ፡ ቆዩ ። እኒያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ዳርቻቸው ፡ ተከፍተው ፡ ሳይረግቡ ፡ አፊታቸው ፡ በቆሙት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የተተከሉ ፡ አይኖች ፡ ከማየት ፡ ይልቅ፡ በዝዝ ፡ ብለው ፡ በጆሮዋቸው ፡ የሚጮኸውን ፡ ድምጽ ፡ የሚሰሙ ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ። " ጉልበቴ ፡ መድከሙን ፡ ክንዴ፡መላሙን ፡ አይተህ ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፡ ብለህ ፡ ነው ! " አለ ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ድምጽ ፡ በጆሮዋቸው ። " ሌላ ፡ ማድረግ ፡ ቢያቅተኝ ፡ መሞት ፡ የማያቅተኝ ፡ መሰለህ ?" "የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ህይወቱና ፡ ክብሩ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ክብሬን ፡ ከቀማኸኝ ፡ ህይወቴን ፡ ጭምር ፡ መውሰድ ፡ አለብህ ! " አለ ፡ ደገመና ። ከዚያ ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ስእል ፡ እዩተለዋወጠ ፡ ታያቸው ። እሁን ፡ በሽምግልናቸው ፡ አምሳ ፡ አመት ፡ ግድም ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ በሰላሳ ፡ አምስትና ፡ ባርባ ፡ አመት ፡ መሀከል ፡ ሳሉ ፡ ሁሉም ፡ በዩተራ ፡ እዩተለዋወጠ ፡ ታያቸው ። ይልቁንም፡ፊታ

ውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አርባ ፡ አመት ፡ ያክል ፡ በነበራቸው ፡ ጊዜ ፡
ስማቸው ፡ በነጋይ ፡ በጎንቻ ፡ በሳርምድር ፡ ባወባልና ፡ በጥላት
ግን ፡- በነገሰበት ፡ ጊዜ ፡ ያንጊዜ ፡ የነበረው ፡ ሁኔታቸው ፡
ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ጎልቶ ፡ ታያቸው ። ያንጊዜ ፡ አደን ፡ ሄደው ፡
ዝሆን ፡ በጎራዴ ፡ ይገድላሉ ፤ አንበሳ ፡ ታግለው ፡ ይጥላሉ ፤ እጉ
ግስ ፡ ላይ ፡ ፈረስ ፡ እየጋለቡ ፡ ካንዱ ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ ዘለው ፡ እሌ
ላው ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፤ ጋሻ ፡ እስከመካቹ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አግ
ምረው ፡ በዘንግ ፡ ይቀዳሉ ፡ እዩተባለ ፡ ሊታመን ፡ የማይቻል ፡
ብዙ ፡ የሀይል ፡ የድፍረትና ፡ የጀግንነት ፡ ወሬ ፡ ይወራላቸው ፡
በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የጎበዝ ፡ ሁሉ ፡ ምኞት ፡ እንደፊታውራሪ፡መሸሻ ፡
መሆን ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የሀይለኝነት ፡ የደፋርነት ፡ የጀግንነት ፡
መለኪያ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ የማያውቁዋቸው፡
ልጃገረዶች ፡ በዩስርጉ ፡ በያመትባሉ ፡ እረኞች ፡ በዩሜዳው ፡
በዩዱሩ ፡ ግጥም ፡ ይገጥሙላቸው ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ አቅራሪው ፡
ፈካሪው ፡ አዝማሪው ፡ ሁሉም ፡ በዩፈናው ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸ
ሻን ፡ ስም ፡ ያወድስና ፡ ያሞግስ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ያንጊዜ ፡ የነበረ፡
ሁኔታቸው ፡ በጣም ፡ ጎልቶ ፡ ታያቸው ። ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ እንደ
ገና ፡ አሁን ፡ ካረጁ ፡ ከሰባ ፡ አመት ፡ በላይ ፡ ከሆናቸው ፡ በሁ
ዋላ ፡ ያለው ፡ ሁኔታቸው ፡ ታያቸው ። አሁን ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ጎልማ
ስነት ፡ የሚሰጠው ፡ የክብር ፡ ዜና ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ አዱኛ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡
ከያፉ ፡ መወደስ ፡ መሞገስ ፡ ከድሜያቸው ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ አልፎ፡
በዲግ ፡ ደብር ፡ ካሉ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎችና ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቻቸው ፡
በቀር ፡ አለም ፡ ረስቶዋቸው ፡ ጉልበታቸው ፡ ደክሞ ፡ ክንዳቸው፡
ልሞ ፡ አንበሳ ፡ ታግለው ፡ እንዳልጣሉ ፡ ሁሉ ፡ እድሜ ፡ ሊጥላ
ቸው ፡ ሲያንገላታቸው ፡ ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ እሳቸው ፡ ፊታው
ራሪ ፡ አሰጌ ፡ የድሜ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ በጦር ፡ ሊወጉዋቸው፡በጎ
ራዴ ፡ ሊመትዋቸው ፡ ከጎን ፡ ሲሰናዱ ፡ ታያቸው ። በዚያን ፡
ጊዜ ፡ ቦዘው ፡ የነበሩ ፡ አይኖቻቸውን ፡ መላልሰው ፡ አርገበገ
ቡና ፡ ታፍነው ፡ እንደቆዩ ፡ ሁሉ ፡ " እሁሁሁሁሁሁ . . . "
ብለው ፡ ዘለግ ፡ ያለ ፡ ትንፋሽ ፡ ተንፍሰው ፡ " አልቀበልም ፤
ፍልሚያውን ፡ አልቀበልም ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ።
" ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በነጋይ ፡ ባወባል ፡ በጥላትግን ፡ በጎ

ንቻ ፡ በሳርምድር ፡ ለታሪክ ፡ ለዘር ፡ ለድንበር ፡ ምስክራችን ፡ ያገራችን ፡ አጥይ ፡ ታቦታችን ፡ ናቸው ። ምንም ፡ ያክል፡እብድ ፡ ብሆን ፡ በታቦት ፡ ላይ ፡ ክንዴን ፡ አላነሳም ! በደለኛ ፡ ለመሆኔ ፡ ምስክር ፡ አያስፈልግ ፤ ፈራጅ ፡ ዳኛ ፡ አያስፈልግ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ምስክርም ፡ ዳኛም ፡ ሆኜ ፡ በራሴ ፡ መስክሬ ፡ ፈርጃለሁ ! እሳቸው ፡ የመረጡትን ፡ ቅጣት ፡ አይኔን ፡ ሳላሽ ፡ ልቀበል ፡ የሚገባኝ ፡ እልም ፡ ያልሁ ፡ በደለኛ ፡ ነኝ ፤ ስለዚህ ፡ አልፋለምም ፤ ሽማውን ፡ ይመልሱ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፤ ና ፡ ጻፍ ፡ አንተ ! ” አሉ ፡ ወደጸሀፊያቸው ፡ ዞወር ፡ ብለው ።

“ የተላከ ፡ ከፊታውራሪ ፡ አስጋኸኝ ፡ በለው ፡ ”

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ አባቴ ፡ ጌታዬ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በሬሁን ፡

እንደምን ፡ ሰንብተዋል ? እኔ ፡ እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ። በቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ እጅ ፡ የላኩልኝ ፡ ደብዳቤና ፡ የፍልሚያ ፡ ሽማ ፡ ደረሰኝ ። ባላሰብ ፡ መከራ ፡ አሳስቶኝ ፡ አባቴን ፡ ጌታዬን ፡ መበደሌን ፡ አሁን ፡ ተረዳሁት ። ደብዳቤዎን ፡ ሳነብ ፡ የተሰማኝ ፡ አዘን ፡ ያቆሰለውን ፡ ልቤን ፡ ገልጦ ፡ ለማሳዬት ፡ የሚቻል ፡ ቢሆን ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡ ነበር ! ደብዳቤዎን ፡ ሳነብ ፡ የተሰማኝን ፡ ስቃይ ፡ የሚያዩ ፡ ቢሆኑ ፡ ኖሮ ፡ ከዚያ ፡ የበለጠ ፡ ቅጣት ፡ ሊቀጡኝ ፡ እንደማይጨክኑ ፡ አምናለሁ ! ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ የሚሰራውን ፡ እንጂ ፡ የሚሰማውን ፡ ለማሳዬት ፡ የማይቻል ፡ ስለሆነ ፡ በሰራሁት ፡ ጥፋት ፡ ሌላ ፡ ሽማግሌ ፡ መምረጥ ፡ ሳያስፈልግ ፡ እርስዎ ፡ የፈለጉትን ፡ ይቅጡኝ ።

ምንም ፡ ከርስዎ ፡ ከጌታዬ ፡ የበለጠ ፡ ባላውቅ ፡ በልግዱም ፡ ቢሆን ፡ የበደለና ፡ የተበደለ ፡ የሚፋለሙ ፡ የበደለ ፡ በደለኛነቱን ፡ ሳያምንና ፡ ካሳ ፡ አልከስም ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንጂ፡በጥፋቱ ፡ ተጸጽቶ ፡ ካሳ ፡ ልካስ ፡ ቅጣት ፡ ልቀጣ ፡ ካለ ፡ ፍልሚያ ፡ የለም ። እኔ ፡ ጌታዬን ፡ አባቴን ፡ የበደልሁ ፡ መሆኔንና ፡ እርስዎ፡ የቆረጡትን ፡ ካሳ ፡ መክፈል ፡ እርስዎ ፡ የመረጡትን ፡ ቅጣት ፡ መቀጣት ፡ የሚገባኝ ፡ መሆኔን ፡ አምናለሁ ። ብቻ ፡ የበደልሁም፡ መከር ፡ አሳስቶኝ ፡ ሰው ፡ የመከረኝን ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ስጥቼ ፡ ማመዛዘን ፡ ጎድሎኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለርስዎ ፡ እንደመሰለዎ ፡

እኔን ፡ ጊዜ ፡ ያነሳኝ ፡ እርስዎን ፡ ጊዜ ፡ የጣለዎ ፡ መሆናችንን ፡ አይቼና ፡ እርስዎ ፡ ስለሸመገሉ ፡ እኔ ፡ እርስዎ ፡ በደረሱበት ፡ እድሜ ፡ ገና ፡ ስላልደረስሁ ፡ ምን ፡ ያደርጉኛል ፡ ብዬ ፡ አውቄ ፡ እንዳልበደልሁዎ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ባህርንና ፡ ጠፈርን ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፡ ያውቀዋል ። ስለዚህ ፡ እኔ ፡ ባጠፋሁት ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ በርስዎና ፡ በኔ ፡ መሀከል ፡ የተፈጠረው ፡ ቅርታ ፡ ሳያንስ ፡ ቤታችን ፡ በደም ፡ ግድብ ፡ ተለያይቶ ፡ እንዳይ ኖር ፡ ፍልሚያው ፡ እንዲቀር ፡ የሚወዱትን ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊ ስን ፡ አማላጅ ፡ አድርጌ ፡ ከጫማዎ ፡ ስር ፡ ወድቄ ፡ እለምንዎታ ለሁ ።

ፈታውራሪ ፡ አሰጋኸኝ ፡ በለው ። ”

ጸሀፊው ፡ ጽፎ ፡ ከጨረሰ ፡ በሁዋላ ፡ ቆሞ ፡ ሲያነብ፡እዚያ ፡ የነበሩ ፡ ሁሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ጭምር ፡ በጣም ፡ ተነኩ ፡ አዘኑ ። “ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ ለፈታውራሪ ፡ ሰጥተው ፡ መልሱን ፡ ያምጡልኝ ፡ ሽማውንም ፡ መልሰው ፡ ይው ሰዱ ፡ አልቀበልም ። ” አሉ ፡ ፈታውራሪ ፡ አሰጌ ። በበነጋው ፡ መልሱም ፡ ሽማውም ፡ ተመልሶ ፡ መጣላቸው ።

“ የተላከ ፡ ከፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በሪሁን ።

ይድረስ ፡ ከፈታውራሪ ፡ አሰጋኸኝ ፡ በለው ፡—

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ። የላክሁልህን ፡ የፍልሚያ ፡ ሽማ ፡ መልሰህ ፡ ከደብዳቤ ፡ ጋር ፡ ለቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ የሰጠኸው ፡ ደርሶኛል ።

ከሰደብኸኝ ፡ ካዋረድኸኝ ፡ በማይለቅ ፡ ጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ጥለህ ፡ ከረገጥኸኝና ፡ ካሳቀልኸኝ ፡ በሁዋላ ፡ የቀባኸኝን ፡ እድፍ ፡ ለመሸፈን ፡ የላክኸውን ፡ ለስላሳና ፡ መልካም ፡ ቃል ፡ ያለበት ፡ ወረቀት ፡ ተመልክቼዋለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ እድፍ ፡ ካል ጠራ ፡ መሸፈኛው ፡ ሲነሳ ፡ ሁልጊዜም ፡ ብቅ ፡ የሚል ፡ ያው ፡ እድፉ ፡ ነው ። ይህ ፡ የቀባኸኝ ፡ እድፍ ፡ መጥራት ፡ እንጂ፡መሸ ፈን ፡ የለበትም ፡ የሚጠራውም ፡ ወይ ፡ ባንተ ፡ ወይ ፡ በኔ ፡ ወይም ፡ በሁለታችን ፡ ደም ፡ ነው ።

መሳርያ ፡ እንድትመርጥና ፡ ቀን ፡ እንድትቆርጥ ፡ ምርጫ ፡ ሰጥቾህ ፡ እንበቢ ፡ ካልህ ፡ እኔ ፡ የምቆርጠውን ፡ ቀንና ፡ የምመር

ጠውን ፡ መሳርያ ፡ መቀበል ፡ አለብህ ትቀኑ ፡ የሀዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ መሳርያው ፡ ጦርና ፡ ጎራዴ ፡ እንዲሆን ፡ ቆርጫለሁ ። መጀመርያ ፡ በፈረስ ፡ ሆነን ፡ በሁ..ት ፡ በሁለት ፡ ጣምራ ፡ ጦር ፡ እንገጥማለን ። ፍልሚያውን ፡ የጠዬቅሁ ፡ እኔ ፡ ስለሆንሁ ፡ የመጀመርያው ፡ ተባራሪ ፡ እኔ ፡ አባራሪ ፡ አንተ ፡ እንሆናለን ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ የጦሩ ፡ ክፍል ፡ እስኪያልቅ ፡ በየተራ ፡ አባራሪና ፡ ተባራሪ ፡ እንሆናለን ። ያንተም ፡ የኔም ፡ ጦር ፡ በለስ ፡ ሳይቀናቸው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ከፈረስ ፡ ወርደን ፡ በጎራዴ ፡ እንገጥማለን ። ለዚህ ፡ ዳኞቻችን ፡ ከዲግ ፡ ግራዝማች ፡ ሁነኛው ፡ መሰረት ፡ ከቢቸና ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ግዛውና ፡ ቀኛዝማች ፡ መብራቱ ፡ ታዬ ፡ እንዲሆኑ ፡ መርጫለሁ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ላንተም ፡ ለኔም ፡ የስጋ ፡ ዝምድና ፡ እንደሌላቸው ፡ ጠይቄ ፡ አረጋግጫለሁ ። ይህን ፡ አልቀበልም ፡ ያልህ ፡ እንደሆነ ፡ መልካም ፡ ስምህ ፡ የሚበላሽ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በገባህበት ፡ ገብቼ ፡ በወጣህበት ፡ ወጥቼ ፡ በሄድህበት ፡ ሁሉ ፡ ሄጄ ፡ እንዳውሬ ፡ አድኜ ፡ ሳልገልህ ፡ የማልቀር ፡ መሆኔን ፡ ካሁኑ ፡ እንድታውቀው ፡ ይሁን ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በሪሁን ። ”

# ምእራፍ ፡ ፲፬ ፡

## ሀዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡

ሀዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፌታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ፌታውራሪ ፡ አስጌን ፡ እፋለማለሁ ፡ ብለው ፡ ቤተዘመድ ፡ በተሰበሰበበት ፡ ከተናገሩ ፡ በሁዋላ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ይውል ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ያ ፡ ሳምንት ፡ ለፌታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤተሰብ ፡ የጭንቅ ፡ የምጥ ፡ የስቃይ ፡ ሳምንት ፡ ሆኖ ፡ ሰነበተ ።

ከፌታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ከራሳቸው ፡ በቀር ፡ ከቤተሰብና ፡ ከዘመድ ፡ መሀከል ፡ በዚያ ፡ እድሜያቸው ፡ ከስመጥሩ ፡ ጀግና ፡ ከፌታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ጋር ፡ በጦርም ፡ ይሁን ፡ በጎራዴ ፡ ተወዳድረው ፡ ያሸንፋሉ ፡ ብሎ ፡ እንኳንስ ፡ የሚያምን ፡ የሚጠረጥር ፡ ስላልነበረ ፡ ሀዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፌታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የሚሞቱበት ፡ ቀን ፡ መሆኑ ፡ ተረጋግጦ ፡ ከቀናች ፡ ሁሉ ፡ ተጠልቶ ፡ የራሱን ፡ የሞትን ፡ ያክል ፡ ተፈርቶ ፡ ሰነበተ ። ያን ፡ ሳምንት ፡ በሙሉ ፡ በፌታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ ግብር ፡ ለወጉ ፡ ይቀርባል ፡ እንጂ ፡ ራብና ፡ ጥም ፡ ተሰምቶት ፡ የሚበላ ፡ የሚጠጣ ፡ አልነበረ ፡ ለወጉ ፡ በዩቦታው ፡ መጋደም ፡ ካልሆነ ፡ እንቅልፍ ፡ የሚተኛ ፡ አልነበረ ፡ የቤቱ ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ለመርዶ ፡ እንደተሰለፈ ፡ ሁሉ ፡ ከሹክሹክታ ፡ በቀር ፡ ድምጹን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ የሚናገር ፡ አልነበረ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲስቅ ፡ እንዲጫወት ፡ አይወድ ፡ እንዲያለቅስ ፡ አይፈቀድለት ፡ እንዲሁ ፡ ታፍኖ ፡ ተጨንቆ ፡ ሰነበተ ። በዚያ ፡ የጨዋታ ፡ የውካታ ፡ የደስታ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ሞት ፡ ከባድ ፡ ክንፉን ፡ ዘርግቶ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ የፌታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ ቤተሰብ ፡ ሲያስጨንቅ ፡ ሲሰቀይ ፡ ሰነበተ ። በኒያ ፡ ሰባት ፡ ቀናች ፡ ውስጥ ፡ የቤቱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሰባት ፡ አመት ፡ እድሜውን ፡ ኖሮ ፡ አረጀ ። እህህ ! ሞት ፡ ሁልጊዜ ፡ እንዲህ ፡ በቀጠሮ ፡ አለመምጣቱ ፡ ምንኛ ፡ መልካም ፡ ነው ! ያለዚያስ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ መፈ

ጠር ፡ የበሰጠ ፡ ያስቅቅና ፡ ደስጠላ ፡ ነበር !

ራሳቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻም ፡ ቢሆኑ ፡ አንዳንድ ጊዜ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ሲያስቡ ፡ እርሳቸው ፡ በእድሜያቸው ፡ ምክናያት ፡ ከጦር ፡ ሜዳ ፡ ካደንና ፡ እነሱን ፡ ከመሳሰሉት ፡ የጀግኖች ፡ ቦታ ፡ ከተሰዩ ፡ ጀምሮ ፡ ከያሩ ፡ የሚሰሙት ፡ የፊታውራሪ ፡ እሰጌን ፡ የጀግንነትና ፡ የጀብድ ፡ ስራ ፡ መሆኑ ፡ ትውስ ፡ ይላቸውና ፡ ለጊዜው ፡ መስጋት ፡ ልባቸው ፡ መሸበር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ለህይወታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ውሳኔ ፡ በችኮላ ፡ በመወሰናቸው ፡ በራሳቸው ፡ መፍረድ ፡ ይጀምራሉ ። በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ - ያባቶቻቸውን ፡ የነገስታቱን ፡ ክብር ፡ የራሳቸውን ፡ ክብር ፡ የልጃቸውንና ፡ ከልጃቸው ፡ በሁዋላ ፡ የሚከተሉትን ፡ ትውልድ ፡ ክብር ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲዋጉ ፡ መሞታቸው ፡ በተወራ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የሚሰጠው ፡ ስሜት ፡ የሚፈጥረው ፡ አድንቆት ፡ ትዝ ፡ ሲላቸው ፡ ስጋታቸው ፡ ወደድፍረት ፡ በልባቸው ፡ የተነሳው ፡ ሽብር ፡ ደስ ፡ ወደሚያሰኝ ፡ሙቀት ፡ ይለወጣል ። ይህ ፡ ጀግንነትን ፡ ከቅድስና ፡ ጋር ፡ አስተባብሮ ፡ የያዘ ፡ ከፍተኛ ፡ መስዋእትነት ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ ሲነዛ ፡ ሁሉም ፡ በዩቤቱ ፡ በዩጉዋዳ ፡ ከልሂቅ ፡ እስከደቂቅ ፡ የሚሰው ፡ ይታሰባቸውና ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። ከዚያ ፡ ትንሽ ፡ ሲያስቡ ፡ ይቆዩና ፡ ብቻቸውን ፡ እንደመሳቅ ፡ ብለው ። " ጊዮርጊስ ፡ በሰተ ፡ ቀኑ ፡ ረድቶኝ ፡ በለስ ፡ ሰጥታኝ ፡ የገደልሁት ፡ እንደሆነስ ? ያንጊዜ ፡ እነማይ ፡ ምን ፡ ይላል ? ጎጃም ፡ ምን ፡ ይላል ? ጠብያ ፡ ምን ፡ ይላል ? " ይላሉ ። ወዲያው ፡ ፊታውራሪ ፡ እሰጌን ፡ በጦር ፡ ወግተው ፡ ከፈረሳቸው ፡ ላይ ፡ ሲጥሉዋቸው ፡ ወይም ፡ መጀመሪያ ፡ በጦር ፡ ያቆስሉዋቸውና ፡ ሁስቱም ፡ ከፈረስ ፡ ወርደው ፡ በጎራዴ ፡ ገጥመው ፡ አንገታቸውን ፡ ቆርጠው ፡ ሲጥሉ ፡ ስእሉ ፡ እየተለዋወጠ ፡ ባይነ ፡ ህሊናቸው ፡ ፊት ፡ ተዘርግቶ ፡ ይታያቸዋል ። ከዚያ ፡ አዝማሪው ፡ አቅራሪው ፡ ፈካሪው ፡ ስማቸውን ፡ በዩቦታው ፡ ማወደሱ ፡ ዜናቸው ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ መንገሱ ፡ ይታሰባቸዋል ። ወዲያው ፡ ይህ ፡ የሚያልሙት ፡ እልም ፡ ልክ ፡ በውን ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉ ፡ ልባ

ቻውን ፡ ይመስጠውና ፡ የሚይዙትን ፡ የሚጨብጡትን ፡ ያሳ ጣቻውና ፡ ሲቃ ፡ ያስይዛቻውና ፡ ሀዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ እስኪደ ርስ ፡ ይቻኩላሉ ።

በመጨረሻ ፡ ሀዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደረሰ ። የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ሰዎች ፡ ከቦታው ፡ ወደሁዋላ ፡ እንዲሸሽ ፡ እዬራቀ ፡ እንዲሄድ ፡ ሲመኙ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲርቅ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲቀርብ ፡ ቶሎ ፡ እንዲደርስ ፡ ሲመኙ ፡ እሱ ፡ ቀኑን ፡ ቆጥሮ ፡ በቀኑ ፡ ደረሰ ። ለሀዳር ፡ ጊዮር ጊስ ፡ እጥቢያ ፡ ሌሊቱን ፡ ከቤቱ ፡ ሰው ፡ እስከመጋደሙ ፡ እንኳዋ፡ ያሰበው ፡ አልነበረም ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ እስበሱ ፡ እዬተንሾካሾከ ፡ እንዲሁ ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ሲንጉዋለል ፡ ሲታመስ ፡ ሲተራመስ ፡ መንጋት ፡ አይቀርም ፡ ነጋ ። ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ብቻ ፡ ከግ ብር ፡ በሁዋላ ፡ አንዳንድ ፡ ተረስቶ ፡ የቆዬ ፡ ኑዛዜያቻውን ፡ አስጽ ፈው ፡ ለንስሀ ፡ አባታቻው ፡ ሰጥተው ፡ ወደ ፡ ምኝታቻው ፡ ሲሄዱ፡ እንደተለመደው ፡ ራስጌያቻው ፡ ተሰናድቶ ፡ የሚጠብቃቻውን ፡ የማብረጃ ፡ ጠጅ ፡ ግቶም ፡ አድርገው ፡ ጠጥተው ፡ ደህና ፡ እንቅ ልፍ ፡ ተኝተው ፡ አደሩ ።

ሲነጋ ፡ ከድሮው ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ተነስተው ፡ እንደድ ሮው ፡ የሰት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሰባት ፡ ቀን ፡ ውዳሴ ፡ ማር ያም ፡ መልክ ፡ ኢየሱስና ፡ መልክ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዳዊት ፡ ደግመው፡ ሲጨርሱ ፡ ባልደራሳቻውን ፡ ዋጋዬ ፡ አንተነህን ፡ አስከትለው ፡ ማሰፊያ ፡ ፈረሶችና ፡ በቅሎዎች ፡ ወደሚታሰሩበት ፡ ሄደው ፡ ሁሉንም ፡ ዞረው ፡ ካዩ ፡ በሁዋላ ፡ ጥርኝ ፡ በብሮ ፡ ሀመር ፡ በነ ሀስ ፡ ዋርዲት ፡ በጥልፍ ፡ እቃ ፡ እንዲጫኑላቻው ፡ አዘዙ ።

" ዋርዲት ፡ ለምን ? " አለ ፡ ዋጋዬ ፡

" ከዚህ ፡ ፈረስ ፡ ሜዳ ፡ ድረስ ፡ በምን ፡ እሄዳለሁ ? "

" እውነት ፡ ነው ፡ እሺ ። " አለ ፡ ዋጋዬ ፡ እጅ ፡ እንደ መንሳት ፡ ብሎ ። ከዚያ ፡ ፊታውራሪ ፡ ወደቤታቻው ፡ ለመመለስ ፡ ዞወሮ ፡ ሲሉ ፡ -

" በጥርኝ ፡ ፊንታ ፡ ቦራን ፡ ብንጭን ፡ ይሻላል ፡ " አለ ፡ ዋጋዬ ።

" ለምን ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቆም ፡ ብለው ።

" ጥርኝ ፡ በጣም ፡ ሀይለኛ ፡ ሆኖ ፡ ጀርባውን ፡ ኮረቻ ፡ ነክቶት ፡ አያውቅም ። ስለዚህ ፡ ጊዜ ፡ እግኝተን ፡ እስክናረትመው ፡ ድረስ ፡ ጌቶች ፡ የሚቀመጡበት ፡ አይደለም ፡ አደገኛ ፡ ነው ። "

" ጥርኝ ፡ አደገኛ ፡ ነው ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ተመልሰው ፡ የጥርኝን ፡ አንገት ፡ ?.. ..ሱ ። ምንም ፡ ተቀምጠውበት ፡ ባያውቁ ፡ ከግለፊያ ፡ ፈረሶቻቸው ፡ ሁሉ ፡ አብልጠው ፡ የሚወዱና ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ በመጡ ፡ ቁጥር ፡ በተለይ ፡ ደንግሎ ፡ ሲያጎርሱ ፡ አንገቱን ፡ ሲደባብሱ ፡ ቆይተው ፡ የሚሄዱ ፡ ጥርኝን ፡ ነበር ።

" አዎ ፡ በጣም ፡ አደገኛ ፡ ነው ፡ ጌቶች ፤ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ እውጭ ፡ ውሀ ፡ አጠጥቶ ፡ ለመመለስ ፡ ስላልተቻለ ፡ እዚሁ ፡ እንደታሰረ ፡ ነው ፡ ውሀ ፡ የምናጠጣው ። በልጉዋም ፡ ካል ሆነ ፡ እንደሌላ ፡ ፈረስ ፡ በሺቦ ፡ ወይም ፡ በልባብ ፡ ይዞ ፡ የሚያቆመው ፡ የለም ። ታዲያ ፡ በልጉዋም ፡ እወንዝ ፡ እውርዶ ፡ ለማጠጣት ፡ ልጉዋም ፡ ሲያወልቁለት ፡ ነጥቆ ፡ ይበራል ።

" ይሀን ፡ ያህል ፡ እመጸኛ ፡ ሆነሃል ፡ ጥርኝ ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አንገቱን ፡ መታ ፡ መታ ፡ እያደረጉ ። "እስቲ ፡ --- እስቲ ፡ ግድየለም ፡ ጥርኝ ፡ ይጫን ። " አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ ካመነቱ ፡ በሁዋላ ።

" እህህህ ... እህህ..." አለ ፡ ጥርኝ ፡ ጌታው ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ እምነት ፡ በመስማቱ ፡ ደስታውን ፡ ለመግለጽ ፡ እንደፈለገ ፡ ሁሉ ።

ፊታውራሪ ፡ ከፈረስ ፡ ቤት ፡ ሲወጡ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ እውጭ ፡ ይጠብቁዋቸው ፡ ስለነበረ ፡ ተያይዘው ፡ ቁርስ ፡ ለማድረግ ፡ ገቡ ። ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ የቁዋንጣ ፡ ጥብስ ፡ በልተው ፡ ሁለት ፡ ብርሌ ፡ ጠጅ ፡ ከመጠጣት ፡ በቀር ፡ እንደዘወትሩ ፡ ሆዳቸው ፡ ተከፍቶ ፡ ሊበሉ ፡ አልቻሉም ።

" ጥሩየና ፡ ሰብለ ፡ የሉም ፡ አንተ ? " አሉ ፡ እረፊታቸው ፡ እጅን ፡ አመሳቅሎ ፡ የቆመውን ፡ አሳላፊ ፡ ጉርርዋቸው ፡ ተዘ

ግቶበት ፡ መግቢያ ፡ ያጣውን ፡ የቁዋንጣ ፡ ጥብስ ፡ ባፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ከቀኝ ፡ ወደግራ ፡ ከግራ ፡ ወደቀኝ ፡ እያንከራተቱ ።

“ አሉ ፡ እመቤቴ ፡ ሰብለ ፡ አልፍኝ ፡ ናቸው ። ” አለ ፡ አሳላፊው ፡ ባዘን ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ።

“ ቁርስ ፡ አያደርጉም ? ”

“ እዚያው ፡ እናደርጋለን ፡ አሉ ። ”

“ ደግ ፡ ግድየለም ፡ ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እጃቸውን ፡ በንጀራ ፡ እዬጠራረጉ ። የቅርታ ፡ ጥላ ፡ በጸሀይ ፡ ፊት ፡ እንደሚያልፍ ፡ ደመና ፡ ፊታቸውን ፡ ሲያጠላው ፡ ጉልህ ፡ ሆኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። እርሳቸው ፡ ፊት ፡ ዘመድ ፡ እዬተጫወተ ፡ ቁርስ ፡ ሲበላ ፡ ምሽታቸውና ፡ ልጃቸው ፡ የውነተኛ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ባለቁርጠቻቸው ፡ ከመብል ፡ ከመጠጥ ፡ ከጨዋታ ፡ ርቀው ፡ የሚያለቅሱት ፡ ልቅሶ ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ፡ አዘን ፡ ተሰማቸው ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ፊታውራሪ ፡ እሰጌን ፡ እፋለማለሁ ፡ ብለው ፡ በቤተዘመድ ፡ ፊት ፡ ሲያስታውቁ ፡ ምሽታቸው ፡ አሳባቸውን ፡ እንዲለውጡ ፡ በግራቸው ፡ ወድቀው ፡ እያለቀሱ ፡ ለምነዋቸው ፡ ነበር ። ልጃቸውም ፡ አባትዋ ፡ የወሰኑትን ፡ እንደሰማች ፡ ዘመድ ፡ በተሰበሰበበት ፡ የተናገረችውና ፡ ያለቀሰችበት ፡ ምክናያት ፡ ለሳቸው ፡ እንደመሰላቸው ፡ ሆድ ፡ ብስዋት ፡ አለመሆኑን ፡ ገልጻ ፡ ይቅርታ ፡ እንዲያደርጉላትና ፡ ለስዋ ፡ ሲሉ ፡ የመወዳደሩን ፡ አሳብ ፡ እንዲተው ፡ እያለቀሰች ፡ ለምናቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ፊታውራሪ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አሳባቸውን ፡ የማይለውጡ ፡ መሆናቸውንና ፡ ወደፊት ፡ ምሽታቸውም ፡ ሆኑ ፡ ልጃቸው ፡ ሲያለቅሱ ፡ ያዩዋቸው ፡ እንደሆነ ፡ ቤቱን ፡ ጥለውላቸው ፡ እስከ ፡ ህዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ድረስ ፡ ከዘመድ ፡ ጋር ፡ የሚሰነብቱ ፡ መሆናቸውን ፡ መላልሰው ፡ ስላስታወቁ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነትና ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ለማልቀስ ፡ እንዲመቻቸው ፡ የተቻለውን ፡ ያክል ፡ ከፊታውራሪ ፡ ሲሸሹና ፡ እሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አልፍኝ ፡ እየተሸሸጉ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ሰነበቱ ። በግብር ፡ ጊዜም ፡ መሰንበቻውን ፡ ዘመድ ፡ ስላልተለዩ ፡ እነሱ ፡ በሩቅ ፡ ሆነው ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ እያሰናዱ ፡ እንዲላክ ፡ ከማድረግ ፡ በቀር ፡ አይቀርቡም ፡ ነበር ። ፊታውራሪ

ም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ገብቶዋቸው ፡ ሲያዝኑ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሚወዱዋቸውን ፡ የምሽታቸውንና ፡ የልጃቸውን ፡ ጣር ፡ ከማዩት ፡ በሩቅ ፡ መገመትን ፡ መርጠው ፡ መጡ–አልመጡ ፡ ብለው ፡ አይጠይቁም ፡ ነበር ። ብቻ ፡ ያ ፡ ቀን ፡ የመጨረሻ ፡ ቀን ፡ ሊሆን ፡ ስለሚችል ፡ ሳያዩዋቸው ፡ በመሄድና ፡ ከነጭንቃቸው ፡ ከነንባቸው ፡ በማየቱ ፡ መሀከል ፡ መምረጥ ፡ አቅቶዋቸው ፡ “ ደግ ፡ ግድየለም ፡ ” አሉ ።

ከቁርስ ፡ በሁዋላ ፡ ሰው ፡ እንዲመለስ ፡ ተደርጎ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታጥቀው ፡ ሲጨርሱ ፡ የንስሀ ፡ አባታቸው ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ እንደገና ፡ ገብተው ፡ ጸሎተ ፡ ማርያምና ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ደግመው ፡ ባርከው ፡ ለበጎም ፡ ይሁን ፡ ለክፉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፍታ ፡ አሉ ።

ከዚያ ፡ ፊታውራሪ ፡ ብድግ ፡ ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነትና ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ፊትና ፡ ሁዋላ ፡ ተከታትለው ፡ ገቡ ። አይናቸውና ፡ አፍንጫቸው ፡ ቆስሎ ፡ ከንፈራቸው ፡ አብጦ ፡ መስንበቻውን ፡ እንባ ፡ ሲወርድበት ፡ የሰነበተ ፡ ፊታቸው ፡ ጎርፍ ፡ እንደበላው ፡ ለስላሳ ፡ መሬት ፡ ቦይ ፡ ያበጀ ፡ መስሎ ፡ ተጎሳቁለው ፡ ተንገላተው ፡ ሲታዩ ፡ ጥሩና ፡ ሰብለ ፡ መሆናቸውን ፡ ለይቶ ፡ ለማውቅ ፡ ያስቸግር ፡ ነበር ።

“እኔስ ፡ ከንግዲህ ፡ ወ....ወዲያ ፡ ብ....ብዙ ፡ አል....አልኖርም ፡ ግድ....ግድየለኝም ። ብቻ ፡ ይቺን ፡ አንዲት....አንዲት፡ ልጅዎን ፡ ያ...ያ...ያባት ፡ ደሃ ፡ ሊያደርጉዋት ፡ ምን....ምን ፡ ይጠቀማሉ ?” ብለው ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ እንባቸው ፡ በፊታቸው ፡ እየጎረፈና ፡ ድምጻቸውን ፡ ሳግ ፡ እያቋዋረጠው ፡ በባላቸው ፡ አንገት ፡ ወደቁ ። ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ እግራቸው ፡ ላይ ፡ ወደቀች ። ምሽታቸው ፡ ፊታቸውን ፡ ልጃቸው ፡ እግራቸውን ፡ በንብ ፡ ውሀ ፡ እያጠቡ ፡ ሲፎሁ ፡ ፊታውራሪም ፡ ድምጻቸውን፡ ከፍ ፡ አድርገውና ፡ ስቅቅ ፡ ብለው ፡ ያለቅሱ ፡ ጀመር ። ከዚያ ፡ ልቅሶውን ፡ የሰሙ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ገብተው ፡ አባብለውም ፡ ተቆጥተውም ፡ ለያዩዋቸው ።

“ያሁን ፡ ልቅሶ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ? ” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡

አካሉ ፡ ተቆጥተው ። “ወዲያውስ ፡ እግዜር ፡ ድሉን ፡ ለማን ፡ እን ደሚሰጥ ፡ አውቃችሁ ፡ ነው ፡ የምታለቅሱ ? በንዲህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ፡ ስቆ ፡ ተጫውቶ ፡ መለያየት ፡ ነውንጂ ፡ በልቅሶ ፡ መለያየት ፡ አይገባም ። ቸር ፡ ተመኙ ፡ ቸር ፡ እንድታገኙ ፡ የሚባለውን ፡ ምክር ፡ ማሰብ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ቀኛዝማች ።

“ልቅሶ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ? ማልቀስ ፡ አይገባም ! ” አለ ፡ ዘመድ ፡ ሁሉ ፡ እዬተቀባበለ ።

የሚወዱት ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ሲሄድ ፡ ልቅሶ ፡ የሚያደርገውን ፡ ለማወቅ ፡ እንደ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነትና ፡ እንደ ፡ ሰብለ ፡ ወን ጌል ፡ ምሽትና ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ ማየት ፡ ያስፈልጋል ! በሰው ፡ ቁስል ፡ እንጨት ፡ ቢሰዱ ፡ አያምም ፤ እመሙ ፡ የሚሰማው ፡ ባለ ቁስሉን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ልባቸው ፡ የቆሰለው ፡ የፊታው ራሪ ፡ መሸሻ ፡ ምሽትና ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ቢፈረድባቸውም ፡ እያለ ቀሱ ፡ ወደሴት ፡ እልፍኛቸው ፡ ተመለሱ ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የሳቸውና ፡ የምሽታቸው ፡ እንባ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተደባልቆ ፡ ያጠበውን ፡ ፊታቸውን ፡ በኩታቸው ፡ ጠራርገው ፡ አድርቀው ፡ ብቅ ፡ ሲሉ ፡-እንዳዘዙት ፡ ጥርኝ ፡ በብር፡ ሀመር ፡ በነሀስ ፡ ዋርዲት ፡ በጥልፍ ፡ እቃ ፡ ተጭነው ፡ ቀሚስ ፡ ለብሰው ፡ ጋሻ ፡ ጀግሬው ፡ ከጠመንጃና ፡ ከጋሻቸው ፡ ሌላ ፡ ሁለት፡ ጣምራ ፡ ጦሮቻቸውን ፡ በፎደራ ፡ አልብሶ ፡ ከፈረሶች ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፤ የሳቸውና ፡ የዘመዶቻቸው ፡ ስድሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ወታደሮች ፡ ጠመንጃቸውን ፡ ይዘው ፡ በድርብ ፡ ተራ ፡ ተሰልፈው ፤ ዘመድ ፡ ወዳጁና ፡ ተመልካቹ ፡ ከተሰለፉት ፡ ወታደሮች ፡ በሁዋላ ፡ ግቢ ውን ፡ ሞልቶ ፡ ተመለከቱና ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ከጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ በፊት ፡ የምሽታቸውና ፡ የልጃቸው ፡ ልቅሶ ፡ አለስልሶት ፡ የነበ ረው ፡ ልባቸው ፡ እንደገና ፡ መጠንከር ፤ እንደገና ፡ መድፈር ፡ እንደገና ፡ በወኔ ፡ መሙላት ፡ ጀመረ ።

“ዋርዲትን ፡ አቅርብ ፡ አንተ !” አለ ፡ ባልደራስ ፡ ዋጋየ ፡ ፊታውራሪ ፡ ከወንድ ፡ እልፍኝ ፡ በራፍ ፡ ቆም ፡ ብለው ፡ ግቢያ ቸውን ፡ የሞላውን ፡ ሕዝብ ፡ ከተመለከቱ ፡ በሁዋላ ፡ ደረጃውን ፡ መውረድ ፡ ሲጀምሩ ። ለጉዋሚው ፡ ፈይሳ ፡ እንደታዘዘው ፡ ዋር ዲትን ፡ አቅርቦ ፡ ቀሚስዋን ፡ ከላይዋ ፡ መግፈፍ ፡ ሲጀምር ።

"ግድየለም ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ድረስ ፡ በግሬ ፡ እሄዳለሁ ! "አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አይናቸው ፡ እርሳቸውን ፡ ለማየት ፡ የሚተራመሰውን ፡ ህዝብ ፡ እዩገዘመ ።

"የፈረስ ፡ ሜዳ ፡ መንገድኮ ፡ በዚህ ፡ ነው ፤ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ አይደለም !" አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ የፈረስ፡ ሜዳን ፡ መንገድ ፡ በጃቸው ፡ እያመለከቱ ።

"እኮ ፡ ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ ስሄድ ፡ ጊዮርጊስን፡ ሳልሳለም ፡ እሱን ፡ ሳልለምነበት ፡ እሄዳለሁ ፡ እንዴ ! አድርጌው ፡ አውቃለሁ ? ሳብ ፡ አንተ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

"ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን !" አለ ፡ ባልደራስ ፡ ዋጋየ ፡ ድምጹን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ሕዝቡ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲያመራ። ከዚያ ፡ እዚያ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ መንገድ ፡ ግልብጥ ፡ አለ ። አጥሩን ፡ ቀድሞ ፡ ለመውጣት ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ሁሉም ፡ እስበሱ ፡ ሲጋፋና ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ሲቆም ፡ ሞት ፡ እያባረረው ፡ ለማምለጥ ፡ የሚሽቀዳደም ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ያጥሩን ፡ በራፍ ፡ ከወጣ ፡ በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ሁሉም ፡ ተራውን ፡ ያዘ ።

ባለብረት ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ መንገድ ፡ ያዘ ። ከዚያ ፡ በብርና ፡ በነሀስ ፡ መጣምር ፤ በሀምራዊ ፡ ቀይ ፡ ቀሚስ ፡ ያጌጡት ፡ ፈረሶች ፡ በጥልፍ ፡ እቃና ፡ በቀይ ፡ በተከፈፈ ፡ ነጭ ፡ ቀሚስ ፡ ከተሸለሙቸው ፡ ዋርዲት ፡ ጋር ፡ ተከተሉ ። ከነሱ ፡ በሁዋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ ከመኩዋንንታቸው ፡ መሀከል ፡ በድጋቸው ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ ዝናራቸውንና ፡ ረሽሮም ፡ ጎራዴያቸውን ፡ ታጥቀው ፡ ይህን ፡ ትጥቅ ፡ ለማሳዩት ፡ እንደፈለጉ ፡ ሁሉ ፡ ኩታቸውን ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ትከሻቸው ፡ መልሰው ፤ ረዥም ፡ ዘንጋቸውን ፡ ይዘው ፡ ነጭ ፡ ጠጕራቸው ፡ እንደ ፡ ተቆጣ ፡ አንበሳ ፡ አፈሮ ፡ ቆሞ፡ ተከተሉ ። በሁዋላቸው ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬቸው ፡ ጠመንጃና ፡ ጋሻቸውን ፡ ቀሚስ ፡ አልብሶ ፡ በግራው ፡ አንግቶ ፡ ጣምራ ፡ ጦርቻቸውን ፡ በሮያራ ፡ እንደገቡ ፡ በቀኙ ፡ ይዞ ፡ ተከተለ ። ከጋሻ ጃግሬው ፡ በሁዋላ ፡ አዛኙ ፡ እድናቂው ፡ አሽሙዋጣጩ ፡ ወሬ ፡ ሸማቹ ፡ ጀሌ ፡ ለጉዋሚው ፡ ፈረሱ ፡ በቅሎው ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡

ላይ ፡ ተደባልቆ ፡ እየተጋፋ ፡ እዬተተረማመሰ ፡ ተከተለ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተዬይዞ ፡ እንደውሀ ፡ ሙላት ፡ እዬተጥመለመለ ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደረሰና ፡ አደባባዩን ፡ አጥለቀለቀው ።

ፊታውራሪን ፡ ያጀበው ፡ ብዙ ፡ ሀዝብ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አደባባይ ፡ አልፈው ፡ አልፈው ፡ በያንዳንዱ ፡ ጽድ ፡ ስር ፡ ጸሎት ፡ ይዘው ፡ ከቆሙ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ ባዶ ፡ ነበር ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በሮች ፡ ዙሪያውን ፡ ተዘግተው ፡ ደረጃው ፡ በሰው ፡ ፈንታ ፡ ርግቦች ፡ ሰፍረውበት ፡ ሲታይ ፡ እንኰዋን ፡ ያመት ፡ ባል ፡ ያዘቦት ፡ ቀን ፡ ዲግ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ።

" ዛሬ ፡ ቅዳሴ ፡ የለም ፡ እንዴ ? " አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በሮች ፡ መዘጋታቸውንና ፡ ገቢው ፡ ጭር ፡ ማለቱን ፡ አይተው ።

" እንዴ ! ያውም ፡ የሀዳር ፡ ጊዮርጊስለት ? " አሉ ፡ ልጅ ፡ እጅጉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ፡ አሉ ።

"ትስቃለህ ፡ እንዴ ?" አሉ ፡ ባላምባራስ ።

"ምን ፡ ላድርግ ፡ ሲገርመኝ ?" አሉ ፡ ቀኛዝማች ።

" እስቲ ፡ ያን ፡ እዚያ ፡ የቆመውን ፡ ጥሩው ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባቅራቢያው ፡ ጥድ ፡ ስር ፡ ቆሞ ፡ ጸሎት ፡ ወደያዘው ፡ ሰው ፡ እመልከተው ። ሰውዬው ፡ እዬሮጠ ፡ መጥቶ ፡ እጅ ፡ ሲነሳ ፡-

" ለምን ፡ ዛሬ ፡ ቅዳሴ ፡ ታጎለ ፡ አንተ ? " አሉት ፡ እሱ ፡ ገበዝ ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉ ።

" ኧረ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አላውቅም ፡ ጌቶቼ ፡ እኔም ፡ ጥዋት ፡ ስመጣ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እንዲህ ፡ የተወረረ ፡ መስሎ ፡ ባዶውን ፡ ሳገኘው ፡ የምጠይቀው ፡ አጥቼ ፡ ስቸገር ፡ ነበር ። "

" ከካህናቱ ፡ አላገኘህም ? "

" አንድ ፡ ካህን ፡ ለምልክት ፡ አልነበረም ፡ ጌቶች ።" እንዲህ ፡ ያለ ፡ ደርሶ ፡ የማያውቅ ፡ ነገር ፡ በመድረሱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተገረመ ። በልማዱ ፡ ሀዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ታቦት ፡ የሚወጣበት ፡ አይሁንንጂ ፡ ከታላላቁ ፡ ክብረ ፡ በአላት ፡ የመጀመሪያው ፡

ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ ዲማ ፡ ታቦቱ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስለሆነ ፡ በጣም ፡
የሚከበር ፡ ነው ። የዲማ ፡ ካህናት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ ያካባቢው ፡
ገጠሮች ፡ ካህናት ፡ ጭምር ፡ ለዋዜማው ፡ መጥተው ፡ ማህሌት ፡
ቆመው ፡ አድረው ፡ የለቱለትም ፡ ከቅዳሴ ፡ በሁዋላ ፡ እስከ ፡
ረፋድ ፡ ድረስ ፡ አገልግሎቱ ፡ ቀጥሎ ፡ ከዚያ ፡ መልስ ፡ ዘመድ ፡
ያለው ፡ ከዬዘመዱ ፡ ዘመድ ፡ የሌለው ፡ እምርፋቅ ፡ ከሚመ
ጣው ፡ ድግስ ፡ ተጋብዞ ፡ የሚለያይበት ፡ አመት ፡ በአል ፡ ነው ።
ያንለት ፡ ብቻ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቀርቶ ፡ ዲማ ፡ ለዘወትር ፡ የማይ
ታጎለው ፡ ቅዳሴ ፡ እንኳዋ ፡ በመታጎሉና ፡ ወሬ ፡ የሚነግር ፡
አንድ ፡ ካህን ፡ እንኳዋ ፡ ባለመገኘቱ ፡ ሰውን ፡ ግራ ፡ ገባው ።
ፊታውራሪ ፡ አይናቸውን ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ተክለው ፡ ግንባራ
ቸውን ፡ እያሹ ፡ ያስቡ ፡ ጀመር ።

“ ጊዮርጊስ ፡ እኔን ፡ ተቀይሞ ፡ ይሆን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ደርሶ ፡ የማያውቅ ፡ ነገር ፡ ያደረሰ ? ያለዚያ ፡ በዛሬ ፡ ቀን ፡
ቅዳሴ ፡ የሚታጎልበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚዘጋበት ፡ ምን ፡
ሌላ ፡ ምክንያት ፡ አለ ? ይሄው ፡ ነው ! ተቀይሞኝ ፡ ተጣል
ቶኝ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባሳባቸው ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ከፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ጋር ፡ የሚ
ገጥሙበት ፡ ቀን ፡ ህዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ እንዲሆን ፡ ሆን ፡ ብለው ፡
መምረጣቸው ፡ ጊዮርጊስን ፡ ተማምነው ፡ እሱ ፡ ይረዳኛል ፡
ብለው ፡ ነበር ። ድሮ ፡ እዶንም ፡ ይሁን ፡ ጦርነት ፡ ሲሄዱ ፡ መጀ
መሪያ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይመጡና ፡ በሩን ፡ ሁል ፡
ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ክፍት ፡ ያገኙታል ፡ ሰተት ፡ ብለው ፡ እስከ ፡
ቅድስቱ ፡ ገብተው ፡ ተንበርክከው ፡ ግንባራቸውን ፡ እመቅ
ደሱ ፡ በር ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ያሳርፉና ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትንና ፡
በሰላመ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤልን ፡ ደግመው ፡ ሲጨርሱ ፡ ተነስ
ተው ፡ ምራቃቸውን ፡ ትፍ ፡ ትፍ ፡ ብለው ፡ እጃቸው ፡ ሲርስ ፡
ፊታቸውን ፡ ቀብተው ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ የደረጃውን ፡ ትቢያ ፡
እዬጠራረጉ ፡ ፊታቸውን ፡ አባብሰው ፡ “ ጌታዬ ፡ ፈጥኖ ፡
ደራሹ ፡ አባክህ ፡ አንተ ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጋሻና ፡ ከለላ ፡
ሆነህ ፡ አቅፈህ ፡ ደግፈህ ፡ በደህና ፡ መልሰኝ ! ” ብለው ፡ ተሳል
መው ፡ ተሰናብተው ፡ ይሄዱና ፡ ጊዮርጊስም ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡

ሁሉ ፡ ጠብቆ ፡ አቅፎ ፡ ደግፎ ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ ይመልሳቸው ፡ ነበር ። ያንለት ፡ ግን ፡ ጊዮርጊስ ፡ ያለወትሮው ፡ በሩን ፡ ዘግቶ ፡ እንኳዋንስ ፡ ባርኮ ፡ ሊያሰናብታቸው ፡ አጠገቡ ፡ እንዳይደርሱ ፡ ከለከላቸው ። የፊታውራሪ ፡ አሰኔ ፡ ክንድ ፡ ገና ፡ እድሜ ፡ ያላዘለው ፡ ከርሳቸው ፡ ክንድ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚበረታ ፡ መሆኑን ፡ እያወቁ ፡ ግዴለም ፡ ጊዮርጊስ ፡ አለኝ ፡ የጊዮርጊስ ፡ ክንድ ፡ ክንዴ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እሱን ፡ በሙሉ ፡ ልባቸው ፡ ተማምነው ፡ ነበር ፤ ይሄው ፡ ፊቱን ፡ አዞረባቸው ፤ ከዳቸው ። ይህን ፡ መጀመሪያ ፡ ከቤታቸው ፡ ሲወጡ ፡ ምሽታቸው ፡ " እንዴት ፡ ልጅዎን ፡ ያባት ፡ ድሃ ፡ አደረጉዋት ፡ " ብለው ፡ ከተናገሩት ፡ ከፉ ፡ ትንቢት ፡ ጋር ፡ አዩይዘው ፡ ሲያስቡ ፡ ቆዩና ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀኑ ፡ የርሳቸው ፡ አለመሆኑን ፡ አወቁ ። ወዲያው ፡ ልባቸው ፡ በደም ፡ ፈንታ ፡ አሞት ፡ እንደሚረጭ ፡ ሁሉ ፡ አፋቸውን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሙሉ ፡ አካላቸውን ፡ ምሬት ፡ ተሰማው ።

ከዚያ ፡ የለመደው ፡ ጉርሻ ፡ እንደቀረበት ፡ ሀጻን ፡ እንጀታቸው ፡ በጊዮርጊስ ፡ እርር ፡ ብሎ ፡ ካንገት ፡ በላይ ፡ ትንሽ ፡ እጅ ፡ እንደመንሳት ፡ አሉና ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ወደፈረስ ፡ ሚዳ፡ መንገዳቸውን ፡ ሲጀምሩ ፡ " ግዴለም " አሉ ፡ ድምጻቸውን ፡ አሰምተው ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ቅጽር ፡ ሲወጡ ፡ ባለብረት ፡ የሆነ ፡ ወታደር ፡ ሁሉ ፡ ቀድሞ ፡ መንገዱን ፡ ይዞ ፡ ተሰልፎ ፡ ፈረሶቻቸው ፡ ቀጥሰው ፡ ቦታቸውን ፡ ይዘው ፡ በቅሎዋቸው ፡ ቀሚስዋ ፡ ተነስቶ ፡ ተዘጋጅታ ፡ ሁሉም ፡ በስራት ፡ ሆኖ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ስለነበረ፡-እበቅሎዋቸው ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ ጉዞዋቸውን ፡ ጀመሩ ።-

ፊታውራሪ ፡ ካጀባቸው ፡ ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የሌለው ፡ ህዝብ ፡ ጋር ፡ በከተማው ፡ መሀከል ፡ ሲያልፉ ፡ በዩቤቱ ፡ በራፍ ፡ ቆሞ ፡ የሚመለከተው ፡ ሴት ፡ አንዳንዱ ፡ ባዘን ፡ ከንፈሩን ፡ ሲመጥ ፡ አንዳንዱ ፡ ሲያዪንቅ ፡ አንዳንዱም ፡ ሲየሽሞቀጥቀ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

" አየ፦ ምነው ፡ ጊዮርጊስ ፡ በለተቀኑ ፡ በረዳቸው !" አለች ፡ እንዱዋ ።

" ይረዳቸው ፡ ይሆናል ፤ ዛሬ ፡ የሚገጥሙ ፡ አስጠንቁ ለው ፡ ነው ፡ አሉ !" አለች ፡ ሁለተኛዋ ።

"ጀግና ፡ ሆነው ፡ ኖረው ፡ ጀግና ፡ ሆነው ፡ ሊሞቱ ፡ ነው !" አለች ፡ ሶስተኛዋ ።

" ጥጋብኮ ፡ ነው ፡ እናንተ ፡ እግዚአብሄር ፡ የሚልክላቸ ውን ፡ ሞት ፡ በሽማግሌ ፡ ወግ ፡ እቤታቸው ፡ እርፈው ፡ ተቀም ጠው ፡ እንዳይጠብቁ ፡ ሞት ፡ የት ፡ አለህ ፡ እያሉ ፡ ፍለጋ ፡ መሄድ ፡ ጥጋብ ፡ አይባልም ?" አለች ፡ ሌላዋ ።

እንዲህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትችት ፡ እየተተቸባቸው ፡ ከተማ ውን ፡ አልፈው ፡ እከተማው ፡ ዳር ፡ ያለችውን ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ ሲሻገሩ ፡ ፈረስሜዳ ፡ ሊደርሱ ፡ የማይችሉ ፡ ሀጻናት ፡ በሽተኞችና ፡ እእሩግ ፡ ከወንዝዋ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ወገን ፡ ቆመው ፡ ቀሩ ። ሌላው ፡ ፈረስሜዳ ፡ የሚደረገውን ፡ ታምር ፡ ለማየት ፡ ተከተለ ። የህዝቡ ፡ ብዛት ፡ ሲታይ ፡ በዲማ ፡ አንድ ፡ ነፍስ ፡ የቀረ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ እስካጀባቸው ፡ ወንዝዋን ፡ ተሻግረው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ረዥም ፡ ሜዳ ፡ እንዳጋመሱ ፡ ከመንገዱ ፡ ዳር ፡ በስተቀኝ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ የግንድ ፡ ጉራጅ ፡ ወይም ፡ የግራኝ ፡ ድንጋይ ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ በሩቅ ፡ ብቅ ፡ አለ ። ሁለት፡ መቶ ፡ ሜትር ፡ ያክል ፡ ቀረብ ፡ እንዳሉ ፦

" ቀበሮ !" አለ ፡ ፊት ፡ ከሚሄዱት ፡ ወታደሮች ፡ አንዱ ፡ ጮሆ ።

" በጥይት ፡ ልበላት !" አለ ፡ ሌላው ፡ እሱም ፡ እንዲሁ ፡ ጮሆ ።

" የለም ፡ ትስታትና ፡ ታቁዋርጠናለች ፡ ግራውን ፡ በፈ ረስ ፡ ቅደምና ፡ ወዳለችበት ፡ ወደቀኝ ፡ መልሳት ፡" አሉ ፡ ባላ ምባራስ ፡ ምትኩ ። ወዲያው ፡ ራሳቸው ፡ ከሰልፉ ፡ ወጥተው ፡ ከመንገዱ ፡ ግራ ፡ ግራውን ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ሽምጥ ፡ ሲጋልቡ ፡ ቀበሮዋ ፡ አዩችና ፡ እስዋም ፡ መንገዱን ፡ ይዛ ፡ ጅራትዋን ፡ ወደታች ፡ ለጥፋ ፡ አውጭኝ ፡ ነፍስዋን ፡ ሮጠች ። ቀበሮዋ ፡ መንገዱን ፡ ሳትለቅ ፡ ባላምባራስ ፡ ግራውን ፡ ይዘው ፡ ሲሸቀ ዳደሙ ፡ ሜዳውን ፡ ዘልቀው ፡ በመጨረሻ ፡ ወደምትገኘዋ ፡

ትንሽ ፡ ዱር ፡ ደረሱ ። እዚያ ፡ ቀበሮዋ ፡ ጠፋች ። ወደቀኝ ፡ ትመለስ ፡ መንገዱን ፡ ትቁረጥ ፡ ባላምባራስ ፡ ሊያውቁ ፡ አል ቻሉም ። የዱርዋን ፡ ዙሪያ ፡ ዞረው ፡ ካዩና ፡ ውስጥ ፡ ለውስ ጥም ፡ ከፈረስ ፡ ወርደው ፡ ከፈለጉ ፡ በሁዋላ ፡ እመንገዱ ፡ ዳር ፡ ቆመው ፡ ሲጠብቁ ፡ ፊታውራሪ ፡ ደረሱ ። የባላምባራስ ፡ ፈረስ፡ በላብ ፡ ጠልቆ ፡ አረፋ ፡ ይፍቆ ፡ ከላይ ፡ ከላይ ፡ ይቀትት ፡ነበር።

" ቆረጠችን ፡ ባላምባራስ ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀኑ ፡ የሳቸው ፡ አለመሆኑን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተረድተው ፡ ተስፋ ፡ ቆረጠው ፡ እንዳልመጡ ፡ ሁሉ ።

" እእ ? የለም ፤ አ. . . . ልቆረጠችንም ። " አሉ ፡ ባላም ባራስ ፡ እፋቸው ፡ እዬፈራ ።

"አዎ ፡ ቆርጣናለች ፡ አውቄዋለሁ ፡ ብቻ ፡ ግዴለም !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባዘን ፡ ድምጽ ።

" አልመሰለኝም ፤ መቸም ፡ ዱሩን ፡ እንዳልወጣች ፡ ርግጠኛ ፡ ነኝ ፤ እዚህ ፡ ዱር ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ የቀረች ። ዱሩን ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ እዬዞርሁ ፡ ስፈልግ ፡ አንድ ፡ የቀበሮ ፡ ጉር ጉዋድ ፡ እዚያ ፡ በስተቀኝ ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ አገኘሁ ፤ ስለዚህ ፡ እዚያ ፡ የገባች ፡ ይመስለኛል ። " አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ የቀበሮ ፡ ጉርጉዋድ ፡ ያለበትን ፡ በጃቸው ፡ እያመለከቱ ።

" ግዴለም !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደገና ። እዚያ ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ አዘነ ።

ቀበሮዋ ፡ ከጠፋችበት ፡ ዱር ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተራራ ፡ ሲታለፍ ፡ ፈረስሜዳ ፡ ነው ። እተራራው ፡ እናት ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ሜዳው ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ ከዳር ፡ እስከዳር ፡ ይታያል ። ፊታውራ ሪና ፡ ያጀባቸው ፡ ህዝብ ፡ እተራራው ፡ እናት ፡ ላይ ፡ እንደደ ረሱ ፡ ከቢቸና ፡ በኩል ፡ የፈረስሜዳን ፡ ዳርቻ ፡ ህዝብ ፡ እጥል ቆት ፡ አዩና ፡ "ቀድሞናል ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የተወዳዳሪ ያቸው ፡ ቀድሞ ፡ እጠሩ ፡ ሜዳ ፡ መገኘት ፡ ትንሽ ፡ ያስቆጣ ቸው ፡ መሆኑ ፡ በፊታቸው ፡ እዬታዬ ። ፊታውራሪ ፡ እስኬን ፡ ተከትሎ ፡ የመጣው ፡ ህዝብ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ ተከትሎ ፡ ከመጣው ፡ ሀያ ፡ ወይም ፡ ሰላሳ ፡ ገዜ ፡

ይበልጥ ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ከተከተላቸው ፡ ህዝብ ፡ ጋር ፡ ተራራውን ፡ ወርደው ፡ ሜዳ ፡ ፈረስሜዳን ፡ ሲጀምሩ ፡ "እንግዴህማ ፡ እዚህ ፡ አረፍ ፡ ብለን ፡ ዳኞቻችን ፡ ያሉበትን ፡ ብናጠይቅ ፡ አይሻልም ፡ ጌታዬ ?" አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ በቅሎዋቸውን ፡ አስገረው ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ።

"ይግ ፡ እውነትክ ፡ ነው ፡ እዚህ ፡ እንረፍ ። " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቅሎዋቸውን ፡ ገትተው ።

" ቆዩ ፡ በል ፡ አንተ ፡ ቆዩ ፡ በል !" አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ ጮህ ፡ ብለው ፡ ፊትፊት ፡ የሚሄደው ፡ ሰራዊት ፡ እንዲቆም ።

ፊታውራሪ ፡ ከበቅሎ ፡ እንደወረዱ ፡ ባልደራስ ፡ ዋጋዬ ፡ የገዛ ፡ በቅሎውን ፡ ምቹና ፡ ግላስ ፡ ቶሎ ፡ አወረደና ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ፈልጎ ፡ አነጠፈ ፡ ፊታውራሪ ፡ እዚያ ፡ ሲቀመጡ ፡ ፊት ፡ ቀድሞ ፡ የነበረው ፡ ሰራዊት ፡ በሙሉ ፡ ግንባሩን ፡ ለቆ ፡ ወደ ሁዋላ ፡ ተመልሶ ፡ በጀርባቸው ፡ በሰፈረ ፡ ጊዜ ፡ ከተቀመጡበት ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ፈረስሜዳ ፡ በቁሙም ፡ በወረዱም ፡ ከዳርዳር ፡ ተዘርግቶ ፡ ቁልጭ ፡ ብሎ ፡ ታያቸው ። -

ፈረስሜዳ ፡ ጀግኖች ፡ ለጨዋታም ፡ ለምርም ፡ ጉግስ ፡ እየተወዳደሩ ፡ የሚገጥሙበት ፡ ብዙዎቹ ፡ የሞቱበት ፡ ብዙዎቹ ፡ የቆሰሉበት ፡ ጥቂቶቹ ፡ ስም ፡ አስረው ፡ የቀሩበት ፡ ነው። ከነዚህ ፡ ከጥቂቶቹ ፡ መሀከል ፡ አንዱ ፡ ራሳቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ነበሩ ። ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በጎልማስነታቸው ፡ የፈረስ ፡ ሜዳ ፡ ንጉስ ፡ ይባሉ ፡ ነበር ። ብቻ ፡ እሱ ፡ በጐልማስነታቸው ፡ ዘመን ፡ ነው ። ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በድሚያቸው ፡ ምክናያት ፡ ከውድድሩ ፡ ተራ ፡ ከወጡ ፡ በሁዋላ ፡ ሴሎች ፡ጉልማሶች ፡ በዩተራ ፡ ነግሰውበታል ። ከኒህ ፡ ከሁዋለኞች ፡ የፈረስ ፡ ሜዳ ፡ ነገስታት ፡ አንዱ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ናቸው ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አይናቸውን ፡ ሳያረግቡ ፡ በፈረስ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ተክለው ፡ አባባቸው ፡ ባለፈው ፡ የሆነውንና ፡ ያንለት ፡ ሊሆን ፡ የሚዘጋጀውን ፡ ግጥሚያ ፡ በተራ ፡ ሲያመዛዝንና ፡ ሲያወዳድር ፡" ምን ፡ ፈረሰኛ ፡ ነው ?"አሉ ፡ ፊታውራራን ፡ ከበው ፡ ከተቀመጡት ፡ አንዱ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ።

አንድ ፡ ፈረሰኛ ፡ ከፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ሰፈር ፡ ሽምጥ ፡ እየጋለበ ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ሰፈር ፡ መጣ ።

" መላከተኛ ፡ ይሆናል ። " አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ እንገታቸውን ፡ እንደደፉ ።

ፈረሰኛው ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ካሉበት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሜትር ፡ ያክል ፡ እንደቀረበ ፡ ከፈረሱ ፡ ዱብ ፡ አለና ፡ ፈረሱን ፡ በወረደበት ፡ ቦታ ፡ ትቶ ፡ እየሮጠ ፡ መጥቶ ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ ሲነሳ ።

"እንዴት ፡ አደረህ ፡ ወዳጄ ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

" መድሀኔአለም ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ ጌታዬ ፡ እንደምን ፡ አደሩ ? ዳኞቻችን ፡ እስኪመጡ ፡ ትንሽ ፡ ብንጠብቅ ፡ አይሻልምወይ ? " ብለዋል ፡ ጌቶች ፡ " አለ ፡ የፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ መላከተኛ ፡ የጌታውን ፡ መልክት ፡ ሲያቀርብ ፡ በሳቸው ፡ ፈንታ ፡ እጅ ፡ እየነሳ ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ መልሱን ፡ ከከበቡዋቸው ፡ ዘመዶቻቸው ፡ እንደሚፈልጉ ፡ ሁሉ ፡ ዘወርወር ፡ ብለው ፡ ቢመለከቱ ፡ ሁሉም ፡ አፋቸውን ፡ ገጥመው ፡ አይናቸውን ፡ ብቻ ፡ አፍጥጠው ፡ ስላዩ ፡ ወደ ፡ መላከተኛው ፡ መለስ ፡ አሉና ፡ "ደግ ፡ ነው ፡ ትንሽ ፡ እንጠብቃለን ፡......እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ አድረሃል ፡ ወንድሜ ፡ ደግ ፡ ነው ፡እንጠብቃለን ፡ በለው ፡ " አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

መላከተኛው ፡ እንደገና ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ እንደታሰረ ፡ ሁሉ ፡ በወረደበት ፡ ቦታ ፡ ቆሞ ፡ ወደሚጠብቀው ፡ ፈረሱ ፡ እየሮጠ ፡ ተመለሰና ፡ ትንሽ ፡ እየሳበ ፡ ሬቅ ፡ ካለ ፡ በሁዋላ ፡ እፈረሱ ፡ ላይ ፡ ውጥቶ ፡ ሽምጥ ፡ እየጋለበ ፡ እንደመጣ ፡ እንዲሁ ፡ ሽምጥ ፡ እየጋለበ ፡ ተመለሰ ።

ጥርኝና ፡ ሀመር ፡ ያን ፡ እንደነሱ ፡ ያልደላው ፡ ከሳርና ፡ ከውሀ ፡ ሌላ ፡ ቀምሶ ፡ የማያውቅ ፡ የወታደር ፡ ፈረስ ፡ ጋልቦ ፡ መጥቶ ፡ ጋልቦ ፡ ሲመለስ ፡ አይተው፡- አቆቋዋሙንም ፡ ግልቢያውንም ፡ መናቃቸውን ፡ በሳቅ ፡ ለመግለጽ ፡ እንደፈለጉ ፡ ሁሉ ፡ እየተቀባበሉ ፡ "እሀሀሀ - ሀሀሀሀ -" አሉና ፡ በፈንታ

ቸው ፡ መጋለብ ፡ አምሮዋቸው ፡ ይንቆራጠጡ ፡ ጀመር ። በተለይ ፡ ጥርኝ ፡ ደረቱን ፡ ብቅ ፡ አንገቱን ፡ ሰበር ፡ ጆሮዎቹን ፡ እንደተደገኑ ፡ ጣምራ ፡ ቀስቶች ፡ ወደፊት ፡ ቀሰር ፡ አድርጎ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ግራቀኝ ፡ የፊት ፡ እግሮቹን ፡ እያፈራረቀ ፡ መሬት ፡ እዬፎገረ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በጌጠኛ ፡ እኩትኩዋቶ፡ ለጉዋሚውን ፡ ፈይሳን ፡ እዬዞረ ፡ ከረዥም ፡ ሀመራዊ ፡ ቀሚስ ፡ ጋር ፡ ሲያረባርብ ፡ ሲታይ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ የጥርኝን ፡ ሁኔታ ፡ ሲመለከቱ ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ እሳቸውም ፡ እንደተቀመጡ ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ ይንቆራጠጡ፡ ጀመር ።

" ጥርኝን ፡ ወዲህ ፡ በል ፡ አንተ ! " አሉ ፡ በመጨረሻ ፡ የጥርኝ ፡ ሰልፍ ፡ ማሳመር ፡ ወኔያቸውን ፡ ቀሰቀሰውና ። ፈይሳ፡ ጥርኝን ፡ እዬሳበ ፡ ሲያቀርብ ፡ -

"ቀሚሱን ፡ አንሳ ! " አሉ ።

"ለምን ? " አለ ፡ ባልደራስ ፡ዋጋዬ ፡

"እሞክረዋለሁ ። "

"የለም ፡ ጌታዬ ፡ አይገኘ ፡ ነው ! "

"እኮ ፡ ታዲያ ፡ ለግጥሚያው ፡ የማይሆን ፡ መሆኑን ፡ አሁን ፡ መሞከር ፡ አያስፈልግም ? "

"ስሞክረውኮ ፡ ነው ፡ የሰነበትሁ ! እስከነማስወጣቱም ፡ ችግር ፡ ነው ። "

"ግዴለም ፡ ቀሚሱን ፡ አንሳ ። " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ተነስተው ።

"ባይሆን ፡ መጀመሪያ ፡ እኔ ፡ ልሞክረው ፡ " አለ ፡ ባልደራስ ፡ ዋጋዬ ።

"ይሻለል ፡ እሱ ፡ መጀመሪያ ፡ ይሞክረው ! አሉ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ እዬተቀባበሉ ።"

"ይግ ፡ በል ፡ ሞክረው ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቅር ፡ እያላቸው ።

ከዚያ ፡ ባልደራስ ፡ ዋጋዬ ፡ ቀሚሱን ፡ አስነስቶ ፡ በጌታው ፡ ግላስ ፡ እንዳይቀመጥ ፡ እጥፎ ፡ ዛብና ፡ ቀዳማ ፡ አጣምሮ ፡ በቀኙ ፡ ደሀራ ፡ በግራው ፡ ጨብጦ ፡ ገና ፡ ርካብ ፡ ሲረግጥ ፡

ጥርኝ ፡ ልጉዋም ፡ ባፉ ፡ እንዳልገባ ፡ ሁሉ ፡ ሽምቅ ፡ ግልቢያ
ጀመረ ። ባልደራስ ፡ ዋጋየ ፡ እንዴት ፡ እንደወጣ ፡ ከመቃየቱ ፡
በፊት ፡ እኮረቻው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ታየ ።

"ሽምጥ ፡ አይደለም ፡ ዋጋየ ፡ ዳንግላሳ ፡ ነው ፡ ዳንግላሳ ፡
አስሂደው ። " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ድምጻቸውን ፡ ከፍ ፡ አድር
ገው ፡ እዩሥሡ ፡ የዳንግላስን ፡ ግልቢያ ፡ ለማሳየት ፡ እንደሙ
ዚቃ ፡ መሪ ፡ እጃቸውንም ፡ እንገታቸውንም ፡ ሳይና ፡ ታች ፡
እያወዛወዙ ። ነገር ፡ ግን ፡ የፊታውራሪ ፡ መሥሡም ፡ ቢሆን ፡
የዋጋየ ፡ ትግል ፡ ጥርኝን ፡ ዳንግላሳ ፡ ሊያስሄደው ፡ አልቻለም።

ዋጋየ ፡ ልጉዋም ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ ይዞ ፡ በሙሉ ፡ ሀይሉ ፡
ወደታች ፡ ሲስብ ፡ ጥርኝ ፡ በሁለት ፡ የሁዋላ ፡ እግሮቹ ፡ ቀጥ ፡
ብሎ ፡ ይቆማል ፡ የቀኝ ፡ ወይም ፡ የግራ ፡ ዛብ ፡ ነጥሎ ፡ ሲይዝ
በት ፡ ቀኝ ፡ ወይም ፡ ግራ ፡ ይዞራል ፡ እጁ ፡ እንደመላላት ፡ ሲል
ለት ፡ ሽምጥ ፡ ግልቢያ ፡ ይጀምራል ። በመጨረሻ ፡ ዋጋየ ፡ የሚ
ያደርገው ፡ ሲያጣ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ በልጉዋም ፡ መታ
ውና ፡ ከጥርኝ ፡ አፍ ፡ ደም ፡ በብዛት ፡ ይወርድ ፡ ጀመር ። ፊታ
ውራሪ ፡ ደሙን ፡ ሲያዩ ፡ ልክ ፡ የሳቸው ፡ አፍ ፡ ተመትቶ ፡ እን
ደቆሰለና ፡ ደሙ ፡ ከሳቸው ፡ አፍ ፡ እንደጎረፈ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡
እምዋቸው ፡ "ውረድ ፡ ከፈረሴ ፡ ፈረሴን ፡ አምጣ ፡ ብዬሃለሁ፡
አንተ ! " አሉ ፡ እዩሥሡ ፡ መውደቅ ፡ ካልሆነ ፡ ለመውረዱም፡
ጥርኝ ፡ ትንሽ ፡ ለዘብ ፡ ካላለ ፡ የሚቻል ፡ አልሆነም ። ብቻ ፡
ኩብዙ ፡ ትግል ፡ በሁዋላ ፡ ሰውዬው ፡ ዋጋየ ፡ በመሆኑ ፡ እንደ
ምንም ፡ ወርዶ ፡ ጥርኝን ፡ እዩሳበ ፡ ይዞ ፡ ሲቀርብ ፡ የዋጋየ ፡
ላብ ፡ ልክ ፡ ከነፋሎት ፡ እንደወጣ ፡ በፊቱ ፡ ይጎርፍ ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ ከቆሙበት ፡ ቦታ ፡ እዩሮጡ ፡ ወርደው ፡
ዛቡን ፡ ከዋጋየ ፡ እጅ ፡ በቁጣ ፡ ነጥቀው ፡ የጥርኝን ፡ አንገት ፡
ቀስ ፡ ብለው ፡ መታ ፡ መታ ፡ ሲያደርጉ ፡ ጥርኝ ፡ የቆሰለ ፡ አፉን፡
በትከሻቸው ፡ ላይ ፡ አስደግፎ ፡ እያሸ ፡-"እ ሀ ሀ . . . እ ሀ ሀ ሁ፡"
ይል ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ርካብ ፡ ረግጠው ፡ የሽማግሌ ፡ ወገብ
ቸውን ፡ ጎትተው ፡ እኮረቻው ፡ ላይ ፡ አሸራሽተው ፡ እስኪያስቀ
ምጡ ፡ ጥርኝ ፡ እንደሚነት ፡ መጋገር ፡ ጆሮዎቹን ፡ ጥሎ ፡ እካ
ሉን ፡ አዝሎ ፡ ጠበቃቸውና ፡ ተደላድለው ፡ ተቀምጠው ፡ ዛብ፡

አመዛዝነው ፡ ጨብጠው ፡ በግራቀኝ ፡ እግራቸው ፡ መካል ከል ፡ ሲጀምሩ ፡ ጥርኝ ፡ ጭራውን ፡ ነስንሶ ፡ አንገቱን ፡ ወደ ታች ፡ ሰበር ፡ ጆሮዎቹን ፡ ወደፊት ፡ ቀስሮ ፡ አድርጎ ፡ ኀብኛ ፡ ዳንኪራ ፡ መምታት ፡ ጀመረ ። ፊታውራሪ ፡ እጃቸውን ፡ ለቀቅ ፡ ሲያደርጉ ፡ ጥርኝ ፡ ትንሽ ፡ ፈጠን ፡ ያለ ፡ ሲያደርጉ ፡ ረገብ ፡ እያለ ፡ እንዳገው ፡ በፋኝ ፡ ደረቱን ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ እያደረገ ፡ ዳንካላሳ ፡ ሲሄድ ፡ ለተመልካች ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ማሰኘቱ ! ለተቀመጡበት ፡ ለፊታውራሪ ፡ መመቸቱ ! ፊታውራሪ ፡ ልባቸው ፡ በደስታ ፡ ኢዮዋና ፡ እዚያው ፡ ባቅራቢያው ፡ ሶስት ፡ ዙረያ ፡ ከዞሩ ፡ በሁዋላ ፡ ለማጥሚያው ፡ እሱን ፡ ለመቀመጥ ፡ ወስነው ፡ እንዳይደክምባቸው ፡ ቶሎ ፡ ወረዱ ።

ጊዮርጊስ ፡ የተለመደ ፡ በራኬውን ፡ ነፍጎዋቸው ፡ ቀበሮ ፡ ከቀኝ ፡ ወደግራ ፡ ቆርጣቸው ፡ ሆድ ፡ ብሰዋቸው ፡ አሲኝ ፡ የሚሉት ፡ ተስፋቸውን ፡ የሚያሳርፉበት ፡ አጥተው ፡ የነበሩት ፡ ፊታውራሪ ፡ የጥርኝን ፡ ፍቅር ፡ ሲያዩ ፡ ጥርኝ ፡ የሳቸውን ፡ ፊቃድ ፡ ብቻ ፡ ለመፈጸም ፡ ለሳቸው ፡ የቆመ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዱ ፡ እንደገና ፡ የደስታና ፡ የተስፋ ፡ ስሜት ፡ ልባቸውን ፡ አሞቀው ። እንደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወዳጁን ፡ የማይከዳው ፡ ታማኙ ፡ ጥርኝ ፡ እንደገና ፡ ለልባቸው ፡ ተስፋ ፡ ሰጠው ።

ፊታውራሪ ፡ ወርደው ፡ የቆሰለ ፡ አፉን ፡ እያዩ ፡ አንገቱንም ፡ ግንባሩንም ፡ እየደባበሱ ፡ "አይዞህ ፡ ጥርኝ ፡ አይዞህ ፡ ጥርኝ ፡ " ሲሉ ፡ ጥርኝም ፡ " ግዴለም ፡ እኔ ፡ አለሁልህ ፡ አትስጋ ፡ " እንደሚል ፡ ሁሉ ፡ አንገቱን ፡ ላይና ፡ ታች ፡ ቀና ፡ ደፋ ፡ እያደረገ ፡ " እ ህ ህ እ ህ ህ ፡ " ሲል ፡ ቆሞም ፡ ተቀምጦም ፡ ይመለከት ፡ የነበረ ፡ ሁሉ ፡ ተገረመ ።

"ያ ፡ ምን ፡ ህዝብ ፡ ነው ፡ እባካችሁ ፡ ወይስ ፡ የሽማግሌ ፡ አዩኔ ፡ ነው ? " አለ ፡ ልጅ ፡ በለቀ ፡ አቋዋርጠው ፡ ወደሰሜን-ምእራብ ፡ እየመለከተ ።

**ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ሰፈር ፡ ሰሜን-ምዕራብ ፡ ከፊታ**ውራሪ ፡ አስጌ ፡ ሰፈር ፡ ሰሜን ፡ ከቢቸና ፡ ወገን ፡ ካሉው ፡ ጋራ ፡ ስር ፡ ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የሌለው ፡ ህዝብ ፡ ድንገት ፡ ታዩ ። ከርቀቱ ፡ የተነሳ ፡ የጉንዳን ፡ ሰራዊት ፡ እንጂ ፡ ህዝብ ፡ አይመስልም ፡

ነበር ። ምንምንኳዋ ፡ በዚያ ፡ ርቀት ፡ ያ ፡ ህዝብ ፡ የሚጉዋዝ ፡ ወይም ፡ የሰፈረ ፡ መሆኑን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ባይቻል ፡ ፊታውራሪና ፡ ሰራዊታቸው ፡ ሲመጡ ፡ እዚያ ፡ ስላልነበረ ፡ አዲስ ፡ መጪንጂ ፡ ሰፍሮ ፡ ያልቆዩ ፡ መሆኑ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነበር ።

ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡ ያ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ የመሰለ ፡ ህዝብ ፡ ቀረብ ፡ ማለትና ፡ አንዳንድ ፡ ያልታዩም ፡ ነገር ፡ መታየት ፡ ጀመረ ።

"ምን ፡ ታምር ፡ ነው ? በህዝቡ ፡ ላይ ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ ብሎ፡ የሚታያችሁ ፡ ነገር ፡ አለ ? " አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ የወታደር ፡ ሰላምታ ፡ እንደሚሰጡ ፡ አንድ ፡ እጃቸውን ፡ አቅንድባቸው ፡ ላይ ፡ አድርገው ፡ እየተመለከቱ ።

"አሞራ ! በህዝቡ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ የሚያንዣብብ ፡ ብዙ ፡ አሞራ ፡ ያለ ፡ ይመስላል ! " አለ ፡ አንድ ፡ ወታደር ።

ያ ፡ አገር ፡ ምድር ፡ አልብሶ ፡ ተስ ፡ እያለ ፡ የሚጉዋዝና ፡ ባሞራ ፡ የታጀበ ፡ ህዝብ ፡ እየቀረበ ፡ እየቀረበ ፡ ሲመጣ ፡ በላዩ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ያንዣብባል ፡ የተባለው ፡ ብዙ ፡ አሞራ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ተለይቶ ፡ ይታይ ፡ ጀመረ።

"አ . . . ! አሞራ ፡ አይደለም ፡ ጃንጥላና ፡ ድባብ ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ የሚወርድ ፡ ታቦት ፡ ነው ! " አለ ፡ አንድ ፡ ወታደር ።

" አ . . . . ! ታቦት ! ታቦት ! " አለ ፡ ገርሞት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እየተቀባበለ ። ከዚያ ፡ ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ጋር ፡ ከነበረው ፡ ህዝብ ፡ አንዳንዱ ፡ በህልም ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ መስሎት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አንዳንዱ ፡ ደርሶ ፡ የማያውቅ ፡ ታምር ፡ የሚደርስ ፡ መስሎት ፡ ይጠብቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ፡ ታቦት ፡ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በሁዋላ ፡ የምን ፡ ታቦት ፡ ወይም ፡ ወንዝ ፡ እንደሚወርድ ፡ እስበሱ ፡ እየተች ፡ ይንጫጫ ፡ ጀመረ ። እውነትም ፡ ታቦት ፡ የሚወርድበት ፡ ወንዝ ፡ በቅራቢያው ፡ ስላልነበረና ፡ አንዳንድ ፡ ትናንሽ ፡ ምንጮችም ፡ ቢኖሩ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ህዝብ ፡ የሚያጅበው ፡ ታቦት ፡ እዚያ ፡ ግድም ፡ መውረዱን ፡ አይቶም ፡ ሰምቶም ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ስላልነ

በረ ፡ ምስጢሩ ፡ ጨርሶ ፡ አልተፈታም ።

የታቦት ፡ ጉዞ ፡ የሚወስደውን ፡ ጊዜ ፡ ከወሰደ ፡ በሁዋላ ፡ ታቦቱና ፡ አጃቢው ፡ በጣም ፡ ቀረበ ። ድባዎችና ፡ ጃንጥላዎች ፡ በዩቀለማቸው ፡ ልብስ ፡ ተክህኖ ፡ የለበሱት ፡ ካልለበሱት ፡ ተለይተው ፡ ለሽማግሌዎች ፡ አይን ፡ ሳይቀር ፡ መታየት ፤ የከበሮው ፡ ድምጽ ፡ መሰማት ፡ ጀመረ ።

ታቦቱ ፡ በፈታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ሰፈር ፡ አቅጣጫ ፡ ሲደርስ፡ ሰፈሩን ፡ ወጀቀኝ ፡ ትቶ ፡ ቀጥታ ፡ ወደደቡብ ፡ የሚሄድ ፡ ከመሰለ ፡ በሁዋላ ፡ እንደገና ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ወደፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ሰፈር ፡ አመራ ።

"ወዲህ ፡ መምጣቱ ፡ ነው ፡ እንዴ ?" አሉ ፡ ልጅ ፡ እጅጉ። ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ፡ ብለው ፡ ሳቃቸው ፡ እንዳይታይባቸው ፡ ኩታቸውን ፡ ወዳፍንጫቸው ፡ ገፉ ፡ አደረጉ ። ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ሁሉ ፡ ጉዳያቸውንንጂ ፡ ስለታቦቱ ፡ ሰው ፡ የሚተቸውን ፡ በሙሉ ፡ አይከታተሉም ፡ ነበር ።

ታቦቱን ፡ ያጀበው ፡ ህዝብ ፡-"እግዚኦ ፡ መሀረነ ፡ ክርስቶስ ፡ በእንተ ፡ ማርያም ፡ መሀረነ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰእሊ ፡ ለነ ፡ ማርያም ፡ ምህረተ ፡ ወልድኪ ፡ የሀውጸነ ፡" እያለ ፡ በዜማ ፡ ምህረት፡ እዩለመነ ፡ ይጉዋዝ ፡ ነበረ ።

"ሁለት ፡ ታቦት ! " አለ ፡ ከወታደሮቹ ፡ አንዱ ፡ እንደገና ።

"አንዱ ፡ የዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ነው ! " አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ደንግጠው ። የዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፡ ፈታውራሪም ፡ በጣም ፡ ደነገጡ ። ያንጊዜ ፡ ብቻ ፡ አሳባቸው ፡ በፊታቸው ፡ የተዘበበውን ፡ ጦርነት ፡ ማሰላሰል ፡ ለቀቅ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መለስ ፡ አለና ፡ እንደ ፡ መሸበር ፡ ብለው ፡ "አምጣ ፡ ጠመንጃየን ! " አሉ ፡ ፈታውራሪ ። ጠመንጃቸውን ፡ ተቀብለው ፡ በትከሻቸው ፡ ሲይዙ ፡ መኩዋንንቱ ፡ ሁሉ ፡ ጠመንጃውን ፡ ከዩጋሻጃግሬው ፡ እዩተቀበለ ፡ ይዞ ፡ እንዳውሬ ፡ አጥማጅ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ ወደፈታውራሪ ፡ ሰፈር ፡ የሚ

ያዘጋሙትን ፡ ሁለት ፡ ታቦቶች ፡ ይጠብቅ ፡ ጀመረ ።

የዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ገዳም ፡ በመሆኑ ፡ ድንግላዊ ፡ መነኩሴ ፡ ተሸክመውት ፡ የቢቸና ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደብር ፡ በመሆኑ ፡ ቄስ ፡ ተሸክመውት ፡ የዲማ ፡ መምህር ፡ በዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ግራ ፡ የቢቸና ፡ አለቃ ፡ በቢቸና ፡ ጊዮርጊስ ፡ ግራ ፡ ሆነው ፡ የሁለቱን ፡ ታቦቶች ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ የለበሱ ፡ ካህናት ፡ በዬታቦታቸው ፡ ፊት ፡ ተሰልፈው ፡ የዲማ ፡ ገዳምና ፡ የቢቸና ፡ ደብር ፡ ካህናት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ ባካባቢው ፡ ያሉ ፡ ገጠሮች ፡ ካህናትና ፡ ለበአሉ ፡ የተሰበሰበው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሳሚ ፡ ሁሉ ፡ በሁዋላ ፡ ተከትሎ ፡ ፈረስ ፡ ሜዳ ፡ ጠቦት ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ “ እግዚኦ ፡” እያለ ፡ መጥቶ ፡ እፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ፊት ፡ ሲደርስ ፡ ቆመ ። ከዚያ ፡ የፊታውራሪ ፡ አሽኬ ፡ ሰራዊት ፡ በሁዋላ ፡ ተከትሎ ፡ መጣ ። ወዲያው ፡ የዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መምህር ፡ አለቃ ፡ ጥኡመ፡ ልሳን ፡ ነጠል ፡ ብለው ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ተራምደው ፡ ቆመው ፡—

“ ይምሀረነ ፡ ወይሰሀለነ ፡ ይቀበነ ፡ ወይትመሀጸነነ ፡ እግዚአብሄር ፡ ለበደለ ፡ ምህረቱን ፡ ለታመመ ፡ መድሀኒቱን ፡ ይስጥልን ፡ እግዚአብሄር ። ወንድማችን ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡- ዛሬ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከሩቅም ፡ ከቅርብም ፡ በደጁ ፡ የሚሰበሰቡትን ፡ ምእመናን ፡ በሚቀበልበትና ፡ የምእመናኑን ፡ ልመና ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ፈጣሪ ፡ ፊት ፡ በሚቀርብበት ፡ የአመት ፡ በአሉ ፡ እርስዎን ፡ በደለኛውን ፡ እርስዎን ፡ እንዳባትዎ ፡ እንዳዳም ፡ የፈጣሪን ፡ ስልጣን ፡ ለመካፈል ፡ ታጥቀው ፡ የተነሱትን ፡ ጥፋተኛ ፡ ተከትሎ ፡ ፈረስ ፡ ሜዳ ፡ ድረስ ፡ መምጣቱ ፡ ይገርምዎ ፡ ይሆናል ። አዎ ! እንደስዎ ፡ የክርስቲያንነትን ፡ ስምንጂ ፡ ግብር ፡ ለማያውቁ ፡ ሁሉ ፡ እንደስዎ ፡ የቅዱሳንን ፡ ባህርይ ፡ ለማያውቁ ፡ ሁሉ ፡ ቢገርማቸው ፡ አያስገርምም ። እግዚአብሄር ፡ በጣም ፡ የሚወደው ፡ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ አልቆ ፡ ባራያው ፡ የፈጠረው ፡ አዳም ፡ የፈጣሪውን ፡ ስልጣን ፡ በመመኘቱ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶበት ፡ ሲኦል ፡ ቢወርድ ፡ እንደሱ ፡ እንደበደለኛው ፡ ሞቶ ፡ ያዳምን ፡ ነፍስ ፡ ፍለጋ ፡ ሲኦል ፡ ድረስ ፡ ወረደ ። እንዲሁም ፡ ዛሬ ፡ እስዎ ፡ በፈጣሪ ፡ ስልጣን ፡ ገብቷል ፡ እሱ ፡

በረቂቅ ፡ ምስጢሩ ፡ ሰማያዊት ፡ ነፍስን ፡ ከምድራዊት ፡ ስጋ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አዋህዶ ፡ የፈጠረውን ፡ ፍጡር ፡ ለማጥፋት ፡ ታጥቀው ፡ ስለተነሱ ፡ በምድር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሰማይ ፡ ጭምር ፡ ሞተው ፡ እንዳይቀሩ ፡ ከዘላለማዊ ፡ ጥፋት ፡ ሊያድንዎ ፡ የሚወዶዎ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፍለጋዎን ፡ ተከትሎ ፡ መጥቶ ፡ እነሆ ፡ እፊትዎ ፡ ቆሞዋል ። ምንም ፡ በደልዎ ፡ ሀያል ፡ ቢሆን ፡ ይቅር ፡ ብለው ፡ ይቅርታ ፡ የለመኑ ፡ እንደሆነ ፡- መሀሪ ፡ ነውና ፡ ይምርዎታል ። ” ብለው ፡ ወደነበሩበት ፡ ተመለሱ ። ከዚያ ፡ የቢቸናው ፡ አለቃ ፡ ንዋይ ፡ እንዲሁ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ እርምጃ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ቆመው ፡—

“ ጌታዬ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡- ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ወንድሜ ፡ መምህር ፡ ጥኡመ ፡ ልሳን ፡ ከተናገሩት ፡ ሌላ ፡ የምጨምረው ፡ ባይኖርና ፡ በሳቸው ፡ ላይ ፡ መናገር ፡ ባይገባኝ ፡ በቢቸና ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስም ፡ ጥቂት ፡ ቃላት ፡ መናገር ፡ ስላለብኝ ፡ ከመላ ፡ ጎደል ፡ እሳቸው ፡ ያሉትን ፡ እደግመዋለሁ ።

የርስዎንም ፡ ሆነ ፡ የሌላውን ፡ ነፍስ ፡ ከስጋ ፡ አዋህዶ ፡ የሰራ ፡ ፈጣሪ ፡ ስለ ሆነ ፡ የሰራውን ፡ ማፍረሱም ፡ የሱ ፡ ስልጣን ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ምንም ፡ ዛሬ ፡ እዳምን ፡ ያሳተ ፡ ሰይጣን ፡ አይነ ፡ ህሊናዎን ፡ ቢሰውረው ፡ ከስዎ ፡ የተሻለ ፡ የሚያውቅ ፡ እለመኖሩን ፡ እናውቃለን ። የስዎን ፡ የራስዎን ፡ ነፍስ ፡ እንኩዋ ፡ የኔ ፡ ናት ፡ ብለው ፡ ከስጋዎ ፡ ለመለዩት ፡ ቢሹ ፡ በፈጣሪ ፡ ፊት ፡ ትልቅ ፡ በደለኛ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ነፍስ ፡ ከእግዚአብሄር ፡ በቀር ፡ የማንም ፡ አይደለችም ፤ የነፍስዎ ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሄር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ዛሬ ፡ ታጥቀው ፡ የመጡለት ፡ ስራ ፡ በፈጣሪ ፡ ፊት ፡ ከበደል ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ በደል ፡ ነው ። ብቻ ፡ እግዚአብሄር ፡ በቸርነቱ ፡ ተሳስተው ፡ በጥፋት ፡ መንገድ፡ የሚሄዱትን ፡ አይተዋቸውም ፤ ይከተላቸዋል ፤ መመለሻ ፡ መንገድም ፡ ሰርቶላቸዋል ። ይህ ፡ ከጥፋት ፡ ወደ ፡ ፈጣሪ ፡ መመለሻው ፡ መንገድ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ ነው ፤ እሱም፡ መጸጸት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ በደልዎ ፡ ታላቅ ፡ ቢሆን ፡ ከተጸጸቱና ፡ ምህረት ፡ ከለመኑ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከመሀሪው፡ ከእግዚአብሄር ፡ እንደሚያስምርዎ ፡ አይጠረጠርም ። አይነ ፡

ሀሊናዎ ፡ ልቡናዎ ፡ በእምጽ ፡ ተሸፍኖ ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ጥፋትዎ ፡ እስኪሄዱ ፡ ድረስ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እየተከተለ ፡ ወደ ፡ ፈጣሪዎ ፡ መመለሻውን ፡ መንገድ ፡ ያመለክትዎታል ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በምሳሌ ፡ ሲያስተምር ፡ "ብዙ ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ቢኖርና ፡ ከመንጋው ፡ መሃከል ፡ አንድ ፡ በግ ፡ ቢጠፋው ፡ ብዙ ፡ መንጋውን ፡ ትቶ ፡ የጠፋውን ፡ አንድ ፡ በግ ፡ ፍለጋ ፡ ይሄድ ፡ የለምን ?" እንዳ ለው ፡ ሁሉ ፡ ዛሬ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በብዙ ፡ ምእመናን ፡ በብዙ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ለፈቃዱ ፡ ያስገዙ ፡ አማኞች ፡ በሩን ፡ ዘግቶ ፡ ቅዳሴውንም ፡ አስቃጉሎ ፡ እስዎን ፡ ከምእመናን ፡ መሀ ከል ፡ ተለይተው ፡ የጠፉትን ፡ አንዱን ፡ ፍለጋ ፡ በዱር ፡ በገደል፡ ተጉዞ ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ መጣ ። በመንበሩ ፡ ተቀምጠ ፡ ከሩቅ ፡ እየመጡ ፡ የሚለምኑት ፡ ሊቀ ፡ ሰማእታት ፡ ጊዮርጊስ ፡ እስዎን፡ በደለኛውን ፡ ተከትሎ ፡ እስዎ ፡ ጠፍተው ፡ እንዳይቀሩ ፡ ሲለም ንዎ ፡ ይቅርታ ፡ ያስጥዎ ፡ ዘንድ ፡ እስዎ ፡ አስቀድመው ፡ ይቅር ፡ እንዲሉ ፡ እነሆ ፡ በፊትዎ ፡ ቆሞ ፡ ይለምንዎታል !" ብለው ፡ ወደነበሩበት ፡ ተመለሱ ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የዲማና ፡ የቢቸና ፡ ጊዮርጊስ ፡ ታቦ ቶች ፡ እፊታቸው ፡ በሙሉ ፡ ግርማ ፡ ቆመው ፡ ሁለቱ ፡ ሊቃው ንት ፡ በደላቸው ፡ ከበደል ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ መሆኑን ፡ በዬተራ ፡ እየተቀባበሉ ፡ ሲገልጹላቸው ፡ ያንለት ፡ ለመፈጸም ፡ ታጥ ቀው ፡ የመጡለት ፡ በደል ፡ በአዳም ፡ እስከ ፡ ዘራዝርእቱ ፡ ሞት፡ ካስፈረደበት ፡ በደል ፡ የሚመዘዘን ፡ መሆኑን ፡ ከሊቃውንቱ ፡ አፍ ፡ ሲሰሙ ፡ በደላቸው ፡ ክርስቶስን ፡ ከመልእልተ ፡ ሰማያት፡ መንበረ ፡ ጸባኦቱ ፡ አስወርዶ ፡ በፍጡሮቹ ፡ እጅ ፡ መከራ ፡ እን ዲቀበልና ፡ እንዲሞት ፡ ካደረገው ፡ ከታላቁ ፡ በደል ፡ የማያንስ ፡ መሆኑን ፡ ሲሰሙ ፡ ያንለት ፡ ሊፈጽሙት ፡ የፈለጉት ፡ እመጽ ፡ የክርስቶስ ፡ ሞት ፡ ብቻ ፡ የማይሽረው ፡ ሆኖ ፡ ሲኦል ፡ እንዲወ ርድ ፡ ካደረገው ፡ ከመጀች ፡ እመጽ ፡ የሚወዳደር ፡ መሆኑን ፡ ሁለቱ ፡ ሊቃውንት ፡ በምሁር ፡ አንደበት ፡ እየተቀባበሉ ፡ ሲነ ግሩዋቸው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በጊዮርጊስ ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ ሲሰሙ፡

እግዚአብሔር ፡ በእለት ፡ ምጻት ፡ በግርማ ፡ መለኮቱ ፡ ወርዶ ፡ በሀጥአን ፡ ስለሚፈርደው ፡ ፍርድ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ሲሰብኩዋቸው ፡ የኖሩት ፡ ያንሸት ፡ ልክ ፡ በነሱ ፡ የተፈጸመ ፡ መስሎዋቸው ፡ ይንቀጠቀጡ ፡ ነበር ።

አለቃ ፡ ንዋይ ፡ ንግግራቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ወደነበሩበት ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ጠመንጃቸውን ፡ ጥለው መጀመሪያ ፡ የዲማውን ፡ ጊዮርጊስ ፡ በተሸከሙት ፡ መነኩሴ ፡ እግር ፡ ወድቀው ፡ “ ማረኝ ፡ ጌታየ ፡ አላዋቂ ፡ ባሪያህን ፤ ደንቆሮ ፡ ባሪያህን ፡ ማር ፤ በጾር ፡ በገዳል ፡ ስላንገላታሁህ ፡ ማረኝ ። ” እያሉ ፡ ሲያማጥኑ ፡ ቆዩና ፡ ከዚያ ፡ ተነስተው ፡ እንደገና ፡ የቢቸናውን ፡ ጊዮርጊስ ፡ በተሸከሙት ፡ ቄስ ፡ እግር ፡ ወድቀው ፡ ያኑ ፡ ለዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ያቀረቡትን ፡ ልመና ፡ እየመላለሱ ፡ ሲደግሙ ፡ ቆይተው ፡ ፊታቸውን ፡ ያረት ፡ መሬትና ፡ ያረቅ ፡ ሳር ፡ በሚጣምርት ፡ ሲነሱ ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ጠመንጃቸውን ፡ በትክሻቸው ፡ ተሸክመው ፡ እግራቸው ፡ ላይ ፡ ሲወድቁ ፡ አዩ ።

“ ተቀበለው ! ተቀበለው ! ጠመንጃውን ፡ ተቀበለው ! ” አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ዝቅ ፡ ብለው ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌን ፡ ከወደቁበት ፡ አንስተው ፡ ሳሙዋቸው ።

“ ይማሩኝ ፡ አባቴ ፡ ጌታየ ፤ በድፍረት ፡ ሳይሆን ፤ ባለውቀት ፡ በድንቁርና ፡ በድየዎታለሁና ፡ ይማሩኝ ፤ ከልብዎ ፡ ይማሩኝ ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ አንገት ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ እየሳሙ ።

“ አውቀህም ፡ ይሁን ፡ ሳታውቅ ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፤ አንተም ፡ ማረኝ ፡ ልጄ ፡ ጌታየ ፡ ማረኝ ፡ ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ።

ከዚያ ፡ የዲማና ፡ የቢቸና ፡ ጊዮርጊስ ፡ ታቦቶች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ጠመንጃቸውን ፡ ይዘው ፡ በታቦቶቹ ፡ ፊት ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ሁለቱን ፡ ታቦቶችና ፡ ሁለቱን ፡ ፊታውራሪዎች ፡ ያጀበው ፡ ህዝብ ፡ ፈረስሜዳን ፡ ሞልቶ ፡ መምህር ፡ ጥኡመ ፡ ልሳን ፡ ካሳረጉ ፡ በሁዋላ ፡ ካህናቱ ፡ ንሴብሆ ፡ በማለት ፡ ህዝቡ ፡ በልልታና ፡ በጭብ

ጨብ ፡ ደስታውን ፡ ገልጾ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የዲማ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ፊታውራሪ ፡ እስጌ ፡ የቢቸና ፡ ጊዮርጊስን ፡ አጅበው ፡ ወደያገራቸው ፡ ተመለሱ ።

# ምእራፍ ፡ ፲፩ ፡

## የጋራ ፡ ድል ፡

በፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ በፊታውራሪ ፡ እሰጌ ፡ መሀከል ፡ ፈረስ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እንዲሆን ፡ ተወስኖ ፡ የነበረው ፡ ውድድር ፡ ሁለቱ ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ በያሳባቸው ፡ ድል ፡ አግኝተው ፡ የወጡበት ፡ ስለሆነ ፡ እነሱንም ፡ ወገኖቻቸውንም ፡ ደስ ፡ አሰኘ ።

ፊታውራሪ ፡ እሰጌ ፡ አያደርጉ ፡ አድርገው ፡ በፍሬት ፡ መሰላል ፡ እስኪ ፡ መጨረሻው ፡ የታችኛ ፡ ደረጃ ፡ ወርደውን ኩዋ ፡ ቢሆን ፡ ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ጋር ፡ መሰላለፉና ፡ ክንድ ፡ መዘረጋጋቱ ፡ እንዲቀናሳቸው ፡ እጥብቀው ፡ ይፈልጉ ፡ ስለ ነበረ ፡ ይህ ፡ የፈለጉት ፡ በመፈጸሙ ፡ ድል ፡ እንዳደረጉ ፡ ቆጠሩት ። ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በዘመናቸው ፡ የጀግኖች ፡ ጀግና ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ የነበራቸው ፡ ስመጥር ፡ ጀግና ፡ ቢሆኑም ፡ ይህ ፡ ጀግንነት ፡ መታሰቢያውን ፡ ብቻ ፡ ትቶ ፡ ከዘመናቸው ፡ ጋር ፡ አልፎ ፡ እሳቸውም ፡ ራሳቸው ፡ የሚያልፉበት ፡ ቀን ፡ የቀረበ ፡ የሚገነዙበት ፡ ገመድ ፡ ተርሶ ፡ የሚቀበሩበት ፡ መቃብር ፡ ተምሶ ፡ የሚጠብቃቸው ፡ ሬሳ ፡ ሽማግሌ ፡ ስለሆኑ ፡ በፊታውራሪ ፡ እሰጌ ፡ አስተያየት ፡ ከሳቸው ፡ ጋር ፡ መወዳደር ፡ ከሬሳ ፡ ጋር ፡ መወዳደር ፡ ነው ። በፊታውራሪ ፡ እሰጌ ፡ አስተያየት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሬሳ ፡ መግደል ፡ የጀግና ፡ ጠርና ፡ ጎራዴ ፡ የሚያጎለድፍ ፡ የጀግና ፡ ስምና ፡ ታሪክ ፡ የሚያሳድፍ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሬሳ ፡ መግደል ፡ እየ ፡ ጎበዝ ፡ አያሰኝም ፡ በጀብድ ፡ ላይ ፡ ጀብድ ፡ አይጨምርም ። በፊታውራሪ ፡ እሰጌ ፡ አስተያየት ፡ ሬሳ ፡ ከመግደል ፡ የበለጠ ፡ ውርደት ፡ ሊኖር ፡ አይችልም፤ ሬሳ ፡ ከመግደል ፡ የማይሻል ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ሬሳ ፡ ከመግደል፡ የሬሳ ፡ እግር ፡ ስሞ ፡ የታቦት ፡ አማላጅ ፡ ይዞ ፡ ምህረት ፡ መለመን ፡ እንደሚያስከብር ፡ አይጠረጠርም ! ስለዚህ ፡ ፊታውራሪ፡ እሰጌ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አስበው ፤ አመዛዝነው ፡ የወሰኑት ፡ ውሳኔ፡ ስለተፈጸመላቸው ፡ ድሉ ፡ የሳቸው ፡ መሆኑን ፡ አምነው ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በበኩላቸው ፡ ምንምንኳ ፡ ውድ ድሩ ፡ ጭራሽ ፡ ባላሰቡት ፡ ጭራሽ ፡ ባልጠረጠሩት ፡ መንገድ ፡ ቢያልቅ ፡ ውጤቱ ፡ የማይጠረጠር ፡ ድል ፡ እንደሰጣቸው ፡ አምነው ፡ ደስታቸው ፡ ዳር ፡ ድንበር ፡ አልነበረውም ።

የዲማና ፡ የቢቸና ፡ ጊዮርጊስ ፡ ታቦቶች ፡ ፈረስሜዳ ፡ ድረስ፡ ወጥተው ፡ የነማይ ፡ ህዝብ ፡ በሙሉ ፡ እግዚእ ፡ ብሎ ፡ ፊታው ራሪ ፡ አሰጌ ፡ እግራቸው ፡ ስር ፡ ወድቀው ፡ ሳር ፡ እየነከሱና ፡ አፈር ፡ እየላሱ ፡ ምህረት ፡ ለምነው ፡ በሰው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በታቦት ፡ አማላጅነት ፡ ጎራዴዎቻቸውን ፡ ወደ ፡ ሰገባው ፡ ጦራቸውን ፡ ወደ ፡ ፎዳራው ፡ እንዲመልሱና ፡ ይቅር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲሉ ፡ እግዚእ ፡ ተብሎ ፡ ይህ ፡ ሁሉ፡ ሆኖ ፡ ይቅር ፡ ያሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ሲያስቡ ፡ ድሉ ፡ የማይጠረ ጠር ፡ የሳቸው ፡ መሆኑን ፡ አምነው ፡ ደስታቸው ፡ ዳር ፡ ድን በር ፡ አልነበረውም ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ለብቻቸው ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ የነማይ፡ ህዝብ ፡ በሙሉ ፡ ሁለት ፡ ታቦት ፡ ተሸክሞ ፡ እግዚእ ፡ እያለ ፡ ፈረስሜዳን ፡ ያጥለቀለቀው ፡ ጊዮርጊስ ፡ ባውዳመቱ ፡ ቅዳሴ ፡ እስታጉሎ ፡ አብዮት ፡ ክርስቲያኑን ፡ ዘግቶ ፡ እሳቸውን ፡ ለመ ማለድ ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ስለመንከራተቱ ፡ ሁለቱ ፡ ሊቃው ንት ፡ የተቀባበሉ ፡ የተናገሩትን ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ጠመን ጃቸውን ፡ ተሸክመው ፡ እግራቸው ፡ ስር ፡ ወድቀው ፡ የተንከባ ለሉትን ፡ ይህን ፡ ያዩና ፡ የሰማ ፡ ሁሉ ፡ በየሸንጎውና ፡ በየድ ግስ ፡ ቤቱ ፡ ስለጀግንነታቸው ፡ የሚያወራውን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ላንድ ፡ ጀግና ፡ የሚበቃ ፡ ታላቅ ፡ ጀግንነት ፡ ከሳቸው ፡ አልፎ ፡ ተርፎ ፡ ለወገናቸው ፡ የሚሰጠውን ፡ ክብር ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቻቸውን ፡ የሚያስደስትና ፡ የሚያስከብር ፡ ጠላታቸውን ፡ የሚያሳፍር ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ባይን ፡ ህሊናቸው ፡ ፊት ፡ አሰልፈው ፡ ሲመለከቱ ፡ ደስታ ፡ ከተቀመጡበት ፡ በክንፉ ፡ ይዞዋቸው ፡ ወደሰማየ ፡ ሰማ ያት ፡ ያርግ ፡ ነበር ።

ከዚያ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌን ፡ እና ለማስሁ ፡ ብለው ፡ ሲወስኑ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ ሁሉ ፡ የለመናቸ

ውን ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ምሽታቸውና ፡ ልጆቻቸው ፡ እንባቸውን ፡ እያጎረፉ ፡ ሲሰናበቱዋቸው ፡ ትንሽ ፡ የመነቱትን ፡ ያስታውሱና ፡ ለብቻቸው ፡ እንደመሳቅ ፡ ብለው ፡ “ያንጊዜ ፡ ልመናውን ፡ እንዳልሰማ ፡ ልቅሶውን ፡ እንዳላይ ፡ ጆሮየን ፡ ደፍኜ ፡ አይኔን ፡ ጨፍኜ ፡ ወደፊት ፡ ባልሄድ ፡ የጥሩየንና ፡ የሰብለን ፡ የንባ ፡ ጎርፍ ፡ ተሻግሬ ፡ ባልሄድ ፡ ይህ ፡ ክብር ፡ ይገኝ ፡ ኖርዋል ? ክብር ፡ ለደፋርና ፡ ለቆራጥንጂ ፡ ለፈሪና ፡ ላመንቺ ፡ ሆና ፡ አታውቅም ፡ ይሉ ፡ ነበር ፡ አባቴ ! ግዶለም ፡ ለወደፊቱ ፡ ማንም ከሚለው ፡ እኔ ፡ ያልሁት ፡ የሚሻል ፡ ለመሆኑ ፡ ይህ ፡ የማያዳግም ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ! ” ይላሉ ። ይህም ፡ ባይሆን ፡ ቅሉ ፡ ፈረስ ፡ ሜዳ ፡ የተገኘው ፡ ድል ፡ ባጋጣሚ ፡ የተገኘ ፡ ቢሆንም ፡ ኖሮ ፡ ዞሮ ፡ የተገኘው ፡ ክብር ፡ በሳቸው ፡ ጥላ ፡ ለሚኖር ፡ ሁሉ ፡ ለዘመድ ፡ ለወዳጅ ፡ ሁሉ ፡ የሚተርፍ ፡ ስለሆነ ፡ በፊታውራሪ ፡ አስተያየት ፡ የሳቸው ፡ ወገን ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ሁሉ ፡ እንደታላቅ ፡ ባለውለታ ፡ እንደታዳጊ ፡ ሲቆጥራቸውና ፡ ሊወዷቸው ፡ ሊያከብሩቸው ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ያለማስተሀቀር ፡ ሊፈጽም ፡ የሚገባው ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። የሚናገሩትን ፡ የሚያስተሀቅር ፡ የሚያዙትን ፡ የማይፈጽም ፡ ቢኖር ፡ እንዲህ ያለው ፡ ሰው ፡ በሳቸው ፡ አስተያየት ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ እንደማይችል ፡ እንደውለታቢስ ፡ ሊቆጠር ፡ የሚገባው ፡ ነበር ።

የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤተሰብ ፡ ከምሽታቸውና ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጀምሮ ፡ እስከነገሌጋዮች ፡ ድረስ ፡ የሙሉ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ ጭምር ፡ ከፊታውራሪ ፡ እሰኄ ፡ ጋር ፡ ሲፋለሙ ፡ የህይወታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጦ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሄር ፡ በማይመረመር ፡ ምስጢሩ ፡ ስላተረፋቸው ፡ ሁሉም ፡ ደስ ብሎት ፡ ሁሉም ፡ ከሞት ፡ አፋፍ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ በሽተኛ ፡ ወይም ፡ ጠፍቶ ፡ እንደተገኘ ፡ ህጻን ፡ አይቶዋቸው ፡ እንኩዋን ፡ የሚፈልጉትን ፡ ተናግረው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸውን ፡ ነገር ፡ እየገመቱና ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እንቢ ፡ ሲሉ ፡ እንደ ፡ ህጻን ፡ እየባበለ ፡ ሊፈጽምላቸው ፡ ይሽቀዳደም ፡ ነበር ። በተለይ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አባትዋ ፡ ህይወታቸውን ፡ ሊያሳልፉ ፡ የነበረ ፡ በስዋ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ እያሰበች ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡

ጀምሮ ፡ እንክዋን ፡ ከሚናገሩት ፡ ለማወቅ ፡ ችሎታ ፡ ቢኖራት ፡ ከሚያስቡትና ፡ ከሚመኙትም ፡ አንድ ፡ ነጥብ ፡ ሳታጎል ፡ ለመ ፈጸም ፡ ታጥቃ ፡ ተነሳች ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ዘወትር ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ጋር ፡ መገኘትዋን ፡ እንደማይወዱና ፡ በዛብህ ፡ እንዲያስተ ምራት ፡ ከፈለጉባቸው ፡ ምክናያቶች ፡ አንዱ ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ጋር የምትገናኝበትን ፡ ጊዜ ፡ ለመቀነስ ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ፍቅርዋ ፡ ባይቀንስም ፡ የተቻላትን ፡ ያክል ፡ ከሱ ፡ ትሸሽ ፡ ጀመር ፡ ትምህርትዋንም ፡ ወዲያው ፡ ጀመረች ። እንዲያው ፡ በጠቅላላው ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ፊታውራሪ ፡ የቤተ ሰቡ ፡ አምላክ ፡ የዘመድ ፡ ሁሉ ፡ ቅምጥል ፡ ሆነው ፡ ቆዩ ፡ማለት፡ ይቻላል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሰጡት ፡ ትእዛዝ ፡ አሽከሮች ፡ ተሳስተው ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ የጎደለ ፡ እንደሆነ ፡ ፊታው ራሪ ፡ እቤታቸው ፡ የተሰበሰበው ፡ ሁሉ ፡ ውስታቢስ ፡ በመሆኑ ፡ መደዳውን ፡ መውቀስና ፡ እሳቸው ፡ ለወገናቸው ፡ ከዛር ፡ ያደ ረጉትን ፡ መስዋእትነት ፡ እየደጋገሙ ፡ መቁጠር ፡ ይጀምራሉ ።

" እመት ፡ ሁለት ፡ እመት ፡ እልሆነምኮ ! ትናንትኮ ፡ ነው ፡ ለናንተ ፡ ብዬ ፡ ለወገኔ ፡ ብዬ ፡ እንገቴን ፡ ለስለት ፡ ያረ ቴን . . . . . . . . ልሰጥ ፡ እጦር ፡ ሜዳ ፡ ሄጄ ፡ የተሰለፍሁ ! ህይ ወቱን ፡ ለወገኑ ፡ የሚያሳልፍ ፡ ከክርስቶስ ፡ በቀር ፡ ማነው ? ሁሉም ፡ እዚህ ፡ ተሰብስቦ ፡ ሲያለቅስ ፡ እኔ ፡ መሸሻ ፡ ነኝ ፡ እን ደክርስቶስ ፡ ህይወቴን ፡ ለወገኔ ፡ መስዋእት ፡ አድርጌ ፡ ያቀረ ብሁ ! ታዲያ ፡ ላደረግሁት ፡ ሁሉ ፡ የሚመለስልኝ ፡ ዋጋዩ ፡ ይህ ፡ ነው ! ግዴለም ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ እገኘዋለሁ ! " ሲሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ዋጋቸውን ፡ የሚያገኙበትን ፡ ወደላይ ፡ በጃቸው ፡ እያመለከቱ ፡ ምሽታቸውም ፡ ዘመዶቻቸውም ፡ ራሳቸውን ፡ መውቀስና ፡ ፊታውራሪን ፡ ማባበል ፡ ይጀምራሉ ። ፊታውራ ሪም ፡ ትንሽ ፡ ተለማምነው ፡ ይቅር ፡ ይላሉ ።

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ብቻ ፡ ፊታውራሪ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ውሀ ፡ በቀ ጠነ ፡ ሲበሳጩና ፡ ቤተሰቡ ፡ ሲጨነቅ ፡ ያይና ፡ " አባ ፡ ማሞ " እያለ ፡ ይስቅባቸዋል ፡ ወይም ፡ የሚናገሩትም ፡ ሆነ ፡ የሚያደ ርጉት ፡ ከመንገድ ፡ የወጣ ፡ ሲሆን ፡ ይቃወማቸዋል ። ብቻ ፡

ያግኑቱ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባህሪውን ፡ ስለሚያውቁ ፡ እሱ ፡ ቢቃወ ማቸውም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢሰድባቸውምንኳዋ ፡ ይስቃሉ ንጂ ፡ አይቀየሙም ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ዘመድ ፡ ተሰብስቦ ፡ ጠጅ ፡ እዬተጠጣ ፡ እንደ ፡ መሰንበቻው ፡ የሀዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፈረስሜዳ ፡ የሆነው ፡ ታምር ፡ ሲወራ ፡-

" ወይፈንና ፡ ባላገር ፡ ኮ      ዛገላ ፡ ካልሜኑት ፡ ልክ ፡ አይገባም ። " አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

"እንዴት ?" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ።

" ከጎንቻ ፡ ጉልቴ ፡ የመጡትን ፡ ባላገሮች ፡ አታይም ! አንድ ፡ የበግ ፡ ግልገልንኳዋ ፡ ሳይዙ ፡ ባዶ ፡ እጃቸውን ፡ እንኳ ዋን ፡ ደስ ፡ ያለዘ ፡ ሊሉኝ ፡ መጡ ። ምክናየቱ ፡ ሽከማቸውን ፡ ስላቀለልሁላቸው ፡ ነው ። እኔ ፡ ገገር ፡ እነሱ ፡ ተገዥ ፡ መሆና ቸውን ፡ እንዲያውቁ ፡ ባደርጋቸው ፡ ሸከማቸውን ፡ ትንሽ ፡ ከበድ ፡ ባደርግባቸው ፡ እንዲህ ፡ ባልተጫወቱብኝ ፡ ነበር ። እግዚአብሄር ፡ ስላወጣህ ፡ ልናይህ ፡ መጣን ፡ አሉኝ ፡ የነሱን ፡ አመዳም ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ ለኔ ፡ ክብር ፡ እንደሚሰጠኝ ፡ ሁሉ ! ግዴለም ፡ እኔ ፡ መሸሻ ፡ መግዛት ፡ ማወቄን ፡ አሳያቸዋለሁ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በጣም ፡ ተቆጥተው ።

" እኔ ፡ ቀድሞ ፡ ስለተቆጣሁዋቸው ፡ ጥፋታቸው ፡ ተሰ ምቶዋቸው ፡ አገሩ ፡ አዋጥቶ ፡ አንድ ፡ ስንጋ ፡ ገዝቶ ፡ እንዲ ልክ ፡ ከመሀከላቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሰዶዋል ። ባላገር ፡ ማጥ ፋቱ ፡ ጌታ ፡ ምህረት ፡ መስጠቱ ፡ የተለመደ ፡ ነውና ፡ ይማሩዋ ቸው ። " አሉ ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ።

" እንዲሁ ፡ መጥተው ፡ የኔን ፡ የሞኙን ፡ እንጀራ ፡ በል ተው ፡ ይሄዳሉንጂ ፡ ለምን ፡ ገንዘባቸውን ፡ ያወጣሉ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባሽሙር ።

" የለም ፡ በጣም ፡ አዝነዋል ፡ ይማሩዋቸው ፡ " አሉ ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ።

" አይደለም ፡ እኒህ ፡ ባላገሮች ፡ በርስዎ ፡ ጉልት ፡ ስለ ፡ ሰፈሩ ፡ ገመታ ፡ ይከፍሉዎታል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስራቸውን ፡ ፈትተው ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ተጉዘው ፡ እርስዎን ፡ እንኩ

ዋን ፡ ደስ ፡ ያለዎ ፡ ለማለት ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ መጡ ፡ አሁን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እርስዎን ፡ ደስ ፡ ስላለዎ ፡ ሰንጋ ፡ የሚከፍሉ ? እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ግፍ ፡ ሲያይ ፡ መአት አያወርድም ? ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

“ እንተን ፡ የጠዬቀህ ፡ የለም ፡ ዝም ፡ በል ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

“ ድሮስ ፡ ማን ፡ ጠይቆኝ ፡ ተናግሬ ፡ አውቃለሁ ፡ እንዲሁ ፡ ጣልቃ ፡ ገብቸ ፡ እናገራለሁንጂ ! እናንተ ፡ እስክትጠይቁኝ ፡ ከቆዩሁማ ፡ ታፍኜ ፡ መሞቴ ፡ ነው ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እዬሳቀ ።

“ ወዬው ፡ ጉድ ! ምን ፡ አፍኖ ፡ ይገድልሃል ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እሳቸውም ፡ በበኩላቸው ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ፡ ብለው ።

“ ካንድ ፡ ወገን ፡ እናንተ ፡ እንደብድ ፡ እንደጉድ ፡ ቆጥራችሁኝ ፡ የማትጠይቁኝ ፡ ስትሆኑ ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ እኔ ፡ ሳልጠዬቅ ፡ አልናገርም ፡ ብዬ ፡ ዝም ፡ ስል ፡ ተዘግቶ ፡ ኖርሁ ፡ ማለት ፡ አይደለም ? ”

“ እሺ ፡ ደህና ፡ ነው ፡ አሁን ፡ አንተም ፡ ተናግረሀል ፡ እኛም ፡ ሰምተንሃል ፡ እንግዲህ ፡ ዝም ፡ በል ። ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

“ ለጠዬቅሁዎ ፡ መልስ ፡ ይስጡኝና ፡ ዝም ፡ እላለሁ ። ”

“ ለምኑ ? ”

“ እርስዎን ፡ ደስ ፡ ስላለዎ ፡ ባላገሮች ፡ ሰንጋ ፡ የሚከፍሉ ፡ በትን ፡ ምክናያት ፡ ”

“ አ አ ! እባክህ ፡ ዝም ፡ በል ፡ አንተ ፡ ይልቅ ፡ ሌላ ፡ የሚጥም ፡ ጨዋታ ፡ እንጫወትበት ! ጎንቻ ፡ ስለ ፡ ፈረስ ፡ ሜዳው ፡ ውድድር ፡ የሚዘፈነውንና ፡ የሚገጠመውን ፡ ግጥም ፡ ሰምታችሁዋል ! ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ አቋዋርጠው ።

“ የለም ፡ አልሰማንም ። ምን ፡ ተባለ ፡ እባክህ ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ከመከዳቸው ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ ተቀምጠው ። ፊታውራሪ ፡ ከማናቸውም ፡ ጨዋታ ፡ የፈረስሜዳ ፡ ጨዋታ ፡ ይጥማቸው ፡ ነበር ።

"የጎንቻ ፡ ባላገሮች ፡ ያሉትን ፡ ሁሉ ፡ በቃሌ ፡ ማስታወስ ፡ አልችልም ፤ ብቻ ፡ ዘፈኑ ፡ ግጥሙ ፡ እንዲህ ፤ አይደለም ፡ አሉ ። በመጀመሪያ ፡ የፊታውራሪ ፡ አስቤን ፡ ስም ፡ እየጠሩ ፡ የሚያዋርድ ፡ ግጥም ፤ የገጠሙት ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሶስት ፡ ሰዎች ፡ ሲታሰሩ ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ህዝቡ ፡ ስም ፡ ሳይጠራ ፡ በምሳሌ ፡ ግጥም ፡ ይገጥም ፡ ጀመር ፡ አሉ ።" አሉ ፡ ባላምባራስ ።

"በሞቴ ፡ አፈር ፡ ስሆን ፤ ምን ፡ ይባላል ፡ አሉ ፡ እባክህ ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በጎንቻ ፡ ስለሳቸው ፡ ጀግንነት ፡ የሚባለውን ፡ ለመስማት ፡ ናፍቀው ።

"እኔ ፡ ስንቱን ፡ አስታውሰዋለሁ ፡ ጌታየ ? ከባላገሮች ፡ አንዱ ፡ ቢጠራ ፡ ሊነግረን ፡ ይችላል ።"

"የጎንቻን ፡ ባላገሮች ፡ ጥራ ፡ አንተ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በጎንቻ ፡ የሚባለውን ፡ እስኪሰሙ ፡ በጣም ፡ ቸኩለው ። የጎንቻ ፡ ባላገሮች ፡ ምን ፡ ሊደርስብን ፡ ይሆን ፡ እያሉ ፡ እየተጋፉ ፡ ሲገቡ ፡—

"ጠጅ ፡ አምጣላቸው !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በደስታ ፡ ፊት ።

"እስቲ ፡ ስለ ፡ ፊረሰሚዳው ፡ . . . . . . . . . ጥዋት ፡ ከነገራችሁኝ ፡ የምታስታውሱትን ፡ ለጌቶች ፡ ንገሩዋቸው ፡" አሉ ፡ ባላምባራስ ።

ከዚያ ፡ ባላገሮች ፡ እስበሳቸው ፡ ተያዩና ፡

"ምን ፡ . . . . . . ስንቱ ፡ ይነገራል ፡ ጌታየ ! እስጽፈን ፡ ያመጣነው ፡ ብቻ ፡ ትንሹን ፡ ከፍል ፡ ሊያሳይ ፡ ይችል ፡ እንደሆን ፡ ነውንጂ !" አሉና ፡ ከባላገሮቹ ፡ አንዱ ፡ በጨርቅ ፡ አራፋ ፡ የተጠቀለለ ፡ ወረቀት ፡ ለቄስ ፡ ሞገሴ ፡ ሰጠ ።

ቄስ ፡ ሞገሴ ፡ መጀመሪያ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ወረቀቱን ፡ ከላይ ፡ እስከታች ፡ ቅንድባቸውን ፡ ላይና ፡ ታች ፡ እያሉ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳቅ ፡ እያሉ ፡ አንብበው ፡ ከጨረሱ ፡ በሁዋላ ፡ ድምጻቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ማንበቡን ፡ ጀመሩ ።

"አንበሳ ፡ አረጀና ፡ እቤት ፡ በመዋሉ ፤
አራዊት ፡ ተጨንቀው ፡ የት ፡ ደረሰ ፡ ሲሉ ፤
ነብር ፡ ተነሳና ፡ ከመሃከላቸው ፤

እኔ ፡ ነኝ ፡ አንበሳ ፡ እጅ ፡ ንሱኝ ፡ አላቸው ፡
ነብር ፡ ነብር ፡ እንጂ ፡ አንበሳ ፡ እንዳልሆነ ፡
ምንም ፡ የታወቀ ፡ ቢሆን ፡ የታመነ ፡
ደፍሮ ፡ ለመናገር ፡ ሁሉም ፡ ስለፈሩ ፡
ለነብር ፡ ማደግደግ ፡ እጅ ፡ መንሳት ፡ ጀመሩ ፡
ሌሎች ፡ እንዲፈሩት ፡ እንዲሰግዱለት ፡
አንበሳ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ በዋሸው ፡ ውሸት ፡
አመነበትና ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡
እሱም ፡ ማን ፡ መሆኑን ፡ ጀመረ ፡ መርሳት ፡
አንበሳ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ተቀምጦ ፡ እቤቱ ፡
ሌሎችም ፡ ነህ ፡ ብለው ፡ ሲሰግዱ ፡ በፊቱ ፡
አንበሳ ፡ መኖሩን ፡ ገና ፡ በህይወቱ ፡
በሩቁ ፡ ሲወራ ፡ ድንገት ፡ በመስማቱ ፡
መሬት ፡ ጠበበችው ፡ ተቆጣ ፡ በብርቱ ፡
ሁሉም ፡ አምኖ ፡ እንዲኖር ፡ ነብር ፡ ያለውን ፡
ከሱ ፡ ሌላ ፡ አንበሳ ፡ አለመኖሩን ፡
አዋጅ ፡ አዋጅ ፡ ብሎ ፡ ሰብስቦ ፡ አለሙን ፡
አንበሳን ፡ ሰደበ ፡ ከፍ ፡ አርጎ ፡ ድምጹን ፡
የተኛው ፡ አንበሳ ፡ እድሜ ፡ ተጭኖት ፡
የነብርን ፡ ስድብ ፡ ሰማና ፡ ድንገት ፡
አጉራርቶ ፡ ቢነሳ ፡ ወኔው ፡ ቀሰቀሰት ፡
ነብር ፡ ግራ ፡ ገባው ፡ መሄጃ ፡ ጠፋው ፡
መሬት ፡ አፍዋን ፡ ከፍታ ፡ ድንገት ፡ አትውጠው ፡
ሰማይ ፡ እንዳይወጣ ፡ ክንፍ ፡ አልነበረው ፡
ልቡን ፡ እፍረት ፡ ሞልቶት ፡ እየተጨነቀ ፡
ጥፋተኛነቱን ፡ ወዲያው ፡ ስላወቀ ፡
አንበሳ ፡ እንዲምረው ፡ እግሩ ፡ ስር ፡ ወደቀ ፡
አንበሳም ፡ ዘቅዝቆ ፡ አየና ፡ ነብርን ፡
እግሩን ፡ እየሳመ ፡ ምህረት ፡ ሲለምን ፡
ታላቅነት ፡ መልካም ፡ ራሱን ፡ ማመን ፡
ሞት ፡ ሊፈረድበት ፡ የሚገባውን ፡
ከግሩ ፡ ስር ፡ አንስቶ ፡ ሳመው ፡ ጠላቱን ፡
አንበሳ ፡ በሰራው ፡ አለም ፡ ተገረመ ፡

የወንጌልን ፡ ትእዛዝ ፡ አይቶ ፡ እንደፈጸመ ፡! ”

“ ይገማችሁ ፡ ጠጅ ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የጎንጅ ፡ ባላገሮች ፡ ያመጡት ፡ ግጥም ፡ ሙተያያ ፡ ባለማምጣታቸው ፡ የተቆጡትን ፡ ብርቱ ፡ ቁጣ ፡ አስረስቶዋቸው ። ከዚያ ፡ ወደ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ዘወር ፡ አሉና ፡–

“ በነብር ፡ የመሰለው ፡ እስጌን ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌን ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡ ያሠጣት ፡ አይለውም ፡ ናሮዋል ? ” ሲሉ ፡ ከቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ በቀር ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሳቁ ።

በውጭም ፡ ሆነ ፡ በቤተ ፡ ሰብ ፡ መሀከል ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ጀግንነትና ፡ የፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ፈርቶ ፡ በታቦት ፡ አማላጅነት ፡ ምህረት ፡ መለመን ፡ በተነሳ ፡ ቁጥር ፡– ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሲቸገሩና ፡ አፋቸው ፡ ሲፈራ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ በጣም ፡ የሚጠሉ ፡ መሆናቸውና ፡ ትውልዳቸው ፡ እኩል ፡ ሲሆን ፡ የራሳቸውን ፡ ክብር ፡ ረስተው ፡ ለፊታውራሪ ፡ አገልጋይ ፡ ለመሆን ፡ የቀረቡ ፡ ሰው ፡ መሆናቸው ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ የመሰንበቻቸው ፡ ሁኔታቸው ፡ የፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ወገን ፡ አስመስሎ ፡ ባስጠረጠራቸው ፡ ነበር ። መሰንበቻቸውን ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ጀግንነትና ፡ የፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ፈሪነት ፡ ሲነሳ ፡ ጥርሳቸው ፡ ሌሎቹን ፡ ለመምሰል ፡ ያክል ፡ ቢስቅም ፡ ግንባራቸው ፡ ሲቋጠር ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ምክንያት ፡ ፈጥረው ፡ ከዘመድ ፡ መሀከል ፡ ተነስተው ፡ ሲወጡ ፡ ወይም ፡ ሌሎቹ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሁሉ ፡ በማድረግና ፡ ባለማድረግ ፡ መሀከል ፡ መቁረጥ ፡ አቅቶዋቸው ፡ ሲያመነቱ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። ምክንያቱ ፡ ሌሎች ፡ የማያውቁትን ፡ ምስጢር ፡ እሳቸው ፡ ያውቁ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌን ፡ እፋለማለሁ ፡ ካሉ ፡ በሁዋላ ፡ የተፉትን ፡ መዋጥ ፡ ውርደት ፡ መስሎዋቸው ፡ ሀይለኝነታቸውን ፡ ለማሳለፍ ፡ መቁረጣቸውንና ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ በበኩላቸው ፡ ለፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ በመሆናቸው ፡ ያለመጠን ፡ ማዘናቸውን ፡ ሲያዩ ፡ የታቦትን ፡

አማላጅነት ፡ አሳብ ፡ መጀመሪያ ፡ ያሳሰቡ ፡ እሳቸው ፡ ነበሩ ።

“ ምነው ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ባገራችን ፡ ሽማግሌ ፡ የለም ? ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ያባቴ ፡ ጉዋደኛ ፡ አባቴ ፡ ናቸው ። እንዴት ፡ የበላቶችን ፡ አንገት ፡ የቆረጠ ፡ ጎራዴዎን ፡ የበላቶችን ፡ ደረት ፡ የወጋ ፡ ጦሩን ፡ ጣቡቱ ፡ አንገት ፡ ባዘቱ ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ልሰንዝር ? ምንም ፡ መጨረሻ ፡ ድሉን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለፈቀደው ፡ የሚሰጥ ፡ ቢሆን ፡ መጀመሪያ ፡ ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ጋር ፡ መሰላለፉ ፡ ብቻ ፡ ለኔ ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ ነው ! ብገድልም ፡ ብሞትም ፡ ለኔ ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ የተፈርዶ ፡ ሞት ፡ ነው። ከንዲህ ፡ ያለ ፡ የተፈርዶ ፡ ሞት ፡ የሚያድን ፡ ሽማግሌ ፡ በሙሉ፡ እንማይ ፡ ጠፋ ?” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እስጊ ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ ደብዳቤ ፡ አንብበው ፡ ከጨረሱ ፡ በሁዋላ ፡ በጣም ፡ አዝነው ።

“ በቅርብ ፡ የምናውቃቸው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሁሉ ፡ ደከመው ፡ ተሸነፉኮ ፡ ጌታዩ ! እሳቸውን ፡ የሚያሸንፍ ፡ አንድ ፡ ዘዴ ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እርስዎ ፡ . . . . ” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ አሳባቸውን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ደፍረው ፡ ለመናገር ፡ ተቸግረው ።

“ እኔ ፡ ምን ? ”

“ እርስዎ ፡ ምናልባት ፡ አይስማሙበት ፡ እንደሆን ? ”

“ ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ጋር ፡ መሰላለፉን ፡ የሚያስቀርልኝ ፡ ነገር ፡ ከተገኘ ፡ ምንም ፡ የማልስማማበት ፡ ነገር ፡ ይኖራል ፡ ብለው ፡ አያስቡ ። አንድ ፡ የመጨረሻ ፡ ነገር ፡ ልንገርዎ ። ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አሳባቸውን ፡ የማይለውጡ ፡ ከሆኑ ፡ እጅና ፡ እግሬ ፡ ታስሮ ፡ እፊታቸው ፡ ቆሜላቸው ፡ በፈለጉት ፡ መሳሪያ ፡ ደብድበው ፡ ቢገድሉኝ ፡ እመርጣለሁ ! ከሳቸው ፡ ጋር ፡ መሰላለፉ ፡ እንዲቀር ፡ የምፈልገው ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ መሆኑን ፡ እንዲረዱት ፡ ነው ። ይህንም ፡ ስል ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ በመናቅ ፡ እንዳይመስልዎ ! የለም ፡ በመናቅ ፡ አይደለም ፡ በማክበር ፡ ነው ። እሳቸው ፡ ዛሬ ፡ የጦር ፡ ሰው ፡ መሆናቸው ፡ ቀርቶ ፡ የጸሎት ፡ ሰው ፡ ሆነዋል ። አዛኞችን ፡ እድሜ ፡

ለማኛችን ፡ ናቸው ። ”

“ እንግዲያስ ፡ የሚስማሙበት ፡ ከሆነ ፡ እሳቸውን ፡ የሚያሸንፍ ፡ ታቦት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ”

“ ታቦት ፡ እንዴት ? ”

“ እማላጅ ፡ ሽማግሌ ፡ ይገባ ፡ ይቅርታ ፡ ልለምናቸው ፡ እያሉ ፡ መላልሰው ። ሲናገሩ ፡ ሰምቼ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በሽማግሌ ፡ ፈንታ ፡ የዲማ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ታቦት ፡ ይዘው ፡ ይቅር ፡ ይበሉኝ ፡ ቢሉዋቸው ፡ ጊዮርጊስን ፡ ስለሚወዱና ፡ ስለሚፈሩ ፡ ሁሉንም ፡ ይተውታል ። ”

“ ይመስልዎታል ? ”

“ መምሰል ፡ አይደለም ፡ ርግጠኛ ፡ ነኝ ። ”

“ የዲማን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የቢቸና ፡ ጊዮርጊስን ፡ ታቦት ፡ ጨምሬ ፡ ዐለመንሁ ! እሺ ፡ የሚሉ ፡ ከሆነ ! ”

“ ይህ ፡ ከሆነ ፡ ነገሩ ፡ አለቀ ፡ ማለት ፡ ነው ። ብቻ ፡ አንድ ፡ አይነተኛ ፡ ነገር ፡ አለ ። ”

“ ምን ? ”

“ ታቦቶቹ ፡ በውድድሩ ፡ ቀን ፡ እቦታው ፡ ላይ ፡ ድንገት ፡ እስኪገኙ ፡ ድረስ ፡ ብርቱ ፡ ምስጢር ፡ ሆኖ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ። ለዲማ ፡ መምህር ፡ በርስዎ ፡ ቃል ፡ የራሴንም ፡ ልመና ፡ ጨምሬ ፡ እኔ ፡ እነግራቸዋለሁ ። የቢቸናን ፡ አለቃ ፡ ጌታዬ ፡ አስጠርተው ፡ ወይም ፡ . . . ይለምኑዋቸው ፡ . . . . . ይንገሩዋቸው ። ”

“ግዴለም ፡ ሄጄም ፡ ቢሆን ፡ እለምናቸዋለሁ ።” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ያልጨረሱትን ፡ ቃል ፡ እሳቸው ፡ ሞልተው ።

ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ህዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ድረስ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ከሁለቱ ፡ አድባራት ፡ አለቆችና ፡ ከፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ጋር ፡ በምስጢር ፡ እየተገናኙ ፡ ያቀዱት ፡ ታላቅ ፡ ስራ ፡ እንደ ፡ ታሰበው ፡ በምስጢር ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ዘዴ ፡ ሲሰሩ ፡ ሰነበቱ ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እያወቁ ፡ የማያውቁት ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ ጀግንነትና ፡ የፊታውራሪ ፡ አሰጌን

ፈሪነት ፡ እያጋነኑ ፡ ሲያወሩ ፡-እውነቱን ፡ ማውጣት ፡ ፊታው
ራሪ ፡ መሸሻን ፡ በጉልደፍ ፡ ከራ ፡ ገዝግዞ ፡ አሲቀድቶ ፡ መግደል ፡
ስለመስላቸው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መስማትና ፡ አብሮ ፡ ማድነቅ ፡
የሚያውቁት ፡ እውነት ፡ በጎን ፡ ህሊናቸውን ፡ እየወጋው ፡ አል
ችል ፡ ስላሉ ፡ በጣም ፡ ይቸገሩ ፡ ነበር ። አለማወቅ ፡ ደግ ፡-ፊታው
ራሪ ፡ መሸሻ ፡ ይህ ፡ ዘዴ ፡ ከቤታቸው ፡ የወጣ ፡ የገባ ፡ ወንድማ
ቸው ፡ ቀኛዝማች ፡ አኪሉ ፡ የፈጠሩት ፡ መሆኑን ፡ ባለማወቃ
ቸው ፡ የሀዳር ፡ ጊዮርጊስን ፡ ድል ፡ ባሰቡ ፡ ቁጥር ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡
ይስቁና ፡ ኩራት ፡ እየተሰማቸው ፡ የተረፈች ፡ እድሜያቸውን ፡
ቆዩ ።

# ምእራፍ ፡ ፲፯ ፡

# የሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ትምህርት ፡

በዛብህ ፡ ዲማ ፡ በቆዩበት ፡ አንድ ፡ አመት ፡ ካሊቃ ፡ክንፉ ፡ የቅኔ ፡ መምህርነት ፡ ተመርቆ ፡ ወጣ ። የሚዘርፈው ፡ ቅኔ ፡ ንባቡ ፡ ያማረ ፡ ምስጢሩ ፡ የረቀቀ ፡ በመሆኑ ፡ የሱ ፡ ስም ፡ ሲነሳ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ "ድንቅ ፡ ቅኔ ፡ አዋቂ ፡ ነው ፡" ይሉ ፡ ነበር ። አለቃ ፡ ክንፉ ፡ ሰው ፡ እማመስገን ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ቁጥብ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ካሳቸው ፡ አፍ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ እንኩዋ ፡ መመስገን ፡ከን ጉስ ፡ እንደ ፡ መሸለም ፡ ነው ፡ ይባል ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ በዛብህ ፡ ምንም ፡ ዲማ ፡ የሄደለትን ፡ ስራ ፡ ቢፈጽም ፡ መጀመሪያ ፡ እንዳሰበው ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ሆኖ ፡ ከተመረቀ ፡ በሁዋላ ፡ ወዲያው ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ እንዳይሄድ ፡ ባለውለታው ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ልጃቸውን ፡ እንዲያስተም ርላቸው ፡ ስለጠዩቁት ፡ አቅዶት ፡ የነበረውን ፡ አሳብ ፡ ቅር ፡ እያለው ፡ መለወጥ ፡ ይሉኝታ ፡ አስገደደው ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ለብቻው ፡ ጠርተው ፡ ሰብለ ፡ ወንጌ ልን ፡ ውዳሴ ፡ ማርያምና ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ትርጉም ፡ ጽህ ፈት ፡ ቁጥር ፡ እንዲያስተምርላቸው ፡ ሲጠይቁት ፡-

"ትምርቴን ፡ ጨርሼ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ለመሻገር ፡ በመ ሰናዳት ፡ ላይ ፡ ነበርሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጌታዬ ፡ በወይዘሮ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ትምህርት ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ያሰቡበት ፡ ከሆነ ፡ እንደ ገና ፡ እዚሁ ፡ አንድ ፡ አመት ፡ ባጠፋ ፡ ግዴለኝም ። የዋሉልኝ ፡ ውለታ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ አንድ ፡ አመት ፡ ባጠፋ ፡ አይከብደኝም ፡" አለ ።

"ያሰቡበት ፡ ከሆነ ? በጣም ፡ አስብበታለሁ ፡ እንጂ ! አየህ ፡ እናቶችዋ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወን ጌል ፡ ስማቸው ፡ የሚጠራ ፡ በሊቅነታቸው ፡ ነው ። እስዋም ፡ ዘር ፡ ከልጉዋም ፡ ይስባል ፡ እንደሚሉት ፡ ከልጅነትዋ ፡ ጀምራ ፡ እንደናቶችዋ ፡ ትምርት ፡ በጣም ፡ ይቀናታል ፡ እንዲያው ፡ ባትፈ ልገውም ፡ ተሳላፊ ፡ ቀለም ፡ ይጣበቅባታል ። ስለዚህ ፡ ለናቶ

ችዋ ፡ ታላቅነትና ፡ ሀብት ፡ ወራሽ ፡ ለመሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ባያቀባት ፡ እንኳዋ ፡ ለሙያችው ፡ ወራሽ ፡ መሆንዋ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ አይመስልህም ?"

"አዎን ፡ እውነት ፡ ነው ።" አለ ፡ በዛብህ ፡ የፊታውራሪ ፡ ክንቱነት ፡ አስገርሞት ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዬ ።

" ስለዚህ ፡ በጣም ፡ የማስብበት ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ይህን ፡ አሁን ፡ ያልሁህን ፡ ትምርት ፡ ለማስተማር ፡ አንድ ፡ አመት ፡ የሚወስድ ፡ አይመስለኝም ፡ ከሰስት ፡ ቢበዛ ፡ ካራት ፡ ወር ፡ እድሜ ፡ የበለጠ ፡ አይወስድብህም ። ሰብለን ፡ ባታውቃት ፡ ነው ፡ በጣም ፡ ብልህ ፡ ናትኮ ! "

" ውዳሴ ፡ ማርያምና ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ትርጉም ፡ ለመማርኮ ፡ ሰዋስው ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ! እመይቴ ፡ ሰብለ ፡ ሰዋስው ፡ የተማሩ ፡ አይመስለኝም ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ አንድ ፡ አመት ፡ ይወስዳል ፡ ያልሁ ። ምናልባት ፡ አንድ ፡ አመት ፡ አያስፈልግ ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አራት ፡ ወር ፡ እንደማይበቃ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። "

" አንድ ፡ ነገር ፡ ልንገርህ ፡ " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በዛብህ ፡ ደስ ፡ እንዳልተሰኘ ፡ አዩና ። አንተን ፡ መጠዬቄ ፡ አስተማሪ ፡ አጥቼ ፡ እንዳይመስልህ ! ለምኖ ፡ እግር ፡ ስሞ ፡ የሚያስተምር ፡ ሞልቶዋል ! አንተን ፡ መምረጤ ፡ አንገትህን ፡ የደፋህና ፡ ልክህን ፡ የምታውቅ ፡ መሆንህን ፡ አይቼ ፡ ነው ። አሁን ፡ ያ ፡ አጎትዋ ፡ ካሳ ፡ ዳምጠ ፡ ያ --- ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አስተምራት ፡ ብንለው ፡ ደስታውን ፡ አይችለውም ። ብቻ ፡ ባለጌ ፡ ነው ፡ ደፋር ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ እንዲያውም ፡ ከሱ ፡ እንድትርቅልኝ ፡ ነው ፡ የምፈልግ ። አንተን ፡ መምረጤ ፡ ለዚህ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እኔ ፡ ስመርጥህ ፡ ደስ ፡ ሊልህ ፡ ይገባል ። "

" እኔኮ ፡ ውዳሴ ፡ ማርያምና ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ትርጉም ፡ ከጽህፈት ፡ ጋር ፡ በሰስትና ፡ ባራት ፡ ወር ፡ የሚያልቅ ፡ ትምርት ፡ አለመሆኑን ፡ እንዲያውቁት ፡ ነውንጂ ፡ ለማስተማሩማ ፡ካንድ ፡ አመት ፡ በላይ ፡ የሚወስድብኝ ፡ ቢሆንም ፡ በጭራሽ ፡ አይከብደኝም ፡ አልሁኮ ! ብቻ ----- "

" ብቻ ፡ ምን ? "

" ብቻ ፡ እኔ ፡ እመይቴ ፡ ሰብለን ፡ መቆጣት ፡ ስለማል ይፍሩ ፡ ጠንከረው ፡ እንዲማሩና ፡ እኔም ፡ ቶሎ ፡ ስራዬን ፡ ጨርሼ ፡ ወዳሰብሁት ፡ አገር ፡ እንድሄድ ፡ ጌታዬ ፡ አጠንክ ረው ፡ ቢነግሩዋቸው ፡ መልካም ፡ ነው ። "

" ለሱ ፡ ግዴለህም ፡ እኔም ፡ እናትዋም ፡ እንነግራታለን ፡ እናትዋ ፡ እንዲያውም ፡ አትለያትም ፡ ተነጋግረንበታል ። "

እውነትም ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ እንኩዋን ፡ ፈልጋው ፡ ያልፈለገችው ፡ ቀለም ፡ ሲያልፍ ፡ የሚጣበቅባት ፡ ነበረች ። ከገዱ ፡ ካሳ ፡ ጋር ፡ የነበራት ፡ ጉዋደኝነት ፡ ረድትዋት ፡ በሰ ዋሰው ፡ ትምርትዋ ፡ ደንበኑን ፡ ብቻ ፡ ለመማር ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደባት ፡ እንጂ ፡ የቃላቱን ፡ ትርጉም ፡ ለማወቅ ፡ ምንም ፡ አላስቸገራትም ። ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ውዳሴ ፡ ማር ያም ፡ ትርጉም ፡ አለፈች ። ጽህፈትም ፡ መጀመሪያ ፡ አስቸግ ሮዋት ፡ ነበር ፡ በሁዋላ ፡ ግን ፡ እርሳሱን ፡ እንደያዘች ፡ በዛብህ ፡ እጅዋን ፡ ይጨብጥና ፡ በሱዋ ፡ እጅ ፡ እንደሚጽፍ ፡ ሁሉ ፡ ሲመራት ፡ ቆይቶ ፡ ሲለቃት ፡ ትንሽ ፡ ደህና ፡ ስትጽፍ ፡ ቆይታ ፡ ሲበላሽባት ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ይዞ ፡ ሲመራት ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ በጣም ፡ ባያምርም ፡ እንደሚነበብ ፡ አድርጋ ፡ ትጽፍ ፡ ጀመር ። ብቻ ፡ ይሀ ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ የማስጻፍ ፡ ነገር ፡ እናትዋን ፡ ደስ ፡ አላሰኛቸውም ።

" እጅ ፡ መያዙ ፡ ቀርቶ ፡ ሌላ ፡ ማስተማሪያ ፡ ዘዴ ፡ የለም ? ይህ ፡ ተዩዩዛችሁ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እንገታችሁን ፡ ማቀርቀሩ ፡ መልካም ፡ አይደለም ----- ይደክማችሁዋል ። " አሉ ፡ ወይ ዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ አዲሱን ፡ የማስተማሪያ ፡ ዘዴ ፡ መጀመሪያ ፡ ያዩ ፡ እለት ፡ ቁጣቸው ፡ በፊታቸው ፡ ጎልቶ ፡ ይታዩ ።

" የለም ፡ አይደክመንም ፡ " አለች ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ በፍጹም ፡ ገርነት ። አሳብዋ ፡ በሙሉ ፡ ተጠቅሎ ፡ እስራዋ ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ ስለነበረ ፡ የናትዋ ፡ አሳብ ፡ የሄደበትንና ፡ እፊ ታቸው ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ የነበረውን ፡ ቁጣ ፡ ሹሬት ፡ አልተ መለከተችም ። በዛብህም ፡ የተናገሩትን ፡ ሰማ ፡ እንጂ ፡ ሁኔታቸ

ውን ፡ አላዩም ። ግልጥ ፡ አድርገው ፡ እንዳይናገሩ ፡ ፈርተው ፡ ዝም ፡ እንዳይሉ ፡ አላስችላቸው ፡ ብሎ ፡ ሲንቆራጠጡ ፡ እያዩኝ፡ ሳቅ ፡ ነፍቶዋት ፡ የምትሐኑት ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ብቻ ፡ ነበረች ። የቀኑ ፡ ትምርት ፡ አልቆ ፡ በዛብህ ፡ ወደሚኖርበት ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ወደልፍኛቸው ፡ ከሄዱ ፡ በሁዋላ ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ የመቤትዋን ፡ አሳብ ፡ ትርጉምና ፡ ፊታቸው ፡ እንዴት ፡ ተለውጦ ፡ እንደነበረ ፡ ለሰብለ ፡ ወንጌል ፡ እዩሳቀች ፡ ስትነግራት ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ በጣም ፡ ደነገጠች ።

እስከ ፡ ጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ድረስ ፡ በዛብህ ፡ የሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ እጅ ፡ ሲይዝ ፡ የሳቸውን ፡ እጅ ፡ እንደያዘ ፡ ሁሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ልባቸው ፡ ይሸበርና ፡ እፍረት ፡ ይሰማቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ነውር ፡ እንኩዋ ፡ ቢሆን ፡ ሲደጋገም ፡ መለመዱና ፡ ነውር ፡ መስሎ ፡ መታየቱ ፡ ስለሚቀር ፡ ይህም ፡ እንዲሁ ፡ ተለመደና ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነትን ፡ ማስቆጣቱም ፡ ማሳፈሩም ፡ ቀረ ።

በዛብህ ፡ ከተማሪ ፡ ቤቱ ፡ እዩተመላለሰ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ እፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ ምሳውንም ፡ ራቱንም ፡ እዩበላ ፡ ይሄድ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ጀምሮ ፡ በቤቱ ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ስለሱ ፡ የነበረው ፡ ስሜት ፡ ካልጠየቁት ፡ የማይናገር ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ዝምተኛ ፡ ቀልድና ፡ ጨዋታ ፡ የማይወድ ፡ እጅግ ፡ ቁም ፡ ነገራም ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነበር ። እውነትም ፡ በጣም ፡ ቁም ፡ ነገራምና ፡ ባልለመደው ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ሲሆን ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ሌሎች ፡ የሚናገሩትን ፡ ከመስማት ፡ በቀር ፡ ካልጠየቁት ፡ መናገር ፡ የማይወድ ፡ ነበር ። በጣም ፡ ከተቀራረባቸውና ፡ ከለመዳቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ግን ፡ ጨዋታ ፡ አጥብቆ ፡ የሚወድና ፡ የሚያሳምር ፡ ነበር ።

በዛብህ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ ማስተማር ፡ ከጀመረና ፡ ከተለማመዱ በሁዋላ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ ልጃቸውና ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ ድሮ ፡ ከሚያውቁት ፡ በጭራሽ ፡ የተለዩ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ማስተማሩን ፡ ሲጨርስ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ ሲሰለቻት ፡ በአንዳንድ ፡ ምክንያት ፡ ትምርቱ ፡ ይቋረጥና ፡ እነሱ ፡ ሳሉ ፡ ወይም ፡ በዩተማሪ ፡ ቤቱ ፡

ሲዞር ፡ ያዬውን ፡ የሰማውን ፡ የገጠመውን ፡ ያወራላቸዋል ፡፡ ወሬው ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንደሚያወራው ፡ ሁሉ ፡ አንዳንዱ ፡ የሚያስቅ ፡ አንዳንዱ ፡ የሚያሳዝን ፡ አንዳንዱም ፡ የማያስቅ ፡ ወይም ፡ የማያሳዝን ፡ እንዲሁ ፡ ተራ ፡ ወሬ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡፡ አቀራረቡ ፡ ግን ፡ የሱ ፡ የግሉ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ አይተውት ፡ ወይም ፡ ሰምተውት ፡ የማያውቁ ፡ አዲስ ፡ ስስ ፡ ነበረ ፡ ደስ ፡ ይላቸው ፡ ነበር ፡ ይወዱት ፡ ነበር ፡፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ጨዋታ ፡ ሲያምራቸው ፡ የያዙት ፡ ፈትልም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ስፌት ፡ ይተዉና ፡ “ በዛብህ ፡ ሰብስን ፡ ይደከማታል ፡ እስቲ ፡ ትንሽ ፡ እረፉና ፡ ጨዋታ ፡ አምጣ ፡” ይላሉ ፡፡ ከዚያ ፡ በዛብህ ፡ ተነስቶ ፡ ጨዋታ ፡ ለመፈለግ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እያሰበ ፡ ሲንጎራደድ ፡ ይቆይና ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በእሳቡ ፡ የመጣለትን ፡ ይነግራቸዋል ፡፡

“ያደረግሁትን ፡ ወይም ፡ ሲደረግ ፡ ያዬሁትን ፡ ወሬ ፡ አውርቼ ፡ ጨረስሁ ፤ የተረፈ ፡ ቢኖር ፡ ፈልጌ ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ አወራችሁዋለሁ ፡ አሁን ፡ ዙራምባ ፡ ሳለሁ ፡ አንድ ፡ ጉዋደኛዬ ፡ የነገረኝን ፡ . . . ልንገራችሁ ፡ ” አለ ፡ በዛብህ አንድ ፡ ቀን ፡ አፉ ፡ እዬፈራ ፡፡ ሊነግራቸው ፡ ያሰበው ፡ ወሬ ፡ ለነሱ ፡ ሊነገር ፡ የሚገባ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ስለተጠራጠረ ፡ የማመንታት ፡ ምልክት ፡ በፊቱ ፡ ይታይበት ፡ ነበር ፡፡

“ግዴለም ፡ ንገረን ፡፡” አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደማፈር ፡ ሲል ፡ አይተው ፡ እንዲደፋፈር ፡ የደስታ ፡ ፊት ፡ እያሳዩ ፡፡

“ አንድ ፡ ተማሪ ፡ ቁራሽ ፡ ልመና ፡ በሄደበት ፡ ወዳንድ ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ደረሰና ፡ “በእንተ ፡ ስማ ፡ ለማርያም ፡ ስለ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሄር ፡” ሲል ፡ አንዲት ፡ ስእሲ ፡ በጣም ፡ ተጠንቅቆ ፡ የሰራት ፡ እንጂ ፡ እንዲሁ ፡ በልማድ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ከሩካቤ ፡ ስጋ ፡ የተገኘች ፡ የማትመስል ፡ እጅግ ፡ የተዋበች ፡ ቀይ ፡ ወይዘሮ ፡ እንደ ፡ ሀር ፡ የሰዘበ ፡ ሳዛ ፡ ጠጉርዋ ፡ በራስዋ ፡ ላይ ፡ ተረፍርፎ ፡ ያይን ፡ ሽፋሎችዋና ፡ ቅንድቦችዋ ፡ በቀጭኑ ፡ ኩል ፡ አልፎባቸው ፡ የቀሚስዋ ፡ ሰፊ ፡ አንገትዮ ፡ በንቅ

ሳት ፡ ያጌጠ ፡ እንገትዋንና ፡ የጸሀይ ፡ ወገገን ፡ የመሰለ ፡ ብሩህ ፡ ደረትዋን ፡ ገልጾ ፡ እያሳዬ ፡ ከታች ፡ በግር ፡ አልቦ ፡ ያጌጡ ፡ ባቶችዋ ፡ ከላይ ፡ ውብ ፡ ዳሌና ፡ ወገብዋ ፡ እንዲታዩ ፡ ሽንቀጥ ፡ አድርጋ ፡ ታጥቃ ፡ ግማሽ ፡ እንጀራ ፡ በዝርግ ፡ ሰፌድ ፡ በግራ ፡ እጅዋ ፡ ዘለግ ፡ አድርጋ ፡ ይዛ ፡ በቁንጠኛ ፡ የወይዘሮ ፡ አካሄድ ፡ ወዲያ ፡ ዘንከት ፡ ወዲህ ፡ ዠርገድ ፡ ወዲህ ፡ ዠርገድ ፡ ወዲያ ፡ ዘንከት ፡ እያለች ፡ መጣችና ፡ "እንካ ፡" አለችው ፡ ሰፌዱን ፡ እስካፉ ፡ ድረስ ፡ አቅርባ ። ወይዘሮዋ ፡ ከደስ ፡ ደስ ፡ ድርና ፡ ማግ ፡ እንደ ፡ ተሰራች ፡ ከግር ፡ ጥፍርዋ ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ጠጉርዋ ፡ በስዋ ፡ ላይ ፡ የማይታዬው ፡ ሁሉ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ ነበር ።

ተማሪው ፡ በህልም ፡ ወይስ ፡ በውን ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ አቅቶት ፡ እስዋን ፡ ፍሊጋ ፡ ወይስ ፡ ቁራሽ ፡ ሊለምን ፡ የመጣ ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ተስኖት ፡ አይኑን ፡ እስዋ ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ እዬተቅበዘበዘ ፡ በዳበሳ ፡ ቁራሹን ፡ ከሰፌዱ ፡ አንስቶ ፡ በኮፊዳው ፡ አገባሁ ፡ ብሎ ፡ እመሬት ፡ ጣለው ።

"ወይ ቀልህ !" አለች ፡ ወይዘሮዋ ፡ እዬሳቀች ፡ እስዋም ፡ አይንዋን ፡ ከተማሪው ፡ ላይ ፡ ሳታነሳ ።

ተማሪው ፡ አሁንም ፡ አይኑን ፡ እስዋ ፡ ላይ ፡ እንደ ተከለ ፡ ቁራሹን ፡ አነሳሁ ፡ ብሎ ፡ የወይዘሮዋን ፡ እጅ ፡ ሲይዝ ፡ ኮፊዳው ፡ ወደቀ ።

"ኮፊዳሀ ፡ ደግሞ ፡ ወደቀልህ ! " አለች ፡ ወይዘሮዋ ፡ አሁንም ፡ እዬሳቀች ።

ከዚያ ፡ ተማሪው ፡ ኮፊዳውን ፡ አነሳሁ ፡ ብሎ ፡ ወይዘሮዋን ፡ አንስቶ ፡ ተሸከመና ፡ እዬሮጠ ፡ እቤት ፡ ቢገባ ፡ ባልዮው ፡ እሳት ፡ ዳር ፡ መደቡ ፡ ላይ ፡ መከዳውን ፡ ተደግፎ ፡ ተጋድሞ ፡ ጠጅ ፡ እዬጠጣ ፡ እሳት ፡ ሲሞቅ ፡ አገኘው ። "ወዲያ ፡ ይነሱ ፡ እሜቴን ፡ ላስቀምጥበት ።" አለ ፡ ተማሪው ፡ ባልዮውን ፡ ሲያይ ፡ ደንግጦ ፡ የሚናገረውን ፡ አጣና ።

"እዚሀ ፡ አስቀምጣት ፡ ግዴለም ፡ መደቡ ፡ ለሶስት ፡ አይብቃም ፡ እንጂ ፡ ለሁለታችን ፡ ይበቃናል ! " አለ ፡ ባልዮው ፡ እዬሳቀ ።

ተማሪው ፡ እንደታዘዘው ፡ ወይዘሮዋን ፡ እባልዋ ፡ አጠገብ ፡ እመደብ ፡ ላይ ፡ አስቀምጦ ፡ የሰራው ፡ ስራ ፡ እሱን ፡ ራሱን ፡ አስገረመውና ፡ "ይበሉ ፡ እንግዲህ ፡ የሚቀጡኝን ፡ ይቅጡኝና ፡ ሳይመሽብኝ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤቴ ፡ ልሂድ ፡ " አለ ።

"ሂድ ፡ ግዴለም ፡ ተሸክሞ ፡ የሄደ ፡ ነውንጂ ፡ ተሸክሞ ፡ ያመጣ ፡ አይቀጣም ፡" አለ ፡ ባልየው ፡ አሁንም ፡ እየሳቀ ። ተማሪው ፡ "እግዜር ፡ ያስጥልኝ ፡ " ብሎ ፡ አመስግኖ ፡ ቢወጣ ፡ እሱ ፡ የሰጡ ፡ ወይዘሮ ፡ ሲሸከሙ ፡ ሙሾች ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ሲለምነው ፡ ያመሸውን ፡ ቁራሽ ፡ በልተውበት ፡ አገኘ ።"

በዛብህ ፡ ሲያወራ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልና ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ በጣም ፡ ይስቁ ፡ ነበር ።

" እግዚአብሄር ፡ አይንዋን ፡ ያፍሰውና ፡ ሲሸከማት ፡ ዝም ፡ ብላ ፡----- ተሸከመኝ ፡ አለችው ፡ እባክህ ? " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ሲስቁ ፡ የወረደውን ፡ እንባ ፡ ከያናቸው ፡ እየጠረጉ ።

" ምን ፡ ታድርግ ፡ ወይዘሮ ፡ አይደለች ? " አለ ፡ በዛብህ ።

" እንዴት ! ወይዘሮ ፡ ሁሉ ፡ ሲሸከሙት ፡ ዝም ፡ ብሎ—— እንደሰልቻ ፡ ይጫናል ፡ እንዴ ? " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ እንደመሳቅ ፡ ብለው ።

" የለም ! እንደሱ ፡ ማለቴ ፡ አይደለም ። ግማሽ ፡ እንጀራ ፡ በሰፌድ ፡ ተሸክማ ፡ ከቤት ፡ እስከ ፡ በራፍ ፡ የተጉዋዘች ፡ ወይዘሮ ፡ ተሸካሚ ፡ ካላገኘች ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ መንገድ ፡ መመለስ ፡ ይደክማታል ፡ ማለቴ ፡ ነው ። " አለ ፡ በዛብህ ፡ እሱም ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ፡ ብሎ ፡ አፍሮም ፡ አይኖቹ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ማረፍ ፡ እንደፈሩ ፡ ሁሉ ፡ ከወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ወደሰብለ ፡ ከሰብለ ፡ ወደ ሀብትሽ ፡ ከዚያ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ሰብለና ፡ ወደናትዋ ፡ እዮሩጡ ።

"እዩት ፡ ሲያሽሙዋጥጠን !" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ እየሳቁ ።

" የለም ፡ ማሽሙዋጠጤ ፡ አይደለም ፡ እውነቴ ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አሁን ፡ የነገርሁዋችሁ ፡ ሁሉ ፡ ጉዋደኛዬ ፡ የነ ገረኝ ፡ ነውንጂ ፡ እኔ ፡ ምንም ፡ አልጨመርሁበትም ። ”

“ በቃሉ ፡ ባትጨምርበት ፡ የሴትዮዋን ፡ የባልዋን ፡ የተማሪውን ፡ ሁኔታ ፡ ለማሳየት ፡ ባይንህ ፡ ባፍህ ፡ ባንገት ህና ፡ በጅህ ፡ የምታደርገው ፡ ሁሉ ፡ ያንተ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረ ጠርም ፡ እኔ ፡ ከወሬው ፡ ይልቅ ፡ አንተ ፡ ስታወራ ፡ ማየቱ ፡ ነው፡ የሚያስቀኝ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ! አይደለም ? አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ወደልጃቸው ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ለጊዜው ፡ የተሰማቸው ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ገፍቶዋቸው ፡ የተናገሩት ፡ ሊያጋልጣቸው ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ስላላቸው ፡ ልባቸው ፡ ትንሽ ፡ እን ደመሸበር ፡ አለና ።

“ አዎን ፡ ” አለች ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አንገትዋን ፡ ደፍታ ። በዛብህም ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ አለና ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ።

ፊታውራሪ ፡ ብቻ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ወደምትማርበት ፡ ወደልፍኝዋ ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ ስለማያውቁ ፡ በዛብህን ፡ ሁልጊ ዜም ፡ ቢሆን ፡ በዚያው ፡ ድሮ ፡ በሚያውቁት ፡ መልኩ ፡ ካል ጠዬቁት ፡ የማይናገር ፡ አንገቱን ፡ የደፋ ፡ ቦታውን ፡ የሚያ ውቅ ፡ አድርገው ፡ ነበር ፡ የሚመለከቱት ። አንዳንድ ፡ጊዜ ፡ ምሳውን ፡ ወይም ፡ ራቱን ፡ ሲበላ ፡ ወይም ፡ እንዲሁ ፡ አስጠ ርተው ፡ የሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ትምርት ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ይጠይቁትና ፡ ቀለም ፡ ተቀባይ ፡ መሆንዋን ፡ በጣም ፡ እያደነቀ ፡ መጀመሪያ ፡ ከገመተው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የምትጨርስ ፡ መሆ ንዋን ፡ ሲነግራቸው ፡ ደስታቸው ፡ ከመጠን ፡ ያልፍና ፡ የስ ዋን ፡ ብልህነት ፡ ለሳቸው ፡ መፈክሪያ ፡ አድርገውት ፡ አጋ ጣሚ ፡ ካገኙ ፡ የመጣው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቢሰማ ፡ ይወዱ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ የሳቸውና ፡ የምሽታቸው ፡ ዘመዶች ፡ አን ዳንድ ፡ ወዳጆችም ፡ ሊጠይቁዋቸው ፡ መጥተው ፡ መጠጥ ፡ እዬተጠጣ ፡ ሲጫወቱ ፡ ምሽታቸው ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ስት ማር ፡ ሲጠብቁ ፡ ከቆዩበት ፡ መጡ ።

“ ትምርት ፡ አልቆ ፡ ነው ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡

" እዎን ። " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ለንግዶች ፡ ሰላምታ ፡ እየሰጡ ።

" አስተማሪው ፡ ሄደ ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

" ሊሄድ ፡ ነው ፡ ተነስቶዋል ። "

"ብቻውን ፡ ከሰዋ ፡ ጋር ------ ወዬው ፡ ጉድ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፊታቸው ፡ ከመቅጽበት ፡ ተለዋውጦ ።

"ሀብትሽ ፡ አለች ፡ እሱም ፡ ተነስቶዋል !" አሉ ፡ ምሽታቸው ።

" ሂድ ፡ ጥራው ፡ አንተ ። " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የቆመውን ፡ አሽከር ።

"መጠጥ ፡ ጠጥተህ ፡ እንድትሄድ ፡ ብዬ ፡ ነው ።" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በዛብህ ፡ ተጠርቶ ፡ ሲገባ ፡ የውሸት ፡ ፈገግታ ፡ በፊታቸው ፡ እየታዩ ።

በዛብህ ፡ የመጣለትን ፡ ጠጅ ፡ ይዞ ፡ ከመቀመጡ ፡-

"የሰብለ ፡ ትምርት ፡ እንዴት ፡ ነው ? እባክህ ? አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በዛብህ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተገረመ ፡ ለሳቸው ፡ የሚነግራቸውን ፡ እዚያ ፡ በተሰበሰቡት ፡ ፊት ፡ እንዲደግምና ፡ ሰሚዎች ፡ በፊንታቸው ፡ እንዲገረሙ ።

"ቀለም ፡ ስትቀበል ፡ መሰል ፡ የላትም ፡ አሁንማ ፡ ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ ጨርሳ ---- " ብሎ ፡ ሊናገር ፡ ያሰበውን ፡ ጨርሶ ፡ ሳይናገር ፡ ፊታውራሪ ፡ በጥፊ ፡ እንደተመቱ ፡ ፊታቸውን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በዛብህ ፡ ከነበረበት ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ዘወር ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሲመልሱት ፡ ቀንዶቻቸው ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ ታዩ ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ ብሎ ፡ ቆይቶ ፡ ነገሩን ፡ ሊቀጥል ፡ ሲል ፡-

"ማዶለም ፡ ተወው ፡ አሁን ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ጠጣና ፡ ሂድ ፡" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፊታቸው ፡ በቁጣ ፡ እንደጋለ ። በዛብህ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተቀምጦ ፡ ጠጁን ፡ አጋመሰና ፡ የተረፈውን ፡ ግማሽ ፡ ጠጅ ፡ እንደያዘ ፡ ብርሌውን ፡ ላሳላፊው ፡ ሰጥቶ ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ ሲወጣ ፡-

" እንዲያው ፡ ማመስገንም ፡ ማማትም ፡ ጊዜን ፡ ነው ፡

እንጂ ፡ ሰውን ፡ ማመስገንም ፡ ማማትም ፡ ከንቱ ፡ ነው ። ሰውን ፡ ባስቀመጡበት ፡ ቦታ ፡ እንዲገኝ ፡ የሚያደርገው ፡ ታማኝ ፡ የሚያሰኘው ፡ ጊዜ ፡ ነው ። እየ ፡ ጊታዬ ፡ ምንው ፡ ያን ፡ መልካም ፡ ጊዜ ፡ ስታሳልፍ ፡ አብረህ ፡ ባሳለፍኸኝ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በዛብህን ከወጣ ፡ በሁዋላ ፡ ገዝም ፡ ብለው ፡ ቆይተው ። የተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ ፊታውራሪ ፡ እንዲያ ፡ የተቆጡበትና ፡ ያዘኑበት ፡ ምክናያት ፡ ስላልገባቸው ፡ እስበሳቸው ፡ በጥያቄ ፡ እይን ፡ ከመተያየት ፡ በቀር ፡ ደፍሮ ፡ የሚናገር ፡ ጠፋ ።

"ከመቼ ፡ ወዲህ ፡ ነው ? ምን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ? ይህ ፡ የገበሬ ፡ ልጅ ፡ ይህ ፡ እከካም ፡ የኔን ፡ ልጅ ፡ የብዙ ፡ መሳፍንትና ፡ ነገስታት ፡ ልጅ ፡ አንቺ ፡ ለማለት ፡ የደፈረ ? እከዙን ፡ በኛ ፡ እንጀራ ፡ ስላረገፈ ፡ ርቃኑን ፡ በኛ ፡ ልብስ ፡ ስለከደነ ፡ ነው ? ግዴለም ፡ እሱ ፡ አይደለም ፡ ጊዜ ፡ ነው !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በተናገሩ ፡ መጠን ፡ ቁጣቸው ፡ እየጠነከረ ።

"እየ - - - - እኔ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ይህስ - - - - ይህን ፡ ያክል ፡ የሚያስቆጣ ፡ አይደለም !" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ።

"የለምኮ ፡ ነገሩ - - - - - - - " ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩአይነት ።

"እእ ? የባላገር ፡ ልጅ ፡ - - - -የገበሬ ፡ ልጅ ፡ ሲሰድበን ፡ ሲያዋርደን ፡ የሚያስቆጣ ፡ ነገር ፡ አይደለም ? ማነው፡ እሱ ፡ እረ፡ ማነውና ፡ ነው ፡ የኔን ፡ ልጅ ፡ አፉን ፡ ሞልቶ ፡ እፊቴ ፡ አንቺ ፡ የሚል ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ምሽታቸውን ፡ አቋርጠው ።

"አስተማሪዋ ፡ ነው ፡ አስተማሪ ፡ ተማሪውን ፡ መቅጣት ፡ መቆጣት ፡ አለበት ፤ ታዲያ ፡ እሰዎ ፡ ብሎ ፡ መቅጣትና ፡ መቆጣት ፡ ይሆናል ?" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ እየሳቁ ።

"እባክህ ፡ ይህ ፡ የሚበቃ ፡ ምክናያት ፡ አይደለም ! እንግዲህ ፡ እኔንም ፡ የሚያስተምረኝ ፡ ቢሆን ፡ አንቱ ፡ ሊለኝ ፡ ነዋ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

"የለም ፡ የስዎ ፡ ልዩ ፡ ነው ። እስዎ ፡ ሽማግሌ ፡ ነዎ ፡ ሰብለ ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ ናት ።"

"ምንም ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ዋናው ፡ ነገሩ ፡ እድሜ ፡ አይደለም ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ አጥንትና ፡ ደም ፡

ነው ! የተከበረ ፡ አጥንትና ፡ ደም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሲወለድ ፡ ጀምሮ ፡ እረ ፡ ከዚያም ፡ በፊት ፡ ከጽንሱ ፡ ጀምሮ ፡ የተከበረ ፡ ነው ። የተከበረ ፡ ደም ፡ በደምስሩ ፡ የሚፈስ ፡ ሀጻን ፡ ከተራ ፡ ሽማግሌ ፡ መብለጡ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። አሁን ፡ አንተ ፡ ከነሽበትህ ፡ ሄደህ ፡ የንጉስ ፡ ልጅ ፡ በድሜ ፡ ሀጻን ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሆነች ፡ ብለህ ፡ አንተ ፡ አንቺ ፡ ልትል ፡ አትችልም ።”

“ይህን ፡ አላውቅም ፡ አልሞከርሁትም ።” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ እየሳቁ ።

“ጌቶች ፡ እውነታቸው ፡ ነው ፡ ክብር ፡ በድሜ ፡ አይደለም ። እግዚአብሔር ፡ ከሌላው ፡ ለይቶ ፡ ከሌላው ፡ አክብሮ ፡ የፈጠረው ፡ ገና ፡ በጽንሱ ፡ ይከበራል ። ጌታችን ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጽንስ ፡ ሳለ ፡ የመጥምቁ ፡ ዮሀንስ ፡ እናት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ እስዋም ፡ ዮሀንስን ፡ እንደ ፡ ጸነሰች ፡ እመቤታችንን ፡ ልትጎበኝ ፡ በሄደችበት ፡ ዮሀንስ ፡ በናቱ ፡ ሆድ ፡ እንዳለ ፡ ለጌታችን ፡ እጅ ፡ ነስቶዋል ። ይህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያከበረው ፡ ገና ፡ በጽንስ ፡ ሳለም ፡ ቢሆን ፡ ሊከበር ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ።” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ።

“እሱ ፡ እውነት ፡ ይሆናል ፡ ብቻ ፡ አሁን ፡ የምንነጋገረው ፡ ክርስቶስ ፡ ስለሰራው ፡ ታምራት ፡ አይደለም ፡ ባስተማሪና ፡ በተማሪ ፡ መሀከል ፡ ስላለ ፡ ግንኙነት ፡ ነው ። ስብለ ፡ ክርስቶስ፡ በዛብህ ፡ ዮሀንስ ፡ አይደሉም ።” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ትንሽ ፡ እንደመከረሩ ፡ ብለው ።

“ጌቶች ፡ እግዚአብሔር ፡ ያከበረው ፡ ገና ፡ በጽንስ ፡ ሳለ ፡ እንኳዋ ፡ ይከበራል ፡ ያሉትን ፡ በምሳሌ ፡ ለማስረዳትኮ ፡ ነው !” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ባላምባራስ ፡ ቆጣ ፡ ሲሉ ፡ አይተው ፡ እንደ ፡ መፍራት ፡ አሉና ።

“እኔን ፡ አልሰማሽ ፡ አላችሁኝ ፡ እንጂኮ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ክርክር ፡ የሚያደርስ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ! እስቲ ፡ አባካችሁ ፡ አሁንም ፡ ስሙኝ ። ”አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ።

“ዝም ፡ በይ ፡ እባክሽ ፡ አንቺ ፡ ደግሞ ፡---በይ ፡ እስቲ ፡ ምንድነው ፡ የምትናገሪ ? ”አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ምሽታቸውን ፡ ለመቆጣት ፡ ካሰቡ ፡ በሁዋላ ፡ እንደገና ፡ አሳባቸውን ፡ ለው

ጠው ።

"ልጁን ፡ በከንቱ ፡ አትውቀሱት ፡ እሱ ፡ እስከብዙ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እሰዎ ፡ ካላልሁ ፡ ብሎ ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ ነበር ። እኛ ፡ ነን ፣ እኔና ፡ ሰብለ ፡ ነን ፡ እንቺ ፡ በል ፡ ብለን ፡ ያስገደድነው ። እሰዎ ፡ እያሉ ፡ ማስተማር ፡ የማይጥም ፡ ስለሆነ ፡ እኛ ፡ ነን ፡ ያስገደድነው ።"አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ።

"እንዲያ ፡ በይኛ ! እንዲያ ፡ በይኝ ። እንግዲያስ ፡ እውነትሽ ፡ ነው ፣ በሱ ፡ አይፈረድም ። ምንተ ፡ ማርያም ፡ እባክህ ፡ ስደበን ፡ ብላችሁ ፣ ለምናችሁ ፡ ከሆነ ፡ ተሰድባችሁ ፣ ተዋርዳችሁ ፡ ሰው ፡ ጥምር ፡ የምታስድቡ ፡ በሱ ፡ አይፈረድም ።" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፊታቸው ፡ ከቀድሞው ፡ የበለጠ ፡ በቁጣ ፡ ገሎ ።

"ወዲያምኮ ፡ እንቺታና ፡ እንተታ ፡ የመላመድ ፡ የመቀራረብ ፡ እንጂ ፡ የመናቅና ፡ የማዋረድ ፡ ምልክት ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ እግዚአብሄርን ፣ ማርያምንና ፡ ታቦቶችን ፡ አንተና ፡ አንቺ ፡ የምንላቸው ፡ ብንወዳቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንቀናቸው ፣ ልናዋርዳቸው ፡ ወይም ፡ ልንስድባቸው ፡ አይደለም ! ነው ፡ እንዴ ?" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ እንደመሳቅ ፡ ብለው ፡ አባ ፡ ሞገሴን ፡ በጎን ፡ እየተመለከቱ ።

"በዮት ፣ በየት ፡ አድርገው ፣ በዙሪያ ፣ መንገድ ፡ መጡብኛ ! አሀሀሀ —— !"አሉ ፡ ቄስ ፡ ሞገሴ ፡ አፋቸውን ፡ በሰፊው ፡ ከፍተው ፣ እዮሳቁ ። ፊታውራሪ ፡ አባ ፡ ሞገሴን ፡ በቁጣ ፡ አይን ፡ አዩና ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደተቀመጡ ፡ ጥለዋቸው ፡ ወደ ፡ ወንድ ፡ እልፍኝ ፡ ሄዱ ።

# ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡

## ትዝታ ፡

በዛብህ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ስቀው ፡ በደስታ ፡ ተቀብለውት ፡ በቅጽበት ፡ የተቀጠቡበትን ፡ ምክንያት ፡ ፈልጎ ፡ ለማግኘት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልወሰደበትም ። ተጠርቶ ፡ ገብቶ ፡ ውጣ ፡ እስኪባል ፡ ድረስ ፡ ፊታውራሪ ፡ የጠየቁትንና ፡ እሱ ፡ የመለሰውን ፡ እንደገና ፡ ተቀምጦ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ሲመረምር ፡ ሰብለን ፡ አንቺ ፡ እያለ ፡ ከመናገሩ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሊያስቆጣቸው ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ ስላጣ ፡ በዚሁ ፡ አንቺ ፡ በማለቱ ፡ የተቆጡ ፡ መሆናቸውን ፡ አረጋገጠና ፡ መጀመሪያ ፡ የፊታውራሪ ፡ ከንቱነት ፡ አስገርሞት ፡ ብቻውን ፡ ሳቀ ። በሁዋላ ፡ "ጠጣና ፡ ሂድ ፡ "ያሉት ፡ ትዝ ፡ አለውና ፡

"በጭራሽ ፡ ማሰናበታቸው ፡ ይሆን ? ወይስ ፡ ለጊዜው ፡ ስለተቆጡ ፡ ዝም ፡ እንድል ፡ የተናገሩት ፡ ይሆን ? "አለ ፡ በአሳቡ ።

ከዚያ ፡ ያ ፡ "ጠጣና ፡ ሂድ ፡ " የመጨረሻ ፡ ስንብት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የሚያስከትለው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተሳስሮ ፡ ታሰበውና ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ቅሬታና ፡ የልብ ፡ ሽብር ፡ ይሰማው ፡ ጀመር ።

ትምርቱን ፡ እንደጨረሰ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሊሄድ ፡ የወሰነውን ፡ ውሳኔ ፡ ትቶ ፡ የፊታውራሪን ፡ ውለታ ፡ ለመክፈልና ፡ እሳቸውን ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ እሱም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ እዳ ፡ ወደሁዋላ ፡ ሳይተው ፡ ለመሄድ ፡ ያሰበው ፡ አሳብ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ መቅረቱና ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ባይበድል ፡ በጎ ፡ ካደረጉለት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ በመጨረሻ ፡ ተቀያይሞ ፡ መለያየቱ ፡ አንድ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ልቡን ፡ ያባባው ፡ ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ ልቡን ፡ ያሸበረው ፡ ከሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ከናትዋና ፡ ከሀብትሽ ፡ ይመር ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ የጨዋታ ፡ ማህበር ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ጉዋደኝነት ፡ መቅረት ፡ ነው ።

ከሰብለም ፡ ይሁን ፡ ከወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ወይም ፡ ከሀብትሽ ፡ ይመር ፡ ጋር ፡ ልዩ ፡ ጉዳይ ፡ ኖሮት ፡ አይደለም ። የለም ፡ ይህ ፡ አይደለም ። እንዲያው ፡ እንዲሁ ፡ ከሶስቱ ፡ ጋር ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ጉዋደኝነት ፡ ይህ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ አግኝቶት ፡ የማያውቅ ፡ ወደፊትም ፡ ምናልባት ፡ የማያገኘው ፡ የቤቶች ፡ ማህበርተኛነት ፡ መቅረቱን ፡ ሲያስብ ፡ ልቡ ፡ ተሸበረበት ። ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩና ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ የሚሉትና ፡ የሚያደርጉት ፡ ሁሉ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ያላዩው ፡ ብዙ ፡ ምስጢር ፡ ብዙ ፡ ትርጉም ፡ እዩያዘ ፡ ታዩው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሰብለን ፡ ሲደክማት ፡ ወይም ፡ እናትዋን ፡ ጨዋታ ፡ ሲያምራቸው ፡ እሱ ፡ ቁጭ ፡ ይልና ፡ ሲያወራ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ይሰፉ ፡ እንደሆን ፡ መስፊያቸውን ፡ ይፈትሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዝርታቸውን ፡ ያሳሱ ፡ ወይም ፡ ያባዝቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥጣቸውን ፡ ይመስምሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመልማሎዎቻቸውን ፡ እፊታቸው ፡ ጣል ፡ ያደርጉና ፡ አንገታቸውን ፡ ትንሽ ፡ ዘንበል ፡ አፉቸውን ፡ ትንሽ ፡ ከፈት ፡ ጥርሳቸውን ፡ ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ አድናቸውን ትንሽ ፡ ወደ ፡ ጎን ፡ ገደም ፡ አድርገው ፡ እያዩ ፡ ሲሰሙ ፡ ቆይተው ፡ “አይ ፡ አንተ ፡ ጉደኛ !” ብለው ፡ የሚስቁት ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እናትዋ ፡ የፈታውራሪን ፡ እግር ፡ ጠብቀው ፡ ሀብትሽን ፡ እንድትጠብቅ ፡ አደራ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ዘመድ ፡ ቤት ፡ ወጣ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ነጠላዋን ፡ ወዲያ ፡ ጣል ፡ ታደርግና ፡ ያን ፡ ውብ ፡ አንገት ፡ ያረጉዋን ፡ እስራቂታ ፡ እዩሳቀች ፡ “ና ፡ ዘጁ ፡ ጻፋ !” ስትለው ፡ እሱም ፡ የሰዋን ፡ ያክል ፡ ባይሆን ፡ በመጠኑ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ይልና ፡ እጅዋን ፡ ይዞ ፡ ያስጻፋት ፡ በጣም ፡ ስለሚያምር ፡ እስዋ ፡ እንደ ፡ ጻፈችው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ብሎዋት ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ አፋራም ፡ አይናቹን ፡ ባፋራም ፡ አይናችዋ ፡ ከትንሽ ፡ ፈገግታ ፡ ጋር ፡ አየት ፡ አድርጋው ፡ መለስ ፡ ትልና ፡ “ይሀና ፡ አርገህ ፡ ያዝ ፡ እንጂ !” የምትለው ፡ ሁሉ ፡ ድሮ ፡ ያላዩው ፡ ብዙ ፡ ምስጢር ፡ ብዙ ፡ ትርጉም ፡ ይዞ ፡ ስለታዩው ፡ የመሄዱን ፡ ነገር ፡ ሲያስብ ፡ ልቡን ፡ ባባት ፡ ባባት ፡ አለው ። ከዚያ ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ ታዩችው ። በተለይ ፡ እመቤትዋ ፡ ጠብቂ ፡ ብለዋት ፡ ሲወጡ ፡

የምታደርገው ፡ ሁሉ ፡ ዘፈንዋ ፡ ሳቅዋ ፡ ደስታዋ ፡ ያሰበችውን ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግም ፡ ለመናገርም ፡ ያላት ፡ ንጹህና ፡ ነጻ ፡ ስሜት ፡ ሁሉ ፡ ትዝ ፡ አለው ። ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ከሌሉ ፡ ትእዛዛቸውን ፡ ጥሳ ፡ ሰብለንና ፡ በዛብህን ፡ ብቻቸውን ፡ ትታ ፡ ወደ ፡ ማድ ፡ ቤትዋ ፡ ከልሄደች ፡ በቀር ፡ በዛብህ ፡ ማስተማር ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ሀብትሽ ፡ ወይ ፡ ትማል ፡ ትገጥመዋለች ፡ ያለዚያም ፡ በጆሮዋው ፡ ትታዘልና ፡ አንገቱን ፡ በሁለት ፡ እጅዋ ፡ ይዛ ፡ ስለ ፡ ተማሪ ፡ ፈሪነት ፡ ስለ ፡ ሆዳምነቱ ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡ አዋቂና ፡ አሳ ማሪነቱ ፡ የሰማችውን ፡ ግጥም ፡ በዜማ ፡ ወይም ፡ በንባብ ፡ ስትደግም ፡ ትቆይና ፡ በጥፊ ፡ መትታው ፡ ወይም ፡ ከሁዋላው ፡ አንገቱን ፡ ስማው ፡ ትሮጣለች ። ሀብትሽ ፡ ደመር ፡ ግጥም ፡ ቶሎ ፡ የመያዝና ፡ ያለመርሳት ፡ ችሎታዋ ፡ በጣም ፡ የሚያስገ ርም ፡ ነበር ። በዛብህ ፡ ሀብትሽ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አንገቱን ፡ እዩያ ዘች ፡ ስለ ፡ ተማሪ ፡ ከተገጠሙት ፡ ግጥሞች ፡ በዜማ ፡ እዩመላለ ሰች ፡ የምትዘፍናቸው ፡ ትዝ ፡ አሉትና ፡ ብቻውን ፡ እንደ ፡ ተቀ መጠ ፡ የቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ አለ ።

“ፍቅርማ ፡ ማን ፡ ያውቃል ፡ ከተማሪ ፡ በቀር ፡-
ዱላ ፡ ሲያነሱበት ፡ ሆዱ ፡ ባይሸበር ፡-
ዱላ ፡ ሲያነሱበት ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ ፈሪ ፡-
አሰጥለት ፡ ነበር ፡ ነፍሴን ፡ ለተማሪ ፡-
ተማሪ ፡ አትውደዱ ፡ ሴቶች ፡ ልንገራችሁ ፡-
ድምጽ ፡ የሰማ ፡ እንደሆን ፡ ባንድ ፡ ተኝታችሁ ፡-
ልባችሁን ፡ ይዞ ፡ እንዳይጠፋባችሁ ፡-
“ጾም ፡ ስጣደቱን ፡ ፈሪሁ ፡ ለቄስ ፡ እንዳልነግር ፡-
ለናንተ ፡ ልናገር ፡ ስሙኝ ፡ ወይዛዝር ፡-
የደረሰብኝን ፡ ፍቅር ፡ እምሮኝ ፡ ሰዞር ፡-
ተሜ ፡ እንሪቤቴ ፡ በቅርቢ ፡ ሲኖር ፡-
ደብሎውን ፡ ለብሶ ፡ ሳየው ፡ ባሻገር ፡-
በግ ፡ እዩመሰለኝ ፡ ከርፋፋ ፡ ጎፈር ፡-
“ከስ ፡” እያልሁ ፡ ከፊቴ ፡ አበረው ፡ ነበር ፡-
መቸም ፡ እንዳንድ ፡ ቀን ፡ መሳሳት ፡ አይቀር ፡-
አንድ ፡ ሌት ፡ ተስቶኝ ፡ አብሬው ፡ ባድር ፡-

አገኘሁት ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ማር ፡ አረቂ ፡ ፍቅሩ ፡
የሚያሰክር ፦
ቆጨጨኝ ፡ ከነከነኝ ፡ ጸፀተኝ ፡ በምር ፦
ያጠፋሁት ፡ ጊዜ ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፦
“መውደድን ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለፈቀደው ፦
መውደዱን ፡ አይደለም ፡ የምናዘዘው ፦
መጥላቱን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሱ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፦
“ያበለውን ፡ ለብሶ ፡ ተሜን ፡ የሚያዩት ፦
ምንም ፡ ቢያጎጥጡት ፡ ምንም ፡ ቢንቁት ፦
ሲጋ ፡ ከሚበሉት ፡ ጠጅ ፡ ከሚጠጡት ፦
ፍቅሩ ፡ ሙቶ ፡ ጊዜ ፡ በልቡ ፡ አገኘሁት ፦
ሽምብራ ፡ መቆርጠም ፡ ውሀ ፡ መጠጣት ፦
ነው ፡ መሰለኝ ፡ እኔስ ፡ የፍቅር ፡ አብነት ፦

“ እንደ ፡ ሰማይ ፡ መና ፡ እንደግዜር ፡ ምግብ ፦
ቢበሉት ፡ ቢበሉት ፡ ተሜ ፡ አይጠገብ ፦

“ ቡኮውን ፡ ደናግል ፡ እያቦኩላት ፦
ምጣዱን ፡ ቅዱሳት ፡ እዬጣዱላት ፦
ሱራፌል ፡ ኪሩቤል ፡ ጻድቃን ፡ ሰማእታት ፦
በከርቤና ፡ በጣን ፡ እያሰሱላት ፦
እሳቱን ፡ መላእክት ፡ እንድደውላት ፦
ዳዊት ፡ በበገና ፡ ሰላም ፡ እያላት ፦
እዝራ ፡ በመሰንቆ ፡ እያጫወታት ፦
ተዋነይ ፡ በቅኔ ፡ እያወደሳት ፦
ያሬድ ፡ ጥኡም ፡ ዜማ ፡ እያዜመላት ፦
የሰማይ ፡ ሰራዊት ፡ ተባብሮ ፡ አንድነት ፦
ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ዘፈን ፡ እያሞገሳት ፦
ወገብዋን ፡ ሸብ ፡ አርጋ ፡ ባልማዝ ፡ መቀነት ፦
እጅዋን ፡ ለቅለቅ ፡ አርጋ ፡ በማየ ፡ ህይወት ፦
በወንበር ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ ስሉስ ፡ በሰሩት ፦
ጸሎት ፡ እያረገች ፡ እንዲሰምርላት ፦
እንደምትጋግረው ፡ የአምላክ ፡ እናት ፦

እንደሰማይ ፡ መና ፡ እንደግዜር ፡ እራት ፡-
ተበልቶ ፡ አይጠገብ ፡ ጠብ ፡ አይል ፡ ባንጀት ፡-
ከመጨመር ፡ በቀር ፡ የመብል ፡ እምሮት ፡-
ከቶ ፡ ከምን ፡ ይሆን ፡ ተማሪን ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠ
ረበት ፡-

" ፍርሀት ፡ ከደሙ ፡ የሚወጣበት ፡-
ጠንቀዋይ ፡ የሚሰጠው ፡ ቢገኝ ፡ መድሀኒት ፡-
አጣንና ፡ መብራት ፡ ሰጥቶ ፡ ለታቦት ፡-
ስስታምነቱ ፡ እንዲጠፋለት ፡-

መጡጫ ፡ የሌለው ፡ ቤት ፡ በጫካ ፡ አሰርቶ ፡-
ተሚን ፡ ከነፍቅሩ ፡ እዚያ ፡ ይዞ ፡ ገብቶ ፡-
እህል ፡ እንዳያምር ፡ ሆድን ፡ ቀዶ ፡ አውጥቶ ፡-
እርጅና ፡ እንዳይመጣ ፡ እርከም ፡ እርዶ ፡ በልቶ ፡-
የሞት ፡ መድሀኒት ፡ ከኤልያስ ፡ ገዝቶ ፡-
ሰው ፡ እንዳያስቸግር ፡ መምጫ ፡ መሄጃውን ፡ ቆፍሮ ፡
አበላሽቶ፡-
እንደ ፡ መናኞቹ ፡ ከዘመድ ፡ ከወዳጅ ፡ ካለም ፡ ተለይቶ ፡-
እዚያ ፡ መኖር ፡ ነበር ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ዘግቶ ፡-"

"ትምህርቴን ፡ ጨርሼ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ለመሄድ ፡ እንዳሰብሁ ፡ ሄጄ ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አይደርስም ፡ ነበር ፡ ፈታውራሪ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ባለመፈጸሜ ፡ ማዘናቸው ፡ ባይቀርም ፡ ባንድ ፡ ወገኑ ፡ ያው ፡ ይሻል ፡ ነበር ፡ አሁንም ፡ ማዘናቸው ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ አልቀረም ፡ ብቻ ፡ ይህ ፡....ሁሉ ፡ አይደርስም ፡ ነበር ፡" አለ ፡ በዛብህ ፡-ሰብለ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩነሽ ፡ ሀብትሽ ፡ ያደረጉትና ፡ ያሉት ፡ ባይኑ ፡ ፊት ሲንቀዋለል ፡ በጆሮው ፡ ውስጥ ፡ ሲንጫጫ ፡ ሲያይና ፡ ሲሰማ ፡ ቆይቶ ፡-

እውነትም ፡ የፈታውራሪ ፡ አዘንና ፡ ቁጣ ፡ ዲማ ፡ የሄደለትን ፡ ትምርት ፡ ጨርሶ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ሊሄድ ፡ በተነሳበት ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ ማስተማር ፡ ሳይጀምር ፡ ከስቃና ከናትዋ ፡ ከሀብትሽ ፡ ይመር ፡ ጋር ፡ የተፈጠረው ፡-ጉዋደኝነት ፡ ሳይፈጠር ፡ ሆኖ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይህን፡

ያክል ፡ ልቡ ፡ አይሸበርም ፡ ነበር ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የራሱን ፡ ጉዳይ ፡ ወደጎን ፡ ትቶ ፡ ፊታውራሪን ፡ ደስ ፡ ሊያሰኝ ፡ ሲጣጣር ፡ ሳይበድላቸው ፡ የቁጣ ፡ አመል ፡ ስላላቸው ፡ ብቻ ፡ ደርሰው ፡ ቢቆጡ ፡ የደም ፡ ስራቸው ፡ እንኩዋን ፡ እንደፍዬል ፡ ቀንድ ፡ መንታ ፡ ሆኖ ፡ በግንባራቸው ፡ መገተር ፡ እንደ ፡ ዋሊያ ፡ ቀንድ ፡ ብዙ ፡ ቅርንጫፍ ፡ አውጥቶ ፡ በሙሉ ፡ አካላቸው ፡ ቢገተር ፡ "ሄእ ፡ — መቸስ ፡ ምን ፡ ላድርግ !" ብሎ ፡ ትከሻውን ፡ ወደላይ ፡ እንስቶባቸው ፡ መንገዱን ፡ ይሄድ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ እያዝንም ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ የሴት ፡ ማህበርተኝነት ፡ የሴት ፡ ጉዋደኝነት ፡ ለካ ፡ ሳያውቀው ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ስሩን ፡ አስፋፍቶ ፡ በውስጡ ፡ በቅሎ ፡ ኖሮ ፡ ለካ ፡ ሳይታወቀው ፡ በውስጡ ፡ መሰረቱን ፡ ጥሎ ፡ ኖሮ ፡ የመለየት ፡ አሳብ ፡ ሲያስብ ፡ የአካሉ ፡ ህንጻ ፡ በሙሉ ፡ ተንቀጠቀጠ ፡ ተናወጠ ።

"ታዲያ ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ላድርግ ? ነገ ፡ እቤቴ ፡ ልዋልና ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ መንገዴን ፡ ላሰናዳ ? ወይስ ፡ ሁለተኛ ፡ እንዴት መጣ ፡ ብለው ፡ ግልጥ ፡ አድርገው ፡ እስኪነግሩኝ ፡ እንደልማዴ ፡ ሄጄ ፡ ላስተምር ? ምናልባት ፡ "ዝም ፡ ብለህ ፡ ጠጣና ፡ ሂድ ፡" ማለታቸው ፡ ለጊዜው ፡ ከቤት ፡ ውጣ ፡ ማለታቸው ፡ እንጂ ፡ ከስራህ ፡ ወግድ ፡ ማለታቸው ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ! ብቻ ፡ ሃሳባቸው ፡ ደጉ ፡ መሆኑስ ፡ እንዴት ፡ ይታወቃል ? '' አለ ፡ በአሳቡ ።

በዛብህ ፡ እንጀው ፡ ተጋድሞ ፡ አይኑን ፡ አፍጦ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በአሳቡ ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ከሌሊቱ ፡ የሚበልጠውን ፡ ክፍል ፡ እንቅልፍ ፡ አጥቶ ፡ ካሳለፈ ፡ በሁዋላ ፡ በተከታዩ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ ሳይሄድ ፡ እንዲውል ፡ ወሰነ ። ይህን ፡ የወሰነበት ፡ እቤቱ ፡ ውሎ ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ መንገዱን ፡ ለማሰናዳት ፡ ሳይሆን ፡ የፊታውራሪን ፡ አሳብ ፡ ለማጣራት ፡ ነው ። በልማዱ ፡ በዛብህ ፡ ለምሳውም ፡ ለራቱም ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ ሳይሄድ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ካንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በቀር ፡ ጠያቂ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይልካሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንዳለቃ ፡ ጥኡመ ፡ ልሳን ፡ ያሉ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አሳባቸውን ፡

ጭምር ፡ በሙሉ ፡ የሚሰጡት ፡ ታላቅ ፡ እንግዳ ፡ የመጣባቸው፡ እንደሆነ ፡ በዛብህን ፡ እስከመፈጠሩም ፡ ይረሱትና ፡ ጠያቂ ፡ ሳይልኩ ፡ ይቀራል ፡፡ ብቻ እንዲህ ፡ ያለው ፡ በጣም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የሚደርስ ፡ ነው ፡፡ ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አጋጣሚ ፡ ካልደረሰ ፡ በዛብህ ፡ እቤታቸው ፡ ሳይሄድ ፡ ውሎ ፡ ሲያድር ፡ መላክተኛ ፡ ካልላኩ ፡ እርግጥ ፡ የማሰናበታቸው ፡ ማስረጃ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ትንሽ ፡ ቢያጠራጥርም ፡ የመጣላታቸው ፡ ምልክት ፡ መሆኑ ፡ አያጠራጥርም ፡፡

በበነጋው ፡ በዛብህ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ ጠያቂ ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ በሽተኛ ፡ ሊጠይቅ ፡ ሄዶዋል ፡ ብሎ ፡ እንዲነግር ፡ ለሚረዳው ፡ ተማሪ ፡ ነግሮ ፡ ልብሱን ፡ ሊያጥብ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ወረደ ፡፡ ከጠባ ፡ ሲመለስ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ወደሚባለው ፡ ወዳጁ ፡ ቤት ፡ ጎራ ፡ ብሎ ፡ እዚያ ፡ እየተጫወተ ፡ ምሳውን ፡ በላና ፡ እጎጆው ፡ ሲደርስ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ ጠያቂ ፡ ደርሶ ፡ ሄዶ ፡ እንደሆን ፡ ቢጠይቅ ፡ ረዳ ፡ ጠያቂ ፡ ያልመጣ ፡ መሆኑን ፡ ነገረው ፡፡ ማታም ፡ እንዲሁ ፡ ጠያቂ ፡ ሳይመጣ ፡ ቀረ ፡፡

" የገበሬ ፡ ልጅ ፡ ጠግቦ ፡ ለምን ፡ ቀና ፡ ብላችሁ ፡ አያችሁኝ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እስቲ ፡ ምን ፡ ተናገርሁት ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ያንለት ፡ ማታ ፡ ራት ፡ ላይ ፡ በበዛብህ ፡ ምክንያት ፡ በቤተሰቡ ፡ መሀከል ፡ በተነሳው ፡ ጭቅጭቅ ፡፡

" እኔኮ ፡ የምለው ፡ ጌታዬ ፡ " አሉ ፡ ባለቤታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ "እኔኮ ፡ የምለው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ልጃችንን ፡ አስተምርልን ፡ ስንለው ፡ ለዝምድናችን ፡ ሲል ፡ መንገዱን ፡ አቋርጦ ፡ የኛን ፡ ፈቃድ ፡ ለመሙላት ፡ ተቀመጠ ፡ እንጂ ፡ በደመወዝ ፡ አልቀጠርነውም ፡፡ ስለዚህ ፡ እንኳንም ፡ ሳያጠፋ ፡ ቢያጠፋም ፡ ያንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ጥፋቱን ፡ አይቶ ፡ እንዳላዩ ፡ ማለፍ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ መቆጣት ፡ ቅር ፡ ሳያሰኘው ፡ አይቀርም ፡፡ ደግሞኮ ፡ እሱ ፡ ከመጣ ፡ በሁዋላ ፡ የተናገርነውንም ፡ ወዲያው ፡ ይሰማዋል ! "

" ይስማዋ ! ይስማው ! የገበሬ ፡ ልጅነቱን ፡ እከኩን

ያራገፈ ፡ በኔ ፡ እንጀራ ፡ መሆኑን ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ይክዳል ? ብቻ ፡ ያም ፡ ሆነ ፡ ያ ፡ እኔ ፡ ዝም ፡ በልኝ ፡ ሂድ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አልተናገርኩትም ።”

“ ወዲያውስ ፡ ጌታ ፡ ሲቆጣ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ ያሳዝናል ? ጌታ ፡ ባለሙዋሉን ፡ ነው ፡ መቸም ፡ የሚቆጣ ፡ ስለዚህ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ አያስቀይምም ። እሱም ፡ የቀረ ፡ ተቀይሞ ፡ አይመስለኝም ፡ አሞት ፡ ወይም ፡ ጉዳይ ፡ አግኝቶት ፡ ይሆናል ። ለመሆኑ ፡ ዛሬ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የቀረ ? ሌላ ፡ ቀን ፡ ቀርቶ ፡ አያውቅም ?” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ።

“ ማስተማር ፡ ከጀመረ ፡ ቀርቶ ፡ አያውቅም ። በፊት ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ ሲቀር ፡ ጠይቂ ፡ ይላክለት ፡ ነበር ። ” አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ።

“ ዛሬ ፡ አልተላከም ? አትልኪም ፡ ኖርዋል ? ወይስ ፡ እንዲያው. . . ሁሉንም ፡ እኔ ፡ ካላሰብኩ ፡---- እዚህ ፡ ቤት ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ? ወዬው ፡ ጉድ ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡-

“ ተቆጥተው ፡ የሰደዱትን ፡ ሰው ፡ እንዲመለስ ፡ መፈ ለግ ፡ አለመፈለግዎን ፡ በምን ፡ አውቄ ፡ ነው ------እኔ ፡ ጠያቂ ፡ የምልክ !”

“ ታውቂያለሽ ፡ ደህና ፡ አድርገሽ ፡ ታውቂያለሽ ! ጥፋቱ ፡ የሱ ፡ አለመሆኑን ፡ ሳውቅ ፡ እናንተን ፡ እንጂ ፡ እሱን ፡ እንዳልተቆጣሁ ፡ ታውቂያለሽ ! እንዲያው ፡ ሰውን ፡ ጥፋተኛ ፡ አስመስሎ ፡ ለማሳየት ፡ ሰውን ፡ ለማስወቀስ ፡ መፈለግ ፡ ስት ፈጠሪ ፡ አብሮሽ ፡ የተፈጠረ ፡ ባህሪ ፡ አብሮሽ ፡ የተፈጠረ ፡ በሽታ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ታውቂያለሽ ! ” አሉ ፡ ፊታ ውራሪ ፡ ተቆጥተው ።

“የለም ፡ ይህ ፡ አያጣላም ፡ ነገ ፡ ጥዋት ፡ በዚያ ፡ ሳልፍ ፡ ደህንነቱንና ፡ ዛሬ ፡ ሳይመጣ ፡ የቀረበትን ፡ ጠይቄው ፡ እል ፋለሁ ። ” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ።

ከራት ፡ በሁዋላ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ አዛዥ ፡ ደስታና ፡ የወ ይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ ዘመድ ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ፡ በዱበኩ

ላቸው ፡ ጨዋታ ፡ ቢጀምሩ ፡ ፊታውራሪና ፡ ምሽታቸው ፡ ተኮራርፈው ፡ ለጨዋታው ፡ ተካፋዮች ፡ ስላልሆኑ ፡ አልጥም ፡ አለ ። ጨዋታው ፡ በሶስቱ ፡ መሀከል ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ቀጠለ ፡ ባለቤቶቹ ፡ አፋቸውን ፡ ዘግተው ፡ ተቀምጠው ፡ እንግዶች ፡ መጫወቱ ፡ ደስ ፡ አልላቸው ፡ ስላለ ፡ አዛዥ ፡ ደስታና ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ድሮ ፡ መጠጥ ፡ እየጠጡ ፡ ብዙ ፡ ሲጫወቱ ፡ የሚያመሹት ፡ ያንለት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ እየተሰናበቱ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ። እነሱ ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልም ፡ አባት ፡ እናትዋን ፡ እጅ ፡ ነስታ ፡ ሀብትሽ ፡ ይመርን ፡ ከማድ ፡ ቤት ፡ አስጠርታ ፡ አስከትላ ፡ ወደልፍኝዋ ፡ ሄደች ። ሀብትሽ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ ደጅ ፡ አውጥታ ፡ መልሳ ፡ እግርዋን ፡ ስታጥባትም ፡ ልብስዋን ፡ አውልቃ ፡ ስታስተኛትም ፡ የምትለፈልፈው ፡ የበዛብህን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ በፊታውራሪና ፡ በወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ፊት ፡ ሲሆን ፡ እንገትዋን ፡ ብትደፋና ፡ ሰብለን ፡ በመቤት ፡ ወግ ፡ የምታከብር ፡ መስላ ፡ ብትታይም ፡ ብቻቸውን ፡ ሲሆኑ ፡ ልክ ፡ ከጉዋደኞችዋ ፡ እንዳንድዋ ፡ ነበር ፡ የምትቆጥራት ። በድሜም ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ያክል ፡ ሰብለ ፡ ትበልጥ ፡ እንጂ ፡ ጉዋደኞች ፡ ናቸው ። ካደጉ ፡ በሁዋላ ፡ ከሌሎች ፡ ሁሉ ፡ ንጽህና ፡ የምትወድ ፡ በመሆንዋ ፡ ለሰብለ ፡ አልባሽና ፡ ተከታይ ፡ ሆና ፡ ተሰጠች ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ካባትዋ ፡ አጥር ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ አለም ፡ ልክ ፡ በውስጡ ፡ ገብታ ፡ እንደምትኖርበት ፡ አድርጋ ፡ የምታውቀው ፡ የሚበልጠውን ፡ ክፍል ፡ በሀብትሽ ፡ አማካይነት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በጣም ፡ ትወዳታለች ።

"እንግዲህ ፡ እንደኛውን ፡ መቅረቱ ፡ ነው ፡ እንዴ ? " አለች ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ።

"ማን ፡ ያውቃል ? መቅረቱ ፡ ይሆናል ! " አለች ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አይንዋን ፡ ሳታረግብ ፡ እፊትዋ ፡ በተዘረጋው ፡ ባዶ ፡ ቦዘገ ፡ አድርጋ ፡ ተክላ ።

"አየ ---- ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ነበር ! አይኑን ፡ ጭፍን ፡ አድርጎ ፡ ሲስቅ ፡ ዘርዛራ ፡ ጥርሱና ፡ ጉንጩ ፡ እንደ ፡ ተወጋ ፡ ወደ ፡

ውስጥ ፡ ስርጎድ ፡ የሚለው ፡ ደስ ፡ ይለኛል ! ደስ ፡ አይልም ?" አለች ፡ ሀብትሽ ።

"ህእ ! " አለች ፡ ሰብለ ፡ አይንዋ ፡ እንደበዘ ፡ የበዛብህ ፡ አሳሳቅ ፡ ታያትና ።

" አይ ፡ አፋራም ፡ ባይሆን ፡ ተበልቶ ፡ የማይጠገብ ፡ ልጅ ፡ ነበር ! አሀሀሀ ... ወይ ፡ ጉዴ ! እስቲ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅሽ ፡ ሰብልዬ ፡ አትሸሽጊኝ ፡ አፈር ፡ ስሆንልሽ ! ያን ፡ ያክል ፡ ስትተቃቀፉ ፡ አንዳንድ ጊዜ ፡ በግራ በኩል ፡ ይቀመጥና ፡ እጁን ፡ ባንገትሽ ፡ ላይ ፡ አሳልፎ ፡ ቀኝ ፡ እጅሽን ፡ ይዞ ፡ ሲያስጽፍሽ ፡ እንዲህ ፡ ገላችሁ ፡ ሲነካካ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ አይሰማሽም ?" አለች ፡ ሀብትሽ ፡

"ምን ፡ ይሰማኛል ? አለች ፡ ሰብለ ፡ የቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ በፊትዋ ፡ እዬታዬ ። በዘው ፡ የነበሩ ፡ አይኖችዋ ፡ ወደ ፡ ሀብትሽ ፡ መለስ ፡ ሲሉ ፡ እንደገና ፡ ህይወት ፡ እንደገና ፡ ውበት፡ ሞልቶባቸው ፡ ነበር ።

" እንጃ ! እኔ ፡ መቼም ፡ ወንድ ፡ እንኩዋንስ ፡ እንዲህ ፡ በደረቱ ፡ አስጠግቶ ፡ ይዞኝ ፡ እጄን ፡ ሲጨብጠው ፡ ልቤ ፡ ይሸበራል ! "

"ወይጅ ፡ እባክሽ ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ በደረቱ ፡ አስደግፎኝ ፡ አያውቅ ! እሱ ፡ በንጹህ ፡ ልቡ ፡ ሲረዳኝ ፡ አስቦ ፡ ነውንጂ ፡ ክፉት ፡ ቢያስብ ፡ በማማና ፡ ባንቺ ፡ ፊት ፡ እጄንና ... እጄን ፡ ይይዛል ? የራስሽን ፡ መስሎኝ ነው !" አለች ፡ ሰብለ ፡ ፊትዋ ፡ ትንሽ ፡ ጠንከር ፡ ብሎ ።

" እይውልሽ ፡ እውነቱን ፡ ስነግርሽ ፡ ጊዜ ፡ ልትቆጪ ፡ ነው ! "

" እኔ ፡ አልቆጣም ! ብቻ ፡ እውነት ፡ አይደለም ፡ አልሁሽንጂ።።"

" እና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንኩዋ ፡ ቆንጠጥ ፡ አድርጎሽ ፡ አያውቅም ፡ ማለት ፡ ነዋ ! "

" ኧረ ፡ ጉንዳን ፡ ይቆንጥጥሽ ፡ እቴ ! እሱ ፡ እንዲህ ፡ አያደርግም ፡ ጨዋ ፡ ነው ። ቢያደርግም ፡ ሁለተኛ ፡ እዚህ

ቤት ፡ አይደርስም ። ” አለች ፡ ሰብለ ፡ እንደገና ፡ ትንሽ ፡ እን ይመሳቅ ፡ ብላ ።

“ እንግዲህ ፡ ወይ ፡ እንቺ ፡ ውሸታም ፡ ነሽ ፡ ወይ ፡ እሱ ፡ በግ ፡ ነው ! በይ ፡ ተነሽ ፡ ተኚ ፡ እኔ ፡ ገብሬ ፡ ይጠብቀኛል ፡ ልሂድለት ፡ እናቴ ! የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዋሽራ ፡ ዙራምባ ፡ እያለ ፡ የሚያወራው ፡ እንዳይቀርብን ፡ እንዳይሄድብን እንጠልያለን ። አይሄድም ፡ ግዴለም ። ” አለች ፡ ሀብትሽ ፡ ሰብለን ፡ አስ ተኝታ ፡ ሄደች ።

በዛብህ ፡ አንድ ፡ አመት ፡ ያክል ፡ እፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ እዬተመላለሰ ፡ ምሳውንም ፡ ራቱንም ፡ እዬበላ ፡ ሲኖር ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ካሽከሮች ፡ እንዳንዱ ፡ እንዲሁ ፡ በሩቁ ፡ እያዬች ፡ ታውቀዋለች ፡ እንጂ ፡ እሱን ፡ የመውደድ ፡ ይሁን ፡ የመጥላት ፡ ስሜት ፡ አልነበራትም ። ድንገት ፡ ባጋጣሚ ፡ ባጠገብ ፡ የሚተላለፉ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እጅ ፡ ሲነሳት ፡ በልጃገረድ ፡ ወይዛዝር ፡ ወግ ፡ እንደ ፡ ተሰደበች ፡ ሁሉ ፡ ፊት ዋን ፡ ከፍቶት ፡ በራስዋ ፡ሰላምታውን ፡ መልሳለት ፡ ትሄዳ ለች ። ይህ ፡ እንኳዋ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ፡ ሰላም ፡ ያለች ፡ እንደ ሆነ ፡ ያባት ፡ የናትዋን ፡ ቁጣ ፡ በመፍራት ፡ ጭምር ፡ ነው ። ካሳ ፡ ዳምጤን ፡ ከሰዋ ፡ ለማራቅ ፡ አባትዋ ፡ እሱ ፡ እንዲያስተ ምራት ፡ ሲመርጡት ፡ ግን ፡ እንዲያውም ፡ ጠላችው ። አባ ትዋ ፡ በሰዋ ፡ ምክናያት ፡ ህይወታቸውን ፡ ለማሳለፍ ፡ እጦር ፡ ሜዳ ፡ ሄደው ፡ ባይሰለፉና ፡ ፈቃዳቸውን ፡ መፈጸም ፡ ለዚህ ፡ ዋጋ ፡ ይሆናል ፡ ብላ ፡ ባታምን ፡ ኖሮ ፡ በጉዱ ፡ ካሳ ፡ ፈንታ ፡ በዛብህ ፡ እንዲያስተምራት ፡ በጭራሽ ፡ አትፈቅድም ፡ ነበር ። ብቻ ፡ ፈታውራሪ ፡ ህይወታቸውን ፡ የሚሰጡበት ፡ ምክ ናያት ፡ ያልነበረ ፡ መሆኑን ፡ ብታውቅም ፡ ለሳቸው ፡ መስሎዋ ቸው ፡ መስዋእት ፡ ሆነው ፡ ቀርበው ፡ ስለነበረ ፡ በበኩልዋ ፡ ፈቃድዋን ፡ ለፈቃዳቸው ፡ መስዋእት ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ፡ ብላ ፡ ትእዛዛቸውን ፡ ተቀበለች ።

በዛብህ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ያክል ፡ ካስተማራት ፡ በሁዋላ ፡ ግን ፡ ስለሱ ፡ የነበረው ፡ አሳብዋ ፡ እዬተለወጠ ፡ ሄደ ። እንደ ፡ ተለመደ ፡ ከበሮ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሄር ፡ ሲነሳ ፡ ብቻ ፡ የሚመሁ ፡

መስሎዋት ፡ የነበረው ፡ ለዛ ፡ ያለው ፡ ጨዋታ ፡ የሚያውቅ ፡ መሆኑን ፡ ስታይ ፡ እንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ትምህርቱንና ፡ ጸሎቱን ፡ ብቻ ፡ የሚያሰላስል ፡ ቀዝቃዛ ፡ መናኝ ፡ መስሎዋት ፡ የነበረው ፡ ህይወትና ፡ ሙቀት ፡ ያለው ፡ ወጣት ፡ መሆኑን ፡ ስታይ ፡ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ በጨዋታውና ፡ በሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ራሱን ፡ ለማስደነቅና ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ለመታየት ፡ ሌሎችን ፡ እንዳያኮስስ ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ስሜት ፡ እንዳይነካ ፡ የሚጠነቀቅ ፡ መሆኑን ፡ ስታይ ፡ ስለሱ ፡ የነበረው ፡ አሳብዋ ፡ እዬተለዋወጠ ፡ ሄደ ። እስዋና ፡ እናትዋን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ወሬ ፡ ሲያወራ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የሚያወራው ፡ ወሬ ፡ ለከብራቸው ፡ የማይስማማ ፡ ሆኖ ፡ እንዳያስቀይማቸው ፡ ሲጠነቀቅ ፤ እጅዋን ፡ ይዞ ፡ በሚያስጽፍበት ፡ ጊዜ ፡ አንገትዋን ፡ ወይም ፡ ጉንጭዋን ፡ የነካ ፡ እንደሆን ፡ ያልተፈቀደለትን ፡ ክፍል ፡ በመንካቱ ፡ ትቀዬም ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ሲሰቀቅ ፡ ስትሳሳት ፡ ያልተሳሳተች ፡ እስመስሎ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ስተትዋን ፡ እንድታርም ፡ ለማድረግ ፡ ሲሞክር ፡ በጠቅላላው ፡ የብርቱና ፡ የትጉ ፡ አስተማሪነት ፡ ተግባሩን ፡ ሳያጎድል ፡ የቅርብ ፡ ጉዋደኝነቱን ፡ መስጠት ፡ የሚያውቅ ፡ መሆኑን ፡ ስታይ ፡ እዬለመደችው ፡ እዬወደደችው ፡ ሄደች ። ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ እንዳለችው ፡ ቆንጥጠዋት ፡ ወይም ፡ ጎንጠዋት ፡ በቃልም ፡ ይሁን ፡ በሌላ ፡ ምልክት ፡ የፍቅር ፡ ስሜቱን ፡ አሳይቶዋት ፡ ሳይሆን ፡ እንዲያው ፡ እንዲሁ ፡ ባጠገብዋ ፡ ሆኖ ፡ ሲረዳት ፡ ሲደግፋት ፡ አይዞሽ ፡ ሲላት ፡ ሲያጫውታት ፡ ለመደችና ፡ እንዲያው ፡ እንዲሁ ፡ ባጠገብዋ ፡ መሆኑ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ከምታውቀው ፡ ጉዋደኝነት ፡ ሁሉ ፡ ትንሽ ፡ ሙቀት ፡ ትንሽ ፡ ህይወት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ አሳያትና ፡ ድንገት ፡ ተለይቶዋት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሲውል ፡ ድንገት ፡ ካጠገብዋ ፡ ስታጣው ፡ የሙቀት ፡ ልብስዋን ፡ ከላይዋ ፡ እንደ ተገፈፈች ፡ ብርድ ፡ ተሰማት ። ከተወለደች ፡ ጀምሮ ፡ አብረዋት ፡ ከኖሩት ፡ አባት ፡ እናትዋ ፡ ከዘመዶችዋ ፡ ካሽከሮች ፡ መሀከል ፡ እንዳልሆነች ፡ ሁሉ ፡ ብቻዋን ፡ የሆነች ፡ መሰላት ።

‘‘ለምን ፡ እንዲህ ፡ ቅር ፡ አለኝ ? ለምን ፡ ልቤ ፡ እንዲህ ፡ ተሸበረ ? እንደኛውን ፡ በሄድ ፡ ምን ፡ ይቀርብኛል ?’’ አለች ፡ ሰብለ ፡ ባሳብዋ ፡ አልጋዋ ፡ ላይ ፡ በጀርባዋ ፡ እንደ ፡ ተኛች ፡

እይንዋን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በጨለማ ፡ አፍጣ ። በዚያ ፡ እይን ፡ ቢወጉ ፡ በማይታይበት ፡ ጨለማ ፡ በዛብሆን ፡ ብቻ ፡ ታይ ፡ ነበር ። በዛብህ ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀጭ ፡ ብሎ ፡ ሲያወራ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይኖቹን ፡ ጭፍን ፡ ጉንጮቹን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሰርጎድ ፡ አድርጎ ፡ ሲስቅ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እጅዋን ፡ ተጠንቅቆ ፡ ይዞ ፡ ሲያስጽፋት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አይኖቻቸው ፡ በጎን ፡ ሰርቀው ፡ ሲያዩ ፡ ሲሞክሩ ፡ ድንገት ፡ ይጋጩና ፡ የሱ ፡ ቀድመው ፡ ሲሸሹ ፡ ወዲያው ፡ የሱ ፡ አደነጋገጥ ፡ ጭምር ፡ እየተለዋወጠ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ይታያት ፡ ነበር ።

"በመሄዱ ፡ ቀርጠ ፡ ይሆን ? አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢመጣ ፡ ባይዞን ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ትምርቴን ፡ እስክጨርስ ፡ እንዲቆይ ፡ እነግረው ፡ ነበር ! ብቻ ፡ እንዴት ፡ ብዬ ፡ እነግረዋለሁ ? አባክህ - - - - - -ትምርቴን ፡ እስክጨርስ ፡ እንኩዋ ፡ - - - - -ቆይልኝ ! የለም ፡ እንኳዋ - - - -ስል ፡ አብሬያት ፡ እንድኖር ፡ ፈልጋለች ፡ ይላል ! እባክህ ፡ ትምርቴን ፡ አስጨርሰኝና ፡ ሂድ ፡ - - - ! ይህ ፡ ይሻላል !" አለች ፡ ሰብለ ፡ ምናልባት ፡ በዛብህ ፡ የመጣ ፡ እንደሆን ፡ ራስዋን ፡ ሳታጋልጥ ፡ አብሮዋት ፡ እንዲቆይ ፡ የምትጠይቅበትን ፡ ቃል ፡ መምረጥ ፡ አቅቶዋት ፡ ስትቸገር ፡ ቆየች ።

ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ የበዛብህን ፡ ነገር ፡ ስታነሳ ፡ ስትጥል ፡ እንቅልፍ ፡ ሳይወስዳት ፡ እስከኩለ ፡ ሌሊት ፡ ቆየች ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ቅዠት ፡ የሞላበት ፡ የማያሳርፍ ፡ እንቅልፍ ፡ ተኛች ። በዛብህ ፡ በበነጋውም ፡ ለምሳ ፡ አልመጣም ። ብቻ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ጥዋት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲሄዱ ፡ በቤቱ ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ በተቀዳሚው ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ በመቅረቱ ፡ ጌቶችም ፡ እሜቴም ፡ መስጋታቸውን ፡ ነግረውት ፡ ወዳጁ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ከከተማ ፡ ሙሴ ፡ ስለ ፡ ታመመ ፡ ሊጠይቅ ፡ ሄዶ ፡ የነበረ ፡ መሆኑንና ፡ ከሰአት ፡ በሁዋላ ፡ ለማስተማር ፡ የሚመጣ ፡ መሆኑን ፡ እምሳ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተናገሩ ፡ የሁሉም ፡ አሳብ ፡ ትንሽ ፡ እረፍ ፡ አለ ።

# ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፡

## የባላገር ፡ መላክተኞች ፡

በዛብህ ፡ ከምሳ ፡ በሁዋላ ፡ ለማስተማር ፡ የሚመጣ ፡ መሆኑን ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ እግብር ፡ ላይ ፡ ሲናገሩ ፡ ቤተሰቡን ፡ በሙሉ ፡ ደስ ፡ አለው ። ፊታውራሪ ፡ እንኳ ፡ ምንም ፡ ሰብለን ፡ አንቺ ፡ ማለቱ ፡ ትልቅ ፡ ስሕት ፡ መሆኑን ፡ ቢያውቁ ፡ ወደዚህ ፡ ስሕት ፡ የመሩት ፡ ምኞታቸውና ፡ ልጃቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ለሱ ፡ ይቅርታ ፡ ያደረጉለት ፡ መሆናቸውን ፡ ሲመጣ ፡ አስጠርተው ፡ ሊመንገር ፡ አስበው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እንግዳ ፡ ውስጥ ፡ ካሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጉልቶቻቸው ፡ ጥቂት ፡ ባላገሮች ፡ ድንገት ፡ ስለሰሙ ፡ እነሱን ፡ ሲያዩ ፡ በዛብህን ፡ ረሱት ።

ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሊሆን ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው ፡ አጋፋሪው ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ከሶስት ፡ ጉልቶቻቸው ፡ ሶስት ፡ የባላገሮች ፡ ወኪሎችና ፡ ሹማቸው ፡ ብላታ ፡ መንግስቱ ፡ ዘላለም ፡ መምጣታቸውን ፡ ሲነግራቸው ፦

"እህ ! መጡ ? ምሳቸውን ፡ አብላቸው ።" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፤

"እአዳራሽ ፡ ይብሉ ፡ ወይስ ፡ እዚሁ ?" አለ ፡ አጋፋሪው ፡ ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሊሆን ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ ያልቀረው ፡ መሆኑን ፡ በመመልከት ።

"እእ---ግድለም ፡ እዚህ ፡ አብላቸው !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

መጀመሪያ ፡ ሹሙ ፡ ከዚያ ፡ የባላገሮች ፡ ወኪሎች ፡ ተጠርተው ፡ ገብተው ፡ ምሳቸውን ፡ በልተውና ፡ አንዳንድ ፡ ብርሌ ፡ ጠላ ፡ ጠጥተው ፡ እስኪወጡ ፡ ድረስ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቁጣ ፡ በቀላ ፡ ክፉ ፡ አይን ፡ ይመለከቱዋቸው ፡ ነበር ።

ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሆኖ ፡ አዳራሽ ፡ እንደ ፡ ተነጠፈ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቶሎ ፡ እዚያ ፡ ሄደው ፡ ተቀምጠው ፡ ባላገሮች ፡ እንዲጠሩ ፡ አዘዙ ። ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ፡ ሌሎችም ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ነበሩ ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሰብለ ፡ በምትማርበት ፡ ሄዶ ፡ አክስቶንና ፡ እስዋን ፡

ሰላም ፡ ካለ ፡ በሁዋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ ከባላገሮች ፡ ጋር ፡ ወደሚ ጨሊቃጨቁበት ፡ ወጸዳሬሽ ፡ መጥቶ ፡ ተጨመረ ።

"እስቲ ፡ እባክህ ፡ አሽከሮችን ፡ ብልዝ ፡ አትላልታችሁ ፡ እንገላታችሁ ፡ ባደጃቸውን ፡ የመለሳችሁበትን ፡ በፋሲካ ፡ ምድር ፡ እናንተ ፡ በዩዚታችሁ ፡ እያረዳችሁ ፡ ስጋ ፡ በልታችሁ ፡ ስትውሉ ፡ እኔ ፡ ሽሮ ፡ በልቼ ፡ እንድውል ፡ የፈረዳችሁብኝ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ንገሩኝ ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሹሙን ፡ በብርቱ ፡ ቁጣ ፡ እየተመለከቱ ።

"እኔ ፡ ጌታዬ ፡ የሠንጋ ፡ እናት ፡ ተንጋላ ፡ ትሞት ፡ እንደሚሉት ፡ ተረት ፡ እዚህ ፡ ጌታዬን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ እዚያ ፡ ባላገሮች ፡ ቀምበር ፡ ከበደን ፡ እንዳያሉ ፡ ለማድረግ ፡ ብሞክር ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ወቀሳ ፡ እንጂ ፡ ምስጋና ፡ አላገኘሁም ። የጌታዬ ፡ አሽከሮች ፡ ተልከው ፡ ሲመጡ ፡ እነሱን ፡ ይገፉ ፡ በሶስቱም ፡ ጉልቶችዎ ፡ እየዞርሁ ፡ ባላገሮችን ፡ እየሰበሰብሁ ፡ መልክቱን ፡ አደርሻለሁ ። ለመስቀልና ፡ ለገና ፡ እዋጥተን ፡ ፍሪዳ ፡ እየገዛን ፡ ሰጥተናልና ፡ አሁን ፡ እንደገና ፡ ፍሪዳ ፡ መግዛት ፡ አንችልም ፡ ዚሉ ፡ ባይሆን ፡ አንዳንድ ፡ ሙክትና ፡ ማር ፡ ወይም ፡ ቅቤ ፡ ይዛችሁ ፡ ሂዳችሁ ፡ ችግራችሁን ፡ አመልክቱ ፡ ብያቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ አንችልም ፡ አሉኝ ። ስለዚህ ፡ ከኔ ፡ የጎደለ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ድካሜን ፡ ሁሉ ፡ ከጌታዬ ፡ ተልከው ፡ መጥተው ፡ የነበሩት ፡ አሽከሮች ፡ ያውቃሉ ። አሁን ፡ ከሶስቱ ፡ ጉልቶችዎ ፡ አገር ፡ እየመረጠ ፡ የላካቸው ፡ ይኸው ፡ ሶስት ፡ ሰዎች ፡ መጥተዋል ፡ እነሱ ፡ ይጠየቁ ።" አሉ ፡ ብላታ ፡ መንግስቱ ፡ ዘላለም ።

"አሽከሮችማ ---- እኔን ፡ አክለው ፡ እኔን ፡ መስለው ፡ ወደናንተ ፡ የተላኩት ፡ አሽከሮችማ ፡ በገዛ ፡ ጉልቴ ፡ በገዛ ፡ አገሬ ፡ አንድ ፡ እንጀራና ፡ አንድ ፡ ዋንጫ ፡ ጠላ ፡ የሚላቸው ፡ አጥተው ፡ በራብና ፡ ጥም ፡ ሲጉላሉ ፡ ሰንብተው ፡ ተመልሰዋል ። ብቻ ፡ ይህ ፡ የሆነበትን ፡ ምክናያት ፡ በሁዋላ ፡ ትነግሩኛላችሁ ፡ ግዴለም ። አሁን ፡ በፋሲካ ፡ ምድር ፡ ሳልገድፍ ፡ ጾም ፡ ሳይፈታልኝ ፡ እንድውል ፡ የተደረገበትን ፡ ምክናያት ፡ ልወቀው !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባላገሮችን ፡ በቀላ ፡ አይን ፡ እየተመለከቱ።

"ደሀ ፡ ምንጊዜም ፡ ዘሆን ፡ ሞልቶለት ፡ አያውቅም ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ከደሀ ፡ ጉድለት ፡ ከጌታ ፡ ምህረት ፡ ተለይቶ ፡ አያውቅም ። ስለዚህ ፡ አልሞላልን ፡ ብሎ ፡ አጥፍተናልና ፡ ጌታችን ፡ ምህረት ፡ እንዲያደርጉልን ፡ ነው ፡ የምንለምነው !" አለና ፡ ከባላገሮቹ ፡ አንዱ ፡ ራሱን ፡ እስከ ፡ ጉልበቱ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ሲያጎነብስ ፡ ጉዋደኞቹም ፡ አብረውት ፡ አጎንብሰው ፡ ምህረት ፡ ይለምኑ ፡ ጀመር ።

"እባክህ ፡ አትሜውቱብኝ ፡ ይልቅ ፡ ተነሱ ! ቀና ፡ በሉ!" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደተቆጡ ። "የልባችሁን ፡ ሰርታችሁ ፡ አሁን ፡ ካንገት ፡ በላይ ፡ ምህረት ፡ ልመና ፡ ወግቶ ፡ በቅቤ ፡ እንደሚሉት ፡ ተረት ፡ ነው ! ለመስቀልና ፡ ለገና ፡ ፍሪዳ ፡ የሰጠ ፡ ባላገር ፡ ለፋሲካ ፡ አይሰጥም ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ያወጀ ፡ ማነው ? እናንተ ፡ ያወጃችሁት ፡ አዋጅ ፡ ይሆናል ! መቸም ፡ ባላገር ፡ ሲጠግብ ፡ ወሰኑን ፡ አያውቅ ፡ ባላገር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አዋጅ ፡ አውጆ ፡ እንደሆን ፡ ንገረኝ ! ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ እናንተ ፡ ገዢዎች ፡ እኛ ፡ ተገዢዎች ፡ እንሆናለን !"

" እሱ ፡ እንኩዋ ፡ አንዳንድ ፡ አላዋቂ ፡ ወጣቶች ፡ የተናገሩት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከስተዋይ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የተናገረ ፡ ስለሌለ ፡ ብላታ ፡ መንግስቱ ፡ እዚህ ፡ በጌታችን ፡ ፊት ፡ ሊደግመው ፡ አይገባም ፡ ነበር ። አሁን ፡ እኛ ፡-----------
"ብሎ ፡ ሁለተኛው ፡ ባላገር ፡ ንግግሩን ፡ ሊቀጥል ፡ ሲል ፡-

"እረ ፡ ለመሆኑ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አቋርጠው ፡ "እ ፡ ለመሆኑ ፡ እነዚህ ፡ ጉልቶች ፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ መሆናቸውን ፡ አታውቁም ? ካያቶቼ ፡ እስከኔ ፡ ተራራ ፡ ዞረን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግረን ፡ አቀበት ፡ ወጥተን ፡ ቁልቁለት ፡ ወርደን ፡ በሩቅ ፡ በቅርብ ፡ ዘምተን ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ደረታችንን ፡ ለመድፍ ፡ አንገታችንን ፡ ለሰይፍ ፡ ሰጥተን ፡ እንዲህ ፡ አድርገን ፡ ያገኘናቸው ፡ የነፍሳችን ፡ ዋጋ ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ ቁጭ ፡ ብለን ፡ ሆዳችን ፡ እስኪነፋና ፡ ብስና ፡ እስኪይዘን ፡ እዬበላን ፡ እዬጠጣን ፡ ፍዬልና ፡ ጥጃ ፡ ዝንጀሮና ፡ ጦጣ ፡ ወይም ፡ አህያ ፡ እዬጠበቅን ፡ ያገኘናቸው ፡ አለመሆናቸውን ፡ አታውቁም ? ታዲያ ፡ ነፍሳችንን ፡ ሰጥተን ፡ ላመትባል ፡ መዋያ ፡ አንዳንድ ፡ ፍሪዳ ፡ ብንጠይቅ ፡

ይብዛብን ? ወዬው ፡ ጉ . . . ድ ! ግሩምኮ ፡ ነው !”

“አይቆጡን ፡ አያጣሉን ፡ ጌታችን ፡ ” አሉ ፡ ከባላገሮቹ ፡ ሳይናገሩ ፡ የቆዩት ፡ ሽማግሌ ። “ እኛ ፡ ያለስዎ ፡ አለዎም ፡ ያለኛ ፡ መኖር ፡ ስለማንችልና ፡ እየተጣሉም ፡ አብሮ ፡ መኖር ፡ የልብና ፡ የአእምሮ ፡ በሽታ ፡ ስለሆነ ፡ አያጣሉን ፡ አይቆጡን ። አለባብሶ ፡ ቢያርሱ ፡ ባረም ፡ ይመለሱ ፡ እንደሚሉት ፡ ተረት ፡ ነገ ፡ የሚገለጠውን ፡ ዛሬ ፡ አለባብሰን ፡ ብናልፈው ፡ ነገ ፡ ደግሞ ፡ ችግር ፡ ተፈጥሮ ፡ እኛም ፡ እንደገና ፡ ተቸግረን ፡ ብለን ፡ እንዳንመጣብዎ ፡ ጌታችንም ፡ እንደገና ፡ ሰላምዎን ፡ እንዳያጡ ፡ ከመጣን ፡ አይቀር ፡ በሶስቱ ፡ ጉልቶችዎ ፡ የሚኖረው ፡ ህዝብ ፡ የተቸገረበትን ፡ ግልጥ ፡ አድርገን ፡ እንነግርዎና ፡ ጌታችን ፡ እግዚአብሄር ፡ ባሳዩዎ ፡ መንገድ ፡ ውሳኔዎን ፡ ወስነው ፡ ይስጡን ። ቅድም ፡ ብላታ ፡ መንግስቱ ፡ ያለው ፡ አንዳንድ ፡ አላዋቂ ፡ ወጣቶች ፡ የተናገሩት ፡ አይደለም ። በሶስቱ ፡ ጉልቶችዎ ፡ የሚኖረው ፡ ህዝብ ፡ ሁሉ ፡ የሚለው ፡ ነው ።

ዘመን ፡ ከተለወጠ ፡ በሶስቱ ፡ ጉልቶችዎ ፡ የምንኖር ፡ ድሆች ፡ ለመስቀል ፡ ሶስት ፡ ለገና ፡ ሶስት ፡ ፍሪዳ ፡ ከብቶቻችንን ፡ እየሸጥን ፡ ከፍለናል ። ይህም ፡ ርስት ፡ የሚያርስ ፡ እርቦ ፡ በጉልት ፡ ተቀምጦ ፡ የሚያርስ ፡ ግመታ ፡ ከምንከፍለው ፡ ሌላ ፡ ነው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ ለወረዳ ፡ ለምስለኔ ፡ ለጭቃ ፡ ሹም ፡ የምንከፍለው ፡ የገንዘብና ፡ የጉልበት ፡ እዳ ፡ አለ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አንችለውም ። በተለይ ፡ ዘንድሮ ፡ እግዚአብሄርም ፡ ተቆጥቶን ፡ እህል ፡ ብንዘራ ፡ በቡቃያው ፡ ትል ፡ ከዚያ ፡ የተረፈው ፡ በሚሰበሰብበት ፡ ጊዜ ፡ በረዶ ፡ ስለወረደበት ፡ እንዲሁ ፡ እጃችንን ፡ አጨብጭበን ፡ ወደየቤታችን ፡ ገባን ። እግዚአብሄር ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ ቢምረን ፡ እንኩዋ ፡ ባላማረርን ፡ ነበር ። ይሄው ፡ አሁን ፡ ባገራችን ፡ የከብት ፡ በሽታ ፡ ገብቶ ፡ ከብቶቻችን ፡ በየቀኑ ፡ ከያንዳንዳችን ፡ አንድም ፡ ሁለትም ፡ ሲሞቱ ፡ ቆመን ፡ እየተመለከትን ፡ እናለቅሳለን ። በሽታውን ፡ በመፍራት ፡ ስጋቸውን ፡ እንኩዋ ፡ አንበላውም ። የሞቱትን ፡ ከብቶች ፡ ስጋ ፡ የበላ ፡ አውሬም ፡ ይሁን ፡ ውሻ ፡ ወዲያው ፡ ይሞታል ። በንደዚህ ፡ ያለ ፡ የሚያሳዝን ፡ ሁኔታ ፡ ነው ፡ ያለን ። በነበረን ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡

ያለ ፡ ችግር ፡ ሳይደርስብን ፡ ሹምን ፡ ከማሳዘን ፡ ጠም ፡ አድሮ ፡ ሹምን ፡ ደስ ፡ ማሰኘትና ፡ ሰላምን ፡ ማግኘት ፡ ይሻላል ፡ እያልን ፡ የኛ ፡ ቀርቶብን ፡ የተቀባችሁትን ፡ ሰዎች ፡ ጌቶቻችንን ፡ ደስ ፡ ስናሰኝ ፡ እንኖር ፡ ነበር ። ሳይኖረን ፡ ግን ፡ ስንቸገር ፡ ባይሆን ፡ ጥንት ፡ የተሰራብንን ፡ እዳ ፡ እንከፍላለን ፡ እንጂ ፡ ያለዳችን እንከፍልም ፡ እንላለን ። ችግራችን ፡ ከዚያ ፡ ያለፈ ፡ እንደሆን ፡ ደግሞ ፡ ጥንት ፡ የተሰራብንን ፡ እዳ ፡ እንኳ ፡ መክፈል ፡ ወደማንችልበት ፡ ሁኔታ ፡ እንደርሳለን ።

“ ጥንት ፡ የተሰራብን ፡ እዳ ፡ መክፈል ፡ የሚገባን ፡ መክፈል ፡ የማይገባን ፡ የምትለው ፡ ምንድነው ፡ አባክህ ? ባላገር ፡ ሊከፍለው ፡ የሚገባውን ፡ ገዢ ፡ ይወስናል ፡ እንጂ ፡ ከመቼ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ ባላገር ፡ መወሰን ፡ የጀመረ ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሽማግሌው ፡ የተናገሩት ፡ ከማስቀጣቱም ፡ በላይ ፡ አስገርሞዋቸው ።

“ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሀብት ፡ ባያድለኝ ፡ እድሜ ፡ አድሎኛል ! በዚህ ፡ በረዥም ፡ እድሜዬ ፡ ርስትና ጉልት ፡ ያለው ፡ እንደጌታዬ ፡ ያለ ፡ ጌታ ፡ ከርስትና ፡ ከጉልቱ ፡ ምን ፡ እንደሚያገኝ ፡ በንዲህ ፡ ያሉ ፡ ርስተጉልቶች ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ እዳቸው ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ የጥንት ፡ ስሪቱን ፡ አውቃለሁ። በታላቁ ፡ አባትዎ ፡ ጊዜም ፡ ልጅ ፡ ልሁን ፡ እንጂ ፡ አባቶቼ ፡ ዘመዶቼ ፡ በጠቅላላው ፡ ባላገሩ ፡ ላባትዎ ፡ የሚከፍለውን ፡ አውቃለሁ ። አሁን ፡ ጌታችን ፡ የሚጠይቁን ፡ ሁሉ ፡ ድሮ ፡ ያልነበረ ፡ ነው ።”

“ ያንተ ፡ እድሜ ፡ ለኛ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ ስለሌለው ፡ እሱን ፡ ተወውና ፡ ምኑ ፡ ነው ፡ ድሮ ፡ ያልነበረው ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በባላገሩ ፡ ድፍረት ፡ በጣም ፡ ተቆጥተው ።

“ ለጌታዬ ፡ የደሀ ፡ እድሜ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ቢመስልዎ ፡ እኔ ፡ በጎውንም ፡ ክፉውንም ፡ ስላየሁ ፡ እድሜዬን ፡ እወደዋለሁ ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ረዥም ፡ እድሜ ፡ የሰጠኝን ፡ አምላክም ፡ አመሰግነዋለሁ ። ሀብት ፡ አጣን ፡ ብለው ፡ እድሚያቸው ፡ እንዲያጥር ፡ የሚፈልጉ ፡ ብዙ ፡ አይመስሉኝም ። ድሮ ፡ ያል

ነበረ ምንድነው ፡ ብለው ፡ ጌታዬ ፡ ለጠየቁኝ ፡ የጉልት ፡ ስሪት ፡ ሁለት ፡ አይነት ፡ መሆኑን ፡ ጌታዬ ፡ ስለሚያውቁት ፡ እኔ ፡ አልነግርዎትም ። እኛ ፡ የምንኖርባቸው ፡ ሶስቱ ፡ ጉልቶችም ፡ ርስትጉልት ፡ ሳይሆን ፡ እንዲሁ ፡ ነጠላ ፡ ጉልቶች ፡ በመሆናቸው ፡ ባላገሮች ፡ ለባለጉልቶች ፡ የሚከፍሉት ፡ ገመታ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ያመት ፡ ሰብላቸውና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ገቢያቸው ፡ በሹም ፡ ተገምቶ ፡ በዚያ ፡ መሰረት ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ጉልተ ገዢዎች ፡ ቢፈልጉ ፡ በገንዘብ ፡ ፈንታ ፡ ባይነት ፡ ግብራቸውን ፡ ይወስዳሉ ። ከዚሀ ፡ ሌላ ፡ የምንከፍለው ፡ እዳ ፡ ጥንት ፡ ያልተሰራ ፡ ነው ። ሳንከፍል ፡ የቀረን ፡ እንደሆነ ፡ የምንታሰርበት ፡ መቀጫ ፡ የምንከፍልበት ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። አሁን ፡ በቅርቡ ፡ በታላቁ አባትዎ ፡ በፊታውራሪ ፡ በረሁን ፡ ጊዜ ፡ እንኩዋ ፡ አባቴና ሌሎቹ ፡ ዘመዶቼ ፡ የሚከፍሉት ፡ ይህ ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ባመትባልና ፡ ባንዳንድ ፡ የደስታ ፡ ወይም ፡ የመከራ ፡ ጊዜ ፡ ዘመዶቻችን ፡ እንኩዋን ፡ አደረሰዎ ፡ እንኩዋን ፡ ደስ ፡ አለዎ ፡ ወይም ፡ እግዚአብሄር ፡ ያጥናዎ ፡ ለማለት ፡ ወደ ፡ ጌቶቻቸው ፡ ሲመጡ ፡ ባዶ እጃቸውን ፡ መጥተው ፡ በልተውና ፡ ጠጥተው ፡ መሄዱ ፡ እየከበዳቸው ፡ የገንትን ፡ ማር ፡ ይሁን ቅቤ ፡ ፍሪዳ ፡ ይሁን ፡ ሙክት ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ያበረክታሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ መጥቶ ፡ ማየቱም ፡ ሆነ ፡ በረከት ፡ መስጠቱ ፡ የበጎ ፡ ፈቃድና ፡ በመልካምም ፡ ቢሆን ፡ በክፉ ፡ ጊዜ ፡ በገገርና ፡ በተገገር ፡ መሀከል ፡ መተሳሰብ ፡ ለመኖሩ ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ ምሳሌ ፡ ነውንጂ ፡ እዳ ፡ አይደለም።

አሁን ፡ ዘመኑም ፡ ሰዎችም ፡ ተለውጡና ፡ ልማዱም ፡ ተለወጠ ። ለበጎ ፡ ፈቃድ ፡ ላንድነትና ፡ ለወዳጅነት ፡ መግለጫ ፡ ተብሎ ፡ ይሰጥ ፡ የነበረው ፡ በረከትም ፡ በግድ ፡ የሚከፈል ፡ እዳ ፡ ሆነ ። ረዥም ፡ እድሜ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያሳየል !” አሉ ፡ ሽማግሌው ፡ ባላገር ፡ ባዘን ፡ በተሰበረ ፡ ድምጽ ።

“ እንዲያው ፡ ባጭሩ ፡ ያመትባል ፡ መዋያ ፡ አልተሰራብንምና ፡ አንከፍልም ፡ ነው ፡ የምትለው ! አይደለም ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አይናቸው ፡ መቅላት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡

ስራቸው ፡ ሁሉ ፡ ግትርትር ፡ ብሎ ።

" አዎን ! ያልተሰራብንን ፡ እዳ ፡ እንከፍልም ፡ ነው ፡ የምንል ! ሲሆን ፡ ሲሆን ፡ ጌታችን ፡ ደጃዝማችዎን ፡ ገፍተው ፡ መሸሻ ፡ በሊበን ፡ ገደል ፡ ባያደርሱን ፡ መልካም ፡ ነበር ። ይህ ፡ ከፋ ፡ ጊዜ ፡ እስኪያልፍልን ፡ ቢታገሱን ፡ መልካም ፡ ነበር ። ከጨከኑብንና ፡ ካስገደዱን ፡ ግን ፡ ያለዳችን ፡ እንከፍልም ፡ ነው ፡ የምንል ! " አሉ ፡ ሽማግሌው ፡ ባዘን ፡ ፈንታ ፡ ድፍረትና ፡ ደስታ ፡ ልባቸውን ፡ ሲያሞቀው ፡ ጸዳሉ ፡ በተዋበ ፡ የሽማግሌ ፡ ፊታቸው ፡ ወገግ ፡ ብሎ ፡ እየታየ ።

"ዝም ፡ ይበሉ ፡ እስዎ ! ምን ፡ ያሉ ፡ የሽማግሌ ፡ ሀፍረ ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ፡ እባክዎ ? እዚህ ፡ ጠብ ፡ ለመፍጠር ፡ የሰይጣን ፡ መላክተኛ ፡ ሆነው ፡ ነው ፡ የመጡት ? " አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ፊታውራሪ ፡ በጣም ፡ ሲቆጡ ፡ ሰላዩ ።

" ምነው ፡ አባቴ ፡ ሃሰት ፡ ተናገርሁ ? " አሉ ፡ ሽማግሌው ።

" ሃሰት ፡ ባይናገሩም ፡ ድፍረትዎና ፡ ንግግርዎ ፡ የሽማግሌ ፡ ንግግር ፡ አይደለም ! "

"ሀእ ! እሰት ፡ ባይናገሩም ! የትኛው ፡ ነው ፡ ከተናገረው ፡ እውነቱ ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የንስሀ ፡ አባታቸውን ፡ በቁጣ ፡ እየተመለከቱ ።

" በተናገሩትማ ፡ ምን ፡ እውነት ፡ አለ ? ብቻ ፡ ከሁሉም ፡ ድፍረታቸው ፡ ይብሳል ፡ ማለቴ ፡ ነውንጂ !"

"እኔ ፡ እውነቱን ፡ ለመናገር ፡ ያልደፈርሁ ፡ ማን ፡ ይደፍር ፡ አባቴ ? ያሰብሁት ፡ ቅን ፡ አሳብ ፡ የሰራሁት ፡ መልካም ፡ ስራና ፡ የተናገርሁት ፡ እውነት ፡ በሚቆጠርበት ፡ አለም ፡ የምሄድበትን ፡ ቀን ፡ የምጠባበቅ ፡ የዚህን ፡ አለም ፡ ኑሮ ፡ ጨርሼ ፡ የወዲያኛ ውን ፡ አለም ፡ ኑሮ ፡ ለመጀመር ፡ የምሰናዳ ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝ ። እኔ ፡ እውነት ፡ ለመናገር ፡ ያልደፈርሁ ፡ ማን ፡ ይደፍር ?"

"አንተ ፡ በየትኛው ፡ ጉልት ፡ የሚኖሩ ፡ ባላገሮች ፡ ወኪል ፡ ነህ ?"አሉ ፡ ፊታውራሪ ።-

"የጉሊት ፡ ባላገሮች ፡ ወኪል ፡ ናቸው ።" አሉ ፡ ብላታ ፡ መንግስቱ ፡ ዘላለም ።

"እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ያልኸው ፡ ሁሉ ፡ የጉሊት ፡ ህዝብ ፡

የላከህ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ?"

"አዎን ።" አሉ ፡ ሽማግሌው ።

" እንግዲህ ፡ የጉሊት ፡ ህዝብ ፡ ሸፍቶዋል ፡ ማለት ፡ ነዋ !"

"አልሸፈተም ። ጾኑ ፡ ችግር ፡ ደርሶብናልና ፡ ጥንት ፡ እዳ ፡ ሆኖ ፡ ያልተሰራብን ፡ ይቅርልን ፡ ብሎ ፡ ለማኝ ፡ መላኩ ፡ ነው ፡ ላኩ ፡ እንጂ ፡ አልሸፈተም ።"

"እንተ ፡ ሁላችሁም ፡ የምትሉት ፡ ይሄው ፡ ነው ? እናንተ ንም ፡ የላኩዋችሁ ፡ እንደ ፡ ጉሊቶች ፡ ሸፍተዋል ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገዥም ፡ ብለው ፡ ይሰሙ ፡ ወደነበሩት ፡ ሁለት ፡ ባላገሮች ፡ እያዩ ።

"እህላችንን ፡ ትል - በረድ ፡ ከብታችንን ፡ ወረርሽኝ ፡ ስላ ጠፋብን ፡ በዚህ ፡ አመት ፡ መክፈል ፡ አንችልምና ፡ ጌታችን ፡ ምህረት ፡ ያድርጉልን ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ አገር ፡ የላከን ። ወዲያውም ፡ ያመትባል ፡ መዋያ -------- ጥንት ፡ ያልተሰራብን ፡ ነውና ፡ አን ከፍልም ፡ ብሎዋል ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ።" አለ ፡ ሁለተ ኛው ፡ ባላገር ፡ ትንሽ ፡ እያመነታ ። "እንዲህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ሲደ ርስብን ፡ ሲሆን ፡ ጌታችን ፡ የተሰራብንን ፡ እዳም ፡ ሊምሩን ፡ ይገባ ፡ ነበር ፡ ይህም ፡ ካልሆነ ፡ ያልተሰራብንን ፡ እዳ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አንከፍልምና ፡ ይህን ፡ ለጌታችን ፡ ንገሩ ፡ ተብለናል ፡" አለ ፡ ሶስተኛው ፡ ባላገር ።

"ሶስቱንም ፡ ያገዛና ፡ በግር ፡ ብረት ፡ አሰራቸው !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በጾኑ ፡ ቁጣ ።

"እስቲ ፡ መታሰራቸው ፡ ይቆይና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡ እውጭ ፡ ሆነው ፡ በነገሩ ፡ እኛ ፡ ትንሽ ፡ እንነጋገርበት ።" አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ።

"ገዥም ፡ በል ፡ አባክህ ! ይህ ፡ ሁሉ ፡ ያንተ ፡ ስራ ፡ ነው ! ብቻ ፡ ግዴለም ፡ እግዚአብሄር ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ በሰማይ ፡ ያፋራር ደናል ! ውሰድና ፡ አሰራቸው ።" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደተቆጡ።

"ግዴለም ፡ አሁን ፡ አትስራቸው ፡ እንዲሁ ፡ ስታስጠብቃ ቸው ፡ ቆይ ።" አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ አጋፋሪው ፡ ባላገሮ ችን ፡ እየገፋ ፡ ሲያስወጣቸው ። ፊታውራሪ ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ መጨረሻ ፡ ላጋፋሪው ፡ ያሉትን ፡ ቢሰሙ ፡

ሰጊዜው ፡ ዝም ፡ አሉ ፡፡

"እየው ፡ አንተ ፡ የምትሰራው ፡ ስራ ፡ የሚያስከትለውን !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉን ፡ በቁጣ ፡ አይን ፡ እያዩ ፡፡ "ባላገርና ፡ ወይፈን ፡ ከባድ ፡ ዛዝላ ፡ ካልጫኑበት ፡ ልክ ፡ አይገባም ፡ ብልህ ፡ የሰው ፡ ባላገርን ፡ መግዛት ፡ ባላገር ፡ መስሎ ፡ነው ፡ እያልህ ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ በባላገር ፡ ተራ ፡ አቁመህ ፡ አሳይተኸን ፡ የነሱ ፡ ጉዋደኞች ፡ አድርገኸን ፡ አሁን ፡ ፍቁንና ፡ ግብር ፡ እንከፍልም ፡ አሉን ፡፡"

"የሰው ፡ ጌታየ ፡ እኔ ፡ የሰራሁት ፡ አይደሰም ፡ ዛሬ ፡ የደረሰውን ፡ ያደረሱ፡፡ ዛሬ ፡ የደረሰው ፡ የደረሰ ፡ እኔ ፡ የምሰው ፡ ባሰ ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ርስተ ፡ ጉልትዎን ፡ እኔ ፡ እንዳስተዳድርልዎ ፡ አደራውን ፡ በኔ ፡ ከጣሉ ፡ በሁዋላ ፡ በጎን ፡ አሽከር ፡ መላክና ፡ ከባላገር ፡ ጋር ፡ መጣላት ፡ ባላስፈሰገ ፡ ነበር ፡፡ ከዛሬ ፡ ቀደም ፡ ይህን ፡ የመሰሰ ፡ ነገር ፡ ስንፈልግ ፡ ይህን ፡ የመሰሰ ፡ ችግር ፡ ደርሶ ፡ አሰማወቁ ፡ እኔ ፡ የምሰው ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ እንጂ ፡ አሰት ፡ መሆኑን ፡ አያስረዳም ፡፡ ብቻ ፡ ሰጊዜው ፡ ይህን ፡ እንተወው ፡፡ የገዛ ፡ ጉልትዎን ፡ የፈሰጉት ፡ ሰው ፡ እንዲያስተዳድርልዎ ፡ መምረጥ ፡ ይችላሉ ፡፡ አሁን ፡ አይነተኛው ፡ ነገር ፡ እነዚህ ፡ ባላገሮች ፡ የታሰሩ ፡ እንደሆነ ፡ ሁሰተኛ ፡ ወደነዚህ ፡ ሶስት ፡ ጉልቶች ፡ ሰው ፡ መላክም ፡ ከነሱ ፡ ግብር ፡ ማግኘትም ፡ አይችሉም ፡ ማሰት ፡ ነው ፡፡"

"በምን ፡ ምክንያት ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡

"ይወጉዎታል ፡ ጦርነት ፡ ይሆናል ፡፡ ጦርነት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነም ፡ በደሰኛ ፡ የሚባሉ ፡ እሰዎ ፡ ይሆናሉ ፡፡"

"ባላገር ፡ እኔን ፡ አሸንፋሰሁ ፡ ብሎ ፡ አስቦ ፡ ጦርነት ፡ ያነሳል ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡፡

"ባላገር ፡ አገሩ ፡ ውስጥ ፡ ካደመ ፡ ማነን ፡ አያሸንፍም ?"

"ባላገር ፡ አድሞ ፡ ማነን ፡ አሸንፎ ፡ ያውቃል ? ባላገር ፡ ደካማ ፡ አይወድም ፡ ባላገር ፡ ብርቱ ፡ ይወዳል ፡፡ በባላገር ፡ ላይ ፡ እጅህን ፡ ማጠንከር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ያሰብህ ፡፡ እጅህ ፡ ከጠነከረ ፡ ባላገር ፡ ታልቦ ፡ አያፈጅም ፡ ጋንህ ፡ እስኪሞላ ፡ ልታልበው ፡ ትችላሰህ ! ባላገር ፡ ያሰቅሳል ፡ ያማርራል ፡ ፊሪ ፡ ካገኘም ፡ ያስ

ፈራራል ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቆራጥና ፡ ደፋር ፡ ካጋጠመው ፡ በመጨ ረሻ ፡ ይሸነፋል ፡፡ በመጨረሻ ፡ የተጠዬቀውን ፡ ይከፍላል ፡፡ ባላ ገር ፡ ቆራጥም ፡ ደሀም ፡ ሆኖ ፡ አያውቅም ፡፡ ባላገር ፡ ምንም ፡ ቢበዛ ፡ ብዙ ፡ የሚወደውና ፡ የሚያስበው ፡ ነገር ፡ ስላሰው ፡ ደፍሮ ፡ አይዋጋም ፡፡ ባላገር ፡ የሚበላው ፡ ቢያጣ ፡ ይከፍለው ፡ አጥቶ ፡ አያውቅም ፡ ይባላል ፡ እስከ ፡ ተረቱ ! " አሉ ፡ ፊታው ራሪ ፡፡

" ባላገር ፡ አድሞ ፡ ማነን ፡ አሸንፎ ፡ ያውቃል ፡ ላሉት ፡ ሩቅ ፡ ሳንሄድ ፡ በስምና ፡ በኔ ፡ እድሜ ፡ እነደጃች ፡ ሽበሽን ፡ እነ ደጃች ፡ ካሳን ፡ እነፊታውራሪ ፡ ይልማ ፡ ተክሉን ፡ ድል ፡ እያደ ረገ ፡ አስሮ ፡ ያገር ፡ ሁሉ ፡ መሳቂያ ፡ አድርጎዋቸው ፡ እንደቀረ ፡ ራስዎ ፡ ያውቃሉ ፡፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ባላገር ፡ እስዎ ፡ እንደሚሉት ፡ አይደለም ፡፡ ባላገር ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ ታጋሽ ፡ ነው ፡፡ ልክ ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ እስኪሰለቸው ፡ ይታረሳል ፤ ይቆፈራል ፤ ይረገ ጣል ፡፡ መሬት ፡ ሲሰለቸው ፡ ሲበቃው ፡ ቢያርሱትም ፥ ቢቆፍሩ ትም ፡ አላበቅልም ፡ አላፈራም ፡ እንደሚል ፤ ባላገርም ፡ ሲሰለ ቸው ፡ ሲበቃው ፡ እንቢ ፡ አልከፍልም ፡ ይላል ! ከዚያ ፡ በሁ ዋላ ፡ ባላገርን ፡ ሊያስገድድ ፡ የሚችል ፡ ሀይል ፡ ከሰማይ ፡ እን ደሆን ፡ እንጂ ፡ ከምድር ፡ አይገኝም ፡፡ ስለዚህ ፡ እኔ ፡ የምመክ ርዎ ፡ እነዚህን ፡ ባላገሮች ፡ ለቀዋቸው ፡ ወደያገራቸው ፡ እንዲሄ ዱና ፡ ነገሩ ፡ እንዲበርድ ፡ ነው ፡፡ አሁን ፡ የተፋፋመው ፡ መጥፎ ፡ ስሜትና ፡ እልክ ፡ ሲቀዘቅዝ ፡ ባላገሩን ፡ በዘዴ ፡ ከቀረቡት ፡ የቀ ረብዎትን ፡ በጥፍ ፡ ያገኙታል ፡፡" አሉ ፡ ቀኛዝማች፡፡

"ቀድሞ ፡ ጌቶች ፡ ባላገርንና ፡ ወይፈንን ፡ አነጣጥረው ፡ የሰጡት ፡ ምሳሌ ፡ የማይገኝ ፡ ትክክለኛ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡፡ ወይ ፈን ፡ ዛዝላ ፡ እንጫንብህ ፡ ሲሉት ፡ እንቢ ፡ በማለቱ ፡ የተሰቀቀ ፡ እንደሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ አንገቱን ፡ አያስነካም ፡፡ አሁንም ፡ እነዚህ ፡ ባላገሮች ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የድፍረት ፡ ንግግር ፡ ተናግረው ፡ የተ ሰመደ ፡ እዳቸውን ፡ አንከፍልም ፡ በማለታቸው ፡ የተለቀቁ ፡ እንደሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ ግብር ፡ ከፈሉ ፡ ብሎ ፡ እደጃቸው ፡ የሚ ሄድ ፡ ሰው ፡ የለም ! " አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ የፊታውራሪን ፡ አይን ፡ እዬተመለከቱ ፡፡

"የሰዎ ፡ ጌታዬ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ የሰጠው ፡ አሳብ ፡ ማለፊያ ፡ ነው ። እኒህን ፡ ሶስት ፡ ባላገሮች ፡ መክሮ ፡ አለዝቦ ፡ መልቀቅ ፡ ነው ፡ የሚሻለው ። ባላገሩ ፡ ክፉ ፡ አስቦዋል ፡ ሹሙም ፡ አለመናገሩ ፡ ፈርቶ ፡ ወይም ፡ አድማውን ፡ ከባላገሩ ፡ ጋር ፡ አድርጎ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ የሆነ ፡ ነገር —እሺ ፡ " አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ።

"ምንድነው ፡ የሚሆነው ፡ ነገር ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በንቀት ፡ መልክ ።

"ትናንት ፡ እዚያ ፡ በርበርማ ፡ በሚባለው ፡ ጉልቴ ፡ ደርሼ ፡ ስመለስ ፡ በመንገድ ፡ ብዙ ፡ ባለጠመንጃም ፡ ባለጦርና ፡ ጋሻም ፡ ህዝብ ፡ "አመልማል ፡ ጉሜ ፡ " እያለ ፡ እየተራበሸ ፡ ሲሄድ ፡ አዩሁና ፡ ምንድነው ፡ ብዬ ፡ ብጠይቅ ፡ የጉሊት ፡ የናሞራና ፡ የጐርጐር ፡ ህዝብ ፡ ጉሊት ፡ ላይ ፡ ተሰብስቦ ፡ ሲመክር ፡ ውሎ ፡ በመጨረሻ ፡ አበጀ ፡ በለው ፡ የሚባለውን ፡ ድሮ ፡ ጐንቻ ፡ ሽፍቶ ፡ ይኖር ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ የጐበዝ ፡ አለቃ ፡ አድርጎ ፡ ሾሞ ፡ መለያየቱንና ፡ በመንገድ ፡ ያዩሁት ፡ ብዙ ፡ ሰራዊት ፡ ከስብሰባው ፡ የሚመለስ ፡ የናሞራ ፡ ህዝብ ፡ መሆኑን ፡ ሰማሁ ። ብቻ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሽፍታ ፡ ለማደን ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እኛን ፡ ለመቃወም ፡ መሆኑን ፡ አሁን ፡ እዚህ ፡ በነዚህ ፡ አገሮችና ፡ በኛ ፡ መሀከል ፡ የተፈጠረውን ፡ ችግር ፡ እስከለማ ፡ ድረስ ፡ አላወቅሁም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ እንደማየው ፡ ባላገሮች ፡ ታጥቀው ፡ የተነሱ ፡ መሆናቸው ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ ነገሩ ፡ የሚበርድበትን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ።" አሉ ፡ ባላምባራስ ።

"እኮ ፡ አንተና ፡ ቀኛዝማች ፡ የምትሉት ፡ ከባላገር ፡ ጋር ፡ ከመጣላት ፡ እያት ፡ ቅድመአያቶችህ ፡ ያቆዩህን ፡ ጉልቶች ፡ ልቀቅ ፡ ነው ! አይደለም ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቁጣ ።

"እውነት ፡ እንነጋገር ፡ ካልን ፡ ላያት ፡ ቅደማያቶችዎም ፡ ይሁን ፡ ለሰዎ ፡ የተሰረላችሁ ፡ ገመታ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ገመታ ፡ ባላገሮች ፡ እንከፍልም ፡ አላሉም ። አሁን ፡ ጭቅጭቁ ፡ የተነሳው ፡ ባመትባል ፡ መዋያ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክናያት ፡ ጦርነት ፡ ቢነሳ ፡ መጀመሪያ ፡ ባላገር ፡ ያዋርደናል ፡ ሁለተኛ ፡ ይንቨናል ፡ በማ

ንለው ፡ ነገር ፡ ጦርነት ፡ ሰናንሳ ፡ በደለኞች ፡ ሆነን ፡ እንገኛ ለን ፡ ነው ፡ የምንለው ። ” አሉ ፡ ቀኛዝማች ።

“ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ለባላገር ፡ አላጐነብስም ፡ ሶስቱንም ፡ እግር ፡ ከወርች ፡ አሰርልኝ ፡ እስቲ ፡ ባላገር ፡ የሚያደርገውን ፡ አያለሁ ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደተቀመጡ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተንቆራጠጡ ።

“ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ባሳብዎ ፡ በሙሉ ፡ ባልስማማ ፡ ዛሬ ፡ ወደድሁዎ ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ መል ካም ፡ አስተያየት ፡ ያለዎ ፡ መሆንዎን ፡ አላውቅም ፡ ነበር ። ጳጳስ ፡ ብሆን ፡ ኖሮ ፡ ያባ ፡ ሞገሴን ፡ ስልጣን ፡ ገፍፌ ፡ ለስዎ ፡ ሰጥቼ ፡ ለፊታውራሪ ፡ የንስሀ ፡ አባት ፡ አደርግዎ ፡ ነበር ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እየሳቀ ።

“እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ ብቻ ፡ አሁን ፡ የያዝነው ፡ ጨዋታ ፡ አይደለም ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነውና ፡ ዝም ፡ በል ፡ አባ ክህ ! ” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ።

“ የለም ፡ እኔም ፡ የተናገርሁት ፡ ቁምነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቀልድ ፡ አይደለም ። መቸም ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደምታውቁዋ ቸው ፡ አካላቸው ፡ አድጎ ፡ ቢያረጅ ፡ አእምሮዋቸው ፡ ህጻን ፡ እንደሆነ ፡ የቀረ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ መሪ ፡ መካሪ ፡ አስተማሪ ፡ ሞግዚት ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ናቸው ። አባ ፡ ሞገሴ ፡ እንደምታውቁዋቸው ፡ የራሳቸው ፡ አሳብ ፡ የሌላቸው ፡ የሰውን ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ ካዩትና ፡ ከማንባሩ ፡ አይተው ፡ ለመ ተርጐም ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ሆዳቸውን ፡ የሞላ ፡ በፈለገው ፡ መንገድ ፡ የሚመራቸው ፡ ተግባራቸውን ፡ ለሆዳቸው ፡ የሸጡ ፡ የለወጡ ፡ ናቸው ። ታዲያ ፡ ጳጳስ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የኒህን ፡ ስል ጣን ፡ ገፍፎ ፡ ዛሬ ፡ እስዎ ፡ እንደሞከሩት ፡ በቅን ፡ መንገድ ፡ ለሚመራ ፡ ሞግዚት ፡ መስጠትና ፡ እሳቸውን ፡ የልፍኝ ፡ አሽ ከር ፡ ወይም ፡ የስራቤት ፡ አለቃ ፡ ማድረግ ፡ አይሻልም ? ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ። - ከዚያ ፡ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ሲስቁ ፡ ፊታው ራሪም ፡ ለጊዜው ፡ አብረው ፡ ሳቁና ፡

" እብድ ፡ እንዳይባል ፡ የሚናገረው ፡ መርዝ ፡ ነው ! ደህና ፡ እንዳይባል ፡ -----እንዲያውኮ ፡ የዲማውን ፡ የሱ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ያስቸግራል ! እስቲ ፡ አሁን ፡ ማን ፡ ጠይቆህ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የምትዘባርቀው ? " አሉ ፡ ወደ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እዩተመለከቱ ።

"ብጠዩቅም ፡ ባልጠዩቅም ፡ የተናገርሁት ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ፊታውራሪ ፡ እሰዎ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይና ፡ በሌላ ፡ አለም ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰው ፡ ስለሆኑ ፡ ደህና ፡ መሪ ፡ ያስፈልግዎታል ። ለምሳሌ ፡- ከዛሬ ፡ አራት ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ሞተው ፡ አጥንታቸው ፡ ወዳፈር ፡ አፈሩ ፡ ወደ ፡ ድንጋይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከተለዋወጠ ፡ በሁዋላ ፡ እናጼ ፡ ዘርአ ፡ ያእቆብን ፡ እናጼ ፡ ልብነድንግልን ፡ አላሳርፍ ፡ ብለው ፡ ገና ፡ በህይወታቸው ፡ እንዳሉና ፡ እሰዎን ፡ በቀጥታ ፡ እንደ ፡ ወለዱዎ ፡ ሁሉ ፡ አባቶቼ ፡ እያሉ ፡ ከንቱ ፡ የሆነ ፡ ምኞትዎ ፡ ሲሞላ ፡ እነሱን ፡ ደስ ፡ እንደሚላቸው ፡ ሲጐድል ፡ እነሱ ፡ እንደሚያዝኑና ፡ እንደተጠቁ ፡ እዩቆጠሩ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ በነሱ ፡ አለም ፡ የሚኖሩ ፡ ነዎ ። ከናጼ ፡ ዘርአ ፡ ያእቆብ ፡ የሚወረስ ፡ ደም ፡ ቢኖር ፡ በዚህ ፡ አራትና ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ በስንቱ ፡ ሰው ፡ የደም ፡ ስር ፡ ውስጥ ፡ ተተንትኖ ፡ ቀጥኖ ፡ ቀጥኖ ፡ ጠፍተዋል ። አጼ ፡ ዘርአ ፡ ያእቆብ ፡ በሞቱ ፡ ባምስት ፡ መቶ ፡ ዘመናቸው ፡ የሰዎ ፡ አባት ፡ የሚሆኑ ፡ ዘሆነ ፡ እንደሰዎ ፡ ወደላይ ፡ ቆጥሮ ፡ የሳቸውን ፡ አባትነት ፡ የሚካፈል ፡ ስንት ፡ ደሀ ፡ ገበሬ ፡ ስንት ፡ ደሀ ፡ ነጋዴ ፡ ስንት ፡ ደሀ ፡ ካህን ፡ እኔ ፡ ጭምር ፡ አለ ፡ ይመስልዎታል ! ይህ ፡ እንኳዋ ፡ የሰዎን ፡ ከንቱነት ፡ ለማስረዳት ፡ ያክል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ከተነሳው ፡ ችግር ፡ ጋር ፡ የተየያዘ ፡ አይደለም ። አሁን ፡ ለተነሳው ፡ ችግር ፡ ማስወገጃ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ያሉት ፡ ነው ። እኒህን ፡ ባላገሮች ፡ ይልቀቁዋቸው ። ያለዚያ ፡ ከሶስቱ ፡ ጉልቶችዎ ፡ አንዱ ፡ እፍኝ ፡ ባቄላ ፡ እንኳዋ ፡ አያገኙም ። በግድ ፡ አስገብራለሁ ፡ ብለው ፡ የሄዱ ፡ እንደሆነ ፡ ባላገር ፡ ደብድቦ ፡ ያስርዎታል ! " አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

" ባላገር ፡ ደብድቦ ፡ የሚያስረኝ ፡ ቆሜ ፡ ነው ፡ ሞቼ ? "

አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደ ተቆጡ ።

“ ይህ ፡ እሰዎ ፡ እንደፈለጉ ፡ ነው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ሄደው ፡ እጅዎን ፡ ከሰጡ ፡ ቆመው ፡ ያስርዎታል ፡ እዋጋለሁ ፡ ካሉም ፡ ገድሎ ፡ ያስርዎታል ! ” አሉ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እዬሳቀ ። የተሰበሰቡትም ፡ ሁሉ ፡ ሳቁ ። ፊታውራሪ ፡ ግን ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ንግግር ፡ ይልቅ ፡ ሌሎች ፡ በመሳቃቸው ፡ በጣም ፡ ተናደዱና ፡-

“ የሁላችሁም ፡ አሳብ ፡ እሱ ፡ እንደሚለው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ? ” አሉ ።

“ እኔ ፡ ባልሁት ፡ ሁሉ ፡ እንደማይስማሙ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ እነግርዎታለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዛሬ ፡ በተነሳው ፡ ችግር ፡ ብቻ ፡ ባላገሮች ፡ ካልተለቀቁ ፡ የከፋ ፡ ችግር ፡ እንደሚከተል ፡ ሁሉም ፡ ይስማማሉ !” አሉ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

“ አንተን ፡ አልጠዬቅሁህም ፡ እነሱን ፡ ነው ። ”

“ እነሱማ ፡ እንደ ፡ ህጻን ፡ በማይገባ ፡ እየተቅበጠበጡ ፡ ግራ ፡ እንዳያገቡዋቸው ፡ እውነቱን ፡ ደፍረው ፡ መንገር ፡ ግድ ፡ ካልሆነባቸው ፡ ይሰጋሉ ። እኔ ፡ ብቻ ፡ እብድ ፡ መባል ፡ ባይሆን ፡ ለዚህ ፡ ለዚህ ፡ ስለሚያገለግል ፡ እኔም ፡ ሌሎችም ፡ ስለሰዎ ፡ የምናስበውን ፡ ግልጥ ፡ አድርጌ ፡ እነግርዎታለሁ ።”

“ ዝም ፡ በል ፡ እባክህ ፡ አንተ ፡ እኛ ፡ ቁምነገሩን ፡ እንነጋገርበት ! ” ብለው ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ እደመቆጣት ፡ አሉና ፡ አዛዡ ፡ ደስታ ፡-

“ከባላገር ፡ ጋር ፡ መጣላት ፡ እግዚአብሄር ፡ አያርገውና ፡ ጥሉ ፡ ከጦ ፡ የምንዋጋ ፡ ብንሆን ፡- የተሸነፍን ፡ እንደሆን ፡ ውርደት ፡ ነው ። ብናሸንፍም ፡ ድሉ ፡ ከድል ፡ አይቆጠርም ። ደግሞ ፡ ጦርነት ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ከሶስቱ ፡ አገሮች ፡ ባላገር ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ የምንዋጋ ፡ እንዳይመስላችሁ ! በቅርብም ፡ በሩቅም ፡ ያለ ፡ ባላገር ፡ ሁሉ ፡ ይረዳዳብናል ። የባላገር ፡ አድማ ፡ ክፉ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እነዚህን ፡ ባላገሮች ፡ ..ቀቃቸውና ፡ ሌላ ፡ ዘዴ ፡ ብንፈልግ ፡ ይሻላል፡ ፊታውራሪ!” ፡ አሉ ።

“ በሉ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ሰማሁዋችሁ ! ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከህጻንነቴ ፡ ጀምሬ ፡ እስከሸምግልናዬ ፡ በግዛት ፡ ላይ ፡ የኖ

ርሁ ፡ ስለሆንሁ ፡ የባላገሩን ፡ አሞት ፡ ከናንተ ፡ ያነሰ ፡ የማውቅ ፡ አይምሰላችሁ ። እኔን ፡ አሸንፋለሁ ፡ ብሎ ፡ ጦርነት ፡ አያነሳም ። ጦርነት ፡ ባንሳ ፡ ቢል ፡ ግን ፡ የናንተን ፡ ርዳታ ፡ ሳልፈልግ ፡ እኔ ፡ ከነሽከሮቼ ፡ እዚታቀዋለሁ ! በል ፡ አንተ ፡ እነዚህን ፡ ባላገሮች ፡ ቅድም ፡ እንዳልሁት ፡ እግር ፡ ከሆሮች ፡ አስርልኝ ፡ ልብ ፡ አድርግ ፡ መጥቼ ፡ አያለሁ ! ” አለ ፡ ፊታውራሪ ፡ በብርቱ ፡ ቁጣ ፡ መንታ ፡ ቀንዳቸው ፡ በግንባራቸው ፡ ተገትሮ ።-

“ እስቲ ፡ ከመታሰራቸው ፡ በፊት ፡ ምናልባት ፡ ተመክረው ፡ እንደሆነ ፡ ተጠርተው ፡ ይጠየቁ ። ” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ።

“ እነሱን ፡ ማባበል ፡ የለብኝም ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

“ ማባበል ፡ አይደለምኮ ! እዳችሁን ፡ ካልከፈላችሁ ፡ መታሰራችሁ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እንንገራቸውና ፡ እንከፍላለን ፡ ቢሉ ፡ ይከፍላሉ ፤ ወይም ፡ የታመነ ፡ ዋስ ፡ ከዚህ ፡ ጠርተው ፡ ይሄዳሉ ፤ አንከፍልም ፡ ቢሉ ፡ መቸም ፡ ያው ፡------ መታሰራቸው ፡ ነው ። ” አሉ ፡ ቀኛዝማች ።

“ ደግ ፡ ነው ፡ ጥሩዋቸው ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደተቆጡ ።

“ እንግዲህ ፡ የሶስት ፡ ፍሪዳ ፡ ዋጋና ፡ የጌቶችን ፡ አሽከሮች ፡ አጉላልታችሁ ፡ ባዶጃቸውን ፡ በመስደዳችሁ ፡ መቀጮ ፡ ጭምር ፡ ካልከፈላችሁ ፡ ወይም ፡ ከፍሎ ፡ በሁዋላ ፡ ከናንተ ፡ የሚቀበል ፡ ደህና ፡ ዋስ ፡ ካልጠራችሁ ፡ የምትታሰሩ ፡ መሆናችሁን ፡ አውቃችሁዋል ? ” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ባላገሮች ፡ ተጠርተው ፡ እያደገደጉ ፡ ሲገቡ ።-

“ ጌታችን ፡ በምህረት ፡ አይን ፡ ካላዩን ፡ እንታሰራለን ፡ እንጂ ፡ የሌለንን ፡ ከየት ፡ አምጥተን ፡ እንከፍላለን ?” አሉ ፡ የጉሊቱ ፡ ሽማግሌ ።-

“ ይሄዋ ! በል ፡ መልሳቸው ። ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቁጣ ፡ የቀላ ፡ አይናቸው ፡ ከፊቱ ፡ በጥፍ ፡ ወጥቶ ።

“ እስቲ ፡ የሶስቱ ፡ ጉልቶች ፡ ይህም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የላከው ፡ ጦማር ፡ ይታይልን ።” አሉ ፡ ሽማግሌው ፡

እጋፋሪው ፡ ሲገፋቸው ፡ ቁልፍ ፡ ከሰለው ፡ እያጠባባቸው ፡ ኪስ ፡ ባደፈ ፡ እራፊ ፡ የተጠቀለለ ፡ ደብዳቤ ፡ እያወጡ ።

"እስካሁን ፡ ለምን ፡ ሸሽገው ፡ አቆዩት ? ያምጡ ፡ ወዲህ ፡ ምን ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ እባካችሁ ! " አሉ ፡ እባ ፡ ሞገሴ ፡ በባላገሮች ፡ ደብዳቤ ፡ ውስጥ ፡ ከተፈጠረው ፡ ችግር ፡ የሚያወጣ ፡ መንገድ ፡ እደሚገኝ ፡ አምነው ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ። ወረቀቱን ፡ ተቀብለው ፡ ሲያነቡ ፡ መጀመሪያ ፡ ፊታቸው ፡ በደስታ ፡ ወገግ ፡ ብሎ ፡ የነበረው ፡ ድምጻቸውን ፡ ሳያሰሙ ፡ እያነበቡ ፡ ወደግማሹ ፡ ሲደርሱና ፡ ከዚያም ፡ እስኪጨርሱ ፡ እንደ ፡ መጥቆርም ፡ እንደ ፡ መቀዋጠርም ፡ ሲል ፡ የተሰበሰበው ፡ ሁሉ ፡ ተመልክተው ፡ መልካም ፡ ወሬ ፡ የያዘ ፡ ወረቀት ፡ አለመሆኑን ፡ ገመቱ ።

" እስቲ ፡ ድምጽዎን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ያንብቡ ! ምንድነው ፡ የሚለው ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

" የተላከ ፡ ከጉሊት ፡ ከናሞራና ፡ ከጐርጐር ፡ ህዝብ ፡ ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ጌታችን ፡ ርእስ ፡ መኳዋንንት ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በረሁን ፡- እግዚአብሄር ፡ ሙሉ ፡ ጤናዎን ፡ እንዲሰጥልንና ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ የሚያዩበትን ፡ የአእምሮ ፡ ብርሃንዎን ፡ እንዳይቀንስብን ፡ ድሆችዎ ፡ እንጸልያለን ።

ጌታችን ፡ እንደሚያውቁት ፡ ጥንት ፡ ከተሰራብን ፡ የገመታ ፡ እዳ ፡ ሌላ ፡ እንዲሁ ፡ በትርፍ ፡ እህል ፡ ማር ፡ ቅቤ ፡ ለጌታችን ፡ እንጭናለን ፤ ዘመን ፡ ከተለወጠ ፡ ከመስከረም ፡ ወዲህ ፡ ከሶስቱ ፡ ጉልቶችም ፡ ላመትባል ፡ መዋያ ፡ ስድስት ፡ ፍሪዳ ፡ ነድተናል ! ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለቤት ፡ ስራና ፡ ላጥር ፡ ማጠር ፡ ዲማ ፡ እየተጠራን ፡ ስራችንን ፡ ፈትተን ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከምንገላላው ፡ ሌላ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለወረዳና ፡ ለምስለኔ ፡ ለጭቃሹም ፡ የምንከፍለው ፡ የገንዘብና ፡ የጉልበት ፡ እዳ ፡ አለብን ።

ለገዢዎቻችን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጥንት ፡ የተሰራብንንም ፡ ያልተሰራብንንም ፡ ካደረግን ፡ በሁዋላ ፡ እህላችንን ፡ አንበጣና ፡ ትል ፡ ሲበላው ፡ ከብታችንን ፡ ወረርሽኝ ፡ ሲፈጀው ፡ ቤት ፡ ንብረታችንን ፡ ሌባና ፡ ሽፍታ ፡ ሲዘርፈው ፡ ለኛ ፡ በማዘንና ፡ እኛን ፡ በመርዳት ፡ ፈንታ ፡ ችግራችንን ፡ ምክንያት ፡ አድርጋችሁ ፡ የተረፈንን ፡

መቀሚያ ፡ ዘዴ ፡ ትፈጥራላችሁ ። ለምሳሌ ፡ በሜካ ፡ የሚኖር ፡ ሽፍታ ፡ ሲዘርፈን ፡ ፈልጎ ፡ ይዞ ፡ በመቅጣትና ፡ እኛን ፡ በመጠበቅ ፡ ፈንታ ፡ ዘራፊውን ፡ ካላመጣችሁ ፡ መቀጫ ፡ ክፈሉ ፡ ትሉናላችሁ ፡ እህላችንን ፡ አንበጣና ፡ ትል ፡ በላብን ፡ ያልን ፡ እንደሆን ፡ አይቶ ፡ የሚመልስ ፡ ሰራዊት ፡ ትልኩና ፡ ለተራበና ፡ ለታረዘ ፡ ሰራዊታችሁ ፡ ገባሪ ፡ ታደርጉናላችሁ ። ከብታችንን ፡ በሽታ ፡ ሲፈጀው ፡ ይሄው ፡ ነው ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ተሸክመን ፡ ኖርን ። አሁን ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ከበደን ፤ አልቻልነም ። ከንግዱህ ፡ ወዲያ ፡ ጥንት ፡ የተሰራብነን ፡ እዳ ፡ ተበድረንም ፡ ይሁን ፡ ተቀድመን ፡ እንከፍላለን ። ከዚያ ፡ በላይ ፡ የምንከፍለው ፡ እዳ ፡ የለብንም ። ይህንም ፡ ለጌታችን ፡ የሚያስረዱ ፡ ከሶስቱ ፡ አገሮች ፡ ሶስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ መርጠን ፡ ልከናል ።

የላክናቸው ፡ መልክተኞች ፡ መልክታቸውን ፡ ካደረሱ ፡ በሁዋላ ፡ በደህና ፡ ይመለሳሉ ፡ ብለን ፡ እናምናለን ። ያለዚያ ፡ ፈረደ ፡ ተካልኝ ፡ ዘሪሁን ፡ ደስታ ፡ በቀለ ፡ የሚባሉት ፡ የጌታችን ፡ አሽከሮች ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ባንዳንድ ፡ ምክናያት ፡ እኛን ፡ ለመዝረፍ ፡ መጥተው ፡ እዚሁ ፡ ስለተገኙ ፡ የኛ ፡ ሰዎች ፡ በደህና ፡ እስኪመለሱ ፡ የክብር ፡ እንግዶቻችን ፡ አድርገን ፡ አቆይተናቸዋልና ፡ በኛ ፡ መልክተኞች ፡ የደረሰ ፡ በነሱም ፡ የሚደርስ ፡ መሆኑን ፡ ጌታችን ፡ አስቀድመው ፡ እንዲያውቁት ፡ እንለምናለን ።

ጌታችን ፡ ጀግንነትዎ ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ እኛን ፡ ድሆች ፡ ባላገሮችዎን ፡ ወግተው ፡ በሀይል ፡ ለማስገበር ፡ ያስቡ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ፊታውራሪ ፡ አይባሉ ፡ እንጂ ፡ በኛ ፡ በድሆች ፡ ባላገሮችዎ ፡ መሀከልም ፡ ብዙ ፡ ጀግኖች ፡ አሉ ። እነሱን ፡ ፊታውራሪ ፡ አድርገን ፡ እንቀበልዎታለን ። የሚያስከብርዎና ፡ የሚያስፈራዎ ፡ ስልጣንዎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስልጣንዎ ፡ ከሌለ ፡ ከመሀከላችን ፡ እንዳንዱ ፡ ደሀ ፡ ሽማግሌ ፡ መሆንዎን ፡ እናስታውስዎታለን ። ይህ ፡ የሚያስከብርዎ ፡ የሚያስፈራዎና ፡ ከኛ ፡ ልዩ ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳይዎ ፡ ስልጣን ፡ የኛን ፡ ህይወትና ፡ ንብረት ፡ ጥቅማችንን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ዋጋ ፡ ሆኖ ፡ የተሰጠዎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለኛ ፡ ማጥቂያ ፡ ለራስዎ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ መጠበቂያ ፡ እንዲሆን ፡

የተሰጠዎ ፡ አይደለም ። በንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ውለታ ፡ የተሰጠዎን ፡ ስልጣን ፡ ላመጽ ፡ መፈጸሚያ ፡ አያደርጉዋለሁ ፡ ካሉ ፡ ግን ፡ ስልጣንዎ ፡ የተመሰረተበትን ፡ ውለታ ፡ ራስዎ ፡ ማፍረስዎ ፡ ስለሆነና ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ እኛን ፡ ገባሬ ፡ የሚያደርገን ፡ ግዴታ ፡ እስዎን ፡ አስገባሪ ፡ የሚያደርገዎ ፡ መብት ፡ በመሀከላችን ፡ ሊኖር ፡ ስለማይችል ፡ ጌታችን ፡ ግብር ፡ አስገብራለሁ ፡ ብለው ፡ ሰው ፡ ቢልኩ ፡ ወይም ፡ ራስዎ ፡ ቢመጡ ፡ ለሀረሩ ፡ እንደመጣችሁብን ፡ ሽፍቶች ፡ ወይም ፡ ቀማኞች ፡ ቆጥረን ፡ ለንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሽፍቶችና ፡ ቀማኞች ፡ የሚገባውን ፡ ቅጣት ፡ ልንፈጽምባችሁ ፡ የታጠቅን ፡ መሆናችንን ፡ እንዲያውቁልን ፡ በትህትና ፡ እንለምናለን ።

በናሞራ ፡ በጉሊትና ፡ በጉርጉር ፡ ህዝብ ፡ የጉበዝ ፡ አለቃ ፡
ሆኖ ፡ የተሾመ ፡ አሽከርዎ ፡ አበጀ ፡ በለው ።”

የባላገሮች ፡ ደብዳቤ ፡ ተነቦ ፡ ሲያልቅ ፡ ፊታውራሪ ፡ በውስጣቸው ፡ ቂጣና ፡ ስጋት ፡ ተደባልቀው ፡ የፈጠሩትን ፡ ስሜት ፡ የሚገልጹበት ፡ ቋንቋ ፡ አጥተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆይተው ፡

“ባላገር ፡ የተሰራበትን ፡ ግብር ፡ አልከፍልም ፡ ብሎ ፡ ሸፈተብን ፡ ማለት ፡ አይደለም ? ግድየለም ፡ እኔ ፡ መሸሻ ፡ እኔ ፡ የደፋር ፡ ጌታ ፡ አሳዩዋለሁ !” አሉ ፡ እንደተቀመጡ ፡ ግራቀኝ ፡ እየተንቆራጠጡ ።

“ብላታ ፡ መንግሥቱንም ፡ ሽማግሎችንም ፡ አስይዘህ ፡ እውጭ ፡ አቆያቸው ።” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ እዚያ ፡ ቆሞ ፡ የጌታውን ፡ ትእዛዝ ፡ የሚጠባበቀውን ፡ አጋፋሪ ። ከዚያ ፡ አጋፋሪው ፡ ባላገሮችንና ፡ ሽማቾውን ፡ እየነዳ ፡ ሲወጣ ፡ “ጌታዬ ፡” አሉ ፡ ቀጠሉና ። “የተደረገው ፡ ስህተት ፡ መሆኑን ፡ ቅድም ፡ ተናግሬያለሁ ። ብቻ ፡ ባለፈ ፡ ነገር ፡ እኔ ፡ እስዎን ፡ እስዎ ፡ እኔን ፡ ብንወቃቀስ ፡ ለምንም ፡ አይረዳምና ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚሻል ፡ እንነጋገር ።”

“ግብር ፡ አስገብራለሁ ፡ ብለህ ፡ የመጣህ ፡ እንደሆነ ፡ እንወጋሃለን ፡ ብሎ ፡ ሰደበ ፡ ልክብኛል ፡ ባላገር ፡ ሃይ ፡ ሲወጋኝ ፡ አያለሁዋ ! ሌላ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ? ባላገር ፡ ስላስፈራራኝ ፡ መልካም ፡ አባት ፡ ያቆዩኝን ፡ ጉልቴን ፡ እለቃለሁ ? ባላ

ገር ፡ አዋርዶኝ ፡ ጉሮሮየ ፡ እህል ፡ ይውጥልኛል ? እንቅልፍ ፡ ይወስደኛል ?” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በብርቱ ፡ ቁጣ ።

“ወደ ፡ ጥል ፡ ከሚመራ ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ መሸሽ ፡ ዘዴ ፡ አዋቂ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ አያዋርድም ! የሚያዋርደው ፡ ጥል ፡ ከተነሳ ፡ በኋላ ፡ መሸሽ ፡ ወይም ፡ በተነሳው ፡ ጥል ፡ ድል ፡ መሆን ፡ ነው !” አሉ ፡ ቀኛዝማች ።

“እኔ ፡ መሸሻ ፡ ጥል ፡ ከተነሳ ፡ ለባላገር ፡ ነው ፡ የምሸሸው ? ወይስ ፡ ባላገር ፡ ነው ፡ ድል ፡ የሚያደርገኝ ? ባላገር ፡ ይገድለኝ ፡ ይሆናል ፤ ነፍስና ፡ ስጋየ ፡ አብረው ፡ እያሉ ፡ ግን ፡ ለባላገር ፡ መሸሽና ፡ ድል ፡ መሆን ፡ አይታሰብም ፤ ባታውቀኝ ፡ ነው !”

“እንኩዋን ፡ እኔ ፡ በቅርብዎ ፡ ያለሁ ፡ ወንድምዎ ፡ በሩቅ ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቅዎ ፡ ጀግና ፡ ነዎ ። ብቻ ፡ ከባላገር ፡ ጋር ፡ መጣላት ፡ ጀግንነት ፡ አይደለም ፤ ቢያሸንፉ ፡ አያኮሩም ፤ ቢሸነፉ ፡ ያዋርዳል !” ብለው ፡ ቀኛዝማች ፡ እካሉ ፡ ለፊታውራሪ ፡ ጀግንነት ፡ ምስክርነታቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቁጣ ፡ ሻክሮ ፡ የነበረ ፡ ልባቸው ፡ እንደ ፡ መለስለስ ፡ ሲል ፡ በፊታቸው ፡ ታዬ ።

“ባላገር ፡” አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ቀኛዝማች ፡ “ባላገር ፡ ምንም ፡ ቢበዛ ፡ እንደሚያሸንፍ ፡ እንኩዋ ፡ ቢያውቅ ፡ ህይወቱንም ፡ ጥይቱንም ፡ ቆጥቦ ፡ ነው ፡ የሚዋጋ ። ጠላቱ ፡ እሱን ፡ በመፈለግና ፡ በራብ ፡ በጥም ፡ እስኪያክም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተሰልፎ ፡ አይገጥምም ። ባገሩ ፡ እህል ፡ ወሀው ፡ የሱ ፡ ስለሆነ ፡ ዱር ፡ ገደሉ ፡ ተራራው ፡ ሸንተረሩ ፡ ሁሉም ፡ የሱ ፡ ስለሆነ ፡ እህል ፡ ውሀውን ፡ ሸሽጎ ፡ እሱ ፡ በዱር ፡ በገደሉ ፡ ተሸሽጎ ፡ ጠላቱን ፡ በራብና ፡ በጥም ፡ በፍለጋ ፡ አድክሞ ፡ በመጨረሻ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሳይሞትበት ፡ ብዙ ፡ ጥይት ፡ እንኩዋ ፡ ሳይጠፋበት ፡ ድል ፡ ያደርጋል ። ይህ ፡ በባለብዙ ፡ ሰራዊት ፡ ታላላቅ ፡ መኩዋንንት ፡ የደረሰ ፡ መሆኑን ፡ እስዎ ፡ ራስዎ ፡ ያውቃሉ ። ያዶመ ፡ ባላገር ፡ አሸንፋለሁ ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ ውቅያኖስን ፡ ጠልቄ ፡ እጨርሳለሁ ፡ እንደማለት ፡ ነው ! ስለዚህ ፡ እኔ ፡ አጥብቄ ፡ የምለምንዎ ፡ ነገሩ ፡ አሁን ፡ ከደረሰበት ፡ አስጊ ፡ ሁኔታ ፡ ሳያልፍ ፡ ለኔ ፡ እንዲተውልኝና ፡ እኔ ፡ በሰላም ፡ እንድጨርሰው ፡ ነው ። በዚህ ፡

ወንድሞቻችን ፡ ሁሉ ፡ እንደሚስማሙ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ።"
አለ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ባይናቸው ፡ አዙረው ፡ ገርፈው ።

"ከሁሉም ፡ የተሻለ ፡ ይሄው ፡ ነው ፡ ቀኛዝማች ፡ ይጨርሱ !" አሉ ፡ አባገር ፡ ደስታ ።

"አዎ ፡ ቀኛዝማች ፡ ይጨርሱት ! ይሻላል ! ጥሩ ፡ ነው !" አሉ ፡ እዚያ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ተንሜጉተው ።

"ወይ ፡ጉድ ! አሽከሮቼ ፡ ተያዘው ፡ እንዲያ ፡ ያለ ፡ የዘለፋ ፡ ወረቀት ፡ ተጽፎልኝ ፡ እንደዒት ፡ አድርጌ ፡ ነው ፡ ቀኛዝማች ፡ በሰላም ፡ የሚጨርሰው ? ግብር ፡ ላላስገብር ፡ ባላገር፦ አልገብርም ፡ ሲል ፡ አስገባሪ ፡ ሹም ፡ ላልልክ ፡ ውል ፡ ገብቼ ፡ ነው ፡ ቀኛዝማች ፡ በሰላም የሚጨርሰው ?

"አሽከሮችዎ ፡ ሳይያዙ ፡ ጥቅምዎም ፡ ክብርዎም ፡ ሳይነካ ፡ ነገሩን ፡ በሰላም ፡ እጨርሰዋለሁ ፡ ብቻ ፡ መልክተኞች ፡ ሆነው ፡ የመጡትን ፡ ሽማግሎች ፡ ይ ልቀቁዋቸው ። እንክዋን ፡ እንደሰዎ ፡ ያለ ፡ ታላቅና ፡ ጀግና ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ይቅርና ፡ በጦርነት ፡ መሀከልም ፡ ቢሆን ፡ መላክተኛ ፡ አያስርም ።" አሉ ፡ ቀኛዝማች ።

"እሱስ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ ስለት ፡ ገበሮች ፡ አስሬ ፡ አልጠቀምም ። እንዲያው ፡ ነገሩ ፡ ግን- - -" አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ ፊታቸው ፡ ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ ቆይተው ፡ "ግብራችን ፡ ካልጐደለ ፡ ድሮውንስ ፡ ምን ፡ ያጣላን ፡ ኖሮዋል ? በል ፡ ደግ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ መሰለህ ፡ ጨርሰው ። እረ ፡ ለመሆኑ- - - -ይሄ- - -በለው ፡ ነው ? በላይ ፡ ማነው ? ይሄ- - - ወረቀቱን ፡ የጻፈልን !" አሉ ።

"አበጀ ፡ በለው !" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ።

"የማነው ፡ አበጀ ፡ በለው !"

"ምነው ፡ ፊታውራሪ ፡ ሽመልስንና ፡ ፊታውራሪ ፡ ይመር ፡ መልኬን ፡ በተራ ፡ ድል ፡ መትቶ ፡ ጎንቻንና ፡ ሳርምድርን ፡ ሰባት ፡ አመት ፡ የገዛውን ፡ ሽፍታ ፡ አጡት ፡ እንዴ ? እሰዎ ፡ እንኩዋ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲያደንቁት ፡ ሰምቻለሁ !" አሉ ፡ ባላምባራስ ።

"እሱንማ ፡ አውቀዋለሁ ! ታዲያ ፡ እዚህ ፡ ምን ፡ ሊያደርግ ፡ መጣ ?"

"ባዋጅ ፡ ገባ ። በዱር ፡ በገደል ፡ የምትኖር ፡ ነፍስ ፡ የጠፋብህ ፡ ሁሉ ፡ ተምረሀልና ፡ ከባለደምህ ፡ እዩታረቅህ ፡ ግባ ፡ ተብሎ ፡ አዋጅ ፡ ሲነገር ፡ ገብቶ ፡ ደም ፡ በተቃባሁበት ፡ አገር ፡ አልኖርም ፡ ብሎ ፡ እዚህ ፡ እስዎ ፡ ጉልት ፡ እናሞራ ፡ ዘር ፡ ቆጥሮ ፡ ርስት ፡ ተካፍሎ ፡ ተቀምጦዋል ። የጎንቻ ፡ ህዝብ ፡ እንኩዋ ፡ በጣም ፡ ስለሚወደው ፡ እንዳይሄድበት ፡ ታቦት ፡ አውጥቶ ፡ ቢለምነው ፡ እንቢ ፡ አለ ፡ ይባላል ።"

"የጎንቻ ፡ ህዝብ ፡ ሽፍታ ፡ ስለሆነ ፡ ሽፍታ ፡ ይወዳል !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

"የለም ፡ ለዚህ ፡ አይደለም ፡ በጠቅላላው ፡ ለባላገር ፡ በተለይም ፡ በግፍ ፡ ለተጠቃ ፡ ታዳጊ ፡ ለመሆን ፡ ታጥቆ ፡ የተነሳ ፡ ነው ፡ ይባላል !"

"እንዴት ?"አሉ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሊጠይቁት ፡ የነበረውን ፡ ጥያቄ ፡ ካፋቸው ፡ ነጥቀው ። ፊታውራሪ ፡ አዛዥን ፡ ትንሽ ፡ ገላመጡና ፡ " እንዴት ?"አሉ ፡ እሳቸውም ።

"መጀመርያ ፡ የሸፈተ ፡ ራሱ ፡ ተበድሎ ፡ አይደለም ። ጎንቻ ፡ የፊታውራሪ ፡ ሽመልስ ፡ አሽከሮች ፡ የባላገሮችን ፡ ከብቶች ፡ ቢሰርቁ ፡ በነሱ ፡ ሀጢያት ፡ አንድ ፡ ተቆርቋሪና ፡ ወገን ፡ የሌለው ፡ አንተነህ ፡ መኩሪያየ ፡ የሚባል ፡ ባላገር ፡ ተፈልጎ ፡ ተከሶ ፡ ባልሰራው ፡ ወንጀል ፡ ከብቱ ፡ ተወርሶ ፡ እሱም ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ በታሰረበት ፡ ስለሞተ ፡ አበጀ ፡ በለው ፡ አይወለደው ፡ አይዘመደው ፡ የዚያን ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ከብቶቹን ፡ ሸጠ ፡ ጠመንጃና ፡ ጥይት ፡ ገዝቶ ፡ ሸፈተ ። ፊታውራሪ ፡ ሽመልስን ፡ ከገደለ ፡ በሁዋላ ፡ በጎንቻና ፡ በሳርምድር ፡ እዩተዘዋወረ ፡ ሲኖር ፡ ለነጋዴ ፡ በሚያስጋ ፡ ቦታ ፡ ዘበኛ ፡ እዩሰጠ ፡ ከማስተላለፍና ፡ ሌሎች ፡ ሽፍቶች ፡ የዘረፉት ፡ ባላገር ፡ ቢኖር ፡ ዘራፊዎችን ፡ እንዳውሬ ፡ አድኖ ፡ የዘረፉትን ፡ ከማስመለስ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንኩዋ ፡ ባላገርን ፡ ወይም ፡ ነጋዴን ፡ እሱ ፡ ወይም ፡ የሱ ፡ ሰዎች ፡ ዘረፉ ፡ ተብሎ ፡ አያውቅም ። ስለዚህ ፡ አገሬ ፡ ገዥዎች ፡ የሚጠሉትንና ፡ የሚፈሩትን ፡ ያክል ፡ ባላገር ፡ ይወደው ፡ ነበር ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ባላገር ፡ እስበሱ ፡ ሲጣላ ፡ ወደገረ ፡ ገዥ ፡ በመሄድ ፡ ፈንታ ፡ ወደሱ ፡

ይሄድና ፡ የፈረደለት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የተፈረደበት ፡ ጭምር ፡ ያስ ፡ ብሎትና ፡ አመስግኖ ፡ ይመለሳል ፡ ይባላል ። ጦቱም ፡ አበጀ ፡ ጎንቻንና ፡ ሳርምድርን ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ መንግስት ፡ የሾማቸው ፡ ገዢቶቹን ፡ አያውቁምኮ !" አሉ ፡ ባላምባራስ ።

"ሰውን ፡ ከስልጣን ፡ የበለጠ ፡ ፍቅር ፡ የሚገዛው ፡ መሆኑን ፡ ይህ ፡ ያስረዳል !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ፊታውራሪን ፡ እየተመለከተ ።

"ብፁ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የታች ፡ ከንፈራቸውን ፡ አስረዝመው ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የተናገረው ፡ ከንቱ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ።

"ብፁ !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ የታች ፡ ከንፈሩን ፡ ከፊታውራሪ ፡ የበለጠ ፡ አስረዝሞ ፡ ንግግራቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አሳባቸው ፡ ጭምር ፡ ከንቱ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ። እዚያ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ የሁለቱን ፡ መነናቆር ፡ ይህንም ፡ መነናቃቸውን ፡ የገለጹበትን ፡ አይተው ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ። ፊታውራሪና ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ የሌሎቹ ፡ ሳቅ ፡ ተጋብቶባቸው ፡ አብረው ፡ ሳቁ ።

ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ እንዳወሩት ፡ የጎንቻ ፡ ሀገሩ ፡ አበጀ ፡ በለውን ፡ መውደዱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ያመልከው ፡ ነበረ ። ያንቶንህ ፡ መኩሪያየን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ፊታውራሪ ፡ ሽመልስን ፡ ከገደለና ፡ ከዚያም ፡ በዙሪዉ ፡ እየታዘዘ ፡ የሚገጥመውን ፡ ጦር ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ እየመታ ፡ መሳሪያውን ፡ እየገፈፈ ፡ ከመለሰው ፡ በሁዋላ ፡ ስለሱ ፡ የሚነገረውና ፡ የሚገጥመው ፡ ግጥም ፡ ሁሉ ፡ ለተጠቁት ፡ ድሆች ፡ ረዳት ፡ ለመሆን ፡ ከእግዚአብሄር ፡ ተልኮ ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሰው ፡ ሲል ፡ መከራ ፡ የሚቀበል ፡ ጥይት ፡ የማይገድለው ፡ እመም ፡ ድካም ፡ የማይነካው ፡ በጭራሽ ፡ ከሰው ፡ የተለዩ ፡ አስመስሎ ፡ የሚያሳይ ፡ ነበር ። በገጠመበት ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ሁሉ ፡ ቆስሎ ፡ ስለማያውቅ ፡- ባላገር ፡ "ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አብሮት ፡ በፈረስ ፡ ይቀመጥና ፡ ከንፉን ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ እንደ ፡ ጥሩር ፡ ሲያለብሰው ፡ እንሌና ፡ እንሌ ፡ ባይናቸው ፡ አይተዋል ፡" ብሎ ፡ ያወራል ። የባለስልጣኖች ፡ ወገን ፡ በበኩሉ ፡- "ጥይት ፡ የማያስነካ ፡

እስማት ፡ አስጠልስሞ ፡ ባንገቱ ፡ አድርጎዋል ፡” እያለ ፡ ያወ
ራል ። ብቻ ፡ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ አበጀ ፡ በለው ፡ ዛሬ ፡ ጎንቻ ፡ ነው ፡
ሲባል ፡ ነገ ፡ ሳርምድር ፡ መታየቱ ፡ ሳርምድር ፡ ጦር ፡ ሲታዘዝ
በት ፡ እነሴ ፡ ቃፎ ፡ መባሉ ፡ ከዚያ ፡ እነብሴ ፡ ባንዱ ፡ ባለስል
ጣን ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥሎና ፡ ንብረቱን ፡ ዘርፎ ፡ መጥፋቱ ፡ በብዙ ፡
ፍለጋ ፡ ተገኝቶ ፡ ጦርነት ፡ የገጠመ ፡ እንደሆነ ፡ ድል ፡ ከማድ
ረግ ፡ በቀር ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ባለማወቁ ፡ በባለስልጣኖች ፡ ዘንድ ፡
እንደ ፡ እግዚአብሄር ፡ መቅሰፍት ፡ ተፈርቶ ፡ በተራው ፡ ህዝብ ፡
ዘንድ ፡ እንደ ፡ ጠባቂና ፡ እንደ ፡ ቃዳጊ ፡ መላክ ፡ ተወዶ ፡ ሰባት ፡
አመት ፡ በሽፍትነት ፡ ኖረ ።

“ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡” አሉ ፡ ባላምባራስ ። “ምን ፡
ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ጎንቻና ፡ ሳርምድር ፡ ሽፍታ ፡ ተለይቶ ፡ አያው
ቅም ። ብዙ ፡ ስመጥር ፡ ብዙ ፡ የሚያስፈሩ ፡ ሽፍቶች ፡ ነበሩ
በት ፡ ዛሬም ፡ አሉበት ። ነገር ፡ ግን ፡ በባላገር ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
አበጀ ፡ በለው ፡ ከሊቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ፡ ተወዶ ፡ የኖረ ፡ ሽፍታ ፡
አይቼ ፡ ሰምቼ ፡ አላውቅም ። መቼም ፡ ሴት ፡ ወንዱ ፡ ፍቅሩ
ንና ፡ አድናቆቱን ፡ ለመግለጽ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ይገጥመው ፡ የነበረ ፡
ግጥም ፡ ቢሰበሰብ ፡ አንድ ፡ መጽሀፍ ፡ አይበቃውም !”

“ባላምበራስኮ ፡ ግጥም ፡ ለመያዝም ፡ የያዘውን ፡ ላለመ
ርሳትም ፡ ያለው ፡ ችሎታ ፡ ልክ ፡ እንደውር ፡ መሆኑን ፡ ታው
ቃላችሁ ? እስቲ ፡ የምታስታውሰውን ፡ ያክል ፡ ከሰማኸው ፡
ግጥም ፡ ትንሽ ፡ ንገረን ፡ እባክህ ፡ በሞቴ !” አሉ ፡ አዛዥ ፡
ደስታ ፡ እዩሳቁ ። ሌሎችም ፡ ሳቁ ። ከዚያ ፡ ባላምባራስ ፡ አዛዥ ፡
ደስታን ፡ ደስ ፡ ከማሰኘቱም ፡ ይልቅ ፡ የፊታውራሪን ፡ ብስ
ጭት ፡ ለማስረሳት ፡ በማሰብ ፡ የሰሙዋቸውን ፡ ግጥሞች ፡ ለማ
ጠረቃቀም ፡ ግንባራቸውን ፡ ሲያሻሹ ፡ ቆዩና ፡ ለጊዜው ፡ ያስ
ታወሱዋቸውን ፡ ግጥሞች ፡ ለማሰማት ፡ ከምን ፡ እንደሚጀምሩ ፡
ቸገራቸው ።

“ መቼም ፡ እንደ ፡ ነገርሁዋችሁ ፡ ግጥሙ ፡ ተነግሮ ፡
አያልቅም ። ሴቱ ፡ የገጠመለት ፡ ለብቻ ፡ ወንዱ ፡ የገጠመለት ፡

ለብቻ ፡ ቢሰበሰብ ፡ ለዩራሱ ፡ መጽሀፍ ፡ ይሞላል ፡ ከዚያም ፤ ከዚህም ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ልንገራችሁ ? ወይስ --- የሴቶችን ፡ ብቻ !" አሉ ።

" ወንዶች ፡ ከነጠሙት ፡ ንገረን ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

" የለም ፡ ሴቶች ፡ ከነጠሙት ! " አሉ ፡ አዛዥ ።

" ከወንዶችም ፤ ከሴቶችም ፡ ግጥም ፡ ትንሽ ፤ ትንሽ ፡ እነግራችሁዋለሁ ! በወንዶቹ ፡ ልጀምር ። " አሉና ፡ ባላም ባራስ ፡ ጀመሩ ፦

" የግዚአብሄር ፡ ዳኝነት ፡ የግዚአብሄር ፡ እውነት ፦
የሚጠበቅበት ፡ የድሆች ፡ መብት ፦
እጅና ፡ እግሩን ፡ ታስሮ ፡ በግፍ ፡ ሰንሰለት ፦
ያላንድ ፡ ጠበቃ ፡ ያላንድ ፡ ረዳት ፦
ፍርድ ፡ ለመቀበል ፡ ቀርቦ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፦
በቀማኞችና ፡ በሌቦች ፡ ችሎት ፦
ይሙት ፡ በቃ ፡ ብለው ፡ ሁሉም ፡ ባንድነት ፦
ያመጽ ፡ ፍርድ ፡ ፈርደው ፡ ገድለው ፡ ሲቀብሩት ፦
" ይህን ፡ ግፍ ፡ አዩና ፡ አበጀ ፡ አሰተውሎ ፦
በጦር ፡ እንደ ፡ ወጉት ፡ ልቡ ፡ ባዘን ፡ ቆስሎ ፦
መንፈሱ ፡ በቁጣ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ተቃጥሎ ፦
የውነትን ፡ ደመኞች ፡ ለመበቀል ፡ ብሎ ፦
ወረደ ፡ በረሀ ፡ ቤት ፡ ንብረቱን ፡ ጥሎ ፦
" ዳኞች ፡ ዳኝነትን ፡ ከቀበሩት ፡ ገድለው ፦
የግዜርን ፡ አደራ ፡ እምነቱን ፡ አጉድለው ፦
የሰጠናቸውን ፡ ስልጣን ፡ ተከልለው ፦
እኛኑ ፡ ሲያጠቁን ፡ ጠባቂዎች ፡ መስለው ፦
መቀማት ፡ ሲመርጡ ፡ መጠበቅን ፡ ጥለው ፦
ካሾች ፡ እኛ ፡ ስንሆን ፡ እነሱ ፡ በድለው ፦
አርደው ፡ ሲጨርሱን ፡ አንድባንድ ፡ አናጥለው ፦
እንደ ፡ ቡዋዘዝ ፡ ከብት ፡ ጠባቂ ፡ እንደሌለው ፦
ለመብት ፡ ሲከላከል ፡ ሊሞት ፡ እንደ ፡ ማለው ፦
እንደ ፡ ቆራጡ ፡ ወንድ ፡ እንዳበጀ ፡ በለው ፦

እኛስ ፡ ለመብታችን ፡ የማንታገለው ፦
ከጅልነት ፡ በቀር ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ አለው ?
" የመብትን ፡ ፋና ፡ ያርነትን ፡ ሥራ ፦
የሚለይበትን ፡ ሰው ፡ ከንስሳ ፡ ተራ ፦
ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ሲሄድ ፡ እያበራ ፦
በነሴ ፡ በርሀ ፡ በጎንቻ ፡ ተራራ ፦
ገፈኞች ፡ ከበውት ፡ ከቀኝ ፡ ከግራ ፦
ቀን ፡ ከሌት ፡ ሲያድኑት ፡ ወንጀል ፡ እንደ ፡ ሰሯ ፦
ለምቾቱ ፡ እያስብ ፡ ለህይወቱ ፡ እይፈራ ፦
እንደ ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ሲቀበል ፡ መከራ ፦
መሄዳችን ፡ ላይቀር ፡ ነገ ፡ ስንጠራ ፦
ወደማንቀርበት ፡ ወደ ፡ ሙታን ፡ ሰፈራ ፦
የበሉትን ፡ ቀጥቶ ፡ የግዜን ፡ አደራ ፦
የማይቀረውን ፡ ሞት ፡ መሞት ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፦
የሚያጸድቅ ፡ ነበር ፡ ወዲያው ፡ የሚያኮራ ፦
የሴቶች ፡ ግጥም ፦
"ጸሀይ ፡ እያጠቁረው ፡ ውርጭ ፡ እያከሰለው ፦
ራብ ፡ እያከሳው ፡ ጥም ፡ እያዝለው ፦
ድካም ፡ እይሰማው ፡ እንቅልፍ ፡ እይጥለው ፦
ጎራዴ ፡ እያቆስለው ፡ ጥይት ፡ እይገለው ፦
ስጋ ፡ እንዳልለበሰ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፦
ይኼ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ያለው ፦
በሱ ፡ አለመኖሩ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ መላው ፦
የጀግኖች ፡ ጀግና ፡ አበጀ ፡ በለው ፦
" ምነው ፡ ባደረገኝ ፡ ጋሻጃግሬውን ፦
ስከተል ፡ እንድኖር ፡ ሁዋላ ሁዋላውን ፦
ምነው ፡ ባደረገኝ ፡ ደበላ ፡ ድጉን ፡
ወይም ፡ ባደረገኝ ፡ እጥፉ ፡ ዝናሩን ፦
ዙሪያ ፡ ተጠምጥሜ ፡ እንዳቅፍ ፡ ወገቡን ፦
ምነው ፡ ጠመንጃውን ፡ ባረገኝ ፡ እግዜር ፦
ከደረቱ ፡ ሳልወርድ ፡ አቅፎኝ ፡ እንድኖር ፡
" እዚህ ፡ ተቀምጠው ፡ ከምኖር ፡ በደስታ ፦

እረፍት ፡ ሳያምረኝ ፡ ወገቤን ፡ ሳልፈታ ፡-
አንተ ፡ ተከትዬ ፡ ከጥዋት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡-
በጎንቻ ፡ በርሀ ፡ ልበል ፡ ገልታ ፡ ገልታ ፡-
እንቅፋት ፡ ሲመታህ ፡ እብሬህ ፡ ልመታ ፡-
አበጀ ፡ በላቸው ፡ የመብቴ ፡ ጠባቂ ፡ ያርነቴ ፡ ጌታ ፡-
" ምጣዱን ፡ አዝዬ ፡ እርኮቴን ፡ አንግቼ ፡-
ሽንብራ ፡ ቆርጥሜ ፡ ጥሩ ፡ ውሀ ፡ ጠጥቼ ፡-
ራበኝ ፡ ደከመኝ ፡ ሳልል ፡ ተገዝቼ ፡-
ባለጸጋ ፡ ባሌን ፡ ዛሬውን ፡ ፈትቼ ፡-
እሱን ፡ እንድከተል ፡ ቤት ፡ ንብረቴን ፡ ትቼ ፡-
የግሩ ፡ አጣቢ ፡ እንድሆን ፡ ግርድና ፡ ገብቼ ፡-
አበጀን ፡ አማልዱኝ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቼ ፡-
" የራስ ፡ የደጃዝማች ፡ ምሽት ፡ ከመሆኔ ፡-
አሽከር ፡ ከመላኬ ፡ ሰጋር ፡ ከማስጫኔ ፡-
ሰባንን ፡ እንድኖር ፡ ሳይከደን ፡ አይኔ ፡-
እንቅልፍ ፡ እንዳልጠግብ ፡ ተኝቼ ፡ በጎኔ ፡-
የሱ ፡ ገረድ ፡ ሆኜ ፡ ልኖር ፡ መሰመኔ ፡-
ወንድ ፡ ብወድ ፡ ነው ፡ ሴት ፡ ስለሆንሁ ፡ እኔ ፡-
" ስማኝ ፡ ያገሬ ፡ ወንድ ፡ ልውቀስህ ፡ ወቀሳ ፡-
አይደለህ ፡ ቀማኛ ፡ አይደለህ ፡ ጀውሳ ፡-
ሳትሰርቅ ፡ ሳትቀማ ፡ ሳይኖርህ ፡ እበሳ ፡-
እየነዱ ፡ ሲያስሩህ ፡ እንዲሁ ፡ ባፈሳ ፡-
የማትፈራገጥ ፡ የማትንቀሳሳ ፡-
ትንሽ ፡ የማትሽከር ፡ ከሆንህ ፡ ለስላሳ ፡-
በሁለት ፡ እግሩ ፡ ቆሞ ፡ ከሚሄድ ፡ እንስሳ ፡-
ወይም ፡ ነፍስ ፡ ከሌለው ፡ ከወደቀ ፡ ሬሳ ፡-
ከቶ ፡ ልዩነትህ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ ነውሳ ?
" በነሴ ፤ እነብሴ ፡ በነማይ ፡ በጎንቻ ፡-
ወንዱ ፡ ሁል ፡ ሴት ፡ ሆኖ ፡ ከቀረ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡-
ለቀማኞች ፡ መቅጫ ፡ ላመጸኞች ፡ መምቻ ፡-
ለደካሞች ፡ ምሽግ ፡ ጋሻ ፡ መመከቻ ፡-
ለሱ ፡ ተሸከሜ ፡ ውሀ ፡ በቅምጫና ፡ ጥሬ ፡ በስልቻ ፡-
እንኩዋን ፡ በማውቀው ፡ ዱር ፡ በማውቀው ፡ ስርቻ ፡-

ስሄድ ፡ አልኖርም ወይ ፡ እስካገር ፡ ዳርቻ ፡-
" ሌሎች ፡ ሲበደሉ ፡ እሱ ፡ መከፋቱ ፡-
ሌላ ፡ ሰው ፡ ሲጠቃ ፡ እሱ ፡ መቆጣቱ፡-
የሰው ፡ ቁስል ፡ እሞት ፡ እንዲህ ፡ መሰቅየቱ ፡-
ግፍንና ፡ አመጽን ፡ እንደ ፡ መርዝ ፡ መጥላቱ፡-
ህይወቱን ፡ ለሰው ፡ መብት ፡ ዋጋ ፡ አርጎ ፡ መስጠቱ ፡-
ግርማው ፡ እዳንበሳ ፡ ሲያዩት ፡ ማስፈራቱ፡-
ምን ፡ ከባህር ፡ እሸዋ ፡ ቢበዛ ፡ ጠላቱ ፡-
ጎራዴውን ፡ መዞ ፡ አውጥቶ ፡ ካፎቱ ፡-
ብቻውን ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ መድረሻ ፡ ማጣቱ ፡-
ሳያስናክለው ፡ ጋራው ፡ ቁልቁለቱ ፡-
ህይሉን ፡ ሳይቀንሰው ፡ ራቡ ፡ ጥማቱ ፡-
ርቀት ፡ ሳይገታው ፡ እዳሳብ ፡ ፍጥነቱ ፡-
እነሴ ፡ ነው ፡ ሲባል ፡ ጎንቻ ፡ መታየቱ ፡-
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ባህሪ ፡ ይዞ ፡ መገኘቱ ፡-
አይመስክርምወይ ፡ ሰው ፡ ከተሰራበት ፡ ከጎስቁዋላ ፡ ጭቃ ፡
ሳለመሰራቱ ፡-
ጥንቱኑ ፡ ሲፈጠር ፡ ሲወለድ ፡ ከናቱ ፡-
የሰው ፡ ቤዛ ፡ እንዲሆን ፡ ታዞ ፡ ለመምጣቱ ፡-
" እየ ! ምን ፡ ያደርጋል ፡ በከንቱ ፡ መመኘት ፡ የማይ
ገኝ ነገር ፡-
ባይሆንማ ፡ ኖሮ ፡ ሹመት ፡ እንደ ፡ ቂጥኝ ፡ የሚወረስ ፡
ከዘር ፡-
ቅን ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ህዝብ ፡ ለማስተዳደር ፡-
የያንዳንዱን ፡ ድሀ ፡ መብት ፡ ለማስከበር ፡-
ለዚህ ፡ ለተጠቃ ፡ ለተበደለ ፡ አገር ፡-
መድህኒት ፡ እንዲሆን ፡ እሱን ፡ መሾም ፡ ነበር ፡"

"ለሽፍታ ፡ የሚሆን ፡ አይመስለኝም ፡ እንጂ ፡ ግጥሙ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ እኔ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደምነግራችሁ ፡ ባላገር ፡ ሀይለኛ ፡ የሚወድ ፡ መሆኑን ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ፡፡" አሉ ፡ ፊታውራሪ፡፡ "እየ ፡ ጉድ ! እዩዋቸው ፡ የኛን ፡ ከንቱ

ለማናቸውም ፡ ነገር ፡ ከሳቸው ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ የሚገጥም ፡ ትርጉም ፡ ይፈልጉለታል ። ” አለና ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ተንስቶ ፡ እዩሳቀ ፡ ሄደ ። ሌሎቹ ፡ ግን ፡ ባይስቁም ፡ ፈታውራሪ ፡ ለግጥሙ ፡ በሰጡት ፡ ትርጉም ፡ አለመስማማታቸውን ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ በማለት ፡ ገለጹ ።

# ምዕራፍ ፡ ፲፱ ፡

## የፍቅር ፡ ዋዜማ ፡

በዛብህ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ማስተማሩን ፡ አስታጉሎ ፡ ከሰብለ ፡ ከወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ከሀብትሽ ፡ ተለይቶ ፡ ውሎ ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ሲገናኛቸው ፡ የሚወዱት ፡ ዘመድ ፡ ብዙ ፡ አመት ፡ ጠፍቶ ፡ ኖሮ ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

" ትናንት ፡ ሳትመጣ ፡ ስለቀረህ ፡ ደህና ፡ ባትሆን ፡ ይሆን ፡ ብለን ፡ ሰግተን ፡ ነበር ፡ በጤንነት ፡ ነው ፡ የቀረህ ? " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ በደስታ ፡ ፊት ፡ ፈገግ ፡ ብለው ።

" ደህና ፡ ነኝ ፡ ወዳጄ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ዘመድ ፡ ታሞ በት ፡ ሊጠይቅ ፡ መሄድ ፡ ስለነበረበት ፡ ብቻውን ፡ እንዳይሆን ፡ አብሬው ፡ ሄጄ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በሁዋላ ፡ ስለተመለስን ፡ ነው ፡ ሳልመጣ ፡ የቀረሁ ።" አለ ፡ በዛብህ ፡ ውሸቱ ፡ ካይኑና ፡ ከፊቱ ፡ እንዳይታወቅበት ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ።

" እንኳዋን ፡ ደህና ፡ ሆንህ ፡ እንጂ ፡ ግዴለም ! " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ። ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ሰላምታ ፡ ከመስጠት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልተናገረችም ። ብቻ ፡ ደስታ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የማታውቀው ፡ ስሜት ፡ ተሰማትና ፡ ፊትዋ ፡ ቀልቶ ፡ አይኖችዋ ፡ ውሀ ፡ ሞልተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ይህ ፡ እንዳይታይባት ፡ ትጠብቅ ፡ ነበር ።

" ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ አንተ ፡ ተጠርተህ ፡ ከመጣህበት ፡ በፊት ፡ ጌታ ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ተቆጥተው ፡ ነበርና ፡ የተጠራህበትን ፡ ጉዳይ ፡ በቅጡ ፡ ሳያነጋግሩህ ፡ ሄድህ ። ከዚያ ፡ በበነጋው ፡ ስትቀር ፡ ጊዜ ፡ ድንገት ፡ ባንተ ፡ የተቆጡ ፡ መስሎህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀረህ — ብዬ ፡ ነው ።" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ፈታ ውራራ ፡ በበዛብህ ፡ ያልተቆጡ ፡ ለማስመሰል ።

" ልጅ ፡ ነኝ ፡ ቢቆጡኝስ ፡ ምን ፡ ያሳዝነኛል ! " አለ ፡ በዛብህ ፡ ፈታውራሪ ፡ የተቆጡ ፡ በሱ ፡ እንደሆነ ፡ ደህና ፡

አድርጎ ፡ ማወቁን ፡ ለመግለጽ ።

“ እሱስ ፡ እውነትህን ፡ ነው ፡ ልጃችን ፡ ነህ ፡ እንደ ፡ ልጃችን ፡ ነው ፡ የምናይህ ! ብቻ ፡ ያንለት ፡ የተቆጣ ፡ ባንተ ፡ አይደለም ፡ አታምነኝም ? ” አሉ ፡ አይናቸውን ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ተክለው ። በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ አለና ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

ከዚያ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ውሸት ፡ መሆኑን ፡ በዛብህ ፡ እንዳወቀባቸው ፡ ከፊቱ ፡ ሲያዩ ፡ ትንሽ ፡ የእፍረት ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ አሉና ፡— “በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ትምህርታችሁን ፡ ጀምሩ ፡ እኔ ፡ ጌታ ፡ ከሄዱበት ፡ ሳይመለሱ ፡ እቴቴ ፡ ላቀች ፡ ታማለች ፡ አሉ ፡ ጠይቄያት ፡ ልምጣ ፡” ብለው ፡ ተነስተው ፡ ወጡ ። እውጭ ፡ ቆመው ፡— አንቺ ፡ ጥንቦ !” አሉ ።

“ እሜት ! አለች ፡ ሀብትሽ ፡ ይመር ፡ ወደመቤትዋ ፡ እየሮጠች ።

“አንቺ ፡ ደንደሳም ፡ እኔ ፡ እስክመለስ ፡ እግርሽ ፡ ከዚህ ፡ ቤት ፡ ልውስ ፡ ይልና ፡ ይህን ፡ ያበጠ ፡ ደረትሽን ፡ አፈርጠዋለሁ ! ዋ ! ቀልድ ፡ አይምስልሽ ! የውስጥ ፡ ገላሽን ፡ ነው ፡ በላይ ፡ የማደርገው !” አሉ ፡ እውስጥ ፡ ያሉት ፡ እንዳይሰሙዋቸው ፡ ወደ ፡ ሀብትሽ ፡ ጆሮ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ የቀኝ ፡ ጠቋሚ ፡ ጣታቸውን ፡ እያወለበለቡ ።

“እሺ ፡ እሜቴ!” አለች ፡ ሀብትሽ ፡ አንገትዋን ፡ ደፍታ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያየች ።

ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ዘወር ፡ ሲሉ ፡ ሀብትሽ ፡ መላስዋን ፡ አውጥታባቸው ፡ አጥሩን ፡ እስኪወጡ ፡ የምትጠብቅ ፡ ለመምሰል ፡ በዛብህና ፡ ስብለ ፡ ባሉበት ፡ ቤት ፡ ገብታ ፡ ተቀመጠች ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ አጥሩን ፡ እንደወጡ ፡ “እንግዲህ ፡ ትምህርታችሁን ፡ ቀጥሉ ፡ እኔ ፡ እሜቴ ፡ ከሄዱበት ፡ ሳይመለሱ ፡ እዮ ፡ ገብሬን ፡ አይቼ ፡ ልምጣ ፡ !” አለችና ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ እርምጃ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ተራምዳ ፡ እየሳቀች ፡ ወደ ፡ ማድ ፡ ቤት ፡ ሮጠች ። ስብለና ፡ በዛብህ ፡ ሀብትሽ ፡ በመቤትዋ ፡ ለማሾፍ ፡ ያለችውንና ፡ ያደረገችውን ፡ አይተው ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ።

“በዚህ ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ እስከሚመ

ባጡ ፡ ወር ፡ አጋማሽ ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያምዎን ፡ ጨርሰው ፡ ጽሀፈ ትምንም ፡ የሻሽሉና ፡ እኔም ፡ ወዳስተምሁበት ፡ እንድሄድ !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ሀብትሽ ፡ ከሄደች ፡ በሁዋላ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ቆዩ ፡ ሰብለን ፡ በጎን ፡ አዩዋ ።

"እግዚአብሄር ፡ ያስተርልኝ!" አለች ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አን ገትዋን ፡ ትንሽ ፡ ደፋ ፡ አይኖችዋን ፡ ቦዘዝ ፡ አድርጋ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያየች ።

"ለምን!"

"ለስምታው ።"

"እኔ ፡ ድሮም ፡ ቢሆን ፡ እመይቱና ፡ እርስዎ ፡ እንዚ ፡ ስላላ ችሁ ፡ ነው ፡ እንጂ . . . .እኔ . . . . ." ብሎ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በጎን ፡ ቢመለከት ፡ አይኖችዋ ፡ እንባ ፡ ሞልተው ፡ አዩ ።

" ለማሳዘን ፡ ወይም ፡ ለማሸመቀዋጠር ፡ ብዬ ፡ አይደለ ምኮ ! አንቺ ፡ በማለቱ ፡ ጌቶች ፡ በጣም ፡ እንዳዘኑና ፡ እንደ ፡ ተቆጡ ፡ ስላዩሁ ፡ በፍቅር ፡ ኖረን ፡ ተጣልተን ፡ እንዳንለያይ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ " አለ ፡ ቀጠለና ፡ በዛብህ ።-

" አውቄዋለሁ ! " አለች ፡ አንገትዋን ፡ ደፋታ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠች ፡ አይንዋን ፡ ሞልቶት ፡ የነበረው ፡ እንባ ፡ ፊት ዋን ፡ ሳይነካ ፡ እዬተደበለበለ ፡ እመሬት ፡ እዬወደቀ ።-

በዛብህ ፡ ሰብለን ፡ ስታለቅስ ፡ ሲያይ ፡ አዘን ፡ ተሰማውና ፡ እንጀቱ ፡ በውስጡ ፡ ይላውስ ፡ ልቡን ፡ ባርባር ፡ ይለው ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ የሱም ፡ አይኖች ፡ የሰዋን ፡ እንዳዩ ፡ እንባ ፡ ቋጠሩ ።

" ላሳዝንሽ ፡ ብዬ ፡ አይደለምኮ ! እባክሽ ፡ አታልቅሺ ! በዚህ ፡ --- የ --- ምታዝኚ ፡ ከሆንሽ ፡ እስከሄድ ፡ ድረስ ፡ አንቺ ፡ እላለሁ ፡ አትልቅሺ ፡ ብቻ ። " አለ ፡ በዛብህ ፡ ልቅሶዋን ፡ ሲያይ ፡ ከተሰማው ፡ አዘን ፡ የተነሳ ፡ ድምጹ ፡ እንደ ፡ መሻከር ፡ ብሎ ።

" እንደ ፡ ፈለግሀ ! " አለች ፡ አይኖችዋንም ፡ አፍንጫዋ ንም ፡ የኩታዋን ፡ ጫፍ ፡ ነጥላ ፡ እዬጠራረገች ። ከዚያ ፡ ሁለ ቱም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ እንደገና ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡

ብለው ፡ እንደ ፡ ቆዩ ፡-

"ወደ ፡ ሸዋ ፡ ለመሄድ ፡ የምትቸኩለው ፡ ለምን ፡ ነው ?" አለች ። የተሰማትን ፡ ቅርታ ፡ ወለል ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳይ ፡ ውብ ፡ ፊትዋን ፡ ወደሱ ፡ መለስ ፡ አድርጋ ፡ አይን ፡ አይኑን ፡ እያዬች ። በዛብህ ፡ አይኖችዋን ፡ ባይኖቹ ፡ ላይ ፡ ሲያይ ፡ ለጠዬቀችው ፡ ጥያቄ ፡ ቶሎ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ድንግርግር ፡ አለውና ፡-

"ሸዋ ? ሸዋ ፡ ለመሄድ ፡ የምቸኩል ? እእ . . . . ሸዋ ፡ አንድ ፡ የምማረው ፡ ትምርት ፡ አለ ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡— እዚያው ፡ ለመኖር ፡ ነው ።"-

" አገርህን ፡ በጭራሽ ፡ ትተህ ? "

" አዎ ። "

" ለምን ፡ እንደ ፡ ነፍስገዳይ ፡ አገርህን ፡ በጭራሽ ፡ ትተህ ፡ ትሰደዳለህ ? " ስትል ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ ማዘን ፡ አለና ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ ያይ ፡ ጀመር ።

" ለምን ? " አለች ፡ አሁንም ።

" አሁን ፡ እንዳልሽው ፡ ነፍስ ፡ ስለገደልሁ ። " አለ ፡ ወደስዋ ፡ ቀና ፡ ብሎ ።

" እባክህ ፡ አትቀልድ ! " አለች ፡ ፊትዋ ፡ በቅርታ ፡ ቀለም ፡ እንደ ፡ ተዋበ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብላ ።

" ቀልድ ፡ አይደለም ፡ እውነት ፡ ነው ። በጄ ፡ ባልገድላቸው ፡ አባት ፡ እናቴ ፡ በኔ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ አገሬን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ላላይ ፡ ወስኛለሁ ። "

" እንዴት ? " አለች ፡ በፊትዋ ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ ቅርታ ፡ ከመ ፡ ቅጽበት ፡ ጠፍቶ ፡ ክርር ፡ ባለ ፡ የድንጋጤ ፡ መልክ ።

" ታሪኩ ፡ ረዥም ፡ ነው ፡ ስራችንን ፡ እንጀምር ። " አለ ፡ በዛብህ ፡ በፈንታው ፡ የቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ።

" የለም ፡ ዛሬ ፡ ትምርት ፡ አላማረኝም ፡ ይቅርብኝ ፡ እባክህ ! ትምርት ፡ ይቅርብኝና ፡ የጠየቅሁህን ፡ ንገረኝ ! " አለች ፡ አንገትዋን ፡ ወዳንድ ፡ ወገን ፡ ዘንበል ፡ አድርጋ ፡ አይን ፡ አይኑን ፡ እያዬች ። ከፍዋ ፡ ይልቅ ፡ ፆይንዋን ፡ ልመና ፡

እንቢ ፡ ማለት ፡ የማይቻል ፡ ነበር ። እሱም ፡ ትንሽ ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ እያትና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡-

" እንጃ ! ከምን ፡ እንደምጀምር ፡ እንኳ ፡ ጠፋኝ ! " አለ ።

" ከመጀመርያ ፡ ከበር ፡ ጀምረህ ፡ ንገረኝ ! "

" በልጅነቱ ፡ " አለ ፡ በዛብህ ፡ ግንባሩን ፡ በግራ ፡ ጣቶቹ ፡ እያሸ ፡ እይኑን ፡ ቦዘዝ ፡ አድርጎ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እየተመለከተ ፡- "ገና ፡ ልጅ ፡ ሳለሁ ፡ ነፍስ ፡ ሳላውቅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እዩታመ ምሁ ፡ ወላጆቼ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ከቆረጡ ፡ በሁዋላ ፡ ነበር ፡ አሉ ፡ የምተርፍ ። ታዲያ ፡ ለናት ፡ ላባቴ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ በመሆኔ ፡ ይልቁንም ፡ እናቴ ፡ በጣም ፡ ትወደኝ ፡ ስለነበረ ፡ በታ መምሁ ፡ ቁጥር ፡ እንዳልሞትባት ፡ ለየታቦቱ ፡ ትሳል ፡ ነበር ። ሳይቸግራት ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እጣን ፡ መብራት ፡ ቀሚስ ፡ ካባ ፡ ጃንጥላ ፡ ድባ ፡ ለመስጠት ፡ በመሳል ፡ ፈንታ ፡ እኔ ፡ ሳላ ውቅ ፡ በኔ ፡ ኑሮ ፡ ትሳል ፡ ነበር ። ነፍስ ፡ ማወቅ ፡ ስጀምር ፡ የመ ንደራችን ፡ ልጆች ፡ ጉዋደኞቼ ፡ የስእለት ፡ ልጅ ፡ እያሉ ፡ ሲሰ ድቡኝ ፡ እንጣላና ፡ እመታቸዋለሁ ፡ ወይ ፡ ይመቱኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሄዱበት ፡ ሁሉ ፡ ለመሄድ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሁሉ ፡ ለማድ ረግ ፡ የሚከለክለኝ ፡ ነገር ፡ ስላልነበረ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ተራ ፡ ስድብ ፡ ቁጥሬው ፡ አይከብደኝም ፡ ነበር ። በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ስጎለምስ ፡ የስእለት ፡ ልጅ ፡ እዩተባልሁ ፡ ስሰደብ ፡ የኖርሁት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ ተረዳሁ ። ጉዋደኞቼ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ለማድረግ ፡ እንዳልችል ፡ ሰው ፡ ሆኜ ፡ ተፈጥሬ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ለመኖር ፡ እንዳልችል ፡ እኔ ፡ ሳላውቅ ፡ የገዛ ፡ እናቴ ፡ ፈርዳ ፡ ያሳ ሰረችኝ ፡ እስረኛ ፡ መሆኔን ፡ ተረዳሁና ፡ ጠላሁዋት ። እሺቀ ፡ መቸም ፡ ስለምትወደኝ ፡ እንዳልሞትባት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔን ፡ ለመጉዳት ፡ ብላ ፡ እንዳላደረገችው ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለኔ ፡ የማልችለው ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ ሆኖ ፡ ታዩኝ ። ከናቴ ፡ ተጣ ልቼ ፡ ምሽት ፡ አግብቼ ፡ ለብቻየ ፡ እዚያው ፡ አገሬ ፡ እንዳልኖር ፡ ብዙ ፡ የቆየሁበት ፡ አገር ፡ ሆነና ፡ አሳፈረኝ ። ይህን ፡ በመሳ ሰለው ፡ ነገር ፡ አገራችን ፡ ከፉ ፡ ነው ። ሽሙጡና ፡ እሚቱ ፡ እን ኳዋን ፡ ሰደት ፡ ሞት ፡ ያስመርጣል ። ስለዚህ ፡ ለደካሞች ፡ ወላ

ጆቹ ፡ ከኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ረዳት ፡ እንደሌላቸው ፡ እያወቅሁ ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ ታስሬ ፡ መኖር ፡ ሰለ ፡ ጠላሁ ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ስእለት ፡ አፍረሽ ፡ እዬተባልሁ ፡ የሰው ፡ መሳቂያ ፡ መሆን ፡ ስላሳፈረኝ ፡ ጥያቸው ፡ ጠፋሁ ። በሁዋላ ፡ ሁለቱም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ታመው ፡ ሞቱ ፡ ማን ፡ አስታሞ ፡ እንደ ፡ ቀበራቸው ፡ አላውቅም ! በሽም ፡ ተቀብረው ፡ ይሆናል !” አለ ፡ በዛብህ ፡ በዘገብለው ፡ ሳይረግቡ ፡ ፈትለፈት ፡ የሚመለከቱ ፡ አይኖቹ ፡ እንባ ፡ ሞልተው ። ሰብለ ፡ አፍንጫዋን ፡ ስትናፈጥ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ እንባዋ ፡ እንደሱ ፡ አይንዋን ፡ መሙላት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከዚያ ፡ ተርፎ ፡ እዬፈሰሰ ፡ ካንገትዋ ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ ልብስዋን ፡ ሲያርስ ፡ አዬ ።

“ስለዚህ ፡ እንዲመችሽ ፡ ኖሮዋል ፡ አውራኝ ፡ ብለሽ ፡ የለመንሽኝ ?” አለ ፡ በቅሬታ ፡ ፈገግታ ፡ በሰለለ ፡ ፊትና ፡ እስተያየት ።

“የለም ።” አለች ፡ በኩታዋ ፡ ጫፍ ፡ አይንዋንም ፡ አፍንጫዋንም ፡ እዬጠረገች ። “እንዲያው ፡- - - -እንዲያው ፡ ለመሆኑ ፡ ወላጆች ፡ በየትም ፡ ቢሆን ፡ ያው ፡ ናቸው !”

“እንዴት ?”

“አሁን ፡ ባንተ ፡ የደረሰብህን ፡ ስታወራኝ ፡ የኔ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉት ፡ ትዝ ፡ አለኝ ። እኔ ፡ የምወደውና ፡ እነሱ ፡ ለኔ ፡ የሚፈልጉት ፡ በጣም ፡ የተለያዬ ፡ ነው ። ባንተም ፡ የደረሰው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነው ! አይደለም ?”

“አዎ ፡ ብቻ ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ መሰለኝ ፡ የለውም ?”

“ልዩነቱ ፡ ያንተ ፡ ወላጆች ፡ ያደረጉትን ፡ ሁሉ ፡ ላንተ ፡ ብለው ፡ አንተ ፡ እንዳትሞት ፡ ብለው ፡ የኔ ፡ ወላጆች ፡ ለራሳቸው ፡ ብለው ፡ የራሳቸውን ፡ ክብር ፡ ለመጠበቅ ፡ ብለው ፡ ማድረጋቸው ፡ ነው !”

“እእም ፡ እንጃ ! መቼም ---- አንቺ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ ስለ ሆንሽ ፡ ለጌታ ፡ ልጅ ፡ የሚገባው ፡ ሁሉ ፡ እንዳያጎድልብሽ ፡ አንቺ ፡ ተከብረሽ ፡ እንድታስከብሪያቸው ፡ ይፈልጉ ፡ ይሆናል !”

“ህእ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ! የጌታ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ እንደኔ ፡ ከሆነ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ መሆን ፡ ከቅጣት ፡ ሁሉ ፡ የከፋ ፡ ቅጣት ፡ ነው !”

"የጌታ ፡ ልጅ ፡ መቸም ፡ መከበር ፡ መፈራት ፡ ይገባዋል ፡ እንቺም ፡ እንድትፈሪ ፡ እንድትከበሪ ፡ ሁኚ ፡ ነው ፡ የሚሉሽ !"

"እኔ ፡ ሰው ፡ እንዲፈራኝ ፡ አልወድም ፡ ሰው ፡ እንዲወደኝ ፡ እንዲቀርበኝ ፡ ነው ፡ የምወድ ። ብቻ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ አላገኘውም !"

"እንዴት ?"

"አዬህ ? እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በኖርሁት ፡ ህይወቴ ፡ ከጉዋደኞቼ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ልቤ ፡ የተጫወትሁበትና ፡ ደስ ፡ የተሰኘሁበት ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ ትንሽ ፡ ህጻን ፡ ሳለሁ ፡ አምስት ፡ ወይም ፡ ስድስት ፡ አመት ፡ እስኪሆነኝ ፡ በነበረው ፡ እድሜዬ ፡ ብቻ ፡ ነው ! በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከመንደሩና ፡ ከቤት ፡ አሽከሮች ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ልቤ ፡ ጭቃ ፡ አቡክቼ ፡ ውሀ ፡ ተራጭቼ ፡ ሰድበውኝ ፡ ሰድቤያቸው ፡ መትተውኝ ፡ መትቻቸው ፡ ታግለን ፡ ወድቀን ፡ ተንስተን ፡ ስቀን ፡ አልቅሰን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አብረን ፡ አድርገን ፡ ስንኖር ፡ የነበረኝን ፡ ህይወት ፡ ሳስበው ፡ በድሜየ ፡ ሙሉ ፡ ደስ ፡ የተሰኘሁበት ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ እንዳልተፈጸመ ፡ መልክም ፡ ህልም ፡ ሲያሳሳኝ ፡ ይኖራል ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ያለው ፡ እድሜየ ፡ ሌሎች ፡ ደስ ፡ ሲላቸው ፡ ሌሎች ፡--- ሲኖሩ ፡ የተመለከትሁበት ፡ ነው ፡ እኔ ፡ የኖርሁት ፡ እኔ ፡ ደስ የተሰኘሁበት ፡ እድሜ ፡ አይደለም !" አለች ፡ አካላዊ ፡ ነፃነቷ ፡ እንደ ፡ በዙ ፡ አይነ ፡ ህሊናዋ ፡ ሌሎች ፡ የሚኖሩትን ፡ የደስታ ፡ ኑሮ ፡ እየተመለከተ ።

"እንዴትኮ ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ የተናገረችው ፡ ሳይገባው ፡ ቀርቶ ፡ ሳይሆን ፡ ያዘንዋን ፡ ጥልቅነት ፡ ከፊትዋ ፡ ሲያይ ፡ ፍራት ፡ ገብቶት ፡ ጨዋታውን ፡ የሚለውጥበት ፡ መንገድ ፡ ጠፍቶት ፡ እየፈለገ ።

"እንዴትኮ ! አንተ ፡ ቅድም ፡ እንዳልከው ፡ የድሜ ፡ ጉዋደኞቼ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ እፈልጋለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልችልም ! የድሜ ፡ ጉዋደኞቼ ፡ በዬዱሩ ፡ በዬደሉ ፡ የሚጫወቱትንና ፡ ደስታቸውን ፡ ሀብትሽ ፡ ስትነግረኝ ፡ እኔም ፡ እንደነሱ ፡ በተጫወትሁ ፡ እኔም ፡ እንደነሱ ፡ ሜካለሜካ ፡

ሮጬ ፡ ደስ ፡ ባለኝ ፡ ብዬ ፡ እመኛለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልችልም !
ጉዋደኞቼ ፡ በየሰርጉ ፡ በየመትባሉ ፡ እንደያቅማቸው ፡ አኒ.
ጠው ፡ እንዳንዶቹ ፡ እመሀል ፡ ገብተው ፡ ባንገታቸው ፡ ሴሎ-
እዳር ፡ ቆመው ፡ ግጥም ፡ እየገጠሙ ፡ በቃላቸው ፡ እየዘፈኑ ፡
የወጣትነት ፡ ስሜታቸውን ፡ ሲገልጹና ፡ የልብ ፡ እንፋሎታቸው ፡
ሲወጣላቸው ፡ ስመለከት ፡ እኔም ፡ እንደነሱ ፡ ተነስቼ ፡ ባንገቴ ፡
ወይም ፡ ግጥም ፡ እየገጠምሁ ፡ በቃሌ ፡ ዘፍኜ ፡ እንዲወጣልኝ ፡
ደስስስ ፡ እንዲለኝ ፡ በጣም ፡ እመኛለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነማማና ፡
ከናባባ ፡ ከጎረቤቶቹ ፡ ጋር ፡ ተቀምጦ ፡ መመልከት ፡ እንጂ ፡ እን
ዲህ ፡ ማድረግ ፡ አልችልም ! ሌላው ፡ ይቅርና ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ ከሚ
መጡት ፡ ዘመዶቻችን ፡ ጋር ፡ ካልሆነ ፡ ከሌላ ፡ ጋር ፡ አንገቴን ፡
ቀና ፡ አድርጌ ፡ እንድናገር ፡ ወይም ፡ እንድስቅና ፡ እንድጫወት ፡
እንኩዋ ፡ አይፈቀድልኝም ! ሀእ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ! የጌታ ፡ ልጅ ፡ መ
ሆን ፡ እንዲህ ፡ እንደኔ ፡ ታስሮ ፡ መኖር ፡ የሚወዱትን ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ መመኘት ፡ እንጂ ፡ ማድረግ ፡ አለመቻል ፡ ከሆነ ፡ ከቅጣት ፡
ሁሉ ፡ የከፋ ፡ ቅጣት ፡ ከባርነት ፡ ሁሉ ፡ የከፋ ፡ ባርነት ፡ ነው !»
አለች ፡ በሻከረ ፡ ድምጽ ፡ የኑሮዋን ፡ ሁኔታ ፡ ስትዘረዝር ፡ ስቃዩ ፡
ተሰማትና ፡ አይኖችዋ ፡ እንባ ፡ ቋጥረው ።

«የለም ! እንደሱ ፡ አይደለም ፡ አይዞሽ ፡ ሆድ ፡ አይባስሽ !»
አለ ፡ በዛብህ ፤ የተዋበ ፡ ፊትዋን ፡ ለልብዋ ፡ የተሰማው ፡ መራር ፡
አዘን ፡ ማበላሸት ፡ መጀመሩን ፡ አይቶ ፡ የሚለው ፡ ቅጡ ፡ ጠፋ
ውና ።

«ከነጻነት ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ የገባሁበት ፡ ቀን ፡ ምንም ፡
ሩቅ ፡ ቢሆን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ትዝ ፡ ሲለኝ ፡ ይኖራል !» አለች ፡ ቀጠ
ለችና ፡ ልቅሶዋን ፡ ለመዋጥ ፡ እየታገለች ።

«ምናልባት ፡ የስድስት ፡ አመት ፡ ልጅ ፡ ብሆን ፡ ነው ! ከዚህ፡
አልበልጥም ፡» እጎረቤታችን ፡ አሰካለ ፡ የምትባል ፡ ጉዋደኛየ ፡
ነበረች ። ምናልባት ፡ አንድ ፡ አመት ፡ ትበልጠኝ ፡ ይሆናል ። ዛሬ፡
አራት ፡ ወይም .....አምስት ፡ ልጆች ፡ ወልዳ ፡ ትልቅ ፡ ሴት ፡ ሆና
ለች ። አንድ ፡ ቀን ፡ ስንጫወት ፡ ተጣላንና ፡ ታገልን ፡ እጭቃ ፡
ውስጥ ፡ ጥላ ፡ ፊቴን ፡ በጥፍርዋ ፡ ቡጭጭራ ፡ አደማችኝ ። ከዚያ ፡
እያለቀስሁ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ስመጣ ፡ ክፉ ፡ አጋጣሚ ፡ አባባ ፡ ከሰ

ዎች ፡ ጋር ፡ አብር ፡ ቆመው ፡ ሲነጋገሩ ፡ ነበርና ፡ በጭቃ ፡ ተነከረ፡ ፈቴ ፡ ደምቶ ፡ ሲያዩ ፡ አብደ ፡ ሆኑ ። ወዲያው ፡ የልጅቱን ፡ አባት፡ አስጠርተው ፡ ሲያበደቡት ፡ ሲሉ ፡ ሰዎች ፡ ገላግለው ፡ ሁለተኛ ፡ የሱም ፡ ልጅ ፡ ሆነች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ አጠገቤ ፡ እንዳይደርሱ ፡ አስጠንቅቀው ፡ ማሩት ። ከዚያ ፡ እያ ፡ ማሽ ፡ የልጅቱ ፡ አባት ፡ እቤቱ ፡ ሄዶ ፡ ልጁን ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ገላዋ ፡ ሁሉ ፡ እስኪቆስል ፡ ገረፋት ። እሷም ፡ ያነለት ፡ ከፉኛ ፡ ተመትቼ ፡ ከመንደሩና፡ ካሽከሮች ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ስጫወት ፡ የተገኘሁ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ የባሰ ፡ ቅጣት ፡ የሚደርስብኝ ፡ መሆኑን ፡ አባባ ፡ አስጠንቀቁኝ ። ታውቃለህ ? ያነለት ፡ አባባ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የተቆጡት ፡ ልጅቱ ፡ እኔን ፡ ስለመታችኝ ፡ አይደለም ፡ እሳቸው ፡ ስለተደፈሩ ፡ ነው !” አለች ፡ ሰብለ ፡ አይኖችዋ ፡ ሳይረግቡ ፡ ቦዘን ፡ እንዳሉ ፡ ያዘን ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ። «እንዴት ፡ ብደፈር ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ በጭቃና ፡ በደም ፡ የምትነከረው ?» ያሉት ፡ ሁልጊዜ ፡ ይታሰበኛል! በበነጋው ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዳልማዳቸው ፡ ከቀረትን ፡ ውጭ ፡ እየተንጫጩ ፡ ሲጫወቱ ፡ ስማሁና ፡ ትናንት ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ረስቼ ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ለመድረስ ፡ ቸኩዬ ፡ ልብሴን ፡ እንኳዋ ፡ በቅጡ ፡ ሳልለብስ ፡ እየሮጥሁ ፡ ብሄድ ፡ ገና ፡ ከሩቅ ፡ ሲያዩኝ ፡ የሚባላ ፡ አውሬ ፡ እንደመጣባቸው ፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሸሹ ። ያነለቱ ፡ ድንጋጤየ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አብሮኝ ፡ ይኖራል ! ከሰው ፡ የተለየሁ ፡ ሰው ፡ የሚሸሽኝ ፡ ፍጡር ፡ መሆኔን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መገንዘብ ፡ የጀመርሁበት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፡ አልረሳውም ! አብሮኝ ፡ ይኖራል !» አለች ፡ አሁንም ፡ ቅሬታ ፡ ባስጌጠው ፡ ፊት ፡ አይኑዋን ፡ ቦዘዝ ፡ አድርጋ ፡ ካስራ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ልጆቹ፡ እርስዋን ፡ ፈርተው ፡ የሮጡት ፡ ሩጫ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ እየታያት ። «ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ስቆም ፡ እነሱ ፡ እንድ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ወደኔ፡ እየተመለከቱ ፡ በጃቸው ፡ ወደኔ ፡ እያመለከቱ ፡ ይነጋገሩ ፡ ጀመር ። እንደገና ፡ ቆመልኝ ፡ ብዬ ፡ ወደነሱ ፡ ስሮጥ ፡ እነሱም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሮጡና ፡ እንደፈቱ ፡ አለመቆሜን ፡ ሲያዩ ፡ ወደ ቤታቸው ፡ ተበታተኑ ። እኔ ፡ አስካለን ፡ ትናንት ፡ የመታችኝን ፡ ልጅ ፡ ተከትዬ ፡ እስከ ፡ ቤትዋ ፡ እየሮጥሁ ፡ ሄድሁ ። አለቅስ ነበር። ከዚያ ፡ ያስካለ ፡ እናት ፡ እቴቴ ፡ ደብረቱ ፡ ያዘችኝና ፡ እንባዬን ፡

በገዛ ፡ ቀሚሴ ፡ እየጠረገች ፡ ለምን ፡ ሆንሽ ፡ የኔ ፡ እመቤት ? እይ ዞሽ ፡ አታልቅሺ !» አለችኝ ። ልሜዘውት ፡ ብመጣ ፡ እናስክለ ፡ ሮጡ ብኝ ! አልሁዋት ፡ ስታባብለኝ ፡ ጊዜ ፡ የባሰውን ፡ እያለቀስሁ ። የታ ባታቸው ፡ መጥፎ ፡ ልጆች ፡ ቆይ ፡ እኔ ፡ እመታልሻለሁ ፡ እንዲያ ውም ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ መጫወቱ ፡ ይቅርብሽ ፡ ይመቱሻል ፡ ልብስ ሽንም ፡ ያሳድፉብሻል !'' ብላ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ይዛኝ ፡ መጣች ። ከዚያ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ለልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ማስፈራሪያ ፡ ሆንሁ ! ሀብትሽ ፡ እንኩዋ ፡ እስተም ፡ እኔም ፡ ካደግን፡ በሁዋላ፡ በትእዛዝ ፡ ለኔ ፡ ተስ ጥታ ፡ በግድ ፡ እስክንላመድ ፡ ድረስ ፡ እዬፈራች ፡ ትሸሸኝ ፡ ነበር። ከዚያ :- - - - - ከዚያ ፡ እያደግሁ :- - - - እያደግሁ ፡ በሄድሁ ፡ መጠን ፡ እስራቱ ፡ እስራ.....ቱ ፡ እዬ....እዬ ... ጠነከረ ፡ ሄ...» አለችና ፡ ስቅቅ ፡ ብላ ፡ ስታለቅስ ፡ ጊዜ ፡ በባላባቱ ፡ ግራ ፡ ገባው ።

«እባክሽ ፡ አታልቅሺ ፡ ልቅሶ ፡ ክፉ ፡ ነው !» አለ ፡ እንባ ፡ ጣምራ ፡ ጣምራ ፡ እዬሆነ ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጮዋ ፡ እዬወረደ ፡ ሳግ ፡ እያነቀት ፡ ልቅሶዋን ፡ ለመዋጥ ፡ ስትታገል ፡ ትሆንው ፡ የነ በረ ፡ ሁኔታ እሳዝናት ፡ እሱም ፡ ልቅሶ ፡ መጣበትና ፡ የሱን ፡ አይ ኖች ፡ እንባ ፡ ሞልቶው ፡ በታይ ፡ ባሰባት ።

ከዚያ ፡ የሚያደርገው ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶት ፡ ከተቀመጠበት ፡ ተነስቶ ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲል ፡ ቆዬና ፡ አጠ ገብዋ ፡ ሄዶ ፡ ተቀምጦ ፡ አንገትዋን ፡ አቅንቶ ፡ እንደ ፡ ህጻን ፡ ልጅ ፡ በግራ ፡ ክንዱ ፡ አስደግፎ ፡ በቀኙ ፡ በገዛ ፡ ኩታዋ ፡ እንባ ዋን ፡ እዬጠረገ ፡ ''እባክሽ ፡ ዝም ፡ በይ ፡ እባክሽ ፡ አታልቅሺ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ለመርሳት ፡ መሞከር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሱን ፡ እያ ሰቡ ፡ ካለቀሱ ፡ ክፉ ፡ ያስከትላል! ሮሺው ፡ ደህና ፡ ነገር ፡ እስቢ ፡ ደህና ፡ እንድታገኚ! እሺ? በይ ፡ ዝም ፡ በይ!'' እያለ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጮችዋን ፡ አይኖችዋን ፡ አፍንጫዋን ፡ እየጠራረገ ፡ ሲያባብ ላት ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ጸጥ ፡ እያለች ፡ ሄደች ። እሱም ፡ አባብሎ፡ ዝም ፡ ማሰኘቱ ፡ ያን ፡ ውብ ፡ መልክ ፡ ሊያበላሽ ፡ የጎረፈውን ፡ የንባ ፡ ጎርፍ ፡ ለማገድ ፡ በመቻሉ ፡ ያን ፡ ውብ ፡ አካል ፡ ከመስ ራቱ ፡ ለማፍረስ ፡ እንደ ፡ ተነሳ ፡ ሁሉ ፡ ያንቀጠቀጠውን ፡ ማእ በል ፡ ለማቆም ፡ በመቻሉ ፡ ደስታው ፡ በፊቱ ፡ ወሰል ፡ ብሎ ፡ እዬ ታዬ ፡ በቅፉ ፡ ላይ ፡ እንዳለች ፡ አይኑን ፡ አይንዋን ፡ እዬተመለ

ከተ ፡ እንብዋ ፡ መቆሙን ፡ ረስቶ ፡ ፊትዋን ፡ በኩታዋ ፡ ማባበሱን፡ ቀጠለ፡፡

በውስጥዋ ፡ ተነስቶ ፡ የነበረው ፡ ያዘንና ፡ የምሬት ፡ ማእበል ፡ ጸጥ ፡ እያለ ፡ ሲሄድ ፡ በውስጥዋ ፡ ተነስቶ ፡ የነበረው ፡ ማእበል ፡ ያናወጠው ፡ ሙሉ ፡ አካልዋ ፡ ዘና ፡ እያለ ፡ ሲሄድ ፡ አጥልሞዋት ፡ የነበረው ፡ ከባድ ፡ ያዘን ፡ ጨለማ ፡ ከፊትዋ ፡ እየገለጠ ፡ ሲሄድ ፡ ልክ ፡ በጥሩ ፡ ሰማይ ፡ እንደምትወጣ ፡ የማለዳ ፡ ጸሀይ ፡ ብርሀንዋ ፡ ውበትዋ ፡ ሙቀትዋ ፡ በውቡ ፡ ፊትዋ ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ ብቅ፡ ይል ፡ ጀመር ፡፡ ወዲያው ፡ ራስዋ ፡ እበዛብህ ፡ ክንድ ፡ ላይ ፡ ዘና ፡ ብሎ ፡ ደገፍ ፡ እንዳለ ፡ ዘቅዝቀው ፡ የሚመለከትዋትን ፡ እፋራም፡ አይኖቹን ፡ አይኖችዋ ፡ ላይ ፡ ተተክለው ፡ ስታይ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የማታውቀው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ሙቀት ፡ በህዋሳትዋ ፡ ሁሉ ፡ ሲሰራጭ ፡ ልብዋን ፡ ሲያሞቀው ፡ ተሰማት፡፡ ወዲያው ፡ ይህ ፡ በውስጥዋ ፡ ሲሰራጭ ፡ የተሰማት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሙቀት ፡ ፊትዋን ፡ በስሱ ፡ ቀይ ፡ እንደተቀባ ፡ አስጌጠው፡፡ እንዲያ ፡ አምሯ ፡ እንዲያ ፡ ተውባ ፡ እንደ ፡ በዛብህ ፡ ክንዱን ፡ እንተርሶ ፡ ዘቅዝቆ ፡ ለሚያያት ፡ ወዬው ፡ ማማርዋ! ወዬው ፡ ማሳዘንዋ!!

በዛብህ ፡ የሰብለ ፡ ፊትና ፡ ስሜትዋ ፡ ሁሉ ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ሲለወጥ ፡ ትንፋሽዋ ፡ ሲፈጥን ፣ ልብዋ ፡ በሀይል ፡ ሲመታ ፡ ተመለከተና ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡ መሸበር ፡ ሰውነቱ ፡ ሁሉ ፡ ለስዋ ፡ እስኪሰማት ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ይል ፡ ጀመር ፡ ፈራ፡፡ ከዚያ ፡ ቀና ፡ አድርጎ ፡ አስቀምጠዋት ፡ እቦታው ፡ ሄዶ ፡ ተቀመጠና ፡ "እ. . .አሁን ፡ ተሻለሽ ፡ አይደለም? እ. .አይዞሽ !" አለ ፡ ከመሸበሩ ፡ የተነሳ ፡ ንግግሩ ፡ እዬተደናቀፈ ፤ ምን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ሳያውቅ፡፡

"ደህና ፡ ነኝ ፡፡" አለች ፡ እሱዋም ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ድንገት ፡ በሆነው ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ ብላ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዬች፡፡

ከዚያ ፡ ሁለቱም ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ስለተሰማቸው ፡ እንግዳ ፡ ስሜት ፡ ስለዚያ ፡ መልካቸውን ፡ እንዲያ ፡ ስለለዋወጠው ፡ ልባቸውን ፡ ስላስሮጠው ፡ ግሩም ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ ስሜት ፡ መነጋገርም ፡ መተያየትም ፡ ተፋፍረው ፡ ተፈራርተው ፡ እንገታ

ቸውን ፡ ደፍተው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡- "አብ ፡ ጉንደ ፡ ወይን ፡ ወልድ ፡ ጉንደ ፡ ወይን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጉንደ ፡ ወይን ፡ አለም ፡ ሁሉ ፡ ያጣፈጠበት ፡ የህይወት ፡ ወይን ፡ ነው !" አለች ፡ ሀብትሽ ፡ ከማድ ፡ ቤት ፡ እዩሮጠች ፡ መጥታ ፡ ገባ ችና ። በዛብህና ፡ ሰብለም ፡ በመሀከላቸው ፡ ከነበረው ፡ መተፋፈር ፡ የሚወጡበት ፡ ምክናያት ፡ አግኝተው ፡ እስበሳቸው ፡ ተያዩና ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ። "አሸተተ ፡ ተንፈስ ፡ እንዳንቺ ፡ ያለ ፡ መአዛና ፡ ደም ፡ ግባት ፡ አላገኘም ፡ በጣም ፡ ወደደሽ ። ወራዙት ፡ ወይም ፡ ጎበዛዝት ፡ በመአልትና ፡ በሌሊት ፡ እበርሽ ፡ ቆመው ፡ ጸሀይ ፡ እያቃጠላቸው ፡ ብርድ ፡ እያንቀጠቀጣቸው ፡ ደጅ ፡ የሚጠኑሽ ፡ አንቺ ፡ ነሽ !" አለች ፡ ቀጠለችና ፡ ሀብትሽ ፡ ሰብለ ፡ ቅዳሴ ፡ ማር ያም ፡ ትርጉም ፡ ስትማር ፡ ከሰማችው ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ከሌ ላው ፡ እደበላልቃ ፡ አንዳንዱንም ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ፈለገችው ፡ ለዋ ውጣ ። ሰብለና ፡ በዛብህ ፡ ጥሩ ፡ ምክናያት ፡ አግኝተው ፡ ከልባ ባቸው ፡ ሲስቁ ፡ ቆዩና ። "ወዬው ፡ ጉድ! አንቺ ፡ እንዲያው ፡ እግዚአብሄርን ፡ እንኳ ፡ አትፈሪም? በመቤታችን ፡ ነው ፡ እን ዲህ ፡ የምትቀልጅው?" አለች ፡ ሰብለ ።

"ለምን ፡ እፈራታለሁ! እሱዋ ፡ አትቆጣ ፡ አትማታ! ያን ቺን ፡ እናት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የምፈራ!"

"ማን ፡ እንዲህ ፡ አለ?"

"መጣፉ ፡ ነዋ! ሌላ ፡ ማን ፡ ይላል! ድንግል ፡ ሆይ ፡ ጥፋትን ፡ አይደለም ፡ ይቅርታን ፡ አሳስቢ ፡ መአትን ፡ አይደለም ፡ ምህረ ትን ፡ አሳስቢ ፡ ለጻድቃን ፡ አይደለም ፡ ለሀጣን ፡ አሳስቢ ፡ ለን ጹሆች ፡ አይደለም ፡ ለተዳደፉት ፡ አሳስቢ ፡ እንደነሰብለና ፡ እን ደነበዛብህ ፡ ላሉት ፡ አይደለም ፡ እንደነሀብትሽና ፡ እንደነገብሬ ፡ ላሉት ፡ አሳስቢ ፡ ይላል ፡ መጣፉ! አይልም ፡ በዙ?" አለች ፡ ሀብ ትሽ ፡ ከመጣች ፡ ጀምራ ፡ ሳትቀመጥ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እዩዘ ለለች ። ከዚያ ፡ ቆም ፡ አለችና ፡ እንደ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ እጆችዋን ፡ እደረትዋ ፡ ላይ ፡ አመሳቅላ ፡ ጥርስዋን ፡ ፈገግ ፡ አንገትዋን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ዘንበል ፡ አድርጋ ፡ "በዛብህ ፡ ሰብለን ፡ ይደከማ ታል ፡ እስቲ ፡ እረፍና ፡ ጨዋታ ፡ አምጣ !" ስትል ፡ ሁኔታዋን ፡ እያዩ ፡ በዛብህና ፡ ሰብለ ፡ ሳቃቸውን ፡ መግታት ፡ አቃታቸው ።

"እንዲያውም ፡ ዛሬ ፡ ማጫወቱ ፡ የኔ ፡ ፈንታ ፡ ይሁን፡፡ የዚያ ፡ የገብሬ ፡ እንዲር ፡ ልቤን ፡ በደስታ ፡ ሞልቶ ፡ ድምጼን፡ ለዘፈን ፡ ቃኝቶ ፡ ሰዶኛል !" አለችና ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ከወዲያ ወዲህ ፡ እዬተንጎራደደች ፡-

"ሌሊቱ ፡ እያጠረ ፡ እንዲህ ፡ ካስቸገረ ፡-

አንተናኔ ፡-

አንቺናኔ ፡

ሳንሞት ፡ እንቀበር ፡ ተኝተን ፡ እንድኖር ፡-" ብላ ፡ በዚያ ፡ መሰል ፡ በሌሰው ፡ ውብ ፡ ድምጽዋ ፡ ዘፈነችና ፡ ከዚያ ፡ ቀጥላ ፡ እዬተንበረከከችም ፡ እዬቆመችም ፡ ባንገትዋ ፡ ዘፍና ፡ ሲደክማት ፡ ወድቃ ፡ ከላይ ፡ ከላይ ፡ እዬተነፈሰች ፡ ትስቅ ፡ ጀመር ፡፡

"አንቺው ፡ ቀናቃኝ ፡ አንቺው ፡ ተቀባይ ፡ አንቺው ፡ ደላቂ ፡ አንቺው ፡ አድማቂ ፡ ሆነሽ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ስራ ፡ ብቻሽን፡ ሰርተሽ ፡ ደከመሽ !" አለ ፡ በዛብህ ፡ እየሳቀ ፡፡

"ምናባቴን ፡ ላድርግ ? እግዚአብሄር ፡ ወኔ ፡ ባልተፈጠረባችሁ ፡ ልባችሁ ፡ ከበረዶ ፡ በተሰራ ፡ ሁለት ፡ ደንጋዮች ፡ መሀከል ፡ ሲጥለኝ ፡ ጊዜ? እስቲ ፡ ሰብለ ፡ ተነሺና ፡ ሁለታችን፡ እንዝፈን !" አለች ፡ ሀብትሽ ፡ ደክሞዋት ፡ ከላይ ፡ ከላይ ፡ እዬተነፈሰች ፡፡

"ዎዎ .... አንቺ ፡ የደላሽ ፡ ነሽ ፡ እናቴ !" አለች ሰብለ ፡፡

"ዋደላሽ! እንደኔ ፡ እንዲደላሽ ፡ ከባሪያ ፡ አትወለጅም ፡ ኖረሻል ? ማን ፡ ከፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ተወለጅ ፡ አለሽ !"

"አይንሽን ፡ ያብሪው !" አለች ፡ ሰብለ ፡ እዬሳቀች ፡፡

"እ ፡ እ ! አይኔስ ፡ ይቆይልኝ ፡ እናቴ ! አይኔ ፡ ከበረረማ ፡ አለቀልኝ ፡ ማለት ፡ ነው ! የባሪያ ፡ እውር ፡ እንደ ፡ ሰባራ ፡ ገል ፡ ዋጋ ፡ የሰውም ፡ አውጥቶ ፡ መወርወር ፡ ብቻ ፡ ነው !" ብላ ፡ ሀብትሽ ፡ እንደገና ፡ ዘፈንዋን ፡ ለመቀጠል ፡ እንጉድጉዶ ፡ ስትጀምር ፡-

"ትምርቱ ፡ አልቆ ፡ ነው ፡ ይቺ ፡ አህያ ፡ ስትለፈልፍ ፡ እስከ ፡ በሩ ፡ የምትሰማ ?" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ከሄዱበት ፡

ተመልሰው ፡ ድንገት ፡ ገቡና ።

" አዎ ፡ ጨርሰናል !" አለች ፡ ሰብለ ። " አዎ !" አሉ ፡ በዛብህም ።

ሀብትሽ ፡ እመቤትዋ ፡ ድንገት ፡ ሲገቡ ፡ ደንግጣ ፡ ጥግ ፡ ይዛ ፡ እንደ ፡ ቆመች ፡ አንገትዋን ፡ ደፍታ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ ስታይ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የነበረችው ፡ ሀብትሽ ፡ አትመስልም ፡ ነበር ።

# ምእራፍ ፡ ፳ ፡

# የባላገሮች ፡ አድማ ፡

ወደ ፡ ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ተልከው ፡ ሄደው ፡ የነበሩት ፡ ሶስት ፡ የባላገር ፡ መላክተኞች ፡ በማላጅ ፡ ተለቀው ፡ ወደ ፡ ይገራቸው ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ የሶስቱ ፡ ጉልቶች ፡ ባላገሮች ፡ መላክተኞቻቸው ፡ ከፈታውራሪ ፡ ያመጡትን ፡ መልስ ፡ ለመስማትና ፡ ወደፊት ፡ የሚያደርጉትን ፡ ለመወሰን ፡ እናሞራ ፡ ላይ ፡ ተሰበሰቡ ። አበጀ ፡ በለው ፡ መያገር ፡ አድርጎ ፡ ሲያስጠብቃቸው ፡ የሰነበቱት ፡ የፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አምስት ፡ አሽከሮችም ፡ በስብሰባው ፡ እንዲገኙ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ።

"ዘመዱ !" አሉ ፡ ብላታ ፡ ንጉሴ ፡ የሚባሉት ፡ ለጉሊት ፡ ህዝብ ፡ መላክተኛ ፡ ሆነው ፡ ከጎርጎራና ፡ ከናሞራ ፡ መላክተኞች፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ተልከው ፡ የነበሩት ፡ ሽማግሌ፡ ድምጻቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ። "ዘመዱ ! የንጨት ፡ ልጅ ፡ እሳት ፡ የሳት ፡ ልጅ ፡ አመድ ፡ የሚባለው ፡ ተረት ፡ የድሮ ፡ ተረት፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ ለፈታውራሪ ፡ በሪሁንና ፡ ለልጃቸው ፡ ለፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የተተረተ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ በተቻለ ፡ ነበር። እንደኔ ፡ በድሜ ፡ የታደላችሁ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እንደምታውቁዋቸው ፡ ፈታውራሪ ፡ በሪሁን ፡ ለተራበ ፡ ፍሬያቸውን ፡ ለደከመው ፡ ጥላቸውን ፡ የማይነፍጉ ፡ ታላቅ ፡ ወርካ ፡ ታላቅ ፡ ግንድ ፡ ነበሩ። ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ባላገር ፡ ግፍ ፡ ለመቀበል ፡ የተሰራ ፡ በመሆኑ ፡ በሳቸው ፡ ጊዜም ፡ አባቶቻችን ፡ መበደላቸው ፡ ባይቀር ፡ በደላቸውን ፡ ሄደው ፡ ሲያመለክቱ ፡ ፈታውራሪ ፡ በሪሁን ፡ አዝነው ፡ ሹሞቻቸውን ፡ ተቆጥተው ፡ ተልከው ፡ የሄዱትን ፡ ሽማግሌዎች ፡ አባብለውና ፡ በመልካም ፡ ፊት ፡ አስተናግደው ፡ ከተቀበሉት ፡ ብዙ ፡ ትንሽ ፡ ሰጥተው ፡ ይሸኙዋቸው ፡ ነበር ። ፈታውራሪ ፡ በሪሁን ፡ መውሰድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ መስጠት ፡ ጭምር ፡ የሚያውቁ ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ ሰጥተው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ጌታ ፡ ነበሩ ።

"እንዲያ ፡ ያሉት ፡ ደግ ፡ እንዲያ ፡ ያሉት ፡ ለምለም ፡

ግንድ ፡ ማለፍ ፡ አይቀርም ፡ ሲያልፉ ፡ እንደ ፡ ተረቱ ፡ በቦታ ቸው ፡ እሳት ፡ ተተካ፡፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ የሚፈጅ ፡ ርጥብ ፡ ከደ ረቅ ፡ ሳይለይ ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ የሚበላ ፡ የቁዋያ ፡ እሳት ፡ በቦታቸው ፡ ተተካ፡፡ እንደምታውቁት ፡ የቁዋያ ፡ እሳት ፡ ርጥብ ፡ ከደረቅ ፡ ቡቃያ ፡ ከድግ ፡ አበባ ፡ ከፍሬ ፡ ሳይለይ ፡ ሁሉንም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ፈጅቶ ፡ ሁሉንም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አመድ ፡ አድርጎ ፡ .. ራሱም ... አመድ ፡ የሚሆን ፡ ነው !" ሲሉ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብለው ፡ የተሰበሰበው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሳቀ ፡፡ "የሚያ ስገርም ፡ ነው !" አሉ ፡ ቀጠሉና፡፡ "የሚያስገርም፡ ነው !" ተበድለናልና ፡ በደላችነን ፡ ይዩልን ፡ ብላችሁ ፡ ልካችሁ ፡ ብትሰዱን ፡ ገና ፡ መላከታችነን ፡ ስንናገር ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ እንደ ፡ ተራበ ፡ አውሬ ፡ በብርቱ ፡ ቁጣና ፡ እንደ ፡ ባሰኔ ፡ በስድብ ፡ ተቀበሉን ፡፡ እኛን ፡ ሶስት ፡ ደካሞች ፡ ሽማግሌዎች ፡ እግር ፡ ከወርች ፡ አሳስሬ ፡ አስደበድባለሁ ፡ ብለው ፡ እማላ ጆችን ፡ ሲያስቸግሩና ፡ በማንገላታት ፡ ብዛት ፡ እዚያ ፡ ሰንጋ ፡ ሊያስወልዱን ፡ ይችሉ ፡ ይመስል ፡ ሶስት ጊዜ ፡ እያስጎተቱ ፡ አስገብተው ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ እያስገፉ ፡ እያዳፉ ፡ እያስወጡ ፡ እኛን ፡ ባዩ ፡ ቁጥር ፡ ይሆኑት ፡ የነበረውን ፡ ሁኔታ ፡ ብታዩ ፡ ከኛ ፡ ከተንገላታነው ፡ ይልቅ ፡ ሰሳቸው ፡ ታዝኑላቸው ፡ ነበር ፡፡ ገንዘብ ፡ መውደዳቸው ፡ ጉምዥታቸው ፡ ከመጠን ፡ አልፎ ፡ በሽታ ፡ ሆኖባቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ በጤናው ፡ እንዲያ ፡ አይሆንም ፡፡ እንዲያ ፡ ተንገላተን ፡ እንዲያ ፡ ተጉላ ልተን ፡ ሰንጋ ፡ ከውስጣችን ፡ ጠብ ፡ ሊል ፡ እንደማይችል ፡ ከተረዱ ፡ በሁዋላ ፡ እስከ ፡ ሶስት ፡ ወር ፡ ስድስት ፡ ሰንጋ ፡ ያላመጣችሁ ፡ እንደሆነ ፡ መቸያ ፡ ልኬ ፡ አዘርፋችሁዋለሁ ፡ ብለው ፡ ሰደዱን ፡፡

"አሁን ፡ የምነግራችሁ ፡ እኔና ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ የላካችሁዋ ቸው ፡ ሁለቱ ፡ ጉዋደኞቼ ፡ ሶስት ፡ ፍሪዳ ፡ አሁን ፡ ሰመክፈል ፡ አቅማችን ፡ አይችልም ፡ ብላችሁ ፡ የላካችሁትን ፡ መላክት ፡ አድርሰን ፡ ያመጣንላችሁ ፡ መልስ ፡ በሶስት ፡ ፍሪዳ ፡ ፈንታ ፡ ስድስት ፡ ፍሪዳ ፡ ያልከፈላችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ቤታችሁ ፡ በመ ቸያ ፡ ይዘረፋል ፡ የሚል ፡ መሆኑን ፡ ነው ፡፡ ስድስት ፍሪዳ ፡

እንከፍላለን ፡ ወይም ፡ እንከፍልም ፡ ማለቱ ፡ የፍንች ፡ ፈንታ ፡ ነው ።" ብለው ፡ ሲጨርሱ ፡ እዚያ ፡ ከሰፈረው ፡ ህዝብ ፡ ፊታውራሪን ፡ የሚሰድበው ፡ ሲሰድብ ፡ የሚረግመው ፡ ሲረግም ፡ ጫጫታው ፡ እንደሜዳ ፡ ገበያተኛ ፡ ጫጫታ ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

ጫጫታው ፡ ትንሽ ፡ ጸጥ ፡ ሲል ፡ ከሶስቱ ፡ ጉልቶች ፡ አንዳንዶቹ ፡ እየተነሱ ፡ "ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቱልጉ ፡ አሺን ፡ ብለው ፡ ወዳገራችን ፡ የመጡ ፡ እንደ ሆን ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ እጃቸውን ፡ የፊጥኝ ፡ አስረን ፡ ወስደን ፡ ለመንግስት ፡ እናስረክባቸዋለን ፡ እንዳበደ ፡ ውሻ ፡ ደብድበን ፡ እንገድላቸዋለን ፡ ለከፋ ፡ ገዢ ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ ቅጣት ፡ እንቀጣቸዋለን ፡ አጥርደን ፡ ላገር ፡ መሳቂያ ፡ እናደርጋቸዋለን ።" እያሉ ፡ የቀጣ ፡ ስሜታቸውን ፡ እየገለጹ ፡ ከተቀመጡ ፡ በሁዋላ ፡ ከናሞራ ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ተነስተው ፡ ድምጻቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ "ስሙኝ ፡ ዘመዶች ፡ ስሙኝ !" ሲሉ ፡ ሁሉም ፡ ሽማግሌውን ፡ ለመስማት ፡ ዝም ፡ አለ ።

" ቅጣ ፡ አያስፈልግም ፡ ቅጣ ፡ የባላገር ፡ ገንዘብ ፡ አይደለም ፡ የባላገር ፡ ገንዘቡ ፡ በትግስት ፡ በማስተዋል ፡ ተመካክሮ ፡ የሚበጀውን ፡ ማድረግ ፡ ነው ! ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ምሳሌ ፡ የሌላቸው ፡ አስቸጋሪ ፡ ሰው ፡ ናቸው ። ካንድ ፡ ወገን ፡ አቅማቸውንም ፡ ጥቅማቸውንም ፡ የማያውቁ ፡ ሞኝ ፡ በመሆናቸው ፡ እንደ ፡ ሞኞች ፡ ሁሉ ፡ ሊታዘንላቸው ፡ ሲገባ ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡ ችግር ፡ የማይሰማቸው ፡ ጨካኝ ፡ ስለሆኑ ፡ መጠላት ፡ የሚገባቸው ፡ ናቸው ። ከእንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ መለየት ፡ ከከፋ ፡ በሽታ ፡ እንደ ፡ መዳን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ። አሁን ፡ እግዚአብሄር ፡ ይስጣቸውና ፡ የምንለያይበትን ፡ መንገድ ፡ ራሳቸው ፡ ስላበጁልን ፡ ይህን ፡ የተደላደለን ፡ መንገድ ፡ ተከትለን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ መሄድ ፡ አለብን ። ይህ ፡ መልካም ፡ አጋጣሚ ፡ እንዳያመልጠን !

" ከውስጣችንም ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ የሚነሱትን ፡ ሌቦችና ፡ ቀማኞች ፡ በሌባደማችን ፡ በጎበዝ ፡ አለቆችን ፡ አስጠብቀን ፡ የምናስያዛቸው ፡ ከሆነ ፡ መተዳደሪያ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይዘን ፡

ወይ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የምንሄድበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። በመሀከላችን ፡ ጥል ፡ ቢነሳ ፡ የዘመድ ፡ ሽማግሌዎቻችንን ፡ የዘመድ ፡ ዳኞቻችንን ፡ እየተስማማን ፡ እየመረጥን ፡ ነገራችንን ፡ ከነገራችን ፡ ሳንወጣ ፡ ከጨረስን ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በግድ ፡ ተጣልታችሁ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ እየመጣችሁ ፡ ዳኝነትና ፡ ውርርድ ፡ ካልከፈላችሁ ፡ ብለው ፡ ምንም ፡ ሊያደርጉን ፡ አይችሉም ። ሌባና ፡ ቀማኞችሁን ፡ ፈልጋችሁ ፡ ያዛችሁ ፡ ወይም ፡ ተጣልታችሁ ፡ መጥታችሁ ፡ ለኔ ፡ ዳኝነትና ፡ ውርርድ ፡ አልከፈላችሁም ፡ ብለው ፡ ሊጣሉን ፡ ከመጡም ፡ ያው ፡ ያላገባብ ፡ ያለህግ ፡ ሊዘርፉን ፡ ሊቀሙን ፡ መምጣታቸው ፡ ስለሆነ ፡ እንደ ፡ ቀማኛ ፡ ቆጥረን ፡ ለቀማኛ ፡ የሚገባውን ፡ አሰናድተን ፡ እንጠብቃቸዋለን ። ቅድም ፡ እንዳልሁት ፡ መቼም ፡ አቅማቸውን ፡ የማያውቁ ፡ የሞኝ ፡ ጥጋበኛ ፡ ናቸውና ፡ “ሞኝ ፡ ገበሬ ፡ አውሬ ፡ ሲያድን ፡ በሬውን ፡ አውሬ ፡ ያስበላል ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ ያልተሰራላቸውን ፡ ለመብላት ፡ ጥል ፡ ሲያጭሩ ፡ የተሰራላቸውን ፡ የሚያሳጣ ፡ መንገድ ፡ ይመርጡ ፡ ይሆናል ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ከሳቸው ፡ ጋር ፡ ጨርሰን ፡ እንለያይ ፡ ይሆናል !” ብለው ፡ ንግግራቸውን ፡ ሲጨርሱ ፡ ከሶስቱም ፡ ጉልቶች ፡ ሌሎች ፡ ሽማግሌዎች ፡ እንደየባንድ ፡ እየተነሱ ፡ ፊታውራሪ ፡ በየጊዜው ፡ የሰሩትን ፡ የጭካኔና ፡ የግፍ ፡ ስራ ፡ እየዘረዘሩ ፡ ከተናገሩ ፡ በኋላ ፡ ሸንጎው ፡ በሙሉ ፡ በናሞራው ፡ ሽማግሌ ፡ አሳብ ፡ በማሌና ፡ በማዘት ፡ ተስማምቶ ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከሶስቱ ፡ ጉልቶች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ እፊታውራሪ ፡ ደጅ ፡ በምንም ፡ ምክንያት ፡ የደረሰ ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡ ከሀዲ ፡ እንዲቆጠርና ፡ ቢታመም ፡ ጠያቂ ፡ ቢሞት ፡ ቀባሪ ፡ እንዳያገኝ ፡ ተወስኖ ፡ አበጀ ፡ በለው ፡ ለጊዜው ፡ ተሹሞት ፡ የነበረው ፡ የጎበዝ ፡ አለቅነት ፡ ለሁልጊዜ ፡ እንዲሆን ፡ ተደርጎ ፡ ተይዘው ፡ የሰንበቴቱ ፡ የፊታውራሪ ፡ አሽከሮች ፡ ይሆን ፡ የተወሰነውን ፡ ሁሉ ፡ ሄደው ፡ ለጌታቸው ፡ እንዲነግሩ ፡ ተደርጎ ፡ ስብሰባው ፡ ተነሳ ።

ፊታውራሪ ፡ የባላገሮችን ፡ አድማ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አድማው ፡ ሲደረግ ፡ እያንዳንዱ ፡ ባላገር ፡ እየተነሳ ፡ የተናገረውን ፡ ተረቱን ፡ ፌዙን ፡ ሳቁን ፡ ስድቡን ፡ ርግማኑን ፡

ጭምር ፡ ተይዘው ፡ ሰንብተው ፡ ከመጡት ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ሲሰሙ ፡ ከቁጣቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ ስሜታቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ የሚበቃ ፡ ቃል ፡ ስላጡ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ይንቀጠቀጡ ፡ ጀመር ። ከዚያ ፡ እንደብድ ፡ ምሽታቸውና ፡ ልጃቸው ፡ ከሴቶች ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ጋር ፡ ወደሚጫወቱበት ፡ ቤት ፡ እልፍኝ ፡ ሄደው ፡ ትንሽ ፡ ቆም ፡ ብለው ፡ አይናቸውን ፡ ካፎቱ ፡ በሙሉ ፡ አውጥተው ፡ ፍጥጥ ፡ አድርገው ፡ አዩና ፡ ምንም ፡ ሳይናገሩ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ወንድ ፡ እልፍኛቸው ፡ ተመልሰው ፡ ሄደው ፡ ተቀመጡ ። ከዚያ ፡ ተነስተው ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ እያንኮራፉ ፡ እልፍኛቸው ፡ ውስጥ ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይሉ ፡ ጀመር ። ማንኮራፋት ፡ ከጀመሩ ፡ የቁጣው ፡ ትኩሳት ፡ ወደ ፡ ተለመደው ፡ ወደ ፡ ደንበኛው ፡ የቁጣ ፡ ደረጃ ፡ ወረደ ፡ ማለት ፡ ነው ! “ወይ ፡ እኔ ፡ መሸሻ !”አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ጠቋሚ ፡ ጣታቸውን ፡ ካውራ ፡ ጣታቸው ጋር ፡ እያጮሉ ፡ “ወይ ፡ እኔ ፡ መሸሻ ፡ ወይ ፡ እኔ ፡ የደፋር ፡ ጌታ እዚህ ፡ ደረስኩ ! የባላገር ፡ መጫወቻ ፡ ሆንሁ !”

የናሞራው ፡ ሽማግሌ ፡ ባድማው ፡ ሸንጎ ፡ እንዳሉት ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ምሳሌ ፡ የሌላቸው ፡ እጅግ ፡ አስቸጋሪና ፡ ብዙ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ባህሪዎች ፡ የነበሩዋቸው ፡ ሰው ፡ ነበሩ ።

ትንሽ ፡ ያዘኑ ፡ ወይም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ያዩ ፡ እንደሆን ፡ አይኖቻቸው ፡ ቶሎ ፡ እንባ ፡ ስለሚሞሉ ፡ ገርና ፡ በጣም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ይመስላሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የተጣሉትን ፡ ሰው ፡ ለማሰቃየት ፡ ወይም ፡ ሲሰቃይ ፡ ለማየት ፡ ልባቸው ፡ ካለት ፡ ድንጋይ ፡ እንደ ፡ ተሰራ ፡ ሁሉ ፡ ትንሽ ፡ እንኩዋ ፡ ነቅንቅ ፡ አይልም ። እቤታቸው ፡ ለሚሄደው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘመድ ፡ ይሁን ፡ ባእድ ፡ ሲያበሉና ፡ ሲያጠጡ ፡ ለለመናቸውም ፡ ሁሉ ፡ ባይኖራቸው ፡ እንኩዋ ፡ ተበድረው ፡ ገንዘብ ፡ ሲሰጡ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ለጋስ ፡ ይመስላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሹምና ፡ ከባላገር ፡ ጋር በቁና ፡ ባቁላ ፡ ወይም ፡ በተፋ ፡ ቅቤ ፡ ምርር ፡ ያለ ፡ ጥል ፡ ሲጣሉ ፡ ይታያሉ ። ለድሀ ፡ ገንዘብ ፡ መስጠት ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ይሰብካሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ድሀ ፡ ገንዘብ ፡ ሲኖረው ፡ አይወዱም ። ሰው ፡ ለክብሩ ፡ ሀይወቱን ፡ እንኩዋ ፡

ማሳለፍ ፡ ይገባዋል ፡ ይላሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለክብሩ ፡ የቆመ ፡ ሰው ፡ ደመኛቸው ፡ ነው ። እንደ ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አጥብቀው ፡ ይወዳሉ ፡ አዲስ ፡ አሳብ ግን ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ይጠላሉ ። የሰው ፡ አሳብ ፡ መቀበል ፡ በጣም ፡ ይከብዳቸዋል ፡ የሳቸውን ፡ አሳብ ፡ የማይቀበል ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሰደባቸው ፡ ሁሉ ፡ ይቀየሙታል ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲያከብራቸው ፡ አጥብቀው ፡ ይፈልጋሉ ፡ እሳቸው ፡ ግን ፡ ሌሎችን እንደ ፡ ትንኝ ፡ ይንቃሉ ። ብቻ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ ሞትንም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ይንቁ ፡ ስለነበረና ፡ ጥሩ ፡ ጀግና ፡ ስለነበሩ ፡ የሚወዷቸው ፡ ጥቂቶች ፡ ቢሆኑ ፡ የሚያደንቋቸውና፡ የሚያከብሩዋቸው ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ። ይህ ፡ ከዘመዱም ፡ ከባእዱም ፡ የሚሰሙት ፡ አድንቆት ፡ ይህ ፡ ከቅርብም ፡ ሆነ ፡ ከሩቅ፡ እየተሰበሰበ ፡ የድሮ ፡ ጀብዳቸውን ፡ ትናንት ፡ ወይም ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ሰሩት ፡ አድሰውና ፡ አጋንነው ፡ አሹርተው ፡ ዋጋቸውን ፡ እስኪጠግቡ ፡ ጠጅ ፡ ጠጥተው ፡ ለመሄድ ፡ የሚፈልጉ ፡ ቀላዋጮች ፡ የሚያደንቋቸው ፡ አድንቆት ፡ ይህ ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ነበር ፡ ፊታውራሪን ፡ ከትቢትና ፡ ከኩራት ፡ በሽታቸው ፡ እንዳይድኑ ፡ የሚከለክላቸው። ከሀያና ፡ ከሀያ ፡ አምስት ፡ አመት ፡ በፊት ፡ ይሰሩት ፡ የነበረውን ፡ ጀብድ ፡ ይሰሩት ፡ የነበረውን ፡ ጀግንነት ፡ ትናንት ፡ ወይም ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ሰሩት ፡ እየታደሰና ፡ እየተደጋገመ ፡ ሲሰሙት ፡ ከሀያ ፡ ወይም ፡ ከሀያ ፡ አምስት ፡ አመት ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ ዘመን ፡ የሚኖሩ ፡ እየመሰላቸው ፡ ያለፈው ፡ ሀያ ፡ ወይም ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ አመት ፡ አቅማቸውን ፡ ሀያ ፡ ወይም ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ጊዜ ፡ የቀነሰው ፡ መሆኑን ፡ ይረሱታል ። አይናቸው ፡ የደከመ ፡ ጉልበታቸው ፡ የላመ ፡ ከሰባ ፡ አመት ፡ በላይ ፡ የሆናቸው ፡ ሽማግሌ ፡ መሆናቸውን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይረሱታል ። በጎልማስነታቸው ፡ ስለ ፡ ሰሩት ፡ የጀግንነት ፡ ስራ ፡ ስለ ፡ ሰሩት ፡ ጀብድ ፡ አዝማሪው ፡ አቅራሪው ፡ ጎበዙ ፡ ቆንጆው ፡ በዩበኩሉ ፡ ይዘፍነው ፡ የነበረውን ፡ ባልቴቱ ፡ ሽማግሌው ፡ ያወራው ፡ የነበረውን ፡ እየታደሰ ፡ እየተደጋገመ ፡ ከቀላዋጮቻቸው ፡ አፍ ፡ ሲሰሙት ፡ በጎልማስነታቸው ፡ ዘመን ፡ የሚኖሩ ፡ እየመሰላቸው ፡ ከሰባ ፡ አመት ፡

በላይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የሰሳሳ ፡ ዓመት ፡ ጎልማሳ ፡ የሚሰራውን፡ መስራት ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ይረሱታል፡፡

ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በመስረቱ ፡ ባላገርን ፡ አጥብቀው ፡ የሚንቁ ፡ ባላገር ፡ ለመኩዋንንት ፡ የተፈጠረ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ መኩዋንንት ፡ የተፈጠረ ፡ የማይመስላቸው ፡ ሰው ፡ ነበሩ፡፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከባላገር ፡ መሀከል ፡ የሚወጡትን ፡ ጀግኖች ፡ ቢያደንቁና ፡ ቢያመሰግኑም፡- የባላገር ፡ ጀግንነት ፡ እዚያው ፡ ለቢጤው ፡ እዚያው ፡ ለባላገር ፡ እንጂ ፡ የባላገርን ፡ ድንበር ፡ ዘሎ ፡ ከመኩዋንንት ፡ ጀግንነት ፡ ጋር ፡ ሊመዛዘን ፡ ይችል ፡ ይሆን? ብሰው ፡ ባሳባቸው ፡ ውስጥ ፡ እንኩዋ ፡ አግብተውት ፡ አያውቁም ፡፡ ባላገር ፡ ለመኩዋንንት ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ መኩዋንንት ፡ የተፈጠረ፡ ባለመሆኑ፡ መኩዋንንትን ፡ ማክበር ፡ መኩዋንንትን ፡ መፍራት ፡ እንደሚገባው ፡- የባላገር ፡ ጥይትም ፡ እንደ ፡ ባለቤቱ ፡ መኩዋንንትን ፡ የሚፈራ ፡ ይመስላቸዋል፡፡

ስለዚህ ፡- የባላገሮችን ፡ አድማ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ እዬጨማመሩ ፡ እያጋነኑ ፡ ሲነግሩዋቸው ፡- እንዲያው ፡ አድማው ፡ መታሰቡ ፡ እሳቸውን ፡ የመናቅ ፡ ምልክት ፡ ስለመሰላቸው ፡ በጣም ፡ ተበሳጩ ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ የባላገር ፡ አድማ ፡ ለጊዜው ፡ እሳቸውን ፡ ከማበሳጨት ፡ አልፎ ፡ ሌሳ ፡ ነገር ፡ ሊያስከትል ፡ ይችል ፡ ይሆን ? ብሰው ፡ ባሳባቸው ፡ ጥርጥር ፡ እንኩዋ ፡ አልገባም፡፡-

እጆቻቸውን ፡ ወደሁዋላ ፡ በጀርባቸው ፡ ላይ ፡ አያይዘው ፡ ራሳቸውን ፡ ደፋ ፡ አድርገው ፡ እወንድ ፡ እልፍኛቸው ፡ ውስጥ ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ! ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እያሉ፡ የባላገርን ፡ አድመኞች ፡ የሚቀጡበትን ፡ ቅጣት ፡ ሲያማርጡ ፡ በራሳቸው ፡ ውስጥ ፡ ከሚተራመሰው ፡ ብዙ ፡ ተሳሳፊ ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡ ጎላ ፡ ብሎ ታያቸውና ፡ ትንሽ ፡ ቆም ፡ ብሰው ፡ ራሳቸውን ፡ ቀና ፡ አድርገው ፡ ፊትለፊት ፡ አይናቸውን ፡ ሳያረግቡ ፡ ሲመለከቱ ፡ ቆይተው ፡ በቁጣ ፡ ተከመታትሮ ፡ የነበረው ፡ ፊታቸው ፡ ትንሽበትንሽ ፡ እንደ ፡ መፍታታት ፡ እያለ ፡ ሄዶ ፡ በመጨረሻ ፡ ፈገግ ፡ ሲል ፡ ላሽከሮቻቸው

ሁሉ ፡ ጎልቶ ፡ ስለታዩ ፡ ምን ፡ አሰቡ ፡ ይሆን ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ሁሉም ፡ ባይናቸው ፡ ተጠያዩቁ ።

የባላገር ፡ አድማ ፡ የባላገር ፡ መሸፈት ፡ በሶስቱ ፡ ለም ፡ ጉልቶቻቸው ፡ ላለው ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ባለቤት ፡ ያደረጋቸው ፡ መሆኑ ፡ ድንገት ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ፡ ስሚታቸው ፡ ስሚታቸውን ፡ ተከትሎ ፡ ፊታቸው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲለወጥ ፡ ታዩ ።

መቸም ፡ በልማዱ ፡ ባላገር ፡ ሸፈተ ፡ ሲባል ፡- ብርቱ ፡ ጦር ፡ ያለው ፡ መኳንንት ፡ ይታዘዝና ፡ ሸፈተ ፡ የተባለውን ፡ ባላገር ፡ ወግቶ ፡ አሳምኖ ፡ ከብቱን ፡ ንብረቱን ፡ ሁሉ ፡ ሙልጭ ፡ አድርጎ ፡ ዘርፎ ፡ ሰራሱና ፡ ለዘራፊ ፡ ሰራዊቱ ፡ እንዲያደርግ ፡ ይፈቀድለታል ። ብቻ ፡- ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በፊታውራሪ ፡ ጉልቶች ፡ የሚኖረው ፡ ባላገር ፡ የተሰራበትን ፡ ግብር ፡ አልከፍልም ፡ ስላላለ ፡ ሸፈተ ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ። ሁለተኛ ፡ የዘላይ ፡ ባለስልጣን ፡ አውቆት ፡ ሸፈተ ፡ በተባለው ፡ ባላገር ፡ ላይ ፡ እንዲዘመትበት ፡ ፈቃድ ፡ ተጠይቆ ፡ አልተሰጠም ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ በፊታውራሪ ፡ አሳብ ፡ ጭራሽ ፡ አልገባም ። በሳቸው ፡ አሳብ ፡ ያመትባል ፡ መዋያ ፡ ሊያመጣ ፡ ያልቻለ ፡ ባላገር ፡ እንደሸፍታ ፡ መቆጠር ፡ አለበት ፤ ከብቱ ፡ ንብረቱ ፡ መዘረፍ ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ መንዳትና ፡ መጫን ፡ ከቻሉ ፡- በሶስቱ ፡ ለም ፡ ጉልቶች ፡ የሚገኘው ፡ ላም ፡ በሬ ፡ በግ ፡ ፍዬል ፡ ማሩ ፡ ቅቤው ፡ እሞሌው ፡ ብሩ ፡ ለሳቸው ፡ መሆን ፡ አለበት ! ይህ ፡ ትዝ ፡ ሲላቸው ፡ ድንገት ፡ ባዘን ፡ ፋንታ ፡ ደስታ ፡ በቁጣ ፡ ፋንታ ፡ ሊቃ ፡ ተሰማቸውና ፡ ፊታቸው ፡ ሁሉ ፡ ተለወጠ ።

“ ወይ ፡ ግሩም ! እንደ ፡ ባላገርኮ ፡ ቸር ፡ የለም ! ” አሉ ፡ ወደ ፡ መሰረት ፡ ተሰራ ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ አሉና ። መሰረት ፡ ተሰራ ፡ የልፍኝ ፡ እስከ ልካይነቱንም ፡ አጋፋሪነቱንም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አጣምሮ ፡ የያዘ ፡ አሽከራቸው ፡ ነው ።

“ እንዴት ? ” አለ ፡ መሰረት ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የጌታው ፡ ስሜትና ፡ መልክ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲለዋወጥ ፡ በማየቱ ፡ በጤናቸው ፡ ይሆን ? ብሎ እዩተጠራጠረ ።

"ስድስት ፡ ፍሪዳ ፡ ከሶስት ፡ አገር ፡ አዋጥተህ ፡ ስጠን ፡ ብንለው ፡ የለም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ተበድለህ ፡ ኖረሀልና ፡ ከብታችንን ፡ ሁሉ ፡ ውሰድ ፡ አለን ! አንድ ፡ እንስራ ፡ ቅቤ ፡ አንድ ፡ እንስራ ፡ ማር ፡ ላመትባል ፡ መዋያ ፡ ስጠን ፡ ስንለው ፡ የሚያለቅሰው ፡ ባላገር ፡- አሁን ፡ ናና ፡ ማራችንን ፡ ቅቤያችንን ፡ ብራችንን ፡ ሁሉ ፡ ውሰድ ፡ አለን ! ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ይቅርና ፡ ይህን ፡ ያክልስ ፡ ቸርነት ፡ አይታችሁ ፡ ታውቃላችሁ ?" አሉ ፡ በውነተኛ ፡ የደስታ ፡ ፊት ።

" ቢወስዱትም ፡ ወጣተው ፡ ይውሰዱት ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ እንዲያው ፡ ይውሰዱትኮ ፡ አላለም ! ከባላገር ፡ ጋር ፡ መዋጋት ፡ ደግሞ ---" አለና ፡ ሊናገር ፡ የፈለገውን ፡ ጨርሶ ፡ እንዳይናገር ፡ ፈሪ ፡ ይሉኛል ፡ ብሎ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ ዝም ፡ አለ ።

" እኔ ፡ ከሃይሁ ፡ ባላገር ፡ አፈሩ ፡ ቆም ፡ ነው ፡ እመዋጋት ፡ የምንደርሰው ? እንዲያው ፡ ውጊስን ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ! "

"ጥንት ፡ የተሰራብንን ፡ እዳ ፡ እንከፍልም ፡ ሳንል ፡ ሊወጉን ፡ ከመጡ ፡ እንወጋቸዋለን ፡ ብሎ ፡ ባላገር ፡ ቆርጦዋል ፡ መሰናዶውም ፡ እንዲህ ፡ አይደለም !" አለ ፡ ተይዘው ፡ ስንብተው ፡ ከመጡት ፡ አሽከሮች ፡ አንዱ ።

" አዎ ፡ ያይጡች ፡ መሰናዶ ፡ ያይጡች ፡ አድማ ፡ ድመት ፡ እስኪደርስ ፡ የሚሉት ፡ ተረት ፡ ነው ! በል ፡ ይልቅ ፡ ተሰናዱ ። መሰረት ፡ ሁሉንም ፡ ተሰናዱ ፡ በልና ፡ ንገር ። እንዲያው ፡ ለምንም ፡ ለምን ፡ ብረት ፡ ላለው ፡ ሁሉ ፡ ስላሳ ፡ ስላሳ ፡ ጥይት ፡ እንዲሰጥ ፡ ለበሻህ ፡ ንገረው ፡ ለዋጋየም ፡ በቅሎየንና ፡ ፈረሶቸን ፡ እንዲያስጭን ፡ ንገረው ።"

" ለዛሬ ፡ ነው ? " አለ ፡ መሰረት ፡ ገርሞት ።

" ታዲያስ ! " ሲሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አዛዥ ፡ ደስታና ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ቢትኞች ፡ በመሆናቸው ፡ ንገሩልን ፡ እንኩዋ ፡ ሳይሉ ፡ ፊትና ፡ ሁዋላ ፡ ሆነው ፡ ገቡ ። መኖሚያ ፡ ቤት ፡ እልፍኝ ፡ ደርሰው ፡ ስለነበረ ፡ የፊታውራሪን ፡ ሁኔታ ፡ ስምተው ፡ ደንግጠው ፡ ቢመጡ ፡ የሚነጋገሩበት ፡ ጉዳይ ፡ ምን ፡

መሆኑን ፡ ባያውቁም ፡ እዩሳቁ ፡ ካሽከሮቻቸው ፡ ጋር ፡ ሲኑ ጋገሩ ፡ ስላገኙዋቸው ፡ ድንጋጤያቸው ፡ መለስ ፡ አለ ።

"አዛዥ ፡ እንዴት ፡ ዋላችሁ ! ኑ ፡ ኑ ፡ ተቀመጡ ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፊታቸው ፡ በደስታ ፡ ወገግ ፡ ብሎ ፡ እሳቸውም ፡ ራሳቸው ፡ ወደ ፡ መቀመጫቸው ፡ እያመሩ ። አዛዥ ፡ ደስታና ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡—

" እኛስ ፡ ባላገር ፡ ማደሙንና ፡ አንተም ፡ በጣም ፡ መበሳጨትህን ፡ ሰምተን ፡ ደንግጠን ፡ ነበር ፡ የመጣን ፡ አሁን ፡ ነገሩን ፡ በትግስት ፡ መያዝህን ፡ ዘማየቴ ፡ እኔ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ ! " አሉ ፡ አዛዥ ።

" በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ! " አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴም ፡ ተቀብለው ።

" እግዚአብሔር ፡ ክፉ ፡ አስመስሎ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሲያደርግልኝ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ያስቆጣኛል ? "

" ደግሞ ፡ ምን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ተገኘ ? ሌላ ውንስ ፡ አልሰማሁም ! " አሉ ፡ አዛዥ ፡ ያልሰሙት ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ መስሎዋቸው ።

" ሌላ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለ ፡ ባላገር ፡ ስለሸፈተ ፡ መቼም ፡ የሸፍታ ፡ ንብረት ፡ ጠግቶ ፡ ላላመነው ፡ ነውና ፡ ዛሬውኑ ፡ ሄጀ ፡ ባላገሩን ፡ ወግቼ ፡ ከብቱንና ፡ ንብረቱን ፡ እወስዳለሁ ፡ ብለው - - - -ይህን ፡ ነው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ አጋጠመኝ ፡ የሚሉ ፡ ጌቶች ።" አለ ፡ መሰረት ፡ ተሰራ ።

" አንተን ፡ እዚህ ፡ ውስጥ ፡ የሚያገባህ ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ ዶልቅ---ዶልቅ ፡ ወይ ፡ ተበዝብዘህ ፡ ሂድ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደ ፡ መቆጣት ፡ ብለው ።

" ከባላገር ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ መግጠም ? ዛሬ ? " አሉ ፡ አዛዥ ፡ በብረቱ ፡ መገረም ።

" እዎ ፡ ዛሬ ! ጉሊት ፡ ወይ ፡ እናሞራ ፡ ገብቼ ፡ ካላደርሁ ፡ ጉሮሮየ ፡ እህል ፡ ውሃ ፡ አይውጥልኝም !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

" አይደለም ፡ እንዲያው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ባላውቅ !

ሰው ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሲሄድ ፡ ከዘመድ ፡ ጋር ፡ ሳይመከር ፡ ለጦርነት ፡ የሚያስፈልገውን፡ መሰናዶ ፡ ሳያሰናዳ ፡ እንዲያው ፡ እንዲሁ ፡ ተነስቶ ፡ ነው ፡ የሚሄድ?"

"ለባላገር ፡ ነው ፡ ከዘመድ ፡ ጋር ፡ መመካከር ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ስንቅ ፡ ማሰናዳት ፡ የሚያስፈልገው ? የባላገር ፡ ድግስ ፡ የባላገር ፡ በግና ፡ ሰንጋ ፡ ማርና ፡ ቅቤ ፡ ምን ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ ስንቅ ፡ ከዚህ ፡ ተሸክሜ ፡ የምሄድ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አዛዥን ፡ እንደ ፡ ሞኝ ፡ ቆጥረው ፡ እዩሳቁ ፡፡-

"አዩህ ? ፊታውራሪ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ አሳብ ፡ መቀበል ፡ ክፉ ፡ አይምሰልህ ! የዛሬ ፡ ባላገር ፡ እንደ ፡ ድሮ ፡ ባላገር ፡ አይምሰልህ ! ዛሬ ፡ አንዳንድ ፡ በሬ ፡ እዩሸጠ ፡ ከወታደር ፡ የተሻለ ፡ ጠመንጃና ፡ ጥይት ፡ የሌለው ፡ ባላገር ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነው ፡፡ ብቻ ፡ ለማናቸውም ፡ ነገር ፡ ዘመድ ፡ ይጠራና ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉም ፡ ሌሎችም ፡ ይጠሩና ፡ እንምክርበት !"

" ህእ! ቀኛዝማች ፡ አካሉ! ለባላገር ፡ የልብ ፡ ልብ ፡ ሰጥቶ ፡ እንዲሸፍት ፡ ያደረገው ፡ ማን ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ የምመካከረው! የሱን ፡ ነገርስ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ እግዜር ፡ ያፈራርደኛል!" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አይኖቻቸውን ፡ እግዜር ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንስተው ፡፡

"እሱ ፡ የሚለው ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ እኛም ፡ በመሀከላችሁ ፡ ያለን ፡ ዘመዶቻችሁ ፡ የምናውቀውን ፡ እናውቃለን ፡ ብቻ ፡ ያም ሆነ ፡ ይህ፡- አሁን ፡ የሚያስፈልገው ፡ የዛሬው ፡ ጉዞ ፡ ቀርቶ ፡ ዘመዶቻችን ፡ ሁሉ ፡ ተጠርተው ፡ መመካከሩ ፡ ነው!"

ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ ራሳቸውን ፡ ደፋ ፡ አድርገው ፡ ካሰቡ ፡ በሁዋላ ፡- ዘመድ ፡ በተሰበሰበበት ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉን ፡ ወቅሶ ፡ አስወቅሶ ፡ አስፈርዶ ፡ ሁለተኛ ፡ በርስት ፡ በጉልታቸው ፡ እንዳይደርሱ ፡ ማድረጉ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ታያቸው፡፡ መቼም ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ በመሰስለሳቸው ፡ በመላላታቸው ፡ ምክናያት ፡ ባላገር ፡ ሸክም ፡ እንደ ፡ ቀለላት ፡ አህያ ፡ ፈንጥዞ ፡ ወደ ፡ ሽፍትነት ፡ መፈርጠጡ ፡ ትልቅ ፡ ጥፋተኛ ፡ አድርጎ ፡ እንደሚያስፈርድባቸው ፡ በፊታውራሪ ፡ አሳብ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ፡፡ ዘመድ ፡ ተሰብስቦ ፡ " ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ይህ ፡

ሁሉ ፡ የደረሰው ፡ ባንተ ፡ ጥፋት ፡ ነውና ፡ ለጉልቶቹ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሌላ ፡ በርታ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ቢደረግ ፡ ይሻላል !” እንደሚል ፡ አይጠረጠርም ። ታዲያ ፡ ሸክም ፡ ሆኖ ፡ የኖረን ፡ የሰለቸን ፡ ዘመድ ፡ በቀጥታ ፡ አፍ ፡ አውጥቶ ፡ ወግድልኝ ፡ ከማለት ፡ የጋራ ፡ ዘመድ ፡ ተሰብስቦ ፡ በጥፋቱ ፡ ፈርዶ ፡ ወግድለት ፡ ሲል ፡ አይሻልም ? እስር ፡ እጥፍ ፡ ይሻላል ! ዘመድን ፡ ወግድልኝ ፡ ከማለት ፡ ወግድለት ፡ የሚል ፡ ማግኘት ፡ ከሸክምም ፡ ከወቀሳና ፡ ከሜትም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ያድናል ።

ፊታውራሪ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ይህን ፡ ሲያሰላስሉ ፡ ቆዩና ፡ “ ደግ ፡ ነው ፡ አዳራሽ ፡ አስነጥፍና ፡ እንመካከርበት ! ” አሉ ፡ ወደ ፡ መሰረት ፡ ዘወር ፡ ብለው ።

ያንለት ፡ ዘመቻው ፡ ቀርቶ ፡ አዳራሽ ፡ ተነጥፎ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆች ፡ ከያሉበት ፡ እየተፈለጉ ፡ ተጠርተው ፡ ተሰበሰቡ ። ጉዱ ፡ ካሳም ፡ ባላገር ፡ ስላደረገው ፡ አድማ ፡ ለመመካከር ፡ እፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ የዘመድ ፡ ስብሰባ ፡ መደረጉን ፡ ስለሰማ ፡ መቸም ፡ ዘመድ ፡ ነውና ፡ ወግድ ፡ የማይባል ፡ መሆኑን ፡ በማወቁ ፡ ምንም ፡ ባይጠራ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ለመቀላወጥ ፡ ሂዶ ፡ ተጨመረ ።

“ በሉ ፡ ለኔ ፡ የነገራችሁኝን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሳታስቀሩ ፡ ለዘመዶቻችን ፡ ንገሩዋቸው ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባላገር ፡ አስሮ ፡ ያስነበታቸውን ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ እያገደገው ፡ በተራ ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ባይናቸው ፡ ገርፈው ። ካምስቱ ፡ አሽከሮች ፡ ማን ፡ እንደሚናገር ፡ አሰበሳቸው ፡ ሲተያዩና ፡ አንተ ፡ ተናገር ፡ አንተ ፡ ተናገር ፡ ሲባባሉ ፡ “ በሉኮ ፡ ተናገሩ ! እድሜ ፡ ለቀኛዝማች ፡ አካሉ ! እድሜ ፡ ለክብሬና ፡ ለጥቅሜ ፡ ታጥቆ ፡ ለቆመው ፡ ወንድሜ ፡ ለቀኛዝማች ፡ አካሉ ! ባላገር ፡ ከጉልቴ ፡ የሚያገኘውን ፡ እንጀራ ፡ እየበላ ፡ ጠግቦ ፡ ጉሹን ፡ እየጠጣ ፡ ሰክሮ ፡ ባደባባይ ፡ የሰደበኝን ፡ ያዋረደኝን ፡ እኔን ፡ ሽሮ ፡ በጉልቴ ፡ ሀሀሀሀ — በጉልቴ ፡ እበጄ ፡ በለውን ፡ መሾሙን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጉድ ፡ ለዘመዶቻችን ፡ ንገሩዋቸውና ፡ ከወንድሜ ፡ ከቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ጋር ፡ ይፍረዱን ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የገዛ ፡

ንግግራቸውን ፡ በሰሙ ፡ መጠን ፡ ስሜታቸው ፡ ምርር ፡ ንግግራቸው ፡ ክርር ፡ እያለ ።

ከዚያ ፡ ከምስቱ ፡ አሽከሮች ፡ መሀከል ፡ ደስታ ፡ የሚባለው ፡ ለንገሩ ፡ መግቢያ ፡ እንዲሆነው ፡ እነሱ ፡ እንደጌቱ ፡ እንደ ፡ ተያዙ ፡ ለመናገር ፡ ሲጀምር ፦ " የንተን ፡ መያዝ ፡ አልጠየቅሁህም ! አንተ --- እናንተ ፡ ብትያዙ ፡ ባትያዙ ፡ ጉዳዩ ፡ አይደለም ! እኔ ፡ የጠየቅሁህ ፡ ሌላ ፡ ነው ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አቋርጠው ። ወዲያው ፡ ደስታ ፡ የጌታውን ፡ ቁጣ ፡ ስላዩ ፡ ደንግጦ ፡ ድንግርግር ፡ ሲለው ፡ ፈረደ ፡ የሚባለው ፡ ሎሌ ፡ ጉዋደኛው ፡ ተመልክቶና ፡ ከፉ ፡ ነጠቅ ፡ አደርጎ ፦ " መቼም --- መቼም ፡ በሶስቱ ፡ ጉልቶቻችን ፡ ከሚኖረው ፡ ሀዝብ ፡ ከህጻናትና ፡ ከበሽተኞች ፡ በቀር ፡ ወንድ ፡ የተባለ ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ተሰብስቦ ፡ በጌቶች ፡ ላይ ፡ ያመርደው ፡ የነበረውን ፡ ስድብና ፡ ርግማን ፡ እንከዋን --- ዝብተኛ ፡ ደግሞ ፡ ለመናገር ፡ መጀመሪያም ፡ ለምን ፡ ሰማሁ ፡ ያሰኛል ። ስለዚህ --- ባልናገር ፡ ይሻላል ! ብቻ ፡ ከስድቡም ፡ ከርግማኑም ፡ በሁዋላ ፡ የሚባሉ ፡ ሰዎች ፡ ቢናሩ ፡ ነገራቸውን ፡ አዚያው ፡ የዘመድ ፡ ዳኞች ፡ አዩመረጡ ፡ እንዲጨርሱ ፡ እንጂ ፡ ተከሰው ፡ ወደ ፡ ጌቶች ፡ እዩመጡ ፡ ዳኝነትና ፡ ውርርድ ፡ እንዳይከፍሉ ፡ በምንም ፡ ምክንያት ፡ ሙተዩዩና ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ወይም ፡ የሙትባል ፡ መዋያ ፡ ይዞ ፡ ወይም ፡ ቢትና ፡ አጥር ፡ እሰራለሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጌቶች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳይመጣ ፡ ከውስጥም ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ ሊባና ፡ ቀማኛ ፡ ቢነሳ ፡ ለሶስቱም ፡ ጉልቶች ፡ የጎበዝ ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ የተሾመው ፡ አበጀ ፡ በሰው ፡ የተነሳውን ፡ ሌባና ፡ ቀማኛ ፡ አድኖ ፡ እንዲይዝ ፡ ካበጀ ፡ በላይ ፡ ያመለጠ ፡ ሌባና ፡ ቀማኛ ፡ ቢኖር ፡ አገር ፡ ተሰብስቦ ፡ ዘሙስ ፡ አውጥቶ ፡ ለጎበዝ ፡ አለቃው ፡ እንዲያስረክብ ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ የሚሰራ ፡ ሰው ፡ ቢኖር እንደ ፡ ከሃዲ ፡ እንዳገር ፡ ጠላት ፡ ተቆጥሮ ፡ ቢታመም ፡ ጠያቂ ፡ ቢሞት ፡ ቀባሪ ፡ እንዳያገኝ ፡ ከተወሰነ ፡ በሁዋላ ፦ ከበተከሲያን ፡ መጣፍ ፡ ሙጥቶ ፡ ሁሉም ፡ መጣፉን ፡ እዩጠፋ ፡ ማለና ፡ በመጨረሻ ፡ ቄሱ ፡ ተነስተው ፡ "ከዚህ ፡ ከማላችሁበት ፡ ብትወጡ ፡ ውግዝ ፡ ከማሪያም" ብለው ፡ ገዘቱ ። ብቻ ፡ ቄስ ፡ ተገዶው ፡ ነው ፡ እሱ!" ፡

አለና ፡ ከጉዋደኞቹ ፡ መሀከል ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ በተናገረው ፡ መስማማታቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ዘወርወር ፡ ብሎ ፡ ሲያያ ቸው ፡ ጉዋደኞቹም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ግንባራቸውን ፡ ወደ ፡ ላይ በመግፋት ፡ በተናገረው ፡ ሁሉ ፡ መስማማታቸውን ፡ ስለገለጹ ለት ፡ ገድሎ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ አሽከር ፡ ኩራቱ ፡ ለሁሉም ጎልቶ ፡ ታዩ ።

" ሰማህ ፡ አይደለም ? ቀኛዝማች ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቀኛዝማች ፡ አነሱ ፡ ላይ ፡ አይናቸውን ፡ ፍጥጥ ፡ አድርገው ፡ ተከለው ።

" አዎ ፡ ሰማሁ ! እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ! "

" አንተማ ፡ ደስ ፡ ይዘልህ ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ያሳዝንሃል ! እኔ ፡ ስዋረድ ፡ ካባቶቸ ፡ ጀምረን ፡ ደማችንን ፡ ባፈሰስንበት ፡ ላባችንን ፡ በጠመቅንበት ፡ ጉልታችን ፡ ባላገር ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ ሲያደርግበት ፡ ባላገር ፡ እኔን ፡ ሽሮ ፡ አበጀ ፡ በለውን ፡ ሲሾምበት ፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ታዝናለህ ! "

" የእኔ ፡ ጥቅም ፡ መጉደልና ፡ የእኔ — መዋረድ ፡ የሚያሳዝነኝ ፡ ወይም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘኝ ፡ መሆኑን ፡ ከእግዚአብሄርም ፡ ሌላ ፡ የጋራ ፡ ዘመዶቻችን ፡ ስለሚያውቁ ፡ እሱን ፡ እንተውና ፡ ይልቅ ፡ አሁን ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ ችግር ፡ ብንነጋገር ፡ ይሻላል ። "

" ለምን ፡ እንተወዋለን ፡ ይገለጽ ፡ እንጂ ! የያዝሁዋቸውን ፡ እስረኞች ፡ እባክህ ፡ ለኔ ፡ ስትል ፡ ልቀቅልኝና ፡ ነገሩን ፡ ክብርህም ፡ ጥቅምህም ፡ በማይጎድልበት ፡ መንገድ ፡ እኔ ፡ እጨርሰዋለሁ ፡ ብለህ ፡ አስለቅቀህ ፡ ከዚህ ፡ ሄደው ፡ ባላገሩን ፡ እንዲያስሸፍቱ ፡ አደረግሀቸው ፡ እዚህ ፡ በተሰበሰቡት ፡ የጋራ ፡ ዘመዶቻችን ፡ ፊት ፡ ለምንህ ፡ አስጨንቀህ ፡ ያስለቀቅሀቸው ፡ ባላገሮች ፡ መሆናቸውን ፡ አገር ፡ ሰብስበው ፡ አድማ ፡ ያስደረጉ ፡ አሁን ፡ ከዚያ ፡ ከመጡት ፡ ሰዎች ፡ ሰምተሀል ። እንግዲህ ፡ ያንተም ፡ የኔም ፡ ዘመዶች ፡ ናቸው ፡ እዚህ ፡ ያሉት ፡ ይፍረዱን !"

"እሺ እንግዲህ ፡ እኛም ፡ የምናገረው ፡ አለኝና ፡ አሽከሮች አንድ ፡ ጊዜ ፡ እውጭ ፡ ይቆዩ ። "አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ እነሱ ።

እሽከሮች ፡ ከመጡ ፡ በሁዋላ ፡- "እዩ ? ፊታውራሪ !" አሉ ፡ ቀጠሉና ። "እዩ ? እኔ ፡ የሰዎን ፡ ቤት ፡ ለመስራት ፡ እስዎ ፡ ለማፍረስ ፡ ስንታገል ፡ እድሜያችንን ፡ እንደ ፡ ገፋ ነው ፡ ከስዎ ፡ በቀር ፡ እዚህ ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ የማያውቅ ፡ የለም ።"ብለው ፡ ሲናገሩ ፡ የፊስጉትን ተናግረው ፡ ሳይጨርሱ ፡-

"አትስደቡኝ ! እብድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የገዛ ፡ ቤቱን ፡ የሚያፈርስ ፡ እኔ ፡ እብድ ፡ አይደለሁም ፡ የገዛ ፡ ቤቴን ፡ የማፈርስ ፡ አትስደቡኝ ፡ ልብ ፡ አድርግ ! "አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቁጣ ፡ ቀኛዝማችን ፡ አቋርጠው ።

"የጋራ ፡ ዘመዶቻችን ፡ ይፍረዱን ፡ ብለው ፡ የለም ? ታዲያክ ፡ እስዎን ፡ ሰምተው ፡ እኔን ፡ ሳይሰሙ ፡ ሊፈርዱ ፡ አይችሉም ! ወዲያውም ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በስዎ ፡ ጉዳይ ፡ እንዳልገባ ፡ ስለ ፡ ወሰንሁ ፡ የመጨረሻ ፡ ቀን ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ ያስገደደኝን ፡ በዘመዶቻችን ፡ ፊት ፡ እንድናገር ፡ ትንሽ ፡ ይታገሱኝ ።"

"አንተ ፡ በኔ ፡ ጉዳይ ፡ ያልገባህ ፡ እንደሆነ ፡ ምንኛ ፡ ተጎዳሁ ፡ እህህህ ! እኔ ፡ መሸሻ ፡ ከፈለግሁ ፡ እንዳንተ ፡ በንብረቴ ፡ በጉልቴና ፡ በርስቴ ፡ አገዙ ፡ እንዳንተ ፡ በኔ ፡ ምክናያት ፡ ታውቆና ፡ ተፈርቶ ፡ ተከብሮ ፡ ለመኖር ፡ የሚመኝ ፡ እንደ ፡ ሳር ፡ ቅጠል ፡ ብዙ ፡ መሆኑን ፡ አታውቅም ? ዛሬውኑ ፡ ቄስ ፡ መነኩሴ ፡ አማላጅ ፡ ልኮ ፡ እግሬን ፡ ስሞ ፡ ለመሾም ፡ የሚመኘው ፡ ብዙ ፡ መሆኑን ፡ አታውቅም ? አንተስ ፡ ብትሆን ፡ --- ለምነህ ፡ አስጨንቀህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለምኘ ፡ ነው ፡ የሾምሁህ ? ወዬው ፡ ጉድ !"

"ርስት ፡ ጉልትዎን ፡ ለማስተዳደርና ፡ ነገረ ፡ ፈጅዎ ፡ ለመሆን ፡ እኔ ፡ ለምኘ ፡ እንጂ ፡ እስዎ ፡ ለምነውኝ ፡ የገባሁበት ፡ ጣጣ ፡ አለመሆኑ ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ በስዎ ፡ ምክናያት ፡ እንድታወቅና ፡ እንድከበር ፡ ወይስ ፡ ከስዎ ፡ ደመወዝና ፡ አበል ፡ እንዳገኝ ፡ ይመስልዎታል ?"

" እያለም ፡ ልትጸድቅ ፡ ነው ! እኔን ፡ ደከማውን አባለ ፡ ጎደሎውን ፡ ረድተህ ፡ ልትጸድቅ ፡ ነው !"

"የለም ፡ ይከማና ፡ አካለ ፡ ጎደሎ ፡ ስለሆኑ ፡ አይደለም ፡ እንዲያውም ፡ ያለቅጥ ፡ ብርቱ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው !" አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብለው ።

"በጎልማስነትዎ ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ጀግንነትዎና ፡ ሀይለኛነትዎ ፡ በስህተት ፡ መንገድ ፡ ስለመራዎና ፡ ረዳት ፡ የሚያስፈልግዎ ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዳሁ ፡ ነው !"

"እንዴት ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ምንም ፡ ቢጠሉዋቸው ፡ ስለጀግንነታቸው ፡ ምስክርነታቸውን ፡ በማረጋገጣቸው ፡ በጣም ፡ ሻክሮ ፡ የነበረ ፡ ልባቸው ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መለስለስ ፡ አለና ።

"በጎልማስነትዎ በፈረስ ፡ በጉግስ በተኩስ ፡ ተወዳዳሪዎችዎን ፡ በማሸነፍዎ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ሄደው ፡ ጠላቶችዎን ፡ ድል ፡ መትተው ፡ በመመለስዎ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲያደንቅዎ ፡ ሲያከብርዎ ፡ ሲፈራዎ ፡ ጊዜ ፡ ለምነው ፡ ሳይሆን ፡ ተለምነው ፡ የጠዩቁትን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ያልጠዩቁትን ፡ ጭምር ፡ ሲያገኙ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሄር ፡ በሰፊ ፡ መሬቱ ፡ ከስዎ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ክብሩንና ፡ ጥቅሙን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ እንዳልፈጠረ ፡ ሰው ፡ ሁሉ የስዎን ፡ ፈቃድ ለመፈጸም ፡ እንጂ ፡ የራሱ ፡ ፈቃድ ፡ የሌለው ፡ ሆኖ እንደ ፡ ተፈጠረ ፡ በሙሉ ፡ ልብዎ ፡ አምነው ፡ በዚሁ ፡ ልመራ ፡ ብለው ፡ ተነሱ ። በዳኝነት ፡ ወንበር ፡ ቢያስቀምጡዎ ፡ በህግ ፡ ፈንታ ፡ ፈቃድዎን ፡ ህግ ፡ አድርገው ፡ ልፍረድ ፡ አሉ ። አገር ፡ ቢሰጡዎ ፡ በህግ ፡ እንዲያስተዳድሩትና ፡ እንዲጠብቁት ፡ የተሾሙበትን ፡ ህዝብ ፡ እንደ ፡ ቀማኛ ፡ ይዘርፉት ፡ ጀመር ። እንዲያው ፡ ባጭሩ ፡ ህዝብ ፡ የጠላው ፡ እግዚአብሄር ፡ የጠላው ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ አቃተዎ ። ስለዚሁ ፡ ያደንቅዎ ፡ ያከብርዎ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይጠላዎ ፡ ጀመር ። ሁሉም ፡ ሞትዎን ፡ ያለዚያም ፡ ሽረትዎን ፡ አጥብቆ ፡ ፈለገ ። የዚህ ፡ መጨረሻ ፡ ምን ፡ ሆነ ? መጨረሻውን ፡ ሁላችን ፡ እስዎ ፡ ጭምር ፡ እናውቃለን ! ከዳኝነት ፡ ወንበርና ፡ ከሹመት ፡ ታግደው ፡ በርስት ፡ ጉልትዎ ፡ ብቻ ፡ እንዲወሰኑ ፡ ተደረገ ፡ ተጋዙ ! ብቻ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ትምርት ፡ ሳይሆንዎ ፡ መቅረቱ ፡ ለዚሁ ፡ ሁሉ ፡ በራስዎ ፡ ጥፋት ፡ ሌላ ፡ ምክናያት ፡

እየፈጠሩ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሲወቅሱና ፡ ሲያማርሩ ፡ መኖርዎ ፡
ያሳዝናል ! ያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ! ያስታውሱት ፡ እንደሆነ ፡ ሹመት ፡
ቢቀርብዎ ፡ ርስት ፡ ጉልትዎ ፡ እስካሁን ፡ ለስዎ ፡ ካለፉ ፡ በሁ
ዋላ ፡ ለተከታይ ፡ ትውልድ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ለማድረግ ፡ ባጠገ
ብዎ ፡ ሆኜ ፡ እዬመከርኩ ፡ በደህና ፡ መንገድ ፡ ለመምራት ፡
የምችል ፡ መስሉኝ ፡ የርስት ፡ የጉልትዎ ፡ አስተዳዳሪና ፡
ነገረ ፡ ፈጅዎ ፡ እንድሆን ፡ የለመንሁዎ ። ከመልካም ፡ አባቶች ፡
የወረዱ ፡ ጉልቶች ፡ በስዎ ፡ ጊዜ ፡ እንዳይፋቁና ፡ ከስዎ ፡ በሁ
ዋላ ፡ የሚከተሉት ፡ ትውልዶች ፡ ያለጥፋታቸው ፡ ቦታ ፡ የሌላ
ቸው ፡ ከንቱዎች ፡ ነው ፡ እንዳይቀሩ ፡ ነበር ፡ ለምኜ ፡ እጣጣ ፡
ውስጥ ፡ የገባሁ ፡ እንጂ ፡ እርስዎ ፡ እደሚሉት ፡ የስዎ ፡ ሹም ፡
በመሆን ፡ ለመከበር ፡ ወይም ፡ ደመወዝ ፡ ለማግኘት ፡ አልነበ
ረም ። ከስዎ ፡ እንኳዋን ፡ ደመወዝ ፡ ከጭቅጭቅና ፡ ከጥል ፡ በቀር፡
እግዚአብሄር ፡ ይስጥልኝን ፡ እንኳዋ ፡ አግኝቼ ፡ እደማላውቅ ፡
እርስዎም ፡ ያውቁታል ። አሁን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሆነ ! ካንድ፡
ወገን ፡ እስዎ ፡ እንደ ፡ ልቤ ፡ አልዘረፍሁ ፡ ብለው ፡ ሲወቅሱኝ ፡
ከሌላ ፡ ወገን ፡ አሸነፍውኝ ፡ በባላገር ፡ ላይ ፡ ለሚያደርጉት ፡
ግፍ ፡ እኔ ፡ አላፊ ፡ ሆኜ ፡ ስቀርብ ፡ ባላገር ፡ ሲወቅሰኝ ፤ ለሚ
ሰሩት ፡ በደል ፡ ሁሉ ፡ መሸፈኛ ፡ ሆኜ ፡ የባላገር ፡ ወቀሳና ፡
እሜት ፡ እንደሳት ፡ ሲገርፈኝ ፡ ጥርሴን ፡ ነክሼ ፡ የደከምሁ
በት ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሆነ ። ይህ ፡ ነው ፡ የሚያሳዝነኝ ፡ የስዎ ፡
መስደብና ፡ መረገም ፡ ይችን ፡ ያክል ፡ አያሳዝነኝም ! ”
አሉ ፤ ቀኛዝማች ፡ የቀኝ ፡ ፊት ፡ ጣታቸውን ፡ ጥፍር ፡ ባውራ ፡
ጣታቸው ፡ ጥፍር ፡ እኖጭተው ።

“ ጨረስህ ፡ ወይስ ፡ የቀረህ ፡ ስድብ ፡ አለ ? የረሳኸው ፡
ስድብና ፡ ዘለፋ ፡ አለ ፡ እንደሆነ ፡ እዬፈለግህ ፡ ጨምርበት ! ”
አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

“ ራሱን ፡ ቀና ፡ አድርጎ ፡ እውነቱን ፡ ፊትለፊት ፡ የሚ
ነገርዎን ፡ ለዘለቃ ፡ ጥቅምዎና ፡ መልካም ፡ ስምዎ ፡ በማ
ሰብ ፡ ከስዎ ፡ ፈቃድና ፡ ምኞት ፡ የተለዬ ፡ ምክር ፡ የሚሰጥ
ዎን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሰዳቢና ፡ እንደ ፡ ዘላፊ ፡ የሚቆጥሩ ፡ በመ
ሆንዎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አልሰደብሁዎም ፤ አልዘለፍሁዎም ።

ሲያጣላን ፡ የኖረም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ "

" በል ፡ ግዴለም ፤ እግዚአብሔር ፡ መልካም ፡ መላስ ፡ አድሎሀል ፤ ራስህን ፡ መላክ ፥ እኔን ፡ ሰይጣን ፡ አስመስለህ ፡ በርስት ፡ በጉልበቴ ፡ ስታዝ ፥ ስትሾም ፥ ስትሽር ፡ የኖርኸውን ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ አድርገህ ፤ አንተ ፡ ሰኔ ፡ የዋልኸውን ፡ ውሰታ ፡ ብቻ ፡ ዳር ፡ ድንበር ፡ የሌለው ፡ አድርገህ ፤ ውሸቱን ፡ ወደውነት ፤ እውነቱን ፡ ወደ ፡ ውሸት ፡ ለዋውጠህ ፡ ስትናገር ፡ መላስህ ፡ ትንሽ ፡ እንኩዋ ፡ አይደናቀፍም ! መልካም ፡ መላስ ፡ ታድሎሀል ! ብቻ ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ መላስህ ፡ ነገር ፡ መስራት ፡ቢያውቅ ፡ ይህ ፡ መላስህ ፡ አሳምሮ ፡ የሰራው ፡ ሁሉ ፡ እውነቱን ፡ ሊሸፍነው ፡ አይችልም ፡፡ እውነቱ ፡ ስትሰራው ፡ የኖርኸው ፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡ ተወደህ ፥ ተከብረህ ፡ እኔ ፡ እንድጠላ ፥ እንድናቅ ፡ ለማድረግ ፡ መሆኑ ፡ አሁን ፡ የደረሰው ፡ መድረሱ ፡ ነው ፤ የማይካደው ፡ ዋና ፡ ምስክር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ማሳመሩ ፡ አይደለም ፡፡"

" እውነቱስ ፡ ሌላ ፡ ነው ! " አሉ ፤ ቀኛዝማች ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብለው ፡፡

" ምን ? "

" ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከባላገር ፡ የሚፈልጉትን ፡ ብዙ ፡ ከመንገድ ፡ የወጣ ፡ ነገር ፡ ከስም ፡ ጋር ፡ እዬተጣላሁ ፡ እንዲቀር ፡ ባይሆንና ፡ እኔን ፡ አሽንፈው ፡ ወይም ፡ እኔን ፡ ሳላውቅ ፡ በጎን ፡ የሚያደርጉትን ፡ የማይገባ ፡ ስራ ፡ እኔ ፡ በስተት ፡ ያደረግሁት ፡ መስዬ ፡ ባላገሮችን ፡ በማባበልም ፤ በመደለልም ፡ እንዲሰዝቡ ፡ ባላደርጋቸው ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ የደረሰው ፡ ገና ፡ ድሮ ፡ ይደርስ ፡ ነበር ፡፡ ሁለተኛ ፦ አሁን ፡ የደረሰውንም ፡ ቢሆን ፡ እንዲደርስ ፡ ያደረጉ ፡ እስዎ ፡ ነዎ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡፡ እዚህ ፡ በተሰበሰቡት ፡ ዘመዶቻችን ፡ መሀከል ፡ እኔ ፡ ባላገሮችን ፡ አሰዝቤ ፡ ነገሩን ፡ በሰላም ፡ እንድጨርሰው ፡ ተስማምተን ፡ እስረኞች ፡ ከተለቀቁ ፡ በሁዋላ ፡ እንደ ፡ ልማድዎ ፡ በጎን ፡ አሽከርዎን ፤ ታምራትን ፡ ልከው ፡ ከሶስት ፡ ወር ፡ በሁዋላ ፡ ስድስት ፡ ፍሪዳ ፡ ያላመጣችሁ ፡ እንደሆነ ፡ መቸያ ፡ ልኬ ፡ እዘርፋችሁዋለሁ ፡ ብለው ፡

የባላገሮችን ፡ መላክተኞች ፡ አስፈራሩዋቸው ። ይዩት ፤ ይህ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያመጣ ፤ ይህ ፡ ነው ፡ እውነቱ ! ብቻ ፡ የሚያስገርመው ፡ እስዎ ፡ ስተት ፡ ሰርተው ፡ ባጋጣሚ ፡ ውጤቱ ፡ ያማረ ፡ እንደሆነ ፡ ይፈክሩበታል ፡ ያላማረ ፡ እንደ ሆነ ፡ ለስተቱ ፡ አላፊ ፡ የሚሆን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ይፈልጉለ ታል ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ ለስተትዎ ፡ ሁሉ ፡ መሸፈኛ ፤ አላፊ ፡ በመ ሆን ፡ ወደ ፡ ፈለግሁት ፡ አላማ ፡ የምደርስ ፡ መስሎኝ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ተቀበልሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ ከስ ምም ፡ ከባላገሮች ፡ ጋር ፡ ከመጣላት ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ተመኘ ሁት ፡ ጉልቶችዎን ፡ ለተከታይ ፡ ትውልድ ፡ እንዲተላለፉ ፡ ለማድረግ ፡ የማልችል ፡ መሆኔን ፡ ስለ ፡ ተረዳሁት ፡ ጥንት ፡ የተሰሩ ፡ ጉልቶች ፡ ሲፋቁ ፡ ላላፊነቱ ፡ ተካፋይ ፡ መሆን ፡ አልፈልግምና ፡ ለርስት ፡ ጉልትዎ ፡ አስተዳዳሪና ፡ ነገረ ፈጅ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ይፈልጉ ። ”

“ አንተ ፡ ስላላስተዳደርሀቸው ፡ ነው ፡ ጉልቶች ፡ የሚ ፋቁ ? እሀ ! ምነው ፡ ራስህን ፡ እንዲህ ፡ አንቱ ፡ አልኸው ፡ እባክህ ! ”

“ አሁን ፡ እደሚሉት ፡ ያመትባል ፡ መዋያ ፡ ካልሰጣች ሁኝ ፡ ብለው ፡ ባላገሮችን ፡ ሊዘርፉ ፡ ከሄዱና ፡ በንዲህ ፡ ያለው ፡ የማይገባ ፡ ዘረፋ ፡ መሀከል ፡ ደም ፡ ከፈሰሰ ፡ ጉልቶ ችዎ ፡ እንደሚፋቁ ፡ አይጠርጥሩ ፤ ይህ ፡ አዲስ ፡ አይደለም ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ የታዩ ፡ ነው ። ”

“አንተ ፡ ስትነግስ ፡ ከጉልትህ ፡ ዳኝነትና ፡ ውርርድ ፡ በላህ፡ ብለህ ፡ መተያየና ፡ ያመትባል ፡ መዋያ ፡ ተቀበልህ ፡ በጉል ትህ ፡ የሚኖረውን ፡ ህዝብ ፡ አዘህ ፡ ቤትህንና ፡ አጥርህን ፡ አሰራህ ፡ ብለህ ፡ ጉልቶችን ፡ ትፍቃለህ ! እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ መሸሻ ፡ አፈር ፡ ሳይጫነኝ ፡ እንከኮዋን ፡ ጥይት ፡ የሚገባበትንና ፡ የሚወጣበትን ፡ የማያውቅ ፡ ባላገር ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የሚከለክለኝ ፡ እንደሌለ ፡ ታያለህ !

“ እስቲ ፡ ለኛም ፡ ትንሽ ፡ ፋታ ፡ ስጡንና ፡ እንናገር ፡ እንጂ ! ” አሉ ፡ አሀዥ ፡ ደስታ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ሲቃጡ ፡ ነገሩን ፡ ከፊታውራሪ ፡ አፍ ፡ ቶሎ ፡

ተቀበሉና ። “ እዚህ ፡-- ” አሉ ፡ ቀጠሉና ። “ እዚህ ፡ የተሰበ
ሰብነው ፡ ባላገር ፡ ስላነሳው ፡ አድማ ፡ ተመካክረን ፡ የሚበጀ
ውን ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ የሁለታችሁን ፡ ማለቂያ ፡
የሌለው ፡ ጭቅጭቅ ፡ ለመስማትና ፡ ሁለታችሁ ፡ ተጣልታ
ችሁ ፡ ስትለያዩ ፡ ምስክር ፡ ለመሆን ፡ አልነበረም ። አዬሀ ፡
ቀኛዝማች ! አሁን ፡ ጥፋተኛ ፡ አንተ ፡ ነህ ! ” ሲሉ ፡ የፊታው
ራሪ ፡ ፊት ፡ በደስታ ፡ ፈገግ ፡ አለ ። “ ፊታውራሪ ፡ ባላገሮች ፡
ባነሱት ፡ አድማ ፡ ተበሳጭቶ ፡ ያላሰበውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ቢና
ገር ፡ እንኳዋ ፡ የተበሳጨበትን ፡ ምክናያት ፡ ተረድተህ ፡ መታ
ገስ ፡ ነበረብህ ፡ እንጂ ፡ በራውን ፡ እለቃለሁ ፡ ማለት ፡ ባልተገ
ባህ ! ዛሬ ፡ ተበሳጭቶ ፡ ያላሰበውን ፡ ቢናገር ፡ ያላንተ ፡ ርዳታ ፡
እሱ ፡ ከባላገር ፡ ጋር ፡ ተጨቃጭቆ ፡ ቁና ፡ እህል ፡ እንኳዋ ፡ እንደ
ማያገኝ ፡ ሁላችን ፡ እናውቃለን ፤ እሱም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚናገ
ረው ፡ ነው ። “ የዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ ከባእድ ፡ ወዳጅ ፡ የሚለዬው ፡
ብርቱ ፡ ችግር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ነው ! ” እንደሚባለው ፡ ተረት ፡
“አሁን ፡ የተፈጠረው ፡ መጥፎ ፡ ችግር ፡ ተመግዶ ፡ ነገሩ ፡ ድሮ ፡
ወደ ፡ ነበረበት ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ እንኳዋን ፡ አንተ ፡ በስራው ፡
ላይ ፡ የቆዬኸው ፡ እኛም ፡ ሁላችን ፡ የምንተባበርበት ፡ ጊዜ ፡
ስለሆነ ፡ ስራውን ፡ እለቃለሁ ፡ ማለትህ ፡ ብርቱ ፡ ጥፋት ፡ ነው !”
ብለው ፡ ሲጨርሱ ፡ በፊታውራሪ ፊት ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ቦግ ፡
ብሎ ፡ የነበረው ፡ የደስታ ፡ ጸዳል ፡ እንደገና ፡ ትንሽበትንሽ ፡
ደብዘዝ ፡ እያለ ፡ ሄዶ ፡ ሲጠፋ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

“ የለም ፡ እዛዥ ፡ የዘመድ ፡ ጥልና ፡ የቁምጥና ፡ በሽታ ፡
ጎልቶ ፡ ከታዬ ፡ በሁዋላ ፡ ድኖ ፡ አይድንምና ፡ ይልቅ ፡ በዚህ ፡
ላይ ፡ ጊዜያችንን ፡ ከማጥፋት ፡ የተነሳው ፡ ችግር ፡ የሚወገድ
በትን ፡ ዘዴ ፡ እንነጋገር ። አሁን ፡ በኔ ፡ የደረሰው ፡- ‘ ወዳ
ጅህ ፡ እንዲጠረጥርህ ፡ ብትፈልግ ፡ አገልግሎትህን ፡ ያለዋጋ ፡
አቅርብለት ፡’ የሚባለው ፡ ተረት ፡ ነው ! አሁን ፡ ፊታውራሪ ፡
ሲናገሩ ፡ እንደ ፡ ሰማችሁዋቸው ፡ ይሆን ፡ ያክል ፡ ዘመን ፡ አገ
ልግሎቴን ፡ ያለዋጋ ፡ ያለምስጋና ፡ እንኳዋ ፡ መስጠቴ ፡ በሳ
ቸው ፡ ከሳራ ፡ ለራሴ ፡ መወደድን ፡ መታወቅንና ፡ መከበርን ፡
ለማትረፍ ፡ መስሎ ፡ ታያቸው ። ይህ ፡ ዛሬ ፡ ለናንተ ፡ እንግዳ ፡

ቢሆንባችሁና ፡ በቁጣ ፡ ተገፍተው ፡ ያላሰቡትን ፡ የተናገሩ ፡ ቢመስላችሁ ፡ ለኔ ፡ እንግዳየ ፡ አይደለም ። በዩጊዜው ፡ በዩምክንያቱ ፡ ሲያሰሙኝ ፡ የኖሩት ፡ ነው ። ወዲያውም ፡ ሰው ፡ ሲቆጣና ፡ የአእምሮውን ፡ ልጉዋም ፡ መያዝ ፡ ሲያቅተው ፡ የሚናገረው ፡ ነው ፡ የውነተኛውን ፡ ስሜቱን ፡ የሚገልጸው ፡ ስሜቱን ፡ ለመግታትና ፡ መርጦ ፡ ለመናገር ፡ በሚችልበት ፡ ጊዜ ፡ የሚናገረው ፡ አይደለም ! ‘ ያልሞላ ፡ ተርፎ ፡ አይፈስም ’ የሚባለው ፡ [illegible]ረት ፡ ለዚህ ፡ ጥሩ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ! ስለዚህ ፡ ወንድማሞች ፡ በጭራሽ ፡ እንዳንቆራረጥ ፡ ለርስት ፡ ጉልታቸው ፡ አስተዳዳሪና ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ የሚሆናቸው ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ቢፈልጉ ፡ ለሳቸውም ፡ ለኔም ፡ የተሻለ ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ አታስቸግሩን ።” አሉ ፡ ቀኛዝማች ።

“ አይደለምኮ ፡ ቀኛዝማች ፡ አሁን ፡ ጥል ፡ ሳይነሳ ፡ ወይም --- የተነሳው ፡ ጥል ፡ ሳይከር ፡ እስዎ ፡ በስራው ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ሄደው ፡ ነገሩን ፡ ካላበረዱት ---” ብለው ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ሊናገሩት ፡ የፈለጉትን ፡ ሳይጨርሱ ።

“ ወዬጉ ፡ ጉድ ! እንዲያው ፡ ለመሆኑ ! ደግመኛ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ በርስት ፡ ጉልቴ ፡ እንዲደርስ ፡ እኔ ፡ እሺ ፡ የምል ፡ ሆኜ ፡ ነው ፡ እሱን ፡ የምትለምኑት ? ከቶ ፡ ምን ፡ ያለውን ፡ ዘመን ፡ አመጣህብን ፡ ጌታየ ! እኔ ፡ ባለርስት ፡ ባለጉልቱ ፡ ሹዋሚው ፡ ሻሪው ፡ ተቀምጬ ፡ ተሹዋሚው ፡ ተሻሪው ፡ እባክህ ፡ ሹመትህን ፡ አትልቀቅ ፡ እዩተባለ ፡ ይለመናል ! ብዙ ፡ ሳትደክሙ ፡ ነገሩን ፡ ባጭሩ ፡ ቁርጥ ፡ አድርጌ ፡ ልንገራችሁ ! ደግመኛ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ እንኩዋን ፡ የሰው ፡ የታቦት ፡ እማላጅ ፡ ይዞ ፡ ቢለምነኝ ፡ በርስት ፡ በጉልቴ ፡ ትውር ፡ ብሎ ፡ አይደርስም ! ሹም ፡ በተሾመበት ፡ ቦታ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከቆዩ ፡ ሹዋሚው ፡ ባለቤቱ ፡ እዩተረሳ ፡ ሹሙ ፡ ባለቤት ፡ የሚሆን ፡ መሆኑን ፡ እያወቅሁ ፦ ለጉልቴ ፡ ባለቤቱ ፡ እኔ ፡ መሆኔ ፡ እስኪረሳና ፡ አሁን ፡ የደረሰው ፡ እስኪደርስብኝ ፡ እሱን ፡ በሹመቱ ፡ ላይ ፡ ማቆዩቴ ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኔን ፡ ይህና ፡ አድርጎ ፡ አስረድቶኛል ! ይህ ፡ ነው ፡ ጥፋቴ ፡ ሁለተኛ ፡ ግን ፡ አልደግመውም !” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ምርር ፡

ብለው ።

" ይህማ ፡ ቅድም --- ቀኛዝማች ፡ እንዳለው ፡ የገዛ ፡ ቤትህን ፡ ልታፈርስ ፡ ታጥቀህ ፡ ተነስተሃል ፡ ማለት ፡ ነዋ ! " አሉ ፡ አዛዥ ።

" እንዴት ! አንተም --- ሁላችሁም ፡ ከሱ ፡ ጋር ---ከቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ጋር ፡ አድማችሁ ፡ ልትሰድቡኝ ፡ ነው ፡ የመጣችሁ ? "

" እኛስ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ የታደመውን ፡ አድማ ፡ የምናፈርስበትን ፡ መንገድ ፡ ነበር ፡ የምንፈልገው ፡ አንተ ፡ መንገዱን ፡ እያጠፋህ ፡ አስቸገርኸን ፡ እንጂ ! አዬህ ፡ ፊታውራሪ ፡ ያመነባል ፡ መዋያ ፡ ካልሰጣችሁኝ ፡ ብለህ ፡ ከባላገር ፡ ጋር ፡ ስትዋጋ ፡ ደም ፡ መፍሰሱና ፡ ነፍስ ፡ መጥፋቱ ፡ ስለማይቀር ፡- ይህ ፡ ከዛሬ ፡ ቀደም ፡ ሹመትህን ፡ ካሻረህ ፡ ምክንያት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በስተኋላ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያመጣብሃል ። ስለዚህ ፡ ነገሩን ፡ ዱሮ ፡ ማብረድ ፡ ያስፈልጋል ። ነገሩንም ፡ ማብረድ ፡ የሚችለው ፡ የባላገሮችን ፡ ባህሪ ፡ ስለ ፡ ለመደው ፡ ቀኛዝማች ፡ ነው ። ቤትህን ፡ ታፈርሳለህ ፡ ያልሁህ ፡ ነገሩን ፡ ማብረድ ፡ የሚችለውን ፡ ሰው ፡ አይድረስብኝ ፡ ስላልህ ፡ ነው ።"

" ነገሩን ፡ ማብረድ ፡ የሚቻል ፡ ከሆነ ፡ እኔ ፡ በስራው ፡ ላይ ፡ ብቆይም ፡ ባልቆይ ፡ ልዩነት ፡ የለውምኮ ፡ አዛዥ ! ከመሀከላችሁ ፡ ካንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ አብረን ፡ ሄደን ፡ ባላገሮችን ፡ መምከርና ፡ አሳቦቸውን ፡ እንዲለውጡ ፡ ለማድረግ ፡ መሞከር ፡ እንችላለን ። ባላገር ፡--- "ብለው ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ባላገሮች ፡ የሚረዘቡበትን ፡ መንገድ ፡ ለመግለጽ ፡ ሲጀምሩ ፡-

" በሉ ፡ ቢቃችሁ ፡ እንግዲህ ፡ ስለ ፡ ምክሩም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ሌላው ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ ! አሳባችሁን ፡ አወቅሁ ፡ የምትፈልጉትን ፡ አወቅሁ ፡ ብቻ ፡ ሁሉም ፡ የማልቀበለው ፡ ነው ። ድሮውንም ፡ ቢሆን ፡ ለባላገር ፡ የልብ ፡ ልብ ፡ እዬሰጠ ፡ በማዘዝ ፡ ፊንታ ፡ ባላገርን ፡ እንለምን ፡ እያለ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ እንዲፈጠር ፡ ያደረገ ፡ ቀኛዝማች ፡ መሆኑን ፡ እናንተ ፡ ባታውቁ ፡ እኔ ፡ አውቃለሁ ! ባላገር ፡ ሲታዘዝ ፡ እንጂ ፡

ሲለምን ፡ አይቼም ፡ ሰምቼም ፡ አላውቅም ! ስለዚህ ፡ ለጉልቴ ፡ ገዢ ፡ ወይስ ፡ ለማኝ ፡ መሆኔን ፡ ለይቼ ፡ የማውቅበት ፡ ጥሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ገጥሞኛልና ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ አጋጣሚ ፡ እንዲያመልጠኝ ፡ አልፈልግም ። ከናንተ ፡ ማንንም ፡ ሳልሻ ፡ እኔ ፡ ካሽከሮቼ ፡ ጋር ፡ ሄጄ ፡ እኔ ፡ ገዢ ፡ ባላገር ፡ ተገዢ ፡ መሆናችንን ፡ እንዳያዳግም ፡ አድርጌ ፡ ለባላገር ፡ አስተምሬው ፡ እመጣለሁ ።" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አቋርጠው ።-

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ የሰበሰቡበት ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉን ፡ በዘመድ ፡ ፊት ፡ ወቅሰው ፡ ካስጠቀሱና ፡ ካስፈረዱባቸው ፡ በሁዋላ ፡ ባላገሮችን ፡ ወግተው ፡ ስለሚያስገብሩበት ፡ ዘዴ ፡ ለመመካከር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የተሰበሰቡት ፡ የጋራ ፡ ዘመዶች ፡ ፊታውራሪ ፡ እንዳሰቡት ፡ ቀኛዝማችን ፡ ወቅሰው ፡ ስራቸውን ፡ እንዲለቁ ፡ በመፍረድ ፡ ፈንታ ፡ ባለፈው ፡ የሰሩትን ፡ አመስግነው ፡ ወደፊትም ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ልመና ። ስለገቡና ፡ ከባላገሮች ፡ ጋር ፡ የተነሳውም ፡ ጥል ፡ በጦር ፡ ፈንታ ፡ በሰላም ፡ እንዲያልቅ ፡ ስላሳሰቡ ፡ ሁሉም ፡ ከቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ጋር ፡ ያደሙባቸው ፡ መስሎዋቸው ፡- እናቱ ፡ ቀጥቃው ፡ ላቤቱታ ፡ ወዳባቱ ፡ ሄዶ ፡ አባቱም ፡ እንደ ፡ ቀጣው ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ተቆጣው ፡ ህጻን ፡ ሆድ ፡ ባሳቸውና ፡ መንፈሳቸው ፡ በዘመዶቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሸፍቶ ፡ መነጫነጭ ፡ ስለ ፡ ጀመሩ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ የሚያደርጉት ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶዋቸው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እስበሳቸው ፡ ይተያዩ ፡ ጀመር ። ከዚያ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ሲፈሩ ፡ ሲቸሩ ፡ ተነስተው ፡-

“ ጌቶች ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ እንኳዋ ፡ ስተት ፡ የለውም ፡ ሁሉም ፡ እውነት ፡ ነው ። እግዚአብሄር ፡ ጌታን ፡ ከድሃ ፡ ገዢን ፡ ከተገዢ ፡ ለይቶ ፡ ሲሰራ ፡ ጌታው ፡ ገዢው ፡ ፍርድ ፡ ቢያጎድል ፡ ድሃ ፡ ቢበድል ፡ ጠያቂው ፡ መንግስት ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ እግዚአብሄር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ድሃ ፡ አቤት ፡ ከማለት ፡ አልፎ ፡ የሚተዳደርበትን ፡ ህግ ፡ እግሩና ፡ ፈራጅ ፡ ሆኖ ፡ አያውቅም ። አሁን ፡ ባላገር ፡ አድሞ ፡ የሚሰራው ፡ [illegible] ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ የለውም ። መተያያና ፡ ያመት

ባል ፡ መዋያ ፡ ጥንት ፡ ያልተሰራ ፡ ነው ፡ የምትሉትም ፡ እው ነት ፡ አይደለም ። " ኢትቁም ፡ ራቀከ ፡ ቅድመ ፡ መሢሀ ፡ እግዚአብሔር ፡" ሲል ፡ መጽሀፍ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀብቶ ፡ በሾመው ፡ ፊት ፡ ባዶ ፡ እጅህን ፡ አትቅረብ ፡ ማለቱ ፡ ነው ። አንድም ፡ ያልተሾመ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ተሾመ ፡ ጌታ ፡ ባመትባል ፡ እንኳዋን ፡ አደረሰዎ ፡ ሲል ፡ ወይም ፡ ችግር ፡ ገጥሞት ፡ ችግሩን ፡ ሊያመለክት ፡ ሲቀርብ ፡ መተያያ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ መባ ፡ ያመትባል ፡ መዋያ ፡ ይዞ ፡ እንጂ ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ አይቅረብ ፡ ሲል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ያመትባል ፡ መዋያና ፡ መተያያ ፡ መጽሀፍ ፡ ያዘዘው ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ ባላገሮች ፡ አጥፊዎች ፡ ቢሆኑና ፡ ጌቶችም ፡ የተቆጡበት ፡ በሚገባ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ከድሀ ፡ ጥፋት ፡ ከጌታ ፡ ምህረት ፡ ተለይቶ ፡ አያውቅምና ፡ ጌቶችን ፡ የምንለምነው ፡ ነገሩን ፡ እንዲተውት ፡ ነው ። መቸም ---"

" እዩዋቸው ፡ እንግዲህ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አቋርጠው ። " እዩዋቸው ፡ ደህና ፡ ቀጥ ፡ ብለው ፡ መጥተው ፡ መጥተው ፡ እመጨረሻ ፡ ሲደርሱ ፡ እንደ ፡ ምሳር ፡ እጀታ ፡ ሲቆለመሙ ! ባላገሮች ፡ አጥፍተዋል ፡ በድለዋል ፡ አንተ ፡ ተበድለሀል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የተበደልኸው ፡ በዳዮቹን ፡ ማባበል ፡ መለመን ፡ ይገባሀል ! ይህ ፡ ነው ፡ ፍርድ ፡ አዋቂው ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ የሚሉት ! አይደለም ! ይዘሉ ፡ ሰማንዎ ፡ ዘማያውቁበት ፡ ስራ ፡ ገብተው ፡ አይዘባርቁ ፡ ይቀመጡ ።"

" በድለዋልና ፡ ይማሩዋቸው ፡ አልሁ ፡ እንጂ ፡ ይስምኑዋቸው ፡ አላልሁምኮ ፡ ጌቶች ! "

" በማያውቁት ፡ ነገር ፡ ገብተው ፡ አያስቸግሩ ፡ ዝም ፡ ይበሉ ፡ ብዬዎታለሁ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደ ፡ ተቆጡ ።

" እናንተ ፡ አልገባችሁ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፊታውራሪኮ ፡ የሚሉት " አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ደንግጠው ፡ ሲቀመጡና ፡ ሌሎችም ፡ የሚናገሩትን ፡ አጥተው ፡ እርስበሳቸው ፡ ሲፋጠጡ ፡ ተመልክቶ ፡- እንደ ፡ ልማዱ ፡ እዩሳቀ ። " ፊታውራሪኮ ፡ የሚሉዋችሁ ፡- እግዚአብሔር ፡ አሳስቶ ፡ አለጊዜየ ፡ አለቦታየ ፡ የፈጠረኝ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ስለዚህ ፡ በሌሎች ፡ አሉም ፡

በሌሎች ፡ ጊዜ ፡ ልኖር ፡ አይገባኝም ፤ የኔ ፡ አለም ፡ የኔ ፡ ጊዜ ፡ ድሮ ፡ ድሮ ፡ ካለፉት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ነውና ፡ ሄጄ ፡ ከባላገር ፡ ጋር ፡ ስዋጋ ፡ ልሙትና ፡ ጥንት ፡ ካለፉት ፡ ሰዎች ፡ ከጉዋደኞቼ ፡ ጋር ፡ ልጨመር ! ነው ። ይህ ፡ ነው ፡ አሳባቸው ፡ እንጂ ፡ ከብዙ ፡ ሽህ ፡ ባላገር ፡ ጋር ፡ ተዋግቼ ፡ ድል ፡ አደርጋለሁ ፡ ብለው ፡ አይደለም ! ታዲያ ፡ የኔን ፡ አስተያየት ፡ የሚጠይቀኝ ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ የሚጠይቀኝ ፡ ቢኖር ፡ የምፈርደውን ፡ ፍርድ ፡ ልንገራችሁ ? የምፈርደው ፡ ፍርድ ፡ እንዲህ ፡ ነበር ፡- ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አዲስ ፡ ስጋ ፡ ለብሰው ፡ እንደገና ፡ ተወልደው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ድሮ ፡ ድሮ ፡ ካራት ፡ ወይም ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ከሞቱት ፡ ከፉ ፡ ሰዎች ፡ ያንዱ ፡ መንፈስ ፡ ናቸው ። እኒህ ፡ ከፉ ፡ አሮጌ ፡ መንፈስ ፡ ባሮጌው ፡ ህይወታቸው ፡ በሰሩት ፡ ከፉ ፡ ስራ ፡ ወደ ፡ ገሀነም ፡ ሄደው ፡ ቅጣታቸውን ፡ በመቀበል ፡ ፈንታ ፡ አምልጠው ፡ እንደገና ፡ ባዲስ ፡ ስጋ ፡ ውስጥ ፡ ተሸሽገው ፡ መጥተው ፡ ልክ ፡ በዚያ ፡ ባሮጌው ፡ ህይወታቸው ፡ የለመዱትን ፡ እያደረጉ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይሰሩት ፡ የነበረውን ፡ ከፉ ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ እዩሰሩ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሰውን ፡ ሲሰቅዩ ፡ ኖሩ ። በተለይ ፡ ባላገርን ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ሲሰቀዩ ፡ ኖሩ ። ስለዚህ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ግፍ ፡ የሰሩ ፡ በባላገር ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ወደዚያው ፡ ሄደው ፡ ያ ፡ ግፍ ፡ የሰሩበት ፡ ባላገር ፡ ደብድቦ ፡ ሲገድላቸው ፡ ይታዩኛል ! ይህ ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ፍርድ ።" ሲል ፡ እዩሳቀ ፡ እዚያ ፡ ከተሰበሰበው ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሳቅ ፡ መጥቶባቸው ፡ እንዳይስሩም ፡ ፈርተው ፡ እጃቸውን ፡ ባፋቸው ፡ ላይ ፡ እያደረጉ ፡ ሲቸገሩ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። ሌሎቹ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሚለፈልፈውን ፡ ትተው ፡ የተፈጣረውን ፡ ችግር ፡ በያሳባቸው ፡ ያወጡ ፤ ያወርዱ ፡ ስለነበረ ፡ እንዲያውም ፡ አልሰሙትም ። ፊታውራሪ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በተናገረው ፡ ለመሳቅ ፡ አፋቸውን ፡ የያዙትን ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ሲያዩ ፡ ከሶ ፡ ይልቅ ፡ በነሱ ፡ ተቆጥተው ፡ ምንም ፡ ሳይናገሩ ፡ ተነስተው ፡ ወደልፍኛቸው ፡ ሄዱ ።

# ምእራፍ ፡ ፴፩ ፡

## ዘመቻ ፡

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ለምክር ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ጋር ፡ ተጣልተው ፡ በተለያዩበት ፡ ቀን ፡ ማግስት ፡ በሶስቱ ፡ ጉልቶቻቸው ፡ በሚኖሩት ፡ ባላገሮች ፡ ላይ ፡ ለመዝመት ፡ ሲነሱ ፡ ምሽታቸውና ፡ ልጃቸው ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እንኩዋ ፡ የለት ፡ ስንቅ ፡ ለማሰናዳት ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጡዋቸው ፡ በግራቸው ፡ ወድቀው ፡ ለምነው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አዋሉዋቸው ።

ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ባላቸውን ፡ ያነለት ፡ ውለው ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ እንዲነሱ ፡ ለምነው ፡ ለማሸነፍ ፡ የቻሉበት ፡ ከስንቁም ፡ ይልቅ ፡ ያ ፡ ሊነሱበት ፡ ያሰቡት ፡ ቀን ፡ ርብ ፡ መሆኑን ፡ በማስታወስ ፡ ነበር ።

" ምነው ፡ ጌታየ ! እንኩዋን ፡ ለጦርነት ፡ ለትንሽ ፡ ጉዳይስ ፡ ቢሆን ፡ እንደሰዎ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በርብ ፡ ቀን ፡ ይነሳል ? እባክዎ ፡ ዛሬን ፡ ውለው ፡ ነገ ፡ ይነሱ ! ነገ ፡ ሀሙስ ፡ ወዲያው ፡ ያመቱ ፡ ሚካኤል ፡ ለኔ ፡ ሚካኤል ፡ ነው ፡ እኛም ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ ስንቅ ፡ አሰናድተን ፡ የተነሱ ፡ እንደሆነ ፡ እንደሁልጊዜው ፡ ቀንቶዎ ፡ ይመለሳሉ !" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ።

ዘማቾችም ፡ ሆኑ ፡ አዳኞች ፡ ርብና ፡ አርብ ፡ ከቤታቸው ፡ የተነሱ ፡ እንደሆነ ፡ አይቀናቸውም ፡ እየተባለ ፡ የሚነገረውን ፡ ፊታውራሪ ፡ ያምኑበታል ። ብቻ ፡ ባላገሮችን ፡ ለመውጋት ፡ ከመቸኮላቸው ፡ ብዛት ፡ ልነሳበት ፡ ያሉት ፡ ቀን ፡ ርብ ፡ መሆኑን ረስተው ፡ ነበርና ፡ ምሽታቸው ፡ ሲያስታውሱዋቸው ፡ ድንግጥ፡ ብለው ፡ አሳባቸው ፡ እንደ ፡ መመለስ ፡ ሲል ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ ታዩ ። ወዲያው ፡ የፊታውራሪን ፡ መልስ ፡ ማለት ፡ ከፊታቸው ፡ አንብበው ፡- "እመይቴ ፡ የሚሉትኮ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ጌቶች !" አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ። " በረቡእ ፡ ቀን ፡ ለዘመቻ ፡ መነሳት ፡ ደግ፡ አይደለም ! ረቡእ ፡ አይሁድ ፡ ጌታን ፡ ለመያዝ ፡ የመከሩበት ፡

ቀን፡ ስለሆነ፡ የከሀዲዎች፡ ያመጻኞች፡ ቀን፡ ነው ፤ የጌታ፡ ቀን አይደለም፡፡ ስለዚህ ፡ ዛሬን ፡ ውሰው ፡ ነገ ፡ ቢነሱ ፡ ይሻላል ፡፡"

"እኔስ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ብውል ፡ ባልውል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ ስለሌለው ፡ ዛሬን ፡ ውዬ ፡ ነገ ፡ ብሄድ ፡ ግዴለሽም ! ብቻ ፡ የሚገርመኝ፡ የባላገር ፡ አድማ ፡ እንደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ተቆጥሮ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ማሳሰቡ ፡ ነው ! ባለጌ፡ ባላገር ፡ ልቅጣ ፡ ብል ፡ እንደ ፡ ጦርነት ፡ መቆጠሩ ፡ ነው ፡ የሚገርመኝ !"

ያነሰት ፡ ሮብ ፡ ሌቶች ፡ ሰንቅ ፡ ሲያሰናዱ ፥ ወንዶች ፡ ጠመንጃ፡ ያለው፡ ሰላሳ፡ ሰላሳ፡ ጥይት፡ እዬተቀበለ፡ ጠመንጃውን ፡ ሲወለውል ፥ ጠመንጃ ፡ የሌለው ፡ ጦርና ፡ ጋሻውን ፡ ሲጠራርግ፡ ባልደራሶች ፡ የኮርቻ ፡ ከብቶችን ፥ አዛገሮች ፡ የጭነት ፡ ከብቶችን ፡ እቃ ፡ ሲያጠባብቁ ፡ ውለው ፡ አሙስ ፡ የሰኔ ፡ ሚካኤል ፡ እለት ጉዞ ፡ ሆነ ፡፡

ፊታውራሪን ፡ ከተከተሉት ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ሰላሳው ፡ ባለ፡ ጠመንጃ ፥ ሀያው፡ ባለ፡ ጦርና ፡ ጋሻ ፡ ነበሩ ፡፡ ከነሱ ፡ ሌላ ፡ በባልደራሶችና ፡ ባዛገሮች ፡ ክፍል ፡ ከብት ፡ የሚጠብቁና ፡ የሚጭኑ ፡ እንዲሁም ፡ ሌላ ፡ የመላላክ ፡ ስራ ፡ የሚሰሩ ፡ ጀሌዎች ፡ አስር ፡ ያክል ፡ ነበሩ ፡፡ ስለዚህ ፡ በጠቅላላው ፡ ስድሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ወንዶች ፡ ከጌታቸው ፡ ጋር ፡ ሲዘምቱ ፡ ቤት ፡ ለመጠበቅ ፡ የቀሩት ፡ ወንዶች ፡ አዛዥ ፡ ዘሪሁንና ፡ ሞላ ፡ ባህሩ ፡ ለከብት ፡ ጥበቃ ፡ ባላንዲሩ ፡ ገብሬ ፡ ሁለት ፡ ያክል ፡ ዘበኞች ፡ ነበሩ ፡፡

በሴቶች ፡ በኩል ፡ ከንጀራ ፡ ቤት ፡ የሀብትሽ ፡ እናት ፡ አመቴ ፥ ከጠላ፡ ቤት ፡ አድቤ ፥ ከጠጅ፡ ቤት፡ ካሰች ፥ ከወጥ ፡ ቤት ፡ ጌጤ ፡ ነሽ ፡ ሆነው ፡ በወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ግሩም ፡ አገዛማችነት ፡ ዘመቱ ፡፡

ወይዘሮ፡ የሰራሽ ፡ ግሩም ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምረው ፡ ፊታውራሪ ፡ ዘመቻም ፡ ይሁን ፡ አደን ፡ ሲሄዱ ፡ ተለይተው ፡ የማያውቁ ፡ አገዛማች ፡ የጭን ፡ ገረድ ፡ ናቸው ፡፡ ከዘመቻ ፡ ወይም ፡ ካደን ፡ ሲመለሱም ፡ ሌሎች ፡ የጭን ፡ ገረዶች ፡ በዬርስቱና ፡ በዬጉልቱ ፡ ቤት ፡ ተሰርቶላቸው ፡ ሲቀመጡ ፡ እሳቸው ፡ ዲማ፡

እዋናው ፡ ቤት ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ምክትል ፡ ሆነው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፡፡ በሁዋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ በመሽምገላቸው ፡ ምክንያት ፡ የጭን ፡ ገረዶቻቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሲያሰናብቱ ፡ "የስራሽንም ፡ ማስና በት ፡ አስብም ! ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ እሱዋና ፡ እኔ ፡ አብረን ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ እንቀመጥም ! ወይ ፡ እሱዋ ! ወይ ፡ እኔ !" ብለው ፡ ዋናዋ ፡ ምሽት ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ስላስቸገሩ ፡ በገላጋይ ፡ ብዛት ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ወይዘሮ ፡ የስራሽ ፡ በጭራሽ ፡ እንዲሰናበቱ ፡ የጠዬቁትን ፡ እንዲተው ፡ ፊታውራሪም ፡ ሁሉቱን ፡ ሴቶች ፡ አብረው ፡ ማስቀመጣቸውን ፡ ትተው ፡ ለወይዘሮ ፡ የስራሽ ፡ የተለዬ ፡ ቤት ፡ ሰርተው ፡ እንዲያወጡዋቸው ፡ ተገላግለው ፡ እዚያው ፡ ዲማ ፡ ከዋናው ፡ ቤት ፡ ራቅ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ማለፊያ ፡ ቤት ፡ ተሰርቶላቸው ፡ ወይዘሮ ፡ የስራሽ ፡ ቀለብና ፡ ደመወዛቸውን ፡ እዬተቀበሉ ፡ ፊታውራሪም ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ ሁልጊዜ ፡ ባይሆን ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ እዬጎበኙዋቸው ፡ ይቀመጣሉ ፡፡

ፊታውራሪ ፡ ሳይሽመግሉ ፡ በዘመቻ ፡ ባይሆን ፡ ባደን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ እቤታቸው ፡ ከሚኖሩበት ፡ በውጭ ፡ የሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ ይበዛ ፡ ስለነበረ ፡ ከወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ይልቅ ፡ ለወይዘሮ ፡ የስራሽ ፡ ነበሩ ፡፡ ከፊታውራሪ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ በወጡ ፡ ቁጥር ፡ የቦታች ፡ ካልሆነ ፡ የበላይ ፡ የለባቸው ፤ በወይ ዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ፈንታ ፡ ምሽት ፡ አከለው ፡ ምሽት ፡ መስለው ፥ ወን ዱንም ፡ ሴቱንም ፡ አዝዘው ፡ እሜቴ ፡ ተብለው ፥ ደስ ፡ ብሎዋ ቸው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡፡ መቸም ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ የጌቶች ፡ ምሽት ፥ እሜቴ ፡ መባሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላውማ ፡ ከሌሎች ፡ ይገኛል ፡፡

ፊታውራሪ ፡ በሽምግልናቸው ፡ ምክንያት ፡ የድንኩዋን ፡ ኑሮዋቸውን ፡ በጭራሽ ፡ ትተው ፡ እቤታቸው ፡ መኖር ፡ ከጀመ ሩና ፡ ወይዘሮ ፡ የስራሽንም ፡ የሚጎበኙበት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ያውም ፡ አሽሙዋጣጭ ፡ በመፍራት ፡ ጨለማ ፡ ለብሰው ፡ በስ ርቆሽ ፡ ከሆነ ፡ በሁዋላ ፡ የወይዘሮ ፡ የስራሽ ፡ ደስታም ፡ ያስፈ ውን ፡ የድንኩዋን ፡ ኑሮ ፡ በማስታወስና ፡ እንዲሁ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በሚያገኙት ፡ ጉብኝት ፡ ተወስኖ ፡ ነበር፡፡

ሮብ ፡ ማታ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ዘንድ ፡ አሽከር ፡ ተልኮ ፡

መጥቶ ፡ ባላገሮች ፡ ስላደሙ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሲዘምቱባቸው ፡ መነሳታቸውንና ፡ እሳቸውም ፡ አብረው ፡ ለመዝመት ፡ ተሰናድተው ፡ እንዲያድሩ ፡ ጌቶች ፡ ማዘዛቸውን ፡ ሲነግሯቸው ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ለጊዜው ፡ የደስታ ፡ ድንጋጤ ፡ አሳባቸውን ፡ በታተነባቸውና ፡ የሚሉትንም ፡ የሚያደርጉትንም ፡ አጥተው ፡ ተርበተበቱ ። ትንሽ ፡ ቆይተው ፡ ብቻ ፡ የተበታተነ ፡ አሳባቸውን ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ለማጠረቃቀምና ፡ ራሳቸውን ፡ ለመግዛት ፡ ሲችሉ ፡ ከተቀመጡበት ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ ተነስተው ፡ የምስራቹን ፡ ላመጣው ፡ አሽከር ፡ ዋጋውን ፡ ከማለፊያው ፡ ጠላ ፡ እንደ ፡ ብርሌ ፡ ሰጥተውት ፡ ሲጠጣ ፡ እንደገና ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ የሚመጣው ፡ የድንኩዋን ፡ ኑሮ ፡ ያለፈውን ፡ እንድ ባንድ ፡ እየጎተቱ ፡ በላመጣው ፡ አይናቸውን ፡ ሳያረግቡ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በዘገ ፡ አድርገው ፡ ተክለው ፡ ይመለከቱ ፡ ጀመር ።

በድንኩዋን ፡ ግብር ፡ ምሳሽ ፡ ሆኖ ፡ አሽከሮች ፡ ሁሉ ፡ ከወጡ ፡ በሁዋላ ፡ እሳቸውና ፡ ፊታውራሪ ፡ ብቻ ፡ ይቀሩና ፡ ፊታውራሪ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ተደልድሎ ፡ በተነጠፈላቸው ፡ ምኝታ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ይሉና ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ከድልዳሉ ፡ በታች ፡ እመሬት ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ የጌቶችን ፡ ሱሪ ፡ ሲያወልቁ ፡ ከዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ጎንለጎን ፡ እድልዳሉ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ከማለፊያው ፡ ጠጅ ፡ በማለፊያ ፡ ብርሌ ፡ እስኪበቃቸው ፡ ጠጥተው ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ኮኛክ ፡ ደግመው ፡ ሁለቱም ፡ ደስስስ— ሲላቸው ፡— ፊታውራሪ ፡— "በይ ፡ ልብስሽን ፡ አውልቂና ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ አልፈሽ ፡ ተኚ ፡ ዛሬ ፡ በጣም ፡ በርዶኛል ፡ ጀርባየን ፡ እሽኝ ፡ ከሱ ፡ ከፍ ፡ ብለሽ ፡ እከኪኝ ፡ ዝቅ ፡ ብለሽ ፡ ጠቁሚኝ ፡ እሱን ፡ እእ--ሱን ! እእ..ንዲያ ! እእ - ዎ !" የሚሉት ፡ ሁሉ ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ፡ ያ ! ሁሉ ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ እንደገና ፡ ታድሶ ፡ መጣባቸውና ፡ ያነሰት ፡ የሆነ ፡ መሰላቸውና ፡ አይናቸው ፡ በዞ ፡ ፊት ለፊት ፡ እንደ ፡ ተተከለ ፡ ልባቸውን ፡ ያሞቀው ፡ ደስታ ፡ በፊታቸው ፡ ወገግ ፡ ብሎ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። እንዲህ ፡ ካለፈና ፡ ከሚመጣ ፡ ደስታ ፡ ጋራ ፡ በልባቸው ፡ ሲጫወቱ ፡ እንዲህ ፡ ያለፈ ፡ ትዝታና ፡ የሚመጣ ፡ ተስፋ ፡ በራሳቸው ፡ ውስጥ ፡ ሲንጫጫና ፡ ሲያወካ ፡ መላክነቱን ፡ ያመጣው ፡ አሽከር ፡ ሁኔታቸ

ሙን ፡ እንደ ፡ ጉድ ፡ እየተመለከተ ፡ የሰጡትን ፡ ጠላ ፡ ጨርሶ ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ ብሎ ፡ ሲሄድ ፡ አላዩትም ፤ አልሰሙትም ። ያንለት ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ እንደ ፡ ሁልጊዜው ፡ ራታቸውን ፡ ሆዳቸው ፡ ተከፍቶ ፡ ሳይበሉ ፡ እንደ ፡ ሁልጊዜው ፡ እንቅልፍ ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ ሳይተኙ ፡ አደሩ ።

ለወጉ ፡ ያክል ፡ ራታቸው ፡ ቀረበላቸው ፡ የሚውጡት ፡ እህል ፡ በጉሮሮዋቸውም ፡ በደረታቸውም ፡ እየቆመ ፡ እንዲያው ፡ ነካ ፡ ነካ ፡ አድርገው ፡ አስነስተው ፡ ልብሳቸውንና ፡ ጌጣቸውን ፡ በስራት ፡ አሰናድተው ፡ ለማሳደር ፡ ቢያስቡ ፡ በተለይ ፡ ጌጣቸው ፡ ምኑ ፡ እምን ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ቅጡ ፡ ጠፋቸው ። የራስ ፡ ወለባው ፡ ያንገት ፡ ነጠላና ፡ ሽርብ ፡ ድሪው ፡ አሸንክታቡ ፡ ጠልሰሙ ፡ መስቀሉ ፡ የጆሮ ፡ ጉትቻው ፡ የጅ ፡ አምባሩና ፡ የጣት ፡ ቀለበቱ ፡ የግር ፡ አልቦውና ፡ ደረጁ ፡ ኧረ ፡ ስንቱ ! እግዜር ፡ በሰጠው ፡ የሴቶች ፡ ውበት ፡ ላይ ፡ ውበት ፡ የሚጨምረውና ፡ በጎደለው ፡ የሚሞላው ፡ ጌጥ ፡ ሁሉ ፡ በዬቦታው ፡ ተበታትኖ ፡ ብዙ ፡ አመት ፡ ተረስቶ ፡ ኖሮ ፡ እየፈለጉ ፡ የማጠራቀሙ ፡ አሳብ ፡ ሊወጡት ፡ የማይቻል ፡ ገደል ፡ መስሎ ፡ ታያቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ "ያስጌጥዋ ፡ የወጣች ፡ ወይዘሮ ፡ ያለመሳሪያው ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ አዳኝ ፡ ድካምዋ ፡ ከንቱ ፡ ነው !" የሚባለው ፡ ተረት ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ፡ የጠፋው ፡ ቢጠፋ ፡ የተገኘውን ፡ ያክል ፡ ከተበታተነበት ፡ ሰብስበው ፡ ይዘውት ፡ የሚሄዱትን ፡ አዘጋጅተው ፡ ለማደር ፡ ቆረጡ ።ስለዚህ ፡- አገልጋያቸው ፡ ልኩራ ፡ በሁሉ ፡ በቤቱ ፡ የሚገኘውን ፡ ሁሉ ፡ አገልግል ፡ ሙዳይ ፡ ከረጢት ፡ ቶፋ ፡ ማሰሮና ፡ ሌላም ፡ ጌጣጌጥ ፡ ሊቀመጥበት ፡ የሚችል ፡ እቃ ፡ ከዬስርቻው ፡ እየበረበረች ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ አውጥታ ፡ በፊታቸው ፡ አሰልፋላቸው ፡ እሳቸው ፡ እያንዳንዱ ፡ እቃ ፡ የያዘውን ፡ እምንጣፍ ፡ ላይ ፡ እየዘረገፉ ፡ ሲፈልጉ ፡ እሷዋ ፡ ሰራቸውን ፡ ሲጨርሱ ፡ ገላቸውን ፡ የሚታጠቡበት ፡ ውሀ ፡ ታሞቅ ፡ ጀመር ።

እውነትም ፡ "ያልቆረጠ ፡ እግሩ ፡ አይደርስም" እንደሚባለው ፡ መቁረጥ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ የፈለጉትን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንኳዋ፡ ሳይፈጅባቸው ፡ ገላቸውን ፡ የሚታጠቡበት ፡ ውሀ ፡ እስኪሞቅ ፡

መርጠው ፡ ጨረሱ ። አንዳንዱ ፡ ጌጥ ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ አርጅቶ ፡ ተበላሽቶ ፡ ከመጣሉ ፡ በቀር ፡ ሊያስጌጥ ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ስላገኙት ፡ ራሱ ፡ በማርጀቱ ፡ እንዲወድቅ ፡ የተፈረደበት ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ የሳቸውን ፡ እድሜ ፡ የሳቸውን ፡ እርጅና ፡ ጭምር ፡ ስላስታወሳቸው ፡ የተበላሸውን ፡ ጌጥ ፡ በጃቸው ፡ እያገላበጡ ፡ ?ር ፡ ብሎዋቸው ፡ ቆዩና ፡ በመጨረሻ ፡ አሮጌውን ፡ ጌጣጌጥ ፡ ?ሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሰብስበው ፡ ባሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ አስረው ፡ ወደ ፡ ጎን ፡ ጥለው ፡ ደህና ፡ ደህናውን ፡ ለኩራ ፡ በሁሉ ፡ እንድትወለውልላቸው ፡ መርጠው ፡ ለብቻ ፡ አስቀመጡ ። ገላቸውን ፡ ታጥበው ፡ ራሳቸውን ፡ ባደስና ፡ በስምቡል ፡ በጠጀሳርና ፡ በሎሚ ፡ ተነጥሮ ፡ ልክ ፡ የተባራ ፡ ጠጅ ፡ መስሎ ፡ በተቀመጠ ፡ ቅቤ ፡ ጣጥም ፡ አድርገው ፡ ተቀብተው ፡ ከውስጥ ፡ በንስት ፡ ቀበል ፡ ከዚያ ፡ በመናሬም ፡ ጨርቅ ፡ ከላይ ፡ በሻሽ ፡ አስረው ፡ ወደ ምንታቸው ፡ ሄዱ ። ልኩራ ፡ በሁሉ ፡ ጌጣጌጣቸውን ፡ ስትወለውልና ፡ የሚዘምተውን ፡ ልብሳቸውን ፡ በከረጢት ፡ ስትከት ፡ እስክከሰ ፡ ሌሊት ፡ ቆዩች ።

"እንቺ ፡ ልኩራ ፡ በሁሉ !" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ እምኝታቸው ፡ ላይ ፡ ሄደው ፡ ሲጋደሙ ፡ የረሱት ፡ ትእዛዝ ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ።

"እሜቴ ፡ ሳሉ !" አለች ፡ ልኩራ ፡ በሁሉ ፡ አቤት ፡ ለማለት ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽና ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ተማክረው ፡ በፈጠሩላት ፡ ቁዋንቁዋ ።

"ቶሎ ፡ ጨርሰሽ ፡ ተኚና ፡ ጥዋት ፡ ወፍ ፡ ሲንጫጫ ፡ ተነስተሽ ፡ ለራሴ ፡ ውሀ ፡ እንድታሞቂልኝ !"

"እሺ እሜቴ !"

"ዋእእ --- አንቺ ፡ እንቅልፍሽም ፡ አሀዮ ! እንደ ፡ ድሮው ፡ መስሎሽ ፡ ተኝተሽ ፡ ታረፍጂና ፡ ልብ ፡ አርጊ ፡ ወፍ ፡ ሲንጫጫ ፡ ብትነሺለሁ ! ገና ፡ ሰማዩ ፡ መሬቱ ፡ ሳይለይ !"

"እሺ እሜቴ ! ኡፍ --- እንጊዴ ፡ ጭቅጭቃት ፡ ጀምርታለች ! መከራን ፡ አብልታለች !" አለች ፡ ልኩራ ፡ የመጨረሻውን ፡ ክፍል ፡ ንግግሯን ፡ እመቤትዋ ፡ እንዳይሰሙ ፡ ድምጽዋን ፡ ዝቅ ፡ አድርጋ ።

ሐሙስ ፡ ጥዋት ፡ ልኩራ ፡ በሁሉ ፡ እንደ ፡ ታዘዘችው ፡ ገና ፡ ሰማይ ፡ መሬት ፡ ሳይለቅ ፡ ውሀዋን ፡ አሙቃ ፡ እመቤትዋን ፡ ቀሰቀሰቻቸው ። ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ሌሊቱን ፡ እንቅልፍ ፡ እንቢ ፡ ብሎዋቸው ፡ ሲወራጩ ፡ አድረው ፡ እንጋት ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፡ ነበረና ፡ ልኩራ ፡ ስትቀሰቅሳቸው ፡ በጣም ፡ ደንግጠው ፡ ስለ ተነሱ ፦

"ስማልፋዲስ ፡ ቂዲስዲስ ! አይዞ ፡ ቲደንጊጥ ፡ ኢሜቴ ፡ ሁንንጋና ፡ ወፍሜሜትኛ ፡ ሁንንጋና ፡ ሜራብንሳማ ፡ ላቀቃትኛ! እስኪ ፡ ልኩራ ፡ እመቤትዋ ፡ ደንግጠው ፡ ሲነሱ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ እንዳይጣረራቸው ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠራች ።

ወዲያው ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ቶሎ ፡ ተነስተው ፡ ውጭ ፡ ደርሰው ፡ ተመለሱና ፡ ራሳቸውን ፡ በሙቅ ፡ ውሀና ፡ በሳሙና ፡ ሙልጭ ፡ አድርገው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ታጥበው ፡ ጠጉራቸው ፡ ደርቆ ፡ እንዳይንጨበረር ፡ በፊት ፡ ጣታቸው ፡ ከንጥፉ ፡ ቅቤ ፡ ትንሽ ፡ ቆንጠር ፡ አድርገው ፡ በመሀል ፡ እጃቸው ፡ ሰብተው ፡ አሸሸሸት ፡ አደረጉና ፡ ተበጥረው ፡ ፊታቸውን ፡ በመስተዋት ፡ ሲመለከቱ ፡ ጊዜ ፡ የድሮዋን ፡ ካስራምስት ፡ አመት ፡ በፊት ፡ የሚያዋቁዋትን ፡ የሰራሽን ፡ አዩ ፤ ያስራምስት ፡ አመት ፡ እድሜያቸው ፡ ከቅቤው ፡ ጋር ፡ በሙቅ ፡ ውሀና ፡ በሳሙና ፡ ታጥቦ ፡ እንደሄደ ፡ ሁሉ ፡ የሰላሳ ፡ አምስት ፡ አመት ፡ የሰራሽ ፡ እመስተዋቱ ፡ ውስጥ ፡ እዩና ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ከዚያ ፡ ተነስተው ፡ ጥልፍ ፡ ቀሚሳቸውን ፡ ለበሱና ፡ የተወለወለውን ፡ ጌጣጌጥ ፡ አቅርበው ፡ ወርቅ ፡ መስቀላቸውን ፡ አልቅታቸው ፡ ላይ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ እየተሰባጠረ ፡ የተሰካ ፡ አሸንክታባቸውን ፡ እደረታቸው ፡ ላይ ፡ ከዚያ ፡ ትንሽ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ እሁንም ፡ እደረታቸው ፡ ላይ ፡ የወርቅ ፡ ሸንብ ፡ ድሪያቸውን ፡ ከዚያ ፡ ደህን ፡ ሁሉ ፡ ከዛና ፡ አቅፎ ፡ በየቦታው ፡ እንዲያገባ ፡ ከባድ ፡ ብር ፡ መስቀል ፡ የተንጠለጠለበት ፡ ጀመሬ ፡ ማተባቸውን ፡ ባንገታቸው ፡ አድርገው ፡ ወርቅ ፡ ጉትቻዎቻቸውን ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጆሮዎቻቸው ፡ ብር ፡ አምባሮቻቸውን ፡ በክንዳቸው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ቀለበቶቻቸውን ፡ በጣቶቻቸው ፡ አልቦና ፡ ድሪዷቸውን ፡ በግራቸው ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ መስቀል ፡ ደመራ ፡

በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጥ ፡ አጊጠው ፡ አምረው ፡ ሲታዩዋቸው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላትና ፡-

“እ-እ - - - ኢሜቴ ፡ ኢሜቴ ፡ እንዴት ፡ እንዴት ፡ ናም ራለች!እንዴት ፡ እንዴት ፡ ተማለች!” አለች ፡ ልኩሬ ።

“እምራለሁ ? ልኩሬ !” አለ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽም ፡ አገል ጋዮቻቸው ፡ ሲያሞግሳቸው ፡ በበኩላቸው ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ። መቾም ፡ ምስጋና ፡ ከየትም ፡ ቢመጣ ፡ የተመሰገነን ፡ ልብ ፡ በደስታ ፡ መማረኩ ፡ አይቀርም ።

ከዚያ ፡ ልኩሬ ፡ በሁሉ ፡ ያደረ ፡ እንጀራ ፡ በትኩስ ፡ የቅቤ ፡ ሽሮ ፡ አቅርባላቸው ፡ ትንሽ ፡ በሉና ፡ አንድ ፡ ብርሌ ፡ ማለፊያ ፡ ጠላ ፡ ጠጥተው ፡ ቡና ፡ ስትቀዳላቸው ፡ “ተጓሽን ፡ ቂቤ ፡ ጨምሬ ለሽ ፡ ጠጣች ፡ ኢሜቴ ፡ ሁዋጢጥትን ፡ ከልክልልሻል!” አለች ።

“ታዲያ ፡ ቅድም ፡ አብረሽ ፡ አታቀርቢም ፡ ኖረሻል!አሀየ! በዶ ፡ አሁንም ፡ ቶሎ ፡ አምጭልኝ ፡ ሰዎች ፡ መምጫቸው ፡ ደር ሶዋል!”

ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ቁርሳቸውን ፡ አድርገው ፡ ታጥቀው ፡ እቃቸውን ፡ ሁሉ ፡ አስናድተው ፡ ሲጠብቁ ፡ አርፍደው ፡ በመጨ ረሻ ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ የሚቀመጡባትን ፡ በቅሎ ፡ እዩሳበ ፡ እራቱ ፡ የፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ አሽከሮች ፡ ለዩስራቸው ፡ የሚያስ ፈልገውን ፡ እቃ ፡ የሚታዘለውን ፡ አዝለው ፡ የሚንጠለጠለውን ፡ እንጠልጥለው ፡ ደረሱ ።

“ጉዋዙ ፡ ቀድሞዋልና ፡ ሳይርቅ ፡ እንድረስበት ፡ እመ ይቴ !”አለ ፡ በቅሎ ፡ እዩሳበ ፡ የመጣው ፡ አሽከር ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽን ፡ እጅ ፡ ከነሳ ፡ በሁዋላ ። ወዲያው ፡ ተሸከሞ ፡ እበቅ ሎዋ ፡ ላይ ፡ ሲያስቀምጣቸው ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ውሎ ፡ ገባ ፡ እንደሚሄዱ ፡ ሁሉ ፡-

“ ልኩሬ ፡ ቤቱን ፡ ደህና ፡ አድርገሽ ፡ ስትጠብቂ ፡ እን ድትቆይኝ ፡ ዋእ---አንች ፡ ቅንዳሻም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ተበላሽቶ ፡ እገኝና ፡ ልብ ፡ አርጊ !” ብለው ፡ በጉዋዙ ፡ ለመድረስ ፡ በቅሎዋ ቸውን ፡ አስገሩ ።

“ ሂጂዲያ ! ቂንዳሻ ፡ ቂንዳሻ ፡ ላለች ፡ ኢሰዋን ፡ ቂን ዳሽ!” አለች ፡ ልኩሬ ፡ እመቤትዋ ፡ በቅሎዋን ፡ እያስገሩ ፡ ሲሄዱ፡

መቻም ፡ አይሰሙኝ ፡ ብላ ።

ጉዋዙን ፡ ይዘው ፡ ፈለግግ ፡ እምትባለዋ ፡ ቦታ ፡ ሲደርሱ ፡ ሰፈሩ ፡ እዚያ ፡ እንዲሆን ፡ አስቀድሞ ፡ ተወስኖ ፡ ስለነበረ፡ ድንኩዋን ፡ አስተክለው ፡ ምንጣፍ ፡ አስነጥፈው ፡ ጌቶችና ፡ ተከታዮቻቸው ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ የሚጠጡትን ፡ መጠጥ ፡ በዬደረጃው ፡ አዘጋጅተው ፡ ቡና ፡ አስፈልተው ፡ ይጠባበቁ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ፊታውራሪ ፡ ከዶረቅ ፡ ጦራቸው ፡ ጋር ፡ ገስግሰው ፡ ደረሱ ።

ከበቅሎዋቸው ፡ ዱብ ፡ ብለው ፡ እድንኩዋናቸው ፡ ጥልቅ ፡ ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ ለጥ ፡ ብለው ፡ እጅ ፡ ነስተው ፡ ጉልበት ፡ ስመው ፡ አፋቸውን ፡ ተስመው ፡ ቶሎ ፡ ተሰልፎ ፡ የሚጠብቀውን ፡ ቁርስና ፡ ቡና ፡ አስቀርበው ፡ ጌቶችን ፡ ካቀመሱ ፡ በሁዋላ ፡ ተከታዮችን ፡ ድንኩዋኑ ፡ እንደሚችለው ፡ እንደዬማእርጋቸው ፡ እያስገቡ ፡ መጠጥ ፡ እያጠጡ፡ እንዲወጡ ፡ አደረጉ ። ከዚያ ፡ ሰው ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ያንገት ፡ የደረት ፡ ጌጣቸውን ፡ ሸፍኖ ፡ የቆዬውን ፡ ኩታቸውን ፡ ከላያቸው ፡ ጠቅለል ፡ አድርገው ፡ ሁለተኛ ፡ እንደማይፈልጉት ፡ ሁሉ ፡ ወዲያ ፡ ወርወር ፡ አድርገው ፡ ፊታውራሪ ፡ ከተቀመጡበት ፡ ድልዳል ፡ ስር ፡ በተነጠፈው ፡ ምንጣፍ ፡ ላይ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ ተቀመጡና ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ የጌቶችን ፡ እግሮች ፡ ከድልዳሉ ፡ ላይ ፡ ጎትተው ፡ አውርደው ፡ እጭኖቻቸው ፡ ላይ ፡ አድርገው ፡ እያሻሹ ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ ባፋቸውም ፡ ባይናቸውም ፡ ያቆላምጡዋቸው ፡ ጀመር ።

" ምነው ፡ ጌታዬ ፡ ያጠጡ ፡ እንጂ ! አልጠማዎም ? ወይስ ፡ ባይጥምዎ ፡ ነው ! ጠጁ ፡ ያለቅጥ ፡ ደርቆ ፡ እንደሆን ፡ ትንሽ ፡ ማር ፡ ላልሰው !"

"ምጣ ፡ ሞጣ ፡- የለም ፡ ደህና ፡ ነው ! ልክ ፡ ነው !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ጠጁ ፡ መድረቅ ፡ አለመድረቁን ፡ ለማየት ፡ አፋቸውን ፡ አጣጥመው ።

" እንግዲያስ ፡ እንደ ፡ እያያዝም ፡ ይጠጡና ፡ ልድገምዎ !"

"የለም ፡ አሁን ፡ አጫውችኝ ፡ በሁዋላ ፡ ትደግሚኛለሽ !

ይልቅ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅሽ ፡" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የጭን ፡ ገረዳቸው ፡ እጅግ ፡ አምረው ፡ ያጌጡበትን ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ጌጥ ፡ አስጊጠው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀና ፡ እያሉ ፡ በጎን ፡ እያዩ ፡ እግራቸውን ፡ ሲያሻሹዋቸው ፡ ዘቅዝቀው ፡ ተመልክተው ፡ ከሀያ ወይም ፡ ከሰላሳምስት ፡ አመት ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የሰራሽ ፡ ግሩም ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ ታዩዋቸው ፡ የራሳቸውም ፡ እድሜ ፡ ያኑ ፡ ያክል ፡ የተቀነሰ ፡ መሰሎ ፡ ተሰማቸውና ።- " ጌጡስ ፡ ይሁን ፤ በጄ ! ውበቱንና ፡ ልጅነቱንም ፡ ከጌጡ ፡ ጋር ፡ ቆጥቦ ፡ ጠብቆ ፡ የሚያስቀምጥ ፡ የምስጢር ፡ ሳጥን ፡ ኖሮሻል ?"

" ውበትና ፡ ልጅነት ፡ ቆጥቦ ፡ የሚያስቀምጥ ፡ ሳጥን ፡ የመስራት ፡ ሀይል ፡ ቢኖረኝ ፡ የጌቶቼ ፡ ሁሉ ፡ እመቤት ፡ ሆኜ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ በተሰራ ፡ ሰገነት ፡ እኖር ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በዚያች ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ ከልኩራ ፡ በሁሉ ፡ ጋር ፡ እኖር ፡ ኖሮዋል ?" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ የሚያባብሉ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ገደም ፡ አድርገው ፡ እሽማግሌው ፡ አይኖች ፡ ላይ ፡ ተክለው ።

" የለም ፡ የለም ፡ ምስጢር ፡ አለሽ ! ለሌላ ፡ ሰው ፡ ከማካፈሉ ፡ በደሳሳ ፡ ጎጆየ ፡ ተቀምጬ ፡ ምስጢሬን ፡ ለራሴ ፡ ብቻ ፡ ማድረጉ ፡ የበለጠ ፡ ይጠቅመኛል ፡ ብለሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ውበትና ፡ ልጅነት ፡ ቆጥቦ ፡ የሚጠብቅ ፡ ምስጢር ፡ እንዳለሽ ፡ ይህ ፡ ይመሰክራል !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ለልባቸው ፡ የተሰማው ፡ ሙቀት ፡ እፊታቸው ፡ ላይ ፡ እየታየ ፡ ከተጋደሙበት ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ የጭን ፡ ገረዳቸውን ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ ቆንጠጥ ፡ አድርገው ።

" ምስጢሩን ፡ ልንገርዎ ፡ መቸም ፡ ከጌታዩ ፡ የምደብቀው ፡ ምስጢር ፡ የለኝ ! "

" በይ ፡ ንገሪኝ ፡ ምንድነው !"

" ጌታዩን ፡ እንዲህ ፡ በገዛዴ ፡ እንዲህ ፡ በሙሉ ፡ የማግኘቱ ፡ ደስታ ፡ ነው ! እሱ ፡ ነው ፡ ያደሰኝ ! ይመጡ ፡ ይሆን ፡ ይቀሩ ፡ ይቆዩ ፡ ይሆን ፡ ያሄዱ ፡ እያልሁ ፡ መስጋቱ ፡ ቀርቶ ፡ እንዲህ ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ከጌታዩ ፡ ያለመለየቱ ፡ አሳብ ፡ አብሮ ፡ የመሆኑ ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ ምስጢሩ ! ሌላ ፡ አይደለም !"

" ወይድ ፡ ተጫፈ ! ይህን ፡ ያክል ፡ ወደሽኝ !" አሉ ፡

ፊታውራሪ ፡ ከጭን ፡ ገረዳቸው ፡ በሰሙት ፡ የፍቅር ፡ ኑዛዜ ፡ ልባቸው ፡ በደስታ ፡ እዬዋኘ ፡ አሁንም ፡ ጨምረው ፡ ለመስማት ።

" እንግዲያ ፡ አልቀረብሁ ! እንደ ፡ መናኝ ፡ ብቻየን ፡ ቤት ፡ ዘግቼ ፡ ይሀን ፡ ያክል ፡ ዘመን ፡ የምኖር ፡ በጌታየ ፡ ፍቅር ፡ ታስሬ ፡ ሌላ ፡ ወንድ ፡ ሁሉ ፡ ወንድ ፡ አልመስለኝ ፡ ብሎ ፡ የሌላ ፡ ወንድ ፡ ክንድ ፡ ተንተርሼ ፡ ከመተኛት ፡ ጌታየን ፡ እያሰብሁ ፡ ብቻየን ፡ መተኛቴን ፡ መርጬ ፡ አይደለም ? ሌላ ፡ ምክንያት ፡ አለው ፡ ብቻየን ፡ ተኮራምቼ ፡ የምኖርበት ? " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ አሁንም ፡ ፊታውራሪን ፡ ገደም ፡ አድርገው ፡ እያዩ ።

ፊታውራሪ ፡ ልባቸው ፡ በፍቅር ፡ ተማረክና፡-" ነይ ፡ እድልዳሉ ፡ ላይ ፡ ውዴ !" አሉ ፡ የጭን ፡ ገረዳቸውን ፡ እጅ ፡ እዬሳቡ ።

" እንቺና ፡ እኔ ፡ የውጭ ፡ ሰዎች ፡ ነን ፤ የቤት ፡ ሰዎች ፡ አይደለንም ፡ ማለት ፡ ነው !" አሉ ፡ ቀጠሉና ፤ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ የጭን ፡ ገረዳቸውን ፡ ፊት ፡ ሲደባብሱ ፡ ቆዩና ።

" እንዴት ?"

" እይውልሽ ፤ እኔም ፡ ይሀን ፡ ጉዞ ፡ ካሰብሁ ፡ ጀምሮ ፡ ሰውነቴ ፡ ቀለል ፡ ብሎኝ ፡ አዲስ ፡ ሀይል ፡ ይሰማኛል ፤ የድሮው ፡ እኔ ፡ መሆኔ ፡ ይሰማኛል ። ሰውን ፡ የሚያደክመው ፡ ሰውን ፡ የሚያስረጀው ፡ እድሜን ፡ እዬቆጠሩ ፡ አርጅቻለሁ ፡ ብሎ ፡ እቤት ፡ መዋል ፡ ነው ። የሚባለው ፡ እውነት ፡ ነው ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፤ የጭን ፡ ገረዳቸው ፡ በጎናቸው ፡ እድልዳሉ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ በፍቅር ፡ አይን ፡ ገደም ፡ አድርገው ፡ ሲመለከቱዋቸው ፡ የሽማግሌ ፡ ልባቸው ፡ ፊጠን ፡ ብሎ ፡ እዬመታ ። ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ የሳቸውን ፡ ልጅነትና ፡ ውበት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ፊታውራሪም ፡ ልጅነትና ፡ ሀይል ፡ የሚሰማቸው ፡ መሆኑን ፡ ጭምር ፡ ስለ ፡ ነገሩዋቸው ፡ ልባቸው ፡ በደስታ ፡ እዬዋኘ ፡ የጋራ ፡ ልጅነት ፡ የሚሰማቸው ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ በሚያደርጉት ፡ ለመድረስ ፡ ሲቸኩሉ ።

" ብዙ ፡ ሰራዊት ፡ መጣ !" አለ ፡ አንድ ፡ አሽከር ፤ ድንገት ፡ ድንኩዋኑን ፡ ገለጥ ፡ አድርጎ ።

" እግር ፡ ካንገት ፡ ይሰርሀና ! ሂድ ፡ የታባትህ ፡ ከዚህ!" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ግዳዩን ፡ እንዳስጣሉት ፡ ነብር ፡ ቁጣቸው ፡ በፊታቸው ፡ እየነደደ ። ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ደን ፡ አሽከር ፡ እዚያው ፡ በቆመበት ፡ እንደ ፡ ሌጥ ፡ ምሽት ፡ ድርቅ ፡ ከርር ፡ አድርገው ፡ ደንጋይ ፡ አድርገው ፡ የሚያስቀሩበት ፡ ሀይል ፡ በ[illegible]ራቸው ፡ ባልማሩት ፡ ነበር !

" ብዙ ፡ ሰራዊት ፡ መምጣቱን ፡ ለጌቶች ፡ ንገር ፡ እንዲጠነቀቁ ፡ ብለው ፡ አጋፋሪ ፡ መሰረት ፡ ስለ ፡ ላኩኝ ፡ ነውኮ!" አለ ፡ አሽከሩ ፡ ከመደንገጡ ፡ የተነሳ ፡ ድንኩዋኑን ፡ ጎልጦ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ እዚያው ፡ ማትር ፡ ብሎ ፡ ቆሞ "

" ወግደኸ ፡ አልሀሁ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

" እህህህ . . .! ግዴለም ፡ ይቁሱ ፡ ይታጠቁ ፡ ጌታዬ ፡ የመጣው ፡ ሰራዊት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ። " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ በረዥሙ ፡ ተንፍሰው"

" የምን ፡ ሰራዊት ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ፡ ብቻ ፡ ብዙ ፡ ሰራዊት ፡ ከወደዲማ ፡ እኛ ፡ የመጣንበትን ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡ ስለመጣ ፡ ለምንም ፡ ለምን ፡ ብንጠነቀቅ ፡ አይከፋም ፡ ብዬ ፡ ነበርኮ ፡ ልጄን ፡ የላክሁት !" አለ ፡ አጋፋሪ ፡ መሰረት ፡ የላከው ፡ አሽከር ፡ ጌቶች ፡ ተቆጥተው ፡ እንዳባረሩት ፡ ሲነግረው ፡ ራሱ ፡ መጥቶ ።

" እኮ ፡ አልፎ ፡ ሂያጅ ፡ ሰራዊት ፡ በመንገድ ፡ አዩን ፡ ብላችሁ ፡ እኔን ፡ እንዳላርፍ ፡ የምታስቸግሩበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ! ትንሽ ፡ ተኝቼ ፡ እንዳላርፍ ፡ ሴራ ፡ ገብታችሁዋል !"

" ጠላት ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ሳንጠነቀቅ ፡ እንዳንያዝ ፡ አስቤ ፡ ያደረግሁት ፡ ነበር !" አለ ፡ አጋፋሪ ፡ የጌታውን ፡ ቁጣ ፡ ሲያይ ፡ እንደ ፡ ማዘን ፡ ብሎ ፡ ፊታውራሪ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ይተጣጠቁ ፡ ጀመር ።

ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡ ሰራዊቱ ፡ ደረሰ ። የፊታውራሪ ፡ የስጋና ፡ የጋብቻ ፡ ዘመዶች ፡ ነበሩ ።

አዛዥ ፡ ደስታ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ባላምበራስ ፡ ታዬ ፡ ጸሀይ ፡ ልጅ ፡ ተሰማ ፡ ሀይሉና ፡ ልጅ ፡

አማረ ፡ መልኬ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ያክል ፡ ባለጠመንጃና ፡ ሰላሳ ፡ ያክል ፡ ባለጦርና ፡ ጋሻ ፡ ጭፍሮች ፡ ይዞ ፡ አስከትለው ፡ ፊታውራሪን ፡ ለመርዳት ፡ መምጣታቸው ፡ ነው ።

" የዝምድና ፡ ማሰሪያ ፡ ምንም ፡ ቢቀጥን ፡ ምንም ፡ ቢሰለስል ፡ ስለት ፡ ሊቆርጠው ፡ አይችልም" እንደሚባለው፡- ምንም ፡ ፊታውራሪ ፡ የዘመዶቻቸውን ፡ ምክር ፡ ጥሰው ፡ ከዘመዶቻቸው ፡ ጋር ፡ የተባሉ ፡ የተቆራረጡ ፡ መስለው ፡ ቢለያዩ፡- በመጨረሻ ፡ ያ ፡ የዝምድና ፡ ማሰሪያ ፡ የቅርብም ፡ ሆኖ ፡ የሩቅ ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ እሳቸው ፡ በሄዱበት ፡ ጎትቶ ፡ አመጣቸው !ሲመከሩት ፡ ለማይሰማ ፡ ሰው ፡ ዘመድ ፡ ሆኖ ፡ አለ መገኘት ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡ ነው ! ባእድ ፡ መክረውት ፡ አልሰማ ፡ ሲል ፡ " ከጥፋትህ ፡ ከጉድፍህ ፡ ንጹ ፡ ነኝ ፡ " ብሎ ፡ እጁን ፡ ታጥቦ ፡ መሄድ ፡ ብቻ ፡ ነው ! የዘመድ ፡ ጥፋት ፡ የዘመድ ፡ ጉድፍ ፡ ግን ፡ ቢያጥቡት ፡ አይለቅም ፡ እብር ፡ ያሳድፋል ! ስለዚህ ፡ ፊታውራሪ ፡ በባላገሮች ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉት ፡ ዘመቻ ፡ አደጋ ፡ የሞላበት ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ፡- የሚያስነቅፍና፡ የሚያስጸይፍ ፡ እንጂ ፡ የሚያስከብርና ፡ የሚያስመሰግን ፡ አለ መሆኑን ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ቢያውቁም ፡ መክረው ፡ መመለስ ፡ ሲያቅታቸው ፡ በዝምድና ፡ ማሰሪያና ፡ በይሉኝታ ፡ ተጎትተው ፡ የጠሉትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከክፉ ፡ አድራጊው ፡ ጋር ፡ ተባብረው ፡ ለማድረግ ፡ መጡ።-

ፊታውራሪ ፡ የሰፈሩበት ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ጋራ ፡ ጥግ ፡ ከወይዲማ ፡ ወገን ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ጋራውን ፡ አልፎ ፡ እናሞራ ፡ ለመድረስ ፡ ከሁለት ፡ ሰአት ፡ ቢያንስ ፡ እንጂ ፡ አይበልጥም ። ስለዚህ ፡ ፊታውራሪና ፡ ዘመዶቻቸው ፡ በሰፈሩበት ፡ አድረው ፡ ከሌሊቱ ፡ አስር ፡ ሰአት ፡ ግድም ፡ ሲሆን ፡ ጉዋዙን ፡ እንዲከተል ፡ አዝዘው ፡ ያረት ፡ ጦር ፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ ገስግሰው ፡ እንጋት ፡ ላይ ፡ እናሞራ ፡ ገቡ ።

ከሴት ፡ ከህጻናትና ፡ ካንዳንድ ፡ ታመው ፡ የቀሩ ፡ ሽማግሎች ፡ በቀር ፡ በሙሉ ፡ እናሞራ ፡ የወንድ ፡ ምልክት ፡ አይታይም ፡ ነበር ። ሽሙ ፡ ብቻ ፡ ተገኘ ። ከብቱ ፡ እንኩዋ ፡ በረት ፡ ከፍቶ ፡ የሚያስወጣው ፡ አጥቶ ፡ በጭበረቱ ፡ እንደ ፡ ታጎረ ፡

ነበር ፡-

"አንተ ፡ ወንዱ ፡ ሁሉ ፡ የት ፡ ደረሰ ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሹሙን ።

"የጌታዬን ፡ መምጣት ፡ ሰምቶ ፡ ሸሸ ! ተበታተነ !" አሉ ፡ ሹሙ ፡ ብላታ ፡ መንግስቱ ።

"መምጣታችንን ፡ ማን ፡ ነገረው ?"

"ሀእም— ! ወፍ ፡ ነገረው ! ጌታዬ !"

"አአ— ! ወፍ ፡ ነገረው ! በል ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ወፍ ፡ እንደ ነገረው ፡ በሁዋላ ፡ ትነግረናለህ ! አንት ፡ ከሀዲ ፡ የኛን ፡ ሹመት ፡ ይዘህ ፡ ከባላገር ፡ ጋር ፡ እያደምህ ፡ የምትሰራውን ፡ የማናውቅ ፡ መሰለህል ! በል ፡ ያዝልኝ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ወደጋፋሪያቸው ፡ ዘወር ፡ ብለው ። ከዚያ ፡ እሹሙ ፡ ቤት ፡ ተነጥፎ ፡ እንዲገቡ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ አሳብ ፡ ቢያቀርቡ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንቢ ፡ ስላሉ ፡ እደጅ ፡ በዮግንዱም ፡ በዮደንጋዩም ፡ ላይ ፡ የበቅሎ ፡ ምቹ ፡ እዮተነጠፈላቸው ፡ ጌቶችም ፡ መኳዋንንቱም ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጠብቁ ፡ ጉዋዙ ፡ ደረሰና ፡ ድንኳዋን ፡ ተተክሎ ፡ እድንኳዋን ፡ ገቡ ። ወዲያው ፡ እንጨት ፡ እዮተቆረጠም ፡ ቤት ፡ እዮፈረሰም ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ አጥር ፡ እሜዳው ፡ ላይ ፡ ታጥሮ ፡ የናሞራ ፡ ከብት ፡ ሁሉ ፡ ከዮበረቱ ፡ እዮተነዳ ፡ አጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ታጎረ ፡- የመጀመሪያው ፡ ውርስ ፡ መሆኑ ፡ ነው !

ፊታውራሪ ፡ እስከ ፡ ሰራዊታቸው ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ እናሞራ ፡ ሲበ[illegible] ፡ ስድስት ፡ የወፋፈሩ ፡ ፍሪዳዎችና ፡ ብዙ ፡ በግ ፡ አሳርደው ፡ ከባላገር ፡ ቤት ፡ የ[illegible]ውን ፡ ድቁስና ፡ ቅቤ ፡ ጠላና ፡ ማር ፡ እያዘረፉ ፡ ትልቅ ፡ ድግስ ፡ ሆኖ ፡ ሰነበቱ ። ሴቶችንና ፡ አንዳንድ ፡ ነፍስ ፡ ያወቁ ፡ ልጆችን ፡ እያስያዙ ፡ አሳስረውም ፡ አስገርፈውም ፡ ያገሩ ፡ ወንድ ፡ ተሰብስቦ ፡ የሄደበትን ፡ ቢጠይቁ ፡ ምንም ፡ ወሬ ፡ ሊያገኙ ፡ አልቻሉ ። ከዚያ ፡ በባላገር ፡ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ ሊያስጭኑት ፡ የሚችሉትን ፡ ያክል ፡ ማርና ፡ ቅቤ ፡ አሞሌ ፡ ጨውና ፡ ሌላም ፡ ጠቃሚ ፡ የመሰላቸውን ፡ የባላገር ፡ ሀብት ፡ አስጭነው ፡ ሊያስነዱት ፡ የሚችሉትን ፡ ያልታመመ ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ አስነድተው ፡ ወደ ፡ ጉሊት ፡ ተሻገሩ ። ጉሊትም ፡ እንዲሁ ፡ በርዋን ፡ በሰፊው ፡ ከፍታ ፡ ከንድዋን ፡ ዘርግታ ፡

ወራሪዎን ፡ ዘራፊዎን ፡ ተቀበለች ። ባገሩ ፡ ወንድ ፡ እንዳልተፈ
ጠረ ፡ ሴቱ ፡ ከቤት ፡ እየተጋባ ፡ እንደሚወልድ ፡ ሁሉ ፡ በየ
ደጁ ፡ እንደ ፡ መቃብር ፡ ሀውልት ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ ሳይተነፍስ ፡ ዝም
ብሎ ፡ ለፍርድ ፡ ወራሪውን ፡ ዘራፊውን ፡ የሚመለከት ፡ ሴትና ፡ ልጅ
ብቻ ፡ ነበር ። ጉሊትም ፡ እንደናሞራ ፡ ከወራሪው ፡ ተርፎ ፡ አውሬ
ውን ፡ ውሻውንና ፡ አሞራውን ፡ የሚመግብ ፡ ፍሪዳና ፡ በግ ፡ ታርዶ ፡
ብዙ ፡ ድቁስና ፡ ቅቤ ፡ ጠላና ፡ ጠጅ ፡ ማር ፡ ተዘርፎ ፡ ለወራሪና ፡ ላው
ሬ ፡ ትልቅ ፡ ድግስ ፡ ሆኖ ፡ ሰነበት ። የጉሊት ፡ ሴቶችና ፡ ልጆችም ፡
እንደናሞራ ፡ ሴቶችና ፡ ልጆች ፡ እየታሰሩ ፡ እየተገረፉ ፡ ወንዶቻ
ቸው ፡ ያሉበትን ፡ እንዲናገሩ ፡ ተጠየቁ ፡ ብዙ ፡ ከባላገር ፡ አፉ ፡ ትን
ሽ ፡ ምስጢር ፡ ከማውጣት ፡ ከጀርባው ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ማውጣት ፡ ስለ
ሚቀል ፡ ፊታውራሪ ፡ የባላገርን ፡ ሴቶችና ፡ ልጆች ፡ እያስገረፉ ፡ እ
ጅግ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ አወጡ ! ምስጢር ፡ ግን ፡ ትንሽም ፡ አላገኙ !

ፊታውራሪና ፡ ወራሪ ፡ ሰራዊታቸው ፡ ጉሊት ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ቆይ
ተው ፡ ከባላገር ፡ ሀብት ፡ ሊያዝ ፡ የሚቻለውን ፡ ይዘው ፡ ሊያዝ ፡ የማ
ይችለውን ፡ አበላሽተው ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ጎርጎር ፡ ለማለፍ
ሲሰናዱ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ባላገር ፡ ራሱን ፡ ተከናንቦ ፡ ከጎርጎር ፡
በኩል ፡ መጥቶ ፡ እንደሚሰልል ፡ ቁጥቁዋጦ ፡ ተተግኖ ፡ የፊታውራሪ
ን ፡ ሰፈር ፡ ሲመለከት ፡ ቆዩና ፡ እንደገና ፡ ወደመጣበት ፡ ተመልሶ ፡
እየተገላመጠ ፡ እያየ ፡ ሲሄድ ፡- አጋፋሪ ፡ መሰረትና ፡ ሌሎች ፡ አሽ
ከሮች ፡ አስቀድመው ፡ አይተውት ፡ ተጠንቅቀውበት ፡ ስለነበረ ፡
ፈረሰኛ ፡ ልከው ፡ አስይዘው ፡ አስመጡት ።

እስረኛው ፡ የፊትን ፡ ጋሻር ፡ እፊታውራሪ ፡ ፊት ፡ ሲቀርብ ፡
እንደ ፡ ጎመገ ፡ እጮሬ ፡ ደሙን ፡ ለማየት ፡ ቸኩለው ፡ ከወዲያ ፡
ወዲህ ፡ እየተንቆራጠጡ ፡ አንድ ፡ ጥያቄ ፡ እንኳዋ ፡ ሳይጠይቁ ፡
"ጣልልኝ ! ጣልና ፡ በለው ! " አሉ ።

"ጌታየ ፡ በሽተኛ ፡ ነኝ ፡ ተገርፌ ፡ አልተርፍም ፡ እሞታ
ለሁ ! የብዙ ፡ ልጆች ፡ አባት ፡ በጅዎ ፡ ብሞት ፡ አሳዳጊ ፡ የሌላ
ቸው ፡ ልጆቼ ፡ በእግዚአብሄር ፡ ዘንድ ፡ ያስጠይቁዎታል ! አባ
ክዎ ፡ እያስገርፉኝ ፡ ተገርፌ ፡ የምናገረውን ፡ ሳልገረፍ ፡ ልና
ገር ! " አለ ፡ እስረኛው ።

"የምትናገረው ፡ እውነት ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ መተማመኛ ፡

አለ ? "

" የሚጠይቁኝን ፡ ከተናገርሁ ፡ በሁዋላ ፡ እስረኛ ፡ አድርገው ፡ የያዙኝና ፡ እውነት ፡ ሳይሆን ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ያን ጊዜ ፡ ይግረፉኝ ፡፡"

" በል ፡ ንገረን ፡ የማን ፡ ሰላይ ፡ ነህ ?"

"ሰላይ ፡ አይደለሁም ፡ የዚህ ፡ አገር ፡ ባላገር ፡ ነኝ ፡፡ ጌታየ ፡ የሶስቱን ፡ ጉልትዎን ፡ ባላገር ፡ ሲመቱ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተወራ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፡ ብሎ ፡ ለመመካከር ፡ ሮብ ፡ የሶስቱም ፡ ጉልቶች ፡ ባላገር ፡ እናሞራ ፡ ተሰብስቦ ፡ መስማማት ፡ ስላቃተው ፡ እሙስ ፡ እዚህ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ወስኖ ፡ ተለያዬ ፡፡ እዚህም ፡ በተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ ስምምነት ፡ ሳይገኝ ፡ ቀርቶ ፡ በበነጋው ፡ ጎርጎር ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ እንሰብሰብ ፡ ስለተባለ ፡ እዚያ ፡ ተሰብስበን ፡ ስንብተን ፡ ከዚያ ፡ መምጣቴ ፡ ነው ፡፡ "

" እኮ ፡ ልትሰልል ፡ አይደለም ፡ የመጣህ ? "

" አይደለም ፡፡ "

" ታዲያስ ? "

" እሶስቱም ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ ስምምነት ፡ አልተገኘም ፡፡ የናሞራ ፡ ህዝብ ፡ ባበጀ ፡ በለው ፡ መሪነት ፡ እንዋጋ ፡ ባይ ፡ ሆነ ፡፡ የዚህ ፡ የጉሊት ፡ ህዝብ ፡ የታቦት ፡ አማላጅና ፡ መተያያ ፡ ይዘን ፡ ከጌታችን ፡ እንታረቅ ፡ አለ ፡፡ የጎርጎር ፡ ህዝብ ፡ በሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ ግማሹ ፡ እንዋጋ ፡ ሲል ፡ ግማሹ ፡ እንደ ፡ ጉሊት ፡ ህዝብ ፡ መታረቅ ፡ ፈለገ ፡፡ በሶስቱም ፡ ስብሰባ ፡ ህዝቡ ፡ እንዲሁ ፡ በሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ ስንጨቃጨቅ ፡ ስንብተን ፡ በመጨረሻ ፡ ጌታችን ፡ እናሞራን ፡ መትተው ፡ እዚህ ፡ መድረስዎ ፡ ስለተሰማ ፡ ጉሊቶች ፡ በሙሉ ፡ አገራችነን ፡ እናስበድልም ፡ ሄደን ፡ ጌታችነን ፡ ይማሩን ፡ እንላለን ፡ ብለው ፡ ከስብሰባው ፡ ወጡ ፡፡ አሁን ፡ ሁሉም ፡ ይመጣሉ ፡፡ እኔ ፡ ቀድሜያቸው ፡ መጥቼ ፡ እዚህ ፡ ከደረስሁ ፡ በሁዋላ ፡ የጌታየን ፡ ሽፍር ፡ ሳይ ፡ ስለፈራሁ ፡ እነሱ ፡ እስኪደርሱ ፡ ዘወር ፡ ብዬ ፡ ለመቆየት ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ ስመለስ ፡ ነው ፡ የተያዝሁ ፡፡ "

" አሁን ፡ እናበጀ ፡ በለው ፡ ጎርጎር ፡ ናቸው ? "

" የለም ፡ አበጀ ፡ በለው ፡ እናሞሮችን ፡ ከጎርጎርም ፡

ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ጨምሮ ፡ ሸሽቶዋል ።"

"ወዴት ፡ ሄደ ?"

"በጥል ፡ ስለሆነ ፡ የተለያዩትን ፡ የሄደበትን ፡ አልገለጠል ንም ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ተወራው ፡ እሱም ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ የመ ጀመሪያ ፡ አሳቡ ፡ ለመዋጋት ፡ ቢሆን ፡ በመጨረሻ ፡ ህዝቡ ፡ እንዳልደገፈው ፡ ስላየ ፡ አማላጅ ፡ ይዞ ፡ ለመታረቅ ፡ ይፈል ጋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የጌታየ ፡ ቂም ፡ እስኪበርድ ፡ ገለል ፡ ብሎ ፡ ሳይቆይ ፡ አይቀርም ፡ ይባላል ። ከጎርጎር ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ የተ ከተሉትም ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አብረን ፡ እንታረቃለን ፡ ብለው ፡ ነው ፡ እዬተባለ ፡ ትናንት ፡ ማምሻውን ፡ ሲወራ ፡ ነበር ።"

"ሌሎች ፡ ባላገሮች ፡ መጡ ፡ አራት ፡ ባላገሮች !" አለ ፡ አንድ ፡ አሽከር ።

"አዎ ፡ አራት ፡ ባላገሮች ፡ ደግሞ ፡ ከነሱ ፡ በሁዋላ ፡ በር ከት ፡ ያሉ ፡ ባላገሮች ፡ ተከትለዋል !" አለ ፡ ሌላ ፡ አሽከር ።

እውነትም ፡ በጠቅላላው ፡ አስራሁለት ፡ ባላገሮች ፡ ከወደ ጎርጎር ፡ ቀጥ ፡ ብለው ፡ የማመንታት ፡ ምልክት ፡ ሳያሳዩ ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ መጡ ። ከሹሙ ፡ ከብላታ ፡ መንግስቱ ፡ ጋር ፡ አስራራት፡ የባላገር ፡ ምርኮኞችና ፡ እጅግ ፡ ቁጥሩ ፡ የበዛ ፡ የባላገር ፡ ውርስ ፡ በፊታውራሪ ፡ እጅ ፡ ገባ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በመጨረሻ ፡ የመጡት ፡ ባላገሮች ፡ ፊት ፡ የመጣው ፡ ባላ ገር ፡ ለፊታውራሪ ፡ የነገረውን ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ሳያዛቡ ፡ በሙሉ ፡ ደግመው ፡- "ክፉ ፡ መከር ፡ አሳስቶን ፡ ጌታችንን ፡ በማስቀየማ ችን ፡ ይማሩን ፡" እያሉ ፡ እፊታቸው ፡ ሲወድቁ ፡- ፊታውራሪ ፡ የልባቸው ፡ ደስታ ፡ ፊታቸውን ፡ ሲያበራው ፡ ኩራት ፡ ትክሻቸ ውን ፡ ሲያንሰራራው ፡ ይታይ ፡ ነበር ።-

ያንለት ፡ ፊታውራሪ ፡- ከጉሊት ፡ እስረኞች ፡ ከራሳቸውና ፡ ከነሞራ ፡ በመያዣቸው ፡ የተዘረፈውን ፡ ከብትና ፡ ንብረት ፡ ነድተውና ፡ ጭነው ፡ ወራሪያቸውን ፡ እንዲከተሉ ፡ ከሀያ ፡ ባለ ብረት ፡ ወታደርና ፡ ከጉዋዝ ፡ እጀቢ ፡ ጋር ፡ ወደሁዋላ ፡ ትተው፡ ሹሙንና ፡ የመጀመሪያውን ፡ እስረኛ ፡ መሪ ፡ አድርገው ፡ ጎር ጎር ፡ ሲደርሱ ፡ ጥቂት ፡ ባላገሮች ፡ አይገድገው ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ተሰልፈው ፡ ቆይተው ፡ ድንጋይ ፡ እዬተሸከሙ ፡ እግራቸው ፡

ላይ ፡ ወደቁ ። ፊታውራሪ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ እንኳዋ ፡ ሳይተነፍሱ ፡ ዘም ፡ ብለው ፡ የወደቁትን ፡ ባላገሮች ፡ ተራምደዋቸው ፡ በልብ ሳቸው ፡ ላይ ፡ እየቆሙ ፡ አለፉ ።

“ ከሁሉ ፡ የሚሻል ፡ ቤት ፡ የቱ ፡ ነው ፡ አንተ ? ” አለ ፡ አጋፋሪ ፡ መሰረት ፡ ወደወደቁት ፡ ባላገሮች ፡ ዘወር ፡ ብሎ ።

“ መሰንበቻውን ፡ ለስብሰባው ፡ ድግስ ፡ የተጋዘበት ፡ እቃ ፡ ሞልቶታል ፡ እንጂ ፡ ከሁሉ ፡ ያማረ ፡ ቤት ፡ የብላታ ፡ ተሰማ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ባጠገቡ ፡ ያሉት ፡ ሁለት ፡ ቤቶችም ፡ ለጌ ቶች ፡ ሹማምንት ፡ የሚሆኑ ፡ ማላለፊያ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ። እንደ ነሱ ፡ የተመቸ ፡ መቸም ፡ እዚህ ፡ የለ ! ” አለ ፡ አንዱ ፡ ባላገር ፡ የተሸከመውን ፡ ድንጋይ ፡ ጥሎ ፡ ቀና ፡ አለና ።

ከዚያ ፡ አጋፋሪ ፡ መሰረት ፡ ሶስቱንም ፡ ቤቶች ፡ ገብቶ ፡ አይቶ ፡-

“ተነሱ ፡ እቃውን ፡ ወዲያ ፡ አውጡና ፡ ቤቶችን ፡ ጠርጋ ችሁ ፡ ጎዝጉዙ ፡” አለ ። እውነትም ፡ ቤቶቹ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ። ይልቁንም ፡ የብላታ ፡ ተሰማ ፡ ቤት ፡ የመኳንንት ፡ ቤት ፡ የመሰለ ፡ ወግ ፡ ማእርግ ፡ ያለው ፡ ነበር ።

ድግስ ፡ ሲጉዋዝበት ፡ የሰነበተ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ እዚያ ፡ የተከማቸው ፡ ሞሰብ ፡ ገንቦ ፡ ቅርጫት ፡ ድስት ፡ እንስራ ፡ ቶሎ ፡- ቢወጣ ፡ ቢወጣ ፡ አላልቅ ፡ አለ ። በመጨረሻ ፡ ባቅራቢያው ፡ ያሉት ፡ ሴቶችና ፡ ልጆች ፡ ጭምር ፡ ተጠርተው ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ እቃውን ፡ ሙልጭ ፡ አድርገው ፡ አውጥተው ፡ ጠርገው ፡ ጉዝ ጉዋዝ ፡ ተጎዝጉዞ ፡ ጉዋዙ ፡ ሲደርስ ፡ እሶስቱም ፡ ቤቶች ፡ ተነ ጥፎ ፡ ፊታውራሪ ፡ እብላታ ፡ ተሰማ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ፡ ከቀኛዝማች ፡ አካሉና ፡ ከባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ባላምባራስ ፡ ታዬ ፡ ከልጅ ፡ ተሰማና ፡ ከልጅ ፡ አማረ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ በጎረቤት ፡ ባሉት ፡ ቤቶች ፡ ገቡ ።

ምንም ፡ ፊታውራሪ ፡ ጎርጎር ፡ የገቡለት ፡ ጸሀይ ፡ ሆኖ ፡ ቢውል ፡ መሰንበቻውን ፡ ሲዘንብ ፡ ስለ ፡ ሰነበተ ፡ ድንኩዋን ፡ መተከሉ ፡ ቀርቶ ፡ ሰራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ በዬቤቱ ፡ ተመራ ። ወዲያው ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ፍሪዳውና ፡ በጉ ፡ መታረድ ፡ ባላገርም ፡ የገዛ ፡ ሀብቱን ፡ እዬዘረፈ ፡ ታጥቆ ፡ ለወራሪዎቹ ፡ መደገስ ፡ ጀመረ ።

ከጎርጎር ፡ ወንዶች ፡ ጥቂት ፡ ስለ ፡ ተገኙና ፡ ፊታውራሪ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ወሬ ፡ ከነሱ ፡ ስላገኙ ፡ የጎርጎር ፡ ሴቶችና ፡ ህጻናት ፡ እንደ ፡ ናሞራና ፡ እንደ ፡ ጉሊት ፡ ሴቶችና ፡ ህጻናት ፡ እየታሰሩ ፡ አልተገረፉም ፡ የጎርጎር ፡ ከብት ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ናሞራና ፡ እንደ ፡ ጉሊት ፡ ከብት ፡ እዬታረደ ፡ ከወራሪው ፡ ተርፎ ፡ ላውሬና ፡ ለውሻ ፡ ላሞራ ፡ ድግስ ፡ መሆኑ ፡ አልቀረም ። እፊታውራሪ ፡ ዘንድ ፡ ለግብር ፡ ከሚታረደው ፡ ፍሪዳና ፡ በግ ፡ ሌላ ፡ በዬቤቱ ፡ የተመራው ፡ አሽከር ፡ በግ ፡ እያረደ ፡ የቤቱን ፡ እናት ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ እያስደገሰ ፡ ሶስት ፡ ቀንና ፡ ሁለት ፡ ሌሊት ፡ ተበላ ፡ ተጠጣ ፡ ተዘፈነ ፡ ተቅራራ ፡ ተፎከረ ፡ ተሰከረ ! ፊታውራሪ ፡ ሶስተኛውን ፡ ሌሊት ፡ ጎርጎር ፡ አድረው ፡ ባራተኛው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ናሞራ ፡ ሄደው ፡ ከራተኛው ፡ ዘረፋ ፡ የተረፈ ፡ ቤቱን ፡ ዘርፈው ፡ ያበጁ ፡ በለውን ፡ ቤት ፡ አቃጥለው ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ "አመልማል ፡ ጉሜ ፡" እያሰኙ ፡ ወደ ፡ ዲማ ፡ እንዲመለሱ ፡ ወሰኑ ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በባላገር ፡ ላይ ፡ ያደረጉት ፡ ዘመቻና ፡ ወረራ ፡ ዲማ ፡ እቤታቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ከተመኙትና ፡ ካሰቡት ፡ የበለጠ ፡ ውጤት ፡ ስለ ፡ ሰጣቸውና ፡ እጅግ ፡ የተቃና ፡ ስለ ፡ ሆነላቸው ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ሲላቸው ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ባለፈው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ መሰናከል ፡ ሆነው ፡ ከንዲያ ፡ ያለ ፡ ጉትጎት ፡ ከንዲያ ፡ ያለ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እግዲዋቸው ፡ መኖራቸው ፡ ከነከናቸው ። ቀኛዝማችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ማየቱ ፡ እንኩዋ ፡ ከበዳቸው ፡ ጠሉዋቸው ።

ያንለት ፡ ማታ ፡ ግብር ፡ ቀምላሽ ፡ ሆኖ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉና ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ወደ ፡ ምንኝታቸው ፡ ተመልሰው ፡ ሲነጋገሩ ፡-

"ቀኛዝማች ፡ 'ደፋርና ፡ ጢስ ፡ መውጫ ፡ አያጣም ፡' እንደ ሚሉት ፡- ያ ፡ ደፋር ፡ ያሀ ፡ ፊታውራሪ ፡ ያሰበውኮ ፡ ሊሆንለት ፡ ነው ፡ መሰለኝ !" አሉ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ።

"እግዚአብሄር ፡ እንዳፍዎ ፡ ቢያደርግልን ፡ መልካም ፡ ነበር ! ብቻ ፡ እኔ ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ መጨረሻውን ፡ እስካይ ፡ አላምንም !"

"መጨረሻ ፡ ማለት ፡ ምንድነው ? ነገኮ ፡ መሄዳችን ፡ ነው !"

"መጨረሻ ፡ ማለትማ ፡ የያዝነውን ፡ ይዘን ፡ ዲማ ፡ ስንገባ ፡ ነው ! በዛሬና ፡ በነገ ፡ መሀከል ፡ ስንት ፡ አለ ? ጌታዬ !"

"እሱስ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ የሶስቱ ፡ ጉልቶች ፡ ባላገር ፡ ሁሉ ፡ ምሽቱን ፡ ልጁን ፡ ከብቱን ፡ ቤቱን ፡ ንብረቱን ፡ ሁሉ ፡ አስረክቦ ፡ ለመሸሽኮ ፡ ከፍራት ፡ በቀር ፡ የምስጠው ፡ ትርጉም ፡ አጥቼ ፡ ነው ! ሰው ፡ መሞት ፡ የሚገባው ፡ ለምሽቱ ፡ ለልጁ ፡ ለንብረቱ ፡ አልነበረም ? የባላገር ፡ ጉልበቱ ፡ አገሩ ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ? አገሩን ፡ ከለቀቀ ፡ ምን ፡ ጉልበት ፡ አለው ? ይህ ፡ ነው ፡ ያስቸገረኝ ።"

"ይህ ፡ ሁሉ ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ሲመለከቱት ፡ እንዲህ ፡ መሆኑ ፡ ቀሉ ፡ ያስፈራል !"

"ምኑ ፡ ነው ፡ የሚያስፈራው ?"

"ይህ ፡ ለድግስ ፡ እንደ ፡ ተጠራን ፡ ያላንድ ፡ ችግር ፡ በተከፈተ ፡ ቤት ፡ ሰተት ፡ ብለን ፡ መግባቱ ፡ ይህ ፡ ባላገር ፡ ከብቱ ፡ ሲታረድ ፡ ንብረቱ ፡ ሲዘረፍ ፡ ምሽቱና ፡ ልጆቹ ፡ ሲገረፉ ፡ በመከላከል ፡ ፈንታ ፡ የሩቅ ፡ ተመልካች ፡ ሆኖ ፡ መመልከቱ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እኛን ፡ ለማዘንጋትና ፡ ልንወጣ ፡ እንደማንችል ፡ አድርጎ ፡ እወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ ለማግባት ፡ በጥንቃቄ ፡ የተሰናዳ ፡ ይሆን ? እያልሁ ፡ እፈራለሁ ! ሁል ፡ ጊዜ ፡ ንብረት ፡ ሲያጠፉ ፡ ሰላም ፡ ሲነሳ ፡ የሚኖርን ፡ አውሬ ፡ ለማጥመድ ፡ ለጊዜው ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ቢጠፋ ፡ አውሬው ፡ ከተያዘ ፡ ንብረቱ ፡ ይተካል ! ይህ ፡ እንዳይሆን ፡ ነው ፡ ባፈ ፡ ውሀ ፡ ይመላና ፡ ዘሾው ፡ ይህ ፡ ይሆን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የምፈራው ! ባላገር ፡ የሚቋቋጥረው ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ አይፈታም !"

"ፍዬለፈጁን ፡ አውሬ ፡ ፍዬል ፡ አርደህ ፡ ያዘው ! የሚባለው ፡ በኛ ፡ እንዳይደርስ ፡ ነው ፡ የምትለው ! አይደለም ?"

"አዎ ፤ እሱ ፡ እንዳይደርስብን ፡ ነው ፡ የምፈራ !"

"እግዚአብሄር ፡ ይሁነና !" አሉ ፡ አዛዡ ፡ የቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ስጋት ፡ በሳቸውም ፡ ተጋብቶባቸው ።

"እግዚአብሄር ፡ ግፍ ፡ ለሰራ ፡ ነው ? ወይስ ፡ ግፍ ፡ ለተሰ

ራበት ፡ የሚሆን ! ስናደርገው ፡ የሰነበትነውን ፡ ሲያዩ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ ?” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ ትንሽ ፡ የቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብለው ።

“እግዚአብሔር ፡ ለበደለኛ ፡ መሆኑን ፡ አታውቅም ፡ እንዴ !” አሉ ፡ አዛዥ ፡ እዮሳቄ ።

ወዲያው ፡ አዛዥ ፡ ሳቃቸውን ፡ ሳይጨርሱ ፡–

“ኡኡ - - - - ኡኡ - - - ኡ -ኡ - ኡኡ - - ”አለ ፡ የቀበሮ ፡ ልቅሶ ፡ የመሰለ ፡ ጩኸት ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ።

“ቀበሮ ፡ ስታለቅስ ፡ ትሰማላችሁ ? መጥፎ ፡ ምልክ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ልብሳቸውን ፡ እወላል ቀው ፡ እንደ ፡ ተጋደሙ ።

“ከሌላ ፡ አገር ፡ የመጣች ፡ ቀበሮ ፡ ትሆናለች ፡ እንጂ ፡ የዚህ ፡ አገር ፡ ቀበሮዎችስ ፡ እድሜ ፡ ለፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ መዝፈን ፡ ካልሆነ ፡ የሚያለቅሱበት ፡ ምክንያት ፡ የለም !” አሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ እዮሳቄ ። አዛዥም ፡ ባላምባራስም ፡ አብረው ፡ ሲስቁ ፡–

“እሳት ፡ እሳት ፡ ጌቶች ፡ ያሉበት ፡ ቤት ፡ ተቃጠለ !” አለ ፡ እጥግ ፡ የተኛ ፡ አሽከር ።

ከዚያ ፡ ሶስቱ ፡ መኩዋንንት ፡ ደንግጠው ፡ የፈቱትን ፡ ትጥቅ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ታጥቀው ፡ ለመውጣት ፡ ወደያስቀመጡ በት ፡ ሲሮሩዋጡና ፡ ሲተረማመሱ ፡– “በያላችሁበት ፡ እርጉ ችሁ ፡ ተቀመጡ ! እጅ ፡ እግራችሁ ፡ የተላወሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ትበላ ሻላችሁ ! እርፉችሁ ፡ ብትቀመጡ ፡ ይሻላችሁዋል ! ” የሚል ፡ ትርጉሙ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ከብዙ ፡ አፍ ፡ ከመስማታቸው ፡ ወዲያው ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ላይ ፡ የሁለት ፡ ጠመንጃ ፡ አፈሙዝ ፡ ተደግኖ ፡ አዩ ። ወዲያው ፡ ተያዙ ። በጎ ረቤት ፡ ያሉት ፡ ሌሎች ፡ ሶስት ፡ መኩዋንንትም ፡ እንዲሁ ፡ ሳይታጠቁ ፡ በዩተጋደሙበት ፡ ተያዙ ።

ፊታውራሪ ፡ ያሉበት ፡ ቤት ፡ ሲቃጠል ፡ እንኩዋንስ ፡ መሳሪያቸውን ፡ ካለበት ፡ ፈልገው ፡ ለመያዝ ፡ ሱሪያቸውንም ፡ ለማጥለቅ ፡ጊዜ ፡ ስላጡ ፡ ከጋቢያቸው ፡ በላይ ፡ በትከሻቸው ፡ አንጠልጥለው ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽን ፡ ብቻ ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡

ይዘው ፡ እዮሮጡ ፡ ሲወጡ ፡- "ጌታዩ ፡ ወዲህ ፡ ይምጡ !" አለና ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ግራ ፡ እጃቸውን ፡ ይዞ ፡ ከሚቃጠለው ፡ ቤት ፡ ራቅ ፡ አድርጎ ፡ አቆማቸው ፡፡

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የተመኙት ፡ ሁሉ ፡ እንዳይሆንም ፡ ተረፍረፍ ፡ ብሎ ፡ ተፈጽሞላቸው ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ አሳባቸውም ፡ ተፈጽሞ ፡ ሳለ ፡ ድንገት ፡ የደረሰው ፡ አደጋ ፡ አፍዞዋቸው ፡ አደንግዞዋቸው ፡ በወይዘሮ ፡ የለራሽና ፡ ግራ ፡ እጃቸውን ፡ በያዛቸው ፡ ሰውዩ ፡ መሀከል ፡ ቆመው ፡ ነበልባሉ ፡ ከሚያቃጥለው ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ እዮተጎረደ ፡ ፊትና ፡ ሁዋላ ፡ እዮተከታተለ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እዮተወረወረ ፡ ሲጠፋ ፡ አይናቸው ፡ ቦዞ ፡ እዮተመለከቱ ፡ ከማን ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ እንኳዋ ፡ አላስተዋሉም ፡ ነበር ፡፡

ፊታውራሪ ፡ ቡራዩቸውን ፡ በትከሻቸው ፡ እንዳደረጉ ፡ እጆቻቸውን ፡ ግራቀኝ ፡ በያዙዋቸው ፡ እጆች ፡ ደገፍ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እዮተከታተለ ፡ የሚወረወረውን ፡ ነበልባል ፡ ሲመለከቱ ፡ ቶዬና ፡ እዚያ ፡ ከተሰበሰበው ፡ ቁጥሩ ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ ሰው ፡ እሳት ፡ ለማጥፋት ፡ አፈርም ፡ ቅጠልም ፡ የሚወረውረው ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ስለ ፡ ነበረና ፡ የሚበዛው ፡ እሳት ፡ ለመሞቅ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ሁሉ ፡ በዳር ፡ ቆሞ ፡ ይመለከት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡- ያ ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ የሳቸው ፡ ተከታይ ፡ መስሎዋቸው ፡-

" ለምን ፡ ዝም ፡ ብላችሁ ፡ ታያላችሁ ? አታጠፉም ? ሰነፍ ፡ ሁሉ !" አሉ ፡፡ ወዲያው ፡ አራት ፡ ጥይት ፡ ተከታትሎ ፡ ሲተኮስ ፡ እሳት ፡ ለማጥፋት ፡ አፈር ፡ የያዘው ፡ አፈሩን ፡ ቅጠል ፡ የያዘው ፡ ቅጠሉን ፡ እንደ ያዘ ፡ አሳቡን ፡ ከሳቱ ፡ ወደ ፡ ጥይቱ ፡ መለስ ፡ ሲያደርግና ፡ በየት ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ ተተኮሰ ፡ ለማወቅ ፡ ዘወር ፡ ዘወር ፡ ሲል ፡- እያንዳንዱ ፡ እሳት ፡ አጥፊ ፡ ባራት ፡ ወይም ፡ ባምስት ፡ ተመልካች ፡ መሀከል ፡ መሆኑን ፡ አዩ !

ተመልካቹ ፡ ሁሉ ፡ ጠመንጃውን ፡ ያጎረሰና ፡ ከሳት ፡ አጥፊዎች ፡ መሀከል ፡ ልንቀሳቀስ ፡ የሚል ፡ ዚናር ፡ እዚያው ፡ ከሳቱ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ለማጥፋት ፡ የሚችል ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አንድም ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ አልነበረም ፡ ሁሉም ፡ እንገቱን ፡ ደፋፉ፡

ዝም ፡ አለ ። ፊታውራሪ ፡ የሰውን ፡ ሁሉ ፡ ሁኔታ ፡ ሲያዩ ፡ ግራ ፡ ገባቸውና ፡ ግራ ፡ እጃቸውን ፡ ወደ ፡ ያዘው ፡ ሰው ፡ ዘወር ፡ ቢሉ ፡ አይተውት ፡ የማያውቁ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ። ወዲያው ፡ ሰውነታቸው ፡ ሽምቅቅ ፡ ብሎ ፡ "የማነህ ፡ አንተ ! ወይድ ፡ እጄን ፡ ልቀቅ !" አሉ ፡ ለመንጠቅ ፡ ሞከሩ ፡ አደረገው ። ነገር ፡ ግን ፡ የያዛቸው ፡ እጅ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ከባድና ፡ ጥብቅ ፡ ነበር ።

" አዎ ፡ ጌታዬ ፡ አያውቁኝም ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሬ ፡ ለመተዋወቅ ፡ ስመኝ ፡ኖሬ ፡ አሁን ፡ በንዲህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ መተዋወቃችንን ፡ ያሳዝነኛል ፡ እኔ ፡ አበጀ ፡ በለው ፡ እባላለሁ !" ሲል ፡ ፊታውራሪ ፡ ራሳቸውን ፡ በዱላ ፡ እንደተመቱ ፡ ሙሉ ፡ አካላቸው ፡ ደንዘዝ ፡ አለ ፡ ራሳቸው ፡ ዞረባቸው ። "አበ--አበጀ ፡ በለው ?" አሉ ፡ መላሳቸው ፡ ታስሮ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆዩና ።

" አዎ ፡ አበጀ ፡ በለው !"

ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ አስመጥቶ ፡ ሁለት ፡ እጃቸውን ፡ አስሮ ፡ እናዛዥ ፡ ያስታ ፡ በነበሩበት ፡ ቤት ፡ ወስዶ ፡ ጨመራቸው ።

ፊታውራሪንና ፡ ወራሪ ፡ ሰራዊታቸውን ፡ ለመያዝና ፡ ከተያዙም ፡ በሁዋላ ፡ ሁለተኛ ፡ ወደቦስቱ ፡ ጉልቶቻቸው ፡ እን ዳይመለሱ ፡ አበጀ ፡ በለው ፡ ያበናዳው ፡ ወጥመድ ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ጠቅላላው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዝርዝሩ ፡ እን ኩዋ ፡ ልክ ፡ እሱ ፡ እንዳቀደው ፡ ሆኖ ፡ ተፈጸሞለት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በጠርነትና ፡ እሱን ፡ በመሳሰለ ፡ እቅድ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ያልታሰበ ፡ ነገር ፡ መድረሱና ፡ እሱም ፡ እቅዱን ፡ ከሞላ ፡ ጎደል ፡ ማቃወሱ ፡ ስለማይቀር ፦ እመጨረሻ ፡ ላይ ፡ አራት ፡ ጥይት ፡ ተተኩሶ ፡ ሶስት ፡ ሰዎች ፡ መሞታቸው ፡ ይደ ርሳል ፡ ተብሎ ፡ መከላከያ ፡ ያልተደረገለት ፡ ነገር ፡ ነው ።

ይህም ፡ አበጀ ፡ በለውን ፡ በጣም ፡ አሳዘነው ። አሳቡም ፡ እምነቱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሳይሞት ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ያገር ፡ መሳቂያ ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ።

ታምራት ፡ የሚባለው ፡ የፊታውራሪ ፡ አሽከር ፡ ማታውን ፡ ጥሬም ፡ ብስልም ፡ ሲጉ ፡ ሌላም ፡ እያቀላቀለ ፡ ከመጠን ፡ እሳ

ልጁ ፡ በልቶ ፡ ኖሮ ፡ ሆዱን ፡ ስላመመው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከተኛ ፡ በሁዋላ ፡ ጉዋሮ ፡ ለመዞር ፡ ጠመንጃውን ፡ አንግቶ ፡ ከሰፈር ፡ ትንሽ ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ፊታውራሪ ፡ የተኙ በት ፡ ቤት ፡ ሲቃጠል ፡ አየ ። ወዲያው ፡ ተነስቶ ፡ ሰራዊቱን ፡ ለመቀስቀስ ፡ ሲታጠቅ ፡ የቀበሮውን ፡ ልቅሶ ፡ ተከታትሎ ፡ ከገቢው ፡ ባላገር ፡ ከዬተሸሸገበት ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ሲጎርፍ ፡ አዬና ፡ አከታትሎ ፡ ተኩሶ ፡ ሁለት ፡ ባላገሮች ፡ ከገደለ ፡ በሁ ዋላ ፡ ባላገሮችም ፡ መልሰው ፡ ተኩሰው ፡ እሱን ፡ ገደሉት ።

ይህ ፡ ያልታሰበ ፡ ነበር ። በተረፈ ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ፊታ ውራሪ ፡ የሰሰቱን ፡ ጉልቶች ፡ ንብረት ፡ ያለተቃዋሚ ፡ እን ዲዘርፉ ፡ ቤቶችና ፡ ሀጻናቱን ፡ እንዲያንገላቱ ፡ የጉሊት ፡ ባላ ገሮች ፡ ፊታውራሪን ፡ በተጠና ፡ ቃል ፡ አታለው ፡ ጎርጎር ፡ አም ጥተው ፡ እብላታ ፡ ተሰማ ፡ ቤት ፡ እንዲገቡ ፡ ማድረጉ ፡ ከተኙ ፡ በሁዋላ ፡ ቤቱ ፡ እንዲቃጠል ፡ ማድረጉና ፡ ሳይጠነቀቁ ፡ ደንግ ጠው ፡ ሲወጡ ፡ ተቀብለው ፡ መደዩ ፡ የቀበሮ ፡ ጬኸት ፡ የማይ ውቀው ፡ ባላገር ፡ ፊታውራሪና ፡ ሰራዊታቸው ፡ ትጥቃቸውን ፡ ፈትተው ፡ ሲተኙ ፡ ቤቱን ፡ አቃጥሎ ፡ በርችቱ ፡ በቀበሮ ፡ ጬኸት ፡ ከባቢውን ፡ ባላገር ፡ ለመቀስቀስ ፡ እንዲመቸው ፡ ከጉሊት ፡ ጀምሮ ፡ በሰረኛነት ፡ ከፊታውራሪ ፡ ሰራዊት ፡ ጋር ፡ እንዲመጣ ፡ ማድረጉ ፡ ይህና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ሁሉ ፡- ፊታውራሪን ፡ ያለጦርነት ፡ ለመደብና ፡ ከተደነዙም ፡ በሁዋላ ፡- ዋና ፡ ዘራፊ ፡ ዋና ፡ ቀማኛ ፡ ከሽፍቶችም ፡ ለቤትና ፡ ለልጅ ፡ እንኩዋ ፡ ምህረት፡ የሌላቸው ፡ ጨካኝ ፡ ሽፍታ ፡ ለመሆናቸው ፡ የሰሩትን ፡ ስራ ፡ ምስ ክር ፡ አድርጎ ፡ ሁለተኛ ፡ ወደ ፡ ሶስቱ ፡ ጉልቶቻቸው ፡ እንዳይመ ለሱ ፡ ማድረግ ፡- አንድ ፡ ላይ ፡ ተፈትለው ፡ በጥመዱ ፡ የተሰራበት ፡ የጠጥመዱ ፡ ድርና ፡ ማግ ፡ ነበር ።

ወረረው ፡ ለብቻ ፡ መሳሪያው ፡ ለብቻ ፡ ተሰብስቦ ፡ ለጠ ባቂዎች ፡ ከተሰጠና ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ባለጠመንጃ ፡ ባላገሮች ፡ ተመርጠው ፡ ፊታውራሪንና ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ እዬተፈራረቁ ፡ ከበው ፡ እንዲጠብቁ ፡ ከተደረገ ፡ በሁዋላ ፡ በማግስቱ ፡ ጥዋት ፡ አበጀ ፡ ብለው ፡ ከሁለት ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ እነፊታውራሪ ፡

ታስረው ፡ ወደ ፡ ተቀመጡበት ፡ ቤት ፡ ሄዶ ፡ በትህትና ፡ እጅ ፡ ነሳ ። ፊታውራሪ ፡ ግን ፡ የሚያሾፉባቸው ፡ መስሎዋቸው ፡ ሰላምታ ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ ፊታቸውን ፡ አዞሩ ።

ሁኔታቸውን ፡ ሲያይ ፡ አበጀም ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መቆጣት ፡ አለና ፡ "እንግዲህ ፡ ጌቶቼ ፡ ወደምትሄዱበት ፡ እስክትሄዱ ፡ ድረስ ፡ ካስቀመጥኋችሁ ፡ ቦታ ፡ ያለኝ ፡ ፈቃድ ፡ እንዳትንቀሳቀሱ ! እናስቸግራለን ፡ ያላችሁ ፡ እንደሆነ ፡ እናንተም ፡ እኛም ፡ የማንወደውን ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ እንገደዳለን ። ለጠባቂዎቻችሁ ፡ አሊቃ ፡ አደራ ፡ እዚህ ፡ ያስቀመጥሁት ፡ ሰው ፡ አለና ፡ የምትፈልጉት ፡ ነገር ፡ ሲኖር ፡ ለሱ ፡ መንገር ፡ ነው ! ምንም ፡ ጌቶቻችን ፡ ብትሆኑ ፡ ለጊዜው ፡ እስረኞቻችን ፡ መሆናችሁን ፡ አለመርሳት ፡ ነው !" ብሎ ፡ ሁሉም ፡ የታሰሩበትን ፡ ድግ ፡ ፊታላቸው።

"እውነትህ ፡ ነው ፡ እኔን ፡ የጣለ ፡ ቀን ፡ ላንተ ፡ ሆኖህ ፡ እስረኛህ ፡ ሆኛለሁ ! ግዴለም ፡ ቀልድብኝ ! እንኳን ፡ እኔ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በፍጡሮቹ ፡ በሌዋ ፡ በከሀዲዎች ፡ በአይሁድ ፡ እጅ ፡ ታስሮ ፡ ተቀልዶበታል ! እኔም ፡ እንዳንተ ፡ ባለ ፡ ከሀዲና ፡ ሽፍታ ፡ እጅ ፡ ታስሬ ፡ ቢቀልድብኝ ፡ ያው ፡ በጌታችን ፡ የደረሰው ፡ ነው ፡ የደረሰብኝ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በብስጭት ፡ ቁጣ ።

"ጌታዬ ፡ እኔ ፡ አልተማርሁም ፡ ስለዚህ ፡ የጌታንና ፡ የይሁዳን ፡ ታሪክ ፡ አላውቅም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደስዎ ፡ ተማርን ፡ ከሚሉ ፡ ሰዎች ፡ እንደሰማሁት ፡ ጌታችን ፡ የመጣ ፡ የሰው ፡ ንብረት ፡ ለመዝረፍና ፡ እንደስዎ ፡ ሰው ፡ ለማሰቃየት ፡ አይደለምኮ ! ስለዚህ ፡ የሰው ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ቀማኛ ፡ ሲዘርፉ ፡ ሴቶችና ፡ ህጻናት ፡ ያለርህራሄ ፡ ሲገርፉ ፡ ተይዘው ፡ የታሰሩትን ፡ ከጌታችን ፡ እስራት ፡ ጋር ፡ አያመሳስሉት" አለ ፡ አበጀ ፡ በለው ፡ ትንሽ ፡ ፈርጠም ፡ ብሎ ።

"እንዴ ፡ ነዋ ! ደግሞ ፡ አንተ ፡ ሆንህ ! አንተ ፡ ሽፍታው ! አንተ ፡ ከሀዲው ! እኔን ፡ ቀማኛ ፡ የምትለኝ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በመገረም ።

"የለም ፡ ጌታዬ ፡ እኔ ፡ ሽፍታም ፡ ከሀዲም ፡ አይደለሁም ።"

"ምንድነኝ ፡ ልትል ፡ ይሆን ? ሰባት ፡ አመት ፡ በጎንቻና– አልሸፈትህም ? የማላውቅ ፡ መስሎሀል !"

"እንደስዎ ፡ እንደ ፡ ጌታየ ፡ ስልጣንን ፡ በዙሪያቸው ፡ አጥረው ፡ በስልጣን ፡ ውስጥ ፡ ተሸሽገው ፡ ድሀ ፡ የሚዘርፉትን ፡ ድሀ ፡ የሚቀሙትን ፡ በራሳቸው ፡ ወንጀል ፡ ድሀ ፡ አስረው ፡ የሚገድሉትን ፡ ግፈኞች ፡ ሽፍቶች ፡ እቃወም ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሽፍታ ፡ አልነበርሁም ። እቤቴ ፡ ተቀምጬ ፡ ባለስልጣኖች ፡ የሚሰሩትን ፡ ግፍ ፡ በህግ ፡ ለመቃወም ፡ ስላልቻልሁ ፡ ቤቴን ፡ ትቼ ፡ መሰደዴ ፡ ሽፍታ ፡ አያሰኘኝም ። አብረውኝ ፡ ሰባት ፡ አመት ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ የተንከራተቱ ፡ ብዙዎች ፡ ስለሆኑ ፡ አንዱን ፡ ባጋጣሚ ፡ አግኝተው ፡ ቢጠይቁት ፡ እንኳን ፡ የሰው ፡ የከብት ፡ ደም ፡ ሲፈስ ፡ ማየት ፡ የማልወድ ፡ መሆኔን ፡ ይነግርዎታል ። ደም ፡ ማፍሰስ ፡ ስለማልወድ ፡ ደም ፡ ሳይፈስ ፡ እይዝዎታለሁ ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ ሶስት ፡ አገር ፡ ሲዘርፉ ፡ አቅም ፡ የሌላቸው ፡ ሴቶችና ፡ ህጻናት ፡ ሲያስገርፉ ፡ እያወቅሁ ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ የሸሸሁ ! ያለዚያስ ፡ ገና ፡ እናሞራ ፡ ሳይደርሱ ፡ ተዋግቼ ፡ እይዝዎ ፡ ነበር !"

"እሱ ፡ ነበራ ! የጎበዝ ፡ ስራ ! ጎበዝ ፡ ብትሆን ፡ ተዋግተህ ፡ መያዝ ፡ ነበር ! አታሎ ፡ መያዝ ፡ ከጉብዝና ፡ አይቆጠርም ! ተዋግተን ፡ ቢሆን ፡ አሳይህ ፡ ነበር ፡ እኔ ፡ መሸሻ !"

"እሱ ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ አታሎ ፡ ከመያዝ ፡ ተዋግቶ ፡ መያዝ ፡ ነው ፡ ጎበዝ ፡ የሚያሰኘው ። ብቻ ፡ እኔ ፡ በጣም ፡ ግድ ፡ ካልሆነብኝ ፡ ደም ፡ ሲፈስ ፡ ማየት ፡ አልወድም ። ግድ ፡ ሲሆንብኝ ፡ ግን ፡ ተዋግቶ ፡ መያዝም ፡ አውቃለሁ !" አለ ፡ አበጀ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ። እዚያ ፡ የነበሩትም ፡ ሁሉ ፡ ከፊታውራሪ ፡ በቀር ፡ መሳቅ ፡ አምሮዋቸው ፡ አንገታቸውን ፡ ደፋ ፡ አደረጉ ።

"አዎ ።" አለ ፡ አበጀ ፡ ቀጠለና ፡ "አዎ ፡ ደም ፡ ሲፈስ ፡ ማየት ፡ አልወድም ። ደም ፡ ሲፈስ ፡ ከማየቴም ፡ ደግሞ ፡ የድሀ ፡ ህይወትና ፡ ንብረት ፡ እንዲጠበቅበት ፡ የተሰራው ፡ ህግና ፡ የተሰጠው ፡ ስልጣን ፡ ተጣምሞ ፡ ተቆልምሞ ፡ ለድሀ ፡ ህይወት ፡ ማጥፊያ ፡ ለንብረቱ ፡ መዝረፊያ ፡ ላመጽ ፡ መፈጸሚያ ፡ ሲሆን ፡

ማየት ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ያስጠላኛል ፡ በጣም ፡ ያንገፈግፈ ኛል ! እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አስጸያፊ ፡ ነገር ፡ ስታደርጉ ፡ ሳይ ፡ ልቤ ፡ አልችል ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ተቃወምሁ ፡ ነው ፡ እንደናንተ ፡ ያላችሁ ፡ ሽፍቶች ፡ ሽፍታ ፡ ያላችሁኝ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ ሽ ፍታ ፡ አይደለሁም ፡ ከሀዲም ፡ አይደለሁ ፡፡ ለመሆኑ ፡ ከሀዲ ፡ ማለት ፡ ለጥበቃ ፡ የሰጠውን ፡ አደራ ፡ የሚበላ ፡ ለመጠበቂያ ፡ የተሰጠውን ፡ ስልጣን ፡ ለመቀሚያ ፡ ለመንጠቅያ ፡ የሚያደርግ፡ አይደለም ?" አለ ፡ አበጀ ፡ አሁንም ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ፡፡

"በል ፡ እንግዲህ ፡ በቃህ ፡ ሂድ ፤ እስካሁን ፡ ሰደብኸኝ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፤ እንደ ፡ ተቆጡ ፡፡ አበጀ ፡ በሰው ፡ ግን ፡ ምንም፡ እንኳ ፡ መጀመሪያ ፡ መጥቶ ፡ እጅ ፡ ሲነሳ ፡ ፊታቸውን ፡ በማ ዞራቸው ፡ ትንሽ ፡ ቀጣ ፡ ቢል ፡ በሁዋላ ፡ ባነጋገራቸው ፡ መጠን ፡ ከንቱ ፡ መሆናቸውን ፡ እያስተዋለ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ከልጅ ፡ ጋር ፡ እንደሚጫወት ፡ ሁሉ ፡ ቁጣውን ፡ ረሳ ፡፡

"እሺ ፡ አይቆጡ ፡ እሄዳለሁ ፡ እንዲያውም ፡ የቁርስ ፡ መቅ መሻችሁ ፡ ጊዜ ፡ ደርሶዋል ፡ ልሂድና ፡ ልላክላችሁ ፡፡ ብቻ ፡ ከመ ሄዴ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልንገርዎ ፡፡ በልጅነቴ ፡ የሰዎን ፡ ጀግ ንነት ፡ ስሰማ ፡ ጀግንነትዎ ፡ ያውሬ ፡ ጀግንነት ፡ መሆኑን ፡ ሳላ ውቅ ፡ በጣም ፡ እወድዎ ፡ በጣም ፡ አደንቅዎ ፡ ነበር ፡፡ ከብት ፡ ስጠብቅም ፡ አባቴ ፡ ሲያርስ ፡ በሬ ፡ ሳጣምድም ፡ በሁዋላ ፡ ጫካለጫካ ፡ ስዞርም ፡ ስለሰዎ ፡ ጀግንነት ፡ የተዘፈነውን ፡ ዘፈን ፡ ነበር ፡ ስዘፍን ፡ የምኖር ! እንዲህ ፡ ያውሬ ፡ ጀግና ፡ አይ መስሉኝም ፡ ነበር ፡ የሰው ፡ ጀግና ፡ ነበር ፡ የሚመስሉኝ ፡፡ ስለ ዚህ ፡ አደንቅዎ ፡ ነበር ! ስለሰዎ ፡ ስዘፍነው ፡ የኖርሁትን ፡ ዘፈን ፡ አሁን ፡ ልንገርዎ?" አለ ፡ አበጀ ፤ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ፡፡

"የኔ ፡ ስም ፡ ባንተ ፡ አፍ ፡ ሲነሳ ፡ መስማት ፡ አልፈልግም ፤ ወግድልኝ፡፡" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡፡ አበጀም ፡ "እሺ ፡ ይተውት፡" ብሎ ፡ ወጣ፡፡

ከዚያ ፡ ቁርስ ፡ በስራት ፡ ተሰናድቶ ፡ መጥቶላቸው ፡ ሌሎች ፡ ሁሉ ፡ ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ ፊታውራሪ ፡ አፌ ፡ በጭራሽ ፡ እህል ፡ ውሀ ፡ አይነካም ፡ ብለው ፡ እንቢ ፡ አሉ ፡፡ እንዲያውም ፡

ወጥቼ ፡ ያንዱን ፡ ባላገር ፡ ጠመንጃ ፡ ነጥቄ ፡ ካላመለጥሁ ፡ ብለው ፡ ያስቸግሩ ፡ ጀመር ፡፡

"ፊታውራሪ ፡ የከበበንን ፡ ታያለህ ፤ ሁሉም ፡ ባለመሳሪያ ፡ ነው ፡፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ እንሞክር ፡ ያልን ፡ እንደሆነ ፡ እንዳችን ፡ እንኳዋ ፡ ለዘር ፡ ሳንተርፍ ፡ ይጨርሱናል ! ስለዚህ ፡ እባክህ ፡ እርፉህ ፡ ተቀመጥ ፡፡" አሉ አዛዥ ፡፡

"እናንተ ፡ ዝም ፡ ብላችሁ ፡ ተቀመጡ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ የባላገር ፡ ምርኮኛ ፡ ሆኜ ፡ አልቀመጥም ፡ እሄዳለሁ !"

"ማን ፡ ይለቅሃል ?"

"ያንዱን ፡ ገበሬ ፡ ጠመንጃ ፡ ነጥቄ ፡ እጅ ፡ ካደረግሁ ፡ ማነው ፡ በፊቴ ፡ የሚቆም ፡ እኔ ፡ መሸሸ !"

"ምን ፡ መሆንህ ፡ ነው ? ጠመንጃውን ፡ እንካ ፡ ብሎ ፡ የሚሰጥህ ፡ አለ ? አንተ ፡ ብቻህን ፡ ነህ ፤ ጠመንጃ ፡ እነጥቃለሁ ፡ ብለህ ፡ካንዱ ፡ ጋር ፡ ስትታገል ፡ ሌሎች ፡ ቢገሉህስ ?"

"ማጂስም ፡ ይግደሉኝ ፡ በባላገር ፡ እጅ ፡ ምርኮኛ ፡ ሆኜ ፡ ከምታሰር ፡ ባላገር ፡ ባልሰራው ፡ ጥይት ፡ መሞት ፡ ይሻለኛል !"

"ባላገር ፡ በሰራው ፡ ዱላ ፡ እናትህን ፡ ብሎ ፡ ቢገልህስ ?" አሉ ፡ አዛዥ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብለው ፡፡ ሌሎችም ፡ ሳቁ ፡፡ ፊታውራሪ ፡ ተቆጡ ፡፡

ፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ ሰራዊታቸው ፡ በተያዙ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ የነጋይ ፡ ገዢ ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ታዝዘው ፡ መጥተው ፡ ወደ ፡ ማርቆስ ፡ ይዘዋቸው ፡ ሄዱ ፡፡ ባላገሮች ፡ እንደ ራሴ ፡ አድርገው ፡ የመረጡዋቸው ፡ ነገር ፡ አዋቂዎች ፡ ሽማግሎችም ፡ ባበጀ ፡ በለው ፡ መሪነት ፡ አብረው ፡ ተያይዘው ፡ ሄዱ ፡፡ የተዘረፈው ፡ የባላገር ፡ ከብትና ፡ ንብረት ፡ ግን ፡ ፊታውራሪ ፡ አስጌ ፡ ካዩት ፡ በሁዋላ ፡ ከብቱ ፡ ለዩባለቤቱ ፡ ተመለሰ ፤ሌላውን ፡ ባለቤቱ ፡ ሊታወቅ ፡ ስላልቻለ ፡ ሽማግሎች ፡ ተመርጠው ፡ ለተዘረፈው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲያከፋፍሉ ፡ ተደረገ ፡፡

# ምእራፍ ፡ ፳፱ ፡

## አዲስ ፡ አለም ፡

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ጎርጎር ፡ በባላገር ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ የመሰንበታቸውና ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ እጅ ፡ ተላልፈው ፡ ወደ ፡ ማርቆስ ፡ የመሄዳቸው ፡ ወሬ ፡ በብዙ ፡ ባላገር ፡ አፍና ፡ ጆሮ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተለዋወጠ ፡ ተዘዋውሮ ፡ መጨረሻ ፡ ዲማ ፡ ሲደርስ ፡- ይህ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ የማይቻል ፡ ብዙ ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ስለደረሰ ፡- ለጊዜው ፡ ዲማ ፡ ቤተሰባቸውን ፡ ግራ ፡ ገባው ። በሁዋላ ፡ ግን ፡ እያደር ፡ ወሬው ፡ ያጌጠበት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለምና ፡ ዘርፋዘርፉ ፡ ቀርቶ ፡ ዋናው ፡ የነገሩ ፡ አካል ፡- ጦርነት ፡ አለመደረጉ ፡ ብቻ ፡ ድንገተኛ ፡ ተኩስ ፡ ሆኖ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ወገን ፡ ታምራት ፡ ከባላገር ፡ ወገን ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መሞታቸውና ፡ ፊታውራሪም ፡ የባላገር ፡ ወኪሎችም ፡ በፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ ዳኝነት ፡ ተየይዘው ፡ ወደ ፡ ማርቆስ ፡ መሄዳቸው ፡- መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡- ነገሩ ፡ ከጦርነት ፡ ወጥቶ ፡ የዳኝነት ፡ መንገድ ፡ መያዙ ፡ ትልቁ ፡ የደህና ፡ ነገር ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ እያለ ፡ የሚያጽናናው ፡ ስለበዛ ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩነሽ ፡ የሰብለ ፡ ስጋት ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄደ ።

" ዋናው ፡ ነገር ፡ ጦርነት ፡ አለመሆኑ ፡ ሰላም ፡ መሆኑ ፡ ጌቶች ፡ ደህና ፡ መሆናቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተከሰው ፡ ማርቆስ ፡ ለመሄዱማ ፡ ሁልጊዜ ፡ እዩሄዱ ፡ ሰንብተው ፡ ይመለሱ ፡ የለም ? አዲስ ፡ መሆኑ ፡ ነው ? " አሉ ፡ አባኘር ፡ ዘሪሁን ፡ እመቤታቸውንና ፡ ሰብለን ፡ ለማጽናናት ፡ ያክል ።

" ባላገር ፡ እንደሚያወራው ፡ ተማርከው ፡ አይሁን ፡ እንጂ ፡ ተከሰውማ ፡ ከሆነ ፡ ማርቆስ ፡ የሄዱ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አለው ! ተማርከው ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ ብስጭቱም ፡ ይገድላቸዋል ፡ ሰው ፡ አይሆኑም ! " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ።

" ጌቶች ፡ ናቸው ፡ በባላገር ፡ እጅ ፡ የሚማረኩ ? ይሞቱ ፡

እንዲሆን ፡ እንጂ ፡ እንከኑዋን ፡ ለባላገር ፡ ለማንስ ፡ ጀግና ፡ ቢሆን ፡ እጃቸውን ፡ ይሰጣሉ ! ይህን ፡ ጭራሽ ፡ ከሳብኸው ፡ ያውጡት ፡ እመይቴ !"

"ምናባቴን ፡ ላድርግ ? ባላገር ፡ የሚያወራው ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ከኛ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንከኑዋ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ሁኔታቸውን ፡ የነገረን ፡ የለ ! "

" ባላገር ፡ ለማድረግ ፡ የሚመኘውን ፡ ሲሆንለት ፡ የሚመኘውን ፡ አደረግሁ ፡ ብሎ ፡ ማውራቱ ፡ ዛሬ ፡ አልተጀመረም ! " አሉ ፡ አባቻ ።

" እንከኑዋን ፡ ደህና ፡ ሆኑ ፡ እንጂ ፡ ተማርከውም ፡ ይሁን ፡ ተከሰው ፡ ማርቆስ ፡ ቀርቶ ፡ የትም ፡ ይሂዱ ! ብቻ ፡ እንከኑዋን ፡ ደህና ፡ ሆኑ !" አለች ፡ ሰብለ ፡ ወደ ፡ ትምርትዋ ፡ ለመሄድ ፡ ስትነሳ ።-

"ተማርከውም ፡ ይሁን ? እናንሽን ፡ ውሀ ፡ ያመላሱ ፡ እቴ ! ምን ፡ ክፉ ፡ ነሽ ? ምን ፡ አውሬ ፡ ነሽ ? " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ልጃቸው ፡ የተናገረችው ፡ አስገርሞዋቸው ።

" ታዲያስ ! ማርቆስ ፡ የሄዱበት ፡ ምንም ፡ ይሁን ፡ ብቻ ፡ ደህና ፡ ይሁኑ ነው ፡ ያልሁ ! ይህን ፡ ማለት ፡ ክፉ ፡ ነው ? "

" ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ የከፋ ፡ ምን ፡ ልትይ ፡ ኖሮዋል ?

" ሳንቺ ፡ ክፉ ፡ መስሎ ፡ ታየሽ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ የተናገርሁት ፡ ክፉ ፡ አይደለም ። "

" እም ! አባትሽ ፡ በባላገር ፡ እጅ ፡ ተማርከው ፡ ሰው ፡ የማይሆኑ ፡ መሆናቸውን ፡ የህይወታቸው ፡ መጨረሻ ፡ መሆኑን ፡ እያወቅሽ ፡ ባላገር ፡ ይማርካቸው ፡ ስትይ ፡ ክፉ ፡ አለመናገርሽ ፡ ነው ! "

"እንግዲያስ ፡ ከፈለግሽ ፡ እንዲያውም ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ ልንገርሽ ፡ እማማ ! ብቻ ፡ አይሙቱ ፡ ታመውም ፡ አልያቸው ፡ እንጂ ፡ ባላገር ፡ ቢማርካቸው ፡ በጣም ፡ ነው ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ! ምክንያቱን ፡ ልንገርሽ ! ባላገር ፡ እንደሳቸው ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ አውቀው ፡ ከባላገር ፡ ጋር ፡ ተስማምተው ፡ በሰላም ፡ የሚኖሩት ፡ ሀይሉን ፡ ሲያሳያቸው ፡ ነው ። ያንጊዜ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ የሚሆኑት !"

“ ወዬው ፡ ጉድ ! በጤናዋ ፡ ናት ፡ ብላችሁ ፡ ነው ? ሂጅ ፡ ወግጂ ፡ አሁን ፡ ከፊቴ ! አንቺ ፡ ሰይጣን ! የዚያ ፡ የከሳ ፡ ጻምዬ ፡ የዚያ ፡ ሰይጣን ፡ ትምርት ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ሰይጣን ፡ ያደረገሽ ! ” አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ልጃቸውን ፡ የሚመቱበት ፡ ነገር ፡ በተቀመጡበት ፡ ዙሪያ ፡ እየፈለጉ ። ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ የናትዋን ፡ ሁኔታ ፡ ስታይ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብላ ፡ ወደልፍኝዋ ፡ ሄደች ።

“ እመቤቴን ፡ ለማናደድ ፡ ብላ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የውነትዋን ፡ መሰለዎ ?” አሉ ፡ አሳዥ ፡ ዘሪሁን ፡ ሰብለ ፡ ከሄደች ፡ በሁዋላ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ልጃቸው ፡ በተናገረችው ፡ ሲያጉረመርሙ ።-

“ያ ፡ ከሳ ፡ ጻምዬ ፡ ነው ፡ ይምጥማጡን ፡ ያጥፋውና ፡ እንዲህ ፡ ያበላሻት !” አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ እርሳቸውም ፡ ሰብለ፡ ወደምትማርበት ፡ ለመሄድ ፡ ሲነሱ ።

ፊታውራሪ ፡ ዘመቻ ፡ ከሄዱ ፡ ጀምሮ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ሰብለንና ፡ በዛብህን ፡ መጠበቅን ፡ ትተውታል ። ሰብለ ፡ ትምርት ፡ ስትጀምር ፡ እንዲያው ፡ ለወግ ፡ ያክል ፡ ስፌትም ፡ ይሁን ፡ ፈትል ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ስራ ፡ ይዘው ፡ ቁጭ ፡ ከማለታቸው ፡ ትግስት ፡ አጥተው ፡ ትንሽ ፡ ሲንቆራጠጡ ፡ ይቆዩና ፡ በሁዋላ ፡ ሁሉንም ፡ ትተውት ፡ ሀብትሽን ፡ “ዋእ ----አንቺ ፡ አበያ ፡ አንቺ ---- ጥምባታም ፡ ከዚሁ፡ ትላወሻና !”ብለው ፡ አስፈራርተው ፡- ኩታቸውን ፡ ከማጣፊያው ፡ ወገን ፡ መለስ ፡ አድርገው ፡ ራሳቸው ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ ያደርጉና ፡ ጌጤነሽን ፡ አስከትለው ፡ በስርቆሽ ፡ በር ፡ ወጣ ፡ ይሉና ፡ ማንም ፡ ሳያያቸው ፡ እወይዘሮ ፡ ላቀች ፡ ቤት ፡ ጥልቅ ፡ ይላሉ ። ሳይሄዱ ፡ ትንሽ ፡ የቆዩ ፡ እንደሆነም ፡ ሙዳይ ፡ የምትባለዋ ፡ የወይዘሮ ፡ ላቀች ፡ ያገልጋዮቸው ፡ ልጅ ፡ እየሮጠች ፡ ትመጣና ፡-“ምነው ፡ ቡና ፡ ገና ፡ ቅድም ፡ ፈልቶ ፡ ወጥቶ ፡ እየጠበቅንአ --- አሉ ፡ እሜቴ ፡” ስትል ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ይሰፉ ፡ እንደሆነ ፡ ወስፌውን ፡

ነቅለው ፡ አከርማው ፡ ወይም ፡ አለላው ፡ በግማሽ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ይፈትሉ ፡ እንደሆን ፡ ድሩ ፡ ወይም ፡ ማጉ ፡ እንደ ፡ ተመዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ ጣጥለው ፡ ተነስተው ፡ ይሄዳሉ ።

ያንለትም ፡ በዛብህ ፡ ሰብለን ፡ ማስተማር ፡ እንደ ፡ ጀመረ ፡ ገባ ፡ ቢሉ ፡ ሙዳይን ፡ ቆማ ፡ ስትጠብቃቸው ፡ አገኙዋት ።

"ምነው ፡ አንቺ ፡ ጥምባታም ? ቡኑ ፡ ፈልቶ ፡ ነው ?"

"አዎ ፡ እሜቴ ፡ ገና ፡ ቅድም ፡ ፈልቶ ፡ ወጥቶ ፡ ይጠብቃሉ ።" አለች ፡ ሙዳይ ፡ አንገትዋን ፡ ደፍታ ፡ በግር ፡ አውራ ፡ ጣትዋ ፡ መሬት ፡ እየጫረች ።

ከዚያ ፡ ወደ ፡ ሀብትሽ ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ "አንቺ ፡ አህያ ፡ ዋ --- !"አሉና ፡ ጌጤነሽን ፡ እንኩዋ ፡ ለማስጠራት ፡ ቡለ ፡ ቸኩሉ ፡ ሙዳይን ፡ አስከትለው ፡ ሄዱ ። የስርቆሽ ፡ በሩን ፡ ወጣ ፡ እንዳሉ ፡ ሀብትሽ ፡ ደግሞ ፡ በፈንታዋ ፡ እንደመቤትዋ ፡ ትንሽ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ተንቆራጠጠችና ፡ "ያ ፡ ፈትለ ፡ ወርቅ ፡ ቡኑን ፡ አፍልቶ ፡ ይጠብቀኝ ፡ ይሆናል ፡ እስቲ ፡ እንዳይበርድበት ፡ ልሂድ !" አለች ።

"ማነው ፡ ፈትለ ፡ ወርቅ ?"አለ ፡ በዛብህ ፡ ሰብለን ፡ እያየ ።

"እበዋን ፡ ጠይቃት !"አለች ፡ ሰብለ ፡ ትንሽ ፡ ፍር ፡ ጥም ፡ ብላ ።

"ማነው ?"

"ጉዋደኛህን ፡ ፈትለ ወርቅን ፡ አጣሽው ? ደብተራውን ?" አለች ፡ ሀብትሽ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መኩራት ፡ ብላ ።

"ፈትለ ፡ ወርቅ ፡ ክዳኑ ?"አለ ፡ በዛብህ ፡ በመደነቅ ።

"አዎ ፡ ፈትለ ፡ ወርቅ ፡ ክዳኑ !"

"ታዲያ ፡ የምን ፡ ቡን ፡ ነው ፡ ፈትለ ወርቅ ፡ የሚያፈላ ?"

"ሰብለ ፡ ይህን ፡ ገልቱሽን ፡ አንድ ፡ በይልኝ !"አለች ፡ ሀብትሽ ፡ እየሳቀች ። ሰብለ ፡ በዛብህን ፡ ግራ ፡ ሲገባው ፡ አይታ ፦ "ይች ፡ እብድ ፡ ለመሄድ ፡ ምክንያት ፡ እንዲሆናት ፡ የምትለፈልፈው ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ መሰለህ ?" አለች ፡ ፈገግ ፡

ብላ ።

"ተዪ ፡ ዪህ ፡ የግዜር ፡ ሰው ፡ ያስኮንንሻል ፡ እውነቱን ፡ ንገረው ፡ ሰብለ ! ያለዚያ ፡ እኔ ፡ እነግረዋለሁ !"

"ወዩው ፡ ጉድ ! ምኑን ፡ ነው ፡ የምነግረው ? አሁን ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ አስዋና ፡ እኔ ፡ የምናውቀው ፡ ምስጢር ፡ ያለ ፡ ይመስላል ! እስቲ ፡ ንገረው ፡ ልስማ !"

"እሺ ፡ እንግዲህ ስማ ፡ ልንገርህ !"አለች ፡ ሀብትሽ ። "አዩህ ? በመንደራችን ፡ ሴት ፡ ቋዋንቋዋ ፡ ቡን ፡ ማለት ፡ ፍቅር ፡ ማለት ፡ ነው ! የቡን ፡ ሱስ ፡ ያለበት ፡ ቡን ፡ ሳያፈላ ፡ እንደማይውል ፡ የፍቅር ፡ ሱስ ፡ ያለበትም ፡ ያለ ፡ ፍቅር ፡ አይደርም ። ስለዚህ ፡ በወንዶች ፡ ፊት ፡ ሳያውቁብን ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡ ለማውራት ፡ ስንፈልግ ፡ በቡን ፡ አስመስለን ፡ እናወራለን ። እነሱም ፡ ቅድም ፡ እንተ ፡ እንዳልኸው ፡ የምን ፡ ቡን ፡ ነው ? እያሉ ፡ ዝም ፡ ይላሉ ። እዩውልህ ! ምሳሌው ፡ ጥሩ ፡ ማይደል ? ያ ፡ እንተ ፡ ብርና ፡ ሰም ፡ ነው ? ወርቅና ፡ ሰም ፡ የምትለው ! እንደሱ ፡ አይደለም ?" አለች ፡ ሀብትሽ ፡ እዩሳቀች ።

"ሰምና ወርቅ !" አልና ፡ በዛብህ ፡ ይስቅ ፡ ጀመር ።

"አዎ ፡ ሰምና ፡ ወርቅ ፡ ወርቅና ፡ ሰም ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ነው ! ይልቅ ፡ ስማ ፡ ልጨርስልህና ፡ ልሂድ ! ፊትለ ፡ ወርቅን ፡ እንደት ፡ እንዳገኘሁት ፡ ልንገርህና ፡ ልሂድ ! ያ ፡ ገብሬ ፡ ያ ፡ ባላንዲራ ፡ ገብሬ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ስወደው ፡ ለካ ፡ ሳላውቅ ፡ በላዩ ፡ የገዛ ፡ ጉዋደኛዬን ፡ ወዶ ፡ ኖሮ ፡ እንዲያውም ፡ ይግረምሽ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ሌሊት ፡ ብቻዬን ፡ አሳደረኝ ። የሌሊቱ ፡ መርዘም ፡ የቁንጫው ፡ መብዛት ፡ ለጠላትህ ፡ አይስጠውና ፡ እንዲሁ ፡ አይኔን ፡ ሳላለብስ ፡ እዩተገላበጥሁ ፡ ስናደድ ፡ ቆሜን ፡ የምወጣበት ፡ መንገድ ፡ ስፈልግ ፡ አደርሁ ። በበነጋው ፡ ልብስ ፡ አጠባ ፡ በወረደሁበት ፡ መቸም ፡ የፍቅር ፡ እምላክ ፡ አማኙን ፡ አይክድ ፡ ፊትለ ፡ ወርቅን ፡ ብቻውን ፡ ልብሱን ፡ ሲያጥብ ፡ አገኘሁት ። ከዚያ ፡ እባክህ ፡ ነጠላዩን ፡ እጠብልኝ ፡ ብለው ፡ ቀሚስሽን ፡ ጭምር ፡ ካልሆነ ፡ አላጥብልሽም ፡ አለኝ ። መቸም ፡ ቀሚስሽን ፡ ልጠብልሽ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ ታውቃለህ !"አለች ፡ ሀብትሽ ፡

አቴዋሮባ ፡

"ምን ፡ ማለት ፡ ነው ? አላውቅም ።" አለ ፡ በዛብህ ።

"ጉዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ምን ፡ ትይዋለሽ ? ሰብለ ! የት ፡ ነው ፡ የሚኖረው ? በል ፡ ወንድሜ ፡ እኔ ፡ ሁሉን ፡ እስ ቀምሬ ፡ አልዘልቀውምና ፡ የጀመርሁትን ፡ ጨርሽልህ ፡ ልሂድ ! ብትፈልግ ፡ ሁዋላ ፡ ጉዋደኞችህን ፡ ጠይቅ ፡ ይነግ ሩሀል ! " አለችና ፡ በዛብህ ፡ ሲስቅ ፡ ሀብትሽ ፡ ወሬዋን ፡ ቀጠለች ። " ጉዲያ ፡ ቀሚስሽን ፡ ጭምር ፡ ልጠብልሽ ፡ ሲለኝ ፡ ብዙ ፡ ሳልግደረደር ፡ ቶሎ ፡ ቀሚሴን ፡ አውልቄ ፡ ሰጠ ሁት ። ብቻ ፡ እውነቱን ፡ ልንገርህ ? ቶሎ ፡ እሺ ፡ ያልሁት ፡ ያን ፡ ገብሬን ፡ አስቀንቼ ፡ ወደኔ ፡ ለመመለስ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያንለት ፡ ፈትለ ፡ ወርቅ ፡ ደሴ ፡ ብለውኝ ፡ አይደለም ። አሁን ፡ እየውልህ ፡ ያችን ፡ የደብተራ ፡ ምናምኑን ፡ አቀመ ሰኝ ፡ መሰለ ፡ የምን ፡ ገብሬ ፡ የምን ፡ ቶላ ፡ የምን ፡ አዬለ ፡ የምን ፡ ተፈራ ፡ ምን ፡ ፈይሳ ፡ የምን ፡ ፈረደ ፡ እረ ፡ ስን ቱን ! እንዲያው ፡ እግዜር ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ወንድ ፡ ያል ፈጠረ ፡ መሰሉ ፡ ጉደቶኝ ፡ ተቸግሬልሀለሁ ! "

" አይደለም ! ለመሆኑ ፡ ይህ ፡ የቆጠርሽው ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ ምንድነው ! " አለ ፡ በዛብህ ፡ የሀብትሽ ፡ ሁኔታ ፡ እያስገረመው ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ሲሰማ ቆይቶ ።

" ጥቂቶቹ ፡ ባሎች ፡ የሚበዙት ፡ ወዳጆች ! "

" ይህ ፡ ሁሉ ? ያንቺ ? "

" እንዴት ? እኔን ፡ መናቅህ ፡ ነው ? "

" የለም ፡ ልጅ ፡ ነሽ ፡ ብዬ ፡ ነው ! "

" ሀአ ! እንግዲያስ ፡ በቅጡ ፡ ይግረምህ ! ከወዳጆቼ ፡ በጣም ፡ የምወዳቸውን ፡ ቆጠርሁልህ ፡ እንጂ ፡ ሁሉን ፡ ቁጠ ሬልኝ ፡ ብትለኝስ ፡ እንዲያውም ፡ ልቆጥርልህ ፡ አልችል ! "

" ስንት ፡ ባል ፡ አገባሽ ? "

ሀብትሽ ፡ ባሎችዋን ፡ ለማስታወስ ፡ አይኖችዋን ፡ እጣራው ፡ ላይ ፡ ሰቅላ ፡ ባውራ ፡ ጣትዋ ፡ የረገርም ፡ ጣት ፡ አንጓዎችዋን ፡ እየመላለሰች ፡ ስትቆጥር ፡ ቆዬችና ፡ " አራት ፡ ወይም ፡ አምስት ፡ ናቸው ፡ መሰለኝ ! ምን ፡ የኛ ፡ ጋብቻ ፡

በወዳጅነት ፡ ይጀመርና ፡ ፍቅሩ ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ባሌ ፡ ነው ፡ ምሽቴ ፡ ናት ፡ ተባብሎ ፡ አውርቶ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ በስርቆሽ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በገሀድ ፡ አብሮ ፡ መተኛቱ ፡ ነው ! በተረፈ ፡ ለማንም ፡ የለ ፡ ሰርግ ፡ የለ ፡ ቤት ፡ መስሪት ፡ ንብረት ፡ ማበጀት ፡ የለ ፡ የሰጡንን ፡ በልተን ፡ ማታ ፡ የምንተኛበት ፡ ቦታ ፡ ፈልገን ፡ አብሮ ፡ መተኛት ፡ ነው ! ይህ ፡ አይነት ፡ ጋብቻ ፡ ቢረሳ ፡ በዚህ ፡ አይነት ፡ ጋብቻ ፡ የተጋባ ፡ ባል ፡ ቢረሳ ፡ ይገርምሀል ? ” አለች ፡ ፊትዋ ፡ ፈገግ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ መሰብሰብ ፡ ሲል ፡ ጥርስዋ ፡ የውሸት ፡ ሳቅ ፡ እዬሳቀ ፡-

በዛብህ ፡ የሀብትሽ ፡ ሳቅ ፡ የውሸት ፡ ሳቅ ፡ መሆኑን ፡ ሲያይ ፡ የወዳጅና ፡ የባል ፡ ነገር ፡ ሲነጋገሩ ፡ ሳይታወቀው ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ኖሮ ፡ በሱ ፡ ቅር ፡ የተሰኘች ፡ መስሎት ፡ ለጊዜው ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ አለና ፡ ወሬውን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ለመምራት ፡ ፈለገ ።

“ ስንት ፡ ልጆች ፡ ወለድሽ ? ” አለ ፡ አሁንም ፡ እዬፈራ ።

ሀብትሽ ፡ ሶስት ፡ የመሀከል ፡ ጣቶችዋን ፡ ቀጥ ፡ የመጨረሻ ፡ ትንሽ ፡ ጣትዋን ፡ አጠፍ ፡ አድርጋ ፡ አሳየችው ።

“ ምን ፡ ማለትዋ ፡ ነው ? ” አለ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ።

“ ሶስት ፡ አሉዋት ፡ የመጨረሻው ፡ በሰባት ፡ ወር ፡ ተወልዶ ፡ ሞተ ፡ ” አለች ፡ ሰብለ ፡ የሀብትሽን ፡ ስሜት ፡ ስለምታውቅ ፡ ፊትዋን ፡ ቅር ፡ ብሎት ።

“ እግዚአብሔር ፡ እነሆን ፡ ካሳደገላችሁ ፡ ይበቃዋችሁዋል ፡ ደግሞ ፡ ልጅ ፡ ነሽ ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ትወልጃለሽ ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ያጽናና ፡ መስሎት ።

“ እግዚአብሔር ፡ እነሆን ፡ ለማን ፡ ካሳደገለት ? ” አለች ፡ ሀብትሽ ፡ ፊትዋ ፡ ምርር ፡ ክርር ፡ ብሎ ። በዛብህ ፡ ሁኔታዋን ፡ ሲያይ ፡ ምንም ፡ መመለስ ፡ አልፈለገም ። አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

“ ላባቶቻቸውና ፡ ለኔ ፡ ለናታቸው ፡ ነው ? ” አለች ፡

ቀጠለችና ። “ ሀአ ! ካሳይገባችሁ ! ለጌቶቻቸው ፡ ካሳይገ ባቸው ፡ በል ! የባሪያ ፡ እናት ፡ አባት ፡ ያስታው ፡ ልጅ ፡ ከመወለዱ ፡ በፊት ፡ አብሮ ፡ ተኝቶ ፡ በሚያደርገው ፡ ፍቅር ፡ ብቻ ነው ! የወለደሁት ፡ ልጅ ፡ ሰደክም ፡ ይረዳኛል ፡ ስታመም ፡ ያስታምመኛል ፡ ሳረጅ ፡ ይጦረኛል ፡ ብሎ ፡ አይደለም ! ባሪያ ፡ ለልጅዋ ፡ እናትነትዋ ፡ አርግዛ ፡ እምጣ ፡ እስክትወልደና ፡ ጡትዋን ፡ አጥብታ ፡ እንደራ ፡ ለመን ከስ ፡ እስክታበቃው ፡ ድረስ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ምንም ፡ አይደለችም ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ልጅም ፡ እናትም ፡ እኩል ፡ የጌቶቻቸው ፡ ንብረቶች ፡ ናቸው ! ” አለች ፡ ሀብትሽ ፡ አይ ኖችዋ ፡ እንባ ፡ ሞልተው ።-

“ ሀብትሽ ፡ ቢቃሽ ፡ እንግዲህ ! ” አለች ፡ ሰብለ ፡ እስዋም ፡ የመጣባትን ፡ ልቅሶ ፡ በምራቅዋ ፡ ለመመለስ ፡ እየሞተችል ፡ ሁሉ ፡ ምራቅዋን ፡ መላልሳ ፡ እየዋጠች ።-

“ ሲያስቡት ፡ ይገርማል ! የባሪያ ፡ አባትማ ፡ እንዲ ያውም ፡ ምንምኮ ፡ አይደለም ! ከቤት ፡ ከብትና ፡ ከቤት ፡ ባርያ ፡ የሚወለድ ፡ በናቱ ፡ እንጂ ፡ ባባቱ ፡ አይታወቅም ! ልክ ፡ እንደ ፡ ላም ፡ ልጅ ፡ የባርያ ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ ማንም ፡ ይሁን ፡ የናቱ ፡ ጌታ ፡ ንብረት ፡ ነው ! እኔ ፡ የወለድሁዋ ቸው ፡ ሁለቱ ፡ ልጆች ፡ አባቶቻቸው ፡ አንዱ ፡ ጨዋ ፡ ነጋዴ ፡ አንዱ ፡ ጨዋ ፡ ገበሬ ፡ ቢሆንም ፡ ልጆቹ ፡ እንደኔ ፡ እንደና ታቸው ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ባሮች ፡ ናቸው ። ወደፊትም ፡ ቅድም ፡ እንዳልሽው ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ መውለድ ፡ ስለምችል ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ሳያወጡ ፡ የብዙ ፡ ባሮች ፡ ጌታ ፡ አደርጋቸዋለሁ ! ” አለች ፡ ሀብትሽ ፡ እንባዋ ፡ በግራቀኝ ፡ ጉንጮችዋ ፡ ጣምራ ፡ ጣምራ ፡ ሆኖ ፡ እየወረደ ። ሰብለ ፡ አይኖችዋ ፡ እንባ ፡ ሞልተው ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ትመለከታት ፡ ነበር ። በዛብህ ፡ የሀብትሽን ፡ ስሜት ፡ ሳያውቅ ፡ ጥያቄ ፡ አብዝቶ ፡ ነገሩን ፡ እዚህ ፡ በማድረሱ ፡ ጥፋቱ ፡ ተሰምቶት ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

ከዚያ ፡ ሀብትሽ ፡ አፍንጫዋን ፡ ተናፈጠች ፤ አይኖችዋን ፡ ጠራረገችና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሰብለን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዛብህን ፡

ዘወር ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ በጎን ፡ አይታ ፡ ከት ፡ ብላ ፡ ከልብዋ ፡ ስትስቅ ፡ ሰብለም ፡ በዛብህም ፡ እንደ ፡ ቂል ፡ አብረው ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ።

"እየውልህ ፡ በዙ ! የቡን ፡ ታሪክ ፡ እንዲህ ፡ እያሳቀ ፡ ያስለቅሳል ፡ እያስለቀሰም ፡ ያስቃል ፡ ከፉ ፡ አይሉት ፡ በጎ ፡ እንደግዜር ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ! ብቻ ፡ ከፉም ፡ ይሁን ፡ በጎ ፡ ሰው ፡ ያወቀውን ፡ ማወቅ ፡ አይከፋምና ፡ አንተም ፡ እንደ ፡ ጉዋደኞችህ ፡ እንደነፈትለወርቅ ፡ እንደነ--- ርእሰ ፡ ደብር ፡ ኢሳይያስ ፡ ቡን ፡ እያፈላህ ፡ መጋበዝ ፡ ተማር !" ስትል ፡-

"አይ ! አሁንስ ፡ አበዛሽው ፡ ሀብትሽ ! በቃሽ ፡ እንግዲህ ፡ ወደምትሄጅበት ፡ ሂጂ !" አለች ፡ ሰብለ ፡ እንደ ፡ መቆጣት ፡ ብላ ። ሀብትሽ ፡ የሰብለን ፡ መቆጣት ፡ ስታይ ፡ ደንገጥ ፡ አለችና ፡ " አትቆጪ ፡ እናቴ ፡ እሄድልሻለሁ ! " ብላ ፡ ተነስታ ፡ ሄደች ።

ርእሰ ፡ ደብር ፡ ኢሳይያስ ፡ ካንድ ፡ አመት ፡ ያክል ፡ ጀምረው ፡ ለወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ባል ፡ እኩል ፡ የሆኑ ፡ ወዳጃቸው ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ሀብትሽ ፡ የሳቸውን ፡ ስም ፡ ስታነሳ ፡ ቶሎ ፡ ካልታገደች ፡ ይህንም ፡ ታወራ ፡ ይሆናል ፡ ከዚያም ፡ አልፋ ፡ እመቤትዋ ፡ እወይዘሮ ፡ ላቀች ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቡና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በበሽታ ፡ እያመካኙ ፡ እዬሄዱ ፡ የሚገናኙዋቸውን ፡ ብዙ ፡ ወዳጆቻቸውን ፡ መቁጠር ፡ ትጀምር ፡ ይሆናል ፡ ብላ ፡ ስለ ፡ ሰጋች ፡ ተቆጥታ ፡ አባረረቻት ።

"እንዴት ፡ የምታስገርም ፡ ልጅ ፡ ናት ! " አለ ፡ በዛብህ ፡ ሀብትሽ ፡ ከሄደች ፡ በሁዋላ ።

" አዎ ፡ ጨዋታ ፡ በጣም ፡ ታውቃለች ። ብቻ ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ አይደለም ፡ እንጂ ፡ እጨዋታ ፡ ላይ ፡ ትዋሻለች ። አሁን ፡ ይሄ ፡ የመንደሩ ፡ ሴት ፡ ወንዶች ፡ እንዳያውቁበት ፡ በቡን ፡ እዬመሰለ ፡ ይነጋገርበታል ፡ ብላ ፡ ያወራችው ፡ ራስዋ ፡ አሁን ፡ የፈጠረችው ፡ ነው ። ይገርማል ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥራ ፡ ስታወራ ፡ መላስዋ ፡ አይደናቀፍም ፡ ታዲያ ፡ እውነት ፡ ይመስልላታል ! ግሩም ፡ ናት ፡ ጨዋታ ፡ ታውቃለች ። አሁን ፡ እንዳዬሁት ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡

ውስጥ ፡ ስቃ ፡ ስታስቅ ፤ አልቅሳ ፡ ስታስለቅስ ፡ ዘፍና ፡ ስታ ዘፍን ፡ የሰዋን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አብሮዋት ፡ የተቀመጠውን ፡ ሰው ፡ ስሜት ፡ ጭምር ፡ እንደ ፡ በይ ፡ ውሀ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እንደ ፡ ፈለገች ፡ እዬመለሰች ፡ በዬጊዜው ፡ አዲስ ፡ አዲስ ፡ አካባቢ ፡ እዬፈጠረች ፡ እዚያ ፡ ስታስቀምጥ፡- ከሰዋ ፡ ጋር ፡ የሚ ኖር ፡ ሰው ፡ አይሰለቸውም ። እግዚአብሔር ፡ እሰዋን ፡ ባይሰ ጠኝ ፡ ምን ፡ ይውጠኝ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ አላውቅም ! ብቻ ፡ እብድ፡ ናት ፤ ሆደባሻ ፡ ናት ፤ ደግሞ ፡ ከሁሉ ፡ የባሰ ፡ ምስጢር ፡ አት ችልም ! እናገራለሁ ፡ ብላ ፡ ሳታስብ ፡ እንዲያው ፡ ጨዋታ ፡ እሳመርሁ ፡ ስትል ፡ ድንገት ፡ ይወጣባታል !"

"ለመሆኑ ፡ እኒህ ፡ የቆጠረቻቸው ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ወዳጆችዋ ፡ ናቸው ?"

"የለም ፤ ከባሎችዋና ፡ ከጥቂቱ ፡ በቀር ፡ የቀሩት ፡ እን ዲያው ፡ ለጨዋታ ፡ አሁን ፡ የፈጠረቻቸው ፡ ናቸው ፡ ባገሩም ፡ የሉ ! ባፍዋ ፡ እንደምታወራው ፡ አመንዝራ ፡ አይደለችም ፡ ይገርምሀል ! ብቻ ፡ መጫወት ፡ ትወዳለች ።"

"ንግግርዋ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነው ፡ እንደሰዋ ፡ ብዙ ፡ የሚ ናገር ፡ ሰው ፡ የሚናገረው ፡ አይደለም ። ከሴት ፡ ከብትና ፡ ከሴት ፡ ባሪያ ፡ የሚወለድ ፡ ሁሉ ፡ በናቱ ፡ እንጂ ፡ ባባቱ ፡ አይ ታወቅም ፡ ያለችው ፡ በጣም ፡ ገረመኝ ! በልማድ ፡ አብሬው ፡ እዬኖርሁ ፡ አሁን ፡ እሰዋ ፡ እንዳለችው ፡ እድርጌ ፡ ተመልክ ቸው ፡ አላውቅም ፡ በጣም ፡ አስተዋይ ፡ ናት ።"

"አዎ ፡ እድሜ ፡ ላይ ፡ ካሳ ፡ የኑሮዋችን ፡ ስራት ፡ እጅግ ፡ ከፉና ፡ ግፍ ፡ የሞላበት ፡ መሆኑን ፡ እያዩን ፡ ለመበሳጨትና ፡ ለማልቀስ ፡ ያክል ፡ አይናችንን ፡ ከፍቶልናል ! ብቻ ፡ ከሱ ፡ መው ጣት ፡ ላንችል ፡ አይናችን ፡ ተከፍቶ ፡ ባላየነው ፡ ባላወቅነው ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ እንኖርበት ፡ ነበር !" አለች ፡ ሰብለ ፡ የተሰማ ትን ፡ ቅርታ ፡ ለበዛብህ ፡ ላለማሳየት ፡ እንገትዋን ፡ ትንሽ ፡ ደፋ ፡ አድርጋ ።

"እሊቃ ፡ ካሳ ፡ እሰዋንም ፡ ያስተምሩዋት ፡ ኖሮዋል ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ እዘንዋ ፡ እሱንም ፡ እላዘኖት ፡ እንገቱን ፡ ደፋ ፡ አደረገ።

" እኔን ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ሲያስተምርኝ ፡ መጥፎ ፡ ልማ
ዳችንን ፡ እዩነቀፈ ፡ ሲናገር ፡ እዚሀ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡
ስትሰማ ፡ ትቆይና ፡ እሱ ፡ ሲሄድ ፡ የተናገረውን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡
ነጥብ ፡ እንኳዋ ፡ ሳታጎድል ፡ ከነድምጹ ፡ ትደግመዋለች ! የተ
ናገረውን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ድምጽም ፡ መቅዳት ፡ ትችላ
ለች !" አለች ፡ ሰብለ ፡ በቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ ያጌጠ ፡ ፊትዋን ፡
ወደ ፡ በዛብህ ፡ መለስ ፡ አድርጋ ፡ አይን ፡ አይኑን ፡ እያዩች ።
አይኖችዋ ፡ ባይኖቹ ፡ ላይ ፡ ሲያርፉ ፡ የስዋን ፡ ውብ ፡ የቅርታ ፡
ፈገግታ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ እንዳስተላለፉት ፡ ሁሉ ፡ የሱም ፡ ፊት ፡
በቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ አጊጦ ፡ ትንሽ ፡ አይን ፡ አይንዋን ፡ ተመለ
ከተና ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ፡ አደረገ ። ወዲያው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
ታሪካቸውን ፡ ተወራርተው ፡ ያለቀስችውና ፡ በቅፉ ፡ ይዞ ፡ ሲያ
ባብላት ፡ ባዘን ፡ ጨልሞ ፡ የነበረው ፡ ፊትዋ ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡
ሰማይ ፡ ወገግ ፡ እያለ ፡ የሄደው ፡ ልብዋ ፡ እንደ ፡ ሞቀው ፡
ፈረስ ፡ ሽምጥ ፡ ይጋልብ ፡ የነበረው ፡ ትንፋሽዋ ፡ ብዙ ፡ ምእ
ራፍ ፡ እንደሮጠች ፡ ሁሉ ፡ ባጭር ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ይል ፡ የነበ
ረው ፡ እንዲያው ፡ በጠቅላላው ፡ የዚያኑለት ፡ ሁኔታዋ ፡ ሁሉ ፡
ትዝ ፡ አለውና ፡ "ምነው ፡ እንደዚያኑለቱ ፡ ባለቀሰችና ፡ እንደ
ዚያኑለቱ ፡ ባቀፍሁዋት !" እያለ ፡ ሲመኝ ፡ ፊቱ ፡ ምኞቱን ፡
በግልጽ ፡ ይነግር ፡ ነበር ።

" ምን ፡ ታስባለህ !" አለች ፡ ፊቱን ፡ ትንሽ ፡ አነበበ
ችና ።

" እ ? ምንም . . .አላስብ ፡ ብቻ ፡ . .በቀደም ፡ የደረሰ
ብኝን ፡ ስነግርሽ ፡ ባንቺም ፡ የደረሰውን ፡ የነገርሽኝ ፡ ትዝ ፡
ብሎኝ ፡ እሱን ፡ ሳስብ ፡ ነበር ። " አለ ፡ ድንገት ፡ ሳይሰናዳ ፡
ያዘችውና ፡ ምን ፡ እንደሚል ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶት ።-

" እሱን ፡ ታስብ ፡ ኖሮዋል ? ያገርማል ! እኔም ፡ ያኑለት ፡
አንተ ፡ የነገርኸኝን ፡ ሳስብ ፡ ነበር !" አለች ፡ የፍረት ፡ ፈገ
ግታ ፡ ውብ ፡ ፊትዋን ፡ አስጊጦት ።

" ሌላስ ፡ ምን ፡ አሰብሽ !"

" ሌላ ? እእ . . .ሌላ ፡ ያማም ፡ ማልቀሴ ፡ ትዝ ፡ አለኝና ፡

ለምን ፡ አለቀስሁ ፡ እያልሁ ፡ ሳስብ ፡ ነበር !" አለችና ፡ እን ደገና ፡ አንገትዋን ፡ ደፋ ፡ አደረገች ።

ከዚያ ፡ ሁለቱም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ብለው፣ እንደቆዩ ፡ "ት" ስትል ፡ ሰብለ ፡ "ት" አለ ፡ በዛብህም ፡ አብሮ ።

" ምን ፡ ልትል ፡ ኖሮዋል ?" አለች ፡ ሰብለ ።

" አንቺ ፡ ምን ፡ ልትይ ፡ ኖሮዋል ?"

" ትምርታችንን ፡ እንጀምር ፡ ልል ፡ ነበር ! "

" እኔም ፡ እሱን ፡ ልል ፡ ነበር!" አለና ፡ በዛብህ ፡ ይስቅ ፡ ጀመር ።

" ይገርማል !" አለች ፡ ሰብለ ፡ አሳሳቁን ፡ ፈትዋ ፡ ፈገግ፡ ብሎ ፡ እየተመለከተች ።

ከዚያ ፡ አሁንም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ በዬበኩላ ቸው ፡ የሚቀራረቡበትን ፡ ዘዴ ፡ ሲያስቡ ፡ ቆይተው፡- " ዛሬ ፡ ጽህፈት ፡ ተማሪ ። " አለ ፡ ቀና ፡ ብሎ ።

" እኔም ፡ እሱን ፡ ልል ፡ ነበር !" አለች ፡ እዬሳቀች ። በዛ ብህም ፡ አብሮዋት ፡ ሲስቅ ፡ ቆዩና፡- "እዎ ፤ ጽህፈትሽ ፡ እን ኩዋ ፡ በጠቅላላው ፡ ጥሩ ፡ ነው ፤ ብቻ ፡ ያንዳንድ ፡ ቀለሞች ፡ አጣጣል ፡ ይልቁንም ፡ የደና ፡ የጸ ፡ አጣጣል ፡ ትንሽ ፡ ያስቸግ ረሽ ፡ ይመስለኛል ። እስቲ ፡ ዛሬ ፡ እነሱን ፡ እንደጋግማቸው።" አለ ፡ በዛብህ ። እውነትም ፡ ሰብለ ፡ ጽህፈትዋ ፡ በጠቅላላው ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ ደና ፡ ጸ ፡ ይደባለቁባታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ያነሳት ፡ በዛብህ ፡ ጽህፈት ፡ እንድትማር ፡ ያሳሰበበት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ተጠጋግተው ፡ መቀመጡን ፡ ስትሳሳት ፡ እጅዋን ፡ መያዙን ፡ መነካካቱን ፡ ፈልጎ ፡ እሱን ፡ ናፍቆ ፡ ነው ።

" እሺ ። " አለችና ፡ ሰብለ ፡ ቶሎ ፡ ተነስታ ፡ ኩታዋን ፡ ከላይዋ ፡ ጠቅለል ፡ አድርጋ ፡ አልጋዋ ፡ ላይ ፡ ወርውራ ፡ ቀሚስዋን ፡ ብቻ ፡ አጠር ፡ አድርጋ ፡ እንደ ፡ ታጠቀች ፡ መጻ ፊያ ፡ ክርታስዋና ፡ እርሳስዋ ፡ ወደ ፡ ተሰቀለበት ፡ ግርግም ፡ ሄዳ ፡ ለማውረድ ፡ ብትሞክር ፡ ስለራቃት ፡ በግር ፡ ጣቶችዋ ፡ ቆማ ፡ ተንጠራርታ ፡ በሁለት ፡ እጆችዋ ፡ የግርግሙን ፡ ጠርዝ ፡ እየዳበሰች ፡ ስትፈልግ ፡ አይኑንም ፡ አፉንም ፡ በሰፊው ፡ ከፍቶ ፡

ዝም ፡ ብሎ ፡ ይመለከታት ፡ ነበር ።

መቸም ፡ ለወደደ ፡ ሰው ፡ በተወዳጁ ፡ ላይ ፡ የሚታዩው ፡ ተራ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተነገሮ ፡ የማያልቅ ፡ ተሰምቶ ፡ የማይጠገብ ፡ የደስታ ፡ ምስጢር ፡ የደስታ ፡ መልክት ፡ የያዘ ፡ ነው ! ቡግር ፡ ጣቶችዋ ፡ እንደቆመች ፡ ከወገብዋ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ አካልዋ ፡ እርሳስና ፡ ክርታስ ፡ የሚፈልጉ ፡ እጆችዋን ፡ ተከትሎ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሳብ ፡ ብሎ ፡ ወገብዋ ፡ ከድሮው ፡ ትንሽ ፡ ቀጠን ፡ ዳሌዋ ፡ ትንሽ ፡ ኮራ ፡ ብሎ ፡ ቅርጽዋ ፡ ቁርጥዋ ፡ ከማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ተውቦ ፡ የጽህፈት ፡ መሳሪያዋን ፡ ስትፈልግ ፡ የምታደርገው ፡ እያንዳንዱ ፡ ትንሽ ፡ እንቅስቃሴ ፡ እያንዳንዱ ፡ ትንሽ ፡ ንቅናቄ፡- በቁጥሩ ፡ አንዳንድ ፡ የደስታ ፡ ምንጭ፡ በልቡ ፡ እንዳፈለቀ ፡ ሁሉ ፡ ልቡ ፡ በደም ፡ ፈንታ ፡ ደስታ ፡ ብቻ ፡ እንደሚነዛ ፡ ሁሉ ፡ ሙሉ ፡ አካሉን ፡ ደስታ ፡ ብቻ ፡ ተሰማው ፡ ካናቱ ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጣቱ ፡ እያንዳንዱ ፡ የሰውነቱ ፡ ክፍል ፡ በደስታ ፡ ሰከረ ።

“ወይ ፡ ግሩም! እንዴት ፡ ታምራለች! እንዴት ፡ እጹብ ፡ ድንቅ ፡ አድርጎ ፡ ሰራት!” አለ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ‘ሲመለከት’፡ ቆይቶ ። “ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻለኛል? ምን ፡ ማድረግ ፡ እችላለሁ ? ያነለት ፡ ነበር ፡ እንዲያ ፡ በቅሎ ፡ ላይ ፡ ተዘርግታ ፡ አይኖችዋ ፡ ሲቅበዘበዙ ፡ ልብዋ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ሲጋልብ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሳም ፡ ባደርጋት ፡ ነገሩ ፡ ይለይ ፡ ነበር! ምን ፡ ትለኝ ፡ ኖሮዋል ? “እንዴት ፡ ብትደፍረኝ ፡ ነው ፡ ለዚህ ፡ ያበቃከኝ ! አንተ? ሁለተኛ ፡ አጠገቤ ፡ትደርስና!” ትለኝ ፡ ነበር ፡ ይሆን? አይ! አትልም ፡ ነበር! የሰም ፡ ያነለትስ ፡ አትልም ፡ ነበር! እኔ ፡ ፈርቼ ፡ ሸሸሁ ፡ እንጂ ፡ መቼም ፡ የማልረባ ፡ ነኝ ። ልቤ ፡ ተሸበረ ፡ እንጂ ፡ እሰዋስ ፡ ፈቃድዋ ፡ ነበር! አይ ፡ የማይደገም ፡ አጋጣሚ ፡ አመለጠኝ! ዛሬ ፡ ግን . . . አይ ፡ ዛሬማ ፡ እንዴት ፡ ብዬ! ዛሬስ ፡ አይሆንም ፡ ዛሬስ ፡ የማይቻል ፡ ነው ።” እያለ ፡ በፍራትና ፡ ራሱን ፡ በመውቀስ ፡ መሀከል ፡ ተቀምጦ ፡ ድምጹን ፡ ሳያሰማ ፡ ሲሙዋገት ፡ እርሳስና ፡ ክርታስዋን ፡ እንደምንም ፡ ከተሰቀሉበት ፡ አውርዳ ፡ ይዛ ፡ መጣችና ፡ አጠገቡ ፡ ተቀመጠች ። የጽህፈት ፡ መሳሪያዋን ፡ ከተሰቀለበት ፡ ለማውረድ ፡ ስትጣጣር ፡ ደክሞዋት ፡

ባጭር / ባጭር ፡ ትተነፍስ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ አጠገቡ ፡ መጥቷ ፡ ስትቀመጥ ፡ የፍራቱም ፡ የፍቅሩም ፡ ስሜት ፡ እየበዛ ፡ እየበዛ ፡ በሄደ ፡ መጠን ፡ የልቡ ፡ መሸበር ፡ ፊቱን ፡ ሲያማመው ፡ ግንባሩን ፡ ሲያወዛው ፡ እረፍት ፡ አጥቶ ፡ ሲቸገር ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ አዩችና ፡-

“ምነ!” አለች ፡ ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ።

“ም - - - ምኑ!” አለ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየቱን ፡ ፈርቶ ፡ አንገቱን ፡ እንደ ፡ ደፋ ።

“ለምን ፡ አላበህ? ሞቀህ?”

“የለ - - - የለም ፡ ደህና ፡ ነኝ ። ”አለ ፡ ልቡ ፡ ካፎቱ ፡ ወጥቶ ፡ ሊሮጥ ፡ ሲንደፋደፍ ፡ ትንፋሹን ፡ እያደናቀፈው ። ስሜቱን ፡ ከሁኔታው ፡ ስታይ ፡ የስዋም ፡ ስሜት ፡ መለወጥ ፡ ጀመረ ። የስዋም ፡ ፊት ፡ መጋም ፡ የስዋም ፡ ልብ መሮጥ ፡ የስዋም ፡ ትንፋሽ ፡ መደናቀፍ ፡ ጀመረ ።

“ደን - - - ጸን ፡ ልጻፍ ፡ ወይስ ፡ ደን?”

“ ሁለ --- ሁለቱንም ፡ ጻፊ ።”

ደንም ፡ ጸንም ፡ ለመጻፍ ፡ ብትሞክር ፡ ሁለቱም ፡ ከማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የባሰ ፡ ተበላሹ ።

“ የለ --- የለም ! እንደ--ሱ ፡ አይ--አይደለም !” አለና ፡ እንደ ፡ ሁልጊዜው ፡ እጅዋን ፡ ይዞ ፡ ለማስጻፍ ፡ ከግራ ፡ ጎንዋ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ራቁት ፡ ክንዷን ፡ በራቁት ፡ ትከሻዋ ፡ አሳልፎ ፡ ቀኝ ፡ እጅዋን ፡ ለመያዝ ፡ እንዲመቸው ፡ ልብሱን ፡ ከቀኝ ፡ ወገን ፡ ጠቅለል ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ትከሻው ፡ ገፋ ፡ ሲያደርግ ፡- በውስጡ ፡ ከተቃጠለው ፡ እሳት ፡ የተነሳ ፡ ታፍኖ ፡ የቆየው ፡ ሙቀት ፡ ልብሱ ፡ ገለጥ ፡ ሲል ፡ ቀሚስዋን ፡ ዘልቆ ፡ ለገላዋ ፡ ተሰማው ። ክንዱ ፡ ትከሻዋን ፡ ቀኝ ፡ እጁ ፡ ቀኝ ፡ እጅዋን ፡ ትኩስ ፡ ትንፋሹ ፡ ጆሮዋን ፡ አንገትዋን ፡ ሲነካት ፡ ልዩ ፡ ሙቀት ፡ የወንድነቱ ፡ ሙቀት ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ማእበል ፡ በሰራካላትዋ ፡ ጎርፎ ፡ አጋላት ። ያ ፡ ለምለም ፡ ያ ፡ ውብ ፡ አካላትዋ ፡ ከማር ፡ ሰፈፍ ፡ እንደ ፡ ተሰራ ፡ ሁሉ ፡ ሙቀት ፡ እንደሚፈራ ፡ ሁሉ ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ መቅለጥ ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ መፍሰስ ፡ ጀመረ ። ሰውነትዋን ፡ መግዛት ፡

በሰውነትዋ ፡ ግዘዝ ፡ ተሳናት ። ወዲያው ፡ ሳታስበው ፡ ሳታዝዘው ፡ ራስዋ ፡ ቀና ፡ ፊትዋ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ዘወር ፡ አለና ፡ አፍዋ ፡ ተከፍቶ ፡ የሱን ፡ አፍ ፡ ፍለጋ ፡ ሲሄድ ፡ በመንገድ ፡ ተገናኙ ። ከዚያ ፡ እጆችዋ ፡ እየሳሰሩ ፡ ክርታሱን ፡ ጥለው ፡ አንገቱን ፡ የሱም ፡ እጆች ፡ የሷዋን ፡ ተጠምጥመው ፡ ያዘው ፡ አፏዋ ፡ ባፉ ፡ አፉ ፡ ባፏዋ ፡ ውስጥ ፡ ቀለጡ ። እሷ ፡ በሷዋ ፡ እሷዋ ፡ በሱ ፡ ውስጥ ጠፉ ። ሁለቱ ፡ ያናግል ፡ ሁለቱ ፡ ንጹህን ፡- ያህን ፡ የተበላሸ ፡ ያህን ፡ የቆሸሸ ፡ ያህን ፡ በከፋ ፡ ነገር ፡ ያደፈ ፡ የጎደፈ ፡ አለም ፡ ጥለው ፡- ወደ ፡ ሌላ ፡ አለም ፡ ወዳንድ ፡ አዲስ ፡ አለም ፡ ገቡ ። እንዴት ፡ ጥሩ ፡ አለም ፡ ነው ! የፍቅር ፡ አለም ! ሳር ፡ እንጨቱ ፡ ፍቅር ፡ ብቻ ፡ አብቦ ፡ የሚያፈራበት ፡ ወንዙ ፡ ፍቅር ፡ ብቻ ፡ የሚያፈስበት ፡ አእዋፍ ፡ ፍቅር ፡ ብቻ ፡ የሚዘምሩበት ፡ የፍቅርና ፡ የፍጹም ፡ ደስታ ፡ አለም ! እኒያ ፡ ሁለት ፡ የከፋ ፡ ባህል ፡ ምርኮኞች ፡ እኒያ ፡ ሁለት ፡ የከፋ ፡ ልማድ ፡ እስረኞች ፡ ማሰሪያቸውን ፡ ቆርጠው ፡ ከወህኒያቸው ፡ አምልጠው ፡- ከፉ ፡ አርጌ ፡ ባህል ፡ ከፉ ፡ አርጌ ፡ ልማድ ፡ በሌለበት ፡ ፍጹም ፡ በማይታወቅበት ፡ አለም ፡ ገቡ ። የከፋ ፡ ልማድ ፡ እስረኛነታቸውን ፡ ባርነታቸውን ፡ ረሱ ። አየ---! ምነው ፡ እንዲያ ፡ ባለው ፡ አለም ፡ ውስጥ ፡ ለሁልጊዜ ፡ በኖሩ ! ምነው ፡ ከንዲያ ፡ ያለው ፡ ጥሩ ፡ የልም ፡ አለም ፡ ወደዚህ ፡ ከፉ ፡ የውን ፡ አለም ፡ ባልተመለሱ ! ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ይመለሳሉ ! ተመለሱ !

ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ አይን ፡ ላይን ፡ ተያዩና ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ አይናቸውን ፡ ከደነው ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ አፍ ፡ ላፍ ፡ ተያይዘው ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተዋህደው ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ወዳገኙት ፡ አዲስ ፡ አለም ፡ ሄዱ ።

ሁለተኛ ፡ ሲመለሱ ፡ መመለሳቸው ፡ ከሱ ፡ ይልቅ ፡ እስዋን ፡ አስፈርትዋት ፡ አንገቱን ፡ በሁለት ፡ እጆችዋ ፡ ተጠምጥማ ፡ እንደ ፡ ያዘች ፡ እየተንቀጠቀጠች ፡- “ ያዘኝ ፡ አትልቀቀኝ ፡ እባክህ ፡ አትልቀቀኝ ! ” አለች ።

“ የለም ፡ አልተውሽም ፡ አልለቅሽም ! ” አለ ፡ እሱም ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ እንዲሁ ፡ አንገት ፡ ላንገት ፡ እንደ ፡ ተያያዙ ፡ ብዙ ፡ ቆይተው ፡ ሰውነታቸው ፡ ጸጥ ፡ ሲል ፡ ለቀቃትና ፡ ሁለ

ቱም ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተው ፡ ዝም --- ብለው ፡ ተቀምጠው ፡ እስበሳቸው ፡ ይተያዩ ፡ ጀመር ።

እስዋ ፡ በሱ ፡ እሱ ፡ በስዋ ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ያዩት ፡ አጹብ ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ አለም ፡ በምን ፡ ቋንቋ ፡ ይነገራል ? ምን ፡ ቃል ፡ ይበቃዋል ? እንዲያው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መገረሙ ፡ እንዲያው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መደነቁ ፡ የበለጠ ፡ ሊገልጸው ፡ ይችል ፡ ይሆናል ! እሱም ፡ ያን ፡ አለም ፡ ያሳዩችውን ፡ እስዋም ፡ ያን ፡ አለም ፡ ያሳየችን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መመልከት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መመርመሩ ፡ ከሁሉ ፡ ይሻላል ! ስለዚህ ፡ ሁለቱም ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተው ፡ እሱ ፡ እስዋን ፡ እስዋ ፡ እሱን ፡ እየተያዩ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ ።

በዛብህ ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ በፍቅር ፡ የሚዋኙ ፡ አይኖቹን ፡ በስዋ ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ ሲመለከታት ፡ ሲመረምራት ፡ ያች ፡ ድሮ ፡ የሚያውቃት ፡ ውብዋ ፡ ደማምዋ ፡ ሰብለ ፡ ከድሮዋ ፡ ሚሊዮን ፡ ጊዜ ፡ የተዋበች ፡ ያበበች ፡ ከመምሰልዋም ፡ በላይ ፡ ባያት ፡ በመረመራት ፡ መጠን ፡ ስአሊ ፡ ስእሉን ፡ በመጨረሻ ፡ ማስጌጫ ፡ ቀለሙ ፡ ሲነካካው ፡ እያማረ ፡ እያማረ ፡ እንደሚሄድ ፡ በዩደቂቃው ፡ በዩንኡስ ፡ ደቂቃው ፡ እየተዋበች ፡ እየተዋበች ፡ የምትሄድ ፡ መስላ ፡ ታየችውና ፡ የሱም ፡ መገረም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ እየበዛ ፡ ሄዶ ፡ ተጠራጠረ ። እልም ፡ ናት ፡ እውን ? ሰው ፡ ናት ፡ መንፈስ ? መንካት ፡ አለበት ! እንደ ፡ ቶማስ ፡ እጁን ፡ ሰዶ ፡ ዳብሶ ፡ ነክቶ ፡ ካልተረዳ ፡ አይኑን ፡ ብቻ ፡ ማመን ፡ አቃተው ! ስለዚህ ፡ አፉን ፡ እንደ ፡ ከፈተ ፡ እጁን ፡ ቀስ --- አድርጎ ፡ ሰዶ ፡ አንገትዋን ፡ አገጭዋን ፡ የተከፈቱ ፡ ከንፈሮችዋን ፡ አፍንጫዋን ፡ አይኖችዋን ፡ ጉንጮችዋን ፡ ጆሮዎችዋን ፡ ከዚያ ፡ አይኖቹ ፡ የሚያዩትን ፡ ሁሉ ፡ የሰውነት ፡ ክፍልዋን ፡ ይዳብስ ፡ ጀመር ። አይኑ ፡ ያየው ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ እጁም ፡ መሰከረ ! አይኑ ፡ አልተሳሳተም ፡ እልም ፡ አይደለችም ፡ እውን ፡ ናት ! መንፈስ ፡ አይደለችም ፡ ሰው ፡ ናት ! ያካልዋና ፡ የመንፈስዋ ፡ ውበት ፡ ከሚያውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ ያው ፡ ሰው ፡ ናት ! እንደ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ከስጋና ፡ ከደም ፡ ከጥንትና ፡ ከጅማት ፡ የተሰ

ራች ፡ ቤት ፡ ናት ! ሰብለ ፡ ናት ! ደግሞ ፡ እንደገና ፡ የተከፈተ ፡ አፍዋን ፡ አይንዋን ፡ ፊትዋን ፡ ሁሉ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ያዳብስ ፡ ጀመር ። አሁንማ ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያማ ፡ መፍራት ፡ የለ ፡ ማፈር ፡ የለ ፡ ምን ፡ ትለኛ ፡ ማለት ፡ የለ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በመሀከ ላቸው ፡ የነበረው ፡ ገደል ፡ ተንዶ ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ እሱን ፡ ራሱን ፡ ሆና ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ያፈራል ? ራሱን ፡ ያፍራል ? ራሱን ፡ ምን ፡ ይለኛ ፡ ይላል ? የለም ! ከንግዲህስ ፡ እሱ ፡ ናት ፡ ራሱ ፡ ናት ፡ በፈለገው ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈለገው ፡ ይዳብሳታል ! እሰዋም ፡ እንዲሁ !

ስለዚህ ፡ መናገር ፡ የለ ፡ መሳቅ ፡ የለ ፡ ፈገግታ ፡ እንኳ ፡ የለ ፡ እንዲያው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ብቻ ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተው ፡ በመገረም ፡ ፊት ፡ እየተያዩ ፡ እየተደባበሱ ፡ ተቀመጡ ። እንዲ ያው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ብቻ ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተው ፡ እሱ ፡ እስ ዋን ፡ እሰዋ ፡ እሱን ፡ እያጠኑ ፡ እየመረመሩ ፡ እያንዳንድዋ ፡ ጥቃቅን ፡ የጊዜ ፡ ክፍል ፡ ባለፈች ፡ መጠን ፡ አዳዲስ ፡ ውበት ፡ አዳዲስ ፡ ደምግባት ፡ ሲገለጽላቸው ፡ እየተገረሙ ፡ እየተደ መሙ ፡ ተቀመጡ ።

የወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ መምጫ ፡ ደረሰ ። ያን ፡ ተራ ፡ ፍቅራቸውን ፡ ዝሙታቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ሱሳቸውን ፡ አሳል ፈው ፡ የደናግሉን ፡ የንጹሀኑን ፡ በሩክ ፡ ቅዱስ ፡ ፍቅር ፡ ለማቋ ቋረጥ ፡ የሚመጡበት ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ! አየ - - - ! እንዲያ ፡ ያለ ውን ፡ ፍቅር ፡ ይዞ ፡ ወዴት ፡ መሄድ ፡ ወዴት ፡ መሸሽ ፡ ይቻላል? እመቤትዋ ፡ የሚመጡበትን ፡ ጊዜ ፡ ስለምታውቅ ፡ ሀብትሽ ፡ ቀደም ፡ ብላ ፡ እየዘፈነች ፡ መጣች ። -

“ ጨረሳችሁ ፡ እንዴ ! ምነው ፡ ምን ፡ ሆናችሁ ? ” አለች ፡ እየዘፈነች ፡ ገብታ ፡ በዛብህና ፡ ሰብለ ፡ ትንሽ ፡ ተራርቀው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተቀምጠው ፡ እርሳሱና ፡ ክርታሱ ፡ ለዩብቻ ፡ ወድቀው ፡ ስታይ ፡ የተጣሉ ፡ መስሎዋት ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ ብላ ።-

“ እ - - - ? ደኅና ፡ ነን ፡ ምን ፡ ሆንን ? ” አለች ፡ ሰብለ ።

“ እእ ! ደኅና ፡ ነን ። ” አለ ፡ በዛብህም ፡ ገና ፡ ከንቅልፉ ፡ እንደ ፡ ነቃ ፡ አይኑን ፡ እያሻሸ ።

" እንጃ ! " አለች ፡ ሀብትሽ ፡ የሰብለንም ፡ የበዛብህንም ፡ ፊት ፡ ስታይ ፡ መጣላታቸው ፡ ርግጥ ፡ መሆኑን ፡ አምና ።-

" የለም ፡ ደህና ፡ ነን ! ቅድም ፡ ጨርሰን ፡ ብቻዋን ፡ ጥያት ፡ እንዳልሄድ ፡ አንቺ ፡ እስክትመጪ ፡ ነበር ፡ የምጠብቅ ። ከመጣሽ ፡ ል - - - ሂድ ፡ እንግዲህ ፡ ልሂድ ! " አለ ፡ በዛብህ ፡ እያመነታ ። ሰብለ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ አይን ፡ አይኑን ፡ ስትመለከት ፡ ቆዩችና ፡- " ትሄድ ? " አለች ። እሱም ፡ እንደሰዋ ፡ አይን ፡ አይንዋን ፡ ትንሽ ፡ ተመለከተና ፡ " አዎ ፡ ልሂድ ፡ ደህናደሩ ። " ብሎ ፡ ወጣ ።-

" እውነት ፡ ምን ፡ ሆናችሁ ? ተጣላችሁ ? " አለች ፡ ሀብትሽ ፡ በዛብህ ፡ ከወጣ ፡ በሁዋላ ። ሰብለ ፡ የማያይ ፡ አይንዋን ፡ በሰፊው ፡ ከፍታ ፡ አይኑ ፡ ሀሊናዋ ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ የነበሩበትን ፡ አዲስ ፡ አለም ፡ እዩተመለከተ ፡ ሀብትሽ ፡ የምትጠይቀውን ፡ ጥያቄ ፡ አትሰማም ፡ ነበር ።

" ተጣላችሁ ? ንገሪኝ ፡ እባክሽ ፡ ሰብለ ። " አለች ፡ ሀብትሽ ፡ እንደገና ፡ ወደመቢትዋ ፡ ቀረብ ፡ ብላ ።

" እእ ? "

" ተጣላችሁ ፡ ወይ ፡ ነው ፡ የምልሽ ፡ ስጠይቅሽ ፡ እንኩዋ ፡ አትሰሚም ! ምን ፡ ሆንሽ ? "

" የለም ፡ አልተጣላንም ። "

"እንግዲያ ፡ ካልተጣላችሁ ፡ ያለድርዋችሁ ፡ ለምን ፡ እንዲያ ፡ ዝም ፡ ብላችሁ ፡ ተቀምጣችሁ ፡ አገኘሁዋችሁ ? ደግሞስ ፡ ፊትሽን ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አረገው ? አንቺ ፡ ፊትሽ ፡ እንዲህ ፡ ደም ፡ የሚመስልና ፡ ከንፈርሽ ፡ እንዲህ ፡ የሚያብጥ ፡ ስታለቅሽ ፡ ነው ! " ሰብለ ፡ ከንፈሮችዋን ፡ ብትዳብስ ፡ እውነትም ፡ በጣም ፡ አብጠዋል ። ወዲያው ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ አለችና ፡- "አዎ ፡ ትንሽ ፡ አለቀስሁ ። ብቻ ፡ ተጣልተን ፡ አይደለም ። " አለች ።

" ካልተጣላችሁ ፡ ለምን ፡ አለቀስሽ ? "

" እሱ ፡ እናት ፡ አባቱ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ እንስቶ ፡ ሲያለቅስ ፡ ሳየው ፡ በጣም ፡ አሳዘነኝ ፡ እኔም ፡ አለቀስሁ ። "

" እእ - - - ! ለዚህ ፡ ነው ፡ የሱም ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ! የሱም ፡ አፍኮ ፡ ግሩም ፡ ሆኖ ፡ አብጦዋል ! አላዩሽውም ? "

"ልብ ፡ አድርጌ ፡ አላየሁትም ።" አለች ፡ ሰብለ ፡ የገዛ ፡ ሙሽትዋ ፡ የመጣባትን ፡ ሳቅ ፡ ለመደበቅ ፡ አንገትዋን ፡ ደፋ ፡ አደረገችና ።-

## ምእራፍ ፤ ፳፫ ፤

# እፍ ፤ ዝም ፤ ቢል ፤ ሌላው ፤ ይናገራል ፤

በዛብሁና ፤ ሰብለ ፤ በከበባቸው ፤ ያዘንና ፤ የብስጭት ፤ የጭቆናና ፤ የባርነት ፤ የሽሙጥና ፤ ያሜት ፤ አለም ፤ ውስጥ ፤ ከዚህ ፤ ሁሉ ፤ ነጻ ፤ የሆነ ፤ ይህ ፤ ሁሉ ፤ የሌለበት ፤ ልዩ ፤ አለም ፤ የፍቅር ፤ አለም ፤ የደስታ ፤ አለም ፤ የነጻነት ፤ አለም ፤ ፈጥረው ፤ አንድ ፤ ወር ፤ ያክል ፤ ደስ ፤ ብሎዋቸው ፤ ነጻ ፤ ሆነው ፤ ኖሩ ።

ብርቱ ፤ ፍቅር ፤ ባለበት ፤ ክፉ ፤ ነገር ፤ የለም ። ብርቱ ፤ ፍቅር ፤ ካለ ፤ የሚቆጣ ፤ የሚቀጣ ፤ የሚስቅ ፤ የሚሳለቅ ፤ የሚያማ ፤ የሚያሽሙዋጥጥ ፤ ይኖራል ፤ ብሎ ፤ መፍራት ፤ መጠርጠር ፤ እንኩዋ ፤ የለም ። ብርቱ ፤ ፍቅር ፤ ክፉውን ፤ ደህና ፤ አስቸጋሪውን ፤ ቀና ፤ ሩቁን ፤ ቅርብ ፤ ጨለማውን ፤ ብርሃን ፤ ዱሩን ፤ ሜዳ ፤ አቀበቱን ፤ ደልዳላ ፤ አድርጎ ፤ ማሳዬት ፤ አለበት ። ያለዚያ ፤ ብርቱ ፤ ፍቅር ፤ አይባልም ። አእምሮን ፤ ከመልካም ፤ በቀር ፤ ክፉ ፤ ሊደርስ ፤ ይችላል ፤ ብሎ ፤ እንዳያስብ ፤ የማይሰውር ፤ አይንን ፤ ከመልካም ፤ በቀር ፤ ክፉ ፤ እንዳያይ ፤ የማያውር ፤ ጆሮን ፤ ከመልካም ፤ በቀር ፤ ክፉ ፤ እንዳይሰማ ፤ የማያደነቁር ፤ ፍቅር ፤ ብርቱ ፤ ፍቅር ፤ አይባልም ። የነሱ ፤ ፍቅር ፤ ግን ፤ በብዙ ፤ ሰው ፤ ደርሶ ፤ የማያውቅ ፤ እጅግ ፤ ብርቱ ፤ ስለነበረ ፤ ክፉ ፤ ነገር ፤ ሊደርስ ፤ ይችል ፤ ይሆናል ፤ ብሎ ፤ ማሰብን ፤ መፍራትን ፤ መጠርጠርን ፤ እንኩዋ ፤ ካሳባቸው ፤ አጥፍቶ ፤ ከሌላ ፤ ወገን ፤ ድፍረትን ፤ ነጻነትን ፤ ተስፋን ፤ ደስታን ፤ ሰጥቶ ፤ ተባብረው ፤ በፈጠሩት ፤ የፍቅር ፤ አለም ፤ ውስጥ ፤ ደስ ፤ ብሎዋቸው ፤ ነጻ ፤ ሆነው ፤ አንድ ፤ ወር ፤ ያክል ፤ እንዲኖሩ ፤ አደረጋቸው ።

የመሳፍንቱ ፤ የንጉስታቱ ፤ ልጅ ፤ ፊታውራሪ ፤ መሸሻ ፤ ልጃቸው ፤ ከዚያ ፤ የረኛ ፤ የገበሬ ፤ ልጅ ፤ ጋር ፤ መዋደድዋን ፤ ቢያውቁ ፤ ምን ፤ እንደሚሉ ፤ ምን ፤ እንደሚሆኑ ፤ ላንድ ፤ አፍታ ፤ እንኩዋ ፤ ትዝ ፤ ቢላቸው ፤ ኖሮ ፤ መዋደዳቸውን ፤ አገር ፤ ቢያውቅ ፤ መሳቂያ ፤ መሳለቂያ ፤ መተረቻ ፤ መዘባበቻ ፤ የሚሆኑ ፤

መሆናቸው ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ እንኳዋ ፡ ትውስ ፡ ቢላቸው ፡ ኖሮ ፡
እረኛው ፡ በየሜዳው ፡ በየዱሩ ፡ ቆንጆው ፡ በየሰርጉ ፡ በየመት
ባሉ ፡ መዝፈኛ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ መሆኑ ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡
እንኳዋ ፡ ትዝ ፡ ቢላቸው ፡ ኖሮ ፡ መዋደዳቸው ፡ ቢታጠቅ ፡
ሽሙጡ ፡ አሜቱ ፡ እፍረቱ ፡ ውርደቱ ፡ እንደ ፡ በሽተኛ ፡ ውሻ ፡
መሸሻ ፡ መሸሸጊያ ፡ የሚያሳጣቸው ፡ መሆኑ ፡ ትንሽ ፡ እንኳዋ ፡
ቢታሰባቸው ፡ ኖር ፡ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡
ቀን ፡ የሚለያይ ፡ ነገር ፡ የደረሰባቸው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ይዞ ፡ ግን
ታዊ ፡ ደስታ ፡ ወደ ፡ መሪር ፡ ሲኣላዊ ፡ አዘን ፡ ሊለወጥ ፡ የሚ
ችል ፡ ለመሆኑ ፡ ትንሽ ፡ ጥርጣሬ ፡ እንኳዋ ፡ ባሳባቸው ፡ ቢኖር ፡
ኖሮ ፡ ደስታቸው ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ፍጹም ፡ ባልሆነ ፡ ነበር ። ነገር ፡
ግን ፡ ሸንጋዩ ፡ አታላዩ ፡ ፍቅር ፡ ወዳጆችን ፡ ደላዩ ፡ በዳዩ ፡
ፍቅር ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አዙረው ፡ እንዳያዩ ፡ እንዳያስቡ ፡ አድርጎ ፡
በባርነት ፡ አለም ፡ ውስጥ ፡ የነጻነት ፡ አምባ ፡ ፈጥሮ ፡ የክፉ ፡
ልማድ ፡ እስረኛ ፡ በሆነ ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ እነሱን ፡ ነጻ ፡ አድ
ርጎ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ያክል ፡ እንደ ፡ ሰከሩ ፡ ሁሉ ፡ የሚኖሩበትን ፡
ክፉ ፡ አለም ፡ ረስተው ፡ እንዲኖሩ ፡ አደረጋቸው ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ጥዋት ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነትኛ ፡ ሰብለ ፡
ወንጌል ፡ ቁርስ ፡ አድርገው ፡ ቡና ፡ ሲጠጡ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ መጣ ።

“ምነው ፡ እንደሚጠሉት ፡ ሰው ፡ በልተን ፡ ከጨረስን ፡
በሁዋላ ፡ መጣህ ? ካሳየ !” አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ።

“የጠሉት ፡ ቀላዋጭ ፡ ከመብል ፡ በፊትም ፡ ቢደርስ ፡ በል
ተን ፡ ከጨረስን ፡ መጣህ ፡ ይባላል ፡ የሚሉትን ፡ ተረት ፡ መድገ
ምሽ ፡ ይሆን ?” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እየሳቀ ።

“ጥልጣል ፡ ያውርድህና ፡ አንተን ፡ ጠልተን ፡ ነው ፡ ሳን
በላ ፡ በልተን ፡ ከጨረስን ፡ በሁዋላ ፡ መጣህ ፡ የምንል ? እንዲ
ያው ፡ ይሄ ፡ ጠማማው ፡ አሳብህ ፡ ሰው ፡ የተናገረውን ፡ ቅን ፡
ነገር ፡ አጣሞ ፡ መመልከት ፡ ይወዳል ! በይ ፡ እንቺ ፡ ወለቴ ፡
እመቴ ፡ ማነሽ ፡ እንጀ ፡ አህዮ ፡ የሚበላው ፡ አምጭለት !”
አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ አጠገባቸው ፡ ያሉት
ንም ፡ የሌሉትንም ፡ የሞቱትን ፡ አገልጋዮቻቸውን ፡ ስም ፡ ሳይ
ቀር ፡ በተራ ፡ ጠርተው ።

"የለም ፡ ስቀልድ ፡ ነው ፡ ቁርስ ፡ አድርጌያለሁ ፡ ቡና ፡ ብቻ ፡ ስጡኝ !"

ከዚያ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የመጣለትን ፡ ቡና ፡ ጠጥቶ ፡ ሲጨርስ ፡ እሱና ፡ ሰብለ ፡ ተዩይዘው ፡ ወደምትማርበት ፡ ወደልፍኝዋ ፡ ሄዱ ።

"ትምርትሽ ፡ እምን ፡ ደረሰ ?" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እሰብለ ፡ እልፍኝ ፡ ገብተው ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ።

"ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ማለዘብ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፡ ጽህፈት ፡ ነበር ፡ ያስቸገረኝ ፡ እሱም ፡ ቢሆን ፡ አሁን - - -" አለች ፡ ሰብለ ፡ ጽህ ፈት ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ አውቄያለሁ ፡ ለማለት ፡ አፍዋ ፡ ፈርቶ ፡ እያመነታች ።

"የበዛብህ ፡ ጥሩ ፡ አስተማሪነትም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ያንቺ ፡ ቀለም ፡ ተቀባይነት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ትምርት ፡ አንቺ ፡ ቶሎ ፡ ጨረስሽ ! ምስጋና ፡ ይገባችሁዋል !"

"ቶሎ ፡ ጨረስሁ ፡ እንዴ ! እማማ ፡ የምትለው ፡ ሌላ ፡ ነው !"

"እስዋ ፡ ምን ፡ ታውቃለች ? በትንሹ ፡ አንድ ፡ አመት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ትምርት ፡ ነው ፡ በ - - - ስንት ፡ ወር ፡ ነው ፡ የጨረስሽ ?"

"ስድስት ፡ ወይም - - - ሰባት ፡ ወር ፡ ቢሆን ፡ ነው ! ሲያስ ተምር - - - እንጂ ! እንዴት ፡ ልበልህ ! እንዲያው ፡ ግልጥልጥ ፡ አድርጎ ፡ ብርሃን ፡ አድርጎ ፡ ስለሚያሳይ ፡ መቀበሉ ፡ አያስቸግ ርም !" አለች ፡ ሰብለ ፡ በዛብህን ፡ በምንም ፡ ይሁን ፡ የምታመሰግ ንበት ፡ ምክንያት ፡ በማግኘትዋ ፡ ለልብዋ ፡ የተሰማው ፡ ደስታ ፡ በጥሩ ፡ ፊትዋ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ እዩታዩ ።

"አይ ፡ ሲያስተምር ፡ ብታየው ፡ አያ ፡ ካሳ ! ግሩምኮ ፡ ነው ! እንዲያው ፡ ግሩም ፡ ነው !" አለች ፡ ፊትዋ ፡ በደስታ ፡ እንደ ፡ በራ ፡ አይኖችዋን ፡ በዘዝ ፡ አድርጋ ፡ እጣራው ፡ ላይ ፡ ተክላ ። አይነ ፡ ህሊናዋ ፡ በዛብህ ፡ እጅዋን ፡ ይዞ ፡ ሲያስተምራት ፡ ነበር ፡ የሚያየው ።

"ረስተሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ጊዜኮ ፡ እዚህ ፡ እዩተቀመጥሁ ፡ ሲያስተምርሽ ፡ አይቻለሁ !" አለ ፡ የፍቅር ፡ ምርኮኛ ፡

መሆንዋን ፡ ሲያይ ፡ ሁኔታዋ ፡ አሳዘነውና ፡ ያዘን ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡፡

"እእዎ ! ለካስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይተህል ! ረስቼ ! ታዲያስ፡ ጥሩ ፡ አይደለም ? ሲያስተምር --- ጥሩ አይደለም?"

"በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው!" አለ ፤ ያዘን ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ እን ዳለ ፡ አንገቱን ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መድፋት ፡ ብሎ ፡፡ ከዚያ ፡ እሰዋ፡ በዛብህን ፤ እሱ ፡ የሰዋን ፡ ሁኔታ ፡ እያሰቡ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆዩ፡፡

"ሰብለ ፡ ድሮኮ ፡ ከኔ ፡ የምትሰውሪው ፡ ምስጢር ፡ አልነበ ረሽም ፡ አሁን ፡ ግን ፡ እንጃ! የተለወጥሽ ፡ መሰለኝ!"

"ምስጢር? ተለወጥሽ? ምን ፡ ተለወጥሁ ? የምን ፡ ምስጢ ር?" አለች ፤ ምስጢር ፡ የሚባለውን ፡ ቃል ፡ ስትሰማ ፡ ካንድ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምስጢር ፡ ስለሌላት ፡ የሱን ፡ መገለጥ ፡ ጠርጥራ ፡ ፊትዋ ፡ ከቀይ ፡ ወደ ፡ ብጫ ፡ ከብጫ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ቀይ ፡ በቅጥበት ፡ ተለዋውጦ ፤ አይንዋ ፡ እንደ ፡ ታነቀች ፡ ሁሉ ፡ ካፎቱ ፡ በጥፍ ፡ ወጥቶ፡፡

"አይዞሽ ፡ አትደንግጪ ! መደንገጥ ፡ አያስፈልግም! ብቻ እንዳንድ ፡ ነገር ፡ ሲገጥምሽ ፡ እንደ ፡ ድሮሽ ፡ ብታማክሪኝ ፡ የም ትፈልጊው ፡ ነገር ፡ እንዲፈጸምልሽ ፡ መንገድ ፡ እመራሽለሁ ፤ ረዳሻለሁ ፡፡ ያለሽኝ ፡ እንቺ ፡ ያለሁሽ ፡ እኔ!" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፤ የሚወዳት ፡ ሰብለ ፡ በፍቅር ፡ ታውራ ፡ ልታዬው ፡ የማትችለውን፡ አደጋ ፡ ስላዬ ፡ የተሰማውን ፡ የልብ ፡ አዘን ፡ በውሸት ፡ ፈገግታ ፡ ለመሸፈን ፡ እዬተጣጣረ ፡፡ "አይዞሽ ፡ አትፍሪ ! የሆነ ፡ ሆኖዋልና፡ ተመካክረን ፡ የሚበጅ ፡ መንገድ ፡ እንፈልጋለን ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ንገሪኝ፡፡" አለ ፡ ደገመና፡፡

"ምኑን ፡ ልንገርህ? " አለች ፤ አንገትዋን ፡ እንደ ፡ ደፋች፡፡

"ከበዛብህ---" ብሎ ፡ ሲጠይቅ ፡ ያሰበውን ፡ ሳይጨርስ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የበዛብህንና ፡ የሰዋን ፡ ምስጢር ፡ ያወቀ ፡ ስለመሆኑ ፡ የሚበቃ ፡ ያክል ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ "እንዴት ፡ አደራችሁ!" አለ ፡ በዛብህ፡፡

"እእ---! እንዴት ፡ አደርህ ፡ በዙ ፡ ለካ ፡ እንዲህ ፡ እያረ ፈድህ ፡ እዬመጣህ ፡ ነው ፡ ትምርቱ ፡ አልገፋ ፡ ያለ!" አለ ፡

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ፊቱ ፡ ከመ ፡ ቅጥበት ፡ ተሸፍኖበት ፡ ከነበረው ፡ ያዘን፡ መጎናጠፊያ ፡ ተገልጦ ።

"ሰብለ ፡ ትምርት ፡ አልገባኝ ፡ አለኝ ፡ ብላ ፡ ነገረችዎ ! እንዴ !" አለ ፡ በዛብህ ፡ እቱ ፡ ለጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሲናገር ፡ አይኖቹ ፡ በጎን ፡ የሰብለን ፡ አይኖች ፡ እዩፈለጉ ። አይኖቻቸው ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ ተገናኙና ፡ የሰብለ ፡ አይኖች ፡ እንደገና ፡ ተመልሰው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ ያዩ ፡ ጀመር ።

በዛብህ ፡ የሰብለን ፡ ሁኔታ ፡ ሲያይ ፡ አንድ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ተጠራጥሮ ፡ ለጊዜው ፡ ግራ ፡ ገባው ። በሁዋላ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብሎ ፡ እሳቡን ፡ አጠረቃቀመና ፡-

"የለም ፡ በውነቱ ፡ ትምርታችንስ ፡ እንዲያውም ፡ መጀመሪያ ፡ ካሰብነው ፡ በላይ ፡ ነው ፡ የተቃናልን !" አለ ።

"እኔም ፡ ስቀልድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያንድ ፡ አመት ፡ ትምርት ፡ ነው ፡ በጥቂት ፡ ወራት ፡ የጨረስሽ ፡ እያልሁ ፡ እስዋንም ፡ አንተንም ፡ እያመሰገንሁ ፡ በዚህ ፡ ስንነጋገር ፡ ነበር --- ከመምጣትህ ፡ በፊት ።"

"እስዋ ፡ ናት ፡ ልትመሰገን ፡ የሚገባት ፡ እኔ ፡ አይደለሁም። እስዋ ፡ የምትማረውን ፡ ትምርት ፡ የማስተምራቸው ፡ ተማሪዎች፡ ለስዋ ፡ የወሰደባትን ፡ እጥፍ ፡ ጊዜ ፡ ወሰዶባቸው ፡ ገና ፡ አላጋመሱም ። ሰብለ ፡ ግን ፡ ሁሉንም ፡ ጨርሳ ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ማለዘብ ፡ ላይ ፡ ናት ፡ እሱንም ፡ ከተጋን ፡ በጥቂት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ እንጨርሳለን ፡ ጽህፈትም ፡ አሁን ፡ ያንድ ፡ ማለፊያ ፡ ጸሀፊ ፡ ያክል ፡ ታውቃለች ! እስቲ ፡ ካለዘብሽው ፡ ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ ወይም ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ አሂጂላቸው !" አለ ፡ ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ ወደስዋ ፡ ዘወር ፡ አለና ። ሰብለ ፡ አይንዋን ፡ እመሬት ፡ ተክላ ፡ ዝም ፡ አለች ።

በዛብህና ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ስለ ፡ ትምርት ፡ ሲነጋገሩ ፡ እስዋ ፡ የተሰወረ ፡ ምስጢርዋ ፡ መገለጹና ፡ እሱን ፡ ተከትሎ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ አደጋ ፡ ሁሉ ፡ ድንገት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አንድ፡ ላይ ፡ ተሰልፎ ፡ ከቦዋት ፡ በሚያስጨንቅ ፡ በሚያሰቅቅ ፡ ቅዠት ፡ ውስጥ ፡ ስለነበረች ፡ የሚሉትን ፡ አትሰማም ፡ ነበር ።

"በይኮ ፡ ሰብለ !" አለ ፡ በዛብህ ።

"እእ ? ምን ?" አለች ፤ ከቅዠት ፡ እንደ ፡ ባነነች ፡ ሁሉ ፡ በድንጋጤ ፡ ፊት ። አይኖችዋ ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ባትተኛ ፡ እንደ ፡ ሰነበተች ፡ ከብደው ፡ ውበትና ፡ ደምግባትዋ ፡ ከፊትዋ ፡ ታጥቦ ፡ ሄዶ ፡ በዚያ ፡ አጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ውብ ፡ አካልዋ ፡ ጠፍቶ ፡ ደብዝዛ ፡ ጥላዋ ፡ ብቻ ፡ ስለታያቸው ፡ ሁለቱም ፡ ደነገጡ ።

"ምን ፡ ሆኗ ፡ እናት ! ጤንነት ፡ አልተሰማሽም ?" አለ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ተነሥቶ ፡ አጠገብዋ ፡ ተቀምጦ ፡ ራስዋንም ፡ ፊትዋንም ፡ እየደባበሰ ።

"ደህና ፡ ነኝ ፡ ተውኝ ፡ ትንሽ ፡ ልተኛ ።"

"ጥሩ ፡ ነው ፡ ተኚ ፡ ብቻሽን ፡ እንዳትሆኚ ፡ ሁበትሽን ፡ ልጥራልሽ ?"

"የለም ፡ ብቻየን ፡ ብሆን ፡ ይሻለኛል ።"

"ደህና ፡ እኛም ፡ በሁዋላ ፡ መጥተን ፡ እናይሻለን ።"

ሁለቱ ፡ ወንዶች ፡ ሰብለን ፡ ብቻዋን ፡ ጥለዋት ፡ ሲወጡ ፡ "ምን ፡ አገኛት ፡ ይሆን ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ እውነት ፡ የታመመች ፡ መስሎት ፡ ደንግጦ ።

"ትናንት ፡ ማታ ፡ ድምር ፡ አጥቶኝ ፡ አደራ ፡ እያለች ፡ ስትነግረኝ ፡ ነበር ፡ ከመምጣትህ ፡ በፊት ፡ ምንም ፡ አትሆን ፤ አሁን ፡ ትንሽ ፡ ተኝታ ፡ ስታርፍ ፡ ይሻላታል ።" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ውሸቱን ።

"እንግዲያስ ፡ እዚህ ፡ ማስተማሩ ፡ ከቀረ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ እፈልግሀለሁና ፡ እንደ ፡ ተመለስህ ፡ ወደኔ ፡ እንድትመጣ ፡ ብለውኛልና ፡ አሁን ፡ ወደዚያ ፡ ልሂድ ።" አለ ፡ በዛብህ ።

"እኔም ፡ አብሬህ ፡ ልምጣና ፡ እጎጆህ ፡ ልቆይህ ።"

"ምን ፡ ያክል ፡ እንደሚያቆዩኝ ፡ አላውቅም !"

"ግዴለም ፡ የፈለጉትን ፡ ያክል ፡ ያቆዩህ ፡ የምቸኩልበት ፡ ጉዳይ ፡ የለኝም ።"

"እሺ ፡ እንግዲያስ !" አለ ፡ በዛብህ ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ያለድሮው ፡ እስከ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ተከትሎት ፡ ሄዶ ፡ እጎጆው ፡ እንዲቆይ ፡ የፈለገበት ፡ ምክንያት ፡ አልገባው ፡ ስላለ ፡ እንደ ፡ መፍራት ፡ ብሎ ።

በዛብህ ፡ አለ.ቃ ፡ ከንፉ ፡ ሆንድ ፡ በጣም ፡ ቆይቶ ፡ ወደ ፡ ጎጆው ፡ ቢሄድ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ እዚያ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲጠብቅ ፡ አገኘው ።

"ውው - - እስካሁን ፡ ይጠብቁኛል ? አለ.ቃ ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ይዘው ፡ ብዙ ፡ ስላቆዩኝ ፡ ሳይሄዱ ፡ አይቀሩም ፡ ብዬ ፡ ነበር !"

"የብቻነት ፡ ብቻነት ፡ እንግዳ ፡ ቤት ፡ ይሻላል !"

"እንዴት ?"

"ብቻውን ፡ ለሚኖር ፡ ሰው ፡ እንግዳ ፡ ቦታ ፡ እንግዳ ፡ አካባቢ ፡ የበለጠ ፡ ያጫውተዋል ! አዩህ ? እዚህ ፡ በዙሪያየ ፡ የማየው ፡ ሁሉ -፡ ክፈፉው ፡ ግብታው ፡ ሌማቱ ፡ እንዛው ፡ መድቡ ፡- ሁሉ ፡ ድሮ ፡ የማውቀውንና ፡ ረስቸው ፡ የነበረውን ፡ ነገር ፡ እንድ ፡ ባንድ ፡ እራቱ ፡ እያመጣ ፡ ሲያጫውተኝ ፡ እንደምት ለው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ማለፉ ፡ ጭራሽ ፡ አልተሰማኝም ። በል ፡ ይልቅ ፡ አሁን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልለምንህ ።"

"ምን ?"

"ብቻየን ፡ መብላቱ ፡ ስለ ፡ ሰለቸኝ ፡ ምሳየን ፡ እንድታብላኝ !"

"ተማሪ ፡ አብሉኝ ፡ ብሎ ፡ ሲለምን ፡ እንጂ ፡ ብላልኝ ፡ ተብሎ ፡ ሲለመን ፡ ገና ፡ ዛሬ ፡ ሰማሁ !" አለ ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ።

"እንደ.አስ ፡ በሰው ፡ መሀከል ፡ ብቻውን ፡ የሚኖር ፡ ካሁን ፡ በቀር ፡ መች ፡ አይተህ ፡ ታውቃለህ !"

"ቢሆንም ፡ - - - የሚያበላ ፡ እንጂ ፡ የሚበላ ፡ ጠፍቶ ፡ አይጠፋም ፡ ብዬ ፡ ነው ። እና ፡ አሁን - - - እውነት ፡ ምሳ ፡ የሚያባላ ፡ አጥተው ነው ፡ እስካሁን ፡ እኔን ፡ ደጅ ፡ ሲጠኑ ፡ የቆዩ ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ የመገረምም ፡ የመጠርጠርም ፡ ምልክት ፡ እፊቱ ፡ ላይ ፡ እየታዩ ።

"ሙት ፡ እውነቴ ፡ ነው ! ማን ፡ አለኝ ? ያችው ፡ እንቆቅ ፡ ናት ፡ እስዋም - - - በል ፡ እንሂድ ፡ እባክህ ! ዛሬ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ እየተጫወትሁ ፡ መብላት ፡ አምሮኛል ! አሁንም ፡ ዛሬ ፡ ከነ ዉሬ ፡ ጋር ፡ ትብላ ?"

እንቆጳ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ትምርቱን ፡ ጨርሶ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ እሰዋም ፡ ገና ፡ ልጅ ፡ ሳለች ፡ እግር ፡ አጣዚ ፡ እንድትሆነው ፡ እናቱ ፡ የሸለሙት ፡ አገልጋይ ፡ ናት ። የጥንት ፡ ስምዋ ፡ አፈረ ፡ ጠላቱ ፡ ነበር ።

አፈረ ፡ ጠላቱ ፡ ከፍጥረትዋ ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ ከመሆንዋም ፡ ሌላ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ትምርቱን ፡ ሲጨርስ ፡ ሽልማት ፡ ሆና ፡ ከተሰጠች ፡ በሁዋላ ፡ እሱ ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ያዛትና ፡ ስለ ፡ ተመቻት ፡ ከጥቁረትዋ ፡ በቀር ፡ በቁጥር ፡ መልከኛ ፡ በደም ፡ ግባት ፡ ውብ ፡ ናቸው ፡ ከሚባሉት ፡ ሴቶች ፡ የምትወዳደር ፡ ሆነች ። ወዲያው ፡ የጉዱ ፡ ካሳ ፡ እናትና ፡ ዘመዶቹ ፡ ምሽት ፡ ሊያጋቡት ፡ ከባላባት ፡ ባላባት ፡ ሲያማርጡ ፡ እሱ ፡ አፈረ ፡ ጠላቱን ፡ "እንቆጳዝዮን" ብሎ ፡ ሰይሞ ፡ አገባና ፡ እናቱንም ፡ ዘመዶቹንም ፡ አሳፈራቸው ።

"ማናቸውሳ ፡ እንቆጳ ?" አለ ፡ በዛብህ ።

"እንቆጳዝዮንን ፡ አታውቃትም ? ባለቤቴ ፡ ናት ! እንዲያውም ፡ መልካም ፡ አጋጣሚ ፡ ነው ፡ ትተዋወቃላችሁ !"

"እንቆጳዝዮን ! ጥሩ ፡ ስም ፡ ነው ፡ የካህን ፡ ልጅ ፡ መሆን ፡ አለባቸው !"

"ስምዋ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ እሰዋም ፡ ጥሩ ፡ ናት !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በላባትዋ ፡ ካህንነት ፡ በዛብህ ፡ ያለውን ፡ እንዳልሰማ ፡ ቾል ፡ ብሎ ።

እጉዱ ፡ ካሳ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ "እንቆጳን ፡ ቶሎ ፡ ጥራት ፡ እዝራ !" አለ ፡ እበር ፡ ቆሞ ፡ ይጠብቅ ፡ የነበረውን ፡ አገልጋይ ።

"ወዲያው ፡ ጥልፍ ፡ ቀሚስና ፡ ቀጭን ፡ ኩታ ፡ የለበሰ ፡ የግር ፡ አልቦውና ፡ ደረጁ ፡ እስኪታይ ፡ ቀሚሱን ፡ አጠር ፡ አድርጎ ፡ የታጠቀ ፡ ከላይ ፡ ወገን ፡ ቀሚሱ ፡ ከጠለቀበትና ፡ ኩታው ፡ ከተጣፋበት ፡ ስንዝር ፡ ያክል ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ መያዣቸው ፡ የማይታይ ፡ ሁለት ፡ የወርቅ ፡ ጉትቻዎች ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ፈንጠር ፡ ብለው ፡ ተቀምጠው ፡ የሚያበሩበት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ከወደ ፡ ጉዋዳ ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ በዛብህ ፡ ደነገጠ ።

" አይውልሽ ፡ እንቆጳ ፡ የቆዩ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያያል !

ከመቆዩት ፡ የተነሳ ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ ሰዎች ፡ እንግዳ ፡ ሠፈ ፡ ቤቴ ፡ ይገፎ ፡ ለመምጣት ፡ በቃሁ ! በዛብህ ፡ የሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አስተማሪ ፡ ነው ፡ ተዋወቁ ።" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ።

" ጤና ፡ ይስጥልኝ ! " አለች ፡ እንቆጳ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ። የከንፈርዋ ፡ ማእዝን ፡ የወተት ፡ አረፋ ፡ የመሰለ ፡ ጥርስዋን ፡ ገልጦ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ሲሸሽና ፡ ጥቃቅን ፡ ውብ ፡ አይኖችዋ ፡ ከሁለቱ ፡ ጉትቻዎች ፡ ገባ ፡ ብለው ፡ በጨለማ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ አልማዞች ፡ ሲያበሩ ፡ እዚያ ፡ ግድም ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ መኖሩን ፡ ከመገመት ፡ በቀር ፡ አጣርቶ ፡ ለማየት ፡ የሚያስቸግር ፡ ነበር ።

' ጤና ፡ ይስጥልኝ ! " አለ ፡ በዛብህም ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሶና ፡ አጊጦ ፡ እፊቱ ፡ለቆመው ፡ ጥላ ፡ ትንሽ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ መንሳት ፡ ብሎ ፡- ምንም ፡ እንኳ ፡ በቂ ፡ ብርሀን ፡ በሌለበት ፡ ቤት ፡ ከውጭ ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ እንቆጳ ፡ ያለ ፡ ጥቁር ፡ ሰው ፡ ለማየት ፡ ችግር ፡ ስለሆነ ፡ የንቆጳን ፡ ድምጽ ፡ ከመስማት ፡ በቀር ፡ ፊትዋን ፡ አጣርቶ ፡ ለማየት ፡ ባይችል ።

" በይ ፡ እንግዲህ ፡ የምንጠጣው ፡ ላኪልንና ፡ ወዲያው ፡ ምሳችንን ፡ ለበዛብህና ፡ ለኔ ፡ እዚህ ፡ አስመጭልን ፡ አንቺ ፡ ከነዝራ ፡ ጋር ፡ የዛሬን ፡ ብትፈልጉ ፡ አዳራሽ ፡ ያለዚያም - - - እማድቤታችሁ ፡ ብሉ ።" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ትንሽ ፡ ሳቅ ፡ ብሎ ፡ "እሺ ! " አለችና ፡ እንቆጳ ፡ በጉዋዳዋ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ መጣችበት ፡ ተመልሳ ፡ ሄደች ።

ወዲያው ፡ ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡ እዝራ ፡ ሁለት ፡ ብርሌዎችና ፡ በማንቆርቆሪያ ፡ ጠጅ ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ ለበዛብህና ፡ ለጌታው ፡ እዩቀዳ ፡ ሲሰጥ ፡ "ከእዝራ ፡ ጋር ፡ መቼም ፡ ሳትተዋወቁ ፡ አትቀሩ ! " አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በዛብህን ፡ እያዩ ።

" እንጃ ፡ የምንተዋወቅ ፡ አይመስለኝም ! " አለ ፡ በዛብህም ፡ በበኩሉ ፡ እዝራን ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ አዩና ።

" አትተዋወቁም ? ተዋወቁ ፡ እንጂ ! እዝራ ፡ መበንቆ ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ስለሚያውቅ ፡ አሁን ፡ የወጣለት ፡ ስም ፡ ነው ፤ የድሮ ፡ ስሙ ፡ ፈረጃ ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ እሱ ፡ የድሮ ፡ ስሙን ፡

ስለሚወዱ ፡ እገሬ ፡ ስንለው ፡ እቤት ፡ አይለንም ፡ ብቻ ፡ ያም ፡ ሆኖ ፡ የምንጠይቀውን ፡ ያደርግልናል !” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እገሬን ፡ በቀልድ ፡ አይን ፡ እየተመለከተ ።

“ እገሬን ፡ አይወድም ? እገሬ ፡ ጥሩ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ለምን፡ ጠላኸው ? ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ወደ ፡ እገሬ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ።

“ ተወልጄ ፡ እስካረጅ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቀኝ ፡ በፈረሼ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ታዲያ ፡ አሁን ፡ ተመሽ ፡ ወዲያ ፡ ተነስቼ ፡ እገሬ ፡ ነኝ ፡ ብል ፡ ሰው ፡ እሺ ፡ ይላል ? እገሬ ፡ በሉኝ ፡ ስል ፡- ‘ስምህን ፡ ብትለውጥ ፡ አንተ ፡ የምትለወጥ ፡ መሰለሁህል !’ እያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ መሳቂያ ፡ አያረገኝ ፡ ስለዚህ - - - ሰው ፡ ከሚስቅብኝ ፡ የድሮ ፡ ስሜ ፡ ምን ፡ አለኝ ? ” አለና ፡ እገሬ ፡ ማንቋርቋሪያውን ፡ እፊታቸው ፡ አስቀምጦላቸው ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ።

እሱ ፡ ከመውጣቱ ፡ እንቆጳ ፡ የባልዋንና ፡ የበዛብህን ፡ ምሳ ፡ በመሶብ ፡ አስቢቃ ፡ ወጡ ፡ በየዶነቱ ፡ ወጥቶ ፡ አስይዛ ፡ መጣች ። ከዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ወንዶች ፡ እጃቸውን ፡ ታጥበው ፡ ለመብል ፡ ሲሰለፉ ፡ ከዱጠጡ ፡ በትንሽ ፡ ቀማመስኝና ፡-“በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ብሉ ፡ እንመጣባችሁም ! ” አለች ፡ የደስደስ ፡ ባስ ጌጠው ፡ ፈገግታ ፡ በጥቃቅን ፡ ውብ ፡ አይኖችዋ ፡ ከባልዋ ፡ በዛብህን ፡ ከበዛብህ ፡ እንደገና ፡ ባልዋን ፡ ገረፍ ፡ አድርጋ ።

“ እውነትም ፡ ጥሩ ፡ ደማም ፡ ናት ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ባሳቡ ። እቤት ፡ በመቆዬቱ ፡ ዙሪያገባው ፡ ብርሀን ፡ ስለሆነለት ፡ መልኩዋን ፡ ልቅም ፡ አድርጎ ፡ ለማየት ፡ ቻለና ፡ አሳቡን ፡ ለወጠ ። “ከጥቁረትዋ ፡ ትንሽ ፡ ቀነስ ፡ ቢያደርጋላት ፡ ኖሮ ፡ እውነትም ፡ ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ! ” አለ ፡ አሁንም ፡ ባሳቡ ፡ የፈገግታ ፡ ምልክት ፡ በፊቱ ፡ እየታዬ ።

“ እንቆጳ ፡ ከወጣች ፡ በሁዋላ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ሲበሉ ፡ ቆዩና ፡- ልጆች ፡ ወልዳችሁዋል ? ” አለ ፡ በዛብህ ።

“ ሁለት ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ወልደን ፡ አንዱ ፡ ባመቱ ፡ ሁለተኛው ፡ በመንፈቁ ፡ ሞቱ ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ይሄው ፡ አራት ፡ አመት ፡ ነው ? ወይስ ፡ አምስት ፡ ሆነን ፡ አልወለድንም ። ”

“ አይይ - - - ምን ፡ ነደላቸው ? ”

" እእ - - ምን ፡ ይታወቃል ? እንቆቅ ፡ የኔን ፡ ዘመዶች ፡ ትጠረጥራለች ! "

"የስምን ፡ ዘመዶች ? እንዴት ?"

"በጥሳ ፡ ወጊ ፡ አስገደሉዋቸው ፡ ብላ !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እዬሳቀ ።

"ኧረ ! እንዴት ! ታዲያ ፡ እስዎ ፡ ያምናሉ ?"

" ማመኑም ፡ አለማመኑም ፡ ችግር ፡ ነው ! "

"እንዴትስ ! ዘመዶችዎን ፡ በንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ይጠረጥሩዋቸዋል ? "

" እዬሀ ? ዘመዶቼ ፡ እስዋን ፡ በማግባቴ ፡ ዘር ፡ አበላሸህ ፡ ብለው ፡ እጅግ ፡ የተቆጡና ፡ የተቀረቀሩ ፡ ስለሆኑ ፡ እቤቴ ፡ አይመጡም ፡ እንጂ ፡ እቤቴ ፡ የሚመጡ ፡ ቢሆኑ ፡ ልጆችንም ፡ እስዋንም ፡ ከመግደል ፡ እንዳይመለሱ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ እዚህ ፡ ሳይመጡ ፡ ወይም ፡ ልጆቹ ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሳይሄዱ ፡ ምን ፡ መንገድ ፡ አግኝተው ፡ እንደ ፡ ገደሉዋቸው ፡ ማመኑ ፡ ቀርቶ ፡ መጠርጠሩ ፡ ያስቸግረኛል ። ስለዚህ ፡ ማመኑም ፡ አለማመኑም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ፡ ያልሁህ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።"

በዛብህ ፡ ነገሩ ፡ ገርሞት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆዬና፡- " እሺ ! ግንም ፡ ቢሆን ፡ ወገኑ ፡ ያከለኛል ፡ ይመስለኛል፡- ከማይለው ፡ ጋር ፡ ሲጋባ ፡ ለጊዜው ፡ ማዘኑና ፡ መቆርቆሩ ፡ አይቀርም ፡ ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ እልፎ ፡ ነፍስ ፡ እስከ ፡ ማጥፋት ፡ ድረስ ፡ የሚያደርስ ፡ ነገር ፡ አለ ? ይልቁንም ፡ እንደስዎ ፡ ያለ ፡ የተማረና ፡ ሌሎችን ፡ ለማስተማር ፡ የሚችል ሊቅ ፡ የመረጣትን ፡ አግብቶ ፡ የፈለገውን ፡ አይነት ፡ ኑሮ ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ የራሱ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ! ዘመድ ፡ ምን ፡ ቸግሮት ፡ ነፍስ ፡ እማጥፋት ፡ ድረስ ፡ ይሄዳል ?

" እሀሀሀ . . .እይ ፡ በዛብህ ! ለካ ፡ ለምትኖርበት ፡ አለም ፡ ገና ፡ እንግዳ ፡ ነህና ! ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያምነው ፡ ካላመንህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚሄድበትን ፡ መንገድ ፡ ተከትለህ ፡ ካልሄድህ፡- ሁሉም ፡ ጉዳዩ ፡ አድርጎ ፡ ይይዘዋል ፡ እንጂ ፡ ማን ፡ የራሱ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይተውሀል ?"

“ እንዴት ?”

“ እዩሀ ፡ በረዥም ፡ ጊዜ ፡ ልማድ ፡ የታመኑ ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ተለጎመች ፡ በቅሎ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ሳያይ ፡ በተመራበት ፡ ብቻ ፡ እንዲሄድ ፡ የሚያደርጉት ፡ ብዙ ፡ እምነቶች ፡ አሉ ። እነዚህ ፡ የልማድ ፡ እምነቶች—ሀዋርያቸው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ እግዚአብሄር ፡ ይወቀው—ሰውን ፡ የጌታ ፡ ዘር ፡ የድሀ ፡ ዘር ፡ የጀሰሪ ፡ ዘር ፡ የባሪያ ፡ ዘር ፡ በሚባል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የዘር ፡ ክፍል፡ ከፍለውታል ። ይህ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እነዚህ ፡ ዘሮች ፡ ምን ፡ ማድ ረግ ፡ እንደሚገባቸው ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደማይገባቸው ፡ እንዴት ፡ እንዲኖሩ ፡ ማን ፡ ከማን ፡ እንደሚጋባ ፡ ማን ፡ ማንን፡ እንዲያከብር ፡ ማን ፡ ማንን ፡ እንዲንቅ ፡ ሳይቀር ፡ በነዚህ ፡ የል ማድ ፡ እምነቶች ፡ ተደንግጎዋል ። ባሪያው ፡ እንዲሸጥ ፡ እንዲ ለወጥ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ እንዲሰራ ፡ እንዲናቅ ፡ እንዲጎሳቆል ፡ ድሀው ፡ በጌታ ፡ እንዲገዛ ፡ እንዲረገጥ ፡ ተመድቦዋል ። ከጌታ ፡ አለቀኑ ፡ የሚ ወርድ ፡ ውራጅ ፡ እሰዎ ፡ እዩተባለ ፡ እንዲወርድ ፡ የድሀ ፡ ሽማ ግሌ ፡ አንተ ፡ እዩተባለ ፡ እንዲሞት ፡ ተደንግጎዋል ። ከንቱ ፡ እ ሰቦ ፡ ከንቱ ፡ የሚናገር ፡ ዘመናይ ፡ ተብሎ ፡ እዩተደነቀ ፡ ገዥ ፡ እንዲሆን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሚሰራ ፡ የተናቀ ፡ ሆኖ ፡ ተገዥ ፡ እንዲሆን ፡ ተመድቦዋል ። ይገርምሀል ! ይሀን፡ የማ ያረጀ ፡ ልማድ ፡ ያዘን ፡ በግፍ ፡ ላይ ፡ የተመሰረተ ፡ ነገሩ ፡ ልማድ ፡ ተመልከተሀ ፡ እንዲሀ ፡ ያለ ፡ ስራት ፡ ሊኖር ፡ የሚገ ባውም ፡ የሚችልም ፡ አይደለምና ፡ ይልቅ ፡ አወዳደቁ ፡ እንዳ ይከፋ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ እንዲለወጥ ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ፡ ብለሀ ፡ የተናገርሀ ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡ ከሀዲ ፡ ተቆጥረሀ ፡ የምትሰቀል በት ፡ ገመድ ፡ ይሰናዳልሀል ! ዝም ፡ ብለሀ ፡ እያዘንሀ ፡ ተመል ልካች ፡ የሆንሀ ፡ እንደሆንም፡— እንዲሀ ፡ እንደኔ ፡ እብድ ፡ ጉድ ፡ እያሉ ፡ በሳምሀን ፡ አሳጥተው ፡ ከማሀበር ፡ አስወጥ ተው ፡ በዘመድ ፡ መሀከል ፡ ባዳ ፡ ተወልደሀ ፡ ባደግሀበት ፡ አገር ፡ እንግዳ ፡ ሆነሀ ፡ እንድትኖር ፡ ያደርጉሀል ። ደግሞኮ ፡ ይሀን ፡ ሁሉ ፡ የሚያደርጉብሀ ፡ የጌታ ፡ ዘር ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ ሁሉንም ፡ ረግጠው ፡ አላይ ፡ የተቀመጡት ፡ ብቻ ፡ ቢሆኑ ፡ ጥቅማቸው ፡ እንዳይጎድልባቸው ፡ ነው ፡ ትላለህ !ነገር ፡ ግን ፡

ባሮቹ ፡ እጀሰራዎቹ ፡ ድሆቹ ፡ ሁሉ ፡ ግፍ ፡ የሚሰራባቸው ፡ ሁሉ ፡ ከግፍ ፡ ሰራዎች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተባብረው ፡ ሲፈርዱብህ ፡ ምን ፡ ትላለህ ? ‘ ከልማድ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ እውነት ፡ ሁልጊዜ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡’ የሚባለውን ፡ የማይረባ ፡ ቁረት ፡ አስብህ ፡ ገዛም ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ነው !እየውልዘ ! በጠቅላላው ፡ የዚህ ፡ ልማድ ፡ እስረኞች ፡ ነን ።

እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ጠቅላላ ፡ ልማድ ፡ ተነስተን ፡ እገር ገዛር ፡ ውስጥ ፡ ስንገባ ፡ በኔና ፡ በንቀጸ ፡ መሀከል ፡ ሊኖር ፡ የሚገባው ፡ ግንኙነት ፡ ያገልጋይና ፡ የተገልጋይ ፡ ግንኙነት ፡ ካል ሆን ፡ ከዚያ ፡ አልፎ ፡ የባልና ፡ የምሽትነት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እሰዋን ፡ አቅሞዋን ፡ የማታውቅ ፡ ብለው ፡ ያሽሙዋጥጡዋታል ፡ እኔን ፡ ወራዳ ፡ ብለው ፡ ይንቁኛል ፡ የወለድናቸውን ፡ ልጆች ፡ ይጠሉዋቸዋል ፡ የጠላም ፡ እንደሚገድል ፡ ታውቃለህ !” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ፡ አይኑን ፡ እበዛብህ ፡ ላይ ፡ ተከለና ። በዛብህም ፡ ትንሽ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ አዩና ፡ የቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ አለ ።

“ እንዲሁም ። ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አይኑን ፡ ከበዛብህ ፡ ላይ ፡ አንስቶ ፡ በር ፡ በሩን ፡ እዩተመለከተ ። “ እንዲሁም ፡ አንድ ፡ የድሀ ፡ ልጅና ፡ አንዲት ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ ቢዋደዱና ፡ ሊጋቡ ፡ ቢፈልጉ ፥ የድሀው ፡ ልጅ ፡ ያላቅሙ ፡ ተንጠራራ ፡ ብለው ፡ ያሽሙዋጥጡኛል ፡ ብሎ ፡ ይሰጋል ። የጌታዋ ፡ ልጅም፡ በበኩልዋ ፡ ማእርግዋን ፡ አልጠበቀችም ፡ እባላለሁ ፡ ብላ ፡ ትፈራለች ። ለወዳጅዋ ፡ ያላት ፡ ፍቅር ፡ ይሉኝታዋን ፡ የሚያያሸንፍ ፡ ቢሆን ፡ እንኩዋ ፡ ወላጆችዋ ፡ ስለማይፈቅዱላት ፡ አዝና ፡ አልቅሳ ፡ እንጀትዋ ፡ ተቆርጦ ፡ የምትወደውን ፡ ሳታገባ ፡ ትቀራለች !” አለና ፡ ቦዘዝ ፡ ብሎ ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ የነበረውን ፡ አይኑን ፡ መልሶ ፡ እበዛብህ ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ ፍጥጥ ፡ አድርጎ ፡ ያየው ፡ ጀመር ።

በዛብህ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በመጨረሻ ፡ የተናገረው ፡ ስለሱና ፡ ስለ ፡ ሰብለ ፡ መሆኑን ፡ ጠርጥሮ ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡ መሸበር ፡ አለና፡ አንገቱን ፡ እንደ ፡ ደፋ ፡ እጁን ፡ በንጀራ ፡ ይጠራርግ ፡ ጀመር።

“ ታዲያስ ፡ እውነት ፡ አይደለም !” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም

እጁን ፡ በንጀራ ፡ እዬጠራረገ ።

"ምኑ ?" አለ ፡ በዛብህ ፤ ቀና ፡ ብሎ ። ከመደንገጡ ፡ የተነሳ፡ እግንባሩ ፡ ላይ ፡ ላብ ፡ ይታይበት ፡ ነበር ።

" እሁን ፡ ያልሁት ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ አይደለም ?"

" ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ይሆናል !"

"አንተና ፡ ሰብለም ፡ ያላችሁበት ፡ ሁኔታ ፡ ይሀን ፡ የመ ሰለ ፡ ነው ! "

" ሞ ሞ--ምንድነው ፡ እኔና ፡ ሰብለ ፡ የ--ያለንበት ?" አለ በዛብህ ፡ ብርቱ ፡ ብርድ ፡ አንጀቱ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ እዬተን ቀጠቀጠ ።

" እዬህ ? በዛብህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ባልገባችሁ ፡ መልካም ፡ ነበር ። ከገባችሁ ፡ በሁ ዋላ ፡ ግን ፡ መውጫ ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እማጥ ፡ ውስጥ ፡ ገብታችሁ ፡ ቆማችሁ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እያዬ ፡ እናንተ ፡ ሰው ፡ አያየንም ፡ መስሎዋችሁ ፡ እማጥ ፡ ውስጥ ፡ አይደለንም ፡ ብትሉ ፡ ከጉዳት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ --- ጥቅም ፡ የለውም ። ይልቅ እንመካከርና ፡ መንገድ ፡ እንፈልግለት ።"

በዛብህ ፡ አንገቱን ፡ደፍቶ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆዬና ፡ በውነቱ ትንሽ ፡ ጸጥ ፡ ሲል ፡ " ለመሆኑ ፡ እንዴት ፡ አወቁት ?" አለ ።

"ብዙ ፡ ሰው ፡ ያውቃል ፡ የሚወራውማ ፡ እንዲያውም ፡ ሌላ ፡ ነው !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፤ ባዘን ፡ በተሰበረ ፡ ድምጽ ፡ አንገ ቱን ፡ በፈንታጡ ፡ ደፋ ፡ አድርጎ ።

"ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ይወራል ? "

" አርግዛለች ፡ እዬተባለ -- ይወራል ፡ እውነት ነው ?"

" ሰብለ ? አርግዛ ---ለች ? ከ---ከማን ?"

" እስረኛ ፡ አይደለች ? ካንተ ፡ በቀር ፡ ማን ፡ አጠገብዋ ፡ ደርሶ ፡ ያውቃል !"

" እኔ ? በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ! ሰብ ለን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ መድፈር ? በስመ ፡ አብ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ! በዚህስ ፡ በጭራሽ ፡ አይጠረጥሩኝ ፤ መዋደ ዳችን ፡ እውነ---ት ፡ ነው ።"

" መዋደዳችሁ ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ እንኪዋን ፡ የናንተ ፡ የል

ጀች ፡ የትልልቅ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ፍቅርም ፡ ወሰን ፡ አያውቅ ! እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ልመንህ ?" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ፊቱ ፡ ባዘን ፡ እንደ ፡ ጨለመ ።

"እንዴት ፡ አባቴ ፡ አድርጌ ፡ ብነግርዎ ፡ ያምኑኛል ? አዩ ? እኔ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ገና ፡ ድንግል ፡ ነኝ ። የሴት ፡ እጅ ፡ እስከ ፡ መጨበጡ ፡ እንኳዋ ፡ ሰብለ ፡ የመጀመሪያየ ፡ ናት ። ስለ ዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ እሰዋን ፡ ሳይ ፡ ወይም ፡ ብቻየን ፡ ተቀ ምጬ ፡ ሳስባት ፡ ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሻማ ፡ እየተቃጠለ ፡ ቢፈስ ፡ ልማድ ፡ ስለሌለኝ ፡ ፍራትም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ስለማ ከብራት ፡ ምክንያቱን ፡ በትክክል ፡ አላውቅም ፡ ብቻ ፡ ከመሳሳም፡ አላለፍንም ። ይህ ፡ የውነተኛ ፡ ኑዛዜ ፡ ነው ። ቢፈልጉ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሄር ፡ ጠርቼ ፡ ልማልልዎ !"

"የለም ፡ መሀላ ፡ አያስፈልግም ፡ አልደረስሁባትም ፡ ካልህ፡ ይሄው ፡ ብቻ ፡ ይበቃል ። እንግዲህ ፡ ነፍሰጡር ፡ ሆናለች ፡ እየተባለ ፡ የሚወራው ፡ ውሸት ፡ ነዋ !"

"በጭራሽ ፡ ውሸት ፡ ነው ።"

"እሁሁ --- ተመስገን ፡ ተመስገን ! እሱ ፡ ነበር ፡ እንደ ፡ መርግ ፡ የተጫነኝ ፡ እንጂ ፡ የቀረውስ :-- ምንም ፡ አይደል ፡ ግዴ ለም !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

ከዚያ ፡ ሁለቱም ፡ እንባ ቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ብለው ቆዩና :-

"ለመሆኑ ፡ እያቱን ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ የለም ፡ እንዴት፡ ታወቀ ? ማን ፡ ተናገረ ?"

"አይቶዋችሁ ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ከሌለ ፡ ከናንተ ፡ ይሆ ናል ፡ የታወቀው !"

"እኛ ? በጭራሽ ፡ አልተነፈስንም !"

"አይ ፡ በሃብሀ ! የሚዋደዱ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አፋቸው ፡ ባይናገር ፡ ፊታቸው ፡ አይናቸው ፡ ግንባራቸው ፡ እንዲያው ፡ በጠ ቅላላው ፡ ሁኔታቸውና ፡ እስተያየታቸው ፡ ሁሉ ፡ ይናገራል ! ይህ ሁሉ ፡ ተናጋሪ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አሳባቂ ፡ ነው !"

"እንጃ ፡ እንግዴህ ፡ ቢሆን ፡ ነዋ ! ቢሆን ፡ ነው !"

"ለመሆኑስ ፡ ለወደፊቱ ፡ ያሰባችሁት ፡ ነገር ፡ አለ ?" አለ

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ቆዩ ።

"ምንም ፡ አላሰብንም !"

"አባትዋ ፡ የመጡ ፡ እንደሆነ ፡ በሰዋም ፡ ባንተም ፡ ምን ፡ እንደሚደርስባችሁ --- አላሰባችሁም ?"

"ይሄም ፡ ኖሮዋል ! ጭራሽ ፡ አላሰብነውም !" አለ ፡ በዛብህ ፡ አንገቱን ፡ እንደ ፡ ደፋ ፡ ትንሽ ፡ ሲያስብ ፡ ቆይቶ ፡ ወደ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አይኑን ፡ ቀና ፡ አደረገና ። ፊቱ ፡ ፈገግ ፡ ይለ ፡ ቢመስልም ፡ አይኖቹ ፡ እንባ ፡ ሞልተው ፡ ነበር ።

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የበዛብህን ፡ ሁኔታ ፡ ሲያይ ፡ እሱም ፡ አዘኑና ፡ እንባ ፡ መጣበት ።

"ያዘሁት ፡ ጥፋ !" አለ ፡ ትንሽ ፡ በዛብህን ፡ እዬተመለከተ ፡ ሲያስብ ፡ ቆይቶ ።

"ወዴት ፡ ይዣት ፡ እጠፋለሁ ?"

"አዲስ ፡ አበባ ፡ ይዘሃት ፡ ሂድ ።"

"እንዴት ፡ አድርጌ ፡ አደርሳታለሁ ? እንዴትስ ፡ አድርጌ ፡ አኖራታለሁ ?" ሲል ፡ በተሰበረ ፡ ድምጽ ፡ እንባው ፡ ማምራ ፡ ማምራ ፡ እዬሆነ ፡ ይወርድ ፡ ጀመር ።

"ግዴለም ፡ እኔ ፡ ረዳችሁዋለሁ ። ሁለት ፡ በቅሎዎችና ፡ አምስት ፡ስድስት ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ ብሸጥ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር፡ ያክል ፡ አላጣም ። ያን ፡ ይዛችሁ ፡ እኔና ፡ እዝራ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እናደርሳችሁዋለን ። ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አንተ ፡ ስራ ፡ እስክት ይዝ ፡ ያቆያችሁዋል ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ጥሩ ፡ ባለሙያ ፡ ነህ ፤ የመምህርነት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ስራ ፡ አታጣም ። ግዴለህም ፡ ደስ ፡ ብሎዋችሁ ፡ ትኖራላችሁ ፡ መቁረጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚያስፈልገው !"

በዛብህ ፡ የሚጠስነውም ፡ የሚናገረውም ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆዩና ፡ "መቸም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጭራሽ ፡ አስበነውም ፡ አንስተነውም ፡ የማናውቅ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ታዲያ - - - እሰዋ ፡ እሺ ፡ የምትል ፡ ይመስልዎታል ?" አለ ።

"ሰብለ ? ደስታውን ፡ ትችለዋለች ? መቸስ ፡ ምን ፡ ያክል ፡ እንደምትዋደዱ ፡ የምታውቁት ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ፡ ይህን ፡ እኔን ፡ አትጠይቀኝ ! እእ ? ብቻ ፡ ከዚህ ፡ ከምትኖርበት ፡ ወህኒ ፡ ትወ

ጫለሽ ፡ ካሉዋት ፡ የማታደርገው ፡ ነገር ፥ የማትሄድበት ፡ አገር ፥ ይኖራል ፡ ብዬ ፡ አልጠረጥርም ፡፡ እዬሀ ? ይህ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ መባሉ ፡ ብዙ ፡ ያካልና ፡ ያእምሮ ፡ ስቃይ ፡ ስላደረሰባት ፡ በማት ታወቅበት ፡ አገር ፡ ሄዳ ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ሴት ፡ ነጻ ፡ ሆና ፡ መኖ ርን ፡ ልክ ፡ ከቁምጥና ፡ በሽታ ፡ እንደ ፡ መዳን ፡ ነው ፡ የምትቆ ጥረው!"

በዛብህ ፡ የጉዱ ፡ ካሳን ፡ ተስፋ ፡ የሞላበት ፡ ንግግር ፡ ሲሰማ ፡ የሰብሰና ፡ የሉ ፡ ጋብቻ ፡ ቀርቦ ፡ ታዬውና ፥ በጅ ፡ የሚ ጨበጥ ፡ መስሎ ፡ ታዬውና ፡ ልቡ ፡ በደስታ ፡ ሲሞቅ ፡ ጸዳሉ ፡ በፊቱ ፡ ታዬ ፡፡

"እሺ ፡ እስቲ ፡ ሳነጋግራት ! ማወቅዎን ፡ ታውቅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስዎም ፡ ያነጋግሩዋት !"

"ማወቄንስ ፡ አውቃለች ፡፡ ጥዋት ፡ በሰፊው ፡ አነጋግራታ ለሁ ፡ ብዬ ፡ ስጀምር ፡ ደንግጣ ፡ ገና ፡ መልስ ፡ ሳትሰጠኝ ፡ አንተ ፡ መጣህ ፡፡ በዚህ ፡ ምክናያት ፡ ነው ፡ እንዲያ ፡ ተለዋውጣ፡ የታመመች ፡ መስላ ፡ ያገኘሀት ፡ እንጂ ፡ አልታመመችም ፡፡ ስለዚህ ፡ በሰፊው ፡ አነጋግራታለሁ ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሳስ ጠንቅቃችሁ !"

"ምን?"

"ቶሎ ፡ መቁረጥና ፡ መሄድ ፡ አለባችሁ ! ያለዚያ ፡ በመሀ ከሉ ፡ አባትዋ ፡ የመጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፥ ሁሉም ፡ ተበላሸ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ሲሆን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ ነበረ ፤ ብቻ ፡ ያለ ፈው ፡ መቸም ፡ አልፎዋልና ፡ ባይሆን ፡ ከንግዲህ ፡ ጊዜ ፡ አይጥፋ!"

"እሺ ፡፡" አለ ፡ በዛብህ ፡፡ ከዚያ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ሲያ ስብ ፡ ቆዬና ፡ "ምስጢርን ፡ የሚያወጣ ፡ አፍ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ያሉት ፡ እውነት ፡ መሆን ፡ አለበት! ይህን ፡ ነገር ፡ እስዎም ፡ ሆነች ፡ እኔ ፡ ለማንም ፡ እንዳልተናገርንና ፡ ማንም ፡ እንዳላዬን ፡ እያወቅሁ ፡ ወጥቶ ፡ መገኘቱ ፡ የሚያስገርም ፡ ነው!" አለ ፡፡

"እሁን ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብለን ፡ እንወጣ ፡ ይሆናል ፤ ሰወ ደፊቱ ፡ ግን ፡ ምስጢሬ ፡ አይታወቅብኝም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ዶሮ ፡ ጫጭት ፡ አፍና ፡ ከመቀመጥ ፡ ድንገት ፡ ቢታወቅስ ፡ ብሎ ፡ መውጫ ፡ መንገድ ፡ ማለናዳት ፡ የሚያስፈልግ ፡ ለመሆኑ ፡ ይህ ፡

ትምርት ፡ ይሁናችሁ ።" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

"አለቃ ! ለጠቃሚ ፡ ምክርዎም ፡ ለርዳታዎም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ! እንጃ - - -እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ባመስግንዎ ፡ የልቤ ፡ እንደሚደርስ ፡ አላውቅም ! ሌላማ ፡ መቸስ ፡ ምን ፡ አደርግልዎታለሁ !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ለማመስገን ፡ የሚያውቀው ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ የማይበቃ ፡ መስሎ ፡ ስለ ፡ ታዬው ።

"ገና ፡ ምንም ፡ ሳላደርግ ፡ አታመስግነኝ ፤ ባደርግም ፡ ለራሴ ፡ ብዬ ፡ የማደርገው ፡ ስለሆነ ፡ ምስጋና ፡ አይገባኝም ። ሰብለ ፡ ራሴ ፡ ናት ! የሚሆን ፡ ከሆነ ፡ የድሜ ፡ ሙሉ ፡ ደስታየን ፡ ላንድ ፡ ቀን ፡ ደስታዋ ፡ ለመለወጥ ፡ አልመለስም ። ይህ ፡ ርግጥ ፡ ነው !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከስሜት ፡ ጋር ።

"ለመሆኑ ፡ እመይቴሳ ፡ የስሙ ፡ ይመስልዎታል ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ ሁለቱም ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በዬበኩላቸው ፡ ሲያስቡ ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ።

"እንጃ ! አይመስለኝም ። ጆሮ ፡ የባለቤቱን ፡ ጉድ ፡ አይሰማም ፡ ይባላልኮ !"

"የስዎ ፡ እንዴት ፡ ሰማ ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ ሳቅ ፡ ብሎ ።

"እኔማ ፡ ከዘመድ ፡ ተራ ፡ ስለወጣሁ ፡ እንደ ፡ ባእድ ፡ ተቆጥሬ ፡ ነው ! ለመሆኑ ፡ በትዬ ፡ ጥሩ ፡ ላይ ፡ ከድሮው ፡ የተለወጠ ፡ ሁኔታ ፡ ታያለህ ? ከሰማች ፡ መቸም ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ የጥርጣሬ ፡ መልክ ፡ ወይም ፡ ያልተለመደ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ ይታይባታል ።"

"እንደ ፡ ድሮው — ብዙ ፡ አብረውን ፡ አይቀመጡም ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታስ ፡ አላዬሁባቸውም ።"

"እንግዴህ ፡ ባትሰማ ፡ ነው ። ብትሰማ ፡ እንዲያውም ፡ አትለያችሁም ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከንግዴህ ፡ መጠንቀቅ ፡ ነው ።"

# ምዕራፍ፡ ፳፬፡
# በዛብህና፡ ቀለሙ፡

በዛብህ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ተሰናብቶ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ወዳጁ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ። ግራ ፡ ጌታ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ አቤቱ ፡ ጥግ ፡ ተቀምጦ ፡ ታምረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ይጽፍ ፡ ነበር ።

" ይህን ፡ ነገር ፡ አልጨረስህም ? አባክህ ! " አለ ፡ በዛብህ ፡ ባርጩማ ፡ ጎተት ፡ አድርጎ ፡ እወዳጁ ፡ አጠገብ ፡ ሲቀመጥ ።

"የጊዮርጊስ ፡ ታምር ፡ እንዲህ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ተጽፎ ፡ የሚያልቅ ፡ ነው ? "

"ሌሎች ፡ የሰሩዋቸውን ፡ ታምራት ፡ ሁሉ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ እዬጨመርህ ፡ ትጽፍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የጊዮርጊስን ፡ ታምር ፡ ለመጻፍ ፡ በጀመርህበት ፡ ጊዜ ፡ አስር ፡ ታምረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጽፈህ ፡ ትጨርስ ፡ ነበር ! "

" እንዳንተ ፡ ፍጡን ፡ ባልሆን ፡ ይሆናል ! " አለ ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ የሽሙጥ ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ።

" በል ፡ እግዚአብሄር ፡ ይስጥልኝ ፡ አሁን ፡ ተነስ ፡ ሲኖዳ ፡ ዮሀንስ ፡ እንሂድ ።" አለ ፡ በዛብህ ።

ሲኖዳ ፡ ዮሀንስ ፡ በግራጌታ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ አማካይነት ፡ በዛብህ ፡ መሪጌትነት ፡ የተቀጠረበት ፡ አገር ፡ ነው ። በዛብህ፡ ሰብለን ፡ ማስተማር ፡ እንደ ፡ ጀመረ ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ መንገዱ ፡ መቆዬቱ ፡ ስለሆነ ፡ ለስንቅና ፡ ለልብስ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ የሚያገኝበትን ፡ ስራ ፡ ሲፈልግ ፡ ግራጌታ ፡ ቀለሙ ፡ ከሲኖዳ ፡ ባላገሮች ፡ ጋር ፡ ተነጋግሮ ፡ ባመት ፡ አስራሁለት ፡ ብርና ፡ ስድስት ፡ ዳውላ ፡ እህል ፡ ሁለት ፡ ዳውላ ፡ በርበሬ ፡ እንዲሰጡት ፡ የመሪጌትነት ፡ ስራ ፡ አስያዘው ። እሁድና ፡ ቅዳሴ ፤ ወይም ፡ ፍታት ፡ ባለበት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ስለነበረ ፡ በዛብህ ፡ ወደ ፡ ሲኖዳ ፡ የሚሄድ ፡ ይህ ፡ የያዘው ፡ ስራ ፡ የራሱን ፡ ትምርትም ፡ ሆነ ፡ ሰብለን ፡ ማስተማሩን ፡ የማ

ያስናከልበት ፡ በመሆኑ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ነበር ።

" ሲኖዳ ? ለምን ፡ ነው ፡ ሲኖዳ ፡ የምንሄድ ? " አለ ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ ብርሉን ፡ አስቀምጦ ፡ በመገረም ፡ አይኑን ፡ ወደ ፡ በዛብህ ፡ መለስ ፡ አደረገና ።

" ደመወዜን ፡ እንዲሰጠኝ ፡ ላገሬው ፡ ትነግርልኛለህ ! እኔ ፡ ብቻዬን ፡ ብሄድ ፡ አይሰጠኝም ፡ ብዬ ፡ ነው ። "

" ስራ ፡ ከጀመርህ ፡ አመት ፡ ሞላህ ? እንዴ ! "

"እሱስ ፡ ገና ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ነው ፤ ብቻ ፡ አሁን ፡ አ ዲስ ፡ አበባ ፡ መሄዴ ፡ ስለ ፡ ሆነ ነው ።"

" አዲስ ፡ አበባ ? ምነው ፡ ምን ፡ መጣ ? መቸ ፡ የታሰበ ፡ ነው ? "

" ዛሬ ። "

" እንዴት ! ዛሬ ፡ አሰበህ ፡ ዛሬ ፡ ቆረጥኸው ? በዛብህ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜኮ ፡ የምትሰራው ፡ ስራ ፡ የልጅ ፡ እያሉት ፡ ያዋቂ ፡ በጣም ፡ የሚያስቸግር ፡ ነው ! "

" የለም ፡ ይሄስ ፡ ድንገት ፡ የደረስ ፡ አደጋ ፡ ነው ። "

" ምን ፡ ድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ደረሰብህ ? " አለ ፡ ግራጌታ ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ ብሎ ።

" አቤት ፡ ሰው ፡ አለ ? " አለ ፡ በዛብህ ፡ በዝቅተኛ ፡ ድምጽ ፡ ገልመጥ ፡ ገልመጥ ፡ ብሎ ፡ የቤቱን ፡ በር ፡ እዩና ።

" ማንም ፡ የለ ፡ ጣይቱም ፡ ወደ ፡ ጎረቤት ፡ ሄዳለች ። "

" እንጃ ፡ ከየት ፡ ጀምሬ ፡ ምን ፡ ብዬ ፡ ልንገርህ ? " አለ ፡ በዛብህ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ግንባሩን ፡ እያሻሸ ። " አዬህ ? ከኖርሁ ፡ ኖሬ --- በማይገባበት ፡ ቤት ፡ ገብቼ ፡ የፍቅር ፡ ወጥመድ ፡ ያዘኝ ፡ አሁን ፡ ቶሎ ፡ ማምለጥ ፡ እፈልጋለሁ ። "

" እስቲ ፡ ረጋ ፡ ብለህ ፡ ንገረኝ ፡ እባክህ ፡ በጣም ፡ አላስ ተዋልሁህም ። መጡደድ ፡ የሸሻል ? ከማን ፡ ነውሳ ፡ ማምለጥ ፡ የምትፈልገው ? "

" ካባትዋ ! አባትዋ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ሳይመጡ ፡ ማምለጥ ፡ እፈልጋለሁ ። እሳቸው ፡ ከመጡ --- በቃ ። "

" አአ --- ! ይሄ ፡ ነው ! ለካ ፡ እውነት ፡ ነው ! "

" ሰምተህ ፡ ኖሮዋል ? "

“ አላመንሁም ፡ እንጂ ፡ ሰምቼ ፡ ነበር ። ”

“ ከሰማህ ፡ ለምን ፡ አልነገርኸኝ ? ”

“ እህህህ --- ለምስጢሩ ፡ ባለቤት ፡ መልሽ ፡ ልንገርህ ? ግዴለም ፡ ለምን ፡ አልነገርኸኝ ፡ እንዳልልህ ፡ ነው ! እሺ ፡ ሁሉም ፡ ይሁንና ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቢመጡ ፡ ምን ፡ ያደርጉሃል ? ያስሩኛል ፡ አትል ፡ ግዛቱ ፡ የሳቸው ፡ አይደለ ! ”

“ እኔንማ ፡ ምን ፡ ያደርጉኛል ! ብቻ ፡ እሳቸው ፡ ከመጡ ፡ እሰዋን ፡ ይዤ ፡ መሄድ ፡ አልችልም ፡ እንጂ ። ”

“ አሁን ፡ እሰዋን ፡ ይዘህ ፡ መሄድ ፡ ነው ፡ የምትፈልገው ? ”

“ አዎ ። ”

“ ይህን ፡ እንጃ ! አልመክርህም ! ”

“ እንዴት ? ”

“ የፊታውራሪ ፡ መሸሻን ፡ ልጅ ፡ ወስደህ ፡ አንተ ፡ ምን ፡ ልትሆን ፡ ነው ? ሎሌ ፡ ልትሆን ፡ ነው ? ወይስ --- ባል ! ”

“ ለምን --- እገባታለሁ ፡ እንጂ ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ።

“ እንደኔና ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ድሀ ፡ የጌታን ፡ ልጅ ፡ ሰርቆ ፡ ወዳጅ ፡ ማድረግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰርቆ ፡ ማግባት ፡ አያሻውም ። ”

“ እንዴት ? ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ? ”

“ አዬህ ? ለጌታ ፡ ልጅ ፡ በስርቆሽ ፡ ወዳጅ ፡ የሆንህ ፡ እንደሆነ ፡ ለሀል ፡ አታስብ ፡ ለወር ፡ ጨው ፡ ወይም ፡ ለስጋ ፡ ለጌሾ ፡ አታስብ ፡ ለማር ፡ ወይም --- ለሌላ ፡- ሁሉም ፡ ከማያልቅ ፡ ከማይደርቅ ፡ ምንጭ ፡ እዬተዘረፈ ፡ ስልጡን ፡ አሽከር ፡ እያሳመረ ፡ እዬሰራ ፡ ሲያቀርብልህ ፡ እያማረጥህ ፡ ትመገባለህ ! የጌታ ፡ ልጅ ፡ በስርቆሽ ፡ ያገባህ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡- እሰዋ ፡ አንተን ፡ በማግባትዋ ፡ ልማድዋን ፡ እንደያዘች ፡ መብትዋን ፡ ታጣና ፡ ለሁሉም ፡ አንተ ፡ አስበህ ፡ አንተ ፡ ሰርተህ ፡ ማብላት ፡ አለብህ ፡ ትንሽ ፡ ከተለመደው ፡ የጎደለ ፡ እንደሆነ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ ምሽትህ ፡ አይንዋ ፡ የሞላ ፡ ቤት ፡ ወዳለው ፡ ማየት ፡ ይጀምራል ! የለም ፡ በዛብህ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ችግር ፡

ውስጥ ፡ እንድትገባ ፡ አልመክርህም ! ”

“ አይሆንም ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ የሚሆን ፡ ቢሆን ፡ ምናልባት ፡ ከታሰርሁበት ፡ ወጥመድ ፡ እፈታ ፡ ይሆናል ፤ ያለዚያ ፡ አሁን ፡ ነገሩን ፡ ስመለከተው ፡ ከሷ ፡ ተለይቼ ፡ መኖር ፡ የምችል ፡ መስሎ ፡ አይታየኝም ! ”

“ ምን ፡ የሆን ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ ከታሰርህበት ፡ ወጥመድ ፡ የምትፈታ ? ”

“በድህነቴ ፡ ምክንያት ፡ የሞላ ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ ስትመለከት ፡ ያዩሁ ፡ እንደሆን ፡ በድህነቴ ፡ ምክንያት ፡ የከዳችኝ ፡ እንደሆነ ፡ ያንጊዜ ፡ እጠላትና ፡ ከፍቅሯ ፡ ነጻ ፡ እሆን ፡ ይሆናል ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ አይኑን ፡ ሳያረግብ ፡ ፊትለፊት ፡ ቦዘዝ ፡ አድርጎ ፡ የሰብለን ፡ ሁኔታ ፡ እያዬ ።

“ ተሳስተሀል ! ”

“ እንዴት ? ”

“ የሚወዱት ፡ ጉዋደኛ ፡ ሲከዳ ፡ ነው ፡ የሚጠላ ፤ የሚወዱዋት ፡ ሴት ፡ ስትከዳ ፡ አይደለም ። የሚወዱዋት ፡ ሴት ፡ ስትከዳ ፡ ታስቀናለች ፡ እንጂ ፡ አትጠላም ! የሚወዱዋት ፡ ሴት ፡ ስትከዳ ፡ ፍቅሯ ፡ በመቀነስ ፡ ፈንታ ፡ ይታጠፍና ፡ ቅናትን ፡ ጨምሮ ፡ ሌላ ፡ ወንጀል ፡ ያሰራል ! ” አለ ፡ ግራጌታ ፡ ክርር ፡ ባለ ፡ ፊትና ፡ ምርር ፡ ባለ ፡ ስሜት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ችግር ፡ በራሱ ፡ ደርሶበት ፡ እንደሚያውቅ ፡ ሁሉ ።

“ እሱ ፡ እውነትህ ፡ ይሆናል ! ብቻ --- ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ጉዋደኛው ፡ የተናገረው ፡ ከፉ ፡ ነገር ፡ ለሰብለ ፡ ካለው ፡ ብርቱ ፡ ፍቅር ፡ ጋር ፡ በራሱ ፡ ውስጥ ፡ ሲሙዋገቱ ፡ እዩበማ ፡ ቅር ፡ ብሎት ፡ አንገቱን ፡ እንደ ፡ መደፋት ፡ አድርጎ ። “ ብቻ --- ” አለ ፡ አሁንም ፡ ደገመና ። “ ሰብለንኮ ፡ በጣም ፡ ባታውቃት ፡ ነው ፡ ቀለሙ ። ”

“ በትጡስ አላውቃትም ፡ ያው ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ ተሸፋፍና ፡ በቀኝ ፡ ዘግራ ፡ ተደግፋ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስትመጣ ፡ ከማየት ፡ በቀር ፡ አላውቃትም ። እርግጥ ! እናውቃታለን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ባህሪዋን ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ሰምቻለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዛብህ ፡ - ባህሪዋ ፡ ይመርም ፡ ይከፋ ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡

ያው ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ ናት ፡ እንኩዋን ፡ መስራት ፡ በግርዋ ፡ መሄድ ፡ አላውቅ ፡ ብላ ፡ ሰው ፡ ደግፎዋት ፡ የምትሄድ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ ናት ፡ እንዳንተ ፡ ላሉ ፡ ደሀ ፡ ምሽት ፡ ልትሆን ፡ ብትወድም ፡ አትችልም ፡ ነው ፡ የምልህ ! ታስተውላለህ ? ”

“ አይ ! መሽፈንና ፡ መያዣ ፡ እንኩዋ ፡ የጌትነት ፡ ምልክት ፡ እንዲያው ቁንጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አይደለም ፤ ጌታ ፡ ሰው ፡ ተደግፎ ፡ የሚሄድ ፡ መሄድ ፡ ስላላወቀ ፡ አይደለም ። አሁን ፡ ነገ ፡ አንተ ፡ ድንገት ፡ ጌታ ፡ ሆነህ ፡ ብትገኝ ፡ አሽቃባጮች ፡ ከግራ ፡ ከቀኝ ፡ መጥተው ፡ እንደ ግፍህ ፡ ይሉሀል ! ታዲያ ፡ መሄድ ፡ ባታውቅ ፡ ነው ?” አለ ፡ በዛብህ ፤ ፊቱን ፡ ቅር ፡ እንዳለው ፡ ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ።

ግራጌታም ፡ ጉዋደኛው ፡ ከተናገረው ፡ ይልቅ ፡ ለራሱ ፡ ድንገት ፡ ትውስ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ አለና ፡- “የለም ፡ በዙ !” አለ ። “ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ እኔ ፡ እንዲሁ ፡ ነገ ፡ ድንገት ፡ ተነስቼ ፡ ጌታ ፡ ሆኜ ፡ አልገኝም ፡ ድንገት ፡ ጌታ ፡ ብሆን ፡ ግን ፡ አንተና ፡ ሌሎች ፡ ወዳጆቼ ፡ ከኔ ፡ ጌትነት ፡ ይልቅ ፡ የናት ፡ ያባቴን ፡ ከዚያም ፡ አልፋችሁ ፡ ያያት ፡ የቅድማያቶቼን ፡ ድሀነት ፡ የምታጋንኑበት ፡ ቃል ፡ ስትፈጥሩ ፡ ትገኛላችሁ ፡ እንጂ ፡ ገራቀኝ ፡ ልትደግፉኝ ፡ አትመጡም ። ”

“ አንተ ፡ ጌታ ፡ ሁንልኝ ፡ እንጂ ፡ ያንተን ፡ ጌትነት ፡ ትቼ ፡ የናት ፡ ያባትህን ፡ ድሀነት ፡ ላላጋንን ፡ ቃል ፡ ልግባ ! ወዲያውም ፡ እናት ፡ አባትህ ፡ ጌቶች ፡ ይሁኑ ፡ ድሆች ፡ አላውቃቸውም ። ” አለ ፡ በዛብህ ፡ እዩሳቀ ።

“ እኔ ፡ ጌታ ፡ የሆንሁለት ፡ ታውቃቸዋለህ ፡ ይህ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ልንገርህ ። ድሀ ፡ ድንገት ፡ ተነስቶ ፡ ጌታ ፡ ሲሆን ፡ ከሚያሽቃብጡለት ፡ የሚያሽሙዋጥጡት ፡ ይበዛሉ ። እዚህ ፡ ጠልማ ፡ ማርያም ፡ የምትባል ፡ አገር ፡ ድሮ ፡ ጉዛም ፡ የነበሩ ፡ በሁዋላ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስጥተው ፡ ፊታውራሪ ፡ የሆኑ ፡ ፊታውራሪ ፡ አንቶነህ ፡ ተስፋዬ ፡ የሚባሉ ፡ ሰው ፡ አሉ ፡ ወሬያቸውን ፡ አንተም ፡ ሰምተህ ፡ ይሆናል ። ” ሲል ፡ በዛብህ ፡ አንገቱን ፡ ነቀነቀ ። “ እየውልህ ፡ እኚህ

ሰውዬ ፡ ፈታውራሪ ፡ እስኪባሉ ፡ ድረስ ፡ የናታቸውን ፡ ትመም ፡ ሽቃጭነት ፡ ሰምቶ ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። እረ ፡ የማታውቃቸውን ፡ ትቼ ፡ የምታውቃቸውን ፡ ልንገርህ ፡ እጹ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ባይነግሡ ፡ የናታቸውን ፡ ኮሶ ፡ ሻጭነት ፡ ታውቅ ፡ ኖሮዋል ? ” ሲል ፡ ሁለቱም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሳቁ ።

“እየውልህ ! መስመሩን ፡ ይዞ ፡ ላልመጣ ፡ ጌትነት ፡ ካሽቃባጩ ፡ ይልቅ ፡ አሽመቀጣጩ ፡ ይበዛል ። እኔም ፡ ነገ ፡ ጌታ ፡ ብሆንና ፡ በግሬ ፡ መሄድ ፡ ቢጠፋኝ ፡ ይስቁብኛል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጌቶች ፡ ልጆች ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ይዘው ፡ ቻቹ ፡ ችግሬ ፡ አይሉኝም ። አለ ፡ እዬሳቀ ።

“ ተው ፡ አባክህ ፡ ቀለመ ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ መቆየም ፡ ብሎ ። “ አዬሀ ? ” አለ ፡ ቀጠለና ። “ አዬሀ ? ሰብለ ፡ ጌትነትን ፡ እንዲሁ ፡ ከዘር ፡ ትውረሰው ፡ እንጂ ፡ አትወደውም ! የጌቶችን ፡ ኑሮ ፡ ስታነሳባት ፡ ኮሶ ፡ በጥብጠህ ፡ እንዳቀረብህላት ፡ ፊትዋን ፡ ሲከፋውና ፡ ስሜትዋን ፡ ሁሉ ፡ ሲመረው ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ይታይሀል ፡ በጣም ፡ ነው ፡ የምትጠላው ! ”

“የያዙት ፡ ወርቅ ፡ ከነሀስ ፡ ይረከሳል ፡ የሚባለውን ፡ ተረት ፡ ታውቅ ፡ የለም ? እንደዚያው ፡ ነው ፡ እስካለችበት ፡ ድረስ ፡ ጌትነቱን ፡ ትጠላው ፡ ይሆናል ፡ ዛሬ ፡ ልጅ ፡ ናት ፡ እንደ ፡ ልብዋ ፡ መሮጥ ፡ መጫወት ፡ የፈለገችውን ፡ ማድረግ ፡ ትፈልጋለች ! ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ እንድትወሰን ፡ ሲያደርጋት ፡ ለጊዜው ፡ ጌትነትን ፡ የምትጠላ ፡ መምሰልዋ ፡ አይቀርም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ፍላጎት ፡ የሚቀነስበት ፡ ጊዜ ፡ አለና ፡ ያ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ አሁን ፡ የጠላችውን ፡ ጌትነት ፡ እንደገና ፡ ትፈልገዋለች ።”

በዛብህ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆዬና ፡ “ ቀለመ ! አንድ ፡ ነገር ፡ ልንገርህ ፡ ” አለ ፡ እፊቱ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ የቅርታ ፡ ምልክት ፡ ከመቅጽበት ፡ ጠፍቶ ፡ ጉዋደኛውን ፡ ፍጥጥ ፡ አድርጎ እዬተመለከተ ። .

“ ምን ? ” አለ ገራጌታ ።

“እኔ ፡ ስለማውቃት ፡ አንተ ፡ ስለማታውቃት ፡ ልጅ ፡

ነው ፡ እስካሁን ፡ ያተነጋገርነው ፡ የመከርኩኽኝም ሁሉ ፡ ወደባሰ ፡ ወጥመድ ፡ እንዳልገባ ፡ ለኔ ፡ እስበዘ ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ ፡ ብቻ ፡ እሰዋን ፡ ካንተ ፡ የበለጠ ፡ ስለማውቀትም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ አእምሮየ ፡ በፍቅር ፡ ታውሮ ፡ የተናገርኽው ፡ ሁሉ ፡ አሳቤን ፡ ትንሽ ፡ እንኳዋ ፡ ከቆመበት ፡ ሊያንቀሳቅሰው ፡ አልቻለም ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ ተውና ፡ ተነስ ፡ ሳይመሽ ፡ እንሂድ ። ”

“ግራ ፡ ጌታ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ገርሞት ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆየና ፡ – “ ስለዚህ ፡ አንተ ፡ ወዳጄ ፡ አሁን ፡ እንዳልኽው ፡ አእምሮህም ፡ አይንህም ፡ ታውሮ ፡ የምትሄድበት ፡ መንገድ ፡ ሜዳ ፡ መስሎህ ፡ ገደል ፡ ልትገባ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ቆመህ ፡ ሳገኝህ ፡ ወደሁዋላ ፡ ጎትቼ ፡ በማዳን ፡ ፈንታ ፡ ለውርንትህ ፡ ተባባሪ ፡ ሆኜ ፡ ገፍቼ ፡ እንድጥልህ ፡ ነው ፡ የምትጠይቀኝ ፡ አይደለም ? ” አለ ።

“ ባላውቅ ፡ ትንሽ ፡ መንገድ ፡ ስጠሁህ ፡ መሰለኝ ! እንደሱ ፡ አይደለም ። ከሜዳ ፡ ኑሮ የገደል ኑሮ ፡ የሚሻለኝ ፡ መሆኑን ፡ አመዛዝኜ ፡ መርጬ ፡ የመረጥሁትን ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ እንድትረዳኝ ፡ ከጠዬቅሁህ ፡ የተጠዬቅኽውን ፡ መፈጸም ፡ የወዳጅነት ፡ ተግባርህ ፡ ነው ፡ ማለቴ ፡ ነው ። ”

“እሺ !” አለ ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ሳይጨምር ፡ ታምሩ ፡ ጊዮርጊስን ፡ እያጠፈና ፡ ብርሉን ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ በጠጉሩ ፡ እዬጠራረገ ። ከዚያ ፡ የቀለም ፡ ቀንዱን ፡ ከከደነና ፡ የጽህፈት ፡ መሳሪያውን ፡ ጠቀላሎ ፡ ካስቀመጠ ፡ በሁዋላ ፡ “ ቆይ ፡ እንግዲህ ፡ ጣይቱን ፡ ጠርቼ ፡ ቤትዋን ፡ እንድትጠብቅና ፡ ፈረስ ፡ እንድትጭንልን ፡ ልንገራት ።” አለ ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ ትንሽ ፡ ፍር ጥም ፡ ብሎ ።

“የምን ፡ ፈረስ ? ከየት ፡ የመጣ ፡ ፈረስ ፡ ነው ፡ ጣይቱ ፡ የምትጭንልን ?”

“ከየት ፡ እንዳመጣችው ፡ እሰዋን ፡ ትጠይቃታለህ ፡ ብቻ ፡ ከዚህ ፡ ጭና ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ አስቀምጣ ፡ የለቀቀችን ፡ እንደሆነ ፡ በቅጽበት ፡ ገና ፡ ከብት ፡ ሳይሰበሰብ ፡ ሲኖዳ ፡ እንደሚያደርሰን ፡ አትጠርጥር ። ”አለና ፡ ግራጌታ ፡ ምሽቱን ፡

ሊጠራ ፡ ሄደ ።

"አንተ ፡ እያ ፡ በዙ ! ለራስህ ፡ ትዳር ፡ አብጅ ፡ ብለን ፡ ብንመክርህ ፡ እንቢ ፡ ማለትህ ፡ አነሰና ፡ ደግሞ ፡ ባለትዳሮችን---
---ቤታቸውን ፡ ልታስፈታ ፡ ታጥቀህ ፡ ተነሳህ ? "አለች ፡ ጣይቱ ፡ ገና ፡ አጥሩን ፡ እንደ ፡ ገባች ፡ የሚያምር ፡ ጥርስዋን ፡ በጣማሽ ፡ ገለጥ ፡ አድርጋ ፡ በዛብህን ፡ በቀልድ ፡ አይን ፡ ገደም ፡ አድርጋ ፡ እያዩች ።

"የሚነን ቤት ፡ ነው ፡ ለማስፈታት ፡ ታጥቄ ፡ የተነሳሁ ? የኔ ፡ እመቤት ! "

"ይችን ፡ የኛን ፡ ቤት ፡ ስታንስ ፡ ጊዜ ፡ ከቤት ፡ አለመቆጠርህ ፡ ነው ? ወይስ ፡ ባሌን ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ይዘኸው ፡ ስትከበልል ፡ አትፈታም ፡ ብለህ ፡ ነው !" አለች ፡ ጣይቱ ፡ አሁንም ፡ ቀልድ ፡ ባስጌጠው ፡ አስተያየት ፡ በዛብህን ፡ ገደም ፡ አድርጋ ፡ እያዩች ።

"ባልሽ ፡ ፈረስና ፡ ገብስ ፡ ያጣላል ፡ አንችንና ፡ እኔን ፡ ለማጣላት ፡ የቀመመውን ፡ አትመኚው ፡ ከሶስት ፡ ቢበዛ ፡ ካራት ፡ ቀን ፡ የበለጠ ፡ አንቆይም ።"

"እእ --- ! ሶስት ፡ አራት ፡ ቀን ! አሁንስ ፡ እዚያ ፡ ሲናዳ ፡ የሚባል ፡ አገር ፡ በዩሳምንቱ ፡ እዩሄዳችሁ ፡ የምትጠነቀሩበትን ፡ ምስጢር ፡ የወፍ ፡ ክንፍ ፡ ኖሮት ፡ ብርር---ብሎ ፡ ሄዶ ፡ ያዩ ፡ ሰው !"

"በይ ፡ ይልቅ ፡ የምንጠጣው ፡ ስጭንና ፡ ሳይመሽብን ፡ እንሂድ ።" አለ ፡ ባልዋ ።

ከዚያ ፡ ገና ፡ አፍላው ፡ ያላለፈ ፡ ጥሩ ፡ የስንዴ ፡ ጠላ ፡ በትልልቅ ፡ ዋንጫ ፡ ስጥታቸው ፡ አንዳንድ ፡ ፈጅተው ፡ ሁለተኛውን ፡ ሲይዙ ፡ "እንዴት ፡ ያለ ፡ ጠላ ፡ ነው ? እባክህ ! "አለ ፡ በዛብህ ።

"እየውልህ ፡ የጣይቱ ፡ ፈረስ ፡ ያልሁህ ፡ ይህ ፡ ነው ! እንግዴህ ፡ ይህን ፡ ጭነን ፡ ከዚህ ፡ የጋለብን ፡ እንደሆነ ፡ እግራችን ፡ እንቅፋት ፡ አይፈራ ፡ እሾህ ፡ መንገድ ፡ የሄድን ፡ ሳይመስለን ፡ ገና ፡ መጣም ፡ ሲጀምር ፡ ነው ፡ የሚያልቅብን ።"

አለ ፡ ግራጌታ ፡ እዩሳቀ ።

እውነትም ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ በዛብህና ፡ ግራጌታ ፡ ቀለሙ ፡ ከዲማ ፡ ጊዜ ፡ ከተጎዳ ፡ ቢንስ ፡ እዩተሜወቱ ፡ መንገድ ፡ የሄዱ ፡ ሳይመስላቸው ፡ ሲኖዳ ፡ ገና ፡ ከብት ፡ ተሰብስቦ ፡ እንዳበቃ ፡ ደረሱ ። እዚያ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ እንደ ፡ ሁልጊዜው ፡ ወደ ፡ ገበዙ ፡ ወደ ፡ ቄስ ፡ ምትኩ ፡ ቤት ፡ ቀጥ ፡ ብለው ፡ ሄዱ ። ቄስ ፡ ምትኩ ፡ የግራጌታ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ዘመድ ፡ ከመሆናቸውም ፡ ሌላ ፡ በዛብህን ፡ በግራጌታ ፡ አይን ፡ እያዩት ፡ በጣም ፡ ወዳጆች ፡ ሆነው ፡ ነበር ። ድንገት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚሄድበት ፡ ጉዳይ ፡ ስለገጠመው ፡ ከታቦቱም ፡ ከገሬውም ፡ ለመሰናበት ፡ መምጣቱን ፡ ሲሰሙ ፡ ብጣም ፡ አዘኑ ።

"እየየ --- ! ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ተጎዳን ! እሬትህ ፡ ስለሆነ ፡ አይደለም ፡ መሪጌታ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ስለው ፡ የኖርሁትን ፡ ነው ፡ የምነግርህ ! ይህ ፡ ታቦት ፡ ከመሪጌታ ፡ ማእጠንቱ ፡ በሁዋላ ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ አገልጋይ ፡ አግኝቶ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። "አሉ ፡ ቄስ ፡ ምትኩ ፡ እያዘኑ ።

"እስቲ --- እሱም ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ እኔም ፡ እዚያ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ካሉት ፡ መምህራን ፡ እንፈልጋለን ፡ ግዴለም ፡ አይታጎልም ። "አለ ፡ ግራጌታ ።

"አየየ -- ፡ እንጃ ! ቢገኝም ፡ እንደሱ ፡ ያለ ፡ አይገኝም ፡ እንደሱ ፡ ያለ ፡ በሙያው ፡ አገር ፡ ከማስከበሩም ፡ በላይ ፡ ትንሽ ፡ ትልቁን ፡ እንደዩባህሪው ፡ መሸኘት ፡ የሚያውቅ ፡ ባለትህትና ፡ የሚገኝ ፡ አይመስለኝም ። አገሬው ፡ ያመት ፡ ቀለቡን ፡ ሰፍረን ፡ ደመወዙን ፡ እጥፍ ፡ እናድርግለትና ፡ እንደኛውን ፡ እዚሁ ፡ ጠቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎቱ ፡ ሌላ ፡ ልጆቻችንን ፡ እንዲያስተምርልን ፡ ንገርልን ፡ እያለ ፡ እዩጨቀጨቀኝ ፡ እኔም ፡ ከዛሬ ፡ ነገ ፡ እነግረዋለሁ ፡ እያልሁ ፡ ሳስብ ፡ ነበር ፡ እንጂ ---እንዲያውም ፡ እንደኛውን ፡ ጥሎን ፡ ይሄዳል ፡ ብዩ ፡ መች ፡ አስቤ ! "አሉ ፡ ቄሱ ። በዛብህም ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ ምስጋናው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፡ ደስ ፡ ቢለው ፡ ቄስ ፡ ምትኩ ፡ የገለጹት ፡ የውነተኛ ፡ ስሜታቸውን ፡ መሆኑ ፡ ስለተሰማው ፡ እንደ ፡ ፈለጉት ፡ ቆይቶ ፡ ፈቃዳ

ቸውን ፡ ሊፈጽም ፡ ባለመቻሉ ፡ አዘነ ።

በተከታዮቹ ፡ ሶስት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ ደመወዙን ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ በመንፈቅ ፡ የሚደርሰውን ፡ የህልና ፡ የበርበሬ ፡ ግምት ፡ ዘጠኝ ፡ ብር ፡ ከፍታት ፡ ተጠራቅሞ ፡ በገበዙ ፡ እጅ ፡ የቆዬ ፡ ድርሻው ፡ ሰባት ፡ ብር ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ አገሬው ፡ ለስንቅ ፡ አዋጥቶ ፡ የሰጠው ፡ አምስት ፡ ብር ፡ በድምሩ ፡ ተጠቃሎ ፡ ሀያ ፡ ሰባት ፡ ብር ፡ ሲላገኝ ፡ በዛብህ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ደስ ፡ አለው ።

በዛብህና ፡ ቀለሙ ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ዲማ ፡ ሲደርሱ ፡ "በል ፡ እንግዴህ ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ እንሂድና ፡ ራታችንን ፡ እዚያ ፡ እንብላ ።" አለ ፡ ግራ ፡ ጌታ ።

" የለም ፡ ተወኝ ፡ በር ፡ ሳይዘጋ ፡ ልሂድና ፡ ሰብለን ፡ ልጠይቅ ። "

" አባክህ ፡ አሁን ፡ ጊዜውም ፡ አጉል ፡ ነው ፡ ነገ ፡ ጥዋት ፡ ሄደህ ፡ እያት ፤ ወዲያውም ፡ የጣይቱ ፡ ባላደራ ፡ መሆንህን ፡ አትርሳ ፤ የወለድኸውን ፡ መልስህ ፡ ሳታስረክብ ፡ በመሀከሉ ፡ ቢጠፉ ፡ ትጣላላችሁ ! " አለ ፡ ግራጌታ ፤ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ።

" እሺ — ይሁን ። " አለ ፡ በዛብህ ፤ ሰብለን ፡ ሳያይ ፡ በማደሩ ፡ ቅር ፡ እያለው ።

ጣይቱ ፡ ባልዋና ፡ በዛብህ ፡ ያኑለት ፡ ይመለሳሉ ፡ ብላ ፡ ስላላሰበች ፡ ራት ፡ አላሰናዳችም ፡ ነበርና ፡ ድንገት ፤ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በሁዋላ ፡ ስለደረሱ ፡ ደነገጠች ። ቢሆንም ፡ ጠላ ፡ ሰጥታቸው ፡ እየጠጡ ፡ እሳት ፡ አዬሞቁ ፡ ሲጫወቱ ፡ እሷ ፡ እላይ ፡ ምድጃ ፡ ድስት ፡ እታች ፡ ምድጃ ፡ ምጣድ ፡ ጥዳ ፡ ትጣደፍ ፡ ጀመር ።

" ለመሆኑ ፡ እኛ ፡ ባንመጣ ፡ ጠም ፡ ልታድሪ ፡ ኖሮዋል ? " አለ ፡ በዛብህ ፡ ለመቀለድ ፡ ያክል ።

" ጠምማ ፡ እንዴት ፡ አድራለሁ ? ያኑ ፡ የሴት ፡ እራት ፡ እበላ ፡ ነበር ፤ እንጂ ። "

" ምንድነው ፡ የሴት ፡ እራት ? ከወንድ ፡ እራት ፡ የተለዬ ፡ ነው ? "

" እኦ — ቤት ፡ ጥሬውን ፡ ምናምኑን ፡ በልታ ፡ ታድራ ለች ፡ የቤት ፡ ልብዋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሆድዋ ፡ አይመርጥም ፡ ይባላል ! " አለች ፡ ጣይቱ ፡ ከጢስ ፡ ጋር ፡ እየታገለች ፡ እን ደምንም ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ ሳቅ ፡ አለችና ። በሻብህም ፡ ባልዋም ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ።

" ምን ፡ አሰብሁ ፡ ታውቃለህ ? " አለ ፡ በሻብህ ፡ ከጣ ይቱ ፡ ጋር ፡ ጨዋታቸውን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ጉዋደኛው ፡ ዘወር ፡ አለና ።

" ምን ፡ አሰብህ ? "

" ለሲኖዳ ፡ ሌላ ፡ መሬጌታ ፡ ከመፈለግ ፡ ለምን ፡ አንተ ፡ አትይዘው ? አሁን ፡ እኔ ፡ ያገኘሁትን ፡ ገንዘብ ፡ አንተ ፡ አመት ፡ ሙሉ ፡ እንገትህን ፡ አቀርቅረህ ፡ ታምረ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ይሁን ፡ ሌላ ፡ ጽፈህ ፡ ከምታገኘው ፡ ጋር ፡ ሳመዛዝነው ፡ እኔ ፡ ያገኘ ሁት ፡ የሚሻል ፡ መስሎ ፡ ታዬኝ ። ስራውም ፡ በጣም ፡ ቀላል ፡ ነው ። አመት ፡ ሙሉ ፡ ጽፈህ ፡ ምን ፡ ታገኛለህ ? "

"ግራ ፡ ጌታ ፡ ገዛም ፡ ብሎ ፡ ቆዬና ፡- "ምንም ፡ አላገኝ ፡ ቢበዛ ፡ ባመት ፡ ሀያ ፡ ሰላሳ ፡ ብር ፡ ባገኝ ፡ ነው ። " አለ ።

" ያዘው ፡ እባክህ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይውሰደው ፡ የጽህ ፈት ፡ ስራህንም ፡ ቢሆን ፡ የሚያስፈታህ ፡ አይደለም ። "

" እስቲ ፡ አስብበታለሁ ፡ የጽህፈት ፡ ስራውስ ፡ እንዲ ያው ፡ ስለምወደው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የድካሙን ፡ ዋጋ ፡ የሚ ከፍል ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ። አሁን ፡ ይህ ፡ ታምረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ አድክሞኝ ፡ ስንት ፡ እንደሚሸጥ ፡ ነግሬሀለሁ ? "

" የለም ። "

" ሀያ ፡ ብር ! "

" ሰላሳም ፡ አጥቶ ? "

" እንኩዋን ፡ ሰላሳ ፡ ሀያ ፡ አምስትም ፡ አጣ ! እዚህ ፡ የደ ብሩ ፡ ገበዝም ፡ ሌሎችም ፡ አይተው — የጊዮርጊስን ፡ ስእል ፡ የከበበው ፡ ሀረግ ፡ በተለይ ፡ ግንዱ ፡ በጣም ፡ ከበደ ፡ ብለው ፡ ለዋጋ ፡ ማራከሻ ፡ ይህን ፡ ምክናያት ፡ ሰጡ ። "

"እሱንስ ፡ እንቢ ፡ አልኸኝ ፡ እንጂ ፡ እኔም ፡ ነግሬህ ፡ ነ በር ፡ ግንዱ ፡ የተቀባው ፡ ቀይ ፡ ከበድ ፡ ብሎዋልና ፡ ትንሽ ፡

ብሎ ፡ ጨምረህ ፡ ቀለል ፡ አድርገው ፡ ብዬህ ፡ ነበርኮ ፡ ታስታውሳለህ ?”

“ አዎ ፡ ብቻ — ስእልኮ ፡ እስተድመህ ፡ ወይም ፡ አሳኩትለህ ፡ ከምትተርከው ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ የተስማማ ፡ መሆን ፡ አለበት ! ለምሳሌ ፡ የጊዮርጊስን ፡ ታምር ፡ የጊዮርጊስን ፡ ግርማ ፡ በምትተርከበት ፡ መጽሀፍ ፡ የምታሳዩው ፡ የጊዮርጊስ ፡ ስእል ፡ ግርማ ፡ ያለው ፡ በግርማ ፡ የተከበበ ፡ ሆኖ ፡ መታየት ፡ አለበት ። በታምረ ፡ ጊዮርጊስና ፡ በገድለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መጻህፍት ፡ የሚሳለው ፡ የጊዮርጊስ ፡ ስእል ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ መሆን ፡ የለበትም ። ይህን ፡ ለኔ ፡ የሚሰማኝን ፡ ልዩነት ፡ ለሌሎች ፡ ማስረዳት ፡ ነው ፡ ያቃተኝ ። አንተም ፡ ሌሎችም ፡ እንዳላችሁኝ ፡ ባደርገው ፡ በሥራሽ ፡ የተበላሸ ፡ መስሎ ፡ ነው ፡ የሚታዩኝ ።”

“ አሁን ፡ በዚሁ ፡ በሀያ ፡ ብር ፡ ተስማማችሁ ፡ ታዲያ ?”

“ አዎ ፡ ተስማምተን ፡ ገንዘቡንም ፡ ወዘፈውልኛል ።”

“ከጨረሳችሁ ፡ መቸስ ፡ ይሁና ! ባትቸኩል ፡ ኖሮ ፡ ግን ፡ ቢቸና ፡ ደህና ፡ ዋጋ ፡ አታጣበትም ፡ ነበር ።”

ከራት ፡ በሁዋላ ፡ በዛብህ ፡ ወደ ፡ ቅኔ ፡ ቤቱ ፡ ለመሄድ ፡ ተሰናብቶ ፡ ሲወጣ ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ “እውጭ ፡ ቆዩኝ ፡ አደርስህለሁ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጉዋዳው ፡ ገባ ።

ቅኔ ፡ ቤት ፡ በራፍ ፡ ሲደርሱ ፡- “በል ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ልመለስ ።” አለ ፡ ግራ ፡ ጌታ ። “አልነገርሁህም ፡ መሰለኝ ፡ ሚሚ፡ እህቴ ፡ ታማለች ፡ ተብሎ ፡ ስለተላከብኝ ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ ወደዚያ ፡ መሄዴ ፡ ነው ። መቸም ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ ተገናኝተን ፡ እንሰነባበታለን ፡ እንዲያውም ፡ እስክሄድ ፡ አልለይህም ። ነገር ፡ ግን፡ እንደዛሬው ፡ የተመቸ ፡ ጊዜ ፡ አናገኝም ፡ ይሆናልና ፡ ይህችን ፡ አሁን ፡ ተቀበለኝ ። በቀደም ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ ያልኸውን ፡ አትርሳ ። ሰው ፡ የሚፈልገውን ፡ ነገር ፡ አመዛዝኖ ፡ ከመረጠ ፡ በሁዋላ ፡ ያ ፡ አመዛዝኖ ፡ የመረጠው ፡ ነገር ፡ እንዲፈጸምለት ፡ የወዳጁን ፡ በጎ ፡ ፈቃድና ፡ ርዳታ ፡ ሲጠይቅ ፡ ያላንዳች ፡ ማጉረምረም ፡ ያላንዳች ፡ ቅርታ ፡ መፈጸም ፡ የወዳጅነት ፡ ተግባር ፡ ነው ።” ብሎ ፡ አስራምስት ፡ ብር ፡ በራፉ ፡ እንደተቆጠረ ፡ በበዛብህ ፡ እጅ ፡ ቁጭ ፡ አደረገለት ።

"ምንድነው ? ቀለሙ !" አለ ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ ብሎ ።

"የታምረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዋጋ ፡ ነው ! የተረፈውን ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ነገ ፡ ከቄስ ፡ ገበዙ ፡ ተቀብዬ ፡ እሰጥሀለሁ ።"

እስቲ ፡ ቆይ ፡ እባክህ ! ሁለታችንም ፡ ሰከርናል ? ወይስ . . . እንዴት ፡ ነው !" አለ ፡ በዛብህ ፡ በነጻ ፡ እጁ ፡ አይኑን ፡ እያሻሸ።

"የለም ፡ አልሰከርንም ፡ ይህና ፡ ነን ።"

"እንግዲያ ፡ አመት ፡ ሙሉ ፡ ተኮራምተህ ፡ የደከምህበትን ፡ ዋጋ ፡ አሁን ፡ ለኔ ፡ መስጠትህ ፡ እንዴት ፡ ነው ?"

"እባክህ ፡ እዋጋ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ መከራከሩን ፡ ለገባየተኞቱ ፡ እንተወውና ፡ አሁን ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ተቀበለኝ !"

"የለም ፤ ይህ ፡ በጭራሽ ፡ የማይሆን ፡ ነው ።"

"ስማ ፡ በዛብህ ! አልሆነም ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ የምታገባ ፡ ብትሆን ፡ ኖሮ ፡ እንከዋን ፡ ገንዘብ ፡ በጄ ፡ እያለ ፡ ባይኖረኝም ፡ ተበድሬም ፡ ይሁን ፡ ለምጄ ፡ እኔ ፡ ነበርሁ ፡ የምድርህ ። ስለዚህ ፡ ያ ፡ ቢቀር ፡ ይህን ፡ ተቀበለኝ ፡ እባክህ !"

"እባክህ ፡ ቀለሙ ፡ አንተ ፡ ምን ፡ አለህና ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ዛሬ ፡ ለኔ ፡ የምትሰጠኝ ? እባክህ ፡ ተወኝ ! ችግርህን ፡ እያወቅሁ ፡ አሁን ፡ ስላስገደድኸኝ ፡ ብቀበልህም ፡ ወዳጄን ፡ ሰርቆ ፡ ወይም ፡ ዘርፎ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ሲጸጸቱኝ ፡ እኖራለሁ ፡ እንጂ ፡ ደስ ፡ አይለኝም !"

"እውነቱን ፡ ልንገርህ ? በዛብህ ! ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ያንተ ፡ ነው ። ገና ፡ ድሮ ፡ ሰብለን ፡ ማስተማር ፡ ሳትጀምር ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እሄዳለሁ ፡ እያልህ ፡ ስትነግረኝ ፡ ለስንቅ ፡ የምሰጥህ ፡ ገንዘብ ፡ በጄ ፡ ባለመኖሩ ፡ ይህን ፡ መጽሀፍ ፡ ጀመርሁ ። ሳልጨርሽ ሳልሸጠው ፡ መሄጃህ ፡ ይደርስብኝና ፡ ዘጉዶ ፡ እመጣለሁ ፡ እያልሁ ፡ ስሰራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ቆየህ ። ስለዚህ ፡ ድሮውንም ፡ ላንተ ፡ አስቤ ፡ አመት ፡ ሙሉ ፡ የደከምሁበትን ፡ ስንቅ ፡ አልቀበልህም ፡ ብትለኝ ፡ በጣም ፡ አዝንብሀለሁ !"

በዛብህ ፡ የወዳጁ ፡ አድራጎት ፡ ልቡን ፡ ነክቶት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንባቱን ፡ ያፈሥ ፡ ቆየና ፡ "ያንድ ፡ አመት ፡ ሙሉ ፡ የስራ ፡ ዋጋ ፡ ለኔ !" አለ ፡ በሸካራ ፡ ድምጽ ፡ ልቅሶ ፡ መጥቶ

በት ።

"ላንተ ፡ ምንድነው ፡ ይሄ ? በዛብህ ! እንደ ፡ ሴት ፡ እንጀራ ፡ እየጋገረ ፡ እያበላ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ፊቱ ፡ ሳይለወጥ ፡ ቆሻሻ ፡ እየጠረገ ፡ አስታሞ ፡ ላዳነ ፡ ወንድም ፡ ይሄ ፡ ምንድነው ? ዝም ፡ በል ፡ ብቻ ! ለሱ ፡ እግዚአብሄር ፡ በምትሄድበት ፡ ዋጋህን ፡ ይክፈልህ ፡ ያንተ ፡ ውለታ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አይበቃውም ። ሁልጊዜ ፡ እንደማስብህ ፡ ስታውቅ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንድታስበኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለውለታህ ፡ ውለታ ፡ ለመክፈል ፡ አይደለም ። ውለታህስ ፡ ሳይከፈል ፡ አብሮኝ፡- አብሮኝ ፡ ይኑር!" አለ ፡ ግራጌታም ፡ በተሰበረ ፡ ድምጽ ፡ ምሽት ፡ ከማግባቱ ፡ በፊት ፡ ጽኑ ፡ በሽታ ፡ ታሞ ፡ ዘመድ ፡ ሁሉ ፡ ሲሸሸው ፡ በዛብህ ፡ እንደሴት ፡ አድርጎ ፡ ያስታምመው ፡ እንደነበረ ፡ ስለታዎው ፡ ልቅሶ ፡ መጥቶበት ። ከዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ጉዋደኞች ፡ ተቃቅፈው ፡ ትንሽ ፡ ተላቀቀሱና ፡ በዛብህም ፡ አስራምስት ፡ ብሩን፡ ቅር ፡ እያለው ፡ ተቀብሎ ፡ ወደየቤታቸው ፡ መንገድ ፡ ሲጀምሩ፡-

"እንዴ ? እየውልህ ፡ የኔን ፡ ነገር ! እንዲያውኑ ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ ከዚህ ፡ ተንስተህ ፡ ሰተት ፡ ብለህ ፡ ሄደህ ፡ እቤትህ ፡ እንድትገባ ፡ አስመስዬ ፡ ነው ፡ የምሰናበትህ ! ለመሆኑ ፡ ይህ ፡ ያሰብኸው ፡ ጉዳይ ፡ ብርቱና ፡ የታመነ ፡ ረዳት ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነው ! ማን ፡ አለህ ?" አለ ፡ ቀለሙ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ወዳጁ ፡ እያመራ ።

"አዲስ ፡ አበባ ፡ ድረስ ፡ የሚያደርሰኝ ፡ ሰው ፡ አግኝቻለሁ ፡ ምንም ፡ አታስብ ።"

"ማነው ?"

"አለቃ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ከሁለቱ ፡ አገልጋዮቻቸው ፡ ጋር ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሊያደርሱኝ ፡ ይሰናዳሉ ።"

"ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ . . .ጉዱ ፡ ካሳ ?"

"አዎ . . . .ጉዱ ፡ ካሳ ።" አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ።

"አይ ፡ በዛብህ . .! እና ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ አምነህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አደገኛ ፡ ነገር ፡ አደርጋለሁ ፡ ብለህ ፡ ትነሳለህ ? እንግዲያስ ፡ እንዲያውም ፡ በጠቅላላው ፡ አሳቡ ፡ ከሱ ፡ የፈለቀ ፡ ይሆ

ናል ! የብድ ፡ አሳብ !"

" እውነትህ ፡ ነው ፡ በጠቅላላው ፡ አሳቡም ፡ ከሳቸው ፡ የፈለቀ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ ሰብለን ፡ እንደማታውቃት ፡ ሁሉ ፡ እሳቸውንም ፡ አታውቃቸውምና ፡ በሳቸው ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ለኔ ፡ ተውልኝ ! እሺ ?"

" እሺ ፡ ብቻ . . . ሜሜ ፡ መሄዱን ፡ ተውሁት !"

" ለምን ?"

" እህቴ ፡ ብሄድላት ፡ አትድንም ፡ ባልሄድላት ፡ አትሞት ! ያንተ ፡ ግን . . . . ልዩ ፡ ነው ፡ በዛብህ ። ባይሆን ፡ እንኩዋ ፡ አባዬን ፡ በደህና ፡ መሸኘቴህን ፡ ማየት ፡ አለብኝ !"

"አባትዋና ፡ ዘመዶችዋ ፡ ሳይመለሱ ፡ ቶሎ ፡ ከሄድን ፡ ምንም ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ ጉዞ ፡ መቃ ፋታችን ፡ እንኩዋ ፡ ሳይታወቅ ፡ አባዬ ፡ ደርሰን ፡ እናድራለን ። ስለዚህ ፡ አንተን ፡ የሚያሳስብ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ቀለሙ ። በደህና ፡ መድረሳችንን ፡ እናለቃ ፡ ካሳ ፡ ሲመለሱ ፡ እንዲያስታውቁህ ፡ እነግራቸዋለሁ ።"

" እኔን ፡ የሚያሳስበኝንና ፡ የማያሳስበኝን ፡ ካንተ ፡ የተሻለ ፡ የማውቀው ፡ እኔ ፡ ስለሆንሁ ፡ ለኔ ፡ ተውልኝ ፡ በዛብህ ! እሺ ?"

" የለም ፡ እባክህ !" አለ ፡ በዛብህ ፡ እየሳቀ ፡ ጉዋደኛው ፡ ከሱ ፡ በወሰደው ፡ ስለት ፡ መቁረጫ ፡ ክርክሩን ፡ ባጭር ፡ ስለ ቆረጠበት ።

"በል ፡ ደህና ፡ እደር !" አለና ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ በዛብህን ፡ እዚያው ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ ትቶት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ።

# ምእራፍ ፤ ፳፫ ፤

## መሰናዶ ፤

በዛብህ ከግራ ፡ ጌታ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ተሰይቶ ፡ እቤቱ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ወዲያው ፡ ወፍራም ፡ ጡዋፋን አብርቶ ፡ ጉዋደ ኛው ፡ የሰጠውን ፡ ብር ፡ ከሲኖዳ ፡ ካመጣው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ቢቆጥር ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ ሆነ ፤ ግራ ፡ ጌታ ፡ እንዳ ሰው ፡ የዲማ ፡ ገበዝ ፡ አምስቱን ፡ ብር ፡ ሲሰጡ ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡ ይሆናል ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ በዛብህ ፡ ራሱ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ቆጥቦ ፡ ያስቀመጠው ፡ ሶስት ፡ ብር ፡ ስለነበረው ፡ ያምሳ ፡ ብር ፡ ጌታ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው !" ጉዱ ፡ ካሳሰ ፡ ስንት ፡ ከብት ፡ ሸጦ ፡ ስንት ፡ ብር ፡ አግኝቶ ፡ ይሆን ? የሸጠውን ፡ ሸጦ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ እንኩዋ ፡ ባይሆን ፡ መቶ . . .ሰባ ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ሰማ ንያ ፡ ቢያገኝልኝ ፡ በበቃኝ ! ያን ፡ ያክል ፡ ካገኘሁ ፡ ቶሎ ፡ መሄድ ፡ ነው ፡ እኒያ ፡ አባትዋ ፡ ሳይመጡ ፡ ቶሎ ፡ መጥፋት ፡ ነው !" አለ ፡ ባሳቡ ፡፡

ከዚያ ፡ ሰብለን ፡ አግብቶ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚኖረው ፡ ኑሮ ፡ እዬተሰዋወጠ ፡ ታዬው ፡፡ ያንድ ፡ ደብር ፡ መሪጌታ ፡ ሲሆን ፡ ከዚያ ፡ አለቃ ፡ ሲሆን ፡ ሰብለንም ፡ እሱንም ፡ ደልቶዋ ቸው ፡ በደስታ ፡ ሲዋኙ ፡ እንደገና ፡ ድሀ ፡ ሆኖ ፡ ተቸግሮ ፡ ሰብለ ፡ ፊት ፡ ስትነሳው ፡ አይንዋ ፡ ሌላ ፡ ሲመለከት ፡ ከባለጸጎች ፡ አን ዱን ፡ ስትወድ ፡ ጠልቶዋት ፡ ከድሀ ፡ ጎጆው ፡ ሲያስወጣት ፡ ቀንቶ ፡ ሲገርፋት ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ሰብለ ፡ ባጭር ፡ ታጥቃ ፡ ከድሆች ፡ ጉዋደኞቹ ፡ ምሽቶች ፡ ጋር ፡ ውሀ ፡ ስትቀዳ ፡ እንጨት ፡ ስትለቅም ፡ ስትፈጭ ፡ ከዚያ ፡ አብረው ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ የድሀ ፡ ራታቸውን ፡ እዬበሉ ፡ "ውው - - - ድህነት ፡ መጣመ ! ጌታ ፡ ሆኖ ፡ ሰብቻ ፡ ከመኖር ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ድሀ ፡ ሆኖ ፡ መኖር ፡ እንዴት ፡ ይጥማል ፡ በዙ !" ስትለው ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እዬተሰዋ ወጠ ፡ ባይኑ ፡ ፊት ፡ ሲሄድ ፡ በራሱ ፡ ውስጥ ፡ ሲንጫጫ ፡ ሌሊቱ ፡ ተጋመሰ ፡፡ ከዚያ ፡ ልብሱን ፡ ለማውለቅ ፡ ቢያስብ ፡ እንደ ፡ ተደ

በደበ ፡ ሁሉ ፡ በውነቱ ፡ ድቅቅ ፡ ብሎ ፡ ብርጉ ፡ ድካም ፡ ስለ ፡ ተሰማው ፡ ሱሪውንም ፡ እጀጠባቡንም ፡ ሳያወልቅ ፡ እንዲሁ ፡ ተንስቶ ፡ እንጨት ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ተጋደመ ።

በበነጋው ፡ በጣም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ተነስቶ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ ለመሄድ ፡ ከቃጣ ፡ በሁዋላ ፡ ሰብለ ፡ ወደልፍኝዋ ፡ የምትመለስ ፡ እናትዋ ፡ እልፍኝ ፡ ቡና ፡ ከተጠጣ ፡ በሁዋላ ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ አለውና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተቀመጠ ። ገና ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ዳዊታቸውን ፡ ውዳሴ ፡ ማርያማቸውንና ፡ መልክ ፡ ጊዮርጊሳቸውን ፡ ደግመው ፡ ገና ፡ አዛዥ ፡ ዘሪሁን ፡ ከስራየቤቶች ፡ ጋር ፡ ተጨቃጭቀው ፡ ቁርስ ፡ አስቀርበው ፡ ተበልቶ ፡ ገና ፡ እናዛዥ ፡ ዘሪሁን ፡ ከነመዶቤ ፡ ፊት ፡ የተመለሰውን ፡ በልተው ፡ እያወሩ ፡ አንዳንድ ፡ ብርሌ ፡ ጠላ ፡ ጠጥተው ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ቡና ፡ ተጠጥቶ ፡ ነው ፡ ሰብለ ፡ ወደልፍኝዋ ፡ የምትመጣ ! በዛብህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሲያስብ ፡ አመት ፡ መስሎ ፡ ታዬውና ፡ ትግስት ፡ አጥቶ ፡ እጎጆው ፡ ውስጥ ፡ ሲንሳ ፡ ሲቀመጥ ፡ ቆይቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄደ ።

እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቆይቶ ፡ ጊዜው ፡ የደረሰ ፡ ሲመስለው ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ እልፍኝ ፡ ቢሄድ ፡ ገና ፡ ከናትዋ ፡ እልፍኝ ፡ ሳትመለስ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ እደጅ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲጠብቅ ፡ ሰብለ ፡ ሀብትሽን ፡ አስከትላ ፡ ብቅ ፡ አለች ። ወዲያው ፡ እደጅ ፡ ተቀምጦ ፡ ስታየው ፡ ልብዋ ፡ መሸበር ፡ ጉልበትዋ ፡ መብረክረክ ፡ ርምጃዋ ፡ ድንግርግር ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ጀመረ ፡ ቆመች ። ፊትዋ ፡ ደም ፡ መስሎ ፡ ከንፈርዋም ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጭዋም ፡ ሲንቀጠቀጥ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

“ምነ ? ሰብለ !” አለች ፡ ሀብትሽ ።

“እንጃ ! ዛሬ ፡ ብዙ ፡ ጤንነት ፡ አይሰማኝም ።”

“ታዲያ ፡ ዛሬ ፡ ትምርቱ ፡ ይቅርብሽ !”

“የለም ፡ አይቀርም ፡ እርሳሴን ፡ እማማ ፡ እልፍኝ ፡ ረስቸው ፡ መጥቻለሁ ፡ መሰለኝ ፡ ተመለሽና ፡ ፈልገሽ ፡ አምጭልኝ ፡ አባክሽ ።”

ሀብትሽ ፡ ወደ ፡ ሴት ፡ እልፍኝ ፡ መመለስዋን ፡ ሲያይ ፡ በዛብህ ፡ የሰብለ ፡ መላ ፡ ገብቶት ፡ ቶሎ ፡ ተነስቶ ፡ እቤት ፡

ገብቶ ፡ ጠበቃት ። የሱም ፡ ልብ ፡ ሽምቶ ፡ ይጋልብ ፡ የሱም ፡ ጉልበት ፡ ይብረከረክ ፡ የሱም ፡ ጉንጭና ፡ ከንፈር ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ነበር ! ወዲያው ፡ እዩሮጠች ፡ መጥታ ፡ እቅፉ ፡ ላይ ፡ ስትወድቅ ፡ ባፉ ፡ ተቀበላት ። እንዴት ፡ አደርህ ፡ እንዴት ፡ አደርሽ ፡ መባባል ፡ የለ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ መለዋወጥ ፡ የለ ፡ አብረው ፡ እንደ ፡ ሰነበቱ ፡ እንዳልተለያዩ ፡ ሁሉ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተገናኝተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተቃቀፈው ፡ እሱዋ ፡ በሱ ፡ እሱ ፡ በሷ ፡ ውስጥ ፡ ሙቀሙ ! ሰላምታ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ? ቃል ፡ ምን ፡ ያደርጋል ? ሰላምታ ፡ የልማድ ፡ ንግግር ፡ ነው ! ቃልም ፡ ስሜታቸውን ፡ ለማይተዋወቁ ፡ ለማይግባቡ ፡ ሰዎች ፡ የአሳብ ፡ መግለጫ ፡ ነው ! ስሜታቸው ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ የጋራ ፡ ፍቅር ፡ ያላቸው ፡ ግን ፡ የልማድ ፡ ንግግር ፡ አያስፈልጋቸውም ፡ ከተራ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ የስሜት ፡ መግለጫ ፡ ያሳብ ፡ መግለጫ ፡ አላቸው ። ፍቅር ፡ ቃሉ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ ሊገልጸው ፡ የማይችለውን ፡ ስሜት ፡ የሚገልጽበት ፡ የራሱ ፡ ቋንቋ ፡ አለው !

ሀብትሽ ፡ እርባቡን ፡ ፈልጋ ፡ ማጣትዋን ፡ ለመንገር ፡ እዩሮጠች ፡ ብትመጣ ፡ አንገት ፡ ላንገት ፡ እንደ ፡ ተየያዙ ፡ ስለ ፡ ደረሰች ፡ አይንዋንም ፡ አፏዋንም ፡ በሰፊው ፡ ከፍታ ፡ በቆመችበት ፡ ደርቃ ፡ ቀረች ። አይንዋን ፡ ማመን ፡ አቃታት ። ትንሽ ፡ ቆማ ፡ እንደ ፡ ተመለከተች ፡ ድንጋጤዋ ፡ አልፎ ፡ ፍራት ፡ ስለ ፡ ያዛት ፡ አፍዋን ፡ በሁለት ፡ እጅዋ ፡ አፍና ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ ቀስ ፡ ብላ፡ አፈገፈገችና ፡ ተመልሳ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እልፍኝ ፡ ብትሄድ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ካባ ፡ ሞገሴ ፡ ጋር ፡ ቆመው ፡ ሲነጋገሩ ፡ አገኘቻቸው ። እዚያ ፡ ትንሽ ፡ ቆም ፡ ብላ ፡ ቆይታ ፡ እመቤትዋ ፡ ንግግራቸውን ፡ ሲጨርሱ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ እልፍኝ ፡ መሄዳቸው ፡ ስለማይቀር ፡ ቀደም ፡ ብላ ፡ ሄዳ ፡ ማስጠንቀቁ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ስለ ፡ መሰላት ፡ እንደ ገና ፡ ወደሰብለ ፡ ሄደች ። አሁንም ፡ አንገት ፡ ላንገት ፡ እንደ ፡ ተዩያዙ ፡ አገኘቻቸው ። ብቻ ፡ አሁን ፡ ሲሳሳሙ ፡ እያደለም ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ጊዜ ፡ ጠፍቶ ፡ የሰነበተበትን ፡ ትጠይቀው ፡ ነበር ።

"እህህ - - " አለች ሀብትሽ ፡ እበር ፡ ቆማ ፡ እንደምትስል ፡ ሁሉ ። ሰብለ ፡ የበዛብህን ፡ አንገት ፡ በሁለት ፡ እጅዋ ፡

እንደ ፡ ያዘች ፡ ዘመሯ ፡ ብላ ፡ አይታት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ንግግርዋን ፡ ቀጠለች ፡ የያዘችው ፡ ሰውዬ ፡ ባልዋ ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ የፍረት ፡ ምልክት ፡ ሳይታይባት ። በዛብህም ፡ የሰብለን ፡ አንገት ፡ እንደያዘ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆመ ።

"እርሳሱን ፡ ፈልጌ ፡ አጣሁት ።" አለች ፡ ሀብትሽ ።

"ተይው ፡ ይጥፋ ።" አለች ፡ ሰብለ ፡ ዘመሯ ፡ እንኩዋ ፡ ሳትል ።

"እሜቴ ፡ ተነስተዋል ፡ ወደዚህ ፡ ሊመጡ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ።"

"ትምጣ ! " አለች ፡ ሰብለ ፡ ዘመሯ ፡ ብላ ። ትምጣ ፡ ስትል ፡ እናትዋን ፡ የመናቅም ፡ የመጥላትም ፡ ምልክት ፡ እፊትዋ ፡ ላይ ፡ ጎልቶ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

"የለም ፡ መጽሀፍሽን ፡ ያገር ፡ እቦታሽ ፡ ተቀመጪ ።" አለና ፡ በዛብህ ፡ እቦታው ፡ ሄዶ ፡ ተቀመጠ ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ እደገኛ ፡ ወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ የሚወድቀው ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ ነው ። አንዱ ፡ የሰራሁትን ፡ ሰው ፡ አያውቅብኝም ፡ ሲል ፡ ሁለተኛው ፡ መችም ፡ ታውቆብኛል ፡ ይሁን ፡ ምናባቱ ፡ ሲል ፡ ነው ።

ሰብለና ፡ በዛብህ ፡ መጀመሪያ ፡ ምስጢራችንን ፡ እኛ ፡ ካልተናገርን ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ ካላዩን ፡ የሚያውቅብን ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ሲገናኙ ፡ ብቻ ፡ በፍቅራቸው ፡ እዩስከሩ ፡ ሊደርስባቸው ፡ የሚችለውን ፡ አደጋና ፡ ዘሱ ፡ የሚያመልጡበትን ፡ መንገድ ፡ ሳያስቡ ፡ የሚያውቁትን ፡ ነፋ ፡ እስም ፡ ጨርሰውረስተው ፡ ኖሩ ። በሁዋላ ፡ ምስጢራቸው ፡ መገለጹን ፡ ሲያውቁ ፡ 'ከታወቀ ፡ ይሁን ፡ ምናባቱ ፡' እሚለት ፡ ተስፋ ፡ መቁረጥ ፡ ደረሱ ። እፍረቱ ፡ ፍራቱ ፡ ሁሉ ፡ ቀረ ። በብርቱ ፡ ፍቅር ፡ ፊት ፡ ያባት ፡ የናት ፡ ቁጣና ፡ ቅጣት ፡ የሰው ፡ ሳቅና ፡ ስላቅ ፡ ምንድነው ! የፈለገ ፡ ሁሉ ፡ አይቶ ፡ ቢስቅ ፡ የፈለገ ፡ ሁሉ ፡ ቢቆጣ ፡ ለወደደ ፡ ከፍቅሩ ፡ የሚብስ ፡ አለ ? የለም ! ስለዚህ ፡ 'ትምጣና ፡ ትይ !' አለች ፡ ሰብለ ፡ እናትሽ ፡ መጥተው ፡ ያዩሻል ፡ ብትባል ።

ሰብለ ፡ መጽሀፍዋን ፡ ሳትገልጽ ፡ በጉልበትዋ ፡ ላይ ፡ ይዛ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠች ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ መጡ ።

" በዛብህ ፡ መጣህ ? የት ፡ ጥለኸን ፡ ሄደህ ፡ ሰነበትህ ? እባክህ ! " አሉ ፤ እንደሁልጊዜው ፡ በደስታ ፡ ፊት ።

" ብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ አግኝቶኝ ፡ ሲኖዳ ፡ ሄጄ ፡ ነበር ። "

"ማንው ፡ ደብረ ፡ ወርቅ ፡ ሄድህ ፡ ብሎ ፡ የነገረኝ ? ይሁን ፡ ብቻ ፡ ደህና ፡ ሄደህ ፡ ኖርዋል ? በደህናስ ፡ ተመለስህ ? "

" ደህና ! የሄድሁለትንም ፡ በደህና ፡ ፈጽሜ ፡ ተመለ ስሁ ። "

" መልካም ! እዩሽ ፡ ሰብለ ፡ የሁላ·ችንንም ፡ ልብ ፡ አዋራ ፡ የበላው ፡ ይመስል ፡ ዛሬ ፡ ኪዳን ፡ ምህረት ፡ መሆንዋን ፡ ረስተን ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄደን ፡ ሳናስቀድስ ፡ ቀረን ። አሁን ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ አውቀን ፡ የቀረን ፡ መስሎዋቸው ፡ ሲቆጡኝ ፡ ነበር ። ተነሺ ፡ አሁንም ፡ ሄደን ፡ ደጀሰላም ፡ ለተቀመጡት ፡ ድሆች ፡ ምጽዋት ፡ ሰጥተን ፡ እንምጣ ። " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ወደ ፡ ልጃቸው ፡ ዘወር ፡ ብለው ።

" እኔ ፡ አልሄድም ፤ አንቺ ፡ ሂጂ ። " አለች ፡ ሰብለ ፡ አንገትዋን ፡ ከደፋችበት ፡ ሳታቀና ።

"ምን ፡ ምን ፡ ሆንሽ ? አሁን ፡ ደህና ፡ አልነበርሽ ? " አሉ ፡ እናትዋ ፤ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እቁርስ ፡ ላይ ፡ ካዩዋት ፡ ተለ ውጣ ፡ ስላገኙዋት ።

" ምንም ፡ አልሆንሁ ። " አለች ፡ አሁንም ፡ አንገትዋን ፡ እንደ ፡ ደፋች ።

" ተደውም ፡ እኔ ፡ እሄዳለሁ ፡ መጥፎ·ብሻል ፡ መሰለኝ ፡ ዛሬ !" አሉና ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ሀብትሽን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጠርተው ፡ አንቺ ፡ ቅንዳሽም ፡ ዋ —— !" ብለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ ሄዱ ።

እመቤትዋ ፡ አጥሩን ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ሀብትሽም ፡ እንደ ፡ ድሮዋ ፡ ሳትቀልድና ፡ ሳትጫወት ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ማድቤትዋ ፡ ሄደች ።

ሰብለ ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ በምስጢር ፡ ፍቅር ፡ ከጀመረች በት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ምስጢርዋ ፡ በብዙ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ መታወቁን ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ እስከትሰማ ፡ ድረስ ፡ እናት ፡ አባትዋን ፡

በክፉም ፡ ሆነ ፡ በበጎ ፡ አሰባቸው ፡ እነሱን ፡ የመጥላትም ፡ ሆነ ፡ የመውደድ ፡ ስሜት ፡ ለልብዋ ፡ ተሰምቶት ፡ አታውቅም ፡ ነበር። ልብዋ ፡ ማንንም ፡ መጥላት ፡ ትቶ ፡ በዛብህን ፡ ብቻ ፡ እዩወደደ ፡ ራስዋ ፡ ማንንም ፡ ማሰብ ፡ ትቶ ። እሱን ፡ ብቻ ፡ እያሰበ ፡ በደስታ ፡ በጸጥታ ፡ ትኖር ፡ ነበር ።አሁን ፡ ከምስጢርዋ ፡ መገለጽ ፡ ጋር ፡ ለፍቅርዋ ፡ ለደስታዋና ፡ ለጸጥታዋ ፡ አፍራሾች ፡ እናትና ፡ አባትዋ ፡ መሆናቸው ፡ ጭምር ፡ አብሮ ፡ ስለ ፡ ታያት ፡ ልትሸፍነው ፡ የማትችለው ፡ የናት ፡ አባትዋ ፡ ጥላቻ ፡ እፊትዋ ፡ ላይ ፡ ጎልቶ ፡ ይታይባት ፡ ጀመር ።

" አየ - - - ምነው ፡ የነዚህን ፡ ሰዎች ፡ አይን ፡ የማላይበት ፡ ቦታ ፡ ባገኘሁ ! " አለች ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ተነስታ ፡ መጥታ ፡ እሱ ፡ በባርጩማ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ እፊቱ ፡ አመሬት ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ በሚያሳዝን ፡ አስተያየት ፡ ሽቅብ ፡ የሱን ፡ አይን ፡ እዩተመለከተች ።

" አለቃ ፡ ካሳ ፣ በሰፊው ፡ አነጋገሩሽ ? " አለ ፡ በዛብህ ፡ እሱም ፡ የሰዋን ፡ ፍቅርና ፡ ችግር ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ የሚያንከራትታቸው ፡ አይኖች ፡ ዘቅዝቆ ፡ እዩተመለከተና ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ እፊትዋ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ያካል ፡ ክፍሎችዋን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ይውር ፡ ፈደል ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እዩዳበሰ ።

" በጣም ፡ ብዙ ፡ አላነጋገረኝም ፡ ሁሉንም ፡ ለበዛብህ ፡ ንገሬዋለሁና ፡ ጊዜ ፡ ሳታጠፉ ፡ ቶሎ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ሂዱ ፡ እኔና ፡ እዝራ ፡ እናደርሳችሁዋለን ፡ ነው ፡ ያለኝ ።"

" ስለ ፡ ገንዘብ - - ምንም ፡ አላሉም ? "

"ስለገንዘብ ? ስለገንዘብስ ---አላነሳም ። "

"እሺ ፣ ታዲያ ፡ . . . ምን ፡ አልሻቸው ? "

" ስለምኑ ? "

" አዲስ ፡ አበባ ፡ ቶሎ ፡ ሂዱ ፡ ሲሉሽ ። "

"ምን ፡ የምል ፡ ይመስልሃል ! እስቲ ፡ ገምት ። " አለች ሰብለ ፡ በቅርታ ፡ የተዋበ ፡ ፈገግታ ፡ ፊትዋን ፡ አስጊጦት ።

"እም ፡ . . . እሺ ፡ አልሻቸው ! " አለ ፡ እሱም ፡ ትንሽ ፡ የቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ።

" እዎ ፡ ደህና ፡ ገምተሀል ። ለመሆኑ ፡ ገንዘብ ፡ ያልኸው ፡ የምን ፡ ገንዘብ ፡ ነው ? "

በዛብህ ፡ የገንዘብ ፡ ነገር ፡ የተነሳበትን ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ እንደሚነግራት ፡ ተቸግሮ ፡ ግንባሩን ፡ ሲያሻሽ ፡ ቆዩና ።–

" እዩሽ ? ሰብለ ! አንቺ ፡ ከተወለድሽ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በምቾት ፡ የኖርሽ ፡ ነሽ ። ታዲያ ፡ አሁን --- ችግርን ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ሳትለምጂው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ እብርቱ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ የወደቅሽ ፡ እንደሆነ ፡ ምናልባት ፡ ታዝኚ ፡ ይሆናል ፡ ትጸጠቺ ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ ካሲቃ ፡ ጋር ፡ ስንነጋገር --- 'ስራ ፡ እስኪትይዝ ፡ የሚያቆያችሁ ፡ ገንዘብ ፡ እኔ ፡ ከብት ፡ ሸጬ እሰጣችሁዋለሁ ፡' ብለውኝ ፡ ነበርና ፡ ስለሱ ፡ ነግሬሽ ፡ እንደ ሆነ ፡ ብዬ ፡ ነው ። " አለ ፡ ሲፈር ፡ ሲቸር ።

"እአ — ! ለዚህ ፡ ነው ፡ ሁለት ፡ በቅሎዎች ፡ ሸጠ ፡ ሲባል ፡ ትናንት ፡ ነው ? ወይስ ፡ ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ የሰማሁ ? ብቻ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልንገርህ ! እኔን ፡ ትቸገሪለቼ ፡ ብለህ ፡ ምንም ፡ አታስብ ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ፡ ወጥተን ፡ አንተና ፡ እኔ ፡ ብቻችን ፡ ከሆን ፡ ብዙም ፡ ይሁን ፡ ትንሽ ፡ አንተ ፡ ከውጭ ፡ የምታመጣውን ፡ እኔ ፡ እቤት ፡ አሰናድቼ ፡ ማቅረብ ፡ አያቅተኝም ። ከሰራዩ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ያደግሁ ፡ መስራት ፡ አውቃለሁ ። ደግሞ ፡ — ካንተ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ ችግር ፡ ቢደርስብኝ ፡ ማዘን ፡ ወይም ፡ መጸጠት --- የለም !" አለች ፡ ቅርኃዋ ፡ ሁሉ ፡ ጠፍቶ ፡ በደስታ ፡ ፊት ።

"ጥሩ ፡ ነው ፡ እንግዴህ !" አለ ፡ እሱም ፡ ደስ ፡ ብሎት ።

" ሁለት ፡ በቅሎዎች ፡ ሸጡ ፡ አሉ ? በምን ፡ ያክል ፡ ሸጡዋቸው ፡ ይሆን ?" አለ ፡ ደኅመና

"በምን ያክል ፡ እንደ ሸጡዋቸውስ ፡ አልሰማሁም ።"

"እሳቸው እንኳዋ ፡ ከብት ፡ ሸጬ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አገኝላችሁዋለሁ ነበር ያሉ ፡ ነገር ፡ ግን መቶ ፡ ብር ፡ ካገኙልን ፡ እኔ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ስላለኝ ፡ ይበቃን ፡ ነበር ! መቶ ፡ ብር ፡ ካገኙልኝ ፡ ጊዜ ፡ ሳናጠፋ ፡ ብንሄድ ፡ እንዴት ፡ ጥሩ ነበር !"

"መቶ ፡ አምሳ ፡ ብርስ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ እዩቆጠብን ፡ ለብዙ ፡

ጊዜ ፡ ይበቃናል ፡ ቶሎ ፡ እንሂድ ፡ እባክህ ፡ በዛብህ ፡ እንዲያውም ፡ ትናንትና ፡ ሌሊት ፡ ከፉ ፡ ቅዠት ፡ ስላቃዠኝ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ ዛሬ ፡ ልቤ ፡ ድንግጥ ፡ ድንግጥ፡ እያለ፡ ፍራት ፡ ፍራት፡ ይለኛል።”

“ እልም ፡ ካልፈሩት ፡ አያያርስም ፡ ያባላል ፡ እያዞሽ ፡ አትፍሪ ። ወዲያውም ፡ የመንገዱ ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልብ ሽን ፡ ድንግጥ ፡ ድንግጥ ፡ የሚያደርገው ፡ ቅዠቱ ፡ አያደለም ። እኔ ፡ እንኩዋን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጉዞ ፡ እፊቴ ፡ ተዘብቦብኝ ፡ ተራ ፡ መንገድም ፡ ቢሆን ፡ ሳስብ ፡ ያሰብሁትን ፡ መንገድ ፡ እስክጀምር ፡ ልቤ ፡ ሲደነግጥ ፡ ይቆያል ። ለመሆኑስ --- ምን ፡ እልም ፡ ነው ፡ ያዬሽ ?”

“ እልም ፡ ከማለት ፡ እንኩዋ ፡ ቅዠት ፡ ቢባል ፡ ይመስለ ዋል ፡ ከፉ ፡ የሚያስፈራ ፡ ቅዠት ! እንዴት ፡ ሆኜ ፡ እዚያ ፡ እንደ ፡ ሄድሁ ፡ ወይም ፡ ማን ፡ እዚያ ፡ እንደ ፡ ጣለኝ ፡ አላውቅም ፡ እገደል ፡ መሀከል ፡ እንዲያው ፡ እገደሉ ፡ ወገብ ፡ ላይ ፡ የቆምሁ ፡ ይመስለኛል ። ከዚያ ፡ የገደሉን ፡ ስር ፡ ዘቅዝቀህ ፡ ስታየው ፡ ከር ቀቱ ፡ የተነሳ ፡ ራስህን ፡ ያዞርሃል ፡ ያንቀጠቅጥሃል ! ወደ ፡ ላይ ፡ አፋፉን ፡ ስታየው ፡ ሩቅ ፡ ነው ። ብቻ ፡ ከስሩ ፡ አፋፉ ፡ ይቀርባል። መያዣ ፡ የለ ፡ ምን ፡ የለ ፡ አፈሩንም ፡ ደንጋዩንም ፡ እዬያዝሁ ፡ ወደፋፉ ፡ ለመውጣት ፡ ስሞክር ፡ ትንሽ ፡ እወጣና ፡ የያዝሁትም ፡ የቆምሁበትም ፡ አፈርና ፡ ደንጋይ ፡ እየተፈረፈረና ፡ እዬተፈነቀለ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ታች ፡ ሲመልሰኝ ፡ ሲያንሻትተኝ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ሲመልሰኝ ፡ ሲያንሸራትተኝ ፡ ደግሞ ስሞክር ፡ ድግሞ ፡ ትንሽ ፡ ከወጣሁ ፡ በሁዋላ ፡ አንሻቶ ፡ ሲመል ሰኝ ፡ ጭንቀቴን ፡ ብታይ ፡ እንዴት ፡ ትጨነቅ ነበር !”

“እንኩዋን ፡ እንዲያ ፡ ስትጨነቂ ፡ አይቸሽ ፡ አሁንም ፡ ስትነግሪኝ ፡ እንዴት ፡ ጨነቀኝ !” አለ ፡ በዛብህ ፤ እውነትም ፡ የብርቱ ፡ ጭንቀት ፡ ምልክት ፡ በፊቱ ፡ እዬታዬ ።

“ ታዲያስ ! ወጣሽ ?”

“ አፋፉ ፡ ላይ ፡ የበቀለውን ፡ ሳር ፡ ይገኝ ፡ እያልኩ ፡ ነበር ፡ መውጣት ፡ አለመውጣቱ ፡ ጥርት ፡ ብሎ ፡ አልታዬኝም ። ቅዠት፡ ከማስጨነቁም ፡ ሌላ እንድ ፡ ከፋቱ ጥርት ፡ ብሎ ፡ አለመታ

የቱ ፡ ነው ።"

" እይ ፡ የሰም ፡ አፋኙ ፡ ላይ ፡ ይርሰሽ ፡ የሚያዝ ፡ ብርቱ ፡ ነገር ፡ ከጨበጥሽ ፡ ጥሩ ፡ ነው ።" አለ ፡ በዛብህ ፡ ምንም ፡ እን ኩዋ ፡ ልቡ ፡ መፍራቱ ፡ ባይቀር ፡ ሰብለን ፡ ለማደፋፈር ፡ ያክል ።

"እንግዲህ ፡ ልሂድና ፡ አለቃ ፡ ካሳ ፡ ምን ፡ እንዳደረጉ ፡ ልጠይቃቸው ።" አለ ፡ ቀጠለና ፡ ሁለቱም ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው፡ በዩበኩላቸው ፡ ሲያስቡ ፡ ከቆዩ በሁዋላ ።

"ተሰናድተ ፡ ጨርሶ ፡ እንደ ሆነ ፡ መቸ ፡ እንነሳለን ?"

" በሳቸው ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ካለቀማ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ ሰው፡ ሲተኛ ! ከዚህ ፡ ሰው ፡ ሲተኛ ፡ ብንነሳ ፡ ባቁዋራጭ ፡ መንገድ ፡ ሄደን ፡ ሲነጋጋ ፡ አባይ ፡ ቆላ ፡ እንደርሳለን ፡ ብለውኛል ። አንቺ መዋል ፡ ማደር ፡ የምትፈልጊበት ፡ ነገር ፡ አለ ?"

" ምንም ፡ የለ ፡ እሰናዳለሁ ።"

" ሸክም ፡ አለማብዛት ፡ ነው ።"

" አንድ ፡ የቤት ፡ እቃየ ን ፡ የምይዝበት ፡ አገልግልና ፡ አንድ ፡ መለወጫ ፡ ልብስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ አልይዝም ። ታዲ ያ ፡ ዛሬ ፡ የምንሄድ ፡ መሆናችንን ፡ ተመልሰህ ፡ ትነግረኛለህ? ወይስ --- ማን ፡ ይነግረኛል ?"

" ዛሬ ፡ የምንሄድ ፡ ከሆነ ፡ ተመልሼ ፡ ስመጣ ፡ ሰው፡እን ዳይጠረጥር ፡ አለቃ ፡ ካሳ ፡ መጥተው ፡ ቢነግሩሽ ፡ ይሻላል ። ብቻ ፡ ጊዜውን ፡ የመቀስቀሻ ፡ ምልክትም ፡ የሚሰጡሽ ፡ እንደ ሆነ ፡ ምልክቱን ፡ ይህና ፡ አድርገሽ ፡ እንድታጠኚው ፡ አደራሽ ።"

" ለሱ ፡ ግዱለም ፡ አትስጋ!"

ከዚያ ፡ እንደገና ፡ ተሳስመው ፡ በዛብህ ፡ ወደ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሄደ ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ መጽሀፋን ፡ ባትሮንስ ፡ ላይ ፡ ዘርግቶ ፡ እዩቱ መለከቱ ፡ እቤቱ ፡ ጥግ ፡ ተቀምጠ ፡ ነበር ።

" እህሀ - -! ዘማች ፡ እንኩዋን ፡ ደህና ፡ ገባህ!ና ፡ ዛሬ ፡ መምጣትህ ፡ ነው? አለ ፡ በዛብህ ፡ ያጥሩን ፡ በር ፡ ገብቶ ፡ ወደሱ፡ ሲያቀና ፡ በሩቁ ፡ አዩና ።

"ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ የተመለስሁ ፡ እንኩዋ ፡ ትናንት ፡ ማታ ፡

ነው ፤ ብቻ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በሁዋላ ፡ ስለ ፡ ደረስሁ ፡ ወደዚህ ፡ ሳል መጣ ፡ ቀረሁ ፡፡" አለ ፡ በዛብህ ፤ ትንሽ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ መንሳት ፡ ብሎ ፡፡

"ሰብለን ፡ አዩሀት ?"

"አዎ ፡ አሁን ፡ ከሰዋ ፡ ዘንድ መምጣቴ ፡ ነው ፡፡"

"እንደ ፡ ምን ፡ ናት ? ያነለት ፡ ካንተ ፡ እንደተለያየን ፡ ሄጄ ፡ ካነጋገርሁዋት ፡ ወዲህ ፡ አላዩሁዋትም ፡፡"

"ደህና ፡ ናት ፡፡"

"የሄድህበት ፡ ጉዳይሳ ፡ ቀናህ ?"

"እዎ ፤ ሲኖዳ ፡ የደግ ፡ እገር ፡ ነው ፡ ደስ ፡ እሰኝቶ ፡ ሰደ ደኝ ፡፡"

"እየውልሀ ! ስንደ ፡ የዘራ ፡ ስንዴ ፡ ያመርታል ! መልካም ፡ ባትሰራ ፡ መልካም ፡ አያደርግልህም ፡ ነበር ፡፡"

"እረ ፡ ከሰራሁት ፡ በላይ ፡ ነው ፡ የተደረገልኝ ፡፡"

"ሀሀሀ--- ሁልጊዜምኮ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ! ቁና ፡ ስንዴ ፡ ዘርቶ ጫን ፡ ስንዴ ፤ ቁና ፡ እንክርዳድ ፡ ዘርቶ ፡ ጫን ፡ እንክርዳድ ፡ እን ደሚገኝ ፡ አታውቅም ?"

"እሱ ፡ እውነት ፡ ነው !" አለ ፡ በዛብህ ፡ እንደመሳቅ ፡ ብሎ፡ "እስዎስ ---ቀናዎ ?" አለ ፡ ቀጠለና ፡፡

"በሙሉ ፡ ባይሆን ፡ በከፊል ፡፡"

"እኔ ፡ እምሳ ፡ ብር ፡ አገኘሁ ፡ ስለዚህ ፡ በቀደም ፡ እንዳሉት፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለማግኘት ፡ ከብቶችዎን ፡ ሁሉ ፡ መሸጥ --- አያስፈልግዎምኮ ፡ እንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ያክል ፡ ከተገኘ ፡ መቶ ፡ እምሳ ፡ ብር ፡ እዬቆጠብን ፡ አንድ ፡ ስራ ፡ እስከገኝ ፡ ይበቃናል ፡፡"

"መቶ ፡ ብርስ ፡ አግኝቻለሁ ፤ እንዲያውም ፡ መቶ ፡ አስር ፡ ብር ፡ አግኝቻለሁ ፡፡ የኮርቻ ፡ በቅሎዬን ፡ ስድሳ ፡ አጋሰሱን ፡ እምሳ ፡ ብር ሸጬ ፡ መቶ ፡ አስር ፡ ብር አግኝቻለሁ ፡፡"

"ደህና ፡ አውጥተዋል !"

"በጥዋና ፡ ቢሸጡ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ያወጡ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የችኮላ ፡ ዋጋ ፡ ነውና ፡ ከፉ ፡ አይደለም ፡፡ የቀንድ ፡ ከብ

ቶች ፡ ናቸው ፡ ዋጋ ያጡ ። ሁሉንም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ግዙኝ ፡ ስላልሁ ፡ ቢቸግረው ፡ ነውና ፡ በግድ ፡ ይሸጣል ፡ ብለው ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ የብድ ፡ ከብቶች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ እነሱንም ፡ እንደብድ ፡ ቆጥረዋቸው ፡ ዋጋቸውን ፡ በጣም ፡ አዋይቁብኝ ። ስለዚህ ፡ ትናንት ፡ የቢቸና ፡ ገበያ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እዚያ ፡ የተሻለ ፡ ዋጋ ፡ ያወጡ ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ አምስቱንም ፡ እዝራ ፡ ይዞዋቸው ፡ ሄደ ። ደህና ፡ ዋጋ ፡ ቢያወጡ ፡ መልካም ፡ ያለዚያ ፡ በተገኘው ፡ ዋጋ ፡ ሸጠሀቸው ፡ ና ፡ ብዬዋለሁ ፡ ዛሬ ፡ ይመጣል ።

"ዛሬ ፡ በጊዜ ፡ የሚደርስ ፡ ይመስልዎታል ፧"

"ትናንት ፡ ሸጦ ፡ ጨርሶ ፡ ዛሬ ፡ ጥዋት ፡ ቢነሳ ፡ እስካሁንም፡ ይደርስ ፡ ነበር ፡ ትናንት ፡ ያልሸጠውን ፡ ዛሬ ፡ እስኪሸጥ ፡ ከቆዬ ፡ ግን ፡ ማታ ፡ ነው ፡ የሚደርስ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዛሬ ፡ እዚህ ፡ ሳይገባ፡ እንዳይድር ፡ በጥብቅ ፡ አስጠንቅቄዋለሁ ።"

"ስብለን ፡ ---እንጃ ፡ ቅገርት ፡ መሳይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተኝተዋታል ፡ መሰለኝ ፡ ስለባባች ፡ የተገኘውን ፡ ያክል ፡ ይዘን ፡ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ እንድንነሳ ፡ ነበር ፡ አስዋም ፡ እኔም ፡ ያሰብነው ።"

"ዛሬማ ፡ ምኑን ፡ ከምን ፡ አድርገን ፡ ይሆንልናል ፧"

"ገንዘቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ብር ፡ ይበቃል ።"

አየ ---- የልጅ ፡ ነገር ! ገንዘቡም ፡ እሺ ፡ እስቲ ፡ ይብቃ ፡ ከዚህ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚሄድ ፡ ሰው ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ መሰናዶ ፡ እንኳዋ ፡ አያስፈልገውም ? ስንቅ ፡ አያስፈልገውም ? አንተም ፡ እኔም ፡ አቋዋራጭ ፡ መንገድ ፡ አናውቅ ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ አያስፈልገንም ? ሁለት ፡ በቅሎዎች ፡ ነበሩኝ ፡ ሁለቱንም ፡ ሸጫለሁ ፡ ለሰብለ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ በቅሎ ፡ እንኳዋ ፡ አያስፈልገንም ? አዬሀ ? ይህ ፡ ሁሉ ፡ ካንድ ፡ ቀን ፡ የበለጠ ፡ መሰናዶ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬና ፡ ነገ ፡ ልንጨርሰው ፡ እንችላለን ።"

"እኔ ፡ እንኳዋ ፡ ገንዘቡ ፡ ከበቃ ፡ በሰው ፡ በኩል ፡ አዝራም ፡ ቢቀር ፡ እስዋና ፡ እኔ ፡ ቀለሙን ፡ ጨምረን ፡ ሶስታችን ፡ እንበቃለን ፡ ብዬ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ቀለሙ ፡ መንገድ ፡ ማወቁን ፡

እንጃ ። ደግሞ — እንዳሉት ፡ አንድ ፡ በቅሎ ፡ ለሰብለ ፡ በግድ ፡ ያስፈልጋል ። ለመሆኑ ፡ ነገሽ ፡ ቢሆን ፡ በቅሎ ፡ እናገኛለን ? ”

“እቃው ፡ የኔ ፡ አለ ፤ በቅሎ ፡ ግን — ሰብለን ፡ ስንሰርቅ ፡ በቅሎዋን ፡ አብረን ፡ ብንሰርቅ ፡ ስለ ፡ በቅሎዋ ፡ ስርቆት ፡ በተለይ ፡ የምንከሰን ፡ አይመስለኝም ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ፡ በዛብህም ፡ አብሮ ፡ ሳቀ ።

“ ስለ ፡ መንገድ ፡ መምራቱ ፡ ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ፡ ቀጠለና፡ ” ስለ ፡ መንገድ ፡ መምራቱ ፡ እዝራ ፡ በዲማ ፡ ደብር ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ መንገዶች ፡ ይልቅ ፡ ባባይ ፡ ቆላ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ መንገዶች ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ያውቃል ፡ ስለዚህ ፡ የሰብለን፡በቅሎ፡ ለመስረቅም ፡ ይሁን ፡ ባቋራጭ ፡ መንገድ ፡ ያለሲጋት ፡ አባይን ፡ ለመሻገር ፡ እዝራ ፡ ያስፈልገናል ።”

“ በቅሎዋን ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ይሰርቃታል? የተያዘ ፡ እንደሆነ ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተበላሸ ፡ ማለት ፡ አይደለም?”

“ እቤት ፡ ገብታ ፡ ከታሰረች ፡ በሁዋላ ፡ ሰርቆ ፡ ሊያወጣት ፡ አይችልም ፤ ይያዛ ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እሚጼ፡ግጦሽ፡ ስለሆነ ፡ የምትውል ፡ ጠባቂው ፡ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ ሰርቆ ፡ ራቅ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ሸሽጎ ፡ ያውልና ፡ ከጨለመ ፡ በሁዋላ ፡ ያመጣታል ።”

“ ስለዚህ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ መነሻችን ፡ ነገ ፡ ማታ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ” አለ ፡ በዛብህ ፤ እፊቱ ፡ ላይ ፡ ቅርታ ፡ እየታየ።

“ ነገ ፡ ርግጥ ፡ እንችላለን ። እዝራ ፡ ዛሬ ፡ ይመጣል ፡ እንቆጳ ፡ የጀመረችውን ፡ ስንቅ ፡ አሰናድታ ፡ ትጨርሳለች ፡ እምስቱ ፡ ቁም ፡ ከብቶች ፡ በመጨረሻ ፡ ዝቅተኛ ፡ ዋጋ ፡ ባስር ፡ ባስር ብር ፡ እንኳ ፡ ቢሸጡ ፡ እስካሁን ፡ ከተገኘው ፡ ጋር ፡ የፊሊጉነውን ፡ ያክል ፡ ገንዘብ ፡ አገኘን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ነገ ፡ መነሳት ፡ ርግጥ ፡ እንችላለን ።”

“እንግዲያስ ፡ ይሁኑ ፡ እስዎ ፡ ለሰብለ ፡ ይንገሩዋት ፡ ወዲያውም ፡ እመጨረሻ ፡ ላይ ፡ ባንዳንድ ፡ ያልተጠና ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ መሰናከል ፡ እንዳይፈጠር ፡ ከዛሬ ፡ ጀምራ ፡ ልታደርገው የሚገባትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ ያስጠኑ

ዋት ፡ እኔም ፡ ቅድም ፡ ነግሬያታለሁ ።”

“ደህና ፡ ነው ፡ ዘምሳ ፡ በሁዋላ ፡ እሄዳለሁ ፡ አአ - - - ምሳ ፡ ስል ፡ ምሳ ፡ የሚያባላ ፡ ታስበኝ ! ዛሬስ ? ምሳ ፡ አታበላ ኝም?”

“ከቀለሙ ፡ ጋር ፡ አብረን ፡ ልንበላ ፡ ተቃጥረናል ፡ ሠዴ ያውም ፡ አምስት ፡ ብር ፡ የሚሰጠኝ ፡ ስላለ ፡ እሱን ፡ መቀበል ፡ አለብኝ ።”

“ አአ - - - ቀለሙ! ቅድም ፡ ስሙን ፡ ስታነሳ ፡ እጠይቅ ሀለሁ ፡ ስል ፡ እንነጋገረው ፡ የነበረው ፡ አስረሳኝ ። ማነሁሳ ፡ ቀለሙ?”

“ ግራ ፡ ጌታ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ፡ የሚባል ፡ የኔ፡ ወዳጅ፡ አሉ፡ ገና ፡ ወጣት ፡ ስለሆነ ፡ ምናልባት ፡ አያውቁትም ፡ ይሆናል ። እሱ ፡ ግን ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ያውቅዎታል ። ”

“ እኔንማ ፡ ማወቅ ፡ አለበት !” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ፍር ጥም ፡ ብሎ ።

“ ትልልቆች ፡ መቸም ፡ ቢሆን ፡ ይታወቃሉ ፡ ወጣቶች ፡ ግን ፡ ከትልልቆች ፡ ጋር ፡ በሚውሉበት ፡ እድሜ ፡ እስኪደርሱ ፡ በጉዋደኞቻቸው ፡ መሀከል ፡ ካልሆነ ፡ በትልልቆች ፡ ዘንድ ፡ አይታወቁም ፡ ማለቴ ፡ ነው ። ” አለ ፡ በቀብሀ ፡ የጉዱ ፡ ካሳን ፡ አሽሙር ፡ ካይኑም ፡ ከፊቱም ፡ ሲያይ ፡ ለፊተኛው ፡ ንግግሩ ፡ እሱ ፡ ያላሰበውን ፡ ትርጉም ፡ እንደሰጠበት ፡ ገምቶ ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ አለና ።

“ እውነትህ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ፡ እንዲታወቅ ፡ ትልቅ ፡ መሆን ፡ አለበት ! ወይም . . .ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የተለዩ ፡ መሆን ፡ አለበት !”

“ እንዴት ፡ የተለዩ ?”

“ ምንም ፡ ይሁን ፡ ይለይ ፡ ብቻ !ከሰው ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ጌታ ፡ ሆኖ ፡ ሀር ፡ አዘውትሮ ፡ እዩለበሰ ፡ የሚሄድ ፡ የሚያገለ ድመው ፡ ቆዳ ፡ እስኪያጣ ፡ ድሀ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሁ ፡ ራቁቱን ፡ በሰው ፡ መሀከል ፡ የሚሄድ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ረዝሞ ፡ ዛፍ ፡ የሚ ያክል ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ አጥሮ ፡ እንቅፋት ፡ የሚያክል ፡ ከሰው ፡

ሁሉ ፡ ነጥቶ ፡ ወተት ፡ የሚመስል ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ጠቁር ፡ ከሰል ፡ የሚመስል ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ አዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ሰው ፡ ያልደረሰበትን ፡ የሚያስብና ፡ የሚናገር ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ የባሰ ፡ አላዋቂ ፡ ሆኖ ፡ መናገር ፡ እንኳዋ ፡ የማይችል ፡ እንዲህ ፡ ያለው ሁሉ ፡ ከሌላው ፡ ሰው ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጉድ ፡ ተቆጥሮ ፡ እንኳዋንስ ፡ በሚኖርበት ፡ አገር ፡ በሩቅም ፡ በወሬ ፡ ይታወቃል ፤ እኔም ፡ እንዲህ ፡ ካሉት ፡ ጉዶች ፡ ተቆጥሬ ፡ የማላውቃቸው ፡ ሁሉ ፡ ያውቁኛል ። ስለዚህ ፡ ቀለሙ ፡ ሳላውቀው ፡ ቢያውቀኝ ፡ የሚያስገርም ፡ አይደለም ፡ ማለቴ ፡ነው !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አሁንም ፡ እሽሙሩ ፡ ከሬቱ ፡ ሳይጠፋ ።

"ታዲያኮ ፡ አሁን ፡ እሰዎ ፡ እንዳሉት ፡ ገና ፡ ሰው ፡ ያልደረሰበትን ፡ የሚያስብና ፡ የሚናገር ፡ አዋቂ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ . . . ." አለና ፡ ለመጨረሻው ፡ ቃል ፡ መለወጫ ፡ ሲያስብ፦

"ጉድ ፡ አይባልም ፡ በል ፡ አያዞህ ፡ ስሜ ፡ ነው ፡ አትፍራ !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አቋርጦ ፡ በዛብህ ፡ ሲቸገር ፡ ተመለከተና ። በዛብህ ፡ ዝም ፡ አለ ።

"አዩህ ?" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ቀጥሎ ። "አዩህ ? ከተለመደው ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ጉድ ፡ መታየቱ ፡ እንኳዋ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይቀርም ። ብቻ ፡ የሚያሳዝነው ፡ ያ ፡ ከተለመደው ፡ ልዩ ፡ በመሆኑ ፡ ጉድ ፡ የተባለው ፡ ልዩነቱ ፡ በመልካም ፡ ወይስ ፡ በክፉ ፡ መንገድ ፡ መሆኑን ፡ ማመዛዘን ፡ በማይችል ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ መኖሩ ፡ መልካሙ ፡ ከክፉ ፡ የሚጠቅመው ፡ ከሚጎዳ ፡ ሳይለይ ፡ ከተለመደው ፡ ልዩ ፡ በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ሁሉም ፡ ባንድነት ፡ ታፍኖ ፡ ተሸፍኖ ፡ እንዲሁ ፡ መቅረቱ ፡ ነው ። ከተለመደው ፡ የተለዩ ፡ መልካም ፡ አሳብ ፡ ወይም፡ መልካም ፡ ስራ ፡ ለጊዜው ፡ እንኳዋ ፡ ባያገለግል ፡ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ እንዲያገለግል ፡ ተጠብቆ ፡ ተሸሽጎ ፡ የሚቆይ ፡ ቢሆን ፡ ካሳቢው ፡ ወይም ፡ ከሰሪው ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ የማያልፍ ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ነበር !"

"መልካም ፡ አሳብና ፡ መልካም ፡ ስራ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይጠፉም ፡ በሚባለው ፡ አያምኑም ?"

" እምናለሁ ፡ እንጂ ! እምናለሁ ። መልካም ፡ አሳብና ፡ መልካም ፡ ስራ ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ የተለመደውን ፡ ጎጂ ፡ አሳብና ፡ ስራ ፡ ሊለውጥ ፡ ባይችል ፡ እንዳይጠፉ ፡ ተቀብሎ ፡ አቆይቶ ፡ ለተከታዩ ፡ ትውልድ ፡ የሚያስተላልፈው ፡ ከተገኘ ፡ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ያገለግላል ፡ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ይጠቅማል ። በጭራሽ ፡ ተቀባይ ፡ ካጣ ፡ ግን ፡ አሳቢው ፡ ወይም ፡ ሰሪው ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ጠፊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አሳቡና ፡ ስራውም ፡ አብሮት ፡ ያልፋል ፡ አብሮት ፡ ይጠፋል ። ይህ ፡ ነው ፡ የሚያሳዝነው ። "

"አየ ፡ ...ጸጥንና ፡ ጅረት ፡ ሁልጊዜ ፡ ወደሁዋላ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ ምንኛ ፡ እውነት ፡ ነው !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆይቶ ።

"እንዴት ?"

"ቀደም ፡ ብዬ ፡ ተዋውቄው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ በቆየሁበት ፡ ጊዜ ፡ ከሱም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ እማር ፡ ነበር ! "

" ቀደም ፡ ብለን ፡ ተዋውቀንስ ፡ ቢሆን ፡ ለእኔም ፡ ብዙ ፡ ሸክም ፡ ታቃልልኝ ፡ ነበር ። "

"የምን ፡ ሸክም ?"

" ሰው ፡ የሚናገረውን ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በጥሞና ፡ ሰምቶ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ተሳስተሀል ፡ የሚለው ፡ አሳቡን ፡ የሚያካፍለው ፡ ማግኘት ፡ እንዴት ፡ እረፍት ፡ ይመስልሀል ! ብናገርስ ፡ ላይሰሙኝ ፡ መቀለጃና ፡ የከንፈር ፡ መምጠጫ ፡ ለመሆን ፡ ምን ፡ አናገረኝ ፡ ብሎ ፡ ታፍኖ ፡ ኖሮ ፡ እንደ ፡ ታፈኑ ፡ መሞት ፡ ከባድ ፡ ሸክምኮ ፡ ነው ! አይመስልህም ?"

"እሱስ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ ብቻ --- እዚህ --- እቤትም ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ማስተማርና ፡ የአሳብ ፡ ተካፋይ ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም ? ጊዜ ፡ ይወስድ ፡ ይሆናል ፤ መቻሉን ፡ ግን ፡ ይቻላልኮ !"

"በመሰረቱ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ሞከሬ ፡ አቃተኝ ።"

"እንዴት ? ለምን ?"

"ሰው ፡ ሁሉ ፡ አብድ ፡ ነው ፤ ጉድ ፡ ነው ፤ ሲል ፡ እዩሰሙ ፡ ይወዱኛል ፤ ያዝኑልኛል ፡ እንጂ ፡ የምናገረውን ፡ አያምኑም ። የምናገረው ፡ የምሰራው ፡ ከተለመደውና ፡ እነሱም ፡ ከሚያውቁት ፡ ልዩ ፡ ስለሆነ ፡ እውነትም ፡ ሰው ፡ እንደሚለው ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ ይላሉ ።"

"አብረዎ ፡ ተቀምጠው ፡ እያዩዎ ፡ እያወቁዎ ፡ የማያውቁትን ፡ ትተው ፡ የሰሙትን ፡ ያምናሉ ?"

"የሚያስገርመው ፡ ይህ ፡ አይደለም ? እንኳዋን ፡ ስለኔ ፡ ስለራሳቸውም ፡ እነሱ ፡ ከሚያውቁት ፡ ይልቅ ፡ አብዛኛው ፡ ሰው የሚለውን የሚያምኑ ናቸው ።"

"እንጃ ! ግስ·ተዋል ፡ አ·ቃተኝ !"

"እውነትህ ፡ ነው ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ብቻ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ፡ አዝራም ፡ ዳዊትም ፡ ዳዊትን ፡ ገና ፡ አላዩኸውም ፡ መስለኝ ፡ ድሮ ፡ የናቴ ፡ አገልጋይ ፡ የነበረ ፡ ነው ፡ ስሙም ፡ ወልዴ ፡ ነበር ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ከመጡ ፡ ዳዊት ፡ ደግመው ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ ጽህፈትም ፡ አውቀዋል ። በመልክም ፡ ከማንም ፡ አያንሱ ፡ እንዲያውም ፡ ጮቀዎች ፡ ናን ፡ ከሚሉት ፡ ከብዙዎቹ ፡ ይሻሉ ፡ ይዞርናል ። ስለዚህ ፡ ገመልክም ፡ ይሁን ፡ በሙያ ፡ ከማንም ፡ እንደማያንሱ ፡ ራሳቸው ፡ የሚያውቁት ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ እኔ ፡ በዩለቱ ፡ ስነግራቸው ፡ ይህን ፡ ትተው ፡ ከሰው ፡ እኩል ፡ እንዳልሆኑ ፡ ለሰው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ እንዳልተፈጠሩ ፡ አብዛኛው ፡ ሰው ፡ አምና ፡ ስላሳመናቸው ፡ ይህኑ ፡ ተቀብለው ፡ በዚሁ ፡ አምነው ፡ ይኖራሉ ። የለም ፡ ይህ ፡ እውነት ፡ አይደለም ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ናችሁ ፡ ስላቸው ፡ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚለው ፡ ጤና ፡ ባይሆን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሲያዝኑልኝ ፡ አይና ፡ እኔም ፡ አዝኜ ፡ ዝም ፡ እላለሁ ። በቀደም ፡ አዝራ ፡ ያለውን ፡ ታስታውሳለህ ? 'ተወልጂ ፡ እስካረጅ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቀኝ ፡ በፈረንጂ ፡ ስም ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ተነስቼ ፡ አዝራ ፡ ነኝ ፡ ብል ፡ ማን ፡ አሺ ፡ ይለኛል ? አዝራ ፡ ነኝ ፡ ስል ፡ እንዳይሳቅብኝ ፡ ፈረንጂ ፡ እንደ ፡ ተባልሁ ፡ ብቀር ፡ ይሻለኛል !' ያለው ፡ ለዚህ ፡ ማስረጃ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ከማንም ፡ አናንስም ፡ ብለው ፡ ሲከራከሩ ፡ ሰው ፡ ከሚሰቅባቸው ፡ ሰው ፡

ናችሁ ፡ ያላቸውን ፡ ተቀብለው ፡ መኖር ፡ የሚመርጡ ፡ ደካሞች ፡ ናቸው ። እንቆጳ ፡ ብቻ ፡ አሳብዋ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መስናዶ ፡ ሆነና ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ስታነሳባት ፡ ጭራሽ ፡ አይጥማትም ፡ እንጂ ፡ እሰዋ ፡ ደህና ፡ ጉዋደኛ ፡ ልትሆን ፡ ትችል ፡ ነበር ። እሰዋን ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብዬ ፡ ምሽቴ ፡ ልትሆን ፡ የምትችል ፡ መሆንዋን ፡ አሳመንሁ ፡ ያሳቤ ፡ ሁሉ ፡ ተካፋይ ፡ ጉዋደኛየ፡ ለማድረግ ፡ ግን ፡ ገና ፡ አልቻልሁም ።"

"ግሩም ፡ ነው ! እሱቴ ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ እንነጋገረው ፤ ዛሬ ፡ የሚያልቅ ፡ አይደለም !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ወደ ፡ ጉዋደኛው ፡ ቤት ፡ ለመሄድ ፡ እሰቦ።

"በል ፡ ሂድ ፡ እንግዴህ ፡ ምሳ ፡ አላበላህም ፡ ካልኸኝ ! ማን ፡ ያውቃል ? አንተና ፡ ሰብለ ፡ አዲስ አበባ ፡ ደህና ፡ ቦታ ፡ ይዛችሁ ፡ እዚያ ፡ ነዋሪዎች ፡ ከሆናችሁ ፡ እንዲያውም ፡ ወደዚያው ፡ ትሰቡኝ ፡ ይሆናል !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፤ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

"እሱማ ፡ እግዚአብሔር ፡ አደለን ፡ ማለት ፡ ነበር ።"

# ምዕራፍ ፡ ፸፯ ፡
# የብራ ፡ መብረቅ ፡

ከምሳ ፡ በሁዋላ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ሄዶ ፡ ጉዞው ፡ በተከታዩ ፡ ሌሊት ፡ መሆኑንና ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ መጥቶ ፡ የሚወስዳት ፡ መሆኑን ፡ ነገራት ።

"ምልክት ፡ ሊያሳስትም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሊያነቃም ፡ ስለሚችል ፡ በምልክት ፡ ከመጥራት ፡ ሰው ፡ ሲተኛ ፡ እውድቅት ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ መጥቼ ፡ ብወስድሽ ፡ የሚሻል ፡ መሰለኝ ። ስለዚህ ፡ የስርቆሽ ፡ በሩም ፡ የቤትሽም ፡ መዝጊያ ፡ ሳይዘጋ ፡ እንዲሁ ፡ ገርበብ ፡ ብሎ ፡ እንዲቆይ ፡ አድርጊው ። የምትወስጂውን ፡ ልብስና ፡ እቃም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አሳስረሽ ፡ ባጠገብሽ ፡ አቆይው ፤ እንደ ፡ መጣሁ ፡ ምንም ፡ ድምጽ ፡ ሳናሰማ ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ ትነስተን ፡ እንድንሄድ !" አለ ።

"እሺ ።"

"እዚህ ፡ መደብ ፡ ላይ ፡ ሀብትሽ ፡ ናት ፡ የምትተኛ ?"

"አዎ ፡ ሀብትሽ ፡ ናት ። ብቻ ፡ ለስሙ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ የማታድርበት ፡ ጊዜ ፡ ይበልጣል ። በምታድርበትም ፡ ጊዜ ፡ የቀን ፡ እብደትዋ ፡ አድክሞዋት ፡ ጎንዋ ፡ ገና ፡ መደቡን ፡ ከመንካቱ ፡ ኩረርዋ ፡ ይቀድማል ፡ እንስተህ ፡ ገደል ፡ ብትወረውራት ፡ አትሰማም ።"

"መልካም ፡ ብቻ ፡ ለማናቸውም ፡ ድምጽ ፡ ሳናሰማ ፡ እንድንሄድ ፡ የስርቆሽ ፡ በሩም ፡ የእዚህ ፡ ቤት ፡ መዝጊያም ፡ እንዳይዘጋ ፡ አደራሽ ! ያለዚያ ፡ አከፍታለሁ ፡ ስል ፡ ሰው ፡ ይነቃል ።"

"ግዴለም ፡ ሰው ፡ ከተኛ ፡ በሁዋላ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ የተዘጋ ፡ እንዲመስል ፡ ገርበብ ፡ አድርጌ ፡ እተወዋለሁ ። ብቻ ፡ ልቤ ፡ በጣም ፡ ተሸበረብኝ ፡ አያ ፡ ካሳ ፡ ለምን ፡ ይሆን ? አለች ፡ ሰብለ ፡ እንገትዋን ፡ ትንሽ ፡ ሰበር ፡ አድርጋ ፡ አጎትዋን ፡ እየተመለከተች ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከደስታዋ ፡ መሀከል ፡ ልብዋን ፡ የሚያሸብረው ፡ ፍራትና ፡ ጭንቀት ፡ በጥሩ ፡ ፊትዋ ፡ ላይ ፡ ጎልቶ ፡ ታዩውና ፡ ለፍራ

ትዋም ፡ ለጭንቀትዋም ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ እሱ ፡ የፈጠረው ፡ አሳብ ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መፍራት ፡ አለ ።

"ይህን የመሰለ ፡ ጉዞ ፡ ሲታሰብ ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ልብ ፡ መሸበሩ ፡ አይቀርም ፡ አሁን ፡ የኔም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፡ ያንቺ ፡ ብቻ ፡ አይምሰልሽ ። ስለዚህ መፍራት ፡ አያስፈልግም ።" አለ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ቆይቶ ።

"አይ ፡ እንዲያው — ልቤ ፡ መሸበሩን ፡ ሆዴን ፡ ባርባር ፡ ማለቱን ፡ ነገርሁህ ፡ እንጂ ፡ መፍራትስ—ምንም ፡ ቢሆን ፡ አልፈራ! ፍራት ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ እንዴ? ፍራት ፡ ማለት —ለማድረግ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ነገር ፡ ፈርቶ ፡ መተው ፡ አይደለም? የኔ ፡ እንደሱ ፡ አይደለምኮ! እንዲያው ፡ ሆዴን ፡ ባርባር ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ።"

"የለም ፡ ፍራት አይደለም ፡ እንዲያው — የልብ ፡ መሸበር ፡ ነው ።" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ትንሽ ፡ የቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ

"እየው ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ቀልድህ ፡ ስትሄድ! እኔ ፡ ዉን ቆኝ ፡ ስጠይቅህ ፡ አንተ ፡ ትቀልዳለህ ።" አለች ፡ ሰብለ ፡ እሷም ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ።

"ሙች ፡ እውነቴን ፡ ነው ፡ ቀልድ ፡ አይደለም ። ፍራትና ፡ የልብ ፡ መሸበር ፡ አንድ ፡ አይደለም ።"

"እንዴት ፡ ነው?"

"ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ በጣም ፡ የምትወጂውን ፡ ነገር ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ ታገኛለሽ ፡ ቢሉሽ ፡ እስክታገኚው ፡ ድረስ ፡ ልብሽ ፡ ሲሸበር ፡ ይቆያል ። ታዲያ ፡ ይሄ ፡ ናፍቆት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፍራት ፡ አይባልም ። አሁንም ፡ አንቺ ፡ ከዚህ ፡ ወጥተሽ ፡ ባሰብሽ በት ፡ እስክትደርሺ ፡ ስለምትናፍቂ ፡ ልብሽ ፡ ቢሸበር ፡ ፈራሽ ፡ አትባይም ፡ ማለቴ ፡ ነው ።"

ሰብለ ፡ አጎትዋ ፡ የተናገረው ፡ ለሚሰማት ፡ የልብ ፡ ሽብርና ፡ የሆድ ፡ ባርባርታ ፡ መልስ ፡ ሊሆን ፡ ይችል ፡ እንደሆነ ፡ ለማየት ፡ አይንዋን ፡ እጣራው ፡ ላይ ፡ ተክላ ዝም ፡ ብላ ፡ ስታስብ ፡ ቆይታ ፡ እጅግም ፡ አጥግቦ ፡ አላጠገባት ፡ ስላለ ፡- "እህሁ—ግዴለም ፡ ይሁን!" አለች ፡ በረዥሙ ፡ ተንፍሳ ፡ ቅርታና ፡ ፈገግታ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ባስጌጡት ፡ አስተያየት ፡ አጎትዋን ፡ እያዩች ።

“እሀሀ — አይዞሽ ፡ ምንም ፡ አንሆን ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ በረዥሙ ፡ ተንፍሶ ፡ ለመሄድ ፡ ቢነሳ ።

ከሰብለ ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፡ የስንቁ ፡ መሰናዶ ፡ እምን ፡ እንደደረሰ ፡ እንቆጳን ፡ ጠየቃት ።

“በኔ ፡ በኩል ፡ ላለው ፡ አትስጋ ፡ ሁሉን ፡ አሰናድቼ ፡ ጨርሼ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ አቀርብልሀለሁ !” አለች ፡ እንቆጳ ።

“ ምን ፡ ምን ፡ አሰናድተሽ ፡ ጨርሰሻል ? ምንስ ፡ ነው ፡ የቀረሽ ? ”

“ዳቦ ፡ ቆሎና የግር ፡ ተልባ ፡ ላራት ፡ ወይም ፡ ላምስት ፡ ሰው ፡ ለሳምንት ፡ የሚበቃ ። እሱ ፡ አልቆዋል ። አንድ ፡ በል ! ቁዋንጣው ፡ ከተዘለዘለ ፡ ዛሬ ፡ ሶስት ፡ ቀኑ ፡ ስለሆነ ፡ ማምሻውን ፡ ይደርቃል ። ሁለት ፡ በል ! የግር ፡ በሶውን ፡ አሁን ፡ በማሰናዳት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፡ ዛሬ ፡ ማምሻየን ፡ እጨርሳለሁ ። ሶስት ፡ አትልም ? በቃ ፡ ይሆን ፡ ሁሉ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ በተራ ፡ እፊትህ ፡ አሰልፍልሀለሁ ። ከዚያ ፡ በየመልኩ ፡ አግብቶ ፡ ማሰሩ ፡ የናንተ ፡ የወንዶች ፡ ፈንታ ፡ ነው ! ” አለች ፡ እንቆጳ ፡ አንገትዋን ፡ ትንሽ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ዘንበል ፡ ውብ ፡ ጥርስዋን ፡ በከፊል ፡ ገለጥ ፡ አድርጋ ፡ ባልዋን ፡ እያዩች ።

“ዳቦ ፡ ቆሎ ፡ የግር ፡ በሶ ፡ የግር ተልባ ፡ ቁዋንጣ ፡ አራት ፡ አይነት ፡ ነው ፡ ሶስት ፡ አይደለም ! ያሰናዳሽውን ፡ መቁጠር ፡ አታውቂም ፡ ማለት ፡ ነው !” አለ ፡ እሱም ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ። “ጥሩ ፡ ነው ፡ ይበቃል ። ብዙ ፡ ስንቅ ፡ የሚሸከም ፡ ሳይበላው ፡ ይወድቃል ፡ የሚሉት ፡ ተረት ፡ እንዳይደርስብን ፡ ስንቅ ፡ በልኩ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ ጥሩ ። ስለዚህ ፡ ይበቃል ።” አለ ፡ ቀጠለና።

“ እረ ፡ ለመሆኑ ፡- ባልዋ ፡ የሚሄድበትን ፡ ሳታውቅ ፡ ስንቅ ፡ አሰናድታ ፡ የምትሸኝ ፡ ምሽት ፡ አይተህ ፡ ታውቃለህ ? ”

“ ባሎቻቸው ፡ የትም ፡ ሄደው ፡ በደህና ፡ እንዲመለሱላቸው ፡ የሚፈልጉ ፡ ምሽቶች ፡ ሁሉ ፡ የት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ ብለው ፡ አይጠይቁም ! ”

“ እዚህ ፡ እሄዳለሁ ፡ ያላለ ፡ ሰው ፡ ቢጠፋስ ፡ ወዴት ፡ ተብሎ ፡ ይፈለጋል ? ”

“ ምነው ፡ ነገረሽ ? ያርሺ ፡ እስክመለስ ፡ እንኩዋንስ ፡ የምሄድበትን ፡ መሄዴንም ፡ ማንም ፡ እንዲያውቅ ፡ አልፈል

ማም ፡ አላልሁሽም ! ስመለስ ፡ ላንቺ ፡ ብቻ ፡ እነግርሻለሁ ፤ ለሌላው ፡ ግን ፡ ሁልጊዜም ፡ ምሥጢር ፡ እንደሆነ ፡ የሚቀር ፡ ነው ።”

“የምትሄድበት ፡ ምክንያት ፡ ምሥጢር ፡ ሆኖ ፡ ይቆይ ፡ እንደሆነ ፡ እንጃ ፡ እንጂ ፡ የምትሄድ ፡ መሆንህስ ፡ ገና ፡ ድሮ ፡ ታውቆልሀል ! ”

“ እንዴት ! ማን ፡ ያውቃል ? ማን ፡ ተናገረ ? ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፤ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ ብሎ ።

“ ምን ፡ አውቃለሁ ! እንዲሁ ፡ በግምት ፡ ይሆናላ ! ነፍስ ፡ ገድሎ ፡ - - - ሊሸሽ ፡ ከብቱን ፡ ሁሉ ፡ ይሸጣል ፤ ሲልሸጥ ፡ ያለውንም ፡ ያሸሻል ፡- እየተባለ ፡ በከተማው ፡ ይወራል ፤ ብሎ ፡ ቅድም ፡ ወልዴ ፡ ሲነግረኝ ፡ ነበር ። ” አለች ፡ እንቆጳ ፤ ባልዋ ፡ ሲደነግጥ ፡ አይታ ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ፡ አለችና ።

“ ዳዊት ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ያወራሽ ? ”

“ አዎን ፡ ዳዊት ፤ ወልዴ ። ”

“ መጀመሪያ ፡ ባገሩ ፡ የተገደለ ፡ ሰው ፡ ሳይኖር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ገዳይ ፡ የሆንሁት ? ደግሞስ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ከብት ፡ ያሸሸሁ ? ”

“ ፈረጃ ፡ ለመሸጥ ፡ ብቻና ፡ የወሰዳቸውን ፡ ከብቶች ፡ ለማሸሽ ፡ የሰደድሀቸው ፡ መስሎ ፡ ታይቶ ፡ ይሆናል ። ብቻ ፡ እኔኮ ፡ የሚወራውን ፡ ነገርሁህ ፡ እንጂ ፡ ወሬውን ፡ አላወራሁም ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ጥያቄህን ፡ መጠየቅ ፡ ያወሩትን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔን አይደለም !” አለች ፡ እንቆጳ ፤ በቀልድ ፡ መልክ

“ይገርማል ! ብዙ ፡ ሰውኮ ፡ የስራትም ፡ የሞት ፡ ፍርድም ፡ የሚፈረድበት ፡ እንዲሁ ፡ በግምት ፡ በተነሳ ፡ ወሬ ፡ ነው ! መጀመሪያ ፡ በግምት ፡ ተናጋሪው ፡- እንዲህ ፡ ወይም ፡ እንዲያ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ብሎ ፡ ይናገራል ። ያን ፡ የሰማው ፡ ሄዶ ፡ እንዲህ ፡ ወይም ፡ እንዲያ ፡ ሆነ ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ ያወራል ። ከዚያ ፡ እንዲህ ፡ ወይም ፡ እንዲያ ፡ አደረገ ፡ ተብሎ ፡ የተወራበት ፡ ሰው ፡ ተጠርጥሮ ፡ ይያዛል ። ከዚያ ፡ ተፈርዶበት ፡ ይታሰራል ፤ ወይም ፡ ይሞታል ። አሁን ፡ ባጋጣሚ ፡ የተገደለ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ እኔ ፡ ተጠርጥሬ ፡ እያዝ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ! ”

“እየውልህ ! ከብት ፡ የሚሸጡበትንና ፡ የሚሄዱበትን ፡ ግልጥ ፡ አድርገው ፡ የሚናገሩ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ከግምት ፡ ተነ

ሰቶ ፡ ከሚታመን ፡ እስኪ ፡ ወሬ ፡ ያመልጣሉ ! ” አለች ፡ እንቆጳ ፡ አሁንም ፡ እዬሳቀች ።

“ እንዲያው ፡ ነገሩን ፡ እልሁ ፡ እንጂ ፡ የኔውስ ፡ እዚህም ፡ አያደርስ ! ያሁኑ ፡ ግምት ፡ እስኪ ፡ ደረጃ ፡ ሳይደርስ ፡ እኔ ፡ ከሄድሁበት ፡ ተመልሼ ፡ እመጣና ፡ ይሄ ፡ ቀርቶ ፡ አዲስ ፡ ግምት ፡ ይገመታል ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ።

“ እሁሁ - - - በል ፡ ተወው ፡ እንግዲህ ! ” አለችና ፡ እንቆጳ ፡ የፈለገችውን ፡ ወሬ ፡ ልታገኝ ፡ ሳትችል ፡ በመቅረትዋ ፡ በረዥሙ ፡ ተንፍሳ ፡ ወደ ፡ ስራዋ ፡ ሄደች ።

በዛብህ ፡ በበኩሉ ፡ ምሳውን ፡ እግራ ፡ ጌታ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ቤት ፡ በልቶ ፡ ከጉዋደኛው ፡ አምስት ፡ ብሩን ፡ ተቀብሎ ፡ ወደ ፡ ተማሪቤቱ ፡ ሄደና ፡ ወላጆቹ ፡ ሲሞቱ ፡ በባላደራ ፡ እጅ ፡ የተውትን ፡ ከብትና ፡ ንብረት ፡ ለማደራጀት ፡ ወደ ፡ ማንኩሳ ፡ በተከታዩ ፡ ቀን ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑን ፡ ለመምህሩ ፡ ላለቃ ፡ ክንፉና ፡ ለጉዋደኞቹም ፡ ለወዳጆቹም ፡ ነግሮ ፡ ከቃው ፡ ለሰው ፡ የሚሰጠውን ፡ ሲሰጥ ፡ የሚወስደውን ፡ እዬመረጠ ፡ ባንድ ፡ ከረጢት ፡ ሲከት ፡ አመሸ ።

“አይደለም ! ሄድህ ፡ እንጂ ፡ የሞትህ ፡ ይመስል ፡ እቃህን ፡ እኛ ፡ የምንወርስበት ፡ ምክናያት ፡ ምንድነው ? ስትመለስ ፡ አይጠቅምህም ? ” አለ ፡ ይትባረክ ፡ የሚባለው ፡ በዛብህ ፡ እቃውን ፡ ከከፋፈላቸው ፡ ወዳጆቹ ፡ አንዱ ።

“ሰው ፡ ሲሄድ ፡ መሄዱ ፡ ርግጥ ፡ ነው ፡ መመለሱ ፡ ግን ፡ ምኞት ፡ ነው ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

“ አገርህ ፡ ሄደህ ፡ ለመቅረት ፡ ታስባለህ ፡ እንዴት ? ”

“ እኔስ ፡ ቶሎ ፡ ለመመለስ ፡ ነው ፡ የማስብ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፈጻሚው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ! በዛሬና ፡ እመለሳለሁ ፡ ብዬ ፡ በማስብበት ፡ ቀን ፡ መሀከል ፡ የሚሆነውን ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ማን ፡ ሊያውቅ ፡ ይችላል ? ”

“ እሱስ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፤ እንኩዋን ፡ በዛሬና ፡ ልትመለስ ፡ በምታስብበት ፡ ጊዜ ፡- በዛሬና ፡ በነገ ፡ መሀከልስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያደርገውን ፡ ማን ፡ ያውቃል ? ” አለ ፡ ይትባረክ ።

እውነትስ ፡ በዛሬና ፡ በነገ ፡ መሀከል ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያደርገውን ፡ ማን ፡ ያውቃል ? ይህ ፡ ይትባረክ ፡ አፉ ፡ እንዳመጣው ፡ የተናገረው ፡ በዛብህን ፡ አስደነገጠው ።

ማታ ፡ ከራት ፡ በፊት ፡ እጉዱ ፡ ካሳ ፡ ቤት ፡ ሄዶ ፡ እዝራ ፡ መመለስ ፡ አለመመለሱን ፡ ለማወቅ ፡ ፈለገና ፡ የይሉኝታ ፡ ስሜት ፡ ተሰማው ።

"በምክናያቱ፡ ራት፡ ፍለጋ ፡ መጣ ፡ ይሉኝ ፡ ይሆን ? ይበሉኛ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ! ብላ ፡ ካለኝም ፡ እበላለሁ! ነገር ፡ ግን፡ራት፡ ፍለጋ ፡ አለመሄዴን ፡ እግዜርና ፡ እኔ ፡ እናውቃለን!" አለ ። ከዚያ ፡ እጉዱ ፡ ካሳ ፡ ቤት ፡ ቢሄድ ፡ እደጅ ፡ ብቻውን ፡ ተቀምጦ ፡ አገኘው ። በዛብህ ፡ ያጥሩን ፡ በር ፡ ሲገባ ፡–

"ማነህ ፡ አንተ? እዝራ ፡ ነህ?" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በዛብህን፡ ከሩቅ ፡ ሲያይ ፡ እዝራ ፡ የመጣ ፡ መስሎት ።

"በዛብህ ፡ ነኝ ፡ እዝራ ፡ ተመለሰ ?"

" የለም ፡ አልተመለሰም ፡ አሁን ፡ መምጫው ፡ ነው ። አንተን ፡ ከሩቅ ፡ ሳይህ ፡ እሱ ፡ የመጣ ፡ መስሎኝ ፡ ነው!"

"እስካሁን ፡ ካልመጣ ፡ ከነገዴህ ፡ ይመጣል ፡ ብለው ፡ ነው?"

"ሳይገባ ፡ አያድርም ፡ ይህን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አትጠርጥር!"

"ታዲያ ፡ ለምን ፡ ብቻዎን ፡ እዚህ ፡ ተቀመጡ!" አለ ፡ በዛብህ ! እጉዱ ፡ ካሳ ፡ አጠገብ ፡ ሄዶ ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ።

"እዝራን ፡ እጠብቃለሁ ! ወዲያውም ፡ ጨረቃዋ ፡ ደስ ፡ ብላኝ ፡ እሷዋን ፡ ሽቅብ ፡ እየተመለከትሁ ፡ የነገ ፡ ጉዞዋችንን ፡ አሰላስላለሁ ። በሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ መጉዋዝ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ምልኪውን ፡ ተከትዬ ፡ አይደለም ፡ ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ የምልህ ! ልብ ፡ አድርግ! እኔ ፡ በምልኪ ፡ አላምንም! ከምልኪው ፡ ውጭ ፡ ነው ።"

" እንደ ፡ ምልኪውማ ፡ ከሆነ ፡ አዲስ ፡ ጨረቃ ፡ ነው ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ የሚባል !. ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ ነው ፡ እንዴ ! "

"እንደ ፡ ምልኪውም ፡ ቢሆን ፡ ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ ነው ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ የሚባል ! ብቻ ፡ እኔ ፡ ለሌሊት ፡ ጉዞ ፡ ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ ነው፡ ጥሩ ፡ ያልሁህ ፡- አዲስ ፡ ጨረቃ ፡ በጊዜ ፡ ትወጣና ፡ ሌሊቱ ፡ ሲከብድ ፡ እጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ጥላህ ፡ ትጠፋለች ። ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ የሆነች ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ እያበራች ፡ ስትመራህ፡ አድራ ፡ ሲነጋ ፡ ለጸሀይ ፡ ታስረክብሀለች ። አዬህ ? ሙሉ ፡ ጨረቃ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ታማኝና ፡ ባለቁርጥ ፡ ጉዋደኛ ፡ በጣም ፡ በምትፈለግበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ትገኛለች ፤ በማትፈለግበት ፡ ጊዜ ፡ አይደለም !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፤ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

"እውነት ፡ ነው!" ለካስ ፡ እኔ ፡ የሰማሁት ፤ ግልብጦሹን፡ ኖርዋል!"

"አዎ ፤ አየውልህ! ነገ ፡ ይህችን ፡ በመሰለች ፡ ጨረቃ ፡ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ሲተኛ ፡ እውድቅት ፡ ላይ ፡ ተነስተን ፡ ባቁዋራጭ ፡ መንገድ ፡ የገሰገስን ፡ እንደሆነ ፡ አባይ ፡ ወንዝ ፡ እንደር ሳለን ።"

" የዘነመ ፡ እንደሆነ ፡ ጭቃውና ፡ ዝናሙ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ያስሄደን ፡ ይሆን?"

"አፋፉን ፡ ከተዘቀዘቅን ፡ ቆላው ፡ ጭቃ ፡ የለውም ፤ አሸዋ ፡ ነው ። ዝናምም ፡ በጨረቃ ፡ የለም ፡ የዛሬውን ፡ ሰማይ ፡ አኳዋውም ፤ የተወለወለ ፡ መስተዋት ፡ መስሎ ! " አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፤ ሰማዩን ፡ ሽቅብ ፡ እያዬ ።

" ውሀውስ ፡ አይሞላም? ዛሬኮ ፡ ሀምሌ ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ላይ ፡ ነው!"

"ውሀውስ ፡ መሙያው ፡ ነው ፤ ብቻ ፡ በዲማና ፡ በቢቸና፡ መሀከል ፡ ወርዶ ፡ በጋ ፡ ከክረምት ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ የሚያሻግር፡ ሰፊ ፡ ‹‹ልካ ፡ አለ ፡ እያለ ፡ አዝራ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲናገር ፡ ሰምቻለሁ ። እዚያ ፡ በደህና ፡ እንድረስ ፡ እንጂ ፡ ግዴለም ፤ አንቸገርም ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ የማያዘወትረው ፡ አንዱ፡ ጥቅሙ ፡ ሽፍታ ፡ አይኖርበትም ። ለመሆኑ ፡ ራት ፡ በልተሀል ? አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

"ገና ፡ ነኝ ፤ አሁን ፡ ሄጄ ፡ እበላለሁ ።"

"ጊዜ ፡ ሳያልፍብህ ፡ ሂድና ፡ ብላ ፤ እኛ ፡ እንቆጳ ፡ የጀመ ረችውን ፡ ስንቅ ፡ አሰናድታ ፡ ሳትጨርስ ፡ አንበላም ፤ እንቆያ ለን ።"

"ስንቅ ፡ ባይከብድ ፡ ይሻላል ፤ ቀለሙም ፡ ምሽቱ ፡ የም ታሰናዳ ፡ መሆንዋን ፡ ነግሮኛል ።"

"ቀለሙም ፡ ይሄዳል? ወይስ ፡ ስንቅ ፡ አሰናድቶ ፡ ለኛ ፡ ለመስጠት ፡ ነው ?"

"አዎ ፡ ይሄዳል ። እኔ ፡ እንኰዋ ፡ እኛ ፡ እንበቃለን፡ያንተ፡ መሄድ ፡ አያስፈልግም ፡ ብዬው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በምትሄ ድበት ፡ አገር ፡ ደህና ፡ መድረስህን ፡ ካላዬሁ ፡ ልቤ ፡ አይርፍ ምና ፡ መሄድ ፡ አለብኝ ፡ ብሎ ፡ እንቢ አለኝ ።"

"በጣም ፡ ይወድሀል ፡ ማለት ፡ ነው! ደህና ፡ ነው ፡ ይሂድ፡ እኛንም ፡ ይረዳናል ፤ እሱም ፡ እንዳለው ፡ ልቡ ፡ ያርፋል ።"

"እሱማ ፡ የሚለው ፡ ይሄው ፡ ነው ፤ ብቻ ---- ውለታው፡ በዛና ፡ እኔን ፡ ከበደኝ ፡ እንጂ ።"

"የልብ ፡ ወዳጅህ ፡ ከሆነ ፡ የልብ ፡ ወዳጅ ፡ ውለታ ፡ ይከ ብዳል?"

"መውደድስ --- ለኔ ፡ የሚያደርገውን ፡ ሁሉ ፡ ስመለ ከት ፡ እንዲያውም ፡ ከራሱ ፡ አብልጦ ፡ የሚወደኝ ፡ ይመስለ ኛል ፡ እኔም ፡ በጣም ፡ እወደዋለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ውለታው ፡ በጣም ፡ በዛና ፡ ለመክፈል ፡ የማልችለው ፡ መስሎ ፡ ስለታዬኝ፡ ከበደኝ ።"

" ለምን ፡ ይከብድሀል? የልብ ፡ ወዳጅኮ ፡ ውለታውን ፡ እንዲያው ፡ ይውላል ፡ እንዲያው ፡ ይሰጣል ፡ እንጂ ፡ አያበድ ርም !"

" አዎ ፡ እንዳሉት ፡ ወዳጅ ፡ ውለታውን ፡ እንዲያው ፡ ይሰጣል ፡ እንጂ ፡ አያበድርም ፤ ብቻ ፡ ከወዳጆች ፡ አንዱ ፡ ሁል ጊዜ ፡ ውለታ ፡ ሰጪ ፡ ሁለተኛው ፡ ሁልጊዜ ፡ ውለታ ፡ ተቀ ባይ ፡ ሲሆኑ ፡ ውለታ ፡ ሰጪው ፡ አይሰለቸውም ? ውለታ ፡ ተቀ ባዩስ ፡ ይሉኝታ ፡ ካለው ፡ አይከብደውም ?"

" አይመስለኝም ! ይልቁንም ፡ ቅድም ፡ እንዳልኸው ፡ እንኰዋንስ ፡ ከራሱ ፡ አብልጦ ፡ የራሱን ፡ ያክልም ፡ የሚወድህ ፡

ከሆነ ፡ አንተም ፡ ያኑ ፡ ያክል ፡ ከወደድኸው ፡ ሰው ፡ ለራሱ ፡ የሚያደርገውን ፡ ውለታ ፡ እንደማይቆጥር ፡ እንዲሁም ፡ እንደ ራሱ ፡ ለሚወደው ፡ ወዳጁ ፡ የሚያደርገውን ፡ ውለታ ፡ አይቆጥርም ። እንዲያውም ፡ ሰው፡- እንደራሱ ፡ የሚወደው ፡ ወዳጅ ፡ እንኳዋ ፡ የለውም ፡ ከልቡ ፡ ለሚወደው ፡ ወዳጁ ፡ ውለታ ፡ ባደረገ ፡ መጠን ፡ ደስታው ፡ እየበዛ ፡ ይሄዳል ፡ እንጂ ፡ አይሰለችም ። የውነተኛ ፡ ፍቅር ፡ ባለበት ፡ ለመሰለቻቸት ፡ቦታ ፡ የለውም !"

"የሚሉት ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እሱ ፡ ለኔ ፡ ያደረገው ፡ ብዙ ፡ ሆኖ ፡ እኔ ፡ ለሱ ፡ አደረግሁት ፡ የምለው ፡ ፈልጌ . . . ስላጣሁ ፡ ትንሽ ፡ ቅር ፡ ይለኛል ። "

"ርዳታ ፡ በሚፈለግበት ፡ ሁኔታ ፡ መሆኑን ፡ እያወቅህ ፡ ርዳታህን ፡ ነፍገኸዋል ? "

"ቀለሙ ፡ ተቸግሮ ፡ የኔን ፡ ርዳታ ፡ የሚፈልግ ፡ ሆኖ ፡ እኔ ፡ ልነፍገው ? እሱስ ፡ የለም !"

"እሺ ፤ እንግዲያ ፡ አንተ ፡ ርዳታ ፡ ለመርዳት ፡ ወይም ፡ ውለታ ፡ ለመዋል ፡ እንዲመችህ ፡ ተቸግሮ ፡ እንድታየው ፡ ትፈልጋለህ ?"

"ኧረ ፡ በስመ ፡ አብ ! ኧረ ፡ ደህና ፡ ይሁንና ፡ የኔ ፡ ውለታ፡ ይቅርበት ፡ ጌታዩ !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

"እየውልህ ! እንግዲያስ ፡ ቅድም ፡ አንተ ፡ ያልኸው ፡ የምቀኛ ፡ አስተያየት ፡ የምቀኛ ፡ስሜት ፡ እንጂ ፡ የልብ ፡ ወዳጅ ፡ አስተያየትና ፡ የልብ ፡ ወዳጅ ፡ ስሜት ፡ አይደለም ። "

"እንዴት ? ምኑ ?"

"ለምን ፡ እኔ ፡ ርዳታ ፡ በምፈልግበት ፡ ወዳጄ ፡ ርዳታ ፡ በሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የሚያዝን ፡ በወዳጁ ፡ መልካም ፡ እድል ፡ በራሱ ፡ ክፉ ፡ እድል ፡ የሚያዝን ፡ ወይም ፡ በወዳጁ ፡ መልካም ፡ እድል ፡ የተመቀኘ ፡ መስሎ ፡ ሊታይ ፡ ይችላል ። "

"እንደሱ ፡ አድርጎ ፡ ከተረጎሙት ፡ ሊተረጎም ፡ ይችላል ፡ ብቻ ፡ እኔ ፡ በትርጉም ፡ ሳይሆን ፡ በቀጥታው ፡ በቀለ

ሙና ፡ በኔ ፡ መሀከል ፡ ያለውን ፡ ፍቅርና ፡ የውለታውን ፡ ብዛት፡ ስመለከት ፡ ምናልባት ፡ ይህ ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ የውለታ ፡ ብዛት ፡ የጋራ ፡ ፍቅራችንን ፡ እንዳይቀንሰው ፡ እንዳያበላሸው ፡ ፈርቾ ፡ ነው ። የቀለሙን ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ አለኝ ፡ ብዬ ፡ ስለምመካበት ፡ እሱን ፡ የሚቀንስብኝ ፡ ምክናያት ፡ እንዳይፈጠር ፡ እጠነቀቃለሁ ። ምንም ፡ ከሰዎ ፡ ባላውቅ ፡ "ከወዳጅህ ፡ ጋር ፡ በፍቅርና ፡ በመከባበር ፡ ለመቆየት ፡ ብትፈልግ ፡ ውለታው ፡ አይለፍብህ ።"የሚባለው ፡ ተረት ፡ ጥሩ ፡ ትምርት ፡ የሚሰጥ ፡ ይመስለኛል !"

" አዎ ፤ በወዳጅነት ፡ ስም ፡ ለሚነጋገዱ ፡ ገባያተኞች ፡ ጥሩ ፡ ትምርት ፡ የሚሰጥ ፡ ተረት ፡ ነው ! በኔ ፡ አስተያየት ፡ ግን ፡ ውለታ ፡ እንዲዋልላቸው ፡ ውለታ ፡ የሚውሉ ፡ ነጋዴዎች ፡ እንጂ ፡ የልብ ፡ ወዳጆች ፡ አይደሉም ! ውለታውን ፡ ቆጥሮ ፡ ሰጥቶ ፡ ቆጥሮ ፡ የሚቀበል ፡ የልብ ፡ ወዳጅ ፡ አይደለም ! በኔ ፡ አስተያየት ፡ የልብ ፡ ወዳጅ ፡ ማለት ፡ ለወዳጁ ፡ የሚያደርገውን ፡ ለራሱ ፡ እደሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡ ሳይቆጥር ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ የሚያደርግ ፡ ወዳጁ ፡ የሚያደርግለትን ፡ ራሱ ለራሱ ፡ እንዳደረገው ፡ ሁሉ ፡ ሳይከብደው ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡የሚቀበል ፡ ነው ! በል ፡ አሁን ፡ ወደራትህ ፡ ሂድ ፡ ከርክራችን ፡ ዛሬ ፡ የሚያልቅ ፡ ክርክር ፡ አልመሰለኝም ።"

" በወዳጆች ፡ መሀከል ፡ ሊኖር ፡ የሚገባው ፡ ወዳጅነት ፡ ልክ ፡ እስዎ ፡ እንደሚሉት ፡ ነው ። ብቻ ፡ አይደለም !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ሊሄድ ፡ ሲነሳ ።

በዛብህ ፡ ቅኔቤት ፡ ሲደርስ ፡ ዘረፋ ፡ ምላሽ ፡ ሆኖ ፡ የተዘረፈውን ፡ ቅኔ ፡ የሚፈታውና ፡ የሚያስፈታው ፡ ግስ ፡ የሚገሰውና ፡ የሚያስገሰሰው ፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሚዳ ፡ ገበያተኛ ፡ ሲንጫጫ ፡ እዚያ ፡ ውስጥ ፡ አስተማሪና ፡ ተማሪ ፡ ተሰሚና ፡ ሰሚ ፡ ይኖራል ፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ እስቸጋሪ ፡ ነበር ።

" ዘረፋ ፡ ምላሽ ፡ ሆኖ ፡ ነው ?" አለ ፤ አጎጀው ፡ ሲደርስ ፡ ረዱን ፡ እደጅ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲጠብቀው ፡ አገኘና ።

" አሁንማ ፡ ቅጸላውም ፡ ወደማለቁ ፡ ነው ! የሚያስቀጽሉዋቸው ፡ ተማሪዎች ፡ መጥተው ፡ የሉም ፡ ብዬ ፡ መለስሁዋ

ቾው ።" አለ ፡ ረዱ ።

"ብርቱ ጉዳይ ፡ ይገፉ አመሽሁ ። ስንት ፡ ቤት ፡ ተዘረፈ ?"

"አንድ ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ነው ።"

" አንድ ፡ ሙሉ ፡ ቤትስ ፡ ትንሽ ፡ ነው ፡ በሌሊቱ ፡ ቅጸላ ፡ አስጨርሳቸዋለሁ ። በል ፡ እንግዲህ ፡ ጡዋፍ ፡ ከማብራት ፡ የጨረቃዋ ፡ ብርሀን ፡ ይሻላል ፡ ራታችንን ፡ እዚሁ ፡ አምጣና ፡ እዩበላን ፡ የተዘረፈውን ፡ ቅኔ ፡ ንገረኝ ።" አለ ፡ በዛብህ ፡ የመምህር ፡ ደንጋይ ፡ በሚባለው ፡ ጠፍጣፋ ፡ ደንጋይ ፡ ላይ ፡ አጎዛ ፡ ጣል ፡ አድርጎ ፡ ሲቀመጥ ። ከዚያ ፡ ረዱ ፡ ሄኖክ ፡ በጊዜ ፡ የሰራውን ፡ ሽሮና ፡ ከብዙ ፡ ቤት ፡ የተለመነ ፡ ብዙ ፡ አይነት ፡ ቁራሽ ፡ አቅርቦ ፡ የተዘረፈውን ፡ ቅኔ ፡ ለበዛብህ ፡ እዩነገረው ፡ ራታቸውን ፡ በልተው ፡ ሲጨርሱ ፡ ቅጸላውም ፡ ጫጫታውም ፡ ጸጥ ፡ አለ ።

" አሁን ፡ ትንሽ ፡ ላስቀጽልህ ? ወይስ ፡ ትተኛለህ ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ ሄኖክን ።

"እንቅልፌ ፡ እንኩዋ ፡ አልመጣም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ ከምንወጣስ ፡ እኛም ፡ እንተኛና ፡ ባንድ ፡ ፊቱ ፡ ሌሊት ፡ ልቀጽል ።"

በዛብህ ፡ የሄኖክን ፡ አሳብ ፡ ተቀብሎ ፡ ለሌሊቱ ፡ ቅጸላ ፡ ለመንቃት ፡ ቶሎ ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ሄዶ ፡ ቢጋደም ፡ እንቅልፍ ፡ አልመጣለት ፡ አለ ። እዚያች ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ እዚያ ፡ እንጨት ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ የሚተኛበት ፡ ያ ፡ የመጨረሻ ፡ ሌሊት ፡ መሆኑ ፡ በተከታዩ ፡ ሌሊት ፡ በዚያ ፡ ሰአት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አስኮብልሎ ፡ የሚኮበልል ፡ መሆኑ ፡ ያ ፡ ሌሊት ፡ የተማሪነት ፡ ህይወቱን ፡ የተማሪነት ፡ ኑሮውን ፡ ጨርሶ ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ ገና ፡ የማያውቀው ፡ ሌላ ፡ አይነት ፡ ኑሮ ፡ ሌላ ፡ አይነት ፡ ህይወት ፡ የሚጀምርበት ፡ አዲስ ፡ ምእራፍ ፡ መሆኑ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሊደርስለትም ፡ ሊደርስበትም ፡ የሚችለው ፡ መልካምና ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የሰብሉ ፡ ቅዠት ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እዩተለዋወጠ ፡ እዩታዩው ፡ ካንድ ፡ ጎኑ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ሲገላበጥ ፡ እንዲሁ ፡ አይኑ ፡ እንደ ፡ ፈጠጠ ፡

ሌሊቱ ፡ ተገባደደ ።

ከመዳዩ ፡ መዳህ ፡ በመገላበጥና ፡ በመወራጨቱ ፡ ስለነበር ፡ ደክሞ ፡ በመጨረሻ ፡ እንቅልፍ ፡ ሊወስደው ፡ ሲል ፡ የሌሊት ፡ ቅጸላ ፡ ደወል ፡ ተደወለ ። ከዚያ ፡ ምንም ፡ እንቅልፍ ፡ ቢከብደው ፡ ሄኖክና ፡ ሌሎቹ ፡ የሚያስቀጽላቸው ፡ ተማሪዎች ፡ እደጅ ፡ ተቀምጠው ፡ መጠበቃቸውና ፡ ይልቁንም ፡ እሱ ፡ እውጭ ፡ በማምሸቱ ፡ የማታ ፡ ቅጸላቸው ፡ የታጎለባቸው ፡ መሆኑ ፡ ስለ ፡ ታሰበው ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብሎ ፡ እዩተንጠራራም ፡ እያዛጋውም ፡ ተነስቶ ፡ እንዲቀለው ፡ ፊቱን ፡ በቀዝቃዛ ፡ ውሀ ፡ አባብሶ ፡ ሱሪ ፡ ሳይታጠቅ ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ ሳይለብስ ፡ ጋቢውን ፡ ብቻ ፡ ተከናንቦ ፡ በርኖስ ፡ በላይ ፡ ደርቦ ፡ ወጣና ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ እጠፍጣፋ ፡ ደንጋይ ፡ ላይ ፡ በተንጠፈለት ፡ አጎዛ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ለባለ ፡ ግሱ ፡ ግስ ፡ እዩገሰሰ ፡ ለባለ ፡ ቅኔው ፡ ማታ ፡ የተዘረፈውን ፡ ቅኔ ፡ እዩፈታ ፡ ታሪኩን ፡ እዩተረከ ፡ ያስተምር ፡ ጀመር ። ሌሎች ፡ አስተማሪዎችም ፡ እንዲሁ ፡ በዩጎጆዋቸው ፡ ደጅ ፡ ባለው ፡ የመምህር ፡ ጠፍጣፋ ፡ ደንጋይ ፡ ላይ ፡ እዩተቀመጡ ፡ የሚያስቀጽሉት ፡ ተማሪ ፡ እዩከበባቸው ፡ ቅጸላው ፡ ጫጫታው ፡ ተጀመረ ።

እፍላ ፡ ቅጸላ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከውጭ ፡ መጥቶ ፡ እጥሩ ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ባለችው ፡ ጎጆ ፡ ደጅ ፡ ተቀምጠው ፡ ከሚቀጥሉት ፡ ተማሪዎች ፡ ካንዱ ፡ ጋር ፡ ትንሽ ፡ ሲነጋገር ፡ ቆዩና ፡ ወደ ፡ በዛብህ ፡ ጎጆ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ መጣ ።

"ያያ ፡ በዛብህ ፡ ጎጆ ፡ ይህ ፡ ነው ?" አለ ፡ አዲስ ፡ መጪው ፡ በዛብህን ፡ ከበው ፡ ተቀምጠው ፡ ከሚቀጽሉት ፡ አዳር ፡ የተቀመጠውን ፡ ጎተት ፡ አድርጎ ።

"አዎ ፤ ምነው ?" አለ ፡ ተማሪው ።

"የት ፡ ነው ፡ እሱ ?"

"እኒያ ፡ እመሀል ፡ ተከናንበው ፡ የተቀመጡት ፡ ናቸው ።" አለ ፡ ተማሪው ፡ እገጩን ፡ ወደ ፡ በዛብህ ፡ እሾሎ ። በዛብህ ፡ አሳቡንም ፡ አይኑንና ፡ ጆሮውንም ፡ አጠቃሎ ፡ እማስተማሩ ፡ ላይ ፡ አሳርፎ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከውጭ ፡ መጥቶ ፡ ከተማሪው ፡ ጋር ፡ የሚነጋገረውን ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ አላደረገውም ።

“እባክህ ፡ ንገርልኝና ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለብቻው ፡ ሳነጋግረው ፤ ብርቱ ፡ መልክት ፡ ይዣለሁ ።” አለ አዲስ ፡ መጪው ። ከዚያ ፡ ተማሪው ፡ ቆስ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ በዛብህ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ እንግዳ ፡ ሰው ፡ የሚፈልገው ፡ መሆኑን ፡ ሲነግረው ፡ ቀና ፡ ቢል ፡ በጨረቃ ፡ ብርሀን ፡ እንግዳው ፡ ሰው ፡ እዝራ ፡ መሆኑን ፡ አዩ ። ወዲያው ፡ ደንግጦ ፡ ተነሳና ፡ የዝራን ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ከተማሪዎች ፡ ትንሽ ፡ ራቅ ፡ እንዳሉ ፡ “እዝራ ፡ ምንድነው ?” አለ ።

“ምንም ፡ አይደለም ። ብቻ ፡ ማታ ፡ ከመንገድ ፡ ገብቼ ፡ ስለ ፡ ደከመኝ ፡ ራቴን ፡ እንኳ ፡ በቅጡ ፡ ሳልበላ ፡ ከተኛሁበት -- አያ ፡ ካሳ ፡ ቀስቅሶ ፡ ሂድና ፡ እቃህን ፡ ይዘህ ፡ ቶሎ ፡ ና ፡ በለው ፡ ስላለኝ ፡ ነው ፡ እንዲያ ፡ ደክሞኝ ፡ ሳለ ፡ እየሮጥሁ ፡ የመጣሁ ፤” አለ ፡ እዝራ ፡ ደክሞት ፡ ከተኛበት ፡ በመቀስቀሱ ፡ ስሞታውን ከመልክቱ ፡ ጋር ፡ ለበዛብህ ፡ ሲነግር ፡ ቅርታ ፡ በፊቱ ፡ እየታየ ፡

“ከሄድህበትሳ ፡ በደህና ፡ ተመለስህ ?”

“ደህና ።” አለ ፡ እዝራ ፤ አሁንም ፡ ቅር ፡ እንዳለው ።

“በል ፡ እንግዲህ ፡ ሂድና ፡ ከጥር ፡ ውጪ ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ቆዩኝ ፤ አሁን ፡ ታጥቄ ፡ እመጣለሁ ።” አለና ፡ በዛብህ ፡ ወደ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ተመልሶ ፡ እጨብጭቦ ፡ ጸጥ ፡ ሲሉ ፦

“መንገድ፡ አብሬያቸው ፡ እንድሄድ ፡ የቀጠሩኝ ፡ ነጋዴዎች ፡ አሁን ፡ የሚነሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለ ፡ ላኩብኝ ፡ መሄዴ ፡ ነውና ፡ ሳሁኑ ፡ በዩምትፈልጉት ፡ አስተማሪ ፡ ዘንድ ፡ ተከፋፍላችሁ ፡ ሂዳችሁ ፡ ስሙ ። ከነገ ፡ ጀምሮ ፡ ለወደ ፡ ፊቱ ፡ ግን ፡ አስተማሪ ፡ እንዲመደብላችሁ ፡ ለየኔታም ፡ ለሌሎች ፡ አስተማሪዎችም ፡ ትናንት ፡ ነግሬያለሁ ። በሉ ፡ እንግዲህ ፡ በደህና ፡ ያገናኘን ።” ብሎ ፡ ለመታጠቅ ፡ ወደ ፡ ጎጆው ፡ ገባ ።

“አሁን ፡ ከዚህ ፡ ተነስተን ፡ የት ፡ ልንደርስ ፡ ነው ? ገና ፡ አፋፉን ፡ ሳንዘቀዝቅ ፡ ይነጋል ፤ ደግሞስ ፡ አለቃ ፡ ካሳ ፡ እሳባቸውን ፡ የሚለውጡበት ፡ ምክናያት ፡ ገጠማቸው ፡ ይሆን ? ከዚህ ፡ ለመነሳት ፡ የተቃጠርንበት ፡ ነገ ፡ ማታ ፡ አልነበረም ?” እያለ ፡ መልስ ፡ የሌለው ፡ ጥያቄ ፡ ራሱን ፡ እዩጠዩቀ ፡ ቶሎ ፡ ተጣጥቆ ፡ እስር ፡ ያስቀመጠውን ፡ ከረ ጢት ፡ እንጠልጥሎ ፡ ሄኖክን ፡ ስሞ ፡ ወጣ ።

"የሄድህለት ፡ ጉዳይ ፡ ቀንቶህ ፡ ተመለስህ ፡ እዝራ ?" አለ ፡ እጥሩን ፡ ወጣ ፡ እንዳለ ፡ እዝራን ፡ ቆሞ ፡ ሲጠብቀው ፡ አገኘና ።

"እባክህ ፡ እንዲያው ፡ የመጣል ፡ ያክልነው ! እያ ፡ ካሳ ፡ ግን ጥሩ ፡ ዋጋ ፡ አውጥተዋል ፡ ይላል !"

"በጠቅላላው ፡ ስንት ፡ አወጡልህ ?"

"በጠቅላላውማ --- ቆይ ፡ እስቲ ! በጠቅላላው -- ለመቶ ፡ አስር ፡ ጉዳይ ፡ አገኘሁ ።"

"ጥሩ ፡ ዋጋ ፡ ነው ፡ እዝራ !"

"አየ --- እያ ፡ በዛብህ ፡ ከብቶቹን ፡ ባታውቃቸው ፡ ነው ! ሁለቱ ፡ በሬዎቹ ፡ ለዩራሳቸው ፡ በሬ ፡ የዋጡ ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ! እንዲያው ፡ አርሰው ፡ ይደክማሉ ፡ የማይባሉ ፡ ነበሩ ። ስንት ፡ ስንት ፡ ተሸጡ ፡ ታውቃለህ ? ሀያ ፡ ሀያ ! አንድዋ ፡ ላም ፡ የደረሰች ፡ ክበድ ፡ ነገ ፡ ሁለት ፡ የምትሆን ፡ ታልባ ፡ የማታፈጅ ፡ በስንት ፡ ጣልሁዋት ፡ ይመስልሀል ? አስዋንም ፡ እንዲሁ ፡ በሀያ ! ሁለቱ ፡ ላሞች ፡ ገና ፡ አሁን ፡ ነበር ፡ የነጠፉ ፡ አሁን ፡ መክበጃቸው ፡ ነበር --- ባስራምስት ፡ ባስራምስት ፡ ጥያቸው ፡ መጣሁ ! እጄን ፡ የተያዘ ፡ ይመስል --- የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ ከፈል ፡ የተባለ ፡ ይመስል --- በተገኘው ፡ ዋጋ ፡ ሸጠሀቸው ፡ ና ! መልሰህ ፡ እንዳታመጣቸው ፡ አለ ! መቸም ፡ እያ ፡ ካሳ ፡ በጣም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው ! ሲናገርም ፡ ደህና ፡ ይመስላል ! ብቻ ፡ የሚሰራው ፡ ስራ ፡ ---እስቲ ፡ በቀደም ፡ እኒያን ፡ የመሳሰሉ ፡ በቅሎዎች ፡ በርካሽ ፡ አውጥቶ ፡ ጣላቸው ! አሁን ፡ ደግሞ ፡ እኒህን ፡ ከብቶች ፡ የተሰረቁ ፡ ይመስል --- በተገኘው ፡ ዋጋ ፡ ይሸጡ ፡ ማለት ፡ ጤነኛ ፡ ሰው ፡ የሚያደርገው ፡ ነው ?"

"እእ ?" አለ ፡ በዛብህ ። የጉዞውን ፡ ነገር ፡ ባሳቡ ፡ እያወጣ ፡ እያወረደ ፡ እዝራ ፡ ከለፈለፈው ፡ ሁሉ ፡ የተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ለመቶ ፡ አስር ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ የሰማ ።

እንዲህ ፡ እዝራ ፡ ያለስሚ ፡ እዩተናገረ ፡ በዛብህ ፡ መልስ ፡ የሌለው ፡ ጥያቄ ፡ ራሱን ፡ እዩጠዩቀ ፡ እግራጌታ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ቤት ፡ አቅራቢያ ፡ ደረሱ ።

"እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ሂድ ፡ እኔ ፡ እዚያ ፡ ቤት ፡ ደርሼ ፡ አሁን ፡ መጣሁ ።" አለ ፡ በዛብህ ፡ የጓደኛውን ፡ ቤት ፡ በፊት

ማቱ ፡ ለዝራ ፡ እያመለከተ ።

"እሺ ! ብቻ ፡ ቶሎ ፡ ድረስ ፡ በለው ፡ ነውና ፡ ያለኝ ፡ እንዳትቆይ !" ብሎ ፡ እዝራ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

"ወይ ፡ በመንገድ ፡ አደርስብህ ፡ ይሆናል !" ብሎ ፡ በዛብህም ፡ ወደ ፡ ጉዋደኛው ፡ ቤት ፡ ሄደና ፡ እዩተጣራ ፡ መዝጊያውን ፡ በያዘው ፡ ሽመል ፡ ቀስ ፡ አድርጎ ፡ ያንኩዋኩዋ ፡ ጀመር ።

"ማነህ ?" አለ ፡ ግራጌታ ፡ ከውስጥ ።

"ተነሳ ፡ ቀለሙ ፡ መሄዳችን ፡ ነው ፡ እኔ ፡ በዛብህ ፡ ነኝ ፡ ቶሎ ፡ ተነሳ ።"

"አሁን ፡ መንጋቱ ፡ አይደለም ፡ እንዴ !" አለ ፡ ግራጌታ ፡ ደንግጦ ፡ ተነስቶ ፡ ሱሪውን ፡ እዩፈለገ ።

"እሱንስ ፡ እኔም ፡ ስል ፡ ነበር ! ብቻ ፡ ይሁን ፡ ቶሎ ፡ በል ፡ በንቁ ፡ አልታሰረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቅር ። ወይም ፡ ጣይቱ ፡ ትስረውና ፡ እዚያ ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ የምንቆይ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሮጠን ፡ መጥተን ፡ እንወስደዋለን ።"

"ጥሩ ፡ ነው !" አለና ፡ ግራጌታ ፡ ቶሎ ፡ ተጣጥቆ ፡ ምሽቱን ፡ "ያልተገናኘን ፡ እንደሆነ ፡ ደህና ፡ ሁኚ ፡ "ብሎ ፡ በዛብህም ፡ ተሰናብቶዋት ፡ እዩሮጡ ፡ ወደ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ።

አጥሩን ፡ ሲገቡ ፡ አደጅ ፡ በቅሎ ፡ አይታይ ፡ የስንቅ ፡ አገልግል ፡ ወይም ፡ ስልቻ ፡ አይታይ ፡ የልብስ ፡ ከረጢት ፡ አይታይ ፡ እንዲያው ፡ በጠቅላላው ፡ ቤቱ ፡ እንኩዋን ፡ ረዥም ፡ ጉዞ ፡ የታሰበበት ፡ ገብያ ፡ ደርሶ ፡ ለመመለስ ፡ የሚደረገውን ፡ ያክል ፡ መሰናዶና ፡ እንቅስቃሴ ፡ የማይታይበት ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ሆና ፡ ስላየት ፡ ከሩሚቸው ፡ ረገብ ፡ አሉ ። በዛብህ ፡ እንዲያውም ፡ ልቡን ፡ ትንሽ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ጅማቱን ፡ ፈዘዝ ፡ የሚያደርግ ፡ ስሜት ፡ ተሰማው ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አመትባል ፡ ሊያከብር ፡ እንደሚሄድ ፡ ሁሉ ፡ ንጹህ ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ በርኖሱን ፡ ደርቦ ፡ አቤቱ ፡ በራፍ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ። በዛብህንና ፡ ቀለሙን ፡ ከሩቅ ፡ እዩሮጡ ፡ መጥተው ፡ አጥሩን ፡ ከገቡ ፡ በሁዋላ ፡ ትንሽ ፡ ረገብ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሲያመሩ ፡ሲያያቸው ፡ ከቤቱ ፡ በር ፡ ወደ ፡ ደጅ ፡ መጥቶ ፡ ተቀበላቸው ።

" እንዴት ፡ አደራችሁ ፡ በዛብህ ! ግራጌታ ፡ ቀለሙ ፡

እሱ ፡ ነው ፤ ንግግር ፡ አይኑረን ፡ እንጂ ፡ በመልክ ፡ እንተዋወቃ ለን !" አለ ፡ ሲገናኙ ።

"እኔ ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ አውቅዎታለሁ ።" አለ ፡ ግራ ፡ ጌታም ።

"በሉ ፡ እንግባ ።" አለና ፡ ቀደም ፡ አለ ፡ እንግዶቹን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ለመምራት ።

የፍልጥ ፡ እሳት ፡ ማው ፡ ብሎ ፡ ነዶ ፡ ቤቱ ፡ በሙሉ ፡ ብር ሀን ፡ ነው ። በዛብህ ፡ ሰብለን ፡ መጥታ ፡ እዚያ ፡ አገኛታለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲያስብ ፡ ስላጣት ፡ ተሰቆ ፡ በውስጡ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ ባዶነት ፡ ተሰማው ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ራሱ ፡ ለጉዞ ፡ ሳይሰናዳ ፡ እሱን ፡ በዚያ ፡ ሰአት ፡ ያን ፡ ያክል ፡ አስቸኩሎ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ አጣድፎ ፡ ያስመጣበት ፡ ምክናያት ፡ ምንድነው ፤ ያ ፡ ሁሉ ፡ ክብት ፡ የተሸ ጠበት ፡ የሌሊት ፡ ጉዞ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነበት ፡ ሰብለን ፡ ሰርቆ ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ሲጉዋዙ ፡ አድሮ ፡ ሊነጋጋ ፡ ሲል ፡ በዚያ ፡ ሰአት ፡ አባይ ፡ ቆላ ፡ ለመግባት ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ የምትሰረቀዋ ፡ ሰብለ ፡ የት ፡ አለች ? ይሆንና ፡ ይሆን ፡ የመሳሰለ ፡ ብዙ ፡ ጥያቄ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ እየጠየቀ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ እንዳይጠይቅ ፡ ፈርቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

እቤት ፡ ገብተው ፡ እሳቱን ፡ ከበው ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ ገና ፡ ሳይቀመጡ ፡- "እየውልህ ፡ በዛብህ ፡ አሳባችነን ፡ ሁሉ ፡ ድካማ ችንን ፡ ሁሉ ፡ - - - ውሀ ፡ በላው ፤ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ሰው ፡ ከተኛ ፡ በሁዋላ ፡ ሌሊት ፡ ገብተው ፡ እዚያ ፡ ስንታመስ - - - " ብሎ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሲናገር ፡ ያሰበውን ፡ ተናግሮ ፡ ሳይጨርስ ፡ በዛብህ ፡ ራሱን ፡ በዱላ ፡ ወይም ፡ በደንጋይ ፡ እንደ ፡ ተመታ ፡ ክው ፡ ሲል ፡ ተሰማውና ፡ "እእ ?" ብሎ ፡ የቆመበት ፡ መሬት ፡ ልክ ፡ እንደንዝርት ፡ ቆርሽ ፡ ዙሪያ ፡ ሲሽከረከር ፡ ስለ ፡ ታዩው ፡ ድጋፍ ፡ እንደሚፈልግ ፡ ሁሉ ፡ እጆቹን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ስዶ ፡ ከመለሰ ፡ በሁዋላ ፡ እንደ ፡ መንገድገድ ፡ አለና ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ተቆረጠ ፡ ዛፍ ፡ ዥው ፡ ብሎ ፡ ወደቀ ። ወደ ፡ ፊት ፡ ወድቆ ፡ ቢሆን ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ ይገባ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዳጋ ጣሚ ፡ አወዳደቁ ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ በመሆኑ ፡ ከሳት ፡ ተረፈ ።

እስኪወድቅ ፡ ድረስ ፡ ራሱን ፡ እንዳዞረው ፡ ጉዱ ፡ ካሳና ፡ ግራ ጌታ ፡ አላወቁም ፡ ነበር ። ሲወድቅ ፡ ሲያዩት ፡ ብቻ ፡ ሁለቱም ፡ ደንግጠው ፡ ቶሎ ፡ ተጋግዘው ፡ አንስተው ፡ ራሱን ፡ ቀና ፡ አድር ገው ፡ እጉዱ ፡ ካሳ ፡ እልጋ ፡ ላይ ፡ ሲያጋድሙት ፡ ደም ፡ ባፍን ጫው ፡ ይጎርፍ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንቆጳን ፡ ጠርቶ ፡ ቶሎ ፡ ጨርቅ ፡ በቀዝቃዛ ፡ ውሀ ፡ ነክራ ፡ እንድታመጣ ፡ ነገራትና ፡ ያን ፡ እምጥታ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ አደረጉለት ። እንዲሁም ፡ ትንሽ ፡ ቆይታ ፡ ሌላ ፡ ጨርቅ ፡ ነክራ ፡ ስታመጣ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ የቆዩውን ፡ አንስተው ፡ ያን ፡ አደረጉለት ።

ሶስት ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ያክል ፡ በቀዝቃዛ ፡ ውሀ ፡ የተነከረ ፡ ጨርቅ ፡ እዩለዋወጡ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ ሲያደርጉለት ፡ እንደ ፡ ቆዩ ፡ ነስሩ ፡ ቆመና ፡ በዛብህ ፡ አይኑን ፡ ገለጠ ። መርዶው ፡ የመታው ፡ ራሱ ፡ አሁንም ፡ አልረጋም ፡ ይዞራል ። ብቻ ፡ ጉዱ ፡ ካሳንና ፡ ቀለሙን ፡ አጠገቡ ፡ ተቀምጠው ፡ ሲያያቸው ፡ አወቃቸው ። ሰብለን ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ይዞ ፡ ለመጥፋት ፡ ከቤቱ ፡ እዩሮጠ ፡ መምጣቱም ፡ ጥርት ፡ ብሎ ፡ አይሁን ፡ እንጂ ፡ ታሰ በው ።

"የት ፡ ነን ? አዲስ ፡ አበባ ፡ ደርሰን ፡ ነው ? ወይስ ፡ የት ፡ ነን ? ሰብለ ፡ የት ፡ ናት ?" ሲል ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንባው ፡ መጣበ ትና ፡ በዛብህ ፡ እንዳያየው ፡ ፊቱን ፡ አዞረ ። ቀለሙም ፡ እንዲሁ ። ደግሞ ፡ አይኖቹን ፡ ከድኖ ፡ ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ሲገልጥ ፡ የራሱ ፡ ቁስል ፡ ይሰማው ፡ እንጂ ፡ መዞሩ ፡ ቀርቶ ፡ ባጠገቡ ፡ የተቀመጡት ፡ ሰዎችና ፡ እቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ምሰሶውም ፡ ወጋግራውም ፡ እሳቱም ፡ ሌላው ፡ እቃም ፡ ቦታ ፡ ቦታውን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ታዩው ። ከዚያ ፡ አይኖቹን ፡ ገልጦ ፡ ሳያረግብ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ቆዩ ፡ ከቅንድ ቦቹ ፡ መሀከል ፡ ግንባሩ ፡ ቁጥር ፡ ሲል ፡ ታዩ ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ "ድካማችነን ፡ ሁሉ ፡ ውሀ ፡ በላው ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ማታ ፡ ገቡ ፡" ያለው ፡ ትዝ ፡ አለው ። ወዲያው ፡ ሆዱ ፡ ድብል ቅልቅ ፡ አለና ፡ የሰራ ፡ አከላቱ ፡ ታወከ ። እንደገና ፡ ባካባቢው ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ይዞርበት ፡ ጀመር ።

"ሊያስታውከኝ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ ሆዴም ፡ ራሴም ፡ ሁለ

መናየ ፡ ተናወጸ ።" አለ ፡ በዛብህ ፡ ከጀርባው ፡ ወደ ፡ ጎኑ ፡ ተገላብጦ ።

"እንቆጳ ፡ ቶሎ ፡ ገበታ ፡ ወይም ፡ ድስት ፡ አምጪ ።" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

እንቆጳ ፡ ሰፊ ፡ ገበታ ፡ ከማምጣትዋ ፡ ቀና ፡ ሲል ፡ ያስታውከው ፡ ጀመር ። አስታውኮ ፡ ሲጨርስ ፡ እዋኪውን ፡ በመብራት ፡ ቢያዩት ፡ የሚበዛው ፡ ደም ፡ ሆና ፡ ስላገኙት ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ ግራ ፡ ጌታም ፡ ደነገጡ ። ብቻ ፡ ከትውኪያው ፡ በሁዋላ ፡ ቀለል ፡ አለውና ፡ ቀና ፡ ማለት ፡ ቻለ ።

ለመሆኑ ፡ ጌቶች ፡ መምጣታቸውን ፡ ለስዎ ፡ ማን ፡ ነገረዎ ?" አለ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲተክዝ ፡ ቆይቶ ።

"እዚያው ፡ እድሬ ፡ እዝራ ፡ ወዳንተ ፡ ሲመጣ ፡ መመለሴ ፡ ነው ።"

"ታዲያ ፡ ጌቶች ፡ መምጣታቸውንና ፡ እኛም ፡ የማንሄድ ፡ መሆናችንን ፡ ካወቁ ፡ እንደምንሄድ ሁሉ ፡ ለምን ፡ እቃህን ፡ ይዘህ ፡ና ፡ ብለው ፡ ላኩብኝ ?"

"ፊታውራሪ ፡ -- ሁሉንም ፡ ሰምተው ፡ መጥተው ፡ ሲነጋ ፡ እንዲይዙህ ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ ሲያዝዙ ፡ ስለሰማሁ ፡ እንዳይዙህ ፡ ብዬ ፡ ነው ።"

"ሰምተዋላ !"

"አዎ ፡ ሰምተዋል ።"

"ሰብለን ፡ ምን ፡ አድርገዋት ፡ ይሆን ? ገ- - ረፉዋት ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ አፉ ፡ እዬፈራ ፡ አይናቹን ፡ ቀስ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ መለስ ፡ አደረገና ።

" አልገረፉዋትም ፡ አሰሩዋት ።" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በተሰበረ ፡ ድምጽ ። አንገቱን ፡ ደፋ ፡ አድርጎ ፡ ሰብለ ፡ ስትታሰር ፡ የሆነችው ፡ ሁኔታ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ አዘን ፡ ተሰማውና ። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ይተክዙ ፡ ጀመር ።

"ነጋ ፡ በዛብህን ፡ ወደኔ ፡ ቤት ፡ ይዤው ፡ ልሂድ ፡ የፊታውራሪ ፡ ሰዎች ፡ ወዲህ ፡ የመጡ ፡ እንደሆነ ፡ አይተው ፡ እንዳይነግሩዋቸው !" አለ ፡ ግራ ፡ ጌታ ።

"እዚህ ፡ ማንም ፡ አይመጣ ፡ ይልቅ ፡ ጉዋደኝነታችሁን ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ያውቅ ፡ እንደሆን ፡ የሚያሰጋው ፡ ያንተ ፡ ቤት ፡ ነው !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

"ጉዋደኝነታችንንማ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል !"

"እንግዲያስ ፡ እዚህ ፡ ቢቆይ ፡ ይሻላል ።"

ጉዱ ፡ ካሳና ፡ ግራጌታ ፡ በዛብህ ፡ ስለሚቆይበት ፡ ሲነጋገሩ ፡ እሱ ፡ አይሰማም ፡ ነበር ። ሰብለን ፡ ሲያንገላትዋት ፡ ሲያስሩዋት ፡ እያዬ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እዚያ ፡ ቢገኝ ፡ የሚያስራትን ፡ ሰው ፡ የሚለውን ፡ የሚያደርገውን ፡ ባሳቡ ፡ ያማርጥ ፡ ነበር ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ፡

## ሰብለ ፡ እንዴት ፡ እንደታሰረች ፡

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ከባላገሮች ፡ ጋር ፡ በፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ማርቆስ ፡ ሲጓዙ ፡ እንደ ፡ መቃብር ፡ ክብዶ ፡ እንደ ፡ ሲኦል ፡ ጨልሞ ፡ እንደ ፡ ሞት ፡ የሚያስፈራ ፡ ግርማ ፡ ተጎናጥፎ ፡ የሚታያቸው ፡ ማርቆስ ፡ ሲደርሱ ፡ በመልክም ፡ በስምም ፡ የሚያውቁዋቸውን ፡ መኩዋንንትና ፡ ሰራዊት ፡ እይን ፡ ማየቱ ፡ ነበር ።

እስከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በብዙ ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ከብዙ ፡ ሀያላንና ፡ ከብዙ ፡ ስመጥር ፡ ጀግኖች ፡ እየተዋጉ ፡ ድል ፡ ከማድረግ ፡ በቀር ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ የማያውቁት ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የወንዶች ፡ ወንድ ፡ የጀግኖች ፡ ጀግና ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ተሰይመው ፡ ሲፈሩ ፡ ሲታፈሩ ፡ ሲከበሩ ፡ የኖሩት ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ምርኮኞቻቸውን ፡ አስረው ፡ ምርኮዋቸውን ፡ አሸክመው ፡ ትከሻቸውን ፡ ነፍተው ፡ ራሳቸውን ፡ አቅንተው ፡ እዩኮሩ ፡ እየተንጠራሩ ፡ እዩፎከሩ ፡ የማርቆስን ፡ አደባባይ ፡ ሲገቡ ፡ ለመታየት ፡ ይናፍቁ ፡ የነበሩት ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ አሁን ፡ የባላገር ፡ ምርኮኛ ፡ የፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ እስረኛ ፡ ሆነው ፡ መሳሪያቸውን ፡ ተገፈው ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ተዋርደው ፡ እንደ ፡ ታገተ ፡ ከብት ፡ እዩተነዱ ፡ ያን ፡ በጀግንነት ፡ የተደነቁበትን ፡ አደባባይ ፡ መግባቱ ፡ ሞት ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ መስሎ ፡ ታያቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ውርደትም ፡ ከቆዩበት ፡ ማሳፈሩ ፡ እዩቀረ ፡ ስለሚሄድ ፡ ማርቆስ ፡ አደባባይ ፡ ገብተው ፡ ውለው ፡ ባደሩ ፡ መጠን ፡ በባላገር ፡ እጅ ፡ መማረካቸውን ፡ እዩተው ፡ ከባላገር ፡ ጋር ፡ ስላላቸው ፡ ሙግት ፡ ያስቡ ፡ ያቸግሩ ፡ ጀመር ።

ፊታውራሪ ፡ አሰጌ ፡ እስረኞቻቸውን ፡ ማርቆስ ፡ ለንጉሱ ፡ ሊጋባ ፡ እንዳስረከቡ ፡ ሊጋባው ፡ ግራ ፡ ቀኙን ፡ ዋስ ፡ አስጠ

ርተው ፡ ወደ ፡ ወንዞሮች ፡ ሠሩዋቸው ። ከዚያ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ባላገሮችም ፡ በዬበኩላቸው ፡ ከሳቸውን ፡ አቅርበው ፡ ዳኞችን ፡ ለመግዛት ፡ የጉቦ ፡ ጨረታ ፡ ገጠሙ ። ባላገሮችም ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻም ፡ የያዙትን ፡ ገንዘብ ፡ ሲጨርሱ ፡ እዬተበደሩ ፡ ለዳኞች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዳኞችን ፡ ያሸንፋሉ ፡ ዳኞች ፡ ይሰሙዋቸዋል ፡ ለሚባሉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጉቦ ፡ እዬሰጡ ፡ ነገራቸውን ፡ እያስረዱ ፡ ትግሉ ፡ ተጀመረ ።

ባላገሮች ፡ የሚፈልጉት ፡ ጥንት ፡ ከተሰራባቸው ፡ ግብር ፡ ምንም ፡ ሳይጎድል ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ያልተሰራላቸውን ፡ ያጣጉ ፡ ባል ፡ መዋያ ፡ ካልከፈላችሁ ፡ ብለው ፡ ያስነሱ ፡ አዋጅ ፡ በሰላማዊ ፡ ህዝብ ፡ ላይ ፡ ዘምተው ፡ እንዲጠብቁ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ህዝብ ፡ እንደ ፡ ሽፍታ ፡ በመዝረፋቸው ፡ ሴቶችንና ህጻናትን ፡ እያሰሩ ፡ በመግረፋቸው ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በማስገደላቸው ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ ከፍለው ፡ የዘረፉትን ፡ ንብረት ፡ መልሰው ፡ ከሰው ፡ ተቀጥተው ፡ ጉልቶቻቸው ፡ እንዲፋቁ ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በበኩላቸው ፡ ባላገሮች ፡ ለግበው ፡ አበጀ ፡ በለው ፡ በሚባል ፡ ሽፍታ ፡ መሪነት ፡ አድመው ፡ ፋሲካን ፡ በማያከል ፡ ትልቅ ፡ አውዳመት ፡ ተገዥ ፡ ለገዥ ፡ እንደሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡ ማርና ፡ ቅቤ ፡ ሙክትና ፡ ፍሪዳ ፡ ዶሮና፡ ቁና ፡ እህል ፡ እንኳዋ ፡ ይዘው ፡ ደጃቸውን ፡ ሳይረግጡ ፡ በመቅረታቸው ፡ ይህን ፡ የሚገባቸውን ፡ ለማስጠጣት ፡ ቢሄዱ ፡ የግቡበትን ፡ ቤት ፡ አቃጥለው ፡ አንድ ፡ አሽከራቸውን ፡ በመግደላቸው ፡ ያሰሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ አበጀ ፡ በለውን ፡ ሲባ ፡ አድም ፡ አደርገው ፡ በመሾማቸው ፡ በሶስቱ ፡ ጉልቶች ፡ የሚባሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ነገራቸውን ፡ በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ እንዲጨርሱ ፡ አድርገው ፡ ዳኝነትና ፡ ውርርዳቸውን ፡ በማስቀረታቸው ፡- በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ያስቀሩባቸውን ፡ ጥቅም ፡ ባጠፊታ ፡ እንዲከፍሉዋቸው ፡ አሽከራቸው ፡ በሞተበት ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፍሉዋቸው ፡ ጉልቶቻውን ፡ በደፈሩበት ፡ እንዲክሱዋቸው ፡ አበጀ ፡ በለውና ፡ ያድማው ፡ መሪዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲታሰሩላቸው ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ።

ይህ ፡ አይነት ፡ ክስ ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ ለጊዜው ፡ በፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ በጉልቶቻቸው ፡ በሚኖሩት ፡ ባላገሮች ፡ መዘ

ከል ፡ ቢነሳ ፡ ስለሱ ፡ የሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጥቅምና ፡ መብት ፡ የሚነካ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ በጠቅላላው ፡ በነገርዎችና ፡ በተነገርዎች ፡ መሀከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ የሚነካ ፡ መስሎ ፡ ስለታዩ ፡ በዱሽንጎው ፡ በዱድግስ ፡ ቤት ፡ በዱመሽታ፡ ቤቱ ፡ የሚገናኘው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚነጋገርበት ፡ የሚከራከርበት ፡ ሆነ ። እችሎትም ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ የባላገሮች ፡ ጉዳይ ፡ በቀረበ ፡ ቁጥር ፡ ለመተቸትና ፡ የሚተቹትን ፡ ለማየት ፡ ወይም ፡ ለመስማት ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ የሚሄደው ፡ ሰው ፡ እንኩዋን ፡ መቀመጫ ፡ መቆምያ ፡ ይጠበው ፡ ነበር ።

መቸም ፡ በልማዱ ፡ ችሎት ፡ የቀረበ ፡ ሙግት ፡ የሚቀረጠው ፡ ወንበሮች ፡ የፈረዱትን ፡ ወይም ፡ ንጉሡ ፡ የተቀመጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንጉሡ ፡ የሰጡትን ፡ ፍርድ ፡ ተከትሎ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ችሎት ፡ ከሚያዘወትሩት ፡ ነገር ፡ መርማሪና ፡ ፍርድ ፡ አዋቂ ፡ መሆናቸውን ፡ በማሳዬት ፡ ደጅ ፡ መጥናት ፡ የሚፈልጉ ፡ ወይም ፡ የተበደለ ፡ ሰው ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ አግኝቶ ፡ ሲሄድ ፡ ማየቱ ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎች ፡ ስለሆኑና ፡ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ችሎት ፡ በቀረበ ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ በነጻ ፡ መተቸት ፡ ነገሩን ፡ ዘርዝረው ፡ አበጥረው ፡ አብራርተው ፡ ማሳዬትም ፡ በፍርድ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ መስጠትም ፡ ስለሚችሉ ፡ ጉቦ ፡ የበላ ፡ ዳኛ ፡ ራሱን ፡ ሳያጋልጥና ፡ ትዝብት ፡ ሳያተርፍ ፡ ፍርድ ፡ አጣሞ ፡ ጉቦ ፡ ለሰጠው ፡ ወገን ፡ ለመበዬን ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ይህም ፡ ጉዳይ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ጥቅምና ፡ መብት ፡ የሚነካ ፡ በመሆኑ ፡ አስቸጋሪ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጉቦ ፡ በበላበት ፡ በኩል ፡ የፍርዱ ፡ ሚዛን ፡ ያዘነበለ ፡ ሲመስል ፡ በሌላው ፡ ቀን ፡ ጉቦው ፡ በቀለለው ፡ በኩል ፡ ሲጨመርበት ፡ ወይም ፡ ተችዎቹ ፡ ሲተቹበት ፡ ፍርዱ ፡ ወደዚያ ፡ ያዘነበለ ፡ ሲመስል ፡ እሱንም ፡ ተከትለው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ፊታውራሪን ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ ባላገሮች ፡ ሲያዝኑ ፡ በሌላው ፡ ቀን ፡ ባላገሮችን ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ ሲያዝኑ ፡ ነገሩ ፡ መቆረጫ ፡ አጥቶ ፡ ሲጎተት ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በላይ ፡ ቆዬ ።

መቸም ፡ ጉቦ ፡ የበላ ፡ ዳኛ ፡ ጉቦ ፡ ለሰጠው ፡ በደለኛ ፡ ከሚ

ያደርገው ፡ ርዳታ ፡ ዋናው ፡ እውነቱ ፡ ጎልቶ ፡ እንዳይታይና ፡ የበደለኛው ፡ በደል ፡ እንዳይታወቅ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። እውነቱ ፡ ጎልቶ ፡ ከታዩና ፡ የበደለኛው ፡ በደል ፡ ከታወቀ ፡ በሁዋላ ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ ጉቦ ፡ የበላ ፡ ዳኛ ፡ ቢሆን ፡ ፍርድ ፡ አጣሞ ፡ ጉቦ ፡ ለሰጠው ፡ በው ፡ መፍረድ ፡ የብዙ ፡ ቀን ፡ ጉቦ ፡ የሚበላበትን ፡ ስራውን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ጉቦ ፡ እንደመለወጥ ፡ ስለሆነ ፡ ጤነኛ ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ዳኛ ፡ ይህን ፡ አያደርግም ። ስለዚህ ፡ የፈታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ የባላገሮች ፡ ነገር ፡ መቁረጫ ፡ አጥቶ ፡ ከቀጠሮ ፡ ወደ ፡ ቀጠሮ ፡ በተንተተ ፡ መጠን ፡ ጉቦ ፡ የበሉ ፡ ዳኞች ፡ እድበስብሰው ፡ ሊያልፉት ፡ የሚፈልጉትን ፡ ጉቦ ፡ ያልበሉ ፡ ተችዎች ፡ እያብራሩ ፡ እያጣሩ ፡ እያበጠሩ ፡ ሲያሳዩ ፡ በዚያውም ፡ መጠን ፡ የፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በደለኛነትና ፡ ግፈኛነት ፡ ጎልቶ ፡ እዩታዩ ፡ በመሄዱ ፡ ከነጋዴም ፡ ከዘመድ ፡ ወዳጅም ፡ እዩተበደሩ ፡ የሰጡት ፡ ጉቦ ፡ ይህን ፡ በደለኛነታቸውንና ፡ ግፈኛነታቸውን ፡ መሸፈን ፡ አልቻል ፡ ስላለ ፡ ዳኞችም ፡ በዘሉት ፡ መጠን ፡ ፈታውራሪን ፡ መርዳት ፡ አልሆንላቸው ፡ ብሎ ፡ በመጨረሻ ፡ ባላገሮች ፡ የጠዩቁት ፡ የነፍስ ፡ ዋጋና ፡ ካሳ ፡ የተዘረፈው ፡ ከብትና ፡ ንብረት ፡ መመለስ ፡ ሁሉ ፡ ይቅር እንጂ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ ከፍለው፡ ቦስቱ ፡ ጉልቶቻቸው ፡ እንዲፋቁ ፡ በፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ተፈረደባቸው ።

ከዚያን ፡ ያክል ፡ ትግል ፡ በሁዋላ ፡ ፍርዱ ፡ የተፈረደ ፡ እለት ፡ ባላገሮች ፡ እዚያው ፡ እችሎት ፡ ላይ ፡ እልል ፡ ሲሉ ፡ ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ በንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ ተነስቶ ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ ሰው ፡ ፍዝዝ ፡ ቡዝዝ ፡ ብለው ፡ ይመለከቱዋቸው ፡ ነበር ። ለባላገሮች ፡ መፈረዱ ፡ በሳቸው ፡ መፈረዱ ፡ እውነት ፡ አልመስላቸው ፡ አለ ። ለዳኞች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለዳኞች ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆች ፡ ጭምር ፡ እዩተበደሩ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተው ፡ እዳኞች ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዳኞችን ፡ ያሸንፋሉ ፡ በተባሉት ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ቤቱ ፡ ጭምር ፡ እንደ ፡ ባታት ፡ ቁዋሚ ፡ ሳይነጋ ፡ እዩሄዱ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ደጅ ፡ ጠንተው ፡ ዳኞችም ፡ የዳኞች ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆችም ፡ "እግዚአብሄር ፡ ይርዳ ፡ እንጂ ፡ እይዞዎ ፡ ግዴለዎትም ፡" እያሉ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የማይታበል ፡ ቃላቸውን ፡

ስጥተዋቸው ፡ አሁን ፡ እንዴት ፡ ይፈረድባቸዋል ? እውነት ፡ የማ ይመስል ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ እውነት ፡ ነው ።

"ዋስ ፡ ይጥሩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ለሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ እቦስቱ ፡ ጉልቶችዎ ፡ ሁለተኛ ፡ ላይደርሱ ፡ እዚህ ፡ በተፈለጉ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀርቡ ፡ ዋስ ፡ ይጥሩ ።" አለ ፡ የወንበሮች ፡ አጋፋሪ ።

"እእ - - - ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ከንቅልፋ ፡ እንደ ፡ ባነነ ፡ ደንገጥ ፡ ብለው ።

"ዋስ ፡ ይጥሩ ።" አለ ፡ ደገመና ፡ አጋፋሪው ።

"ዋስ ፡ የለኝም --- ፡ ዋስ ፡ አልጠራም !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ያ ፡ ቅጣት ፡ መስሎዋቸው ፡ የነበረው ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ መሆኑ ፡ ሲረጋገጥ ፡ እንደ ፡ መቆጣት ፡ አሉና ።

"ዋስ ፡ ቢጠሩ ፡ ይሻላል ፡ ጌታዬ ፡ እንዳይታሰሩ !"

"እታሰራለሁዋ ! ምን ፡ አለ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡ ከመቀበል ፡ መታሰር ፡ ይሻላል ፡ እታሰራለሁ !"

"የደረሰብን ፡ ሳያንስ ፡ ደግሞ ፡ ታስረው ፡ ቢገላሉ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ጌታዬ ! እባክዎ ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ዋስ ፡ ይጥሩ !" አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀረብ ፡ አሉና ። ከዚያ ፡ አዛዥ ፡ ደስታና ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉም ፡ ሌሎች ፡ በመያዣቸውም ፡ ሲያባብሉዋቸው ፡ ቆይተው ፡ ትንሽ ፡ መለስ ፡ ሲሉ ፡-

"ቀኛዝማች ፡ አዩለ ፡ ሀይሉ ፡ ተዋሰኝ ፡" አሉ ።

" አልችልም !"

" ፊታውራሪ ፡ አበራ ፡ ጸሀይ ፡ ተዋሰኝ !"

" አልችልም !"

" ግራዝማች ፡ ግሩም ፡ ተሰራ ፡ ተዋሰኝ !"

" አልችልም !"

" ይሄው ፡ ዋስ ፡ አጣሁ ! ባደግሁበት ፡ ባረጀሁበት ፡ አደባባይ ፡ ዋስ ፡ አጣሁ ! ራሴ ፡ ዋስ ፡ እንግዴሀ ፡ እሰሩኝ !" ሲሉ ፡ ፊታውራሪ ፡-

" እኔ ፡ እዋሳለሁ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ድን በሩ ።

" ይድገሙ ። "አለ ፡ ኢጋፋሪው ።

" እኔ ፡ እልበቃ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ ዋስ ፡ ማስፈለጉ ? ለመቀጫውም ፡ ሆነ ፡ ሲፈለጉ ፡ ለማቅረቡ ፡ ለሁሉም ፡ እኔ ፡ እዋሳለሁ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ወደ ፡ ወንበሮች ፡ ዘወር ፡ ብለው ።

" እኛ ፡ ምንቸገረን ! ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ለሁሉም ፡ እኔ ፡ እበቃለሁ ፡ ካሉ ፡ ግዴለም ፡ ቅጠሩቸው ፡ ኢጋፋሪ !" አሉ ፡ ከወንበሮች ፡ አንዱ ።

ከዚያ ፡ ግራቀኙን ፡ የሚያውቃቸው ፡ ህዝብ ፡ ከዛ ፡ የተፈረደላቸውን ፡ እንኩዋን ፡ ደስ ፡ አላችሁ ፡ እያለ ፡ የተፈረደባቸውን ፡ እያጽናና ፡ ሁሉም ፡ ከችሎት ፡ ተመለሱ ። ፊታውራሪ ፡ ፍዝዝዝ ፡ ብለው ፡ አጥርተው ፡ ማሰብም ፡ መናገርም ፡ አይችሉም ፡ ነበር ። በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ውለው ፡ አድረው ፡ ብስጭታቸው ፡ እየበረደ ፡ በሄደ ፡ መጠን ፡ በጦር ፡ ሜዳም ፡ ሆነ ፡ በችሎት ፡ በባላገር ፡ እጅ ፡ ድል ፡ ለመምታታቸው ፡ አላፊው ፡ ዘመኑ ፡ እንጂ ፡ በሳቸው ፡ ድካም ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ አለመሆኑን ፡ አረጋግጠው ፡ ስላመኑ ፡ በሙሉ ፡ ተጽናንተው ፡ ላገኙት ፡ ሁሉ ፡ ዘመኑን ፡ እየወቀሱ ፡ እያማረሩ ፡ ይናገሩ ፡ ጀመር ።

" ምን ፡ እናድርግ ? እግዚአብሔር ፡ እድሜያችንን ፡ አስረዝሞ ፡ በንዲህ ፡ ያለ ፡ አባይ ፡ አታላይ ፡ ዘመን ፡ እንድንኖር ፡ ሲፈርድብን ፡ ጊዜ ! እንደሌባ ፡ ተሸሽጎ ፡ አታሎ ፡ አባብሎ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ማረከሁ ፡ ብሎ ፡ የሚፈክርበት ፡ ዘመን ! ሊረዳ ፡ ባርባ ፡ አራት ፡ ታቦት ፡ ምሎ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ የበላ ፡ ዳኛ ፡ ምንም ፡ እንዳልቀመሰ ፡ አይኑን ፡ አፍጦ ፡ የሚፈርድበት ፡ ዘመን፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ዘመን ፡ ሲያመጣብን ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ እናድርግ ! በኛ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ መታሁ ፡ ብሎ ፡ የሚፈክር ፡ ጀግና ፡ ልቡ ፡ የደፈረ ፡ ክንዱ ፡ የጠነከረ ፡ ጠላቱን ፡ ፊትለፊት ፡ ተሰልፎ ፡ ተዋግቶ ፡ አሸንፎ ፡ የማረከ ፡ ነበር ! በኛ ፡ ጊዜ ፡ እንኩዋንስ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ በልቶ ፡ እንዲያውም ፡ ቢሆን ፡ ዳኛ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቃሉን ፡ ከሰጠ ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ አያጥፍም ፡ ነበር ። ዛሬ፡ ግን ፡ ዘመኑ ፡ ያታላይ ፡ የቃል ፡ አባይ ፡ ዘመን ፡ ሆኖ ፡ አታላ

ዮች ፡ ማታለላቸውን ፡ እንደ ፡ ጀግንነት ፡ ቆጥረውት ፡ ይፈክሩ በታል ፡ ቃል ፡ አባዮች ፡ በቃላባይነታቸው ፡ ተሹመው ፡ ይኮ ሩበታል ! ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ መሸሻ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ድል ፡ መሆንና ፡ መረታት፡- ድል ፡ ሆንሁ ፤ ተረታሁ ፡ ብዬ ፡ ጭራሽ ፡ ካሳቤ ፡ አላገባውም !'' ይላሉ ።

''እውነት ፡ ነው ፡ እውነት ፡ ነው !'' ይሉዋቸዋል ፡ ዘመዶ ቻቸው ፡ እሳቸው ፡ በሚሉት ፡ አምነው ፡ ሳይሆን ፡ ሆድ ፡ እንዳ ይብሳቸውና ፡ ደግሞ ፡ እንዳይበሳጩ ፡ በማሰብ ።

ከዚያ ፡ ፊታውራሪ ፡ እችሎት ፡ ላይ ፡ የተቹትን ፡ ሰዎች ፡ የሚያውቁዋቸውን ፡ በስማቸው ፡ የማያውቁዋቸውን ፡ በምል ክት ፡ ያነሱና ፡ የተቹባቸውን ፡ መንቀፍና ፡ ተራ ፡ ስድብ ፡ መስ ደብ ፡ የተቹላቸውን ፡ ማመስገን ፡ ይጀምራሉ ።

'' እንዲያውኮ ፡ '' አሉ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ '' እንዲያውኮ ፡ የጭዋ ፡ ልጅ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ጭዋነቱን ፡ አይረሳም ! እስቲ ፡ አሁን ፡ ያ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ድንበሩ ፡ አንድ ፡ ጠበት ፡ አልሰጠነው ! አንድ ፡ ቀን ፡ እደጁ ፡ አልደረስን ! በሩቁ ፡ ካል ሆነ ፡ በቅርብ ፡ እንኳዋ ፡ አንተዋወቅ ! ያን ፡ ያክል ፡ ታጥቆ ፡ ለኛ ፡ የተከላከለና ፡ በሁዋላም ፡ ሳንጠይቀው ፡ የተዋሰን ፡ ያው ፡ የጭዋ ፡ ልጅነቱ ፡ አስገድዶት ፡ አይደለም ? የጭዋ ፡ ልጅ ፡ በመሆኑ ፡ ለምን ፡ የጭዋ ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ይጎድላል ! ለምን ፡ እውነት ፡ ይጠፋል ! ብሎ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል !'በብዙ ፡ ቀጣፊ ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡ እውነተኛ ፡ ቢገኝ ፡ ቀጣፊ' ፡ ይባ ላል ፡ የሚሉት ፡ ተረት ፡ ነው ፤ ለምን ፡ እውነት ፡ ተናገረ ፡ ብሎ፡ ሁሉም ፡ ሀይ ፡ ሀይ ፡ አለው ። ''

'' ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ሰው ፡ መሆኑ . . . . . . የታወቀ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ እሱም ፡ ቢሆን ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ለኛ ፡ ታጥቆ ፡ የቆመበት ፡. . . . .ምክናያት ፡ አለው !'' አሉ ፡ አባ'ነ ፡ ደስታ ።

''ምን ፡ ምክናያት ! እውነት ፡ ከመፈለግ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ምክናያት ፡ አለው ? እንዲያው ፡ እናንተ ፡ የሰው ፡ ዋጋ ፡ ማሳነስ ፡ ትወዳላችሁ ! ሰው ፡ ክፉ ፡ ሲሰራ ፡ እንዳይወቀስ ፤

መልካም ፡ ሲሰራ ፡ እንዳይመስገን ፡ ለሁሉም ፡ ምክናያት ፡ ትፈልጉለታላችሁ ፡ እንዲያው ፡ በውነት ፡ ክፉ ፡ አመል ፡ ነው ፡ አዛዥ ፡ ”

“የለም ፡ እንደሱ ፡ አይደለም ፡ ፊታውራሪ ! ለውነት ፡ ብሎ ፡ አልሰራም ፡ ብዬ ፡ ወይም ፡ ዋጋውን ፡ ለመቀነስ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፊታውራሪ ፡ ቃፈረ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ለውነት ፡ ብሎ ፡ በመስራቱ ፡ የሚመሰገን ፡ ቢሆን ፡ ደጅ ፡ ጥናት ፡ ስላለው ፡ ከውሊታ ፡ እንዲቆጠርለት ፡ ጭምር ፡ ነው ፡ ማለቴ ፡ ነው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ውሊታ ፡ ስለዋለልን ፡ የሚፈልገውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ማግኘት ፡ ይገባዋል ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዋጋውን ፡ ለማሳነስ ፡ አይደለም ።”

“ማንን ፡ ነው ፡ ደጅ ፡ የሚጠና ? ምን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ነው ፡ የሚፈልገው ?” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ፡ የተናገሩት ፡ ስላልገባቸው ። አዛዥ ፡ ደስታ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉን ፡ እዩና ፡ “እስቲ ፡ ርዱኝ ፡ እባካችሁ ፡” አሉ ።

“ፊታውራሪ ፡ ቃፈረ ፡ የሰብለን ፡ እጅ ፡ እንዲሰጡኝ ፡ እባካችሁ ፡ ለምኑልኝ ፡ እያለ ፡ አዛዥንና ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉን ፡ እኔንም ፡ ማርቆስ ፡ ከመጣን ፡ ጀምሮ ፡ አላስወጣ ፡ አላስገባ ፡ ብሎ ፡ ሲያስቸግረን ፡ ነው ፡ የሰነበተ ፡ እኛም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሳያልቅ ፡ እንነግራቸውም ፡ ብለን ፡ አቆይተነው ፡ ነበር ። ትናንት ፡ እድንኩዋናችን ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ ወዳገሬ ፡ ልሄድ ፡ ነውና ፡ ቁርጡን ፡ ንገሩኝ ፡ ብሎ ፡ ውጥር ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ያዘን ፡ ዛሬ ፡ እንነግራቸዋለን ፡ ብለን ፡ መለስነው ። ይህንን ፡ ነው ፡ አዛዥ ፡ ደጅ ፡ ጥናት ፡ አሉበት ፡ የሚሉት ። ሰውዬው ፡ መቼም ፡ እንዳዩት ፡ ማለፊያ ፡ ሰው ፡ ነው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ አዋቂ ፡ ያደባባይ ፡ ሰው ፡ ነው ።” ሲሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ “ጌትነቱስ ! ያለው ፡ ላምና ፡ በሬ ፡ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ ቁጥሩ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ይባላል ?” አሉ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ። “ወዲያው ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ ነው ! ንጉሱ ፡ ለስሙ ፡ ነገሱ ፡ እንጂ ፡ ጎጃምን ፡ በጊዜያቸው ፡ እንደ ፡ ሰም ፡ አቅልጠው ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ቀጥቅጠው ፡ የገዙት ፡ አባቱ ፡ አዛዥ ፡ ድንበሩ ፡ አልነበሩም ?” አሉ ፡

ቀኛዝማች ፡ አካሉ።

ዘመዶቻቸው ፡ እንዲህ ፡ እዬተቀባበሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ድንበሩን ፡ ሲያሞግሱ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ አይናቸውን ፡ ፍጥጥ ፡ አድርገው ፡ መጀመሪያ ፡ የድንጋጤ ፥ ከዚያ ፡ የደስታ ፥ ከዚያ ፡ የቅሬታ ፡ ምልክት ፡ ተከታትሎ ፡ በሽማግሌ ፡ ፊታቸው ፡ ላይ ፡ ሲያልፍ ፡ ይታይ ነበር።

ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈረን ፡ እችሎት ፡ ላይ ፡ ሲተቹ ፡ እንደበታቸው ፡ የረታ ፡ በመሆናቸው ፥ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ እንዲከበር ፡ ባላገር ፡ ተገዥነቱን ፡ አውቆ ፡ እንዲኖር ፡ የሚፈልጉ ፡ በመሆናቸው ፡ ጥንት ፡ ክስር ፡ ከመሰረቱ ፡ መብት ፡ ሰገዥ ፡ ግዴታ ፡ ሰተገዥ ፡ የተሰሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ሰይተው ፡ የሚያውቁ ፡ አስተዋይ ፡ በመሆናቸው ፡ ከመውደድና ፡ ከማድነቅ ፡ በቀር ፡ ልጃቸውን ፡ ሰብለን ፡ ለማግባት ፡ ይፈልጉ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ትንሽ ፡ ጥርጥር ፡ እንኳዋ ፡ ባሳባቸው ፡ ውስጥ ፡ ስላልነበረ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ መላክቱን ፡ ሲነግሩዋቸው ፡ ሰጊዜው ፡ ደነገጡ ። ወዲያው ፡ መሰረተ ፡ ጌታ ፡ ከመሆናቸውም ፡ ሌላ ፡ ባደባባይ ፡ አሉ ፡ ከሚባሉት ፡ ባላዱኞዎች ፡ መሀከል ፡ አንዱ ፡ መሆናቸው ፡ ትዝ ፡ ሲላቸው ፡ ልባቸው ፡ በደስታ ፡ ሞቆ ፡ ጸዳሉ ፡ በፊታቸው ፡ ወገግ ፡ ሲል ፡ ታዬ ፡ ከዚያ ፡ የሰብለን ፡ እጅ ፡ እዬሰመኑ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ ያፈገፈጉትን ፡ ብዙ ፡ የታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ልጆች ፡ ሲያስቡ ፡ የሳቸውም ፡ መጨረሻ ፡ ያው ፡ እንዳይሆን ፡ ፍራት ፡ ተሰማቸውና ፡ ቅር ፡ አላቸው።

"ግሩም ፡ ነው ! ሰብለን ፡ ሰማግባት ፡ ይፈልጋል ፡ ብዬ --- እንዲያው --- አስቤው ፡ አላውቅም ! መቸም :--- አባቱ ፡ ማሰፊያ ፡ ዘመናይ ፡ ነበሩ ! አውቃቸዋለሁ ! ስለዚህ ፡ ጋብቻው ፡ የሚሆን ፡ ከሆነ ፡ ቢሹት ፡ የማይገኝ ፡ ነው! ብቻ ---" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ብዙ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ፡ ፊታቸውን ፡ ቅርታ ፡ እንዳጠሰሰው ፡ አንገታቸውን ፡ ከደፉበት ፡ ወደ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ቀና ፡ አደረጉና።

" ብቻ ፡ ምን ? " አሉ ፡ አዛዥ ፡ ደስታ ፡ ፊታውራሪ ፡ "ብቻ ፡" ብለው ፡ ሲናገሩ ፡ ያሰቡትን ፡ ሳይጨርሱ ፤ የቦዘ ፡ አይናቸውን ፡ ሳያረግቡ ፡ ፊት ፡ ሰፊት ፡ ተክለው ፡ ዝም ፡ ስላሉ ።

"ብቻ ፡ እንደ ፡ ከዛሬ ፡ ቀደሙ ፡ ሁሉ ፡ ምቀኛ ፡ ተንኮለኛ ፡ ዝርጋሬ ፡ ገብቶበት ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ እንዳይቀር ፡ እንጂ --- ጋብቻውስ ፡ ቢሹት ፡ የማይገኝ ፡ ነበር ፡ ማሊቴ ፡ ነው ።"

"እሱ ፡ መቸም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈንታ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰጠዬው ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ ቆሟል ፡ አይመስለኝም ። ትናንት ፡ እንኩዋ ፡ ወዳገሬ ፡ ከመመለሴ ፡ በፊት ፡ የፊታውራሪን ፡ እሺታ ፡ ያስታወቃችሁኝ ፡ እንደሆን ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ጥሎሽ ፡ አሁንን ፡ ጥዬ ፡ ልሄድ ፡ ቢለን ፡ እሱም ፡ ቢፈቅድ ፡ እናትዋ ፡ ሳትስማማ ፡ ዘመድ ፡ ዘሙሉ ፡ መክሮበት ፡ ሳይስማማ ፡ ጥሎሽ ፡ መጣል ፡ አይሆንም ፡ አልነው ። ስለዚህ ፡ በጣም ፡ ቸኩሎዋል ። ወደ ፡ ሁዋላ ፡ የሚያፈገፍግ ፡ አይመስልም ።" አሉ ፡ አዛዥ ።

"መልካም ፡ ብላችሁታል ፡ ብቻ ፡ መቆዬቱ ፡ ደግሞ --- ማፋረስ ፡ ለሚፈልግ ፡ ምቀኛ ፡ መንገድ ፡ እንዳይሰጥ ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ዘዴያውም ፡--- ልጃችን ፡ ባል ፡ አጥታ ፡ የተቸገርንና ፡ 'ምሽት ፡ ፈላጊ ፡ ወዲህ ፡' የምንል ፡ እንዳንመስል ፡ መከረን ፡ እናስታውቅሀለን ፡ ማለቱ ፡ መልካም ፡ ነው ።" አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

ስለ ፡ ሰብለ   መታጨት ፡ ፊታውራሪና ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ ሲነጋገሩ ፡ የፊታውራሪ ፡ የጭን ፡ ገረድ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽም ፡ ሲቸገሩበት ፡ ለሰነበቱት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መንገድ ፡ ያገኙ ፡ መስሎዋቸው ፡ በበኩላቸው ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ያዳምጡ ፡ ነበር ።

ወይዘሮ ፡ የሰራሽ   ፡ ሰብለን ፡ ምንም ፡ ያደረገቻቸው ፡ ወይም ፡ የተናገረቻቸው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ባይኖር ፡ የጎባን ፡ ልጅ ፡ በመሆንዋ ፡ ብቻ ፡ እናትዋን ፡ በሚያዩበት ፡ አይን ፡ እያዩዋት ፡ አይወዱዋትም ። ነገር ፡ ግን ፡ አባትዋ ፡ በጣም ፡ ስለሚወዱዋትና ፡ የሚጠሉትን ፡ ሁሉ ፡ እንደሚጠሉ ፡ ስለሚያውቁ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንዳይጠሉዋቸው ፡ የሚወዱዋት ፡ መስለው ፡ ለመታየት ፡ ይጣጣሩ ።-

ሰብለ ፡ ከዘዛብዛ ፡ አረዛዘች ፡ እየተባለ ፡ የሚጠራውን ፡ ወሬ ፡ ከዲማ ፡ የመጣ ፡ ነጋዴ ፡ አረጋግጦ ፡ ስለነገራቸው ፡ እስዋን ፡ ከናትዋ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ የሚሙኩበት ፡ ጥሩ ፡ መሳ

ሪያ ፡ በማግኘታቸው ፡ መሰንበቻውን ፡ ልባቸው ፡ ደስታውን ፡ አልችለው ፡ ብሎ ፡ የሚያደርጉት ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶዋቸው ፡ ሰንብተው ፡ ነበር ። ብቻ ፡ ያሰሩኑ ፡ ዘዴ ፡ ካልታወቀ ፡ ጥሩ ፡ መሳሪያ ፡ ከሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ የሚያስከትለው ፡ ጉዳት ፡ ሊበልጥ ፡ ይችላል ! ስለዚህ ፡ የማይጠቅሙትን ፡ እንደማያዳግም ፡ አድርጎ ፡ ለማጥፋት ፡ ጥሩ ፡ መሳሪያ ፡ ማግኘት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ደህና ፡ አጋጣሚና ፡ ጥሩ ፡ ያሰራር ፡ ዘዴ ፡ ጭምር ፡ ማግኘት ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አጋጣሚ ፡ እስኪገኝ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። ያንለት ፡ ተገኘ ! እንግዲህ ፡ የውስጥ ፡ ደስታን ፡ ባዘንና ፡ በንባ ፡ መሸፈን ፡ ጥልቅ ፡ ጥላቻን ፡ ጥልቅ ፡ ፍቅር ፡ አስመስሎ ፡ ማሳየት ፡ ለመበቀል ፡ የሚደረገውን ፡ ትጥቅ ፡ ለመቆርቆርና ፡ ከብር ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚደረግ ፡ ትጥቅ ፡ አስመስሎ ፡ ማሳየት ፡ ማወቅ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚያስፈልገው ! ይህን ፡ ማድረግ ፡ ምንም፡ አያስቸግርም ። መጀመሪያ ፡ እንባቸው ፡ ሲጠሩት ፡ ቶሎ ፡ አቤት፡ ብሎ ፡ የሚደርስ ፡ ታዛዥ ፡ ስለሆነ ፡ ያለቅሳሉ ! ከዚያ ፡ ፊታውራሪ ፡ "ምነው ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡" ሲሉዋቸው ፡ "ምንም ፡ አልሆንሁ ፡" እያሉ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ልቅሶዋቸውን ፡ ይቀጥላሉ ! ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ፊታቸውን ፡ እየደባበሱ ፡ ሲያባብሉዋቸው ፡ ንግግራቸውን ፡ ሳግ ፡ እያቋዋረጠው ፡ አፍንጫቸውን ፡ እየተናፈጡ ፡ እንባቸውን ፡ ካይኖቻቸው ፡ እየጠራረጉ ፡ በሳቸውና ፡ በፊታውራሪ ፡ የደረሰውን ፡ መከራ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ መንገር ፡ ይጀምራሉ ! ይህ ፡ ነው !

ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ይህን ፡ ባሳባቸው ፡ ለደራጅተው ፡ በተራ ፡ አስቀምጠው ፡ የሚያስረቅስ ፡ ነገር ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ። ብቻ ፡ የሚያስገርመው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሲያስቡት ፡ የሚያስለቅሳቸው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያንለት ፡ ስሜታቸውን ፡ አልነካው ፡ አለ ! እንባቸው ፡ እንኩዋንስ ፡ ትእዛዛቸውን ፡ ልመናቸውን ፡ ማባበላቸውን ፡ ማቆላመጣቸውን ፡ እንቢ ፡ አለ ! እንባ ፡ የሚፈልቀው ፡ ከለስላሳ ፡ ልብ ፡ ነው ! ዘቂምና ፡ በበቀል ፡ ከጠጠረ ፡ ከጠነከረ ፡ ልብ ፡ አይደለም ! የወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ልብ ፡ ያንለት ፡ የበቀል ፡ አቅዳቸውን ፡ ሲያቅዱ ፡ ጥርሳቸውን ፡ ነክሰው ፡ የጠላቶቻቸውን ፡ ጥፋት ፡ ብአይኔ ፡ ሀሊናቸው ፡ ሲያዩ ፡ ልባቸው ፡ ጠጥሮ ፡

እልነካ ፡ እለ ፤ እንባ ፡ አላፈልቅ ፡ አለ ፤ ስለዚህ ፡ የሚያደርጉት ፡ ጠፍቶዋቸው ፡ ይሽበሩ ፡ ጀመር ። ያቀዱት ፡ አቅድ ፡ እንኩዋ ፡ ተራው ፡ ጠፋቸው ።

" ምነው ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡ የሰሩ ? " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የጭን ፡ ገረዳቸውን ፡ ሁኔታ ፡ አይተው ።

"ም— ምን ፡ ሆንሁ ? ደህና ፡ ነኝ !"

"ልጃችን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጌታ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ ባል ፡ ማግኘትዋ ፡ ስንመኘው ፡ የኖርነውን ፡ አይነት ፡ ባል ፡ ማግ ኘትዋ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ አይደለም ?"

" በጣም ፡ እንጂ ! " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ እንዲሁ ፡ አፋቸው ፡ እንዳመጣው ። ሁኔታቸው ፡ ሁሉ ፡ ሲሰርቅ ፡ እንደ ፡ ተያዘ ፡ ሌባ ፡ የሚሉትን ፡ አጥተው ፡ ሲቸገሩ ፡ የሚያሳይ ፡ ነበር ።

"ምነ ፡ ደስ ፡ አላለሽም ? ያንቺም ፡ ልጅሽ ፡ ናት ?"

" እንዴት ፡ ደስ ፡ አይለኝ ? " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ትንሽ ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ መግዛት ፡ አሉና ።

"ባትወልጃትም ፡ ያሳደግሻት ፡ ልጅሽ ፡ ናት ፡ ደስ ፡ ይበ ልሽ !"

"እዩተሳልሁ ፡ እንባየን ፡ እያፈሰስሁ ፡ ፈጥኖ ፡ ደራሹን ፡ የዲማ ፡ ጊዮርጊስን ፡ በለምን ፡ ሳማጥን ፡ የኖርሁበት ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ የሚፈጸምልኝ ፡ ከሆነማ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘኝ ፡ ነገር ፡ ይኖራል ? ነገር ፡ ግን ---" አሉ ፡ የፊታውራሪ ፡ የጭን ፡ ገረድ ፡ በመጨረሻ ፡ እንባቸው ፡ መጣ ላቸውና ።

" ነገር ፡ ግን ፡ ምን?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ እንደ መፍራት ፡ ብለው ።

" የለም ፡ ከቤት ፡ የሚመጣው ፡ ወሬ ፡ — ደስ ፡ ስለማያሰኝ፡ ይመከርበት ፡ ተብሎ ፡ ውሉ ፡ ሳይታሰር ፡ መቆየቱ ፡ መልካም ፡ ሆነ ፡ ማለቴ ፡ ነው ። "

" ከቤት ፡ ምን ፡ ተሰማ ? ጥሩየ ፡ ምን ፡ ሆነች ? ምን ፡ ደረሰባት ?"

" እሳቸውማ ፡ ምን ፡ ይሆናሉ ? "

" ታዲያ ፡ ልጄ ፡ ናት ? ምን ፡ ሆነች ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ሁለመናቸው ፡ እዬተንቀጠቀጠ ።

"ሁለቱም ፡ ደህና ፡ ናቸው ፡ ጌታየ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ለማጥፋት ፡ ታጥቀው ፡ የተነሱ ፡ ተንኮለኞች ፡ የፈጠሩት ፡ ወሬ ፡ በዲማና ፡ ባካባቢው ፡ ሁሉ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ስለ ፡ ተወራ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ወሬው ፡ እሰት ፡ መሆኑ ፡ የማይጠረጠር ፡ ቢሆን ፡ --- እንደ ፡ ጌታየ ፡ ያለ ፡ ስመ ፡ መልካምና ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ የታወቀ ፡ ሰው ፡ ቃሉን ፡ ከመስጠቱና ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ውል ፡ ከማሰሩ ፡ በፊት ፡ የሚወራውን ፡ ወሬ ፡ ማጣራት ፡ ለክብርም ፡ ለስምም ---መልካም ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ነው ።" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ የፊታውራሪ ፡ ሁኔታ ፡ ያስናዱትን ፡ ዘዴ ፡ ሁሉ ፡ አስረስቶዋቸው ።

" እሺ ፡ አሰትም ፡ ይሁን ፡ ለክብሬ ፡ እስበሽም ፡ ይሁን ፡ ብቻ ፡ የተወራውን ፡ ወሬ ፡ ንገሪኝ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቤታቸው ፡ ደረሰ ፡ የተባለውን ፡ ከፉ ፡ ወሬ ፡ መስማቱ ፡ ከጭንቀታቸው ፡ እንደሚገላግላቸው ፡ ሁሉ ፡ እስኪሰሙት ፡ ትግስት ፡ አጥተው ።

"የሚወራውማ ፡ - እግዚአብሔር ፡ እውነት ፡ አያድርገው ፡ እንጂ ፡ እመይቴ ፡ ቤቱን ፡ ጥለው ፡ የትም ፡ እዬዋሉ ፡ -- ሰብለ ፡ ካስተማሪዋ ፡ ጋር ፡ ያለጠባቂ ፡ ብቻቸውን ፡ ስለሚውሉ ፡ ደፍሮዋት --- ነፍሰጡር ፡ ሆናለች ፡--- ነው ። ብቻ ፡ እኔ ፡ እላመንሁም ፡ ጭራሽ ፡ ውሸት ፡ ነው ። " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ የፊታውራሪ ፡ ፊት ፡ ከቀይነት ፡ ወደብጫነት ፡ ከዚያ ፡ ወደጥቁርነት ፡ እዬተከታተለ ፡ ተለዋውጦ ፡ ሰውነታቸው ፡ በሙሉ ፡ በቁጣ ፡ ሲንቀጠቀጥ ፡ አይተው ፡ እዬፈሩ ።

" እንዴት ! ምንድነው ፡ የምትይዉ ! ደህና ፡ አይደለሽም ? ዝም ፡ በይ ፡ አንቺ ! የኔ ፡ ልጅ ፡ ሰብለ ፡ ተደፈረች ! አረገዘች ! ምንድነው ፡ የምትይዉ ? አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መንታ ፡ ቀንዳቸው ፡ በራሳቸው ፡ ተገትሮ ፡ ደም ፡ የጐረሱ ፡ አይኖቻቸው ፡ ከሮታቸው ፡ ጨርሰው ፡ ወጥተው ፡ እፊታቸው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳያስቡት ፡ ተነስተው ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽን ፡ ለማነቅ ፡ እንደ ፡ ፈለጉ ፡ ሁሉ ፡ የሁለት ፡ እጅ ፡ ጣቶቻቸውን ፡ እንጨፍርረው ፡

ወዳንገታቸው ፡ እዬሄዱ ፡፡

"ለስምም + ለክብርም ፡ መጣራቱ ፡ ይሻላል ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብዬስ ፡ አይደለም ፡ እስት ፡ መሆኑስ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ! " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ሊያንቁኝ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ደንግጠው ፡ እዬተርበደበዱ ፡፡

" ወይ ፡ እኔ ፡ መሽሽ ! ሳልሞት ፡ አፈር ፡ ሳልሆን ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ እልፍኜ ፡ ውስጥ ፡ ተደፈረች ! አረገዘች ! አለሁ ፡ ሲመስለኝ ፡ ለካስ ፡ የለሁም ! ሞቻለሁ ! እያት ፡ ቅድመ ፡ አያቶቼ ፡ በደማቸው ፡ ያስጎሰቱዋቸው ፡ ጉልቶች ፡ እኔ ፡ ልጃቸው ፡ እንደ ሌለሁ ፡ እንደ ፡ ሞትሁ ፡ ተፋቁ ፡ ልጄ ፡ አባት ፡ እንደሌላት ፡ አባትዋ ፡ እንደሞተ ፡ ተደፈረች ፡ አም ፡ ባልኖር ነው ! ብሞት ፡ ነው !" እያሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በሰፊ ፡ ድንኩዋናቸው ፡ ውስጥ ፡ እጃቸውን ፡ ወደሁዋላ ፡ በጀርባቸው ፡ ላይ ፡ አስተሳስረው ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲንጎራደዱ ፡ ቆይተው ፡ ሲደክማቸው ፡ እድልዳላቸው ፡ ላይ ፡ ሄደው ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ተቀምጠው ፡ ያስቡ ፡ ጀመር ፡፡

እንዲህ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ አካላዊ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ከድነው ፡ አይነ ፡ ህሊናቸውን ክፍተው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ መከራ ፡ በመከራ ፡ ላይ ደራርቦ ፡ የላከባቸውን ፡ እግዚአብሄርን ፡ ለመውቀስ ፡ ሄዱ ፡፡ ከዚያ እግዚአብሄር ፡ በመንበረ ፡ ጸባኦቱ ፡ በግርማ ፡ መለኮቱ ፡ ተቀምጦ ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክቱ ፡ ጻድቃን ፡ ሰማእታቱ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ተሰልፈው ፡ እሳቸው ፡ እፊቱ ፡ ቆመው ፡ የበደላቸውን ፡ በደል ÷ የሰራባቸውን ፡ ግፍ ፡ በድፍረት ፡ ሲነግሩት + ሲወቅሱት ÷ እሱም + ያላግባብ ፡ መበደላቸውን ፡ ተረድቶ ፡ እንደ ፡ መጸጠት ፡ ሲል ፡ ታያቸው ፡፡

"ምነው ፡ ጌታዩ ፡ ጾምህን ፡ ጾሜ ፡ ባላትህን ፡ አክብሬ ፡ ምጽዋት ፡ መጽውቼ + ከህግህ + ከትእዛዝህ ፡ ሳልወጣ ፡ የምኖረውን ፡ እማኝ ፡ አሽከርህን + እንዲህ ፡ ታደርገኛለህ ? እንዴት ፡ በብዙ ፡ ክፉ ፡ ሰዎች ፡ ያልደረሰ ፡ ግፍ + ያልደረሰ ፡ መከራ ፡ በኔ ባማኝ ፡ አሽከርህ ፡ ታመጣብኛለህ ? እንኩዋን ፡ ያልበደልሁህን ብበድልህስ ፡ አክብረህ ፡ ደስ ፡ አሰኝተህ ፡ ያኖርኸኝን ፡ አሽከርህን ፡ ወዳንተ ፡ መምጫዬ ፡ ሲደርስ ፡ መሞቻዬ ፡ ሲደርስ ፡ ክብ

ሬን ፡ ገፈህ ፡ እፍረትና ፡ ውርደት ፡ እንናዋፈህ ፡ ትጠራኛለህ ?
ድሆች ፡ ለማኞች ፡ እንኩዋን ፡ ተዋርደው ፤ ራቁታቸውን ፡ ሆነው ፡
ሲቸገሩ ፡ ሲለምኑ ፡ ኖረው ፡ በሚሞቱበት ፡ ጊዜ ፡ የማያውቁ
ትን ፡ ክብር ፡ አግኝተው ፡ ያልነበራቸውን ፡ ንጹህ ፡ ሸማ ፡ ለብ
ሰው ፡ ነው ፡ ወደ ፡ መቃብራቸው ፡ የሚሄዱ ፤ ወዳንተ ፡ የሚ
መጡ ! እኔ ፡ ምን ፡ እልሁህ ፡ ምን ፡ በደልሁህና ፡ እስከሬኔ ፡ በነ
ውርና ፡ በውርደት ፡ የጎደፈ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡
እንዲሄድ ፡ ትፈርድብኛለህ ? እስቲ ፡ ያጠፋሁትን ፡ ንገረኝ ? ሳላ
ውቅ ፡ የበደልሁህ ፡ በደል ፡ ቢኖር ፡ እንኩዋ ፡ ቶሎ ፡ እንዳማ
ረብኝ ፡ እንደ ፡ ተከበርሁ ፡ አትጠራኝም !" ሲሉት ፡—
እግዚአብሔርም ፡ ሁኔታቸው ፡ አሳዝኖት ፡ ሲጸጠት፡ ሲራራ ፡
ወዲያው ፡ የተወራው ፡ ወሬ ፡ እስት ፡ እንዲሆን ፡ ሲያዝ ፡ የታ
ያቸው ፡ መሰላቸውና ፡ "እሱ ፡ ካለ ፡ ምን ፡ ይቸግረዋል ? " አሉ፡
ራሳቸውን ፡ ከደፉበት ፡ ቀና ፡ አድርገው ፡ በረዥሙ ፡ ተንፍሰው ።

ከዚያ ፡ ራሳቸውን ፡ አንጋጠው ፡ አይናቸውን ፡ አድንኩዋኑ ፡
ጣራ ፡ ላይ ፡ ተክለው ፡ ብዙ ፡ ሲያስቡ ፡ ቆዩና ፡—

"መስረትን ፡ ፈረሴን ፡ አስጭንልኝ ፡ በይው ፡ ባለፈረስና ፡
መርጥ ፡ የሚችሉ ፡ አግረኛ ፡ ብቻ ፡ ይከተለኝ ፤ አሁን ፡ ወደ ፡
ዲማ ፡ መነሳቴ ፡ ነው ። አንቺ ፡ ጉዋዙንና ፡ የቀረውን ፡ ሰው ፡
ይዘሽ ፡ ነገ ፡ ተነሺ ፡" አሉ ።

"አሁን ፡ ተነስተው ፡ የት ፡ ሊደርሱ ፡ ጌታየ ?"

"ያልሁሽን ፡ አድርጊ ፡ ብቻ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቁጣ ።

ፊታውራሪ ፡ በድንገት ፡ መነሳታቸውን ፡ ሲሰሙ ፡ ቀኛዝ
ማች ፡ እካሉና ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ በፈረስ ፡ ጋልበው ፡ ተከት
ለው ፡ የጨሞጋ ፡ ወንዝ ፡ ሞልቶ ፡ መሻገሪያ ፡ አጥተው ፡ ሲቸ
ገሩ ፡ ደረሱባቸው ። አዛዥ ፡ ደስታና ፡ ሌሎች ፡ መኩዋንንት ፡
አድረው ፡ በበነጋው ፡ ከጉዋዙ ፡ ጋር ፡ ተነሱ ።

የጨሞጋ ፡ ውሀ ፡ ሙላት ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ የገጠመውን ፡ ሁሉ ፡
ዛፉን ፡ ሳይቀር ፡ እያገበሰበሰ ፡ ዘቅዝቆ ፡ ከመጉዋዙ ፡ በላይ ፡
ውሀው ፡ የወንዙን ፡ ግንጅ ፡ አልፎ ፡ ተርፎ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ሜዳ ፡
ውን ፡ አልብሶት ፡ ሲታይ ፡ ባህር ፡ እንጂ ፡ ወንዝ ፡ አይመስልም፡

ነበር ። ፊታውራሪ ፡ ዋኘተን ፡ እንሻገር ፡ ብለው ፡ እስቸገሩ ። ቀኛዝማች ፡ እካሉና ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ግን ፡ ሙላቱ ፡ ደጋ ፡ ከዘነመ ፡ ዝናም ፡ የመጣ ፡ ጎርፍ ፡ ስለሆነ ፡ ማለፉ ፡ አይቀርምና ፡ እስኪጎድል ፡ እንቆይ ፡ ብለው ፡ ፊታውራሪን ፡ ለምነው ፡ ትንሽ ፡ እንደቆዩ ፡ እውነትም ፡ ጎርፉ ፡ ሲያልፍ ፡ ጨምጋ ፡ ጎደለ ። ቢሆንም ፡ ሙላቱ ፡ እዚያ ፡ የነበረውን ፡ የንጨት ፡ ድልድይ ፡ ሰብሮ ፡ ስለወሰደው ፡ ሰዎችም ፡ ሆኑ ፡ ፈረሶች ፡ ዋኝተው ፡ መሻገር ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ።

ጨምጋን ፡ ተሻግረው ፡ ፈረሶች ፡ ለመጋለብ ፡ እግረኞች ፡ ለመሮጥ ፡ ቢሞክሩ ፡ ያ ፡ በዝናም ፡ የቀለጠ ፡ ወልካ ፡ መሬት ፡ የሩ ዋጮችን ፡ እግር ፡ እያዳጠ ፡ የፈረሶችን ፡ ኮቴ ፡ እያሰመጠ ፡ እንደ ልብ ፡ አላስሄዳቸው ፡ አለ ። እንዲህ ፡ እዩታገሉ ፡ እዩወደቁ ፡ እዩተነሱ ፡ ቀኑንም ፡ ሌሊቱንም ፡ ሄደው ፡ ዲማ ፡ በሁለተኛው ፡ ሌሊት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከተኛ ፡ በሁዋላ ፡ ደረሱ ።

ከዚያ ፡ የሌሊት ፡ ዘበኛው ፡ ለሴት ፡ እልፍኝ ፡ አሽከርዋ ፡ ነግሮ ፡ የሴት ፡ እልፍኝ ፡ አሽከርዋ ፡ እመቤትዋን ፡ ቀስቅሳ ፡ የጌቶችን ፡ መምጣት ፡ ስትነግር ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ሳያስቡት ፡ ሳይሰናዱ ፡ ድንገት ፡ ባላቸው ፡ በዚያ ፡ ሰአት ፡ በመድረሳቸው ፡ ደንግጠው ፡ ግራ ፡ ገባቸው ። ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ መኝታ ፡ ሳይቀር ፡ ተደናግሮዋቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አሳለፉ ።

ከዚያ ፡ የምኝታ ፡ ቤት ፡ ገረዳቸውን ፡ አስከትለው ፡ ፊታውራሪ ፡ እሳት ፡ አስነድደው ፡ ተከትለዋቸው ፡ የመጡት ፡ ዘመዶቻቸውና ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ከበዋቸው ፡ በተቀመጡበት ፡ አዳራሽ ፡ ሲገቡ ፡ እዚያ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ እልቅሶ ፡ እንደ ፡ ደከመው ፡ እዘንተኛ ፡ ሁሉም ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እዚያ ፡ መሀከል ፡ እሳቱ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ከፍተኛ ፡ መደብ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፊታቸው ፡ የሚያስፈራ ፡ ቁጣ ፡ ለብሶ ፡ አይናቸው ፡ ደም ፡ ጎርሶ ፡ ነጭ ፡ ጠጉራቸው ፡ ተንጨብሮ ፡ መንታ ፡ ቀንዳቸው ፡ ግራቀኝ ፡ ተገትሮ ፡ የተኮነነች ፡ ነፍስ ፡ ተቀብሎ ፡ ለመሰቅየት ፡ የተሰለፈ ፡ የሰይጣናት ፡ አለቃ ፡ መስለው ፡ ተቀምጠው ፡ አዩና ፡ ጉልበታቸው ፡ መብረክረክ ፡ ራሳቸው ፡ መዞር ፡ አይናቸው ፡ መኾብርበር ፡ ጀመረ ። ከዚያ ፡ እእምሮውን ፡ ጨርሶ ፡ እንዳልሳተ ፡ ሰካራም ፡ እዩተንገራ

ደዱ ፡ ሄደው ፡ የባላቸውን ፡ ጉልበት ፡ ለመሳም ፡ ጎንበስ ፡ ለማለት፡ ሲሞክሩ፡-

"እንዳትስሚኝ ! ያንቺ ፡ መሳም ፡ የይሁዳ ፡ መሳም ፡ ነው ! ሂጂ ፡ እዚያ ፡ ተቀመጪ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የመደቡን ፡ ጫፍ ፡ ባገጫቸው ፡ ለምሽታቸው ፡ እሳይተው ። ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ እዬተንቀጠቀጡ ፡ ሄደው ፡ ሲቀመጡ ፡-

"ያችን ፡ ደግሞ ፡ ልጅ ፡ ተብዮይቱን ፡ ጥሪያት ፡ አንቺ !" አሉ ፡ ምሽታትውን ፡ ተከትላ ፡ የመጣችውን ፡ አሽከር ።

አሽከርዋ ፡ እሰብለ ፡ እልፍኝ ፡ ሄዳ ፡ ቀስ'ቀስ ፡ ጌቶች ፡ መምጣታቸውንና ፡ ከመቆጣታቸው ፡ የተነሳ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ፈርቶ ፡ የሚተነፍስ ፡ የሌለ ፡ መሆኑን ፡ ስትነግራት ፡ ያኑ ፡ የሰዋን ፡ ጉድ ፡ ሰምተው ፡ መምጣታቸው ፡ ገብቶዋት ፡ ለጊዜው ፡ ደነገጠች ፡ በሁዋላ ፡ ትንሽ ፡ ተቀምጣ ፡ ስታስብ ፡ ቆይታ ፡ ያለኝታዋ ፡ የተስፋዋ ፡ መጨረሻ ፡ መሆኑን ፡ ስትረዳ ፡ ፍራቱም ፡ ድንጋጤውም ፡ ተዋትና ፡ ለሚጠይቁዋት ፡ ሁሉ ፡ በድፍረት ፡ ለመመለስ ፡ ቆርጣ ፡ ሳትሸበር ፡ ሳትቸኩል ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ ሄዳ ፡ አባትዋን ፡ ለመሳም ፡ መሞከር ፡ ይቅርና ፡ ሰላም ፡ እንኩዋ ፡ ሳትል ፡ እፊታቸው ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ቆመች ።

" አለንጋየን ፡ አምጣ ፡ አንተ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ጋሻ፡ ጃግሬውን ፡ ልጃቸው ፡ ገና ፡ በሩን ፡ ስትገባ ፡ ሲያዩዋት ፡ ቁጣቸው ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ በፊታቸው ፡ ሲነድ ፡ እዬታዬ ።

" እስቲ ፡ ለሁሉም ፡ አሽከሮች ፡ ይመለሱ ። " አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ። አሽከሮች ፡ ወጥተው ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ብቻ ፡ ሲቀር።-

" በይ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ንገሪኝ ፡ አንቺ ፡ ......."

አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የልጃቸውን ፡ መጥፎነት ፡ ለመግለጽ ፡ የሚበቃ ፡ ስድብ ፡ አጥተው ፡ እዬፈለጉ ። " በይ ፡ ንገሪኝ ፡ የውስጡን ፡ ገላሽን ፡ ገልብጨ ፡ በላይ ፡ ሳላረገው ! ንገሪኝ ፡ አንቺ ፡ እምነተ ፡ ቢስ ፡ ወራዳ ! አንቺ ፡ ባስቀመጡሽ ፡ ቦታ ፡ የማትገኝ፡ ሰው ፡ አዋራጅ !"

" ምን ፡ ለማወቅ ፡ ነው ፡ የሚፈልጉት ፡ ? ይጠይቁኝና ፡ የውስጡን ፡ ገላየን ፡ በላይ ፡ ለማድረግ ፡ ሳይደክሙ ፡ እውነ

ቱን ፡ ልንገርዎ ! እንዲያው ፡ ያስ ፡ የሚልዎ ፡ የሙስጡን ፡ ገላየን ፡ በላይ ፡ ማድረጉ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ መጠየቅም ፡ አያስፈልግ ፡ ይሄው ፡ አፌትዎ ፡ ቆሜልዎታለሁ !” አለች ፡ ሰብለ ፡ ለኦሮ ፡ ተስፋ ፡ መቁረጥዋ ፡ አባትዋን ፡ እንደ ፡ ኮሶ ፡ መጥላትዋ ፡ እንደ ፡ ጥንብ ፡ መጠየፍዋ ፡ እንደ ፡ ትንኝ ፡ መናቅዋ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ ሊገልጸው ፡ እንደማይችል ፡ ሆኖ ፡ በፊትዋ ፡ አዩታዩ ።

ፊታውራሪ ፡ የልጃቸውን ፡ ሁኔታ ፡ ከፊትዋ ፡ ሲያዩ ፡ በቁጣ ፡ ፈንታ ፡ ፍራት ፡ ገባቸው ። እንኳዋን ፡ ከሰውነት ፡ የተቆረሰ ፡ ከደም ፡ የተቀነሰ ፡ የሚወዱት ፡ ልጅ ፡ የባእድ ፡ ወዳጅ ፡ ምርር ፡ ብሎ ፡ ሲጠላ ፡ ያሳዝናል ፡ ያስጨንቃል ። ስለ ዚህ ፡ ፊታውራሪ ፡ ተስፋ ፡ የመቁረጥና ፡ የመጥላት ፡ ፊት ፡ በልጃቸው ፡ ላይ ፡ ሲያዩ ፡ ያ ፡ ቀን ፡ ያባትና ፡ ልጅነታቸው ፡ መጨረሻ ፡ መስሎ ፡ ታያቸውና ፡ ፈርተው ፡ ከማርቆስ ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ጋልበው ፡ የመጡለትን ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ያሸበሩበትን ፡ ነገር ፡ አለሳልሰው ፡ የሚናገሩበት ፡ መንገድ ፡ አጥተው ፡ ይቸገሩ ፡ ጀመር ።

“ ሰብለ ! አንቺ ፡ ነሽ ፡ ሌላ !” አሉ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ፊትዋን ፡ ሲያጠኑ ፡ ቆይተው ።

“ እኔ ፡ ሰብለ ፡ ነኝ ! ምኑ ፡ ሌላ ፡ መሰለዎ ?”

“ አነጋገርሽ ፡ ፊትሽ !”

“ ማወቅ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ይጠይቁኝና ፡ እውነቱን ፡ ልንገርዎ ፡ ነው ፡ ያልሁ ! አሁንም ፡ ይጠይቁኝና ፡ ልንገርዎ!”

“ አባትሽኮ ፡ ነኝ ! አባት ፡ ልጁን ፡ መቆጣት ፡ በኔ ፡ አልተጀመረም ! እውነትም ፡ ይሁን ፡ አሰት ፡ ያንቺንም ፡ የኔንም ፡ ክብር ፡ የሚነካ ፡ በቤታችን ፡ ላይ ፡ ውርደትና ፡ እፍረት ፡ የሚያመጣ ፡ ወሬ ፡ ማርቆስ ፡ ድረስ ፡ ተወርቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ለኔም ፡ ስለደረሰኝ ፡ . . . በዚህ ፡ ባዝንና ፡ ብቆጣ ፡ ይብዛብኝ ? በዚህ፡ ያልተቆጣሁ ፡ በምን ፡ ልቆጣ ? እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ እንደኔ ፡ ላለ ፡ ሰው ፡ የቁም ፡ ሞት ፡ አይደለም ? ስለ ዚህ ፡ ነው ፡ እውነቱን ፡ ንገሪኝ ፡ ያልሁ ። ”

“ ስለ ፡ ምኑ ?”

“ ያ . . . .እንዲያስተምርሽ ፡ አደራ ፡ ያልነው ፡ ሰው ፡ አደራውን ፡ በልቶ ፡ እምነቱን ፡ አጉድሎ ፡ ማርቆስ ፡ ብሏደ ፡ እንደ ፡ ሞትሁ ፡ ቆጥሮኝ ፡ . . . . . .ስለ ፡ ደፈረሽ ፡ ነፍሰጡር ፡ ሆነሻል ፡ ተብሎ ፡ ነው ፡ የተነገረኝ ። ይህ ፡ እስት ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ እውነት ?”

“ አልደፈረኝም ፡ ነፍሰጡርም ፡ አልሆንሁ ፡ በፊልጉ ፡ ባልቴት ፡ ያሳዩኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ እወደዋለሁ ። ” ስትል ፡ ሰብለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ገብቶ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠና ፡ ተቀመጠ ።እሱም፡ ማዘኑ ፡ ከፊቱ ፡ ጎልቶ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

“ ተመስገን ፡ ጌታዬ ! ቃልህን ፡ የማትበላ ፡ እማኝህን ፡ የማትከዳ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ! ተመስገን !” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጠው ፡ ማርቆስ ፡ በመንበረ ፡ ጸባኦቱ ፡ በግርማ፡ መለኮቱ ፡ ተቀምጦ ፡ የተወራው ፡ ወሬ ፡ እስት ፡ ይሁን ፡ብሎ ፡ ያዘዘው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደገና ፡ ታያቸውና ። ከዚያ ፡ ዘወር ፡ ብለው፡-

“ እንኩዋን ፡ ይህ ፡ እስት ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ የነገር ፡ እሱን ፡ መውደድ ፡ ሞላ ፡ ነው !የኔ ፡ ልጅ ፡ ያን ፡ እከካም ፡ የለማኝ ፡ ገበሬ ፡ ልጅ ፡ አትወጂም ! ዘሩ ፡ ባባት ፡ በናቱ ፡ የጠራ ፡ባደባ ባይ ፡ የሚያኮራ ፡ የታላቅ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ታላቅ ፡ መኮንን ፡ ለምኖኝ ፡ ቃል ፡ ሰጥቸ ፡ መጥቻለሁ ። ” አሉ ።

“ ገበሬም ፡ ሰው ፡ ነው !የገበሬ ፡ ልጅም ፡ የሰው ፡ልጅ ፡ ነው ! የመኩዋንንት ፡ ዘር ፡ ጥሩ ፡ የገበሬ ፡ ዘር ፡ ጉድፍ ፡ መሆኑን ፡ አውቆ ፡ መኩዋንንት ፡ የሚመርጥ ፡ ይቸገርበት ! እኔ ፡ የገበሬ ፡ ልጅ ፡ የሚሉትን ፡ እወደዋለሁ ! እሱ ፡ ምንም ፡ ሳይ ጠፋ ፡ እኔ ፡ ስለ ፡ ወደድሁት ፡ ብቻ ፡ የሚሰደብበት ፡ ምክና ያት ፡ የለም ! ከፈለጉ ፡ ከ . . .ከፈ. . . . ለጉ ፡ እኔን፡- . . . እኔን ፡ ይስደቡ !” አለች ፡ ሰብለ ፡ እንባዋ ፡ ጣምራ ፡ ጣምራ ፡ ሆኖ ፡ እየወረደ ፡ ንግግርዋን ፡ ሳግ ፡ እያቋዋረጠው ።

“ ያ ፡ መተታም ፡ አስማተኛ ፡ ደብተራ ፡ ያ ፡ ጠንቋዋይ ፡ በልጄ ፡ አስማት ፡ አዙሮባት ፡ ነው ! በጤናዋ ፡ እንዲህ ፡

አልሆንችም ! ግዴለም ፡ ይንጋ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደ ገና ፡ ተቆጥተው ።

" እሱ ፡ መተቷም ፡ አይደለም ! ከማናቸውም ፡ መኳ ንንት ፡ ነኝ ፡ ከሚለው ፡ ዘሎ ፡ የሚሻል ፡ ጭዋ ፡ ነው !" አለች ፡ ሰብለ ፡ በልቅሶ ፡ ፈንታ ፡ እልክ ፡ ያዛትና ፡ እንባዋን ፡ እዩጠ ረገች።–

" በጤናሽ ፡ ቢሆን ፡ እንዲህ ፡ የምትናገሪኝ ፡ አዝን ፡ ነበር ! ነገር ፡ ግን ፡ ጤና ፡ አይደለሽም ፡ ያ ፡ አስማተኛ ፡ ተማሪ ፡ ምናምን ፡ አዞሮብሽ ፡ ነው ፡ እኔን ፡ አባትሽን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ የምትናገሪኝ ፡ ስለዚህ ፡ በምትናገሪው ፡ አላዝንም ። የማዝነው ፡ ብቻ ፡ ጭዋ ፡ ነኝ ፡ ብዬ ፡ ለጭዋ ፡ ቃሌን ፡ መስ ጠቴ ፡ ነው ። "

" ከዛሬ ፡ ጀምረው ፡ ይጠቁት ፡ ነፍስና ፡ ስጋየ ፡ አብረው ፡ እያሉ ፡ ለማልፈልገው ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አልሸጥም ! ሬሳየ ፡ ዋጋ ፡ አይወጣላችሁም ፡ እንጂ ፡ በሱ ፡ እንደፈለጋችሁ ፡ ተጫወቱ ። " ስትል ፡ ሰብለ ፡ በብርቱ ፡ ቁጣ ፡ በዛብህ ፡ ያቆ ራኛት ፡ ሰይጣን ፡ ህይወትዋን ፡ በገዛ ፡ እጅዋ ፡ እንድታሳልፍ ፡ ያደርጋት ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ፊታውራሪ ፡ ፈርተው ፡ እግ ርዋ ፡ በግር ፡ ብረት ፡ እጅዋ ፡ ተገጥሞ ፡ በመቀነት ፡ ታስሮ ፡ እሳቸው ፡ አልፍኝ ፡ እንድትቀመጥና ፡ ራሳቸው ፡ እንዲጠብ ቁዋት ፡ አደረጉ ።

" አይደለም !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሰብለ ፡ ስትታሰር ፡ እዮቶ ፡ ንዴቱም ፡ አዘኑም ፡ አላስችለው ፡ አለና ።

" አይደለም ! ምነው ፡ ይችን ፡ ልጅ ፡ እስከዛሬ ፡ የሰቀዩ ዋት ፡ አንሶ ፡ ያባት ፡ ደመኛ ፡ ሆነው ፡ ስቃዩዋን ፡ ባያስረዝ ሙባት ! ቢበቃት ፡ ምን ፡ አለ ? እውነቱን ፡ ካልነገርሽኝ ፡ እገ ርፍሻለሁ ፡ ብለው ፡ ማስፈራራት ! እውነቱን ፡ ስትነግርዎ ፡ እውነቱ ፡ ከሰዎ ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ ባለመስማማቱ ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፡ ያናገረሽ ! አስማት ፡ ዞሮብሽ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስረው ፡ መሰቀየት ! ምን ፡ አድርጊ ፡ ይሉዋታል ? አባክዎ ፡ ይተዋት ፡ የፈለገችውን ፡ ደስ ፡ የሚላትን ፡ ታድርግ !"

"የኔ ፡ የመሸሻ ፡ ልጅ ፡ የገበሬ ፡ ልጅ ፡ የደሀ ፡ ልጅ ፡ ታግባ ?"

"የገበሬ ፡ ልጅ ፡ ማግባት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛት ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ ለሚወዳት ፡ ልጁ ፡ የምትወደውን ፡ ከማድረግ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ የተሻለ ፡ ነገር ፡ አለ ? ለሀብቱ ፡ እንደሆነ ፡ የርስዎ ፡ ሀብት ፡ እንኳዋን ፡ ላንዲት ፡ ልጅዎ ፡ ለብዙ ፡ ይበቃል ፤ ያለዚያም ፡ እኛ ፡ ዘመዶችዋ ፡ ተረዳድተን ፡ እናቋቁማቸዋለን !"

"ዘሩንስ ? ደሙንስ ? አንተና ፡ ዘመዶችዋ ፡ ተረዳድታችሁ ፡ ለውጣችሁ ፡ የጌታ ፡ ዘር ፡ የባላባት ፡ ልጅ ፡ ታደርጉታላችሁ ?"

"ሰው ፡ ጌታ ፡ ተብሎ ፡ ልጁም ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ ተብሎ ፡ የሚከበርና ፡ የሚታፈር ፡ በሀብቱ ፡ ቀጥሎም ፡ በችሎታው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዘሩ ፡ በደሙ ፡ አይደለም ። እርስዎ ፡ ብዙ ፡ ሎሌ ፡ አሳድረው ፡ እንዲህ ፡ ተዘባነው ፡ የሚኖሩ ፡ በሀብትዎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዘርዎ ፡ አይደለም ። በዘር ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከርስዎ ፡ ዘመዶች ፡ ብዙዎቹ ፡ አንዳንድ ፡ በሬ ፡ እንኳዋ ፡ አጥተው ፡ ለሰው ፡ ግብርና ፡ ተቀጥረው ፡ ባልኖሩ ፡ ነበር ! ብዙዎች ፡ የጅ ፡ ወረት ፡ እንኳዋ ፡ አጥተው ፡ የነጋዴ ፡ ኀረደማኞች ፡ የነጋዴ ፡ ሎሌዎች ፡ ባልሆኑ ፡ ነበር ! ብቻ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እንተውና ፡ እባክዎ ፡ ይተዋት ፡ የምትወደውን ፡ ታግባ !"

"እባካችሁ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የሚናገረውን ፡ አያውቅምና አንድ ፡ በሉልኝ ! የምትወደውን ፡ ታግባ ፡ ይለኛል ! ሰው ፡ አስማት ፡ ከሠረበት ፡ ሰይጣን ፡ ከተቆራኘው ፡ የሚወደው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ያውቃል ? ሰው ፡ ጤና ፡ ከሆነ ፡ ያላቻው ፡ ያለ ፡ ጉዋደኛው ፡ ይወዳል ? ቢወድስ ፡ እንኳዋን ፡ እንደርሶዋ ፡ ያለች ፡ ቆንጆ ፡ በገኝስ ፡ ብትሆን ፡ በብዙ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ እገሌን ፡ ወድጃለሁና ፡ አግባለሁ ፡ ብላ ፡ ተናግራ ፡ ታውቃለች ? እባካችሁ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ዝም ፡ አሰኙልኝ ! የምትወደውን ፡ ታግባ ፡ ይለኛል ! ቆይ ፡ ታያለህ ! ነገ ፡ ያን ፡ አስማተኛ ፡ ተማሪ ፡ አስይዤ ፡ አስመጥቼ ፡ ጀርባውን ፡ እንደ ፡ አባያ ፡ በሬ ፡ አስገጥቤ ፡ ያሰረውን ፡ አስማት ፡ ካስፈታሁ ፡ በሁዋላ ፡ ሰብለ ፡ ዛሬ ፡ የተናገረችውን ፡ የደገመችው ፡ እንደሆነ ፡ እውነትም ፡ አንተ ፡ አዋቂ ፡

እኔ ፡ ደንቆሮ ፡ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ ለልጂ ፡ ያባት ፡ ደመኛ ፡ ነኝ ! አሁን ፡ ገዞ ፡ በለኝ ፡ በንጉስ !"

"ካሳ ! ለሰብለ ፡ አጎት ፡ ነህ ፡ እንጂ ፡ አባት ፡ አይደለህም ! ስለዚህ ፡ ለሾዋ ፡ ደስታ ፡ ካባትዋ ፡ የበለጠ ፡ አስባለሁ ፡ ብትል ፡ ሰው ፡ ቀብጥህ ፡ ይልሀል ! እንዲያውም ፡ ዘዛላህ ፡ አስማት ፡ አዞረባት ፡ ሰይጣን ፡ አቀራኛት ፡ ተብሎ ፡ በዘንቱ ፡ ይታማል ፡ እንጂ ፡ ለልጂቱ ፡ አስማትና ፡ ሰይጣን ፡ የሆናት ፡ ያንተ ፡ ትምርት ፡ ነው ። 'ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ነው ! ሰው ፡ የሚወደውን ፡ እንጂ ፡ የሚመስለውን ፡ ማግባት ፡ የለበትም !' እያልህ ፡ ሰብከህ ፡ ነው ፡ እዚህ ፡ ያደረስሀት ! አንተ ፡ ባሪያ ፡ አግብተህ ፡ ለወገንህ ፡ ሁሉ ፡ ማፈሪያ ፡ መሆንህ ፡ አንሶ ፡ ደግሞ ፡ እሰው ፡ ቤት ፡ ገብተህ ፡ አትበጥብጥ ! ሁለተኛም ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ እንዳትደርስ !" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ባላቸው ፡ ከተቆጡዋቸው ፡ ጀምሮ ፡ ገዞ ፡ ብለው ፡ ቆይተው ።

"አዎ ፡ ሁለተኛ ፡ እዚህ ፡ እንዳትደርስ !" አሉ ፡ ፊታውራሪም ፡ ተቀብለው ።

"እኔ ፡ ድሮውንም ፡ እስዋን ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ የምመጣ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ የለኝም ። ከእንግዴህ ፡ ወዲያ ፡ ግን ፡ እስዋም ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ እስዋ ፡ አትሆን ፡ እኔም ፡ ሌላ ፡ አይነት ፡ ሰብለ ፡ ለማየት ፡ አልመጣ ! ብቻ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልንገራችሁ ። ይህች ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብትሆን ፡ ደሟ ፡ መላሽዋ ፡ እኔ ፡ መሆኔን ፡ እወቁ ።" ብሎ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የመጣበትን ፡ ልቅሶ ፡ ለመዋጥ ፡ እዬታገለ ፡ ተነስቶ ፡ ሄደ ። ሰብለ ፡ ታስራ ፡ አባትዋ ፡ እልፍኝ ፡ ትሰቀስቅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ይህና ፡ ሁኔ ፡ እንዘዋ ፡ አላዩትም ።

## ምእራፍ ፡ ፷፰

## ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ መስቀል ፤

ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ከታሰረችበት ፡ ባስረኛው ፡ ቀን ፡ እስከትፈታ ፡ ድረስ ፡ አባትዋም ፡ እግራቸው ፡ በግር ፡ ብረት ፡ ውስጥ ፡ አይግባ ፡ እንጅ ፡ እንደሰዋ ፡ እስረኛ ፡ ሆነው ፡ ሰነበቱ ።

የጅዋ ፡ መታሰር ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ ልብስ ፡ በመልበስም ፡ ጊዜ ፡ ችግር ፡ ስለፈጠረ ፡ ወዲያውም ፡ እሳቸው ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ካጠገብዋ ፡ የማይለዩ ፡ በመሆናቸው ፡ የማያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ስለተገኘ ፡ በታሰረች ፡ ማግስት ፡ እጅዋን ፡ እንድትፈታ ፡ ተደረገ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለት ፡ ወይም ፡ ሹልነት ፡ ያለው ፡ ብረትም ፡ ሆነ ፡ እንጨት ፡ ባጠገብዋ ፡ እንዳይደርስ ፡ የምትበላውንም ፡ ሆነ ፡ የምትጠጣውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ በሳቸው ፡ ፊት ፡ አቅራቢዎቹ ፡ ሳይቀምሱት ፡ ለስዋ ፡ እንዳይቀርብላት ፡ አጥብቀው ፡ ይጠነቀቁ ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ልጃቸውን ፡ ሲጠብቁ ፡ ፊትዋ ፡ ህይወት ፡ እንደሌለው ፡ ጥሩ ፡ ምስል ፡ ፍዝዝ ፡ ብሎ ፡ አይኖችዋ ፡ ቡዝዝ ፡ ብለው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተተክለው ፡ ይቆዩና ፡ ድንገት ፡ እንባዋ ፡ በጉንጭዋ ፡ ያወጣውን ፡ መንገድ ፡ ተከትሎ ፡ ሲሄድ ፡ የማያቋርጥ ፡ ሳግ ፡ ሲተናነቃት ፡ ያዩና ፡-

"ወይ ፡ እኔ ፡ መሽሻ ! ይህ ፡ እጥማጅ ፡ ይህ ፡ እስማተኛ ፡ ተማሪ ፡ በልጄ ፡ ተጫወተባት ! ምነው ፡ ጌታየ ! ላንድ ፡ አፍታ ፡ በጄ ፡ ጥለኸው ፡ በልጄ ፡ እንደተጫወተ ፡ ጅርባውን ፡ የዝንብ ፡ መጫወቻ ፡ ባደርገው ! ሌላ ፡ ምንም ፡ አልለምንህም ! ይህን ፡ ብቻ ፡ ጌታየ ! ይህን ፡ ብቻ ፡ አድርግልኝ !" ይላሉ ፡ በብርቱ ፡ ስሜት ፡ አይኖቻቸውን ፡ እግዚአብሄር ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንስተው ። ነገር ፡ ግን ፡ ፈረሰኞች ፡ የማንኩሳን ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ የደብረ ፡ ወርቅንና ፡ የሲናዳን ፡ መንገድ ፡ እዮተከተሉ ፡ እግረኞች ፡ ዱማ ፡ ውስጥ ፡ የበዛብህ ፡

ወዳጆች ፡ ናቸው ፡ የሚባሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ በዱም ክናያቱ ፡ እዩገቡ ፡ ስለት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ በዛብህን ፡ ፈልገው ፡ ስላጡት ፡ እንደማያገኙ ፡ ተስፋ ፡ ተቁርጦ ፡ ፊታውራሪ ፡ መፍትሔ ፡ ጸርና ፡ መፍትሔ ፡ ስራይ ፡ የሚያውቅ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በምስጢር ፡ ተፈልጎ ፡ ቢገኝ ፡ የጠዩቀውን ፡ ዋጋ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብለው ፡ ያስፈልጉ ፡ ጀመር ።

በዛብህ ፡ በዚኑሉ ፡ የፍቅርና ፡ የፍራት ፡ እስረኛ ፡ ሆኖ ፡ እጉዱ ፡ ካሳ ፡ ቤት ፡ ተሸሽጎ ፡ በሰብለ ፡ የደረሰው ፡ ከሰማው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጎልቶ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በርክቶ ፡ እዩታዩው ፡ ነጻ ፡ ሳለች ፡ የነበረችውና ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሆነችው ፡ እዩተለዋ ወጠ ፡ እዩታዩው ፡ የሚበላው ፡ በፋ ፡ እየተንከራተተ ፡ አይ ዋጥለት ፡ ቢተኛ ፡ እንቅልፍ ፡ አይወስደው ፡ እያደር ፡ እንደ ፡ ቀረፈቱት ፡ ዛፍ ፡ እዩጠወለገና ፡ እዩደረቀ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

"ያሰሩዋት ፡ እኔን ፡ አስማት ፡ አድርጎባታል ፡ ብለው ፡ ከሆነና ፡ እኔ ፡ ሄጄ ፡ ፈታሁ ፡ ካላልሁ ፡ የማይፈትዋት ፡ ከሆነ ፡ አሁን ፡ ብሄድና — ነእኩተከን ፡ ወይም — ጸሎተ ፡ ሃይማኖ ትን ፡ ደግሜ ፡ ፈትቻታለሁ ፡ ብል ፡ ምናለ ? መቸም ፡ ፀም ደግመውን ፡ እያሰማሁ ፡ ድገም ፡ አይሉኝ !" አለ ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ጋር ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ እንስተው ፡ ሲወያዩ ።

"ነገሩ ፡ በዚህ ፡ ብቻማ ፡ የሚያልቅ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ያስቸግር ፡ ኖሮዋል ?"

"ታዲያ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ይኖራል ?"

"ምነው ፡ ነግሬህ ፡ የለም ? እገርፈዋለሁ ፡ ብለውኮ ፡ ነው ፡ የሚፈልጉ ! ደግሞ ፡ ካገኙህ ፡ እንደ ፡ ፈከሩት ፡ ማድረ ጋቸው ፡ አይቀርም ፡ ባለጌ ፡ ናቸው !"

"ታዲያ ፡ ይግረፉኝ ፡ እንጂ ፡ ምናለ ! እሰዋ ፡ ታስራ ፡ ከምትሰቀይ ፡ ይግረፉኝ ! ነገ ፡ የሚድን ፡ ቁስል ፡ አይደል ?"

"እዎ ፡ የተገረፈ ፡ ጀርባ ፡ ቶሎ ፡ ይድን ፡ ይሆናል ፡ የተሰበረ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ እንጃ !"

"እንዴት ?"

"ስትገረፍ ፡ አይታ ፡ ወይም ፡ መገረፍህን ፡ ሰምታ ፡ ሰው ፡ የምትሆን ፡ ይመስልሀል ? ባትሞት ፡ ልብዋ ፡ እንደ ፡

ተሰበረ ፡ ይቀራል ። ለምን ፡ ሰደቡት ፡ ብላ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ያለቀሰች ፤ ያን ፡ ያክል ፡ የምትሆነውን ፡ ያጣች ፡ መገረፍ ሆን ፡ ያዩች ፡ ወይም የበግች እንደሆነ ፡ ሰው ፡ እንደማት ሆን ፡ አውቃለሁ ። ስለዚህ ፡ ከምትሞት ፡ ወይም ፡ ሌብ ፡ የሚ ሰብር ፡ አዘን ፡ ከሚደርስባት ፡ ታስራ ፡ ብትቆይ ፡ ይሻላል ። ወዲያውስ ፡ ስንት ፡ ቀን ፡ አስረው ፡ ያኖርዋት ፡ መሰለህ ? አሁን ፡ ይፈትዋታል !"

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሲናገር ፡ በዦብሀ ፡ እንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ እዩ ሰማ ፡ እንባው ፡ ፊቱን ፡ ሳይነካ ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ይንጠባጠብ ፡ ነበር ።

እውነትም ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንዳለው ፡ መፍትሔ ፡ ጸርኖ ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ የማያውቁ ፡ ሰው ፡ እዚያው ፡ ዲማ ፡ ተገ ኝተው ፡ መፍትሄውን ፡ ስላደረጉላት ፡ ሰብለ ፡ በታሰረች ፡ ባስረ ኛው ፡ ቀን ፡ ተፈታች ።

" ጌቶች ! አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለብቻ ፡ ባነጋግርዎ ፡ እወድ ፡ ነበር ፡ " አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ፊታውራሪ ፡ እልፍኛቸው ፡ እሰ ብለ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጠው ፡ ዳዊት ፡ በሚደግሙበት ፡ በቾ ኮላ ፡ ገብተው ።

" ወዬው ፡ ጉድ ! ምን ፡ እንደማደርግ ፡ አያዩም ? ዳዊ ቴን ፡ አቋርጨ ፡ ነው ፡ እስምን ፡ የማነጋግር ?"

" ግዴለም ፡ ያቋርጡት ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ነው ! "

ከዚያ ፡ ፊታውራሪ ፡ የንስሀ ፡ አባታቸው ፡ እሳቸውን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ካልያዙ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ እንደማይደ ፍሩ ፡ ስለሚያውቁ ፡ ያባ ፡ ሞገሴን ፡ ቃል ፡ ለማክበር ፡ ሳይ ሆን ፡ ወሬያቸውን ፡ ለመስማት ፡ በመቸኮል ፡ ዳዊታቸውን ፡ አጥፈው ፡ በሩን ፡ ወጣ ፡ አሉና ፡ ሰብለን ፡ ለማየት ፡ በሚችሉ በት ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ ቆሙ ።

" የምስራች ! " አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ሰብለ ፡ እንዳት ሰማ ፡ ድምጻቸውን ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ።

" ምስር ፡ ይብሉ ! ምንድነው ? "

"መፍትሄ ፡ አርኖ ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ የሚያውቁ ፡ ሰው ፡ እዚሁ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ተገኙ ።"

"የት ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፊታቸው ፡ ሁሉ ፡ በቅጽበት ፡ ተለውጦ ። ከደስታቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ ፊታቸው ፡ እንዳሉ ፡ ከንፈሮቻቸውና ፡ ጉንጮቻቸው ፡ ሲንቀጠቀጡ ፡ አይኖቻቸው ፡ እንባ ፡ ሲሞሉ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ።

"እዚሁ ፡ ዲማ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ የሚኖሩ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ የሚባሉ ፡ መነኩሴ ፡ ናቸው ።"

"መቼ ፡ የመጡ ፡ ናቸው ?"

"እ —ከመጡስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜያቸው ፡ ነው ! ብቻ ፡ ከመቃብር ፡ ቤታቸው ፡ አይወጡም ፡ አንዳንድ ፡ ምክር ፡ ሊጠይቋቸው ፡ ከሚሄዱ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ በቀር ፡ ከብዙ ፡ ሰውም ፡ አይገናኙ ።"

"ታዲያ ፡ እሸም ፡ እንዴት ፡ አወቋቸው ? ደግሞስ ----እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰው ፡ ከሆኑ ፡ ይህን ፡ ነገር ----ደህና ፡ አድርገው ፡ የሚያውቁ ፡ ይመስልዎታል ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መጠራጠር ፡ አሉና ።

"እኔማ ፡ በዩጊዜው ፡ እዩሄድሁ ፡ መንፈሳዊ ፡ ምክር ፡ ስለምጠይቃቸው ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ አውቃቸዋለሁ ። ይህ ፡ ነገር ፡ ከደረሰብን ፡ ወዲህ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ የማይነገር ፡ ስለሆነ ፡ እስቲ ፡ እግዚአብሄር ፡ ከኛ ፡ ለሳቸው ፡ ቅርብ ፡ ነውና ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ የሚገልጽላቸውን ፡ መንገድ ፡ ያሳዩን ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ሄጄ ፡ በምስጢር ፡ ባዋያቸው ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ላደርገው ፡ እችላለሁ ፡" አሉኝ ።

"ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ዘርዝረው ፡ ነግረዋቸው ፡ አውቃለሁ ፡ አሉ ?"

"አዎ ፡ ለማንም ፡ የሚነገር ፡ አለመሆኑን ፡ ጭምር ፡ አደራ ፡ ብዬ ፡ ነግሬያቸው ፡ ለሁሉም ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ብለውኛል ።"

"እንግዲህ ፡ ማታ ፡ ያምጡዋቸውና ፡ ለብቻ ፡ ላነጋግራቸው ።"

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ልደታቸው ፡ በወሎ ፡ ውስጥ ፡

ጉድሩ ፡ በሚባል ፡ ክፍል ፡ ነው ። በልጅነታቸው ፡ በዘር ፡ መዝሪያ ፡ አካላቸው ፡ አደጋ ፡ ያደረሰባቸው ፡ ወዲያው ፡ ቁስሉ ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ከዘመዶቻቸው ፡ ከተባለለው ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ ተሻግረው ፡ ካንዱ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ንባብና ፡ ዜማ ፡ ከዚያም ፡ ትንሽ ፡ ቅኔ ፡ ከተማሩ ፡ በሁዋላ ፡ መንኩሰው ፡ ከጎጃም ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ አመት ፡ ያልተቀመጡበት ፡ አይገኝም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዲማ ፡ ከተቀመጡ ፡ አንድ ፡ አመት ፡ አልፎዋቸዋል ። በደረሰባቸው ፡ አደጋ ፡ ምክንያትም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ከፍጥረታቸው ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ከመጨመር ፡ ብቸኝነትን ፡ ከመናገር ፡ መስማትን ፡ የሚመርጡ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ። ብዙ ፡ ሰምተው ፡ ትንሽ ፡ የተናገሩ ፡ እንደሆነም ፡ ያቺ ፡ ትንሽን ፡ ሳይጨርሱ ፡ መዝፈው ፡ ስለሚተውት ፡ በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ የሚተረጎም ፡ ይሆንና ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ “ አባ ፡ ተክለሀይማኖትማ ፡ ብለው ፡ ነበር ፡ ” የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ባለመጥፋቱ ፡ አዋቂ ፡ ባህታዊ ፡ ይባላሉ ። “ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖትን ፡ ለማናገር ፡ ቀጥሎም ፡ የተናገሩትን ፡ ለማስተዋል ፡ ከተቻለ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ቃላቸው ፡ እመሬት ፡ ጠብ ፡ አይልም ። ” ይባላል ።

ስለዚህ ፡ እንደሳቸው ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ በጸሎት ፡ ለተጠመዱ ፡ ምእመናን ፡ ከቤተክርስቲያን ፡ ከሚላክላቸው ፡ መሀራ ፡ ሌላ ፡ በመልክም ፡ በወሬም ፡ የሚያውቁዋቸው ፡ ሰዎች ፡ “ አደራችሁን ፡ ” እያሉ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ልብስም ፡ ገንዘብም ፡ እየላኩላቸው ፡ ደህና ፡ ይቀመጣሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ አዘውትረው ፡ የሚለብሱት ፡ ደበሎ ፡ ስለሆነ ፡ ሰው ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ጋቢም ፡ ሆነ ፡ ኩታ ፡ መልሰው ፡ ልብስ ፡ ለሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ይሰጡታል ። እንዲሁም ፡ ገንዘብና ፡ መጠጥ ፡ ሲሰጡ ፡ አይታዩም ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ከሚልክላቸው ፡ ምግብ ፡ የሚበልጠውን ፡ መሸት ፡ ሲል ፡ ተሸክመው ፡ ወስደው ፡ ደጀሰላምና ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ለወደቁ ፡ ድሆችና ፡ በሽተኞች ፡ እየዞሩ ፡ ይመጸውታሉ ። ታዲያ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያዩ ፡ ስለሚያወሩ ፡ ተመጽውተው ፡ መመጽወታቸውም ፡ የሚመጸውቱበት ፡ ሁኔታም ፡ ለት

ልቅ ፡ ጻድቅነታቸው ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክር ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠርላቸው ፡ ነበር ፡፡

ፊታውራሪ ፡ አባ ፡ ሞገሴንና ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖትን ፡ በቀጠሩበት ፡ ማታ ፡ ከራት ፡ በሁዋላ ፡ ምሽታቸውን ፡ ከለ ብሰ ፡ ጋር ፡ አስቀምጠው ፡ " ስእል ፡ ቤት ፡ " በሚሉዋት ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ ብቻቸውን ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጠብቁ ፡ የንስሀ ፡ አባታቸው ፡ እንግዳውን ፡ ይዘው ፡ ደረሱ ፡፡

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ እንደሳቸው ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ እንደ ፡ ደረሰባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ዘለግ ፡ ብለው ፡ ከትከሻቸው ፡ ትንሽ ፡ ሰግደድ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡፡ ልብ ሳቸውም ፡ ቆባቸውም ፡ ደበሎ ፡ ነው ፡፡

ከርዝመታቸውና ፡ ከቅጥነታቸው ፡ የተነሳ ፡ የለበሱት ፡ ደበሎ ፡ በረኝም ፡ መስቀያ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተንጠለጠለ ፡ ሁሉ ፡ ከጉልበታቸው ፡ በታች ፡ ረዥም ፡ ቅልጥማቸውን ፡ ራቁት ፡ አድርጎ ፡ ባርኔ ፡ ጨርቅ ፡ የተጠቀለለ ፡ ነገር ፡ በሁለት ፡ እጃ ቻቸው ፡ ቀደም ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ ፊታውራሪን ፡ ምሀረት ፡ እንደሚለምኑ ፡ ሁሉ ፡ አንገታቸውን ፡ ቀልሰው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ሳይተነፍሱ ፡ እፊታቸው ፡ ቆሙ ፡፡ ሲገቡ ፡ ሰላምታ ፡ እንኳ ፡ ባለመስጠታቸው ፡ ፊታ ውራሪ ፡ ገርሞቀቸው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እያዩዋቸውን ፡ ፍጥጥ ፡ አድርገው ፡ ይመለከቷቸው ፡ ጀመር ፡፡

"ጌቶች ! አባቴ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ እሳቸው ፡ ናቸው ፡፡" አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ የተፈጠረውን ፡ ሁኔታ ፡ ሲያዩ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሸበር ፡ አሉና ፡፡

" እህ --- እሳቸው ፡ ናቸው ? እንደምን ፡ ነዎ ፡ አባቴ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ አንገታቸውን ፡ ከደፉበት ፡ አሁንም ፡ ትንሽ ፡ ዝቅ ፡ አደረጉ ፡ ሰላምታውን ፡ ለመመለስ ፡፡

" ይምጡ ፡ እዚህ ፡ ይቀመጡ ! " አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ መቀመጫ ፡ ላባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ እያሳዩ ፡ አባ ፡ ሞገሴን ፡ እውጭ ፡ ቆመው ፡ ሰው ፡ ሲመጣ ፡ እንዲከለክሉ ፡ አዘዙዋ

ቸው ።

“ የደረሰብኝን ፡ ችግር ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ነግረዎዎታል ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ።

“ እ -- አዎ ! ”

“ ታዲያ ፡ ይሆንልዎታል ? ”

“ ለግዚአብሄር ----- የማይሆን ፡ አለ ? ”

“ ለግዚአብሄርማ ፡ ምን ፡ የማይሆን ፡ አለ ! እዩ ? ልጄ ፡ መፍትሄ ፡ ጸርና ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ እንዲያደርጉላት ፡ ነው ፡ ያስመጣሁዎ ! ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ከዛሬ ፡ ቀደም ፡ አድርገዋል ፡ ወይ ፡ ማለቴ ፡ ነው ! ”

“ እኔስ --- እሱን ፡ ማለቴ ፡ አይደል ! ”

“ ድጋም ፡ ነው ? ወይስ ፡ ምንድነው ፡ የሚያደርጉላት ? ”

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ለተጠዩቁት ፡ ጥያቄ ፡ የቃል ፡ መልስ ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ ባሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ ጠቅልለው ፡ የያዙትን ፡ ነገር ፡ ገልጠው ፡ ለፊታውራሪ ፡ አሳዩዋቸው ።

“ እእ --- መስቀል ! ታዲያ ፡ በመስቀሉ ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ? ”

“በሰው ፡ እጅ ፡ የተሰራ ---- መስቀል ፡ አይደለም ።

“ታዲያስ ? ”

“ አስራ ፡ አምስት ፡ ቀንና ----- አስራ ፡ አምስት ፡ ሌሊት ፡ ባንድ ፡ እግሬ ፡ ቆሜ ፡ ስጸልይ ፡ የተሸለምሁት ፡ ነው ፡ በአቃቤ ፡ ስራይ ፡ በጸላኤ ፡ ሰናይ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ስልጣን ፡ ያለው ፡ ነው ! ”

“ከማን ፡ ነው ፡ የተሸለሙት ? ”

“ ጸሎቱ ፡ ላረገለት ፡ ፍጡር ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ ሸላሚ ፡ አለ? ”

“ ከእግዚአብሄር ፡ የወረደልዎ ፡ መስቀል ፡ ነው ? ”

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆዩና ፡ “ አለመጠርጠር ፡ ነው ፡ ምንም ፡ የሚያስቸግር ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ነገሩ ---- ቀላል ፡ ነው ። ነገ ፡ ማታ ----እዚሁ ፡ ቦታ ፡ ልጅቱን ፡ ብቻዋን ፡ ላግኛት ! ” ብለው ፡ ለመሄድ ፡ ተነሱ ።

" ይቆዩ ፡ መጠጥ ፡ ጠጥተው ፡ ይሂዱ ፡ አባቴ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

" አይደለም ፡ ይቆዩኝ ፡ "

ፊታውራሪ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖትን ፡ አሰናብተው ፡ ወደልፍኛቸው ፡ ተመልሰው ፡ የተነጋገሩትን ፡ ሁሉና ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ መስቀል ፡ ማየታቸውን ፡ ለሰብለ ፡ ሲነግሩዋት ፡--- ዶብተሮችና ፡ አንዳንድ ፡ አዋቂዎች ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ አታላዮች ፡ ብዙዎችን ፡ ከፉ ፡ መንፈስ ፡ ተቆራኝቶዋቸዋል ፡ ወይም ፡ አብነት ፡ ተደርጎባቸዋል ፡ እያሉ ፡ በማጥመቅ ፡ በመማረፍ ፡ ሰውነት ፡ በማቃጠል ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ ነገር ፡ በማብላትም ፡ ሆነ ፡ በማጠጣት ፡ እንደሚያሰቃዩዋቸው ፡ በሰዋም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ እንዳይደርስባት ፡ ለጊዜው ፡ ፈራች ። ይህን ፡ ስታወጣ ፡ ስታወርድ ፡ ሌሊቱ ፡ እስኪገባደድ ፡ እንቅልፍ ፡ አጥታ ፡ ቈይታ ፡ በመጨረሻ ፡ ታስራ ፡ ከመቀመጥ ፡ የደረሰ ፡ ደርሶባት ፡ ከታሰረችበት ፡ መፈታት ፡ የሚሻል ፡ መሆኑን ፡ ወሰነች ። ይልቁንም ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ የታሰረችበት ፡ እግር ፡ ብረት ፡ በጨርቅ ፡ ቢጠቀለል ፡ እግሮችዋን ፡ ከፉኛ ፡ አቍስሎ ፡ በተቀመጠችበትም ፡ መንቀሳቀስ ፡ ስላቃታት ፡ ከግር ፡ ብረት ፡ እስክትገላገል ፡ ቸኰለች ።

በማግስቱ ፡ ማታ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ በተቀጠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ሲመጡ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሰብለን ፡ ይዘው ፡ በእል ፡ ቤት ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።

" እንዴት ፡ ዋሉ ፡ አባቴ ! እስዎ ፡ እስኪመጡ ፡ ብቻዋን ፡ እንዳትሆን ፡ ብዬ ፡ ነው ፤ እዚህ ---- የቆዩሁም ! ይበሉ ፡ እንግዴህ ፡ ሲጨርሱ ፡ ያጨብጭቡ ፡ እወዲያኛው ፡ ቤት ፡ እቆያለሁ ! " አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ ወጡ ። አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ሰብለን ፡ ትንሽ ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ አዩና ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ ብለው ፡ እንደገና ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ቆሙ ።

" ወዲህ ፡ ይም ጡ ፡ እንጂ ፡ አባቴ ፡ ይም ጡ ፡ እዚህ ፡ ይቀመጡ ! " አለች ፡ ሰብለ ፡ መቀመጫ ፡ በጅዋ ፡ እሳይታ ። አባ ፡ ተክለ ሀይማኖት ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ መስ

ቀላቸውን ፡ ከተጠቀለለበት ፡ አሮጌ ፡ ሐርቅ ፡ ይፈቱ ፡ ጀመር ።

ከዚያ ፡ የብረት ፡ መስቀላቸውን ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይዘው ፡ ትንሽ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ እግሮቻቸውን ፡ ገጥመው ፡ ቆመው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ ይደግሙ ፡ ጀመር ። አፋቸው ፡ ሲንቃንቅ ፡ ከመታየት ፡ በቀር ፡ ድምጻቸው ፡ አይሰማም ። ይደግሙ ፡ ይደግሙና ፡ እፍፍ ፡ እፍፍ ፡ እያሉ ፡ አዩሩን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ በመስቀሉ ፡ ይቀዝፉታል ። እንዲህ ፡ ላይና ፡ ታች ፡ እያዩ ፡ ሲደግሙ ፡ እፍፍ ፡ እፍፍ ፡ እያሉ ፡ አዩሩን ፡ በመስቀል ፡ ሲቀዝፉ ፡ ደግሞ ፡ ሲደግሙ ፡ ደግሞ ፡ አዩሩን ፡ ሲቀዝፉ ፡ ብዙ ፡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ ቀረብ ፡ አሉና ፡ ጎንበስ ፡ ብለው ፡ “መስቀሉን ፡ ሳሚ !” አሉ ። ሰብለ ፡ መስቀሉን ፡ ሳመች ።

“ ተሳለሚው ! ”

ሰብለ እንደ ፡ ታዘዘችው ፡ አደረገች ። ከዚያ ፡ መስቀሉን ፡ ገልብጠው ፡ ያዙና ፡– “በይ ፡ አፍሽን ፡ እመስቀሉ ፡ ላይ ፡ ግንባርሽን ፡ እመያዣው ፡ ላይ ፡ አሳርፊሽ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለሽ ፡ ቆይና ፡ በሁዋላ ፡ ለምጠይቅሽ ፡ ትመልሽልኛለሽ ፡”

አሁንም ፡ ሰብለ ፡ እንደ ፡ ታዘዘችው ፡ አደረገች ።

“አይንሽን ፡ ጨፍኚው !”

“ እሺ ፡ ”

“ ምን ፡ ይታይሻል ? ”

“ምንም ፡ አይታዩኝ ”

“ ምን ፡ ይሰማሻል ?

“ ምንም ፡ አይሰማኝ ! ”

“ እስቲ ፡ አስቢና ፡ መጀመሪያ ፡ ባሳብሽ ፡ ውስጥ ፡ የሚመጣውን ፡ ንገሪኝ ! ”

“ እሺ ። ”

“ አሁን ፡ ባሳብሽ ፡ ምን ፡ መጣ ? ”

“መስቀል ፡ ሀይልነ ፡ መስቀል ፡ ቤዛነ ፡ መስቀል ፡ ጽንነ ፡ መስቀል ፡ መድሀኒተ ፡ ነፍስነ ፡ የሚለው ፡ ንባብ ፡ ታሰበኝ ! ”

“ መልካም ! ሌላ —– ምንም ፡ አልታሰበሽ ? ”

"የለም ።"

"ይህን ፡ ሁሉ ---- ችግር ፡ ያመጣብሽ ፡ ሰው ፡ አልታሰበሽም ?"

ሰብለ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ቆዩችና ፡ የ --- የለ --- የለም !" ስትል ።

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ መስቀሉን ፡ ይዘውላት ፡ እንዳጎነበሱ ፡ በጃቸው ፡ ለበብ ፡ ያለ ፡ ውሀ ፡ የፈሰሰባቸው ፡ መስለው ፡ ተስማቸውና ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ ብለው ፡ -- "እንግዴህ ፡ በቃ ! ቀና ፡ በይ ! "አሉ ።

ከዚያ ፡ አባ ፡ ተክሌ ፡ መስቀሉም ፡ እጃቸውም ፡ የታጠበበትን ፡ እንባ ፡ መስቀላቸውን ፡ በሚጠቀልሉበት ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ ጠራርገው ፡ አድርቀው ፡ ሲያጨበጭቡ ፡ ፈታውራሪ ፡ ቶሎ ፡ መጡ ።

"ለብቻዎ ፡ ሳነጋገርዎና ፡ ልሂድ ! "አሉ ፡ መነኩሴው ።

ፈታውራሪ ፡ ሰብለን ፡ ደግፈው ፡ አስነስተው ፡ ወደልፍኛቸው ፡ ወስደው ፡ ከናትዋ ፡ ጋር ፡ ካስቀመጥዋት ፡ በሁዋላ ፡ ተመልሰው ፡ መጥተው ፡ እመደባቸው ፡ ላይ ፡ ሲቀመጡ ፡ "ይበሉ ፡ እንግዴህ ፡ ሁሉንም ፡ ይንገሩኝ ፡ አባቴ ! አደራዎ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳይሰውሩኝ ! "አሉ ፡ በዛብህ ፡ ልጃቸውን ፡ ያቀራኛት ፡ ከፉ ፡ መንፈስና ፡ ያደረገባት ፡ አስማት ፡ ምን ፡ አይነት ፡ እንደነበረ ፡ ለማወቅ ፡ እጅግ ፡ ቸኩለው ።

"ከንግዲህ ፡ ----ምንም ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ----የለም ! " አሉ ፡ አባ ፡ ተክሌ ፡ በጣም ፡ በለሰለሰ ፡ ድምጽ ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ።

" ምን ፡ ኖሮዋል ፡ ለመሆኑ ? ጸላኢ ፡ ሰናይ ፡ ነው ? "

"የለም ፡ ጸላኤ ፡ ሰናይ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ከፉ ፡ መንፈስ --- አይደለም ! "

"ታዲያስ ? "

"ብርቱ ፡ አስማት ፡ ብርቱ ፡ ድጋም ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ያልተለመደና ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ሊፈታ ፡ የማይቻል ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያስጠላ ፡ ድጋም ፡ ነበር ፡- ተፈታ ፡ አሁን ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ---የለም ፡ "

“እንዴትኮ ---እዚህ ፡ አገር ፡ ያልተለመደ ፡ ከሆነ ፡--- እዚህ ፡ አገር ፡ ሊፈታ ፡ የማይቻል ፡--- ከሆነ ፡ እንዴት ፡ ነው ?” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በሻከረ ፡ ድምጽ ፡ ልትሶ ፡ መጥቶባቸው ።

“ከየት ---እንደ ፡ ተማረው ፡ እንጃ ! ብቻ ፡ ለመፍታቱ ፡ ግን ፡---መቸም ፡ የመስቀሉ ፡ ስልጣን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ባለመሆኑ ፡ የመስቀሉ ፡ ስልጣን ፡ ካጽናፍ ፡ እስካጽናፍ ፡ በመሆኑ ፡ የማይፈታው ፡ አስማት ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ተፈታ ።”

“እዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥሉ ፡ አይጥለኝም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ስላልጣለኝ ፡ ነው ፡ እስዎን ፡ የጣለልኝ !” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አይኖቻቸው ፡ እንባ ፡ ሞልተው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ባነሱ ፡ ቁጥር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ጣራው ፡ እያዩ ።

“እንግዲህ ፡---ልጅቱ ፡ ትፈታ ! ብቻ ፡ መበቀት ፡ ነው !”

“እንዴት ?”

“ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያህ ፡ የደረሰው ፡ ነገርና ፡---የሰውዬው ፡ ስም ---በፊትዋ ፡ እንዳይነሳ ፡ ከሞዛ ፡ ፈዛዛው ፡---እዩተቀንሰ ፡ መንፈሳዊ ፡ ታሪክ ---እንዲተረክላት ፡ ማድረግ ፡ መልካም --- ነው ! ”

“እዩ ፡ አባቴ ፡ የኔዋ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ እሱም ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ እጅዋን ፡ ለምኚን ፡ ለመስጠት ፡ እስቤያለሁ ፡ ታዲያ --- ምን ፡ ይመስልዎታል ? ”

“እሱማ ፡---ድንቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ! እስከዚያ ፡ ግን .---- እንዲህ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ”

“እስከ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ?”

“የሰስት ፡---ያራት ፡ ወር ፡ እድሜ ፡”

“ያን ፡ ያክልስ ፡ መስናዶውም ፡ ይፈጅል ! ታዲያ ----- ለዚህ ፡ አጭር ፡ ጊዜ --- እስዎ ፡ ባጠገብዋ ፡ ሆነው ፡ ቢመክሩ ዋትና ፡ አሁን ፡ እንዳሉት ፡----የሚስማማውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ታሪክ ፡ እዩመረጡ ፡ ቢተርኩላት ፡ ይመችዎታል ?”

“ምን ፡ ከፋኝ ፡ ነበር ! ነገር ፡ ግን ---- ለብዙ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ባለአደራ ፡ ስለሆንሁ ፡ ጸሎት ፡ እንዳይታጎልብኝና ፡ ደግሞ ----

ከምእመናን ፡ እዩ-ተመጸወትሁ ፡ የምመጸውታቸው ፡ ድሙያን ፡ እንዳይቸገሩብኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤" አሉ ፡ አባ ፡ ለመስማት ፡ በሚያስቸግር ፡ ዝቅተኛ ፡ ድምጽ ።

"ጸሎትዎን ፡ ሲጨርሱ ፡ የሚሰጡዎት ፡ ምክር ፡ ይበቃል ! ለምጽዋቱ ፡ ግን ፡ ጭራሽ ፡ አያስቡ ፡ እህል ፡ ውሀም ፡ ይሁን ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ያክል ፡ እንሰጥዎታለን ! ልጂ ፡ ይሀና ፡ ሆና ፡ ያባት ፡ ወግ ፡ ከደረሰኝ ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ገንዘብ ፡ ቆጥቤ ፡ የማደርገው ፡ ነገር ፡ የለም ፤ እንኩዋን ፡ ዛሬ ፡ ድሮም ፡ ገንዘብ ፡ ቆጣቢ ፡ አይደለሁም ።"

"እስቲ ፡ ጸሎት ፡ አድርጌ ፡---የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ልጠይቅና ፡---መልሱን ፡ ነገ ፡ አባቴ ፡ ሞገሴ ፡ መጥተው ፡ ልንገራቸው ። "

"መልካም ! እንግዲህ ፡ መጠዋ ፡ ጠጥተው ፡ ይሂዱ ! የድካምዎንም ፡ አሁን ፡ እሰጥዎታለሁ ! "አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ ገንዘብም ፡ መጠጥም ፡ ለመስጠት ፡ መነኩሴውን ፡ ይዘው ፡ ወደልፍኝ ፡ ለመሄድ ፡ ሲነሱ ፡--- "መጠጡ ፡ ነው ፡ እንጂ --- ገንዘቡ ፡ ለኔ ፡ አይደለም ፡ አሁን ፡ ወስጂ ---ለተቸገሩ ፡ ድሆች ፡ የምመጸውተው ፡ ነው ፡ የምመጸውተውም ፡ ስለራሴ ፡---- አይደለም ፡ ስለመጸወቱኝ ፡ ሰዎች ---ነው ! "አሉ ፡ አባ ፡ ተክሌ ።

" ነው ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ ነው ! እስዎማ ፡ ምን ፡ ሀጢአት ፡ ኖሮብዎ ፡ ይመጸውታሉ ! ስለኛ ፡ ስለሁላችን ፡ ነው ! "

በበነጋው ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ መጥተው ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ ፊታውራሪ ፡ የጠየቁትን ፡ ለመፈጸም ፡ የተፈቀደላቸው ፡ መሆኑን ፡ አስታወቁ ።

የሰብለን ፡ መፈታት ፡ እስከ ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ በዛብህም ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። ከታሰረች ፡ ጀምሮ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንኩዋን ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ ሄዶ ፡ የሳቸውንም ፡ ያክስቱንም ፡ አይን ፡ ማየት ፡ በሩቅ ፡ ሆኖ ፡ ሲያስባቸውም ፡ ሆዱ ፡ መታወክና ፡ ምራቁ ፡ ባፉ ፡ ውስጥ ፡ መምረር ፡ ይጀምራል ። በዛብህ ፡ መችም ፡ እዩፈራ ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ተሸሽጎ ፡ ነው ፡ የሚውል ። ነፋስ ፡ ለመቀበል ፡ ውጭውን ፡ የሚያየው ፡ ማታ ፡ ጨለማ ፡ ለብሶ ፡ ነበር ።

ሰብለ ፡ በተፈታች ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ማታውን ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ከቤት ፡ ወጥቶ ፡ አጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ሲዘዋወር ፡ ቆይቶ ፡ ሲሰለቸው ፡ እቤቱ ፡ ጥግ ፡ በተጋደመው ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ሄዶ ፡ ተቀመጠና ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ይጠብቅ ፡ ጀመር ፡፡

“ ምን ፡ አግኝቶዋቸው ፡ ይሆን ፡ እስካሁን ፡ የቆዩ ? ይህን ፡ ያክል ፡ አምሽተው ፡ አያውቁም ! ” አለ ፡ ብቻውን ፡ እግንዱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡፡

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በጊዜ ፡ ነፋስ ፡ ተቀብዬ ፡ ልምጣ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ አልተመለሰም ፡ እውነትም ፡ በዛብህ ፡ እዚያ ፡ ቤት ፡ ከተቀመጠ ፡ ጀምሮ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ እውጭ ፡ አምሽቶ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ፡፡

ወዲያው ፡ ከጥር ፡ ውጭ ፡ የግር ፡ ዳና ፡ የሰማ ፡ መሰለውና ፡ ለማረጋገጥ ፡ አንድ ፡ ጆሮውን ፡ ዳናውን ፡ ወደሰማበት ፡ ደቅና ፡ ቆይቶ ፡ በሁዋላ ፡ ወዳጥሩ ፡ በር ፡ ቢመለከት ፡ ሰው ፡ ሲገባ ፡ አየ ፡፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ነው ፡፡

“ ማነህ ፡ አንተ ? ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እጥግ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ የተቀመጠውን ፡ ሰው ፡ በሩቁ ፡ ሲያይ ፡፡

“ እኔ ፡ በዛብህ ፡ ነኝ ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ! ምነው ፡ በጤናዎ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ያመሹ ? ”

“ የምስራች ! ”

“ ተፈታች ? ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ከተቀመጠበት ፡ እንደ ፡ ኩዋስ ፡ ነጥሮ ፡ ተነስቶ ፡፡ ጩኸቱ ፡ በሩቅ ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ ይቀሰቅስ ፡ ነበር ፡፡

“ ቀስ ፡ ቀስ ፡ ቀስ ፡ በል ! ና ፡ እቤት ፡ እንግባ ! ” አለና ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሲገባ ፡ በዛብህ ፡ እዬሮጠ ፡ ገብቶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የቀኝ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የግራ ፡ ጉልበቱን ፡ እዬመላለሰ ፡ ይስም ፡ ጀመር ፡፡

ከዚያ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ታግሎ ፡ ቀና ፡ ሲያደርገው ፡ የደስታው ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ጸደቀች ፡ ነፍስ ፡ የሚያደርገውንም ፡ የሚለውንም ፡ አሳጥቶት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንባው ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጩ ፡ እዬወረደ ፡ “ ተመስገን ፡ ተመስገን ፡

ተመስገን ---- ሲል ፡ ሁኔታውን ፡ ሁሉ ፡ ተመልክቶ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ ልቅሶ ፡ መጣበትና ፡ አንገት ፡ ላንገት ፡ ተያይዘው ፡ እዬሳቁ ፡ ብዙ ፡ እንባ ፡ አፈሰሱ ።

" ለመሆኑ ፡ ማን ፡ ነገረዎ ? " አለ ፡ በዛብህ ፡ በውነቱ ፡ ትንሽ ፡ ጸጥ ፡ ካለ ፡ በሁዋላ ።

" ወዳፋፍ ፡ ሄጄ ፡ ነፋስ ፡ ተቀብዬ ፡ ስመለስ ፡ ሀብትሽን ፡ ውሀ ፡ ልትቀዳ ፡ ስትሄድ ፡ አግኝቻት ፡ ነገረችኝና ፡ ሄጄ ፡ አዬ ሁዋት ። "

" ሰብለን ፡ ራስዎ ፡ ሄደው ፡ አዩዋት ? "

"አዎን ፡ አዬሁዋት ፡"

" እንዴት ፡ ናት ? ከሳታለች ? ትናገራለች ? ትስቃለች ? "

"ከስታለች ፡ ገርጥታለች ፤ ምንዋም ፡ ምንዋ ፡ ሰብለን ፡ አይመስል ! " አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ባዘን ፡ ድምጽ ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ፡ አድርጎ ። በዛብህም ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ።

" ለመሆኑስ ፡ እንዴት ---- ፈቱዋት ? እስማት ፡ አብነት ፡ ይሉት ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ? አለ ፡ በዛብህ ፡ ሁለ ቱም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ።

" ተፈታ ! " አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ በዛብህ ፡ ቀና ፡ አለና ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

" እንዴት ? ምኑ ? "

"አንተ ፡ ያደረግህባት ፡ አስማት ! "

በዛብህ ፡ ከድንጋጤም ፡ ከመገረምም ፡ ብዛት ፡ የሚና ገረው ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

" አስማቱም ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ ያልተለመደና ፡ የጎጃም ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ አዋቂ ፡ ሁሉ ፡ ሊፈታው ፡ የማይችል ፡ ነበረ ፡ አሉ ! " አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አሁንም ፡ ያሽሙር ፡ ፍር ጥምታ ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

"እንግዲያ ፡ ማን ፡ ፈታው?"

"ካባይ ፡ ማዶ ፡ ከጉድፉ ፡ የመጡ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት፡ የሚባሉ ፡ ስልብ!"

"በዚህ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ እንዴት - - - አድርገው ፡ ከጉድሩ ፡ ማስመጣት ፡ ቻሉ ?"

"እዚህ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ ግሁስ ፡ ነኝ ፡ እያሉ ፡ ሰውን ፡ ሲዘርፉ ፡ ቆይተዋል ፡ እንጂ!"

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ! እኒህ - - - ዘግተው ፡ ይኖራሉ ፡ የሚባሉት?"

" አ --- ዎ! ዘግተው ፡ ይኖራሉ ፡ የሚባሉት!"

"እሳቸው ፡ ናቸው ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ ያልተሰመደ ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ የማይፈታ ፡ አስማት --------- የሚሉት ? "

"እሳቸው ፡ ናቸው!" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ! እፊቱ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ በነበረው ፡ አሽሙር ፡ ፈንታ ፡ ቁጣ ፡ ተተክቶ ፡ አይኑ፡ በቅጥበት፡ ቀልቶ ፡፡

"እየውልህ! ቤተ ፡ እግዚአብሄራችን ፡ እንደነዚህ ፡ ላሉት ፡ ሽፍቶች ፡ እንደነዚህ ፡ ላሉት ፡ ዘራፊዎች ፡ ዋሻ ፡ ሆነች! እየውልህ! ከካህናቶቻችን ፡ ከሀዋርያቶቻችን ፡ የሚበዙት ፡ ካለቆች ፡ ጀምሮ ፡ በመነኮሳቱ ፡ አልፎ ፡ እስከ ፡ ተራ ፡ ደብተሮች ፡ እስከ ፡ ዲያቆናቱ ፡ ድረስ ፡ አንዱ ፡ አስማት ፡ አድራጊ ፡ አንዱ ፡ አስማት፡ ፈቺ ፡ ሌላው ፡ ጋኔን ፡ ስቦ ፡ አምጪ ፡ ሌላው ፡ አስወጪ ፡ አንዱ ፡ መቅሰፍት ፡ አምጪ ፡ ሌላው ፡ ምህረት ፡ አሰጪ ፡ ነን ፡ እያሉ ፡ ውሸታቸውን ፡ በዱጥምጥማቸው ፡ በዱቆባቸው ፡ በዱደበሎዋ ቸው ፡ ሸሽገው ፡ ሲመሩት ፡ ሲያስተምሩት ፡ በተሰጣቸው ፡ መንጋ ፡ የሚጫወቱ ፡ ናቸው! ታዲያ ፡ ከነዚህ ፡ ጋር ፡ ማህበር ተኛ ፡ ሆኖ ፡ ባንድ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሄርን ፡ መጥራት ፡ በተቀ ደሰ ፡ ስሙ ፡ ማፌዝ ፡ አይደለም ? እየውልህ! ይሀ ፡ ነው ፡ ከምወ ዳት ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሄር ፡ ያራቀኝ! ሰው ፡ የሚሰው ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እውነቱ ፡ ይሀ ፡ ነው ፡፡ አሁን ፡ አንተ ፡ በራስህ ፡ ባይ ደርስ ፡ ኖሮ ፡ እኒህ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ያደርጋሉ ፡ ብዬ ፡ ብነግርህ ፡ አታምንም ፡ ነበር ፡፡ ታምን ፡ ኖሮዋል?"

"በጭራሽ ፡ አላምንም ፡ ነበር ፡"

"እየውልህ ፡ ብዙዎቹ ፡ እንዲህ ፡ ናቸው ፡፡"

"ታዲያክ ፡ እንደሰዎ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በካህናቱ ፡ ክፉ ፡ ስራ ፡ ተቀይሞ ፡ ከመሸሽ ፡ እመሀከላቸው ፡ ሆነው ፡ ለነሱም ፡ ለሚያታ

ልሉት ፡ ህዝብም ፡ ቢሰብኩ ፡ በጠቅላላው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ መልካም ፡ ነበር!”

“ያልጀመርሁት ፡ መሰለህ? ለምናገረው ፡ ሰው ፡ ዋጋ ፡ እን ዳይሰጠው ፡ እብድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እስወሩብኝ ፤ እብዱ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሚባለውን ፡ ስም ፡ ያስጠኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።”

በዛብህ ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ፡ አደረገና ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆይቶ ፡ “እንኩዋን ፡ ተፈታች ፡ እንጂ ፡ ግዴለም!” አለ ።

በበነጋው ፡ ጥዋት ፡ ቡና ፡ ተጠጥቶ ፡ እንቆጳም ፡ ሌሎችም ፡ ሁሉ ፡ ወደዬስራቸው ፡ ከተሰማሩ ፡ በሁዋላ ፡

“ምን ፡ አሰብህ ? በዛብህ ?” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

“እንዴት? ስለምኑ?”

“እንግዲህ ፡ ሰብለ ፡ ተፈታች ፤ ስለራስህ ፡ ምን ፡ ለማድረግ፡ ታስባለህ ፡ ማለቴ ፡ ነው!”

“ማሰብማ ፡ ሌሊቱን ፡ እንቅልፍ ፡ እጥቼ ፡ ሳስብ ፡ ነው ፡ ያደርሁ ፤ ብቻ ፡ የምጨብጠውን ፡ ነገር ፡ አጥቼ ፡ ተቸገርሁ ፡ እንጂ!”

“የሚሻል ፡ የመሰለኝን ፡ እኔ ፡ ልንገርህ?”

“ምን ፡ ይሻለኛል? እስቲ ፡ ይንገሩኝ!”

“አዲስ ፡ አበባ ፡ ሂድ! ወደዚያ ፡ መሄድህ ፡ ነው ፡ የሚ ሻለው ።”

“እንዴት?” አለ ፡ በዛብህ ፡ ደንግጦ ።

“እስከ ፡ መቼ ፡ እዚህ ፡ ተሸሽገህ ፡ መቀመጥ ፡ትችላለህ? ለመቀመጥ ፡ ብትችልስ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ?”

“እሱስ ፡ እውነት ፡ ነው !” አለ ፡ በዛብህ ፤ አንገቱን ፡ ደፍቶ፡ ሲያስብ ፡ ቆይቶ ። “ብቻ ፡ አዲስ ፡ አበባስ ፡ ሂጄ ፡ ምን ፡ አደርጋ ለሁ? ይህን ፡ አደርጋለሁ ፡ የምለውን ፡ ነገርኮ ፡ አጣሁ!”

“አዲስ ፡ አበባ ፡ ሂድ ፡ ያልሁበትን ፡ ምክናያት ፡ ልንገርህ? አንደኛ ፡ በጎጃም ፡ መሬት ፡ መኖርህ ፡ ከታወቀ ፡ ፊታውራሪ ፡ መከታተላቸው ፡ ስለማይቀር ፡ አንተም ፡ ሰብለም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በስጋት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የምትኖሩ ። ሁለተኛ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄደህ ፡ ስራ ፡ የያዝህ ፡ እንደሆነ ፡ አሳብህ ፡ በስራህም ፤ በሌላ ውም ----መሀከል ፡ ይከፋፈልና ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ እዚህ ፡ የደ

ረሰውን - - - - - ሁሉ ፡ መርሳት ፡ ትችል ፡ ይሆናል ። እንዲያ ውም ፡ ግልጥ ፡ አድርጌ ፡ ልንገርህ ፡ ቶሎ ፡ ስራ ፡ ይዘህ ፡ ልብህ፡ የሚደነግጥላት ፡ ልጅ ፡ ብታገኝ ፡ ቶሎ ፡ እንድታገባ ፡ ነው ፡ የም መክርህ !”

እሱን ፡ አንኩዋ ፡ ይተውት ! ሰብለ ፡ ከቀረች ፡ እመነኩሳ ለሁ ፡ እንጂ ፡ ምሽት ፡ አላገባም !”

“ተሳስተሀል ! እግዚአብሄር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሴት ፡ የፈ ጠረ ፡ ሰብለን ፡ ብቻ ፡ ነው ?”

“ሴትማ ፡ ሞልቶዋል ! ከሰብለ ፡ ጋር ፡ ባልገናኘና ፡ እስ ዋን ፡ ባላውቅ ፡ ኖሮ ፡ እንድዋን ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ አግብቼ ፡ ለመ ኖር ፡ ምኞቴ ፡ ነበር ። አገሬንም ፡ የለቀቅሁ ፡ በቀደም ፡ እንዳሚወ ትሁዎ ፡ ምሽት ፡ አግብቼ ፡ ቤት ፡ ሰርቼ ፡ ለመኖር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሄር ፡ ሲፈጥረኝ ፡ ለዚህ ፡ አልመደበኝም ፡ መሰለኝ፡ ከስዋ ፡ ጋር ፡ አገናኘኝ ። ከንግዲህ ፡ ወዲያስ ፡ አላገባም ። ሌላ ፡ ምሽት ፡ ከማግባቱ ፡ ላጭር ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እስዋ ፡ የሰጠችኝን፡ ደስታ ፡ እያሰብሁ ፡ መቀመጡ ፡ ይሻለኛል !” አለ ፡ በዛብህ ፡ እን ባው ፡ ባይኑ ፡ ሞልቶ ።

“ይገርማል ! ለካ ፡ ከቶም ፡ ሆነ ፡ በጎ ፡ የሚሰሩ ፡ ሰዎች ፡ መሳ ሪያዎች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ሰራተኛው ፡ እግዚአብሄር ፡ ስለሆነ ፡ እነሱን ፡ መጥላቱና ፡ ማማት ፡ ወይም ፡ መውደዱና ፡ ማመስገኑ ፡ ከንቱ ፡ ነው ! እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ባይኖሩ ፡ ያ ፡ ክፉ ፡ የተሰራበት፡ ወይም ፡ በጎ ፡ የተሰራለት ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ክፉውን ፡ ወይም ፡ በጎ ውን ፡ በሌላ ፡ አማካይነት ፡ አያጣውም ፡ ማለት ፡ ነው !” አለ ፡ በዛብህ ፡ ቀጠለና ።

“ እንዴት ?”

“ በቀደም ፡ እንደነገርሁዎ ፡ እናቴ ፡ ምሽት ፡ ሳላገባ ፡ በድ ንግልና ፡ ታቦት ፡ እንዳገለግል ፡ በስእለት ፡ ስለሰጠችኝ ፡ በስዋ ፡ አገሩ ፡ ከታሰርሁበት ፡ አምልጬ ፡ ምሽት ፡ አግብቼ ፡ ለመኖር፡ ነበር አገሬን ፡ የለቀቅሁ ። ይዩት ፡ አሁን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ወደ ዚያው ፡ ጥንት ፡ ወደተመደበልኝ ፡ ህይወቴ ፡ መመለሴ ፡ ነው !”

“ እስቲ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ ፡ በዛብህ !”

"መችም ፡ ዲማ ፡ ከመጣህ ፡ ጀምሮ ፡ ሰብለን ፡ ታውቃታለህ ! መቼ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ከተፈጠረው ፡ ሴት ፡ ሁሉ ፡ የተለየች ፡ ሆና ፡ ትታይህ ፡ የጀመረች ?"

"መጀመሪያ ፡ ሳያትም ፡ ልቤ ፡ ደንገጥ ፡ ብሎዋል ፤ ብቻ ፡ እሱ ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ ሴት ፡ ሲታይ ፡ የሚያስደነግጠውን ፡ ያክል ነው ። እንጃ --- እንዲያውም ፡ ትንሽ ፡ እፈራት ፡ ነበር ፡ መሰለኝ። የቀረው ፡ አሁን ፡ በቅርቡ --ነው ።"

"እየውልህ!ብዙ፡ጊዜ፡መተዋወቃችሁ፡የብዙ፡ጊዜ፡ጉዋደኝነታችሁ ፡ ጭዋታችሁ ፡ መላፋታችሁ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ መጨረሻ ፡ አደረሳችሁበት ፡ ላይ ፡ አደረሳችሁ ! ከዚያ ፡ በጣም ፡ ተዋደዳችሁ ! ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ እንደሰዋ ፡ በቅርብ ፡ ካወቅሀቸው ፡ ከብዙዎቹ ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡ የምትወዳት ፡ የምታጣ ፡ ይመስልሃል ?"

"የሰም ፡ አላገኝም ፤ አለቃ ! ሰብለ ፡ ልዩ ፡ ናት ። ከሌሎች ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ ናት ! ምሽትም ፡ ባላገባ ፡ ብዙ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ አውቃለሁ ። ታዲያ ፡ የማውቃቸው ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ ሁሉ ፡ የሚዋደዱትም ፡ ባሳብ ፡ ባለመስማማት ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ጭቅጭቅ፡ አያጣቸውም ። ይገርምዎታል ፡ ሰብለና ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነፍስ፡ እንደ ፡ ተጋራን ፡ ሁሉ ፡ እሰዋ ፡ ያሰበችውን ፡ እኔ ፡ ስናገር ፡ እኔ ፡ ያሰብሁትን ፡ እሰዋ ፡ ስትናገር ፡ እንገኝና ፡ ተያይዘን ፡ መሳሳቅ ፡ ብቻ ፡ መደሰት ፡ ብቻ ፡ ነው ! ምነው ፡ አብረን --- እንዲህ ፡ ስንሆን ፡ ቢያዩን ፡ ኖሮ ! አለና ፡ በዛብህ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ደስታ ፡ መቅረቱ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ እንባው ፡ ይወርድ ፡ ጀመር ።

"ግሩም ፡ ነው ! አንተም ፡ እንደ ፡ ፈታውራሪ ፡ ያለ ፡ አባት ፡ ቢኖርህ ፡ ሰብለ ፡ አስማት ፡ አድርጋበታለች ፡ ትባል ፡ ነበር ።"

" ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይንዋን ፡ የማይበት ፡ ዘዴ ፡ የሚገኝ ፡ ይመስልዎታል !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ዝም ፡ ብሰው ፡ ቆይተው ።

" አልነገርሁህም ፡ መሰለኝ ፤ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖትኮ ፡ ጠባቂ ፡ ጭምር ፡ እንዲሆኑ ፡ ተቀጥረዋል !"

" እምሳ ፡ ብር ፡ አሉኝ ፤ እሱን ፡ ብሰጣቸውና ፡ አንድ ፡ ማታ

እስገብተውኝ ፡ አይቻት ፡ ብሄድ --- እሺ ፡ የሚሉ ፡ አይመስሉ ምትም ፤

" እንደሳቸው ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሴት ፡ ስመጠበቅ ፡ የሚመረጡ ፡ በጥብቅነታቸው ፡ የታወቁ ፡ በመሆናቸው ፡ መሆኑን ፡ አታውቅም ?"

" ጥብቆችና ፡ ታማኞች ፡ ናቸው ፡ ሲባሉስ ፡ እሰማለሁ ፤ ብቻ ፡ ተሰናብቼ ፡ ስመሄድ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ልስጥ ፡ ስል ፡ ገንዘቡ ፡ ያጉዋጉዋቸው ፡ ይሆናል ፤ ወዲያውም ፡ እምነት ፡ አጎደሉ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ አይኖርም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ !"

. "·እምነት ፡ እንኩዋ ፡ አይደለም ፤ ቅናት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ ቢወዱ ፡ ቅናታቸው ፡ ከገንዘብ ፡ ፍቅራቸው ፡ ይበልጣል ። ዝም ፡ ብለህ ፡ ሂድ ፡ እንዳያስይዙህ ። ሁላችንም ፡ ደህና ፡ ከሆን ፤ የተመቸ ፡ አጋጣሚ ፡ ካገኘሁ ፤ ከቻልሁ --- ሰብለን ፡ ስርቄ ፡ አንተ ፡ ባለህበት ፡ ስማድረስ ፡ መሞከሬ ፡ አይቀርም ፤ ብቻ፡ እግዚአብሄር ፡ ይርዳ ። እዚያ ፡ እንደ ፡ ደረስህ ፡ ቶሎ ፡ ስራ ፡ ያዝና፡ የተቀመጥህበትን ፡ ቦታ ፡ አስታውቀኝ ።"

በሻብህ ፡ እንባው ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጩ ፡ እዬወረደ ፡ ተንስቶ ፡ የጉዱ ፡ ካሳን ፡ ጉልበት ፡ ሳመ ።

"ግዴለህም ፡ አፈር ፡ ካልተጫነኝ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሰብለን ፡ በጅህ ፡ አገባታለሁ ! ብቻ ፡ ቶሎ ፡ ሂድና ፡ ስራ ፡ ያዝ ፡ ትንሽም ፡ ቢሆን ፡ ስራ ፡ ያዝ !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

# ምእራፍ ፡ ፸፱

## አዲስ ፡ አበባ ፡

በዛብህ ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከግራ ፡ ጌታ ፡ ቀለመወርቅና ፡ ከእዝራ ፡ ጋር ፡ ከዲማ ፡ በጨለማ ፡ ወጥቶ ፡ ድምጽ ፡ የሰማ ፡ በመሰለው ፡ ቁጥር ፡ እሳቡ ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ እዩ-ተገተተ ፡ ተራሮች ፡ እስኪጋርዱት ፡ ድረስ ፡ በዩደቂቃው ፡ ዲማን ፡ እዩዞረ ፡ እያዩ ፡ አባይ ፡ ደረሰ ። ከዚያ ፡ ከወዳጆቹ ፡ በንባ ፡ ተሰነባብቶ ፡ ከሞጣ ፡ ነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ ተጨምሮ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገባ ።

ካባይ ፡ እስከ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ አስር ፡ ቀን ፡ ሲጉዋዝ ፡ ስላዲስ ፡ አበባ ፡ የነገሩት ፡ ወሬ ፡ እሰበሱ ፡ የሚማቱና ፡ ማነኛውን ፡ መያዝ ፡ የሚያስቸግር ፡ ስለነበረ ፡ ሰግቶ ፡ ነበር ።

" ስራ ፡ ለሚያውቅ ፡ ሰው ፡ እግር ፡ እስኪላጥ ፡ ቢሄዱ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ የመሰለ ፡ አገር ፡ ይገኛል ፡ ብለህ ፡ እታስብ ! " ይለዋል ፡ አንዱ ።

" አዲስ ፡ አበባ ፡ የሌቦች ፡ አገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰርተው ፡ የሚያድሩ ፡ ሰዎች ፡ አገር ፡ አይደለም ! ያዲስ ፡ አበባ ፡ ሌባ ፡ እንዳገርህ ፡ ሌባ ፡ ጨለማ ፡ ለብሶ ፡ የሚሰርቅ ፡ መሰለህ ? የለም ፡ አይንህ ፡ እያዩ ፡ ብርሀን ፡ ከኪስህ ፡ አውጥቶ ፡ ይወስደዋል ! እንዲያው ፡ እንጃ ፣ ያፍዝ ፡ ያደንግዝ ፡ አለው ፡ መሰለኝ ! " ይለዋል ፡ ሌላው ።

" እ — ! ጽህፈት ፡ የሚያውቅማ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ልፋፈ ፡ ጽድቁንና ፡ ከታቡን ፡ እየጻፈ ፡ ብሩን ፡ በቁና ፡ መስፈር ፡ ነው ! " ይለዋል ፡ አንዱ ።

" ምን ፡ ዛሬማ ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ረከሰ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ! ድሮ ፡ አንድ ፡ ገድል ፡ ወይም ፡ ታምር ፡ ጽፈህ ፡ ላንድ ፡ መኰዋንንት ፡ ብትሰጥ ፡ አንድ ፡ ጠብደል ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ አምሳ ፡ ስድሳ ፡ ብር ፡ ታገኝ ፡ ነበር ፡ ዛሬስ — ካንድ ፡ ሊቅ ፡

አንድ ፡ የኔ ፡ ብጤ ፡ ደንቆሮ ፡ ይሻላል ፡ እንጨቱን ፡ ይሁን ፡ ድንጋዩን ፡ ወይም ፡ ውሀውን ፡ ተሸክሞ ፡ ሆዱን ፡ሞልቶ ፡ ያድራል ! ” ይለዋል ፡ ሌላው ።

“ አዲስ ፡ አበባ ፡ የማውቀው ፡ ሰው ፡ የለኝም ፡ ምን ፡ ባደርግ ፡ የሚሻለኝ ፡ ይመስልዎታል ? እስቲ ፡ ይምከሩኝ ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛውን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሊገቡ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሲቀራቸው ፡ ሱሉልታ ፡ በሰፈሩበት ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጫወቱ ።

“ ገንዘብ ፡ ካለህ ፡ አትቸገርም ፡ ገንዘብም ፡ የምታውቀው ፡ ሰውም ፡ የሌለህ ፡ እንደሆን ፡ ነው ፡ ችግሩ ! እስቲ —— ለማና ቸውም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ጉለሌ ፡ ሰፈርና ፡ አንተም ፡ እኛም ፡ ስራ ፡ እስከታገኝ ፡ የምትቀይበት ፡ ሰው ፡ እንፈልጋለን ። ” አሉ ፡ ነጋድራስ ።

“ ገንዘብስ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ያገጣጠሙኝ ፡ ወዳጆች ፡ አዋጥተው ፡ የሰጡኝ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አለኝ ። ”

“ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ካለህማ ፡ ማለፊያ ፡ ቤት ፡ ተከራ ይተህ ፡ ማለፊያ ፡ ቀላቢ ፡ ቀጥረህ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያቆይሀል ። ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ አገሩን ፡ እስክትለምደው ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ብት ቆይ ፡ ይሻላል ። ገንዘብህም ፡ እንዳይጠፋብህ ፡ መጠንቀቅ ፡ ነው ። ”

በዛብህ ፡ ሰፈሩን ፡ ጉለሌ ፡ ከነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ አድርጎ ፡ ጥዋት ፡ አብሮዋቸው ፡ ይወጣና ፡ አራዳ ፡ ሲደርስ ፡ ተለይቶ ዋቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ የሚሸጥባቸውን ፡ ሱቆች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ትልልቅ ፡ ግቢዎችንና ፡ አደባባዮችን ፡ እዩ ዞረ ፡ ሲያይ ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ ደክሞት ፡ ይመለሳል ። ከገንዘቡ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ አስቀርቶ ፡ የቀረውን ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነ ኛው ፡ እንዲይዙለት ፡ ስለሰጠ ፡ እሰረቃለሁ ፡ ወይም ፡ እቀማ ለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚሰጋበት ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ቢሄዱት ፡ የማያልቅ ፡ ትልቅ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ የህዝቡ ፡ ኑሮ ፡ ልማዱ ፡ እንዲያው ፡ በጠቅላላው ፡ ምኑም ፡ ምኑ ፡ ጎጃሞን ፡ እስኪለቅ ፡ ከሚያውቃቸው ፡ እንደ ፡ ሞጣ ፡ እንደ ፡ ደብረ ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ ዲማ ፡ ካሉት ፡ ከተሞች ፡ በጭ

ራሽ ልዩ ፡ ሆኖ ፡ ስለታዩው ፡ ለጊዜው ፡ ድንግርግር ፡ አለው ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ባንድ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ መነገሩ ፡ አስገረመው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ አማርኛ ፡ ተብሎ ፡ የሚነገረው ፡ ስብሩም ፡ ሆነ ፡ ቃሉ ፡ አማርኛ ፡ አልመሰለው ፡ አለ ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ልማዱን ፡ አለማወቁ ፡ አንድ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ይጥለኝ ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ ይሰጋ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ኩታውን ፡ ተከናንቦ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሊሄድ ፡ ገና ፡ ከሰፈሩ ፡ ሲወጣ ፡ አንድ ፡ መንገደኛ ፡ አገኘና ፡- “ እንዴት ፡ አደሩ ፡ ጌታው ! ” አለ ፡ ከንንቡን ፡ አውርዶ ።

“ እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ አደርክ ? ” አለ ፡ መንገደኛው ፡ ምን ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቆም ፡ አለና ። በዛብህ ፡ ግን ፡ ኩታውን ፡ እንደገና ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ። ሰውዬው ፡ ገርሞት ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ በዛብህን ፡ እስኪርቅ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ጉድ ፡ ሲመለከተው ፡ ቆይቶ ፡ እሱም ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ መንገደኛ ፡ አገኘና ፡ አሁንም ፡ እንደፊተኛው ፡ ከንንቡን ፡ አውርዶ ፡ “ እንዴት ፡ አደሩ ፡ ጌታው ! ” አለ ።

“ እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ ” አለ ፡ መንገደኛው ፡ እሱም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ መንገደኛ ፡ ምን ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቆም ፡ አለና ። በዛብህ ፡ አሁንም ፡ ኩታውን ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ገፋ ፡ አድርጎ ፡ መንገዱን ፡ ሊቀጥል ፡ ሲል ፡-

“ የት ፡ ታውቀኛለህ ? አባክህ ! ” አለው ፡ መንገደኛው ።

“ እረ ፡ አላውቅዎም ፡ ጌታው ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ መፍራት ፡ ብሎ ።

“ ታዲያ ፡ ሳታውቀኝ ፡ ነው --- እንዲሁ ፡ ተነስተህ ፡ እንዴት አደርክ ፡ ያልከኝ ?”

“ እረ ፡ አላውቅዎም ፤ የእግዚአብሄርን ፡ ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ ይገባል ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ።”

“ይህ ፡ አታላይ ፡ መልተኛ ፡ እድፍ ፡ ጨርቅ ፡ ብለብስ ፡ ባላ

ገር ፡ መሰልኩህ ?”

“ ኧረ ፡ እኔ —”

“አትኬድም ፡ አሁን ? አንት ፡ ሽአባ ! እንዳንት ፡ ያለውን ፡ ሌባ ፡ የማላእ ፡ መሰለህ ? አሁን ፡ ዘበኛ ፡ ጠርቼ ፡ አስኧፈድድህ ፡ ነበር !”

በዛብህ ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ ሰውዬው ፡ የተናገረውን ፡ ቃል በሙሉ ፡ አጣርቶ ፡ ለማወቅ ፡ ባይችል ፡ በጠቅላላው ፡ አሳቡ ፡ ስለ ገባው ፡ ደንግጦ ፡ መንገደኛው ፡ የተቆጣበትን ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ ባለማወቁ ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፡ እዚያ ፡ ቆሞ ፡ ሲሳደብ ፡ ትቶት ፡ ሸሸ። ከዚያ ፡ የከተማው ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ እዚያ ፡ የገጠመውን ፡ ችግር፡ ይዞ ፡ የሚቆዬው ፡ ስለመሰለው ፡ በመንገድ ፡ የሚያገኘው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘበኛ ፡ ጠርቶ ፡ የሚያሳስረው ፡ ስለመሰለው ፡ ወደ ፡ ከተማ፡ መሄዱን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ተመለሰና ፡ ተሸሽጎ ፡ ድምጽ ፡ በሰማ ፡ ቁጥር ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ዘበኛ ፡ መጣብኝ ፡ እያለ ፡ ሲሸበር ፡ ዋለ ። ማታ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛውና ፡ ጉዋደኞቻቸው ፡ ከገበያ ፡ ሲመለሱ ፡ የደረሰበትን ፡ ሲነግራቸው ፡ ጊዜ ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ።

“ አየህ ? እዚህ ፡ አገር ፡ እንዳገራችን ፡ በመንገድ ፡ ለምታገኘው ፡ የማታውቀው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ የለብህም !” አሉ ፡ ነጋድራስ ።

“ እንዴት ? እንዲያው ፡ እንዲሁ ፡ እንደተቀያዬሙ ፡ ሁሉ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መተላለፍ ፡ ነው ? ”

“ ልማድ ፡ ሆኖ ፡ ሰው ፡ ለማያውቀው ፡ ሰው ፡ ሰላምታ ፡ አይሰጥም ። መንገድ ፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ ሲጠፋህ ፡ ብቻ ፡ የማታውቀው ፡ ሰው ፡ ቢሆንም ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥተህ ፡ የጠፋህን ፡ ብትጠይቅ ፡ ግዴለም ። ያለዚያ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማለፍ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ጠንካራ ፡ ጸሀይ ፡ ወይም ፡ ዝናብ ፡ ካልሆነ ፡ ተከናንቦ ፡ መሄድ ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ልማድ ፡ አይደለም ። ያላንድ ፡ ምክንያት ፡ ተከናንበው ፡ የሚሄዱ ፡ ሰዎች ፡ ፊታቸው ፡ እንዲታይ ፡ የማይፈልጉ ፡ ሌቦች ፡ ወይም ፡ ቀማኞች ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ በደህና ፡ ጊዜ፡ ተከናንበህ ፡ ሄደህ ፡ ለማታውቀው ፡ ሰው ፡ ሰላምታ ፡ ስትሰጥ ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ አታላይ ፡ ትመስለዋለህ ። ለዚህ ፡ ነው ፡ ሰውዬው ፡

የተቆጣ ።”

“ግሩም ፡ ነው ! እንግዲህ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ቀዋንቋዋና ፡ ልማድ ፡ እስኪጠና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መፍጀቱ ፡ ስለማይቀር ፡ ስራ ፡ ፈልጌ ፡ ባገኝም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ነው ፡ ማለት፡ ነው !” አለ ፡ ዘዛ ብዙ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ቋዋንቋዋና ፡ ልማድ ፡ አለማወቁ ፡ ቶሎ ፡ ስራ ፡ ፈልጎ ፡ ለማግኘት ፡ መሰናክል ፡ ስለመሰለው ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ተስፋ ፡ እንዲሰጠው ፡ ስብለን ፡ ያመጣለት ፡ እንደዞን ፡ እቶርቶ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ የሚወድቅ ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ ገዝም ፡ ብሎ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ሲያስብ ፡ ቆዩና ፡

“ የለም ፡ አይዞህ ፡ ሁሉንም ፡ አሁን ፡ ትለምደዋለህ ። ቋዋ ንቋዋው ፡ መቸም ፡ ያው ፡ የምታውቀው ፡ አማርኛ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ ‘ቀን’ ፡ በ‘እ’ ፡ ‘ከ’ን በ‘ኸ’ ፡ እዩለወጡ ፡ ስለሚናገሩና ፡ ጆሮህ፡ ስላለመደው ፡ ለጊዜው ፡ ልዩ ፡ ቋዋንቋዋ ፡ ይመስላል ። ” አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ ፍርጥም ፡ ብለው ።

‘እሺ ፡ ቋዋንቋዋውስ ፡ ይሁን ፡ ልማዱ ፡ እስኪታወቅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይፈጅም ? ለምሳሌ ፡ የግዜርን ፡ ሰላምታ ፡ መስ ጠት ፡ ነውር ፡ ሆኖ ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ አታላይ ፡ የሚያስመስልና ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ የሚያጣላ ፡ ከሆነ ፡ ነውር ፡ ያልሆነው ፡ ምንድር ፡ ነው ? እንዴትስ ፡ አድርጎ ፡ ቀርቦ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ለመተዋወቅና ስራ ፡ ተጠያይቆ ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ?”

“ አይዞህ ፡ አትፍራ ፡ ልማዱም ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ካገራችን ፡ የተለዩ ፡ አይደለም ፡ ትንሽ ፡ ብቻ ፡ ንቃ ፡ ማለት ፡ ነው፡ የሚያስፈልግ ። ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ ለምን ፡ አታላይ ፡ አስመሰሉ፡ አሳዩ ፡ ለምትለው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከያገሩ ፡ ብዙ ፡ አታላዮች ፡ የሚሰበሰቡበት ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ አንዳንዶቹ ፡ አታላዮችም ፡ ካን ተና ፡ ከኔ ፡ አገር ፡ የሚመጡ ፡ ናቸው ። ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያሉት፡ ሰዎች ፡ እንግዳ ፡ ወይም ፡ የሚታለል ፡ ሰው ፡ ያዩ ፡ ሲመስላቸው ፡ መጀመሪያ ፡ ሰላምታ ፡ በመስጠት ፡ ቀጥሎም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የማ ታለያ ፡ መንገድ ፡ ደጎችና ፡ ረዳቶች ፡ በመምሰል ፡ ቀርበው ፡ የስ ርቆት ፡ የቅምያና ፡ ሌላም ፡ የወንጀል ፡ ስራቸውን ፡ የሚፈጽሙ ፡ መሆናቸው ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የታወቀ ፡ ሆኖዋል ። ስለ ዚህ ፡ ለማታውቀው ፡ ሰው ፡ ተከናንበህ ፡ ሄደህ ፡ ሰላምታ ፡ ስት

ሰጥ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ተጠራጥሮ ፡ ቢቆጣ ፡ አይግረምህ ። ይልቅ ፡ ቅድም እንዳልኩህ ፡ አለመፍራት ፡ ነው ። ስትሰጋና ፡ የንግድነት ፡ መልክ ፡ ስታሳይ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ አይን ፡ ይከታተልሃና ፡ አንተም ፡ በበኩልህ ፡ ያን ፡ ስታይ ፡ ነውር ፡ የሰራህ ፡ መስለህ ፡ ፍራት ፡ አይለይህም ፡ ስትባንን ፡ ትኖራለህ ።”

ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ ከተገናኙ ፡ ጀምረው ፡ ትህትናውንና ፡ በጣም ፡ የታረመ ፡ አመል ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ በማየታቸው ፡ ይወዱት ፡ ስለነበረ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ኑሮ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ሊፈራው ፡ እንደማይገባና ፡ በራሱ ፡ እምነት ፡ እንዲኖረው ፡ በየጊዜው ፡ እየመከሩ ፡ ያደፋፍሩት ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከሚኖሩ ፡ አንዳንድ ፡ የሚያውቋቸው ፡ ደህና ፡ ሰዎች ፡ አስተዋወቁት ። ብቻ ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ በዛብህ ፡ ከመንጋው ፡ ለይተው ፡ ከንግዳ ፡ መንጋ ፡ እንደ ፡ ጨመርዋት ፡ ላም ፡ መቡዋ ዘዙና ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ ብቸኝነት ፡ የሚሰማው ፡ መሆኑ ፡ አልቀረም ። አዲስ ፡ አበባ ፡ ተቀምጦ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚታየው ፡ የሰብስ ፡ መልክ ፡ የሚሰማው ፡ የሰብስ ፡ ድምጽ ፡ የሚታሰበው ፡ ሰብስን ፡ አስከብሎሉ ፡ ለማሟሟት ፡ ያቀያው ፡ እቅዱና ፡ በመጨረሻ ፡ በስዋ ፡ ፈንታ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሰጠውን ፡ በጥርጣሬ ፡ የተከበበ ፡ ተስፋ ፡ ይዞ ፡ መምጣቱ ፡ ነበር ። “ሁላችንም ፡ ደህና ፡ ከሆን ፡ የተመቸ ፡ አጋጣሚ ፡ ከተገኘ ፡ ከቻልሁ ---- ስብለን ፡ ሰርቄ ፡ በጅህ ፡ ሳላገባት ፡ አልቀርም ፡” ብሎ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሲሰናበተው ፡ የተናገረው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ መሀከል ፡ እንኳ ፡ በተቀመጠበት ፡ በጆሮው ፡ ውስጥ ፡ ጎልቶ ፡ ይሰሙበትና ፡ ድንገት ፡ እቱዋርጦ ፡“እግዚአብሔር ፡ ደህና ፡ ያድርግዎ ፡ የተመቸ ፡ አጋጣሚ ፡ ያምጣልዎ ፡ ያስችልዎ፡” ሲል ፡ አብረውት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ይደነግጣሉ ፡ ወይም ፡ ሳይተኛ ፡ ይቃዣል ፡ ብለው ፡ ይስቁበታል ።

“በዛብህ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ቁምንቁምና ፡ ለማድምበተር ፡ ልብህ ፡ የሚያሰቀልልበት ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ይሰማኛል ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ምንድነው ፡ ብለህ ፡ ብትጠይቀኝ ፡ ልነግርህ ፡ አልችልም ። ብቻ ፡ ይህ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በንቅልፉ ፡ ተነስቶ ፡ እንደ

ማሄድ ፡ ሰው ፡ ፍዝዝ ፡ የሚያደርግህ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም፡ባፍላ ፡ ጭዋታ ፡ መሀከል ፡ የሚያቃኝህ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ልማድ ፡ አለማወቅ ፡ ነው ፡ ብትለኝ ፡ የማልቀበለው ፡ ነገር ፡ ነው !" አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ሲጫወቱ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ያልጠየቁትን ፡ ተናግሮ ፡ ወዲያው ፡ ሲደነግጥ ፡ አይተው ።

"ሌላ ፡ ምን ፡ ልቤ ፡ የሚያሰቀልልበት ፡ ነገር ፡ ይኖር፡መሰለዎ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ ብሎ ።

"ስሙን ፡ ጠርቼ ፡ ይሀ ፡ ነው ፡ ልልህ ፡ አልችልም፡እንጂ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከመድረሳችንም ፡ በፊት ፡ ገና ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ተገናኝተህ ፡ አባይን ፡ ስትሻገር ፡ ጀምሮ ፡ የወለደችውን ፡ ሞጭቀው፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ እንዳስቀሩባት ፡ እራስ ፡ ላም ፡ ልብህ ፡ ወደ፡ሁዋላ፡ ሲጎተትና ፡ ሲያስቀልል ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ ተመልክቻለሁ ።"

"ነገሬ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በመውጣቴ፡ ምናልባት፡በሌሎች ፡ ላይ ፡ የማይታይ ፡ ቅሬታ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ አይተው፡ይሆናል።"

"ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከጎጃም ፡ ወጥቶ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ሲመጣ ፡ ያዩሁት ፡ ሰው ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ ይመስልሀል ?"

"እገሩን ፡ ለሁል ፡ ጊዜ ፡ ለቆ ፡ የሚሰደድ ፡ ማለቴ ፡ ነውኮ ፡ ደርሶ ፡ ተመላሽ ፡ አይደለም!"

"ቢሆንም ።"

"እንግዴህ ፡ እንደዬስሜቱ ፡ ቢሆን ፡ ነው ።"

"እይ ፡ በዛብህ! እኔኮ ፡ ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ ነኝ! ጥሩ ፡ ነጋዴና ፡ ጥሩ ፡ ጠንቁዋይ ፡ ግምት ፡ አዋቂዎች ፡ መሆናቸውን ፡ አታውቅም?"

"እንዴት?"

"እዩህ? እገሌ ፡ ጥሩ ፡ ጠንቁዋይ ፡ ነው ፡ እዬተባለ ፡ የሚደነቀው ፡ ጠንቁዋይ ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ከዛርና ፡ ከጋኔን ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ ሰው ፡ የማያውቀውን ፡ ከነሱ ፡ እያገኘ ፡ አለመሆኑን ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ምናልባት ፡ አንተ ፡ ደብተራው ፡ ታውቅ ፡ ይሆናል፡ ካብዛኛው ፡ ሰው ፡ የተሻለ ፡ የግምት ፡ ስጦታ ፡ ስላለው ፡ ገምቶ ፡ ከሚናገረው ፡ የሚበዛው ፡ ስለሚያዝለት ፡ ነው ። ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ የሚባለውም ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ የሚወደደውን ፡

ገምቶ ፡ ዛሬ ፡ የሚገዛ ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ የሚረክሰ ውን ፡ ገምቶ ፡ ዛሬ ፡ የሚሸጥ ፡ ነው ። ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ግምት ፡ የገብያውም ፡ የሰውም ፡ ሁኔታ ፡ ተጠንቶ ፡ የሚደረስ በት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲሁ ፡ የሚገኝ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ የገ ብያና ፡ ያጋሰስ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሰው ፡ ሁኔታ ፡ ቈጥሮ ፡ መገ መት ፡ የምችል ፡ ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ ነኝ ፡ ማለቴ ፡ ነው ።” አሉ ፡ ነጋ ድራስ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብለው ።

“ይህ ፡ ሁሉ ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ እስዎ ፡ እንዳሉት ፡ ጥሩ ፡ ጠንቀዋይም ፡ ይሁን ፡ ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ ከሚገምቱት ፡ አብዛ ኛው ፡ እንጂ ፡ ሁሉ ፡ ስለማይገዝ ፡ ስለኔ ፡ የገመቱት ፡ ከማይዘው ፡ ከጥቂቱ ፡ መሀከል ፡ ሊሆን ፡ አይችልም?”

“ይሁን ፡ ተሰስቼ ፡ ይሆናል ! ” አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ በዛብህ ፡ ምስጢሩን ፡ ሲነግራቸው ፡ አለመፍቀዱን ፡ ሲያዩ ፡ አንገታቸ ውን ፡ ደፋ ፡ አደረጉና ።

“አገርህም ፡ ይሁን ፡ እዚህ ፡ የተቸገርህበት ፡ ነገር ፡ እንዳለ፡ ልረዳህ ፡ እችል ፡ እንደሆነ ፡ ብዬኮ ፡ ነው ፡”አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ነጋድራስ ።

“እስከ ፡ ዛሬ ፡ የረዱኝ ፡ መች ፡ አነሰና?”

“እየ----እባክህ ፡ እስከ ፡ ዛሬስ ፡ ምንም ፡ አላደረግሁልህ፡ ልቤ ፡ ወደ ፡ ገብያው ፡ ተሰቅሎ ። አሁን ፡ መሄጃየ ፡ ስለደረሰ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ስትያዝ ፡ አይቼህ ፡ እንድሄድ ፡ ነበር ። አንዳንድ፡ ጊዜ ፡ ሩፋኤል ፡ ትሄዳለህ? እዚያ ፡ ካህናቱ ፡ እጅግም ፡ ስለማይ ጠጉት ፡ ከፋት ፡ ቦታ ፡ አይጠፋም ፡ ይባላል ።”

“ከማህሌት ፡ ተለይቼ ፡ አላውቅም ።”

“ካለቃው ፡ ተዋውቀሀል ?”

“የለም ። እሳቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይመጡም ፡ ሲመጡም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ስለሚከባቸው ፡ እንግዳ ፡ ሰው ፡ ሊያገኛቸው ፡ የሚ ችል ፡ አይመስለኝም ።”

“ቆይ ፡ ነገ ፡ ጥዋት ፡ ገበያ ፡ መሄዱን ፡ ትቸ ፡ እደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ዘንድ ፡ እወስድህና ፡ እሱ ፡ ያገናኝሀል ።”

“ማነው ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ !”

“የኛ ፡ ነው ፡ ያገራችን ፡ የሞጣ ፡ ሰው ፡ ነው ። በቀድሞም ፡

አስቤው ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ለመሄድ ፡ ስቸኩል ፡ ረሳሁት ።"

በበነጋው ፡ እሁድ ፡ ጥዋት ፡ ነጋድራስ ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ ማር ፡ የሸጡበትን ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ ሀሚድ ፡ የሱፍ ፡ ከሚ ባል ፡ ቱጃር ፡ ጋር ፡ ቀጠሮ ፡ ቢኖራቸው ፡ ወደሱ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ልከው ፡ እሳቸው ፡ በዛብህን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሩፋኤል ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ሄዱ ።

ሩፋኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅዳሴ ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ አገልግ ሎቱ ፡ አልቆ ፡ ካህናቱ ፡ ለግብር ፡ ወደ ፡ ግቢ ፡ ሲሄዱ ፡ ሲጠሩሩ ፡ ደረሱ ። ደብተራ ፡ መንበሩንም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲሄድ ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ አገኙትና ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ አስተዋውቀው ፡ ብርቱ ፡ ስራ ቸውን ፡ ትተው ፡ እሱን ፡ ፍለጋ ፡ የሄዱበትን ፡ ጉዳይ ፡ አንድ ባንድ ፡ ዘርዝረው ፡ ነገሩት ።

"ከዛሬና ፡ ከነገ ፡ ማለፍ ፡ የለበትም ፡ ማለትዎ ፡ ነው ፡ እንጂ፣ ያስቸገረኝ ፡ ጊዜ ፡ ከሰጡኝ ፡ ካለቃ ፡ ስርግው ፡ ጋር ፡ ማስተዋወ ቁም ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ማስታወሱም ፡ አያስቸግረኝምኮ ፡ ነጋድ ራስ ! አለቃ ፡ ዛሬ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እግቢ ፡ ግብር ፡ ስለሚውሉ ፤ ነገ ፡ ጥዋትም ፡ ወደ ፡ ርስታቸው ፡ ይሄዳሉ ፡ ተብሎ ፡ ስለሚወራ ፡ ሳይመች ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ቃል ፡ አባይ ፡ አድርገው ፡ እንዳይጣ ሉኝ ፡ ፈርቸዎ ፡ ነው ። መቸም ፡ እስዎ ፡ ስራዎም ፡ ሆነ ፡ ቃልዎ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሚዛን ፡ ነው !" አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ፍርጥም፣ ብሎ ።

"አደለምኮ ፡ መንበሬ ፡ ግቢ ፡ ቢውሉ ፡ ግቢ ፡ ያድራሉ ? ማታም ፡ ቢሆን ፡ እቤታቸው ፡ ድረስ ፡ ወስደህ ፡ አገናኝተህ ፡ ስራ፣ እንዲሰጡት ፡ አደራ ፡ በላቸው ። በፈለግህበት ፡ ጊዜ ፡ እቤታቸው ፡ የምትገባ ፡ ባለሙዋል ፡ መሆንህንና ፡ አንተ ፡ ካልሀቸው ፡ የማ ይወጡ ፡ መሆናቸውን ፡ ስምቻለሁ ። እንግዲህ ፡ አደራ ፡ ለእሱ ፡ የምታደርገውን ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ እንደምታደርገው ፡ ቁጠረው !" ሲሉ ፡ ነጋድራስ ፡ በደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ ስልጣን ፡ ያላቸው ፡ ወይም ፡ ባለብርቱ ፡ ውለታው ፡ መሆናቸው ፡ ለበዛብህ ፡ ተሰማውና ፡ ጉዳዩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቀና ፡ መንገድ ፡ የያ ዘለት ፡ መስሎ ፡ ታይቶት ፡ ደስ ፡ አለው ።

" እየ --- ብርቱ ፡ ሸክም ፡ ጣሉብኝ ፡ ነጋድራስ ፡" አለ ፡

ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ እውነትም ፡ የጣሰበት ፡ ሸክም ፡ እንደ ፡ ከበደው ፡ ሁሉ ፡ ትከሻውን ፡ ትንሽ ፡ ጎበጥ ፡ አንገቱን ፡ ወደታች ፡ ሰበር ፡ አድርጎ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያየ ።

ከዚያ ፡ ነጋድራስ ፡ ከሁለቱ ፡ ደብተሮች ፡ ተለይተው ፡ ወደ ስራቸው ፡ ሲሄዱ ፡ " አንድ ፡ ነገር ፡ አሰብሁ ፡" አለ ፡ ደብተራ መንበሩ ።

" ምን ?"

"ማታ ፡ እቤታቸው ፡ ሄደን ፡ ከምናስቸግራቸው ፡ ለምን ፡ አሁን ፡ እግቢ ፡ አንሄድ ? እዚያ ፡ ከግብር ፡ ሲወጡ ፡ እናገኛቸዋለን ፡ ወዲያውም ፡ ግብር ፡ እንበላለን ።"

" ማን ፡ ያስገባናል ?"

"መቸስ ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ ተጠርቶ ፡ ሄዶ ፡ የሚበላ ፡ የለ ፡ ያው ፡ እግሩ ፡ የደረሰውና ፡ እዚያ ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ የሚበላው ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚገባ ፡ እንገባለን ።"

ደብተራ ፡ መንበሩና ፡ በላይ ፡ በየ ፡ ወደ ፡ ግቢ ፡ ሲሄዱ ፡ ገና ፡ ከሩቅ ፡ ነጋሪት ፡ እያስተጋባ ፡ "ገብር ፤ እር- እር- ገብር" ሲል ፡ በዛብህ ፡ ሰማና ፡ " የምን ፡ ነጋሪት ፡ ነው ፡ ይሀ ፡ የምንሰማው ?" አለ ።

" ሰውን ፡ ለግብር ፡ የሚጠራ ፡ ነው ።"

" ሁልጊዜም ፡ ሰው ፡ ግብር ፡ የሚበላ ፡ እንዲህ ፡ በነጋሪት እየተጠራ ፡ ነው ?"

"አዎ ፡ ግብር ፡ ሲሆን ፡ አዎ ። ከዛሬ ፡ ቀደም ፡ አይተህ ፡ አታውቅም ?"

"የለም ፡ አይቼ ፡ አላውቅም ።"

"ማየቱ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ መብላቱን ፡ ግን ፡ እኔ ፡ አልወደውም፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ዛሬ ፡ እንኳዋ ፡ ካህኑ ፡ ሁሉ ፡ ሲሄድ ፡ እኔ ፡ ተለይቼ ፡ ቀርቼ ፡ የነበረ ። ታዲያ ፡ እየውልህ ፤ በኔ ፡ጉሮሮ ፡ ውረድ ፡ ያለው ፡ እህል ፡ ውሀ ፡ የማይቀር ፡ ሆኖ ፡ ነጋድራስን ፡ ምክናያት፡ አድርጎ ፡ አመጣኝ ። ነጋድራስ ፡ ባለብርቱ ፡ ውለታዩ ፡ ናቸው ። ካገሬ ፡ አምጥተው ፤ ስራ ፡ እስካገኝ ፡ ስንቅ ፡ ሰጥተው ፡ እዚህ ፡ ያደረሱኝ ፡ እሳቸው ፡ ናቸው ። ታዲያ ፡ እኔ ፡ ምንም ፡ አድርጌላቸው ፡ አላውቅም ፤ ሲመጡ ፡ እንኳዋ ፡ ጠይቁያቸው ፡ አላውቅም።"

“ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ሰው ፡ ናቸው ።” አለ ፡ በዛብህ ።

እግቢ ፡ ሲደርሱ ፡ ከመጀመሪያው ፡ አጥር ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ በቅሎና ፡ በቅሎ ፡ ያገር ፡ አሽከር ፡ ሞልቶታል ። ከመጀመሪያው ፡ አጥር ፡ እስከ ፡ ሁለተኛው ፡ ያለውን ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሞልቶታል ። ከዚያ ፡ እግብር ፡ መብያው ፡ አዳራሽ ፡ ድረስ ፡ እለፍ ፡ እለፍ ፡ እያለ ፡ ብዙ ፡ አቁዋራጭ ፡ አጥር ፡ ይታያል ። በያቁዋራጩ ፡ መሀከል ፡ ያለው ፡ ሜዳ ፡ ሁሉ ፡ እታች ፡ ሆኖ ፡ ሲመለከቱት ፡ መላወሻ ፡ የሌለበት ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ የሞላው ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሳያቁዋርጥ ፡ የሚጎርፈው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እዬመጣ ፡ በላይ ፡ በላይ ፡ ሲጨመር ፡ ያ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ የሞላ ፡ የሚመስለው ፡ ግቢ ፡ ሁሉንም ፡ እዬተቀበለ ፡ ይውጣል ።

እንዳንዶቹ ፡ መኩዋንንት ፡ ታጅበው ፡ መጥተው ፡ ገና ፡ የመጀመሪያውን ፡ በር ፡ ሳይገቡ ፡ ከበቅሎ ፡ ይወርዱና ፡ እዚያው ፡ ውጭ ፡ አደግድገው ፡ እጀባቸውን ፡ ትተው ፡ የሁለተኛውን ፡ በር ፡ ገብተው ፡ እዚያ ፡ ያርፋሉ ። እንዳንዶቹ ፡ በበቅሎ ፡ እንዳሉ ፡ የመጀመሪያውን ፡ በር ፡ ገብተው ፡ እዚያ ፡ ይወርዱና ፡ አደግድገው ፡ የሶስተኛውን ፡ በር ፡ ሲገቡ ፡ ይታያሉ ። እንዲሁም ፡ እንደዬማእርጋቸው ፡ ከሶስተኛው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ አቁዋራጭ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ በበቅሎ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ሲገቡ ፡ የሚታዩ ፡ ነበሩ ። ስም ፡ የለሹ ፡ ተራው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እንኩዋን ፡ በበቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ በግሩም ፡ ቆሞ ፡ ሁለተኛውን ፡ በር ፡ መግባት ፡ አይችልም ።

ያ ፡ ሁሉ ፡ ቁጥሩ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊገመት ፡ የማችል ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ህዝብ ፡ የመጀመሪያውን ፡ በር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እዬገባ ፤ ከዚያ ፡ እስካዳራሹ ፡ ባሉት ፡ ብዙ ፡ ጠባብ ፡ በሮች ፡ እዬተጣራ ፡ በዬማእርጉ ፡ ሲቀመጥ ፡ ከረፈደ ፡ በሁዋላ ፡ ከሁለተኛው ፡ ጀምሮ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ በሮች ፡ ሁሉ ፡ ተዘጉና ፡ እላይ ፤ አዳራሹ ፡ አጠገብ ፡ ከተቀመጡት ፡ መኩዋንንት ፡ ጀምሮ ፡ ለግብር ፡ መኮልኮል ፡ ተጀመረ ።

በዛብህ ፡ የህዝቡን ፡ ብዛት ፡ ሲያይ ፡ እዚያ ፡ እሱ ፡ በነበረበት ፡ ለሰፈረው ፡ ተራ ፡ ህዝብ ፡ ያነሰት ፡ ፊንታ ፡ ይደ

ርሰዋል ፡ ብሎ ፡ አልገመተም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ባዳራሹ ፡ አጠገብና ፡ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ካለው ፡ አቁዋራጭ ፡ ውጪ ፡ በነበረው ፡ ሜዳ ፡ የተቀመጠው ፡ መኳንንት ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እየተኮለኮለ ፡ በጸጥታና ፡ መልክ ፡ ባለው ፡ አየሁዋን ፡ ከገባ ፡ በሁዋላ ፡ ሌላው ፡ ከዚህ ፡ መለስ ፡ እየተባለ ፡ በጅምላ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ መንጋ ፡ እየተነዳ ፡ መግባት ፡ ስለ ጀመረ ፡ ከሁለት ፡ ሰአት ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እላይ ፡ ግብሩ ፡ ከሚበላበት ፡ አዳራሽ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሁለተኛው ፡ አቁዋራጭ ፡ ድረስ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ ሞልቶ ፡ ምን ፡ ቦታ ፡ ይበቃው ፡ ይሆን ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገብቶ ፡ አልቆ ፡ በዛብህ ፡ የነበረበት ፡ የተራው ፡ ህዝብ ፡ ፈንታ ፡ ደረሰ ። ብቻ ፡ ያገባቡ ፡ ስነ ፡ ስራት ፡ እንደ ፡ በዛብህ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለሚያየው ፡ ሰው ፡ ከማስገረሙም ፡ ሌላ ፡ እጅግ ፡ የሚያሰቅቅ ፡ ነበረ ።

ከላይ ፡ ካደራሹ ፡ አጠገብ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መጀመሪያው ፡ በር ፡ ድረስ ፡ በያቁዋራጩ ፡ በርና ፡ ባካባቢው ፡ የነበረው ፡ የከልካይ ፡ ብዛት ፡ ቁጥሩ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ የሚያስቸግር ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ አጋፋሪ ፡ የያዘው ፡ ረጃጅም ፡ ጨፈቃ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ቢሰበሰብ ፡ አንድ ፡ አዳራሽ ፡ ይሰራል ።

የበላይ ፡ አጋፋሪዎች ፡ አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ አይተው ፡ ሰው ፡ በርከት ፡ ብሎ ፡ እንዲገባ ፡ ሲያዝዙ ፡ ሰው ፡ በሰፈረበት ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ አጋፋሪ ፡ ከዚህ ፡ መለስ ፡ ተነሱ ፡ ይልና ፡ በመንጋ ፡ ያገባል ። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተነስቶ ፡ እየተራበሸ ፡ አቅም ፡ የሌለው ፡ ሲወድቅ ፡ አቅም ፡ ያለው ፡ በላዩ ፡ እየቆመ ፡ አጋፋሪዎች ፡ ሲደበድቡት ፡ ጨፈቃቸው ፡ በላዩ ፡ እየተሰባበረ ፡ በሩን ፡ ለመግባት ፡ ሲሮጥ ፡ ከሞት ፡ የሚሸሽ ፡ እንጂ ፡ መብል ፡ የሚፈልግ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ እየተራበሸ ፡ ሁሉም ፡ አይኑን ፡ እየጨፈነ ፡ የሚቆምበትን ፡ ሳያውቅ ፡ እጁን ፡ የገዛ ፡ አካሉ ፡ ክፍል ፡ እንዳልሆነ ፡ ሁሉ ፡ በላዩ ፡ ለሚወርድበት ፡ የጨፈቃ ፡ መአት ፡ እዬጋረደ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አጋፋሪዎችንም ፡ እሸንፎ ፡ እንደ ፡

ውሀ ፡ ሙላት ፡ ጠርጎ ፡ ይዞዋቸው ፡ ይገባል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከታች ፡ አመጣጡን ፡ ያዩና ፡ አጋፋሪዎች ፡ ቶሎ ፡ ተረዳድተው ፡ በሩን ፡ ዘግተው ፡ በጨፈቃ ፡ ደብድበው ፡ ይመልሱታል ።

ከሁለተኛው ፡ አቁዋራጭ ፡ ውስጥ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ እዬተነዳ ፡ እዬተነሳ ፡ ሆራ ፡ እንደሸተተው ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ አፍንጫውን ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲንጋጋ ፡ በግድ ፡ እዬተደበደበ ፡ እዬተመሰሰ ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ከወ ዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲታመስ ፡ ቆይቶ ፡ ገብቶ ፡ ሲያልቅ ፡ በዛብህ ፡ በነበረበት ፡ ሜዳ ፡ የነበረው ፡ ህዝብ ፡ መግባት ፡ ጀመረ ።

እዚያ ፡ የነበረው ፡ ህዝብ ፡ የመጨረሻው ፡ ስም ፡ የሰሙ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ዱላው ፡ ረብሻው ፡ ድብልቅልቁ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስመርጥ ፡ ነበር ። በዛብህ ፡ ገና ፡ አጀማመሩን ፡ ሲያይ ፡ እዚያ ፡ ረብሻ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በጤናው ፡ ለመውጣት ፡ የማይችል ፡ ስለ ፡ መሰለው ፡ ግብር ፡ ለመግባት ፡ ጭራሽ ፡ አለመሞከርን ፡ መረ ጠና ፡ በሩቁ ፡ አጥሩ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ሰቀላ ፡ ቤት ፡ ስላዩ ፡ ወደ ዚያ ፡ ሸሸ ።

እሰቀላው ፡ ጥግ ፡ ሁለት ፡ ጭዋ ፡ ሰዎች ፡ እዘን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ሁሉ ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ይነጋገራሉ ።

በዛብህ ፡ ግብር ፡ መብላቱም ፡ ቢቀርበት ፡ ለመብላት ፡ የሚፈልጉት ፡ የሚያደርጉትን ፡ ተጋድሎና ፡ ያን ፡ የሚያስገ ርም ፡ ረብሻ ፡ ማየቱ ፡ እንዳይቀርበት ፡ ከሩቅ ፡ የሚመለከትበት ፡ ቦታ ፡ ሲፈልግ ፡ እሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ቁዋጥኝ ፡ ደንጋይ ፡ ስላዩ ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀመጠ ። ነገር ፡ ግን ፡ ረብሻው ፡ ያስነሳው ፡ አጉዋራ ፡ ግቢውንና ፡ ከግቢውም ፡ በላይ ፡ ጠፈሩን ፡ በሙሉ ፡ እንደ ፡ ከባድ ፡ ጭጋግ ፡ ሸፍኖት ፡ ስለነበረ ፡ እዚያ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ትግልና ፡ ድብልቅልቅ ፡ የሚነሳ ሠውን ፡ አጉዋራ ፡ አይቶ ፡ ከመገመት ፡ በቀር ፡ ማየት ፡ አይቻ ልም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በዛብህ ፡ አጉዋራውን ፡ ብቻ ፡ እያዩ ፡ አጉዋራው ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ትግል ፡ እዬገመተ ፡ ተቀ መጠ ።

“ ላጋፋሪ ፡ ተምትሜ ፡ ጉቦ ፡ ሳልሰጥ ፡ ኧረቶኮ ፡ ነው --- የሞስብ ፡ ጉዋደኞቹ ፡እመሁዋንንት ፡ ማረፊያ ፡ ሲኾመጡ --- እኔን ፡ ከነሱ ፡ ለይቶ ፡ እዚህ ፡ ተኾምጠህ ፡ ጠብእ ፡ እነሱ ፡ ሲገቡ ፡ ትጠራለህ ፡ ያለኝ ። እየው ፡ አሁን ፡ እኛ ፡ እዚህ ፡ ተኾምጠን ፡ ተራውን ፡ ሰው ፡ መደዴውን ፡ ማስገባት ፡ ጀመሩ ።” አሉ ፡ አዝነው ፡ ከተቀመጡት ፡ አንዱ ፡ እንባቸው ፡ ባይናቸው ፡ ቅርር ፡ ብሎ ፡ እዬታዬ ።

“ እኔስ ፡ ያው ፡ ጉቦ ፡ ባለመስጠቴ ፡ አይደል ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ጥፋት ፡ ተገኘብኝ ! ከጦር ፡ ሜዳ ፡ ስሸሽ ፡ ታዬሁ ? ወይስ ፡ የጌታ ፡ ትእዛዝ ፡ አልፈጽም ፡ አልሁ ? እንደ ፡ ግዞተኛ ፡ ከጉዋደኞቼ ፡ ተለይቼ ፡ ከገዛ ፡ አሽከሮቼ ፡ በሁዋላ ፡ እንድቀር ፡ መደረጉ ፡ ጉቦ ፡ ባለመስጠቴ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ ሁለተኛው ።

“ የንጉስ ፡ ግብርና ፡ ቁርባን ፡ አንድ ፡ በመሆኑ ፡ ከረድኤቱ ፡ ለመሀፈልና ፡ ጌታችን ፡ ከተራ ፡ ህዝብ ፡ እንድንለይበት ፡ የሰጡንን ፡ ደረጃ ፡ ለመጠበእ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንጀራማ ፡ በዬቤታችን ፡ ከኛ ፡ ተርፎ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እናበላ ፡ የለ ? ” አሉ ፡ አይናቸውን ፡ እንባ ፡ የሞላው ፡ ሰው ።

ሁለቱ ፡ መኳንንት ፡ እንዲህ ፡ እያዘኑ ፡ ሲወያዩ ፡ ከከልካዮች ፡ አንዱ ፡ እዬሮጠ ፡ መጥቶ ፡ አይናቸው ፡ እንባ ፡ ያዘለውን ፡ መኮንን ፡ ጠራቸው ።

“ አሁን ፡ ከማን ፡ ጋር ፡ ልታስኾምጡኝ ፡ ነው ፡ የምትጠሩኝ ፡ አጋፋሪ ፡ ጉዳታ ! ካሽከሮች ፡ ጋር ፡ ልታስኾምጡኝ ፡ ነው ? ግዴለም ፡ ተውት ፡ እግዚአብሄር ፡ ይስጥልኝ ! ያደባባዩ ፡ አምላክ ፡ ያፈራርደን ፡ ብቻ ! እንግዴህስ ፡ እቤቴ ፡ እሄዳለሁ !” አሉና ፡ ሰውዬው ፡ ለመሄድ ፡ ሲነሱ ፡-

“ ኢሂ ! ኢንጉቢን ፡ ጊብሪሞ ፡ መርጌጣትኖ ? ና ፡ ማሊስ ! ” አለ ፡ አጋፋሪ ፡ ጉዳታ ፡ በብርቱ ፡ ቁጣ ፡ የተሰባበረ ፡ ሡፈቃውን ፡ አስቀድሞ ።

አኩርፈው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሊሄዱ ፡ የተነሱት ፡ ሰውዬ ፡ ታግዶ ፡ የቆዬው ፡ ቁጣቸው ፡ ገንፍሎ ፡ ከልካዩን ፡ ለማነቅ ፡ እዬተንቀጠቀጡ ፡ እጃቸውን ፡ ከዘረጉ ፡ በሁዋላ ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ አልበላም ፡ ብለው ፡ ከከልካይ ፡ ጋር ፡ መጣላታቸው ፡ ሊያ

ስከትል ፡ የሚችለውን ፡ በመገመትም ፡ ይሁን ፡ በሌላ ፡ ቁጣቸ ውን ፡ እንደገና ፡ ውጠው ፡ በረድ ፡ ሲሉ ፡ ሲያይ ፡ ክልካዩ ፡ በበኩሉ ፡ በጣም ፡ ተቆጣ ።

"ኢንትሲን ፡ ጊብሪ ፡ ኢናትን ፡ ኢንጃራኖ ፡ ፈሊጋለሽ ፡ በላል ፡ አልፈሊጋለሽ ፡ አልበላል ! አይ ፡ ኢናት ፡ አራዳን ፡ ጎርጊ.....ስ ! ኢስቲ ፡ ቂስቂስን ፡ ብላል ፡ ውርዳቱን ፡ መባለሽ ! ሊቢን ፡ አርጋል ! ኢንትሲን ፡ ጊብሪ ፡ ጊዲዳት ፡ ባላልኖንጂ ፡ ውዲዳት ፡ ባላልኖ ? ጉ ! " አለ ፡ ኢጋፋሪ ፡ ጉይታ ፡ እኒያን ፡ ሰውዬ ፡ በመናቅና ፡ በመጸየፍ ፡ ቁጣው ፡ እንደሳት ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ሲነድ ፡ እየታዩ ።

ኢጋፋሪ ፡ ጉይታና ፡ አኩርፈው ፡ ለመሄድ ፡ የተነሱት ፡ ሰው ፡ ተፋጠው ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ አንድ ፡ ካለባበሳቸውና ፡ ካጀ ባቸው ፡ የክልካይ ፡ ብዛት ፡ በግምት ፡ ከጋፋሪዎች ፡ ሹማምንት እንዱ ፡ የሚመስሉ ፡ ሰው ፡ መጡና ፡ ሁለቱንም ፡ እዚነው ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ሲያስጠሩዋቸው ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ እዚን ፡ ወዲያው ፡ ተረስቶ ፡ ሁለቱም ፡ ፊታቸው ፡ በቅጥበት ፡ በደስታ ፡ በርቶ ፡ ያጋፋሪዎችን ፡ ሹም ፡ ተከትለው ፡ ሄዱ ።

በዛብህ ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ መብላት ፡ ግዴታ ፡ እንጂ ፡ ውዴታ ፡ አለመሆኑን ፡ ካጋፋሪ ፡ ጉይታ ፡ ሲሰማ ፡ ኢጋፋሪው ፡ ካኮረፉት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ እዩተጨቃጨቀ፡ልብ፡ሳያደርገው ፡ ቀስ፡ ብሎ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ደንጋይ ፡ ወረደና ፡ ሄዶ ፡ ግብር ፡ ለመብ ላት ፡ ከሚተራመሰው ፡ ህዝብ ፡ ጋር ፡ ተጨመረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሚበላው ፡ ሰው ፡ ገብቶ ፡ የቀረው ፡ ጥቂት ፡ ስለ፡ ነበረ ፡ ዱላውም ፡ ረብሻውም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ተቀንሶ ፡ ብዙ ፡ ሳይንገላታና ፡ ዱላም ፡ ሳያገኘው ፡ ገባ ።

እንደ ፡ ገባ ፡ አብሮት ፡ የገባው ፡ ሁሉ ፡ ደህና ፡ ቦታ ፡ ፍለጋ ፡ እዩጣለው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲሮጥ ፡ እበሩ ፡ አጠገብ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ ስላገኘ ፡ ሳይገፋ ፡ ለመውጣትም ፡ እንዲመቸው ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ እዚያው ፡ ተቀመጠና ፡ መብላቱን ፡ ትቶ ፡ አዳራ ሹንና ፡ የግብሩን ፡ ስነ ፡ ስራት ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ። ያዳራሹ ፡ መጠን ፡ በወርዱም ፡ ሆነ ፡ በቁመቱ ፡ እሱ ፡ ከተቀመ ጠበት ፡ ሆኖ ፡ ዳርቻውን ፡ አጥርቶ ፡ ለማየት ፡ አይቻልም ።

ልክ ፡ በመግቢያው ፡ በር ፡ እንጣር ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ ቢል ፡ ባንድ ፡ ከፍተኛ ፡ ድልዳል ፡ ላይ ፡ ከራት ፡ በኩል ፡ በስፊው ፡ ግልጥ ፡ የሆነ ፡ ጠርዙ ፡ ሁሉ ፡ በወርቅ ፡ የተከፈፈና ፡ ራሱም ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ የሆነ ፡ ስፋቱ ፡ ካንድ ፡ መጠነኛ ፡ ቤት ፡ የማያንስ ፡ አጎበር ፡ ይታያል ። እዚያ ፡ አጎበር ፡ ውስጥ ፡ እን ዲሁ ፡ በወርቅና ፡ የቀለሙ ፡ ሁብር ፡ የብርሃን ፡ ጸዳል ፡ ተከትሎ እየተለዋወጠ ፡ አይን ፡ በሚያሳስት ፡ ዘር ፡ ያጌጠ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዙፋን ፡ ተዘርግቶ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የለበሰው ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ጸሀይ ፡ ጮራ ፡ አይን ፡ የሚለግጥ ፡ ሰው ፡ ተቀምጠዋል ፡ "እእ . . . ! እኒያ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ ጃንሆይ ፡ ናቸው ፡ "አለ ፡ በዛብህ። ከዙፋኑ ፡ አካባቢ ፡ አድልዳሉ ፡ ላይ፡የተ ቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ጸደቁ ፡ ነፍሳት ፡ ከጌታቸው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አብረው ፡ የሚካፈሉ ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ። ስጋውን ፡ በወሳሳ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ የስጋ ፡ መልከኞች ፡ ቀሚስ ፡ አልብ ሰው ፡ እየተሸከሙላቸው ፡ ጠጁ ፡ ባሳላፊዎች ፡ እጅ ፡ የበሰለ ፡ እንኮይ ፡ መስሎ ፡ ተንዠርግጎ ፡ እየተረበላቸው ፡ በጸጥታ ፡ ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ በውነት ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ይመስላሉ ። ከዙ ፋኑ ፡ አቅራቢያ ፡ ድልዳሉን ፡ ከበው ፡ የቆሙት ፡ አምዶች ፡ እንኩዋ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ ባለው ፡ ጨርቅ ፡ ተሸልመው ፡ ከሩቅ ፡ ሲታዩ ፡ ላይን ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ያሰኛሉ ። ከዙፋኑ ፡ ራቅ ፡ ከድልዳሉ ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሲሄድ ፡ ግን ፡ የሁሉም ፡ አይነት ፡ ይለወጣል ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከድልዳሉ ፡ በታች ፡ አደራ ሹን ፡ በወርዱም ፡ በቁመቱም ፡ ከዳር ፡ እስከዳር ፡ የሞላው ፡ ህዝብ ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ እየተደራረበ ፡ ለፍሮ ፡ የሚተ ራመስ ፡ የንብ ፡ ሰራዊት ፡ እንጂ ፡ በተራ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚበ ላና ፡ የሚጠጣ ፡ ሰው ፡ አይመስልም ። ስጋውን ፡ መልከኞች ፡ ሙዳ ፡ ሙዳ ፡ አድርገው ፡ እየቆራረጡ ፡ በሳጠራ ፡ ሞልተው ፡ አሸክመው ፡ ያመጡና ፡ ከሩቅ ፡ እየወረወሩ ፡ አንዱን ፡ ፊቱን ፡ ሌላውን ፡ ደረቱን ፡ ሲሉት ፡ ልበኛ ፡ ቀልቦ ፡ ያስቀረዋል ፡ የዘ ነጋ ፡ አምልጦት ፡ አመራት ፡ ይጠይቅበታል ። ጠጅ ፡ አሳላፊ ዎች ፡ ጠላት ፡ እንደሚያሳድዳቸው ፡ እየተጣደፉ ፡ ጠጁን ፡ በኩባያ ፡ እየቀዱ ፡ ሲያድሉ ፡ በሚጠጡት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡

እስኪደርስ ፡ ግማሹ ፡ ያክል ፡ በሰውነታቸውም ፡ በልብሳቸውም ፡ ይፈሳል ፡ ወዲያው ፡ የተረፈውን ፡ ቢጨርሱም ፡ ባይጨርሱም ፡ ላልደረሰው ፡ ለማድረስ ፡ ኩባያውን ፡ ከጃቸው ፡ ነጥቀው ፡ ይወስዱባቸዋል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ የኩባያውና ፡ የቢላዋው ፡ ኩዋኩዋታ ፡ ያሳላፊውና ፡ ያቅራቢው ፡ ያጋፋሪው ፡ ጫጫታ ፡ በውነት ፡ ራስ ፡ ያሳምማል። አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ የቆሙትን ፡ ወጋግራዎች ፡ እዬተደገፉ ፡ የቆሙ ፡ ብዙ ፡ አዝማሪዎች፡ እሱ ። ነገር ፡ ግን ፡ እጃቸው ፡ መሰንቆውን ፡ ሲገዘግዝ ፡ ያንገታቸውም ፡ የደም ፡ ስር ፡ ተገትሮ ፡ አፋቸው ፡ በሙሉና ፡ በከፊል ፡ ሲከፈት ፡ በማየት ፡ የሚያዘምሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ከመገመት ፡ በቀር ፡ የመሰንቆውም ፡ ሆነ ፡ የነሱ ፡ ድምጽ ፡ በጭራሽ ፡ አይሰማም ። እንዲሁም ፡ ጥሩምበኞች ፡ እምቢልተኞችና ፡ መለከተኞች ፡ እያደገደጉ ፡ ተደርድረው ፡ መሳሪያቸውን ፡ በያፋቸው ፡ ለግበው ፡ ጉንጫቸው ፡ እንደፊኛ ፡ ተነፍቶ ፡ አይናቸው ፡ ፈጦ ፡ የደም ፡ ስራቸው ፡ በዬግንባራቸው ፡ ተገትሮ ፡ ሲታዩ ፡ ሁሉም ፡ በዬመሳሪያቸው ፡ ሲጫወቱ ፡ ፎቶግራፍ ፡ የተነሱ ፡ ምስሎች ፡ እንጂ ፡ ያነለት ፡ እዚያ ፡ ቆመው ፡ የሚነፉ ፡ ነፍስና ፡ ስጋ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ አይመስሉም ።

በዛብህ ፡ ያንለት ፡ እቤተ ፡ መንግስቱ ፡ እደባባይ ፡ ከደረሰ ፡ ጀምሮ ፡ ሲያየው ፡ የዋለውና ፡ ያንጊዜም ፡ እዚያ ፡ ግብር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚያየው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ መንግስቱ ፡ ከነበረው ፡ አሳብና ፡ ግምት ፡ በጭራሽ ፡ የተለዩ ፡ ሆኖበት ፡ በመገረም ፡ ፈት ፡ ፍዝዝ ፡ ብሎ ፡ ሲመለከት ፡ በጎኑ ፡ የተቀመጠው ፡ ሰው ፡ በክርን ፡ ጎሰም ፡ አደረገና ፡ ወደጆሮው ፡ ቀረብ ፡ ብሎ "ስማህ ? ወንድሜ ፡ እንግዲህክ ፡ ጠጅ ፡ ከታደለ ፡ ያስወጡናል! ስለዚህ ፡ መቸም ፡ ግብር ፡ በልቼ ፡ መጣሁ ፡ እንጂ ፡ አይቸ ፡ መጣሁ ፡ አይባልምና ይህን ፡ ለማለት ፡ እንዲመችህ ፡ ባይሆን ፡ ከስጋው ፡ ትንሽ ፡ ብላ ፡ " አለው ።

"እእ ? እሺ ፡" አለና ፡ በዛብህ ፡ አይኑን ፡ ወደንጀራው ፡ መለስ ፡ ቢያደርግ ፡ እንኩዋን ፡ ለመብላት ፡ ለማየቱም ፡ የሚያስፈራራ ፡ ሆነበት ። እንጀራው ፡ ከጥቁር ፡ ጭቃና ፡ ከሳር ፡ በስሉ ፡ ተጠፍጥፎ ፡ የደረቀ ፡ እንጂ ፡ ከህል ፡ የተጋገረ ፡ እን

ጀራ አይመስልም ፡፡ ወጡም ፡ እንዲሁ ፡ ወፈር ፡ ብሎ ፡ የተበጠበጠ ፡ ጭቃ ፡ ይመስላል ፡፡ ከዚያ ፡ እንጀራውን ፡ ተወና፡ ከስጋው ፡ ልብላ ፡ ልተው ፡ እያለ ፡ ሲያመነታ ፡

"ተነሱ ፡ በል ! ተመለሱ ፡ በል!" አለ ፡ እዚያ ፡ አጠገብ ፡ ከቆሙት ፡ ያጋፋሪዎች ፡ ሹሞች ፡ አንዱ ፡፡ ከዚያ ፡ መጋፋቱ ማዳፋቱ ፡ ረብሻው ፡ ድብልቅልቁ ፡ እንደገና ፡ ተጀመረ ፡፡ በዛብህ ፡ እሰዬ፡ቃው ፡ መጨረሻ ፡ እበሩ ፡ አጠገብ ፡ ስለነበረ ፡ የተቀመጠ ፡ ቶሎ ፡ ተነስቶ ፡ በገባበት ፡ በር ፡ ሲወጣ ፡ ሲሄድ ፡ አንዱ ፡ ከልካይ ፡ አንገቱን ፡ ይዞ ፡ ቢወረውረው ፡ ከመሬት ፡ ተደባለቀ ፡፡ ከዚያ ፡ ተነስቶ ፡ እንደገና ፡ ወደበሩ ፡ ለመሄድ ፡ ሲሞክር፡ "ወየታባቱ ፡ ሲሄድ ፡ ነው ? በል ! እዬተመላለሰ ፡ ሲበላ ፡ ሲውል ፡ አሰበዋል?" አለ ፡ ከልካዩ ፡ ለመማታት ፡ ዱላውን ፡ እያመቻቸ ፡፡ በዛብህ ፡ ግራ ፡ ገባውና ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚወጣበት ፡ ሌላ ፡ በር ፡ መሆኑን ፡ ስላዬ ፡ ቶሎ ፡ ወደዚያ ፡ ሮጦ ፡ አመለጠ ፡፡ ከዚያ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩን ፡ እበሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ሲጠብቀው ፡ አገኘ ፡፡

"የት ፡ ጠፋኸኝ ? " አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡፡

"እስዎ ፡ ጠፉኝ ፡ እንጂ ! ጭራሽ ፡ አላገኝዎም ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጬ ፡ ነበር ፡፡"

"ወዲያው ፡ የመጀመሪያውን ፡ በር ፡ እንደገባን ፡ ካንድ ፡ አጋፋሪ ፡ ጋር ፡ ስነጋገር ፡ ባጠገቤ ፡ አልነበርህም ?"

"ያንጊዜማ ፡ አብሬዎ ፡ ነበርሁ ፡ የህዝቡ ፡ ብዛት ፡ አስገርሞኝ ፡ ስዚህ ፡ ሁሉ ፡ ህዝብ ፡ የሚበላ ፡ ነገርስ ፡ ቢገኝ ፡ የሚበላበት ፡ ቦታ ፡ ይገኛል ፡ ወይ ፡ እያልሁ ፡ በማያገባኝ ፡ ጉዳይ ፡ ገብቼ ፡ ይህን ፡ ሳወጣ ፡ ሳወርድ ፡ ቆይቼ ፡ ዘወር ፡ ብል ፡ አጣሁዎ ፡፡"

"እኔማ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ የማውቀው፡ አጋፋሪ ፡ ስላገኘሁ ፡ ላንተም ፡ ለኔም ፡ የተሻለ ፡ ቦታ ፡ እንዲሰጠን ፡ ትንሽ ፡ አጎረስሁትና ፡ እዬመራ ፡ የሁለተኛውን ፡ አቁዋራጭ ፡ በር ፡ አስገብቶ ፡ እዚያ ፡ የምቆይበት ፡ ቦታ ፡ ሲሰጠኝ ፡ ተከትለኸኛል ፡ መስሎኝ ፡ ዘወር ፡ ብል ፡ ስለጠፋህብኝ ፡ መቸም ፡ ካንተ ፡

ቀደሚ ፡ ገብቼ ፡ መውጣቴ ፡ ስለማይቀር ፡ መጠውጫውን ፡ ይገፍ ፡ እስከመጨረሻ ፡ ከጠበቅሁ ፡ አታመልጠኝም ፡ ብዬ ፡ ያሄው ፡ ቅድም ፡ የጠባሁ ፡ እጠብቅሀለሁ ። ”

“አሲቃ ፡ ወጡ ? ”

“እሳቸውማ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ገብተው ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ ከሚወጡት ፡ መሀከል ፡ ናቸው ። እንግዲህ ፡ መውጫቸው ፡ ነው ። ”

“እኔማ ፡ በገባንበት ፡ የምንወጣ ፡ መስሎኝ ፡ ተመለስ ፡ ሲባል ፡ ሳልገናኝ ቶሎ ፡ ስመውጣት ፡ ወደ ፡ ገባሁበት ፡ በር ፡ ስሮጥ ፡ አጋፋሪው ፡ እዩተመላለስህ ፡ ስትበላ ፡ ልትውል ፡ ነው ፡ ወይ ፡ ብሎ ፡ ሠርወሮ ፡ ባለኝና ፡ ያዩትልዎ ፡ ስወድቅ ፡ ፊቴ ፡ ተጋጠ ። ”አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ።

“አይ ---ጎደቶሀል ! አጋፋሪዎች ፡ ጩኸኞች ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ የማያዩ ፡ ናቸው ። ”

“እኔማ ፡ አዳራሹ ፡ በፊቱ ፡ እዩዋጠ ፡ በሁዋላው ፡ የሚቶፋ ፡ መሆኑን ፡ ሳላውቅና ፡ የሚገባ ፡ እንጂ ፡ የሚወጣ ፡ ሰው ፡ ስላላዩሁ ፡ እንደዉት ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የሚገባውን ፡ ሁሉ ፡ እዩከተተ ፡ ዝም ፡ የሚል ፡ ብዬ ፡ ነርሞኝ ፡ ነበር ። ”

በዛብህና ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ እመውጫው ፡ በር ፡ እጠገብ ፡ ቆመው ፡ ሲነጋገሩ ፡ የፋፋአል ፡ አሲቃ ፡ ብቅ ፡ ስላሉ ፡ ሁለቱም ፡ ወደሳቸው ፡ ሄደው ፡ እጅ ፡ ነሱ ።

“አአ ---ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ምን ፡ ታደርጋላችሁ - እዚህ ፡ ቆማችሁ ? ያ ፡ በቀደም ፡ እማነግርሁ ፡ ሲጮሌ ፡ ያዩሁት ፡ ልጅ ፡ አይደለም ? ”አሉ ፡ አሲቃው ፡ በዛብህን ፡ ትኩር ፡ አድርገው ፡ እያዩ ።

“አዎን ፡ ነው ፡ ጌታዩ ፡ እሱን ፡ ከጌታዩ ፡ ጋር ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ጌታዩን ፡ ነበር ፡ የምንጠብቀው ፡ ”አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ።

“ማለፊያ ፡ ማለፊያ ፡ ከዩት ፡ መጣህ ? ”

“ከጎጃም ፡” አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ ብሎ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡

"ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ሩፋኤል ፡ ማገልገል ፡ ትሻለህ ? "

"ቦታ ፡ ቢገኝልኝማ ---ለሱ ፡ ደጅ ፡ ለመጥናት ፡ ነበር ። "

"እይነተኛ ፡ ሙያህ ፡ ምንድነው ?"

"ለዜማና ፡ ለቅኔ ፡ መምህርነት ፡ ተመርቄያለሁ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ሳለሁ ፡ መጽሀፍም ፡ እስተማል ፡ ነበር ። "

"እንዲያው ፡ ድምጹ ፡ መልካም ፡ ብቻ ፡ አይደለህም ፡ ባለሙያም ፡ ነህና ! "አሉ ፡ አለቃ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብለው ።

"ነገ ፡ እቤት ፡ ድረስ ፡ ያዘኸው ፡ ና ፡ "አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ዘወር ፡ ብለው ።

ከዚያ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩና ፡ በዛብህ ፡ አለቃን ፡ በቅሎ ዋቻቸውና ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ባሉበት ፡ አድርሰዋቸው ወደ ፡ ጉለሌ ፡ ሲሄዱ ፡-

"እንኳንም ፡ ደሳለህ ! እንግዲህ ፡ ምንድነው ፡ የደስደስ ፡ የምትሰጠኝ ? "አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ።

"ስለምኑ ? "አለ ፡ በዛብህ ።

"ስራ ፡ ስላገኘህ ፡ "

"ገና ፡ መቼ ፡ አገኘሁ ? "

"አለቃ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ከተናገሩ ፡ ስራ ፡ ሰጡህ ፡ ማለት ፡ ነው ። እኛ ፡ ዘንድ ፡ የነበሩ ፡ ደብተሮች ፡ እዮለቀቁ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስለሄዱ ፡ አንዳንድ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አለ ፡ የቅኔ ፡ መምህ ራችንም ፡ በቅርቡ ፡ ሞተው ፡ ቦታቸው ክፍት ፡ ነው ። ልጅ ፡ ነህ ፡ ይሉ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሱንማ ፡ ቢሰጡህ ፡ ጌትነት ፡ ነበር ። "

"ደመወዙ ፡ ምን ፡ ያክል ፡ ነው ? "

"ባመት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አንድ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ለም ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ማደሪያና ፡ በወር ፡ ሶስት ፡ ዳውላ ፡ እህል ፡ አለው ። "

"እንግዲህ ፡ እሱም ፡ ያረዱኝ ፡ እኳደሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ ዘመድ ፡ አለኝ ! ስለሙያዩ ፡ ልብዎን ፡ ሞልተው ፡ ቢናገሩ ፡ የማሳፍርዎ ፡ አይደለሁም ። ለቅኔ ፡ መምህርነት ፡ መመረቅ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዱጋ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ መምህራን ፡ ወንበር ፡ ተሰጥቶኝ ፡ ብዙ ፡ ተማሪ ፡

አስተምር ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ታሪክ ፡ ይሁን ፡ ሰምና ፡ ወርቅ ፡ ወይም ፡ ሀብር ፡ ቅኔ ፡ ከጉባኤ ፡ ቃና ፡ እስከ ፡ መወድስ ፡ እስከ ፡ እጣንሞገር ፡ እፈታቸው ፡ ዘንድ ፡ ላሳይ ፡ እችላለሁ ።”

“ትልቅ ፡ እድል ፡ ነው ፤ ትልቅ ፡ እድል ! በል ፡ እስቲ ፡ ለሁሉም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳ ፡ እንኳዋን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሙያ ፡ እያለህ ፡ ባይኖርህም ፡ ለነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ስል ፡ የምችለውን ፡ ያክል ፡ ብያክም ፡ ይስታዋ ፡ ነው ። መቸም ፡ ቀድሞ ፡ እንዳልሁህ ፡ አለቃ ፡ ስራ ፡ ሰጥተው ፡ ሩፋኤል ፡ እንድትሆንላቸው ፡ መፈለጋቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ ፡ ብቻ ፡ ላረጋግጥልህ ፡ የማልችልና ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲረዳን ፡ መለመን ፡ የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ እንዲሰጡህ ፡ ነው ። ብችል ፡ እስቲ ፡ ማታ ፡ ሄጄ ፡ እሞክራለሁ ።”

በዛብህ ፡ ያን ፡ ሌሊት ፡ እንቅልፍ ፡ አልተኛም ። የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ ቢያገኘው ፡ ጥሩ ፡ ቤት ፡ ተከራይቶ ፡ ስልጡን ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አሽከሮች ፡ ቀጥሮ ፡ ሰብለን ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሰርቆ ፡ አምጥቶለት ፡ ምሽቱ ፡ ሆና ! ማንንም ፡ ሳይፈሩና ፡ ከማንም ፡ ሳይሸሽጉ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ” ቢቅ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ ” እያለ ፡ እየተነጋገረላቸው ፡ የሚኖሩት ፡ የደስታና ፡ የፍቅር ፡ ኑሮ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ይታዩጡና ፡ ወዲያው ፡ ያህ ፡ ምኞት ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ሁሉ ፡ ልቡን ፡ የደስታ ፡ ሙቀት ፡ ሲያግለው ፡ ይሰማዋል ። ከዚያ ፡ ትንሽ ፡ ይቆይና ፡ “አለቃ ፡ እንቢ ፡ ይሉ ፡ ይሆን ? የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ ባይሰጡኝ ፡ ሌላ ፡ ስራ ፡ እንደማላጣ ፡ ያብተራ ፡ መንበሩ ፡ አረጋግጦ ልኛል ። ለመሆኑ ፡ ከኔ ፡ የተሻለ ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ያገኛሉ ? እስቲ ፡ ለሁሉም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳ !” ይላል ። ከዚያ ፡ ቀን ፡ እግቢ ፡ ሄዶ ፡ ሲያየው ፡ የዋለው ፡ ሁሉ ፡ ይታየዋል ። ህዝቡ ፡ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከላይ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ በዱላ ፡ እየተደበደበ ፡ ሲነዳ ፡ እንዲያ ፡ እየተደበደበ ፡ ከገባ ፡ በሁዋላ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ እጃንሆይ ፡ ፊት ፡ እንዲበላ ፡ ተሰናድቶ ፡ የቀረበለት ፡ የእንጀራውና ፡ የወጡ ፡ አይነት ፡ አጋፋሪዎችና ፡ አሳላፊዎች ፡ የሚያስተናግዱበት ፡ ሁኔታ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ታዩው ።” የንጉስ ፡

ግብር ፡ ማለት ፡ ለካስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነው ! ” አለ ፡ ቀን ፡
ሲያየው ፡ የዋለው ፡ ሁሉ ፡ እንደገና ፡ ባይኑ ፡ ሀሊናው ፡ ፊት ፡
ተራ ፡ ገብቶ ፡ ሲሄድ ፡ እየተመለከተ ፡ “ ኧረ ፡ ለመሆኑ ! ሙሉ ፡
ኢትዮጵያን ፡ እየገዙ ፡ ከዚያ ፡ የተሻለ ፡ እንጀራና ፡ ወጥ ፡
አጥተው ፡ ነው ፡ ሰውን ፡ በነጋሪት ፡ ጠርተው ፡ እንዲያ ፡
ያለ ፡ ነገር ፡ አቅርበው ፡ ብሉ ፡ የሚሉ ? ወይስ ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡
ሰው ፡ ባይቆጥሩት ፡ ይሆን ? ሰውስ ፡ ያን ፡ ለማየት ፡ እንኩዋ ፡
የሚያስፈራራ ፡ ነገር ፡ ለመብላት ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የሚስገበ
ገበበት ፡ ምን ፡ ይሆን ?” የንጉስ ፡ ግብር ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ እንጀራማ ፡ እቤታችን ፡ መች ፡ አጣን ? ” አሉ ፡ ከከል
ካዩ ፡ ጋር ፡ የተጣሉት ፡ መኮንን ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ ዛሬ ፡
እንዳየሁት ፡ ከሆነ ፡ ጭራሽ ፡ አያስመኝም ! ከድሃ ፡ ቤት ፡
ተለምኖ ፡ የሚበላው ፡ ቁራሽ ፡ በስንት ፡ ጣመ ! የለም ፡ የንጉስ ፡
ግብር ፡ ለመብሉ ፡ አይደለም ፡ የሚፈለገው ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ይኖረ
ዋል ! ምን ፡ ይሆን ? የንጉስ ፡ ግብር ! ግብር ፡ መቸም ፡ እዳ ፡ ነው ።
ታዲያ ፡ ንጉስ ፡ እዳ ፡ ይከፍላል ? የለም ፡ ህዝብ ፡ ነው ፡ ለንጉስ ፡
እዳ ፡ የሚከፍል ። ነገር ፡ ግን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አልተስማማም ። ሀ
ዝቡ ፡ በላ ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ እዳ ፡ ከፈለ ? አአ - - - -? አሁን ፡ አገኘ
ሁት ! ህዝብ ፡ ለንጉስ ፡ የሚከፍለው ፡ የክብር ፡ እዳ ፡ ነው ! ህዝብ ፡
ከሰውነት ፡ ወደ ፡ እንስሳነት ፡ ደረጃ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ተገ
ፍቶ ፡ ተመትቶ ፡ የሰውነት ፡ መብቱንና ፡ ክብሩን ፡ ሁሉ ፡ ትቶ ፡
የማይበላ ፡ ነገር ፡ በልቶ ፡ ተንቆ ፡ ተደቅድቆ ፡ ለንጉስ ፡ የሚገዛ ፡
መሆኑን ፡ የሚያሳይበትና ፡ ንጉሱም ፡ ያን ፡ እያዩ ፡ ደስ ፡ የሚሰኙ
በት ፡ ዘዴ ፡ ነው ! ከሀብቱ ፡ ሀብት ፡ ከፍሎ ፡ እንደሚገብር ፡ ከሰ
ውነቱ ፡ ከፍሎ ፡ ለንጉስ ፡ የሚገብረው ፡ የመንፈስ ፡ ግብር ፡ ነው !
ልክ ፡ መሰረቱ ፡ ይህ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ማስረጃውም ፡ ከንጉስና ፡
ከትልልቅ ፡ መኳንንት ፡ ቤት ፡ በቀር ፡ በተራ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡
ግብር ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ የለም ። ብዙ ፡ ሰው ፡ ተጠርቶ ፡ የሚበ
ላው ፡ ድግስ ፡ ባዘቦት ፡ የሚበላው ፡ ራትና ፡ ምሳ ፡ ነው ፡ የሚባ
ለው ። ብቻ ፡ ሰው ፡ መሰረቱን ፡ ሳያውቅ ፡ በረዥም ፡ ጊዜ ፡ ልማ
ድ ፡ የውርደቱን ፡ ምልክት ፡ እንደ ፡ ክብር ፡ ምልክት ፡ ቆጥሮት ፡
ለምን ፡ ቀረብኝ ፡ ብሎ ፡ እንደኒያ ፡ ከጉደታ ፡ ጋር ፡ እንደተጣሉት ፡

ሰውዬ ፡ ያስቅሳል ። ጉዳታ ፡ ይልቅ ፡ ጎበዝ ፡ ነው ። አማርኛው ፡ ይጥፋው ፡ እንጂ ፡ የግብር ፡ መሰረት ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ የሚ ያውቅ ይመስላል ።” አለ ። ከዚያ ፡ ጉዳታ ፡ ኢንጉሲን ፡ ጊብሬ ፡ ጊዲዳት ፡ በላልኖንጂ ፡ ውድዳት ፡ በላልኖ ?” ያለው ፡ ትዝ ፡ እለ ውና ፡ ብቻውን ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ ሳቀ ።

እንጋት ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ እንቅልፍ ፡ ሊወስደው ፡ ሲል ፡ ነጋዴ ዎች ፡ ሲንጫጩ ፡ ተነሳ ። ከዚያ ፡ ቡና ፡ ጠጥቶ ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ሄደ ።

“አንተ ፡ እድላም ፡ ነህ ፡ እባክህ !” አለ ፡ ደብተራ ፡ መን በሩ ፡ በጣብህን ፡ ከሩቁ ፡ ሲያይ ፡ እንዴት ፡ አደርህ ፡ ከማለቱ ፡ እንኳዋ ፡ አስቀድሞ ።

“ እንዴት ? ” አለ ፡ በጣብህ ፡ ልቡ ፡ በደስታ ፡ ፈንጥዞ ፡ ካፎቱ ፡ ሊወጣ ፡ እንደ ፡ ፈለገ ፡ ሁሉ ፡ በደረቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲንደ ፋደፍ ፡ ከሩቅ ፡ እየተሰማ ።

“እድላም ፡ ነህ ፡ የቅኔ ፡ ትምህርትህን ፡ እንደ ፡ ነገርኸኝ ፡ አድርጌ ፡ ትንሽም ፡ ሁኔማምሬ ፡ ስነግራቸው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ “ ደህና ፡ ነው ፡ ስራውን ፡ ይጀምር ፡ ” አሉ ። “ ብቻ - - - - - ረስቸ - - - - - - - - ትናንት ፡ ያልነገርሁህ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። ”

“ምን ?”

“ ቦታው ፡ ከፍተኛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መሾሚያ ፡ ይከፈልበታል፡

“ ምን ፡ ያክል ? ”

“ መቶ ፡ ብር ። ”

“ መቶ ፡ ብርማ ፡ የት ፡ አገኛለሁ ? ”

“ መቶ ፡ ብር ፡ ከሌሎች ፡ የሚቀበሉት ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንተን ፡ አጥብቀው ፡ የሚፈልጉህ ፡ ስለሚመስሉ ፡ መቶም ፡ ባይሞላ ፡ ይቀበሉ ፡ ይሆናል ፡ እንዲያው ፡ ግን ፡ እንደማይ ሰጡህ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። ”

ነጋድራስ ፡ ሁናቴው ፡ ይህን ፡ ሲሰሙ ፡ አንድ ፡ ጆምብ ፡ ማርና ፡ አንድ ፡ ጆምብ ፡ ቅቤ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብለው ፡ ለደብተራ ፡

መንበሩ ፡ ቃል ፡ ሰጡ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ በሣብህ ፡ ከራሱ ፡ ሀያ ፡ ብር ፡ ጨምሮ ፡ የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ አገኘ ። ከዚያ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ወዳገራቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ስራ ፡ መያዙንና ፡ የሚኖርበትን ፡ ቦታ ፡ ዘርዝሮ ፡ ጽፎ ፡ እግረ ፡ መንገዳቸውን ፡ ሲያልፉ ፡ ዲማ ፡ ሲጉዱ ፡ ካሣ ፡ ሰጥተውለት ፡ እንዲያልፉ ፡ አደራ ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ።

# ምእራፍ ፡ ፴

## መርዶ ፡

ሰው ፡ ደስታ ፡ የሚያገኘው ፡ ሀብት ፡ በማግኘት ፡ ለነገ ፡ ሹመትና ፡ ሽልማት ፡ በመታጨት ፡ ዜናው ፡ ተስፋፍቶ ፡ በመስማት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዛብህ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በደረሰ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አገኘ ።

የያዘው ፡ ስራ ፡ ባገልግሎት ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከቆዩት ፡ እንኩዋ ፡ ጥቂት ፡ እድላሞች ፡ ብቻ ፡ ሊደርሱበት ፡ የሚችሉ ፡ እሱም ፡ አገኘዋለሁ ፡ ብሎ ፡ በጭራሽ ፡ ተስፋ ፡ ያላደረገው ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ ስራ ፡ ነው ። ባመት ፡ መቶ ፡ ብርና ፡ በወር ፡ ሶስት ፡ ዳውላ ፡ እህል ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ለም ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ማደሪያ ፡ እንኩዋንስ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ በወጡ ፡ ማግስት ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ አገልግሎት ፡ በሁዋላም ፡ ቢሆን ፡ ብድር ፡ ይከፍላል ፡ የሚባል ፡ ወገንና ፡ ጉቦ ፡ የሚሰጡት ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ የሌላቸው ፡ የሚያገኙት ፡ አይደለም ። ስሙም ፡ እንደ ፡ የሩሳሌም ፡ ባላዩት ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀና ፡ የገነነ ፡ ሆነ ።

“ ከስመጥሩ ፡ ካለቃ ፡ ክንፉ ፡ ተመርቆ ፡ የወጣ ፡ ሊቅ ፡ የሩፋኤልን ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ወንበር ፡ ያዘ ፡ ” ተብሎ ፡ እንደተወራ ፡ መልኩን ፡ ያላዩት ፡ ቅኔውን ፡ ያልሰሙት ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡ ደመወዙን ፡ እጥፍ ፡ ላድርግ ፡ ሲል ፡ ሌላው ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ ላድርግ ፡ ሲል ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ሶስት ፡ እጥፍ ፡ ላድርግ ፡ ሲል ፡ እንዲሁ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ የደመወዝ ፡ ብልጫ ፡ እሰጣለሁ ፡ በማለት ፡ አባብለው ፡ ወደየደብራቸው ፡ ለመውሰድ ፡ ይሟረቱበት ፡ ጀመር ። ያዲስ ፡ አበባ ፡ ካህናት ፡ በየመሀራው ፡ የሚያወሩት ፡ አዲሱ ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ያለቃ ፡ ክንፉ ፡ ደቀመዝሙር ፡ መሆኑንና ፡ የሩፋኤልን ፡ ወሬ ፡ ነበር ። ሩፋኤል ፡ እንኩዋ ፡ በበዛብህ ፡ ምክንያት ፡ ለጊዜው ፡ ስመጥር ፡ ሆነ ፡

ካዲስ ፡ አበባም ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ ሩፋኤል ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ የተሰበሰበው ፡ ተማሪ ፡ ቁጥሩ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ አይባልም ። የበዛብህን ፡ ቤት ፡ ከቦ ፡ የተሰራው ፡ የተማሪ ፡ ጎጆ ፡ ሜዳውን ፡ የዘማች ፡ ሰፈር ፡ አስመስለው ። ያውም ፡ ከየቤቱ ፡ ተመላልሶ ፡ ከሚማረው ፡ ሌላ ፡ ነው ። ጊዜ ፡ ባለፈ ፡ መጠን ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄደ ፡ እንጂ ፡ እመጀመሪያው ፡ ላይማ ፡ ከተማሪ ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ ሜዳው ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፡ የሰፈሩም ፡ ሰው ፡ መመረር ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ።

መቸም ፡ እንኳዋንስ ፡ እንደ ፡ በዛብህ ፡ ያለቃ ፡ ክንፉን ፡ ትልቅ ፡ ስም ፡ ያስከተለ ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ አዲስ ፡ አስተማሪ ፡ አዲስ ፡ እንደ ፡ ፈለቀ ፡ ጠበል ፡ ዜናው ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ገናና ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በየጠበሉ ፡ ዞረው ፡ ተስፋ ፡ የቆረጡ ፡ እውሮችና ፡ ደንቆሮዎች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ በሽተኞች ፡ አዲስ ፡ ጠበል ፡ ፈለቀ ፡ ሲሉዋቸው ፡ ባዲስ ፡ ተስፋ ፡ ወዳዲሱ ፡ ጠበል ፡ እንደሚሽቀዳደሙ ፡ እንዲሁም ፡ የቅኔ ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ ተሰወረባቸው ፡ የዜማ ፡ ጣም ፡ ስላልተሰማቸው ፡ ከትምርት ፡ የሸሹ ፡ ትምርት ፡ አልገባቸው ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ያዲስ ፡ አስተማሪ ፡ ወሬ ፡ ሲሰሙ ፡ ደነዝ ፡ አእምሮዋቸውን ፡ አውጥቶ ፡ ጥሎ ፡ አዲስ ፡ ስለት ፡ አእምሮ ፡ እንደሚተካላቸው ፡ ወደሱ ፡ መጉረፋቸው ፡ የተለመደ ፡ ነው ። እንደነሱ ፡ ባሉት ፡ ላይ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ እንሄዳለን ፡ ብሎ ፡ ማሁራቱ ፡ ከብር ፡ የሚመስላቸው ፡ ዲያቆናት ፡ ተሐምረው ፡ ቅኔ ፡ ቤቱን ፡ የሜዳ ፡ ገብያ ፡ አስመስሉት ። በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ለመብራት ፡ በተስፋ ፡ የመጡት ፡ የቅኔ ፡ እውሮችና ፡ ለወሬ ፡ የመጡት ፡ ዲያቆናት ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ወደየመጡበት ፡ ተመልሰው ፡ በውነት ፡ ቅኔ ፡ ለመማር ፡ ፈቃዱም ፡ ችሎታውም ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፡ የሩፋኤል ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ የቅኔ ፡ ቤት ፡ መልክ ፡ አገኘ ። ያም ፡ ሆኖ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ ሁሉ ፡ በሩፋኤል ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ ተማሪ ፡ ሩብ ፡ እንኳዋ ፡ ያለው ፡ አንድም ፡ አልነበረ ።

አለቃ ፡ ስርግው ፡ የሩፋኤሉ ፡ አለቃ ፡ በበኩላቸው ፡

ያዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ አለቆች ፡ በዙብሀን ፡ እንደ ፡ ከፉ ፡
ቀን ፡ እህል ፡ ሲሸሙትና ፡ እያከፋሉ ፡ ከፋለው ፡ ለመውሰድ ፡
ሲፈልጉ ፡ ሲያዩ ፡ ሁሉንም ፡ አሸንፈው ፡ ከሳቸው ፡ ጋር ፡
ሊያስቀሩት ፡ የሚችሉበትን ፡ ዘዴ ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ። በደ
መወዝ ፡ በኩል ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ ጭማሬ ፡ ቢያደርጉ ፡ የጊ
ዮርጊስና ፡ የሌሎች ፡ ዘብቷም ፡ አድባራት ፡ አለቆች ፡ ከሚ
ስጡት ፡ ጋር ፡ ለመወዳደር ፡ እንደማይችሉ ፡ ያውቃሉ ። ስለ
ዚሁ ፡ በደመወዝ ፡ ብልጫ ፡ ላይ ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡
ማግኘት ፡ አሰባቸው ። ጸአዳ ፡ ስርግው ፡ ያስጥርጥር ፡ ያዲስ ፡
አበባ ፡ አድባራት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሊሰጡ ፡
ከሚችሉት ፡ ደመወዝ ፡ ትበልጣለች ! ጸአዳ ፡ ለአለቃ ፡ ስር
ግው ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ የሌላት ፡ አንዲት ፡ ልጃቸው ፡
ናት ። ባል ፡ ባገባች ፡ በሶስት ፡ ሳምንትዋ ፡ ተፋታ ፡ ተመልሳ ፡
አባትዋም ፡ እንደ ፡ ፈታችው ፡ ባልዋ ፡ ከምሽት ፡ ጋር ፡ ወር ፡
የሞላ ፡ አብረው ፡ መቆየት ፡ ስለማይችሉ ፡ እንድዋ ፡ ምሽት ፡
ሄዳ ፡ ሌላዋ ፡ እስክትመጣ ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ አሰማሪና ፡
ተቆጣጣሪ ፡ ቤታቸውን ፡ አስተዳዳሪ ፡ እስዋ ፡ ናት ። እንደ ፡
ምሽት ፡ መለወጫ ፡ የሌላት ፡ አለችኝ ፡ ብለው ፡ የሚኮሩባት ፡
እስከሉ ፡ የምቾት ፡ ይሁን ፡ የችግር ፡ ተካፋያቸው ፡ ሲያልፉ ፡
ወራሻቸው ፡ ናት ። እስዋን ፡ ከዳሩለት ፡ የጸአዳ ፡ ባል ፡ ያለቃ ፡
ስርግው ፡ የልጅ ፡ ባል ፡ ከሆነ ፡ በዙብሀ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡
ይሁን ፡ የሚያስለውጥ ፡ ዋጋ ፡ አገኘለሁ ፡ ብሎ ፡ እንደማይ
ስብ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ሩፋኤል ፡ የቅኔ ፡ መም
ህራን ፡ ሁሉ ፡ ካዲስ ፡ አበባም ፡ ሆነ ፡ ከየት ፡ እየተሰበሰበ ፡
የሚመረቁበት ፡ ስመጥር ፡ ይሆናል ! ሰው ፡ ሁሉ ፡ “ እድሜ ፡
ላለቃ ፡ ስርግው ፡ ሩፋኤልን ፡ ከወደቀበት ፡ አንስተው ፡ የሊ
ቃውንቱ ፡ የቅኔ ፡ መመሳከሪያ ፡ አደረጉት ! ከሁሉ ፡ በታች ፡
የነበረውን ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ አደረጉት !” ይላል ። ከዚያ ፡ በሁ
ዋላ ፡ ደሀ ፡ ደንቅ ፡ ስራቸው ፡ ለከፍተኛ ፡ ሹመት ፡ ቢያሳጫ
ቸው ፡ ሩፋኤልን ፡ እሻረለሁ ፡ ብለው ፡ እንዳይሰጉ ፡ የታመነ ፡
ዋስ ፡ ይሆናል ! ከዚያ ፡ ልጃቸውን ፡ ላንድ ፡ ስም ፡ የሌለው ፡
የቅኔ ፡ መምህር ፡ ሰጡ ፡ እንዳይባሉ ፡ የበዙብሀን ፡ ሙያና ፡

የልጃቸው ፡ ባል ፡ መሆኑን ፡ ለጃንሆይ ፡ ነግረው ፡ በቅኔ ፡ መምህርነቱ ፡ ላይ ፡ ሹመትና ፡ ሽልማት ፡ ሲያስጡት ፡ የሳቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሱም ፡ የልጃቸውም ፡ ጥቅም ፡ ይጠበቃል ! ጎድቶ ፡ መጠቀም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጠቅሞ ፡ መጠቀም ፡ በሰውም ፡ ሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አያስወቅስም ! አዎ ! እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ክብር ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የግዜር ፡ ስጦታ ፡ የሚያስለውጥ ፡ ከጊዮርጊስም ፡ ይሁን ፡ ከሌላ ፡ ደብር ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። ይህ ፡ ነው ፡ ማሸነፊያቸው ፡ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ አሰባቸው ።

እውነትስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ድንገት ፡ ሳይታሰብ ፡ እንዲሁ ፡ ከጥሩ ፡ ሰማይ ፡ ሲዘንብለት ፡ ደስ ፡ የማይለው ፡ ማነው ? ልቡ ፡ ከፎቱ ፡ ወጥቶ ፡ በደስታ ፡ ክንፍ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የማያርግ ፡ የማይሰርግ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው ! --------- የምቾትን ፡ የደስታን ፡ የስልጣንንና ፡ እነሱን ፡ የመሰሉትን ፡ የሰው ፡ ፍላጎቶች ፡ ይዞ ተፈጥሮ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ እድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ ደስ ፡ የማይለው ፡ ሰው ፡ አይገኝም !

በሣብህ ፡ ራሱ ፡ እንዲያ ፡ በቅኔ ፡ ገብያ ፡ ብቻውን ፡ ተገኝቶ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚመሰክርለት ፡ መሆኑን ፡ ሳይረዳ ፡ የፋሲሌልን ፡ ተራ ፡ የቅኔ ፡ መምህርነት ፡ በማግኘቱ ፡ እንኳዋ ፡ የነበረው ፡ ደስታ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ያስቸግራል ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ የመጣው ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ከሱ ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ስለነበረ ፡ እደርስበት ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ አስቦትም ፡ ተመኝቶትም ፡ የማያውቅ ፡ ነገር ፡ ነው ።

እንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ በልሙ ፡ ወይም ፡ ሰብለን ፡ የሚያናግርበት ፡ በዶ ፡ ፍሊጋ ፡ ራሱን ፡ ሲበጠብጥ ፡- ያንድ ፡ ደብር ፡ አለቅነት ፡ ወይም ፡ ሊቀጠበብትነት ፡ ይሾምና ፡ ሀር ፡ ሲለብስ ፡ ባለድግድግ ፡ መረሻት ፡ በቅሎ ፡ ሲያስጭን ፡ እቤቱ ፡ ስጋ ፡ እንደ ፡ ጎመንና ፡ ዱባ ፡ ሲቆረጥ ፡ ጠጅና ፡ አረቄ ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ ሲፈስ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍራሽና ፡ ለስላሳ ፡ ዙር ፡ ምንጣፍ ፡ ላይ ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ተቀምጦ ፡ ከግራቀኝ ፡ መኳዳዎች ፡ መዘከል ፡ ሲንፈላሰስ ፡ ይቆይና ፡ ድንገት ፡ ከንቅልፉ ፡ ሲነቃ ፡

ወይም ፡ አእምሮውን ፡ ሲገዛ ፡- ያ ፡ ሁሉ ፡ ውሸት ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ጨዋታ ፡ መሆኑን ፡ ሲያይ ፡ ሲቀልድበት ፡ ቆይቶ ፡ በኋይው ፡ እልም ፡ ወይም ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ ብቻውን ፡ ይቢቃል ። ይህ ፡ መቸም ፡ እልም ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አእምሮ ፡ ሲታወክ ፡ የሚመጣ ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ ነው ። አእምሮውን ፡ ገዝቶ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ስለኑሮው ፡ ሲያስብ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አገኛ ለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ማድረግ ፡ ይቅርና ፡ ምኞት ፡ እንኳዋ ፡ አልነበረውም ።

« ስራ ፡ ሳልይዝ ፡ ስብለ ፡ ትደርስና ፡ ትቸገርብኛለች ፡ ብሎ ፡ ሲፈራና ፡ ሲሸበር ፡ ለሰው ፡ ፍቅር ፡ የታደለ ፡ በመሆኑ ፡ ነጋድ ራስ ፡ ሁነኛው ፡ ከመንገዳቸው ፡ ወጥተው ፡ ረድተውት ፡ የሩ ፋኤልን ፡ የቅኔ ፡ መምህርነት ፡ ሲያገኝ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለው ። ወዲያው ፡ እንደ ፡ ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ የከበበው ፡ ቤት ፡ ካቅሙ ፡ በላይ ፡ ተከራይቶ ፡ በውስጥ ፡ ግር ግዳውንና ፡ ወለሉን ፡ ባመድ ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ አስለቅልቆ ፡ ስብለ ፡ እውጭ ፡ ተቀምጣ ፡ ሜዳውን ፡ የምትመለከትበት ፡ ባርጩማና ፡ ሌላም ፡ እወዳለሁ ፡ ስትል ፡ ከሰማው ፡ እቃ ፡ የሚች ለውን ፡ ያክል ፡ ገዝቶ ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አሽ ከር ፡ ቀጥሮ ፡ ሰብለን ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ ይዞ ፡ ይደርሳል ፡ እ ያለ ፡ በናፍቆት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎ ቱንና ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ማስተማሩን ፡ ሲጨርስ ፡ ግረፍ ፡ ወይም ፡ መ ጫወት ፡ ሳያምረው ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡- ይሰፍርበታል ፡ በሚባለው መደብር ፡ ሁሉ ፡ እየዞረ ፡ ከዲማ ፡ ወይም ፡ ከሞጣና ፡ ከቢቸና ፡ የመጣ ፡ ነጋዴ ፡ ሲፈልግ ፡ ራስዋን ፡ ተሸፍና ፡ በበቅሎ ፡ ተቀ ምጣ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ወንዶች ፡ ያጀብዋት ፡ ወይዘሮ ፡ ባዩ ፡ ቁ ጥር ፡ እንደ ፡ ሰላይ ፡ ያላዩ ፡ መስሎ ፡ ለማየት ፡ ሲከተል ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ አራት ፡ ወር ፡ አለፈ ። እንኳዋን ፡ ሰብለን ፡ ወሬዋን ፡ የሚ ያመጣ ፡ ሰው ፡ ጠፋ ። ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ እንኳዋን ፡ ይህና ፡ ከሆንሁ ፡ ተናን ፡ ተመልሼ ፡ እቤቴ ፡ ለመዋል ፡ እንድችል ፡ ቀደም ፡ ብዬ ፡ እመጣለሁ ፡ ያሉት ፡ ሳይመጡ ፡ ቀሩ ፡ የሚያደርገውን ፡ አጣ ። ግራ ፡ ገባው ። ማንን ፡ ይጥራ ? የማን ፡ ያለህ ፡ ይበል ?

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሽምብራ ፡ ብቻ ፡ ቆርጥሞ ፡ ውሀ ፡ እየጠጣ ፡
ሶስትም ፡ ሰባትም ፡ ቀን ፡ እየጾመ ፡ ሲጸልይ ፡ እንኩዋ ፡ እንደ ፡
ድሮው ፡ ሕልም ፡ አያይም ። የሚያየውም ፡ ያክል ፡ የሚያስፈራራ
ቅዠት ፡ እንጂ ፡ የሚያጽናና ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ አይደለም ።
ስለዚህ ፡ ጊዜ ፡ እያለፈ ፡ ሲሄድ ፡ ሰብለን ፡ የማግኘቱ ፡ ተስፋ ፡
እየተቀነሰ ፡ እያነሰ ፡ መሄድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ያ ፡ ብቅ ፡
ጥልቅ ፡ እያለ ፡ አብሮት ፡ የሚኖረው ፡ በሄደበት ፡ ሁሉ ፡ የሚከ
ተለው ፡ ፍራት ፡ ባሳቡ ፡ ውስጥ ፡ እየጎላ ፡ ይታየው ፡ ጀመር ።
ግና ፡ ሲፈጠር ፡ ፈጣሪው ፡ የመደበለትን ፡ ህይወት ፡ በመሸሹ ፡
ወላጆቹንም ፡ እግዚአብሄርንም ፡ የበደለ ፡ መሆኑ ፡ ቅጣት ፡
የሚገባው ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑ ፡ በጉልህ ፡ ድምጽ ፡ ራሱ ፡
ውስጥ ፡ ሲጮህ ፡ ይሰማው ጀመር ። ለመስዋትነት ፡ እንጂ ፡
ደስ ፡ ብሎት ኖሮ ፡ ለማለፍ ፡ ያልተፈጠረ ፡ መሆኑን ፡ ይጠረ
ጥር ፡ ጀመር ።

"ብቻ ፡ ለምን ? ከተወለድሁ ፡ ጀምሮ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ፍርድ ፡ ሊያስፈርድብኝ ፡ የሚችል ፡ በደል ፡ እግዚአብሄርን ፡
አልበደልሁም ! ሳልወለድም ፡ ልበድለው ፡ አልችልም !
ታዲያ ፡ ሳልበድል ፡ ለምን ፡ የግዞት ፡ ኑሮ ፡ እንድኖር ፡ ይፈረድ
ብኛል ?" ይላል ፡ በዛብህ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡
እግዚአብሄር ፡ ባልበደሉት ፡ ላይ ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ የሚፈር
ድበት ፡ ምክናያት ፡ አልገባው ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡
ሰሚ ፡ ያለ ፡ ዳኛ ፡ እየተሟገተ ።

ከዚህ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ከደረሰው ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በጠቅላላው ፡
ሰው ፡ የሚኖርበት ፡ የማህበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ስራት ፡ ይታዩዋል ።
በጌታና ፡ በባሪያ ፡ በስጋዊም ፡ ሆነ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ገዢዎችና ፡
በተገዢው ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ ያለው ፡ በግፍ ፡ ባድልዎና ፡
በጭካኔ ፡ ላይ ፡ የተመሰረተ ፡ ስራት ፡ ይታዩዋል ። ከዚያ ፡ ደካማ ፡
ይደገፍበታል ፡ የተበደለ ፡ ይካሰበታል ፡ የሰው ፡ መብትና ፡
ነጻነት ፡ ይከበርበታል ፡ ብሎ ፡ ይገምተው ፡ የነበረው ፡ የንጉሱ ፡
አደባባይ ፡ ደካማ ፡ በመደገፍ ፡ ፈንታ ፡ ወድቆ ፡ የሚረገጥበት ፡
የተበደለ ፡ ሰው ፡ እንኩዋንስ ፡ ሊካስ ፡ ተበደልሁ ፡ ብሎ ፡
ለማኩረፍ ፡ ነጻነት ፡ የማያገኝበት ፡ መሆኑን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እግ

ብር ፡ ላይ ፡ ያዩው ፡ ትዝ ፡ ይለዋል ። ከዚያ ፡ የመንፈሳዊ ፡ መሪ ዎችና ፡ አስተማሪዎች ፡ ነን ፡ በሚሉት ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ስጋውያን፡ ገዥዎች ፡ ከሚያደርጉት ፡ የማያንስ ፡ መገበያየት ፡ጉቦ ፡ ግፍ ፡ በደል ፡ ተንኮል ፡ ሁሉ ፡ ይታዩዋል ።

" እዎ ፡ አለሙ ፡ እንደ ፡ ለማኝ ፡ እህል ፡ ድብልቅልቅ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ባለጌዎች ፡ ሽንጎ ፡ ትልቅ ፡ ድምጽ ፡ ያላቸው ፡ ብቻ እንዲሰሙበት ፤ ብርቱ ፡ ጡንቻ ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ እንዲያሸንፉ በት ፡ ሆኖ ፡ የተሰራ ፡ ነው ! እኔም ፡ ተሰሚ ፡ ድምጽና ፡ ብርቱ ፡ ጡንቻ ፡ ከሌላቸው ፡ አንዱ ፡ ነኝ ! ብቻ ፡ ይሆን ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ እንዲሆን ፡ ያደረገው ፡ ማነው ? እግዚአብሄር ፡ ነው ? ወይስ፡ ጉዱ፡ ካሳ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደሚለው ፡ ልማድ ፡ ነው ? " ይላል፡ በዛብህ፡ የማያዩ ፡ አይኖቹን ፡ ፍጥጥ ፡ አድርጎ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተክሎ ። "ይህ ፡ ሁሉ ፡ አይንና ፡ ጆሮ ፡ በሌለው ፡ አድልዎ ፡ ላይ ፡ የተ መሰረተ ፡ ስራት ፡ እውነት ፡ አዋቂው ፡ ትክክለኛው ፡ ቸሩ፡ ትልቁ፡ እግዚአብሄር ፡ የሰራው ፡ ነው ? እሱስ ፡ ባይሰራው ፡ የሰሩትንና ፡ ሲሰሩት ፡ የሚኖሩትን ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ ይላቸዋል ? እንጃ ! የሱ ፡ ስራት ፡ አይደለም ፡ እንዳልል ፡ ጌታና ፡ ባርያ ፡ ገዢ ፡ ንጉስና ፡ ተገዢ ፡ ህዝብ ፤ አባትና ፡ እናት ፡ ልጃቸውን ፡ እንደ ፡ ያእቆብ ፡ መስዋእት ፡ አድርገው ፡ ማቅረብ ፡ ሁሉ ፡ ከኦሪት ፡ ጀምሮ ፡ በመ ጽሀፍ ፡ ይገኛል ! እሱ ፡ የሰራው ፡ ስራት ፡ ነው ፡ እንዳልል ፡ ፍጥ ረቱን ፡ ያላንዳች ፡ ምክናያት ፡ በበዳይና ፡ በተበዳይ ፡ መሀከል ፡ እንዲከፋፈል ፡ ማድረግ ፡ ያልበደለ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደ ፡ ተቀጣ ፡ የበደለ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ በደለ ፡ እንዲኖር ፡ ማድረግ ፡ እን ኩዋንስ ፡ ያዋቆች ፡ ሁሉ ፡ አዋቂ ፡ የሆነው ፡ እግዚአብሄር ፡ የመ ንደር ፡ ዳኛም ፡ የሚፈርደው ፡ አይደለ ! ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ነው ? እንጃ ! "

በዛብህ ፡ እንዲህ ፡ ሲኖር ፡ ወይስ ፡ ላይኖር ፡ የተፈጠረ፡ መሆ ኑን ፡ ማወቅ ፡ አቅቶት ፡ ይህ ፡ አለም ፡ ተጠይፈው ፡ ጥለውት ፡ ሊሄዱ ፡ ወይስ ፡ በውስጡ ፡ ተቀምጠ ፡ ግፍ ፡ ሊቀበሉበት ፡ ወይም፡ ከግፍ ፡ ሰሪዎች ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ግፍ ፡ ሊሰሩበት ፡ የሚገባ፡ መሆ ኑን ፡ ማወቅ ፡ አቅቶት ፡ ሲጨነቅ ፡ " የጊዮርጊስ ፡ አለቃ ፡ ደመ ወዝህን ፡ እጥፍ ፡ አደርግልህለሁና ፡ መጥተህ ፡ እንነጋገር፡ አሉህ፡

የመድሀኔ ፡ አለም ፡ አለቃ ፡ ሶስት ፡ እጥፍ ፡ አደርግልሀለሁ፡ ብለውሀል ፤ የስላሴ ፡ አለቃ ፡ ከጃንሆይ ፡ ጋር ፡ አገናኝሀለሁ ፡ ብለውሀል ፡ አለቃ፡ስርግው ፡ አደራህ፡ በሞቴ ፡ አፈር ፡ ስሆን ፡ ዛሬ ፡ ሰራት ፡ እንዳትቀር ፡ እጠብቅሀለሁ ፡ ብለውሀል ። " የሚል ፡ መላክተኛ ፡ ከዮወገኑ ፥ ይላክበትና ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ የሚጠይቁትን ፡ ለመቀበልም ፤ ላለመቀበልም ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ስላልሆነ ፡ ከሁሉም ፡ መሸሽን ፡ ይፈልጋል ። ነገር ፡ ግን፡ ከሁሉም፡ ቢያመልጥ ፡ ካለቃ ፡ ስርግው ፡ ማምለጡ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ።

አለቃ ፡ ስርገው ፡ በዛብህን ፡ በልጃቸው ፡ ለመማረክ ፡ ለለወሰኑ ፡ ልማድ ፡ አድርገው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከራት ፡ በሁዋላ ፡ ከልጃቸው ፡ ጋር ፡ ትተውት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክናያት ፡ እዬፈጠሩ ፡ ሲወጡ ፡ ብቻውን ፡ ከጸአዳ ፡ ጋር ፡ የሚቆይበት ፡ጊዜ ፡ ከተወሰደ፡ ጀምሮ ፡ ከኖረው ፡ እድሜ ፡ ረዝሞ ፡ ይታዬዋል ።

ጸአዳ ፡ ቁንጅናዋን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያደንቀው ፡ ቀጠን ፡ ረዘም ፡ ያለች ፡ ፊትዋ ፡ ሰልከክ ፥ አይኖችዋ ፡ ጎላ ፡ ያሉ ፡ አፍንጫዋ ፡ ከላይ ፡ ቀጥ ፡ ክመሀከል ፡ ሰጉደድ ፡ ያለ ፡ ከንፈሮችዋ ፡ እነስ ፡ እነስ ፡ ብለው ፡ የሽፈኑዋቸውን ፡ ያልማዝ ፡ ድርድር ፡ የመሰሉ ፡ ጥቃቅን ፡ ጥርሶችዋን ፡ ገለጥ ፡ ሲያደርጉ ፡ ደስ ፡ የምትልና ፡ ልቅም ፡ ያለ ፡ መልክ ፡ ያላት ፡ ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ናት ። ለበዛብህ ፡ ግን ፡ ህይወትና ፡ ሙቀት ፡ የሌለው ፡ ቀዝቃዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ገና ፡ ቀለም ፡ ያልተቀባ ፡ የስእል ፡ ንድፍ ፡ እንጂ ፡ አጥንትና ፡ ስጋ ፥ ደምና ፡ ቆዳ ፥ በዚያ ፡ ላይ ፡ ነፍስ ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ መስላ ፡ አትታዬውም ፡ ነበር ። ጸአዳ ፡ ሴቱን ፡ ሁሉ ፡ ካስጠሉት ፡ አንድዋ ፡ ናት ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አባትዋ ፡ እንደ ፡ ነገሩዋት ፡ እጠገቡ ፡ ተቀምጣ፡ እያጫወተች ፡ ጠጅ ፡ ቀድታ ፡ ስትሰጠው ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተነካኩና ፡ ልክ ፡ በረዶ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ቅዝቃዜዋ ፡ የሰራ ፡ አካላቱን ፡ ያደነዘዘው ፡ መሰለው ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ መጥላት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ ጣረሞት ፡ ይፈራት ፡ ጀመረ ። እሰዋም ፡ ብትሆን ፡ አብራው ፡ በተቀመጠች ፡ ቁጥር ፡ ሲጨነቅና ፡ መድረሻ ፡ ሲያጣ፡ እያዬች ፡ እንደሚጠላት ፡ ተረድታ ፡ ያባትዋን ፡ ፈቃድና ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ሆኖባት ፡ አብራው ፡ ተቀምጣ ፡ መ

ጠጥ ፡ ስትጋብዘው ፡ ትቆያለች ፡ እንጂ ፡ የራስዋ ፡ ፈቃድ ፡ ቢኖራት ፡ ጠልቶዋት ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ሲቸገር ፡ ማየት ፡ ልክ ፡ የሞት ፡ ያክል ፡ የምትጠላው ፡ ነገር ፡ ነው ::

ከጸአዳ ፡ ቀጥላ ፡ በዛብህን ፡ ለማጥመድ ፡ የሞከረች ፡ ተዋበች ፡ ናት :: ተዋበች ፡ ቤትዋ ፡ በዛብህ ፡ በሚወጣ ፡ በሚገባበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይተያያሉ :: ከመተያየትና ፡ ሰላምታ ፡ ከመለዋወጥ ፡ ያለፈ ፡ እውቂያ ፡ ግን ፡ አልነበራቸውም:: በቁጥር ፡ መልክም ፡ ሆነ ፡ በደም ፡ ግባት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ የሚያደንቃትና ፡ ብዙ ፡ መኩዋንንት ፡ የሚጣሉባት ፡ በመሆንዋ ፡ በዛብህ ፡ እንዲሁ ፡ ሰላምታ ፡ ብቻ ፡ እዬሰጣት ፡ ማለፉና ፡ በውበትዋ ፡ አለመማረኩ ፡ አስቆጭቶዋት ፡ ኩርፊያውንም ፡ ግልምጫውንም ፡ ሌላውንም ፡ ሴቶች ፡ የወንዶችን ፡ አሳብ ፡ ወደነሱ ፡ የሚስቡበትን ፡ ዘዴ ፡ ሁሉ ፡ ሞክራ ፡ ሲያቅታት ፡ ጊዜ ፡ የሴቶችን ፡ ትታ ፡ የወንዶችን ፡ መንገድ ፡ ለመከተል ፡ ወሰነች :: አንድ ፡ ቀን፡ በዛብህ ፡ አራዳ ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ ፍለጋ ፡ ሄዶ ፡ ቆይቶ ፡ ሲመለስ ፡ ተዋበች ፡ እቤትዋ ፡ ጥግ ፡ ተቀምጣ ፡ ጠብቃ ፡ " እንዴት ፡ አመሸህ ፡ አለቃ ፡" አለችው :: "እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ ማነው ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ መሽቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ተዋበች ፡ መሆንዋን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ስላልቻለ ::

"እኔ ፡ ነኝ ፡" አለች ፡ ተዋበች ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ተነስታ ፡ ወደሱ ፡ እዬሄደች :: "ወንድሜ ፡ ካገር ፡ ቤት ፡ ወረቀት ፡ ልኮልኝ ፡ የሚያነብልኝ ፡ አጣሁ ፡ እባክህ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እቤት ፡ ግባና ፡ አንብብልኝ ::"

"የማስተማር ፡ ጊዜ ፡ ደርሶብኛል ፡ እንጂ ፡ ደስ ፡ ባለኝ ፡ ነበር::"

"መጻፍኮ ፡ አይደለም ፤ ማንበብ ፡ ነው :: ማንበብ ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳል?"

እቤት ፡ ሲገቡ ፡ ተዋበች ፡ ከጉዋዳ ፡ በወረቀት ፡ ፈንታ ፡ ሁለት ፡ ብርሌ ፡ ጠጅ ፡ አምጥታ ፡ አንዱን ፡ ለሱ ፡ ሰጠችና ፡ አንዱን ፡ እስዋ ፡ ይዛ ፡ አጠገቡ ፡ ተቀመጠች ::

"ወረቀቱ ፡ የታል?" ላንብብልሽና ፡ ልሂድ ፡ እባክሽ ::"

"ፈጥኖ ፡ ከመሄድ ፡ ያድንህ ፡ ይላል ፡ መራቂ ! ፈጥኖ ፡ መሄድ ፡ ደግ ፡ አይደለም !"

"እቤቴኮ ፡ ነው ፡ ወደሌላ ፡ ልሂድ ፡ አላልሁም! "

"ምሽት ፡ የሌለው ፡ ወንድ ፡ ሴት ፡ ያለችበት ፡ ሁሉ፡ቤቱ ፡ ነው!" አለችና ፡ አንገቱን ፡ በሁለት ፡ እጆዋ ፡ ጥምጥም ፡ አድርጋ ፡ ይዛ ፡ ለመከላከል ፡ ብርሌውን ፡ እስኪያስቀምጥ ፡ ድረስ ፡ አፉን.፡ ባፍዋ ፡ ጎርሳ ፡ ሳመችው ። በዛብህ ፡ ብርሌውን ፡ አስቀምጦ ፡ ልክ ፡ ከጣረሞት ፡ ለማምለጥ ፡ እንደሚጣጣር ፡ ሀይሉን ፡ ሁሉ ፡ አጠራቀመና ፡ ከላዩ ፡ ገፍትሮ ፡ ጥሎዋት ፡ ተነሳ ፡ ፍራት፡ ከቁጣ ፡ ጋር ፡ ተጨምሮ ፡ እያንቀጠቀጠው ። ተዋበች ፡ በበኩልዋ፡ ከወደቀችበት ፡ ለመነሳት ፡ ስትጣጣር ፡ ዘቅዝቆ ፡ ቢመለከታት፡ ጠጉርዋ ፡ ጭብርር ፡ ፊትዋ ፡ ክርር ፡ አይንዋም ፡ አፍዋም ፡ በሰፊው ፡ ክፍት ፡ ብሎ ፡ እውነትም ፡ ጣረሞት ፡ መስላ ፡ ታዩችው። ከዚያ ፡ አፉን ፡ እዩጠረገ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሮጠ ።

ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ በተዋበች ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ማለፉን ፡ እንኩዋ ፡ እዩፈራ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይሁን ፡ ወደ ፡ ሌላ፡ የሚሄድበትን ፡ መንገድ ፡ ለወጠ ። ስለዚህ ፡ በጸአዳና ፡ በተዋበች ፡ ምክናያት ፡ ሴቱን ፡ ሁሉ ፡ መጥላት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ይፈራ፡ ጀመር ። በጸአዳና ፡ በተዋበች ፡ ምክናያት ፡ ከሰብለ ፡ በቀር ፡ ሌላው ፡ ሴት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተዋበች ፡ የሚባላ ፡ እንደ ፡ ጸአዳ ፡ ቅዝቃዜው ፡ የሚያደነዝዝ ፡ መስሎ ፡ ታዩው ። በተዋበችና ፡ በጸአዳ ፡ ምክናያት ፡ እግዚያብሄር ፡ በሰፊ ፡ መሬቱ ፡ ከሰብለ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሴት ፡ ያልፈጠረ ፡ መስሎ ፡ ታዩው ። ሰብለን ፡ ካላገኘ፡ሌላ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ ንብረት ፡ አበጅቶ ፡ መኖር ፡ የማይችል፡መስሎ፡ ታዩው ። አገሩን ፡ ለቆ ፡ የተሰደደበት ፡ ወላጆቹ ፡ እንደ ፡ መካኖች ፡ ያላስታማሚ ፡ በባዶ ፡ ቤት ፡ ታመው ፡ እንዲሞቱ ፡ ያደረገበት ፡ ዋና ፡ አላማው ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ መቅረቱ ፡ ታዩው ።

በዛብህ ፡ ገና ፡ ድሮ ፡ አገሩ ፡ ማንኩሳ ፡ ዲያቆን ፡ ሆኖ ፡ ሲቀድስ ፡ ጀምሮ ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚመኛቸው ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ነበሩ ። የመጀመሪያው ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ ንብረት ፡ አበጅቶ ፡ መኖር ፡ ሁለተኛው ፡ በተሰይ ፡ የቅኔ ፡ ሊቅ ፡ መሆን ፡ ናቸው ። ሀብታም ፡ መሆን ፡ ሰብለን ፡ ከወደደ ፡ በሁዋላ ፡ የጨመረው ፡ ሶስተኛ ፡ ምኞት ፡ ነው ። የሰብለ ፡ ወሬ ፡ እዩራቀው ፡ ሲሄድ ፡ እንኩዋ ፡ የሀብት ፡ የመኖር ፡ ምኞቱም ፡

እዬተቀነሰ ፡ ሄደ ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስራውን ፡ ጨርሶ ፡ ቁጭ ፡ ሲል ፡ ወይም ፡ ሌሊት ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ቃልኪዳን ፡ ከተገባላቸው ፡ ታቦቶችና ፡ ከወላጆቹ ፡ በመሸፈቱ ፡ እግዚአብሄር ፡ የተጣላው ፡ በደለኛ ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ይለውና ፡ ፍራት ፡ ሲያዘው ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ ከእግዚአብሄር ፡ ለመታረቅ ፡ ሁሉንም ፡ ጥሎ ፡ መመነን ፡ ያስባል ።

“ሽፍታ ፡ ቀማኛ ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ አመንዝራ ፡ ልሆን ፡ አልሸሸሁ ! በህግ ፡ አግብቼ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ይዤ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እያገለገልሁ ፡ ለመኖር ፡ ብሸሽ ፡ ምን ፡ ጥፋት ፡ አደረግሁ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሄር ፡ ይቀጣኛል? የለም! በዚህ ፡ የሚቀጣ ፡ አይመስለኝም! ብቻ ፡ እኔ ፡ መበደል ፡ አለመበደሌን ፡ እሱ ፡ መቀጣት ፡ አለመቀጣቱን ፡ እንዴት ፡ ማወቅ ፡ ይቻላል?” ይላል ፡ እንደገና ፡ መልሶ ።

አንድ ፡ ሌሊት ፡ ይሆን ፡ ሲያሰላስል ፡ ድምጽ ፡ የሰማ ፡ መሰለውና ፡ በጣም ፡ ደንግጦ ፡ አይኑንም ፡ አፉንም ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ ከፍቶ ፡ እባቡን ፡ ጥቅልል ፡ አድርጎ ፡ ያዳምጥ ፡ ጀመር ። የሰማው ፡ ድምጽ ፡ አእምሮው ፡ በአሳብ ፡ ተውጦ ፡ ሳለ ፡ ሳይታወቀው ፡ ከራሱ ፡ ይውጣ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ በጭራሽ ፡ ሊረዳው ፡ አልቻለም ።

“ይህ ፡ እኮ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይሆን ፡ ያክል ፡ አያስቸግርም ። ሰብለ ፡ እስከ ፡ ፋሲካ ፡ ካልመጣች ፡ እግዚአብሄር ፡ ያልፈቀደ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ ንቱን ፡ እግዚአብሄር ፡ የመደበውን ፡ መንገድ ፡ መከተል ፡ ነው ።” የሚል ፡ ነበር ፡ ድምጹ ።

“ጥሩ ፡ መልስ ፡ ነው !” አለ ፡ በዛብህ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲያዳምጥ ፡ ቆይቶ ። “እንግዴህ ፡ አምላኬ ፡ እስከ ፡ ፋሲካ ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ ያገናኘኸኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሌላው ፡ ፍጥረትህ ፡ ሁሉ ፡ የፈቀድኸውን ፡ ህይወት ፡ ለኔ ፡ ያልነፈግኸኝ ፡ መሆንህንና ፡ እስከዛሬም ፡ የነበረኝ ፡ ፍራት ፡ ከንቱ ፡ መሆኑን ፡ አረዳለሁ! ካልመጣችግን ፡ ያው ---- የምጠረጥረውና ፡ የምፈራው ፡ እውነት ፡ መሆኑ ፡ ነው!”

በልማዱ ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ የገናንም ፡ ይሁን ፡ የፋሲካን ፡ አመትባል ፡ ተመልሶ ፡ በዩቤቱ ፡ ለመዋል ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ካመትባሉ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የንግድ ፡ እቃውን ፡ እዩጫነ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መድረስ ፡ አለበት ። በዛብህ ፡ ይህን ፡ ስላጠና ፡ የገና ፡ አመትባል ፡ እስኪያልፍ ፡ ያደርገው ፡ እንደነ በረ ፡ ሁሉ ፡ ከፋሲካ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ያክል ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የጎ ጃም ፡ ነጋዴ ፡ የሚሰፍርበትን ፡ መደብር ፡ ሁሉ ፡ በቀን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳይረግጠው ፡ ውሎ ፡ አያድርም ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ በዩመደብሩ ፡ ሲዞር ፡ አምሽቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲመለስ ፡ ሁለት ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴዎች ፡ እዩተጫወቱ ፡ ወደ ፡ ጉለሌ ፡ ሲሄዱ ፡ ደረሰባቸው ።

" አሁንኮ ፡ አሲ ፡ ጀብሪ ፡ ቆዳችነን ፡ መዝንልንና ፡ ዋጋ ፡ እንነጋገር ፡ ብንለው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሚዛኑ ፡ ተሰብሮዋል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መዛኙ ፡ ታሙዋል ፡ እያለ ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ የሚለን ፡ ፋሲካ ፡ እስኪደርስለት ፡ ነው ! " አለ ፡ አንዱ ፡ ነጋዴ ።

"ፋሲካ ፡ ሚዛን ፡ ይሆናል ? ወይስ ፡ መዛኝ ! " አለ ፡ ሁለተኛው ።

"የለም ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ እያልሁ ፡ ፋሲካ ፡ እስኪለግት ፡ ካቆ ዩሁዋቸው ፡ ለማጫረት ፡ ጊዜ ፡ ያጥራቸውና ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ ጥለውልኝ ፡ ይሄዳሉ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ! "

"ኧረግ ፡ የዲማው ፡ አባቴ ! ዋጋ ፡ ሰብረን ፡ ከምንሸጥ ፡ በምናውቀው ፡ አገር ፡ አስቀምጠነው ፡ አንሄድም ?"

" ላዲስ ፡ አበባ ፡ እንግዶች ፡ መስለነው ፡ ይሆናል።"

ነጋዴው ፡ የዲማን ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፡ በዛብህ ፡ ልቡ ፡ ተር ተር ፡ ብሎ ፡ በህዋሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ወራሪ ፡ ተነዝቶ ፡ የሚበዘብዘው ፡ መሰሎ ፡ ተሰማው ። ጉልበቱ ፡ እንደ ፡ መብረክረክ ፡ አይኖቹ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መድበዝበዝ ፡ አሉና ፡ ወዲያው ፡ የተናወጸ ፡ አካላቱ ፡ ጸጥ ፡ አሳቡም ፡ ጠቅለል ፡ አለ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ነጋዴ ዎች ፡ የተነጋገሩትን ፡ አልሰማም።

"ጌቶች ፡ ከየት ፡ ጎጃም ፡ ነው ፡ የመጣችሁ? እኔ ፡ ጎጃሜ ፡ ስለ ሆንሁ ፡ ያገሬ ፡ ሰዎች ፡ መሆናችሁን ፡ ስለተረዳሁ ፡ ነው ፡

ደፍሬ ፡ የምጠይቃችሁ ።” አለ ፡ አስተካክሎ ፡ ለመናገር ፡ እስኪችል ፡ ትንሽ ፡ ቆይቶ ።

“ ከነማይ ። ” አለ ፡ አንዱ ፡ ነጋዴ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ በዛብህን ፡ አዩና ።

“ የት ፡ እነማይ ? ”

“ ዲማ ። ”

“ ዲማ ፡ ደብሩ ? ”

“ ዲማ ፡ እምብርቱ ። ”

“ ዲማ ፡ ማንን ፡ ታውቃላችሁ ? ፊታውራሪ ----- መሸሻን ፡ ታውቃላችሁ ?”

“እር ! ምን ፡ ማለታቸው ፡ ነው ፡ እያ ! ዲማ ፡ እዩኖርን ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ይጥፉን ? ”

“አለቃ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤንሳ ?”

“እዋ! ጉዱ ፡ ካሳን ?”

“ ታዲያ ፡ ሁሉም ፡ ደህና ፡ ናቸው ? ”

“ ደህና ፡ ናቸው ። ”

“ አለቃ ፡ ካሳ ፡ አመጣለሁ ፡ ብለው ፡ ጽፈውልኝ ፡ ስጠብቃቸው ፡ ስለቀሩ ፡ ደህና ፡ ባይሆኑ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ሰግቼ ፡ ነበር ።”

“ ሁሉም ፡ ደህና ፡ ናቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ልጃቸውን ፡ ለፋሲካ ፡ ሊድሩ ፡ ይሰናዳሉ ። ሰርጌም ፡ ተስካሩም ፡ የልጂ ፡ ሰርግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስታውቀው ፡ እነማይ ፡ በሙሉ ፡ ይደግሳል ። እኛ ፡ እንኩዋ ፡ ከዚህ ፡ ለሙሽራዋም ፡ ለሙሽራውም ፡ የሚሰጡት ፡ ሽልማት ፡ ገዝተን ፡ እንድንወስድላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተውን ፡ ነበር ፤ አይነቱን ፡ የሚመርጥልን ፡ አጥተን ፡ ገና ፡ አልገዛንም ። ጌታው ፡ እንግዲህ ፡ እስዎ ፡ ዘመድ ፡ ከሆኑ ፡ ለትልቅ ፡ ሰው ፡ ሽልማት ፡ የሚሆን ፡ ልብስ ፡ መምረጥ ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ቢያገኙን !” አለና ፡ ነጋዴው ፡ መልስ ፡ ሲያጣ ፡ ጊዜ ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ በዛብህ ፡ በሁዋላቸው ፡ የሉም ። በዛብህ ፡ ነጋዴው ፡ “ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ልጃቸውን ፡ ለፋሲካ ፡ ሊድሩ ፡” ሲል ፡ መብረቅ ፡ እንደመታው ፡ በቆመበት ፡ ደርቆ ፡ ቀረ ። ወዲያው ፡ ሳይታወቀው ፡ እዚያው ፡ ተቀመጠ ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ነጋዴው ፡ የተናገረው ፡ ሁሉ ፡ ከጉዋደኛው ፡

በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰሚ ፡ አልነበረውም ። ሁለቱ ፡ ነጋዴዎች ፡ በዛብህን ፡ በሩቅ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲያዩት ፡ ታምሟል ፡ ብለው ፡ ወደሱ ፡ እየሮጡ ፡ ሄዱ ። ለጊዜው ፡ መነሳት ፡ ያቅተው ፡ እንጂ ፡ አእምሮውን ፡ ገዝቶ ፡ አገኙት ።

" ምነው ! አመመዎ ? " አለ ፡ ከነጋዴዎቹ ፡ አንዱ ፡

" ትንሽ ፡ ራሴን ፡ አዞረኝ ፡ ነው ፡ ግዴለም ፡ ሂዱ ፡ አሁን ፡ ይተወኛል ። "

" መልኮ ፡ ጠጥተው ፡ ገርጥዋል ! "

" የለም ፡ መንሸ ፡ አለብኝ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ማለፉ ፡ ነውና ፡ አትቸገሩ ፡ ሂዱ ። "

" እንዴ ፡ ይመኛ ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ ጥለንዎ ፡ እንሄዳለን ? ሰፈራችን ፡ እዚህ ፡ ነው ፡ ዘና ፡ ጠጥተው ፡ ሲሻለዎ ፡ እቤትዎ ፡ እናደርስዎ ፡ እንጂ ! "

በዛብህ ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ነጋዴዎች ፡ ወደ ፡ ተከራዩት ፡ ቤት ፡ አብረዋቸው ፡ ሄዶ ፡ ዘና ፡ ሲጠበሱ ፡–

" ወደ ፡ ሺማ ፡ መቼ ፡ ለመነሳት ፡ ታስባላችሁ ? " አለ ።

" ከዛሬ ፡ ሳምንት ፡ እናልፍም ። "

" እስከትሄዱ ፡ ድረስ ፡ እየመጣሁ ፡ እጠይቃችኋለሁ ። "

ከዚያንለት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እንቅልፍ ፡ ይሁን ፡ እረፍት ፡ የለው ፡ የመብል ፡ ይሁን ፡ የመጠጥ ፡ ፍላጎት ፡ የለው ፡ ገና ፡ መብል ፡ ሲያስብ ፡ አፉን ፡ እየመረረው ፡ ራሱ ፡ እስበባቸው ፡ የሚጣሉ ፡ አሳቦች ፡ የሚዋጉበት ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ሆኖ ፡ ደከመው ።

"እዚያው ፡ ዲማ ፡ ብቆይ ፡ ኖር ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አይደርስም ፡ ነበር ! ምን ፡ ለማድረግ ፡ እችል ፡ ኖርዋል ? ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወዳጄ ፡ መስሎ ፡ አታሎ ፡ ሰዶ ፡ ጉድ ፡ አደረገኝ ! አይ ፡ የለም ፡ ባይሆንለት ፡ ነው ! ስብለ ፡ ካደችኝ ፡ የለም ፡ ተገዳ ፡ ነው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ፈቅዳ ፡ አይደለም ! በግድ ፡ ነው ! በቃችኝ ፡ ጠላሁዋት ፡ እንግዲህ ፡ አባትዋ ፡ በግድ ፡ አንቀው ፡ ሲሸጥዋት ፡ ምን ፡ አደረግሽ ፡ ብዬ ፡ ልጥላት ?"

በዛብህ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ያሳብ ፡ ውሽንፍር ፡ ሲያጠናፍረው ፡ ሰንብቶ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የታመከ ፡ የአሳብ ፡ ማእበል ፡

ሶስት ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ሲያንገላታው ፡ ሰንብቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ያለ ጥፋት ፡ ከተፈረደበት ፡ ቅጣት ፡ ለማምለጥ ፡ ከሙታን ፡ ኑሮ ፡ የህያዋን ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ በጀመረው ፡ ትግል ፡ ድል ፡ መሆኑን ፡ አምኖ ፡ መሸነፉን ፡ ተቀብሎ ፡ ጸጥ ፡ ማለት ፡ ማረፍ ፡ ጀመረ ። ተንጠልጥሎ ፡ እወድቅ ፡ አልወድቅ ፡ ከማለት ፡ መውደቅ ፡ በስንት ፡ ጣሙ! መውደቅ ፡ ያሳርፋል! ስለዚህ ፡ በዛብህ ፡ ወደቀና ፡ አረፈ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ዲማ ፡ ነጋዴዎች ፡ ቤት ፡ ቢሄድ ፡ ወዳገራቸው ፡ ለመነሳት ፡ ጭነታቸውን ፡ ሲቀረቅቡ ፡ ደረሰባቸው ።

"እኛስ ፡ ሲቀሩ ፡ ጊዜ ፡ ሳናገኝዎ ፡ ልንሄድ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ፈርተን ፡ ነበር ።" አለ ፡ ከነጋዴዎቹ ፡ አንዱ ፡ በዛብህን ፡ ሲያይ ፡

"ጤና ፡ እጥቼ ፡ ሰነበትሁ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ ላለቃ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ታደርሱልኛላችሁ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ አንድ ፡ እንሽሎግ ፡ ከኪሱ ፡ አውጥቶ ።

"የገባሁ ፡ እለት ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ እቤቱም ፡ አላሳድረው ፡" አለ ፡ ነጋዴው ፡ እዬሳቀ ።

"ይድረሳቸው ፡ እንጂ ፡ ቢያሳድሩትም ፡ ግዴለ ።"

ነጋዴው ፡ እንዳለው ፡ ዲማ ፡ የገባለት ፡ ደብዳቤውን ፡ ለጉዱ ፡ ካሳ ፡ አስረከበ ። የተጻፈው ፡ ለሰብለ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በበነጋው ፡ ደረሳትና ፡ በዛብህና ፡ እሷዋ ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ የፍቅር ፡ አለማቸውን ፡ ባዩባት ፡ እልፍኝዋ ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጣ ፡ አነበበችው ። የስንብት ፡ ደብዳቤ ፡ ነው!

"ሰብለ ፡ ሰብለ ፡ ሰብለ ፡ ወዳጄ ፡ እመቤቴ ፡-
የመአልት ፡ ምርኩዜ ፡ የሌሊት ፡ መብራቴ ፡-
ስራብ ፡ እንጀራዬ ፡ ስጠማ ፡ ወተቴ ፡-
ሳዝን ፡ መጽናኛየ ፡ ስደክም ፡ ጉልበቴ ፡-
ሳጣ ፡ አለኝታዬ ፡ ስጠቃ ፡ ኩራቴ ፡-
የስጋ ፡ የመንፈስ ፡ ያለሽኝ ፡ አንድ ፡ ሀብቴ ፡-
ቁርጥ ፡ ከሆነማ ፡ እኔ ፡ አንቺን ፡ ማጣቴ ፡-
ምን ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ ከንግዲህ ፡ ህይወቴ?
የለም! ህይወት ፡ ቢቀኝ! ይገላግለኝ ፡ ሞቴ ፡-
ትቀማሁ ፡ ወደኔ ፡ ድህ ፡ በመሆኔ ፡-

ጥዬሽ ፡ የሄድሁለት ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሬ ፡-
የደም ፡ እንባ ፡ አልቅሼ ፡ በድሌ ፡ አግርሬ ፡-
የሁዋሊት ፡ ስንተት ፡ በፍቅርሽ ፡ ታስሬ ፡-
ወደፊት ፡ መራመድ ፡ እያቃተው ፡ እግሬ ፡-
አሁንም ፡ አሁንም ፡ ቆሜ ፡ እያየሁ ፡ ዞሬ ፡-
ምን ፡ ልቤ ፡ ቢፈራ ፡ ባይቀር ፡ መጠርጠሬ ፡-
በተስፋ ፡ ነበረ ፡ የወጣሁ ፡ ከገሬ ፡-
እስከዛሬም ፡ ድረስ ፡ በሀይወት ፡ መኖሬ ፡-
ተስፋ ፡ ሆኖኝ ፡ ነበር ፡ ፍቅርሽና ፡ ፍቅሬ ፡-
ግን ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ የነገሩኝ ፡ ወሬ ፡-
ሊያገባሽ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ባለብዙ ፡ በቅሎ ፡ ባለብዙ፡ በሬ፡-
በፍቅር ፡ ለሞተ ፡ መቃብሪያ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ መቃብሬ ፡-
መኖር ፡ አልፈልግም ፡ ሞቼ ፡ ልደር ፡ ዛሬ ፡-
    ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ ፡
    ለብለ ፡ ልጠይቅሽ ፡ እስቲ ፡ ተናገሪ ፡
ከሁሉ ፡ እኔን ፡ ብቻ ፡ እንደምታፈቅሪ ፡-
ከኔ ፡ ተለይተሽ ፡ እንዳትችይ ፡ ልትኖሪ ፡-
ላባትሽ ፡ ነግረሻል ፡ በድፍረት ፡ ሳትፈሪ ፡-
እንቢኝ ፡ አሻፈረኝ ፡ ያለሱ ፡ አላገባም ፡ ብለሻል ፡ ሳታፍሪ ?
ወይስ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ታፍና ፡ ተዳሪ ፡-
ዝም ፡ ብለሽ ፡ ተቀበልሽ ፡ ሳትከራከሪ?
ወይስ ፡ ተለይተን ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ስትኖሪ ፡-
መቸም ፡ ሰው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ሲፈጥረው ፡ ፈጣሪ ፡-
ተለውጦ ፡ ይሆን ፡ ከቶ ፡ ያንችም ፡ ባህሪ ፡-
የሰም ፡ ግሪኝ! ግሪኝ! ርሺ ፡ አትዘከሪ ፡-
ዱብዳ ፡ ወድቆብኝ ፡ ለሸክሙ ፡ አስቸጋሪ ፡-
ጨንቆኝ ፡ ስለፈለግ፡ እንደ ፡ ቀባዣሪ ፡-
ባንቺ ፡ እምነት ፡ የሌለኝ ፡ ብመስል ፡ ጠርጣሪ ፡-
መሆንሽን ፡ አውቃለሁ ፡ ፍቅርሽን ፡ አክባሪ ፡-
በሀብት ፡ ለመደለል ፡ የማትሞከሪ ፡-
    ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ ፡
    አውቃለሁ ፡ አባትሽን ፡ እንዳማጠንሽቸው ፡-

ነፍስና ፡ ስጋ ፡ ነን ፡ አባክዎ ፡ አይለዩን ፡ አባባ ! እንዳልሻቸው ፡
ከዚህ ፡ አይሻለሁ ፡ ወድቀሽ ፡ ከፊታቸው ፡-
እዩ፡ተሰቀዩሽ ፡ ስትለምኛቸው ፡-
እንባሽ ፡ ይታዩኛል ፡ ሲፈስ ፡ በገራቸው ፡-
እየ ! ያባት ፡ ክፉ ፡ ምቀኝ ፡ የሞላቸው ፡-
እስቲ ፡ እኛ ፡ ደስ ፡ ቢለን ፡ ምኑ ፡ ጎድሎባቸው ፡-
የሳቸውን ፡ ህይወት ፡ ኖረው ፡ በፈንታቸው ፡-
የኛን ፡ ህይወት ፡ እንዲህ ፡ ከንቱ ፡ ማድረጋቸው ?
እኔስ ፡ ባእዳቸው ነኝ ፡ ይቅር ፡ ልበላቸው !
ደስታ ፡ በብዙ ፡ ሀብት ፡ ይገዛ ፡ መስሎዋቸው ፡-
እንዴት ፡ ይነግዱ ፡ በገዛ ፡ ልጃቸው ?
ዳኛ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ የሚጠይቃቸው ፡-
ከቶ ፡ የሚሰጡት ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ መልሳቸው ?
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !..
ዳኛ ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ ቢኖርማ ፡ ዳኛ ፡-
ህሊናው ፡ ባድልዎ ፡ በጉቦ ፡ ያልተኛ ፡-
እንዳንቺ ፡ አባት ፡ ያለ ፡ ጨካኝ ፡ አመጸኛ ፡
በልጁ ፡ የሚነግድ ፡ ሲገኝ ፡ ግፈኛ ፡-
እጁን ፡ ወደሁዋሊት ፡ ታስሮ ፡ በመጫኛ ፡-
ይሰቀል ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
እግዚአ ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ ለማን ፡ ልጩህ ፡ እኔ ?
ነፍሴን ፡ ወስደውብኝ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ በድኔ ፡
አልቅሶ ፡ እንዳይቀብረኝ ፡ እንዳያዝን ፡ ወገኔ ፡-
ቆሞ ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ ይታያል ፡ ግብኔ ፡-
በማን ፡ ደርሶ ፡ ያውቃል ፡ እንዲህ ያለ ፡ ብዩኔ ?
ሳያጠፉ ፡ ቅጣት ፡ ሳይሞቱ ፡ ኩነኔ ?
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
ጉልበቴን ፡ ሳላጥፍ ፡ ወገቤን ሳልፈታ ፡-
ቀን እረፍት ፡ ሳያምረኝ ፡ ወይ ፡ ሌሊት ፡ ምኝታ ፡-
እርም ፡ ብዬ ፡ ትቸ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ጭዋታ ፡-
ስጸልይ ፡ ስማለል ፡ ከጥዋት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡-

ያሳዩኛል ፡ ብዬ ፡ አይንሽን ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡-
አጥፊዎችን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ባዩ ፡ ጌታ ፡-
መቸም ፡ ያልጻፈኝ ፡ ነኝ ፡ ስፈጠር ፡ ለደስታ ፡-
አመጣልኝ ፡ መርዶ ፡ በምስራች ፡ ፈንታ ፡-
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
እግዚአብሔር ፡ ሲፈጥረኝ ፡ ጥንቱን ፡ በዚህ ፡ መሬት ፡-
ሳለቅስ ፡ ተወልጄ ፡ ሳለቅስ ፡ ኖሬበት ፡-
ሳለቅስ ፡ እንድሄድ ፡ ነው ፡ ወዳማልቀርበት ?
መከራ ፡ ጠግቤ ፡ ደስታ ፡ እንድራብበት ?
ሌሎች ፡ የበሉትን ፡ እዳ ፡ እንድከፍልበት ?
ሌላው ፡ ጠግቦ ፡ ሲደሰት ፡ እኔ ፡ እንዳልቀምስበት ?
እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡ አድሎ ፡ የሞላበት ፡-
አቅም ፡ ስለሌለኝ ፡ የምቀጠምበት ፡-
ገዛም ፡ ብዬ ፡ እቆጣለሁ ፡ መቸስ ፡ ምናለበት ፡-
ብቻ ፡ ሳላጠፋ ፡ በተቀጣሁበት ፡-
የሰጠኝ ፡ አእምሮ ፡ ልመራመርበት ፡-
ቅንና ፡ ጠማማ ፡ ለይቼ ፡ እንዳውቅበት ፡
ምንም ፡ እንኳ ፡ ባይችል ፡ ቅጣት ፡ ሊጥልበት ፡
ይኖራል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈረደበት ፡-
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
እኔስ ፡ ግዴለም ፡ ይቅጣኝ ፡ ይደብድበኝ ፡-
መቸም ፡ ለመከራ ፡ ለጣር ፡ የመደበኝ ፡-
ሳዝን ፡ ኖሬ ፡ እንድሞት ፡ የተፈጠርሁ ፡ ነኝ ፡-
አንጀቴን ፡ የበላው ፡ አሁን ፡ ያሳዘነኝ ፡-
ታምሜ ፡ እማልድነው ፡ በሽታ ፡ የሆነኝ ፡-
እሱ ፡ የጠላኝን ፡ ተገኝተሽ ፡ ስትወጂ ፡-
አንቺንም ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መቅጣቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡-
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
ከልብ ፡ የማያስማማ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ ጠፍቶ ፡-
ጨንቆኝ ፡ ጠበበኝ ፡ ምን ፡ ላርግ ፡ ይሆን ፡ ከቶ !
እንጀራ ፡ በመሶብ ፡ ጠጅ ፡ በንስራ ፡ ሞልቶ ፡-
ጌትነት ፡ ሲጠራኝ ፡ በሩን ፡ በዋ ፡ አርጎ ፡ ከፍቶ ፡-

ሹመት ፡ ሲለምነኝ ፡ እጆቹን ፡ ዘርግቶ ፦
ልቤ ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ስብለ ፡ ላንቺ ፡ አደልቶ ፦
ጌትነት ፡ ያላንቺ ፡ ከንቱነቱን ፡ አይቶ ፦
አንቺ ፡ በሌለሽበት ፡ መደሰትን ፡ ጠልቶ ፦
ወዳጁን ፡ ከሀዲ ፡ እንዳይባል ፡ ፈርቶ ፦
ሁሉንም ፡ እንቢ ፡ አለ ፡ ድምጹን ፡ አሰምቶ ፦
ምከረው ፡ እባክሽ ፡ አርፎ ፡ እንዲያሳርፈኝ ፡ ከንቱ ፡ ትግሉን
ትቶ ።
ድል ፡ ከሆኑ ፡ በላይ ፡ መሸረፍ ፡ የማይቀር ፡ መሆኑን ፡ ተረ
ድቶ ፦

ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !
ልቤን ፡ ባባብለው ፡ ተጽናናልኝ ፡ ብዬ ፦
እንቢ ፡ አለኝ ፡ ምን ፡ ላርገው ፡ ንገሪኝ ፡ ሰብልዬ ፦
ካንቺ ፡ ከሚወድሽ ፡ ስለተለዬ ፦
ቀን ፡ ከሌት ፡ ያለቅሳል ፡ ይላል ፡ ወዬ ፡ ወዬ ፡
በጦር ፡ እንደወጉት ፡ እዬተሰቀዬ ፡

ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !
ሰብለ ፡ የኔ ፡ ተስፋ ፡ የልቤ ፡ ደስታ ፡
የመንፈሴ ፡ ድጋፍ ፡ ያሳቤ ፡ ጸጥታ ፡
መቸም ፡ ልንገናኝ ፡ አልፈቀደም ፡ ጌታ ፡
ብናለቅስ ፡ ኡ ፡ ብንል ፡ ደረት ፡ ብንመታ ፦
እንግዴህ ፡ እንተወው ፡ ይከተተው ፡ ዝምታ ፦
ብቻ ፡ እንዳትረሺ ፡ የፍቅሬን ፡ ትዝታ ፦
ቀን ፡ ስትቀመጪ ፡ ስትተኚ ፡ ማታ ፦
እንግዲህ ፡ ደህና ፡ ሁኚ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አይለይሽ ፡ የግዚአብ
ሔር ፡ ርዳታ ፦
መከፋት ፡ አይንካሽ ፡ የልብ ፡ ቅሬታ ፡
ካለሽበት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ባለሽበት ፡ ቦታ ፦

ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !
ለባለድል ፡ ከሆንሽ ፡ እኔ ፡ ስላልታደልሁ ፦
በደስታ ፡ እንድትኖሪ ፡ እመኝልሻለሁ ፡
እኔ ፡ ግን ፡ ከንግዴህ ፡ ካንቺ ፡ ከተለየሁ ፦

ልቤን ፡ ለሌላ ፡ ሴት ፡ እንዳልሰጥ ፡ ምያለሁ ፡-
እስኪጠራኝ ፡ ድረስ ፡ በህይወት ፡ እስካለሁ ፡-
ከትዝታሽ ፡ ጋራ ፡ ቆርቤ ፡ እኖራለሁ ።

እንግዲህ ፡ ደህና ፡ ሁኚ ፤ ባያሌው ፡ ደህና ፡ ሁኚ ፡ ሰላም ፡ ብዬሻለሁ !

ወይኔ ፡ ወይኔ ፡ ተቀጣሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !”

“ በሣብህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎትን ፡ የተወበት ፡ ምክናያት ፡ ምንድነው ? ደብተራ ፡ መንበሩ !” አሉ ፡ አለቃ ፡ ስርግው ፡ አንድ ፡ ቀን ።

“ ከቤት ፡ ከጠፋ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፡ ተማሪው ፡ ሁሉ ፡ መበተን ፡ መጀመሩን ፡ አልሰሙም ? ጌታየ !”

# ምእራፍ ፡ ፴፭ ፡

## ሰርግና ፡ ተዝካር ፡

በቆብሀ ፡ ዲማን ፡ ትቶ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ከሄደ ፡ በሁዋላ ፡ ወዲያው ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ድንበሩ ፡ ሰብለን ፡ አጭተው ፡ ሰርጉ ፡ ለገና ፡ እንዲሆን ፡ ተወሰነ ። ነገር ፡ ግን ፡ በመሀከሉ ፡ ሰብለ ፡ በጽኑ ፡ ታማ ፡ የገናን ፡ አመትባል ፡ ሁሉ ፡ ትተርፍ ፡ አትተርፍ ፡ እዩተባለ ፡ ቤተዘመዱ ፡ ገና ፡ በስጋት ፡ ላይ ፡ ስለነበረ ፡ ለገና ፡ የተቀጠረው ፡ ሰርግ ፡ ወደ ፡ ፋሲካ ፡ ተላለፈ ።

ቀኑ ፡ ሲደርስ ፡ ከሰባት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ በዩወገኑ ፡ በዝርዝር ፡ ሲሰናዳ ፡ የኖረው ፡ ድግስን ፡ ድግስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እዩሆነ ፡ የመጨረሻ ፡ መልኩን ፡ መያዝ ፡ ጀመረ ። ዳሱ ፡ መሰራት ፡ እንጀራው ፡ መጋገር ፡ ጠጁና ፡ ጠላው ፡ በዩጋኑ ፡ መሸም ፡ ወጡ ፡ በያይነቱ ፡ መሰራት ፡ ጀመረ ።

እቤት ፡ ከሚሰናዳው ፡ ሌላ ፡ እንደያቅማቸው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ ፍሪዳ ፡ እያረዱ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ካንድ በላይ ፡ እቆልቁጥይ ፡ የሚይዙ ፡ መሆናቸውን ፡ ያስታወቁ ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ ባለቁርጥ ፡ ዘመዶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ ከነጋዴ ፡ ከወባልና ፡ ከጥላትግን ፡ ከጎንቻና ፡ ከሳር ፡ ምድር ፡ ለደስታው ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ የተጠሩ ፡ መኳንንትና ፡ ስማቸው ፡ የታወቀ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እንደያቅማቸው ፡ ፍሪዳ ፡ በግ ፡ ግር ፡ ወይም ፡ ቅቤ ፡ ያልሰጡ ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ። ፊታውራሪ ፡ የራሳቸው ፡ ሀብት ፡ አልበቃቸው ፡ ብሎ ፡ ከዲማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እዩተወደሩ ፡ የገሙትና ፡ ከዩመኳንንቱ ፡ የተላከላቸው ፡ ፍሪዳና ፡ በግ ፡ በዩመንጋው ፡ ታግዶ ፡ ሲታይ ፡ ብዛቱ ፡ የነጋዴን ፡ የጎንቻንና ፡ የሳር ፡ ምድርን ፡ ያወባልንና ፡ የጥላትግን ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡

ሳይሆን ፡ የኒህን ፡ ያምስቱን ፡ አውራጃዎች ፡ ጅብ ፡ ጭምር ፡ የሚመልስ ፡ ነብር ። በዛብህ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ያገኘው ፡ ነጋዴ ፡ እንዳለው ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ “ ሰርጌም ፡ ተዝካሬም ፡ የልጄ ፡ ሰርግ ፡ ነው ፡ ” ስላሉ ፡ እነማይ ፡ በሙሉ ፡ ገልበቱንም ፡ ሀብቱንም ፡ በልግስና ፡ ሰጣቸው ! ደስ ፡ አሰኛቸው !

ዳሱ ፡ በቁመቱ ፡ ይሁን ፡ በወርዱ ፡ ካንዱ ፡ ዳር ፡ ወደሌላው ፡ ፈረስ ፡ አስጋልቦ ፡ ያደክማል ። በውስጡ ፡ የተሰራው ፡ የሳቸውና ፡ የባለቁርጥ ፡ ዘመዶች ፡ እያንዳንዱ ፡ ከመቶ ፡ የማያንስ ፡ ሰው ፡ የሚያስቀምጥ ፡ አቶልቁዋይ ፡ ቁጥሩ ፡ ያስስታል ። የድግሱ ፡ ብዛትና ፡ የመሰናዶው ፡ ማማር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እየሳቀ ፡ እየተጫወተ ፡ እየዘፈነ ፡ በየስራው ፡ የሚጣደፈውን ፡ ሴት ፡ ዘመድ ፡ የቤት ፡ አሽከርና ፡ ያገር ፡ ሰው ፡ እንዲሁ ፡ በጎን ፡ ቆሞ ፡ ለሚመለከት ፡ ሰው ፡ የሚያስገርም ፡ ነው ።

ፊታውራሪ ፡ በሴቶች ፡ በኩል ፡ ላላው ፡ ስራ ፡ ምሽታቸውን ፡ አሾራ ፡ ብለው ፡ ወንዶች ፡ የሚሰሩትን ፡ ስራ ፡ እየዞሩ ፡ ሲጎበኙ ፡ ሰራተኞችን ፡ ሲያበረታቱ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በህይወታቸው ፡ ሙሉ ፡ አድርገውት ፡ የማያውቁትን ፡ ራሳቸው ፡ ካንዱ ፡ ወይም ፡ ከሌላው ፡ እጅ ፡ መሳሪያ ፡ ተቀብለው ፡ ሲሰሩ ፡ የድካም ፡ ምልክት ፡ በጭራሽ ፡ አይታይባቸውም ። ደስታ ፡ ባለበት ፡ ድካም ፡ የለም !

“ተመስገን ፡ ጌታዬ ! እንኩዋን ፡ የልጄን ፡ አዱኛና ፡ አበባ ፡ አሳዩኸኝ ፡ እንኩዋን ፡ የወለዱ ፡ አባቶች ፡ የሚያዩትን ፡ ወግ ፡ ማእርግ ፡ እንዳይ ፡ አደረግኸኝ ፡ እንጂ ፡ ከንግዲህስ ፡ የደረሰ ፡ ቢደርስብኝ ፡ ግዴለኝም ! ” ይላሉ ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ መሰናዶ ፡ ቆም ፡ ብለው ፡ ሲመለከቱና ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በሁዋላ ፡ ሰብለ ፡ ሙሽራ ፡ ሆና ፡ እነማይ ፡ አወባልና ፡ ጥላትማን ፡ ዘፍኖ ፡ መርቆ ፡ ቤት ፡ ዘመድ ፡ ስሞ ፡ የደስታ ፡ ልቅሶ ፡ አልቅሶ ፡ ከዚያ ፡ እስዋና ፡ ባልዋ ፡ ፊታውራሪ ፡ ራሳቸው ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ያስገዙትን ፡ በወርቅ ፡ የተንቀለቀለ ፡ ሽልማት ፡ ተሸልመው ፡ በድግድግመረሻትና ፡ በጥልፍ ፡ እቃ ፡ በተሸለሙ ፡ በቅሎዎች ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ ተቀምጠው ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፡ እልልታው ፡ ሆሆታው ፡ ተኩሱ ፡ ደስታው ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ እልም ፡ ሲታሰባቸው ፡ ልባቸው ፡ በደስታ ፡

ተማሪኮ ፡ እያናቻቸው ፡ እንባ ፡ ያሞሉና ፡-

ከሰርጉ ፡ ቀን ፡ ሳምንት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ለሰራተኞቹና ፡ ለዲማ ፡ ህዝብ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ሰርግ ፡ ነበር ። ከመብልና፡ ከመጠጥ ፡ በሁዋላ ፡ ዘፈን ፡ ይጀመርና ፡ የደከመው ፡ በየቦታው ፡ እስኪወድቅ ፡ እንዲሁ ፡ ሲዘፈን ፡ ያድራል ። ፊታውራሪ ፡ የማያውቁበትን ፡ አመሀል ፡ ገብተው ፡ ሆንጎታቸው ፡ ሲዘፍኑ ፡ ምሽታቸውንም ፡ አዩንተው ፡ ሲያዘፍኑ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ግጥም ፡ ገጠምሁ ፡ ብለው ፡ እንከዋን ፡ ሲገጥሙ ፡ የማይቀራረቡ ፡ ቃሎች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሰብስበው ፡ ሳይዘማሩ ፡ ሲነግሩ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ በሳቅ ያገድሉታል ። ብቻ ፡ ያ ፡ የግጥምን ፡ ደንብ ፡ ያልተከተለና ፡ ቅጡን ፡ ያጣ ፡ ግጥማቸው ፡ ከመጠኑ ፡ አልፎ ፡ ቅጡን ፡ ያጣ ፡ ደስታቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ስለነበረ ፡ ማሳቅ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝም ፡ የሚያሳዝንም ፡ ጭምር ፡ ነበር ።

" የኛ ፡ ሙዚትዋ ፡ ልጅ ፡ ስብለ ፡ ስትዳር ፡-
እናትዋና ፡ እኔ ፡ በህይወታችን ፡ ሳለን ፡-
ባል ፡ አግኝታ ፡ ማን ፡ ይደራታል ፡ ይሆን ፡ ሳትባል ፡ ልጃችን ፡-
ደስታችን ፡ እንደ ፡ ባና ፡ ባዘር ፡ ቢጠልቁት ፡ አያልቅ ፡-
ይህን ፡ ደስታችንን ፡ ማን ፡ መግለጽ ፡ ይችላል ፡-
እኛ ፡ እንግለጽ ፡ እንጂ ፡ ግጥሙ ፡ ቢያምር ፡ ባያምርም ፡-
መቸስ ፡ ሰው ፡ መዝፈኑ ፡ ደስታውን ፡ ሊገልጽ ፡ አይደለምወይ?
ግጥም ፡ ለማሳመርማ ፡ አዝማሪ ፡ አለ ፡ አይደለምወይ !"

"እግዚአብሄር ፡ ትልቅና ፡ ቸር ፡ ጌታ ፡ ነው ። ባንድ ፡ እጁ ፡ ሲቀጣ ፡ በሌላው ፡ ይክሳል ። ጥሩ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ተስፋ ፡ አያስቆርጥም ። እምና ፡ ከደረሰብኝ ፡ መከራ ፡ በሁዋላ ፡ ይህን ፡ ደስታ ፡ ባያመጣልኝ ፡ ኖሮ ፡ ያን ፡ መከራ ፡ የሚያስረሳኝ ፡ ልቤን ፡ ማጽናናት ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ የት ፡ አገኝ ፡ ነበር ? አዎ ፡ እግዚአብሄር ፡ ቢበድልም ፡ መካስ ፡ ያውቃል ! በደሉን ፡ እንርሳና ፡ ስለ ፡ ካሰን ፡ እናመስግነው ፡ ጥሩዬ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ምሽታቸውን ፡ ከሰራም ፡ ከንቅልፍ ፡ ማጣት ፡ ብዛትም ፡ የተነሳ ፡ ደክሞዋቸው ፡ ከሰራተኞች ፡ ትንሽ ፡ ገለል ፡ ብለው ፡ ተቀምጠው ፡ ሲመለከቱ ፡ ለባገኙዋቸው ፡ እሳቸውም ፡ ሄደው ፡ አጠገባቸው ፡ ተቀመጡና

"አዎ ፡ ጌታየ ፡ ምስጋና ፡ ይገባዎል !" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ።

"አዎ ፡ እልማችን ፡ ምኞታችን ፡ ሞላ ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ ጥሩየ !"

"የኛስ ፡ እልማችን ፡ ሞላ ፡ ነገር ፡ ግን ---"

"ነገር ፡ ግን ፡ ምን ?"

"እንዲያው ፡ የሰዋን ፡ ሁኔታ ፡ ስመለከት ፡ በደስታየ ፡ መሀከል ፡ ፍራትና ፡ እዘን ፡ ይሰነቀራል ።"

"ድሮውንስ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ከናት ፡ ካባትዋ ፡ ስትለይ ፡ ደስ ፡ ብሎዋት ፡ ተለይታ ፡ ታውቃለች ? እንቺ ፡ ወደኔ ፡ ስትመጪ ፡ እያለቀስሽ ፡ መምጣትሽን ፡ ረሳሽው !"

"የሰም ፡ የሰዋ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ጌታየ ።"

"ምንም ፡ ልዩ ፡ አይደለም ፡ ቆይ ፡ አሁን ፡ መልስ ፡ ጠርተናት ፡ ስትመጣ ፡ ጭራሽ ፡ ተለውጣ ፡ ደስ ፡ ብሎዋት ፡ ያላገኘሻት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ትይኛለሽ !"

"እስቲ ፡ እንዳፋችዎ ፡ ያርግልን !"

"ይህን ፡ አትጠርጥሪ ፡ ግዴለሽም ። "

"አሁን ፡ ደግሞ ፡ ብሰባታል ፡ ከማልቀስ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ስራ ፡ የላትም ።"

"መለያያው ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ነዋ ! ሌላ ፡ ምን ፡ መሰለሽ!

"እሱም ፡ ይሆናል ፡ ደግሞ ፡ ከሱ ፡ ሌላ ፡ በቀደም ፡ እባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሄዱበት ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ መጥቶ ፡ እብሮዋት ፡ ቆይቶ ፡ ከሄደ ፡ ወዲህ ፡ ጭራሽ ፡ ባሰባት ፡ አሉኝ ።"

"ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ በጭራሽ ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ እንዳይደርስ ፡ አላልሁም ፡ ኖሮዋል ? ለምን ፡ መጣ ?"

"ያነለት ፡ ያሰኘውን ፡ ሰይጣን ፡ እንጃለት ፡ እንጂ ፡ ቤታችንን ፡ እርም ፡ ብሎ ፡ ከተወው ፡ ስንት ፡ ጊዜው ፡ ነው ? ጌታየ !"

"መነኩሴውም ፡ አይረቡም ፡ እባክሽ ! ሰው ፡ ያለቅጥ ፡ መጠጥ ፡ ከወደደ ፡ አይረባም ። በመጠጥ ፡ አባብሎ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄድሁ ፡ እንዲሉ ፡ አድርጎዋቸው ፡ ይሆናል ።"

"እሱስ ፡ አይመስለኝም ፡ ከካሳየ ፡ ጋር ፡ ተስማምተው ፡ ያደረጉት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ያዩትን ፡ ሁሉ ፡ እንዲያ ፡ አገነው

እየነገሩኝም፡ ነበር ።”

“ ምን ፡ አዩሁ ፡ አሉ ?”

“ ከሳምን ፡ በስርቆሽ ፡ በር ፡ ሲወጣ ፡ አዩሁና ፡ እቤት ፡ ብገባ ፡ ሰብለን ፡ ወረቀት ፡ እያነበበች ፡ ስታለቅስ ፡ አገኘሁዋት ፡ አሉ ።”

“የምን ፡ ወረቀት?” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ደንግጠው ።

“ምን ፡ አውቃለሁ? እባ ፡ ተክሌ ፡ ከነገሩኝ ፡ በሁዋላ ፡ ብጠይቃት ፡ የተማርሁትን ፡ እንዳልረሳ ፡ ጽፌ ፡ የማጠናበት ፡ ነው ፡ አለችኝ ።”

“አሳይኝ ፡ አላልሻትም?”

“ብያት ፡ ነበር ፡ ጣልሁት ፡ አለችኝ ።”

“በይ ፡ ተያው ፡ ግድየለም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ማለፊያው ፡ ይደርሳዋል ።” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ ሲያስቡ ፡ ቆይተው ፡ ሲነሱ ።

በጎጃም ፡ ያላገባች ፡ ልጃገረድ ፡ ቆንጆ ፡ የገባች ፡ ሴት ፡ በገኝ ፡ ትባላለች ። የቆንጆና ፡ የበገኝ ፡ መለያ ፡ ከሆኑት ፡ ምልክቶች ፡ አንዱ ፡ መጌጠቂያቸው ፡ ነው ። የበገኞች ፡ መጌጠቂያ ፡ መቀነት ፡ ሲሆን ፡ የቆንጆዎች ፡ መጌጠቂያ ፡ ሚዶ ፡ የሚባል ፡ ጠፍር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የሰርጉ ፡ ዋዜማ ፡ ማታ ፡ ሙሽራዋ ፡ ከቆንጆነት ፡ ኑሮ ፡ ወደ ፡ በገኝነት ፡ ኑሮ ፡ ለመተላለፍ ፡ የምትጀምርበት ፡ በመሆኑ ፡ ሆማም ፡ የሚዶ ፡ መፍቻም ፡ ይባላል ።

በዚያንለት ፡ የተጠራው ፡ ሁሉ ፡ መኳዋንንት ፡ ወይዛዝር ፡ ሽማግሌው ፡ ባልቴቱ ፡ ቆንጆው ፡ ጎረምሳው ፡ ልጁ ፡ የሚዶ ፡ መፍቻ ፡ የሚባለውን ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ከቦ ፡ የሚቀመጠው ፡ ተቀምጦ ፡ የሚቆመው ፡ ቆሞ ፡ ሲጠብቅ ፡ ሙሽራዋ ፡ ሚዶዋን ፡ እንደማይፈታ ፡ አድርጋ ፡ ውሉን ፡ አሳጥታ ፡ ተብትባ ፡ በቆንጃጅቱ ፡ ታጅባ ፡ ትመጣና ፡ ተመልካቹ ፡ በከበበው ፡ ቦታ ፡ ገብታ ፡ ትቀመጣለች ። ከዚያ ፡ ከቆንጃጅቱ ፡ መሀከል ፡ የሙሽራዋን ፡ የተተበተበ ፡ ሚዶ ፡ ለመፍታት ፡ ብርቱዋ ፡ ትመረጥና ፡ እሷዋ ፡ ለመፍታት ፡ ሙሽራዋ ፡ ላለማስፈታት ፡ ትግል ፡ ይጀመራል ። ሙሽራዋና ፡ ሚዶ ፡ ፈቺዋ ፡ ያከመው ፡ እስኪያልባቸው ፡ ሲታገሉ ፡ የከበባቸው ፡ ሰውም ፡ ትግላቸውን ፡ እየተመለከተ ፡ ሲስቅና ፡ ሲያወካ ፡ ብዙ ፡ ቆይቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ሚዶ ፡ ሲፈታ ፡ እዚያ፡

ያለው ፡ ሁሉ ፡ መነኩሴዎች ፡ እንኳዋ ፡ ቢሆኑ ፡ ተነስተው ፡ መዝፈን ፡ አለባቸው ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ሙሽራዋ ፡ ወደምታድርበት ፡ ቦታ ፡ ተመልሳ ፡ እሮ ፡ የሚባል ፡ ቡኮ ፡ መሳይ ፡ ነገር ፡ ተቀብታ ፡ ታድርና ፡ ገና ፡ ሳይነጋ ፡ በሙቅ ፡ ውሀ ፡ ስትታጠብ ፡ የማታምረዋ ፡ እንኳዋ ፡ በጣም ፡ ታምራለች ።

ሰብለ ፡ የባል ፡ ማግቢያዋ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፣ ዘመን ፡ ስለሌለው ፡ ሚርዋን ፡ ታግሎ ፡ አሸንፎ ፡ ለመፍታት ፡ ወንዶች ፡ ካልሆኑ ፡ እንኩዋንስ ፡ ከቆነጃጅቱ ፡ መሀከል ፡ ከበገኞች ፡ መሀከልም ፡ የሚችል ፡ መኖሩ ፡ ያጠራጥር ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እንደልማዱ ፡ በቆነጃጅቱ ፡ ታጅባ ፡ መጥታ ፡ ስትቀመጥ ፡ ሚር ፡ ፈቺ ፡ ሆና ፡ የተመረጠችውን ፡ እስኪያዩ ፡ ድረስ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አይኑንም ፡ አፉንም ፡ በሰፊው ፡ ከፍቶ ፡ በናፍቆት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ አንዲት ፡ ካስራ ፡ ሶስት ፡ አመት ፡ በላይ ፡ የማትሆን ፡ ልጅ ፡ ከቆነጃጅቱ ፡ መሀከል ፡ ተለይታ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ ስትሄድ ፡ የሁለቱን ፡ ልዩነት ፡ አይቶ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሁሉ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ በሳቅ ፡ አወካ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሙሽራዋ ፡ ለሰው ፡ ይምሰል ፡ ያክል ፡ ትንሽ ፡ ስታስቸግር ፡ እንደ ፡ ቆዬች ፡ ሚር ፡ ፈቺዋ ፡ ሚሩን ፡ ከሰብለ ፡ ወገብ ፡ መዘዝ ፡ አድርጋ ፡ ስትነሳ ፡ እልልታው ፡ ጡኩታው ፡ ከዚያ ፡ ዘፈኑ ፡ ተጀመረ ። ሰብለ ፡ እንደልማዱ ፡ ዘፈኑን ፡ ባርካ ፡ ሌላው ፡ ሲዘፍን ፡ እሮ ፡ ልትቀባ ፡ ወደልፍኝዋ ፡ ሄደች ። አባትና ፡ እናትዋ ፡ የዘፈን ፡ መሪዎች ፡ ሆኑ ።

ሙሽራዋን ፡ አጅበው ፡ የተመለሱት ፡ ቆነጃጅት ፡ ከወንዶች ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እዘፈኑ ፡ ውስጥ ፡ መገፋፋቱ ፡ መረጋገጡ ፡ መቆነጣጠጡ ፡ መሽኮርመሙ ፡ አብሮ ፡ መዝፈኑ ፡ አመሰጠን ፡ ብለው ፡ ሙሽራ ፡ አጃቢ ፡ በመሆናቸው ፡ ማዘናቸው ፡ ከፊታቸው ፡ ይታይ ፡ ነበር ። ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ተገናኝተው ፡ ያለ ፡ ተቆጪ ፡ ያለቀጪ ፡ ንጹህ ፡ የድንግልና ፡ ፍቅራቸውን ፡ የሚለዋወጡበት ፡ ሰርግ ፡ ወይም ፡ አመትባል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቻ ፡ የሚገኘው ፡ አጋጣሚ ፡ ሲያመልጥ ፡ እውነትም ፡ ያሳዝናል ።

"ልጆች ፡ ወደ ፡ ጨዋታው ፡ ሂዱ ፡" አለች ፡ ሰብለ ፡ ሁኔታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ተመለከተችና ።

"እሮውንስ ፡ ማን ፡ ይቀባሻል?" አለች ፡ ማር ፡ ፈትዋ ።

"ግዴለም ፡ ሀብትሽ ፡ ትቀባኛለች ።" አለችና ፡ ሰብለ ፡ ቀንጃጅቱ ፡ እዬሮጡ ፡ ሲወጡ ፡ ወደ ፡ ሀብትሽ ፡ ዘወር ፡ ብትል ፡ ሀብትሽ ፡ በበኩልዋ ፡ አኩርፋ ፡ ከንፈርዋን ፡ አስረዝማ ፡ አዬቻት።

"ሀብትሽ ፡ ላባቴና ፡ ለኔ ፡ ራታችንን ፡ አምጥልንና ፡ አንችም ፡ ወደ ፡ ጨዋታው ፡ ሂጂ ።"

"እሮውንስ?"

"ግዴለም ፡ እኔ ፡ እቀባዋለሁ ። ፊቴን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሌላ አካላቴን ፡ አልቀባም ። ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡ በጣም ፡ ሳይነጋ ፡ ሙቅ ፡ ውሀና ፡ ልጃችን ፡ ይዘሽ ፡ መጥተሽ ፡ እንድታጥቢኝና ፡ ልብሴን ፡ እንድታለብሱኝ ! እደራሽ ፡ ስታገቢዱ ፡ እድራችሁ ፡ ጥዋት ፡ እንቅልፍ ፡ እንዳያሸንፋችሁና ፡ እሮ ፡ እሽከማችሁ ፡ እንዳ ታስረፍዱኝ !"

"ግዴለሽም ፡ ለሱ ፡ አታስቢ!" አለችና ፡ ሀብትሽ ፡ ራት ፡ ለማምጣት ፡ መሮጥ ፡ ስትጀምር ።

"ለእስ ፡ ራት ፡ ቀርቶብኝ ፡ የምጠጣው ፡ ባገኘሁ!" አሉ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ።

"መጠጣት ፡ ከቻሉ ፡ ጠጅ ፡ በገምቦ ፡ ሞልቶ ፡ መጥቶልዎታል ።" አለች ፡ ሰብለ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ።

"አረቄስ?"

"አ! አረቄውን ፡ ሳስብ ፡ ቆይቼ ፡ ረሳሁት ፡ አንድ ፡ ጠርሙስ ፡ አረቂ ፡ ጨምረሽ ፡ አምጪ ፡ ሀብትሽ ።"

ሀብትሽ ፡ ሮጣ ፡ ራት ፡ እስክታመጣ ፡ ድረስ ፡ አባ ፡ ተክለ ሀይማኖት ፡ ሁለት ፡ ብርሌ ፡ ጠጅ ፡ ጠጥተው ፡ ሶስተኛውን ፡ ይዘው ፡ ነበር ። ራት ፡ በልተው ፡ እስኪጨርሱ ፡ ስድስት ፡ ብርሌ ፡ ጠጅና ፡ ዘትልቅ ፡ መለኪያ ፡ ሶስት ፡ አረቂ ፡ ጠጥተው ፡ ስከሩና ፡ ተነስተው ፡ ደበሎዋቸውን ፡ እንደለበሱ ፡ ይዘፍኑ ፡ ጀመር ።

"ደበ-ደበበበ-- ሎየየየን ፡ ላውል—ቀው ?"

" የሌም ፡ ከነደበሎም ፡ ሲዘፍኑ ፡ ነው ፡ ጥሩ ፡"

" ጥሩ ---ነኝ ?"

“ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡”

“ እ---ነቾ ---ኛሽ ፡ ጥ----ሩ ።”

“እሺ ፡”

“አ---ንቺ ፡ ነሽ ፡----ጥ---ሩ ፡ ብቻ---ብ---ቻ ፡ ምን ፡ ይሆና---ል !”

“ ግዴለም ፡ ይቀመጡና ፡ ይጠጡ ፡ አረቄ ፡ ይጠጡ ።”

“ እሺ ፡---የኔ ፡ እመ---ቤቤቤ---ት ፡” አሉና ፡ አዛ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ጠርሙሱን ፡ አንስተው ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ ግጥም ፡ አድርገው ፡ ጠጥተው ፡ ሲያንገሙሱ ፡ ስብለ ፡ በጉድ ፡ ታግላ ፡ ቀማቻቸው ። ደም ፡ ሆኖ ፡ አይኖቻቸው ፡ ፍጥጥ ፡ ብለው ፡ ሰውነታቸው ፡ ሁሉ ፡ በላብ ፡ ተንከሮ ፡ ወደቁ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ጅብ ፡ ቢቀራመታቸው ፡ በጭራሽ ፡ አይሰማቸውም ።

ዘፈኑ ፡ እንዲሁ ፡ አደረ ። የጠማው ፡ በዱቦታው ፡ ከተቀመጠው ፡ ጠላ ፡ ይሁን ፡ ጠጅ ፡ እየጠለቀ ፡ እየጠጣ ፡ የደከመው ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ በተገኘበት ፡ ሁሉ ፡ ትንሽ ፡ ሸልብ ፡ ብሎ ፡ ለማረፍ ፡ ሲወድቅ ፡ አርፎ ፡ የቆየው ፡ እየተተካ ፡ ሰው ፡ ይለዋወጣል ፡ ዘፈኑ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ሳይቋረጥ ፡ እንዲሁ ፡ አደረ ። ጠላቶቻቸው ፡ የማይጠጡ ፡ ደካሞቻቸው ፡ የማያርፉ ፡ እየጠጡና ፡ እያረፉ ፡ ከሚመለሰው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ሲዘፍኑ ፡ ያደሩ ፡ የሚፈራረቅባቸውን ፡ ሁሉ ፡ ያሸንፉ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ከመንጋቱ ፡ በፊት ፡ ሀብትሽ ፡ እመቤትዋ ፡ እንደ ፡ ነገረቻት ፡ ውሀዋን ፡ አሙቃ ፡ ማር ፡ ፈችዋንና ፡ የሙሽራዋ ፡ ደንጊጥር ፡ እንዲሆኑ ፡ የተመረጡትን ፡ ቆንጆጆች ፡ ከያሉበት ፡ እየፈለገች ፡ ሰብስባ ፡ ሰብለን ፡ አጥበው ፡ ልብስ ፡ ለማልበስ ፡ እየዘፈኑ ፡ ሄዱ ። ከዚያ ፡ እንደ ፡ ወጉ ፡ አበር ፡ ቆመው ፡ ትንሽ ፡ ዘፈኑና ፡ ሙሽራዋ ፡ በሩን ፡ ዘግታ ፡ አላስገባም ፡ ማለትና ፡ መታገል ፡ የተለመደ ፡ ስለ ሆነ ፡ ብርቱ ፡ ትግል ፡ ይገጥመናል ፡ ብለው ፡ አስበው ፡ ሀይላቸውን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አድርገው ፡ የተዘጋውን ፡ በር ፡ ለመግፋት ፡ ሲሰናዱ ፡ ያንደኛዋ ፡ እጅ ፡ ተሰስቶ ፡ ትንሽ ፡ ነካ ፡ ቢያደርገው ተከፈተ ።

“ ደካሞዋት ፡ ሳትዘጋው ፡ ተኝታለች !” አለች ፡ ሀብትሽ።

" ታዲያ ፡ አበሮ ፡ ቆመን ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ስንዘፍን ፡ ተን ስታ ፡ ያልዘጋችው ፡ እንዴት ፡ ነው ? " አለች ፡ ሚሪ ፡ ፊትዋ ።

" ተንቀልፍታ ፡ ብትስማ ፡ ነው ። ቆይ ፡ መብራት ፡ ላብራ ። አለችና ፡ ሀብትሽ ፡ ጡዋፍ ፡ አበራች ። ሰብለን ፡ ሊመ ቀስቀስ ፡ ወዳልጋዋ ፡ ቀስ ፡ እያለች ፡ ስትሄድ ፡

" የለም ፡ አትቀስቅሻት ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ እንዝፈንና ፡ ሰምታ ፡ በገዛ ፡ እጅዋ ፡ ትነሳ ። " አለች ፡ ሚሪ ፡ ፊትዋ ።

ከዚያ ፡ ቆንጃጅቱ ፡ ይዘፍኑ ፡ ጀመር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ እስኪደክማቸው ፡ ቢዘፍኑ ፡ ሰብለ ፡ ዘፈኑን ፡ ሰምታ ፡ አል ተነሳችም ።

" ሂጂና ፡ ኩታዋን ፡ ከላይዋ ፡ ግፈፊያት ! " አለች ፡ ሚሪ ፡ ፊትዋ ፡ የመጀመሪያ ፡ አሳብዋ ፡ ከንቱ ፡ እንደሆን ፡ አይታ ። ከዚያ ፡ ሀብትሽ ፡ የጡዋፉ ፡ መብራትዋን ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ አልጋ ፡ ቀረብ ፡ አለችና ፡ ከራስጌ ፡ ወገን ፡ ኩታ ውን ፡ ብድግ ፡ ከማድረግዋ ፡ ድንገት ፡ እንደ ፡ ተወጋች ፡ ሁሉ ፡ ዋዋይ ! ብላ ፡ ጩሀ ፡ ወደ ፡ ሁዋላዋ ፡ ስትመለስ ፡ ቆን ጃጅቱ ፡ ሁሉ ፡ እየሮጡ ፡ ወዳልጋው ፡ ሄደው ፡ ቢያዩ ፡ እሮ ፡ በተቀባች ፡ ሙሽራ ፡ ፈንታ ፡ በዋኪ ፡ የተጨማለቁ ፡ መነ ኩሴ ፡ አገኙ ! በሰብለ ፡ ፈንታ ፡ አልጋዋ ፡ ላይ ፡ የተኙት ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ነበሩ ። በዋኪያቸው ፡ ተጨማልቀው ፡ ኩታ ፡ ተከናንበው ፡ ተኝተዋል ። እንኩዋን ፡ እጠገባቸው ፡ መዝፈን ፡ በጆሮ ፡ ቢደበድቡዋቸው ፡ አይሰሙም ።

እንዴት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ነው ? ምን ፡ ጉድ ፡ ነው ? ቅዠት ፡ ነው ? ወይስ ፡ ሰብለን ፡ ወዳባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ የሚለውጥ ፡ ታምር ፡ ተሰራ ? እዚያ ፡ የሰብለን ፡ አልጋ ፡ ከበው ፡ የቆሙ ፡ ቆንጃጅት ፡ ሁሉ ፡ በየራሳቸው ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ መንጋ ፡ አሳብ ፡ እየታመሰ ፡ የሚያዩት ፡ ጠፍቶዋቸው ፡ ሳይናገሩ ፡ ፍዝዝ ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ቆዩ ። ሁሉም ፡ አይናቸውን ፡ እንደ ፡ ጠረጠሩት ፡ ሁሉ ፡ ያሻሹና ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ የተኛውን ፡ ሰው ፡ ሲያዩ ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ያው ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ናቸው !

" እንዴት ፡ ነው ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ የምናየው ? " አለች ፡

ሚር ፡ ፈትዋ ።

" ምን ፡ እናርግ ? " አለች ፡ ሌላዋ ፡

" ሀብትሽ ፡ ሂጂና ፡ ለመይሳ ፡ ንገሪ ፡"

" የለም ፡ መጀመሪያ ፡ እያንዳንዳችን ፡ በሚዘፈንበትም ፡ ስራ ፡ ዘሚሰራበትም ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ እንፈልጋትና ፡ ቶሎ ፡ ተመልሰን ፡ እዚህ ፡ እንሰብሰብ ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ አለመኖርዋን ፡ አረጋግጥ ፡ ስናውቅ ፡ ሂጂ ፡ ላጋፋሪ ፡ መሰረት ፡ እንነግራለሁ ። " አለች ፡ ዘብትሽ ።

ከዚያ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የሚፈልጓትን ፡ ቦታ ፡ ተከፋፍለው ፡ ሁሉም ፡ እየሮጡ ፡ ተበተኑ ። እንኳዋን ፡ ስራ ፡ የሚሰራበትና ፡ የሚዘፈንበት ፡ ቦታ ፡ ከጥር ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ትንንሽ ፡ ስርቻ ፡ አልቀሩትም ። ከጥር ፡ ጊዜ ፡ በሁዋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተሰበሰቡ ። አላገኙዋትም ! ስብለ ፡ የለችም ! ለጋፋሪ ፡ መሰረት ፡ የደረሰውን ፡ ጉድ ፡ ሀብትሽ ፡ ስትነግረው ፡ የሰከረች ፡ መስሎት ፡ ተቆጣ ።

" ይቺ ፡ እዚያ ፡ በልኩ ፡ አትጠጣም ፡ ኖሮዋል ? " አለ ።

" እውነትዋን ፡ ነው ፡ አልሰከረችም ፡ ይምጡና ፡ ይዩ ፡ ይምጡና ፡ ይዩ ። " አሉ ፡ ሌሎች ፡ ልጆች ፡ እየተቀባበሉ ። ከዚያ ፡ እግሩ ፡ የሚቆምበትን ፡ ሳያውቅ ፡ እየሮጠ ፡ እሰብለ ፡ አልፋኝ ፡ ቢገባ ፡ እውነትም ፡ ሀብትሽ ፡ የተናገረችውን ፡ ሰክራ ፡ ያልተናገረች ፡ መሆንዋን ፡ ተረዳ ። ሙሽሪዋ ፡ መጥፋትዋን ፡ ዘሙሽሪዋ ፡ ቦታ ፡ ተተክተው ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የሚዘፈንላቸው ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የሚደገስላቸው ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ መሆናቸውን ፡ አዩ ! ጠገቡ ፡ በሰይፍ ፡ እንደ ፡ ተመታ ፡ ለሁለት ፡ የተከፈለ ፡ መስሎ ፡ ተሰማው ፡ አካሉን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ያስተሳሰረው ፡ ማሰሪያ ፡ እንደ ፡ ተፈታ ፡ ሁሉ ፡ ሰውነቱ ፡ በሙሉ ፡ እየተለያዩ ፡ የወደቀ ፡ መሰለ ፡ ተሰማው ! ትንሽ ፡ ራሱን ፡ ደፋ ፡ አይኖቹን ፡ ለበሰ ፡ አድርጎ ፡ ቆይቶ ፡ ድንጋጤው ፡ እያለፈ ፡ አሳቡን ፡ መግዛት ፡ ሲጀምር ፡ የጌታው ፡ የመቤቱ ፡ ሁኔታ ፡ ታየው ! በዚያ ፡ ደስታቸው ፡ መሀከል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መከራ ፡ ሲደርስባቸው ፡ የሚሆኑት ፡ ታየው ! በዚያ ፡ ደስታ ፡ መሀከል ፡ ይህን ፡ መከራ ፡ መንገር ፡

ከጭካኔ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ጭካኔ ፡ ነው ! በዚያ ፡ ደስታ ፡ መሀከል ፡ ይህን ፡ መከራ ፡ መንገር ፡ መንግስቱ ፡ ሰማያትን ፡ አሳይቶ ፡ እገሀነም ፡ ውስጥ ፡ ከመጣል ፡ የከፋ ፡ ነው ! መግደል ፡ አይሻልም ? እንዲያ ፡ ደስ ፡ እንዳላቸው ፡ ይህን ፡ መከራ ፡ ሳይሰሙ ፡ በሚዘፍኑበት ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ባንዳንድ ፡ ጥይት ፡ የሚያሳርፋቸው ፡ ዘመድ ፡ ቢያገኙ ፡ የውነተኛ ፡ ዘመድ ፡ ከልብ ፡ የሚወዳቸው ፡ ርህሩህ ፡ ዘመድ ፡ ማለት ፡ እንዲያ ፡ ያለው ፡ ዘመድ ፡ ነው ! አጋፋሪ ፡ መሰረት ፡ እጅግ ፡ ተጨነቀ ። መከራን ፡ ከማርዳት ፡ መረዳት ፡ ቀላል ፡ ነው !

በመጨረሻ ፡ አጋፋሪ ፡ መሰረት ፡ ዘቀጥታ ፡ ስፊታውራሪና ፡ ለወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ እይነት ፡ መንገሩን ፡ ፈርቶ ፡ አባ ፡ ሞገሴን ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉን ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩንና ፡ አዛዥ ፡ ደስታን ፡ ከያሉበት ፡ እዩጠራ ፡ እሙጭ ፡ ራቅ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሰብስቦ ፡ ሲነግራቸው ፡ ሁሉም ፡ በዝምድናቸው ፡ ከተሰማቸው ፡ እዘን ፡ በላይ ፡ የፊታውራሪና ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ እዩታሰባቸው ፡ ምርር ፡ ብለው ፡ አለቀሱ ። ፊታውራሪና ፡ ምሽታቸው ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ተጠርተው ፡ መከራውን ፡ ሲረዱ ፡ ፊታውራሪ ፡ እንደ ፡ ታረደ ፡ በሬ ፡ ጉዋጉረው ፡ ወድቀው ፡ ውሀ ፡ አምጥተው ፡ ካፈሰሱባቸው ፡ በሁዋላ ፡ ነፍስ ፡ እስቲዘራባቸው ፡ ድረስ ፡ በድን ፡ ሆነው ፡ ብዙ ፡ ቆዩ ። ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ቀሚሳቸውን ፡ ከደረታቸውም ፡ ከጀርባቸውም ፡ ቀደው ፡ ፊታቸውን ፡ ሙልጭ ፡ አድርገው ፡ ፈጅተው ፡ እዩተንከባለሉ ፡ ሲጮሁ ፡ ያን ፡ ከሀር ፡ የለሰለሰ ፡ ገላቸውን ፡ ደረቅ ፡ አፈርና ፡ ሳር ፡ ሾህና ፡ ጋሬጣ ፡ እዩቦጨቀ ፡ ሲያስቀረው ፡ ማየት ፡ ብቻ ፡ ያስቅቅ ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ተነስተው ፡ ኩታቸውን ፡ ሳይደርቡ ፡ እንዲሁ ፡ እንጠልጥለው ፡ በሁዋላቸው ፡ እዩጎተቱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፍግም ፡ ቀና ፡ እያሉ ፡ ሲሮጡ ፡ ወንድማቸው ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ተከተሉዋቸው ። ፊታውራሪ ፡ ነፍሳቸውን ፡ አውቀው ፡ ቅርብ ፡ ዘመድ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ መንገዱን ፡ ተከፋፍሎ ፡ በፈረስ ፡ ሰብለን ፡ ፍለጋ ፡ መሄዱን ፡ ሲሰሙ ፡ እሳቸውም ፡ በበኩላቸው ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ዋጋየን ፡ አስከትለው ፡ የቢቸናን ፡ መንገድ ፡ ተከትለው ፡ ጋለቡ ። ሲጋልቡ ፡ እንዲሁ ፡ ግብናቸውን ፡

ይጋልባሉ ፡ እንጂ ፡ እፈረስ ፡ ላይ ፡ መሆናቸውን ፡ ወዴት እንደሚሄዱ ፡ ምን ፡ እንደሚፈልጉ ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እግራቸው ፡ ርካብ ፡ ለቆ ፡ ብቻውን ፡ ሲወናጨፍ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ዛብ ፡ ለቀው ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ሲነጩ ፡ ዋጋየ ፡ ከሁዋላቸው ፡ እየጋለበ ፡ ይወድቃሉ ፡ ብሎ ፡ በፍራት ፡ ይጨነቅ ፡ ነበር ። አቀበትና ፡ ቁልቁለት ፡ ላይ ፡ ዛብ ፡ ሰብስቦ ፡ አድርጎ ፡ መያዝ ፡ ርካብ ፡ ተጠንቅቆ ፡ መርገጥ ፡ የግልቢያን ፡ ፍጥነት ፡ ትንሽ ፡ መቀነስ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑ ፡ ባሳባቸው ፡ ጭራሽ ፡ አልመጣም ። አቀበቱም ፡ ቁልቁለቱም ፡ ሁሉም ፡ ከሜዳው ፡ ጋር ፡ ሜዳ ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉ ፡ ሁሉንም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሽምጥ ፡ እየጋለቡ ፡ ፈረስ ፡ ሜዳን ፡ አልፈው ፡ ከቢቸና ፡ ወገን ፡ አንድ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ደረሱ ። ወንዙ ፡ በክረምት ፡ ውሀ ፡ ይሞላል ። በበጋ ፡ ግን ፡ ከው ፡ ብሎ ፡ ደርቆ ፡ ክረምት ፡ ክረምት ፡ ውሀ ፡ የሚሄድበት ፡ መሆኑን ፡ ከሚያስታውስ ፡ ጥቁር ፡ አሸዋና ፡ አለት ፡ ድንጋይ ፡ በቀር ፡ የውሀ ፡ ምልክት ፡ አይታይበትም ። ገና ፡ እወንዙ ፡ ሳይደረስ ፡ መንገዱ ፡ በሁለት ፡ ይከፈልና ፡ አንዱ ፡ ባለከብቶች ፡ ወደሚሻገሩበት ፡ ሁለተኛው ፡ ገደልነት ፡ ቢኖረውም ፡ አቋራጭ ፡ በመሆኑ ፡ እግረኞች ፡ ወደሚሻገሩበት ፡ ያመራሉ ። እዚያ ፡ መንገዱ ፡ መንታ ፡ በሚሆንበት ፡ ላይ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባለከብት ፡ የሚሻገርበትን ፡ ትተው ፡ የግረኞችን ፡ መንገድ ፡ ሲይዙ ፡–

"ላዩን ፡ ጌቶች ፡ እሱ ፡ ገደል ፡ ነው ። ገደል ፡ ገደል ፡ ገደል !" ብሎ ፡ ጮኸ ፡ ዋጋየ ፡ ሁዋልሁዋላቸውን ፡ እየጋለበ ።

ፊታውራሪ ፡ እገደሉ ፡ አፋፍ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ የዋጋየን ፡ ጩኸት ፡ ሲሰሙ ፡ ፈረሱን ፡ በሀይል ፡ በዛብ ፡ መትተው ፡ ለማቆም ፡ ቻሉ ! እሳቸውን ፡ ግን ፡ እፈረሱ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ለማስቀረት ፡ የሚችል ፡ ሀይል ፡ አልነበረም ! ፈረሱ ፡ ድንገት ፡ ሲቆም ፡ እሳቸው ፡ ሲጋልቡ ፡ በመጡበት ፡ ፍጥነት ፡ ከኮርቻው ፡ ላይ ፡ ተወርውረው ፡ ክረምት ፡ ውሀ ፡ በሚሄድበት ፡ አለት ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አረፉ ። የደረሰባቸውን ፡ መከራ ፡ በቅጡ ፡ ሳይሰሙ ፡ አረፉ ! አሳባቸውን ፡ አጠቃለው ፡ በጥሞና ፡ ተቀምጠው ፡ በሚወዱዋት ፡ ልጃቸው ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ መጥፎ ፡

ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያባት ፡ እንጀራቸውን ሳይርደው ፡ ልባቸውን ፡ ሳይቀጥለው ፡ ራሳቸውን ፡ ሳይበዘብዘው ፡ ልጄ ፡ እንዴት ፡ አውሬ ፡ በላሽ ? ገደል ፡ ወደቅሽ ? አፋኝ ፡ ሸጠሽ ? እያሉ ፡ ሳያምጡ ፡ ሳይጨነቁ ፡ አረፉ ! በሳቸው ፡ የደረሰው ፡ ጉድ ፡ ደርሶ ፡ ለማያውቅ ፡ ጉድ ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ ዘመን ፡ ሳይሽረው ፡ ርቀት ፡ ሳይወስነው ፡ ሁልጊዜ ፡ በየትም ፡ ሲተረክ ፡ የሚኖር ፡ በህይወት ፡ መቀበርን ፡ የሚያስመርር ፡ መሆኑ ፡ በሙሉ ፡ ከብደቱ ፡ ሳይሰማቸው ፡ አረፉ ! ጥሩ ፡ እረፍት ፡ ነው !

ዋጋዩ ፡ የፊታውራሪን ፡ ሬሳ ፡ በፈረስ ፡ ጭኖ ፡ እያለቀሰ ፡ እቤታቸው ፡ ሲደርስ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የዘፈን ፡ የውካታ ፡ የደስታ ፡ ቤት ፡ የነበረው ፡ ያዘን ፡ ቤት ፡ ዞኖ ፡ ቆየው ።

ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይናት ፡ ከቤታቸው ፡ እያለቀሱ ፡ የሚቀመጡበትን ፡ ሳይስተውሉ ፡ ሮጠው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ሄዱ ፡- እዬሮጡ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ደረጃ ፡ ወጥተው ፡ ሲጨርሱ ፡ አፈንግጠው ፡ በቆዩ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ቁመና ፡ ተገልብጠ ፡ ጣላቸው ። ከዚያ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩም ፡ ደንግጠው ፡ ይዞ ፡ ለማንሳት ፡ ሳይችሉ ፡ ቀርተው ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ዘቅዝቀው ፡ ሲንከባለሉ ፡ የላይኛው ፡ ደረጃ ፡ እየነጠረ ፡ ለታችኛው ፡ እያቀበለ ፡ አስራ ፡ ሁለቱ ፡ ደረጃ ፡ በሙሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እንዳሴረባቸው ፡ ሁሉ ፡ ደብድቦ ፡ እታች ፡ ጣላቸው ። ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ ሲያነሱዋቸው ፡ ነፍሳቸውን ፡ አያውቁትም ። ካንድ ፡ ወገን ፡ ሁለት ፡ ጎድን ፡ አጥንቶቻቸውና ፡ ቀኝ ፡ ክንዳቸው ፡ ድቅቅ ፡ ብለው ፡ ተሰብረው ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ ባላምባራስ ፡ ጮኸው ፡ ረዳት ፡ ሲደርስላቸው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ወሰዱዋቸው ። ዘመዱም ፡ እንግዳውም ፡ በዚህ ፡ እዘን ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ነው ፡ የፊታውራሪ ፡ ሬሳ ፡ የደረሰ ። ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ነፍሳቸውን ፡ ሳያውቁ ፡ ብዙ ፡ ቆይተው ፡ እግዚአብሄር ፡ የባላቸውን ፡ ሞት ፡ ለማሰማት ፡ አብረው ፡ እንደ ፡ ኖሩ ፡ አብረው ፡ የሚሄዱ ፡ የማይለያዩ ፡ መሆናቸውን ፡ እንዲያውቁ ፡ ለማድረግ ፡ እንደ ፡ ፈለገ ፡ ሁሉ ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ ዘርቶባቸው ፡ ሰሙ ። ወዲያው ፡ ደስ ፡ እንዳላቸው ፡ ለመሳቅ ፡ እንደ ፡ ሞከሩ ፡ ሁሉ ፡ በህይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ አይናቸውን ፡

ትንሽ ፡ ወደጎን ፡ ትኩር ፡ አሉባቸውን ፡ ትንሽ ፡ ፍርፃም ፡ አድር ገው ፡ አረፉ !

ሙሽራው ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ድንበሩ ፡ በፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ የደረሰውን ፡ መከራ ፡ ሳይሰሙ ፡ እንደሳቸው ፡ ያሉ ፡ ጌታና ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ሊያስከትለው ፡ የሚችለውን ፡ ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የሌለው ፡ ሰርገኛ ፡ አስከትለው ፡ እምቢልታ ፡ ጥሩምባና ፡ መለከት ፡ እየተወዳደረ ፡ እያጫወታቸው ፡ ያለ ፉበት ፡ መንደር ፡ ሁሉ ፡ በልልታ ፡ እየተቀባበላቸው ፡ ከገ ራቸው ፡ ተጉዘው ፡ እቀትር ፡ ላይ ፡ ዲማ ፡ ገቡ ። እዚያ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ በሰርገኛ ፡ ወግ ፡ ከሙሽራዋ ፡ ወላጆችና ፡ ዘመዶች ፡ ወገን ፡ ሽማግሎች ፡ ተልከው ፡ እስኪጠሩዋቸው ፡ ከከተማው ፡ ውጭ ፡ የጠራ ፡ ሜዳ ፡ ፈልገው ፡ የሳቢሳ ፡ ሰራዊት ፡ መስለው ፡ ሰፈሩ ።

ሰርገኛው ፡ በሰፈረበት ፡ ቦታ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ጠበቀ ፡ እውነትም ፡ ከሙሽራዋ ፡ ወላጆችና ፡ ዘመዶች ፡ ወገን ፡ ሽማ ግሎች ፡ ተመርጠው ፡ ለመጥራት ፡ ሄዱ ። ብቻ ፡ ወደ ፡ ሙሽ ራዋ ፡ ወላጆች ፡ ቤት ፡ አይደለም ። ወደ ፡ መቃብራቸው ! ወደ ፡ ዘፈኑ ፡ አይደለም ። ወደ ፡ ልቅሶው !

ሙሽራው ፡ ሰርገኞቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ እቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ሲደርሱ ፡ የሙሽራዋ ፡ ወላጆች ፡ ለሰርግ ፡ የጠሩት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጧት ፡ ክርስቲያኑን ፡ ቅጽር ፡ ሞልቶ ፡ የፊታው ራሪ ፡ መሸሻንና ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩን ፡ ሬሳ ፡ ከቦ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ።

"እያደረስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ያለን ፡ ጉድ ፡-
ሰው ፡ ሲዘፍን ፡ መጥቶ ፡ አልቅሶ ፡ መሄድ ፡-
መሸሻና ፡ ጥሩ ፡ መካን ፡ ሆኑ ፡ ብሎ ፡ ዘመድ ፡ ሲያዝንላቸው ፡-
ሴት ፡ ልጅ ፡ ወለዱና ፡ ሆነች ፡ መጠሪያቸው ፡-
ያልታደሉ ፡ ናቸው ፡ መሸሻና ጥሩ ፡-
ወንድ ፡ ልጅ ፡ አጡና ፡ በሴት ፡ ልጅ ፡ ተጠሩ ፡-
መሸሻና ፡ ጥሩ ፡ የማያውቁበትን ፡ ሰዎች ሲሉ ፡ ሰምተው ፡-
ሰው ፡ ያደረገውን ፡ ማድረግ ፡ ተመኝተው ፡-
ሰርግ ፡ ብለው ፡ ብለው ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ጠርተው ፡-

እንግዳው ፡ ሲመጣ ፡ ሲሰበሰብ ፡ አይተው ፡
ተዩይዘው ፡ ጠፉ ፡ ቤታቸውን ፡ ዘግተው ፡-"

የመቃብሩ ፡ ስነስራት ፡ ተፈጽሞ ፡ ዘመድ ፡ እያዘነ ፡ ሌላው ፡ እዩተገረመ ፡ ሲመለስ ፡-

" ነፍስ ፡ ካወቅሁበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሄር ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ሲፈርድ ፡ ያዩሁ ፡ ዛሬ ፡ ብቻ ፡ ነው ! " አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡-

" እንዴት ? "

" እኒህን ፡ ሁለት ፡ አጥፊዎች ፡ እንዲህ ፡ በገሀድ ፡ በገሃዱ ፡ ማጥፋቱ ፡ እንዲህ ፡ በግልጽ ፡ መቅጣቱ ፡ ጥሩ ፡ ፍርድ ፡ ነው ! ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ማጥፋቱ ፡ ላይቀር ፡ ንጹሀዋን ፡ እሁቱን ፡ ሳያጠፋ ፡ ቢያጠፋቸው ፡ ይሀና ፡ ነበር !"

" አባክህ ፡ ዝም ፡ በል ፡ የሰማ ፡ ጉድ ፡ ይላል ! "

" የተናገርሁትስ ፡ ከደረሰው ፡ ጉድ ፡ የበለጠ ፡ ጉድ ፡ የሚያሰኝ ፡ አይደለም ። ይልቅ ፡ ሊደርስ ፡ የነበረ ፡ ሌላ ፡ ጉድ ፡ ልንገርዎ ። "

" ምን ? "

" ሰብለን ፡ እንቅበራት ፡ እንጂ ፡ መቸም ፡ ሞታ ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ እስዋ ፡ ሞታ ፡ እነሱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እን ኩዋ ፡ በህይወታቸው ፡ ውለው ፡ እንዳያድሩ ፡ ምኞ ፡ ነበር ! እግዚአብሄር ፡ ቀደመኝ ፡ እንጂ ፡ ዛሬውኑ ፡ ሁለቱንም ፡ እኔ ፡ እገድላቸው ፡ ነበር ! "

# ምእራፍ ፡ ፴፪ ፡

## አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡

አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ሁለት ፡ ሌሊትና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጦማቸውን ፡ ሚካለሚካ ፡ ሲጉዋዙ ፡ ደከመው ፡ ከንቅልፍና ፡ ከራብ ፡ ሌላ ፡ እንቅፋት ፡ ከመታቸውና ፡ ሾህ ፡ ከወጋቸው ፡ እግሮቻቸው ፡ የሚጎርፈው ፡ ደም ፡ ከስቃዩ ፡ ጋር ፡ አላስሄዳቸው ፡ ስላለ ፡ ሾህ ፡ ለማውጣትና ፡ የግሮቻቸውን ፡ ቁስል ፡ ለማሰር ፡ መቀመጥ ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ። ስለዚህ ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ ሲደርሱ ፡ መንገዱን ፡ ትተው ፡ ወንዙዋን ፡ ተከትለው ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ሄዱ ፡ ያባይ ፡ በርሀ ፡ የሲኦልን ፡ ግርማ ፡ ተጎናጥፎ ፡ እስሩ ፡ ያባይ ፡ ወንዝ ፡ ያናቱና ፡ የጅራቱ ፡ መጨረሻ ፡ እንደማይታይ ፡ ዘንዶ ፡ ተጋድሞ ፡ በሚታይበት ፡ አፋፍ ፡ ደረሱ ። እዚያ ፡ ከወራጁ ፡ ውሀ ፡ በፍኛቸው ፡ እያፈሱ ፡ ሶስት ፡ አራት ፡ ጉንጭ ፡ ዋጡና ፡ አንዲት ፡ ከስር ፡ ቀጥ ፡ ብላ ፡ ወጥታ ፡ እላይ ፡ ቅርንጫፍዋ ፡ በሰፊው ፡ የተንዘረፈፈ ፡ ለምለም ፡ ወርካ ፡ ባትራቢያቸው ፡ ስላዩ ፡ ወደስዋ ፡ ሄደው ፡ ስርዋን ፡ ተደግፈው ፡ ቁጭ ፡ ከማለታቸው ፡ ከጠጡት ፡ ውሀ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚበልጥ ፡ ላብ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ነከረው ። ወዲያው ፡ ሾህና ፡ ጋሬጣውን ፡ ከግራቸው ፡ ሳያወጡ ፡ ቁስላቸውን ፡ ሳያስሩ ፡ ድካም ፡ እይሉት ፡ እንቅልፍ ፡ ወይም ፡ ሞት ፡ ስሙ ፡ የማይታወቅ ፡ ነገር ፡ እንዳዘዚም ፡ ተጫናቸው ። ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ እየሰሙ ፡ ለመነሳት ፡ ቢሞክሩ ፡ ሰውነታቸው ፡ ከዛፍዋ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ታሰረ ፡ ሁሉ ፡ መንቀሳቀስ ፡ አቃተው ። ራሳቸው ፡ ብቻ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ቀና ፡ እያለ ፡ ከተመለሰ ፡ በሁዋላ ፡ በሶስተኛው ፡ ከዛፍዋ ፡ ስር ፡ ሸተት ፡ ብሎ ፡ እደንጋዩ ፡ ላይ ፡ ዘንበል ፡ ብሎ ፡ እዚያው ፡ ሲቀር ፡ ቆባቸው ፡ ሸሸጎት ፡ የሰነበተውን ፡ ዛል ፡ ጠጉር ፡ እንደ ፡ ተፈታ ፡ የሀር ፡ ነዶ ፡ በትከሻቸውና ፡ በተደገፉት ፡ ደንጋይ ፡ ላይ ፡ ዘርግሮት ፡

እመሬት ወደቀ።

እዚያች ፡ የወርካ ፡ ዛፍ ፡ ስር ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ የተለቀዩ ፡ እግሮቻቸውን ፡ ለተት ፡ አድርገው ፡ ዘርግተው ፡ ወገባቸውን ፡ በወርካ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ዘና ፡ አድርገው ፡ አስጠግተው ፡ አንገታቸው ፡ የተሸከመው ፡ የሀር ፡ ነዶ ፡ እንደ ፡ ከበደው ፡ ሁሉ ፡ ትንሽ ፡ ዘንበል ፡ ብሎ ፡ ያ ፡ የተፈታ ፡ የሀር ፡ ነዶ ፡ የመሰለ ፡ ጠጉራቸው ፡ በትከሻቸውና ፡ በተንተራሱት ፡ ደንጋይ ፡ ላይ ፡ ተመሰቃቅሎ ፡ ለምለም ፡ ከንፈሮቻቸው ፡ ለመላቅ ፡ እንደ ፡ ሞከሩ ፡ ትንሽ ፡ ሸርመም ፡ አይኖቻቸው ፡ ለርቀው፡ ለማየት ፡ እንደ ፡ ሞከሩ ፡ ትንሽ ፡ ገርበብ ፡ ብለው ፡ እጆቻቸው ፡ ከላይ ፡ ያነገት ፡ የደረታቸውን ፡ ከታች ፡ የባታቸውን ፡ መልካም ፡ ቅርጽ ፡ ለማሳዬት ፡ እንደ ፡ ፈለጉ ፡ ሁሉ ፡ የለበሱትን ፡ ጥቁር ፡ ደበሎ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ገልጠው ፡ ዛል ፡ ብለው ፡ ወድቀው ፡ ላያቸው ፡ ሁሉ ፡ ለአሊ ፡ ተጨንቆ ፡ ተጠቦ ፡ አላምሮ ፡ ለስእል ፡ ያስቀመጣቸው ፡ እንጂ ፡ ርበዋቸው ፡ ደክሞዋቸው ፡ ተንገላተው ፡ የወደቁ ፡ መንገደኛ ፡ አይመስሉም ፡ ነበር ። አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ በጥቁር ፡ ደበሎ ፡ የተሸፈኑ ፡ ከንዶቻቸውን ፡ ግራቀኝ ፡ ዘርግተው ፡ ከሰማይ ፡ የወደቀ ፡ መላክ ፡ መስለው ፡ ተጋድመው ፡ ሲታዩ ፡ የሰሩዋቸውን ፡ አምላካዊ ፡ እጆች ፡ ለማስመስገን ፡ ለዘላለም ፡ እንዲኖሩ ፡ ተጠንቅቆ ፡ የፈጠራቸው ፡ እንጂ ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ መቃብርን ፡ ለማስጌጥና ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ለመፍረስ ፡ ለመበስበስ ፡ የተፈጠሩ ፡ አይመስሉም ፡ ነበር ። እንዲያ ፡ አምረው ፡ የወደቁበትን ፡ ቦታ ፡ ጭምር ፡ አሳምረው ፡ እንደ ፡ ተጋደሙ ፡ ቀኑ ፡ አልፎ ፡ ሌሊቱ ፡ ተተካ ።

መንገደኛ ፡ መነኩሴ ፡ ከሌሊቱ ፡ ተላላፊ ፡ ሁሉ ፡ ጨለማን ፡ ብቻ ፡ ጋርደው ፡ ጨለማን ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ብርቱ ፡ ምሽግ ፡ በዙሪያቸው ፡ አጥረው ፡ በጨለማ ፡ ብቻ ፡ እንደሚያምኑት ፡ ዘበኛ ፡ ከርተው ፡ ዘንተው ፡ እንቅልፋቸውን ፡ ቀጠሉ ። እሱም ፡ እንደ ፡ ከዳተኞች ፡ እንዳታላዮች ፡ ሁሉ ፡ ለጊዜው ፡ ታማኝ ፡ ለጊዜው ፡ ቁምነገራም ፡ ለጊዜው ፡ አደራ ፡ የማይበላ ፡ መስሎ ፡ እኩለሌሊት ፡ እስኪያልፍ ፡ ከማናቸውም ፡

ነገር ፡ ጥላ ፡ ከለላ ፡ ሆኖ ፡ ሲጠብቃቸው ፡ ቆይቶ ፡ ድንገት ፡ ጨረቃ ፡ ከምስራቅ ፡ ብቅ ፡ ስትል ፡ ጥሎዋቸው ፡ አጋልጠዋቸው ፡ ሸሸ !

አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ እዚያ ፡ እንደ ፡ ተጋደሙ ፡ የጨረቃ ፡ ብርሀን ፡ በውበት ፡ ላይ ፡ ውበት ፡ ጨምሯላቸው ፡ ደግሞ ፡ ከፊተኛው ፡ አምረው ፡ ደግሞ ፡ ከፊተኛው ፡ የበለጠ ፡ አጊጠው ፡ ከሌሊት ፡ ተላላፊ ፡ ባለድሉን ፡ ሲጠባበቁ ፡ ጅብ ፡ ከንድ ፡ ወገን ፡ ተኩላ ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ መጡ ። መጀመሪያ ፡ ሁለቱም ፡ የዛፍ ፡ ስር ፡ ሙሽራቸውን ፡ እንጂ ፡ እሰበሳቸው ፡ አልተያዩም ፡ ነበር ። በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ከያሉበት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ቀረብ ፡ ሲሉ ፡ ተያዩና ፡ በመቀናናት ፡ ጥል ፡ ሲጀምሩ ፡ ከነሱ ፡ የበለጠ ፡ ሀይለኛ ፡ ባጠገባቸው ፡ ስላዩ ፡ ለዩራሳቸው ፡ ፈርተው ፡ ወደዩመጡበት ፡ ሮጡ ። ወዲያው ፡ የተኙት ፡ መነኩሴ ፡ ከንቅልፍ ፡ ወደንቃት ፡ መመለስ ፡ ሲጀምሩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡ በእንቅልፍና ፡ በንቃት ፡ መሀከል ፡ እንዳሉ ፡ አይናቸውን ፡ ገለጥ ፡ ቢያደርጉ ፡ እዚያች ፡ ወርካ ፡ ስር ፡ ገደም ፡ ብለው ፡ ተቀምጠው ፡ ከበታቻቸው ፡ ያባይ ፡ በረሀ ፡ ወንዙ ፡ የማዶው ፡ ተራራና ፡ መንደሮች ፡ ዛፎች ፡ ሳይቀሩ ፡ በጨረቃ ፡ ብርሀን ፡ ልቅም ፡ ብለው ፡ ታዩዋቸውና ፡ ለጊዜው ፡ እልም ፡ መሰላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ እንቅልፉ ፡ አልፎ ፡ በሙሉ ፡ ሲነቁ ፡ ትናንት ፡ እዚያች ፡ ዛፍ ፡ ስር ፡ መጥተው ፡ ሲቀመጡ ፡ የደረሰባቸው ፡ ሁሉ ፡ ከመጀመሪያው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ትዝ ፡ እያላቸው ፡ ሄዶና ፡ እልም ፡ እለመሆኑን ፡ አወቁ ።

ከቤታቸው ፡ ከወጡ ፡ ያ ፡ ሶስተኛ ፡ ሌሊት ፡ በመሆኑ ፡ በሌሊት ፡ ብቻቸውን ፡ እዚያ ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ መገኘታቸው ፡ መጀመሪያ ፡ በጣም ፡ አላስፈራቸውም ፡ ነበር ። ብቻ ፡ ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ሌሊቶች ፡ ብቻቸውን ፡ ጫካለጫካ ፡ ሲዞሩ ፡ እግሮቻቸው ፡ ሾህና ፡ ጋሬጣ ፡ እንቅፋትም ፡ ተፈራርቆባቸው ፡ ይቁሰሉ ፡ ይሰቅዩ ፡ የደም ፡ ጎርፍ ፡ ያንገላታቸው ፡ እንጂ ፡ መሄድ ፡ ይችሉ ፡ ስለነበረ ፡ አውሬ ፡ ቢያጋጥማቸው ፡ ሮጠው ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ለመጠጋት ፡ መንደር ፡ በራቀበት ፡ ዛፍ ፡

ወጥተው ፡ ለማምለጥ ፡ ይችሉ ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ እኒያ ፡ ሲሰቀቁ ፡ የሰነበቱ ፡ እግሮች ፡ እንኳዋንስ ፡ እሳቸውን ፡ ተሸክመው ፡ ሊሮጡ ፡ እሳቸው ፡ ሊሸከሙዋቸው ፡ እንኳ ማይችሉ ፡ ሆነው ፡ ስላበጡ ፡ የሰይጣን ፡ ጆሮ ፡ አይስማና ፡ አውሬ ፡ ቢመጣ ፡ እንደተቀመጡ ፡ ያውሬ ፡ ራት ፡ ከመሆን ፡ በቀር ፡ ሮጠው ፡ ለማምለጥ ፡ ትንሽ ፡ እንኳዋ ፡ የተስፋ ፡ ጭራ ፡ አልታያቸው ፡ አለና ፡ ፍራት ፡ ገባቸው ። ይህን ፡ አሳብ ፡ ረስተው ፡ ሌላ ፡ የሚያበረታታ ፡ ነገር ፡ ለማሰብ ፡ በሞከሩ ፡ ቁጥር ፡ ሌላውን ፡ ሁሉ ፡ እያባረረ ፡ እሱው ፡ እየተመለሰ ፡ እየመጣ ፡ ስላስቸገራቸው ፡ አምላካቸውን ፡ ይጠሩ ፡ ጀመር ።

“ አምላኬ ፡ አባክህ ፡ ጠብቀኝ ! ሰለስቱ ፡ ደቂቅን ፡ ከሳት ፡ ዳንኤልን ፡ ከጉበ ፡ አናብስት ፡ ያዳንህ ፡ አምላክ ፡ አባክህ ፡ አድነኝ ! አምላኬ ፡ የምሕረት ፡ መላክተኛህን ፡ ላክልኝ ! ” አሉና ፡ መልክ ፡ ኢየሱስ ፡ ለመድገም ፡ “ ለዝክረ ፡ ስምከ ” ሲሉ ፡ በፊታቸው ፡ ሀያ ፡ ሜትር ፡ ያክል ፡ ራቅ ፡ ብላ ፡ የነበረች ፡ ትንሽ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ክብዳ ፡ ታየቻቸው ። ወዲያው ፡ መልክ ፡ ኢየሱሳቸውን ፡ አቋርጠው ፡ አይኖቻቸውን ፡ አሻሹና ፡ እንደገና ፡ ቢገልጡ ፡ ያ ፡ እቁጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ ከብዶ ፡ የታያቸው ፡ ነገር ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ መሰላቸው ። እንደገና ፡ አይኖቻቸውን ፡ አሻሽተው ፡ ቢገልጡ ፡ ያ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ነገር ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ወደሳቸው ፡ ሲመጣ ፡ አዩት ። አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ርምጃ ፡ ወደፊት ፡ ይራመድና ፡ ቆም ፡ ወደሳቸው ፡ ይመለከታል ፡ ከዚያ እንደገና ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ርምጃ ፡ ይራመዳል ። እንዲህ ፡ እየተጠነቀቀ ፡ ዙሪያ ፡ ገባው ፡ አማን ፡ መሆኑን ፡ እያስተዋለ ፡ ቀረብ ፡ ሲል ፡ ካናቱ ፡ እስከ ፡ ጅራቱ ፡ ጥርት ፡ ብሎ ፡ ታያቸው ። እግዚአብሔር ፡ መላክ ፡ ምሕረቱን ፡ እንዲልክላቸው ፡ ቢለምኑት ፡ ያልለመኑትን ፡ መላክ ፡ መቅሰፍቱን ፡ ላከላቸው ! “ ነብር ! ” አሉ ፡ አባ ፡ እለም ፡ ሰምኔ ፡ ቀስ ፡ ብለው ። “ነብር !” አሉ ፡ እንደገና ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ እንደበታቸው ፡ ታሰረ ፡ ልባቸው ፡ እንደተቃጠለ ፡ ሻማ ፡ ቀልጦ ፡ በውስጣቸው ፡ የፈሰሰ ፡ መሰ

ላቸው ። ሙሉ ፡ አካላቸው ፡ ቆርጦ ፡ ለጸሀይ ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡
ሲጋ ፡ ተክል ፡ ዛለ ፡ አእምሮዋቸው ፡ ድንዝዝ ፡ አለ ፡ አይናቻ
ቸው ፡ እንቅልፍ ፡ እንደ ፡ ከበዳቸው ፡ ሲስለመለሙ ፡ እንዱ ፡
ነብር ፡ ሁለት ፡ እየሆነ ፡ ይታያቸው ፡ ጀመር ፡ ለመሮጥ ፡ እየሞ
ከሩ ፡ የሚበቃ ፡ ትንፋሽ ፡ አጡ ።

ነብሩ ፡ እንዲህ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ተጉዞ ፡ አባ ፡ አለም ፡
ለምኔ ፡ እሰብበት ፡ ለመድረስ ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው ፡ ቆም ፡ ብሎ ፡
እያጉረመረመ ፡ እሳቸውን ፡ ትንሽ ፡ ተመለከተና ፡ ከዚያ ፡ አይና
ቹን ፡ ወደ ፡ ወንዝዋ ፡ አተኩሮ ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ፡ መነኩሴ
ውም ፡ የመጀመሪያው ፡ የፍራት ፡ ሰመመን ፡ እንደ ፡ ማለፍ ፡
ብሎላቸው ፡ አእምሮዋቸውን ፡ መግዛት ፡ ሲጀምሩ ፡ አይናቻቸ
ውን ፡ ሲፈሩ ፡ ሲቸሩ ፡ ገለጥ ፡ ቢያደርጉ ፡ ነብሩ ፡ ሽንጡን ፡ ለሳ
ቸው ፡ ሰጥቶ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ወንዝዋ ፡ አዙሮ ፡ እዩተመለከተ ፡
ጅራቱን ፡ በቀስታ ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲያወዛ
ውዝ ፡ አዩና ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ ነብሩ ፡ ወደሚመለከትበት ፡ አይና
ቻቸውን ፡ ቢልኩ ፡ ከወንዝዋ ፡ ወዲህ ፡ ማዶ ፡ የሳር ፡ ክምር ፡
በራሱ ፡ የተሸከመ ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ ቆሞ ፡ አዩ ። ምንም ፡ እን
ኳ ፡ ያንበሳን ፡ ስም ፡ እንጂ ፡ መልኩን ፡ አይተው ፡ ባያውቁ ፡
እንዲሁ ፡ በግምት ፡ አዲስ ፡ መጪው ፡ እሱ ፡ መሆኑን ፡ አወቁ ።

ሁለቱ ፡ ጎበዞች ፡ ሀያ ፡ ሜትር ፡ ያክል ፡ በሚሆን ፡ ርቀት ፡
ቆመው ፡ ትንሽ ፡ ከተፋጠጡ ፡ በሁዋላ ፡ አንበሳ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡
አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲራመድ ፡ ነብር ፡
ያኑ ፡ ያክል ፡ ወደ ፡ ሁዋላው ፡ ማፈግፈግ ፡ ጀመረ ። እንዲሁ ፡
አንበሳ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲራመድ ፡ ነብር ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ወደ ፡
ሁዋላ ፡ ሲያፈገፍግ ፡ ቆመው ፡ ትንሽ ፡ ሲፋጠጡ ፡ ነብር ፡ ሲያ
ፈገፍግ ፡ አንበሳ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ሲከተል ፡ እዩተጠባበቁ ፡
ካይናቸው ፡ ሲጠፉ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ያ ፡ እንደ ፡ ተቃጠለ ፡
ሻማ ፡ ቀልጦ ፡ የፈሰሰ ፡ ልባቸው ፡ ሀይሉን ፡ እንዴት ፡ እንዳጠ
ራቀመ ፡ እኒያ ፡ ከተዘረጉበት ፡ ለማጠፍ ፡ አስቸግረው ፡ የነበሩ ፡
እግሮቻቸው ፡ እንዴት ፡ ተነስተው ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ ሳይታወቃ
ቸው ፡ እንደ ፡ ብርቱ ፡ እንደ ፡ ጤናማ ፡ ሮጠው ፡ እዛፉ ፡ ላይ ፡
ለመውጣት ፡ ቢሞክሩ ፡ ግንዱ ፡ ወፍሮ ፡ መታቀፍ ፡ ስላልቻሉና ፡

ያበጡ ፡ እግሮቻቸው ፡ መቆንጠጥ ፡ ስላቃታቸው ፡ ተንሻተው ፡ ወደቁ ። እንደገና ፡ ለመውጣት ፡ ሲሞክሩ ፡ ተመልሰው ፡ ሲወድቁ ፡ ሲነሱ ፡ ሲወድቁ ፡ ዛፉ ፡ ከላጠውና ፡ ጋሬጣ ፡ ከወጋው ፡ ገላቸው ፡ እዚያ ፡ ወርካ ፡ ስር ፡ የፈሰሰው ፡ ደም ፡ ሲታይ ፡ በደም ፡ ስራቸው ፡ አንድ ፡ ጠብታ ፡ የቀረ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠው ፡ ማልቀስ ፡ ሲጀምሩ ፡ አንዲት ፡ ከትልቅዋ ፡ ወርካ ፡ አጠገብ ፡ ለብቻዋ ፡ በቅላ ፡ እላይ ፡ ከትልቅዋ ፡ ወርካ ፡ ቅርንጫ ፎች ፡ ጋር ፡ የተገናኘች ፡ ቀጭን ፡ ዛፍ ፡ አዩ ። ወዲያው ፡ እዬሮጡ ፡ ሄዱና ፡ እሷን ፡ አቅፈው ፡ በልባቸው ፡ እዬተሳቡ ፡ ወጥተው ፡ እወርካዋ ፡ ቅርንጫፎች ፡ መሀከል ፡ ሲደርሱ ፡ ከዚያ ፡ እንደም ንም ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ወርካዋ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ተላልፈው ፡ ለመቀ መጫም ፡ ለእግሮቻቸውና ፡ ለራሳቸው ፡ ለወገባቸው ፡ መደገፊያም ፡ የሚሆኑ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ባሉበት ፡ ሄደው ፡ ሲቀመጡ ፡ ራሳቸው ፡ መዞር ፡ ጉልበታቸው ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ጀመረ ። ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ እእምሮዋቸው ፡ ደንዝዞ ፡ ቆይተው ፡ ነፍስ ፡ ሲገዙ ፡ ሰውነታቸው ፡ ሁሉ ፡ በቀዝቃዛ ፡ ላብ ፡ ተጠምቆ ፡ አገኙት ። ከዚያ ፡ ትንፋሻቸ ውን ፡ አጠራቅመው ፡ በረዥሙ ፡ ተነፈሱና ፡ ሰውነታቸውን ፡ ትንሽ ፡ አሳርፈው ፡ ቆይተው ፡ ወደ ፡ ወርካዋ ፡ ስር ፡ ቢመለከቱ ፡ አንበሳው ፡ ለካ ፡ ተመልሶ ፡ ኖሮ ፡ አፍንጫውን ፡ በየማእዘኑ ፡ እዬ ዞረ ፡ ሲፈልጋቸው ፡ አዩ ። ለጊዜው ፡ አፍንጫው ፡ ወደሳቸው ፡ በዞረ ቁጥር ፡ ስቦ ፡ የሚያወርዳቸው ፡ እዬመሰላቸው ፡ ፍራት ፡ እንደ ፡ ብርቱ ፡ ብርድ ፡ እልባቸው ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሲያንቀጠቅጣቸው ፡ ቆዬ ። በሁዋላ ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ልባቸው ፡ እዬሞላ ፡ ሄደና ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ ተቀምጠው ፡ ሁኔታውን ፡ ይመለከቱ ፡ ጀመር ።

አንበሳ ፡ እወርካዋ ፡ ስር ፡ የፈሰሰው ፡ ደምና ፡ ጠረናቸው ፡ ሲሸተው ፡ እዚያ ፡ ግድም ፡ መሆናቸውን ፡ እያወቀ ፡ ፈልጎ ፡ ስላ ጣቸው ፡ በብርቱ ፡ ጉምዥትና ፡ ቁጣ ፡ እያገሳ ፡ መሬቱን ፡ ሲፎ ግር ፡ ደንጊያውን ፡ ሲፈነቅል ፡ ቁጥቋጦውን ፡ ሲጥስ ፡ ወርካዋንና ፡ በወርካዋ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ በየደቂቃው ፡ ሲዞር ፡ ቆዬና ፡ በሁዋላ ፡ ከፈዳቸውንና ፡ ዱላቸውን ፡ በፊት ፡ እግሮቹ ፡ ረግጦ ፡ ቁጭ ፡ እንዳለ ፡ እሳቸውም ፡ የወርካ ፡ ቅጠላቸውን ፡ ለብ ሰው ፡ አይናቸውን ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ እንደተከሉ ፡ መንጋት ፡ አይቀ

ርም ፡ ነጋ ።

ጸሀይ ፡ ሠጥታ ፡ ትንሽ ፡ ሞቅ ፡ ሲል ፡ አንበሳ ፡ በወርካዋ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ ቁጥቋጦ ፡ ሁሉ ፡ እየገባ ፡ ፈልጎ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ ባባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ከፊዳና ፡ ዱላ ፡ ሲጫወት ፡ ቆይቶ ፡ በመሄድና ፡ ባለመሄድ ፡ መሀከል ፡ እያመነታ ፡ እየሄደ ፡ እየቆመ ፡ ትንሽ ፡ ድምጽ ፡ የሰማ ፡ ሲመስለው ፡ ወደ ፡ ሁዋላው ፡ እየተመለሰ ፡ አፋፉን ፡ ዘቅዘቅ ፡ አለ ። አፋፉን ፡ ከወረደ ፡ በሁዋላ ፡ እንኩዋ ፡ አሳቡ ፡ ከዚያች ፡ ወርካ ፡ ጋር ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ እየጎተተው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንደገና ፡ እየተመለሰ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ተመለከተና ፡ በመጨረሻ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጦ ፡ በረሀውን ፡ ወርዶ ፡ ሄደ ።

አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ አንበሳው ፡ አፋፉን ፡ ከወረደም ፡ በሁዋላ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ብቅ ፡ እያለ ፡ ሲያደባ ፡ ስላዩት ፡ ተስፋ ፡ ቆርጦ የሄደ ፡ አልመሰላቸውም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይቶ ፡ በሩቁ ፡ ሲያገሳ ፡ ስለሰሙት ፡ መሄዱን ፡ አረጋገጡ ።

“ ምስጋና ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ የቸርነትህ ፡ ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የሌለው ፡ አምላክ ፡ ምስጋና ፡ ላንተ ፡ ይሁን ! ” አሉ ፡ አንበሳ ፡ እሳቸውን ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲጠባበቅ ፡ ያደረበትን ፡ የወርካ ፡ ስር ፡ ዘቅዝቀው ፡ እየተመለከቱ ። ብቻ ፡ እንዲህ ፡ እግዚአብሄርን ፡ እያመሰገኑ ፡ መሬቱን ፡ ዘቅዝቀው ፡ በተመለከቱት ፡ መጠን ፡ ያ ፡ አንበሳ ፡ ተቀምጦበት ፡ ሳለ ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ ሆኖ ፡ ይታያቸው ፡ የነበረ ፡ ያ ፡ አንበሳ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሮ ተመለከተ ፡ ቁጥር ፡ ከቅርበቱ ፡ የተነሳ ፡ ዘሎ ፡ የሚያወርዳቸው እየመሰላቸው ፡ ሲፈሩት ፡ የነበረ ፡ መሬት ፡ አሁን ፡ ሩቅ ፡ ሆኖ ፡ ታያቸው ። “እንዴት ፡ እወርዳለሁ ? ትናንት ፡ እንዴት ፡ ወጣሁ ?” አሉ ፡ በመፍራትም ፡ በመገረምም ።

ትናንትስ ፡ እኒያ ፡ ወሬያቸው ፡ ብቻ ፡ የሚያስደነግጠው ፡ የሚያንቀጠቅጠው ፡ አንበሳና ፡ ነብር ፡ ባካል ፡ በገሀድ ፡ አፋቸውን ከፍተው ፡ ጥርሳቸውን ፡ አስልተው ፡ ሊዘነጣጥሉዋቸው ፡ ሲሽቀዳደሙ ፡ ፍራት ፡ መሰላል ፡ ሆኖ ፡ ያን ፡ መርገጫ ፡ መጨበጫ ፡ የሌለው ፡ ዛፍ ፡ አወጣቸው ! ዛሬ ፡ ግን ፡ እሱ ፡ የለም ! እውነት ፡ እንዴት ፡ ይወርዱ ፡ ይሆን ?

የሚወርዱበት ፡ ዘዴ ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶዋቸው ፡ ሲቸገሩ ፡ ቆዩና፡ "እስቲ ፡ እመቤቴ ፡ መንገድ ፡ ብትመራኝ ፡ ውዳሴ ፡ ማርያምዋን፡ ልድገም !"አሉና ፡ ጀምረው ፡ የሰኞዋን ፡ ለመጨረስ ፡"ብርሃን ፡ ዘበአማን ፡ ዘያበርህ ፡ ለኩሉ ፡ ሰብእ ፡" ሲሉ ፡- "እየ ፡ ጉድ! እዚህ፡ ዛፍ ፡ ስር ፡ አውሬ ፡ ሰው ፡ በልቶ ፡ አድሮዋል ! አዬሀ ፡ ደሙን ! ኮፊዳውና ፡ ሽመሉም ፡ ያው ፡ እዚያ ፡ ወድቆዋል ! ተማሪ ፡ ኖሮ ዋል !" አለ ፡ አንድ ፡ ድምጽ ።

"አውሬ ፡ ቢበላውማ ፡ ትንሽ ፡ ፍርፋሪ ፡ ይቀር ፡ ነበር፡ ሰው ፡ ገሎ ፡ ቀብሮት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡" አለ ፡ ሌላ ፡ ድምጽ ።

አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ የሰሙት ፡ የሰው ፡ ድምጽ ፡ ለጊዜው ፡ ያንበሳውን ፡ ያክል ፡ አስደነገጣቸው ። በሁዋላ ፡ ትንሽ ፡ ቆይ ተው ፡ ሰውነታቸው ፡ ጸጥ ፡ ሲል ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ የጋረዳቸውን ፡ የወርካ ፡ ቅጠል ፡ ገለጥ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ወርካው ፡ ስር ፡ ሲመ ለከቱ ፡ ከመሬቱ ፡ ርቀት ፡ የተነሳ ፡ የተቀመጡ ፡ የሚመስሉ ፡ ሁለት ፡ ባላገሮች ፡ ኮፊዳቸውንና ፡ ሽመላቸውን ፡ ከወደቁበት ፡ አንስተው ፡ ይዘው ፡ እያዘኑ ፡ ሲነጋገሩ ፡ አዩና ፡ እየፈሩ ፡ በደ ከመ ፡ ቃል ፡ "ወንድሞቼ ፡ እግዚአብሄር ፡ በታምራቱ ፡ አድኖ ኛል ፡ አሁን ፡ ብቻ ፡ መውረጃ ፡ አጥቼ ፡ ተቸግሬያለሁና ፡ እባክ ችሁ ፡ ርዱኝ ፡" አሉ ። ሁለቱ ፡ ቀፎ ፡ አውራጆች ፡ ባላገሮች ፡ ሰው ፡ በሌለበት ድምጽ ፡ ሰለሰሙ ፡ ደንግጠው ፡ ዙሪያ ፡ ገባውን ፡ ሲመለከቱ ፡ "እዚህ ፡ ነኝኮ ፡ እዛፉ ፡ ላይ ፡ ነኝ !" አሉ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ የዛፉን ፡ ቅርንጫፍ ፡ በጃቸው ፡ እያወዛ ወዙ ።

"እኒያውና ፡ አንድ ፡ መለኩሴ ፡ እቅርንጫፉ ፡ ውስጥ ! ታያ ቸዋለህ ?" አለ ፡ ከቀፎ ፡ አውራጆቹ ፡ አንዱ ።

"ወይ ፡ እናቴ ፡ ኪዳነምረት ! እንዴት ፡ አድርገው ፡ ወጡ ፡ እባክህ ! እንዴት ፡ ወጡ ፡ አባቴ ?" አለ ፡ ሁለተኛው ፡ ወደ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ አንጋጦ ።

"እንዴት ፡ እንደ ፡ ወጣሁ ፡ እኔም ፡ አላውቀው ፡ ወንድ ሞቼ ! ብቻ ፡ ትናንትና ፡ ሌሊት ፡ አውሬዎች ፡ ሊበሉኝ ፡ እሬቱ ፡ ተሰልፈው ፡ ይጣሉብኝ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አስታውሳለሁ ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ እዚህ ፡ መገኘቴን ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ እዚህ ፡ እንደ ፡ ደረስሁ ፡ አላውቅም ።"

"እንዴት ፡ ግሩም ፡ ነው ፡ እባክህ ! ገረመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በክንፉ ፡ አውቶዋቸው ፡ ነው ፡ እንጂ !" አለ ፡ አንዱ ።

"መለኩሴ ፡ አይሉ ! ፈጣሪያቸው ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ጠሎታቸውን ፡ ሰምቶላቸዋል ፡ ጣድቃን ፡ ቢሆኑ ፡ ነው !" አለ ፡ ሁለተኛው ።

ከዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ጎበዛዝት ፡ እስበሳቸው ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ ተነጋገሩና ፡ አንደኛው ፡ መጥረቢያና ፡ ዱላውን ፡ አስቀምጦ ፡ የቀፎ ፡ ማውረጃ ፡ ጀመሬ ፡ ገመዱን ፡ በወርካው ፡ ግንድ ፡ ጠምጥሞ ፡ መረጋገጫ ፡ ርካብ ፡ አበጀና ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ የተረፈውን ፡ ገመድ ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ እንደገና ፡ ጠምጥሞ ፡ ርካብ ፡ አበጅቶ ፡ ወደዚያ ፡ ተሳልፎ ፡ የታችኛውን ፡ ሳብ ፡ ሲያደርገው ፡ አውቆ ፡ ተፈታ ። እንዲሁ ፡ አንድ ፡ ርካብ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ከበላዩ ፡ ሌላ ፡ እያሰረ ፡ ወደዚያ ፡ ሲተላለፍ ፡ የታችኛውን ፡ እዬፈታ ፡ ከበላዩ ፡ ሌላ እያሰረ ፡ ወደዚያ ፡ እየተላለፈ ፡ ግንዱን ፡ አልፎ ፡ እቅርንጫፎቹ ፡ ሲደርስ ፡ ገመዱን ፡ ሰብስቦ ፡ ይዞ ፡ ከቅርንጫፍ ፡ ወደ ፡ ቅርንጫፍ ፡ በሚያስገርም ፡ ቅልጥፍና ፡ ተረማመደና ፡ መነኩሴው ፡ በተቀመጡበት ፡ ደረሰ ። ከዚያ ፡ በደበሎዋቸው ፡ ላይ ፡ ወገባቸውን ፡ በጀመሬ ፡ ገመድ ፡ አሰረና ፡ ወገባቸውም ፡ እንዳይጎዳ ፡ ገመዱን ፡ ቀጥለቀጥ ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ እንዲጨብጡ ፡ አደረገና ፡ ማር ፡ እንደ ፡ ሞላ ፡ ቀፎ ፡ በትልቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ቀስ ፡ አድርጎ ፡ እመሬት ፡ አስቀመጣቸው ። ከዚያ ፡ እመሬት ፡ ያለ ፡ ጉዋደኛው ፡ ገመዱን ፡ ከመነኩሴው ፡ ወገብ ፡ ፈቶ ፡ ሲለቅለት ፡ ያን ፡ ገመድ ፡ እኩል ፡ እጥፎ ፡ በርታ ፡ ባለው ፡ ቅርንጫፍ ፡ ጠምጥሞ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ለቀቀና ፡ በሱ ፡ ተንጨዋሎ ፡ በቅጽበት ፡ እመሬት ፡ ዱብ ፡ አለ ።

"በል ፡ መጥረቢያህን ፡ አንሳ ፡ ሳይረፍድብን ፡ እንሂድ !" አለ ፡ እመሬት ፡ የቆየው ፡ ቀፎ ፡ አውራጅ ።

"ይበሉ ፡ እስዎም ፡ ጠሀይ ፡ ሳይጠነክርብዎ ፡ አፋፉን ፡ ይውጡ ፡ አባቴ ፡ ለመሆኑ ፡ የት ፡ ነው ፡ የሚሄዱ ?" አለ ፡ ሁለተኛው ፡ ለመሄድ ፡ መጥረቢያውን ፡ ሲያነሳ ።

"እግሮቼ ፡ የተሸከሙት ፡ ሸሀና ፡ ጋሬጣ ፡ እንዴት ፡ እንደ ሚያስሄደኝ ፡ አላውቅም ፡ እንጂ ፡ የምሄድበትስ ፡ሩቅ ፡ ነው ።"

እሱ ፡ መነኩሴው ፡ ያበጡ ፡ እግሮቻቸውን ፡ ዘቅዝቀው ፡ እዩተ መለከቱ ።

"ውውው ! እባክህ ፡ ጉድ ፡ እይ ! እግራቸው ፡ እንዴት ፡ አብጦዋል !" አለ ፡ አንዱ ።

"መቸም ፡ ካስቸገርሁዋችሁ ፡ አይበልጥምና ፡ እባካችሁ ፡ እስሬ ፡ ላይ ፡ የወጋኝን ፡ ሾህና ፡ ጋሬጣ ፡ አውጡልኝ ፡ ያለዚያ ፡ እዚሁ ፡ እንደ ፡ ተቀመጥሁ ፡ እንደገና ፡ ይመሽና ፡ ያውሬ ፡ ራት ፡ መሆኔ ፡ ነው !"

"ረፈደብና ፡ አባቴ ! ጠሀይ ፡ ከሞቀኮ ፡ ቀፎዋችንን ፡ ማውረድ ፡ አንችልም ፤ ንቡ ፡ አያስቀርብም !" አለ ፡ ከቀፎ ፡ አውራጆቹ ፡ አንዱ ።

"ግዴለም ፡ ለነፍስ ፡ ይሆኑናል ፡ እናውጣላቸው ፡" አለ ፡ ጉዋደኛው ።

ከዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ቀፎ ፡ አውራጆች ፡ ያባ ፡ አለም ፡ ለምኔን ፡ እግሮች ፡ ተከፋፍለው ፡ በወረንጦ ፡ እዩነቀሱ ፡ ሾሁንና ፡ ጋሬጣውን ፡ አንድባንድ ፡ እዩመዘዙ ፡ ሲያወጡላቸው ፡ ሾዞና ፡ ጋሬጣ ፡ ከወጣላቸው ፡ የደም ፡ ስሮች ፡ የሚፈሰው ፡ ደም ፡ ማገጃ ፡ ስላጣ ፡ ለቀፎ ፡ መሸከሚያ ፡ ከያዙት ፡ ዳባ ፡ በስንጢ ፡ ቆርጠው ፡ የመነኩሴውን ፡ እግሮች ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ ሸፍነው ፡ በሲባጎ ፡ ጥብቅ ፡ አድርገው ፡ አሰሩላቸው ።

ቀፎ ፡ አውራጆቹ ፡ መጥረቢያቸውን ፡ ገመዳቸውን ፡ ሸመላቸውንና ፡ የስንቅ ፡ ስልቻቸውን ፡ አጠገባቸው ፡ ጣል ፡ አድርገው ፡ ካባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ እግሮች ፡ ሾዞና ፡ ጋሬጣ ፡ ሲያወጡና ፡ እግራቸውን ፡ ሲያስሩላቸው ፡ እሳቸው ፡ አይናቸውን ፡ እስንቅ ፡ ስልቻዋ ፡ ላይ ፡ ጥለው ፡ በውስጥዋ ፡ የያዘችውን ፡ ይመረምሩ ፡ ነበር ።

ያቺ ፡ አሮጌ ፡ የስንቅ ፡ ስልቻ ፡ ሁለት ፡ ድብልብል ፡ ነገሮች ፡ የያዘች ፡ መሆንዋን ፡ ታሳያለች ። አንዱን ፡ ድብልብል ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አንዱን ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ አድርጎ ፡ በትክሻ ፡ ጣል ፡ ለማድረግ ፡ እንዲመች ፡ ስልቻዋ ፡ አፍዋና ፡ ወገብዋ ፡ እመሀከል ፡ ላይ ፡ ተቁዋርጣ ፡ ታስራለች ።

ሁለቱ ፡ ድብልብል ፡ ነገሮች ፡ እዬተቀዋረጡ ፡ በታሰሩበት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ስልቻዋ ፡ ወዝታ ፡ ትታያለች ። «በቅቤና ፡ በድቁስ ፡ የተጨበጡ ፡ ጭብጦዎች ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም !» አሉ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ባሳባቸው ። « አዎ ፡ እንጎቻዎች ፡ ቢሆኑ ፡ ስልቻዋ ፡ እንዲህ ፡ አትወዛም ፡ ነበር ፡ ወዲያውም ፡ እንጎቻ ፡ እንዲህ ፡ ድብልብል ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ። በቅቤና ፡ በተቀመመ ፡ ድቁስ ፡ የተጨበጡ ፡ ጭብጦዎች ፡ ናቸው !»

በቅቤና ፡ በተቀመመ ፡ ድቁስ ፡ የተጨበጠ ፡ ጭብጦ ፡ ሲያስቡ ፡ ሰውነታቸው ፡ በሙሉ ፡ ከፍንጫ ፡ ብቻ ፡ እንደተሰራ ፡ ሁሉ ፡ በቅቤና ፡ በተቀመመ ፡ ድቁስ ፡ የተጨበጠ ፡ ጭብጦ ፡ ሸተተው ። በቅቤና ፡ በድቁስ ፡ የሚገቡትን ፡ ቅመሞች ፡ አንድ ባንድ ፡ ባስታወሱ ፡ መጠን ፡ ሽታው ፡ እዬበረታ ፡ ሄደና ፡ ህዋሳታቸውን ፡ ሁሉ ፡ በዘበዘው ፡ በዚያም ፡ መጠን ፡ ራብ ፡ ጥርሱን ፡ ስሎ ፡ አሹሎ ፡ ያላምጣቸው ፡ ጀመር ።

« ከዚህ ፡ ጭብጦ ፡ ልለምናቸው ? ምን ፡ ብዬ ፡ እለምናቸዋለሁ ? አልለምናቸውም ! እንዲሁ ፡ በደፈናው ፡ እህል ፡ ከቀመስሁ ፡ ሶስተኛ ፡ ቀኔ ፡ ነው ፡ ልበላቸው ። ምንም ፡ ቢሆን ፡ ከሚበቃቸው ፡ በላይ ፡ እህል ፡ ተሸክመው ፡ ሲተርፋቸው ፡ ለመጣል ፡ ሰው ፡ በራብ ፡ ሲሞት ፡ ዝም ፡ አይሉም ! ብቻ ፡ ያልተራበ ፡ ሆድ ፡ የተራበ ፡ ሆድ ፡ እመም ፡ ስለማይሰማው ፡ እንዲሁ ፡ ስምተው ፡ ዝም ፡ ያሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ ምን ፡ እሆናለሁ ?» እያሉ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ መለመኛ ፡ ቃል ፡ ሲያማርጡ ።

« ያው ፡ እንግዴህ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ እያነከሱ ፡ እመንደር ፡ ይድረሱ ፡ አባ ! መቸም ፡ እግርዎ ፡ የተሸከመውን ፡ ሾህና ፡ ጋሬጣ ሁሉ ፡ ለማውጣት ፡ ሙሉ ፡ ቀን ፡ ያስፈልጋል ፡ እስርዎ ፡ ላይ ፡ ያገኘነውን ፡ ግን ፡ አወጣንልዎ !» አለ ፡ ከቀፎ ፡ አውራጆቹ ፡ አንዱ ።

« የተሰፋልዎ ፡ ጫማም ፡ እስዎን ፡ ካልደከመዎ ፡ እስካለም ፡ ዳርቻ ፡ ያደርሰዋል ፡ እንዲህያል ፡ ጫማ ፡ የንጉሱም ፡ የላቸው !» አለ ፡ ጉዋደኛው ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ።

«እግዚአብሄር ፡ ይስጣችሁ ፡ አስተነፈሳችሁኝ ! እህል ፡ ባፌ ፡ ከገባ ፡ ሶስት ፡ ቀን------ሆኖኝ ፡ ከግሬ ፡ ስቃይ ፡ የተነሳ

ነው ፡ መሰለኝ ---ራብ ፡ ---አይሰማኝም !» አሉ ፡ መነኩሴው ፡ ስልቻዋን ፡ እያዩ ።

« እውነታቸውኮ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ትንሽ ፡ እንኩዋ ፡ ከታመመ ፡ ራብ ፡ አይሰማውም ! ለምን ፡ ይሆን ?» አለ ፡ አንዱ ።

« ኧረኔ ፡ ምናውቁ ፡ ወንድሜ ! ተነስ ፡ ተነስ ፡ ረፈደብን!» አለ ፡ ሁለተኛው ፡ ቀፎ ፡ አውራጅ ።

ከዚያ ፡ አንዱ ፡ ገመድና ፡ መጥረቢያውን ፡ ሁለተኛው ፡ የስንቅ ፡ ስልቻውን ፡ አንግተው ፡ መነኩሴውን ፡ አይናቸው ፡ ሲቅበዘበዝ ፡ « ደህና ፡ ይሁኑ ! » ብለዋቸው ፡ እዬሮጡ ፡ ወዳባይ ፡ ቆላ ፡ ሲወርዱ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ሰምኔ ፡ ወገባቸው ፡ በሰይፍ ፡ እንደ ፡ ተመታ ፡ ለሁለት ፡ የተከፈለ ፡ መስሎ ፡ ተሰማቸው ። ልባቸው ፡ በደም ፡ ፈንታ ፡ አሞት ፡ እንደሚነዛ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ምሬት ፡ ተሰማው ፡ የሰውን ፡ ዘር ፡ በሙሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ሳይቀር ፡ ነፍሳቸው ፡ እንደ ፡ ጥንብ ፡ ተጸየፈችው ፡ ያች ፡ ጊዜ ፡ የህይወታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ያለሙ ፡ መደምሰሻ ፡ መስላ ፡ ታዬቻቸው ፡ የኑሮ ፡ ተስፋቸውን ፡ አለኝታቸውን ፡ ህይወታቸውን ፡ እነዚያ ፡ ሁለት ፡ ቀፎ ፡ አውራጆች ፡ ከጭብጦዋቸው ፡ ጋር ፡ በስልቻቸው ፡ ይዘውባቸው ፡ እንደ ፡ ሮጡ ፡ ሁሉ ፡ በውስጣቸው ፡ ፍጹም ፡ ባዶነት ፡ ተሰማቸው ። እነዚያ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ካይናቸው ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ አይኖቻቸው ፡ ሳይረግቡ ፡ ፍዝዝ ፡ ድንዝዝ ፡ ብለው ፡ ሲያዩ ፡ ቆዩ ። ሰዎቹ ፡ አፋፉን ፡ ወርደው ፡ ከጠፉ ፡ በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ትንሽ ፡ ቆይተው ፡ አይኖቻቸውን ፡ መላልሰው ፡ አርገብግበው ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ዙሪያገባውን ፡ ቢመለከቱ ፡ ሰማዩ ፡ ምድሩ ፡ ዛፉ ፡ ደንጋዩ ፡ ተራራው ፡ ወንዙ ፡ እሳቸው ፡ ከፈዳቸው ፡ ሽመላቸው ፡ ሁሉም ፡ በዬቦታው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አሁንም ያለ ፡ መሆኑን ፡ ተመለከቱ ! አለም ፡ አለመደምሰሱን ፤ እሳቸውም ፡ ከነተለቀዩ ፡ እግሮቻቸው ፡ ከነደከመ ፡ ሰውነታቸው ፡ ከነኑሮ ፡ ተስፋቸው ፡ ከነለኝታቸው ፡ መኖራቸውን ፡ ተመለከቱ ! ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ምሬታቸው ፡ ባፋቸው ፡ ውስጥ ፡ በመምረር ፡ ፈንታ ፡ መጣፈጥ ፡ ስሜታቸው ፡ መሰወጥ ፡ ጀመረ ! አለምና ፡ ባለም ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ የሚያስጸ

ይፍ ፡ መጥፎ ፡ መልክን ፡ አዞሮ ፡ ውበቱን ፡ አሳያቸው ! የጉዞዋ ቸው ፡ የሰቃያቸው ፡ የመጨረሻ ፡ አላማ ፡ ትግ ፡ አላቸውና ፡ ወዲያው ፡ የሰውነታቸውን ፡ ክፍሎች ፡ ሁሉ ፡ የሚያዘና ፡ ሙቀት ፡ ዘውስጣቸው ፡ ሲሰራጭ ፡ ተሰማቸው ።

"ወይ ፡ ጉድ ! እነዚያን ፡ ደግ ፡ ሰዎች ፡ በከንቱ ፡ ጠላሁዋ ቸው ! "አሉ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ሲያስቡ ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ። "ሰው ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ሌሎችን ፡ መጥላት ፡ ጉድ ፡ አይደለም ? ርቦኛል ፡ አባካችሁ ፡ አብሉኝ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ---ራብ ፡ አይሰማኝም ፡ ብዬ ፡ የተናገርሁ ፡ እኔ ! ታዲያ ፡ ጆሮዋቸው ፡ የተናገርሁትን ፡ ቃል ፡ ትቶ ፡ ያልተናገርሁትን ፡ አሳብ ፡ ካልሰማ ፡ ብዬ ፡ በነሱ ፡ ማዘንና ፡ እነሱን ፡ መጥላት ፡ ይገባኛል ? የለም ! እንዲህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ከከንቱነት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ የለውም ! ከንቱነት ፡ ነው ! ይቅር ፡ በለኝ ፡ ጌታዬ ! "

ወዲያው ፡ " ጉድጉድጉድጉድጉድ --- ጉድጉድጉድ --- " የሚል ፡ ድምጽ ፡ የሰሙ ፡ መሰላቸውና ፡ ፊታቸውን ፡ ድምጹን ፡ ወደ ፡ ሰሙበት ፡ አቅጣጫ ፡ መለስ ፡ አድርገው ፡ እያዩ ፡ ቢያዳምጡ ፡ በብዙ ፡ ደንጋዮች ፡ መሀከል ፡ እዬተማታ ፡ እያ ለፈ ፡ አንድ ፡ ሰባራ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ እንደ ፡ ትንሽ ፡ ፏዋፏዌ ፡ ሆኖ ፡ የሚወርደው ፡ ባጠገባቸው ፡ ያለው ፡ የወ ንዝ ፡ ውሀ ፡ መሆኑን ፡ ስላዩ ፡ እስከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሳይሰ ሙትና ፡ ሳያዩት ፡ በመቆዬታቸው ፡ ተገረሙ ። ለካ ፡ አእምሮ ፡ በሌለበት ፡ ጆሮም ፡ ቢሆን ፡ አይን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ህዋሳት ፡ የሉም ! ህዋሳት ፡ ሁሉ ፡ ያእምሮ ፡ ጭፍሮች ፡ ስለሆኑ ፡ ያባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ አእምሮ ፡ ሌላውን ፡ ሁሉ ፡ ትቶ ፡ ወዳንበሳውና ፡ ወደ ፡ ቀፎ ፡ አውራጆች ፡ ጭብጦ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ጆሮዎቻቸው ፡ አይኖቻቸው ፡ አፍንጫቸው ፡ ፊት ፡ አንበሳውን ፡ ሁዋላም ፡ የስል ቻዋን ፡ ጭብጦ ፡ ብቻ ፡ ያዩ ፡ ይሰሙ ፡ ያሸቱ ፡ ነበር ። አእምሮዋ ቸው ፡ አንበሳውንና ፡ ጭብጦውን ፡ ወዳባይ ፡ ቆላ ፡ ሸኝቶ ፡ ከተመ ለሰ ፡ በሁዋላ ፡ ግን ፡ ጆሮዎቻቸውና ፡ አይኖቻቸው ፡ ባካባቢያ ቸው ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ መስማትና ፡ ማየት ፡ ጀመሩ ።

አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ የታሰሩ ፡ እግሮቻቸውን ፡ ከተዘረጉ
በት ፡ ሰብስበው ፡ ሽመላቸውንና ፡ ኮፈዳቸውን ፡ ከዱወደቁበት ፡
አንስተው ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ በሽመላቸው ፡ ተደግፈው ፡ ተነስተው ፡
ወደ ፡ ወንዝዋ ፡ ሄዱና ፡ በፍኛቸው ፡ እያፈሱ ፡ ከጠጡ ፡ በሁዋላ ፡
አንድ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ፉዋፉዋቴውን ፡ ይመለ
ከቱ ፡ ጀመር ።

" ይገርማል ! ውሀው ፡ ከገደልዋ ፡ ሲወርድ ፡ ልክ ፡ እንደሚ
ታሰብ ፡ ወተት ፡ ነጭ ፡ ነው ፤ እገደልዋ ፡ ስር ፡ ከደረሰ ፡ በሁዋላ ፡
ግን ፡ እዚያ ፡ የተጠራቀመው ፡ እንዴት ፡ ይጠቁራል ! እንዴት ፡
ይጠራል ! ከውሀው ፡ ስር ፡ ያሉት ፡ ድንጋዮች ፡ ሁሉ ፤ ጠጠሮች ፡
ሳይቀሩ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ይቆጠራሉ ! እስቲ ፡ ቆይ ፡ ልቁጠር ፡
አንድ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ አራት ፡ ቆይ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡
አይ ፤ - - - አልቻልሁም ፤ ተደባለቀብኝ ! " አሉ ፡ አባ ፡ ትንሽ ፡
እንደ ፡ መሳቅ ፡ አሉና ።

ከዚያ ፡ መነኩሴው ፡ አሸዋ ፡ መቁጠሩ ፡ እንዳልሆነላቸው ፡
ሲረዱ ፡ እሱን ፡ ትተው ፡ በተቀመጡበት ፡ እንዳሉ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡
የፉዋፉዋቴውን ፡ አወራረድና ፡ እታች ፡ የሚጠራቀመውን ፡ ውሀ ፡
እያዩ ፡ ያደንቁ ፡ ጀመር ። ይልቁንም ፡ እታች ፡ የተጠራቀመውን ፡
ውሀ ፡ ትኩር ፡ ብለው ፡ በተመለከቱት ፡ መጠን ፡ ውበቱ ፡ ጥራቱና ፡
በራድነቱ ፡ ጠራቸው ፤ አባበላቸው !

" ገብቸ ፡ ብታጠብ ፡ ራቁቴን ፡ እንደሆንሁ ፡ ሰው ፡ ይደርስ
ብኝ ፡ ይሆን ? እዚህ ፡ ምን ፡ ሰው ፡ ይመጣል ? ቀፎ ፡ አውራጆቹ ፡
አሁን ፡ ሲመለሱ ፡ አይችሉ ! መንገደኛም ፡ ከመንገድ ፡ ወጥቶ ፡
ወዲህ ፡ የሚመጣበት ፡ ምክናያት ፡ የለ ! ልግባና ፡ ልታጠብ ! "
አሉና ፡ ቆባቸውን ፡ ደበሎዋቸውን ፡ ነጠላቸውን ፡ ቀሚሳ ፡ ሱሪያ
ቸውን ፡ ያንገት ፡ ክታባቸውን ፡ አውልቀው ፡ እግሮቻቸው ፡ የታ
ሰሩበትን ፡ ዳባ ፡ ለመፍታት ፡ ቢሞክሩ ፡ ማሰሪያው ፡ ውሉ ፡ የጠፋ ፡
በመሆኑ ፡ አስቸጋሪ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በሁዋላ ፡ እንደገና ፡
ማሰሩን ፡ የማያውቁበት ፡ ስለመሰላቸው ፤ እንዲሁ ፡ እንዳለ ፡
ይዘውት ፡ ውሀው ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ። " እፍ ፡ - - እፍ ፡ እፎይ ! እ ፡ እ ፡
እንዴት ፡ ያበርዳል ! እ ፡ እፎይ ! " አሉ ፤ እስካንገታቸው ፡ ጠል
ቀው ፡ ሲቀመጡ ።

እዚያ፡ እዩ፡ተገላበጡ፡ ገላቸውን፡ ሲያጥቡ፡ አንዳንድ፡ ጊዜም፡ እንደተቀመጡ ፡ ጉንጫቸውን ፡ ነፍተው ፡ እንደ ፡ ዋናተኞች ፡ እጆቻቸውን ፡ እያፈራረቁ ፡ ውሀውን ፡ ሲጠፉ ፡ ቆይተው፡ ሲበቃቸው ፡ ተለቃልቀው ፡ ወጡና ፡ ሰው ፡ ሳይደርስባቸው ፡ ለመልበስ፡ ሰውነታቸውን ፡ በሱሪያቸውም ፡ በነጠላቸውም ፡ ያደራርቁ ፡ ጀመር። እንደ ፡ ቆሙ ፡ የፊት ፡ ከፍለ ፡ አካላቸውን ፡ ዘቅዝቀው ፡ ቢመለከቱ ፡ እንጀታቸው ፡ ከቦታው ፡ ሸሽቶ ፡ ከጀርባቸው ፡ ጋር ፡ ተጣብቆ ፡ አይታይም ። ያንጀታቸው ፡ ከቦታው ፡ መጥፋት፡ ደረታቸውንና ፡ ድሮ ፡ አንጀታቸው ፡ ከነበረበት ፡ በታች ፡ ያለ ፡ አካላቸውን ፡ ከድሮው ፡ የበለጠ ፡ አጉልቶ ፡ ስላሳያቸው ፡ ባለፈው፡ ሌሊት ፡ ዛፍ ፡ ታቅፈው ፡ በልባቸው ፡ እዩ፡ተሳቡ ፡ የወጡት ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ፡ በዚያ ፡ ምክንያት ፡ ያበጠ ፡ መስለዋቸው ፡ ፈገግ ፡ ተው ፡ ከላይ ፡ እስከታች ፡ እጃቸውን ፡ ጫን ፡ እያደረጉ ፡ ቢዳብሱት ፡ ሕመም ፡ አልሰማቸው ፡ አለ ። " እሁሁ ---- ! ተመስገን ፡ ጌታዬ ፡ እብጠት ፡ ቢሆን ፡ እንዲህ ፡ ስጫነው ፡ ያመኝ ፡ ነበር ፡ ደህና ፡ ነኝ ! አሉና ፡ ቶሎ ፡ ልብሳቸውን ፡ " ለበሱ ።

በውሀ ፡ ተነክረው ፡ ከወጡ ፡ በሁዋላ ፡ ትንሽ ፡ በርታ ፡ አሉ። "ተመስገን ፡ ጌታዬ ! ውሀ ፡ ውስጥ ፡ እንድነክር ፡ ያሳሰብኸኝ ! ቀዝቃዛ ፡ ውሀ ፡ የቀለጠ ፡ ብረት ፡ ያጠነክራል ፡ ሲሉ ፡ ከንቱ ፡ ተረት ፡ ይመስለኝ ፡ ነበር ፡ ለካስ ፡ እውነት ፡ ነው ! ከቀድሞ ፡ አሁን ፡ ተሻለኝ ፡ " አሉና ፡ -- ሽመላቸውንና ፡ ኮፊዳቸውን፡ አንስተው ፡ ጉዞዋቸውን ፡ ለመቀጠል ፡ ተነሱ ።

መጀመሪያ ፡ የሚገኘው ፡ መንደር ፡ መነኩሴው ፡ ካሉበት ፡ ቅርብ፡ መስሎ፡ ይታያል። ነገር ፡ ግን ፡ በመሀከሉ ፡ ከፉ፡ አቀበት ፡ ስላለና ፡ መንገዱ ፡ አቀበቱን ፡ ቀጥታ ፡ በመውጣት ፡ ፈንታ ፡ እባብወረድ ፡ ስለሆነ ፡ ቢዘረጋ ፡ በትንሹ ፡ አራት ፡ እጥፍ ፡ ይሆ ናል ።

አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ትንሽ ፡ ቆም ፡ ብለው ፡ መንደሩን ፡ ከዚያ ፡ አቀበቱንና ፡ መንገዱን ፡ ሲመለከቱ ፡ ቆዩና ፡ ምርኩዛቸውን ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ ያዘው ፡ ከውስጥ ፡ በደም ፡ ከጡጫ ፡ በውሀ ፡ በዘበዘበ ፡ ዳባ ፡ የታጀለ ፡ እግሮቻቸውን ፡ ሲጎትቱ ፡ የመንገዱን ፡ አፈርና ፡ ጠጠር ፡ እዩ፡ጠረጉ ፡ የዚያን ፡ አቀበት ፡ እባብወ

ረድ ፡ መንገድ ፡ ጀመሩ ።

ወዲያ ፡ ሄደው ፡ እንደገና ፡ ታጥፈው ፡ ወዲህ ፡ ሲመለሱ ፡ እንደገና ፡ ወዲያ ፡ ሲሄዱ ፡ ደግሞ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ወዲህ ፡ ሲመለሱ ፡ ይቆዩና ፡ ቆመው ፡ የሄዱትንና ፡ ገና ፡ የሚሄዱትን ፡ መንገድ ፡ ያመዛዝናሉ ። ገና ፡ ምንም ፡ አልሄዱም ! ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ሄደው ተመልሰው ፤ ሄደው ፡ ተመልሰው ፤ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ይቆሙና የሄዱትን ፡ ገና ፡ ከሚሄዱት ፡ መንገድ ፡ ያመዛዝናሉ ። አሁንም ፡ ገና ፡ ያልሄዱት ፡ ይበልጣል ! ደከማቸው ! ዛሉ ! እግሮቻቸው ፡ እሳቸው ፡ የፈለጉትን ፡ ትተው ፡ ባልፈለጉት ፡ ላይ ፡ ይቆሙ ፡ ጀመር ! ደልዳላውን ፡ መሬት ፡ ስተው ፡ በንቅፋት ፡ ላይ ፡ ሲቆሙ ፤ እንቅፋቱ ፡ ለጋሬጣ ፤ ጋሬጣው ፡ መልሶ ፡ ለንቅፋት ፡ ሲያቀባብሉዋቸው ፡ ቁስላቸው ፡ ተሸፍኖ ፡ የታሰረበት ፡ ሲባን ፡ እየተበጣጠሰ ፡ ይወድቅ ፡ ጀመር ። ከዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ እግራቸውን ፡ ተብትበው ፡ ትንሽም ፡ አርፈው ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ጉዞ ፡ ጀመሩ ። ደግሞ ፡ እንደገና ፡ በቆሰለ ፡ እግራቸው ፡ እንቅፋት ፡ ሾህና ፡ ጋሬጣ ፡ እየጠረጉ ፡ ወዲያ ፡ ሄዶ ፡ ወዲህ ፡ መመለስ ፡ ጀመሩ ! እንዲያ ፡ ሲሰቀዩ ፡ እንዲያ ፡ ሲንገላቱ ፡ ውለው ፡ እኩለ ፡ ቀን ፡ ላይ ፡ አቀበቱን ፡ ወጥተው ፡ አፋፉ ፡ ደረሱ ።

አቀበቱን ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ጉልበታቸው ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ጀመረ ፡ ራሳቸውን ፡ አዞራቸው ፡ አይኖቻቸው ፡ የሚቆሙበትን ፡ መሬት ፡ አጥርተው ፡ ማየት ፡ አቃታቸው ። ወዲያው ፡ መንገዱን ፡ ትተው ፡ ወዳንዲት ፡ ዛፍ ፡ ሄዱና ፡ እስርዋ ፡ በግድ ፡ ሲጋደሙ ፡ እምቡዋለሌ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ወደቁ ፡ ሁሉ ፡ የተጋደሙባት ፡ መሬት ፡ ይዛቸው ፡ ስትዞር ፡ ብዥ ፡ ቆዩኝ ። በሁዋላ ፡ ትንሽ በትንሽ ፡ መሬትዋ ፡ እየረጋች ፡ እሳቸውም ፡ ጸጥ ፡ ማለትና ፡ ሀዋሳታቸውን ፡ በሙሉ ፡ መግዛት ፡ ጀመሩ ።

ከዚያ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ተጎትተው ፡ ዛፉን ፡ ተደግፈው ፡ ተቀመጡና ፡ ጥዋት ፡ የተነሱበትን ፡ ቦታ ፡ ዘቅዝቀው ፡ ቢመለከቱ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ዘሎ ፡ የሚደረስበት ፡ መሰላቸው ። ዘወር ፡ ብለው ፡ መንደሩ ፡ ያለበትን ፡ ቢመለከቱ ፡ ጥዋት ፡ ካቀበቱ ፡ በታች ፡ ቆመው ፡ ካዩበት ፡ ቦታ ፡ አስር ፡ ጊዜ ፡ ርቆ ፡ የተቀመጠ ፡ መስሎ ፡ ታያቸውና ፡ አሞታቸው ፡ ፈሰሰ ። ያነለት ፡ እመንደር ፡

ደርሰው ፡ እህል ፡ ቀምሰው ፡ የሚራቸውን ፡ ሸህና ፡ ጋሬጣ ፡ እስ ወጥተው ፡ እሳት ፡ ሞቀው ፡ እንቅልፍ ፡ ተኝተው ፡ ለማደር ፡ የነበራቸው ፡ ተስፋ ፡ ሁሉ ፡ ከውስጣቸው ፡ ጠፍቶ ፡ ፍጹም ፡ ባይ ነት ፡ ተሰማቸው ። "ይህ ፡ የእግዚአብሄር ፡ ቁጣ ፡ ካልሆነ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ሊባል ፡ ይችላል ? እዚህ ፡ የነበረው ፡ መንደር ፡ እኔ ፡ ስመጣ ፡ ሸሽቶ ፡ እዚያ ፡ ሄደ !" አሉ ፡ አባ ፡ መንደሩ ፡ ከሳቸው ፡ ሸሽቶ ፡ ሄዶ ፡ የተቀመጠበትን ፡ በጃቸው ፡ እያመለከቱ ። ይህ ፡ የእግዚአብሄር ፡ ቁጣ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እግር ፡ አውጥቶ ፡ ከቦታው፡ ተነስቶ ፡ የሚሄድ ፡ መንደር ፡ እንደሌለ ፡ የታወቀ ፡ ነው ! ምነው ፡ ርዳኝ ፡ እባክህ ፡ ጌታዬ !" ሲሉ ፡- "የሸሽሽ--- ነይ ፡ ተመ ሊሽ !" አለ ፡ አንድ ፡ ድምፅ ። መነኩሴው ፡ ደንግጠው ፡ ዞሬያ ገባውን ፡ ዘወርወር ፡ ብለው ፡ ባይናቸው ፡ ሲገዘሙ ፡ እሳቸው ፡ ከወደመጡበት ፡ መንገድ ፡ አንዲት ፡ የተጫነች ፡ በቅሎ ፡ ወደ ሳቸው ፡ ስትመጣ ፡ አዩ ። ወዲያው ፡ በቅሎዋን ፡ ተከትሎ ፡ አንድ ሰው ፡ እዬሮጠ ፡ ብቅ ፡ አለ ። "ለበቅሎ ፡ ያዘነ ፡ ውግዝ ፡ ከማሪ ምስ ፡ አሉ ፡ አባ ፡ እውነታቸውን ፡ ነው !" አለ ፡ በቅሎዋን ፡ ተከ ትሎ ፡ የሚሮጠው ፡ ሰው ። አባ ፡ አለም ፡ ስምኒን ፡ አላዩም ፡ ነበር ። በቅሎዋ ፡ መነኩሴው ፡ ወዳሉበት ፡ ዛፍ ፡ ሄዳ ፡ ስትቆ ምና ፡ ዛፉን ፡ ተደግፈው ፡ የተቀመጡትን ፡ መነኩሴ ፡ ሲያይ ፡ ብቻ ፡ ሰው ፡ የለም ፡ መስሎት ፡ ብቻውን ፡ በመናገሩ ፡ ትንሽ ፡ የፍረት ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ "እኔን ፡ ተሸክማ ፡ ጋራውን ፡ መውጣት ፡ ይደክማታል ፡ ብዬ ፡ አዝኘ ፡ ብወርድላት ፡ እዚህ ፡ ትታኝ ፡ ልትሄድ ፡ ስለፈለገች ፡ ገርሞኝ ፡ ብቻየን ፡ ተረት ፡ ተረ ትሁ !" አለ ።

" ቆመችኮ ፡ አልሄደችም ፡ " አሉ ፡ አባ ።

" አዎ ፡ ቆመች ፡ ብቻ ፡ እስዎን ፡ ስታይ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የቆ መች ። እስዎ ፡ ደክሞዎ ፡ ነው ፡ እዚ ----- ያረፉ ? አለ ፡ ሰው ዬው ፤ በቅሎዋ ፡ እንዳታመልጠው ፡ ዛቡን ፡ እስኪይዝ ፡ ድረስ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ በግር ፡ ጥፍሮቹ ፡ ቆሞ ፡ ወደሷዋ ፡ እያጠቀሰ ። በቅ ሎዋ ፡ እንኩዋንስ ፡ ልትሮጥ ፡ ከቆመችበት ፡ አልተንቀሳቀሰችም።

" ካቀበቱ ፡ ስር ፡ ጥዋት ፡ የተነሳሁ ፡ እመንደር ፡ ደርሼ ፡ እህል ፡ ቀምሼ ! አርፌ ፡ አድራለሁ ፡ ብዬ ፡ አስቤ ፡ ነበር ፡ የግሬ ፡

ቁስል ፡ አላስሄደኝ ፡ ብሎ ፡ ዛሬም ፡ እውጭ ፡ ላድር ፡ ነው ! ”
አሉ ፡ አባ ፡ የሰውዬውን ፡ አይን ፡ ወደግራቸው ፡ ለመሳብ ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ቀኝ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ግራ ፡ እግራቸውን፡ እያዩና ፡ እዬዳበሱ ።

“እመንደር ፡ ድረስስ ፡ እኔ ፡ በበቅሎ ፡ በወሰድሁዎ! እዚያ ፡ የሚያውቁት ፡ ሰው ፡ አለ ? ” አለ ፡ ሰውዬው ፡ ፊታቸውን ፡ ብቻ፡ አተኩሮ ፡ እያዬ ።

“ የእግዚአብሄር ፡ እንግዳ ፡ ነኝ ፡ ስል ፡ ቤት ፡ አይነፍጉኝም፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማውቀው ፡ ሰውስ ፡ የለኝም ።”

“ የሚያውቁት ፡ ሰው ፡ ከሌለዎማ ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ ያድራሉ ፡ ቤት ፡ ለግዜር ፡ ነው ። ”

“ እግዚአብሄር ፡ ይስጥዎ ! ” አሉና ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ከተቀመጡበት ፡ ለመነሳት ፡ ቢሞክሩ ፡ አቃታቸው ።

“ ዉዉዉ - - - - - እግርዎ ፡ ምን ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ደም ፡ የሚተፋ ? አባቴ ! ” አለ ፡ ሰውዬው ፡ ደግፎ ፡ አስነስቶ ፡ እበቅሎ ፡ ላይ ፡ ሲያስቀምጣቸው ፡ እግሮቻቸው ፡ የታሰሩበትን ፡ ጻባ ፡ የዘለቀውን ፡ ደም ፡ ማየቱ ፡ ብቻ ፡ ከሳቸው ፡ የበለጠ ፡ አሳ ምሞት ።

“ እ ፡ እ ፡ እ ፡ እ ፡ - - - ሾህና ፡ ጋሬጣ ፡ ወጋቶኝ ፡ እንቅፋት፡ መትቶኝ !” አሉ ፡ አባ ፡ ያበጡ ፡ እግሮቻቸው ፡ ርካብ ፡ ሲነካቸው ፡ እሞዋቸው ።

“ ዱር ፡ ገብተው ፡ ይሮጡ ፡ ኖሮዋል ? ”

“ ኧረ ፡ ከመንገድም ፡ አልወጣሁ ፤ እንዲያው ፡ በሌሊት ፡ ሲጉዋዙ ፡ እንቅፋት ፡ ጋሬጣ ፡ ሾህ ፡ ማየቱ ፡ የማይቻል ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ”

ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ይመስል ፡ ለምን ፡ ሌሊት ፡ ብቻዎን ፡ ይሄ ዳሉ ? ”

“ እንዲህ ፡ አሁን ፡ ሳይሆን ፡ ሊቀር ፡ ለተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለመድረስ ፡ አስቤ ፡ ነበር ፡ ቀን ፡ ከሌት ፡ የም ሄድ ።”

“የተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ምን ፡ አለ? ድግስ ፡ አለ?”

“ጳጳሱ ፡ ቁምስና ፡ ይሰጣሉ ።”

“ምንድር ፡ ነው ፡ ቁምስና?”

“ለመነኩሴ ፡ የሚሰጥ ፡ ማእርግ ፡ ነው ፡”

“እህ! ቅምስና ፡ የመለኩሴ ፡ ሹመት ፡ መሆኑ ፡ ነው! አላውቅም ፡ ነበር ።”

“ቅምስና ፡ አይደለም ፤ ቁምስና!” አሉ ፡ አባ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብለው ።

“ሰምቸው ፡ የማላውቀውን ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ልወቀው ? አባቴ ፡ ሰው ፡ እንደዬሚውልበት ፡ ነው ! አሁን ፡ እስዎ ፡ በዚህ ፡ ጠበንጃ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዝባዝንኪ ፡ ሁሉ ፡ ያውቁታል ? እኔም፡ ያ ፡ ቅድም ፡ ያሉት ፡ ምን ፡ ነበር ?”

“ ቁምስና ፡ ”

“ አዎ ፡ እሱን ፡ አለማወቄ ፡ የማልውልበት ፡ ስለ ሆነ ፡ ነው ። ”

“ እውነት ፡ ነው ። ” አሉ ፡ አባ ።

እንዲህ ፡ እያወሩ ፡ ሳባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ያመት ፡ መንገድ ፡ መስሎዋቸው ፡ ወደነበረው ፡ መንደር ፡ ወዲያው ፡ ደረሱ ።

# ምእራፍ ፡ ፴፫ ፡

## ስርቅታ ፡

ይሁን ፡ በፈቃዱ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔን ፡ እያጫወተ ፡ እቤቱ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ከበቅሎ ፡ ሲያወርዳቸው ፡ “ እባክዎ ፡ ቶሎ ፡ ትንሽ ፡ እህል ፡ እንድቀምስ ፡ ያድርጉኝ ፡ በጣም ፡ ርቦኛል ! ” አሉ ፡ መነኩሴው ፡ የውነተኛ ፡ ስሜታቸውን ፡ ለቀፎ ፡ አውራጆች ፡ ባለመንገራቸው ፡ የተቀጡት ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ይሉኝታ ፡ የሚባለውን ፡ ጥፋት ፡ እንዳይደግሙ ፡ አስተምሮዋቸው ።

“ ቶሎ ፡ እህል ፡ ቶሎ ፡ እህል ! ” አለ ፡ ይሁን ፡ በፈቃዱ ፡ ምኞቱ ፡ መምጣቱን ፡ አውቃ ፡ ልትቀበለው ፡ እዩሮጠች ፡ ስትወጣ ።

የይሁን ፡ ባለቤት ፡ ባልዋ ፡ የሚመጣበትን ፡ ጊዜ ፡ ካለማወቅዋም ፡ ሌላ ፡ የምሳ ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ የራት ፡ ጊዜ ፡ ሳይደርስ ፡ እንግዳ ፡ ይዞ ፡ በመምጣቱ ፡ ትንሽ ፡ ተደነጋገራትና ፡ “ በስራት ፡ የተሰናዳ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ የዋለ ፡ እንጀራ ፡ በተልባ ፡ ወይም ፡ በርጎ ፡ ይሆናል ? ” አለች ፡ እንግዳው ፡ እንዳይሰሙ ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ በጆሮው ።

“ ወጥ ፡ ገና ፡ አልተሰራም ፡ አሉ ፡ አባቴ ! እንጀራ ፡ በተልባ ፡ ወይም ፡ በርጎ ፡ ወይም ፡ ተልባና ፡ ርጎ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በሻርዶ ፡ ቀምሰው ፡ ቢቆዩ ፡ ምን ፡ አለ ? ” አለ ፡ ይሁን ።

“ ሻርዶ ? ጥሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ! ማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ ጥሩ ፡ ነው !

ራብ ፡ ባለበት ፡ ምርጫ ፡ አለ ? ምርጫ ፡ ራብ ፡ ሳይኖር ፡ ነው ! ምርጫ ፡ ምሳ ፡ በልቶ ፡ ራት ፡ ለደነመ ፡ ለተመቸው ፡ ሆድ ፡ ነው ! ራብ ፡ በስለት ፡ ለሚዘለዝለው ፡ ለሚያባጥለው ፡ ሆድ ፡ አይደለም ! ራብ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ የሚቀራመተው ፡ ሆድ ፡ ዋና ፡ ምርጫው ፡ ቶሎ ፡ ተገኝቶ ፡ ራብን ፡ የሚያስታግስ ፡ ትንሽ ፡ የሚያስተነፍስ ፡ ነገር ፡

ነው ! ከራብ ፡ ስቃይ ፡ የሚያሳርፍ ፡ የራብን ፡ ስለት ፡ ጥርስ ፡ የሚያጎለድፍ ፡ ከሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ ጥሩ ፡ ነው !

ይሁን ፡ በፈቃዱ ፡ በቅሎዋን ፡ አራግፎና ፡ አስሮ ፡ ድርቆሽ ፡ ጥሎላት ፡ እስኪመለስ ፡ ምሽቱ ፡ ተልባዋን ፡ በርኅ ፡ መትታ ፡ ሽርዶ ፡ ካደረ ፡ እንጀራ ፡ ጋር ፡ ለመነኩሴው ፡ አቅርባላቸው ፡ ሲበሉ ፡ ደረሰ ።

የይሁን ፡ ባለቤት ፡ ሁለት ፡ እንጀራ ፡ በትንሽ ፡ ሌማትና ፡ ሽርዶውን ፡ አቅርባ ፡ እያወጣች ፡ ልትጋብዛቸው ፡ መጥታ ፡ እመነኩሴው ፡ ፊትለፊት ፡ ስትቀመጥ ፡ በማመስገን ፡ ፈንታ ፡ ልባቸው ፡ ረገጣት ! በመውደድ ፡ ፈንታ ፡ ጠሉዋት !

ያንጊዜ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ እንዲያ ፡ ርበዋቸው ፡ ሳሉ ፡ እንዲያ ፡ እህል ፡ ሁሉ ፡ የማይበቃቸው ፡ መስሎዋቸው ፡ ሳሉ ፡ የተመኙት ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ እንጀራ ፡ በምንም ፡ አይነት ፡ ወጥ ፡ አቅርቦ ፡ እጃቸው ፡ መቁረስ ፡ አፋቸው ፡ መጉረስ ፡ የሚችለውን ፡ ያክል ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ በልተው ፡ ራባቸውን ፡ እንዲያስወግዱ ፡ ቤቱን ፡ የሁዋሊት ፡ ዘግቶባቸው ፡ የሚሸሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሁለት ፡ እንጀራ ፡ አቅርቦ ፡ እሱንም ፡ እንዴት ፡ እንደሚጎርሱት ፡ እፊታቸው ፡ ተቀምጦ ፡ የሚመለከት ፡ ታዛቢ ፡ አልፈለጉም ፡ ነበር !

" ጠላ ፡ ልስጥዎ ፡ ወይስ ፡ ወተት ? " አለች ፡ ባለቤትዋ ፡ መሸያውን ፡ ከወጣችላቸው ፡ በሁዋላ ።

" ወተት ! " አሉ ፡ አባ ፡ ቶሎ ፡ ብለው ። ዋናው ፡ ነገር ፡ ቶሎ ፡ ከፊታቸው ፡ እንድትሄድ ፡ ነው !

ወተት ፡ ከጉዋዳ ፡ ይዛላቸው ፡ እስክትመጣ ፡ አራት ፡ አምስት ፡ ጉርሻ ፡ በርከት ፡ እያደረጉ ፡ ጎርሰው ፡ ብዙም ፡ ሳያላምጡ ፡ የዋጡት ፡ የህል ፡ ናፍቆታቸውን ፡ ትንሽ ፡ መለስ ፡ አደረገላቸው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ ከወተቱ ፡ ግማሹን ፡ ያክል ፡ እንደ ፡ ጠጡ ፡ ትንሽ ፡ በልተው ፡ አንዱን ፡ እንጀራ ፡ እንኩዋ ፡ ሳይጨርሱ ፡ ያ ፡ ሲቀርብ ፡ አንሶ ፡ የታያቸው ፡ እንጀራ ፡ በዝቶ ፡ አሸነፋቸው ። ወዲያው ፡ ራቡ

ሲያልፍ ፡ እንቅልፍና ፡ ድካም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ያን ገላቱዋቸው ፡ ጀመር ። መጨረሻ ፡ የጎረሱት ፡ ባፋቸው ፡ እንዳለ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ባፍንጫቸው ፡ ማንኮ ዋረር ፡ ስለጀመሩ ፡ ይሁንና ፡ ባለቤቱ ፡ በግድ ፡ ቀስቅሰው ፡ የጎረሱትን ፡ እንዲውጡ ፡ አደረጉና ፡ እዚያው ፡ በተቀመጡ በት ፡ ትራስ ፡ አምጥተው ፡ አጋደሙዋቸው ።

" እንዲህ ፡ ሆነው ፡ የተኙት ፡ እንቅልፍ ፡ እረፍትም ፡ አይሆናቸው ! " አለ ፡ ይሁን ።

" እንዴት ? "

"እግራቸው ፡ የተሸከመውን ፡ አታይም ? ይህን ፡ በደ ምና ፡ ባፈር ፡ ባሸዋ ፡ ጭምር ፡ የተመረገ ፡ ዳባ ፡ በግራቸው ፡ ተሸክመው ፡ የተኙት ፡ እንቅልፍ ፡ የሚያሳርፍ ፡ ነው ? "

"ታዲያ ፡ ውሀ ፡ ላሙቅና ፡ ልጠባቸዋ ! "

"አይነቁም ? "

"ቀዝቃዛ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሙቅ ፡ ውሀ ፡ አያነቃምኮ "

"እንግዲያስ ፡ አሙቂና ፡ እጠቢያቸው ፡ "

ይሁን ፡ በፈቃዱ ፡ የመነኩሴውን ፡ እግር ፡ በዳባ ፡ ተጠ ቅሎ ፡ ከታሰረበት ፡ ሲፈታው ፡ በደምና ፡ ባፈር ፡ ባሸዋ ፡ የተ ጨማለቀው ፡ ዳባ ፡ ከውጭ ፡ እንደሚያሳዩው ፡ የሚያስጸይ ፍና ፡ የሚያስፈራራ ፡ አይደለም ። ሾህና ፡ ጋሬጣ ፡ የወጋለት ፡ አሁንም ፡ ከነደሙ ፡ ያልወጣለት ፡ ከነጋሬጣውና ፡ ከነሾሁ ፡ እንዳበጠ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ እግር ፡ የነበረ ፡ ለመሆኑ ፡ ምልክቱ ፡ አልጠፋም ። ይልቁንም ፡ የረጋው ፡ ደም ፡ ከላዩ ፡ እየታጠበ ፡ በጠራ ፡ መጠን ፡ መልካምነቱ ፡ ይህና ፡ ሆኖ ፡ እዩ ታዩ ፡ ሄደ ።

"ጨጨጨ . . . . እባክህ ፡ ይህን ፡ እግር ፡ እይልኝ ! እዩሀ ? አሁን ፡ ይህን ፡ እግር ፡ ይዞ ፡ ገዞ ፡ ይሄዳል ፡ ሰው ? " አለች ፡ በዛብሽ ፡ ውበቱ ፡ የይሁን ፡ በፈቃዱ ፡ ምሽት ።

"እንዴት ? "

"የውስጡን ፡ አለባለስ ፡ ብታይ ! ጭራሽ ፡ መሬት ፡ ነክቶ ፡ የማያውቅ ፡ የወይዘሮ ፡ እግር ፡ ይመስላል ! "

"ምን ፡ ነበር ፡ ያሉኝ ? እባክሽ ! አንድ — ትልቅ ፡

ሹመት ፡ ሊሾሙ ፡ የሚሄዱ ፡ ናቸው ፤ የትልቅ ----- መለኩሴ ፡ ልጅ ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ! ”

“እንዲያ ፡ እንጅ ፡ የኛ ፡ ሊቃውንት ! ደሞ ፡ ብለህ ፡ ብለህ ፡ መለኩሴ ፡ ልጅ ፡ ይወልዳል ፡ በል ! ” አለች ፡ በዛብሽ ፡ እዬሳቀች ።

“ባንድ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ሊቃውንት ፡ መች ፡ አነስ ! ጎጃም ፡ የተደነቀበት ፡ ያንቺ ፡ ሊቃውንትነት ፡ ይበቃናል ! ” አለ ፡ ይሁን ፡ አሽሙር ፡ ባስጌጠው ፡ ፊት ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ፡ ምሽቱን ፡ የጎድን ፡ እያዬ ።

“መችም ፡ ታንተ ፡ እሻላለሁ ፡ ባይሆን ፡ እንኩዋ ፡ መለ ኩሴ ፡ ልጅ ፡ የማይወልድ ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ ፡-” አለች ፡ በዛብሽ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ፍርጥምታ ፡ የጎድን ፡ የሚያዩ ዋትን ፡ አይኖች ፡ የጎድን ፡ እያዬች ።

“እናቢ ፡ ተግባሩ ፡ መለኩሴ ፡ አይደሉም ? ለምን ------ አንድ ፡ ብቻ ፡ እንኩዋ ፡ አይደለም ! አራት ፡ ልጆች ፡ አሉዋ ቸው ? ”

“ሳይመለኩሱ ፡ የወለዱዋቸው ፡ ናቸዋ ! ከመለኮሱ ፡ የወ ለዱዋቸው ፡ ናቸው ፡ አሉህ ? ”

“ታዲያ ---- የኔህ ፡ አባት ፡ ሳይመለኩሱ ፡ ሊወልዱ ፡ አይ ችሉም ፡ ያለሽ ፡ ማነው ? ”

“ሳይመለኩሱማ ፡ ሊወልዱ ፡ ይችላሉ ፡ ሳይመለኩሱ ፡ የወለዱት ፡ የመለኩሴ ፡ ልጅ ፡ አይባልም ፡ እንጂ ! ያለዚያ ---- ያንተም ፡ የኔም ፡ አባት ፡ መልኩሰው ፡ ስለሞቱ ፡ የመለኩሴ ፡ ልጆች ፡ መባል ፡ አለብን ! ኧረ ፡ እንዲያው ፡ አብዛኛው ፡ ሰው ፡ የመለኩሴ ፡ ልጅ ፡ መባሉ ፡ ነው ! ”

“እህ ! እውነትም ፡ ምሽቴ ፡ ሊቃውንት ፡ ሆናልኛለች ! ” አለ ፡ ይሁን ፡ ክርክሩን ፡ ትቶ ፡ ጉንጭዋን ፡ እዬደባበሰ ። በክ ርክር ፡ ልትረታው ፡ ነበር ፡ በመደባበስ ፡ ረታት ።

“በይ ፡ ተነሺ ፡ እንግዴህ ! ” አለ ፡ እርጥብ ፡ እጆችዋን ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ትክሻዎቹ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጋ ፡ እቅፉ ፡ ላይ ፡ የወደቀች ፡ ምርኮኛውን ። “ተነሺ ፡ የፍዬል ፡ ሞራ ፡ እናቅል ጥና ፡ ቁስላቸውን ፡ ሁሉ ፡ ቀብተን ፡ በንጹህ ፡ እራፊ ፡ ጥቅልል ፡

አድርገን ፡ እንሰርላቸው ፡፡ እግራቸው ፡ በሞራ ፡ ታጅሎ ፡ ያደረ ፡ እንደሆነ ፡ ነገ ፡ ጋሬጣና ፡ ሾህ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ እዩተፈተለከ ፡ ነው ፡ የሚወጣ ! ”

ማታ ፡ በራት ፡ ጊዜ ፡ ባልና ፡ ምሽቱ ፡ መነኩሴውን ፡ ቀስቅሰው ፡ ለማብላት ፡ ቢሞክሩ ፡ የተጫናቸው ፡ እንቅልፍና ፡ ድካም ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ አልንቀሳቀስ ፡ ስላሉ ፡ እንዲሁ ፡ የጋራ ፡ ተሸክመው ፡ ወስደው ፡ እንግዳ ፡ ሲመጣ ፡ እንዲተኛ በት ፡ ተሰናድቶ ፡ በሚኖረው ፡ መደብ ፡ አስተኙዋቸው ፡፡

መንገደኛው ፡ በበነጋው ፡ በጣም ፡ ከረፈደ ፡ በሁዋላ ፡ ቢነቁ ፡ እግሮቻቸው ፡ በዳባ ፡ ፈንታ ፡ በጨርቅ ፡ ታስረው ፡ የቁስል ፡ ስሜት ፡ ይሰማቻው ፡ እንጂ ፡ የብጠቱ ፡ ክብደትና ፡ መነዝነዙ ፡ ጠፍቶ ፡ ራብና ፡ ድካም ፡ ወደዩመጡበት ፡ ሄደው ፡ በጠቅላላው ፡ ቀሎዋቸው ፡ ስላገኙ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡፡ ከዚያ ፡ ተነስ ተው ፡ ውጪ ፡ ደርሰው ፡ ተመልሰው ፡ ጸሀይ ፡ ለመሞቅ ፡ እደጅ ፡ መቀመጣቸውን ፡ በዛብሽ ፡ አዩችና ፡ ሙቅ ፡ ውሀ ፡ ጨው ፡ ጨምራ ፡ እምጥታ ፡ እግሮቻቸውን ፡ ዘፍዝፋላቸው ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ቆዩ ፡ ጋሬጣውም + ሾሁም ፡ በገዛጁ ፡ ሹልክ ፡ እያለ ፡ እዩ ወጣ ፡ በውሀው ፡ ላይ ፡ ይንሳፈፍ ፡ ጀመር ፡፡ የቀረው ፡ ትንሽ ፡ጫን፡ ሲሉት ፡ ይሁን ፡ በፈቃዱ ፡ እንዳለው ፡ እዩተፈተለከ ፡ አንድ ፡ ሳይ ቀር ፡ ሙልጭ ፡ ብሎ ፡ ወጣ ፡፡

አባ ፡ እሰም ፡ ለምኔ ፡ እግራቸውን ፡ በዛብሽ ፡ በንጹህ ፡ ውሀ ፡ ለቅልቃ ፡ አድርቃላቸው ፡ ሰብሰብ ፡ አድርገው ፡ ሲቀመጡ ፡ ባለፈው ፡ ቀን ፡ የነበረው ፡ ስቃያቸው ፡ ራባቸው ፡ መንገላታታቸው ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ታያቸውና ፡ ከዚያ ፡ የገላገሉዋቸውን ፡ ሰዎች ፡ የሚያመሰግኑበት ፡ ቃል ፡ አጥተው ፡ እንባ ፡ ባዘሉ ፡ አይኖች ፡ በዛብሽን ፡ እያዩ ፡ ከንፈሮቻቸው ፡ እዩተንቀጠቀጡ ፡ ዝም ፡ ስላሉ ፡፡–

“ ምነ ? አባቴ ! ” አለች ፡ በዛብሽ ፡፡

“ ምንም ፡ አይደል ! የትናንት ፡ ጭንቀቴና ፡ የዛሬ ፡ ድሎቴ ፡ ታይቶኝ ፡ ነው ! የእግዚያብሄር ፡ መሳሪያዎች ፡ ሆናችሁ ፡ ላደረጋችሁልኝ ፡ አድርጎት ፡ የምለው ፡ ጠፍቶኝ ፡ ነው ! ትንሽም + ትልቅም ፡ ላደረገ ፡ ማመስገኛው ፡ ቃል ፡

እግዚአብሄር ፡ ይስጥልኝ ፡ ስለሆነ ፡ እሱን ፡ ማለት ፡ ውለታ ችሁን ፡ ወደ ፡ ተራ ፡ ውለታ ፡ ደረጃ ፡ የሚያወርድብኝ ፡ መስሎ ፡ ታዩቶኝ ፡ ሌላም ፡ የምለው ፡ አጥቼ ፡ ጨንቆኝ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ አባ ፡ እንባቸው ፡ ቸርፈፍ ፡ ብሎ ፡ በሻከረ ፡ ድምጽ ።

“የእግዚአብሄር ፡ እንግዳ ፡ እያለ ፡ ለሚመጣው ፡ ሁሉ ፡ ከምናደርገው ፡ የተለዩ ፡ ምን ፡ አደረግንልዎ ?”

“እናንተስ ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ መስራት ፡ ልማዳችሁ ፡ ሆኖ ፡ ለኔ ፡ የሰራችሁት ፡ ከሌላው ፡ የተለዩ ፡ አይመስላችሁም ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግንኮ ፡ የበጎ ፡ ስራ ፡ ዋጋው ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ የሚለው ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ የሚሰራለት ፡ ሰው ፡ በሚገኝበት ፡ ሁኔታ ፡ መጠን ፡ ነው ።

“ እንዴት ?  ያሉትን ፡ አላስተዋልሁትም ፡ አባቴ ! ”

“ ለኔ ፡ ያደረጋችሁትን ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ እንደኔ ፡ ርቦት ፡ ደክሞት ፡ እግሮቹ ፡ በጋሬጣና ፡ በሾህ ፡ ሽባ ፡ ሆነው ፡ መንቀሳ ቀስ ፡ አቅቶት ፡ አይኑ ፡ እያዩ ፡ አውሬ ፡ እንዳይበላው ፡ በፍራት ፡ ላልተጨነቀ ፡ እንዲሁ ፡ ብቻ ፡ መሽቶበት ፡ ማደሪያ ፡ ፍለጋ ፡ ለሚመጣ ፡ ብታደርጉለት ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ቤታችሁ ፡ ሲመጣ ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ ያደረገውን ፡ መስተንግዶ ፡ በማግኘቱ ፡ ማመስገኑም ፡ ባይቀር ፡ ለበጎ ፡ ስራችሁ ፡ ልዩ ፡ ዋጋ ፡ አይሰጠውም ። እኒህን ፡ የመሰሉ ፡ ችግሮች ፡ ሊደርሱበት ፡ ለማይችል ፡ በዚህ ፡ አልፎ ፡ ለሚሄድ ፡ አንድ ፡ መነኩዋንንት ፡ ብታደርጉለት ፡ ግን ፡ እንዲያውም ፡ እናንተ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ በመስተናገዱ ፡ ትልቅ ፡ ውለታ ፡ እንዳደረገላ ችሁ ፡ ቆጥሮ ፡ እንድታመሰግኑት ፡ ይፈልጋል ። ስለዚህ ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ በጣም ፡ ለሚፈልጉት ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ በመጠኑ ፡ ለሚፈልጉት ፡ ዋጋው ፡ መጠነኛ ፡ ለማይፈልጉት ፡ በጭራሽ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ማለቴ ፡ ነው ።”

“ ያገርማል ! እንዴት ፡ አወቁት ? አባቴ ! አንዳንድ ፡ የግዜር ፡ እንግዶች ፡ ጠላ ፡ በሌለበት ፡ ይመጡና ፡ ልክ ፡ እኛ ፡ እንደምናደርገው ፡ አድረው ፡ ሲሄዱ ፡ ሰድበውን ፡ ወይም ፡ ረግመውን ፡ ይሄዳሉ ! ” አለች ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡

ብላ ።

ዮሁን ፡ በፈቃዱ ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ሄዶ ፡ ከቆዩበት ፡ ሲመለስ ፡ እንግዳው ፡ መነኩሴ ፡ እግሮቻቸውን ፡ ፈትተው ፡ ሀኪምናው ፡ በጣም ፡ አሽሎዋቸው ፡ ጠውልጎ ፡ የነበረ ፡ አካላ ታቸው ፡ ጠል ፡ እንዳገኘ ፡ የደረቅ ፡ ተክል ፡ ለምልሞና ፡ ሀይወት ፡ አግኝቶ ፡ ስላያቸው ፡ ደስ ፡ አለው ።

" በረቱ ፡ አደሩ ? አባቴ ! " አለ ።

"ከሞት ፡ ቀምታችሁ ፡ እንዳስቀራችሁኝ ፡ እቆጥረዋለሁ!"

" አየ ------ ምን ፡ አደረግንና ? ራትዎን ፡ እንኳዋ ፡ ሳይበሉ ፡ ጦም ፡ አደሩ ! "

" በጊዜ ፡ ብዙ ፡ በልቼ ፡ ነበር ! " አሉ ፡ አባ ፡ ባለቤትዋ ፡ ወተት ፡ ልታመጣላቸው ፡ ሄዳ ፡ ሳለች ፡ ሳትመለስ ፡ ተሸምተው ፡ አፋቸው ፡ ሞልቶ ፡ ማላመጥ ፡ እስኪያቅታቸው ፡ እዩጎረሱ ፡ የዋጡት ፡ ትልልቅ ፡ ጉርሻ ፡ ትዝ ፡ ስላላቸው ፡ ሳቅ ፡ መጥቶባ ቸው ። ወዲያው ፡ ምሳ ፡ ደረሰ ፡ ተባለ ።

እምሳ ፡ ላይ ፡ ዮሁን ፡ ምሽቱና ፡ እንግዳው ፡ እዩተጫ ወቱ ፡ ሲበሉ ፡ " ይገርማል ! ትናንት ፡ እግዚአብሔር ፡ እስዎን ፡ ባያወርድልኝ ፡ እዚያው ፡ በተቀመጥሁበት ፡ መሽቶ ፡ እንደ ፡ ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ ሌሊት ፡ አራዊት ፡ ከበው ፡ ይበሉኝ ፡ ነበር ! " አሉ ፡ አባ ፡ ዓለም ፡ ለምኔ ።

" ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ ሌሊት ፡ አውሬ ፡ ከበ ፡ በላዎ ? " አለ ፡ ዮሁን ፡ እዩሳቀ ። ምሽቱም ፡ አባም ፡ ከት ፡ ብለው ፡ ሳቁና ፡

" መብላትስ ፡ አልበሉኝም ፡ ከበውኝ ፡ ነበር ። "

" እንዴት ? ምን ፡ አውሬ ፡ ነው ? " አለ ፡ ዮሁን ።

ከዚያ ፡ መጀመሪያ ፡ ነብር ፡ በሁዋላ ፡ አንበሳ ፡ የመጡበ ትንና ፡ የሄዱበትን ፡ እሳቸው ፡ እንዴት ፡ እንደወጡ ፡ ሳያው ቁት ፡ እዛፉ ፡ ላይ ፡ የተገኙበትን ፡ አንበሳው ፡ እሳቸውን ፡, ፍለጋ ፡ የወጡበትን ፡ ዛፉ ፡ ስር ፡ አንቆ ፡ ሲጠብቅ ፡ ያደረበትን ፡ ጥዋት ፡ በቀኑ ፡ አውራጆች ፡ ርዳታ ፡ የወረዱበትን ፡ ሁኔታና ፡ ቀኑ ፡ አውራጆች ፡ የዋሉላቸውን ፡ ውለታ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሳያስቀሩ ፡ ዘርዝረው ፡ ሲተርኩ ፡ ባልና ፡ ምሽቱ ፡ መብላታ ቸውን ፡ ትተው ፡ አፋቸውንም ፡ አይናቸውንም ፡ በሰፊው ፡

ከናፍተው ፡ ሲስሙ ፡ ቆዩና ፡ አቢታቸው ፡ በእንግዳ ፡ ስም ፡ የመጡት ፡ መነኩሴ ፡ ያለጥርጥር ፡ ጻድቅ ፡ መሆናቸውን ፡ አምነው ፡ በደስታም ፡ በመገረምም ፡ እያዩ ፡ ተጠቃቀሱ ።

“ እንበሳ ፡ የቅድስገብሬል ፡ ምሳሌ ፡ ነው ? ” አለች ፡ በዛብሽ ፡

“ እዎ ፡ ቅድስገብሬል ፡ እንዲጠብቅዎ ፡ ልኮት ፡ ነው ! እንበሳው ፡ ባይደርስልዎ ፡ ነብሩ ፡ ይበላዎ ፡ ነበር ! ” አለ ፡ ባልዋ ።

“ እዛፉ ፡ ላይ ፡ ሳልወጣ ፡ ቢደርስብኝ ፡ እንበሳው ፡ እይበላኝም ፡ ኖሮዋል ? ”

“ አይበላዎም ። እዚህ ፡ እኛ ፡ አገር ፡ እንበሳ ፡ የገብሬል ፡ መላክተኛ ፡ ነው ፡ ይባላል ! ”

“ ታዲያ ፡ ለምን ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ጎምዥቶ ፡ መሬት ፡ እየ ፎገረ ፡ ደንጋይ ፡ እየፈነቀለ ፡ ሲያገሳና ፡ የወጣሁበትን ፡ ዛፍ ፡ ስር ፡ እንቆ ፡ ይዞ ፡ ሲጨነቅ ፡ አደረ ? ”

“ ነብሩ ፡ ተመልሶ ፡ እንዳይበላዎ ፡ ሲጠብቅዎ ፡ ለማ ደር ፡ ነው ! እሱ ፡ እዚያ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲጠብቅዎ ፡ ባያድር ፡ ነብር ፡ ዛፍ ፡ መውጣት ፡ ስለሚችል ፡ ተመልሶ ፡ ይበላዎ ፡ ነበር ! ”

አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ማመኑም ፡ አለማመኑም ፡ ቸግሮ ዋቸው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እያሰላሰሉ ፡ መብላቸውን ፡ እንደገና ፡ ሲጀምሩ ፦

“ ገብሬል ፡ በለተቀኑ ፡ ታምራት ፡ ነው ፡ የሰራልዎ ! የሚጣፍ ፡ ነው ! እኔንም ፡ ትናንት ፡ በዚያ ፡ መንገድ ፡ ያመ ጣኝ ፡ ገብሬል ፡ ነው ! ”

“ እንዴት ? ” አሉ ፡ አባ ።

“ ሰዎች ፡ አቋራጭ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ እሰማለሁ ፡ እንጂ ፡ ከትናንት ፡ በፊት ፡ በዚያ ፡ መንገድ ፡ ሄጄ ፡ አላውቅም ። ትና ንት ፡ የዲማን ፡ መንገድ ፡ ስሄድ ፡ ውሎ ፡ ይከብደኝ ፡ ሳለ ፡ ይዞኝ ፡ በበቅሎ ፡ ተቀምጬ ፡ የምመጣበትንና ፡ የማውቀውን ፡ ትቼ ፡ መንገዱን ፡ ለማየት ፡ ስል ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ መጣሁ ። እንግዲህ ፡

ሲደክመኝ ፡ በበቅሎ ፡ የምመጣበትን ፡ አስትቶ ፡ በግሬ ፡ የምመጣበትን ፡ ያስመረጠኝ ፡ ገዛሬል ፡ ነው ! ”

“ ዲማ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ ወዳጅ ፡ አለዎ ? ”

“ ኧረ ፡ የለኝም ፡ እንዲያው ፡ እዚያ ፡ እንድ ፡ ደርሶ ፡ የማያውቅ ፡ ታምር ፡ ነገር ፡ ደረሰ ፡ ተብሎ ፡ ተወርቶ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲሄድ ፡ ጊዜ ፡ እኔም ፡ እስቲ ፡ ሄጄ ፡ ጉዱን ፡ አይቼ ፡ ልመለስ ፡ ብዬ ፡ ሄድሁ ! ”

“ ምን ፡ ታምር ፡ ነገር ፡ ደረሰ ? ክፉ ፡ ነው ፡ በጎ ? ”

“ ከክፉም ፡ ክፉ ! አባቴ ! ”

“ እንዴት ? ምን ? ” አሉ ፡ መነኩሴው ፡ የጎረሱት ፡ ባፋቸው ፡ እንዳለ ፡ ማላመጣቸውን ፡ አቁዋርጠው ።

“ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ የሚባሉ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ የደረሰች ፡ ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ ነበረቻቸው ። ያችን ፡ ልጅ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ድንበሩ ፡ አጭተዋት ፡ ሰርጉ ፡ ሲደገስ ፡ ሬሳዋን ፡ ትድሩ ፡ እንደሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በህይወቴ ፡ እያለሁ ፡ ከም ወደው ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አላገባም ፡ እያለቻቸው ፡ መላ ዋን ፡ መስሎዋቸው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ድግሳቸውን ፡ አሰና ድተው ፡ ጨርሰው ፡ የጎጃም ፡ መኳዋንንት ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ ተጠርቶ ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ከተዘፈነ ፡ በሁዋላ ፡ የሆማውለት ፡ ሌሊቱን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እዩበላ ፡ እዩጠጣ ፡ ሲዘፍን ፡ እሰዋ ፡ እንደ ፡ ፈከረችው ፡ ከቤት ፡ በርሬ ፡ እመሙላድ ፡ ገደል ፡ ወድቃ ፡ አጥንትዋ ፡ እንኩዋ ፡ ለምልክት ፡ ሳይገኝ ፡ ቀረ ! ”

“ አይይ ----- ! አባት ፡ እናትዋ ፡ ሰዎች ፡ አይሆኑም ! ጸጠት ፡ ይገድላቸዋል ! ” አሉ ፡ አባ ፡ የጎረሱትን ፡ ባፋቸው ፡ እንደ ፡ ያዙ ።

“ ጎጃምን ፡ እግዚአ ፡ ያሰኘውም ፡ ያባትና ፡ የናትዋ ፡ ነው ! ”

“ እንዴት ? ”

“ አባትዋም ፡ እናትዋም ፡ መጥፋትዋን ፡ ሲሰሙ ፡ እብድ ፡ ሆነው ፡ በገደል ፡ እዩወደቁ ፡ ሞተው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተቀበሩ !” ሲል ፡ ይሁን ፡

" ኧ ---- ? " አሉ ፡ መነኩሴው ፡ ፈሽሸው ። ወዲያው ፡ ባፋቸው ፡ ያዘውት ፡ የቆዩው ፡ እህል ፡ ያለመንገዱ ፡ ሄዶ ፡ ትን ፡ ስላላቸው ፡- ትንፋሽ ፡ አጥተው ፡ ወዲያው ፡ እያሳላቸው ፡ አይኖቻቸው ፡ ፍጥጥ ፡ ብለው ፡ ላባቸው ፡ ከንባቸው ፡ ጋር ፡ ተደባልቆ ፡ በፊታቸው ፡ እየጎረፈ ፡ ሲጨነቁ ፡ ይሁንና ፡ ምሽቱ ፡ ይንግበው ፡ የሚያደርጉት ፡ ቅጡ ፡ ጠፋቸው ።

" ውሀ ፡ ውሀ ፡ ቶሎ ፡ ውሀ ፡ ያጠጡበት ፡ አባቴ ! " አለ ፡ ይሁን ፡ ውሀ ፡ እንዴት ፡ እንደሚጠጣ ፡ ለማሳየት ፡ እጁን ፡ ጨብጦ ፡ ባፉ ፡ ለግዞ ።

" አፍንጫዎን ፡ ያዘው ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ይተንፍሱ ! " አለች ፡ በዛብሽ ፡ እስዋም ፡ አፍንጫዋን ፡ ይዛ ፡ መነኩሴው ፡ አፍንጫ ፡ መያዝ ፡ እንደማያውቁ ፡ ሁሉ ፡ ለማሳየት ። ነገር ፡ ግን ፡ የያሁንም ፡ ሆነ ፡ የምሽቱ ፡ መድሀኒት ፡ ለጊዜው ፡ በማሻል ፡ ፈንታ ፡ አባሰባቸውና ፡ መነኩሴው ፡ ወደቀው ፡ ይንፈራፈሩ ፡ ጀመሩ ።

" እስቲ ፡ ቀና ፡ አድርገን ፡ እንያዝና ፡ ጀርባቸውን ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ መታ ፡ መታ ፡ አድርገው ! " አለች ፡ በዛብሽ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተርበተበተች ። እውነትም ፡ ተጋግዘው ፡ ቀና ፡ አደርጎው ፡ ያዘው ፡ ይሁን ፡ በያበሎቻቸው ፡ ላይ ፡ ጀርባቸውን ፡ መታ ፡ መታ ፡ ሲያደርግ ፡ እየተሻላቸው ፡ ሄደ ።

" ውሀ ! " አሉ ፡ አባ ፡ ዘሳሉ ፡ መሀከል ፡ እንባቸውንም ፡ ላባቸውንም ፡ እየጠራረጉ ። ውሀ ፡ ደጋግመው ፡ ሲወጡ ፡ ትንታው ፡ ተዋቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ትንታው ፡ ሲሄድ ፡ በስ ፡ እግር ፡ ስርቅታ ፡ ተተካ ! ስርቅታው ፡ ከምሳ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እንዲሁ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ውሎባቸው ፡ እምሽቱ ፡ ላይ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ደከሙ ።

ይሁንና ፡ ባለቤቱ ፡ የስርቅታ ፡ መድሀኒት ፡ ነው ፡ የሚባለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሞከረው ፡ ስለ ፡ ተሸነፉ ፡ ግራ ፡ ገብቶዋቸው ፡ እየወጡ ፡ እየገቡ ፡ ሲጨነቁ ፡ ዋሉ ።

"ምነው ፡ እግዜር ፡ መከራቸውን ፡ እንዲህ ፡ አበዛባቸው ? " አለችው ፡ በዛብሽ ።

"ጣድቃን ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ! ጣድቃን ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡

ተፈታታኙ ፡ ብዙ ፡ ነው !" አለ ፡ ባልዋ ።

"እሱስ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ የትናንቱ ፡ ቃምራት ፡ ሁሉ ፡ የጣድቃን ፡ ስራ ፡ ነው ። "

"እግዜር ፡ ከዚያ ፡ አውጥቶ ፡ እዚህ ፡ ለከፉ ፡ ይሰጣቸው ፡ ይሆን ? "

"ኧረ ፡ ባፍህ ፡ ውሀ ፡ ይሙላ ፡ አያ ! "

"ምናባቱ ፡ ልበል ? ደከሙኮ ! እንዲሁ ፡ ካደረባቸው ፡ አይተርፉም ! "

"ይተዋቸው ፡ ይሆናል ። አሁንኮ ፡ እንደ ፡ መጀመሪያው ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ አያፍቃቸውም ። "

"እቡቴ ፡ እንዳፍሽ ፡ ያርግልን ፡ ከተፈርዶ ፡ እንድንድን ! "

"ከምን ፡ ተፈርዶ ? "

"እግዜር ፡ አያርገውና ፡ እቤታችን ፡ ቢሞቱ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይላል ? "

"ጣድቃን ፡ ከሩቅ ፡ መጥቶ ፡ እቤቱ ፡ የሞተበት ፡ ሰው ፡ ይመሰገናል ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ተፈርዶ ፡ ያገኘዋል ? እግዜር ፡ ከፉ ፡ አያምጣ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ ምንም ፡ ተፈርዶ ፡ የለብን ! "

"እሱስ ፡ እውነትሽ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ደህና ፡ ሆነው ፡ መርቀውን ፡ ቢሄዱ ፡ ነበር ፡ መልካሙ ! "አለና ፡ ይሁን ፡ እንገቱን ፡ ደፋ ፡ አድርጎ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ ሲመለከት ፡-

"አንድ ፡ ነገር ፡ አሰብሁ ፡ እቡቴ ፡ እንሞክረው ! " አለች ፡ ምሽቱ ። ከዚያ ፡ ያሰበችውን ፡ ነገረችውና ፡ ተመካክረው ፡ ወደ ፡ መነኩሴው ፡ ሄዱ ። አባ ፡ አሰም ፡ ለምኔ ፡ ከቀድሞው ፡ የባሰ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እያፋቃቸው ፡ እንባቸው ፡ ማገጃውን ፡ እንደ ፡ ናደ ፡ የቦይ ፡ ውሀ ፡ ዘቅዝቆ ፡ እየፈሰሰ ፡ እጆቻቸውንና ፡ እግሮቻቸውን ፡ መሰብሰብ ፡ ተስኗቸው ፡ ደክሞቀቸው ፡ ነበር ።

"ትንሽ ፡ አልተሻለዎም ? "አለ ፡ ይሁን ፡ ሲገባ ፡ መነኩሴው ፡ ራሳቸውን ፡ ነቀነቁ ፡ አልተሻለኝም ፡ ለማለት ።

"ትንሽ ፡ ወተት ፡ ልስጥዎ ። "አለች ፡ በዛብሽ ። አባ ፡ አሁንም ፡ ራሳቸውን ፡ ነቀነቁ ።

"አይ ፡ ነብር ---! "አለችና ፡ በዛብሽ ፡ ሙሀ ፡ ወዳንድ ፡ ወገን ፡ ስትሮጥ ፡

"አንበሳ ---! "ብሎ ፡ ሙሆ ፡ ይሁን ፡ ተከትሎዋት ፡ ሮጠ ። ወዲያው ፡ በሽተኛው ፡ መነኩሴ ፡ መጠጊያ ፡ ተደግፈው ፡ ከተጋደሙበት ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተነሱ ፡ ሳያውቁት ፡ ይሁንን ፡ ተከትለው ፡ ይሮጡ ፡ ጀመር ። ይሁን ፡ በፈቃዱ ፡ መነኩሴውን ፡ ባንድ ፡ እጁ ፡ ምሽቱን ፡ በሌላው ፡ ይዞ ፡ እየሮጠ ፡ ሂዶ ፡ ካንድ ፡ የሳር ፡ ክምር ፡ ጀርባ ፡ ተሸሸጉ ። አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ በባልና ፡ ምሽቱ ፡ መሀከል ፡ ከድርቆሽ ፡ ክምር ፡ ሁዋላ ፡ እንደ ፡ ተሸሸጉ ፡ አንበሳው ፡ መጥቶ ፡ ሲይዛቸው ፡ እንዳያዩ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ጨፍነው ፡ ከግር ፡ እስከ ፡ ራሳቸው ፡ ሰውነታቸው ፡ ሁሉ ፡ ስቅቅ ፡---ብሎ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ያዘኝ ፡ እያሉ ፡ ሲጠባበቁ ፡

"አትንቀሳቀሱ ፡ ትንፋሻችሁንም ፡ አጥፉ ! "አለ ፡ ይሁን ፡ ቀስ ፡ ብሎ ።

"እሺ ---፡ እሺ ---- ! "አሉ ፡ አባና ፡ ምሽቱ ፡ በጣም ፡ ቀስ ፡ ብለው ።

እንዲህ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ሁሉ ፡ ትንፋሻቸውን ፡ አጥፍተው ፡ ትንሽ ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ፡

"እስቲ ፡ ወጥቼ ፡ ልይ ! "አለ ፡ ይሁን ፡ ትንሽ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡

"የለም ፡ አውሬዎች ---ይጣሉዎታል ! "አሉ ፡ አባ ፡ እጁን ፡ አጥብቀው ፡ ይዘው ።

"ይህን ፡ ያክል ፡ አይቆዩም ፡ ሂደው ፡ ይሆናል ! "አለና ፡ ይሁን ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ተነስቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ በሩፋ ፡ ሂዶ ፡ ከዚያም ፡ የቤቱን ፡ ዙሪያ ፡ አይቶ ፡ ሲመለስ ፡-"የሉም ፡ ሂደዋል ! " አለ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

"አይመለሱም ?" አሉ ፡ አባ ፡ ፍራት ፡ እልባቸው ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እያንቀጠቀጣቸው ።

"የለም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሄዱ ፡ አይመለሱም ! "

"ፋቂምኮ ፡ አብሮዋቸው ፡ ሂደ ! እሱም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሄደ ፡ አይመለስም ! "አለች ፡ በዛብሽ ፡ እስዋም ፡ እንደ ፡ ባልዋ ፡ ፍርጥም ፡ ብላ ።

ባልና ፡ ምሽቱ ፡ በደስታ ፡ ፊት ፡ እስበሳቸው ፡ እዩ ተያዩ ፡ ሲስቁ ፡ መንኩሴው ፡ በሳቸው ፡ ፍራትና ፡ መንቀጥቀጥ ፡ የሚስቁ ፡ መስሎዋቸው ፡ በበኩላቸው ፡ የፍረት ፡ ፍርጥምታ ፡ ፍርጥም ፡ አሉና ፡ እንገታቸውን ፡ ደፋ ፡ አድርገው ፡ ዝም ፡ አሉ ።

“በዛብሽና ፡ እኔ ፡ የሳቅንበት ፡ ጠፍቶዎ ፡ ተቸገሩ ፡ መሰለኝ ! ” አለ ፡ ይሁን ፡ አባን ፡ ግራ ፡ ሲገባቸው ፡ ተመልክቶ ።

“እንበሳውን ፡ ፈርቼ ፡ ምናልባት ፡ ሳይታወቀኝ ፡ የሚያስቅ ፡ ነገር ፡ አድርጌ ፡ ይሆን ፡ እያልሁ ፡ ሳስብ ፡ ነበር ። መቸም ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አንበሳ ፡ እንኳንስ ፡ ባካል ፡ መጥቶብኝ ፡ ስሙ ፡ ብቻ ፡ ሲያስፈራኝ ፡ ይኖራል ! ”

“ የበዛብሽ ፡ አንበሳ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የግዜር ፡ አንበሳስ ፡ አልመጣም ! ”

“ እንዴት ? ” አሉ ፡ አባ ፡ እንደገና ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ ብለው ።

“ ፋቅ ፡ ሲደነግጡ ፡ ስለሚለቅ ፡ ማስደንገጤ ፡ አጥፍተን ፡ ስንፈልግ ፡ ሁለን ፡ በመጨረሻ ፡ በዛብሽ —— የፈጠረቻቸው ፡ አንበሳና ፡ ነብር ፡ ናቸው ፡ እንጂ —— የውነተኞቹ ፡ አንበሳና ፡ ነብርስ ፡ አልመጡም ፡ ነበር ! ”

አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ከነገሩም ፡ ይልቅ ፡ ባልና ፡ ምሽቱ ፡ እሳቸውን ፡ ለመርዳት ፡ በተጨነቁት ፡ ጭንቀት ፡ ልባቸው ፡ መንካቱን ፡ አጉልቶ ፡ የሚያሳይ ፡ የቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብለው ፡ እንደገና ፡ እንገታቸውን ፡ ደፉ ።

ያንለት ፡ ማታ ፡ ራት ፡ ላይ ፡ እንግዳው ፡ መንኩሴ ፡ መብላቱም ፡ መጫወቱም ፡ አልጥማቸው ፡ ስላለ ፡ ሁሉንም ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ምኝታቸው ፡ መሄድ ፡ ፈለጉ ። ይሁንና ፡ ምሽቱ ፡ ግን ፡ በንግዳ ፡ ስም ፡ እግዜር ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ለላካቸው ፡ መላክተኛው ፡ ባደረጉት ፡ ሁሉ ፡ አገልግሎት ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ እዩተጫወቱ ፡ እንዲበሉ ፡ አጥብቀው ፡ ለመኑዋቸው ።

“አሁን ፡ እግዜር ፡ ይመስገን ፡ ፋቂም ፡ ትቶዎታል ! እዩተጫወቱ ፡ ትንሽ ፡ ቢበሉ ፡ ምናለ ? ” አለች ፡ በዛብሽ ።

“ ፋቁ ፡ ልቤን ፡ አቁስሎኝ ፡ ሄዶ ፡ ወጡን ፡ ፈራሁት ፡

ወዲያውም ፡ እደከመኝ ፡ ስለዚህ ፡ ማረፍ ፡ ይሻለኝ ፡ እንደ ሆን ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ”

“ ባልጫ ፡ ተልባ ፡ ትንሽ ፡ በልተው ፡ ሙቀት ፡ ይጠጡ ፡ ያለዚያ ፡ ቢተኙም ፡ እንቅልፍ ፡ አያወስድዎ ! ” አለች ፡ ባለቤትዋ ፡ የውነተኛ ፡ ጭንቀትዋ ፡ እፊትዋ ፡ ላይ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ እዬታዬ ።

“ እሺ ፡ ” አሉ ፡ አባ ፡ ምንም ፡ እንከዋ ፡ መብላት ፡ ባያምራቸው ፡ ያስተናጋጆቻቸውን ፡ ጭንቀት ፡ ስላዩ ፡ እን ሱን ፡ ይስ ፡ ለማስኘት ።

“ በጣም ፡ አስቸገርሁዎችሁ ! ” አሉ ፡ መነኩሴው ፡ ትንሽ ፡ እንጀራ ፡ ባልጫ ፡ ተልባ ፡ በልተው ፡ እንድ ፡ ዋንጫ ፡ ሙቀት ፡ ከጠጡ ፡ በሁዋላ ፡

“ ኧረ ፡ እንኩዋን ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብሬል ፡ ፊቱን ፡ መለ ሰልዎ ፡ እንጂ ፡ የኛ ፡ ችግርስ ፡ ምንም ፡ አይደል ! ” አለ ፡ ይሁን ።

“ እንዴት ፡ ምንም ፡ አይደል ? ይሄው ፡ ትናንት ፡ ከተ ገናኘን ፡ ጀምሮ ፡ እሀል ፡ እንኩዋ ፡ አርፋችሁ ፡ የምትቀምሱ በት ፡ ጊዜ ፡ አሳጣሁዎችሁ ! ”

“ በዚህ ፡ አሳብ ፡ አይግባዎ ፡ ምንም ፡ አይደል ! ” ቅድም ፡ የጎደለ ፡ ቢኖር ፡ አሁን ፡ እንሞላዋለን ። እንዲያውም ፡ እኔስ ፡ ለበሽብሽ ፡ አልነገርሁዎትም ፡ እንጂ ! የትንታና ፡ የፋቅ ፡ በሽታ ፡ ያመጣሁብዎ ፡ እኔ ፡ እሆን ? ብዬ ፡ በምስጢር ፡ ራሴን ፡ ወቅሸ ፡ ነበር ! ”

“ እርስዎ ? እንዴት ፡ አድርገው ? ”

“ መቸስ ፡ ሰው ፡ ሲጨንቀው ፡ የማያስበው ፡ አለ ? በፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ የደረሰውን ፡ ሲነግርዎ ፡ ወዲ ያው ፡ ደንግጠው ፡ ትን ፡ ሲልዎ ፡ ጊዜ ፡ ድንገት ----- መቸም ፡ የሰው ፡ ስርና ፡ ቅርንጫፍ ፡ ብዙ ፡ በመሆኑ ፡ ዘምድና ፡ ይኑ ርዎ ፡ አይኑርዎ ፡ ሳላውቅ ፡ ስለተናገርሁ ፡ አስቀድሜ ፡ እስዎ ፡ ከዩት ፡ እንደ ፡ መዝሙና ፡ ከሙዋቾቹ ፡ ጋር ፡ አውቂያ ፡ እን ዳለዎ ፡ ሳላጣራ ፡ ምን ፡ አስሰፈለፈኝ ፡ ብዬ ፡ ጠጠተኝ ። ”

“ ከመውዋቻቸስ ----እንኩዋን ፡ ዝምድና ፡ ሲኖረኝ ፡ አገራቸውን ፡ ዲማንም ፡ በስም ፡ ካልሆነ ፡ መልኩን ፡ አላው ቀው ! ነገሩ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝንና ፡ የሚያስደንግጥ ፡ ነው ። ”

“ ነገሩማ ---- የሚያሳዝንና ፡ የሚያስደነግጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ? የማያረሳ ፡ መተረቻ ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ነው ፡ እንጂ ! መቸስ ፡ ልጅቱ ፡ እጅግ ፡ የምታምር ፡ ቡቃያ ፡ ነበረች ፡ አሉ ። የሚያውቁዋት ፡ ሰዎች ፡ የመልኩዋን ፡ የጠባዩዋን ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ የትምርትዋን ፡ ነገር ፡ ሲናገሩ ፡ የሰማውን ፡ ሁሉ ፡ እንኩዋን ፡ አላወቅናት ፡ አሰኘው ! ”

“ የሰዋ ፡ መቸም ፡ ሬሳዋ ፡ እንኩዋ ፡ አልተቀበረም ! ?”

“እየ ፡ አባቴ ! የመሙላድን ፡ ገደል ፡ ባያውቁትኮ ፡ ነው ! በዚያ ፡ ገደል ፡ የወደቀ ፡ ሰው ፡ እንኩዋን ፡ ሬሳው ፡ ቁራጭስ ፡ ይገኛል?”

“ሌሊት ፡ ከሆነ ፡ የጠፋች ፡ ገደል ፡ ስትገባ ፡ ማን ፡ አያት?”

“ማን ፡ እንዳያት ፡ እንጃ ፡ ብቻ ፡ በመሙላድ ፡ ገደል ፡ መጣ ባትዋ ፡ ርግጥ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ፡ እልቅሰው ፡ ላይ ፡ ሲወራ ፡ የዋለ ።”

“እዎ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው!” አሉ ፡ አባ ፡ አላባቸው ፡ እዚያ፡ ትቶዋቸው ፡ በፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ የደረሰውን ፡ መከራ ፡ ሲያዩ ፡ ሲሄድ ፡ የማያዩ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ቦዘዝ ፡ አድርገው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተክለው ።

“ልጅቱስ - - - -”አለ ፡ ይሁን፡ ትንሽ፡ ዝም ፡ ብሎ፡ ቆይቶ ። “ልጅቱስ ፡ ያንለት ፡ ገደል ፡ ገብታ ፡ ባትሞትም ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ የሞተች ፡ ናት!”

“እንዴት?”አሉ ፡ አባ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ከተከሉበት፡ ወደ፡ ይሁን ፡ መለስ ፡ አድርገው ።

“ምን - - ያባት ፡ የናትዋ ፡ ደም ፡ በዩሄደችበት ፡ እዩተከ ተለ ፡ ሲረብሀባት ፡ እረፍት ፡ ታገኛለች ፡ ብለው ፡ ነው?”

“እውነትዎ ፡ ነው ፡ እረፍት ፡ አታገኝም! አሉ ፡ አባ ፡ አይ ኖቻቸውን ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ መልሰው ።

“እንደ ፡ ተወራው ፡ ካልሞተችስ ፡ ከሁሉም ፡ ማዘን ፡ የሚ ገባው ፡ ለሰዋ ፡ ነው!” አለች ፡ በዛብሽ ።

"እንዴት?" አለ ፡ ባልዋ ።

"እናትና ፡ አባትዋስ ፡ ሳይስቀዩ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ እስዋን ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እንዳልኸው ፡ በስዋ ፡ ምክናያት ፡ የፈሰሰው ፡ ደማቸው ፡ ውቃቢያቸው ፡ በሄደችበት ፡ ሁሉ ፡ ተቆራኝቶ ፡ እየከሰሰ ፡ እየወቀሰ ፡ ሲያሰቃያት ፡ ይኖርና ፡ በመጨረሻ ፡ ወይ ፡ አሳብዶ ፡ ወይ ---- አንድ ፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ የማይቀረውን ፡ ሞት ፡ ያነግድላታል! ታዲያ ፡ ለንደዚች ፡ ያለች ፡ ያልታዘነ፡ ለማን፡ ይታዘናል?"

"እዎ ፡ በጣም ፡ ታሳዝናለች! እንግዲህ ፡ ልሂድና፡ ልረፍ።" አሉ ፡ መነኩሲው ፡ የይሁንን ፡ መልስ ፡ ሳይሰሙ ፡ ወይ ፡ ምንታቸው ፡ ለመሄድ ፡ ቸኩለው ።

"አ ----! ይሂዱ ፡ አባቴ ፡ ይሂዱ ፡ ይከሞኛል ፡ ልረፍ ፡ ሲሉ ፡ እንደገና ፡ በወሬ ፡ ጠመድኅዎ!" አለ ፡ ይሁን ፡ ለመሰናበት፡ እሱም ፡ ምሽቱም ፡ ተነስተው ።

አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ እዮሁን ፡ በፊቃዱ ፡ ቤት ሲየገጣሙ ፡ ስንብተው ፡ ባምስተኛው ፡ ወይ ፡ መንደር ፡ ሂዶ ፡ ከቆዩበት ፡ ሲመለስ ፡ "የምስራች ፡ አባቴ !" አላቸው ።

"ምስር ፡ ይብላ! ምን ፡ የምስራች ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ተገኘ?"

"አዲስ ፡ አበባ ፡ በበቅሎ ፡ የሚያደርስዎ ፡ ነጋዴ ፡ ተገኘ! ለትርፍ ፡ ሳይሆን ፡ ለበቅሎዋ ፡ ሳር ፡ መግዣ ፡ የሚሆን ፡ ትንሽ ፡ ገንዘብ ፡ ይስጡታል ። ገንዘብ ፡ አለዎ?"

"ስንት?"

"አ ----- ሁለት ፡ ቢበዛ ፡ ሶስት ፡ ብር ። ከዚህ ፡ አያበልጥም ፡"

"ከሶስት ፡ ብር ፡ ካልበለጠ ፡ ለቁምስና ፡ መቀበያ ፡ ከያዝሁት ፡ አጉድዬ ፡ እከፍላለሁ ፡ግዴለም !"

"እአ ----! ቅምስና!" አለ ፡ ይሁን ፡ ምሽቱን ፡ እያየ ፡ መነኩሴው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄደው ፡ የሚሾሙት ፡ ሹመት ፡ ስሙ ፡ ጠፍቶት ፡ ሳይነግራት ፡ ቀርቶ ፡ ስለነበረ ፡ ድንገት ፡ ስለተገኘ ፡ ደስ ፡ ብሎት ።

“ቅምስና!” አለች ፡ ምሽቱም ፡ ባልዋ ፡ ያለውን ፡ ደግማ ።

“ቂምስና!” አሉ ፡ አባ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብለው ።

አባ ፡ አለም ፡ ሰምኔ ፡ ከነጋዴ ፡ ጋር ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሲደርሱ ፡ “እጸጸቱ ፡ ግቢ ፡ እንውሰድዎ? ወይስ ፡ ሌላ ፡ ማረፊያ ፡ አለዎ ፡ አባቱ?” አለ ፡ ነጋዴው ።

“የማያስቸግራችሁ ፡ ከሆነስ ፡ መጀመሪያ ፡ ሩፋኤል ፡ ብደርስ ፡ እወድ ፡ ነበር !”

“እንዲያውም ፡ ይቀናናል ፡ እንጂ!ሰፈራችን ፡ ሩፋኤል ፡ አጠገብ ፡ ጉለሌ ፡ ስለሆነ ፡ ከባታችን ፡ ግቢ ፡ ሩፋኤል ፡ ይቀርበናል ።”

“እንግዲያውስ ፡ ሩፋኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንድደርስ ፡ ያድርጉኝ ፡ እባክዎ ፡”

ሩፋኤል ፡ ደርሰው ፡ ከበቅሎ ፡ ሲወርዱ ፡ ሶስት ፡ ብር ፡ አውጥተው ፡ ለነጋዴው ፡ እያሳዩ ፡ “ልጨምር?” ወይስ ፡ ይህ ፡ ይበቃል? ሌላውን ፡ ትቼ ፡ ለበቅሎዋ ፡ ማለቴ ፡ ነው!” አሉ ፡ አባ ።

“ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ አለ? አባቱ!”

ከጎጃም ፡ እስከዚህ ፡ እኔን ፡ ደስ ፡ እንዲለኝ ፡ እኔን ፡ እንዲመቸኝ ፡ ሲቸገሩ ፡ የመጡት ፡ የልብ ፡ ርህራሄዎ ፡ ብቻ ፡ አገዘዎ ፡ ሲያደርጉልኝ ፡ የመጡት ፡ ሊቆጥረውም ፡ ሊረሳውም ፡ የማልችል፡ ብዙ ፡ ችሮታና ፡ ርዳታ ፡ እሱን ፡ እሱን ፡ ሁሉ ፡ ትቼ ፡ ለበቅሎዋ ፡ ብቻ ፡ ማለቴ ፡ ነው! ሌላውን ፡ በገንዘብ ፡ መገመት ፡ የውነተኛ ፡ ዋጋውን ፡ ማርከስ ፡ ይሆናል!”

“ለበቅሎዋም ፡ ይሁን ፡ ለሌላው ፡ ቡራኬዎን ፡ ብቻ ፡ አባቴ! ገንዘብ ፡ አልፈልግም!”

“ይህንንም?”

“እሱንም!”

“ይህንስ ፡ እባክዎ ፡ ይቀበሉኝ ፡ ለበቅሎዋ ፡ ሳር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለርስዎም ፡ አይደለም ።”

“የመነኩሴ ፡ ቡራኬው ፡ ያተርፋል ! ገንዘቡ ፡ ግን ፡ ያከስራል ! ስለዚህ ፡ ነጋዴ ፡ ነኝና ፡ ማትረፍ ፡ እንጂ ፡ መክሰር ፡ አልፈልግም ። ቡራኬዎን !”

"እግዚአብሔር ፡ ወረትምን ፡ ያለምልመው ! ሁል ፡ ጊዜ ፡ ርዳታ ፡ በሚሰጡበት ፡ እንጂ ፡ በሚቀበሉበት ፡ ሁኔታ ፡ እያቀምም !" አሉ ፡ አባ ፡ ነጋዴውን ፡ ሲሰናበቱ ፡ ስለ ፡ ደግነቱ ፡ ለልባቸው ፡ የተሰማው ፡ ከፍተኛ ፡ አድንቆት ፡ በፊታቸው ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ እየታየ ።

ደጀሰላሙን ፡ ሲገቡ ፡ ጊዜው ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ገድም ፡ ስለነበረ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በሮች ፡ ሁሉ ፡ ተዘግተው ፡ በደረጃው ፡ ዙሪያ ፡ ጥምድ ፡ ጥምድ ፡ እየሆኑ ፡ ከተቀመጡት ፡ ርጋቦች ፡ በቀር ፡ የሰው ፡ ምልክት ፡ አይታይ ፡ የወፍ ፡ ጫጫታ ፡ ይሁን ፡ የነፋስ ፡ ሽውሽውታ ፡ አይሰማ ፡ እዚያ ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔሩ ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ የተጫነው ፡ የዝምታ ፡ የጭልታ ፡ የጸጥታ ፡ ግርማ ፡ ያስፈራል ። ልብ ፡ ያርዳል ! አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ የርምጃቸውንና ፡ በሀይል ፡ የሚመታ ፡ ልባቸውን ፡ ድምጽ ፡ ብቻ ፡ እየሰሙ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መስቀል ፡ ባይናቸው ፡ በመስቀሉ ፡ ላይ ፡ የተሰቀለውን ፡ ባይነ ፡ ሀሊናቸው ፡ እየተመለከቱ ፡ ቀስ ፡ እያሉ ፡ ሄደው ፡ በምእራብ ፡ በር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እደረጃው ፡ ስር ፡ ሲደርሱ ፡ እያለቀሱ ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፉ ። እዚያ ፡ በወደቁበት ፡ ብዙ ፡ እንደ ፡ ቆዩ ፡ ሰውነታቸውን ፡ በሙሉ ፡ ቅፍፍ ፡ አላቸው ። አንድ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ሊጫናቸው ፡ በላያቸው ፡ የተዘበበ ፡ መሰሉ ፡ ተሰማቸው ። ለመነሳት ፡ እየፈለጉ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየቱን ፡ ፈርተው ፡ ሲያመነቱ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ተደፋፍረው ፡ እንባቸውን ፡ ካይናቻቸው ፡ እየጠራረጉ ፡ ቀና ፡ ቢሉ ፡ አንድ ፡ የጠመጠመ ፡ ሰው ፡ አጠገባቸው ፡ ቆሞ ፡ ዘቅዝቆ ፡ ይመለከታቸዋል ። "ምንድነው ? መላክ ፡ ይሆን ፡ ሰው ? ስመጣ ፡ አልነበረም ፡" አሉ ፡ መነኩሴው ፡ ባሳባቸው ፡ ትክክል ፡ ማየቱንም ፡ ፈርተው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ።

" ደህና ፡ ነዎ ?" አለ ፡ ሰውዬው ።

" አዎን ፡ ደህና ፡ ነኝ !" አሉ ፡ መነኩሴው ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ እያዩ ።

"እዚያ ፡ ወዲያኛው ፡ ጽድ ፡ ስር ፡ ቆሜ ፡ ጸሎተ ፡ ማርያም ፡

ስደግም ፡ ኸው ፡ ብለው ፡ ሲወድቁ ፡ አዬሁና ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ይነሳሉ ፡ ስል ፡ በወደቁበት ፡ ስለቀሩ ፡ ደህና ፡ አይደሉ ፡ እንደሆን ፡ ልጠይቅዎ ፡ ነበር ፡ የመጣሁ ።”

“ የለም ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ የኔታ ፡” አሉ ፡ አባ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ እፊታቸው ፡ የቆመውን ፡ ሰው ፡ አዩና ።

“ እዚህ ፡ የሚፈልጉት ፡ ነገር ፡ አለ ! ምናልባት ፡ ልረዳዎ ፡ እችል ፡ እንደሆን ?”አለ ፡ ሰውዬው ፡ እመነኩሴው ፡ ፊት ፡ እደረ ጃው ፡ ላይ ፡ ተቀመጠና ።

“ ቅኔ ፡ ለመማር ፡ ነው ፡ የመጣሁ ፤ ቅኔ ፡ ቤቱን---ቢያሳዩኝ !” አሉ ፡ አባ ፤ አፋቸው ፡ እየፈራ ።-

“ እህህ---- ቅኔ ፡ ቤቱስ ፡ እዚያ ፡ ታች ፡ ነው ፤ ቅኔ ፡ አስተ ማሪው ፡ የለም ፡ እንጂ !” አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ በፈንታው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ።

“ እእ ---- ? ወዴት ፡ ሄ ---- ሄዱ ?”

“ ይመንን ፡ ወይስ ፡ ወንበዴ ፡ ገድሎ ፡ ሸሽጎ ፡ ይቅበረው ፡ ማን ፡ ያውቃል ! እኛም ፡ የምናደርገው ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶን ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ ተቀምጠናል ። መሪ ፡ ጌታ ፡ በዛብህ ፡ ትልቅ ፡ ሊቅ ፡ ነበር ። ደብራችንንም ፡ አስከብሮ ፡ ትልቅ ፡ አድርጎልን ፡ ነበር ፡” ስብሰ ፡ ይቁድሶ ፡ ለመካን ፡” እንደሚለው ፡ ደብራችን ፡ በሱ ፡ ምክና ያት ፡ ትልቅ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ትልቅነት ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ጠፋ !” አለና ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ከመነኩሴው ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሲያጣ ፡ ጊዜ ፡ አይኑን ፡ ወደሳቸው ፡ መለስ ፡ ቢያደርግ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እዬተመለከቱ ፡ ግን ባራቸውም ፡ ፊታቸውም ፡ ቁጥር ፡ ፈታ ፡ ሲል ፡ አዬ ።

“ስለዚህ ፡ ቅኔ ፡ ቤቱ ፡ አሁን ፡ ወና ፡ ነው ፡ ማንም ፡ የለበ ትም ፡ ለዛሬ ፡ ማደሪያ ፡ የለዎ ፡ እንደሆነ ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ ያደሩ ።” አለ ፡ ቀጠለና ። መልስ ፡ የለም ።

“አባቴ ፡ ሰሙኝ?” አሁንም ፡ መልስ ፡ የለም ።

“ አባ ! ”

“ምን ፡---በስዋ ፡ ምክናያት ፡ የፈሰሰው ፡ የናት ፡ አባትዋ ፡

ዶም ፡ በሂደችበት ፡ አረፍት ፡ ይሰማታል ፡ ብለህ ፡ ነው ?" አሉ ፡ አባ ፡ አይኖቻቸውን ፡ ከመሬት ፡ ሳይነቅሉ ፡ ግንባራቸውም ፡ ፊታቸውም ፡ ቁጥር ፡ ፈታ ፡ እያለ ።

"አባቴ ፡ ደህና ፡ አይደሉም ? "አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ደንግጦ ፡ ተነስቶ ፡ የመነኩሴውን ፡ ክንድ ፡ ይዞ፡ እየነቀነቀ ።

" እእ -----? ደህና ፡ ነኝ ! አሉ ፡ አይኖቻቸውን ፡ መላልሰው፡ አርገበገበው ።

" ቅኔ ፡ ቤቱ ፡ ሰው ፡ የለበትም ፡ ወና ፡ ነውና ፡ የዛሬን ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ ይደሩ ፡ ስልዎ ፡ ሌላ ፡ ሲናገሩ ፡ ጊዜኮ ---- ያመመዎ ፡ መሰሎኝ ፡ ነው !"

" የለም ፡ ደህና ፡ ነኝ ።"

" ይነሱ ፡ እንግዲያስ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንሂድ ።"

"የለም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ ደጀሰላም ፡ አድራለሁ ።"

" ቤትኮ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እባክዎ ፡ ይነሱ ፡"

" ደጀሰላሙስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አይደል !"

"ቢሆንም ፡ ቤት ፡ ካለ.ታማ ፡ ደጀሰላም ፡ አይታደርም ፡ ብዬ፡ ነው !"

"እግዚአብሔር ፡ ለኔ ፡ ያዘዘው ፡ ቤት ፡ እዶዶሰም ፡ ደጀሰላም፡ ነው !"

"እንግዲያስ፡ ማታ ፡ ራት ፡ እስይገቡ ፡ ደጀሰላም ፡ መምጣቴ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይቀርምና ፡ ሌይሬዎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንዳይገፉኝ ፡" አሉና ፡ ትተዋቸው ፡ ሄደ ። ነገር ፡ ግን ፡ ማታ ፡ ራት ፡ እስያዘ ፡ ቢሄድ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔን ፡ ደጀሰላም ፡ አላገኛቸውም ፡ ጠፉ !

# ምእራፍ ፡ ፴፬ ፡

## ፍቅር ፡ እስከ ፡ መቃብር ፡

አባይ ፡ ለቆላው ፡ የመኪና ፡ መንገድ ፡ ለወንዙ ፡ ድልድይ ፡ ሳይሰራለት ፡ ከጎጃም ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ የሚሄድ ፡ መንገደኛ ፡ ሁሉ ፡ ጎሀ ፡ ጽዮን ፡ ወይም ፡ ደጀን ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ልክ ፡ የመከራ ፡ ትንቢት ፡ እንደ ፡ ተነገረ በት ፡ ሰው ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ መከራው ፡ ደረሰብኝ ፡ ብሎ ፡ ልቡ ፡ እየፈራና ፡ እየራደ ፡ የሚያልፍበት ፡ ቦታ ፡ ነበር ።

አባይ ፡ አንድ ፡ ሞት ፡ ብቻ ፡ አያደለም ፡ ብዙ ፡ ሞት ፡ ተሰ ብስቦ ፡ የሰፈረበት ፡ ብዙ ፡ ስቃይ ፡ ብዙ ፡ ጣር ፡ ተሰብስቦ ፡ የሰ ፈረበት ፡ ቦታ ፡ ነበር ፡-

ባንድ ፡ አመት ፡ ውስጥ ፡ ያባይ ፡ ውሀ ፡ የሚወስደውን ፡ አዞ ፡ የሚበላውን ፡ ሽፍታ ፡ የሚገድለውን ፡ እባብ ፡ ነድፎት ፡ ወይም ፡ ወባ ፡ እሞት ፡ የሚሞተውን ፡ ተደብድቦ ፡ ወድቆ ፡ አውሬ ፡ የሚቀራመተውን ፡ ልብሱ ፡ የሚገፈፈውን ፡ ሀብቱ ፡ የሚዘረፈውን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሞት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጣር ፡ መከ ራው ፡ የደረሰበት ፡ ቤት ፡ መከራው ፡ የደረሰበት ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ይቆጥረዋል ፡ እንጂ ፡ ቆጥሮ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ሊል ፡ የሚ ችል ፡ የለም ።

አባይ ፡ ውስጥ ፡ ተሰ ብስቦ ፡ ከሰፈረው ፡ ሞትና ፡ ስቃይ ፡ የበለጠ ፡ ደግሞ ፡ ወሬው ፡ ያስፈራ ፡ ነበር ። መከራ ፡ የደረሰበት ፡ የደረሰበትን ፡ መከራ ፡ በመቶ ፡ አብዝቶ ፡ ያልደረሰበት ፡ በጉ ልበቱ ፡ በብልሀቱ ፡ ወይም ፡ በግዜር ፡ ታምራት ፡ ባያመልጥ ፡ ኖሮ ፡ ሊደርስበት ፡ የነበረውን ፡ ራሱ ፡ ፈጥሮ ፡ ወዲያው ፡ የፈ ጠረውን ፡ በሽህ ፡ እያበዛ ፡ ሲያወራ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ወሬ ፡ እየተስፋፋ ፡ አባይን ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ገሀነም ፡ የማያውቁት ፡ ሁሉ ፡ በወሬው ፡ ብቻ ፡ ይፈሩት ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ከጎጃም ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ አል ፈው ፡ የሚሄዱ ፡ መንገደኞች ፡ ደጀን ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ አባይን ፡ ክረምት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጉም ፡ በጋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጭ

ጋግ ፡ ተሸፍና ፡ የሚታወቀውንም ፡ የማይታወቀውንም ፡ ሞትና ፡ ጣር ፡ ሁሉ ፡ በጉያው ፡ ሸሽጎ ፡ እንደ ፡ ሲኦል ፡ ንጉስ ፡ በሚያስፈራ ፡ ግርማ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ተጋድሞ ፡ ሲመለከቱት ፡ ልባቸው ፡ ሲሸበር ፡ ይቆይና ፡ ወዲያው ፡ ከጉሙ ፡ ወይም ፡ ከጭጋጉ ፡ በላይ ፡ አሻግረው ፡ ጎሀጽዮንን ፡ ሲያዩ ፡ እዚያ ፡ ከደረሱ ፡ ሞቱ ፡ ሁሉ ፡ ጣሩ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሁዋላቸው ፡ የሚቀር ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የማይገጥማቸው ፡ ሆኖ ፡ ስለሚታያቸው ፡ ጎሀጽዮን በደህና ፡ የሚደርሱበትን ፡ ዘዴ ፡ ብቻ ፡ ማሰብ ፡ ማሰናዳት ፡ ይጀምራሉ ። የጉዞዋቸው ፡ መጨረሻ ፡ ጎሀጽዮን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁሉ ፡ ምኞታቸው ፡ ጸሎታቸው ፡ መሰናዶዋቸው ፡ ሁሉ ፡ እዚያ ፡ ለመድረስ ፡ ይሆናል ። ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ያለው ፡ መንገድ ፡ እስካዲስ ፡ አበባም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዳርቻ ፡ ለጊዜው ፡ አይቆጠርም ! እሱ ፡ ጎሀጽዮን ፡ ከተደረሰ ፡ በሁዋላ ፡ የሚመጣ ፡ ነው !

እንዲሁም ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ይሁን ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ የሚሄዱ ፡ መንገደኞች ፡ ጎሀጽዮን ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ አባይንና ፡ ከዚያ ፡ አሻግረው ፡ ደጀንን ፡ ሲያዩ ፡ ስሜታቸው ፡ ደጀን ፡ ሆነው ፡ አባይንና ፡ ጎሀጽዮንን ፡ እንደሚመለከቱት ፡ መንገደኞች ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ጎሀጽዮንና ፡ ደጀን ፡ አባይን ፡ የሚሻገሩ ፡ ነጋዴዎችና ፡ ሌሎች ፡ መንገደኞች ፡ እዚያ ፡ ውስጥ ፡ የሚቆዩቸውን ፡ ከፉ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ለማግጠም ፡ እስኪጠራቀሙ ፡ ድረስ ፡ የሚጠባበቁባቸው ፡ የሚጠነቀቁባቸው ፡ የሚታጠቁባቸው ፡ በደህና ፡ እንዲሻገሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚለምኑባቸው ፡ የሚናዘዙባቸው መሳፈሪዎች ፡ ናቸው ። አባይን ፡ ከተሻገሩትም ፡ በደህና ፡ የተሻገሩት ፡ የሚያርፉባቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመሰግኑባቸው ፡ በደህና ፡ ያልተሻገሩት ፡ እግዚአብሔርንና ፡ እድላቸውን ፡ የሚወቅሱባቸው ፡ የሚያማርሩባቸው ፡ ሽፍታ ፡ ደብድቦዋቸው ፡ ወይም ፡ በሽታ ፡ አሞዋቸው ፡ የወጡት ፡ የሚያገግሙባቸው ፡ ወይም ፡ ሞተው ፡ የሚቀበሩባቸው ፡ ቦታዎች ፡ ናቸው ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ አባይን ፡ ለመሻገር ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ብረት ፡ ያላቸው ፡ ነጋዴዎችና ፡ ሌሎች ፡ መንገ

ደኞች ፡ እስኪጠራቀሙ ፡ ጎሀጽዮን ፡ በፍር ፡ ሲጠባበቅ ፡ የቆዩው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንጋት ፡ ላይ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ ወዳባይ ፡ ከወረደ ፡ በሁዋላ ፡ አንድ ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ የሚሄዱ ፡ መነኩሴ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ሶስት ፡ ሳምንት ፡ ተጉዘው ፡ ጎሀጽዮን ፡ ደረሱ ። ያባይ ፡ መንገደኞች ፡ ከመነሳታቸው ፡ በፊት ፡ ቢደርሱም ፡ ኖር ፡ ያነለት ፡ መንገዳቸውን ፡ ለመቀጠል ፡ አሳብ ፡ አልነበራቸውም ።

በትንሹ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ካላረፉ ፡ ከዚያም ፡ በሁዋላ ፡ በቅሉ ፡ የሚያከራያቸው ፡ ካላገኙ ፡ እንዲያ ፡ ደክሞዋቸው ፡ እንዲያ ፡ እግሮቻቸው ፡ እዩተወላከፉ ፡ ሊሸሹት ፡ በሚገባቸው ፡ እንቅፋትና ፡ ጋሬጣ ፡ ላይ ፡ እዩቆሙ ፡ እንዲያ ፡ ሀይላቸው ፡ በጭራሽ ፡ ጥሎዋቸው ፡ ሊሄድ ፡ ሜፉን ፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ እዩተጠራሞቱ ፡ ያባይን ፡ በርሀ ፡ እስካቀበቱና ፡ ቁልቁለቱ ፡ ሊዘልቁ ፡ እንደማይችሉ ፡ ተረድተው ፡ እዚያ ፡ የሚያርፉበት ፡ ለማግኘት ፡ ነበር ፡ የሚቸኩሉ ።

መንገደኛው ፡ መነኩሴ ፡ ወፍራም ፡ ምርኩዛቸውን ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ ይዘው ፡ የከሳ ፡ ሰውነታቸው ፡ ያለውን ፡ ክብደት ፡ ሁሉ ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ አሳርፈው ፡ ትንሽ ፡ ቆም ፡ ብለው ፡ ባካባቢው ፡ ያሉትን ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ተመለከቱና ፡ ከሁሉም ፡ ለመንገዱ ፡ ቀረብ ፡ ወደምትለው ፡ ቤት ፡ ሄዱ ። እዚያ ፡ አንድ ፡ እጃቸውን ፡ አስቀድመው ፡ መሬት ፡ አስይዘው ፡ በሱ ፡ ርዳታ ፡ በግድ ፡ ተጎትተው ፡ ሲቀመጡ ፡ “እሁሁ---------እናቴ !” አሉ ፡ ድምጻቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ በረዥሙ ፡ ተንፍሰው ።

የቤቱ ፡ እመቤት ፡ ያን ፡ ረዥም ፡ “ እሁሁ -- እናቴ ፡” ሲሰሙ ፡ ከውስጥ ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ጠጋ ፡ አሉና ፡ አስወጥተው ፡ ቢመለከቱ ፡ አንድ ፡ ደበሎ ፡ የለበሱ ፡ የደበሎ ፡ ቆብ ፡ የደፉ ፡ እግሮቻቸው ፡ በቆዳ ፡ ተሸፍነው ፡ በጠፍር ፡ የተተበተቡ ፡ መነኩሴ ፡ ወፍራም ፡ ምርኩዛቸውን ፡ ባጠገባቸው ፡ አጋድመው ፡ እሳቸው ፡ ክርናቸውን ፡ እመሬት ፡ ተክለው ፡ በጃቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ደግፈው ፡ ተጋድመው ፡ አዩ ። መነኩሴው ፡ ጀርባቸውን ፡ ለበሩ ፡ ሰጥተው ፡ ስለ ፡ ተጋደሙ ፡ ከዚያ ፡ ፊታቸውን ፡ ለማየት ፡ አይቻልም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የቤቱ ፡ እመቤት ፡ ግፋፑን ፡ ወደ፡

መንገደኛው ፡ ሄዱና ፡-

"እንዴት ፡ አደሩ ፡ አባቱ ፡ ምን ፡ ይሻሉ ?" አሉ ፡ በደግ፡ ፊት ፡ ፈገግ ፡ ብለው ።

"ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ እመይቴ ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ የምሄድ ፡ የደከመኝ ፡ መንገደኛ ፡ ነኝ ። እዚህ ---- ሲሆን ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ያለዚያም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የሚያሳርፈኝ ፡ ባገኝ ፡ በቅሎ ፡ ፊልጌ ፡ ተከራይቼ ፡ ለመሻገር ፡ አስቤ ፡ ነበር ። እስዎ ፡ ቤት --- ማረፊያ ፡ ይገኛል ? እንዲያው ፡ አይደለም ፡ ገንዘብ ፡ እከፍላለሁ።" አሉ ፡ አባ ፡ አፋቸው ፡ እየፈራ ።

"እኔም ፡ የምኖረው ፡ እንግዳ ፡ እየተቀበልሁ ፡ ከዚያ ፡ በማገኘው ፡ ስለሆነ ፡ እዚህ ፡ ቢያርፉ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ለስዎ ፡ አይመችዎትምና ፡ ሌላ ፡ ቤት ፡ ቢፈልጉ ፡ ይሻላል ።"

"ለእስ ፡ ከዚህ ፡ ተነስቶ ፡ ሁለት ፡ ርምጃ ፡ እንኳዋ ፡ ከመራመድ ፡ የማያሻልና ፡ የማይመች ፡ ነገር ፡ የለም !"

"እእምኮ ፡ ድካምዎን ፡ ስላዩሁ ፡ ደህና ፡ እርፈው ፡ በሚተኙበት ፡ ቤት ፡ ቢገቡ ፡ ይሻልዎታል ፡ ብዬ ፡ ነው ! እኔ ፡ ቤት ፡ በሽተኛ ፡ አለ ። ሌሊት ፡ አቅኑኝ ፡ እገላብጡኝ ፡ ሲል ፡ መብራት ፡ አብርቼ ፡ እሱን ፡ ስጠብቅ ፡ ነው ፡ የማድር ። ስለዚህ ፡ እንቅልፍ ፡ አግኝተው ፡ አያድሩም ፡ ብዬ ፡ ነው ።"

"እንዲያስ ፡ ከሆነ ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ እፈልጋለሁ ። ብቻ ፡ አሁን ፡ ውሀ ፡ ቢሰጡኝና --- ትንሽ ፡ እርፌ ፡ ቆይቼ ፡ ብሄድ ፡ ይፈቅዱልኛል ?"

"ምነው ፡ አባቴ ! የሚፈልጉትን ፡ ያክል ፡ ቆይተው ፡ ይረፉ ! ቅራሪ ፡ ልስጥዎ ?"

"የለም ፡ ጥሩ ፡ ውሀ !"

ከዚያ ፡ ውሀ ፡ በኩባያ ፡ አምጥተው ፡ ለመነኩሴው ፡ ሰጥተዋቸው ፡ ሲጠጡ ፡-

"የሚስማማ ፡ ቤት ፡ ካላገኙ ፡ ተመልሰው ፡ ይምጡ ፡ እርፈው ፡ እንዲተኙ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሌላው ፡ ቤት ፡ የሚገኘው ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ እዚህም ፡ አለ ! ገንዘብዎን ፡ ከከፈሉ ፡ ምንም ፡ የሚቸግር ፡ ነገር ፡ የለም ። አሉ ፡ ባለቤትዋ ።

"እሺ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ።" አሉ ፡ አባ ፡ ውሀውን ፡ ጠጥተው ፡ ሲጨርሱ ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ ያስተናጋጃቸውን ፡ ደኅና ፡ ፊት ፡ እዩተመለከቱ ።

መነኩሴው ፡ እዚያው ፡ በተጋደሙበት ፡ ብዙ ፡ ቆይተው ፡ ካረፉ ፡ በሁዋላ ፡ ተነስተው ፡ ባቅራቢያው ፡ ያሉትን ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ እዩዞሩ ፡ ቢያዩ ፡ አንዳንዶቹ ፡ መሸተኞች ፡ ተሰብስበው ፡ የሚያወኩባቸውና ፡ አዝማሪዎች ፡ የሚዘፍኑባቸው ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንግዶች ፡ ቀድመው ፡ ገብተው ፡ የያዙዋቸው ፡ ሆነው ፡ ስላገኙ ዋቸው ፡ ሌሎቹም ፡ በጣም ፡ ርቀው ፡ ስለ ፡ ታዩዋቸው ፡ ሁሉንም ፡ ትተው ፡ መጀመሪያ ፡ ወዳረፉበት ፡ ቤት ፡ ተመለሱ ።

"ተመልሰው ፡ መጡ ? አባቴ ! ምነው ፡ የሚስማማ ፡ ቤት ፡ አጡ ?" አሉ ፡ ባለቤትዋ ።

"ሁሉንም ፡ አዩሁት ። እስዎ ፡ ይሻሉኛል ፡ ብዬ ፡ መጣሁ ።

"የኔ ፡ ቤት ፡ የሚሻል ፡ ከመሰለዎ ፡ ይምጡ ፡ ይግቡና ፡ እዚህ ይቀመጡ !" አሉ ፡ የቤቱ ፡ እመቤት ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ መደብ ፡ ላይ ፡ የበግ ፡ እንዛ ፡ ጣል ፡ አደረጉና ።

መንገደኛው ፡ መነኩሴ ፡ ከተቀመጡበት ፡ መደብ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ትንሽ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ባንድ ፡ የጠፍር ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ በሽ ተኛው ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ግርግዳው ፡ አዞሮ ፡ ተከናንቦ ፡ ተኝቶ ዋል ። አባ ፡ የቤቱ ፡ እመቤት ፡ በሽተኛ ፡ አለና ፡ እረፍት ፡ አያገ ኙም ፡ ሲሉዋቸው ፡ በሽተኛው ፡ የሚያቃስት ፡ ወይም ፡ ከላይ ፡ ከላይ ፡ የማያቃትተው ፡ መስሉዋቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እን ዲያ ፡ ያለ ፡ ማቃሰትና ፡ ከላይ ፡ ከላይ ፡ መተንፈስ ፡ ከገቡ ፡ ጀምሮ ፡ ስላልሰሙ ፡ ሌላ ፡ ቤት ፡ ፍለጋ ፡ ሲዞሩ ፡ የደከሙት ፡ አስ ጸጠታቸው ።

በሽተኛው ፡ ድምጹን ፡ አጥፍቶ ፡ ብዙ ፡ ያቆይና ፡ "እእ----" ብሎ ፡ እንደሚያንጎራጉር ፡ ሁሉ ፡ በዝቅተኛ ፡ ድምጽ ፡ ካማለለ በሁዋላ ፡ ወዲያው ፡ እከታትሎ ፡ " ውሀ " ይላል ። ከዚያ ፡ ባ ቤትዋ ፡ ተጠንቅቀው ፡ ከራሱ ፡ ቀና ፡ ያደርጉና ፡ ትንሽ ፡ አጠ ተው ፡ ወደ ፡ ትራሱ ፡ ይመልሱታል ። ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ውሀ ፡ የሚ ማውን ፡ ያክል ፡ ብዙ ፡ አይጠጣም ።

"ምንም ፡ ናቸው ?" አሉ ፡ አባ ፡ ባለቤትዋ ፡ ለበሽተኛው

የሚጨነቁትን ፡ ጭንቀትና ፡ የሚጠነቀቁትን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሲመለከቱ ፡ ቆይተው ፡ ልጃቸው ፡ ወይም ፡ የሚወዱት ፡ የቅርብ ፡ ዘመዳቸው ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ ገምተው ።

" እዚህ ፡ አምጥተው ፡ እስኪጥሉልኝ ፡ ድረስ ፡ አይቸው ፡ የማላውቅ ፡ የግዜር ፡ መንገደኛ ፡ ነው ! "

" እንዲያው ፡ የማያውቁዋቸውን ፡ መንገደኛ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ እንደናት ፡ ተጨንቀው ፡ የሚያስታምሙ ?" አሉ ፡ መነኩሴው ፡ በጣም ፡ ተገርመው ።

"ለጽድቅም ፡ ለጥቅምም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማወቅስ ፡ አላውቀውም ።"

" እንዴት ?"

" እዚህ ፡ አምጥተው ፡ የጣሉልኝ ፡ ነጋዴዎች ፡ አስር ፡ ብር ፡ አዋጥተው ፡ ለኛም ፡ ባንችም ፡ ለነፍሳችን ፡ ይሆናልና ፡ አደራሽ ፡ አስታምሚ ፡ አድኚው ፡ ብለው ፡ ጥለውልኝ ፡ ስለሄዱ ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ ገንዘቡ ፡ ትንሽ ፡ ባለመሆኑ ፡ ለገንዘቡ ፡ ስል ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የሱ ፡ ሁኔታ ፡ ስላሳዘነኝ ፡ ይሄው ፡ ካስራ ምስት ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ እንግዳ ፡ አልቀበል ፡ ትቸው ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እንኩዋ ፡ አልል ፡ እንዲህ ፡ እንደሚያዩኝ ፡ ቀን ፡ ከሌት ፡ እሱን ፡ ቀና ፡ ገደም ፡ እንዳደረግሁ ፡ ነኝ ። እስከ ፡ ትናንት ፡ ድረስ ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ እህል ፡ ይቀምስ ፡ ነበር ። ከትናንት፡ ማታ ፡ ጀምሮ ፡ ግን ፡ እህሉን ፡ ጨርሶ ፡ ትቶ ፡ ውሀ ፡ ብቻ ፡ አይለየኝ ፡ ይላል ! ውሀውንም ፡ ቢሆን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ስጡኝ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ሲሰጡት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጥሙን ፡ ቆርጦ ፡ አይጠጣም ። አሁንስ ፡ እንጃ ! ድካሙ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ መሰለኝ !"

" ለመሆኑ ፡ በሽታቸው ፡ ምንድነው ?"

" አባይ ፡ በርሀ ፡ ውስጥ ፡ ሽፍታ ፡ ደብድቦ ፡ ጥሎት ፡ እዚያ በደምና ፡ በዝናም ፡ ተነክሮ ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ የሚሄዱ ፡ ነጋዴዎች ፡ ደርሰው ፡ ወዲህ ፡ አመጡት ።"

" እሳቸው ፡ የየት ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ይሆኑ ?"

" የጎጃም ፡ ሰው ፡ ነው ። አዲስ ፡ አበባ ፡ ቆይቶ ፡ ወዳገሩ ፡ ሲመለስ ፡ እግዚአብሄር ፡ ያሳይን ፡ መቅሰፍት ፡ አዘዘበት ! ዋ ፡

ልጇን ! ከንበል ፡ ያርገኝ ! ይህን ፡ መሳይ ፡ ወጣት !" አሉ ፡ ባለ ቤትዋ ፡ እንባቸው ፡ ቸርፈፍ ፡ ብሎ ።

"የት ፡ ጎጃም ፡ ይሆኑ ፡ ይሆን ?"

"እሱን ፡ እንኳዋ ፡ አልጠዩቅሁትም ፡ እስቲ ፡ ትንሽ ፡ ቢሻ ሰው ፡ እንጠይቀዋለን ። እስከ ፡ ትናንት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ይህና ፡ ይናገር ፡ ነበር ። እስዎስ ፡ የት ፡ ጎጃም ፡ ነዎ ፡ አባቴ ?"

"ልደቴ ፡ እንኳዋ ፡ ትግሬ ፡ ነው ፡ ወላጆቼም ፡ ትግሬ ፡ ነው ፡ ያሉ ። እኔ ፡ ግን ፡ ለትምርት ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ ሄጄ ፡ ሞጣም ፡ ደብረ ፡ ወርቅም ፡ ዲማም ፡ ቆይቻለሁ ። አሁን ፡ ወደ ፡ ሞጣ ፡ መመ ለሴ ፡ ነው ።"

"አ --- ! ትግሬ ፡ ስለሆኑ ፡ ነዋ ፡ በልጅነትዎ ፡ የመለኩሱ!

"እንዴት ? በልጅነቱ ፡ የሚመነኩሰው ፡ ሁሉ ፡ ትግሬ ፡ ነው ?"

"በዚህ ፡ ሲያልፉ ፡ ከምናያቸው ፡ ወጣት ፡ መለኩሲዎች፡ አገራቸውን ፡ ስንጠይቃቸው ፡ የሚበዙት ፡ ትግሮች ፡ ነን ፡ ይሉናል ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ወዲያውም ፡ ትግሬ ፡ በልጅነት ፡ የሚመለኩስበት ፡ አገር ፡ ቢሆን --- ያስመሰግነዋል ፡ የበይማኖ ተኛ ፡ አገር ፡ ያሰኘዋል ፡ እንጂ ፡ አያስነውረውም !" አሉ ፡ ባለ ቤትዋ ፡ መነኩሴው ፡ የተቀየሙ ፡ መስለዋቸው ።

"እሱስ ፡ እውነትዎ ፡ ነው ።" አሉ ፡ አባ ፡ እንግዶቸውን ፡ ይፋ ፡ አድርገው ።

"ስምዎስ ፡ ማን ፡ ይባላል ? እስቲ ፡ የስዎን ፡ ስራ ፡ ቀምሼ ፡ ላናግሬዎ ፡ እንጂ !" አሉ ፡ የቤቱ ፡ እመቤት ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳ ቅ ፡ ብለው ።

"ጥሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መተዋወቅ ፡ ምን ፡ ከፋት ፡ አለው ! አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ እባላለሁ ።"

"አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ! እውነተኛ ፡ የመነኩሴ ፡ ስም ፡ ነው ! እኔ ፡ የሽመቤት ፡ ዘውዴ ፡ እባላለሁ ። ከጎንደር ፡ መጥቼ ፡ እዚህ ፡ ብዙ ፡ አመት ፡ ስለ ፡ ተቀመጥሁ ፡ አገሬን ፡ ረስቸዋለሁ ።"

"አዎ ፡ አገር ፡ የሚኖሩበት ፡ ነው ! እኔም ፡ ብዙ ፡ የኖርሁ ፡ ጎጃም ፡ ስለሆነ ፡ ከትግሬ ፡ ይልቅ ፡ አገሬ ፡ የሚመስለኝ ፡ ጎጃም፡ ነው ።"

“ እስቲ ፡ አባቴ ፡ ምንም ፡ ቢያክምዎ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልለምንዎ !”

“ ምን ? ስለ ፡ ደኅነቴ ፡ እያሰቡ ፡ አሁን ፡ በጣም ፡ ተሽሎኛል !”

“በሽተኛው ፡ ውሀ ፡ ያለ ፡ እንደሆን ፡ እንዲሰጡልኝ ፡ ነው ። እኔ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሮጥ ፡ ብዬ ፡ እገበዙ ፡ ቤት ፡ ደርሼ ፡ እመጣለሁ ። ልቡ ፡ ሲባባ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ አቅርቡኝ ፡ እያለ ፡ መስመን ፡ ከጀመረ ፡ ሶስት ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ስለሆን ፡ ድንገት ፡ የሚሆነው ፡ አይታወቅምና ፡ የፈለገው ፡ እንዲፈጸምለት ፡ አደራ ፡ ብያቸው ፡ ልምጣ ።”

የቤቱ ፡ እመቤት ፡ በክራይ ፡ የሚያስታምሙትን ፡ በሽተኛ እንዲያቀርቡላቸው ፡ ገበዙን ፡ ለመስመን ፡ ወጥተው ፡ ሲሮጡ ፡ አባ ፡ አለም ፡ ለምኔ ፡ ደግነታቸውን ፡ እያደነቁ ፡ ካይናቸው ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ሲመለከቷቸው ፡ ቆይተው ፡ ከዚያ ፡ አይናቻቸውን ፡ መለስ ፡ አደረጉና ፡ ጀርባውን ፡ ለሳቸው ፡ ሰጥቶ ፡ ተከናንቦ ፡ በተኛው ፡ በሽተኛ ፡ ላይ ፡ ተክለው ፡ ይመለከቱ ፡ ጀመር ።

ያን ፡ የማይንቀሳቀሰና ፡ ድምጹን ፡ አጥፍቶ ፡ እፊታቸው ፡ የተጋደመ ፡ በሽተኛ ፡ ትኩር ፡ ብለው ፡ በተመለከቱ ፡ መጠን ፡ ስለሱ ፡ ወይዘሮ ፡ የሽመቤት ፡ ያሉት ፡ ሁሉና ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ሊያያዝ ፡ የሚችለው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳብ ፡ ተሰብስቦ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ መጥቶ ፡ እንደ ፡ ባለጉዳዮች ፡ ሸንጎ ፡ ራሳቸው ፡ ውስጥ ፡ ይንጫጫባቸው ፡ ጀመር ።

ከዚያ ፡ ጆሮዎቻቸው ፡ እንደ ፡ ተከፈቱ ፡ ካካባቢያቸው ፡ የሚመጣውን ፡ ድምጽ ፡ መስማት ፡ ትተው ፡ እዝነ ፡ ህሊናቸው ፡ በራሳቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚንጫጫውን ፡ አሳብ ፡ መስማት ፡ ጀመረ ። አይኖቻቸው ፡ ፍጥጥ ፡ ብለው ፡ በተተከሉበት ፡ ቦታ ፡ እንዳሉ ፡ ማየታቸውን ፡ ትተው ፡ አይነ ፡ ህሊናቸው ፡ ካስራምስት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ያ ፡ ሰውዬ ፡ የነበረበትን ፡ ሁኔታና ፡ ከዚያም ፡ አባይ ፡ በረሀ ፡ ተከትሎት ፡ ወርዶ ፡ ሽፍቶች ፡ ከበው ፡ ሲደበድቡት ፡ ይመለከት ፡ ጀመረ ።

“ የጎጃም ፡ ሰው ፡ ነው ! አዲስ ፡ አበባ ፡ ቆይቶ ፡ ሲመ

ለስ ፡ እግዜር ፡ ያባይን ፡ መቅሰፍት ፡ አዘዘበት ! ዋ ፡ ልጄን ፡ ከንፀል ፡ ያርገኝ ! ይህን ፡ የመሰለ ፡ ወጣት ! በይምና ፡ በገዘናብ ፡ ተነከሮ ፡ ወድቆ ፡ ተገኘ ! ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ እህል ፡ ይቀምስ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ጨርሶ ፡ ተወው ! አሁንስ ፡ እንጃ ! ድካሜ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ መሰለኝ ! ልቡ ፡ ሲባባ ፡ ጊዜ ፡ አቁርቡኝ ፡ አለ ! ” ይህና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድምጽ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ከዚያ ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ከዚያ ፡ ሌላው ፡ የበለጠ ፡ ለመጀመጥ ፡ እንደሚፎካከር ፡ ሁሉ ፡ እዬጮኸ ፡ ሲንጫጫባቸው ፡ ጆሮዋቸው ፡ ደነቆረ ፤ ራሳቸውን ፡ አመማቸው !

ከዚያ ፡ ሰውዬውን ፡ ማየት ፡ ጀመሩ ። አንድ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቁመት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክብደት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ እዬተለዋወጡ ፡ ታዩዋቸው ።

መጀመሪያ ፡ ዘለግ ፡ ብሎ ፡ ወፈር ፡ ያለ ፡ ጠይም ፡ ሰው ፡ ታያቸው ። ብዙ ፡ አይነ ፡ ሀሊናቸው ፡ ብዙ ፡ አልተከተለውም ። ስለዚህ ፡ እሱ ፡ ሲያልፍ ፡ ዘለግ ፡ ብሎ ፡ ቀጠን ፡ ያለ ፡ ቀይ ፡ ሰው ፡ ብቅ ፡ አለ ። እሱንም ፡ አይነ ፡ ሀሊናቸው ፡ አልተከተለውም ። ወዲያው ፡ አጠር ፡ ወፈር ፡ ያለ ፡ ወይ ፡ ጥቁርነቱ ፡ የሚያደላ ፡ ሰው ፡ ተተካ ። የለም ! እሱም ፡ ላይ ፡ አይነ ፡ ሀሊናቸው ፡ ብዙ ፡ አርፎ ፡ አልቆዩም ። ከዚያ ፡ ትንሽ ፡ አጠር ፡ ወዲያውም ፡ ቀጠን ፡ ያለ ፡ ቀይ ፡ ጠጉሩ ፡ ላዛ ፡ ትንሽ ፡ ፊቱን ፡ ቅር ፡ ያለው ፡ የሚመስል ፡ ወጣት ፡ መጣ ። እሱ ፡ ላይ ፡ አይነ ፡ ሀሊናቸው ፡ አረፈ ። አሳባቸው ፡ ከሱ ፡ በሁዋላ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ወጣት ፡ አመጣ ፡ አይነ ፡ ሀሊናቸው ፡ ግን ፡ ሁዋላ ፡ የመጣውን ፡ ትንሽ ፡ አየት ፡ አድርጎ ፡ ፊት ፡ ወደረፈበት ፡ ተመለሰ ። ልባቸው ፡ ያ ፡ መከራ ፡ በዚያ ፡ ወጣት ፡ ላይ ፡ እንዲደርስ ፡ ስላልፈለገ ፡ ከሱ ፡ በፊት ፡ ያለፉትንም ፡ አዲሶችንም ፡ እያለዋወጠ ፡ አመጣ ። አይነ ፡ ሀሊናቸው ፡ ግን ፡ ሁሉንም ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ በዬሄደበት ፡ ይከተል ፡ ጀመር ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄዶ ፡ ከተነሳበት ፡ ቦታ ፡ ተከትሎት እስከ ፡ ጎሀጽዮን ፡ መጥቶ ፡ እነጋዴዎች ፡ መደብር ፡ ሰፈረ፡ ከዚያ ፡ ነጋዴዎች ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ካልተጠራቀመ ፡ እንነሳም፡

ስላሉ ፡ ያ ፡ ወጣት ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ በመንገድ ፡ ሰው ፡ አላጣም ፡ ብሎ ፡ ብቻውን ፡ ወዳባይ ፡ ሲወርድ ፡ አብሮት ፡ ወረደ ። እዚያ ፡ አንድ ፡ መጥፎ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አራት ፡ ናቸው ? አምስት ፡ ሽፍቶች ፡ እንዲያ ፡ ያለ ፡ ነጠላ ፡ መንገደኛ ፡ ሲያጋጥማቸው ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ እንዲመቻቸው ፡ መንገዱን ፡ እመሀል ፡ አድርገው ፡ ደንጋዩንም ፡ ዛፉንም ፡ በየፊታቸው ፡ ጋርደው ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ! ወጣቱ ፡ እዚያ ፡ መጥፎ ፡ ቦታ ፡ ሲደርስ ፡ በቅርብ ፡ የነበረው ፡ ሽፍታ ፡ ራሱን ፡ ለመምታት ፡ ያነዘረው ፡ ዱላ ፡ ራሱን ፡ ስቶ ፡ እትከሻው ፡ ላይ ፡ ስላረፈ ፡ የመጀመሪያው ፡ ዱላ ፡ አስደነገጠው ፡ እንጂ ፡ አላሸነፈውም ! ከዚያ ፡ ወጣቱና ፡ ሽፍታው ፡ ግብ ፡ ለግብ ፡ ሲገጥሙ ፡ ሌሎች ፡ ሽፍቶች ፡ ከያሉበት ፡ ተሰብስበው ፡ ከጉዋደኛቸው ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ተያያዘ ፡ አንዱ ፡ ግንባሩን ፡ ሌላው ፡ ማጅራቱን ፡ ሌላው ፡ ወገቡን ፡ በዱላ ፡ ይደበድቡት ፡ ጀመር ! ሆኖም ፡ በጦር ፡ ነው ? ወይስ ፡ በጩቤ ፡ ወግተውት ፡ እስኪወድቅ ፡ ድረስ ፡ ይታገል ፡ ነበር ! “ ሙሆ ፡ እንዳያስይዘን ፡ እንግደለው ! ” አለ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ አንዱ ። “ አባክህ ፡ ያው ፡ የሞተ ፡ ያክል ፡ ነው ! አሁን ፡ ባይሞት ፡ ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡ ይሞታል ! ይልቅ ፡ የያዘውን ፡ ቶሎ ፡ እንውሰድና ፡ ሰው ፡ ሳይደርስ ፡ እንሂድ ! ” አለ ፡ ሌላው ። ከዚያ ፡ ያገኙትን ፡ በርብረው ፡ ወስደው ፡ እሱን ፡ እዚያ ፡ በደም ፡ እዬዋኘ ፡ ጥለውት ፡ ሄዱ ።

አባ ፡ እለም ፡ ለምኔ ፡ ባሳባቸው ፡ ፈጥረው ፡ እፊታቸው ፡ ከተጋደመው ፡ በሽተኛ ፡ ጋር ፡ ያዋሀዱት ፡ ወጣት ፡ ከሽፍቶች ፡ ጋር ፡ ሲታገል ፡ አብረው ፡ ሲታገሉ ፡ ሲደበደብ ፡ አብረው ፡ ሲደበደቡ ፡ ቆይተው ፡- ተወግቶ ፡ ሲወድቅ ፡ ልክ ፡ እሳቸው ፡ እንደ ፡ ተወጉ ፡ አሞዋቸው ፡ “ እእ — ! ” አሉ ።

እንዲያ ፡ እሡንት ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ እንዲያ ፡ ከገሀነም ፡ በሚያስፈራ ፡ ቅዠት ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ከዚያ ፡ የሚወጡበት ፡ አጥተው ፡ ሲሰቃዩ ፡- “ እእ — ውሀ — ! ” አሉ ፡ በሽተኛው ፡ በደካማ ፡ ድምጽ ። ወዲያው ፡ ያ ፡ ሲያደነቁራቸው ፡ የነበረ ፡ ያሳብ ፡ ጫጫታ ፡ ገዥ ፡ አለ ። ያ ፡ ሲያስጨንቃቸው ፡ የነበረ ፡ ቅዠት ፡ ከፊታቸው ፡ ጠፋ ። አሁን ፡ ያን ፡ መከራ ፡

የተቀበለ ፡ ሰው ! ባሳብ ፡ አይደለም ፡ በገሀድ ፡ ባካል ፡ ሊያዩት ፡ ነው ! ባይን ፡ ሀሊና ፡ ያዩት ፡ ባካል ፡ የሚያዩት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ምን ፡ ሊውጣቸው ፡ ነው ?

“ እየ ፡ መከራየ ! ምን ፡ ልሁን ፡ ይሆን ? እባክህ ፡ በርታ ፡ ልቤ ! እባክህ ፡ ታጠቅ ! ” አሉ ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ውሀውን ፡ ለመቅዳት ፡ ሲሄዱ ።

የምን ፡ መበርታት ! የምን ፡ መታጠቅ ! ልባቸው ፡ በመበርታት ፡ ፈንታ ፡ እንዲያጠውም ፡ ካለበት ፡ ቦታ ፡ ወጥቶ ፡ ለመብረር ፡ እንደ ፡ ፊኛ ፡ ሁሉ ፡ በደረታቸው ፡ ውስጥ ፡ ይንገፈገፍ ፡ ጀመር ። ጉልበታቸው ፡ ከቅሙ ፡ በላይ ፡ ሸክም ፡ እንደሚጫንበት ፡ ሁሉ ፡ ይብረከረክ ፡ ጀመር ። አንጀታቸው ፡ ወራራ ፡ እንደ ፡ ገባው ፡ ይደበላለቅ ፡ ይንጫጫ ፡ ጀመር ።

እንዲያ ፡ እየሆኑ ፡ ውሀ ፡ በኩባያ ፡ ይዘው ፡ በሽተኛው ፡ ፊቱን ፡ ባዞረበት ፡ በግርግዳው ፡ በኩል ፡ ዞሩ ። ከንንቡ ፡ ከሁዋላ ፡ በኩል ፡ መጥቶ ፡ እስከ ፡ ግንባሩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከግርግዳው ፡ ወገን ፡ ፊቱ ፡ ደህና ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

ግንባሩ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ እግድም ፡ የተፈነከተው ፡ ቁስሉ ፡ ደርቆ ፡ ጥቁር ፡ ቅርፍት ፡ ይዞዋል ። ፊቱም ፡ እንዲሁ ፡ ሽፍቶች ፡ የደበደቡት ፡ ከሽፍቶች ፡ ጋር ፡ ሲታገል ፡ ጫካ ፡ የላጠው ፡ ሲወድቅ ፡ ድንጋይ ፡ ወይም ፡ ደረቅ ፡ መሬት ፡ የጋጠው ፡ ቁስሉ ፡ ደርቆ ፡ ጥቁር ፡ ቅርፍት ፡ ይዞዋል ። ከንፈሮቹና ፡ የተከደኑ ፡ አይኖቹ ፡ ብቻ ፡ በጥቁር ፡ ቅርፍት ፡ አልተሸፈኑም ። የበሽተኛው ፡ ፊት ፡ እንዲያ ፡ ከሰል ፡ ብሎ ፡ ወዲያው ፡ ከትኩሳቱ ፡ የተነሳ ፡ ላቡ ፡ እየተንጠፈጠፈ ፡ ሁሉንም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ሲመለከቱት ፡ በፍም ፡ የሚጠበስ ፡ ያረረ ፡ ስጋ ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ አይመስልም ።

ያን ፡ በሽተኛ ፡ ድሮ ፡ የሚያውቀው ፡ ሰው ፡ ያንለት ፡ እንዲያ ፡ እርር ፡ ብሎ ፡ እንዲያ ፡ ከስሎ ፡ ሲያየው ፡ እንኩዋንስ ፡ እንዲሁ ፡ ሊያለዩው ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ምሎ ፡ ቢነግረውም ፡ ማመኑ ፡ ባስቸገረው !

“ ማነህ ፡ አንተ ! በዛ——ብህ ፡ ነ——ህ ? እባክህ ፡ እባክህ ፡ አትሁን ! እባ——እባክህ ፡ ሌላ ፡ ሁን ! ” አሉ ፡ አባ ፡ ገና ፡ በሽተኛ

ውን ፡ ሲያዩ ፡ በኩባያ ፡ የያዙትን ፡ ውሀ ፡ ጥለው ፡ እዩተንቀጠቀጡ ።

በሽተኛው ፡ ስሙን ፡ ሲሰማ ፡ የተከደኑ ፡ አይኖቹን ፡ ገለጥ ፡ አድርጎ ፡ እፊቱ ፡ የቆሙትን ፡ መነኩሴ ፡ አዩና ፡ ''ሰ---ብለ !'' እለ ፡ ባር ፡ በሚጎትተው ፡ ድምጹ ።-

ምንም ፡ ደበሎ ፡ ሰብሳ ፡ የደበሎ ፡ ቆብ ፡ ደፍታ ፡ ልትደርስባት ፡ ትችላለች ፡ ተብሎ ፡ በማይገመት ፡ ቦታ ፡ ብትገኝ ፡ ምንም ፡ ደምዋ ፡ ደርቆ ፡ ስጋዋ ፡ አልቆ ፡ የባሳ ፡ ቆዳዋ ፡ ባጥንትዋ ፡ ላይ ፡ በማሸግያ ፡ የተለጠፈ ፡ ቢመስል ፡ ምንም ፡ የሰብለ ፡ ጥላ ፡ እንጂ ፡ ሰብለ ፡ ባትሆን ፡ ምንም ፡ ውበትዋንና ፡ ደምግባትዋን ፡ ራብና ፡ ጥም ፡ መንገላታት ፡ ቢቀሙዋት ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ሰብለን ፡ ሰብለ ፡ ካደረጋት ፡ ሁሉ ፡ ከመንፈስዋ ፡ ውበትና ፡ ብርሃት ፡ በቀር ፡ የተረፋት ፡ ነገር ፡ ባይኖር ፡ በዛብህ ፡ አይኑን ፡ ገለጥ ፡ አድርጎ ፡ ሲያያት ፡ ወዲያው ፡ አወቃት !

" እንዲህ ፡ ላላመልጠው ፡ መከራየን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ መግጠሙን ፡ ፈርቼ ፡ ስሸሽ ፡ ቆዩሁ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ መሆንህን ፡ ገና ፡ ቅድም ፡ ሰውነቴ ፡ ነግሮኛል ! ካንተና ፡ ከኔ ፡ በቀር ፡ እግዚአብሄር ፡ በሌላ ፡ እንዲህ ፡ እንደማይጨክን ፡ አውቄዋለሁ ! ምነው ፡ አንተ ፡ እግዚአብሄር ፡ ርሀሩህ ፡ ነህ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነህ ፡ ትባልየል ? የት ፡ ነው ፡ ርሀራሄህ ? ምን ፡ አለህ ? ምን ፡ አልሁህ ? እግዚኦ ! እግዚኦ ! " እያለች ፡ እዩጮኸችና ፡ እንደብድ ፡ እዩለፈለፈች ፡ ስትወድቅ ፡ ስትነሳ ፡ ብዛብህ ፡ የተኛበትን ፡ አልጋ ፡ እዩዞረች ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እግሩን ፡ እያቀፈች ፡ ስትስም ፡ እንባዋን ፡ እያጎረፈች ፡ እዩወደቀችም ፡ እዩተነሳችም ፡ እግዚአብሄር ፡ እዚያ ፡ እፊትዋ ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ ሁሉ ፡ አይንዋን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ፍጥጥ ፡ አድርጋ ፡ እሱን ፡ ስትወቅስና ፡ ስታማርር ፡ ደግሞ ፡ ተመልሳ ፡ በበዛብህ ፡ ላይ ፡ እዩወደቀች ፡ እግዚኦ ፡ እያለች ፡ ስትጮህ ፡-

" ዋ ፡ ልጄን ! ዋ ፡ ልጄን ! ከንበል ፡ ያርገኝ ! ሞተ ? አረፈ ? " አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሽመቤት ፡ ከውጭ ፡ ልቅሶውን ፡

ሲሰሙ ፡ እዬሮጡ ፡ ገብተው ፡ ደረታቸውን ፡ እዬመቱ ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ በሽተኛው ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ ቢያዩ ፡ እሱም ፡ ያያል ፡ ይንቀሳቀሳል ፡ አልሞተም !

" ምንድነው ፡ ነገሩ ? ምን ፡ ሆኑ ? አባቴ ? አመመዎ ? " እሱ ፡ ሰብለን ፡ እበዛብህ ፡ እግር ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ከምታለቅስበት ፡ እንሰተው ።

" እኔማ ፡ ምን ፡ እሆናለሁ ! ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ ባይረግ ውማ ፡ ደህና ፡ ነበር ! ይህን ፡ ሳላይ ፡ ብሞትማ ፡ መልካም ፡ ነበር ! "

" ምን ፡ ሆኑ ? እስቲ ፡ ይንገሩኝ ፡ እባክዎ ! "

" እባክዎ ፡ ቀና ፡ ያድርጉኝ ፡ እመይቴ ! " አለ ፡ በሽተኛው ፡ አቁዋርጦ ፡ ወይዘሮ ፡ የሽመቤት ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ በንግድነት ፡ የተቀበሉዋቸው ፡ መነኩሴ ፡ ቆባቸውን ፡ ጥለው ፡ እያለቀሱ ፡ እንደብድ ፡ ያልተያያዘ ፡ ነገር ፡ ሲናገሩ ፡ እዬተመለከተ ፡ የሚያደርጉትን ፡ አጥተው ፡ ግራ ፡ ገብቶዋቸው ፡ ሳለ ። ከዚያ ፡ ወደሱ ፡ ሄደው ፡ ከተኛበት ፡ ቀና ፡ ሲያደርጉት ፡ እሱንም ፡ ሲያለቅስ ፡ አዩ ።

"ምን ፡ ነገር ፡ ነው ? ምን ፡ ጉድ ፡ ነው ? " አሉ ፡ በዛብህን ፡ ደግፈው ፡ አስቀምጠው ። ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ወጥተው ፡ ቢመለሱ ፡ ለቤታቸው ፡ ፍጹም ፡ እንግዳ ፡ መሆናቸው ፡ ከማስገረሙም ፡ ሌላ ፡ አስፈራቸው ።

" እባክዎ ፡ አታልቅሺ ፡ ይበሉ---ዋት ! ወዲህ ፡ ነይ ፡ ይበሉ---ዋት !" አለ ፡ በዛብህ ፤ በደከመ ፡ ድምጽ ።

" ማንን ? "

" ሰ---ብለን ። "

" ምን ፡ አለ ? ይሻለው ፡ ይሆን ? ይተርፍ ፡ ይሆን ? ሰው ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ይተርፋል ? " አሉ ፡ ሰብለ ፡ ባለቤትዋ ፡ በሽተኛውን ፡ ሲያነጋግሩ ፡ ቀረብ ፡ ብላ ።

" እሱስ ፡ ያው ፡ መሰንበቻውን ፡ ሲያተኩሰው ፡ የሚቃዥውን ፡ ነው ፡ አሁንም ፡ የሚቃዥ ። እተኩሶት ፡ ሲቃዥ ፡ ከሰብለ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ ካፉ ፡ አይወጣም ። ሰብለን ፡ ጥሩ

ልኝ ፡ ሰብለ ፡ ታንሳኝ ፡ ሰብለ ፡ ታስተኛኝ ፡ ሰብለ ፡ ትደግፈኝ ፡ እያለ ፡ የሰዋን ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ እንደ ---ጠሎት ፡ ሲደግም ፡ ነው ፡ የሰነበተ ። አሁንም ፡ እንደዘያው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ሰብለን ፡ ጥሩልኝ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ አተኩሶት ፡ መቃዠቱ ፡ ነው ! ያቺ ፡ ሰብለ ፡ የሚላት ፡ ምኑ ፡ እንደሆነች ፡ ከሱና ፡ ከእግዜር ፡ በቀር ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ! አሁን ፡ ግራ ፡ የገባኝ ፡ የስዎ :---" ብለው ፡ ሊጠይቁ ፡ ያሰቡትን ፡ ሳይጠይቁ ፡-

"ሰብለማ ፡ እኔ ፡ እያለቢስዋ ፡ እኔ ፡ ርጉምዋ ፡ ነኝ ! ባለቃልኪዳኑ ፡ ነኝ ! እመይቴ ፡ እባክዎ ፡ ይተርፍ ፡ ይመስልዎታል ? ሰው ፡ ይሆን ፡ ይመስልዎታል ! እስቲ ፡ እግዚአብሄር ፡ ያሳይዎ ፡ እመይቴ ! ሰው ፡ በሰው ፡ እንዲህ ፡ ይጨክናል ? ልብሱን ፡ ገፈው ፡ ገንዘቡን ፡ ዘርፈው ፡ ቢተዉት ፡ ምናለ ? ዘመድ ፡ አልገደለባቸው ፡ ርስት ፡ አይከፈላቸው ፡ አይተውት ፡ እንኳዋ ፡ አያውቁ ! ለምን ፡ እንዲህ ፡ ጨከኑበት ? ሰዎች ፡ አይደሉም ? የሚወዱትና ፡ የሚወዳቸው ፡ የላቸውም ? " አለች ፡ ሰብለ ፡ አቀዋርጣ ፡ እንባዋን ፡ እየጎረፈች ። ወይዘሮ ፡ የሽመቤት ፡ የሚናገሩት ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶዋቸው ፡ እንዲያው ፡ ፍዝዝ ፡ ብለው ፡ ሰብለን ፡ እየተመለከቱ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆሙ።

"ደ--ህና ፡ ነኝኮ ! እ ይ--- እይ--ሆሽ ፡ ደ.ህ---ና ፡ ነኝ ! ነይ ፡ እ--ዚህ ፡ ተቀመጭና ፡ ደ--ደግፊኝ !" አለ ፡ በዛብህ ።

እንዳንዱን ፡ ቃል ፡ መጨረስ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ከፉ ፡ ዳገት ፡ አድክሞት ፡ እመሀሉ ፡ ላይ ፡ እያቋረጠ ፡ እያረፈ ። ከዚያ ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ወጥታ ፡ እየለቀሰች ፡ ደግፋው ፡ ተቀመጠች።

ወይዘሮ ፡ የሽመቤት ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ የበዛብህና ፡ የሰብለን ፡ ታሪክ ፡ በሙሉ ፡ ባያውቁ ፡ የዚያንለት ፡ ሁኔታቸውን ፡ በማየት ፡ ብቻ ፡ ስቅቅ ፡ ብለው ፡ አለቀሱ ። ትንሽ ፡ ቆይተው ፡ ቀሚስና ፡ ኩታ ፡ ሰጡዋትና ፡ ልብሰዋን ፡ ለወጠች ።

ወደ ፡ ማታ ፡ በዛብህን ፡ የተሻለው ፡ መሰለ ። ሰብለን ፡ ለመቀበል ፡ የቀረውን ፡ የሀይል ፡ ትርፍራፊ ፡ የቀረውን ፡ የህይወት ፡ እንጥፍጣፊ ፡ ከያለበት ፡ እንድ ፡ ላይ ፡ እንዳጠ

ራቀመ ፡ ሁሉ ፡ በርታ ፡ ያለ ፡ መሰለ ! እህልም ፡ ከመሰንበቻው ፡ የተሻለ ፡ በላ ። በተከታዮቹ ፡ ሁለት ፡ ቀኖች ፡ ሲያነሱትም ፡ ሆነ ፡ ሲያስተኙት፡ ራሱ፡ ጭምር፡ እዬረዳ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያውም ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ እዬተጫወተና ፡ ለመሳቅም፡ እዬሞከረ ፡ ለልብዋ ፡ የተስፋ ፡ ጮራ ፡ ሲያሳዬው ፡ ሰነበተ። ከዚያ ፡ በሰስተኛው ፡ ቀን ፡ እንደገና ፡ መድከም ፡ ጀመረ። የሀይል ፡ ትርፍራፊ ፡ የሀይወት ፡ እንጥፍጣፊ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ቢጠራቀም ፡ ትንሽ ፡ ሲያቆይ ፡ ይችል ፡ እንደሆነ እንጂ ፡ ያኖራል ፡ አይባልም ! የፍርፋሪ ፡ ፍርፋሪ ፡ የንጥፍጣፊ ፡ እንጥፍጣፊ ፡ የለውም ! ያልቃል ! አለቀ ! በተገናኙ ፡ ባምስተኛው፡ ቀን፡ ደግፋው ፡ እንደ ፡ ተቀመጠች ፡ እቅፍዋ ፡ ላይ ፡ አረፈ።

በዛብህ ፡ በሞተ ፡ ባስራሁለት ፡ ዓመቱ ፡ አንድ ፡ የጎጃም ፡ ሰው ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ሰንብቶ፡ ወደ፡ ጎጃም፡ ለመመለስ ፡ ካሽከሩ ፡ ጋር ፡ ጎሀጽዮን ፡ ከቀትር ፡ በሁዋላ ፡ በዘጠኝና ፡ ባስር ፡ ሰዓት፡ መሀከል ፡ ላይ ፡ ደረሰና ፡ እዚያ ፡ ከበቅሎው ፡ ወርዶ:-

" እንካ ፡ በቅሎውን ፡ ይዘህ ፡ የምናድርበት ፡ ደህና ፡ ቤት ፡ ፈልገህ ፡ ስታገኝ ፡ ተመልሰህ ፡ እዚሀ ፡ ቆዬኝ ።" ብሎ፡ በቅሎውን ፡ ላሽከሩ ፡ ሰጥቶ ፡ እሱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገባ ።

ደጀሰላሙን ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ መጀመሪያ ፡ ወደሚገኘው ፡ ጥድ ፡ ሄዶ ፡ ተሳለመና ፡ ጸሎተ ፡ ማርያም ፡ ከደገመ ፡ በሁዋላ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆሞ ፡ በዙሪያ፡ ገባው ፡ ያለውን ፡ ይመለከት፡ ጀመር ። "ይገርማል ! ጎጃም ፡ ስመጥር ፡ የሆኑት ፡ ትልልቅ ፡ አድባራት ፡ ሁሉ ፡ ከዳናቸው ፡ ሳር ፡ ሆኖ ፡ እዚህ ፡ እንደ ፡ ጎሀጽዮን ፡ ያሉት ፡ ትንንሽ ፡ ደብሮች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እቃቤታቸው ፡ ሳይቀር ፡ ቆርቆሮ ፡ ተከድኖዋል ! ቆርቆሮውን ፡ መንግስት ፡ ሰጥቶ ፡ ይሆን ? ወይስ ፡ አገሬው ፡ አዋጥቶ ፡ መግዛት ፡ ይችላል? የምጠይቀው ፡ ባገኝ ፡ ጥሩ ፡ ነበር!" እያለ ፡ ባሳቡ ፡ ሲተች:-

"አንቺ ፡ እታገኘሁ ፡ እባክሽ ፡ ወፍጮውን ፡ ቶሎ ፡ እጠቢና ፡ አውጭልኝ ፡ ጸሀይ ፡ ሳይበርድ ፡ እንዲደርቅና ፡

መገበሪያውን ፡ እንድፈጩው !" አለ ፡ አንድ ፡ ድምጽ ። መንገደኛው ፡ ዘወር ቢል ፡ በስተቀኙ ፡ በኩል ፡ እሱ ፡ ከቆመበት ፡ አቅራቢያ ፡ አንድ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ አንድ ፡ መነኩሲት ፡ ስንዴ ፡ እስጥተው ፡ ይለቅማሉ ። ጀርባቸውን ፡ ለመንገደኛው ፡ ሰጥተው ፡ ስለ ፡ ተቀመጡ ፡ ፊታቸው ፡ ሊታዬው ፡ አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሽበት ፡ በርነት ፡ ብሎ ፡ ያሰረገው ፡ ጠጉራቸው ከሁዋላ ፡ በኩል ከቆባቸው ፡ በታች ፡ ስለሚታይ ፡ በድሜ ፡ ጠና ፡ ያሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ከሩቅ፡ መገመት ፡ ይቻላል ። "አአ — ! እኒህ ፡ እቅቢትዋ ፡ ናቸው ! እስቲ ፡ ልሂድና ፡ ልጠይቃቸው ። እሳቸው ፡ ሳያውቁ፡ አይቀሩም !" አለና ፡ መንገደኛው ፡ ወደ ፡ መነኩሲትዋ ፡ አመራ ።

" እንዴት ፡ ዋሉ ? እማሆይ ።" አለ ፡ እንግዳው ።

"እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ ዋሉ ? ጌታው ።" አሉና ፡ መነኩሲትዋ ፡ አንድ ጊዜ ፡ ቀና ብለው ፡ እንግዳውን ፡ የውልብታ ፡ ያክል ፡ ባይናቸው ፡ አሳልፈው ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ስንዴ ፡ ለቀማቸው ፡ ጎንበስ ፡ አሉ ። ብቻ ፡ ያ ፡ ሳንድ ፡ አፍታ ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ ያዩት ፡ እንግዳ ፡ እንደሚያውቁት ፡ ሁሉ ፡ በውስጣቸው ፡ አንድ ፡ ሽብር ፡ አስነሳና ፡ እንደገና ፡ ቀና ፡ ብለው፡ ማየቱንም ፡ ፈርተው ፡ አሳባቸው ፡ ስለ ፡ ታወከ ፡ ስንዴውን ፡ ከጉድፍ ፡ መለዬት ፡ አቅቶዋቸው ፡ እንዲሁ ፡ እጃቸውን ፡ እተሰጣው ፡ ስንዴ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርገው ፡ "ቀና ፡ ብዬ ፡ ልይ ? ልቅይ !" እያሉ ፡ ሲጨነቁ ፡-

"እባክዎ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅዎ ፡ እናቴ ።" አለ ፡ መንገደኛው ።

"ምን ?" አሉ ፡ መነኩሲትዋ ፡ ቶሎ ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ አይናቸውን ፡ እንግዳው ፡ ላይ ፡ ተክለው ። እሱም ፡ አለተያየታቸው ፡ አስገርሞት ፡ ሊጠይቅ ፡ የፈለገውን ፡ መጠየቅ ፡ ትቶ ፡ ገ[illegible] ፡ ብሎ ፡ ይመለከታቸው ፡ ጀ[illegible] ዘሊያ ፡ አይንዎን ፡ [illegible] እንደሆነ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ያ[illegible] ፡ አንደ ፡ ተባሉ ፡ [illegible] እንዲሁ ፡ አይናቸውን ፡ ሳያ[illegible] ፡ አድርገው ፡ [illegible]ው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተከሉ [illegible]ለው ፡ ተነሱና፡-

"[illegible]ነህ ፡ አንተ? ኢያ ፡ ካሳ ፡ [illegible] እቃኘሰሁ "

አሉ ፡ በሻከረ ፡ ድምጽ ። መንገደኛው ፡ ልክ ፡ መብረቅ ፡ እፊቱ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ ክው ፡ ብሎ ፡ ደንግጦ ፡ አይኖቹን ፡ በጥፍ ፡ አውጥቶ ፡ መነኩሲትዋን ፡ እየተመለከተ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆመ ። እንዴት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ነው ? ስሙን ፡ እንዲያ ፡ አድርጋ ፡ በንዲያ ፡ ያለ ፡ ድምጽ ፡ የምትጠራው ፡ ሰብለ ፡ ነበረች ! ብቻ ፡ እስዋ ፡ ከሞተች ፡ አስራሁለት ፡ አመትዋ ፡ አልፏዋል ! የሰብለን ፡ የወዳጁን ፡ የሀቱን ፡ ድምጽ ፡ ለዚያ ፡ አሮጊት ፡ መነኩሲት፡ ማን ፡ ሰጣቸው ? ምን ፡ አይነት ፡ ነገር ፡ ነው ? አይኑን ፡ አፍጦ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ ትንሽ ፡ ሲያስብ ፡ ቆዩና ፡

“አዎ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ነኝ ። እስዎ ፡ ማንዎ ? የምንተዋወቅበትን ፡ ዘነጋሁት ፡ ይቅር ፡ ይበሉኝ ፡ እናቴ ! ” አለ ።

“አዩ ፡ ካሳ ፡ በሀይወትህ ፡ አለህ ? ሰብለኮ ፡ ነኝ ! ረሳኸኝ ?” ብላ ፡ እንባዋ ፡ እንደ ፡ መስከረም ፡ ዝናም ፡ ዶቦል ፡ ዶቦል ፡ ሆኖ ፡ ፊትዋን ፡ ሳይነካ ፡ እየወደቀ ፡ ክንዶችዋን ፡ እንደክንፍ ፡ ቀኝና፡ ግራ ፡ ዘርግታ ፡ አንገትዋን ፡ ልታቅፍ ፡ ስትሄድ ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ተወጋ ፡ አውሬ ፡ ጉዋጉሮ ፡ እፊትዋ ፡ ወድቆ ፡ መሬት ፡ እየነከሰ ፡ እግርዋን ፡ እየሳመ ፡ ዶሬሁ ፡ እግዚአ ፡ ዶል ፡ ጀመር ። ወድቆ ፡ ከሚንከባለልበት ፡ ለማንሳት ፡ አቅም ፡ አጣች ፡ ብትለምነውም ፡ ብታባብለውም ፡ አልሰማት ፡ አለ ። ስለዚህ ፡ እስዋም፡ ቆማ ፡ ሁኔታውን ፡ እየተመለከተች ፡ ጮሁ ፡ ማልቀስ ፡ ጀመረች ።

“ሰብለ ፡ ልጄ ፡ እሁቴ ፡ እናቴ ፡ እንጀቴ ፡ አንቺ ፡ ነሽ ፡ እንዲህ ፡ ከሰውነት ፡ የወጣሽ ? አንቺ ፡ ነሽ ፡ እንዲህ ፡ ምልክትሽ ፡ ጠፍቶ ፡ የተረሳሽ ? እኔ ፡ ከሰውነት ፡ ልውጣ ፡ የኔ ፡ ምልክት ፡ ይጥፋ ፡ እኔ ፡ ልረሳ ፡ ልጄ ፡ ልጄ ፡ ልጄ !” እያለ ፡ እግርዋን ፡ በንባው ፡ እያጠበ ፡ ሲስም ፡ የሱ ፡ ልቅሶ ፡ ያጣችውን ፡ ብዙ ፡ መልካም ፡ ነገርና ፡ ያገኘችን ፡ ብዙ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንድ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ በእውነተኛ ፡ መልኩ ፡ አሳያትና ፡ እስዋም ፡ እንደሱ ፡ ስቅቅ ፡ ብላ ፡ አለቀሰች ።

ከዚያ ፡ በየመቃብር ፡ ቤቱ ፡ ያሉት ፡ መነኩሳትና ፡ ልቅሶውን ፡ የሰሙት ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ሰብለና ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሚያለቅሱበትን ፡ ምክንያት ፡ ሳያውቁ ፡ እንዲያው ፡ የነሱን ፡

አሊቃቀስ ፡ በማየት ፡ ብቻ ፡ አብረው ፡ ሲያለቅሱ ፡ ብዙ ፡ ቆዩ ተው ፡ ሲያከማቸው ፡ ለልቅሶው ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ መጠየቅና ፡ ሰብለንም ፡ አጎትዋንም ፡ ገዝም ፡ እንዲሉ ፡ መለ መን ፡ ጀመሩ ።

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሚገላግሉትን ፡ መነኮሳት ፡ ላለማሳዘን ፡ ለጊዜው ፡ ገዝሞ ፡ ቢል ፡ እንኳ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ሰብለን ፡ ካዩ ፡ ቱተር ፡ ሳጉን ፡ መዋጥና ፡ እንባውን ፡ ማገድ ፡ አቅቶት ፡ እንዲሁ ፡ እንዳለቀሰ ፡ አመሸ ። በኋላ ፡ ብቻ ፡ በሰው ፡ ማጽናናትና ፡ ማባበል ፡ ብዛት ፡ ጸጥ ፡ እያለ ፡ ሄደ ።

"ለመሆኑ ፡ ምንድነው ፡ እንዲህ ፡ ያደረገሽ ? ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታመሽ ፡ ኖርዋል ?"

"ምን ፡ ሆንሁ ? ደህና ፡ ነኝ ፡ እየ ፡ ካሳ ! ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አስተኝቶ ፡ የሚያቆይ ፡ በሽታም ፡ የለኝ ፡ ደህና ፡ ነኝ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ድንገት ፡ ብርቱ ፡ ድካም ፡ ይደክመኝና ፡ ወዲያው ፡ ራሴን ፡ አዞር ፡ ይጥለኛል ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ቢበዛ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ተኝቼ ፡ እነሳለሁ ። ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ በሽታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ የለብኝም ።"

"መቼ ፡ ጀመረሽ ?"

"ወዲያው ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ ሞተ ።"

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የበዛብህን ፡ መሞት ፡ ሲሰማ ፡ ድምጹን ፡ ሳያሰማ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ እንባውን ፡ ሲያፈስ ፡ ቆዬና ፡-

"ተገናኝታችሁ ፡ ኖርዋል ! "አለ ፡ አንገቱን ፡ ከደፋበት ፡ ሳያቀና ።

"አዎ ፡ ሳምንት ፡ ቀን ፡ ብቻ ።"

"ምን ፡ ገደለው ?"

"ያባይ ፡ ሽፍታ ፡ ያብድበት ፡ ያከሞ ፡ ቆዬኝ ።"

ከዚያ ፡ ሁለቱም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ብዙ ፡ ሲተክዙ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡-

"ለምን ፡ መነኮስሽ ? "አለ ።

"ቆርበን ፡ ነበር ፡ ስለዚህ ፡ እሱ ፡ ሲሞት ፡ መነኮስሁ ።"

"ታዲያ ፡ ያክም ፡ ካደረስሽ ፡ እንዴት ፡ ቆረባችሁ ?"

"ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ሲቆርብ ፡

በቃል ፡ ኪዳን ፡ አጋብተው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እንዲያቆርቡን ፡ ገበዙን ፡ ለምኜ ፡ አቆረቡን ፡፡"

"አንችስ ፡ ይሁን ፡ ለጊዜው ፡ ባዘንሽ ፡ ምክናያት ፡ ይህን ፡ አሰቢ ፡ ካህናቱ ፡ ግን ፡ ደክሞ ፡ እመቃብር ፡ አፋፍ ፡ የቆመ ፡ ሰው ፡ ከጤነኛ ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ አጋብተው ፡ ማቁረባቸው ፡ የሚያስገርም ፡ ነው !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ትንሽ ፡ ሲያስብ ፡ ቆይቶ ፡፡

" እድግ ፡ ደጎች ፡ ናቸው ፡፡ የኔን ፡ ፈቃድ ፡ ለመፈጸም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መጀመርያ ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ እንዳልኸው ፡ ከደከመ ፡ በሽተኛ ፡ ጋር ፡ ጤነኛ ፡ ሴት ፡ አጋብተን ፡ አናቆርብም ፡ ብለው ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ ነበር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ መመንኮሴ ፡ የማይቀር ፡ መሆኑን ፡ ሲረዱ ፡ የፈለግሁትን ፡ አደረጉልኝ ፡፡"

"መቸም ፡ የሆነው ፡ ሆኖዋል ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ ተመልሶ ፡ የሆነውን ፡ መለወጥ ፡ አይቻል ! ብቻ ፡ እንዲያው ፡ ለነገሩ ፡ ለምን ፡ መመንኮስ ፡ ፈለግሽ?" አለ ፡ ዘለግ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲተክዝ ፡ ከቆዬ ፡ በሁዋላ፡፡

"ምን ፡ ላድርግ?"

"እንዴት ፡ ምን ፡ ላድርግ? ሰው ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ያደርጋል? የሚወደው ፡ የሞተበት ፡ ያዝናል ፡ እንጂ ፡ አብሮ ፡ ሞቶ ፡ ያውቃል?"

"እኔም ፡ አዘንሁ ፡ እንጂ ፡ አልሞትሁም !" አለች ፡ ትንሽ ፡ የቅርታ ፡ ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ፡፡

"እንዳንቺ ፡ ላሉት ፡ መመንኮስ ፡ መሞት ፡ ነው! " አለ ፡ በሻከረ ፡ ድምጽ ፡፡

"ለመመንኮስ ፡ ያስወሰኑኝ ፡ ሁለት ፡ ምክናያቶች ፡ ናቸው ፡፡" አለች ፡ አንገትዋን ፡ ደፍታ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩች ፡ ስታስብ ፡ ቆዩችና ፡፡

"ምንና ፡ ምን?"

"አንዱን ፡ ስሙን ፡ አላውቀውም ፡ ሁለተኛው ፡ ፍራት ፡ ነው ፡፡"

"ፍራት ፡ ያልሽውን ፡ ምን ፡ እንዳስፈራሽ ፡ በሁዋላ ፡

ትነግሪኛለሽ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስሙን ፡ አላውቀውም ፡ ያልሽው ፡- ስሙን ፡ እንኳ ፡ የማያውቁት ፡ ነገር ፡ ለኑሮ ፡ ተስፋ ፡ አስቆርጦ ፡ እንዴት ፡ ሊያስመነኩስ ፡ ይችላል ? ”

“ ስሜቴን ፡ ልንገርህና ፡ አንተ ፡ ስም ፡ ስጠው ። ”

“ እሺ ። ”

“ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ የተዋወቅንበትን ፡ ጊዜ ፡ ታስታውሳለህ ? ሰው ፡ ሁሉ ፡ ትቶዋት ፡ ተረስታ ፡ መውደቅያ ፡ አጣች ፡ እዬተባልሁ ፡ ለሚያውቁኝም ፡ ለማያውቁኝ ፡ እንኳዋ ፡ በወሬ ፡ መሳቂያ ፡ ሆኜ ፡ እንገቴን ፡ ቀና ፡ አድርጌ ፡ ሰው ፡ ለማየት ፡ አፍር ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በዛብህ ፡ ብቻ ፡ ከልቡ ፡ የሚወደኝ ፡ መሆኑን ፡ ስረዳ ፡ ልክ ፡ ወድቄ ፡ ከተረሳሁበት ፡ ፈልጎ ፡ ያነሳኝ ፡ ከሙታን ፡ መሀከል ፡ ለይቶ ፡ ህይወት ፡ የሰጠኝ ፡ መስሎ ፡ ተሰማኝ ። ከሱ ፡ ከተለዩሁ ፡ እንደገና ፡ ወድቄ፡ ወደምረሳበት ፡ የምመለስ ፡ መሰለኝ ። ከሱ ፡ በቀር ፡ ለኔ ፡ የተፈጠረ ፡ ያለ ፡ አልመሰለኝ ፡ ብሎ ፡ እሱን ፡ ፍለጋ ፡ ብሰደድ ፡ እመቃብር፡አፋፍ፡ላይ፡ቆሞ፡ደረስሁበት።ይገርምሀል!በቅፌ ፡ ይዤው፡ጣር፡ሲያንገላታው፡ይቆይና፡ትንሽ፡ሽልብ፡አድርጎት ፡ ሲቃዥ ፡- “ ሰብለን ፡ ለማን ፡ ትቻት ፡ ልሙት ? የለም ፡ አልሞትም ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ እኖራለሁ ፡ ” ይልና ፡ ወዲያው ፡ ሲነቃ ፡ እኔ ፡ ከሞት ፡ የማድነው ፡ ይመስል ፡ በደካማ ፡ እጁ ፡ ጥብቅ ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡- “ አትለይኝ ፡ እባክሽ ፡ እፈራለሁ ፡ ” ይላል ። ያንጊዜ ፡ እንኳዋንስ ፡ በህይወቱ ፡ እያለ ፡ ቢሞትም ፡ ሬሳውን ፡ ትቼ ፡ መሄድ ፡ ውለታ ፡ ቢስ ፡ የሚያደርገኝ ፡ መሰለኝ ። ሬሳው ፡ የሚፈራና ፡ ብቻውን ፡ ትቼው ፡ በመሄዴ ፡ የሚታዘበኝ ፡ የሚወቅሰኝ ፡ መስሎ ፡ ተሰማኝ ። ስለዚህ ፡ በሄደበት ፡ እስከከተለው ፡ ድረስ ፡ መንኩሼ ፡ በሬሳው ፡ አጠገብ ፡ እንድኖር ፡ ቆረጥሁ ።

ሁለተኛው ፡ ፍራት ፡ ነው ፡ ያልሁህ ፡ አባባንና ፡ እማማን ፡ በጀም ፡ ባልገድላቸው ፡ ገዳያቸው ፡ እኔ ፡ በመሆኔ ፡ በእግዚአብሄር ፡ ፊት ፡ ወንጀለኛ ፡ ሆኜ ፡ መታየቴ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነውና ፡ መንኩሼ ፡ እሱን ፡ ካላገለገልሁ ፡ ምህ

ረት ፡ አላገኘም ፡ ብዬ ፡ አመንሁ ። ”

“ ላባትሽና ፡ ለናትሽ ፡ ገዳያቸው ፡ የገዛ ፡ ከንቱነታ ቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንቺ ፡ አይደለሽም ። ስለ ፡ በዛብህ ፡ ለነገርሽኝ ፡ ግን ፡ የምሰጠው ፡ ስምም ፡ መልስም ፡ የለኝም ። ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንባው ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጮቹ ፡ እዬወ ረደ ።

“ አባክህ ፡ አታልቅስ ፡ አያ ፡ ካሳ ። እኔኮ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ነው ፡ የምኖር ! አንተ ፡ ተለወጥሽ ፡ ሌላ ፡ ሆንሽ ፡ አልሽኝ ፡ እንጂ ፡ ለኔ ፡ መለወጤ ፡ በጭራሽ ፡ አይታወቀኝም ። እዬሁ ፡ በዛብህን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ በቀን ፡ በቀን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አውጥቼ ፡ ምኝታውን ፡ ጠርጌ ፡ ሳላስተኛው ፡ ውዬ ፡ አላውቅም። ታዲያ ፡ በዬቀኑ ፡ ሳየው ፡ በህይወቱ ፡ ያለና ፡ አብረን ፡ የምን ኖር ፡ እዬመሰለኝ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ እኖራለሁ ። ”

“ እንዴት ? ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ግራ ፡ ገብቶና ።

“ በዛብህን ፡ ላሳይህ ? ”

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሰብለን ፡ ጤንነት ፡ ተጠራጥሮ ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ እንዲሁ ፡ ትኩር ፡ አድርጎ ፡ ይመለከታት ፡ ጀመር ።

ከዚያ ፡ ተነስታ ፡ ወፍራም ፡ ጡዋፍ ፡ አበራችና ፡ ተቀ ምጠው ፡ ሲነጋገሩ ፡ ከመሹበት ፡ መደብ ፡ አንጣር ፡ አንድ ፡ ያበባ ፡ ምንጣፍ ፡ የለበሰ ፡ የሳንቃ ፡ ክዳን ፡ ከፈት ፡ አድ ርጋ ፡ - “ እየውልህ ! ” አለች ።

መቃብሩ ፡ ከውስጥ ፡ በደንጋይ ፡ ተገንብቶ ፡ ከተለ ሰነ ፡ በሁዋላ ፡ ወለሉም ፡ ሀንጻውም ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ ባመድ ፡ ተለቅልቆ ፡ ተጠንቅቆ ፡ የያዙት ፡ ቤት ፡ እንጂ ፡ የመቃብር ፡ ጉርጉዋድ ፡ አይመስልም ። እዚያ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ንጹህ ፡ ሸማ ፡ የለበሰ ፡ ሳጥን ፡ በቀኝ ፡ አንድ ፡ ያልለበሰ ፡ ሳጥን ፡ በግራ ፡ ሆነው ፡ ይታያሉ ። ጉርጉዋዱ ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ሳጥንም ፡ ሊያስቀምጥ ፡ የሚችል ፡ ሰፊ ፡ ነው ።

“ ሸማ ፡ የለበሰው ፡ በዛብህ ፡ ነው ። ” አለች ፡ ሰብለ ።

“ ያልለበሰውስ ? ”

“ ያልለበሰውማ ---- እሱቴ ፡ ነዎት ። ” አለች ፡ ፈገግ ፡ ብላ ።

"የማነው?"

"መገመት ፡ አቃተህ? የኔ ፡ ነው!"

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ስቅቅ ፡ ብሎ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር፡፡

" አታልቅስ ፡ እንጂ እንድታለቅስኮ ፡ አይደለም ፡ በዛብህን ፡ ያሳየሁህ!"

" አንድ ፡ ነገር ፡ ልለምንሽ ፡ ሰብለ፡፡ " አለ ፡ አይናቹንም ፡ አፍንጫውንም ፡ ኩታውን ፡ ነጥሎ ፡ በጫፉ ፡ እዬጠራረገ፡፡

"ሰብለ ፡ አልባልም ! እማሆይ !"

"እሺ ፤ እማሆይ !"

"ምን?"

"ስሞት ፡ እዚህ ፡ አብሬያችሁ ፡ ልሁን ፡ ቦታው ፡ ሰፊ ፡ ነው ፤ ይበቃል፡፡"

"አገርህን ፡ ትተህ?"

"አገሬን ፡ ያገሬ ፡ ሰው ፡ ካስለቀቀኝ ፡ ብዙ ፡ ጊዜየ ፡ ነው፤ እንቆጳም ፡ ከሞተች፡ ሶስት ፡ አመት፡ ሆኖዋታል፡፡"

"እንግዲያስ ፡ ደህና ፡ አሳብ ፡ ነው!" አለች ፡ አንገትዋን ፡ ደፍታ ፡ ካቆዬችበት ፡ ቀና ፡ አድርጋ ፡ እንባ ፡ በሞሉ፡ አይኖችዋ ፡ አጎትዋን ፡ እዬተመለከተች ፡ እሱም ፡ እንደሷ፡ በመከራ ፡ የኖረ ፡ መሆኑ ፡ ታስባትና ፡

ጉዱ ፡ ካሳና ፡ ሰብለ ፡ በተገናኙ ፡ ባስራምስተኛው ፡ ቀን፡ የልብ ፡ በሽታዋ ፡ ተነሳባትና ፡ እንደ ፡ ልማድዋ ፡ ወደቀች፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ዳግም ፡ አልተነሳችም፡፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከባልዋ ፡ አጠገብ ፡ አስተኛት ፡ በሶስተኛ ፡ አመቱ ፡ እሱም ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ተጨመረ፡፡

# ማረሚያ

በዚህ ፡ መጽሀፍ ፡ መቅድም ፡ እንደ ፡ ተገለጸው፡-

አንደኛ ፡ የፊደሎቻችንን ፡ ብዛት ፡ ለመቀነስ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ ድምጽ ፡ ካላቸው ፡ ፊደሎች ፡ አንዳንድ ፡ ብቻ ፡ እዬተያዘ፡ የቀሩት ፡ እንዲወድቁ፣ እንዲሁም ፡ በፊደሎቻችን ፡ መጨረሻ፡ ተመድበው ፡ የሚገኙት ፥ እንደ፡- "ኰ-ቈ-ጐ-ኈ -" ያሉት ፡ ጎደሎ ፡ ፊደሎችና ፡ ሌሎችም ፡ በመደበኛ ፡ ፊደሎች ፡ መሀከል፡ ጣልቃ ፡ እዬገቡ ፡ የሚገኙት ፡ እንደ፡-"ሟ-ሯ-ሷ-ቧ- ኗ" ያሉ ፡ ፊደሎች ፡ እንዲወድቁ፡

ሁለተኛ፡ ልክ ፡ እንዳነጋገራችን ፡ ባጻጻፋችንም ፡ የማጥበቂያ ፡ ምልክት ፡ ቢኖረን ፡ ይልቁንም ፡ የተለያዬ ፡ ትርጉም ፡ ያላቸው፡- እንደ፡- "ሰውዬው ፡ ሲበላ ፡ እንጀራው ፡ ሲበላ፡" ያሉ፡ ቃሎች ፡ ሲገጥሙን ፡ ትርጉማቸውን ፡ ወዲያውኑ ፡ ልናውቅ ፡ ስለምንችል ፡ ከዜማ ፡ ምልክቶቻችን ፡ "አያያዝ፡" የሚባለው ፡ ነጥብ ፡ በሚጠብቀው ፡ ፊደል ፡ ራስጌ ፡ እንዲደረግ ፡ አመልክተን ፡ ነበር፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያሰው ፡ አዲስ ፡ አሳብ ፡ እስኪለመድ፡ ለሰራተኛም ፡ ሆነ ፡ ለመሳሪያ ፡ ማስቸገሩ ፡ ስለማይቀር ፡ የማጥበቂያው ፡ ምልክት ፡ ሊጠብቁ ፡ በሚገባቸው ፡ ፊደሎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ፡ አልተደረገም፡፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሊጠብቁ ፡ በማይገባቸው ፡ ፊደሎች ፡ ላይ ፡ ተደርጎ ፡ ይታያል ፡፡ እንዲሁም ፡ ይውደቁ፡ የተባሉት ፡ ፊደሎች ፡ ተይዘው ፡ ይገኛሉ፡፡

ስለዚህ ፡ አንባቢዎችን ፡ የምንለምነው ፡ የደራሲውን ፡ አሳብ ፡ ከተረዱት ፡ ራሳቸው ፡ እያረሙ ፡ እንዲያነቡ ፡ ነው፡፡ ለሌላው ፡ የተሰመደና ፡ ተራ ፡ ስህተት ፡ ማረሚያው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ተመልክቶዋል፡፡

| ገጽ | መስመር | የተሳሳተ | የታረመ |
|---|---|---|---|
| 45 | 18 | የሚያደንቁትና | ‘የሚያደንቁትና’ ተብሎ ይነበብ |
| 47 | 5 | እሉ | ‘እሱ’ ተብሎ ይነበብ |
| 68 | 29 | እሉ | ‘እስ’ ተብሎ ይነበብ |
| 86 | 3 | እየተናነቃ | ‘እየተናነቃቸው’ ተብሎ ይነበብ |
| 92 | 14 | በሙሉ ሰውነት | ‘ሙሉ ሰውነት’ ተብሎ ይነበብ |
| 94 | 5 | በሚቴን | ‘በሚትን’ ተብሎ ይነበብ |
| 102 | 4 | ያባቶቹን | ‘ያባቶቼን’ ተብሎ ይነበብ |
| 114 | 11 | እንጀ | ‘እንጂ’ ተብሎ ይነበብ |
| 140 | 11 | በፍራትና በፍረት ቆመው | ‘በፍራትና በፍረት መሀከል ቆመው’ ይባል |
| 142 | 17 | ቀልበሰ | ‘ቀበሰ’ ተብሎ ይነበብ |
| 153 | 16 | ያበጠውን | ‘ያጠበውን’ ተብሎ ይነበብ |
| 174 | 16 | ያስመበተሀቅር | ‘ያስገበተሀቀር’ ተብሎ ይነበብ |
| 184 | 27 | ባትቾዋ | ‘ለናቶችዋ’ ተብሎ ይነበብ |
| 206 | 6 | የሚያወራ | ‘የሚያወራው’ ተብሎ ይነበብ |
| 226 | 12 | በጊሊትና | ‘በጉሊትና’ ተብሎ ይነበብ |
| 228 | 20 | ካልገደለ | ‘ካልጉደለ’ ተብሎ ይነበብ |
| 233 | 13 | የማዜን | ‘የማዜርን’ ተብሎ ይነበብ |
| 241 | 30 | ነገር | ‘አገር’ ተብሎ ይነበብ |
| 249 | 15 | ማናባቱን | ‘ምናባቱን’ ተብሎ ይነበብ |
| 270 | 28 | የማባለው | ‘የሚባለው’ ተብሎ ይነበብ |
| 316 | 18 | በመለከት | ‘ሲመለከት’ ተብሎ ይነበብ |
| 321 | 23 | ፈትሽ | ‘ፌትሽ’ ተብሎ ይነበብ |
| 362 | 11 | ነግረሽው | ‘ነግረውሽ’ ተብሎ ይነበብ |
| 373 | 25 | እየተመከተች | ‘እየተመለከተች’ ተብሎ ይነበብ |
| 375 | 31 | ይፋሰጋል | ‘ይፈሰጋል’ ተብሎ ይነበብ |
| 400 | 26 | የማደገን | ‘የማይገን’ ተብሎ ይነበብ |
| 428 | 31 | ነው | ‘ሰው’ ተብሎ ይነበብ |
| 443 | 25 | የማችል | ‘የማይችል’ ተብሎ ይነበብ |
| 446 | 2 | እመሁዋንን | ‘እመሁዋንንት’ ተብሎ ይነበብ |
| 448 | 9 | የሚለጣጥ | ‘የሚስገጥ’ ተብሎ ይነበብ |
| 449 | 24 | በክርኑ | ‘በክርን’ ተብሎ ይነበብ |
| 454 | 27 | ቤተ | ‘ቤት’ ተብሎ ይነበብ |
| 458 | 4 | የውም | ‘ያውም’ ተብሎ ይነበብ |
| 468 | 19 | በማጨረት | ‘ለማጣረት’ ተብሎ ይነበብ |
| 479 | 16 | ስትባል | ‘ሳትባል’ ተብሎ ይነበብ |
| 502 | 20 | ስለማይሰማ | ‘ስለማይሰማው’ ተብሎ ይነበብ |
| 502 | 20 | እርስዎ | ‘እስርዎ’ ተብሎ ይነበብ |